# “ድርጅታዊ ምዝበራ”

# የኢትዮጵያ “እድገታዊ መንግሥትና” የስልጣን ባለጠጋዎች ኢኮኖሚ።

አክሎግ ቢራራ (ዶር)

## መታሰቢያነቱ ለማን ነው?

1. ኢትዮጵያ፤ ቻድ፤ ካሜሩን፤ ዓለም ባንክ፤ ለተወሰኑ አመታት በሞያየ ካገለገልኩ በኋላ፤ ዓለም ባንክ ተመልሼ ሰላሳ አመታት ሰራሁ። "ጡሮታ ሰወጣ" እኔም ለሃገሬ ኢትዮጵያ የተቻለኝን ማበርከት ግዴታየ ነው ብየ ስነሳ፤ "ግፋበት። ከጎንህ ሆኘ የተቻለኝን እረዳሃለሁ። የሞራልና የሃሳብ ድጋፍ እሰጥሃለሁ" ላለችኝ። ድክመቴን ወደ ጥንካሬ ለለወጠችው ባለቤቴ ለአምሳልነሽ ወረታ አክብሮቴንና ምስጋናዬን እገልጻለሁ።

2. የሃይማኖት፤ የጎሳ፤ የእድሜ ልዩነት ሳያሳዩ ላሳደጉኝ። በክብር፤ በነጻነት፤ በኢትዮጵያዊነቴ እንዳምን ላስተማሩኝ ለአባቴ፤ ለብላታ ቢራራ ታምራትና ለእናቴ ለወይዘሮ ገበየሁ ካሳ ምስጋናዬን ደጋግሜ እገልጻለሁ።

3. ይህ መጽሃፍ፤ ለሰላም፤ ለፍትህ፤ ለነጻነት፤ ለአገር አንድነት፤ ለእኩልነትና ለዲሞክራሲ ለሞቱ፤ ለተሰደዱ፤ለታሰሩ፤ አሁንም ለሚታገሉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ እንደ ማስታወሻ ቀርቧል። ለፍትህ ታጋዮች ሁል ጊዜ እንዲያስታውሷቸው አደራ እላለሁ።

4. ተከታታይ የአገር መሪ፤ አስታዋሽ፤ አስተማሪ፤ አጋር፤ ተቆርቋሪ የሌለው ህብረተሰብ ይጠፋል። በፍጥነት በሚለወጥ ዓለም ቦታውን ለመያዝ አይችልም። የአሁኑንና ተከታታዩን ትውልድ አደራ የምለው፤ ታሪክ አለህ፤ ባህል አለህ። በራስህ ተማምነህ፤ ራስክን አኩርተህ፤ አገርህን ለማጎልመስ ትችላለህ። በጠባብነት፤ በትምክተኛነት፤ በመለያየት፤ በአኩራፊነት፤ በምቀኛነት፤ በቂም በቀልነት፤ በራስ ወዳድነት፤ በሙሰኛነትና በአድሏዊይነት አትመን።በኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅነትና በሕዝቧ እኩልነትና በሃገር ወለድ እድገት እመን የሚል አደራ አስተላልፋለሁ። ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሃብት አላት። የታሪክ፤ የባህል፤ የሰው ሃይል ደሃ አይደለችም። ዘመናዊ እድገት ከፍትህ ጋር ለመጎናጸፍ ትችላለች። ይህን ለማድረግ እንድትችል ሁሉን የሚያካትትና የሚያሳትፍ። ለሁሉም እድል የሚከፍትና በሕግ የበላይነት የሚያምን የመንግሥት ስርአት ያስፈልጋታል። ለዚህ ኢትዮጵያውያን መስዋእት ላደረጉበት አላማ ሁሉም በበኩሉ አስተዋጽኦ የማድረግ ታሪካዊ ሃላፊነት አለበት።

5. ይህ መጽሃፍ ብዙ ጥረትን፤ ትእግስትን፤ እውቀትን፤ አስተዋይነትንና ጌዜን ጠይቋል። እነዚህና ሌሎች ስጦታዎች ያሉት ወዳጀ አቶ ግርማ ተፈራ ሙሉ ድጋፍ ባይሰጠኝ ኖሮ መጽሃፉ አያልቅም ነበር። እያንዳንዱን ሃሳብ፤ አረፍተ ነገር፤ ቃልና ፊደል በቅርበት መርምሯል። ምስጋናየ ከፍ ያለ ነው። መጽሃፉ የሁለታችን ስራ ውጤት ነው ለማለት እችላለሁ።

6. መጽሃፉን አንብበው ዘገባ ያደረጉትን የልማት ኢኮኒሚስት አቶ ገለታው ዘለቀንና ከብዙ አመታት አገልግሎት በኋላ ከዓለም ባንክ በጡሮታ የወጣውን አቶ ግርማ ተፈራን፤ የመጽሃፉን ሽፋን በጥበብ ያዘጋጀውን ወዳጄን እንጂኔር ስዮም ገበየሁን ከልብ አመሰግናለሁ።

7. ሰንጠረዦቹን ያዘጋጀልኝንና ባስፈላጊው ቦታ ያስቀመጠልኝን ልጄን ኑብዩ አክሎግን አመሰግናለሁ። ማንኛውም ግድፈትና መሰረተ ሃሳብ የደራሲው ነው።

## ማውጫ

1. መታሰቢያነቱ......................................................................2

2. መግቢያ..............................................................................4-16

3. ከመለስ ባሻገር....................................................................17-55

4. የሠብአዊ መብቶች መታፈን....................................................56-121

5. የጎሳ ተኮር ፌደራሊዝም........................................................122-171

6. ጎጠኛ ባለጠጋዎች..........................................................172-223

7. “ሃሰትና ስንቅ እያደር ያልቅ”.............................................224-270

8. በደሃነት የተሸመተ ሁለ-ገብ ሙስና.......................................271-315

9. ስደተኛነት የእድገት ውድቀት ነው.......................................316-339

10. የፖሊሲ አቅጣጫዎች....................................................340-382

11. መረጃ/ጥቅስ/ብብሊኦግራፊ...............................................383--388

## መግቢያ

የዚህ መጽሃፍ መሰረተ ሃሳብ (Fundamental thesis) ኢትዮጵያ፤ በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን በዓለም የተከበረችና የተደነቀች፤ ለሁሉም ቤተሰቧ የምታኮራ ሃብታም አገር ለመሆን ትችላለች የሚል ነው። ይህን ሊገኝ የሚችል የተቀደሰ አላማ ለመጎናፀፍ አስተማማኝ ሆኖ የምናገኘው የአገዛዝ ስርአት ሁሉን ዜጎች በእኩልነት የሚያስተናግድ፤ ለሕዝብ ተገዢ የሆነ መንግሥት ሲመሰረት ብቻ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ መሰረታዊ ችግር የአገዛዝ በደል ነው። የአሁኑ የአንድ አምባገነናዊ ፓርቲ የጎሳ ፖለቲካና አመራር ይህን ስኬታማ ሊሆን የሚችል እድል በፍጥነት እንደ ጤዛ ሲያረግፈው እናያለን። የአገዛዙ በደል በሰብአዊ መብቶች መረገጥ፤ በኃይማኖት ነጻነት አፈና፤ በዋጋ ግሽፈት፤ በወጣቱ ትውልድ ስደት፤ በስራ አጥነት፤ በመሬት ነጠቃ፤ በአገሪቱ አለመረጋጋት፤ በአካባቢ ውድመት ወዘተ ተከስቷል። ስለዚህ፤ የወቅቱ ትውልዳዊ ጥያቄ ጥቃቅን ልዩነቶችን ወደ ጎን ትቶ አገሪቱን ከውድቀት፤ ሕዝቧን ከውርደት ማዳን ነው። በእኛ አመለካከት፤ ለሁሉም ሰብሳቢ የሚሆነው መርህ የኢትዮጵያ ብሄራዊ አንድነት፤ የሕዝቧ <u>እኩልነትና ፍትህ</u> ናቸው። ይህ መጽሃፍ ያቀረበው ግንዛቤ በፍትህ-ርትእ የማይመራው ጎሳዊ አገዛዝ በህብረተሰቡ ላይ የፈጠረውን የኢኮኖሚ በደል፤ ግፍና ኢትዩጵያን የማፈራረስ ሂደት ነው።

የጸሃፊውና የአሁኑ ትውልድ ለኢትዮጵያ ህብረተሰብ (Society) የፈጠራቸውና ሊፈታቸው ያልቻለው የፖሊሲና የአመራር መሰናክሎች ጠባብ ጎሰኛ ወይንም ብሄርተኛ በሆነ አምባገነናዊ አገዛዝ ሊፈቱ አይችሉም። ዋናው ምክንያት፤ በመሳሪያ ሃይልና በውጭ አገር ደጋፊዎች የፖለቲካ ስልጣን ይዞ ለጥቂት ጠባብ ጎሰኛ ግለሰቦች፤ ቤተሰቦችና ወዳጆች የሚያንፈላስስ የኢኮኖሚ የበላይነት ያስገኘው አገዛዝ አሳሳቢ የሆኑ የህብረተሰብ ችግሮችን በያቅጣጫው ፈጥሯል። ይህ በቀጥታ ከፖለቲካ ስልጣን ጋር የተቆራኘ ባለጠጋነት የተጠቀመው ጠባብ ጎሰኛነትን፤ ፓርቲን፤ መንግሥትንና ተቋሞችን በስልት ባያያዘ ህጋዊ በሚመስል የአገዛዝ መረብ ነው። ጠባብ ጎሰኛነት፤ ፓርቲ፤ የመንግሥት ስነስርአት፤ ሕግና ተቋሞች የተቆላለፉ ሆነዋል። የሕግ የበላይነት የለም። የኢኮኖሚው አመራር ለጠባብ ጎሰኞች የበላይነት (The preponderance of ethnic elites at the top) ምዝበራ አመች ሆኗል። ይህን የማህበራዊና የኢኮኖሚ አገዛዝ "የተደራጀ ምዝበራ" እንለዋለን። ኪራይ ሰብሳቢነትና ሙሰኛነት የገነው ፓርቲ ዋና መታወቂያ ሆኗል። (Ethnic elites at the top of the government are able to extract rents and other assets from the society). ቅድመ ህወሓት/ኢህአዴግ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሳዊ መብቶቹ እንዳልተከበሩ ምንም አያከራክርም። ዛሬ ህወሓት/ኢህአዴግ ብሄራዊ ተቋሞችን በሙሉ ንዷል። በምትካቸው የክልል አገዛዝና የጥቂት ባለጠጋዎችን ጥቅም አስከባሪ የሆነ አገዛዝ ተቋማዊ አድርጉል። መሰረታዊ መብቶችንና ነጻነትን በሙሉ በባሰ ሁኔታ አፍኗል። ኢትዮጵያዊነትን ንዷል። የህወሓት አገዛዝ የፈጠረው ስርአት፤ ለጥቂት ከስልጣን ጋር የተቆራኙ ግለሰቦችና ቤተሰቦች በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነትን አበርክቷል።

ዛሬ በኢትዮጵያ፤ ከባዶ (ዜሮ ካፒታል) ተነስቶ ባለጠጋና ከበርቴ መሆን የፖለቲካ የበላይነት ውጤት ነው። ለዚህ አመቻች የሆነው፤ ህገመንግሥቱ ጎሳ-ተኮር ስለሆነ ነው። በኢትዮጵያ የተከሰቱ አበይት ችግሮች--የቁሳቁስ ዋጋ ግሽበቶች፤ የብር ዋጋና ጥቅም መቀነስ፤ ስራ አጥነት፤ ስደት፤ ረሃብ፤ ድህነት፤ ጥገኝነት፤ ሙስና ወዘተ ወዘተ--የተፈጠሩት በገዢው ፓርቲ ብቻ ነው ለማለት ባይቻልም፤ ያባባሳቸው ህብረተሰቡ ሳይሆን ሕዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ (ህወሓት) በመሪነት የያዘው፤ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ዲሞክራሳዊ ግንባር (ኢህአዴግ) በአጋርነት የሚመራው የአገዛዝ ስርአት ነው። ይህ የብሄር/ብሄረሰብ የፖለቲካ ስብስብ፤ የኢትዮጵያን ህብረተሰብ ተባባሪነትና አንድነት ባልተጠበቀና በአደገኛ ሁኔታ ከስሩ አናግቶታል። አዲሱ ትውልድ በኢትዮጵያዊነት ሳይሆ በጎሰኛነት፤ አማራ፤ ትግሬ፤ ኦሮሞ ወዘተ ሆኖ እንዲደራጅ፤ ለስግብግብነት እንዲገዛ፤ ለራስ ጥቅም ብቻ እንዲወዳደር፤ እንዲያስብ  እየተገደደ ነው። በተለይ አድካሚ የሆነው፤ ወጣቱ ትውልድ ሃገሩ ታሪክ፤ ባህል፤ የመፍጠር ችሎታ እንዳያምን መገደዱ ነው። በአንጻሩ፤ ገዢውን ፓርቲ ከመኮነን ውጭ፤ ተቃዋሚው ክፍልና ምሁሩ ወቅቱ የሚጠይቀውን ታሪካዊ ግዴታ አላሟላም። ሕዝቡ ለራሱ መብት እንዲነሳ አላደራጀም፤ አላስተማረም፤ መስዋእት አልሆነም። የአፈና አገዛዝ ስልት ዘላቂነት የማይኖረው ተቃዋሚው ክፍል፤ ምሁሩና ህብረተሰቡ አሻፈረኝ፤ መብቴ መከበር አለበት ብሎ በተከታታይ ሲነሳ ነው። አንዱ ሌላው እስከሚነሳና እስኪሞት ይጠብቃል። "እኔም ለሙብቴ" መቆም አለብኝ ብሎ ተባብሮ አልተነሳም።

<u>ላለፉት ሃያ ሶስት አመታት</u> ኢትዮጵያን በአምባገነንነት ሲገዛ የቆየው ህወሓት፤ አሁንም ለሚቀጥሉት መቶ አመታት እገዛለሁ ብሎ ወስኗል። ህወሓት፤ በተቀጣይነትም የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ዲሞክራሳዊ ግንባር (ኢህአዴግ)፤ ከመለስ ባሻገር የሚያሳየው አምባገነናዊነት፤ እብሪት፤ ግትርተኛነትና ትምክህተኛነት የሃገሪቱንም ሆነ የህብረተሰቡን አንጋፋ ችግሮች በጋራ ተመካክሮ፤ የፖለቲካ ስልጣንን ተካፍሎ፤ የሕዝቡን ድምጽ አክብሮ፤ በተለይ የወጣቱን ትውልድ ፍላጎት ለማሟላት የተዘጋጀ አይመስልም። የአብዛኛው ህብረተሰብ የኑሮ ሁኔታ ተባብሷል። የአብዛኛው ወጣት

ትውልድ እድል ሰራ በማግኘት ፋንታ ስደት ሆኗል። በማንኛውም መመዘኛ ሲታይ፤ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ "የእኔ ነው" የሚለው ተጨባጭ ጥሪትና ሃብት የለውም። ወደፊት የእድሉ ባለቤት ለመሆን ከፈለገ፤ ሃላፊነትና ተጠያቂነት ያለው መንግሥት አለኝ ለማለት መቻል አለበት። ህብረተሰቡ የወደፊት እድሉን የመወሰን ግዴታ አስቸኳይ ሆኗል። ምርጫው ሁለት ነው። ያለውን አፋኝ ስርአት ተቀብሎ መኖር ወይንም መብቴ ይከበር ብሎ <u>ለፍትህ  በአንድ  ላይ መነሳት።</u>

ነባር ሁኔታዎች እየተለወጡ መሄዳቸውን እናያለን። የአሁኑ ጠባብ ጎሰኛና ግፈኛ አገዛዝ (Governance) ከቀጠለ፤ ስርአቱን የሚያንበረክከው የአብዛኛው ሕዝብ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ኑሮ መናጋት ይሆናል። መንግስት ሁሉን አይቀጥርም። ተፈላጊ ቁሳቁሶች አለመገኘት፤ ሲገኙም ዋጋቸው የመግዛት አቅም ከሚችለው በላይ ሆኖ፤ የኑሮ ሁኔታ አሰቃቂ ደረጃ ላይ መድረስ፤ የወጣቱ ትውልድ የስራ እድል ማግኘት ህልም መሆን፤ የማህበረሰቡ ነጻነትና ሰብአዊ መብት መገፈፍ ናቸው። የቋናቋ ፌደራላዊ አመሰራረት፤ ከባህል "እኩልነት"ና ለጎሳ-ተኮር የፓርቲ አለቃዎች ጥቅም ከማስገኘት ባሻገር፤ ክልሎች በራሳቸው እድል ላይ የመወሰን መብት አልሰጣቸውም። የገዢው ፓርቲ ዋናው የህብረተሰቡ እድል ወሳኝ ሆኗል። የክልል አስተዳደር የህብረተሱቡን ፍትሃዊ እድገት እየገታው ነው። በአብዛኛው፤ የሁሉም ብሄር/ብሄረሰቦች አባላት የደረሰባቸው ዋጋ መክፍል ያይላል። የክልል ፌደራሊዝም የጠቀመው የፓርቲውን አለቃዎችና የበላይ ተባባሪዎችን ነው ለማለት የሚያስችሉ ብዙ ማስረጃወች አሉ። ባጭሩ፤ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች መብታቸውን የሚያስከብር፤ ሃላፊነትና ተጠያቂነት ያለው መንግሥት ይፈልጋሉ። ይህ በልመና አይገኝም። ከአሰቃቂ ኑሮው አንጻር ሲታይ፤ የመረረው ሕዝብ መነሳቱ አይቀርም ለማለት የሚያስችሉ ክስተቶች አሉ። የሚያሳዩት፤ የአብዛኛው ህብረተሰብ የኑሮ ሁኔታ--የፈለገው እድገት አለ ቢባል-- እንዳልተሻሻለ ነው። መንግሥቱ ብዙ ፈሰስ የሚያደርገው የህብረተሰቡን የመፍጠር ሃይል በማጎልመስ ተግባሮች አይደለም። የቁጥጥር መረቡን ማጠናከርና ክልላዊ የልማት ልዩነቶችን ማጠናከር ነው። ለሰለላና ለመከላከያ የሚወጣውን መዋእለንዋይ ማየት ይበቃል።

እነዚህን ከአመራር ጉድለት፤ ከመዋቅር አለመለወጥ የመነጩ ችግሮች፤ የገዢው ፓርቲ ብቻውን ሊፈታቸው አይችልም። ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ጥገናዊ ለውጥ አይደለም። እምርታዊ ለውጥ መሆኑን በዚህ መጽሃፍ እናሳያለን። ባለፉት ሃያ ሶስት አመታት <u>የተሞከረው በውጭ ለጋሶች የተገኘ</u> የእድገት ጎዳና ማህበራዊና ክልላዊ መዛባት ፈጥሯል። ለአንድ ቡድን ጡንቻ የሰጠው "እድገታዊ መንግሥት" ያለምንም ነጻነት፤ ያለምንም ኢትዮጵያዊ የሆነ የግል ክፍል ተሳትፎ፤ በፓርቲ፤ በመንግሥት፤ በጥቂት ምርጥና ታማኝ በሆኑ፤ በአብዛኛው፤ የትግራይ ቤተሰቦችና ግለሰቦች፤ ከውጭ በግብዣ በመጡ ኢንቬስተሮች የበላይነት ኢኮኖሚው የስራ እድል ይፈጥራል። ገቢን ይጨምራል። መካከለኛውን መደብ ያስፋፋል። ኢትዮጵያን ወደ መካከለኛ እድገት ደረጃ (Middle Income Status) ያሸጋግራል የሚል ነበር። በመሰረተ ልማት መለኪያ ሲታይ---በመንገድ፤ በወንዝ ግድብ፤ በድልድይ፤ በትምኅርት ቤቶችና በጤና ጣቢያ ስራዎች፤ በሰማይ ጠቀስ ፎቆች፤ በቪላዎች፤ በተራ ቤቶች፤ በሆቴሎች፤ በምግብ ቤቶች፤ በመሰብሰቢያ ህንጻዎች--የማይናቅ ልማት ተካሂዷል ለማለት እንችላለን። ሰው መንገድ፤ ሆቴል፤ ግድብ ወዘተ ሊበላ አይችልም፤ ተራው ሰው ሸራቶን ሊያድር አይችልም። ከአርባ ቢሊዮን ዶላር እርዳታ በኋላ፤መሰረተ ልማት ቢስፋፋ አያሰደንቅም። ይህ እድገት ግን ከብልጭልጭነት በላይ የማህበረሰቡን ኑሮ አላሻሻለም። የኢኰኖሚው መዋቅር አሁንም ወደኋላ የቀረ፤የገጠር ኢኮኖሚ ነው። ኢንዱስትሪ በተፈለገው ደረጃ አልተስፋፋም። የነፍስ ወከፍ ገቢ ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር ለመወዳደር አልቻለም። ለወጣቱ ትውልድ የስራ እድል፤ የግለሰብ ድርጅት የማቋቋም እድል አልከፈተም። ወጣቱን ለስደት ዳርጎታል። የተማረ የሰው ኃይል ከተሰደደ አገር ወለድ የሆነ ብሄራዊ ልማት አይቻልም። እድገት አለ የሚለው አያከራክርም። አብዛኛዎቹ ከሳሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ አገሮች፤ ባለፉት አስር አመታት በአመት ከስድስት እስከ ሰባት በመቶ አድገዋል። የዓለም የገንዘብ ድርጅትና ዓለም ባንክ እንደሚሉት ከሆነ፤ በሚቀጥሉት አምስት--አስር አመታት ቢያንስ በአመት ስድስት በመቶ ያድጋሉ። እነዚህ ድርጅቶች የሚሉት፤ ኢትዮጵያ ከስድስት ወይንም ከሰባት በመቶ በላይ ለማደግ አትችልም ነው። አንዱና ዋናው ምክንያት፤ አገሪቱ የራሷ የሆነ የምትመካበት፤ በቁጠባ የተገኘ፤ የትርፍ ገንዘብ (Domestic Savings) የላትም። የሁለት ሶስተኛው ዘመናዊ ክፍል ቀጣሪ መንግሥት ነው፤ የግል ክፍሉ ታፍኗል። የግል ክፍሉ ካላደገ በያመቱ ስራ ለሚፈልገው ሁለት ሚሊዮን ተኩል ወጣት የስራ እድል የተወሰነ ይሆናል ። ሌላው ከውጭ የሚገኘው ብድርና ድጋፍ አምራችነትን ለማጠናከር አልዋለም። ብዙ ቢሊዮን ዶላር እየተሰረቀ ይሸሻል። (Substantial and recurring capital flight). ህብረተሰቡ በእድገቱ አይሳተፍም። የግል ክፍሉ ታፍኗል የሚሉ ናቸው። ችግሮቹ እንዳሉ ሆነው፤ በአመት በአምስት፤ ስድስት ወይንም ሰባት በመቶ ካደገች ያስመስግናል እንጅ አያሳፍርም። የእድገቱ ጠቃሚነት የሚፈረጀው ለተራው ዜጋ በሚያደርገው የኑሮ ለውጥ ነው። ሁሉን ተቃዋሚ በጠላትነት የሚፈርጀው ህወሓት ሊቀበል ያልቻለው፤ ኢትዮጵያ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ብታድግ ተቃዋሚው ደጋፊ እንደሚሆን  አለመገንዘቡ ነው። ባለስልጣናትና ደጋፊዎቻቸው የማይቀበሉት፤ የኢትዮጵያን እድገት አደጋ ውስጥ ያስገቡት፤ ስርአቱ የወለዳቸው በግልጽ የሚታዩ ችግሮች  መሆናቸውን ነው። አንዱና ዋናው፤ የአንድ ፓርቲ የበላይነት "ስልጣን ወይም ሞት" ብሎ የጀመረውና

የሚከተለው የበላይነት ስርዓት ነው። ይኼ ቢያንስ ዘጠና በመቶ የሚሆነውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ያገለለ ስርዓት የፈለገውን ያህል ተቃዋሚ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ቢያስር ዘላቂነት የለውም። ሌሎችን ከፖለቲካ ምድሩ ወይንም መስኩ ሙሉ በሙሉ ዘግቶ ለይስሙላ ምርጫ ቢያካሂድ ተቀባይነት አይኖረውም። እንዲያውም ሁኔታውን ያባብሰዋል። ተቃዋሚዎች ለመሳተፍ ስለተከለከሉ፤ የአገሪቱን ችግር አብረው ተወያይተው ለመፍታት አልቻሉም። የሚጎዳው ህብረተሰቡ ነው። ሁሉን አቀፍ የሆነ የፖለቲካ ስርአት ካልተፈጠረ ፍትሃዊ የሆነ ህብረተሰብ አይፈጠርም። ሰላም አይኖርም። አገሪቱ እርጋታ እንዲኖራት ከተፈለገ ያሉት አማራጮች የፖለቲካና የኢኮኖሚ ውድድር እንዲኖር መፍቀድ፤ አለያ፤ መንግሥት ብዙ ቢሊዮን ብር ለስለላና ለአፈና እያወጣ ተቃዋሚውንና ህብረተሰቡን መቆጣጠር ናቸው። በእኛ ግምት ሁሉን አቀፍ የሆነ አገዛዝ፤ ለሁሉም፤ ያለ-አድልዎ፤ የኢኮኖሚ እድል መፍጠር ዘላቂነት ያለው የሰላም መሰረትይፈጥራል። ለመሻሻል፤ የመስራት፤ የመማር፤ የመንቀሳቀስ፤ የማምረት እድል ክፍት መሆን አለበት። የህወሓት/ኢህአዴግ አምባገነናዊ አገዛዝ፤ ለሕዝቡ ድምጽ ዋጋ አልሰጠውም። ያጠናከረው አድሏዊ ፈሰስን (Preferential flow and allocation of resources) ነው፤ ይህን ስላየ፤ ህብረተሰቡ በመንግሥት ላይ እምነት የለውም። ከሁሉ በላይ የልማት ማነቆው አገዛዙ ነው።

ሁለተኛውና ነቀርሳ የሆነው-- ልክ እንደ ፖለቲካው የፖለቲካው ዝግነት-- ዘመናዊ የሆነው የኢኮኖሚ ክፍል እድገትም ዝግ መሆኑ ነው (State, party and endowment monopolies crowding out the domestic private sector)። የህወሓትን ኢኮኖሚ ከቻይና የሚለየው አንዱ ዓመራር የግል ክፍሉ ጫጬት መሆኑ ነው። የቻይና የግል ክፍል ከመንግሥቱ ክፍል ጋር ተወዳዳሪ ነው። የቻይና የመካከለኛ መደብ በፍጥነት እያደገ የሄደበት ዋና ምክንያት የግል ክፍሉ ተወዳዳሪ አቅም ስላለው ነው። በኢትዮጵያ ጎሳዊ አድልዎና ሙስና ህብረተሰቡን በሙሉ በክለውታል። ከቻይናና ከቬትናም ጋር ሲነጻፀር፤ በኢትዮጵያ አገር በቀል የሆኑ ግለሰቦች፤ ድርጅቶች እንደልባቸው ለመንቀሳቀስ፤ የውጭ ምንዛሬ፤ ብድር፤ መሬት፤ ፈቃድ ለማግኘት አልቻሉም። ገዢው ፓርቲ በሕግ የበላይነት ስለማያምን፤ ማንኛውም የግል ክፍል የፖለቲካ ታማኝነቱ ከጥያቄ ውስጥ ከገባ፤ በፈቃድ ወይንም በቀረጥ ጫና ሊዘጋ ይችላል። ባጠቃላይ ለማለት የምንችለው፤ "እድገታዊው መንግሥት" የእድገቱን ጥቅም የሰጠው ለፓርቲው ከፍተኛ ባለስልጣናት፤ ቤተሰቦች፤ ምርጥ ለሆኑ የህወሓት ታማኞችና ወዳጆች ነው። ከፍተኛ ገቢና ሃብት የሚገኘው ከመንግሥት ኮንትራት በማግኘት፤ ስልጣን ተጠቅሞ ኮሚሽን በመሰብሰብ ወዘተ ነው። የግል ክፍሉ በጣም ስላላደገ፤ የባለጠጋነት እድል፤ በአብዛኛው፤ የሚወሰነው ከመንግሥት ጋር ባለው ግንኙነት ነው። አድሏዊ በሆነ የመንግሥት ኮንትራት፤ በተለይ፤ በኮንስትራክሽን ስራ፤ ከባዶ ካፒታል ተነስተው ወደ ሚሊዮኔርነትና ቢሊዮኔርነት የደረሱ ግለሰቦች፤ ቤተሰቦች፤ የፓርቲው ምርጥ ድርጅቶች ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ሕዝብ እያራቆቱት፤ እያዳከሙት፤ እየመዘበሩት ነው። አድልዎና ሙስና ስር ሰደዋል፤ ነቀርሳ ሆነዋል። የግል አገር ወለድ ክፍሉ እንዳያድግ፤ እንዳይወዳደር ማነቆ ሆነዋል። መለስ "እድገታዊ መንግሥት" ብሎ የሰየመው አመራር፤ በሚዘገንን ደረጃ ያሳደገው የፖለቲካ ስልጣን የያዙትን፤ ቤተሰቦቻቸውን፤ ታማኝ ወገኖቻቸውን፤ ወዳጆቻቸውንና የራሱን ክልል ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ የእድገቱ ባለቤት አይደለም። የነጻነቱ ባለቤት አይደለም። የወደፊት እድሉ ወሳኝ ወይንም ተጠቃሚ አይደለም። አለመሆኑን ለመረዳት ከተፈለገ መጠየቅ ያለበት "እድገታዊው መንግሥት" የተራውን ሰው ህይወት ለዋጭ ሆኗል ወይንስ አልሆነም?" ነው። "በሬ ወለደ" የሚል በማር የተሸፈነ፤ በመንግሥት የተፈጠረ የእድገት ማስረጃ ለህብረተሰቡ፤ በተለይ ለወጣቱ ትውልድ መስጠትና ሊጋሶችን አሁንም ድጋፍ ስጡ ማለት አያዋጣም። አንድ ምሳሌ እንጥቀስ።

የህወሓት/ኢህአዴግ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ኑሮ አመራር ለአሁንና ለወደፊቱ ትውልድ እድል ከፋች አልሆነም። ኢትዮጵያ ወደ ውጭ የምትልከው ዋናው (Primary Export) የተማረ የሰው ሃይል ነው። የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት ከጎዳቸው መካከል፤ ወጣቱ ትውልድ የመጀመሪያውን ደረጃ ይዟል። የሰው ሃይል ፍልሰት (Human Capital Flight or Braindrain) የኢትዮጵያን ህብረተሰብ እያናጋው ነው። በተለይ በገፍ የሚሰደደው፤ አንድ የመንግሥት መሪ ብቻ የሚያውቀው፤ ወጣቱ ትውልድ ነው። መንግሥቱ ሃይለማሪያም የጀመረውን የስደት ባህል፤ የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት ተከታታይ በሆነ ገጽታ አባብሶታል። ለውጭ ምንዛሬ ማግኛና ተቃዋሚውን ለማብረድ ተጠቅሞበታል። በ2012 መጨረሻ፤ በሳውዲ አረቢያና በገልፍ አገሮች፤ ሁለት ሚሊዮን ስደተኞች ይሰሩ ነበር። 150,000 ሰራተኞች ከሳውዲ አረቢያ ተባረዋል። የህወሓት መንግሥት መብታቸውን አላስከበረም። በአገር ቤት ስራ ስለሌለ፤ በሰሜን ሱዳንና በደቡብ ሱዳን ሁለት ሚሊዮን ስደተኞች ይሰራሉ። በምእራብ አገሮች፤ ቢያንስ ሁለት ሚሊዮን ስደተኞች እና ከስደተኞች የተወለዱ ይሰራሉ። በሌሎች የአፍሪካ ሃገሮች ብዙ መቶ ሽህ ኢትዮጵያዊያን ይኖራሉ የሚል ግምት በየቦታው ይነገራል። የማይካደው የኢትዮጵያ አዲስ ትውልድ እየፈለሰ ነው። ቢያንስ፤ ሰባት በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በተለይ ወጣቱ፤ በስደት ይኖራል። ይህ ስደተኛ የአገሪቱን አቅም ጎድቶታል። ሆኖም፤ አቅሙ በሚፈቅደው መሰረት ወገኑን ይረዳል። የውጭ ምንዛሬ ለመንግሥት ካዝና ያስገባል። ሃቁ የሰው ሃይል ስደት ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል። የተማረውና የሰለጠነው የሰው ኃይል ከአገር በጎርፍ መልክ ስለሚወጣ፤ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ

የመካከለኛ መደብ የሚኖረው በካናዳ፤ በአሜሪካ፤ በአውሮፓ፤ በአውስትራሊያ፤ በኒውዚያላንድ፤ በደቡብ አፍርካና ሌሎች አገሮች ነው።

ልናስተውልው የሚገባን፤ ወደ ውጭ፤ በአመት በብዙ መቶ ሺህ የሚጎርፈው ወጣቱ ትውልድ ነው። ዋና ምክንያቱ በኢትዮጵያ የስራ እድል ስለሌለ ነው። አድሏዊው ኢኮኖሚ በተለይ የጎዳው ወጣቱን ትውልድ ነው። የህወሓት ደጋፊዎች፤ የመለስ "አምላኪዎች" ሊክዱት የማይችሉት ሃቅ የውጭ አገር ተመልካቾች የሚያቀርቡትን ማስረጃ ስለሆነ፤ የ "እድገታዊ መንግሥትን" በደል፤ ቀረብ ብሎ መመርመርና ለዓለም ሕዝብ እውነቱን ማቅረብ ያስፈልጋል። እንዲሁ በስንኩልነትና በቂም በቀልነት፤ እውነቱን ውሸት ነው ማለቱ ለማንም አይጠቅምም። የእድገቱን ውጤት ማየት የሚገባው ከተጠቃሚውና ከተጎዳው ህብረተሰብ አንጻር ነው። ለምሳሌ፤ November 11, 2012፣ አማል አል-ያሲሪ (Amal Al-Yasiri) በ Yemen Times ሰለ ኢትዮጵያ ወጣት ስደተኞች፤ አብዛኛዎቹ ልጃገረዶች፤ እነደዚህ ብላለች። ኢትዮጵያውያን ሰደተኞች የመንን "መሸጋገሪያ አድርገው ሲጠቀሙ" ቆይተዋል። አሁን የስደተኛው ብዛት "በሚያስፈራ" ሁኔታ እያደገ ሄዷል። ለዚህ ዋናው ምክንያት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ "እየወደቀ መሄድ፤ የስራ እድል መጥፋት" ነው። እ.አ.አ. ከ July, 2012 እስከ November, 2012 ብቻ፤ 51,000 ሰደተኞች የመን ገብተዋል። የዴንማርክ የስደተኞች ካውንስል ይህን ማስረጃ ከተቀበለ በኋላ፤ "ሰው እየጫኑ፤ ገንዘብ እያስከፈሉ፤ በጀልባ እያሳፈሩ፤ ወደ የመን ማጓጓዙ አድጓል (Human Trafficking on the Rise)" ይላል። የሚዘገንነው፤ የኢትዮጵያ ስደተኞች ሁኔታ እየተባባሰ እንጅ እየቀነሰ አለመሄዱ ነው። በመንገድ እንዳሉ፤ "የልጃገረዶች ክብር በይፋ እንደሚደፈር፤ ሰደተኞቹ፤ በየመንም ሆነ በሳውዲ አረቢያ ምንም አይነት የሰብአዊ መብት እንደሌላቸው" የታወቀ ነው። በአገር እድል ጠፍቶ ብዙ መቶ ሺህ ኢትዮጲያውያን በያመቱ ለስደተ የሚዳረጉ ከሆነ፤ ነውም፤ "እድገታዊው መንግሥት" አዲሱን ትውልድ ለሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን "የጉልበት ባርነት" (21st century slave labor) ዳርጎታል። ስርአቱ በጎሳ ዙሪያ አድሏዊ ቢሆንም ችግሩ ያልደረሰበት የለም ። በስደት መስፈርት ሲታይ ሁሉም እኩል ሆኗል። መንግሥትና ደጋፊዎች ይህን ይክዳሉ። ሆኖም፤ ውሸት ነው ለማለት የሞራል ብቃት የላቸውም። (TPLF/EPRDF advocates and supporters are entitled to their own stories; but they cannot speak for those whose rights are violated or deny well documented facts).

በሁሉም መስፈርት የመንግሥት መሪዎች በተደጋጋሚ ይዋሻሉ። የሚዋሹ ከሆነ፤ ደጋፊዎቻቸውም ፈለግ ተከትለው ቢዋሹ አያስገርምም። አፋኝ፤ ጨቋኝ አገዛዝ በመጀመሪያ ከሚቀብራቸው ነገሮች መካከል እውነትን፤ ሃቅን፤ ጨዋነትን፤ አርቆ አስተዋይነትን፤ ለሰው ክብር ማሰብን ነው። ነጻ ፕሬስ የማይፈቅደው እውነቱ እንዳይነገር ስለሚፈልግ ነው። ለምን? እድገትን የሚያየው ከግለሰብ፤ ከህብረተሰብ፤ ከተከታታይ ትውልድ መብትና ከአስቃቂ ድህነት ነጻ መውጣት፤ ከኑሮው መሻሻል፤ ከክብሩና ማእረጉ አይደለም። የሚመለከተው በጠባቡ ነው። ለምሳሌ፤ ከኪራይ ሰብሳቢነትና-- ማለትም፤ ስልጣን ተጠቅሞ በታክስ፤ በጉቦ፤ በሙስና፤ በኮሚሽን ወዘተ፤ ለግል ጥቅም ገንዘብና ሌላ ሃብት ማከማቸት ማለታችን ነው-- ሳይሰሩ፤ ሳይፈጥሩ በፖለቲካ ስልጣን ከበርቴ መሆንን ነው። የሚያዩበት መነጸር አንድ ነው። ከገንዘብ፤ ከሃብት፤ ከራስና ከቤተሰብ ኑሮ መሻሻል አንጻር። ግልጽነት፤ ውድድር፤ ለሕዝብ መገዛት፤ ለሕዝብ ሃላፊ መሆን፤ ያለውን የልማት ጥቅም አያዩም። ካዩም እንዳላዩ ያልፏቸዋል። አቋሙን፤ አገዛዙን ለማቆየት ሲሉ መዋሸትን እንደ ባህል ያስተጋቡታል። ለአዲሱ ትውልድ ያስተላልፉታል። ኢትዮጵያ፤ ተአምራዊ የሆነ የእርሻ እድገት አሳይታለች ተብሎ ተነግሯል። የዓለም ባንክ ኢኮኖሚስቶች ተገርመው፤ "ኢትዮጵያ፤ መንግሥት በሚለው ደረጃ የእርሻ ምርት ካሳደገች፤ በዚህ ዓለም ታይቶ የማይታወቅ እምርታዊ ለውጥ ስኬታማ አድርጋለች ማለት ነው። ችግሩ፤ የእርሻ ምርት ከሕዝብ እድገት ጋር ጎን ለጎን ሊያድግ አልቻለም" ብለዋል። ለዚህ አቢይ ማስረጃው፤ ዛሬ ከአምስት እስከ አስር ሚሊዪን የሚገመቱ ኢትዮጵያውያን የሚደጎሙት በለጋስ መንግስታትና አበዳሪዎች ነው።

እአአ በ2013 ጥቂት ወራቶች፤ ባንኮች የውጭ ምንዛሬ እጥረት አለ። የግል ባለሃብቶች "የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት እየተቸገርን ነው" እያሉ ይበሳጩ ነበር። የአይኤምኤፍ ዘገባም የሚያሳየው፤ የኢትዮጵያ "የውጭ ምንዛሬ ከሚያሳስብ፤ የአንድ ነጥብ ስምንት ወራት ብቻ የውጭ እቃ የሚያስሸምት መተማመኛ ደረጃ ላይ ደርሷል። ቢያንስ፤ የሶስት ወራት ተቀማጭ (ሪዘርብ) ያስፈልጋል" የሚል ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ነበር። አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር፤ አቶ ሃይለማሪያም ደሳለኝ፤ የመለስን ፈለግ ተከትሎ ለፓርላማ ቀርቦ ሲናገር፤ "የውጭ ምንዛሬ እጥረት የለም" ብሏል። በንግድ የሚገኘው የውጭ ምንዛሬ ሰባት በመቶ ቀንሷል። ከሶስት ቢሊዮን ዶላር በላይ ከሃገር በድብቅ ሸሽቷል። እንዴት ችግር የለም ለማለት እንደደፈረ አንባቢው ይፍረድ። ቁም ነገሩ፤ በመንግሥት ባለስልጣናት ስለ ኢኮኖሚው የሚነገረው የፖለቲካ አነጋገር ነው። እውነተኛውን ስእል ለህብረተሰቡ በሃቅ፤ በእውነት፤ በሚዛናዊነት ማስረዳት ከቀረ ቆይቷል። መለስ ለዚህ ተሰጦ ነበረው። ለጋሶችን አሳምኖ ነበር። ሃይለማሪያም ደሳለኝ በቅርቡ "የፖለቲካ እስረኞች የሉም" ብሎ ሲናገር ውሸት እንደተራ ነገር ተደጋጋሚ የሆነ መሰረት መያዙን ያሳያል።

ባጭሩ፤ ለቁጥጥር አመች የሆነው የ“እድገታዊው መንግሥት” ለአብዛኛው የኢትዮጵያ ድሃ ሕዝብ (For the Vast Majority of Ethiopians) ህይወት ለዋጭ ጥቅም አላመጣም። ለዚህ ድምዳሜ ብዙ ማስረጃዎች አሉ። በቅርቡ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ሁኔታ ትንተና ያቀረበችው የፈረንሳይ ጋዜጠኛና ፀሃፊ ሪኔ ሌፎርት ብዙ ኢትዮጵያውያን ታዛቢዎችን አነጋግራ የደረሰችበት ግንዛቤ እኛና ሌሎች ታዛቢዎች ከሚሉት አይለይም። መሰረት ልማት በሰፊው ይካሄዳል ለሚለው ታዛቢዎች “ለእኛ ምን ፋይዳ አለው፤ መንገዱና ህንጻው ምግብ አይሆን፤ አንተኛበት” ወዘተ የሚል መልስ ሰጥተዋታል። Rene’ Lefort, Open Democracy, “Ethiopia: a leadership in disarray,” July 5, 2014, reports that “The Party’s pinnacle is at least in disarray…the state economy is no longer adequate for driving growth; the private sector needs the scope to take up the slack.” ገዢው ፓርቲ የኢትዮጵያ የግል ክፍል እንዲያብብ አይፈልግም። ዋናው ምክንያት፤ የግል ክፍሉ እያደገ ከሄደ ለገዢው ፓርቲ የበላይነት ተወዳዳሪ ይሆናል። ካደገ ብዙ ኢትዮጵያውያን ይቀጥራል። ከቀጠረ የመካከለኛው መደብ እየሰፋ ይሄዳል። ይኼ ሲሆን፤ የመካከለኛው መደብ ለመብቱ መታገል ይጀምራል። ከፍተኛ ውድድር ካለ ጥቂቶች ለሃብት ያላቸው ስግብግብነት ከፍትነት ይዘጋል፤ ቢያንስ ተወዳዳሪ ይኖራል። ሌሎች ታዛቢዎችም የሚሉት የኼኑ ነው። በዓለም አቀፉ የኢኮኖሚ መድረክ (World Economic Forum: global competitiveness report: 2012-2013) ዘገባ፤ የአገሮችን ህብረተሰብ በኑሮ የሚለይ ጤናማነት፤ የውስጥ ውድድር የእድገት አውታሮችን (Pillars) በመጠቀም የኢትዮጵያን የእድገት ደረጃ በትክክል አስቀምጦታል። ዋናው መመዘኛ የጥቂቶች በድሎት መኖር አይደለም። ገንዘብ ታትሞም፤ ተበድሮም፤ ተሰርቆም ይገኛል። ዋናው መለኪያ፤ የአፍሪካ መንግስታት ነጻ ከሆኑ በኋላ፤ በአሩሻ፤ ታንዛኒያ በ 1967 ያወጡት ጥበብ የያዘ መስፈርት (The Arusha Declration) ነው። መስፈርቱ ማእከል ያደረገው የሕዝብንና የግለሰቦችን  የኑሮ መሻሻል (Human Development)  ነበር። እንዲህ ይላል። “የአንድን አገር ልማት የሚወስነው ሕዝቡ ነው። እድገቱ ስለ ህዝብ ኑሮ መሻሻል ነው። ስለገንዘብ (ኪራይ ሰብሳቢነት(Political elite extraction of rent from society) አይደለም።” በሌላ አነጋገር የገንዘብ ጭማሬና የእርዳታ መጨመር ብቻውንና (Money in circulation) የጥቂቶች ከፖለቲካ ስልጣን የተገኘ የሃብት ክምችት ወይንም ባለጠጋነት አይደለም:: ኢኮኖሚው በጥቂት አዲስ ከስልጣን ጋር የተቆራኙ ከበርቴዎች ተይዟል። በአብዛኛው እድገቱ ዘጠና በመቶ የሚሆነውን ሕዝብ ህይወት አመርቂ በሆነ መልክ ባይለውጠውም፤ ብዙ አዲስ ኃብታሞች ፈጥሯል። የነፍስ ወከፍ ገቢ በዓመት $470 በሆነው በኢትዮጵያ የአዲስ ሚሊዮኔሮች ቁጥር ከ1,300 (2007) ወደ 2,700 (2013) አድጓል፤ የተራው ሰው ኑሮ ምንም አልተሻሻለም፤ እንዲያውም ተባብሷል (The Guardian, April 28, 2014). “There are a few rich people at the top but the majority of the people are at the bottom.” የመካከለኛው መደብ እንደ አዲስ ሚሊዮኔሮች አላደገም። ይህ የተዛባ ኑሮና ገቢ አደጋዎችን ፈጥሯል። ሰው ሰርቶ፤ ደክሞ፤ አምርቶ፤ በራሱ ጥሮና ግሮ ሃብታም ቢሆን ምንም አያጠያይቅም። ይኼ ሁኔታ በኢትዮጵያ መኖሩ ያከራክራል። ሚሊዮኔር ለመሆን ከገዢው ፓርቲ ጋር ቁርኝት አስፈላጊ ነው።

ብዙ ቢሊዮን ዶላር ተሰርቋል። ከአገር ሸሽቷል። ገንዘቡ ሲመዘበርና ከአገር ሲወጣ ለአብዛኛው ህብረተሰብ ጉዳት ያመጣል። ሁሉን አሳታፊ በሆነ ኢኮኖሚ፤ የገንዘብ ዝውውር ቢያድግ (Money in Circulation)ና ለህብረተሰቡ ጥቅም ቢውል የእድገቱ ውጤት ነው ለማለት ያስችላል።  ህብረተሰቡ ይሰራል። ያመርታል። ይሸምታል። ይሸጣል። አገልግሎት ይሰጣል። ይቀበላል። በሃገሩ ኮርቶ ይኖራል። ለክፉ ጊዜ ይቆጥባል። ልጆቹን ያስተምራል። ቤት ይሰራል ወዘተ። የአፍሪካ መንግስታት ያስጠነቀቁት፤ በእርዳታ ሆነ በሌላ የሚገኝ “ገንዘብ” ቢግበሰበስ፤ ለህብረተሰቡ አገልግሎት፤ ለኑሮው መሻሻል፤ ለነፍስ ወከፍ ገቢ እድገት፤ ለድህነት መቀነስ ተግባሮች ካልዋለ ጥቅሙ የጥቂቶችን ኪስ መሙላት ይሆናል የሚል ነው። ከዚያ ወዲህ የወጡ ዓለም አቀፍ አመታዊ የእድገት መመዘኛዎች የሚለኩት፤ የግለሰቦችንና የህብረተሰቡን ከድህነት ነጻ መውጣት፤ የተሻለ ገቢንና ኑሮን፤ ከፍርሃት ዓለም መላቀቅን ወዘተ ነው። ዓለም አቀፉ የኢኮኖሚ ጤናማዊ ውድድር ዘገባ፤ ስለ ኢትዮጵያ የደመደመው እነደሚከተለው ነው።

በሕግ የበላይነትና በሚዛናዊና ወይንም መልካም አስተረዳደር፤ በነጻነት፤ በሙስና መከሰት፤ አለመከሰት፤ ስለውጭ ምንዛሬ በምስጢር ከአገር ተደብቆ መውጣት፤ ወይንም ንግድን ተጠቅሞ ዋጋን በመደለዝ ማጭበርበር፤ (Under Invoicing or Over Invoicing and the like) ኢትዮጵያ ከመቶ አርባ አራት አገሮች መቶ አሥራ ስምንተኛ ናት። የሕግ የበላይነት፤ መልካም አስተዳደር፤ የሉም። ሙስና፤ አድልዎና ከህግ ውጭ የሚወጣ የውጭ ምንዛሬ እያደገ ሄዷል። ወደ ውጭ የሚላከውን እቃ አይቶ ከዚህ በአመት የሚገኘው ገቢ ምን ያህል ነው? ለመሰረተ ልማት በአመት የሚወጣው ምን ያህል ነው? ከስደተኞች የሚገኘው ምን ያህል ነው? ከብድርስ ብሎ መርምሮ ወደ ውጭ የሚሸሸውን ገንዘብ ማመሳከር ይቻላል። የሚሸሸው ገንዘብ ከአገር ከሚላከው እቃ የሚገኝ ገቢ ብቻ ነው ለማለት የኢትዮጵያ ኤክስፖርት ከፍተኛ ነው ብሎ መደምደም የሚያስፈልግ ማስረጃ መኖር አለበት። ዝቅተኛ ስለሆነ፤ አብዛኛው የሚሰረቀው ገንዘብ ሊገኝ የሚችለው ከመንግሥት ካዝናና ስደተኛው ከሚልከው የውጭ ምንዛሬ ነው። የሙስንናው ችግር ነቀርሳ ከሚመስል ደረጃ ስለደረሰ ለሙስና አንድ ምእራፍ ሰጥተነዋል።

በመሰረተ ልማት ሲታይ፤ ምንም እንኳን “እድገታዊው መንግሥት” ብዙ ጥረት ማድረጉ ባይካድም- በመንገድ፤ በድልድይ፤ በሃዲድ ስራዎች መስፋፋት--አገራዊ የሆነ የግል ክፍል በማስፋፋት፤ ኢትዮጵያ ከመቶ አርባ አራት አገሮች መቶ አስራ ዘጠንኛ ናት። በክልሎች መካከል የከፋ የልማት ልዩነቶች ይታያሉ። ትግራይና ጋምቤላ አይወዳደሩም። የጎሳ አድልዎ አለ። የቤርተልስማን ስቲፉን ተሃድሶ ዘገባ (Bertelsmann Stitfune Transformation Index (BTI)-Ethiopia country report 2012) የተባበሩት መንግስታትን ማስረጃዎችና የራሱን ዘገባ መሰረት አድርጎ፤ “ኢትዮጵያ አሁንም በዓለም ዝቅተኛ እድገት ከሚታይባቸው አንዷ ናት። መንግሥት በአመት ከአስር እስከ አስራ አንድ በመቶ እያደገች ነው ብሎ ቢናገርም በ2010 እድገቷ በንጥር ሲታይ ከሁለት በመቶ በላይ አይሆንም (2 percent)” በማለት ደምድሟል። 1/

ይህን አንቀበልም ከማለታችን በፊት ከዚህ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ያስቻሉትን ምክንያቶች እንይ። የአንድ አገር የእድገት ዘላቂነትና ሚዛናዊነት የሚለካው አመራሩ (ፖሊሲው) ቅድመ ሁኔታዎችን አመቻች፤ ለሁሉም አሳታፊና አገልጋሽ፤ ግልጽነት ያለው፤ በሕግ የሚገዛ ሲሆን ነው። በዚህ መለኪያ፤ ኢትዮጵያ ከአገሮች መቶ አስራ አራተኛ ናት። የኢኮኖሚ አመራር ግልጽነት የለውም። አድሏዊ ነው። አገር ወለድ ለሆኑ ተቋሞች ድጋፍ አይሰጥም። ውድድር የለም። በብሄር/ብሄረሰብ ዙሪያ ሲታይ ጎሳ-ተኮር “ከፋፍለህ ግዛው” ለአገሪቱና ለህብረተሰቡ እድገት ጫና ሆኗል። እርጋታን ለመግዛት ሲባል የሚፈሰው ወጭ ከአገሪቱ አቅም በላይ ነው። ሕዝብ ለማፈንና ለመቆጣጠር ሲባል ለልማት የሚወጣውን ገንዘብ ለቁጥጥር ማዋል የጥሩ አገዛዝ መስፈርት ሊሆን አይችልም። የታፈነ፤ ጤናማ ያልሆነ ግለሰብ፤ ህብረተሰብ፤ ለመስራት፤ ለማምረት፤ ለመወዳደር፤ ለመደራደር፤ አይችልም። የጤና ጥበቃ መሰረተ ልማት ተስፋፍቷል ቢባልም፤ ዘገባው ኢትዮጵያ አሁንም መቶ አስራ ስድስተኛ ናት። “የጤና አገልግሎት መሰረተ ልማት ኋላ ቀር ነው” ብሎ ደምድሟል። በተለይ የሚሰቃዩት፤ እናቶች፤ ህጻናት፤ ልጃገረዶች፤ ሽማግሌዎች ናቸው። በጤና አገልግሎት የሰለጠነው የሰው ሃይል በብዛት ወደ ውጭ ይሰደዳል። ለስደቱ ዋና ምክንያት የሆነው ስርአቱ ነው። የትምኅርት ስርጭትና ጥራት ለዘላቂና ለፍትሃዊ እድገት ቁልፍ ነው። በጥራት ሲታይ የኢትዮጵያ የትምኅርት ደረጃ መቶ ሰላሳ አራተኛ ነው። መንግሥት ለጥራት ችግር መፍትሄ አላገኘለትም። ያተኮረው የእርዳታ ድርጅቶች የሚፈልጉትን ለማሟላት፤ የስልጣን ቆይታውን ለማረጋገጥ፤ ትምኅርት ተስፋፍቷል ከሚለው ላይ ነው። የተማረውን ክፍል ተንከባክቦ በማያዝ ፋንታ፤ ለስደት ዳርጎታል። የተማረ፤ ልምድ ያለው የሰው ሃይል ከሌለ እድገቱን ይጎዳዋል። የጥራት ትምኅርት ያተኮረው ከትግራይ ተወላጆች ላይ ነው።

የአገር ውስጥ ገበያ ግልጽነት የለውም። ጫና ያለበት፤ ጥቂት የመንግሥት፤ የገዢው ፓርቲ፤ የባለስልጣን ቤተሰቦች የሚቆጣጠሩት ሆኗል። ቅልጥፍና የለውም። ዘገባው፤ ኢትዮጵያ መቶ ሃያኛ ደረጃ ይዛለች የሚል ነው። በብድርና በውጭ ምንዛሬ፤ በቤት መስሪያ፤ በስራ ማስፋፊያ፤ በመሬት ባለቤትነት ባለው ችግርና በአድልዎ ኢትዮጵያ መቶ ሃያ ዘጠንኛ ደረጃን ይዛለች።

የመስራት፤ እውቀትን ወደ ተግባር የመለወጥ፤ እንደልብ የመንቀሳቀስ መብት የለም። ለውጥ ለማምጣት አስቸጋሪ ነው። መሻሻል (Innovation) ታፍኗል። የኢኮኖሚው መዋቅር እንዳለ ይቆያል። የገጠሩ ኢኮኖሚ ወደ ዘመናዊነት አይለወጥም። የአገሪቱን እድገት ይጎትተዋል። ዘገባው፤ ኢትዮጵያ፤ መቶ አስራ አራተኛ ናት ብሏል። ሲደመድም፤ “የኢትዮጵያ አንኳር ችግሮች፤ የዋጋ ግሽበት፤ የአመራር አስተማማኝ አለመሆን፤ የገዢው ፓርቲ አምባገነንነት፤ የመንግሥት ከፍተኛ ባለስልጣናት፤ ቤተሰቦች፤ ታማኝ ግለሰቦችና ወዳጆች፤ ድርጅቶች፤ የኢኮኖሚ የበላይነት (Monopoly and political elite capture) መሆናቸውን ጠቅሷል። ታይቶ የማይታወቅ ጎሳዊ አድልዎ፤ ከቁጥጥር የወጣ ጉርሻ፤ ጉቦና ሙስኛነት፤ ግልጽነትና ሚዛናዊነት የሌለው የብድር፤ የፈቃድ፤ የታክስ አስተዳደር፤ ቅልጥፍና የሌለውና ውድ የመንግሥት አገልግሎት፤ ወደኋላ የቀረ የጤና አገልግሎት፤ የከፍተኛ ትምኅርት ጥራት ማነስ፤ በግል ክፍሉ ላይ ያለው ቁጥጥር” ከሚያሳስብ ደረጃ ላይ መድረሳቸውን አመልክቷል። 2/

ከላይ የተጠቀሱት አገዛዝ ወለድ የሆኑ፤ ገዢው ፓርቲ ብቻውን የማይፈታቸው መሰናክሎች፤ በህወሓት/ኢህአዴግ የፖለቲካ አፋኝ፤ ግፈኛ፤ አግላይ፤ አመራር የተፈጠሩ ናቸው። ስለዚህ፤ “እድገታዊ መንግሥት” የሚለው ፍልስፍና ለአብዛኛው ህብረተሰብ የኑሮ፤ የገቢ፤ የመኖሪያ ቤት፤ የጤና፤ የትምኅርት ወዘተ የመሻሻል ህልም፤ ተስፋና ጥረት መፍትሄ ለማምጣት አለመቻሉን ያመለክታሉ። ተጨማሪ ማስረጃ ካስፈለግ--መንግሥትና ደጋፊዎች ሁልጊዜ በጭፍን የለም ብለው ስለሚክዱ-- እንደ ፍሪደም ሃውስ፤ የተባበሩት መንግስታት የእድገት ድርጅት፤ ሞ-ኢብራሂም የአገዛዝ መለኪያ፤ የሰብአዊ መብቶች ድርጅት ደጋግመው ሁኔታዎች በመሻሻል ፋንታ እየተባባሱ እንደሄዱ ተናግረዋል። ከእነዚህ፤ Freedom House: freedom in the world, 2012 በተባለው አመታዊ ዘገባው፤ በ2011 ከ 195 አገሮች፤ 87ቱ “በሙሉ ነጻ ሆነዋል። 48ቱ ነጻ አይደሉም። ከእነዚህ ኢትዮጵያ ትገኝበታለች” ይላል። “ነጻ አለመሆን” ምን ማለት

ነው? ከእድገት ጋር ምን አገናኘው" የሚለውን ጥያቄ ባጭሩ እንይ። አንባቢው ከዘነጋው፤ የመለስ መንግሥት ይለው የነበረው-- የቻይናን የእድገት አርአያ አድርጎ በመውሰድ-- "በእድገትና በነጻነት መካከል፤ ምንም ግንኙነት የለም ነው። እድገት ያለነጻነት ይቻላል። ነጻነትና ዲሞክራሲ እድገቱ እያደገ ሲሄድ እውን ይሆናሉ" የሚል ፍልስፍና ነበር። ይህን ፍልስፍና "የመለስ አምላኪዎች" አጠንክረው እያራመዱት ነው። የዚህን አድሏዊ ውጤቱ በመግቢያው አሳይተናል። መጀመሪያ፤ ፍልስፍናው የሚያጠናክረው የአንድ ጎሳዊ የሆነ ፖለቲካ ፓርቲን ፍጹም የበላይነት ነው። ይህ የበላይነት ማን ባለጠጋ፤ ማን ደሃ፤ ማን ልጁን አስተማሪ፤ ማን ልጁን ለስደት ላኪ እነደሚሆን እየወሰነ ነው። የማንጠራጠረው፤ ዛሬ፤ የኢትዮጵያ እድገት በለጋሶች የተደገፈ፤ በፖለቲካ የሚመራና የሚወሰን መሆኑን ነው። ፍጹም ጎሳዊ ነው። አብዮታዊ "ዲሞክራሲ" የተባለው ለዚህ ነው። ማን አብዮታዊ እንደሆነ የሚፈርጀው ፓርቲው ነው። የህወሓት/ኢህአዴግ መስራቾች ያለፉትን የኢትዮጵያ መንግሥታት ስርአቶች አንቀበልም ብለው መተኪያ  አድርገው "አዲስ አገዛዝ" የፈጠሩት፤ ሶሻሊዝም፤ ኮሙኒዝም፤ ካፒታሊዝም፤ ስቴት ካፒታሊዝም፤ ፓርሊሜንታሪ ዲሞክራሲ፤ እውነተኛ፤ ሕዝብ ወካይ ፌደራል ዲሞክራሲ ወዘተ አይደለም። የፈጠሩት የተለየ፤ የብሄር/ብሄረሰብና ሕዝቦች የፖለቲካ አለቃዎችን (Ethnic Political Elites) የሚወክልና ጥቅማቸውን የሚያገለግል አመራር ነው። ጠባብ ጎሰኛነት፤ ፓርቲ፤ መንግሥትና ተቋሞች አንድ መሆን አለባቸው። በፓርቲውና በመንግሥት መካከል ምንም ልዩነት የለም። ህገመንግሥቱ ማገልገል ያለበት ይህን አህዳዊ (የተያያዘ) የአገዛዝ ሰንሰለት ነው የሚል ነው። ስለዚህ፤ ሌላው መፈናፈኛ የለውም።

ፍሪደም ሃውስ ነጻ የሆነ አገዛዝ የሚለው "የፖለቲካው መስክ ለፖለቲካ ውድድር ክፍት ሲሆን ነው።  የሰው ክብርና የሰብአዊ መብቶች በህግ ሲከበሩ ነው። ከመንግስት ቁጥጥር ነጻ የሆነ መገናኛ ብዙሃን ወይንም ፕሬስ ሲኖር ነው። የማህበረሰብ ድርጅቶች በነጻ ሲንቀሳቀሱ ነው። አድልዎ የሌለበት፤ ውድድር ያለበት የኢኮኖሚ አመራር ሲኖር ነው። ይህን መሰረት በማድረግ፤ ፍሪደም ሃውስ እንዲህ ብሏል። "በአለም ከሚገኙ፤ የግለሰብ/የህብረተሰብ ነጻነት ደረጃ በጣም ዝቅ ካለባቸው አገሮች መካከል ኢትዮጵያ፤ ጋምቢያ፤ ቡሩንዲ፤ ሯዋንዳና ጅቡቲ ይገኙበታል። በእነዚህ፤ የሕግ የበላይነት፤ የመናገር፤ የመሰብሰብ፤ የመወዳደር መብቶች ታግደዋል። በኢትዮጵያ የነጻነት፤ የመብት ሁኔታዎች እየተባባሱ፤ ወደታች ወርደዋል።  ዋናው ምክንያትት ላለፉት አስር አመታት፤ ጠቅላይ ሚንስትር መለስ ዜናዊ፤ አምባገነናዊ አገዛዝን ሆነ ብሎ ከስራ ላይ ስላዋለ ነው። በ"ጸረ-ሽብርተኛነት"ሕግ የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን፤ ጋዜጠኞችን፤ ሌሎች ተቃዋሚዎችን አስሯል። አሳዷል። ከስራቸው፤ ከቤተሰባቸውና ከቤታቸው አባሯል"። የመለስ ኢትዮጵያ፤ ከኤርትራ የተሻለ "ክብር" ተቀብላለች። ከጋና ለመድረስ ህልም ሆኖባታል። ጋና "በሙሉ ነጻ" ከሚባሉ አገሮች አንዷ ሆናለች። ከጥቂት አመታት በፊት በአምባገነኖች ትገዛ ነበር። ዛሪ ህብረተሰቧ በሙሉ የእድገቱ ተካፋይ ነው። ነጻ የፖለቲካ ውድድር አለ። ነጻ የመገናኛ ብዙሃን አለ። የኢኮኖሚ ውድድር አለ። ጠባብ ብሄርተኛነትና በብሄር ለፖለቲካ ስልጣን መደራጀት በህገመንግስቱ ተከልክሏል።

በአንጻሩ፤ በርቴልስማን ስለ ኢትዮጵያ ኢኮኖሚ መዋቅር ኋላ ቀርነት ያወጣው ዘገባ እንዲህ ብሎ ደምድሟል። "ኢትዮጵያ አሁንም፤ የዘመናዊ ኢኮኖሚ ማእከል የላትም። የሚያይለው የገጠሩ ክፍል እጅግ ኋላ ቀር ነው። (No Center of Modernization and a huge backward rural sector). መንግሥቱ ድህነትን ለመቀነስ ያደረገው ጥረት እኛ ይህን ምርምር ባደረግንበት ወቅት መሻሻል አላሳየም። (Government's efforts to alleviate poverty show little effect over the review period (2012)." ዘገባው የተባበሩት መንግስታት የእድገት ድርጅቶች ካወጡት አይለይም። የሚለየው፤ በፖለቲካው የብሄር ፌደራል አወቃቀርና አስተዳደር ላይ ነው። የተባበሩት መንግስታት፤ የዓለም ባንክና ሌሎች ፖለቲካን አንነካም ከሚሉት የሚለየው እነደዚህ በማለቱ ነው። "የብሄረሰብ ፌደራል አወቃቀር ህብረተሰቡንና አገሪቱን በማዋሃድ በኩል ወድቋል። እንዲያውም ከተፈለገው ሃገራዊነት ወደ ተጻራሪው አመዝኗል። (Ethnic federalism has failed in resolving national integration; the opposite has happened)." ሌላው በብዙ ማስረጃ የሚደገፈው፤ "መለስ ያጎለመሰው የራሱን ብሄረሰብ፤ ትግሬዎችን ነው። ይህን ያደረገው ሌሎችን በማዳከም፤ ዋጋ በማስከፈል ነው። (Meles empowered Tigreans at the expense of others)" ያለው ነው። 3/

እየተባባሰ የሄደው፤ የሃብት፤ የገቢ፤ የኑሮ፤ የስራ እድል ልዩነት፤ የከፍተኛና ጥራት ያለው ትምኅርት ክፍተት፤ የጤና፤ የቴክኖሎጂ ስርጭት፤ የክልል እድገት ወዘተ ልዩነቶች በተመሳሳይ ተገልጸዋል። የፖለቲካ ስልጣን የበላይነት ውጤቶች ናቸው። <u>የተወሰኑ የትግራይ ተወላጅ ቤተሰቦች፤ ወዳጆች፤ ደጋፊዎች፤ ታማኞችና የራሱን ክልል  ለይቶ</u> ለፖለቲካ ስልጣን ከሰጠ፤ ውጤቱ የኢኮኖሚ የበላይነት ነው። የገቢና የሃብት ልዩነት እየባሰ መሄዱ ነው። ይህ የአንድ አናሳ ብሄር ቡድን የበላይነት በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ ብሄር ነክ የሆኑ የኑሮ፤ የገቢ፤ የሃብትና የክልል እድገት ልዩነቶች ፈጥሯል። ባለጠጋ የመሆን እድል ከመንግሥት ስልጣን፤ ከኮንትራት፤ ከንግድ ፈቃድ፤ ከመሬት፤ ከብድር፤ ከውጭ ምንዛሬ፤ ከፌደራል ባጀት፤ ከቤት ባለቤትነት ወዘተ በቀላሉ ከማግኘት ጋር የተያያዙ ሆነዋል። የመለስ መንግሥት ለራሱ ቡድንና ክልል ለጋስ፤ ለሌላው ንፉግ ነበር። ሌላው፤ ኦሮሞ ሆነ አማራ፤ አፋር ሆነ ሶማሌ፤ ጉራጌ ሆነ አኝዋክ፤ ወዘተ

እድሉ የሚወሰነው በሙብቱ ሳይሆን፤ በታማኝነቱ ነው። በታማኝነት ኑሮውን ለማሻሻል የሚችለው የተወሰነ፤ በግምገማ ፈተና ያለፈ፤ ታማኝነቱ የተረጋገጠ፤ ሌላውን ለመቆጣጠር የሚደፍር መሆኑ ሊያከራክር አይችልም። የትምኅርት፤ የመቀጠርና ሌላ እድል ያለው ተከታታይ ትውልዱንና ክልሉን ያጠናክራል። ሌለው ኑሮውን ለማሻሻል ራስ ዳሽንን የመውጣት ያህል ጥረት ማድረግ አለበት። አድርጎም፤ እድል ካገኘም ሃብት ካከማቹ ለመድረስ አይችልም፡፡ በአሜሪካ አንድ በሙቶ ሃብታም፤ ዘጠና ዘጠኝ በሙቶ መካከለኛና ደሃ የሆኑ መደቦች ትግልን ያስታውሳል። የኢትዮጵያው የገቢና የኑሮ ልዩነት ከማንም አገር የባሰ መሆኑን ማስረጃው ያመለክታል። ሽራቶን ገብቶ ማን ምን እነደሆነ ማየት ችግሩን እንደ ስእል ያሳያል።

ባጭሩ፤ ዘላቂነትና ፍትሃዊነት ያለው እድገት ያለ ፖለቲካ ተሳትፎና ውድድር፤ ያለ ነጻ መገናኛ ብዙሃን፤ ያለ ሕዝብ የፖለቲካ የበላይነት፤ ያለ ስልጣን ክፍፍል ሊመሰረት አይችልም፡፡ የህወሓት ጠባብ ብሄርተኞች፤ በተለይ፤ ግትሮች (TPLF Diehards) ህብረተሰቡን ወደ አደጋ መርተው ለራሳቸውም አደጋ መፍጠራቸውን አላጤኑትም። በእኛ አመለካከት፤ የመሪዎች ዋና ሃላፊነት ሌሎችን ያለ ምንም አድልዎ መርዳት ነው። የህወሓት የበላይ አመራር ሌላው ቀርቶ በዓለም የሚካሄዱትን ወሳኝ ለውጦች በአንክሮ አልተመለከታቸውም። ሁለት ምሳሌወች። አንድ፤ የቻይና ሕዝብ፤ የመንግስት አመራር ሽግግርን በሚመለከት ነው። ቻይና፤ የኰሙኒስት ፓርቲውን ለአደጋ የሚጋብዙ አገራዊ ችግሮች አሉ። ከእነዚህ፤ "አድልዎና ሙስና፤ የኑሮና የሃብት ልዩነት፤ የሙብት፤ የነጻነት፤ የእውነተኛ ወካይ መንግስት" ጥያቄዎች አለመኖር ይገኙበታል። ህብረተሰቡ፤ ለውጥ (reform) ያስፈልጋል። አለበለዚያ፤ የቻይና አስደናቂ እድገት ይቀንሳል። እርጋታ፤ ሰላም አይኖርም እያለ ነው። ሕዝቡና ፓርቲው ከሚነጋገሩባቸው ለውጦች መካከል የፓርቲውና የመንግሥት ባለስልጣናትና ቤተሰቦቻቸው የያዙትን ሃብት መግለጽ አለባቸው (Public Disclosure of Assets) የሚል ነው። ለዚህ ባለስልጣናት ሃላፊነትና ተጠያቂነት እንዳለባቸው አምነውበታል። ቻይና ይህን የሕዝብ ጥያቄ ለመመለስ ከሞከረች፤ የህወሓት መሪዎች ዕልከኛ፤ እኛን አይመለከተንም ባይነት አያዋጣቸውም። ሁለተኛው ምሳሌ፤ የበርማ አምባገነናዊ አገዛዝ በሕዝብ አመጽ እየተለወጠ ይገኛል የሚል ነው። ለውጡ ጊዜ እንደሚወስድ ይታመናል። የፖለቲካ መስኩ ግን እየተከፈተ ነው። ፕሬዚደንት ኦባማ በርማን በ November 2012 የጎበኘበት ምክንያት ይህን የዲሞክራሲ በር ለማጠናከር ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት እንደዚህ ያለ እድል ለማምጣት ፍላጎት የለውም። የአመራሩን ጥበበኛነት የሚያሳየው ከእነዚህ ለመማር ሲችል ነው። ልክ እንደ በርማ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብም በአገሩ አገዛዝና አስተዳደር የመሳተፍ፤ አገራዊ እድገት የመቀየስ ሙብት አለው። ቅንጅት ያሳየው ሕዝብ ቆርጦ ሲነሳ ምን ለማድረግ እንደሚችል ምልክት ነው። አመራሩ ቢያውቅበት ኖሮ ኢትዮጵያም በርማን የመሆን እድል ነበራት። ገዢው ፓርቲ ይህን እድል ዘግቶታል።

አገር ወለድ የሆነ ልማት ለመገንባት፤ ብሄራዊ የሆነ፤ ሁሉን የሚያሳትፍ የፖለቲካና የማህበረሰብ አመራር ያስፈልጋል። የትምኅርት እድል፤ በብዛትም ሆነ በጥራት፤ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ክፍት መሆን አለበት። የኢንዱስትሪ ማእከል አስፈላጊ ነው። ሆኖም በእቅድ፤ በጥናት፤ አገራዊና ሚዛናዊ በሆነ መንገድ መፈጠር አለበት። ትግራይን የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ማእከል ለማድረግ የሚደረገው የፖለቲካ ሽር ጉድ ያለውን የኢኮኖሚ አድልዎና ወልጋዳነት ያባብሰዋል። አንድ ክልል ያለ ጥናት፤ያለ እቅድ፤ የማንኛውም የእድገት ማእከል ነው ተብሎ በፖለቲካ ከተወሰነ የተዛባውን እድገት በበለጠ ያዛባዋል። ይህ የጎሳ አድልዎ ኢትዮጵያውያንን የሚያይዛቸውን ክር በጣጥሶታል። አደገኛ ነው። አንዱ ብሄር አስገባሪ፤ ሌላው ገባሪ የሆነበት ስርአት ተቀባይነት የለውም። አንዳንዶች እንደሚሉት፤ "የውስጥ ወረራ" ነው። ሚዛናዊ እድገት አያመጣም። ሰላምን ያናጋል። ያለውን የገቢ፤ የሃብት፤ የኑሮ ልዩነት እንደሚያባብሰው አስቀድሞ መገመት ፈላስፋ አያስፈልገውም። "መለስ ለራሱ ጠባብ ቡድን፤ ለራሱ ክልል ብቻ" ያስብ ነበር የሚለውን የአድልዎ ምልክት ማስተካከል ከባሰ አደጋ ያድናል። ባለፉት ሃያ ሶስት አመታት ጎልቶ የሚታየው፤ የጥቂት ቤተሰቦች የጥቅም ቁርኝት ውጤቱ ለአብዛኛው ድህነትና ስደተ መንስኤ መሆኑን መጽሃፉ በማስረጃ ያሳያል። የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ህብረተሰቡን የሚወክል ልማት ያስፈልገዋል።

ኢትዮጵያ፤ የሰው ፍጥረት ማእከል፤ የብዙ ሽህ አመታት ስልጣኔና ታሪክ ማእከል፤ የልዩ ልዩ ሃይማኖቶች ማእከል፤ "የጥቁር ሕዝቦች ነጻነት" ማእከል የነበረች ሃብታም ለመሆን የምትችል አገር ናት። ዛሬ፤ በቁሳቁስ፤ በዲፕሎማሲ፤ በሞራል፤ በምሳሌነት የደገፈቻቸው ከሳሃራ በታች የሚገኙ፤ ቅኝ ገዥዎች ይዘርፏቸው የነበሩ አገሮች አዲስ የእድገት ምእራፍ ከፍተዋል። ለተከታታይ ትውልድ አገር ወለድ የእድገት መሰረት እየጣሉ ነው። እነዚህ፤ የኢትዮጵያን አኩሪ አስተዋጾ የሚያውቁ አገሮች፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ "ደሃ መሆን የለበትም" ይላሉ። ድህነቷ የተፈጥሮ ጥሪት--ወንዞች፤ ዝናብ፤ ለም መሬት፤ ማእደን፤ የታሪክ ቅርሶች፤ ጠንክሮ ለራሱና ለአገሩ የሚሰራ ሕዝብ-- ሰለሌላት አይደለም። የልማት ጥሪቶች አሏት። ክፍተቱ፤ ለመላው ህብረተሰብ የቆመ፤ ሁሉን አሳታፊ የሆነ፤ በእኩልነት፤ በሕግ የበላይነት የሚያምን የፖለቲካ አመራር አለመኖሩ ነው። ይህ የፖለቲካ አጣብቂኝ (Crisis) የኢኮኖሚውን ማነቆዎች አይፈታም።

"እድገት አለ" ቢባልም፤ ፍትሃዊ ልማት የለም። የሰላም፤ አብሮ የመኖር፤ አብሮ የማደግ፤ የእውነተኛ ሕዝብ አሳታፊ አገዛዝ ጥሪ እጅግ አስቸኳይ የሚሆነው ያለፈውና የአሁኑ አገዛዝ ማነቆነት የሃገሪቱን እድገት ስለገታው ነው። ኢትዮጵያ በስደተኛ ሕዝቧ የምትታወቅበት ከስደተኛው የመጣ ውሳኔ ውጤት አይደለም። በኃይለ ሥላሴ ዘመን መንግሥት፤ ለከፍተኛ ትምህርት ውጭ የተላኩ ኢትዮጵያውያን ትምህርታቸውን እንደጨረሱ "ዲግሪየን ላኩልኝ" ብለው አገራቸውን ለማገልገል ይመለሱ ነበር። ዛሬ፤ የተማረው፤ ዲግሪውን እንዳገኘ፤ ወደየትኛው ዓለም ክፍል ልሰደድ የሚልበት ዘመን ሆኗል። ለዚህ "ተምረህ ተሰደድ፤ አገርህ ውስጥ እድል የለህም" ለሚል ስርአት ዋናው ተጠያቂ የህወሓት/ኢህአዴግ ጠባብ ጎሰኛና ብሄርተኛ አመራር ነው። አስኳሉ ችግር የመንግሥት ስነ ሥርዓት ነው ካልን፤ በበኩላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች፤ የማህበረሰብ ስብስቦችና አገር ወዳድ ግለሰቦች ቀን በቀን በተናጠል የሚደርስባቸውን አሰቃቂ አፈና ለመቋቋም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ቢቻል በመዋሃድ፤ ባይቻል በመተባበር ለመስራት መወሰን አለባቸው። ይኼ ታሪክ የሚጠይቀው ሕብረተሰባዊና አገራዊ ግብ ለነገ የሚተው አይመስለንም። ሌላው ሳይቀር የውጭ መንግሥታትና የሰብአዊ መብት ጠበቃ ድርጅቶች ደጋግመው የሚያሳስቡት "ተባበሩ፤ በአንድነት ለአንድ ዓላማ ስሩ፤ አለበለዚያ የሚያዳምጣችሁ የለም" ነው። ከዚህ ውጭ "ተቃዋሚ ነኝ ብሎ በተናጠል መስራት" ቂልነት ነው። ከሰርጎ ገብነት አይለይም። አያዋጣም።

ይህ መጽሃፍ የመግቢያውን መሰረተ ሃሳብ ፈለግ ተከትሎ ልዩ ልዩ አበይት የሆኑ፤ ከጠባብ ጎሰኛነት አመራር (ፖሊሲ) የመነጩ የፖለቲካ ኢኮኖሚና የማህበረሰብ ማነቆዎችን (Governance Hurdles) በማስረጃ ይተነትናል። ገንቢ የሆኑ የለውጥ አቅጣጫዎችን ለውይይት፤ ለተከታታይ ትውልድና ለታሪክ ያቀርባል።

## ምእራፍ አንድ

### ከመለስ ባሻገር፤ የማይገኝ እድል ወይንስ የባሰ ፈተና?

"ከብዙ ቢሊዮን ዶላር እርዳታ በኋላ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የኑሮ ሁኔታ፤ የዛሬ ሃያ አምስት አመታት በፊት ከነበረው አልተሻሻለም"

The Economist, summer 2010

"የአእምሮና የመንፈስ ችግር አለብን? በአእምሮና በመንፈስ ኃይሉ የማይጠቀም ሕዝብ አህያ ከመንዳት ሊወጣ አይችልም።"

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም--የክሕደት ቁልቁለት

በህወሓት/ኢህአዴግ የሚገዛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የገጠመው ችግር "በአእምሮውና በመንፈሱ ኃይል" እንዳይጠቀም መታገዱ ብቻ አይደለም። ነጻነቱ ተገፎ "አህያ እየነዳ" እንዲኖር ለድህነትና ለረሃብ መዳረጉ ጭምር ነው። ይህ የአገዛዝ በደል ነው እንላለን። የአፍሪካ አገሮች ከአውሮፓውያን ቅኝ አገዛዝ ቀንበር በ 1960ዎቹ አመታት ነጻ ሲወጡ፤ የመጀመሪያና ተቀዳሚ ስራቸው አድርገው የተስማሙበት፤ የተፈጥሮ ሃብታችውን ተጠቅመው በድህነት፤ በረሃብ፤ በድንቁርና፤ በበሽታ፤ በስራ አጥነት ወዘተ የሚሰቃየውን ህብረተሰባቸውን በፍጥነት ነጻ ማውጣት ነበር። ለብዙ አስር አመታት፤ እንደ ናይጀሪያ፤ ጋና፤ ዩጋንዳ፤ ኬንያ፤ ማሊ፤ ሱዳን፤ ግብጽ፤ ቱኒሲያ፤ ሶማሊያ፤ ኢትዮጵያ ወዘተ የመሳሰሉት፤ የመንግሥት ስርአቶቻቸው በመፈንቅለ መንግሥት፤ በሚሊታሪ አምባገነንነት፤ በእርስ በእርስ ጦርነት፤ ሲበከሉ ቆይተዋል። ያላቸውን የተፈጥሮ ሃብት የውጭ መንግስታትና ዓለም አቀፍ ኮርፖሬሽኖች ዘርፈውታል። ብዙ ትሪሊየን ዶላር ሃብት ከአፍሪካ ሸሽቷል። አፍሪካ፤ ለራሷ ሳይሆን፤ ለአውሮጳ አገሮች ልማት አስተዋጽኦ አድርጋለች። ልዩ ልዩ የውጭ ሊቆች የአፍሪካን ከአምባገነን አገዛዝ አፈና፤ጫና የመጣ ድህነትና የአህጉሪቱን ኋላ ቀርነት ሲገልጹ፤ "የአፍሪካ፤ ጥቅም የለሽ፤ ዋጋ የለሽ የብዙ አስር  አመታት" ጥፋት (Africa's Lost Decade (s)  ይሉታል። በእነዚህ አመታት፤ አፍሪካውያን ከቅኝ ገዥዎች ቀንበር ነጻ ሆነው፤ በራሳቸው አምባገነኖች ተሰቃይተዋል። ይህ፤ ከአገዛዝና ከአመራር ድክመት ጋር የተያያዘ ውድቀት፤ ለውጭ እርዳታ መጉረፍ ምክንያት ነበር። ሊጋሶች፤ በአንድ በኩል፤ አፍሪካ ተስፋ የላትም እያሉ፤ በሌላ በኩል በአፍሪካ፤ ያልሞከሩት የእድገት መንገድ የለም። የሶሺሊስት። የኮሙኒስት። የሚሊታሪ አምባገነን። የሊበራል ዲሞክራሲ። የቅይጥ (Mixed Economy)። የአሜሪካ አይነት የነጻ ገበያ (Free Market)። መዋቅራዊ የፖሊሲ ለውጥ። ከላይ ወደታች። ከታች ወደላይ። በእርሻ የተመሰረተ እድገት። በውጭ ንግድ ወዘተ የሚሉ ይገኙበታል። ኢትዮጵያ የእነዚህ የእድገት መለማመጃዎች ማእከል ሆና ቆይታለች። (Laboratory in development and the center of the aid business). ላለፉት ሃያ አንድ አመታት፤ በአገዛዝ በኩል የሚለያት፤ በብሄረሰቦች ልዩነቶችና ለመታረቅ አለመቻል የተመሰረተው "የከፋፍለህ ግዛው" "የክልል" አስተዳደር ስርአት፤ ከፈለገ፤ አንድ ብሄር/ብሄረሰብ ለመገንጠል ይችላል የሚለው አንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝ በህገ መጽደቁ ነው። ለመለያየት ትችላለህ የተባለ ህብረተሰብ ህብረት ሊኖረው አይችልም። እድገቱ ሚዛናዊ ሊሆን አይችልም።ሕብረተሰቡ እንደሚበከል እያየን ነው። ይህ አንቀጽ ለሃገራዊ ውህደት (National social and economic integration) ፤ ለእርጋታ፤ ለተሳትፏዊ እድገት ማነቆ ሆኗል። ባለፉት ሶስት አመታት፤ በተደጋጋሚ የሚወጡ ዘገባዎች፤ ኢትዮጵያ ወደ አለመረጋጋት፤ ያለ ምርኩዝ፤ ያለ ድጋፍ ለመቆም ወደማትችልበት ደረጃ እያመራች ነው (Fragile) ነው በሚል አስጠንቅቀዋል።

የአፍሪካ ልማት ባንክ (the African Development Bank, Briefing Notes for AfDB: long-term strategy 5, March 7, 2012) ባወጣው ሰፊ ትንተና፤ ኢትዮጵያን "ዝቅተኛ ገቢ (low income) ያለባት፤ አለመረጋጋት አደጋ የሚታይባት (fragile") አድርጎ አቅርቧታል። ያለመረጋጋቱና "ያለ ምርኩዝ ለመቆም" አለመቻሏ ምክንያቶች ብዙ ናቸው። ሰማንያ በመቶ (80 percent youth unemployment) የሚሆነው ወጣት ስራ አልባ ወይንም አስተማማኝ ስራ የሌለው መሆኑ አንድ ምሳሌ ነው። ስራ ከያዘው ሰባ ሁለት በመቶው በቀን የሚያገኘው ከሁለት ዶላር በታች እንደሚሆን ባንኩ ያመለክታል። በየመን የሚሰደደው ወዶ አይደለም። እርጋታ ከሌለ፤ ወጣቱ ትውልድ ለስደት ከተዳረገ፤ አገራዊ ውህደትና ፍትሃዊ እድገት (National social and economic integration) አይኖርም። የተዛባ ክልላዊ እድገት (Uneven and inequitable development) በምንም አይወገድም። አንዱ ያድጋል። አንዱ ወደኋላ ይቀራል። አንዱ ሃብታም ይሆናል። ሌላው ደሃ ይሆናል ወይንም በቃኝ ብሎ ይሰደዳል/ይገነጠላል። የጠባብ ጎሰኞቹ ኢኮኖሚ የሚፈጥረው ጣጣ እንደዚህ ያለ ነው። ዛሬ፤ ኢትዮጵያ እድል የሚወሰነው በፖለቲካ ስልጣን ነው። 4/

በሌሎች የአፍሪካ አገሮች ይሆን የነበረው አሁን በኢትዮጵያ በከፋ ሁኔታ ይካሄዳል። ብዙ የአፍሪካ አገሮች የአገዛዛቸውን ስርአት ለውጠዋል። ወይንም በመለወጥ ላይ ይገኛሉ። ጋና ጥሩ ምሳሌ ናት። ለብዙ አስር አመታት የአፍሪካ አገሮች ለማየት ያልቻሉት፤ መንግስታትና የመንግስት መሪዎች፤ ቤተሰቦቻቸው፤ ወይንም ነገድ/ብሄራቸው የኢኮኖሚው እድገት ዋና ተቀዳሚ ተጠቃሚዎች ሆነው ነበር። የፖለቲካ ስልጣን መያዝ፤ ለሃብት ክምችት ዋና መንገድ ነበር። አሁንም፤ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች ቀጥሏል። ብዙ ቢሊዮን ዶላር እየተሰረቀ ወደ ውጭ ይላክ ነበር። አሁንም ቀጥሏል። አበዳሪዎች ሆኑ፤ ህብረተሰቡ፤ ሙስናን፤ አድልዎን፤ የሃብት ሽሽትን አልገቱትም። ሞቡቱ ሴኮ ሴሴ (ዛየር) አምስት ቢሊዮን ዶላር ሰርቋል። የኬንያው አራፕ ሞይ፤ አራት ቢሊዮን ዶላር ሰርቋል። የናይጀሪያ ጀኔራሎችና ቤተሰቦቻቸው የሰረቁት ከአርባ ቢሊዮን ዶላር በላይ ነው። የሞባረክ ቤተሰቦች ሰባ ቢሊዮን ዶላር ሰርቀዋል ተብለው ተከሰዋል። ልክ እንደ ኢትዮጵያ፤ የአፍሪካ መሪዎች ሲሰርቁ በትንሹ አይወሰኑም። ስልጣን በሰላም የማይለቁበት ዋና ምክንያት፤ የኢኮኖሚ፤ የገንዘብ ጥቅማቸው ይቀንሳል። የሰረቁትና ያሸሹት በህግ ይመለሳል ብለው ስለሚፈሩም ጭምር ነው። የስልጣን ሌባ ቢቃኝ የሚባል ቃል አያውቅም። የቤተሰቦች አሰራረቅ ስልት አለው። ይህ ስርቆት እንዳለ ሆኖ፤ የምእራብ ለጋስ አገሮች፤ ዓለም ባንክ፤ የዓለም የገንዘብ ድርጅት፤ የአፍሪካ እድገት ባንክ፤ ኢ.ኢ.አ ከ 1970-2002 ድረስ ብቻ $294 billion ብድር ሰጥተዋል። ባንድ በኩል ብድር ይሰጣሉ። በሌላ በኩል መልሰው ይወስዳሉ። ቁጥጥር የለም። ጉዳቱ በዚህ አይወሰንም። ለጋሶች፤ ሁል ጊዜ፤ በቀጥታ ሆነ፤ በሌላ ዘዴ ያበደሩትን፤ አንዳንድ ጊዜ፤ እጥፍ ያገኛሉ። ሁለት ምሳሌወች። ዓለም ባንክና ሌሎች አበዳሪ ድርጅቶች፤ ለአቅም ግንባታ (Capacity Building) እያሉ፤ ለኢትዮጵያ በአመት ብዙ መቶ ሚሊዮን ዶላር ያወጣሉ። የዚህ ዋና ተጠቃሚዎች የምእራብ አገሮች አማካሪዎች ናቸው። የአፍሪካ አገሮች አሁንም በአመት ከአራት ቢሊዮን ዶላር በላይ ለደሞዝ ይከፍላሉ። የአቅም ግንባታው ውጤት አይታይም። የተማሩ፤ በሁሉ ዘርፍ የሰለጠኑ አፍሪካውያን ሊሰሩት የሚችሉትን--ከአምሳ አመታት በኋላ--ፈረንጆች የሚሰሩበት ምክንያት የፖለቲካ ውሳኔ ነው። የአፍሪካውያን ችሎታ ማነስ አይደለም። ኢትዮጵያን በተመለከተ፤ ሮበርት ኮልደሪሲ፤ ካናዳዊ፤ በዓለም ባንክ የኢኮኖሚ ባለሞያ፤ "የመለስ መንግሥት የኢትዮጵያን ምሁራን፤ የመንግሥት አገልግሎት ድርጅት (the Ethiopian civil service) አፈራርሷል። የፖለቲካ መሳሪያ በማድረግ ለብዙ አመታት የተደከመባቸውን "ኢትዮጵያዊ ተቋሞች እንዳልነበሩ አድርጓል። አገሪቱን ወደ ኋላ ወስዷታል። አምባገነኑ መንግስቱ ሃይለማሪያም አትንኳቸው ያለውን ተቋሞች መለስ አፍርሷቸዋል" እያለ የጻፈውን ማስታወስ ይረዳል። አገር ወለድ እድገት፤ ያለ አገሩ የሰው ሃይል ጥረት ስኬታማ አይሆንም። 5/

ሁለተኛው ምሳሌ የምግብ እርዳታን ይመለከታል። ኢፍፐሪ (International Food Policy Research Institute) ባወጣው ዘገባ፤ ኢትዮጵያ የምግብ እጥረትን ችግር ካልፈታች፤ ድህነት አይቀንስም ብሏል። ቢል ጌትስ፤ "ከየትኛውም አገር በባሰ ደረጃ፤ ኢትዮጵያ የምግብ እጥረት፤ የመመገብ ዋስትና የሌለባት አገር ናት" ብሏል። ኮፊ አናን፤ "ማንኛውም የአፍሪካ መንግሥት ከሁሉ በላይ ማተኮር ያለበት ሕዝቡ የምግብ ዋስትና እንዲኖረው ማድረግ ነው" ብሏል። መሬት ማከራየት፤ መሸጥ አያዋጣም። የአሜሪካ መንግሥት ለኢትዮጵያ ረሃብተኛ በያመቱ የሚሰጠው እርዳታ የሚገዛው የአሜሪካን እህል ነው። የምርት ትርፍ ባለበት ፈልጎ ኢትዮጵያ መግዛት መቻሉን አጥቶት አይደለም። ገንዘቡ ከአሜሪካኖች እጅ እንዳይወጣ ስለፈለገ ነው። ኢትዮጵያ ጥገኛ ሆና እንድትቆይ በማሰብ ጭምር ነው። የምግብ እርዳታ በበለጠ የሚረዳው የአሜሪካን ገበሬዎች መሆኑን ብዙ የእድገት ሊቆች ጽፈውበታል። ኦክስፋም ያደረገው ዘገባ ብቻ ይበቃል። ባጭሩ ያስቀመጠው፤ የምግብ እርዳታ በመስጠት ፋንታ፤ "የኢትዮጵያን ዝቅተኛ አምራች አቅም መገንባት ዘላቂነት ያለው እድገት ያመጣል። ድህነትን ይቀንሳል" የሚል ነው። ጠባቡና ጎሰኛው ህወሓት፤ ይህን በተግባር ትግራይ ክልል ውስጥ ስራ ላይ አውሎታል። ረሃብተኛን ነጻ ለማድረግ ከተፈለገ፤ ገበሬው የመሬት ዋስትና እንዲኖረው፤ ራሱን እንዲችል የአቅም ግንባታ ማድረግ ይቻላል። ቻይናዎች እነደሚሉት፤ "ለአንድ ሰው አሳ መስጠት ለአንድ ቀን ይመግበዋል፤ አሳ እንዴት እነደሚያጠምድ ማሳየት ግን ለህይወቱ ይመግበዋል።" የምግብና ሌላው እርዳታ፤ ጥገኝነትን ልምድ ካደረገ፤ ከጥቅሙ ጉዳቱ ይበልጣል። የምግብ ሆነ፤ የልማት እርዳታ ዋና አላማው እርዳታ እንዳያስፈልግ ማድረግ ነው። ለዚህ ነው፤ ዳሚቢሳ ሞዮ የተባለችው የዛምቢያ ኢኮኖሚስት የውጭ እርዳታ ከጥቅሙ ጉዳቱ (Dead Aid) ያመዝናል የምትለው። ጉዳቱ ካመዘነ መንግሥታት ለምን እርዳታ ፈለጉ? የግል ጥቅም ስላለው። ተቆጣጣሪ የሌለው እርዳታ መሰረቁ አይቀርም። ለሃገሩና ለህብረተሰቡ መሻሻል የሚያስብ መንግሥት እርዳታ እንዲሰረቅ አይፈቅድም፤ አያመቻችም። ህወሓት ከዚህ ይለያል። የመንግሥት መሪ መሆን ለሕዝብ ሃላፊነት፤ ለሕዝብ ተጠያቂነት ፈቃደኛ መሆንን ይጠይቃል።

ማንኛውም ኋላ ቀር ደሃ አገር፤ የህብረተሰቡን የማምረትና የአገልግሎት አቅም በተቻለው መጠን በፍጥነት ማጎልመስ አለበት። ለዚህ በሃገር የማይገኙ ግብአቶችን (መሳሪያ፤ ማዳበሪያ፤ መድኃኒት፤ የእርሻ መኪና፤ እውቀት፤ የዘመናዊ አስተዳደር የሚችል የሰው ሃይል) ወዘተ መሸመት ግዴታ ነው። ህወሓት ትግራይ ክልል ያደረገው ማለት ነው። ጥሬ እቃ (ቡና፤ ቦሊቄ፤ የዘይት ፍሬ፤ ዘይት፤ ወርቅ፤ እንቁ፤ ወዘተ) ወደ ውጭ ልኮ የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ይሞክራል።

ያገኘውን ይሸምትበታል። እንደ ዘይት ያለ፤ ብዙና አስተማማኝ የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኝ ጥሬ ሃብት የሌለው ሃገር፤ ጥገኛ፤ ለማኝ፤ ተበዳሪ ይሆናል። ያለውን በጥንቃቄ መጠቀም አለበት። የሚገኘው የውስጥ ገቢ ለእድገቱ ፍላጎት አያሟላም። ስለማይበቃ፤ ገንዘብ ያላቸውን ትርፍ ፈላጊዎች ይጋብዛል። የውጭ እርዳታ ጠይቆ ያለውን የካፒታል እጥረት ለማሟላት ይሞክራል። ከተሰረቀ ግን መሟላቱ ይቀንሳል። አንድ፤ የውስጥ አዋቂዎች፤ የሚሉት "በኢትዮጵያ 90 በመቶ የሚሆነውን የእድገት ባጀት የሚሸፍነው የውጭ እርዳታ" ነው። ይህን እነደ እንቁ የሚቆጠር የውጭ እርዳታ ገንዘብ የህብረተሰቡን የማምረት አቅም፤ የኢኮኖሚውን መዋቅር እንዲያሻሽል ማድረግ የመንግሥት አመራር ሃላፊነት ነው። ለሕዝብ ሃላፊነትና ተጠሪነት ከሌለ፤ የውጭ ምንዛሬ እነደ ውሃ ቢጎርፍ መዋቅራዊ ለውጥ አያመጣም። ሙስኛና አድሏዊ የነበሩ፤ አሁንም የሆኑ የአፍሪካ መሪዎች የተማሩት፤ እርዳታውን ሆነ፤ ከልዩ ልዩ የተፈጥሮ ጥሪት ሽያጭ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬ ለራሳቸው፤ ለቤተሰቦቻቸው፤ ለወዳጆቻቸው፤ ለታማኞቻቸው መስጠት ነበር። በአብዛኛው አሁንም ነው። እርዳታው ከተሰረቀ ለልማት አይውልም። ጥቂቶችን ያከብራል። እርዳታ የግል ጥቅም አለው። ብዙ ከተገኘን ግዙፍ መሰረተ ልማት ከተካሄደ፤ በኮንትራት፤ በአቅርቦትና በልዩ ልዩ መንገድ ለመስረቅ ያመቻል። አዲስ ሚልዮኔር ለመሆን ተአምር አይደለም ማለት ነው። ሚሊዮኔር ለመሆን የሚያስቸግረው በራሱ ፈጥሮ፤ በራሱ ሰርቶ ማደግ ግዴታና ልምድ ሲሆን ነው።

በዚህ መጽሃፍ እንደምናሳየው፤ ቢያንስ አርባ በመቶ የሚሆነው የውጭ ምንዛሬ ለህብረተሰቡ አገልግሎት ወይንም የማምረት አቅም ግንባታ አይውልም። በልዩ ልዩ ዘዴ ይሰረቃል። ሂሳቡን መፍጠር አያስፈልግም። ጀፍ ዊንተርስ የተባለው የኖርዝዌስተርን ዩንቬርስቲ ኢኮኖሚስት (አሜሪካ) ባደረገው ጥናት፤ ዓለም ባንክ ለአፍሪካ መንግስታት ካበደረው ብቻ ቢያንስ $100 billion ተሰርቋል። የሰረቁት ባለስልጣናትና ደጋፊዎቻቸው ናቸው። የት እንደደረሰ አይታወቅም። ከአንድ አበዳሪ ብቻ። ዓለም ባንክ ከሚባል። በኢትዮጵያም ከፍ ያለ ከእርዳታ የሚገኝ የውጭ ምንዛሬ በሙስና፤ በኮንትራት፤ በተደለዘ የንግድ ልውውጥ፤ ወዘተ ቢያንስ በዓመት ሶስት ቢሊዮን ዶላር ወደ ውጭ ይሸሻል። እስከ 2014 ሃያ አምስት ቢሊዮን ዶላር ከኢትዮጵያ ሕዝብ ተሰርቆ ወጥቷል። የህወሓት ዓመራር ይኼን ሲያደርግ በኢትዮጱያ ዘላቂነት እምነት የሌለው ያስመስለዋል። በአገሪቱ ዘላቂነት የሚያምን መንግሥት የሚያስበው ለወደፊቱ ነው። ለማመዛዘን ባለፉት ሃያ ሶስት ዓመታት ገዢው ፓርቲ ከለጋስ መንግሥታትና ድርጅቶች፤ ከአበዳሪዎች አግኝቷል ተብሎ የሚገመተው እርዳታ አርባ ቢሊዮን ዶላር ነው። ይኼን ግምት ብንቀበልና መደብ ብናደርገው ስድሳ ሁለት በመቶው ተሰርቋል ማለት ነው። ሆኖም፤ የተሰረቀው ከእርዳታ የተገኘው ብቻ ነው ለማለት ማስረጃ የለም። የተሰረቀው ከየት መጣ፤ ማን አሸሸው፤ እንዴት ብሎ መጠየቅ የሞራል ግዴታ ነው። "ድርጂታዊ ምዝበራ" ያልነው ለዚህ ነው። ቁም ነገሩ ሙስና ኢትዮጵያን እያደማት ነው።

የአፍሪካ መንግሥታት አሳሰበው የነበረው፤ እድገት "ገንዘብ ብቻ አይደለም። ገንዘብ ብቻ ከሆነ የህብረተሰብ ኑሮ መሻሻልን አያሳይም" ያሉት የስግብግብነትን፤ የአድልዎንና የሙስናን ጎጅነት አስቀድመው ስላወቁት ነው። የፖለቲካ ስልጣን ለዘረፋ መሳሪያ መሆኑን ስላዩት ነው። የገንዘብ አምልኮ ካለ፤ ስርቆት፤ ጉቦ፤ ሙስና መስፋፋቱ አይቀርም። ሁሉም "ለራሴ፤ ለቤተሰቤ፤ ለብሄሬ" የሚል አዙሪኝ ውስጥ ይገባና የህብረተሰቡ አገልግሎት ይረሳል። እድገት በጠባቡ ይታያል። "መንገድ ተሰርቷል፤ ትምኅርት ተስፋፍቷል፤ የተሃድሶ ግድብ እየተሰራ ነው፤ ፎቅ በፎቅ ሆነናል" ወዘተ። የአይቮሪ ኮስትን- ዓለም ባንክ አስደናቂ እድገት" ብሎ የሰየመውን-- እንደ እምቧይ ካብ መፈራረስ ያየ፤ መልካም፤ ሁሉን አቀፍ አገዛዝ እንዴት ቁልፍ እንደሆነ ይገነዘባል። አይቮሪ ኮስት የተሰራው መንገድ፤ ትምኅርት ቤት፤ የጤና ጣቢያ፤ ሰማይ ጠቀስ ፎቅ ወዘተ ፈራርሶ ነበር። ጥገና ተቋርጦ ነበር። ፀሃፊው በስራ ምክንያት አይቶታል። አድልዎ፤ ጉቦ፤ ሙስና፤ የውጭ ተጽእኖ፤ ብሄርተኛነት፤ የጎሳ ፖለቲካ ስልጣን ውድድር፤ ስራ አጥነት፤ አገዛዙን አንበረከከው። የየአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሙስና፤ አድልዎና የውጭ ምንዛሬ ሽሽት ነቀርሳነት ሰላሳሰበው ሰፊ ጥናት አድርጓል። በአመት መቶ አምሳ ቢሊዮን ዶላር ከአፍሪካ እየተሰረቀ ወደ ውጭ እንዲሚጎርፍ አረጋግጧል። <u>ከ 2000-2014 ባለው ጊዜ፤ ከኢትዮጵያ ብቻ $25 ቢሊዮን ዶላር</u> <u>ተሰርቆ ወደ ውጭ ተወስዷል</u>። ሲንጋፖር፤ ሆንግ ኮንግ፤ የካይመን ደሴቶች፤ ኒው ዮርክ፤ ሎንዶን፤ ስዊትዘርላንድ ወዘተ መደበቂያዎች ሆነዋል። ይህ ሃብት ለኢትዮጵያ ሕዝብ መመለስ አለበት።

ጥያቄው ማን ወሰደው፤ ማን አሸሸው አይደለም። ማጤን ያለብን ድርጊቱንና ጉዳቱን ነው። ደሃና የምግብ እርዳታ ጥገኛ በሆነች፤ ዘጠና በመቶ የሚገመተው የእድገት ባጀቷ ከውጭ በሚገኝ እርዳታ የሚደገፈው ህብረተሰብ ይህን ያህል የውጭ ምንዛሬ ከተሰረቀበት፤ የእርዳታው ተጠቃሚ ህብረተሰቡ አይደለም። ጥቂት የፖለቲካ ስልጣን የበላዮች፤ ቤተሰቦቻቸው፤ የባለስልጣኖች ድጋፍ ወይንም መከታ (Guardian) ያላቸው ወዳጆች፤ ታማኝ ደጋፊዎች፤ ሃብታም የግል ሰዎች ናቸው። በመንግሥቱ ላይ እምነት የሌላቸው፤ ተሰደው የሚወጡ፤ ወዘተ የግል ባለጠጋዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ለማሸሽ የሚችል የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት እድል ያለው ነው። ስልጣን ያላቸውና ስልጣን ካላቸው ጋር ግንኙነት ያላቸው መሆናቸው አያጠራጥርም። አንዱ ማስረጃ መንግሥት ከፍተኛ ሙሰኞችን ለፍርድ ለማቅረብ

አለመቻሉ ነው። አስር ሽህ ቶን ቡና ከአገር ተሰርቆ ሲወጣ፤ ጠቅላይ ሚንስትር መለስ “ማን እንደሰረቀው እናውቃለን። እንተዋወቃለን” ብሎ ክትትል ሳይደረግ ቀርቷል። ሁለት ቢሊዮን ዶላር “በውጭ ባንኮች ያሏቸው ኢትዮጵያውያን እንዳሉ እናውቃለን” ማለቱም ይታወሳል። ከደሃ አገር ሁለት ቢሊዮን ዶላር ያላቸው እነማን ናቸው? ለምን ከአገር አሸሹት ተብሎ ክትትል አልተደረገም? ገንዘቡ እንደወጣ ቀርቷል።

ሙስና ገንዘብ መስረቅ ብቻ አይደለም፤ ምርጫን መደለዝ፤ ማጭበርበር ሙስና ነው። በሌላ ወንጀል ለፍርድ የሚቀርቡት፤ ዝቅተኛ ሌቦች ናቸው። የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሙሰኝነት የጀመረው ከቁንጮው ነው። ቁንጮው ካልተወገደ፤ ግንዱ ሊነካ አይችልም። “የሞተ አሳ የሚገማው ከራሱ ነው” እንደሚሉት፤ ሙስና የከፋው ከላይ ነው። መንግሥት የሚከራከረው፤ “ሙሰኛው፤ ገንዘብ የሚያሸሸው የግል ክፍሉ፤ ነጋዴው ነው” በሚል ከእውነት በወጣ አቅዋም ነው። የግል ክፍሉ በሙሰኝነት አይሳተፍም አንልም። የግሉ ሙሰኛ ለመሆን የሚችለው፤ ባለስልጣናት ሙሰኞች ሲሆኑ ነው። ተባባሪ ሲኖር። የመንግሥትም ሆነ የግል ሙሰኛ፤ ከህግ ውጭ ብዙ ቢሊዮን ዶላር ደብቆ ሲያሸሽ የአገሪቱ የማምረት ችሎታ፤ ድህነት የመቀነስ፤ ስራ የመፍጠር አቅም በጣም እየተጎዳ ይሄዳል። የህብረተሰቡን ባህል፤ በተለይ፤ የወጣቱን ትውልድ እየበከለው ሄዷል። በመንግሥቱና በአመራሩ ላይ ምንም እምነት አይኖርም። ለአገር የማያስብ አመራር፤ ለአገር የማያስብ ትውልድ ወልዷል። ሙስኝነት፤ ህገወጥ የውጭ ምንዛሬ ሽሽት ነቀርሳ ሆኗል። የዚህ መጽሃፍ አንዱ አላማ የቀረው የአፍሪካ መጥፎ የአገዛዝ ልምድ ወደ ኢትዮጵያ በስፋትና በጥልቀት የገባውና ስር የሰደደው መለስ በገነባው የጠባብ ጎሰኞች አምባገነናዊ መንግስት አማካይነት ነው የሚል መሰረተ ሃሳብ ነው። ለምን? የአንድ ጠባብ ብሄርተኛ “እድገታዊው መንግስት” አድልዎን፤ ጉቦን፤ ሙስኝነትን፤ የሃብት ሽሽትን አዝሎ መላውን ህብረተሰብ በክሎታል። ወጣቱን ትውልድ ተስፋ አስቆርጦታል። ለስደት ዳርጎታል። ህግ አውጪው፤ ህግ አስፈጻሚው አንድ ከሆነ፤ ለአገሪቱ ተከራካሪ የላትም። አድልዎንና ሙስናን የሚያጋልጥ አይኖርም። በአመት ብዙ መቶ ሽህ ወጣት ከአገሩ የሚሰደደው አገሩን፤ ወገኑን፤ ዘመዱን ጠልቶ አይደለም። ባስቸኳይ፤ መፈታት ባለባቸው ምክንያቶች ነው። ወጣቱን ዋና ምሳሌ ያደረግነው እድገት ስለተከታታይ ትውልድ የተሻለ ኑሮ መኖር ስለሆነ ነው። ለምን?

አንድ፤ ተምሮም ሆነ ሳይማር፤ የስራ እድል ስለሌለ። ይኼ አስቃቂ የሰው ኃይል ፍልሰትን ፈጥሯል።

ሁለት፤ የመንግሥት አፈና፤ ጫና፤ ጭቆና፤ ተደጋጋሚ (recurrent) ስለሆነ። ነጻነት ስለተገፈፈ። ነጻነት ከሌለ እንደልብ ካፒታል ለማዘዋወር፤ የግል ክፍል ለማቋቋም ወዘተ አይቻልም።

ሶስት፤ በጠባብ ብሄርተኛነት የፖለቲካ ስልጣን፤ የህወሓት የበላዮች በግልጽ አድሏዊ በሆነ መንገድ ለራሳቸው፤ ለቤተሰቦቻቸው፤ ለጓደኞቻቸው፤ ለታማኝ ደጋፊዎቻቸውና ለክልላቸው ወዘተ፤ የኢኮኖሚ የበላይነትን ስለሰጡ። ይህም፤ ግልጽ የሆነ የኑሮ፤ የመማር፤ የመስራት፤ የገቢና የሃብት ልዩነቶች (Staggering social inequality) ስለፈጠረ። የዛሬዋ ኢትዮጵያ የምታስታውሰን የመሳፍንት ዘመንን ነው፤ ሁሉም ለራሱ ጥቅም፤ ጉሉም ለጎጡ። “እኔ ኦሮሞ፤ ትግሬ፤ ወላይታ፤ አማራ ነኝ” ወዘተ የሚል ትውልድ። በዚህ አመለካከት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት የሚል ማእከል ለመፍጠር አስቸጋሪ ነው እንላለን። የብሄራዊ ኢኮኖሚው በተፈለገው ደራጃ ለማምረት፤ ስው ለመቅጠር፤ አንዱ ሌላውን ለመደገፍ አይችልም።

አራት፤ የኑሮ ሁኔታ የማይመችና አስጊ ስለሆነ። በከተማ የሚኖርው ተራ ሕዝብ ኑሮ አስመርሮታል። የብር ዋጋ ቀንሷል። የዋጋ ግሺፈት ንሯል። ገቢ አላደገም። ከስደተኛው ገቢ የማያገኝ ለመኖር አይችልም። ችግር፤ ችግር።

አምስት፤ የኢኮኖሚና የማህበረሰብ አገዛዙ እድልን ስላገደ። ክብርን ስለገፈፈ። ለሙብት መከራከርን ወንጀል ስላደረገ ወዘተ ነው። ከምርጫ ዘጠና ሰባት በፊት፤ የውጭ ተመልካቾች በአብዛኛው የሚያተኩሩት በመጀመሪዎቹ ሶስት አፈናዎች ነበር። አሁን፤ የአፍሪካ እድገት ባንክን ጨምሮ፤ በኢትዮጵያ የሚታየው የገቢ፤ የሃብት፤ የኑሮና የክልል እድገት ልዩነት ከሚያሰጋ ደረጃ ላይ መድረሱን በማስረጃ ያመለክታሉ። እነዚህ መሰረታዊ ችግሮች (Systemic hurdles) ናቸው። መሰረታዊ ችግር ያለበት አገር እርጋታ ስለሌለው መሰረታዊ ለውጥ ያስፈልገአዋል። ይኼን ለውጥ ፈረንጆች አያበረክቱም፤ ሕዝቡ ሙብቴ ነው ማለት አለበት።

የሊጋሶች ቼክ መጻፍ ብቻውን ውጤት አያመጣም

የውጭ እርዳታ ብቻውን ማንንም አገር ሃብታም አድርጎ አያውቅም። “አስደናቂ” የተባለው እድገት ከአብዛኛው ሕዝብ አኳያ ሲታይ አጥጋቢ አይደለም። አበው ሲናገሩ፤ “ያልተዘራ አይበቅልም” እንደሚሉት ሁሉን አቀፍ ያልሆነ የፖለቲካ አመራር ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እድልን ለሁሉም ከፍቶ እድገት ለማምጣት አይችልም። “ዘሩ አልተዘራም።” ጠባብ

አስተሳሰብ ካለ፤ ከጠባብ እድል ላይ ይቆማል። ብዙ፤ ደሃና ኋላ ቀር የነበሩ ከሳሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ አገሮች፤ የአፍሪካ መንግሥታት መሪዎች የዛሬ አርባ አምስት አመት በአሩሻ የሰጡትን፤ "እድገት ስለገንዘብ ሳይሆን ስለሰው ክቡርነት፤ ስለ ሰው የኑሮና የህይወት መሻሻል ነው። የመንግሥት ዋና ሃላፊነት ህብረተሰቡን ማገልገል ነው" ያሉትን በቅንነት፤ በእኩልነት፤ በህግ የበላይነትና በሃላፊነት የሚሰሩ መንግስታት አሉ። ቦትስዋና ምሳሌ ናት። ለጋሶች የሚሰጡት ገንዘብ ጥቅም የለውም ማለታችን አይደለም። ለመንግሥት ካዝና ቼክ መጻፍ ብቻውን ለህብረተሰብ አጥጋቢ ውጤት አያመጣም። ህንድ የዝቅተኛ ገበሬዎችን ምርት ለማሳደግና ተደጋጋሚ ረሃብን (Recurring Famine) ለማጥፋት የበቃችው ቼክ ስለተጻፈ አይደለም። ቼኩ ለተወሰነ አላማ፤ ማለትም "ለአረንጓዴው አብዮት" ስለዋለ ነው። የቢል ጌትስ ፋውንዴሽን በህንድ አገር ፖሊዮ ያጠፋው ገንዘቡ ለተወሰነ አላማ እንዲውል ቀጥታ ቁጥጥር ስለተደረገበት ነው። የአፍሪካን አህጉራዊ አመለካከት ከመጥፎነት ወደ ጥሩነት የሚለውጡት ሃላፊነት የሚያሳዩ መንግሥታት ናቸው። የተፈጥሮ ሃብትን የህብረተሰብ አገልጋይ የሚያደርጉ። እድል ፈጣሪና አመቻች የሆኑ መንግሥታት የህብረተሰቡ አገልጋይ መሆናቸውን የሚያመለክቱ ብዙ መለኪያዎች አሉ። አንዱ የነፍስ ወከፍ ገቢ እያደገ መሄዱ ነው። ሆኖም፤ የነፍስ ወከፍ ገቢ ስርጭት የተዛባ ከሆነ የእድገቱ ውጤት ለጥቂቶች ይሆናል።

አይኤምኤፍ April 2012, World Economic and Finanial Surveys: Regional Economic Outlook for Sub-Saharan Africa በሚል ባወጣው ስፊ ጥናት፤ ኢትዮጵያ ዝቅተኛ ገቢና "በምርኩዝ የቆመች፤ ዝቅተኛ ኑሮ ያለባት" (Fragile) አገር ናት ያለው ቁልፍ ነው። እነደ ማላዊ፤ ኒጀር፤ ጋምቢያ፤ ማሊ ማለት ነው። የዋጋ ግሽበት፤ በ 2011 አምሳ ሁለት በመቶ ነበር። በ 2012 ሰላሳ አራት በመቶ። በሚቀጥሉት ሁለት አመታት፤ በአመት፤ ከሃያ ሶስት በመቶ በላይ እንደሚሆን ይገመታል። ድርጅቱ የነፍስ ወከፍ ገቢ እድገት ከሁለት እስከ ሶስት በመቶ በላይ እንደማያድግ ያሳያል። የአገሪቱ እድገትም በ 2012፤ 5 በመቶ፤ በ2013 5.5 በመቶ እንደሚሆን ገምቷል። የኢትዮጵያ መንግሥት ይህን እንደሚከድ አንባቢው ማወቅ ይኖርበታል። ከክልል አንድ ውጭ፤ ባለፉት አመታት እጥፍ ድርብ አድጓል ተብሎ የሚነገርለት ኢኮኖሚ መንግሥት ባለው ደረጃ ማደጉ ያጠራጥራል። አደገ ቢባልም ምንም አያስደንቅም። በአመት አራት ቢሊዮን ዶላር (ከስምንት መቶ ቢሊዮን ብር በላይ) በእርዳታ፤ ከዚህ የማያንስ ገቢ ከስደተኛ የሚፈስለት መንግሥት እድገት ማሳየት አለበት። የማንም ግለሰብ ወይንም ቤተሰብ ህይወት ተሻሻለ ለማለት የሚቻለው ገቢው ከፍ ብሎ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን ለመሸመት ሲችል ነው። ይህ ዝቅተኛ መስፈርት ነው። ከዚህ በላይ ወደ መካከለኛ መደብ አባልነት ሲሻገር ጤናው በበለጠ ይጠበቃል። ቤት ይገዛል። ልጆች ያስተምራል። ያደለው ይዝናናል። ቱሪስት ሆኖ አገሩን ይጎበኛል። ዘመድ ይጠይቃል። ለቀውጢ ቀን ይቆጥባል። አውቶቡስ በመውሰድ ፋንታ ታክሲ ይወስዳል። ከጊዜ በኋላ መኪና ይገዛል ወዘተ። የእድገት ዋናው መለኪያ የግለሰቦች፤ የቤተሰቦች ኑሮ መሻሻል ነው። ለዚህ ከነፍስ ወከፍ ገቢ የበለጠ መስፈርት የለም። የኢትዮጵያን "አስደናቂ እድገት" ውጤት ከሌሎች መካከለኛ ገቢ ደረጃ ከደረሱ ለናሙና የተመረጡ አምስት የአፍሪካ አገሮች ወስደን የነፍስ ወከፍ ገቢን በመጠቀም እናመዛዝን። 6/

| የመካከለኛ ገቢ አገሮች ስም * | የነፍስ ወከፍ ገቢ በዶላር፤ በዓመት (2014)<br><br>(ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ) |
|---|---|
| ኢኳቶሪያል ጊኒ | **$30,000.00** |
| ቦትስዋና | **$15,800.00** |
| ጋቦን | **$14,900.00** |
| ሞሪሺየስ | **$ 12,400.00** |
| ሴሽልስ | **$ 7,800.00** |

*ደቡብ አፍሪካ የተለየች፤ ከብራዚል፤ ቻይና፤ ራሺያና ሕንድ ጋር ስለምትነጻጸር አልተጨመረችም። ብዙ ሺህ ኢትዮጵያውያን የተሰደዱባት ዋን መከንያት ለዚህ ነው። የነፍስ ወከፍ ገቢዋ በዓመት ከአስር ሺህ ዶላር በላይ። በአጠቃላይ ሲታይ፤ በ2014 ዘገባ፤ ሰላሳ አምስት የአፍሪካ አገሮች የነፍስ ወከፍ ገቢያቸው በዓመት ከአምስት መቶ ዶላር በላይ ነው---ጊኒ፤ ሴሸልስ፤ ጋቦን፤ ቦትስዋና፤ ሞሪሽየስ፤ ደቡብ አፍሪካ፤ ናሚቢያና አንጎላ (መካከለኛና ከፍተኛ ገቢ ያላቸው፤ ኮንጎ ብራዛቪል፤ ኬፕ ቬርዴ፤ ስዋዚላንድ፤ ሱዳም (ሰሜን)፤ ጋና፤ ናይጀሪያና ጂቡቲ ከአንድ ሺህ አምስት መቶ ዶላር በላይ በዓመት ገቢ ያላቸው፤ ሳዖ ቶሜ፤ ዛምቢያ፤ ካሜሪን፤ ማሪታኒያ፤ ሴኔጋል፤ አይ ቮሪ ኮስትና ሌሶቶ በዓመት ከአንድ ሸህ ዶላር በላይ ገቢ ያላቸው እና ቻድ፤ ኬንያ፤ ኮሞሮስ፤ ማሊ፤ ቤኒን፤ ዚምባብዌ፤ ቡርኪና ፋሶ፤

ጋምቢያ፤ ጊኒ ቢሳው፤ ሩዋንዳ፤ ሞዛምቢክ፤ ታንዛኒያና ቶጎ በዓመት ከአምስት መቶ ዶላር በላይ ገቢ ያላቸው። ይህ መፅሃፍ በተዘጋጀበት ወቅት የአፍሪካ አማካይ ገቢ በዓመት $1,700 ተገምቷል። የኢትዮጵያው በዓመት ከአምስት መቶ ዶላር በታች ነው፤ ከአንድ ሶስተኛ በታች ማለት ነው። እርግጥ ነው። የነፍስ ወከፍ ገቢ ብቻውን የተራውን ሕዝብ ኑሮ መሻሻል አያሳይም። ተራው ሰው በልቶ ሲያድር፤ ጤናው ሲጠበቅ፤ ለመጓጓዝ ሲችል፤ መጠለያ ሲኖረው፤ መፀዳጃ ቤት ሲኖረው፤ ንፁህ ውሃ ለመጠጣት ሲችል፤ በኩራዝ ሳይሆን የመብራት አገልግሎት ሲያገኝ ወዘተ ገቢ ትርጉም ይኖረዋል። የሃብትና የገቢ ስርጭቱ ፍትሃዊ ካልሆነ የነፍስ ወከፍ ገቢ ህይወትን አሻሻለ ለማለት አያስችልም። አሜርካ የነፈስ ወከፍ ገቢ ከፍተኛ ነው። ሆኖም፤ የመካከለኛውና የደሃው ሕዝብ ኑሮ ወደ ታች ሄዷል። ፍትሃዊ አይደለም ማለት ነው። ኢትዩጵያ የምትከተለው የእድገት ፈለግ አደገኛ ነው የምንለው ለዚህ ነው። የጠቅላላ ገቢ ማደግ ብቻውን የተራውን ሕዝብ ኑሮ አይበይንም። ለጥቂርቶች ገነት፤ ለአብዛኛው ሲኦል ነው ለማለት እንገደዳለን። የኢትዮጵያ መንግሥት እድገቱን የሚመዝነው ኢትዮጵያ ከኢትዮጵያ ጋር በማወዳደር ነው። የዚህ አይነቱ ራስን ከራስ ጋር የማነጻጸር መስፈርት ትሩጉም የለውም። ዜሮን መደብ አድርጎ እጥፍ ድርብ አድገናል ማለት በሂሳብ መጫወት ነው። ትላንት አንድ የአንደኛ ትምህርት ቤት የነበረው መንደር ዛሬ ሌላ ትምህርት ቤት ቢሰራለት እጥፍ ሆነ ማለት ነው። ይኼን እድገት አስደናቂ ነው ካልን የህወሓት መመዘኛዎች ያዋጣሉ። እኛ የምንለው ኢትዮጵያ ከሌሎች ፈጣን እድገት ከሚያሳዩ ታዳጊ አገሮች ጋር ትወዳደር ነው። በዚህ መሰረት ኢትዮጵያ ከላይ ከተጠቀሱት ሰላሳ አራት የአፍሪካ አገሮች ጋር ለመወዳደር አልቻለችም። የምትነጻፀረው ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዢ ካቀረብናቸው ደሃና ኋላ ቀር አገሮች ጋር ነው።

ዝቅተኛ የነፍስ ወከፍ ገቢ የሚያሳዩ የአፍሪካ አገሮች ናሙና (ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ)

| | የነፍስ ወከፍ በዶላር (2014) |
|---|---|
| ቡሩንዲ | $226.00 |
| የመአከላዊ አፍሪካ ሪፐብሊክ | $333.00 |
| ኒጀር | $413.00 |
| የኮንጎ ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ | $454.00 |
| ኢትዮጵያ | $498.00 |

እነዚህ አምስት አገሮች፤ በአፍሪካ ፍጹም ደሃ፤ "በራሳቸው ለመቆም" ያልቻሉ፤ የሃገር ውስጥ እርጋታ የሌለባቸው ተብለው የሚገመቱ ናቸው። መለስ በህየወቱ ከተናገራቸው አበይት አገራዊ ጉዳዮች መካከል የማንረሳው በአዲስ አበባ ከንግድ አንቀሳቃሾች ጋር ተገናኝቶ፤ "እኛ ኢትዮጵያውያን፤ ቁልፍ የሆኑ የኢኮኖሚ አውታሮች (Pillars of the National Economy, for example, manufacturing) ካልያዝን፤ አገራችን የማጣት እድላችን ከፍ ያለ ነው፤ እንደ ሶማሊያ ልንሆን እንችላለን" ያለው ታሪክ የመዘገበው አባባል ነው። ይህ አስተሳሰብ ወደ ፖሊሲ አልተለወጠም። በአንድ በኩል ለራሱ ጎጠኛ ክልል ቅድሚያ መስጠት፤አገሪቱን የባህር በር አልባ ማድረግ፤ የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን መስጠት፤ ብዙ ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለውጭ ኢንቢስተሮች ማሺጋገር፤ በሌላ በኩል ስለውጭ አደጋ ማውራት ሃቀኛነትና አርቆ አስተዋይነት አያሳይም። ጎሳዊ አድልዎ ባያሳይ፤ ማለትም፤ አገር ወዳድነትን ቢያስተጋባ ኖሮ የተሻለ ውጤት ይገኝ ነበር። ንግግሩ፤ በውስጥ ባሉ ቅራኔዎች ይሁን በሌላ ወደ ስራ አልተተረጎመም። ተርጉሞ፤ አገር ወለድ የሆነ፤ ሁሉም የሚሳተፍበት የፖለቲካ፤ የማህበራዊና የኢኮኖሚ አመራር አልመሰረተም። ባንድ አፍ፤ "ኢትዮጵያ ሃኪሞች፤ ምሁሮች፤ ወዘተ አያስፈልጓትም" ማለት፤ በሌላ፤ "ወሳኝ የሆኑትን የልማት ተግባሮች የውጭ ድርጂቶች እየነጠቋቸው" ነው ማለት ተጻራሪ ሃሳቦች ናቸው። የሃገርን የኢኮኖሚ አውታሮች ላለማስነጠቅ፤ አመቻችና አሳታፊ የሆነ ፖሊሲ፤ ደንብና የስራ አፈጻጸም መኖር አለበት። ኢትዮጵያውያን በማንኛውም ሰላሳ ዩንቬርስቲ ተምረው በአገራችው ለመስራት መቻል አለባቸው። ተምረው ለድደት መዳረግ የለባቸውም። የህወሓትን መንግሥት የወደፊት ትውልድ "የስደት መንግሥት ነበር" ቢሉት አያስደንቅም።

ከገገርው ፓርቲ ውጭ "ሑሉም ኪራይ ሰብሳቢ ነው" ብሎ፤ በሌላ በኩል፤ የህወሓትን፤ "ምርጥ የትግራይ ብሄረሰብ ተወላጆች" የኢኮኖሚ አውታሮችን ለብቻም ሆነ፤ በጋራ (in collusion with others, including foreigners) ማስረከብ አገር ወለድ ለሆነ እድገት ጸር ሆኗል። ከዚሮ ካፒታል የጀመረው EFFORT የተባለው ህወሓት የሚቆጣጠረው ሞኖፖሊ ዛሬ አምሳ ቢሊዩኦን ብር ካፒታል አካብቷል። ማንም ሊፈትሸው አይችልም። ከቀረጥ ነጻ ነው። አገር አቀፍ ሚና አለው። ይኼ የኢኮኖሚ የበላይነት ያሳየው ኢኮኖሚው ከፖለቲካ ስልጣን ጋር ቀጥታ የሆነ ግንኙነት እንዳለው ነው። መለስ የኢትዮጵያ ድልድይ መሪ ሆኖ የሁሉን አቀፍ የእድገት መሰረት አልጣለም። የጥቂቶች የኢኮኖሚ የበላይነት የምርት ኃይሎችን ያግባል። መካከለኛ ገቢ ከደረሱ የአፍሪካ አገሮች ለመድረስ ምን ያህል መሻሻል እንደሚያስፈልግ፤ ከግል ክፍሉ ጫጩጥነት፤ ከወጣቱ ትውልድ ስራ አጥነትና ስደት፤ ከነፍስ ወከፍ ገቢው ክፍተት ለማጤን ይቻላል። ጠባብና ጎሳዊ ስለሆነ፤ አገዛዙ፤ የኢትዮጵያን ህብረተሰብ ደህንነት፤ የገቢ እድገት ዋስትና አባብሰውታል። የአገዛዙ አፋኝነት (Poor, repressive and exclusionary governance)፤ የተማረ ሰው እጥረት (በስደት የተነሳ)፤ የዋጋ ግሽበት፤ አድልዎና ሙስና የአገዛዙን ጫና ያሳያሉ። እድገቱ እጥፍ ነው የሚለውን ከተቀበልን የነፍስ ወከፍ ገቢ እያደገ መሄድ አለበት። የስራ እድሎች መስፋፋት አለባቸው። የኑሮ ውድነት መቀነስ አለበት። የእርሻ ሰብል ውጤት ማደግ አለበት። ቢያንስ ህብረተሰቡ በልቶ ማደር ሙብቱ ነው።

የአገዛዝ ቁልፍነት

ወደ ዋናው የአገዛዙ ጥያቄ (Governance) እንሂድ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ተከታታይ ችግር፤ የስልጣን ባለቤት አለመሆኑ ነው። የድህነቱ፤ የስራ እድል ማጣቱ፤ የስደቱ፤ የታዛዥነቱ መነሻም የአስተዳደር በደል፤ ጫና፤ አፈና ነው። በእኛ እድሜ ሶስት የመንግስት ለውጦች አይተናል። የአጼ ኃይለ ሥላሴ ንጉሳዊ፤ ፊውዳላዊ፤ የመንግሥቱ ሃይለማሪም ወታደራዊ አምባገነናዊ ሶሻሊዝም፤ የመለስ ዜናዊ፤ የጠባብ ብሄርተኛ/ጎሰኛ የአንድ ፓርቲ የበላይነት "እድገታዊ መንግሥት።" አንጻራቸው ይለያያል። የሚጋሩት አንድ ነገር አለ። ሁሉም፤ የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚ፤ የማህበረሰብ፤ የስራ እድል፤ የትምኅርት፤ የሃይማኖት አድልዎና የጥቅም የበላይነት አሳይተዋል። የሃይሉ ሚዛን፤ የጥቅሙ ክብደት ተመሳሳይ አይደለም። በአገሪቱና በተራው ሕዝብ ላይ ያስከተሉት በደል፤ ክብደት ያለው ነበር። በተለያየ ደረጃ፤ አድሏዊ ነበሩ። የልዩ ልዩ፤ ህብረተሰብ ክፍሎችን ችግር በጥበብና በዘላቂነት ሊያስወግዱ አልቻሉም። ከሕዝብ ድምጽና ስልጣን አንጻር ሲመዘዘኑ፤ ተከታታይ መንግሥታት ትተውት ያለፉት ችግር መሰረታዊ የሆነውን የሕዝብ የፖለቲካ፤ የማህበረሰብና የኢኮኖሚ የበላይነት ጥያቄ አልመለሱም።

የህወሓት/ኢህአዴግን መንግሥት ከሁለቱ የሚለየው ዋና ራእይ፤ "በማይታረቅ፤ የብሄር ልዩነት" የታነጸ፤ በልዩነት ላይ ተጠቅሞ፤ አናሳ ቡድን የበላይነትን የያዘ፤ ሃይሉን አጠንክሮ፤ "ኪራይ ሰብሳቢ፤ ሙሰኛና አድሏዊ" መሆኑ ነው። "ከስብስቡ ውጭ ያሉትን ኪራይ ሰብሳቢዎች" ብሎ የሚከሰው አመራር፤ እራሱ ኪራይ ሰብሳቢ መሆኑን ለመደበቅ ነው። አደጋው ከፍ የሚለውም ለዚህ ነው። በመለስ ዜናዊ የተመራው መንግሥት የታላላቅ፤ በተለይ፤ የምእራባውያንን፤ በቅርቡ ደግሞ፤ የቻይናን አመኔታና ድጋፍ በማግኘቱ፤ ጡንቻ አግኝቷል። የአሜሪካ መንግስት፤ ከባጀት ውጭ ለስለላ፤ ለጦር ሃይሎች የሚሰጠው በአመት ብዙ መቶ ሚሊዮን ዶላር እርዳታ ጡንቻውን አጠናክሮታል። ለመቆጣጠር የሚያስችል ድጋፍ ሸምቶለታል። አንባቢ እንዲገነዘበው የምንፈልገው፤ ለመከላከያ የሚወጣ የገንዘብ ብዛት ለአገር እድገት ቢውል፤ የህብረተሰቡን ኑሮ ሊለውጠው ይችል ነበር። ያባባሰው፤ እርዳታ ሰጭዎች ቼክ ስለጻፉ ለሕዝብ የማይታየውን፤ ኢትዮጵያ ያልታየ እድገት (Growth) አስመዝግባለች እያሉ ሃላፊነት የጎደለው የፕሮፓጋንዳ የበላይነት ለገገርው ፓርቲ መስጠታቸው ነው። ሱዛን ሪይስ በመለስ ቀብር ስነስርአት የተናገረችው ድጋፍ የሰጠው ለኢትዮጵያ ደሃ ሕዝብ አልነበረም። እንዲያውም ሕዝቡን ሰድባለች። ድጋፍ የሰጠችው ለግፈኛውና አግላይ ለሆነው አገዛዝ ነው።

ከአበዳሪ ድርጅቶችና መንግስታት ውጭ፤ ብዙ ታዛቢዎች የሚሉት፤ በሰው ኑሮ ሁኔታ ሲመዘን የእድገቱ ተጠቃሚዎች ጥቂት ቤተሰቦች፤ ባለስልጣናት፤ ታማኝ ብሄርተኛ ግለሰቦች ናቸው። የሚሉት በስሜት ሳይሆን በማስረጃ ደግፈው ነው። እነዚህ ታዛቢዎች የግል ጥቅም አያገኙም። በእድገት፤ በስብአዊ መብቶች ስራ የተሰማሩ ስለሆነ ሃቁን መናገር ሞያቸው ነው። በአንጻሩ ደግሞ፤ በመለስ "እዱብ ድንቅ" አመራር የሚያምኑ፤ "የመለስ አምልኮት"ተከታዮች የአመራሩን ጠንካራ ጎን እንጅ፤ ወሳኝና ብልጫ ያለውን ደካማ ጎኑን ለመቀበል ሲቸገሩ ይታያል። በፖለቲካ ስልጣን፤ በመሳሪያ ሃይል ጡንቻ ሃገርን የሚገዛ፤ ሁል ጊዜም ድክመቱን አይቀበልም። ጥቅም ስላገኘበት። አገዛዙ በጋራ የሃገሪቱን ችግር ለመወጣት ማነቆ ሆኗል። ህወሓት እልከኛ የሆነበት ምክንያት "የልማት ምሽግ" ስለፈጠረ ነው። ይኼ የልማት ምሽግ የበላይነትን አመቻቶ አገሪቱን ለኪራይ ሰብሳቢው ቡድን ዳርጓታል። ኪራይ ሰብሳቢ የሆነ ቡድን ተወዳዳሪዎች አይፈልግም። አገር ወዳድ፤ ሕዝብ ወዳድ ስላልሆነ እድገትን የሚያይበት መነፅር ጠባብ ነው። አንዱ ከቻይና የሚለይበት ባህርይም ይኼው ነው። የቻይና መሪዎች ከሁሉም በላይ አገር ወዳድ ናቸው። አገር ወዳድነታቸውን

የሚያሳዩበት የእድገት መሰፈርት ድሃው ሕዝብ ወደ መካከለኛውና ከፍተኛ መደብ እንዲሸጋገር አመቻች መሆንን ነው። ርሃብ፤ ድህነት፤ ስራ አጥነት፤ መጠልያ አጥነት ወዘተ ለሃገሪቱ ሰላምና እርጋታ እንደሚነሱ ያውቃል። የቻይና መንግሥት ልማታዊ ነው ቢባል አግባብ አለው የምንለው ለዚህ ነው።

የመሰረተ ልማት አስተዋጽዖ

የመለስ መንግሥት አስተዋጽኦ በነጻነት፤ በፍትህ፤ በተሳትፎ፤ በህግ የበላይነት አይደለም። መሰረተ ልማት በማካሄድ ነው። በሃይል ማመንጫ ግድብ፤ በመንገድ ስራ፣ በትምኅርት ስርጭት፤ በጤና ጣቢያዎች መስፋፋት፤ በህንጻ፤ በከተሞች ስፋት፤ ወዘተ ያሳየው ለውጥ ሊናቅ አይችልም። ሆኖም፤ መሰረተ ልማት ከአብዛኛው ሕዝብ ኑሮ መሻሻልና ከምርት መጎልመስ ጋር አልተያያዘም። በመሰረተ ልማት የተገኘው እድገት አያስደንቅም። ሌሎች የኢትዮጵያ መንግስታት እነደዚህ ከፍተኛ የለጋሶች ድጋፍ አግኝተው አያውቁም። በእርዳታ ማግኘት መላቅ፤ መለስን ከነ ሌኒን፤ ማኦ፤ ሆችሚን፤ ኔልሰን ማንዴላ፤ አጼ ቴዎድሮስ፤ አጼ ምኒልክ፤ አጼ ኃይለ ሥላሴ ወዘተ ጋር የሚያወዳድር አይደለም። እድገቱ የማያስደንቀበት ዋና ምክንያት አለ። ከአጼ ኃይለ ሥላሴና ከመንግስቱ ሃይለማሪያ መንግሥታት ጋር ሲንጻጸር፤ መለስ የመራው መንግሥት ከልዩ ልዩ ለጋስ መንግስታት፤ ድርጅቶችና የግል ተቋሞች ቢያንስ $40 ቢሊዮን አግኝቷል። ወደ ሰላሳ ቢሊዮን የሚጠጋው ለልማት ተብሎ የተሰጠ ነው። ከእርዳታ ዘጠና በመቶ የሚሆነው የእድገት ባጀት ይሸፍናል ተብሎ የሚነገረው ለዚህ ነው። ዛሬ የብድሩ መጠን በአመት አራት ቢሊዮን ዶላር ደርሷል። በስደት ላይ የሚገኘው፤ ከአረብ አገሮች ውጭ ብቻ፤ ከሁለት ሚሊዮን በላይ የሚገመተው፤ የእድገቱ ተካፋይ ሆኗል። ቢያንስ፤ በአመት አራት ቢሊየን፤ ሰባት መቶ ሚሊዮን ዶላር ይልካል። ተሳትፎው ጎልቶ የሚታየው በተለይ በፍጀት ስራ ነው። የመጦሪያ ቤት፤ ህንጻ፤ የምግብ ተቋሞች፤ ሆቴሎች፤ ወዘተ፤ ቤተሰብ፤ ዘመድና ጓደኛ በመደጎም።

ስደተኛው የእድገቱ ደጋፊና ተጠቃሚ መሆኑ ተገቢ ነው የሚሉ ብዙ ታዛቢዎች አሉ። ይህ ብዙም አያከራክርም። አከራካሪ የሆነው፤ ስደተኛው ጠባብ ጎሰኛነት ያመጣውን ናዳ አለማየቱና ድጋፉ ግፈኛ አገዛዝ ማጠናከሩ ነው። አንዳንድ ተመለካቾች ስደተኛው ለግፈኛው አገዛዝ የሚሰጠው ድጋፍ የመንፈሳዊና የሞራል ሃላፊነቱን ጥያቄ ውስጥ አስገብቶታል ይላሉ። ይህን እንጋራለን። አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ በቀን ሶስት ምግብ ለመብላት ተቸግሯል። ወጣቱ ተስፋ ቆርጦ በሚሰደድበት፤ ልጃገረዶች በድህነት "ራሳቸውንና ክብራቸውን በሚነግዱበት"፤ ገበሬው የሚያርሰውን መሬት ባለቤትነት በተከለከለበት አገር ተአምራዊ እድገት አለ ብሎ ማስተጋባት ችግሩን አባብሶታል። አክብሮት ሊሰጠው የማይገባ አፋኝ መንግስት ተቀባይነት አለኝ እንዲል አደፋፍሮታል። ይህ የስደተኛ ደካማ ጎን ነው። ጠንካራ ጎንም አለው።

ዓለም ባንክ እንደሚገምተው፤ ቢያንስ አምስት ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን የሚደገፉት ስደተኛው በሚልከው ገንዘብ ነው። ሌሎች በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን የእለት ምግብ የሚያገኙት ለጋስ የሆኑ መንግስታትና ድርጅቶች በሚሰጡት ገንዘብና ምግብ ነው። ከሁለቱ መንግሥታት ጋር ሲወዳደር፤ የኃይለ ሥላሴ መንግሥት የእርዳታ ማሰረጃ መሰብሰብ ከተጀመረበት አንስቶ ያገኘው በአመት ከ $100 ሚሊዮን በልጦ አያውቅም። የወታደራዊ መንግሥት፤ በተለይ ከሶቪየት ህብረት ለመሳሪያ መግዣያ የወጣውን ጨምሮ ያገኘው $3.4 ቢሊዮን ብቻ ነበር። የደርግ መንግሥት በአስራ ሰባት አመታት ያገኘውን ህወሓት/ኢህአዴግ ዛሬ በአንድ አመት ያገኛል። ሁለቱ መንግሥታት ከእርዳታ የተገኘ ገንዘብ በመስረቅና በማሸሽ (*Massive Illicit Transfer)* አልተከሰሱም። በአንጻሩ፤ የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት በሙስና፤ ከህግ ውጭ ገንዘብ በማሸሽ የመጀመሪያውን ቦታ ይዟል። በአመት፣ ቢያንስ፤ $3.26 ቢሊዮን ከህግ ወጭ ከአገር ይወጣል። ሙስናና ከህግ ውጭ የገንዘብ ሽሽት ባይኖር፤ ስርአቱ ተሳትፏዊና ፍትሃዊ ቢሆን፤ የኢትዮጵያ የእድገት ደረጃና የስራ እድል ከፍ ይል ነበር። የዋጋ ግሽበት አይባባስም ነበር ወዘተ። የተገኘው እድገት ዘላቂና ፍትሃዊ ነው ለማለት አይቻልም። የነፍስ ወከፍ ገቢ ፍጹም ደሃ ከተባሉት እንደ ናይጀርና ማሊ ካሉት ሊለይ አይችልም። የአፍሪካ አማካኝ የነፍስ ወከፍ ገቢ $1,070 ነው። የኢትዮጵያ አሁንም ከ$ 240 እስከ $374 ይገመታል። በዓለም ዝቅተኛ ከሆኑት መካከል አንዷ መሆኑ ነው። ስደተኛው በውጭ ሰርቶ ኢትዮጵያ ለሽርሽር ሲመላለስ፤ ቤትና ንብረት ሲይዝ አጠያያቂ የሆነው በግልጽ የሚታይ የሃብትና የኑሮ ልዩነት እያየ ለምን ለህብረተሰቡ ጠበቃ ለመሆን አልቆረጠም የሚለው ነው። "ስደተኛው የኑሮውንና የሃብት ክምችትን አሰቃቂ ልዩነት እንደ ፈረንጆች ማየት ጀምሯል" የሚል "ወቀሳ" ከዚህ የመነጨ ነው የሚሉ በአገር ቤት የሚኖሩ ብዙ ናቸው። ስደተኛው ከያለበት ወደ አገር ቤት የሚወስደው መጥፎ ባህል የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥሩ ባህል እየጎዳው ነው የሚል በግልፅ ይሰማል።

"አስደናቂ እድገት ተጎናጽፋለች" በምትባለው ኢትዮጵያ፤ በደሃና በሃብታም መካከል ያለው የኑሮ ልዩነት አደገኛ ደረጃ ላይ ደርሷል። ሊገታ የማይችል የዋጋ ግሽበት የሰውን ኑሮ ጎድቷል። የወጣቱ እድል ተምሮ መሰደድ ተደጋጋሚ ሆኗል። የክልሎች እድገት በፖለቲካ እየተወሰነ ነው። ፖሊሲውና መዋቅሩ የፈጠራቸው፤ ያለ ዲሞክራሳዊ ለውጥ፤

ህወሓት/ኢህአዴግ ብቻውን ሊፈታቸው የማይችል መሆኑን የሚያሳዩ መለኪያዎች ናቸው። ነጻነት፤ የሕዝብ ድምጽና ቀጥተኛ ተሳትፎ አለመኖሩ፤ ስርአቱ ለፍትህ፤ ለሰላም፤ ለእርጋታ፤ አብሮና ተቻችሎ ለማደግ፤ ድህነትንና ኋላ ቀርነትን ለማጥፋት፤ "ሽብርተኛነትን" ለመከላከል፤ አስጊ ሁኔታዎችን ፈጣሪ ሆኗል። መፍትሄ ሰጭ አለመሆኑን የሚያሳዩ መለኪያዎች ብዙ ናቸው። እነዚህ ችግሮች አጥጋቢ በሆነ ደረጃ ቀንሰዋል ለማለት ምልክት ለማግኘት አንችልም። ህወሓት/ኢህአዴግ አገሪቱን ከኋላ ቀርነት፤ ከረሃብ፤ ከስደት፤ ከጥገኛነት፤ ከተስፋ መቁረጥ ነጻ ለማድረግ አልቻለም። ገዢው ፓርቲ የእነዚህን ችግሮች መኖር ለመካድ አይችልም። የእድገት ማስረጃዎች እየፈጠረ፤ የእርሸ ምርት "አስደናቂ በሆነ ደረጃ አድጓል" ብሏል።

የእርሻ ምርት ካደገ ለምን ሕዝብ እንደሚራብ፤ ለምን የምግብ እጥረት፤ የዋጋ ግሸበት እንዳለ ለማስረዳት አልቻለም። አድናቂ የሆኑ መንግስታትና ለጋሶች ተሳትፎ፤ ከተሳትፎ የሚመጣ ፍትህ አለመኖሩን ያውቃሉ። ጠለቅ ብሎ ያየ አገር ወዳድ፤ የገዢው ፓርቲ ተራ አባል፤ የውጭ ተመልካች፤ ህወሓት/ ኢህአዴግ እነዚህንና ሌሎችን አገራዊ ችግሮች ብቻውን ሊፈታቸው እንደማይችል ይገነዘባል። ግንዛቤ ካለ፤ የፖለቲካ ፈቃደኛነት መኖር አለበት። የፖለቲካ፤ የማህበራዊ ኑሮ፤ የኢኮኖሚ ተሳትፎ ሜዳ (Space and Field) ከአድሏዊነት ወደ ተሳታፊነት መሸጋገር አለበት።

አዲስ የለውጥ ምእራፍና አዲስ አቅጣጫ ይታያልን?

የዚህ ምእራፍ ዋና አላማ፤ የኢትዮጵያን ሁለ ዘርፍ የሆኑ ችግሮች በጋራ ለማስወገድ ከተፈለገ የአንድ ፓርቲ የበላይነት አገዛዝ ሳይውል ሳያድር መለወጥ አለበት የሚል ነው። መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የስልጣኑ ባለቤት እንዲሆን፤ መንግሥትና መሪዎች የሕዝብ ተገዥ፤ ለሕዝብ አገልጋይ እንዲሆኑ፤ አዲስ ምእራፍ መከፈት አለበት። አሳታፊ የሆነ የኢኮኖሚ አመራር ቀጣይነት ላለው ልማት መሰረት ነው። አገሪቱን ከከፋ አደጋ ለማዳን ከተፈለገ፤ ፍትሃዊነትንና እኩልነትን የሚያስተናግድ መንግሥት መቋቋም አለበት። በእውቀትና በብልሃት የተጸነሰ ሽግግር ማድረግ አስፈላጊ ነው የሚለውን መሰረተ ሃሳብ ህወሓት/ኢህአዴግና ተቃዋሚ ሃይሎች ከተጋሩ፤ ወደዚህ የሚያደርሱ አመቻች የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን (Favorable Conditions) መፍጠርና ድልድይ መስራት አለባቸው። ለኢትዮጵያ አገራዊ አንድነት፤ ለመላው ሕዝቧ ሰላም፣ ለፍትህ፤ ለብልጽግና፤ ለእኩልነት፤ ለነጻነት፤ ለከብር፤ ከረሃብ አለንጋ፤ ከጥገኝነትና ከስደት ነጻ ለመሆን፤ ቆመናል የሚሉ መንግስታት፤ ተቋሞችና ግለሰቦች ሊረዱ የሚገባቸው ለህወሓት/ኢህአዴግ ቼክ በመጻፍ አይደለም። አገዛዙ ስልጣን ለሕዝብ እንዲያመቻች መቀስቀስ ነው። ገንቢ አስተዋጽኦ ነው ብለን የምንቀበለው ለጋሶች ገዢው ፓርቲና ተቃዋሚ ሃይሎች በአስቸኳይ ሁሉን አቀፍ የሆነ፤ አገራዊ ስብሰባ እንዲያደርጉ መቀስቀስ ብቻ ነው። ይህ ካልተደረገ፤ መለስ "ኢትዮጵያ እንደ ሶማሊያ ትሆናለች" ያለው ትንብይት ሊደርስ ይችላል።

"እርቅ፤ በወርቅ የማይገዛ እሴት ነው"

መቻቻል ለልማት ቁልፍ ነው። እስካሁን ያልተደረገ የፖለቲካ ባህልና ሂደት ቢኖር፤ ኢትዮጵያንና መላውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ማእከልና ተቀዳሚ አድርጎ ለሰላም፤ ለፍትህና ለሕዝብ የበላይነት፤ ለእርቅ፤ ለእኩልነት፤ ለመግባባት፤ በውይይት ልዩነቶችን ለመዳኘት መሞከር አለመቻሉ ነው። የህወሓት ጠባብ ጎሰኛ አገዛዝ የተዋቀረው በብሄር ጥላቻ ነው። የአማራን ብሄረሰብ ለማንበርከክ። ጥላቻ የልማት ዋጋ ይከፈልበታል። ሰላም፤ እርቅ፤ ይቅር ባይነት፤ ለወደፊቱ ትውልድ ማሰብ፤ የአገርን፤ የሕዝብን ችግሮች በጋራ ለማስወገድ መሞከር የተለመደ ዘመናዊ ባህል አይደለም። የህወሓት የበላዮች አብሮ መኖር "ያዳክመናል፤ የስበላናል፤ የዘረፍነውን ያስመልስብናል" የሚሉ ይመስላሉ። በዚህ ከቀጠሉ የሚበላው መላው ህብረተሰብ ሊሆን ይችላል። ለዚህ ጠባብ አመለካከት የረዳው፤ የተማረው ክፍል የፖለቲካ ባህል ኋላ ቀርነት ነው። ሃሜት፤ መኮራረፍ፤ አንዱ በሌላው ላይ ሴራ ማካሄድ። ስም መጠፋፋት። ለግልና ለቡድን ጥቅም መከራከር። በጠመንጃ አፈሙዝ አስፈራርቶ መግዛት ወዘተ ናቸው። እነዚህን ለለውጥ ማነቆ የሆኑ እሴቶች ማስወገድ ለተከታታይና ለፍትሃዊ ልማት አስፈላጊ ነው። አዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር ሃይለማሪያም ደሳለኝ  ለዚህ አዲስ ምእራፍ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ የማይገኝ እድል ተሰጥቶታል። ይህን እድል መጠቀም ለመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ጠቃሚ መሆኑን ማወቅ የራሱ ሃላፊነት ነው። የኢትዮጵያ የደህንነትና የመከላከያ ሰራዊት ቃል በገባው የሕዝብ አደራ መሰረት፤ የአንድ ፓርቲ የበላይነት ጠባቂና አገልጋይ መሆኑን ማቆም አለበት። የወገኑን አገልግሎት፤ የሕዝቡን አለኝታነትና ክብር፤ የኢትዮጵያን ግዛታዊ አንድነት ብቻ ማስቀደም የወቅቱ ዋና ስትራተጂክ ጥያቄ እየሆነ መጥቷል። የጦሩ የበላዮች በጥቅም መገዛት የመከላከያውን ሃላፊነት ይጎዳዋል የሚል ግምት አለን። ዘጠና በመቶ የሚሆነውን ከሁሉም ብሄር/ብሄረሰቦች የተወጣጣ ተራ የመከላከይ ሃይል አባል፤ መካከለኛ እዝ፤ ከአንድ ብሄር የተወጣጣው የበላይ የአንድ ብሄር እዝ ሊወክለው አይችልም። ተራው አባል፤ ይህ አድልዎ አይገባም ብሎ አደራውን እንዲወጣ መነጋገር ይኖርበታል። መንግሥት የግለሰቦችን መብት ማክበር አለበት ብሎ ወገኖቹን አልገድልም ሊል ይችላል። የሰላም፤ የእርቅ፤ የመወያየት፤ አብሮ ችግሮችን የመፍታት ጥሪን እንዲደግፍ ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ የሚያስፈልገው ለዚህ ነው። መብቶች ካልተከበሩ፤

ሰላምና እርጋታ አይኖርም። ሰላምና እርጋታ ከሌለ ዘላቂነት ያለው፤ ለሁሉ አሳታፊ የሆነ ልማት አይኖርም። ጠንካራ ኢትዮጵያ ልትመሰረት የምትችለው ጠንካራ፤ ኑሮው የተሻሻለና አስተማማኝ የሆነ ሕዝብ ሲኖር ብቻ ነው። ጠንካራ ሕዝብ ያለ ፍትህ፤ ያለ እድገት፤ ያለ ነጻነት፤ ያለ ኑሮ መሻሻል ሊኖር አይችልም። ይህን የመከላከያ ሃይሉ ማወቅ ታሪካዊ ግዴታው ነው።

ከመለስ ለቅሶ ባሻገር እንይ

የኢትዮጵያ ሕዝብ አገር አቀፍ በሆነ ሁኔታ፤ ተገዶም ሆነ ፈቅዶ ለመለስ ማልቀሱ በአብዛኛው ሕዝብ ላይ ያለውን ብሶትና ጭንቀት፤ በወጣቱ ላይ የደረሰውን አሳፋሪ የስደት እጣ፤ በፍትህ ላይ ያለውን ተደጋጋሚ (Recurring) አፈና፤ በአገሪቱ ላይ የሚያንዣብበውን ግልጽ አደጋ ሊሸፍነው አይችልም። ተማሪዎች፤ በሆስፒታል የሚታከሙ በሽተኞች በለቅሶው እንዲሳተፉ መገደዳቸው ያሳፍራል። ከዘጠና አራት ሚሊዮን ሕዝብ አምሳ ሽህ፤ መቶ ሽህ፤ ተሳተፈ ቢባል፤ መለስን እንደመላክ አመለከ ማለት አይደለም። ፓርቲው የመንግሥት ባጀት ተጠቅሞ፤ ከስድስት ሚሊዮን በላይ አባል መሰብሰቡን አንርሳ። ሆኖም፤ ተሳትፎው አያስገርምም ብለን ልናልፍ እንችላለን። ስሜን ኮሪያም በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ለኪም ኢል ሶንግ አልቅሷል። በደርግም ጊዜ ሰው ተገዶ ተሰልፏል። ንግግሩ፤ ውይይቱ፤ የውጭ መንግስታት ፕሬዘደንቶችና ተወካዮች ለለቅሶው ለምን መጡ። መለስን ለምን አሞገሱ። በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ፤ ኢትዮጵያውያን በዘር፤ በሃይማኖት፤ በጾታ፤ በእድሜ፤ በገቢ፤ በኑሮ ሳይገቱ ለምን አለቀሱ። በለቅሶው ወቅት ለምን ሕዝቡ የእምቢተኛነት ስሜት አላሰማም የሚለው አይደለም። ስሜት ስለሆነ፤ የዚህ አይነት አስተያየት የትም አያደርስም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ጨዋነቱን፤ ኢትዮጵያዊነቱን፤ ሰብእነቱን፤ አስመስክሯል። ሁኔታው ቢፈቅድለት ኖሮ፤ አጼ ኃይለ ሥላሴ ሲያርፉ፤ አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ በሆነ መልኩ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ባለቀሰ ነበር። የሚያሳፍረው፤ የደርግ መንግሥት፤ ለአፍሪካ ሕዝብ ነጻነት ፊት ለፊት ሆነው የታገሉትን፤ ከደሃ አገር ገቢ ለአፍሪካ ታጋዮች ድጋፍ የሰጡትን፤ ለአፍሪካ አንድነት ማህበር መደራጀት የሚያኮራ አስተዋጽኦ ያደረጉትን፤ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በአዲስ አበባ እንዲመሰረት ያደረጉትን መሪ በድብቅ እንዲቀበሩ አደረገ። ክብራቸውን በመግፈፍ የኢትዮጵያን ሕዝብ ክብር ገፈፈ። በዚያ ጊዜ የነበሩ እንደሚያስታውሱት፤ በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በየቤታቸው አልቅሰዋል። ከዚያ ወዲህ፤ ሁኔታዎች አስደናቂ በሆነ መልክ ተለውጠዋል። ከግማሽ በላይ (More than 50 percent of the Ethiopian population) የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያውቀው አንድ መሪ ነው። መለስ ዜናዊን። ከንግሥት ዘውዲቱ በኋላ፤ (መቶ አመት)፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በጤና ምክንያት ከዚህ ዓለም ያለፈ መሪ ሲቀብር የመጀመሪያው መለስ ነው። ከሃዘኑ ባሻገር ልብ ብለን ማየት ያለብን፤ መለስ የተለቀሰለት፤ የተቀበረው እንደ አንድ ብሄር ተወካይ፤ እንደ አንድ ትግራይ ተወላጅ ሳይሆን፤ "እንደ ኢትዮጵያዊ መሪና እንደ ኢትዮጵያዊ ዜጋ" ነው። ይህ የኢትዮጵያን ሕዝብ ታላቅነት፤ ይቅር ባይነት፤ ያሳየ የለውጥ ምልክት ነው። የዚህን ትርጉም ለታሪክ ተመራማሪዎች እንተወዋለን። በህይወቱ ሳለ፤ መለስ የአፍሪካ አንድነት ማህበር፤ ታላቅ ህንጻ በቻይና መንግስት ወጭ ተሰርቶ ሲመረቅ፤ ከፊቱ የሚቆመው ሃውልት ለአጼ ኃይለ ሥላሴ ይገባል ብሎ አልተከራከረም። የንክሩማ ይሁን አይሁን አይደለም። ለአፍሪካ ነጻነትና አንድነት ከማንም በላይ የታገለች ኢትዮጵያ ናት። ይህን ታሪካዊ አስተዋጽኦ የመሩት አጼ ኃይለ ሥላሴ ናቸው። ለዚህ ክብርና ማስታወሻ፤ መለስ ቁሞ አልተናገረም። የትምኅርት እድል ለሱም፤ ለእኔም፤ ለሌችም የከፈቱትን ንጉሥ አላከበረም ። ክብር የሚገባው ሌላውን ያከበረ፤ የሌላውን መብት የተቀበለ፤ እውነቱን ሁልጊዜ የተናገረ፤ ታሪኩን የማይክድ፤ የግዛት አንድነትን የሚጠብቅ መሪ ነው። በማንም አገር የመሪ ታላቅነት በጥቂቶች የበላይነት ተወስኖ አያውቅም። ህወሓት ኢትዮጵያን ለይቷታል።

ይህ እንዳለ ሆኖ፤ ለመለስ የተደረገው ለቅሶ ትርጉም እንዳለው እናምናለን። ኢትዮጵያውያን የሚፈልጉት በኢትዮጵያዊነቱ ኮርቶ፤ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን አገልጋይ የሆነ መንግሥትና መሪ ነው። አገሪቱ ከታላቅነት ደረጃ እንድትደርስ ከተፈለገ፤ ለመዳዝ የሚቻለው በኢትዮጵያዊነት፤ በእውነተኛ እኩልነት፤ በዲሞክራሳዊ አገዛዝ፤ በሕግ የበላይነት ወዘተ መንገድ ነው። ለመላው ኢትዮጵያውያን አገልጋይ የሆነ ፍትሃዊ ስርአት ለሃገሪቱ ህልውና ወሳኝ ነው። ህወሓት ባለፉት ሃያ ሶስት አመታት የፈጠረውን የብሄርተኛነት/ጎሰኛነት ጥላቻና የአድልዎ ፖለቲካ አወቃቀር ስናይ፤ ሁሉም የሚጋራው መንገድ መቀየስ ቀላል አይደለም። ተቃዋሚውና አዲሱ ትውልድ አልለመደውም። ያልተለመደ አገዛዝ ያስቸግራል። የህወሓት/ኢህአዴግ ብዙ ዘርፍ ያለው አፋኝ አገዛዝ መለስ በማለፉ አልተለወጠም። የአንድ አምባገነን ስርአት፤ ለአንድ አምባገነን ፓርቲ አገልጋይ የሆኑ ተቋማት ተክሎ አልፏል። በአሁኑ ወቅት፤ በህወሓት ውስጥ የሚካሄደው የጦፈ ግብግብ፤ "የመለስን ራእይ እንቀጥል፤ አለበለዚያ መጥፊያችን ነው" በሚሉ ግትሮችና "ገነሳ አድልዎ፤ ሙስናው ይቁም። ሌሎችም በስልጣን መሳተፍ አለባቸው። አዲሱን ጠቅላይ ሚንስትር እንደግፈው" በሚሉ መካከል

እንደሆነ ለመገመት አያዳግትም። ቅድመ ሁኔታዎች ተስተካክለው፤ ሁሉን የሚያካትት መንገድ ካልተቀየሰ፤ የአምባገነኑ ስርአት እንዳለ ይቆያል። ወይንም በሕዝብ አመጽ ይናዳል። አደጋው በዚያው ልክ ያይላል።

ለዚህ ነው፤ የጠቅላይ ሚንስትሩ የውጭ አገር አድናቂዎች፤ ለኢትዮጵያ እርጋታ፤ ለመላው ሕዝቧ ሰላም፤ ከረሃብ አለንጋ፤ ከስደት፤ ከበሽታ፤ ከመጠለያ ማጣት ወዘተ ነጻ መውጣት ካሰቡ፤ የስርአቱን ደካማ ጎን ማሳየት ይኖርባቸው ነበር የምንለው። ፕሬዘደንት አባማ ለነጻነት፤ ለሰላም፤ ለዲሞክራሲ መቆሙን ለራሱ በተወዳደረበት በ 2012 ምርጫ አስመስክሯል። ለውጥ ፈላጊ ኢትዮጵያውያን ከበረቱ አዳማጭ እንደሚያገኙ እናምናለን። በመለስ ለቅሶ ላይ የሆነው "የመለስ አምልኮን" አጠናካሪ ምስጋና የአሜሪካ ሕዝብ የሚቀበለው አይደለም። የዲፕሎማቲክ ፕሮቶኮል ካልፈቀደ፤ ሱዛን ራይስ ሆነች ሌሎች አድናቆቱን ለዛ፤ ሚዛናዊና እውነተኛነት በተሞላበት፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ "ደንቆሮ" በማያደርግበት መልክ ማቅረብ ነበረባቸው። ፌዝ ካሪሚ በሲኤንኤን September 3, 2012, "የሰብአዊ ሙብት ተቋሞች እንደሚሉት ከሆነ፤ መለስ የግለሰቦችን ነጻነትና ሙብቶች ደጋግሞ ጥሷል። የመገናኛ ብዙሃንን አጥፍቷል። ጋዜጠኞችን አስሯል። አሳዷል። ተቃዋሚ ድርጅቶችንና መሪዎችን መንጥሯል። የምእራብ አገሮች ይህ ሁሉ ሲሆን፤ የመለስን ድክመት እንዳላዩ አልፈውታል። ለእነሱ፤ የመለስ ጸረ-ሽብርተኛ ሆኖ በአፍሪካ ቀንድ መቆም የወዳጅነት ዋና መለኪያ ነበር።" አመስጋኞቹ፤ ጠናካራ ጎን ብቻ በማንሳት፤ የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት ተቃዋሚ የሆነውን ሁሉ መግደሉን፤ ማሰሩን፤ ማሳደዱን፤ ከሃብትና ከመሬት ማንሳቱን የአገዛዙ ስልትና መለያ አድርጎ መጠቀሙን መቀጠል ደግፈዋል።

የአጃንስ ፍራንስ ፕሬስ ጀኒ ቮጋን፤ በ September 1, 2012, ሚኬላ ሮንግን (Michela Wrong, an authority on ethnic elites and corruption in Africa) በመጥቀስ፤ የመለስን ማረፍ እንዲህ ብላ አስቀመጠችው። "የገዢው መደብ የበላዮች (the Ruling Ethnic Elites) ፍላጎት ጥቅማቸውን ማስከበር ብቻ ነው። እርጋታን የሚፈልጉት ለዚህ ነው።" እርጋታ መፈለጋቸው በቀጥታ ከምእራባውያን መንግስታት ጋር ያላቸውን ግንኙነት ያጠናክርላቸዋል። ሁለቱም፤ ከነጻነትና ከእውነተኛ ዲሞክራሳዊ ስርአት በላይ እርጋታን ይፈልጋሉ። ተቃዋሚዎችም ሆኑ፤ ህወሓት/ኢህአዴግ ይህን የተሳሰረ የጥቅም ግንኙነት በመነጋገር ለመፍታት ካልቻሉ ህብረተሰቡ ይጎዳል ። ሁለቱም ወገኖች፤ የተፈጠረውን የእድል ቀዳዳ ተጠቅመው፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብሩህ የሆነ አቅጣጫና መልስ መስጠት አለባቸው። ገዢው ፓርቲ ምርጫ ማካሄዱ ጥቅም የለውም። ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዳይሳተፉ በሩን ዘግቷል። ሁለቱም ወገኖች፤ በመጀመሪያ ማመን ያለባቸው፤ መልሱን ለመስጠት የሚችለው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በጋራ ለሙብቱ ሲቆምና ሲታገልና በውሳኔው ሲካፈል ብቻ መሆኑን ነው። አገልጋይነታቸውና ተጠሪነታቸው ለድርጅት ወይንም ለአንድ ብሄር/ብሄረሰብ መሆኑ መቆም አለበት። ለኢትዮጵያና ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑን ካወቁ ሌላው ሁሉ ችግር ይፈታል። የትግሉ አላማ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሳዊ ስልጣንና የበላይነት። የትግሉ ሜዳ፤ ኢትዮጵያ። ታጋዩ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ነው በማለት በመደጋገም ከሌሎች አገሮች ልምድና ከኢትዮጵያ ሕዝብ መስዋእት ጋር በማያያዝ ያቀርብኩትን ዘገባ አስታውሳለሁ። 7/

ከአንዳንድ ግለሰቦችና ቡድኖች እንደሚነገረው ሳይሆን፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ገዢው ፓርቲ ከመረጣቸው ውጭ ያለው አብዛኛው፤ ሰነፍ አይደለም። "ደንቆሮ" አይደለም። በታሪኩም፤ ሰነፍና "ደንቆሮ" ሆኖ አያውቅም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀን ከሌት ሰራተኛ ነው። ራሱን ለማሻሻል ይፈልጋል። የሚፈልገውን ስርአት ያውቃል። ወዳጅና ጠላቱን ለይቶ ያውቃል። ሁኔታው ሲፈቅድለት፤ አገዛዙ የተዛባና ጸረ- ፍትህ መሆኑን እያየ ሲሄድ፤ የመሻሻል ቀዳዳዎች ሁሉ ሲዘጉበት መነሳቱ አይቀርም። አሁንም በየቦታው በእውን እያሳየ ነው። የእስልምና ሃይማኖት ተከታዩ የሚታገለው ለራሱ ሙብት ብቻ አይደለም፡፡ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጭምር ነው። በዋልድባ ያሉ ክርስቲያኖች ሲታገሉ ለራሳቸው ብቻ አይደለም። ለኢትዮጵያ ሕዝብ እኩልነት ጭምር ነው። ሁለቱም የሃይማኖት ተከታዮች የሚሰጡት መልእክት አለ። ሕዝብ ያልፈለገው፤ ያልመረጠው፤ መንግሥትና አመራር ያስከተለውን ጉዳትና በደል "እናውቃለን" የሚል ነው። ሕዝቡ በገፍ ለመለስ ለቅሶ መውጣቱ ያለውን ብሶትና ሰቆቃ እንደማይሸፍነው የተረዳ ሕዝብ ነው።

በሃይማኖት ነጻነት ላይ የሚደረገው ጣልቃ ገብነት ለኢትዮጵያ የውጭ ጠላቶች እሮይ የሚያሰኝ አደገኛ አደገኛ ሂደት ነው። አብሮና ተቻችሎ ለሚኖረው ህብረተሰብ እርጋታና ሰላም መንሳቱ፤ መሪዎች መታሰራቸው፤ የግብጽ መንግስት የአባይን ግድብ አስመልክቶ፤ እዋጋለሁ የሚለው ከፈርኦኖች ታሪክ ጀምሮ ኢትዮጵያን ሲያደክማት፤ ሲያከፋፍላት፤ ለጦር ሲዳርጋት፤ ሕዝቡን እርስ በእርሱ ሲያምስ የቆየው አሁንም አለመብረዱ ምሳሌ ናቸው። የግብፅ መንግስትም ሆነ ገዢው ፓርቲ የሚጠቀሙበት ዘዴ መከፋፈልን ነው። ይህ ያላየው በሃይማኖት ልዩነት ሰበብ የውጭ ጣልቃነት ኢትዮጵያን ለማድከም፤ እርስ በእርስ ለማዋጋት፤ ወደኋላ ለማስቀረት፤ ከሚደረገው ሴራ ጋር የተያያዘ ነው። ይህን ችግር የተከለውና ያባባሰው ህወሓት/ኢህአዴግ ነው። " ኑ፤ ግቡ፤ ስሩ፤ ተዝናኑ" ካለ በኋላ "ሽብርተኞች ቀሲቃሽ ናችሁ" ይላል። ዋናው ጠንቅ ጠባብ ጎሰኛነት ነው።

የጠባብ ብሄርተኛ የፖለቲካ አቀራረጽና አመራር ለግለሰብ መብቶች፤ ለሕዝብ ነጻነት፤ በእኩልነት ብቻ ለሚገኝ ህብረት ማነቆ ነው። ለአገር ግዛታዊ አንድነት ጸር ይሆናል። ለጥቂት የበላዮች (Ethnic elites) የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት አስተማማኝ መሆኑ ጊዜያዊ ጥቅም ሰጥቷል። በውስጡ ግን የሚፈነዳ ቦምብ ቀብሯል። በውስጡ "የተጣላ ህብረተሰብ" በክብሪት ቢጭሩት የሚቃጠልበትን ሁኔታ እየፈጠረ ነው። ማንም ሊቆጣጠረው የማይችል ሊሆን ይችላል። ይህን የተቀበረ ቦምብ መፍታት የአመራር ብስለት ይጠይቃል። ችግሩን የሚፈታው፤ ሁሉም ኢትዮጵያውያን የሚያድጉባት፤ በእኩልነት፤ በፍትህ የተመሰረተ አገዛዝ ሲመሰረት ነው። ኑሮው የተሻሻለን ህብረተሰብ፤ የግብጽ መንግስት ሆነ ሌላ አያጠቃውም። የተፈጥሮ ሃብቱን ማንም አይቀማውም። በአንጻሩ፤ ጎሳዊና አድሏዊ የሆነ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ስርአት ለህብረተሰቡ፤ በተለይ ለወጣቱ ትውልድ እድል ፈጣሪ አይሆንም። ለስደት የዳረገው መሆኑን አይተናል። ስደት ለክብርና ለዜግነት/ኢትዮጵያዊነት ማነቆ መሆኑን በይፋ እያስመሰከረ ነው። ከሰባ እስከ ሰማንያ በመቶ የሚሆነው ወጣት ስራ ለማግኘት ተቸግሯል። ተስፋ ቆርጧል። በመንግሥቱ ላይ እምነት የለውም። ይህ ሁኔታ ለኢትዮጵያ ህብረተሰብ ድክመት አስተዋጽኦ እያደረገ ነው። ጥቂት የህወሓት/ኢህአዴግ ቤተሰቦች፤ ባለስልጣናት፤ የፓርቲው ተቋሞች ዋና ተጠቃሚዎች ሆነዋል። ኤፈርትና ሌሎች የህወሓት ድርጅቶች ኢኮኖሚውን በሙሉ ቁጥጥር ስለያዙት፤ ነጻ የገበያና ውድድር የለም። ኢኮኖሚው የፍጆት እቃዎችን፤ ምግብን፤ መድኃኒትን፤ ማዳበሪያን፤ ወዘተ ለማቀርብ አልቻለም። አቅርቦትና ፍላጎት የሰማይና የምድር ያህል ተራርቀዋል። የዋጋ ግሽበት፤ የምግብ እጥረት፤ የብር ዋጋ መውረድ ተራውን ሆነ መካከለኛውን መደብ አድክመዋል። ሕዝቡ ቤት ለመግዛት ቀርቶ ለመከራየት አልቻለም። ልጆቹን ማስተማር ህልም ሆኖበታል። ተስፋ የቆረጠ ጎልማሳ በትጥቅ እታገላለሁ ብሎ ቢነሳ ሊያቆመው የሚችል ሃይል የለም። በድምራቸው ሲታዩ፤ እነዚህ ድክመቶች ለኢትዮጵያ መናጋት አስተዋጽኦ እያደረጉ ነው። የዚህ ተጠቃሚዎች የኢትዮጵያ ጠላቶች እንደሚሆኑ አንጠራጠርም።

በህወሓት የበላይነት የሚመራው መንግሥት የትምኅርት እድል አስፋፍቷል። ተመጣጣኝ የስራ እድል ለመፍጠር አልቻለም። ትምኅርቱ ጥራት የለውም። ለሃያ አንደኛው መቶ ዘመን የውድድር ዓለም በቂነት አላሳየም። የተማረው ወጣት እጣው ስደት ሆኗል። ስደተኞች በሚሄዱበት ሁሉ ክብራቸው ይገፈፋል። ህይወታቸው ለአደጋ ይዳረጋል። ይህ የእድገት ምልክት ነው ብሎ ለመቀበል አይቻልም። እድገቱ የእድል በር የከፈተው ለበላይ ባለስልጣናትና ቤተሰቦቻቸው፤ ለታማኞቻቸውና ወዳጆቻቸው፤ ለካድሬዎችና ወጣት ልጆቻቸው ነው። የእድገት ሊቆች፤ ጥራት ያለው ትምኅርት፤ ለሁሉም እድል የሚሰጥ የወደፊት እድል ወሳኝ ነው ይላሉ። በብሄር ልዩነት፤ ተማሪዎች የሚያገኙት ግብአት- መጽሃፍ፤ አስተማሪ፤ ላይብራሪ፤ ኮምፒዩተር ወዘተ- የተለያየ ከሆነ የተለያየ ውጤት ያመጣል። የተለያየ ውጤት የተለያየ እድል ይከፍታል። በአብዛኛው ሲታይ፤ ህወሓት ስልጣኑን ተጠቅሞ፤ በትምኅርት እድልም በብሄር የተለያየ ድጋፍ ይሰጣል። በትግራይ ያሉ ትምኅርት ቤቶችና በኦሮሚያ ያሉ ተመሳሳይ አይደሉም። በትግራይና በአማራ ክልል ያሉ ተመሳሳይ አይደሉም። በወጣት ብዛት ያለው የባጀት ድጋፍ በጣም የተዛባ ነው። እየባሰ የሄደው ልዩነት፤ በገቢና በሃብት ብቻ ሳይሆን፤ የወደፊቱን የወጣት ህይወት ሂደት በሚመለከት የትምኅርት እድል ዙሪያ ነው። የትምኅርት ባለሙያዎች ጥልቀት ያለው ጥናት አካሂደው ያለውን ልዩነት ቢያሳዩና መፍትሄ ቢያመለክቱ ይረዳል። መሻሻል አልታየም ማለት አይደለም። ከምርጫ ዘጠና ሰባት ወዲህ ያለው የትምኅርት እድል ስፋት ከዚያ በፊት ከነበረው ይሻላል። ምርጫው ለወጣቱ እድል ከፍቷል። ወደፊትም ተወዳዳሪነት ያለው ምርጫ ቢካሄድ አሁን ያለው የትምኅርት መዛባት ይሻሻላል ከሚል ድምዳሜ እንደርሳለን።

ከትምኅርት ጋር አብሮ የሚሄደው ዘመናዊ የመገናኛ፤ የእውቀት መሸመቻ ቴክኖሎጂ መስፋፋት ነው። ሌሎች አገሮች የመገናኛ ብዙሃንን በማስፋፋት፤ በማዳረስ፤ ለነጻነትና ለእድገት ከስራ ላይ አውለውታል። የባንግላደሽን፤ የኬንያን፤ የጋናን፤ ሁሉን አቀፍ እድገት ከኢትዮጵያ የሚለየው አንዱ የዘመናዊ መገናኛ ብዙሀን ስርጭት በእነዚህ መስፋፋቱና በኢትዮጵያ መከልከሉ ነው። በአንጻሩ፤ ገዢው ፓርቲ ቁጥጥሩን አስፋፍቶ እድልን መወሰኑ፤ ተማሪዎች፤ አስተማሪዎች የመፍጠር፤ የማሰብ፤ የመጻፍ መብታቸው ታግዶ ፓርቲው ያለውን ብቻ ተቀበሉ መባላቸው፤ በገፍ አባል እንዲሆኑ መገደዳቸው፤ ለአገሪቱ እድገት ማነቆ ሆኗል። እድገት ያለእውቀት፤ እውቀት ያለ መገናኛ ብዙሃን ሊንቀሳቀስ አይችልም። ነጋዴ ሆነ ታክሲ ነጅ፤ አስተማሪ ሆነ፤ ተማሪ፤ የመንግሥት ሰራተኛ ሆነ የግል ንብረት አንቀሳቃሽ፤ የሚጠይቀው ተገቢ ጥያቄ አልተመለሰም። ጠያቂዎች እንደወንጀለኛ እየተቆጠሩ ችግር ላይ ወድቀዋል። የኢትዮጵያ መንግሥት የሚያዳምጠው እራሱን ነው። በመገናኛ ብዙሃን ያለው ገደብ፤ በግል የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ያለው የአተዳደር ጫና፤ ለእድገት ማነቆ ሆነዋል። መንግሥት ለማስተዳደሪያና ለስለላ የሚያወጣው ባጀት ከአገሪቱ አቅም ጋር አብሮ የማይሄድ ሸክም ሆኗል። ይኼን ከባድ እዳ የተሸከመው ሃብቱን ያሸሸውና በማሸሽ ላይ ያለው ስርዓት ወለዱ ሃብታም አይደለም። የኢትዮጵያ ደሃ ሕዝብና ተከታታይ ትውልድ ነው።

የቀረው ዓለም፤ በተለይ እንደ ጋና፤ ቦትስዋና፤ ኬንያ፤ ናይጀሪያ ያሉ የአፍሪካ አገሮች የፕሬስ ነጻነትን ጥቅም አይተው ስራ ላይ አውለዋል። ህወሓት/ኢህአዴግ ጋዜጠኞችን ያስራል። ከአገር ያባርራል። የመናገር፤ የመጻፍ፤ የመሰብሰብ፤ የመደራጀት መብቶችን አግዷል። ይህ ለፍትህ፤ ለዲሞክራሲ ጸር ሆኗል። ህገመንግሥቱ በፈቀደው መሰረት የተደራጁ፤ በሰላም ብቻ የሚሰሩ፤ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ የፖለቲካና ማህበራዊ ድርጅቶች ሁሉ፤ በተከታታይ ህልውናቸው ጠፍቷል። መሪዎቻቸውና አባሎቻቸው በግልጽና ባልታወቀ ሁኔታ ተገድለዋል። ባልሰሩት ወንጀል ታስረዋል። ተሰደዋል። ህገመንግሥቱ የሚፈቅደው የመድብለ ፓርቲ ሚና ፍጹም በሆነ ደረጃ ጠፍቷል። የህወሓት/ኢህአዴግ የበላይ መሪዎች ለህገመንግስቱ፤ ለህግ የበላይነትና ለፍትህ እንዳያገለግል አድርጎታል። በምርጫ ዘጠና ሰባትና እአአ ፤ በ 2002 ህወሓት/ኢህአዴግ ፍጹማዊነቱን በማሳየት፤ አፍሪካ ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ ከሙቶ 99.6 ድምጽ አግኝቻለሁ ብሎ የዓለምን ሕዝብ አጭበርብሯል። የአምባገነኑ መንግሥት በምርጫ ዘጠና ሰባት ተሸንፎ አልተሸነፍኩም ብሏል። ሰላማዊ ወጣቶችን፤ አባቶችን፤ እናቶችን ገድሏል። ከአርባ ሽህ በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያንን አስሯል። መለስ ባስመረበት መስመር መሰረት፤ ህወሓት/ኢህአዴግ በተከታታይ ለማሸነፍ ወስኗል። ለዚህ ብቃት ለማግኘት ሲል፤ የመንግሥት ሰራተኞች፤ ተማሪዎች፤ ገበሬዎች፤ ሴቶች የፓርቲ አባል እንዲሆኑ፤ ከመንግሥት ባጀት እየመደበ አባላቱን ወደ ስድስት ሚሊዮን እንዲደርስ አድርጓል። በብዙ መቶ ሽህ የሚቆጠሩ ያለፈቃዳቸው አባል እንዲሆኑ አስገድዷል። ስርአቱ፤ የሶቪየትና የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ የቁጥጥር ቅጅ ነው። ከዲሞክራሳዊ አገዛዝ ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው አሳይቷል። በሌላ አነጋገር ምርጫን በአገሪቱ ባጀት ይሸምታል። ምርጫን አስቀድሞ በመንግስት ባጀት ተጠቅሞ አባላትን መግዛትና መጨመር የሙስና መስፈርት ነው። ይህ የፖለቲካ ሙስና ይባላል።

የቻይናን ኮሙኒስት ፓርቲ ቀድቶ ፍትሃዊ እድገት አይገኝም

ቻይና ያደረገችው የእድገት ፍጥነት የሚደነቅ ነው። ከሁሉም በላይ፤ የቻይና ሕዝብ አይራብም። በአብዛኛው፤ የምግብ ፍላጎቱን ያሟላው በሃገሩ ምርት ነው። ስለሆነም፤ በአገሩ አያፍርም። ራሱን ቀና አድርጎ ይኼዳል። ሆኖም፤ የቻይና እድገት እያደረ በውስጡ ያዘለውን የፖሊሲና መዋቅራዊ ችግር እያሳየ ነው። የውስጥ ውጥረቱ ኢትዮጵያን ይመስላል። ተራው ሕዝብ፤ በተለይ የመካከለኛ መደቡ፤ ወጣቱ ትውልድ “ለውጥ ያስፈልጋል። የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ አለቃዎች ሃላፊነት መውሰድ አለባቸው” እያለ ነው። ድምጹ በዓለም እየተሰማ ሄዷል። “If everthing in China is going well, why do so many of its citizens think about moving?” Washington Post, November 18, 2012, በሚል የቀረበ ዘገባ ችግሮቹን አውጥቷቸዋል። እነዚህ ጥልቀት ያላቸው ችግሮች ከኢትዮጵያ የህብረተሰብ አፈና ጋር ተመሳሳይነት አላቸው። መነሻቸው፤ የመንግሥቱ አያያዝ። የፓርቲው ፍጹም የበላይነት። የከፍተኛ ባለስልጣናት ቤተሰቦች በስልጣናቸው መባለግ። ስልጣናቸውን ተጠቅመው የራሳቸውንና የቤተሰቦቻቸውን ሃብት ማሳደግ። የአድልዎና ሙስና መስፋፋት። በጥቂት ሃብታሞችና በአብዛኛው የቻይና ሕዝብ መካከል ያለው የገቢ፤ የኑሮና የእድል ልዩነት እየባሰ መሄድ ይገኙበታል። የዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣ፤ ነዋሪዎችን ጠይቆ የተረዳቸው ኢትዮጵያውያን ከሚያሰሟቸው አይለዩም። “ኑሮን ከፍ ለማድረግ፤ ከመንግሥት ባለስልጣናት ጋር ግንኙነት ያስፈልጋል። ግንኙነት ያለው ያድጋል። የሌለው አያድግም” የሚሉ ከአብዮታዊ ዲሞክራሲ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ናቸው። መቀበል ያለብን፤ በአብዛኛው፤ደሃ በሆነች ኢትዮጵያ፤ አንድ ግለሰብ ሃብታም ሳይደክም፤ የራሱን ድርጅት በራሱ ካፒታል አቋቁሞ ሰርቶ ሃብት ካላገኘ፤ ከመንግሥት ጋር ግንኙነት አለው ማለት ነው። ሌላው በራሱ ጥረት የሚኖር ተራ ግለሰብ ቀን ከሌት ቢሰራ፤ ኑሮውን ለማሻሻል ተቸግሯል። በተመሳሳይ፤ በቻይና የሚታየው የፓርቲውና የመንግሥቱ የበላዮች ሙሰኛ መሆናቸው ነው። ስለሆነም፤ “ቻይና ትልቅ ለውጥ ያስፈልጋታል። ለውጥ ከሌለ ሕዝቡ መነሳቱ አይቀርም። እርጋታ አይኖርም። ለፓርቲው አደገኛ ነው” የሚሉ ይገኙበታል።

ሌላው ከኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር የሚመሳሰለው፤ የተማረው፤ መካከለኛ መደቡ፤ ብዙ ሃብታሞች ቻይናን ለቀው ለመሰደድ እነደሚፈልጉ የተገኘው ማስረጃ ነው። በኢትዮጵያ ከስድሳ እስከ ሰባ በሙቶ የሚገመተው፤ በተለይ፤ ወጣትና የተማረ መሰደድ ይመርጣል። በቻይና፤ “ስድሳ በሙቶ የሚሆኑት፤ በራሳቸው ጥረት ሃብታም የሆኑትን ጨምሮ፤ ወደ ምእራብ አገሮች፤ በተለይ ወደ አሜሪካ መሰደድ ይፈልጋሉ።” የሚሰጧቸው ምክንያቶች አሉ። የገቢና የኑሮ ልዩነት እየባሰ መሄዱ። ሙስና፤ የፓርቲው የበላዮችና ቤተሰቦች የተለየ ኑሮ መኖሩ። ለህብረተሰቡ ተጠያቂ አለመሆን ይገኙበታል። እነዚህ ከኢትዮጵያ አይለዩም። አባባሉ የሚያስታውሰን፤ ሳራህ ፈሪታስ፤ (Global Financial Integrity Report on Ethiopia)፤ በኢትዮጵያ፤ ሰለ ህገ-ወጥ የውጭ ምንዛሬ ሽሽት (Illicit outflow of funds) ያለችው ነው። “የኢትዮጵያ ድሃ ሕዝብ፤ ምንም በርትቶ ቀን ከሌት ቢሰራ፤ በሙስና፤ ከህግ ውጭ በሚሸሸ ምዝበራ፤ እየደማ ነው። የፈለገውን ያህል ቢሰራና ቢደክም ካለበት አሰቃቂ ኑሮ ለመላቀቅ ልክ ሃይለኛ በሆነ ወንዝ ወደላይ ለመዋኘት እንደመሞከር ሆኖበታል” ያለችው። የቻይናን ኮሙኒስት ፓርቲ አምላክ፤ አርአያ አድርጎ “እድገታዊ መንግሥት” ነኝ፤ የደሃውን ህይወት ለውጨዋለሁ ማለት ለቻይናም አላዋጣም። ሁኔታው በኢትዮጵያ የባሰ ነው። አንዱ ልዩነት፤ ማኦ

ባደረገው አብዮትና የእድገት መሰረት፤ የቻይና ህብረተሰብ አይራብም። ምግብ ከሊጋስ ሃገሮች አይለምንም። ሆኖም፤ የሁለቱም ህብረተሰቦች ሁኔታ የሚያመለክተው ችግር አለ። እድገት ስራን ካልፈጠረ፤ ለመካከለኛው መደብ አባላት የኑሮ መሻሻል ካላመጣ፤ በጥረታቸው ሃብታም ለሆኑ የመስፋፋት እድል ካልከፈተ፤ የሚያገለግለው ጥቂት የፖለቲካ ስልጣን ያላቸውንና ሰልጣን ካላቸው ጋር የጥቅም ትስስር የመሰረቱትን ብቻ ነው። እንደሚታወቀው፤ ቻይና የገንዘብ፤ የውጭ ምንዛሬ ችግር የለባትም። ለሌች አበዳሪ ናት። ሆኖም፤ የገንዘብ ክምር ብቻውን ህብረተሰብን አያሻሽልም። ሳውዲ አረቢያ የውጭ ምንዛሬ ክምር ያላት አገር ናት። አብዛኛው ወጣት ስራ የለውም። አብዛኛዎቹ ከፍተኛ ትምኅርት ያላቸው የሳውዲ ሴቶች ስራ የላቸውም። ተምረው በቤታቸው ቁጭ ብለዋል። አቤቱታ ለማቀረብ አይችሉም። ልክ እንደ ኢትዮጵያ፤ በቻይና፤ በጥቂት ሃብታሞችና በአብዛኛው የመካከለኛ መደብ፤ ደሃና ወጣት መካከል ያለው የኑሮ ልዩነት "ከአደገኛ ደረጃ ላይ ደርሷል" የምንለው ለዚህ ነው። የአብዛኛው ህብረተሰብ ክፍል ህይወት አልተሻሻለም። "ፍትህ፤ ፍትህ፤ ፍትህ" እያለ ነው።

ልክ እንደ ኢትዮጵያው ህወሓት/ኢህአዴግ፤ የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ ተቃዋሚዎችን ይከታተላል። ያስራል። ያሳድዳል። በኢትዮጵያ፤ ንጹህ ኢትዮጵያውያንን ለመወንጀል እንዲያመች "የጸረ ሽብርተኛ" ህግ ደንግጎ፤ አገሪቱን ወደ እስር ቤት ለውጦታል። የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚከራከርለት ነጻ የሆነ የማህበራዊ ድርጅት እንዳይኖር፤ የመንግስት ያልሆኑ ተቋሞችን የሚዳኝ፤ ገደብን የሚያጠናክር ህግ አውጥቶ ከስራ ላይ አውሏል። የነጻ ፕሬስ እንዳይኖር፤ ህገ መንግሥቱን በመጣስ፤ የፕሬስ ነጻነት ሙሉ በሙሉ እንዲታገብ ማድረጉ፤ በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞችን ኢ-ሰብአዊ በሆነ መንገድ እሥር ቤት ማጎሩ፤ አገዛዙ ለእርጋታና አብሮ ለመኖር እንቅፋት ሆኗል። በቻይና፤ ቀስ በቀስ፤ ህብረተሰቡ፤ ዘመናዊ መገናኛ እየተጠቀመ፤ ብሶቱን እርስ በእርሱ ይወያያል። በኢትዮጵያ ይህ እድል ተከልክሏል። የኢትዮጵያ መንግሥት የሚቆጣጠርበት የመገናኛ መሳሪያ ከቻይና አግኙቷል። ቴክንኖሎጂውን ተጠቅሞ በባሰ ሁኔታ ህብረተሰቡን መቆጣጠሩን አጠናክሯል።

ስለላና ቁጥጥር ለህወሓት የኢኮኖሚ የበላይነት ጥቅም አለው

በጋምቤላ፤ አኝዋኮችን በገፍ እየገደለ አልገደለኩም ብሏል። በኦጋዴን ሴቶች፤ ልጆች፤ እናቶች፤ አባቶች እያሳደደ፤ እየገደለ፤ ሴቶችን እያስደፈረ፤ ለዚህም ተጠያቂ አይደለሁም ብሏል። በአማራ ህብረተሰብ ላይ፤ በተደጋጋሚ፤ ከመኖሪያቸው እንዲሰደዱ፤ ከመሬታቸው እንዲወገዱ አድርጓል። አሁንም ያደርጋል። በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ፤ በተለያዩ ቦታዎችና ወቅቶች ባልታወቀና በታወቀ ሁኔታ ገድሏል። አሁንም እንዲገደሉ ያደርጋል። በገደል እንዲወረወሩ አድርጓል። የዘረኛ ቂም በቀል በንጹህ ኢትዮጵያውያን ላይ እንዲካሄድ በተከታታይ እያወቀ እንዳላወቀ አልፎታል። ለዚህ ሃላፊ የሆኑትን በህጉ መሰረት ለፍርድ ለማቅረብ አምቢ ብሏል። ሰለሆነም የሕዝብ እምነትን አጥቷል። ለስደት ምክንያት ሆኗል። በኦሞ ሸለቆ፤ በልማት ስም፤ የመሬት ነጠቃና የኦሞ ሸለቆ ሕዝብ እንዲሰደድ ማድረጉን፤ Survival International፤ ልብን በሚቀስቅስ፤ እንቅልፍን በሚነሳ ሁኔታ ለዓለም ህብረተሰብ አቅርቦታል።

"የመለስ አምልኮ" ተከታዮች እንደሚሉት ሳይሆን፤ ህወሓት አድሏዊ ነው። ለምሳሌ፤ ምርጥ የትግራይ ተወላጆች፤ የህወሓት የበላይ ቤተሰቦች፤ ታማኝ የኢህአዴግ መሪዎች፤ ከውጭ አገር የመጡ ኢጋሮች ጋር ሆነው የአገሪቱን ቁልፍ የኢኮኖሚና የተፈጥሮ ሃብቶች (Pillars of the National Economy) እንዲቆጣጠሩ አድርጓል። ከአራት ሚሊዮን ሄክታር በላይ የሚሆን ለም መሬትና ወንዝ ለውጭ አገር መንግስታት፤ ለግለሰብ ኢንቤስተሮች፤ ለምርጥ የትግራይ ተወላጆች አስተላልፏል። ነዋሪዎችን ከመሬታቸው ማስወጣቱ፤ በብዙ ሽህ የሚቆጠሩትን ለስደት መዳረጉ፤ ተከታታይ ትውልድ የሚጠይቀው ብቻ ሳይሆን፤ በአፍሪካ፤ አሩሻ በሚገኘው የሰብአዊና የኢኮኖሚ መብቶች ፍርድ ቤትና በሌሎችም የዓለም ተመሳሳይ ፍርድ ቤቶች እንዲከሰሱ የሚያደርጉ ወንጀሎችን ፈጽመዋል።

የመለስ መንግሥት፤ ከሰሜን ሱዳን መንግስት ጋር በመመሳጠር፤ ከአንድ ሽህ ስድስት መቶ ኪሎሜትር በላይ የሚገመት የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን መንግስት በድብቅ ሰጥቷል። የኢትዮጵያን ግዛታዊ አንድነት አስደፍሯል። እንደሚታወሰው፤ ስልጣን እንደያዘ፤ ህወሓት ኤርትራን ከእናት አገሯ ለይቶ ያለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ድምጽና ፍላጎት እንድትገነጠል አድርጓል። የኢትዮጵያ አንጡራ ወደብ የሆነችውን አሰብን ሆነ ብሎ ማስረከቡ፤ ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደብ አልባ መሆኗ፤ መለስ ዜናዊ ጥፏቸው ከሄደው በደሎች መካከል አንኳር ሆነው ይታያሉ። ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ሆና በፍጥነት ለማደግ አትችልም። የሃገሪቱ ደህንነት ሊጠበቅ አይችልም። የኢትዮጵያ የወደብ መብት የህልውና ጥያቄ ነው። የማደግ ያለማደግ ጥያቄ ነው። ጥገኛ የመሆን ያለመሆን ጥያቄ ነው። መለስ ካለፈ በኋላ፤ ስብሃት ነጋና ሌሎች፤ "አሰብ የኢትዮጵያ አይደለችም። ኤርትርያ የኢትዮጵያ አካል ሆና አታውቅም" ብለው ሲናገሩ፤ ለኢትዮጵያና ለመላው ሕዝቧ፤ትግሬዎችን ጨምሮ፤ አክብሮትና ሃላፊነትና ለወደፊቱ ትውልድ ፍትሃዊ እድገት ደንታ እንደሌላቸው አሳይተዋል። ደንታ ያላቸው ለስልጣን፤ ለግል ጥቅም መሆኑን እንደገና እያስመሩበት ነው። የትግራይ

ሕዝብ፤ ይህን አደገኛ አነጋገር መኮነን አለበት። ወደፊት፤ ከሁሉ በላይ በኢኮኖሚው በኩል፤ ከፍተኛ ዋጋ የሚከፍለው የትግራይ ክልል ጭምር ነው።

ከብድር የሚመጣው እዳ ለምን አላማ ይውላል?

የድሃ ሃገር መበደር አያከራክርም። አከራካሪው ህወሓት/ኢህአዴግ የኢኮኖሚውን ፖሊሲና መዋቅር ለመለወጥ ባለመቻሉ ኢትዮጵያ ከመቸውም የበለጠ የሊጋስ አገሮች ጥገኛ እንድትሆን ማድረጉ፤ ከአደጋዎቹ አንዱ እየሆነ ሄዷል። በቅርቡ የገንዘብ ሚንስቴር ባወጣው ዘገባ መሰረት፤ የኢትዮጵያ የውጭ እዳ አስራ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ደርሷል። የውስጡ ከባንኮች የተገኘ የመንግስት ብድር እዳ ከስድሳ ቢሊዮን ብር በላይ ነው። ለተሃድሶ ግድብ ተብሎ ከሕዝብ የተሰበሰበው ገንዘብ ብዙ ቢሊዮን ብር ደርሷል። መከፈል አለበት። መንግሥት በታክስና በቁጠባ የሚሰበስበው ከእዳው ጋር ተመጣጣኝ አይደለም። አንዳንድ አገሮች እንደሚያደርጉት፤ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት እዳን ለመክፈል፤ ከውጭ አበዳሪዎች ብድር መፈለጉ የማይቀር ይመስላል። እዳን ለመክፈል እዳ ውስጥ መግባት ጥገኛነትን ያጠናክራል። ዋናው ነገር፤ ብድሩን የሚከፍለው፤ የአሁኑና ተከታታይ ትውልድ ነው። እዳው ብቻ አይደለም፤ ህወሓት/ኢህአዴግ እነዚህን ሁሉ ፖሊሲ ነክ፤ መዋቅራዊና ስርአታዊ ችግሮች (Structual and Systemic Hurdles) ብቻውን ለመፍታት አይችልም። ሰው መደነቅ ያለበት፤ ብቻውን ለመፍታት የማይችልበት ደረጃ ላይ ከደረሰ፤ ለምን ከተቃዋሚ ሃይሎች ጋር አይደራደርም የሚለውን ነው። ኢትዮጵያ የጋራ አገር ነች። ችግሮችን በጋራ ለመፍታት ይቻላል። ከተቻለ፤ ለለውጥ ፈቃደኝነት ማሳየት ጥበብ ነው። ሌሎች፤ በፖለቲካው ሂደት የማይሳተፉ ተቃዋሚዎች ሁሉ ያገባቸዋል ብሎ ወደ መቻቻል መሸጋገር ይጠቅማል እንላለን ።

መፍትሄው በፊታችን ይታያል

ለመለስ ዜናዊ አገራዊ እውቅናና "አምልኮ" የሚመስል ታሪካዊ ቦታ የመስጠት ጥያቄ ወሳኝ መሆን ያለበት የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ውሳኔው ለተራው ሕዝብ ጥቅም፤ ለኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነት፤ ለህብረተሰቡ ሰላምና እርቅ፤ ለተከታታይ ትውልድ የኑሮ መሻሻል ባደረገው አስተዋጽኦ እንደሚሆን መገመት ይቻላል። መለስን የሚወዱ፤ የሚያከብሩ፤ ለዲሞክራሳዊ ለውጥ አሜን ማለት አለባቸው። ብሄራዊ ችግሮች ሳይፈቱና ሕዝብ ሳይወያይበት--በአንድ ፓርቲ አዛዥነት-- እንደነ ማኦ ሲቱንግ፤ እንደነ ሌኒን፤ እንደነ ሆቺሚን፤ እንደነ ኪም ኢል ሱንግ፤ እንደነ ሊንከን/ዋሽንግቶን/ጀፈርሰን፤ ኔልሰን ማንዴላ እንዲታወስ ሃውልት (Mausoleum) መስራት አምባገነናዊነት ያሳያል። ኢትዮጵያውያን በሙሉ፤ ከትውልድ ወደ ትውልድ፤ ኮርተው፤ ተከብረው፤ ከድህነት ነጻ ሆነው፤ በነጻነት ተነጋግረው፤ መሪዎቻቸውን መርጠው፤ አገራቸውን ከአደጋ ጠብቀው፤ የሚኖሩባትን ሁሉን የምታሳትፍ ዲሞክራሳዊ ኢትዮጵያን መመስረት የጊዜው ጥያቄ ነው።

የህወሓት የበላዮች፤ የኢትዮጵያን የመንግሥታትና የመንፈሳዊ መሪዎች አስተዋጽኦና እውቅና በመፈታተን ላይ ይገኛሉ። ማንም ሃገር በአንድ የመንግሥት አመራር ዘመናዊ አይሆንም፤ ዘመናዊነት ተከታታይነት፤ ታሪክ፤ ባህልና ልምድ አለው። የሰማዕቱ የብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ታሪክ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ ነው። የክርስትና ኃይማኖት ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባና እንዲስፋፋ ያደረጉት የአክሱሙ፤ ንጉሥ እዛና ታሪክና አስተዋጽኦ የመላው ኢትዮጵያ ታሪክ ነው። የአገር ወዳዱ ጀግና የአጼ ምኒልክ ታሪካዊ ድል--የአድዋ ጦርነት-- የዘመናዊነት መሰረትና የሁሉም ኢትዮጵያውያን ድል ነው። የአጼ ኃይለ ሥላሴ አመራር የመጀመሪያው እውነተኛ የኢትዮጵያ ዘመናዊነት ታሪክ ነው። የእነዚህና የሌሎች የኢትዮጵያዊነት መታወቂያዎች ለፖለቲካ ጥቅም መለዋወጥ የለባቸውም። ታሪኩን ለመቀበል የማይፈልግ አመራር ታሪክ ሰሪ ሊሆን አይችልም።

የቻይና ሕዝብ ማኦን የሚያከብርበት ማርክሲስት ሌኒኒስት በመሆኑ ብቻ አይደለም። ቻይናዊና አገር ወዳድ ስለነበረ። ታሪኩን ሳይክድ፤ ቻይና እንደገና ታላቅ አገር እንድትሆን ስለጣረ። ደሃው በልቶና በሃገሩ ኮርቶ እንዲኖር ስላደረገ። በግለሰብ ደረጃ፤ ሙሰኛና በጎሳው አድሏዊ ስላልነበረ ነው። መለስ "በግል ደረጃ ሙሰኛ አልነበረም" የሚሉ እንዳሉ እናውቃለን። ይህን በቅርብ የወጡ ማስረጃዎች አይደግፉትም። "የገንዘብ ሙሰኛ "አልነበረም ብለን እንቀበል። ሆኖም የፈጠረው ፖሊሲው ምን ይመስል ነበር? ለማን ጠቀመ? ማንን ጎዳ? ምን አይነት ተቋሞችን ፈጥሮ ሄደ የሚሉት የፖሊሲ ጥያቄዎች ናቸው። ግለሰቡን፤ ከፖሊሲውና ከስርአቱ መለየት አስፈላጊ ነው። ከትችቱ ባሻገር ለማለት የምንገደደው፤ ላወቀበት፤ አምባ ገነን መሪ ከዚህ ዓለም ሲያልፍ ተተኪው፤ የሚገኘውን እድል ለሁሉም በሚበጅ መልክ ለመጠቀም የማካተት በሩን ይከፍታል። የአመራር ጥበብ የሚለይበት በዚህ መለኪያ ነው። የፈለገው የምስጋና ጎርፍ ከየአቅጣጫው ቢታይ--የአፍሪካ መሪዎች፤ ዴቪድ ካሜሮን፤ የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚንስትር፤ ጎርደን ብራውን፤ የታወቀው እንግሊዛዊ የመለስ ወዳጅ፤ ሱዛን ራይስ፤ በተባበሩት መንግስታት የአሜሪካ አምባሳዶር፤ ቢል ጌትስ፣ ሊጋሽ

ቢሊየኔር፤ ፕሬዘዳንት ኦባማ፤ ወዘተ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የኖረበትን ስቃይ፤ የደረሰበትን ችግር በቀጥታ ሊያውቁት አይችሉም። አገሮቻቸው እንዴት በፈተና እንዳለፉ ረስተውታል። የሚያዩበት መነጽር ከራሳቸው ጥቅም አንጻር ነው። በኢትዮጵያ ሕዝብ ሰቆቃ አይደለም። የሟቹን ታሪክ በተዛባ መልክ አሞግሰው ቢናገሩም ባይናገሩም፤ ከፊታችን ላይ ተደቅነው የሚገኙት ስርዓታዊ አደጋዎች አይለወጡም። እነዚህ አድናቂዎች--የአፍሪካ መንግስታት ያዋጣናል ብለው እአአ በ 1967 አሩሻ፤ ታንዛኒያ ያወጁትን-- ማህበረሰብ ነክ የልማት መመሪያ (The Arusha Declration) ረስተውታል። ይህ አዋጅ የሚለው፤ “የአንድ ሃገርን ልማት የሚወስነው ሕዝቡ ነው። የሕዝብ ኑሮ መሻሻል መለኪያና ውጤት ነው። የፖለቲካ ስልጣን ይዞ በኪራይ ትርፍ አግኝቶ ለግል ጥቅም ገንዘብ፤ ሃብትና ኑሮ መሻሻያ ማድረግ እድገት አያሳይም” የሚል ነበር። ግንዛቤ ማድረግ ያለብን፤ የህወሓት/ኢህአዴግ የበላዮች፤ ገንዘብ ከየትም፤ አስገድደውም ቢሆን ለምነው፤ የመሰብሰብ ችሎታቸው አስደናቂ ደረጃ ላይ የደረሰ ነው። ይህ አያከራክርም። ጥቅም ለመስጠት ካልቻሉ ይህን ከፍተኛነት አያገኙም ነበር። ኢትዮጵያ በእርዳታ በአፍሪካ ከፍተኛ ደረጃ የያዘችው ጠበቃ ስለነበራት ነው። ኃይለማሪያም ደሳለኝ የመለስን ፈለግ ተከትሎ ሰፊ እርዳታ ያግኝ አያግኝ ወደፊት ይታያል። ቁም ነገሩ ግን ገንዘብ ማግኘቱ አይደለም። አስተዳደሩ፤ አመራሩና አጠቃቀሙ ነው። ኮሪያም እርዳታ ታገኝ ነበር። ኮሪያ ዛሬ አበዳሪና ለጋስ ናት። ላወቀበት፤ እርዳታ፤ አገር ወለድ ኢኮኖሚ በፍጥነት ለመፍጠር ይረዳል። ኮሪያ እንዳደረገችው። የመንግሥት አመራር አገራዊነት የሚረዳው ለዚህ ነው።

ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎች የህወሓት/ኢህአዴግ ደጋፊ የሆኑ መንግሥታት፤ ኢንቬስተሮችና ሃብታም ግለሰቦች ሚዛናዊ አቀራረብ አላደረጉም። “የመለስ  መንፈስ፤ ርእዮት፤ አመራር፤ “እድገታዊ መንግስት አስደናቂ፤ መተኪያ የሌለው፤ ብርሃን” ነበር የሚሉትን የህወሓት የበላዮችና ደጋፊዎች የድፍረት መሳሪያ ሰጥተዋቸዋል። በዚህ ምእራፍ ለመመለስ የምንፈልገው የተቆላለፈ አንኳር ጥያቄ ኢትዮጵያ “ከመለስ እልፈት በኋላ ምን አይነት የፖለቲካና የኢኮኖሚ ስርአት ትጠብቃለች? ኢትይጵያውያንስ ምን ማድረግ ይኖርባቸዋል?” የሚለውን ነው። ወደ ዝርዝሩ ከመግባታችን በፊት፤ ጠቅላይ ሚንስትር መለስ ለሃያ አንድ አመታት ከስር ገንብቶ የመራው መንግሥት ምን እድሎችን፤ ምን ችግሮችን ተክሎ ሄደ፤ (Legacy) ብለን መጠየቅ ይኖርብናል። ችግሩን በጥልቀት ካላወቅን መፍትሄ ለማግኘት አንችልም። ትንተናው የሚያተኩረው በመለስ ህይወት፤ ማንነት ላይ አይደለም። ይህን፤ ከእኛ የበለጠ ሌሎች ይነጋገሩበታል። የመለስ “አምልኮ” ደጋፊ ምሁራን ይተቹበታል። እውነቱ በማሞግስና በነቀፋ መካከል ይገኛል። ማሰብ ያለብን ግን ላለፈው ችግር መለስ ብቻ ከገነባው ስርአት ለይተን  መውቀስ አያዋጣነም። መለስ አልፎ ስርአቱ ቀጥሏል። ለመለስ ደጋፊዎችና እንደመላክ “መለስ የእድገት ጀግና” ባዮችም ጠባብ፤ ከእውነቱ የራቀና ወገናዊ የሆነ አቅርቦት በምንም አያዋጣቸውም። ዓለም እየተለወጠ እንደሚሄድ መጠን፤ ኢትዮጵያም ትለወጣለች። ስትለወጥ የታሪክ ቀፎ ሆኖ መገኘት አለ። መዳሰስ የምንፈልገው ስርአት ወለድ የሆኑ አንኳር የፖሊሲ ማነቆዎችን ነው።

ዋናው የአገዛዝ መሰረት፤ ማለትም፤ የህወሓት መንግሥት፤ የጠባብ ጎሳ ድርጅት ስለሆነ ነው። መለስ የመራው መንግሥት፤ የትግራይ ጠባብ ብሄርተኛነት ቡድንን ማእከል ያደረገ። የማይበገር። ለሕዝብ ግልጽ ያልሆነ። በምስጢር የሚሰራ። በትግራይነቱ የሚታወቅ የፖለቲካ ፓርቲ የበላይ አዛዥ እንዲሆን ተደረጓል። ይህን ጥቅም ያስገኘ ስልጣን ለመልቀቅ በጣም አስቸጋሪ ሆኗል። ቁልፍ የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚ፤ የማህበራዊ ኑሮ፤ የሃይማኖት፤ የውጭ ጉዳይ፤ የፖሊስ፤ የህግ፤ የምርጫ፤ የመገናኛ፤ የባንክ ወዘተ ተቋሞችን በሙሉ የራሱ አድርጓል። እነዚህን የኪራይ መሰብሰቢያ (ለግል ጥቅም)፤ የግለሰብና የህብረተሰብ መቆጣጠሪያ ተቋሞች ባጭሩ ለመልቀቅ አይቻልም። ሌሎች አግባብ የላቸውም የሚለው አስተሳሰብ መሰረት የያዘበትን የአገዛዝ አቀራረጽ፤ ሶሻል ሳይንቲስቱ ደሳለኝ ራሃማቶ በግልጽ አስቀምጦታል። “እድገታዊ አመራርን የሚያውቅ ገዢው ፓርቲ፤ ህወሓት/ኢህአዴግ ብቻ ነው። ሌሎቹ--የግል ክፍሉ፤ ልዩ ልዩ ማህበራት፤ ምሁራን በሙሉ--ኪራይ ፈላጊዎችና ኪራይ ሰብሳቢዎች ናቸው” ብሎ የህወሓት አመራር ደንግጓል። ይህን በማድረጉ፤ ማን የመበደር፤ መሬት የማግኘት፤ ከውጭ እቃ የማስመጣት፤ ከመንግስት ኮንትራት የማግኘት፤ እድል ይወስናል። ባጭሩ፤ የመንግሥት ስልጣን ተጠቅሞ ወይንም ከበላዮች ጋር ተጋርቶ የማይሰራ ሊከብር አይችልም የሚል አመራር ነው።  ይህ ከፓርቲውና ከወዳጆቹ ውጭ ሕብረተሰቡን ለማገልገል የማይችልና የማይፈቅድ ጠባብ ጎሰኛ አመራር እድገትን በፖለቲካ ይወስናል። ጉዳቱን ለማየት (Marginalization) ማን በግንባታ ስራ (Government funded construction) ይሰማራል። ማን ከጉምሩክ ድጋፍ ያገኛልና ለአቅርቦት (Procurement of goods and services) እድል ይወዳደራል ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው። እንደ ኢትዮጵያ ባለ መንግሥት ወሳኝ ሚና በሚጫወትበት አገር፤ የመንግሥት ድጋፍ ለህይወት ወሳኝ ነው። የመንግሥት አድልዎ ከፍተኛ ከሆነ፤ እውነተኛ የገበያ ውድድርና ሚዛናዊ ልማት ሊኖር አይችልም። መሬት፤ የስራ ፈቃድ፤ ብድር ለማግኘት አስቸጋሪ ነው። ዓለም ባንክ ስለ ግል ክፍሉ “ጫጩትነት” ያደረገው ጥናት “የፓርቲውና ፓርቲው የፈጠራቸው ድርጅቶች-- እንደ ኤፈርት ያሉ-- የግል ክፍሉ እንዳያድግ አፍነውታል” ብሏል። በዓለም የመወዳደር መለኪያዎች ኢትዮጵያ፤ በ 2010 Global Competitiveness Index ከ 133 አገሮች 118 ኛ ናት። ውድድር አለመኖሩ ለዘላቂና ለፍትሃዊ እድገት መሰናክል ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ

"እንባ ጠባቂ" ወይንም ተቆርቋሪ የለውም። ተቀናቃኝ ሃይል የለም። ፓርቲው ራሱን በራሱ ይዳኛል። አገዛዙ በመጀመሪያ ላቀረብነው የሕዝብ የበላይነትና እኩልነት ፍላጎት ዋና ማነቆ ሆኗል። ሰፊው የክልሎች ልማት ልዩነት የተፈጠረው በህወሓት ነው።

የጎሳ ፓርቲዎችን በውስጡ ያቀፈ የጠባብ ጎሰኛ ፓርቲ

የህወሓት ጎሳዊ የሆነ የፖለቲካ አደረጃጀትና አመራር ሆነ ብሎ ያጠፋው የኢትዮጵያን መአከላዊነት የፖለቲካ አመራር ነው። ሑሉም በጎሳና ለጎሳ ጥቅም ስለሚታገል፤ የፖለቲካ መዓከል የሚባል ስብስብ የለም። የህወሓት መሪዎችና አባቶች ኢትዮጵያውያን ከየብሄር/ብሄረሰቡ ተሰባስበው በአንድ ላይ፤ ለአንድ ብሄራዊ ዓላማ፤ ለሚጋሩት የፍትህና የዲሞክራሲ ስርዓት ምስረታ እንዳይቆሙ ሲከፋፍላቸው ቆይቷል። ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ከቡድን ባሻገር ለሃግርና ለሰብሳቢ ዓላማ በአንድ ላይ ለመስራት አልቻሉም። ይህ የፖለቲካ ማእከል ለመፍጠር አለመቻል ለገዢው ፓርቲ በገንዘብ የማይገዛው አቅም ለግሶታል ለማለት እንችላለን። ህወሓት በበከሉሉ ለይስሙላ--አገር አቀፍና ዲሞክራሳዊ ለማስመሰል፤ ኢህአዴግ--የኦሮሞ ሕዝብ ዲሞክራሳዊ ንቅናቄ፤ የአማራ ብሄራዊ ዲሞክራሳዊ ንቅናቄ፤ የደቡብ ሕዝቦች ዲሞክራሳዊ ግንባርና ህወሓት--ያሉበትን የአራት የብሄር ፖለቲካ ድርጅቶች ሰበሰበ። የብሄር ልዩነቶችን፤ ጥላቻን፤ ለማስታረቅ አለመቻልን ከጅምሩ የመንግሥት አወቃቀር መሰረት ያደረገው ህወሓት የፈለገው የበላይነቱን ለማረጋገጥ ነበር። መንግሥቱ በዚህ በብሄር ስብስብ እንዲመራ ተደረገ። ኃይለማሪያም ደሳለኝ (Wolayta) ተተኪ ሆኖ የተሾመበት መሰረትም የዚህ ዘዴ ውጤት ነው። ዛሬ በኢትዮጵያ አንድ ወጥ መንግሥት አለ ለማለት አይቻልም። ሁለት መንግሥታት ያሉ ይመስላል፤ አንዱ ለሕዝብ የሚታይ፤ ሌላው በጀርባ ሆኖ የሚወስን። በጀርባው ሆኖ የሚወስነው፤ የህወሓት የስለላ፤ የፖለቲካ አመራር ሃይል ነው። ዋናአ ፈላጭ ቆራጭ ማለት ነው። ዘዴው፤ ትግራዩ መለስ በሌላ የትግራይ ተወላጅ ቢተካ የሚያመጣው ችግር ከፍ ያለ ይሆናል የሚል ነው። የመተካካት መለኪያው ለሕዝብ ግልጽ አለመሆኑ ብቻ አይደለም። የኦሮሞ፤ የአማራ፤ የደቡብ፤ የሶማሌ፤ የአፋር፤ ወዘተ ብሄረሰብ አባላት በአገራቸው ወሳኝ የሆነ ሚና ለመጫወት አልቻሉም። ብሄራዊና በአንድ ላይ ከጎሳ በላይ አስበው ካልሰሩ እውነተኛ የስልጣን ተካፋይ ለመሆን አይችሉም። ስለዚህ፤ አገዛዙ ቀስ በቀስ፤ ወደ ችግር የሚያመራ መሆኑን መተንበይ አያስቸግርም። ባለፈው አመት የአሜሪካ ነጮች ራምኒ ይመረጣል ብለው የተዘጋጁት፤ አብዛኛው የአሜሪካ ሕዝብ ለመሰብሰብ የሚፈልገው፤ አባማ ጥቁር በመሆኑ ነው። አባማን የሚጠላውም የነጩ ክፍል ነው በሚል አስተሳሰብ ነበር። አስተሳሰቡ፤ የአሜሪካን ህብረተሰብ ቅይጥነት ዋጋ አልሰጠውም። አብዛኛው ደንቆሮ ነው ብሎ ከማሰብ ነበር። የተሳሳተ አስተሳሰብ ውጤቱ ያልተጠበቀ የሚሆነው ለዚህ ነው። አባማ የድምጽ ብልጫ አግኝቶ ተመረጠ። የራምኒ ዘገባ ወደቀ። የጎሳ ስብስቦች አመለካከት ተመሳሳይነት አለው። የኢትዮጵያን ሕዝብ ቅይጥነትና አንድነት ዋጋ አልሰጠውም። የሚያቻችልና ሁሉን የሚያስተናግድ ብሄራዊ ማእከል ከሌለ መፈራረስ አይቀርም፤ልክ እንደ መሳፍንት ዘመን።

የመለስ ህወሓት አቀራረጽና አመራርም በፍቅር፤ የኢትዮጵያን ህብረተሰብ በየረድፉ መያያዝ መሰረት በማድረግ፤ በአገር ዘላቂነትና ጥቅም ሳይሆን፤ በተጻራሪው፤ በቂም በቀልነት፤ (Vendata)ና በብሄር ጥላቻ የተመሰረተ ነው። አማራውን በመጥላት። በማዋረድ። በማሳደድ። በማግለልና መግቢያ በማሳጣት። ጥናቶች የሚያሳዩት፤ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ቂም በቀል፤ የዘርና የኃይማኖት ጥላቻ አይቀበልም። በኢትዮጵያ ነጻ ምርጫ ቢካሄድ፤ አሜሪካ እንደሆነው--ከአምሳ በመቶ በላይ የሆነው አባማን መርጧል--ህወሓት/ኢህአዴግ በነጻ ምርጫ፤ ኪሳራ እንድሚገባ አንጠራጠርም። ምርጫ 97 ይደገማል። አብዛኛው የኢህአዴግ አባል ነኝ የሚለው እንደ ቅንጅትና እንደ ሕብረት ያለ አማራጭ ቢደራጅ ተቃዋሚውን እንደሚደግፍ ይገመታል። ከማንኛውም አቅጣጫ ይምጣ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቂም በቀል፤ ጥላቻ፤ የስልጣንና የሃብት ስግብግብነት አይፈልግም። በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት "ታላቅ ረሃብ"፤ ዓለም ያደነቀው፤ የምግብ እርዳታ ሲመጣ፤ "ለሌላው አስበው፤ እኔ እቆያለሁ" ያሉትን ማስታወስ ለህሊና ጥሩ ነው። የህወሓት ባለስልጣናት ይህን ለጋስነት አያስታውሱም። የኢትዮጵያ ሕዝብ በውይይት ችግሮችን የመፍታት፤ ድህነትን ባጋራ የማጥፋት፤ ወዘተ ፍላጎት እንዳለው ይታመናል። ስልጣን ተጠቅመው የከበሩትን፤ "ሃብታቸውን እንደያዙ ይቆዩ። በቃን ይበሉ" ብሎ የሚናገር ህብረተሰብ ያለባት አገር ናት።"ችግሩ በቃን" የሚል አገዛዝ አለመኖሩ ነው።

በአሁኑ ወቅት፤ የሚደረግ አገራዊ ድርድር፤ እርቅ፤ ውይይትና ሽግግር ያለ ህወሓት ፈቃድ ስራ ላይ ሊውል አይችልም። አሁን ያለው ሹኩቻ የቀጠለው ይህን የጠባብ ቡድን የበላይነት ለመጠበቅ ነው። "የመለስ አምልኮት" የበከላቸው ግለሰቦች የሚከዱት፤ መለስ አስተማማኝ፤ ለዲሞክራሲ በር ከፋች አልነበረም። ሁሉን የሚያሳትፍ አመራርና ተቋም አልፈጠረም። ቁልፉ መልእክት፤ ለስሙ መንግሥቱን የሚመራው ኢህአዴግ ይባላል። ፖሊሲ አውጭው፤ ውሳኔ ሰጭው የህወሓት የአመራር ኮሚቴ (The TPLF Executive Committee) ነው። ስብሃት ነጋ፤ በረከት ሰምኦን የፈለጉትን "የኢትዮጵያን ጥላቻ" የሚያሳይ ፖለቲካ የሚያስተጋቡት አገራዊ ተቋም ስለሌለ ነው። የሚጠይቃቸው

ድርጅት ወይንም ግለሰቦች የሉም። በወሳኙ ኮሚቴ ጀርባ ከእነዚህ ገለሰቦች ሌላ፤ የስለላ፤ የፌደራል ፖሊስ፤ የመከላከያ መሪዎች አሉ። ሲያስፈልግ፤ በምርጫ ዘጠና ሰባት እንደሆነው፤ ትግሪያዊ የሆነ "እጋዚ" የተባለ መአት እንደሚወርድ ይጠበቃል። መለስ ጠባብነትን አጥፍቶ አላለፈም። በጥበብ የፈጠረው፤ ከማርክሲስት ሌኒኒስት ርእዮት የተቀዳ፤ አብዮታዊ ዲሞክራሲ የተባለ አገዛዝ አሁንም ህያው ነው። አገልግሎቱ፤ ለምርጥ የህወሓት ባለስልጣናትና ቤተሰቦቻቸው፤ ለጎሳ የበላዮች መሆኑ አይካድም። አንዳንድ ተመልካቾች ህወሓት የቻይናን ኮሚኒስት ፓርቲ አሰርራ ይመስላል የሚሉት ለዚህ ነው። በእኛ ምርምርና አመለካከት፤ ሁለቱ በአንድ ፓርቲ የበላይነት፤ በሙስና፤ በኑሮ ልዩነት ተመሳሳይነት አላቸው። የሚለያዩበት መሰረታዊ ምክንያት አለ። ህወሓት የኢትዮጵያ ሕዝብ ፓርቲ አይደለም። የጠባብ ብሄርተኛ ቡድን ስብስብ ነው። ስሙ ትግራይ ነው። የሚያዳላው ለትግራይ ነው። የቻይና ኮምኒስት ፓርቲ ከሁሉ በላይ አገራዊ ወይንም ቻይናዊ ነው። የሃን ፓርቲ አይባልም። የህወሓት ጠባብ ብሄርተኛ መዋቅር ካልፈረሰ ወይንም ኢህአዴግ ራሱን ከውስጡ ካልለወጠ ወይንም ካልተከፋፈለና ከተቃዋሚው ሃይል ጋር አብሮ ካልቆመ፤ ህወሓት የበላይነትን እንደ ያዘ ይቆያል። በቀጥታም ባይሆን በምስጢር፤ ከጀርባ ሆኖ ይገዛል። እንዴት ቢባል፤ ቁልፍ ተቋሞችን የሚቆጣጠር፤ የጦርና የገንዘብ የበላይነት ያለው፤ አዛዥ ህወሓት ነው። ጠቅላይ ሚንስትር ኃይለማሪያም ያለበት የፖለቲካ ችግር ይህ ነው። ታዛዥ ሆኖ መስራት አለበት። ወሳኞች ከጀርባ ሆነው "ይህን አድርግ፤ ያን አድርግ" ይሉታል። ታዲያ፤ የውጭ አገር መንግሥታትና ደጋፊዎች፤ በተለይ፤ የአሜሪካ መንግሥት፤ የመለስን ዘመን ያዩት ከዚህ ችግር ጎሳዊነት አንጻር አይደለም። ከሁለት ሁኔታዎች አንጻር ነው።

አንደኛ፤ በአፍሪካ ቀንድ ያለውን የሽብርተኛነት አደጋ በመለስ ይመራ የነበረው መንግሥት ተወካይ ሆኖ ስለተዋጋ። በሶማልያ ጦር ስለላከ። ለአሜሪካኖች የሙብረሪያ መሬትና ፈቃድ ስለሰጠ። በአፍሪካ ግጭቶችን ለማብረድ ሚና ስለተጫወተ (ደቡብና ሰሜን ሱዳን) አመኔታን አግኝቷል። ለዚህ አመኔታ ቁልፍ ሚና የተጫወተው የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አይደለም። የመከላከያና የስለላ ክፍል ባለስልጣናት ናቸው የሚል ዘገባ አለ። አሁንም፤ ይህ የጠነከረ፤ ከአሜሪካ ጥቅም ጋር የተያያዘ ግንኙነት ቀጥሏል። ህወሓት፤ በያመቱ፤ ብዙ መቶ ሚሊዮን ዶላር እርዳታ ለመከላከያና ለስለላ ድርጅቶች ያገኛል። ታማኝ ጀኒራሎችን ይንከባከባል። የገዢው ፓርቲ ከፍተኛ የጦር ተቋም ለማደራጀት አስችሎታል።

ሁለተኛ፤ ወደኋላ የቀረችውን ኢትዮጵያን በፍጥነት አሳድጋለሁ በማለት ነው። በተለይ፤ ከምርጫ ዘጠና ሰባት በኋላ፤ በአመት አሁን አራት ቢሊዮን ዶላር የደረሰ እርዳታ አግኝቷል። ይህን ለማስመስከር፤ መሰረተ ልማት፤ መንገድ፤ የውሃ ግድብ፤ የትምህርትና የጤና አገልግሎት አስፋፍቷል ፤ህንጻዎች በብዛት ተሰርተዋል። የሚታይ ለውጥ አለ የሚል ግምት ስለሰጡት አመኔታን አጠናክሯል። ሆኖም፤ ከብዙ ቢሊየን ዶላር እርዳታ በኋላ፤ አብዝኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ደሃ ወይንም ፈረንጆች እንደሚሉት "ምስኪን" (Destiute) ነው። ሶስት ምግብ በልቶ መዋል ህልም ሆኗል። ከእድገቱ ጥቅም ያገኘው ክፍል የተወሰነ ነው። በግልጽ የሚታየው ተጠቃሚ የፖለቲካ ስልጣን ያለው፤ ከመንግሥት ኮንትራት፤ ከባንኮች ያለ መያዣ ብድር፤ ከጉቦና ሙስና ብዙ ቢሊዮን ብር እያገኘ አዲስ ከበርቴ የሆነው ክፍል ነው። የመንግሥት ኩንትራት ማግኘት ለመክበር ወሳኝ ነው። በመንገድ፤ በትምኅርት ቤት ስራ፤ በጤና ጣቢያ ስራ ወዘተ የከበረው የህወሓት አጋር፤ ታማኝ፤ ከፍተኛ አባል የሆነው ነው። የነስፍ ወከፍ ገቢና የመካከለኛ መደብ አላደገም። የነፍስ ወከፍ ገቢ አሁንም ከዓለም ዝቅተኛዎች ጋር የሚጋራ መሆኑን አሳይተናል። እነዚህን ችግሮች-- የኢትዮያን ኋላ ቀርነት፤ የአብዛኛውን ሕዝብ ድህነት-- የአሜሪካ መንግስት ሰላይ ድርጅት ወይንም ሌሎች ባለስልጣናት ያውቃሉ። ጥቅማቸው እስካልተነካ ድረስ ስኬታማ ያለው የዲፕሎማቲክ ጫና አያደርጉም። የተቃዋሚው ክፍል ጥሩ አማራጭ ስላላቀረበ፤ ለችግሩ አስተዋጽኦ አድርጓል። 8/

ጥያቄው፤ የውጭ አገር መንግሥታት፤ በተለይ የአሜሪካ መንሥት፤ የዚህን አድሏዊ የሆነ ስርአት አደጋ እያወቁ ለምን ሰላማዊ፤ ዲሞክራሳዊ፤ ፍትሃዊ፤ ሁሉን አቀፍ የሆነ ለውጥ እንዲመጣ የሚሰጡትን እርዳታ መሰረት አድርገው (Leverage) አልተጠቀሙበትም የሚለው ነው። ምክንያቶቹ እንደሚከተሉት ናቸው። ከሙባረክ አወዳደቅ እንዳየነው፤ የምእራብ አገሮች፤ ከነጻነት፤ ከሰብአዊ ሙብት፤ ከሰላምና ከፍትህ በፊት የሚመርጡት መረጋጋትን ነው። የመለስ መንግሥት፤ መረጋጋትን እደግፋለሁ ይላል። ተቃዋሚ እያሰረ፤ እየገደለ፤ እያሳደደ እያዩ፤ በሽብርተኛነት አመካኝቶ "ጸረ ሽብርተኛ ህግ"ና የመንግሥት ያልሆኑ ድርጅቶችን የሚያግብ ህግ ሲያወጣ (2009) ዝም ያሉት ጥቅማቸው ስላልተነካ ነው። ለእርጋታ፤ ለጸረ-ሽብርተኛነት ትግል የኢትዮጵያ መንግሥት "ቁልፍ" ነው ይላሉ። <u>የዲፕሎማሲ ዋና መመሪያ የራስ ሃገር ጥቅም መገልገሉ ብቻ</u> ነው። ሌላው ምክንያት፤ የተቃዋሚው ክፍል ደካማ መሆን። በአንድ ድምጽ፤ ለአንድ አላማ፤ ለአንድ አገር ለመቆም አለመቻሉ ነው። ሶስተኛው፤ የኢትዮጵያ ስደተኛ ለአገሩ ያለውን ሃላፊነት በድምጽ አለማሰማቱ ነው። በውጭ ያለው ስደተኛ በስድብ ብቻ የትም እንደማይደርስ ማወቅ አለበት። ቁም ነገሩ፤ በመተባበር ለአንድ ሃገራዊና ሕዝባዊ አላማ ቆሞ፤ ብሩህ አማራጭ መስጠት ሲቻል ሁኔታው ሊለወጥ ይችላል የሚሉ ብዙ

አሜሪካኖች አሉ። ለአገሩ ካሰበ፤ ስደተኛው ተቃዋሚ የዲፕሎማሲ ስራ በብልሃትና በቀጣይነት መሰራት አለበት። የተቃዋሚው ክፍል ችግር የመረጃ እጥረት አይደለም። ያቃተውና ያስጠቃው በአንድ ድምጽ፤ ለአንድ ታሪክ ላላት አገር ጠበቃ መሆን አለመቻሉ ነው። ሃልቮርሰንና ግላድስቲን በፎርብስ August 22, 2012 ያቀረቡት ዘገባ እንዲህ ይላል። "መለስ የብሄራዊ ደህንነት፤ ጸረ ሽብርተኛነት፤ የዓለም የእድገት እንዱስትሪ ኢጋፋሪ" በመሆኑ የአሜሪካን መንግሥት ታማኝነትና ድጋፍ አግኝቷል።" ቀጥለውም፤ "በእውነት መነፀር ሲታይ ግን፤ የምእራብ ዲሞክራሳዊ መንግስታት፤ ዜናዊን ማመስገናቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሰብአዊ መብቱ፤ ለክብር ለሚደረገው ትግል ፍትሃዊነትን የሚያደርገውን ትግል የሳተ (Injustice) አስተሳሰብ ነው" ብለዋል። አሜሪካ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ግንኙነት እንድትመረምር አሳስበዋል። ከላይ ወደታች የሆነው የአምባገነን አገዛዝ፤ በሙስና፤ በስርቆት፤ ከሕግ ውጭ በብዙ ቢሊየን ዶላር የገንዘብ ሽሽት በተራቀቀ አሰራር የታወቀ ነው። ከፍተኛውን የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚ፤ የስለላ፤ የመከላከያ ስልጣን የያዙት የህወሓት የበላዮች ናቸው። ለእነዚህ ግለሰቦች፤ የራሳቸው ጥቅም ከአገሪቱ ደህንነትና ከህብረተሰቡ ኑሮ መሻሻል በላይ ነው።

ሌላው የውጭ መንግሥታት የሚሉት፤ አማራጭ የሆነ የተባበረ፤ በአንድ ድምጽ የሚታገል ተቃዋሚ የለም ነው። በዚህ ላይ ምንም ልንከራከር አንችልም። የኢትዮጵያ ችግር፤ መለስና ጠባብ ብሄርተኛ ቡድኑ የፈጠረው የህወሓት/ኢህአዴግ ፍጹም የበላይነት ብቻ አይደለም። በበለጠ የጎዳት፤ የተቃዋሚው ክፍል ድክመት። መከፋፈል። ራስ ወዳድነት። መጠላለፍ። ሰርጎ ገብነት። ደሞዝ ወይንም ስንቅ ፈላጊነት። ጉረኛነት። ቂም በቀለኝነት። ቡድናዊነት። ከአንዳንድ የውጭ መንግሥታት ጋር ተቆላልፎ መታየት። ፍርሃት። በስራ ሳይሆን፤ በመናገር ለውጥ አመጣለሁ ባይነት ጭምር ናቸው። ለውጥ በፓልቶክ/በሬዲዮ ሊመጣ አይችልም። ለውጥ በአስመራ/በግብፅ/በአሜሪካ ወይንም ሌላ አገር መንግሥት ድጋፍ ሊመጣ አይችልም። የለውጡ ሃላፊና መሪ የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በተለይ ወጣቱ ትውልድ ብቻ ነው። ህወሓት እስር ቤቶችን ቢሞላቸው ወጣቱ ትውልድ ለራሱ ህይወት ሲል መታገል ግዴታው ነው። ይህን ለጊዜው ወደጎን እንተውና የውጭ አገር መንግሥታትና ሌሎች ደጋፊዎች ያላዩት የጨለማ ጎን ምን ይመስላል የሚለውን እንመርምር።

አንድ፤ ሰማንያ በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በህወሓት/ኢህአዴግ መንግስት ምንም እምነት የለውም። አፈናው አማሯታል። የዋጋ ግሽበት አቆርቁዟታል። ከሰባ እስከ ሰማኒያ በመቶ የሚሆነው ወጣት ስራ ማጣቱ አማሮታል። ቤትና መሬት ማጣት አሰቃይቶታል። ሙስና ዘግንኖታል። የእርስ በርስ ጥላቻን አይቀበልም።

ሁለት፤ የሃያ-አንድ አመታት የመለስ አምባገነናዊ መንግሥት ስርአት ለአገሪቱና ለመላው ሕዝቧ አደጋ እየጋበዘላቸው ነው። ገዢው ፓርቲ፤ በክርስቲያንና በእስልምና ሃይማኖት መሪዎችና ተከታዮች መካከል ጥላቻ ለማጠናከር ሞክሯል። የሃይማኖት ነጻነት በይፋ ከልክሏል። የአገሪቱና የአብዛኛው ሕዝቧ ችግር እየተባባሰ ሄዷል። የብሄረሰቦች መሪዎች (Ethnic elites) ለለም መሬት፤ ለተፈጥሮ ሃብትና ለስልጣን ይሻማሉ። የተራውን ሕዝብ አደራ እረስተውታል። በሃብትና ገቢ ስርጭት ሲታይ እውነተኛ የብሄረሰብ እኩልነት የለም። ሆኖም፤ ጠንክሮ የሚታየው ክስተት፤ የጎሰኛነት ልዩነት፤ጥላቻና የበላይነት ነው።

ሶስት፤ በእድገት ስም፤ የኢኮኖሚ አውታሮች ከኢትዮጵያ ሕዝብ ወደ ህወሓት የበላዮች፤ ታማኝ ደጋፊዎችና ወደ ውጭ ሃብታሞች እየተዘዋወሩ ነው። ገዢው ፓርቲ የሁሉ ነገር፤ በተለይ የተፈጥሮ ሃብት ደላላና አሰራጭ ተግባሮችን ይፈጽማል። አድሏዊ የሆነ፤ በጥቂቶች ቁጥጥር የተያዘ ገበያና ኢኮኖሚ፤ በሕግ የማይገዛ አስተዳደር (Party, endowment and individual monopoly) ፍትሃዊ እድገት እንዳይኖር አድርጓል። ኢትዮጵያውያን እንዳይወዳደሩ ማነቆ ሆኗል። ከህግ ውጭ ከሃገር ተደብቆ የሚሸሸው በዓመት ከሶስት ቢሊዮን ዶላር የሚገመተው የሚያሳየው በደል በመንግሥቱ፤ በአስተዳደሩ፤ በወደፊቱ ሁኔታ አስተማማኝ ፖሊሲ አለመኖሩንና የገንዘብ አጠቃቀም "በወንፊት" ቀዳዳ እየወጣ ለግል ጥቅም መዋሉን ነው። ገዢው ፓርቲ የሕብረተሰቡን ገንዘብ ልክ እንደ ቤተሰብ ገንዘብ ቸክ እየጻፈ የታማኞች መሸመቻ፤ የተቃዋሚዎች ማገቻ አድርጎታል። ይህ የአስተዳደር በደል፤ አድልዎና ሙስና የሚያስከትለው ውጤት ከትውልድ ወደ ትውልድ ይሸጋገራል። ዛሬ ገቢና ኃብት የሌለው ወጣት ትውልድ በሃገሩ እስከ ኖረና ስራ እስከሌለው ድረስ ደሃ ይሆናል። ባጭሩ ጥቂት አዲስ ባለጠዎች አገልጋይ የሆነ እድገት የብዙ ተከታታይ ትውልዶችን እድል ይወስናል (Multigenerational shift of natural resources and wealth). የተባበሩት መንግሥታት የልማት ድርጂት ሁሉን አቀፍ (Multidimensional poverty—income, food, health, education, shelter). የድህነት መስፈርት ተጠቅሞ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ አሁንም ደሃ ነው የሚለው ለዚህ ነው።

አራት፤ በማንም አገር ባማይታይና በማይታሰብ ደረጃ ሙስናና የጎሳ አድልዎ "ብሄራዊና መዋቅራዊ ነቀርሳ ሆኗል።" የበላይ ተቋሞች በሙሉ በትግራይ ምርጥ ተወላጆች፤ በተለይ፤ የህወሓት ታማኞች ቁጥጥር ተይዘዋል። የፍርድ፤ የጉምሩክ፤ የምርጫ ቦርድ፤ የመከላከያና የስለላ ተቋሞችን ማየቱ ይበቃል። የእነዚህ ሙሉ ቁጥጥር ለብዙ ነገሮች ይጠቅማል። በዓለም የታወቁ ልሂቃን በጥናት የደረሱበት ድምዳሜ አንድ ነው። ልዩ ልዩ ብሄር/ብሄረሰብና ኃይማኖቶች

ያለበት አገር በኃሳ የተመሰረተ አድልዎ ከተካሄደበት ሰላም፤ እርጋታ፤ ዘላቂና ፍትሃዊ እድገት አይኖርም ይላሉ፤ ለምሳሌ በአፍሪካ አገሮች የእርስ በርስ ጦርነትን ያጠናው እንግሊዙ ፖል ኮሊ፤ የአምባ ገነናዊ ስርዓቶች፤ የኢትዮጵያን ጨምሮ ያስከተለው የተዛባ የሃብትና የገቢ ስርጭት። ዛሬ በኢትዮጵያ ክልሎች ሁሉም ለራሱ ጥቅም የሚከራከረው፤ የጎሳ ማፅዳት ዘመቻ የተስፋፋውና አደገኛ ደረጃ ላይ የደረሰው የክልል ስርዓቱ ያስከተለው የጎሰኞች የበላይነትና ይገባኛልነት ውጤት ነው።

አምስት፤ የገቢ ደሃና የእርዳታ ጥገኛ በሆነችው ኢትዮጵያ በታሪኳ ባልታየ ባልታየ ደረጃ፤ ከሙስና ጋር በተያያዘ ሁኔታ፤ በአመት ቢያንስ ሶስት ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ዶላር ከህግ ውጭ ከኢትዮጵያ ሕዝብ እየተሰረቀ ይወጣል። እአአ ከ 2000-2009 ብቻ ወደ አስራ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ተዘርፏል። በአንድ አመት አስር ሽህ ቶን ቡና የት እንደደረሰ አለመታወቁ ማስረጃ ነው። ይህን ለማድረግ የሚችሉት፤ ስልጣን፤ ገንዘብ፤ ጠንካራና አስተማማኝ የፖለቲካ ግንኙነት ያላቸው ናቸው። የጉቦን፤ የሙስናን፤ የአድልዎን፤ የብር ዋጋ ማጣትን ጉዳት ለማየት፤ የኑሮ ውድነት በአመት ከሃያ አምስት እስከ አምሳ ሁለት በመቶ መሆኑን (ያለፈውና ሊደገም የሚችለው)፤ የስራ አጥነት እያደገ መሄዱን፤ ብዙ-ሽህ ወጣት ተምሮ የስራ እድል ስለሌለው ስደት አማራጩ መሆኑን ማየት ተገቢ ነው። የሴቶችን ችግር ለማየት የምንችለው ከዚህ አንጻር ነው። ችግሩን ስርአቱ ስለፈጠረው፤አልፈጠረውም ቢባልም ለመፍታት ስላልቻለ ህብረተሰቡ ለመኖር ከማይችልበት ደረጃ ደርሷል። አብዛኛው በድህነትና በሰብአዊ ሙብቶች መገፈፍ ጫና ደክሟል። እድገቱ፤ መዋቅራዊና የፖሊሲማነቆዎችን ለመፍታት አልቻለም። ህወሓት ችግሮች የሉም ሊል አይችልም። የሚበጀው ሰላምና እርቅ፤ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫዎች በተከታታይ፤ ያለ ምንም ገደብ እንዲካሄዱ የፖለቲካውን ሜዳ ክፍት ማድረግ ነው።

ስድስት፤ "እድገታዊ መንግሥት" የተባለው የመለስ "ፍጥረት" ያለምንም ነጻነት የሚገኝ የሰውን ህይወት ለዋጭ ፍልስፍና ነው ብለው የህወሓት የበላዮች ወስነዋል። አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ በፖሊሲ፤ በውሳኔ ምንም የሚያገባው የለም ተብሏል። መንግሥት ለሕዝብ ተጠሪነት የለውም እንደማለት ነው። ለጋሶች የዚህ አይነት የእድገት ፍልስፍና ጸረ-ፍትህ እንደሆነ፤ በደሃና በሃብታም መካከል ያለውን ልዩነት እንደሚያሰፋውና ለእርጋታ አደገኛ እንደሆነ አሳሰበው አያውቁም። አሁንም ቼክ እየጻፉ ግፈኛ የሆነ አገዛዝ ይደግፋሉ። እርዳታቸውን ጨምረዋል። ለተራው ሰው ያለውስ ጥቅም ምንድን ነው ብለን ብንጠይቃቸው መልስ ለመስጠት አይችሉም። እርዳታ ያለ ነጻነትና እኩልነት፤ ያለ ተሳትፎና የሕዝብ ድምጽ ሲካሄድ ያለውን ጎጅነት፤ Human Rights Watch, 2010, Development without Freedom በሚል አግባብ ያለው አርእስት ያቀረበውን ትንተና ማየት ተገቢ ነው።

ከሁሉም በላይ ችግሩን ማየት ያለብን ከተራው ሰው ኑሮ አንጻር ነው። ከእድገቱ የበላይ ተጠቃሚዎች፤ ከጎብኝ ስደተኞች፤ ከቱሪስቶች፤ ከአበዳሪዎች አንጻር አይደለም። ተራው ሰው እንዲህ ይላል። "እድገት አለ፤ ዳቦ የለም።" መንግሥት ግን፤ የገጠር ሚሊየነሮች ተፈጥረዋል" ይላል። ታዛቢዎች፤ የእድገት መለኪያዎች የድህነቱ ጥልቀትና ስፋት ነው ይላሉ። በሰብአዊ እድገት መለኪያ ኢትዮጵያ ከ187 አገሮች 174ኛ (2011 Index) ናት። የነፍስ ወከፍ ገቢዋ $365 ነው ይላሉ። ይህን ስናይ፤ መጠየቅ ያለብን፤ እድገቱ ለማን ጠቀመ። ማን ከበረ። ማን ደሃ ሆነ ወዘተ ነው። የተራው ኢትዮጵያዊ የኑሮ ሁኔታ ሊደበቅ አይችልም። በልቶ ለማደር የማይችለው ግለሰብ፤ ቤተሰብ ኑሮ ሊደበቅ አይችልም። በጠለላ የሚኖረው በሚሊዮን የሚቆጠር የአዲስ አበባ ሕዝብ ኑሮ ሊደበቅ አይችልም። በብዙ መቶ ሽህ የሚቆጠረው በመንገድ አዳሪ ወጣት ከቆሻሻ ምግብ ሲለቅም ሊደበቅ አይችልም። በአንጻሩ፤ አዲስ የኮንትራት ሃብታሞች ቦሌ የሰሩት ህንጻና ቪላ ሊደበቅ አይችልም። የእድገትን ውጤት ማነጻጸር እነደዚህ ያሉ ግልጽ የሆኑ የኑሮ ልዩነቶች መስፈርቶች በማመዛዘን ነው።

ሰባት፤ ሙስናውና ከአገር የሚሸሸው ሃብት ምን ያሳያል? ስርአቱ ምርጥ የኢኮኖሚ ተጠቃሚዎች (Social Elites) ማፍራቱን በግልጽ ያሳያል። በአዲስ አበባ የሚታየው የእድገት ብልጭጭጭ በውስጡ የተከማቸውን ድህነት በመጋረድ እውነተኛውን ገጽታ ሸፍኖታል። መንግሥቱም እንደሌለ ያቀርበዋል። የውጭ ተመልካቾች የሚያዩት ብልጭልጩን፤ ሆቴሉን፤ መመገቢያ ቤቱን፤ አፓርትሜንቱን፤ ህንጻውን ነው። በድህነት መቀነስ በኩል ያለውን ቀፎነት አያዩም። መለስ፤ "ነጻነትና እድገት ግንኙነት የላቸውም" ባለበት ወቅት፤ ለጋሶች ጉዳቱና ጥቅሙ ለማን ነው ብለው መጠየቅ ነበረባቸው። አሁንም መጠየቅ አለባቸው። "ነጻነትና እድገት" የተያያዙ ናቸው። አምባገነናዊ መንግሥት ከተፈለገ ግንኙነት የላቸውም።

*ያልተፈታው የፖለቲካ አመራር ችግር*

ስምንት፤ ከሁሉም በላይ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማነቆ የሆነው ለመንቀሳቀስ። ለመደራጀት። ለፍትህ ለመከራከር። ለመናገር። ለመጻፍ። አቤቱታ ለማሰማት። ለመወያየት። የግል ሃብት በችሎታ ለማቋቋም። ያለ ምንም ገደብ ተወካዮችን

ለመምረጥ። ለፖለቲካ ስልጣን በሰላም ለመወዳደር አለመቻሉ ነው። ይህ መብት ከሌለ፤ እርጋታ፤ ሰላም፤ ዘላቂነትና ፍትሃዊ የሆነ እድገት ሊገኝ አይችልም። የአካባቢ ሰላም ሊኖር አይችልም። የኃይማኖት ነጻነት እንደ ሌላው መብት ይታፈናል። ሁሉን አቀፍ የሆነ የፖለቲካ አመራርና ሁሉን አቀፍ የሆነ እድገት መመስረት ለሁሉም በሮችን ይከፍታል። ለተገንጣዮችና ለውጭ ጠላቶች በር አይከፍትም።

ዘጠኝ፤ ነጻነት ስለሌው፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚኖረው በፍርሃት አለም ውስጥ ነው። አምሳ በመቶ የሚሆነው የዓለም ህዝብ በከተማ ኗሪ ነው። የዛሬ ሃያ አመት ወደ ሰባ በመቶ ይለወጣል። በአንጻሩ፤ ሰባ ሰባት በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በገጠር ይኖራል። ስለሆነም፤ አብዛኛው ሕዝብ ለሙሉ ቁጥጥር ያመቻል። ከልማት ሰራተኞች በስተቀር፤ የሚደርስበትን ረሃብና አሰቃቂ ኑሮ የሚያውቅለት የለም። ይህ የሕዝብ ስርጭት ለግፈኛ አገዛዝ አመች ሆኗል። ያባባሰው ህወሓት የፈጠረው አገዛዝ ለሰው መብትና ክብር ግድ የሌለው መሆኑ፤ የመገናኛ ብዙሃን ነጻነት አለመኖሩ ነው። የዓለም ጋዜጠኞች ተሟጋች የሆነ ተቋም በአፍሪካ "ጋዜጠኞችን በማሰርና ከሃገር በማባረር ከኤርትራ ቀጥላ ሁለተኛውን ደረጃ የያዘችው ኢትዮጵያ ናት" ብሏል (CPJ, 2014 on Ethiopia and Human Rights). የህወሓት/ኢህአዴግ ዋና አዛዥ መለስ ከፈጠረውና እንደ ቅርስ (Asset) ከተወው ማነቆዎች መካከል የተራው ሰው ከስር ዓቱ የተፈጠረው ፍርሃት ዋናው ነው። በተለይ ከመንግሥት የስለላ፤ የልዩ ፖሊስ፤ የመከላከያ መረብ የመጣ ፍርሃት። ይህን ፍርሃት ወደ ኃይማኖት ተቋሞች አዛምቶት ይታያል። ፍርሃት ከአፈና የመጣ ባህል ነው። መሳሪያውና አጠናካሪው ስለላ ነው። የስለላ መዋቅሩ ከመንደር ጀምሮ፤ ወደቤተሰብ ተስፋፍቷል። አምስት ለአንድ ይባላል። አባት በልጁ ላይ። ልጅ በአባቱ ላይ እንዲሰልል እየተደረገ ነው። መንግሥት፤ በአመት ብዙ መቶ ሚሊዮን ብር የሚያወጣው ለዓስተዳደር ቅልጥፍና አይደለም። ለማስፈራራት፤ ለመወንጀልና ለመቆጣጠር ነው። በሌላ አቀራረብ ስናየው፤ የሕዝብ ድምጽና ክብር ካልተከበረ፤ ለሕዝብ ተገዥና አገልጋይ የሆነ መንግስት ካልተቋቋመ፤ ፍርሃት ይቀጥላል። ሌላው ቀርቶ በነጻ በውጭ የሚኖሩ ግለሰቦች የሚኖሩበት በፍርሃት ዓለም ነው። ባለፈው አመት ኖርዌይ በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ላይ የተደረገው ህወሓት ያቀደው የስለላ ሴራና በአሜሪካ በአበበ ገላው ላይ ሊደረግ የተሞከረው የግድያ ሴራ ይፋ ሲሆን፤ የኖርዌይና የአሜሪካ ህዝብ ብቻ ሳይሆን፤ መላው ዓለም ስለላው እንዲቆም ብዙ ጥረት እያደረገ ነው። ማጋለጡ ወደፊት በሰፊው መደረግ ይኖርበታል። ለምን? መፍራት ያለባቸው ሰላዮች፤ ነፍሰ ገዳዮች፤ የሰብአዊ መብቶች ገፋፊዎች፤ ሙሰኞች፤ ሌቦች ናቸው። ለሰላም፤ ለነጻነት፤ ለፍትህ፤ ለዲሞክራሲ የሚታገሉ ግለሰቦች መሆን የለበትም። በተለይ ሕገ መንግሥቱን አክብረው ለሰላማዊ ለውጥ የሚታገሉ። ፍርሃት ለእድገት፤ ለእርጋታ፤ለሰላም፤ ለነጻነት ተጻራሪ ነው። ፍርሃት ካልተወገደ፤ ለነጻነት፤ ለፍትህ፤ ለዲሞክራሲ ለመታገል አይቻልም። አገርን ለመታደግ አይቻልም። ፍትሃዊ እድገት ያለነጻነትና ያለ ሕዝብ ተሳትፎ አይቻልም። የኃይማኖት ነጻነት ጥያቄን ለመፍታት አይቻልም። የህወሓት/ኢህአዴግ ህገመንግሥት፤ አንቀጽ 27፤ የሃይማኖት "መብቶችን" ያረጋግጣል፤ "መንግሥት በሃይማኖት ውስጥ ጣልቃ እንዳይገባ" ያግዳል። ይህ አንቀጽ ዋጋ እንደሌለው ሆኗል።

አንድ፤ ህወሓት፤ ኃይማኖትን እነደማንኛውም ነገር የፖለቲካ የበላይነት መሳሪያ አድርጎታል። የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤትክርስቲያን በምትተዳደርበት ደንብ መሰረት የተሾሙትን ብቃት ያላቸውን ፓትሪያርክ አስወግዶና ለስደት ዳርጎ የፖለቲካ ምርጫ አድርጎ ሾሟል። ቤተክርስቲያኑን ከሁለት ከፍሏል። ሁለት፤ ባለፉት ብዙ ወራት፤ የእስልምና መሪዎችንና ተከታዮችን ተገቢ የኃይማኖት ነጻነት ጥያቄ ጥሶ አስሯል። አስታራቂዎችን ጭምር ቃሊቲ አስገብቷል። የሚያስከትለውን አደጋ አላጤነውም። ተከታታይ አፈና ተከታታይ ዓመጽ ይወለዳል፤ ለውጭ ጠላቶች በር ይከፍታል፤ የአገሪቱን አቅም ያደከማል። ለእልቂት ይጋብዛል።

ከሁሉ በላይ ህወሕት/ኢህአዴግ የጣሰው፤ የግለሰቦችን ነጻነት፤ እኩልነት፤ ሰብአዊነት መብቶች ያጸደቀውን የራሱን ህገመንግሥት ነው። በጽሁፍ ደረጃ፤ ህገመንግሥቱ፤ ከአንቀጽ አስራ አራት እስከ አንቀጽ ሃያ ዘጠኝ፤ ህጋዊ ያደረገው እነዚህንና ተመሳሳይ መብቶችን ነው። በደተጋጋሚ የጣሳቸውም እነዚህን በህግ የታወቁ መብቶች ነው። በኃይማኖት መብቶች ላይ የሚደረገው ሀገወጥነትና ጭቆና፤ በፖለቲካና ተመሳሳይ መብቶች ላይ ሲካሄድ ቆይቷል። በጽሞና ላየው፤ ሀገመንግሥቱና የመንግሥቱ አመራር፤ አስተዳደርና የህግ አፈጻጸም ምንም ግንኙነት የላቸውም። ህገመንገሥት ያወጣው ህወሓት/ኢህአዴግ ራሱ ባጸደቀው ህግ አይገዛም። ወንጀለኞችን ለህግ አያቀርብም። በአኟክ ሕዝብ ላይ ግድያ የፈጸሙ፤ በሶማሌ ህብረተሰብ ላይ ግድያና ሌሎች ወንጀሎች የፈጸሙ፤ በኦሮሞ፤ በአማራና በሌሎች ላይ እንደዚሁ በሕግ አይጠየቁም። የህግ ተቋሞች ለፖለቲካ የበላይነት አገልጋይ ሆነዋል። ገዢው ፓርቲ የራሱን ሕግ የማይከብርበት ዋና ምክንያት ተቀናቃይ ስለማይፈልግ ነው። የሕግ የበላይነት በሌለበት በዚህ ስርዓት ማንኛውንም ተቃዋሚ "ሺብርተኛ ነህ/ነሽ" ብሎ መክሰስ ቀላል ሆኗል። አዲሡ ትውልድ መጠየቅ ያለበት "አሸባሪው ማነው" የሚለውን ነው። በሰላም ለፍትህ፤ ለእኩልነት፤ ለዲሞክራሲ የሚታገሉ አሸባሪ ሊሆኑ አይችሉም።

አስር፤ በመጨረሻ፤ አብዛኛው የኢትዮጵያ የተማረ፤ እውቀት የገበየ፤ የስራ ልምድ ያለው ህብረተሰብ የሚገኘው ውጭ አገር ነው። ስለሆነም፤ የኢትዮጵያ ከፍተኛና መካከለኛ መደብ የሚገኘው ዋሺንግቶን ዲ ሲ፤ ሎንዶን፤ ኦቶዋ፤ ባንኩቨር፤ ወዘተ ነው። አንድ ናይጀሪያዊ እንዲህ ሲል ተናግሯል። "ዋሺንግቶንን የሚቆጣጠሯት የኢትዮጵያ ስደተኞች ይመስላሉ። የትም ቦታ ስሄድ እነሱ የሌሉበት የለም።" ሌላ በምእራብ አገሮች የሚኖረው ብቻ ከሁለት ሚሊዮን በላይ ነው። በሳውዲ አረቢያና በገልፍ ሃገሮች ሌሎች ሁለት ሚሊዮን የሚሆኑ ኢትዮጵያውን እየሰሩ ይገኛሉ። እነዚህ ሲደመሩ፤ በአመት ቢያንስ አራት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ዶላር ወደ ኢትዮጵያ ይልካሉ። ይህ ሰደተኛ፤ ለአገሩ፤ ለወገኑ በጎ ማሰቡ አይካድም። ሆኖም፤ ለመላው ህብረተሰብ ህይወት ለዋጭ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል ተብሎ ሲገመት እስካሁን፤ በአብዛኛው፤ ህይወትና አገር ለዋጭ የሆነ አስተዋጽኦ አላደረገም። የተማረና አገር ወዳድ የሆነ የሰው ሃይል አጠቃቀም ከሌለ እድገት ዘላቂነትና ብሄራዊነትና ፍትሃዊነት አይኖረውም። ህወሓት፤ ኢትዮጵያውያንን ያሳድዳል። የውጭ አማካሪዎችን በየቦታው አሰማርቷል። አንድ ጥናት የሚያመለክተው፤ ቢያንስ ሃያ ሽህ የውጭ በጎ አድራጊ፤ እድገት አስፋፊ የመሰሉ ድርጅቶች አሉ የሚል ነው። አገር ወለድ የሆኑ ድርጅቶችን አጥፍቶ በውጭ ድርጅቶች የሚተካ አገዛዝ ለመላው ህብረተሰብ አያስብም። የወለደው ጥገኝነትን ነው። ሌላ ጥናት የሚያሳየው፤ ቁልፍ በሆኑ ተቋሞች ውስጥ ቢያንስ ስምንት ሽህ የውጭ አገር አማካሪዎች ተሰማርተዋል። በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የሰው ሃይል ብቁነት እያገኘች የነበረች ኢትዮጵያ አሁን በውጭ የሰው ሃይል ድጋፍ የምትታወቀው የፖለቲካ ውሳኔ እንጅ እጥረት አይደለም። እጥረቱ የመጣው በተማረ ሰው ፍልሰት (massive brain drain) ነው። የተሰደደው ቁልፍ ሚና ሊጫወት ይችል ነበር። ስደተኛው፤ የኢትዮጵያን ግዛታዊ አንድነት፤ የመላውን ሕዝብ ሰላም፤ እኩልነት፤ ነጻነት፤ ፍትሃዊ እድገት፤ ከዲሞክራሳዊ ስርአት ብቻ የሚገኝ የሕዝብ ስልጣን ከፈለገ፤ መጀመሪያ፤ በውስጡ ያሉ ጥቃቅን ልዩነቶችን በጨዋነት መፍታት አለበት። ከጨቋኙ ፓርቲና ከደጋፊዎቹ በላይ ማሰብና አገሩን በፓልቶክ ለመለወጥ እንደማይችል መገንዘብ አለበት። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለስደተኛው የነበረው አክብሮት እየቀዘቀዘ መሄዱ የሚነገረው ባለው "ጠባብ አመለካከት፤ ልዩነትና ጨዋነት ማጣት፤ ራስ ወዳድነት ነው" ይባላል። ሁሉም በያለበት ኢትዮጵያ ዲሞክራሳዊ አስተዳደር እንዲኖራት በርትቶ ከሰራ፤ አስተዋጽኦው የሚያስደንቅ ይሆናል የሚል ግምት አለን።

አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለጉብኝት የሚሄዱ፤ ወይንም "የውጭ ባህል እንደ ስልጣኔ" ኢትዮጵያ ወስደው የግል ድርጅት የሚያቋቁሙ ወይንም ለጡሮታ የሚመለሱ፤ ወጣቱ ትውልድ ባህሉን፤ ታሪኩን እንዲረሳ የሚያደርጉትን፤ " ይቃወማል" የሚሉ አሉ። የኢትዮጵያን ታሪክ፤ የመላው ሕዝቧን ባህልና ልምዶች፤ ክብር፤ ተቋሞች ካላከበረና ካልጠበቀ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት አይኖሩም። ሕዝቡ ለስደተኛው የሚለው "ለአንድ አገራዊ አላማ፤ እውቅና፤ መለያ አብሮ መቆምና በአንድ ድምጽ ለመናገር መቻል አለበት። አለበለዚያ ያለው ሁኔታ አንዳለ ይቀጥላል። ያልተፈለገ የውጭ ባህል ይስፋፋል" ነው። በእኛ ግምት፤ ስደተኛው ራሱን ሳይለውጡ፤ በህወሓት ላይ ብቻ መጮህ፤ የሚታወቀውን ችግር መደጋገም፤ "አለን " እያሉ መፎከር አያዋጣም። የኢትዮጵያ ሕዝብ በስደተኛው የሚኮራው፤ ስደተኛው፤ ለአገርና ለወገን ጠቃሚ፤ ለህብረተሰብ ገንቢ፤ የሆነ ታሪክ የሚመዘግበው፤ ሕዝብ የሚኮራበት አስተዋጽኦ ለማድረግ ፍላጎት፤ ውሳኔና ብቃት ሲያሳይ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ በገዢው ፓርቲ እምነት እንደሌለው የጋለፐ ፖል ባደረገው ዘገባ አይተናል። በተለይ፤ "በመሪዎች፤ በፍርድ ቤቶችና በወሳኞች፤ በፌደራል ፖሊስ ፤ በመንግስት ቁልፍ ተቋሞች፤ በምርጫ ቦርድ፤ በምርጫ ነጻነትና ሚዛናዊነት እምነት የለውም።" እምነት ያለው በኃይማኖቱና በኃይማኖት ተቋማት ነው። ህወሓት እነዚህን በማጥፋት ላይ ይገኛል። ስደተኛው እነዚህን ድክመቶች ተገንዝቦ በያለበት አብሮ ለመስራት ሙከራ ሲያደርግ አይታይም። አሁንም፤ መከፋፈሉና "የሽሙጥ" አይነት ፖለቲካው፤ ከራሱ ወገን ይልቅ የውጭ መንግሥታትን አቤቱታ ማቅረቡ፤ ሳይዘጋጅ፤ ድጋፍ አለኝ ማለቱ፤ ወዘተ ቀድሟል። ይህ የማህበረሰብ ድክመት የሚያገለግለው የገዢውን ፓርቲ ነው። የመጨረሻው ነጥብ፤ ምን እናድርግ? ምን ለማድረግ እንችላለን? እንዴት? ወደሚሉ ሃሳቦች ያመራናል።

ለውጥ የሚመኝ ራሱን መለወጥ አለበት

ለውጥ የሚጀምረው ከእያንዳንዳችንና ከቤተሰቦቻችን ነው። እያንዳንዳችን፤ በግል ሆነ በጋራ፤ በኢትዮጵያ ሰላም፤ እርጋታ፤ ፍትህ፤ እኩልነትና ዲሞክራሲ እውን እንዲሆኑ ለማድረግ መሞከር የዜግነት ግዴታችን ነው። የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት የመናገር፤ የመደራጀት፤ የመሰብሰብ፤ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ፤ ወዘተ መብቶችን እንዲፈቅድ ጠንክሮ መስራት ይቻላል። የታሪክ ግዴታ ነው። በርማ የተደረገውን፤ ፕሬዘደንት ኦባማ ያደነቀውን ሰብአዊ መብት፤የሰው ክብር፤ የዲሞክራሲ ጭላንጭል ያመጣው የበርማ ሕዝብ ነው። በተለይ፤ ህይወቷን ለነጻነት የለወጠችውና በፍርሃት ያልተበገረችው የሰላም ኖቤል ተሸላሚ፤ ኦንግ ሳን ሱ ኪይ ናት። ኢትዮጵያ እንደሷ የመሰሉ ታጋዮች አሏት። አብዛኛዎቹ በእስር ቤት ናቸው። የተቀሩት በስደት ይኖራሉ። ሌሎች አልፈዋል። የራሱን ህይወት ለማሻሻል በገፍ ወደ ውጭ የተሰደደው ኢትዮጵያን የጎዳት ችሎታውና ልምዱ ለህብረተሰቡ አለመዋሉ ብቻ አይደለም። ተሰዶም አገሩን ለፍትሃዊ ሽግግር አለመደገፉ ነው። ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ ለማደግ የምትችለው በእርዳታ ብቻ

አይደለም። እንዲያውም፤ ተከታታይ እርዳታ ጥገኝነትን ወልዷል፤ ሙስናን አስፋፍቷል። የሳን ሱ ኪይ፤ የማንዴላ፤ የማርቲን ሉዘር ኪንግ፣ የፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ አይነት የህሊና ታጋዮች ደፍረው እንዲነሱ ያልተቆጠበ ቅስቀሳና ድጋፍ ሲሰጡ ነው። ይህን ለማድረግ የሚቻልባቸው ብዙ መንገዶች አሉ። በምንሰራበት መስሪያ ቤት። በምንጠቀምበት ቤተክርስቲያን ወይንም መስጊድ። በምንኖርበት ከተማ። ልጆቻችን በሚሄዱበት ትምህርት ቤት። በምንመርጥበት ከተማ፤ ወረዳ፤ ክፍለ ሃገርና አገር ለመስራት የሚያስችሉ ብዙ እድሎች አሉ። መጠቀሙ የእኛ ሃላፊነት ነው። አይሁዶች፤ አርመኖች፤ ኢራኒያኖች፤ ሶማሌዎች፤ ጋናዎች፤ ህንዶች ወዘተ የሚያደርጉትን ተከታታይ ስራ እናያለን። ከእነርሱ ለመማር እንችላለን። ፈቃደኝነትና ቆራጥነት ያስፈልጋል። በጣም የሚያሳዝነው፤ ስደተኛው ኢትዮጵያዊ ለሃገር ውይይት ሲጋበዝ አስር በመቶ የሚሆነውን ጊዜውን፤ ገንዘቡን፤ እውቀቱን አያጠፋም። ህሉን የፖለቲካ ንትርክ ያደርገዋል። አገር ቤት መሄድ ራሱ የፖለቲካ ውሳኔ መሆኑን ዘንግቶታል። የዘፈን፤የኳስ ጨዋታ፤ የሰርግና የመሳሰሉ መዝናኛዎች ግብዣ ሰብሳቢ ሲሆኑ፤ በኢትዮጵያ ጉዳይ መወያየት ሰብሳቢ ሊሆኑ አልቻሉም። የዚህን ጉዳት እያየነው ነው።

ለማለት የምንገደደው እያንዳንዳችን፤ በግል ሆነ በጋራ፤ የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት ሁሉንም የፖለቲካ እስረኞች ያለ ቅድመ ሁኔታ እንዲፈታ ድምጻችን ማሰማት እንችላለን። በምንኖርበት ሁሉ፣ መንግስታትን፤ የሃይማኖት ተቋሞችን፤ የሰብአዊ ሙብቶች ደጋፊዎችን፤ ወዘተ መቀስቀስ እንችላለን። መንግሥታት የሚሰጡት እርዳታ፤ ከመሰረተ ነጻነት፤ ከሰብአዊ ሙብቶችና ክብር፤ ከግል ክፍል የኢኮኖሚ ውድድር፤ ከግል ሃብት አስተማማኝነት፤ ከፖለቲካ እስረኞች መፈታት፤ ከነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ጋር እንዲያያዝ ድምጽ ለማሰማት እንችላለን። አፓርታይድ የወደቀው በተቀላለፈ የዓለም አቀፍ ሰላማዊ ትግል ጭምር ነው። በርማ የተለወጠችው፤ በውጭ ያለው በውስጥ ያለውን በመደገፉ ነው። ጋናም እነደዚሁ። እኛ ከሌላው ከምንኖርበት፤ ከምንሰራበት ህብረተሰብ ጋር ውይይት ብንጀምር ስራችን ዘላቂነት ይኖረዋል። ነጻነት፤ እኩልነት፤ መድብለ ፓርቲና የፖለቲካ ውድድር ያለ ፕሬስ ነጻነት ሊገኙ አይችሉም። እያንዳንዳችን፤ በግል ሆነ በጋራ፤ የፕሬስ ነጻነት፤ የINTERNET አጠቃቀም ነጻነት በፍጥነት እንዲለቀቅ ዘመቻ ማድረግ አንችላለን። ዘመናዊ መገናኛ መከልከሉ፤ የኢትዮጵያን ህብረተሰብ እድል ዘግቶታል። ኢትዮጵያ ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር ስትነጻጸር ወደኋላ ቀርታለች። አንዱና ዋናው ምሳሌ የመገናኛ ብዙሃን ገደብ ነው። የሕዝብ ግንኙነት ገመድ ወይም ትሥስር ጠንካራ የሚሆነው ዘመናዊ የመገናኛ ቴክኖሎጂ ሲሰራጭ ነው። ህወሓት የሕዝብ ግንኙነትን፤ በተለይ የወጣቱን ይፈራል። በሰለጠነው ዓለም የሚኖረው ስደተኛ የኢትዮጵያ መንግሥት በዘመናዊ መገናኛ ስርጭት ላይ የሚያደርገውን አፈና ፈጽሞ ወደ ጎን ትቶታል። The Economist put Ethiopia's lag as follows. "The absence of competition has seen a country of 80 million lag behind the rest of the continent in an industry that has generally burgeoned alongside economic growth…with mobile phone penetration of 70 percent in Sub-Saharan Africa compared to a paltry of 2.5 percent in Ethiopia; Internet access of 40 percent in Kenya." The Economist, August 2013. ይኼን ከህወሓት ፍራቻና የመቆጣጠር ስልት የመጣ እገባ ለመቀበል አይቻልም። ኢትዮጵያን፤ በተለይ ወጣቱን ትውልድ እየገጎዳው ነው። ተቀባይነት የማይኖረው ኢትዮጵያ ከአፍሪካ አገሮች ቀድማ የቴሌኮሙኒኬሽን ጥቅም ከስራ ላይ ያዋለች አገር መሆኗ ነው። አጼ ምኒሊክ በአፍሪካ የመጀመሪያውን የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ቢያስገቡም፤ ህወሓት/ኢህአዴግ ከላይ እየተቆጣጠረ፤ በማስፋፋት ፋንታ፤ ለመሰለያ ተጠቅሞበታል። ዘመናዊ የመገናኛ ቴክኖሎጂ እድል ከፋች አልሆነም። ይህ፤ የኢኮኖሚ ሙብት ገፈፋ ነው ለማለት እንችላለን። ገገርውን መንግሥት ያስጠቀዋል።

እያንዳንዳችን፤ በግል ሆነ በጋራ፤ ህወሓት/ ኢህአዴግ በመለስ አሳሳቢነትና ጫና፤ በተለይ፤ ከምርጫ ዘጠና ሰባት ወዲህ ሙሉ በሙሉ የተዘጋው የፖለቲካ ውድድር ሜዳ ያለምንም ገደብ እንዲለቀቅ ድምጽ ለማሰማት እንችላለን። ማንኛውም አገራዊ ምርጫ በሙሉ ነጻነት፤ በግልጽነት እንዲካሄድ እጃችን ማንሳት እንችላለን። ያለበለዚያ፤ ኢትዮጵያ ወደ ሌላ አደገኛ የእርስ በእርስ ጦርነት እነደምትገባ ማሳሰብ አለብን። ሙስና እንደ ካንሰር እየተስፋፋ፤ አብዛኛውን ሕዝብ ለድህነት፤ ወጣቱን ለስደት እንደዳረገው ልናሳሳስብና ልናስተምር እንችላለን። የመለስ "አምልኮ" የገንዘብ አምልኮ መሆኑን ልናያይዝ የምንችልበት ማስረጃ በዚህ መጽሃፍና በሌሎች ማስረጃዎች በብዛት አለ። የጠፋው ማስረጃ ሳይሆን የእኛ ቆራጥነትና ተሳታፊነት ነው።

እያንዳንዳችን፤ በግል ሆነ በጋራ፤ የምርጫ ቦርድ፤ ፍርድ ቤቶች፤ ፖሊስ፤ የመከላከያ ተቋሞች ከህወሓት/ኢህአዴግ ቁጥጥር በሙሉ ነጻ እንዲሆኑ ድምጽ ማሰማት አለብን። ይህ ካልሆነ፤ የፈለገው እርዳታ ቢጎርፍ ኢትዮጵያ ካለችበት ድህነት፤ ኋላ ቀርነት፤ ስጋት፤ ጥገኛነት ነጻ እንደማትሆን ማሳመን ግዴታችን ነው። ለዚህ ከበርማ፤ ከጋና፤ ከሲራ ሊዮን ወዘተ ለመማር እንችላለን።

እያንዳንዳችን በግል ሆነ በጋራ፤ በአገርም ሆነ በውጭ የሚገኙ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና የሲቪክ ድርጅቶች ጥቃቅን ልዩነቶቻቸውን አስወግደው በአንድ አገራዊ፤ በአንድ ህዝባዊ አላማ፤ በአንድ የሠብአዊ መብቶችና ዲሞክራሳዊ አርማ ላይ ተሰብሰበው መስራት እንዲጀምሩ ድምጽ ማሰማት እንችላለን። የጀመሩት እንዲቀጥሉ በያለንበት ግፊት ማድረግ ብሄራዊ ግዴታችን ነው። “ተባበሩ። አብራችሁ ስሩ። አገር ቤት ላሉ እውነተኛ ተቃዋሚ ድርጅቶችና የነጻ ጋዜጦች የገንዘብ ድጋፍ መስጠት እንችላለን። የሃሳብ፤ የዲፕሎማሲ፤ የሞራል፤ የገንዘብ” ድጋፎች ስጡ የማለት ጊዜው አሁን ነው። “ኢትዮጵያውያን መጀመር እንጅ መጨረስ አይችሉም” የሚለውን ባህል በስራችን መቀየር አለብን። ስደትን እንደ መድረሻ ከቆጠርን እጃችን ይታሰራል።

እያንዳንዳችን በግል ሆነ በጋራ፤ ለህወሓት/ኢህአዴግ እርዳታ የሚሰጡ መንግሥታትና ድርጅቶች እርዳታቸውን ከሰብአዊ መብቶች፤ ከፕሬስ ነጻነት፤ ከፖለቲካ ውድድር፤ ከኢኮኖሚ ፍትህ ጋር እንዲያያዙ በያለንበት ተግተን በዘላቂነት ለመስራት እንችላለን። በቅርቡ ከካናዳ መንግሥት ባለስልጣናት ጋር የተደረገ ውይይት የሚያሳየው ተባብረን ከሰራን የዓለም ሕዝብ እንደሚቀበለን፤ እንደሚያከብረን ነው። ገዢው ፓርቲ፤ የበላይነቱን የሚያረጋግጠው፤ የጦር መሳሪያ በመግዛት፤ የስለላ ተግባሮች በማስፋፋት፤ እኛን በያለንበት በማስፈራራት፤ ፕሮፓጋንዳውን በማሰራጨት፤ እርዳታን ለፖለቲካ መሳሪያ በመጠቀም ነው። እርዳታ ለፖለቲካ መሳሪያ፤ ለጥቂቶች የሃብት ማካበቻ እስከሆነ ድረስ፤ ደሃው ሊጠቀም አይችልም። መካከለኛው መደብ ሊስፋፋ አይችልም። ገቢው ከእጅ ወደ አፍ እየሆነ፤ ሶስት ምግብ ለመብላት ያዳግተዋል። ልጆቹን ለማስተማር አይችልም። ጤናው ሊጠበቅ አይችልም። ሰደተኛው፤ የማህበረሰብና የፖለቲካ ተቃዋሚ ክፍሎች፤ ምሁራን፤ የኃይማኖት፤ የሙያና ሌሎች ስብስቦች፤ በአመት ከአራት ቢሊዮን በላይ የሚሆነው እርዳታ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከድህነት፤ ከተሰፋ መቁረጥ፤ ቤት ከማጣት፤ ለልጆቹ የስራ እድል ካለማግኘት፤ ከምግብ ጥገኝነት ነጻ እንዳላወጣው ማሳየትና ማሳመን የእያንዳንዳችን ታሪካዊ ግዴታ ነው። እርዳታ ከሙስናና ከህግ ውጭ ከሚወጣው የውጭ ምንዛሬ ጋር መያያዝ አለበት። ይቻላል። በተለይ፤ የምእራብ አገሮች ለጋስ ሕዝብ በደሉን እንዲያውቅና ለፓርላማ፤ ለመንግሥት ተወካዮች ጩኸት እንዲያሰማ ማድረግ አለበት። የሙስናን፤ የአድልዎን ነቀርሳነት ለማሳየት የፕሬስ ነጻነት በሌለበት አገር አጋዥ ድምጽ ያለው በውጭ ነው። ይህ ድምጽ መከታ መሆን ያለበት አሁን ነው። አዳማጭ እንዳለው አንጠራጠርም። አፓርታይድ የወደቀበት አንዱ ዘዴ ይህ ነው። ሙባረክን፤ ወዘተ የጣለው የሙስናው መጠን ከሚዘገንን ደረጃ መድረሱ በተደጋጋሚ ለዓለም ተራ ሕዝብ ሲሰራጭ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የታወቀው ብቻ፤ ከዚች ደሃ አገር በስርቆት የሸሸው፤ ይህን መጽሃፍ ባዘጋጀንበት ወቅት፤ ሃያ አምስት ቢሊዮን ዶላር ደርሷል። በአመት ከሶስት ቢሊዮን በላይ። ሰረቅህ ተብሎ የተጠየቀ፤ የታሰረ፤ ገንዘቡን የመለሰ የለም። ከማረፉ በፊት መለስ “ሁለት ቢሊዮን ዶላር በውጭ ባንኮች እንዳለ እናውቃለን። ማን እንዳሸሸ እናውቃለን” ብሎ ነበር። አገር እንደዚህ ሲዘረፍ የመንግሥቱ የበላይ መሪና መንግሥት ለምን ዝም አለ ብለን ብንጠይቅ መልሱን እናገኘዋለን። ተጠቃሚው ከላይ ከላይ ስለሆነ ጭምር ነው። ከሌላው ጋር የሚተባበርና የህግ ተገን የሚሆን ከሆነ፤ ሃላፊነት፤ በህግ ተጠሪነት አይኖርም። መንግሥቱ ሙሉ በሙሉ ሙስኛ፤ አድሏዊና ጎሰኛ ሆኗል። ራሱን፤ ከፍተኛ ባለስልጣናትን፤ ታማኝ ደጋፊዎቹን ማጋለጥ አይችልም። “ሌባ ነኝ” ብሎ ራሱን መከሰስ አይጠበቅበትም። አገዛዙ የተፈጠረው ምስጢርንና ጥቅምን በማስከበር ነው። አቤቱታ ለማቅረብ የምንችለው በነጻነት የምኖር ኢትዮጵያውያን ነን፤ ይቻላል።

እያንዳንዳችን በግል ሆነ በጋራ፤ በኢትዮጵያ ሰላም፤ እርጋታ፤ ፍትህ እንዲገኝ፤ ሁሉም ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ገዢው ፓርቲ፤ ሽማግሌዎች፤ የኃይማኖት አባቶች፤ የታወቁ ግለሰቦች፤ የማህረሰብ መሪዎች የሚገኙበት አገራዊ የሆነ፤ የእርቅና ሰላም ጉባዔ (National Conference for Peace, Reconciliation and Democratic Governance) በአስቸኳይ እንዲካሄድ መቀስቀስ አለብን። ይህ ጉባኤ፤ የሁሉን ክፍሎች ተወካይነትና ጥቅም የሚያንጸባርቅ የሽግግር መንግስት አቋቁሞ ኢትዮጵያን ለእውነተኛ ምርጫ የሚያመቻች መሆን አለበት። ለህወሓት/ኢህአዴግ ይጠቅማል። ሂደቱ ለቂም በቀል መሆን የለበትም፤ ለእውነተኛ እርቅና ሰላም መሆን ይኖርበታል። ህብረተሰቡ የተወያየበትና ያጸደቀው ህገመንግስት ወዘተ እንዲያመቻች መቀስቀስ፤ የዓለም መንግሥታት ይህን የተቀደሰ አላማ እንዲድግፉ፤ ቴክኒካል እርዳታ እንዲሰጡ፤ ማሳሰብ ይቻላል። የካናዳ መንግሥት ይኼን ሃሳብ እንደሚጋራ ተናግሯል። ህወሓት/ኢህአዴግ የኢትዮጵያን ሁለ-ዘርፍ ችግሮች ብቻውን ሊወጣቸው አይችልም። የምእራብ ለጋስ ሃገሮች፤ በተለይ የአሜሪካ መንግሥት መረዳት ያለበት፤ ለሰላም፤ ለጸረ-ሽብርተኛነትና ለአፍሪካ ቀንድ እርጋታ ዋናው ቁልፍ የኢትዮጵያ መጠናከርና ከድህነት ነጻ መውጣት ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ የእድገቱ ተካፋይ ሆኖ ኑሮው ከተሻሻለ እርጋታ ይኖራል። ይህን ማስረዳት አለብን። የኢትዮጵያ ዘላቂ ጥቅም ተከብሮ፤ ሕዝቧ የራሱ እድል ወሳኝ ሆኖ፤ አብዛኛው የእድገቱ ዋና ተጠቃሚ ከሆነ፤ የአሜሪካ መንግሥት አስተማማኝ የሆነ ወዳጅ ይኖረዋል። ሁሉን አቀፍ የሆነ የፖለቲካ አመራር፤ ዘላቂነትና ፍትሃዊ ያለው እድገት ሊያመጣ ይችላል። እንደ ፕሬዘደንት ኦባማ፤ ለሰው መብት፤ ክብር፤ ነጻነት ደፍሮ ከልቡ የሚናገር መሪ አናገኝም። እኛ በርትተን፤ በአንድ ድምጽ ከተነሳን አዳማጭ እናገኛለን። የተቃዋሚው ክፍል መከፋፈል፤ ደካማ መሆን፤ አማራጭ ለማቅረብ አለመቻል የም እራብ አገኞችን፤ በተለይ የአሜሪካን አቋም በልዞታል። ጥሪው “ተባብራችሁ፤

አማራጭ ይዛችሁ ኑ" ነው። ጥቅማቸውን ለማስከበር ብቻ አስተማማኝ ሽግግር ይፈልጋሉ። እነዚህን ካላደረግን አባማን መውቀሱ አያዋጣም። ያለው የህወሓት/ኢህአዴግ የጠባብ ብሄርተኞች/ጎሰኞች ስብስብ (Governance by Ethnic Elites for Ethnic Elites) ለአብሮ ማደግና ተቻችሎ መኖር ጠንቅ ሆኗል። ይህን ማስረዳት አገራዊ ጥሪ ሆኗል።

እያንዳንዳችን በግል ሆነ በጋራ፤ የቻይና መንግሥት በኢትዮጵያ የሚያደርገውን የኢኮኖሚ የበላይነት እንዲገታ ዘመቻ ማድረግ ያስፈልጋል። የአሜሪካ መንግሥት ለህወሓት/ኢህአዴግ የሚሰጠው ድጋፍ ለቻይና ጠቃሚ መሆኑን በዘዴ ለማስረዳት መነሳት ይጠቅማል። ይህን ስንል፤ ቻይናና ኢትዮጵያ የንግድ ግንኙነት አይኑራቸው ማለታችን አይደለም። ኢትዮጵያ ጥቅሟ እስከተጠበቀ ድረስ ከማንኛውም አገር ጋር ግንኙነት ማድረግ አለባት። ከጥገኝነት ግን መቆጠብ አለባት። የቻይናን ኮሙኒስት ፓርቲ (CPC) ና የህወሓትን ተመሳሳይነትና ልዩነቶች አቅርበናል። የኢኮኖሚውን ግንኙነት ጎጅ የሚያደርገው፤ በምስጢር ስለሚካሄድና ውድድር ስለሌለበት ነው። የአንድ ፖለቲካ ፓርቲን የበላይነት ስለሚያጠናርና አገር ወለድ እድገት እንዳይኖር ጥገኛ እያደረገው ስለሄደ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም ቻይናን፤ ወይንም አሜሪካን፤ ወይንም እንግሊዝን፤ ወዘተ በማሞገስ አይገኝም። ማሞገስና መደገፍ ያለብን የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥቅም ነው። የቻይና መንግሥት የደረሰበት፤ ከአድልዎና ሙስና የመነጨ የሕዝብ ተቃውሞ በይፋ ተሰምቷል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ተቃውሞ ለማቅረብ ተከልክሏል። አዲሱ የቻይና መሪ፤ ዥይ ጂንፒንግ ባደረገው ገለጻ፤ የቻይና መንግሥት "ሙስናን ካላጠፋ፤ ቢያንስ ካልተቆጣጠረ፤ አገሪቱን ያጠፋታል። ፓርቲውም ይወድቃል" ያለውን በአንክሮ ማስተዋል ያስፈልጋል። ዋሽንግተን ፖስት "ወረርሽኝ (Scourage)" ብሎ የሰየመውን ሙስና፤ ዠይ ጂንፒንግ ለአመራሩ ባደረገው ንግግር፤ "ገዢው ፓርቲ ሙስና፤ ጉቦና አድልዎ ለሃገር አጥፊ መሆኑን ተገንዝቦ ካልታገለው አደጋው ግልጽ ነው ። ለቻይናና ለፓርቲው መጥፊያ ይሆናል (The party must be vigilant against graft...corruption will lead to the ruin of the party and the country)" ብሎ አስጠንቅቋል። በኢትዮጵያ  የጎሳ አድልዎ፤ ጉቦና ሙስና ልክ የእድገቱ ውጤት ነው የሚሉ ባለስልጣናት አሉ። ውይይት አይካሄድም። ለኢትዮጵያ ከፍተኛ አደጋ ያመጣል። እንደዚህ በውስጡ የተበላሸና የገማ፤ የስልጣን ብልግና ያለበት፤ በግልጽ አድሏዊ የሆነ አገዛዝ ለኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጠቃሚ ነው ለማለት አንችልም። አደገኛ ነው።

እርግጥ ነው፤ ቻይና ጠቃሚ የሆኑ መሰረተ ልማቶች--መንገዶች፤ ድልድዮች፤ ግድቦች፤ መሰብሰቢያዎች--በመላው አፍሪካ እንደምታካሂድ እናውቃለን። ሆኖም፤ ኮንትራቶች በውድድር አይካሄዱም። ኢንቬስትሜንቶች በግልጽነትና የኢትዮጵያ ሆነ የሌሎች አፍሪካ አገሮች የማምረት አቅማቸው እንዲጎለምስ በማድረግ ላይ የተመሰረተ መሆኑ ያጠራጥራል። ሴኔጋል፤ ዛምቢያ ወዘተ፤ በቻይና ላይ ያለው የሕዝብ ጥላቻ፤ ቻይና የራሷን የቀን ሰራተኞች በማምጣቷ ነው። የተፈጥሮ ሃብት ለራሷ ጥቅም በመፈለጓ ነው። የአፍሪካን የውስጥ ገበያዎች በራሷ የፋብሪካ ውጤቶች በማጥለቅለቋ ነው። ለሃገር ውስጥ ጥቃቅን ፋብሪካዎች መወዳደርና ማደግ ማነቆ በመሆኗ ነው። ከአምባገነን መንግሥታት ጋር እየተቀራኘች በሰብአዊ መብቶች አፈና፤ በሙስናና በአድልዎ "ምንም አያገባኝም፤ የውስጥ ጉዳይ ነው" በማለቷ ነው። ኢትዮጵያ የቀን ሰራተኛ ወደ ውጭ እየላከች፤ ከቻይና ሆነ ከህንድ ወዘተ የቀን ሰራተኛ መሸመት የለባትም። እንዲያውም፤ የሰለጠነና የተማረ የሰው ኃይል እያላት ከውጭ ማስመጣቷ የፖለቲካ ውሳኔ ነው እንላለን። ስለዚህ፤ የቻይና አቋም ከጥቅሟ ጉዳቷ ያይላል የሚሉ ብዙ ታዛቢዎች አሉ። ኢትዮጵያውያንም የቻይና መንግሥት ሚዛናዊ የሆነ ሚና እንዲጫወት፤ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ከቻይና እርዳታና ብድር ተጠቃሚ እንጅ ጥገኛ እንዳይሆን መቀስቀስ ግዴታቸው ነው። የኦባማ መንግሥት የቻይናን አደገኛነት፤ በአፍሪካ ውስጥ እያደገ የሄደ የንግድ፤ የኢንቬስትመንት የበላይነት ያውቃል። በኢትዮጵያ ውስጥ የሕዝብ ድምጽ አለመከበር፤ የፖለቲካ ውድድር አለመኖር፤ የግሉ ክፍል በፓርቲና በመንግሥት የበላይነት መታፈን ያጠነከረው ገዢውን ፓርቲና የቻይናን የበላይነት ነው። ይህን አደጋ በጥናት ማስረዳት የኢትዮጵያውያን ሃላፊነት ነው። ምሁራን ግዴታ አለባቸው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በተለይ፤ የገጠሩ አርሶ አደር፤ ለህይወቱ፤ ለቤተሰቡ፤ ለተከታታይ ትውልድ ህይወት ለዋጭ የሆነውን የተፈጥሮ ሃብቱን፤ በተለይ፤ መሬቱን ተቀምቷል።

ኢትዮጵያውያን የተፈጥሮ ሃብታቸው ባለቤት አይደሉም። ህገመንግሥቱ የተፈጥሮ ሃብት በሙሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ የወል ሃብት ነው የሚለው ተጥሷል። የተፈጥሮ ሃብት የገዢው ፓርቲ ሃብት ሆኗል። የመሬት ዋስትና የሌለው ህብረተሰብ ኑሮው አይሻሻልም። እድሉ ዝግ ነው። አደጋው ከፍተኛ ስለሆነ፤ ኢትዮጵያውያን በግል ሆነ በጋራ፤ ህወሓት/ኢህአዴግ የሚቸበችበውን የለም መሬትና የወንዞች ስጦታ እንዲያቆም መቀስቀስ አለባቸው። ገበሬው የመሬት ዋስትና እንዲኖረው፤ የከተማ ቦታ አመራር፤ አስተዳደር፤ አጠቃቀም ግልጽና ፍትሃዊ እንዲሆን ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ አለባቸው። ይህን ቅስቀሳ ከግል ሃብት አስተማማኝነት ጋር ለማያያዝ ይቻላል። በጠቅላላ ሲታይ፤ የገዢው ፓርቲ የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም፤ የኢኮኖሚ አመራር ስርአትና ደንብን (Regulatory Framework)  አፋኝ፤ ጎሳዊና

አድኗዊ ነው። ለፓርቲ፤ ለጥቂት ቤተሰቦች፤ ለውጭ አገር ኢንቬስተሮች ያዳላል። ለኢትዮጵያውያን የግል ኢኮኖሚ አስፋፊዎች ገደብ ያበዛል። ይህ ለግል ኢኮኖሚ እድገት የሚጎዳ መሆኑን ማስረዳት ይቻላል። የግሉ ኢትዮጵያዊ የሆነ የኢኮኖሚ ክፍል ወሳኝ ሚና ካልተጫወተ፤ አገር ወለድና ፍትሃዊ እድገት ሊኖር አይችልም። ዛሬ እንደሚታየው፤ ዘመናዊውን የኢንዱስትሪ ክፍል ቻይናዎች፤ ህንዶች፤ ቱርኮች፤ ሱዳኒሶች፤ምርጥ የሆኑ የገዢው ፓርቲ ደጋፊዎች ይቆጣጠሩታል። የኦሮሞ፤ የአፏከ፤ የደቡብ፤ የጉራጌ፤ የትግራይ ተራ ዜጋ ሊወዳደር አይችልም። ዱሮ አፍሪካውያን ስለ ኢትዮጵያ ሲያወሩ "እናንተ ኢትዮጵያውያን የራሳችሁን የተፈጥሮ ሃብትና አውታር የኢኮኖሚ ክፍሎች በበላይነት ይዛችኋል" ይሉን ነበር። ዛሬ ኢትዮጵያውያና የራሳቸውን የተፈጥሮ ሃብት አይቆጣጠሩም። የመንግሥት ሆነ የግል ክፍሉ ኢትዮጵያዊነት አከራካሪ ሆኖ ይታያል። መሰፈርቱ የስራ እድል፤ የስራ እድል ፈጣሪ የመመስረት እድል ናቸው ብለን ከወጣቱ ትውልድ አንጻር እንየው። በያመቱ ከሁለት ሚሊዮን ተኩል ለሚሆነው ወጣት ስራ ፈላጊ እድል ለመስጠት የሚችለው የግል ክፍሉ እያደገ ሲሄድ ብቻ ነው። የአሁኑ የተፈጥሮ ሃብትና የኢኮኖሚ የበላይነት አመራር ከቀጠለ፤ ለህብረተሰቡ፤ ለግል ክፍሉ፤ ለወጣቱ ትውልድ ብቻ ሳይሆን፤ ለገዢው ፓርቲ መውደቅ ዋና ምክንያት እንደሚሆን አመልካቾች አሉ። እድገቱ አሳታፊ ያልሆነ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የህብረተሰብ አመራር ለዘላቂና ለፍትሃዊ ልማት ወጥመድና ማነቆ መሆኑን በሌሎች አገሮች አይተነዋል። እንደ ጋና፤ ታንዛኒያ፤ ኬንያ ያሉ አገሮች ካለፈው ድክመት ተምረው ለተሳትፎ የሚያመች ፖሊሲና አመራር በተግባር አሳይተዋል። አኩሪ የስልጣኔ፤ የነጻነት፤ ከልዩ ልዩ ብሄርና ብሄረሰቦች የሚገኙ ኢትዮጵያን የሚለዩ ባህሎች ያሏት የተፈጥሮ ሃብት ባለጸጋዋ ኢትዮጵያ የምግብ ጥገኛ መሆኗ ለዚህ ትውልድ ያሳፍራል። ደሃና ኋላ ቀር መሆን የሌለባት ኢትዮጵያ የተማሩና የሰለጠኑ ልጆቿን እያባከነች ነው። ይኼ የገዢውን ፓርቲ ጠባብነትና ጎሳዊነት ያሳያል። ለወጣጡ ትውልድ ደንታ የለውም። ያባባሰው ከስተት አመራሩ ድክመት ያለው መሆኑን በምንም አያምንም። ድክመቱን አለማወቁ የችግሩን ከባድነት ያሳያል።

በዓለም ዙሪያ ያሉ አገሮች፤ ህብረተሰባቸውን ለማስቀደም ሩጫ ሲያደርጉ ይታያል። ቬትናም፤ ቻይና፤ ጋና ምሳሌዎች ናቸው። ሩጫ የማያደርጉ ሲወድቁ ይታያል። ሶማልያ፤ ደቡብ ሱዳን። የቻይና አመራር ይህን የሩጫ መንገድ ለሁሉም እድል ሲከፍት ይታያል። ከላይ ወደታች በምስጢር የሚሰራው የፖለቲካ አመራር ለተወሰነ ጊዜ መስራቱ አይካድም። አሁን ግን የሕዝብን ሮሮ ካልሰማ፤ ራሱን ከውስጥ ካልለወጠ አደጋ ይደርስበታል ተብሎ ይነገራል። ይህን የሚያዳምጠው የቻይና አመራር "ብልሃተኛ ነው ለማለት እንችላለን፤ ሁሉን ችግር ፈትቷል ማለት አይደለም። ይኼን የማይሰማ ደንቆሮ ነው" ሲል አንድ ታዛቢ ተናግሯል። ራሷን ባትለውጥ ቻይና ትፈርሳለች ማለት አይደለም። ለራሷ ስትል ትለወጣለች። ምክንያቱም አገሩን የሚመራው ፓርቲ አገር ወዳድ ነው። አገራዊ/ብሂራዊና አገር ወዳድ አመራር ቁልፍ የሚሆነው ለዚህ ነው። የቻይና የበላይ አመራር ከህወሓት/ኢህአዴግ አመራር የሚለይበት አንድ አበይት ጉዳይ አለ። ቢያንስ የሌሎችን ሃሳብ ይሰማል። አገር ወዳድ ነው። ለቻይና ታላቅነት፤ ለመላው ሕዝቡ ሃብታምነት ቅድሚያ ይሰጣል። ጠቃሚውን ሃሳብ ወደ አመራር ወይንም ፖሊሲ ይለውጠዋል። የኢትዮጵያ ዝግ ነው። በቅርቡ የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲና መንግሥት አመራር ለውጥ/ሽግግር ከመካሄዱ በፊት ለአመራሩ የቀረቡ ሃሳቦች እንደሚከተሉት ናቸው። ሃሳቡን የሰጡት በውስጥና በውጭ የሚገኙ፤ የቻይና ምሁራንና ሌሎች ታዛቢዎች ናቸው። የኢትዮጵያ መንግሥት ሁሉን ተቃዋሚ በጠላትነት ስለፈረጀ ተፃራሪ ሃሳብ አይቀበልም። የቻይና ምሳሌዎች።

1) ፓርቲው ከመንግሥት እንዲለያይ። የፖለቲካ ለውጥ (Political Reform) እንዲካሄድ። ግልጽነት እንዲኖር። ይኼን ለማድረግ የሚደፍር አገር ወዳድ መንግሥት ብቻ ነው።
2) የፓርቲውና የመንግሥት ባለስልጣናት በሙሉ የያዙትን ሃብት፤ የቤተሰቦቻቸውን ጨምሮ፤ ለሕዝብ እንዲያስታውቁ። (Disclosure). የህወሓት መንግሥት ይኼን ደፍሮ አያደርግም።
3) መንግሥቱ በሙሉ ግልጽነት እንዲሰራ። የመሬት አጠቃቀም ለህብረተሰቡ እንዲገለጽ።
4) የመንግሥት ባጀት አጠቃቀም ለህብረተሰቡ ግልጽ እንዲሆንና የማህረሰብ ክፍሎች እንዲቆጣጠሩት።
5) የመገናኛ ብዙሃን ነጻነት እንዲኖር። የፖለቲካ ውድድር እንዲጀመር።
6) አዲሱ አመራር ሙስናን ለመከላከል ቆርጦ እንዲነሳ የሚሉ ይገኙበታል። ጠቅላይ ሚኒስትር ደሳለኝ ኃይለማሪያም ይኼን ለማድረግ የጀመረውን አመራር ወደ ከፍተኛ ሙሰኞች ሊያሸጋግረው ይችላል፤ መድፈር አለበት።

እነዚህ በሙሉ ወይንም በከፊል ከስራ ላይ ይውላሉ ለማለት ማስረጃ የለም። ዋናው ነገር፤ ውይይት መኖሩ ነው። በአንጻሩ፤ የታሪክ፤ የሰው ፍጥረት መሰረት በሆነችው ኢትዮጵያ፤ ሕዝቡ በማንኛውም ሃገራዊ ጉዳይ ላይ ውይይት አያደርግም። አይሳተፍም። አይቻልም። ፖሊሲ ፈጣሪውና ፈጻሚው አንድ ፓርቲ ነው። ለመወያየት የማችል ዓመራር በመሰረቱ በፍርሃት የተበከለ ነው ለማለት እንችላለን። ህወሓት በፈጠረው---የአንድ፤ በጠባብ ብሄርተኛ ቡድን የተጠነሰሰና የሚዳኝ የአምባገነንነት ጫና ላይ--ጥናታችን የደረሰበት ግንዛቤ፤ ህወሓት/ኢህአዴግ የህብረተሰቡን የማሰብ፤

የመሰብሰብ፤ የመናገር፤ አማራጮች የማቅረብና፤ በአብዛኛው፤ የመፍጠርና የማምረት ችሎታ አፍኖታል የሚል ነው። ሌላው ቀርቶ ከቻይና ጋር ለመወዳደር አይችልም። አገር ወዳድ ስላልሆነ። የፓርቲው ባለስልጣናት ከህብረተሰቡ ጋር በቀጥታና በግልጽ የመወያየት ልምድ የላቸውም። ለምሳሌ፤ ስብሃት ነጋ ደፍሮ የሚወያየው ከራሱ ምሽግ ብሄረሰብ/ጎሳ ጋር ነው። ከአፏከ ወይንም ከሶማሌ፤ ወይንም ከኦሮሞ፤ ወይንም ከአማራ፤ ወይንም ከአፋር ተራ ሕዝብ ጋር ተገኝኝቶ ለመወያየት አይደፍርም። በአንድ ኢትዮጵያዊ ተመልካች አቀራረብ፤ "ህወሓት/ኢህአዴግ የአገሪቱን ኢኮኖሚ የሚያንቀሳቅሱት ልክ "ለነጻነት እንደሚዋጋ ግንባር ነው" ያለው በዚህ ምክንያት ነው። ነገ ኢትዮጵያ ብትፈራርስ መደበቂያው የትጋራይ ክልል፤ ክልል አንድ ይመስላል። የቻይና መሪዎች የዚህ አይነት አመለካከት የላቸውም። ገዢው የጎሳ ግንባር የእለት ከእለት የሆነውን የራስ ጥቅም ድል እንደ ህብረተሰቡ ድል ይቆጥረዋል። አብዛኛው እንዴት እንደሚኖር። እድገቱ ማንን እንደ ጠቀመ። ማንን እንዳገለለና እንደ ጎዳ አያይም። ፖሊሲ የሚጸንሱት፤ የስራ ፕሮግራም የሚቀርጹት፤ የአገር ባጀት የሚጠቀሙት፤ ከውጭ ድርጅቶችና መንግሥታት ጋር ውል የሚገቡት "በምስጢር" ነው። በአጠቃላይ ሲታይ፤ የገዢው ፓርቲ ከሁሉ በላይ የሚፈራውና ያፈነው የሰብአዊ መብቶች መከበርን ነው።

ምእራፍ ሁለት የሚያሳየው፤ ሰብአዊ መብቶች--የፖለቲካ፤የማህበረሰብ (Civil Liberties)፤ ካልተከበሩ፤ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚና የማህበረሰቡ ኑሮ በተፈለገው ደረጃ ሊያድጉና ሊሻሻሉ አይችሉም። ህወሓት/ኢህአዴግ፤ ቢፈልግም፤ ባይፈልግም ብቻው ችግሮቹን ሊወጣቸው ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል። የፈለገውን ያህል ሰው ቢያስርና እስር ቤቶችን ቢሞላ ፖሊሲና መዋቅራዊ ችግሮችን ለመፍታት አቅም አይኖረውም። በተለይ የወጣቱን ትውልድ የስራና የነጻነት ፍላጎት ማሟላት። ጠባብ ጎሳዊ አድልዎ በማህበረሰቡ መካከል አስከፊ ልዩነቶች ፈጥሯል። ባጭሩ፤ የፖለቲካው ችግር ካልተፈታ፤ የማህበረሰቡ በግልጽ ጎልተው የሚታዩ ችግሮች ሊፈቱ አይችሉም። ኢኮኖሚው በዘላቂነትና በፍትሃዊነት ሊያድግ አይችልም። ለዚህ፤ በመጀመሪያ ደረጃ ተከታታይ ትውልድና ታሪክ በሃላፊነት የሚጠይቁት የአምባገነኑን መንግሥት መሪዎች ነው። በሁለተኛ ደረጃ፤ ተቃዋሚውን ክፍል እንደሚሆን አያጠያይቅም። ቢያውቁበት ሁለቱም ለኤትዮጵያ ዘላቂነትና ለመላው ዘጠና አራት ሚሊዮን ሕዝቧ ህይወት መሻሻል ሲሉ ስልጣን በመከፋፈል፤ ውይይት በማካሄድ፤ ሰላምን በመፍጠር ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ይሰሩ ነበር። እኛ የምንመኘው ይህን ከዚህ በፊት ያልተሞከረ የኢትዮጵያን ሕዝብ ታላቅነት የሚያስመሰክር መንገድ ነው። ይኼ የሰላም መንገድ ለፖለቲካ ተወናዋኒያን የተለመደ አይደለም። የተለመደው መንገድ ስልጣን በጦርነት የሚል ስለሆነ። ወጣቱ ትውልድ የሚያዋጣው ሰብአዊ መብቱን፤ ሕገ መንግሥቱ የሚፈቅደውንና ዓለም የሚቀበለውን አገር አቀፍ የሆነና የተያያዘ የሕዝብ አመፅ ቀስቅሶና ተደራድሮ እውነተኛ ዲሞክራሳዊ ስርዓት መመስረት ነው። የኤትዮጵያ ሕዝብ የስልጣኑ ባለቤት እንዲሆን።

## ምእራፍ ሁለት

## የሰብአዊ መብቶች መታፈን የተዛባ እድገት ፈጥሯል

*"እኔም ለራሴ፤ ለልጆቼና ለኢትዮጵያ ሁሉ፤ ዲሞክራሲና ነጻነት እነደሚገባን በማመን አቅሜ በፈቀደው መጠን ታግያለሁ። ይህን በማድረጌ በማንም ላይ በክፋት አልተነሳሁም። ይህን በማድረጌ፤ ሕግ ጥሸ አላውቅም። ይህን በማድረጌ፤ በድሃዋ አገሬ ጥቅም ላይ አልተነሳሁም። ይህን በማድረጌ፤ ፈጣሪየን፤ የኢትዮጵያን ሕዝብም ሆነ፤ ህሊናየን የሚያሳዝን አንዳች ነገር ፈጽሚያለሁ ብየ አላምንም። እኔን <u>እዚህ ያቆመኝ የነጻነት ናፍቆት ነው።"</u>*

*አንዱአለም አራጌ፤ የፍርድ ቤት ውሎ ንግግር*

*"በድፍረት ብቻ አለማወቅን መሳሪያ አድርጎ አንድ ሕዝብን ማተራመስ መቻል ሕዝቡን ያዋርዳል።"*

*መስፍን ወልደ ማሪያም*

*"እኛ እንደፈለግነው መብት እንዳናፍን ቀፍድዶ የሚይዘን የለም።"*

*መለስ ዜናዊ*

*የመሳሪያ የበላይነት የያዙት የገዢው ፓርቲ የበላዮች፤ በተለይ የህወሓት አለቃዎች፤ ማንንም ማዋረድ እንደ አገዛዝ ስጦታ ያዩታል። ፍትሃዊ እድገት ሰውንና የሰውን ክብር ከማይጠብቅ አመራር ሊመጣ አይችልም።<u> የዚህ ም እራፍ ሰብሳቢ ሃሳብ ነጻነት፤ ተሳታፎ፤ እውነተኛ እኩልነት፤ የሕግ የበላይነት፤ ግልፅነትና ተወዳዳሪነት የሌለበት የእድገት አመራር እድገት ቢያሳይም ዘላቂነትና ፍትሃዊነት ያለው ልማት ስኬታማ አይሆንም የሚል </u>ነው። የሁሉን ኢትዮጵያውያን ኑሮ ለማሻሻል የሚፈልግ አገዛዝ፤ የሁሉን ዜጋ ሠብአዊ መብት ማክበር አለበት። ህወሓት በበላይነት የሚመራው መንግሥት ሁለቱንም መብቶች ከልክሏል። የፖለቲካም፤ የማህበረሰብም። በ2013 Human Rights Watch ያወጣው ዘገባ የሰብአዊ መብቶች ካለፈው በባሰ ሁኔታ እየተጣሱ መሆኑን አስታውቋል። ("Ethiopia's human rights record has sharply deteriorated, especially over the past few years")፤ መንግሥት ለአፈና የሚያመች "ሽብርተኛ ናችሁ" ብሎ የሚወነጅልበትን የፀረ-ሽብርተኛ ህግ፤ የመንግሥት ያልሆኑ ድርጅቶችን ለማስተዳደር ያወጣው ህጎ ውጤት የመንግሥቱን ግፈኛነት ያሳያሉ። ሁለተኛው ሕግ የማህበረሰብን ሰንሰለት አውድሞታል፤ የማህበረሰብ እንቅስቃሴ የሌለበት አገር ለመቡቱ፤ ለፍትህ፤ ለሕግ የበላይነት፤ ለዲሞክራሲ ለመቆም አይችልም። ከሁሉም በላይ ትኩረት የሚያስፈልገው የሲቪክ ድርጅቶች እንዲፋፋና እንዲስፋፉ መታገል ነው። ህወሓት ባወጣው አፋኝ ሕግ መሰረት ባለፈው አመት በሰላሣ ጋዜጠኞች፤ የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎችና የፖለቲካ ተቃዋሚዎች ላይ ፈርዷል። በቅርቡም በተከታታይ ጋዜጠኞችን፤ የዲሞክራሲ ተከራካሪዎችንና ሌሎችን አስሯል። ከ2011 ወዲህ ብቻ በአስራ አንድ ጋዜጠኞች ላይ የረጅም ጊዜ የእስራት ፍርድ ተወስኗል። ውብሸት ታየና ርዮት አለሙ (አምስት አመት)፤ እስክንድር ነጋ (አስራ ስምንት አመት)፤ አቢይ ተክለማሪያምና መስፍን ነጋሽ (በሌሉበት)፤ የፖለቲካ ተቀናቃኝ ነህ፤ ህገመንግሥቱን አዋርደሃል። "ሽብርተኞችን ደግፈሃል" በሚል የፈጠራ ማስረጃ፤ አንዱአለም አራጌን ወዘተ ፈርዶባቸዋል። አቤቱታ ለማድረግ የማይቻልበት የፖለቲካ ፍርድ በእስራት አያቆምም። ዋናው አላማ የእነዚህንና በብዙ ሺህ የሚገመቱ የፖለቲካ እስረኞች መንፈስ መስበርና ህልውናቸውን ማጥፋት ነው። የህወሓት/ኢህአዴግ የፖለቲካ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የእስክንድር ነጋንና በውጭ የሚኖረውን የታወቀ ጋዜጠኛ የአበበ ገላውን የግል ንብረት እንዲወረስ አድርጓል። ፍርዱ የቤተሰብን ህልውናም ያጠፋል። የመለስ አገዛዝ ዘዴ እስር ለመፍታት እስረኛውን ማዋረድ ነበር። አሁንም ነው።*

*ህወሓት/ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘበት ጀምሮ በተለይ ለማፈንና ለማጥፋት ያተኮረው ነጻ ጋዜጠኞችን፤ የሰብአዊ መብት ጠበቃዎችንና የፖለቲካ ተቃዋሚዎች ነው። እነዚህ፤ ብሄራዊ የሆኑ ችግሮችን በመተንተን መሰረታዊ ለውጥ እንዲመጣ የሚፈልጉና የሚታገሉ አገር ወዳድ ሃይሎች ስለሆኑ ለስርአቱ "አደገኛ ናቸው" ተብለው ክትትል ይደረግባቸዋል። ይታሰራሉ። ከአገር ጠፍተው ይሰደዳሉ። የሰብአዊ መብቶች ድርጅት ያለውን እንጋራለን። "More journalists have fled Ethiopia than any other country in the world, due to threats and intimidation… in the last decade at least 79 journalists have fled, according to the Committee to Protect Journalists (CPJ)." ዛሬ በኢትዮጵያ ነጻ የሆኑ ጋዜጠኞትና ጋዜጠኞች የሉም። ነጻ የሆኑ የሠብአዊ መብት ጠበቃዎች የሉም። ነጻ የሆነ የመንግሥት ያልሆነ የማህበረሰብ ድርጅት የለም። አገር አቀፍ የሆነውን መኢአድን ገዢው ፓርቲ አላንቀሳቀሰውም። ሌሎች ብሄራዊ ፓርቲዎች አሉ ለማለት አይቻልም። ያሉትም፤ ለምሳሌ አንድነት፤ ሰማያዊ፤ አሬና፤ መድረክ ወዘተ*

እንደልባቸው ለመንቀሳቀስ አልቻሉም። ለመተባበር ሲሞክሩ የውስጥ ጠለፉ ይደረግባቸዋል። እንደ ልባቸው ገንዘብ ለመሰብሰብና ለማንቀሳቀስ አይችሉም። ከመለስ እልፈት በኋላ የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት ከፍጹም ግፈኛነቱ ፈቀቅ አላለም። ያዝ ለቀቅ የሚለው የሰላማዊ ሰልፍ አገር አቀፍና ለውጥ ለማምጣት በሚቻልበት ደረጃ ሊካሄድ አልቻለም። በየቦታው ወጥመዶች ተተክለውበታል። ህወሓት/ኢህ አዴግ የፈለገውን ያህል ታጋዮችን ቢያስር ያለው አማራጭ አንድ ነው። ይኼን ሰብሮ መውጣት ግዴታ ነው።

በዚህ መጽሃፍ እንደምናሳየው፤ የህወሓት/ኢህአዴግ ግፈኛ አገዛዝ (Tyrannical Governance) በተከታታይ የሚያደርገው አፈና ከተፈጥሮ ሃብትና ከገንዘብ ቁጥጥር ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለው። ቢጋምቤላና በሌሎች ክልሎች የሚደረገው የመሬት ነጠቃ ወደ ሁለት ሚሊዮን የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ከመሬታቸውና ከኑሯቸው እንዲባረሩ አድርጓል። በጋምቤላ ብቻ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ነዋሪዎች ለጋሶች በሚደግፏቸው “አዲስ መንደሮች” እንዲኖሩ እየተደረገ ነው። በኦሞ ሸለቆ ቢያንስ ሁለት መቶ ሺህ ነዋሪዎች መሬታቸውን እንዲለቁ ተደርጓል። ጥንታዊው የዋልድባ ገዳም የጎሰኞች “የስኳር ማምረቻ” እንዲሆን ተወስኗል። የመሬት ነጠቃ በሚካሄድባቸው ቦታዎች ሁሉ፤ የኢትዮጵያውያን ቤተሰቦች ኑሮ እንደተናጋ ሂውማን ራይትስ ዋች፤ ኦክላንድ ኢንስቲቱት፤ ሰርቫይቫል ኢንተርናሽናልና ሌሎች በማስረጃ አቅርበውታል። በጉራ ፈርዳ፤ በቤኒ ሻንጉል ጉሙዝና ሌሎች ክልሎች የአማራው ብሄረሰብ በገፍ እንዲባረር የተደረገው ይህን ህብረተሰብ በኢኮኖሚ ለመጉዳትና ለማንበርከክ ነው። ይህ ከተፈጥሮ ሃብት ቁጥጥር ጋር የተያያዘ አፈና እንደሚቀጥል አንጠራጠርም። እንዲያውም እየተባባሰ ሊሄድ ይችላል የሚሉ የውስጥ ታዛቢዎች ብዙ ናቸው። የሰውን ህይወት ከተፈጥሮ ሃብት ቁጥጥር ዝቅ አድርጎ የሚመለከተው ህወሓት የሚቆጣጠረው መንግሥት፤ ባለፈው አመት ለልዩ ክትትልና አፈና የሚያገለግል “ልዩ የፌደራል ፖሊስ አቋቁሟል። በኦጋዴን አስር ሰላማዊ ዜጋዎች ገድሏል። በአዲስ አበባ፤ በሰላም ተቃውሞ የሚያሰሙ የእስልምና ተከታዮችን በትኗል። አስሯል።” የኦሮሞን ወጣቶች በገፍ ጨፍጭፏል። የስርአቱ ግፈኛነት በዚህ አያቆምም። ከገዢ ፓርቲና ከመንግሥቱ የበላዮች ጋር ቀጥታ የሆነ ግንኙነት የሌላቸው ወጣቶች የመቀጠር ወይንም ስራ የመፍጠር እድል ስለሌላቸው በገፍ ይሰደዳሉ። ከላይ የተጠቀሰው ጥናት እንዲህ በሚል ደምድሟል። “የኢትዮጵያ ደሃ ስደተኞች በውጭ የሚሰሩበትና የሚኖሩበት ሁኔታ “ከባርነት አኗኗር” ሊለይ አይችልም። በተለይ በተባበሩት የአረብ ኤምሬትስ፤ በሌባኖንና በሳውዲ አረቢያ (Ethiopian migrant workers abroad live under slavery-like conditions in the UAE, Saudi Arabia and Lebanon.” ለጋሶች ለዚህ የተዛባ የኢኮኖሚ አመራር ድጋፍ መስጠታቸው ሁኔታውን አባብሶታል። ዓለም ባንክ የሰብአዊ መብቶች መከበር ከፍትሃዊ ልማት ጋር ያለውን ቀጥተኛ ግንኙነት ራሱ እየሰበከ ግፈኛውን የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት ይደግፋል። ይህን የልማት ድጋፍ ነው ለማለት አንችልም። የታወቀው የደቡብ አፍሪካ መሪ፤ የዘመናዊዋ አፍሪካ አባትና የኢትዮጵያ ወዳጅ ኔልሰን ማንዴላ ስለ ነጻነትና መብት ሲናገር እንዲህ ብሏል። “በእስር ቤት የሚኖር ግለሰብ ወይንም እስረኛ ለመብቱ ሊከራከር አይችልም።” ነፃነት የሌለው ሕዝብ ለፖለቲካ፤ ለማህበራዊ፤ ለኃይማኖትና ለኢኮኖሚ መብቶች ለመከራከር አይችልም።

የዚህ ምእራፍ ዋና አላማ የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት የተፈጥሮ ሃብትን በሙሉ ለመቆጣጠርና የገንዘብ ትርፍ ምንጮችን በበላይነት ለመያዝ ባለው ግብ መሰረት ብሄራዊ የሆኑ ተቋሞችን ማፈራረስ፤ በህብረተሰቡ መካከል ያሉ ተከታታይ ትሥስሮችን፤ ግንኙነቶችን ማድከምና ለብሄራዊ ጥቅሞችና ለሰብአዊ መብቶች የሚታገሉትን ሁሉ ማፈን አለበት የሚል ነው። “ስልጣን ወይም ሞት” የሚለው ፍልስፍና ለዚህ ዘዴ ወሳኝ መሆኑን አይተናል፤ አሁንም እያየን ነው። የህወሓት አመራርና ደጋፊዎች ኢትዮጵያን ለሃያ ሶስት አመታት በአምባገነንነት የመራውን መለስ ዜናዊይን “የለውጥ ሃዋርያ” ብለው ሰይመውታል። የማይካደው፤ እሱ የመራው መንግሥት ህይወት ለዋጭ የሆነ መሰረተ ልማት መካሄዱ ነው። ሆኖም፤ ይህ ልማት ለብቻው ታይቶ መሪውን “የለውጥ ሃዋርያ” ሊያደርገው አይችልም። ሰብአዊ መብቶችን ፍፁም በሆነ ደረጃ አፍኖ “የለውጥ ሃዋሪያ” ለመሆን አይቻልም። ህወሓት የጀመረው ኢትዮጵያን በመበታተን ነው። የሃገሪትን የባህር በር በመዝጋት። ሕዝቡን በማጋጨት ወዘተ። በመንግሥቱ ኃይለማሪያም የጭካኔ አገዛዝ የመጣውን ከፍተት ተጠቅሞ በውጭ መንግሥታት ድጋፍ ስልጣን የያዘው ህወሓትና ተባባሪ የሆኑት የጎሳ ፖለቲካ ስብስቦች ሊክዱት የማይችሉት ሃቅ አለ። ቅድመ ህወሓት/ኢህአዴግ ብሄር፤ ብሄረሰቦች ቋንቋቸውን እንዲጠቀሙና እንዲያዳብሩ መብት አልተሰጣቸውም። የራሳቸውን እድል በራሳቸው ለመምራት አልቻሉም። መሬታቸው ተነጥቆ በተፈጥሮ ሃብታቸው ለማዘዝ አልቻሉም ወዘተ የሚሉ ትችቶች። እነዚህና ሌሎች የግፍ መለኪያዎች የሚያመለክቱት፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የፖለቲካ ስልጣን ባለቤት አለመሆኑን ነው። በሌላ አነጋገር፤ ሕዝቡ ብዙ መስዋእት የከፈለው አንዱን አምባገነን በሌላ አምባገነን ለመተካት አልነበረም። “የለውጥ ሃዋርያው” መለስ ብሄራዊ ተቋሞችንና ባህልን ከስራቸው በማይለወጥ መልክ ነቅሎ በምትኩ የመሰረተው ጎሳዊ ጥላቻና ግጭት የሚያጠናክር፤ ሙሰኛ፤ ተቋማዊ የሆነ የፖለቲካ ባህል ነው። በግለሰብ መብቶች ህጋዊ የሆነ የዲሞክራሲ ስርአት ምኞት የውሃ ሽታ ሆኗል።

በአገር ወዳድነትና በመላው ሕዝብ አፍቃሪነት ላይ ያልተመሰረተው የህወሓት "እድገታዊ መንግሥት" ዋና መርህ፤ በልማትና (Economic and Social Development) በሰብአዊ መብቶች መካከል ምንም ግንኙነት የለም የሚል ነው። "እድገታዊ መንግሥት" በሰብእነት ላይ ካልተመሰረተ የመጨረሻ አላማው ምን ይሆናል፤ የጥቂቶች ሃብታምነት። የፖለቲካ አውራ ሆኖ የሚመራ ፓርቲ "እድገታዊ ነኝ" ማለቱ አያስገርምም። ከጅምሩ በሁሉም ክፍሎች የበላይነትን ለመያዝ የተሰናዳ ድርጅት ያገኘውን ጥቅም ለመጠበቅ ከፈለገ ሰብአዊ መብቶችንና ነጻነትን ማገብ አለበት። ይኼን የሚያደርገው በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ነው። በየትም አገር ቢሆን ይህ የአገዛዝ ዘዴ አሁንም የአምባገነኖች ዋና መመሪያ ነው። ሰብአዊ መብቶችን የሚረግጡ መንግሥታት--ሰሜን ኮርያ፤ አይቮሪ ኮስት፤ ጋቦን፤ ካዛክስታን፤ ኢራን፤ ፓኪስታን፤ የተባበሩት የአረብ ኤምሬትስ፤ ቬኔዙዌላ፤ ሶሪያ፤ ቻይና ወዘተ የሚከተሉት አገዛዝ የአንድ ፓርቲ የበላይነትን የሚያንጸባርቅ ነው። የኢትዮጵያን ከአብዛኛዎቹ የሚለየው በሁሉም ዘርፍ የበላይነቱን ይዞ ህብረተሰቡን የሚያሽከረክረው አንድ ጠባብ ብሄርተኛ ቡድንና ራሱ ገብግሞ የሾማቸው ተባባሪዎች ናቸው። ቁጥራቸው የማይታወቀው፤ ግን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩት፤ ለፖለቲካና ለኢኮኖሚ ፍትህ፤ ለሰብአዊ መብቶችና ክብር፤ ለነጻነት፤ ለእኩልነት፤ የቆሙ፤ በኢትዮጵያ እስር ቤቶች የሚሰቃዩ ሁሉ የዚህ አምባገነን መንግሥት ሰለባዎች ናቸው። አንዱአለም አራጌ ምሳሌ ነው።

አንዱአለም አራጌ ከሳሾቹ "እንድጠጣው የሚፈልጉትን የግፍ ጽዋ በጸጋ ከመጠጣት ውጭ" ባልፈጸምኩት "ወንጀል፤ ማቅለያ አልጠይቅም። አልፈልግም። ለመቀበል አልገደድም" ሲል የሰጠው ምስክርነት ለሁሉም ህሊና መቀስቀሻ ይሆናል። በአሜሪካ፤ በ 2012 በተካሄደው ተመሳሳይ የሌለው የፕሬዘደንትነት ምርጫ ማግስት፤ አንድ ታዛቢ ሲጽፍ እንዲህ ብሏል። "የራምኒ ሚሊየኔር፤ ቢሊየኔር፤ ነጭ ደጋፊዎች የሳቱት አሜሪካ የነጭ አገር ብቻ አይደለችም። ጥቁሮች፤ ሂስፓኒኮች፤ ኤዥያውያን፤ ደሃዎች፤ ነጮች" የሚኖሩባት አገር ናት፡ "እነ ራምኒ፤ የሁሉም አገር መሆኗን "እረስተውታል።" ራምኒ ያሸንፋል ብለው የተዘጋጁ መራጮች ያሰቡት አሜሪካ አሁንም "የነጭ አገር ብቻ ናት" የሚል ነው። ማሸነፉ አይቀርም የሚል የተሳሳተ ግንዛቤ ነው ሲል አስተያየቱን ደምድሟል። "ድር ቢያብር አንበሳ ያስር" የሚለውን የኢትዮጵያውያን አባባል የፕሬዘደንት ኦባማ ደጋፊዎች በስራ ላይ አዋሉት። ኦባማ አሼነፈ። ታሪክን እንደገና ሰራ። ለዲሞክራሲ፤ ለግለሰብ መብት፤ለነጻነት፤ ለሰው ክብር፤ በጋራ መታገል የተቀደሰ ተግባር መሆኑን አስመሩበት። ከላይ የተጠቀሰው ታሪካዊ አባባል አንዱአለምን ከከሳሾቹ ለይቶታል። መለስ የመሰረተው ጠባብ ብሄርተኛ አገዛዝ ኢትዮጵያ የምትባል አገር ለሁሉም ሳይሆን፤ ለጥቂቶች የኢኮኖሚ ጥቅም አገልጋይ እንድትሆን አድርጓታል። እኛ የምንጋራው አንዱአለም አራጌ ያለውን ነው። መለስ "የኢትዮጵያ ባንዲራ ጨርቅ ነው። በዲሞክራሲና በእድገት ግንኙነት የለም። የተቃዋሚ ድርጅቶች፤ የማህበረሰብ ስብስቦች፤ ምሁራን ኪራይ ሰብሳቢዎች ናቸው። አማራ አውራ ጠላታችን ነው። ይህን ብሄረሰብ ማጥፋት ቀላል ነው" ያለውን አይደለም። የአንዱአለም አራጌ ዓለም የወደፊቱን ያሳያል። የመለስ የጥላቻ ርእዮት ጊዜ ያለፈበትን ያሳያል። አንዱ ብሩህ፤ ሌላው ጨለማ ነው። የመለስ አባባሎች ሁሉ የሚየመለክቱት፤ የአንድ የጠባብ ጎሳ ስብስብ ፓርቲን የበላይነት ፍጹም ለማድረግ ነው። የአንዷአለም አባባል ክፋት የለውም። የቆመው ለፍትህ፤ ለሰብአዊ መብቶች፤ ለአንድ አገር፤ ለአንድ ህብረተሰብ ነው። የመለስ አባባል ክፋት አለው። ህብረተሰቡን በብሄር ጥላቻ ከፋፍሎታል። የአንድ ብሄረሰብን የበላይነት አስምሮበታል። አገዛዙ አገናኝና ድልድይ አይደለም። አራራቂ፤ ፀረ-እርጋታ፤ ፀረ-ፍትህ ነው። በብሄር ልዩነት አመካኝቶ የሰብአዊ መብቶችን መርገጥ ለተከታታይ ትውልድ መርዝ ነው። አንዱ ጎሳ ሌላውን ከመሬቱ ውጣ ቢል አያስገርምም፤ ሆነ ተብሎ ሕጋዊ ሽፋን የተሰጠው መብት ነው።

እንደሚወራው ከሆነ፤ የመለስ ዜናዊ በነሓሴ (August 2012) ባልታሰበበት ወቅት ከዚህ አለም መለየት የህወሓትን አመራር ሽብር ሰዶበታል። የሚያሽከረክረውን በጠባብ ብሄርተኛነት የተመሰረተ ፓርቲ፤ ኢህአዴግን፤ አነጋግሮታል። እርጋታ ነስቶታል። በሹክቻ እንዲበከል፤ እርስ በእርሱ እንዲጠራጠር አድርጎታል ለማለት የሚያስችሉ ሁኔታዎች ይታያሉ። የመለስ ራእይ ዘላቂነት እንዲኖረው ማን ይተካል የሚለው ጥያቄ ገና አልተፈታም። ስልጣን ከጠባቡ የትግራይ የበላይ ቡድን እንዳይወጣ የውስጥ ትግል አይሎ ይታያል። በፈረንጆች አመት መጨረሻ (በ2012) እና ዛሬ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ትርኢት የሚያሳየው የህወሓት/ኢህአዴግን ጥንካሬ አይደለም። የአመራርና የአስተዳደር ድክመትን ነው። በአሁኑ ወቅት፤ አዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር አቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝ፤ አተኩሮ የሚሰራው፤ በብዙ አማካሪዎች ተከቦ አገርን በእርጋታ ማስተዳደር ነው። ተተኪነት በእርጋታ እንደሚካሄድ ለማስመስከር፤ መለስን መስሎ እንዲገኝ ተገድዷል። ለህብረተሰቡ የሚረዳው አስፈላጊ የሆኑ ለውጦችን መቀበል፤ (Fundamental and essential reforms)፤ የሕዝቡን የኑሮ ችግሮች መፍትሄ መሻት፤ ለሰላም፤ ለእርቅ፤ ለፍትህ፤ ለውይይት፤ ለዘላቂ ዲሞክርሳዊ ስርአት፤ ለሃገር ግዛታዊ አንድነትና ጥቅም አማራጮችን መሻት ነው። የስልጣን ሹክቻው፤ ለሃይልና ለስልጣን የሚደረገውን ግብግብ ለማቻቻል ይመስላል። መለስን መስሎ ለመታየት መሞከር የጠቅላይ ሚንስትሩን የአመራር ነጻነት አያሳይም። የሚያሳየው የስርዓቱን ድክመት ነው (fundamental flaws of the politics of ethnicity).

*በኢትዮጵያ አለመረጋጋት መኖሩ ምን “ አደጋን” ያሳያል? በዚች የእርዳታ ጥገኛ በሆነች አገር፤ ብዙ መቶ ሚሊዮን ብር ለአበል፤ ለስብሰባ፤ ለመጓጓዣ እየተከፈለ፤ በትግራይ ክልል ብቻ፤ ከመንደር ጀምሮ እስከ ክልል አስተዳደር ግምገማ የሚመስል ስብሰባ ለምን አስፈለገ? ማን፤ ማንን ፈርቶ ነው? ምንን ለማረጋገጥ፤ የስልጣን ሽሚያው ከማን ጋር ነው? መለስ ዜናዊ ያቋቋመው የማይበገር የሚመስል አብዮታዊ ዲሞክራሲ፤ የገቢና የሃብት ክምችት ለጥቂት ግለሰቦችና ቤተሰቦች ያስገኘው የቁጥጥር መዋቅር የገጠመውና ሊገጥመው የሚችል አደጋ ምንድን ነው? ዲሞክራሳዊ፤ ህሉን አቀፍና ፍትሃዊ ከሆነ ምን አስፈራው? ጠቅላይ ሚንስትር ከተሾመ፤ ስልጣኑ የት ይጀምራል፤ የት ያቆማል? ጠቅላይ ሚንስትሩ የመምራት መብት ካለው ተደራራቢ መንግሥት (የህወሓት) ለምን አስፈለገ? የኢህአዴግ የብሄር አባል ድርጅቶች የመወሰን፤ ስልጣን የመረከብ መብት አላቸው ወይንስ “ሻንጣ ተሸካሚ”፤ ታዛዥና አጎብዳጅ ሆነው ለሌላ ሃያ፤ አምሳ፤ መቶ አመታት ይቆያሉ? እነዚህን ሙሉ በሙሉ ለመመለስ አስቸጋሪ ነው። ወሳኝ የሆኑትን የፖሊሲና የመዋቅር ችግሮች ለማሳየት ይቻላል። ደጋግሞ ማሳየት የሚያስፈልገው፤ የሰብአዊ መብቶች ሙሉ በሙሉ መገፈፍ ለጥቅም፤ ለቁጥጥር ስለሆነ ነው። “በእድገትና በሰብአዊ መብቶች መካከል ምንም ግንኙነት የለም” ሲባል ዋናው ኢላማ ማንኛውንም ተቃዋሚ ለማገብ ነው። ሰብ አዊ መብቶች ከታፈኑ ማንም ግለሰብ ወይንም ቡድን ለመብቱ ለመከራከርና ለመደራደር አይችልም። ማንዴላ እንዳለው “እስረኛ ለመብቱ ለመከራከር አይችልም።” ለዚህ፤ ጸረ-ሽብርተኛነት ዋና መሳሪያ ሆኗል። የተቃወመ ሁሉ እንደ እስክንድር ነጋ፤ እንደ አንዱአለም አራጌ ወዘተ፤ ሽብርተኛ ነህ/ነሽ ተብሎ ሊታሰር ይችላል። ወይንም አገር ለቆ እንዲወጣ ይገደዳል። ከሃገርም ቢወጣ የህወሓት ፍርድ ቤት በሌለበት ሊፈርድበት ይችላል፤ በብዙ ንፁሕ ኢትዮጵያውያን ላይ ፈርዷል። በአምባገነናዊ አገዛዝ እውነት የሚባል ነገር አያዋጣም። እውነትን የሚያስተናግድ ተቀባይ ዳኛ የለም።*

*ዲሞክራሲና ነጻነት በሌለበት አገር ውሸት እንደ እውነት እንዲነገር የሚያስተጋባው የመንሥቱን ቁንጮ የያዘው አለቃ ነው። በስለላ፤ በፌደራል ፖሊስ፤ በመከላከያ፤ በፍርድ ቤት ወዘተ የበላይነት ያለው ፓርቲ። ሌላው፤ ቢፈልግም ለመናገር፤ ለመሰብሰብ፤ ለፍትህ ለመቆም አይችልም። በቅርቡ ቻይና እንደሆነው፤ ዘመናዊ መገናኛ ተጠቅሞ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ አማራጭ ሃሳቦች ለማቅረብ አይቻልም። ለመብትና ለፍትህ የቆመ፤ የአንዱአለም አራጌ እድል ይገጥመዋል። ችግሩ በመለስ ማለፍ አሁን ግልጽ ይሁን እንጅ መነሻው ቀደም ሲል ነው። የስልጣን አበጋዝ በነበረበት ወቅት፤ መለስ ያለውንና ያደረገውን በአጭሩ እንመልከት። ከአምባገነናዊ ስርአቱ ጋር ግንኙነት አለው። የመለስ “አምላኪዎች” ይህን ጸረ-ኢትዮጵያና ፀረ-ሕዝብ ባህል ሊቀጥሉት ወስነዋል።*

- *ምንጊዜም ቢሆን፤ “ህወሓት/ኢህአዴግ፤ ምርጫዎችን ማሸነፍ አለበት።”*
- *“የግለሰቦችን የአይን ቀለም ካልወደድን ለማባረር መብት አለን።”*
- *የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ “ጨርቅ ነው።” ዋጋ የለውም። እኛን አይወክልም።*
- *የኢትዮጵያ ታሪክ በምኒልክ ወረራ የመጣ “የመቶ አመታት ታሪክ ነው። ከዚህ የተለየ ታሪክ አላት የሚሉ ሁሉ ባዶ ታሪክ አቅራቢዎች ናቸው።” የፀረ-ምኒሊክ ዘመቻውን ያመቻቸው የዚህ አይነት አባባል ነው።*
- *“እነዚህ አህያ አማራዎች የማይረሱት ትምህርት መማር አለባቸው። ሰላማዊና ሃይማኖተኛ የሚሆኑት ካላሽንኮብ ሲጠመድባቸው ብቻ ነው።” የአማራ ብሄረሰብን ማስወገድና ማደኼየት ዘመቻ የተመቻቸው በዚህ አይነት አባባል ነው።*
- *“እኔ የመናዊ ነኝ። እኛ ዘራችን የመናዊ ነው። ከንጉስ ነገስቱ ውጭ፤ ኢትዮጵያውያን አረቦች ናቸው”*
- *“አንድነትና አንድ አገር የፈጠራ ወሬ ነው።” ኢትዮጵያ የባህር በሯን ያጣችው በዚህ አይነት ፍልስፍና ምክንያት ነው።*
- *“ስርቆ አለመያዝ የጉብዝና መለኪያ ነው። እውነት፤ ሃቀኛነት የሰነፍ መለኪያ ነው።” ጉቦ፤ አድልዎና ሙስና ከዚህ የአገዛዝ ፍልስፍና ጋር የተያያዘ ነው፤ መስረቅ እንደ ጉብዝና ይታያል። ለህሊና አይቀፍም።*
- *“መሬት የሚሸጥና የሚለወጥ በመቃብራችን ላይ ነው።” ቢያንስ አራት ሚሊዮን ሄክታር ለም መሬት ለውጭ ኢንቬስተሮች፤ ህንዶች፤ አረቦች፤ቻይኒሶች ወዘተ ተሸጋግሯል፤ ተሺጧል ለማለት ይቻላል።*
- *ከህወሓት ውጭ “ማንኛውም ተቃዋሚ፤ ምሁር፤ የግል ክፍል፤ ኪራይ ሰብሳቢ ነው።” ህወሓት ሌላውን ሌባ ነህ ብሎ ለፓርቲው አለቃዎች፤ ለቤተሰቦችና ለወዳጆች ታይቶ የማይታወቅ ሃብትና ገቢ አበርክቷል።*

*ታሪክ የሌለው ሕዝብ፤ ታሪክ ሊሰራ አይችልም*

የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ የሰራ ነው። ከላይ የጠቀስናቸው አባባሎች መርዝ ናቸው። ታሪክን፤ መታወቂያን፤ የሕዝብን አንድነት ወዘተ ይንዳሉ። ንደዋል። የታወቀው ጋዜጠኛና ደራሲ፤ ተመስገን ደሳለኝ፤ "የመለስ አምልኮ" በተባለው መጽሃፉ፤ ከላይ የተጠቀሱትን አባባሎች በልምድ ያያቸውን ማስረጃዎች በመተንተን ገልጿቸዋል። "የመለስ አምልኮ" በቀጥታ፤ ከእነዚህ በይፋ ከተነገሩ አባባሎች ተለይቶ ሊታይ አይችልም። እንደዚህ በአንደበት ለመናገር የሚችል ጠቅላይ ሚኒስትር፤ አምባገነንነቱን ያረጋገጠ። እንደፈለገው መርጦ ለመናገር የቆረጠ። ታሪክ እንደገና እፈጥራልሁ ብሎ የተነሳ። ተወዳዳሪ እንደሌለው የሚያምን ብቻ ነው። ዛሬ፤አገር ወዳድነት እንደ መርዝ ተፈርቶ በምትኩ ጠባብ ጎሳዊነት ተተክቷል። አደጋው፤ የተካው የፖለቲካና የአገዛዝ ባህል በውስጡ የአገሪቱን ህልውና ለጥያቄ ዳርጎታል። የህወሓት አመራር ሰብአዊ መብቶችን ለማፈንና ለመግፈፍ ፈቃድ አይጠይቅም። ታሪክን እንደገና ለመፍጥርና አዲሱን ትውልድ ብሄራዊ ታሪክ የለህም ለማለት ወደ ኋላ አይልም። ዛሬ የኢትዮጵያ አስደናቂ ታሪክ ትምህርት በአብዛኛው ክልክል ነው። ህወሓት ይህን ሁሉ ለማድረግ የቻለውና ተከታዮቹ አሁንም እንችላለን የሚሉት በጠመንጃ ትግል ያገኘነው መብታችን ነው ብለው ስለሚያምኑ ነው።

የመለስን አምልኮ የሚከተሉ ግለሰቦችንና ፓርቲውን ከሌሎች አምባገነኖች የሚለያቸው ብዙ ነው። የኢትዮጵያን አኩሪ ታሪክ ማጥፋት አንዱና አንጋፋው ነው እንላለን። ታሪክ የሌለው ህብረተሰብ በራሱ አይተማመንም። ህይወቱን ለማዳን ወደ ውጭ ማየት ይገደዳል። ጥገኛ መሆን ልምዱ ይሆናል። የታሪክ ተመራማሪዎች የሚያስተምሩን፤ ኢትዮጵያ ከሶስት ሽህ አምስት መቶ አመታት በላይ ታሪክ አላት። የሰዎች ፍጥረት ማእከል ነች። ለመጀመሪያ ጊዜ በአገርና በመንግሥት ደረጃ የክርስቲያን ኃይማኖት የተቀበለችና የተከተለች ነች። ልዩ ልዩ ሃይማኖቶችንና ህዝቦችን ያስተናገደች ነች። ራሷን በሕዝቧ አንድነት ጠብቃ የቆየች ነች። የራሱ የተፃፈ ቋንቋ፤ የትምኅርት ስርዓት ያላት አገር ናት። የጥቁር ሕዝቦች ሁሉ መኩሪያ ነች። ሕዝቧን ከሌሎች የሚለዩ ብዙ ጥሪቶች ያሏት አገር ነች። የዓባይ ወንዝ እናት ናት።

የአክሱም፤ የላሊበላ፤ የጎንደር፤ የሃረርና የሌሎች ታሪክ የመላው የኢትዮጵያ ስብጥር (Diverse) ሕዝብ ታሪክ ነው። የመቶ አመታት ታሪክ በማለት፤ የህወሓት/ኢህአዴግ መስራቾች የካዱት የራሳቸውን ታሪክ ጭምር ነው። ኢትዮጵያውያን አረብ አይደሉም። ጥቁርና አፍሪካዊ ናቸው። አረቦች ወደ አፍሪካ የመጡት ኢትዮጵያውያን ግብጽ ከሄዱ በኋላ ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ ከግብጽ በፊት የተጀመረ ነው። የህወሓት መስራቾችና መሪዎች የራሳቸውን ታሪክ ክደው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፈለጋቸውን እንዲከተሉ አስገድደውታል። ፈረንጆችና አረቦች የዶሉቱትን አስፈጻሚ ሆነዋል ለማለት የሚያስደፍሩ ብዙ ምሳሌዎች አሉ፤ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን ጥቁር አፍሪካውያንን ያስቆጡ። ወጣቱ ትውልድ ታሪክ የለህም ሲባል፤ማንነትህ አጠራጣሪና አከራካሪ ነው ማለት ነው። ታሪኩንና ማንነቱን የማያውቅ ትውልድ ወደ የትና ከማንጋር መሄድ እንዳለበት ለማወቅ ይቸገራል። እንደ ከብት ሊነዳ ይችላል፤ በሄደበት ይለምዳል፤ አገሩንና ባህሉን ይረሳል። ታሪክ ያለው ሕዝብ ከብት አይደለም፤ የትም ቢኖር መነሻውንና መድረሻውን ያውቃል።

ብሄራዊ ታሪክና ባህል ለልማት ቁልፍ ናቸው

<u>ማንነቱንና የቆየ ታሪኩን የተካደ ሕዝብ ለወደፊቱ ለማሰብ ያስቸግረዋል።</u> የህወሓት መስራቾች የኢትዮጵያን ተከታታይነትና የሕዝቧን አመሰራረት ሂደት አይቀበሉም፤ እንዲያውም ከመሰረቱ አፈራርሰው በአዲስ መልክ በመተካት ላይ ናቸው። ተከታታይነት የሌለው አገርና ህብረተሰብ የሚያያዙትን እሴቶች ከስራቸው ከመነጠረ ወደ አደጋ ያመራል። ግብጾች፤ ቻይናዎች፤ ግሪኮች፤ ጣሊያኖች፤ አሜሪካኖች፤ ጃፓኖች፤ ኮሪያኖች ወዘተ ከሚታወቁበት አንዱ፤ የውጣ ውረድ ታሪካቸውን እንደ ጥሪት መቀበልና ማስታወስ ነው። ተከታታይነትን ተቀብለው የገጠሟቸውን መሰናክሎች በጋራ ለመፍታት ይሞክራሉ። ጉዞው ቀላል አይደለም። ብዙ መስዋእት ይጠይቃል። ግብጾች፤ ለታሪካቸው ቀናተኞች ናቸው። ኢትዮጵያውያንም እንደነሱ ነበሩ። የህወሓት ፈጣሪዎች ይህን አይቀበሉም። የማንኛውም ሃገር ታሪክ፤ የጦርነት ታሪክ ነው። ያለ ውጣ ውረድ፤ ያለ ጦርነት የተፈጠረ አገር የለም። ቻይና ለብዙ ሺህ አመታት ሰላም ያልነበራት፤ ሞንጎሎች፤ ጃፓኒሶች፤ ራሺያኖች፤ እንግሊዞች ወዘተ፤ የወረሯት፤ ያደከሟት፤ የገዟት አገር ነበረች። አሜሪካ፤ ጥቁሮችን በባርነት የገዛችና ፕሬዘደንት ሊንከን ከራሷ የማያኮራ ታሪክ ነጻ ያወጣት። ህንዶችን ያጠፋች። ጥቁሮችን እንደ ሸቀጥ የሸመተች። ከብዙ አገሮች ጋር የተዋጋች አገር ናት። አሜሪካኖች፤ የደረሰውን ግድያ፤ ጥፋት፤ እንደ ተፈጠሮ ሂደት ያዩታል። ወደ ኋላ ሄደው "ጸጉር አይፈልጡም።" የአባይን ወንዝ ተካፋይና በአባይ ዋና ተጠቃሚ ሆና የቆየችው ግብጽ፤ ለግብጽ ታሪክ እውቅና አስተዋጾ ያደረጉትን መሪወቿን አልኮነነችም። እንዲያውም፤ ፈርኦኖችን ሆነ ናስርን፤ ወይንም ሳዳትን እንደ ጀግኖቻቸው ተቀብለው የሃገራቸውን ግዛታዊ አንድነት፤ የሚለያቸውን ታሪክና ባህል ለጥቅማቸው አውለውት እናያለን። ታሪክና ባህል የኢኮኖሚ ጥቅም አለው። የመከበርና የእውቅና ጥቅም አለው። ግብጾች ይህን በደንብ ያውቃሉ። የገዢው ፓርቲ አለቃዎች አዲሱ ትውልድ ታሪኩንና ባህሉን እንዳያውቅ አስገድደውታል። ወደ ጎሳው፤ ወደ መንደሩ እንዲያመራ አስገድደውታል። የገዢውን ፓርቲ የታሪክና የባህል ናዳ አንቀበልም የማለቱ ሃላፊነት የሚጠበቀው

ከኢትዮጵውያን ምሁር ነው። አዲሱ ትውልድ በቋንቋና በጎሳ የተመሰረተ አዲስ ማንነት እንዲቀበል እየተገደደ ነው። በየቀኑ የሚያልፈው አገር ወዳድ ትውልድ የማስተማር ሃላፊነት አለበት። ካለፈ በኋላ ትቶት የሚሄደው ጥሪት ምን መሆን አለበት ብሎ የሚጠይቅበት ወቅት ነገ ሳይሆን ዛሬ ነው። ኢትዮጵያ እየጠፋች መሆኑን ተረድተን ይህች ታሪካዊ አገር አትጠፋም፤ እንድትጠፋ አንፈቅድም ብለን የመነሳቱ ኃላፊነት የህወሓት/ኢህአዴግ አይደለም። ሃላፊነቱ የእኛ ነው።

የኢትዮጵያን ታሪክ እንዳያውቅና እንዲጠላ የተገደደ ትውልድ ያሳየው የማንነት ጦርነት እንደታወጀበት ነው። ግብጾች፤ ናይል የእኛ ነው ይላሉ። መንግስታቸው ድጋፍ ሲጠይቅ የግብጽ ሕዝብ በሙሉ በአንድ ላይ ይሰለፋል። ከሌሎች ሃገሮች የበለጠ የሚያኮራ ታሪክ ያለውን የኢትዮጵያን ሕዝብ፤ የሻቢያና የህወሓት ፈጣሪዎች ለምን ታሪኩን ሊክዱት ፈለጉ ብሎ መጠየቅ ያለበት እውቀትና ልምድ ያለው የኢትዮጵያ ምሁር ነው። ካለፈ ታሪክ ከቡርነት ባሻገር፤ ለታሪክ፤ ለባህል፤ ለማንነት ቆርጦ አለመነሳት የታሪክ ተጠያቂ እንደሚያደርግ አንጠራጠርም። ራስን "ዘላለማዊ ነኝ" ብሎ አገርና ህብረተሰብ ሲጠፋ ቆሞ ወይንም ችላ ብሎ ማየት የህሊና ፀፀት ማምጣቱ አይቀርም። ከዚህ ባሻገር፤ የምሁራን ክፍል ፍርሃት ያሳያል። ህወሓት የሚፈልገው ይህን ነው። ብዙ ኢትዮጵያውያን ተመልካቾች፤ በተለይ ምሁራን፤ የህወሓትን ፀረ-ኢትዮጵያዊነት እያዩ ወጣቶች ይከራከሩበት ይላሉ። የነገዋን ኢትዮጵያ እድል የሚወስኑት ወጣቶች መሆናቸው አያከራክርም። ሆኖም፤ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ከአምሳ በመቶ በላይ የሆነው ወጣት ትውልድ--ማለትም፤ ከደርግ ስልጣን ጀምሮ የተወለደውና ከህሓት ዘመን በኋላ ተወልዶ ቁጥሩ ከአርባ አመስት ሚሊዮን በላይ የሚገመተው--ኢትዮጵያን ፍጹም በሆነ ደረጃ እንዳያውቃት ተገዷል። "አንት ትግሬ፤ አማራ፤ ኦሮሞ፤ አፏከ፤ ሶማሌ፤ ጉራጌ" ወዘተ ነህ። ይኼን እውቅና አድርግ፤ ኢትዮጵያዊነት አያዋጣህም እየተባለ ነው። ስለዚህ፤ የእኛ ትውልድ እውቀቱን፤ ልምዱን፤ ባህሉን ለተተኪው ትውልድ ማስተላለፍ ብሄራዊ ግዴታው ነው። የኢትዮጵያን ታሪክ ስናስብ፤ ምሁራን፤ ባለፉት ሶስት ሺህ አምስት መቶ አመታት ስሟ የታወቀ ሃገር ማን አንደ ቋሚ ሃውልት አነጻት የሚል ጥያቄ መጠየቅ አለበት። የአክሱምን ሃውልት አንድ ሰው አልሰራውም። አንድ ጎሳ፤ አንድ ንጉሥ ብቻውን አላነጸውም። የግብጾችን ፒራሚድ፤ አንድ ፈርኦን፤ አንድ ግብጻዊ አላነጸውም። ከአንድ ሺህ ሁለት መቶ አመታት በላይ የቆዩትን የጃፓን የጸሎት ቤቶች (Temples of Worship)፤ አንድ አጼ፤ አንድ ጃፓኒስ አልሰራቸውም ወዘተ። አንድን ሃገር የሚገነባው ቆራጥ የሆነ፤ እራሱን ያወቀ፤ ክብሩን ለማስጠበቅ የቆረጠ፤ ተከታታይ ትውልድ ነው። ይህ ትውልድ ማንነቱን ካላወቀ አገሩንና ህብረተሰቡን ዘመናዊ ለማድረግ አይችልም። ቢበዛ የሚረዳው ራሱን፤ ቤተሰቡንና ጎሳውን ነው። ራሱ በሰራው ይወድቃል። ስደተኛ ይሆናል። መሰደድንም ብንቀበል የመንፈስ ስደተኞች መሆን የለብንም። ራሳችን እንደ ከብት አንቁጠር።

ኢትዮጵያ ሆነ ግብጽ፤ ጃፓን ሆነ ኮሪያ፤ አገርን ለመገንባት ተከታታይ አመራር፤ አገር ወዳድ መሪ ያስፈልጋል። መሪዎች ባይኖሩ የአክሱም ሃውልት፤ የላሊበላ ቤተ ክርስትያኖች፤ ሊገነቡ አይችልም ነበር። የመሪው፤ ወይንም ጀግናው ዋና ሚና ሃገሩን ወይንም ህንጻውን ብቻውን መስራቱ አይደለም። ዋናው ሚና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን መሰብሰብ፤ ማገናኘት፤ ለአንድ አላማ መምራት ነው። አመራር ማለት ይኼው ነው። አላማውን ከግብ ማድረስ ነው። የኢትዮጵያ ነገሥታት ያደረጉት ከዚህ አይለይም። ኦሮሞው፤ ሃረሬው፤ ወላይታው፤ አገዌው፤ ጎንደሬው፤ ጉራጌው፤ አፋሩ፤ አማራው ወዘተ፤ በአንድ ላይ ቆሞ ሃገሩን ከጠላት እንዲቋቋም ነው ያደረጉት። ሰላም ሲሆን፤ ለተከታታይ ትውልድ ማስታወሻ ህንጻዎች፤ የጸሎት ቤቶች፤ ግድቦች፤ ሃውልቶች ይሰራሉ። እነዚህ የሃገርን እውቅና መሰረቶች ይጥላሉ። ለዚህ ወይንም ለዚያ ጎሳ ማስታወሻ ብለው አይደለም። ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ማስታወሻ ብለው ነው። እንደዚህ ያለን፤ ብዙ ህይወትና ብዙ ንብረት የጠፋበትን ታሪክ ማፍረስ ቀላል ነው። ሆኖም፤ የሚከፈለው ዋጋ ሊታሰብ አይቻልም (Incalculatable Costs)። ታሪክን የሚበርዙና የሚያጠፉ የማያስቡት ይህን የዋጋ ክፍያ ነው። የሚመለከቱት የጊዜ ስልጣንና ጥቅምን ብቻ ነው። አክሱምን፤ ፋሲለደስን፤ ላሊበላን ወዘተ መገንባት ቀላል አልነበረም። ማፍረስ ግን በጣም ቀላል ነው። ኢትዮጵያን ለመገንባትና እውቅና ለማስገኘት የተከፈለው ዋጋ ማንም ሊያስበውና በዶላር ሊተምነው አይችልም። ሃገር መገንባትና ዘላቂነት እንዲኖረው ማድረግ ከዋጋ፤ ከሃብት፤ ከገዘብ፤ ከሰው ህይወት በላይ ነው። ይህን ተተኪ የማይገኝለት ጥሪት ማስተማር ያለበት የተማረው ክፍል ነው። ስራው ለነገ አይቆይም። ገዢው ፓርቲ የናደው የማይተካውን ነው።

ኢትዮጵያን የገነቧት መሪዎች ከሁሉ በላይ ሃገር ወዳድ ነበሩ። ለወንዞች፤ ለጅረቶች፤ ለተራራዎች፤ ለለም መሬቶች፤ ለሃውልቶች፤ ለልዩ ልዩ ባህሎች፤ ለህብረተሰባቸው ቀና ነበሩ። ህብረተሰቡን ሰብስበው አገራቸውን ከአደጋ ጠብቀዋታል። ጎሳ፤ ሃይማኖት፤ ጾታና እድሜ ሳይለዩ ሲሰበስቡና ሲመሩ ዋናው አላማቸው፤ ኢትዮጵያን ማዳን ነበር። ለእነሱ ኢትዮጵያን ማዳን ሕዝቡን ከውርደት፤ ከባርነት ማዳን ማለት ነው። አገሩን የሚወድ መሪ፤ ሕዝቡንም ይወዳል። ሕዝቡ ባይወደውና ባያከብረው ተከታይ አይኖረውም። የኢትዮጵያ አገር ወዳድ መሪዎችና ጀግኖች፤ ኢትዮጵያን

ከውጭ ጠላት ሲከላከሉ ለራሳቸው፤ ወይንም ለቤተሰባቸው ጥቅም ብለው አይደለም። ለታሪክ፤ ለኢትዮጵያ፤ ለሕዝቧ ክብርና ዘላቂነት፤ ለቤተሰባቸው፤ ለባህላቸው፤ ለኃይማኖታቸው፤ ለመሬታቸው፤ ለጓሯቸው ብለው ነው። የአሁኑና ተከታታይ ትውልድ ማጤን ያለበት፤ ይህ በሰው ህይወት ዋጋ የተከፈለበት እውቅናና ታሪክ እየፈራረሰ መሆኑን ነው። ናዳው የመጣው ከአገር ወዳድ ስራ ሳይሆን አገርን ከሚጠላ አመራር መሆኑን መረዳት የወቅቱ ዋና አርእስት ሆኗል። ታሪክ የሚያስተምረን፤ እንዳሁኑ የዓለምና የአፍሪካ ሁኔታ ከመለወጡ በፊት-- ቻይና፤ ብራዚል፤ ህንድና ሩሲያ የምእራብ የበላይነት ተወዳዳሪ ከመሆናቸው በፊት-- በየተኛውም የሶስተኛ ዓለም ክፍል ወሳኞች የምእራብ አገሮች ነበሩ። ግብጽ፤ ለዚህ የበላይነት ዋጋ ከፍላለች። ጥገኛ ነበረች። ናስርና ጓደኞቹ ይህን የግብጽ የበታችነት ታሪክ ለውጠውታል። ይህን ያደረጉት ግብጽነታቸውን ይዘውና ዋና መመሪያ አድርገው ነው። ለማሳሰብ የምንፈልገው፤ ከናስር በፊት፤ ለዓለም የጥቁር ሕዝቦች፤ በተለይ፤ በቅኝ ገዥዎች ከብራቸው ለተገፈፈ አፍሪካውያን አርአያ የነበረች ኢትዮጵያ ናት። ናስር አሁን ሲሲ እንዳደረገው ኢትዮጵያ ሲጎበኝ ከኢትዮጵያ የሚፈልገው ነገር ስለነበር ነው፤ የዓባይን ውሃ አስተማማኝነት። ግብጽ የምትመካው ከዓባይ በሚመጣ የኢትዮጵያ ለም አፈር ነው። ይህን ከኢትዮጵያ የሚመጣ ውሃና አፈር ተጠቅማ፤ ግብጽ፤ ለአምስት ሺህ አመታት ተከታታይ ስልጣኔ ፈጠረች ተብሎ ይነገርላታል። አክሱምን፤ ፋሲለደሰን፤ ላሊበላን፤ ሓረርን ወዘተ የፈጠረችው ኢትዮጵያ ተመሳሳይ ክብርና እውቅና አላገኘችም። አረቦችና ፈረንጆች የኢትዮጵያን ታሪክና አስተዋፆ አልተቀበሉም። የውስጥም ችግር ነበር።

አንዱ ዋና ምክንያት፤ ነገሥታቱ ሃገር ወዳድ በመሆናቸውና ለፈረንጅ አንታዘዝም በማለታቸው ነው። ሌላው፤ ኢትዮጵያ የጥቁር ህብረተሰብ አገር በመሆኗ ነው። ሶስተኛውና ዋናው፤ ለብዙ ሺህ አመታት፤ ነጻነቷንና ክብሯን የጠበቀች አገር በመሆኗ ነው። የግብጽ ታሪክ እንደ ተከታታይ ታሪክ ይነገራል። “An early civilization was born and has continued without interruption for over five thousand years.” ግብጽ፤ ይህን ተከታታይ ታሪክ ለመቀዳጀት የቻለችው በሯሷ ወንዝ፤ በራሷ አፈር አይደለም። በኢትዮጵያ ነው። አባይ ከሌለ፤ ግብጽ አትኖርም። ከጥቂቶች በስተቀር፤ ፈረንጆች፤ ጥቁር አፍሪካውያን፤ ኢትዮጵያን ጨምሮ፤ እንደዚህ ያለ ታሪክ ይሰራሉ ብለው አስበው፤ ጽፈው አያውቁም። ኢትዮጵያውያን ግን ማንነታቸውን አውቀው ቆይተዋል። ታሪካቸውን መዝግበዋል። ለዚህ አስተዋጽኦ ያደረጉት መሪዎች፤ ጀግኖች፤ የልዩ ልዩ ሃይማኖት ተከታዮች፤ ገበሬዎች፤ እናቶች፤ አባቶች፤ ደራሲዎች ከሁሉም ጎሳዎች የተውጣጡ አገር ወዳዶች ስለነበሩ፤ አሁንም ስላሉ ነው። ይህን ህወሓትና ሌሎች ጠባብ ጎሰኞች ሆነ ብለው ሊያጠፉት የወሰኑት ታሪክ ለአዲሱ ትውልድ ማስተማር የምሁሩ ሃላፊነት ነው።

ልማት ተከታታይ ነው

የተከታታይነት ሂደት በአገርና በሕብረተሰብ አመሰራረት ውጣ ውረድ ብቻ አይንፀባረቅም። በእደገትና በልማትም ያለው ሄደት የድሮውን አፈራርሶ በአዲስ መተካት የሚል አይደለም። የአክሱም ሃውልት አፍርሶ መተካት ታሪካዊ ጥቅሙን ይቀንሰዋል። እንደ ዛሬው ሳይሆን፤ የኢትዮጵያን ታላቅነት፤ የኢትዮጵያውያንን በዓለም ህብረተሰብ መከበር ለማወቅ፤ አንባቢውን ወደኋላ ለመውሰድ እንገደዳለን። በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የተወለድን ወይንም ያደግንና ተጠቃሚና ተማሪ የነበርን፤ አሁን ቁጥራችን እየቀነሰ የሄደው የአይን ምስክር ነን። የአይን ምስክርነት በቂ አይደለም። አንድ ተከታታይ ትውልድ ሊያስታውሰው የሚችል ነገር መስራት ቁልፍ ነው። የኔ ትውልድ ምንም እንኳን ድክመቶች ቢኖሩትም ለሃገሩና ለሕብረተሰቡ ፍትህ፤ ሙብትና ዲሞክሳዊ አገዛዝ ከራሱ ጥቅም በላይ ታግሎ መስዋእት ሆኗል። ለህብረተሰቡ የማይናቁ እሴቶችን አስተላልፏል። ችግሮችንም እንደዚሁ። የህወሓት መስራቾች የዚህ ዘመነ መንግስት ተጠቃሚዎች ናቸው። የትምኅርት እድል አግኝተውበታል። ሆኖም፤ ኢትዮጵያ የነበራትን እውቅና እንደሌለ አድርገው ከደውታል። ደሃና ኋላ ቀር በሆነች አገር፤ የአገር ወዳድ አመራርን ጥቅምና የሚያስገኘውን ክብር አይተናል የምንልበት ምክንያቶች አሉ።

1. ከማንም የአፍሪካ አገሮች የበለጠ በነጻነቷ ኩሩ የነበረች፤ ለሌሎች የአፍሪካ ሃገሮች ነጻነት የታገለች ኢትዮጵያ ናት። በዓለም እውቅና ከነበራቸው መሪዎች አንጋፋ የነበሩት አጼ ኃይለ ሥላሴ ናቸው፤ የአድዋን ድል ስኬታማ ያደረጉት ታላቅ ጥቁር መሪ አፄ ምኒሊክ ናቸው።

2. ኢትዮጵያ፤ በደቡብ ኮርያና በኮንጎ፤ በተባበሩት መንግሥታት አማካኝነት፤ የጦር አስተዋጽኦ አድርጋ የዜጎቿን ጀግንነት፤ ታዋቂነትና ዝና ያተረፈች አገር ናት። በጦሩ የተሳተፉት የዚህ፤ የዚያ ጎሳ አባላት አልነበሩም። ኢትዮጵያውያን ተብለው የሚጠሩ ጀግኖች ናቸው። የኮሪያና የኮንጎ ሕዝብ ውለታቸውን አልረሳውም። የኢትዮጵያን ስም አሁንም ያስታውሳል።

3. ኢትዮጵያውያን ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጭ ሲላኩ ዲፕሎማቸውን ሳይዙ ሃገራቸውን ለማገልገል፤ ወደ ሃገራቸው ይመለሱ ነበር። ደራሲውም አድርጎታል። ወደ አገሩ የሚመለሰው አማራ፤ ትግሪ፤ ኦሮሞ፤ ወላይታ ወዘተ ስለነበረ አይደለም። ኢትዮጵያዊ ስለነበረ። አገሩን ስለሚወድና ለማልማት ስለመረጠ ነበር። ህወሓት ይህን የተቀደሰ እሴት አጥፍቶታል። ዛሬ ወጣቱን ትውልድ ለስደት ዳርጎታል።

4. ኢትዮጵያ፤ በዲፕሎማሲ ብቻ ሳይሆን፤ በስፖርትም እውቅና ነበራት። ጃፓንን ወይንም ሜክሲኮን የጎበኘ ግለሰብ እንደሚያውቀው፤ አበበ ቢቂላን የማያስታውስ የለም። የሚታወቀው ማራቶን አሸናፊው ኢትዮጵያዊ፤ "በእግሩ የሮጠ ደፋር" በሚል ነው። ያስታወቀው የራሱን ጎሳ አልነበረም። ያስከበረው ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ሕዝብ በሙሉ ነበር።

5. በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ኢትዮጵያ ብዙ የተማረ ሰው አልነበራትም። ቁጥራቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ የጨመረ፤ ጥራት ያላቸው፤ በዓለም እውቅና የነበራቸው ብዙ ነበሩ። ከእነ ኮፊ አናን ጋር ተወዳዳሪ የሆኑ። በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን በዓለም ተቀባይነትና ብቁነት የነበራቸው። ይህን እውቅናና ዓለም አቀፋዊ ሚና ኢትዮጵያ ያጣችው በደርግ ጭካኔና በህወሓት/ኢህአዴግ ግፍና ጠባብ ብሄርተኛነት ነው። ዛሬ፤ ኢትዮጵያ እንደ ኮፊ አናን በዓለም የታወቁ መሪዎች የሏትም። ህወሓት፤ የነበሩትንና አሁንም በህይወት ያሉትን ስማቸው እንዲጠፋ፤ ስራቸው እንዲበረዝና እንዲሰረዝ እያደረገ ነው። እነዚህ ሲጠፉ የኢትዮጵያም ታሪክ አብሮ እንደሚጠፋ በማሰብ ሆን ተብሎ የሚደረግ ፀረ-ኢትዮጵያዊነት ነው። ታሪክ ዋጋ አለው።

6. በደቡብ አፍሪካ፤ በካሪቢያን፤ በተለይ በጃሜይካ፤ በሃርለም፤ የኢትዮጵያ ታሪክ ከፍተኛ እውቅናና ክብር ነበረው። ለታሪኳ፤ ለሃይማኖቷ፤ ለባህሏ፤ ለጀግናውና ኩሩ ሕዝቧ ጠበቃዎች አፍርታ ነበር። ጃሜይካን ያየ የሚታዘበው፤ ከኢትዮጵያ ምሁራን የበለጠ ለኢትዮጵያ ማንነት፤ ለኢትዮጵያዊነት  ተቆርቋሪ ጃማይካውያን አሉ። የኢትዮጵያን ሕዝብ ከፍ አድርገው፤ የኢትዮጵያን ታሪክ ለጥቁር ሕዝቦች ሁሉ አኩሪ ነው ብለው ያስተጋቡ የነበሩ ጃማይካውያን አሉ። ድርጊታቸው የጎሳ፤ የሃይማኖት ልዩነቶችን በማሰብ አይደለም። የኢትዮጵያውያንን ኩሩነት፤ ጀግንነት፤ ደፋርነት፤ ባህላዊነት፤ ጨዋነት ተገንዝበው ነው። ኩሩነት ስንል፤ "እኔ ከማንም አላንስም" ባይነት ማለታችን ነው። በማንነት/ኢትዮጵያዊነት ማመን ማለታችን ነው።

እነዚህ ጥቂት ምሳሌዎች የቀረቡት፤ የኢትዮጵያውያን መታወቂያዎች መሆናቸውን አሳይቶ የታሪክ ክለሳ ለሰብአዊ መብቶች መከበርና ለፍትሃዊ እድገት ምን ያህል አደገኛ መሆኑን ለማመልከት ነው። አደገኛ የምንለው ነገር ለማጋነን አይደለም። ማንነቱንና ሰብአዊ መብቶቹን ያጣ ህብረተሰብ በራሱ ተማምኖና ኮርቶ አገሩን ሊጠብቅና ሊጋራ የተሻሻለ ኑሮ፤ በጋራ ሊገነባ እንደማይችል ለማመልከት ነው። አንባቢውን የምንጠይቀው፤ ግብጽ የኢትዮጵያን ውሃና ህይወት ለዋጭ የሆነ አፈር ተጠቅማ የሰኳር አገዳ፤ ሙዝ፤ ቅጠላ ቅጠል፤ ጥጥ ለማፍራት፤ ራሷን ያስቻለ የኢንዱስትሪ ልማት ለመገንባትና ሕዝቧን ለመመገብ ከቻለች፤ ኢትዮጵያ ለምን ተመሳሳይ እድገት አላደረገችም የሚል ጥያቄ ለመመለስ ስለፈለግን ነው። የግብጽ መሪዎች የናይልን (ዓባይን) ጥቅም ስላወቁ፤ ኢትዮጵያን ከውስጥ ማድከም ዋና የውጭ ጉዳይ መሳሪያቸው አድርገው ተጠቅመውበታል። ኤርትራን ከእናት አገሯ ለማስገንጠል ያላደረጉት ነገር የለም። "ቀይ ባህር አረብ እንጂ አፍሪካዊ አይደለም" በሚል መመሪያ። ናይል ከሌለ፤ ግብጽ አትኖርም የሚለውን መመሪያ የግብጽ ህጻን ከልጅነቱ ያውቃል፡፡ ሻቢያና ህወሓት፤ የኢትዮጵያ ህጻንና ጎልማሳ ታሪኩን አውቆ፤ ለአገሩ እንዲቆም አላደረጉም። ያደረጉት ተጻራሪውን ነው።  የኢትዮጵያ ታሪክ የመቶ አመታት ታሪክ የሚል ። መለስ ዜናዊ በይፋ እንደ መመሪያ አድርጎ፤ የኢትዮጵያ ታሪክ "አጼ ምኒልክ የፈጠሩት፤ የወረራ ታሪክ ነው። አማራው ምኒልክ ቅኝ ገዥ ነበር" ብሎ ሲናገር፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ እንደ ግብጽ፤ ተከታታይ የሆነ፤ የሚያኮራ ታሪክ የለውም ማለቱ ነው። ይህ አባባል፤ "ራስን የመግደል። ራስን የመበደል። ታሪክን እንዳልነበረ በይፋ ለጠላቶች መሳሪያ ማስረከብ" የሚል ፀረ-ኢትዮጵያ አስተሳሰብ ነው። አረቦች፤ በተለይ ግብጾች ይኼን ድክመት ለራሳቸው ጥቅም አውለውታል፤ ሲሲ ኢትዮጵያን መጉብኘቱ አደጋውን አያስወግደውም።

ግብጾች በኢትዮጵያ ላይ፤ ኢትዮጵያውያንን በመጠቀም ያደረጉት፤ ለቅኝ ገዥዎች ዋና መሳሪያ ሆኗል። የእንግሊዝ መንግስት በኢትዮጵያ ላይ ያደረገው በደል የመጣው ግብጽን፤ ሱዳንና ተገንጣይ ሃይሎችን በመጠቀም ነው። አጼ ምኒልክ፤ ኢትዮጵያ ለቅኝ ገዥዎች አትንበረከክም ብለው ለሃገራዊ ነጻነትና አንድነት ዘመቻ ሕዝቡን ሲያስነሱና የአድዋን ድል ሲጎናጸፉ የተገኘው ድል ለመላው ኢትዮጵያና ለመላው የጥቁር ሕዝብ ያኮራል በማለት ፋንታ ምኒልክ ጠላት ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ የመቶ አመታት ታሪክ ነው ብለዋል። አጼ ምኒሊክን በጠላትነት የሚበይን ኃውልት መሰራቱ አግባብ አለው የሚሉ አዲስ ከፋፋይ፤ ጥላቻችን እንደ እውቀት የሚሰብኩ ኃይሎች ተነስተዋል፤ በጀርባቸው ግፉበት የሚሉ የዓረብ አገሮች እንዳሉ አያከራክርም። ቀደም ሲል የሻቢያና የህወሓት አለቃዎች ይህን ሲያደርጉ፤ የጠባብ ጎሰኛ ፖለቲካ መሪዎች ለውጭ ሃይሎች መሳሪያ ሆኑ ማለት ነው። እነዚህ ጠባብ ጎሰኞች በአጼ ምኒልክ ጊዜ ቢኖሩ፤

የኢትዮጵያን ዓርበኞች ከጀርባ ሆነው ይወጉ ነበር። ለኦሮሞ፤ ለአማራ፤ ለትግራይ፤ ለጉራጌ፤ ለሱሉልታ፤ ለደቡብ ወዘተ አርበኞች ዋጋ አልሰጡም ማለት ነው። ፍሽስት ኢትዮጵያን ሲወጋ፤ የውስጥ "ባንዳዎች" ለጣሊያኖች ስለላ ያደርጉ እንደነበር ብዙ ታዛቢዎች ጽፈዋል። ዛሬም ይኼ የተለመደ የውስጥ አርበኝነት ቀጥሏል።

ብሄራዊ እንድነት፤ የግል መብትና ፍትሃዊ እድገት ግንኙነት አላቸው

በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ኢትዮጵያውያን የነበራቸው ክብር ባለፉት ሰላሳ ስምንት፤ በተለይ ባለፉት ሃያ ሶስት አመታት ጠፍቷል። የአጼ ምኒልክን ታሪክ መበረዝ የተጀመረው ሆን ተብሎ የኢትዮጵያውያንን ክብርና ማንንነት ለማጥፋት ነው። ታሪክን እንደ ገና በአዲስ ለመጻፍ ነው። አጼ ምኒልክ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያደረጉት ታሪካዊ አስተውጽኦ በብዙ ቢሊዮን ዶላር ሊገዛ አይችልም። <u>ነጻነትና ክብር ነው።</u> የግብጾች ታሪክ የሚያስተምረን፤ ታላቁ ግሪካዊ አሌክሳንደር ግብጽን ከወረራት በኋላ፤ ሞሃመድ አሊ የተባለ መሪ ግብጽን አስተባብሮ አንድ አገር ማድረጉ። የዘመናዊ እድገት መሰረት መጣሉ። የናይልን ወንዝ ተጠቅሞ ዘመናዊ የእርሻ ልማት ማስፋፋቱ ወዘተ ናቸው። ይኼን ሲያደርግ፤ የዓባይን ወንዝና ሸለቆ ለግብፅ ጥቅም ለማዋል ኢትዮጵያን ወግቷል። ሆኖም፤ ኢትዮጵያውያን ስለተባበሩ ተሸንፏል። የቻይናው ማኦ ሲቱንግ ከኮሙኒስትነቱ በላይ ያየው፤ ቻይናን ታላቅ አድርጎ ከጥገኛነትና ከውጭ ቁጥጥር ነጻ ማውጣቱ ነበር። የአሜሪካው ጆርጅ ዋሽንግቶን ያደረገውም ተመሳሳይ ነው። በእነዚህ አገሮች የታሪክ ሂደት ብዙ ሚሊዮን ሕዝብ አልቋል። ታሪክ የሚያስታውሰው፤ ማለቁን ሳይሆን የእነዚህን አገሮች ለነጻነትና ለክብር ያደረሷቸውን መሪዎች ታላቅነት ነው። እነዚህ መሪዎች፤ ሃውልት ተሰርቶላቸዋል። ሃውልታቸው የነጻነትና የክብር ምልክቶቻቸው ናቸው። አጼ ምኒልክ ያደረጉትም ተመሳሳይ ነው። የኢትዮጵያ ብሄራዊ ነጻነት የዘመናዊነት መስፈርት ነው። ታግሎ አገርን ከቅኝ ገዥዎች ወረራ ማዳን የዘመናዊነት መስፈርት ነው። የአጼ ምኒልክ አስተዋጽኦ ከሌሎች መሪዎች ከፍ የሚልበት ምክንያት አለ። የሻቢያ፤ የህወሓትና ሌሎች ጠባብ ጎሰኛ የፖለቲካ መሪዎች የማይቀበሉት--የጥቁር ሕዝቦች ታሪክ መታደሱን ነው። ኢትዮጵያ፤ ብቸኛ የነበረች የነጻነትና የክብር ደሴት ሆና ቆይታለች። የውስጥ ችግር አልነበረም። በደል አልነበረም። ግፍ አልነበረም ማለት አይደለም። ሆኖም፤ ኢትዮጵያን ከሌሎች በቅኝ ከሚተዳደሩ አገሮች የለያት መታወቂያ፤ ህብረተሰቧ በአንድነት ነጻነቷንና ክብሯን መጠበቁ ነው። ሕዝብ ለማንቀሳቀስና ጠላትን ለማጥቃት፤ መሪ ያስፈልጋል። መሪው አማራ፤ ኦሮሞ፤ ትግሬ፤ ጉራጌ፤ ቅይጥ ወዘተ ሊሆን ይችላል። ብቻውን ተዋግቶ ድል አያገኝም። ህብረተሰቡን ሰብስቦ፤ ባለው መሳሪያ ተጠቅሞ፤ ለአላማው ሲታገል ነው። በተመሳሳይ፤ የልማት ዘላቂነት ስኬታማ ሊሆን የሚችለው ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሳተፉበትና ኑሯቸውን የሚያሻሽሉበት የኢኮኖሚ አመራር ሲኖር ነው።

በሌላ አቀራረብ እንየው። አጼ ምኒልክ ትግሬ፤ ወይንም ኦሮሞ፤ ወይንም ሌላ አማራ ያልሆኑ መሪ <u>ቢሆኑ ታሪካቸውን እንደ ወራሪ አድርገን እናቀርበውም ነበር ማለት ነው? የሻቢያ፤ የህወሓት፤ የኦነግና ሌሎች የጎሳ ፖለቲካ መሪዎች ይህን መመለስ አለባቸው።</u> አጼ ምኒልክ፤ አማራ በመሆናቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጀግና አልነበሩም ማለት የሚዘገንን በደል ነው። ኢትዮጵያ ነጻ ከምትሆን ይልቅ፤ ጣሊያን ሆነ አረብ ወይንም ሌላ ቢገዛት፤ የሕዝቡ ክብር ቢገፈፍ እንመርጣለን ከሚል ድምዳሜ ላይ ያደርሳል። አሁንም፤ ኢትዮጵያውያን በአገራቸው ተከብረው፤ ከረሃብ ነጻ ሆነው ከሚኖሩ፤ የውጭ መንግሥታትን ኩባንያዎች የአገሪቱን የተፈጥሮ ሃብት ቢቆጣጠሩት ይሻላል። ጥቂት የፖለቲካ ስልጣን የያዙ ጠባብ ብሄርተኞች ትርፍ እስካገኙ ድረስ ሁሉም ነገር ተቀባይነት አለው። የውጭ ቁጥጥር ተቀባይነት አለው እንደማለት ነው። "የከፋፍለህ ግዛው" መሰረተ ሃሳብ፤ ከአገር ግዛታዊ አንድነት፤ ከነጻነት፤ ከእኩልነት፤ ከፍትህ የበለጠ ጥቅምን መርጧል። ጠባብ ጎሰኛው ቡድን፤ አዲስ ታሪክ መስራት አለብን ብሎ ያለፈ ታሪክን ዋጋ ቢስ ያደረገው ለግልና ለአጭር ጊዜ ጥቅም ነው። ለጠላት ቀዳዳ ከፋች አገዛዝ ይህን ይመስላል።

ግብጽ፤ ልክ እንደ ኢትዮጵያ፤ የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖችና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች አገር ናት። ግብጾች የሚያምኑት ግን በግብጻውነታቸው ነው። ተቀዳሚው እሴት ግብጻዊነት ነው። ግብጽ፤ የአረቦች፤ የግብጾች፤ የኑባውያንና የሌሎች አፍሪካውያን ሃገር ናት። ኢትዮጵያም ከየመን የመጡ፤ ከአፍሪካ የመጡ፤ ወዘተ፤ ሕዝቦች ስብስብ የሚገኙባት ሃገር ናት። በሰላም አብረው የሚኖሩ ሃይማኖቶች አሉባት። በረጅም ታሪኳ፤ የኢትዮጵያ የታሪክ ሂደት እንደሌሎች ሃገሮች ነው ለማለት ይቻላል። ኢትዮጵያን የሚለያት፤ የአባይና የሌሎች ወንዞች አጠቃቀምና ቁጥጥር ነው። የአገሪቱ የተፈጠሮ ሃብት አጠቃቀም፤ አገልግሎትና አስተዳደር ይለያታል። የአገሪቱ አቀማመጥና ደህንነት ሃላፊነት ይለያታል። የስብጥር ሕዝቧ አብሮ መኖርና ከድህነት ነጻ መውጣት አመራር ይለያታል። በአብዛኛው ዓለም እነዚህ እንደ ችግር አይታዩም። አገዛዙ አቻችሎና አመዛዝኖ ለመላው ህብረተሰብ ጥቅም ያውላቸዋል። በኢትዮጵያ ረጅም ታሪክ፤ የውጭ ጠላቶቿና ጎሳ-ተኮር የሆኑ የፖለቲካ መሪዎች የሃገሪቱን የተፈጥሮ አቀማመጥና ሃብት። የሕዝቧን ስብጥርነት ጥቅም ተቀብለው አያውቁም። እነዚህን የተፈጥሮና የሠብአዊ ሃብቶች ለራሳቸው ጥቅም ለማዋል ሞክረዋል። አሁንም

ይሞክራሉ። ስለሆነም፤ ለውጭ ተቀናቃኞች ኢጋር መሆን ወይንም ቀዳዳ መስጠት ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተከታታይ ልማት ማነቆ ነው። የአገዛዝ መልሱ ሕዝቡን በጎሳና በሃይማኖት መለያየት፤ በተከታታይ መንግሥታት የተሰሩ ቅርሶችንና ሃብቶችን ማውደም አይደለም። የሁሉን ጥቅም የሚያስተናግድ። በእኩልነት የተመሰረተ ዲሞክራሳዊ ስርአት መገንባት ነው። ጠባብ ጎሳዊነትና ፍትሃዊ ልማት አብረው አይሄዱም። ለጠላት ወንፊቶች ናቸው።

መለስ፤ እኛ "የመናች ነን" ብሏል። ኢትዮጵያውያን አፍሪካውያን መሆናቸውን ዘንግቷል። "ግብጽና ሱዳን" በሚል መጽሃፍ፤ ላሪ ሄንደርሰን፤ የጐብኝት ግንዛቤውን እንዲህ ሲል ገልጿል። "በናይል ሸለቆ የሚኖረው ሕዝብ፤ ከአምሥት ሺህ አመታት በላይ ምንም ክፍተት ሳይኖረው፤ የሰሜን አፍሪካና የምስራቅ አፍሪካ ሕዝቦች የኖሩበት ምድር ነው። የግብጽ ስልጣኔ የእነዚህ ሕዝቦች አስተዋጽኦ ውጤት ነው። ግብጾች፤ በግብጽ የማያድጉ ዛፎች፤ እንቁ፤ ወርቅ፤ ቅባቶችና ቅመሞች ያገኙት ወደ ምስራቅ አፍሪካ በመነገድ ነው። የግብጽ ስልጣኔ ውጤት የእነዚህ ሁሉ ውጤት ነው" ብሏል። በውራንታ (basket) የሚሰፈር ወርቅ የፈርኦን መሪዎች ያስገብሩ፤ ወይንም ይሸምቱ የነበረው በግብጽ ስለተመረተ አልነበረም። ወርቅ ከሚገኝበት አገር ጋር ስለነገዱ ነው። ሱዳን ወርቅ አያመርትም። ኮንጎ እሩቅ ነው። ወርቅ ሊገኝ የሚችለው ከኢትዮጵያ ነው። ግብጾች፤ በሌሎች ሃገሮች እንደሚመኩ ካወቁ አምስት ሺህ አመታት በላይ ሆኗቸዋል። በራሳቸው የሚመኩበት አንድም የተፈጥሮ ሃብት የላቸውም። ኢትዮጵያ አላት። ይህን ያወቁ ተከታታይ የኢትዮጵያ መንግሥታት በንቃት ኢትዮጵያን የጠበቋት ለዚህ ነው። ይህ ከተቀናቃይ ጋር ግብግብ የነበረበት የታሪክ ሂደት፤ የኢትዮጵያን እድገት ቢገታው አያስደንቅም። አገርን ከውጭ ወራሪዎች ተባብሮ ጠብቆ ለተከታታይ ትውልድ ማስተላለፍ የጥንካሬ መስፈርት ነው።

አንባቢ እንዲያውቀው የምንመኘው የህወሓት/ኢህአዴግ ጎሰኛ መስራች የሆኑ የበላዮች ያስተጋቡት ይህ አስደናቂና ውጣ ውረድ የነበረበት ታሪክ እንደሌለ ነው። ላሪ ሄንደርሰን የሚያስተምረን፤ "የግብጽ ሃውልቶች በሙሉ የሚነግሩን ታሪክ፤ ግብጾች የግብጽን ታላቅነት፤ የታሪክ ተከታታይነት የሚቀበሉና የሚያከብሩ መሆኑን ነው።" ስለሆነም፤ ግብጾች፤ በአንድ አገር፤ በአንድ ህብረተሰብ ከሚያምኑ ሃገሮች መካከል የመጀመሪያውን እውቅና ይዘዋል። ከሁለት ዓመታት በፊት በሆነው ጸረ-ሙባረክ ትግል ግብጾች የታገሉት አሁንም የሚታገሉት በዘር፤ በጎሳ፤ በሃይማኖት ተለያይተው አይደለም። የሚለያዩት ምን አይነት ዲሞክራሳዊ ለውጥ ያስፈልጋል በሚለው ነው። ልዩነት ቢኖራቸውም ሁሉም በግብጻዊነታቸው ያምናሉ። ኢትዮጵያውያን ተረዳድተው ለለውጥ መነሳት ተገቢ ነው የምንለው ከራሳቸውና ከሰሜን አፍሪካ ለውጦች መማር ይችላሉ በሚል እምነት ነው። በአንድ ላይ ካልተነሱ "የጎሰኛ ከፋፍለህ ግዛው" አስተዳደር የያንዳንዱን ዜጋ አኗኗርና የኢትዮጵያን የወደፊት እድል ይወስናል። ለማስታወስ፤ ከግብጾች የበለጠ፤ ኢትዮጵያውያን አንድ የሚያኮሯቸው አለ። የተፈጥሮ ሃብት፤ የኢትዮጵያ ታላቅነትና ነጻነት። ግብጽ፤ በተከታታይ፤ የሮማን፤ የግሪክ፤ የቱርክ፤ የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ሆና ነበር። አስዋን የተሰራው በግብጾች ገንዘብ፤ መሃንዲሶች ወዘተ፤ አይደለም። ጥበበኛው ናስር ሶቬየቶችን ተንከባክቦ ባደረገው ጥረት ነው። ይህን አንጋፋ መሪ ግብጾች ያከብሩታል። ጀግና ብለው ተቀብለውታል። ኢትዮጵያ የብዙ ከሁሉም ብሄረሰቦች የመጡ ጀግኖች አሏት። ህወሓት የሚፈልገው አዲሱ ትውልድ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጋራቸው መሪዎችና ጀግኖች የሉትም የሚለውን እንዲቀበል ነው። ይህ ጠባብ ጎሰኛ አስተሳሰብ ለኢኮኖሚ የበላይነትና የራስን ክልል በፍጥነት ለማልማት ይረዳዋል። ለኢትዮጵያ አይበጅም።

አጼ ቴኦድሮስ፤ አጼ ዮሓንስ፤ አጼ ምኒልክ፤ አጼ ኃይለ ሥላሴ አገር ወዳድ ነበሩ። በአቅማቸው፤ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ከሁሉም በላይ፤ በዓለም ለኢትዮጵያና ለጥቁር ሕዝቦች ዝናን ያስገኙለት አጼ ምኒሊክ ናቸው። የአድዋ ጸረ-ቅኝ ገዥ ጦርነት የነጻነትና የክብር ማረጋገጫ ጦርነት ነው። የሱሉልታ ኦሮሞ፤ የጎንደር አማራ፤ የጉራጌና ሌልች የህብረተሰብ ክፍሎች በህይወታቸው ዋጋ ከፍለውበታል። ዓለም ያደነቀው የትግል ውጤት ነው። በቅኝ ገዥዎች ቀንበር "እዚህ ምግብ ቤት አትበላም። ጥቁሮችና ውሾች ክልክል ናቸው። ለጥቁር ትምኅርት አያስፈልገውም" ወዘተ የሚል ቅኝ ገዥን አንፈለግም። "ኢትዮጵያ የኢትዮጵያውያን ናት" ብለው በብልሃት የመሩትን መሪ፤ ከነጮች ጋር በማመሳሰል፤ እንደ ቅኝ ገዥ፤ "ጡት ቆራጭ፤ ጨቋኝ፤ ሰላቢ"ብሎ መኮነን የኢትዮጵያን ሕዝብ በሙሉ መናቅ ነው፤ ኦሮሞውን ጨምሮ። የጥቁር ሕዝቦችን የነጻነትና ክብር መሪ ማዋረድ ነው። አንባቢው ማሰብ ያለበት ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረበት ዘመን፤ በጅምላ አገር ወዳዶችን፤ አርበኞችን የገደለው ነጻ የሆነች፤ አጼ ምኒልክ የታደጓትን ሃገር ለባርነት ለመዳረግ ነበር። አገሪቱ በወራሪዎች ብትያዝ፤ ትግሬ፤ አማራ፤ ጉራጌ፤ ኦሮሞ፤ ሶማሌ ወዘተ፤ እንደ "ውሻ፤ እዚህ ለመብላት፤ ለመተኛት፤ ስራ ለመያዝ፤ መሬት ለመያዝ፤ ቤት ለመስራት አትችልም" እንደሚባል አንጠራጠርም። ይኼ እኮ ኤርትራ፤ ኬንያና ህንድ አገር ሆኗል። የህወሓት/ኢህአዴግ ጠባብ ጎሰኛ መሪዎች ያዋረዱት ራሳቸውንና እንወክልሃለን የሚሉትን ህብረተሰብ ጭምር ነው። አጼ ምኒልክ የተዋጉትና ድል ያደረጉት፤ የጎሳ መሪ ስለነበሩ አይደለም። ዓለም ያደነቃቸው በቁሳቁስ ኋላ ቀር፤ በመንፈስና በኃይማኖት ጠንካራ" የሆነውን የኢትዮጵያን ሕዝብ፤ "ተነሳ። ያለህን አቅም፤ ቁሳቁስ ተጠቅመህ ወራሪውን ሃይል ወደመጣበት መልስ። ኢትዮጵያዊነትህን አስመስክር" በሚል ብሄራዊ ጥሪ ነው። ዛሬ ያለው

ጦርነት ድህነትን ማጥፋት ነው። ድህነትን፤ ስደትን ለማሸነፍ ብሄራዊ ቆራጥነትና ተባብሮ መስራት ይጠይቃል። አገዛዙ የሚያደርገውን ጠባብ ጎሳዊነት በመቀበል አይደለም።

አጼ ምኒልክ፤ የኢትዮጵያ ጆርጅ ዋሽንግተን፤ ማኦ ሲቱንግ ወይንም ሻንጋይ ሼክ፤ ከማል አታቱርክ፤  ገማል አብደል ናስር፤ ሆቺ ሚን ወዘተ አይነት መሪ ናቸው። በጠባብ ጎሰኛ ጥላቻ የእኒዚህን አኩሪ መሪ አስተዋጽኦ መካድ "ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ" በደል ነው። ራስን መጥላት ነው። የበታችነትንና ባርነትን መቀበል ነው። ሃገር ወለድ የሆነ እድገት በዚህ አይነት የጥላቻ አመራር አይገኝም። ክህደት የሚከተል አመራርና በማንኛውም ፖሊሲ ሰው ሰራሽ ማስረጃ እንደ እውነት እያቀረበ ሰብአዊ መብቶችንና የኢኮኖሚ እድሎችን ይዘጋል። ለማሳየት የምንፈልገው ዋና ነጥብ በአምባገነናዊ አገዛዝ፤ በሰብአዊ መብቶች መከበርና  በግለሰብ ኑሮ መሻሻል ቀጥታ የሆነ ግንኙነት መኖሩን ነው። ሰብአዊ መብቶችንና የኢኮኖሚ እድሎችን በረቀቀ መንገድ ማፈን ለጥቂቶች ኪራይ ሰብሳቢነትና የኢኮኖሚ አውራነት የማይተኩ መሳሪያዎች ሆነዋል። ይህ የበላይነት እንዴት ተግባራዊ ሆነ ብለን እንጠይቅ።

አንዱና ዋናው የአገዛዝ ዘዴ ህብረተሰቡን መከፋፈል ነው። እትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት የሚል የፖለቲካ ማእከል ክፍተት መኖሩ። ህወሓት/ኢህአዴግ የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነቱን ድልድይ አዋቅሮታል። የፀረ-ሽብርተኛና የመንግሥት ያልሆኑ ድርጅቶችን የሚዳኙ ደንቦችና መመሪያዎች የታወጁት አፈናን ሕጋዊ አድርጎ የበላይነትን ለማጠናከር ነው። እነዚህ ሕጎች የግል መብት ያፍናሉ። ኢትዮጵያውያን ሃገራቸውን በሚመለከቱ ውሳኔዎች ምንም ሚና እንዳይኖራቸው ያደርጋሉ። ህወሓት/ኢህአዴግ ኢትዮጵያውያንን ገለል አድርጎ ውሳኔ መስጠት የጀመረው ዛሬ አይደለም። ገና ስልጣን ሲይዝ ነው። ለምሳሌ፤ የአገሪቱን ወደብ አልባነት ቀርበን ብናይ፤ ከጅምሩ ኢጋሩን የኤርትራን ሕዝባዊ ነጻነት ግንባር ፍላጎት በሙሉ ማሟላት ነበረበት። የኤርትራን መገንጠል ተቀበለ። እንዲያውም የአፍሪካ አንድነት ማህበር መገንጠል አንደግፍም ሲል፤ መለስ ዜናዊ ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ፀሃፊ "የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የኤርትራን መገንጠል ይፈልጋል፤ ይደግፋል" ብሎ ፈርሞ የላከው ደብዳቤ ምስክር ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምጽ ሳይሰጥበት፤ አሰብን አስረከበ። ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ሆነች። ለኢኮኖሚው እድገት፤ ለሃገር ደህንነት ቁልፍ የሆነውን የኢትዮጵያን የባህር በር ዘግቶ አገሪቱን ለአደጋ አጋለጣት። የሕዝብ ተሳትፎቶ መከልከሉ የሰብአዊ መብቶች አፈና መስፈርት ሆነ። የዚህ ጉዳት ምንድን ነው ብለን ስንጠይቅ፤ ህብረተሰቡና ነጋዴዎች በዋጋ ግሸበት ተጎድተዋል። የቁሳቁስ ዋጋዎች ሰማይ ነክ ሆነዋል። አስመጭና ላኪ ወይንም ተራ ሸማች ከዓለም ዋጋ በላይ እንዲከፍሉ ተገደዋል። ስለሆነም፤ ማንኛውም ተተኪ መንግሥት ይህን መለስ ጥሎት የሄደውን የአመራር ስህተት ማስተካከል ይገደዳል። ስለዚህ ብሄራዊ ተጠቂነት አንዳንድ የፖለቲካ ተቃዋሚ ድርጅቶች የወሰዱት አቋም ተገቢነት አለው። ማንኛውም ተቃዋሚ ድርጅት ኢትዮጵያን ካፈረሰው ከሻቢያ ጋር ሆኖ፤ ለኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነት፤ ለመላው ሕዝቧ የኑሮ መሻሻል እታገላለሁ ቢል አስቸጋሪ የሚሆነው፤ "የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው" የሚለው አባባል ከአጠያያቂነት በላይ ጎጅነቱ የላቀ ስለሆነ ነው። ባለፈው የፖለቲካ ታሪክ ታይቷል። የኢሳይያስ አፈወርቂ ፓርቲ ለኢትዮጵያ ዋና ጠላት ሆኖ ኤርትራን ከእናት አገሯ አስገንጥሏል። ወደብ አልባ አድርጓታል። አሁንም በልዩ ልዩ መልክ ህብረተሰቡን ሰላም ነስቶታል። ሻቢያ፤ ከኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነትና ልማት በላይ ከህወሓት የበላዮች ጋር ያለው የጠበቀ ግንኙነት ይዳኘዋል። ተቃዋሚዎችን የሚያስተናግደው ኢትዮጵያን ለማድከም እንጅ ለማጠንከር አይደለም። ከፅንሱ "አረባዊ" አመለካከት ያለው መሪ ለኢትዮጵያ ዘላቂ ጥቅም ቆሟል ማለት ቀልድ ነው። በዘላቂነት ሲታይ፤ ለሁሉም ልማት የሚበጀው አማራጭ የኢትዮጵያና የኤርትራ ወንድማማች ሕዝብ በሰላም አንድ አይነት ፌደሬሽን ለማቋቋም ቢሞክሩ ነው። ኢትዮጵያና ኤርትራ የሚጋሩት ከሚለያያቸው ይበልጣል።

ሁለተኛው ዘዴ በህገመንግሥቱ የሚታይ፤ ብሄር/ብሄረሰቦች ሊታረቁ አይችሉም በሚል የግራ ክንፍ እርዩተ ዓለም ቅጅ በመጠቀም፤ በብሄር/ብሄረሰብ/ሕዝቦች "መብቶች" ላይ የተመሰረተ ሕገ-መንግሥት ማጽደቁና በስራ ማዋሉ ነው። ይህን ያደረገበት ጥበብ በእኩልነት፤ በፍትህ፤ በዲሞክራሲ ስም የብሄር ክልል አስተዳደር መንግሥት በመመስርትና ለዚህ የኢኮኖሚ ጥቅሞችን በማመቻቸት ነው። "የማይታረቁ" ብሄሮች የመገንጠል መብታቸውን ሕጋዊ ለማድረግ፤ አንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝን (Article 39) በሕግ ተቀብሏል። ይህን ተቋማዊ ስላደረገ እውነተኛ  መረጋጋትን አናግቷል። የሕዝብ መተሳሰርን፤ አብሮ ተቻችሎና ተከባብሮ በእኩልነት የመኖርን፤ የመፈላለግን፤ እውቀትና ልምድ የመከፋፈልን ጥቅሞች አደፈረሷል። ከላይ ወደታች የሆነ የፖለቲካ ስልጣን (devolution and decentralization of political and economic power) ማለትም፤ በአመራር ላይ የመወሰን፤ በተፈጥሮ ሃብት ላይ ወሳኝ ድምጽ የመስጠት፤ ጥቅሙን የመካፈል፤ አቤቱታ አቅርቦ ፍትህ የማግኘት መብት፤ ለተጎዱ፤ "ለተጨቆኑ" የህብረተሰብ ክፍሎች የሚያሳየው ውጤት ከስሜት ባሻገር ሲታይ ተራውን ኢትዮጵያዊ ጎድቶታል። የጋምቤላና የኦሞ ሸለቆ ሕዝብ ዋና ምስክር ነው። በቋንቋ፤ በባህል፤ በታሪክ፤ ወዘተ የሚገኙ ጥቅሞችን ማንም ሕዝብ መጠበቅ መብቱ ነው። ኦሮሚያ ብሄራዊ ቋንቋ ቢሆን ይጠቅማል፤ ይኼ አያከራክርም። ደርግም የጎሳዎችን እኩልነት በተግባር አሳይቶ ነበር።

እነዚህ የባህል፤ የታሪክ፤ የልምድ እሴቶች የኢትዮጵያ ሕዝብ መለያዎች ናቸው። ማንኛውም መንግሥት ሊያከብራቸው ይገባል። ወጣቶች በቋንቋቸው መማር መብታቸው ነው። የኢትዮጵያን ተራ ዜጋና ህብረተሰብ የጎዳው ገዢው ፓርቲ ሆነ ብሎ “በቋንቋ እኩልነት” የጋራ የሆኑትን ለሁሉም ኑሮ መሻሻል የሚረዱትን እሴቶች ማጥፋቱ ነው። ይህን የምንለው ላለፈ ታሪክ ታላቅነት አይደለም። የሚጎዳው ሁሉንም ስለሆነ ነው። ክፍፍሉ ለመላው ህብረተሰብ ብሄራዊና ተቋማዊ የሆነ ኢጋር ነስቶታል። በአገር ደረጃ የሚከራከር አንድም የማህበረሰብ ወይንም የፖለቲካ ፓርቲ ተቀናቃኝ የለም። የዚህ ጣሊያንና ሌሎች የኢትዮጵያ የውጭ ጠላቶች የፈጠሩት በብሄር ጥላቻ የተመሰረተ የፖለቲካ “ወረርሽኝ” የመጀመሪያ ተጠቃሚዎች የውጭ መንግስታትና ኩባንያዎች እንደሚሆኑ አንጠራጠርም። ይህን በሕዝብ መካከል በልዩ ልዩ መልክ መሰረት የያዘ ግንኙነት ማፈራረስ የሕዝቡን አቅም ማዳከም ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ለዚህ ተጠያቂዎችና ሃላፊዎች የሻቢያና የህወሓት አለቆች ናቸው። የኢትዮጵያም ግራ ክንፍ ተጠያቂነትና ሃላፊነት አለበት። ጠንቁ ለኑሮ መሻሻልና ለአገሪቱ ልማት ወሳኝ ስለሆነ ምሳሌ ተጠቅሞ ማሳየት ይጠቅማል። የክልል አገዛዝ ከሁሉም በላይ የሚያገለግለው የአንድ ጠባብ ብሄርተኛ የሆነ አምባገነንነትን ነው። ፌደራላዊ መንግሥትና የክልል አስተዳደር በአንድ ሆነው፤ ሰብአዊ መብቶችን በእርጋታ፤ በጸረ-ሽብርተኛነት፤ በሃገራዊ አንድነት ስም ለማፈን ህገመንግሥቱን እንደሚጠቀሙበት አሳይተናል። የብሄረሰብ ፖለቲካ ድርጅቶች የበላዮች (Ethnic elites) የቋንቋ ልዩነትን “ማስፈራሪያን ማግለያ” አድርገው ለራሳቸው ስልጣንና የኢኮኖሚ የበላይነት መሳሪያ አድርገውታል። የመሳፍንት ዘመን አይነት ያለነው ለዚህ ነው።

ብሄራዊ ልማትና የብሄር ጥላቻ አብረው አይሄዱም

በማንኛውም አገር መንግሥትን መለዋወጥ የተለመደ ነው፤ አብዛኛው በነጻና ፍትሃዊ ምርጫ፤ ሌለው በአመፅ። መንግሥት ቢለዋወጥም የእድገት መሰረሮችና ብሄራዊ ተቋሞች እንደ ሸሚዝ አይለወጡም፤ እንክብካቤ ይደረግላቸዋል። የሕዝብ ኢንቨስትመንትና ሃብት ስለሆኑ። ጎሰኞት በዚህ አያምኑም። የሚያምኑት ያለውን በማፈራረስና ራሳቸው በሚጠቅሙ ተቋሞች በመተካት ነው። ዋናው መሳሪያ የጎሳ ጥላቻ ነው። አንድ ጎሳን ወይንም የህብረተሰብን ክፍል ለማግለል (Marginalization) ከተፈለገ “የጎሳ ወይንም የሃይማኖት ጥላቻ” መመሪያችን ነው ብሎ ሰብአዊ መብቶችን ፈጽሞ ለማጥፋት ይሰራል። መለስ “የአማራ ብሄረሰብ አውራ ጠላታችን ነው። ይህን ብሄረሰብ ማጥፋት ቀላል ነው” ሲል የሰጠው መልእክት፤ ከራሱ ቡድን፤ ብሄር ውጭ አማራም፤ ኦሮሞም፤ ሶማሌም፤ አፏከም፤ አፋርም ሆነ ጉራጌ ወዘተ፤ የበታች ሆኖ መገዛት አለበት ማለቱ ነው። በገቢና በኑሮ ሲታይ አማራው ተለይቶ ያገኘው የኢኮኖሚ ጥቅም የለም። አብዛኛው አማራ እንደሌላው ደሃ ነው። አማራው ዋና “ጠላት” ሆነ ተብሎ ቢፈረድበትም፤ ሶማሊው፤ ኦሮሞው፤ አፏኩ ወዘተ ዋጋ እየከፈለ ነው። የጋምቤላ፤ የአኖ ሸለቆ፤ የኦሮሞ፤ የደቡብ፤ የሶማሌ ወዘተ ሕዝብ በነጻነትና በድሎት አይኖርም። UNESCO በ2014 Education for All Global Monitoring Report በተባለ ዘገባ በኢትዮጵያ በትምሕርት አቅርቦት የጥራት ጉድለት፤ የትምኅርት እድል በማግኘት በኩል ያለውን መዛባትና አድልዎ እንዲህ ሲል አቅርቦታል። “የአፍሪካ መንግሥታት ደሃነትን ለማጥፋትና ለወጣቱ ትውልድ እድል ለመፍጠር ካላፈው በበለጠ ደረጃ የትምሕርት እድልን ማጠናከር አለባቸው፤ በተለይ ችላ ለተባሉ ጎሳዎችና የማህበረሰብ ክፍሎች፤ ለምሳሌ ልጃገረዶች። ለዚህ አስፈላጊው የአመራር ጥራትና መዋቅራዊ ችግሮችን፤ ለምሳሌ በገጠር የሚኖረውን ሕዝብ ደሃነት፤ የገቢና የሃብት ልዩነቶች ማስወገድ ነው። በግልፅ የሚታየው በሃብታምና በደሃ ልጆች መካከል ያለው ትምኅርት የማግኘት፤ ያለማግኘት ልዩነቶች ተከታታይ ትውልድን ይበክላል። የሃብታም ልጆች የተሻለ እድል ይኖራቸዋል፤ የደሃ ልጆች ተመሳሳይ እድል አይኖራቸውም።” በኢትዮጵያ ወጣት ሴቶች፤ በተለይ የገጠሮቹ በሁለተኛ ደረጃና በከፍተኛ ትምህርት ተሳትፏቸው ከሌላው አፍሪካ ወደ ኋላ የቀረ ነው። ይኼ መዋቅራዊ ችግር ካልተፈታ ተከታታይ ደሃነት አይቀርም። ከማንኛውም በላይ ደሃነትን ለማስወገድ የሚቻለው ሁሉም ዜጎች የትምህርት እድል ሲኖራቸውና ትምህርቱ ጥራት ሲኖረው ነው። “In Ethiopia, children who scored in the bottom quarter in maths at the age of 12 were more than twice as likely as those who were in the top quarter to drop out by age 15.” ይኼ ማንኛውንም ወጣት የሚመለከት ሲሆን፤ በጣም አሳሳቢ ሆኖ ያገኘሁት በጎሳዎች መካከል የሚታየው የትምኅርት እድል መዛባት ነው። አደገኛ ሁኔታዎችን የሚፈጥር፤ ለሽብርተኞች መሳሪያ የሚሆን ክስተት።

“In Ethiopia, where 48 percent of teachers are trained, only 20 percent of teachers were trained in grades 1-4 in 2010…The percentage of lower primary teachers who were trained was as low as 1 percent in the Somali Region and 4 percent in the Afar Region.” ይኼ የትምኅርት እድል ኋላ ቀርነት በሌሎች መስፈርቶችም--በነፍስ ወከፍ ገቢ፤ በመሰረተ ልማት፤ በንፁህ ውሃ አቅርቦት፤ በምግብ ወዘተ እንደሚከሰቱ መገመት አያዳግትም። ለጭቁን ብሄር፤ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች መብትና ጥቅም ቆሚያለሁ የሚለው የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት በጭቁኖች ህይወት የፖለቲካ ስልጣን ጨብጦ አሁንም ይነግድባቸዋል ብንል ከሃቁ የራቅን አይመስለኝም።

እነዚህ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ አካሎች ሌላው ቀርቶ ግፍ ሲፈጸምባቸው ለመንግሥታቸው አቤቱታ ለማቅረብ አይችሉም። ስለሆነም፤ የውጭ እርዳታ ከሰብአዊ መብቶች አፈና ጋር ሲከሰት ያለው ምርጫ እርዳታ ሰጨን ድርጂት በሚወክለው አገር ፍርድ ቤት መክሰስ ነው። የጋምቤላ ሕዝብ ክሱን በማያሻማ ማስረጃ ተደግፎ በእንግሊዝ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ማሸነፉ ጥሩ ምሳሌ ነው። ባጭሩ፤ የህወሓት/ኢህ አዴግ መንግሥት የተባበሩት መንግሥታትና የአፍሪካ አንድነት ማህበር የተስማማባቸውን የሰብ አዊ መብቶች ሁሉ አፍኗል፤ ወደፊትም ያፍናል። የስልጣን ቆይታው ከሰብአዊ መብቶች በላይ ነው።

የራሳችን ጠላት ራሳችን ነን

ስለዚህ ለማለት የምንችለው፤ "ለጭቁን ብሄረሰቦች" ሆነ ለሌሎች የብሄር ጥላቻውና አፈናው ወሰን የለውም። ሁሉም በየተራው ደርሶታል፤ ይደርሰዋል። ዛሬ አማራ። ነገ ኦሮሞ። ከነገ ወዲያ ሶማሌ። ከዚያ አኟክ እያለ ይቀጥላል። ሊገባን ያልቻለው ስርዓቱን የሚቃወመው ክፍል የገዢውን ፓርቲ የበደል ቋንቋ (አስተሳሰብ) መቀበሉና ራሱን ተቀጭ ማድረጉ ነው። እኛ የራችን ጠላት ሆነናል የምልበት ዋና ምክንያት በአንድ ላይ ለሰው ክብሩነት፤ ነጻነት፤ ለሰብአዊ መብቶች፤ ለእውነተኛ እኩልነት፤ ለህግ የበላይነትና ለዲሞክራሳዊ ስርዓት አማራጭ ለመታገል አለመቻላችንን ነው። ጥላቻና አንቀበልም እያልን ራሳችን የጥላቻ ፖለቲካን እናስተጋባለን፤ "ኢህአፓ፤ መኤሶን፤ ኢሴፓ፤ አነግ፤ ግንቦት ሰባት" ወዘተ እያልን። ህወሓት ከማንኛውም በላይ ያስከተለው ናዳ ሕዝቡ እርስ በርሱ እንዲከፋፈል፤ እንዲጣላ፤ እንዳይተማመን የጫነው ሸክም ነው--ከቋንቋ ውጭ አማራው፤ ኦሮሞውና ሌላው ከቤተሰብና ከመንደር ጀምሮ ተከፋፍሏል፤ ተናንቋል፤ የዓላማ አንድነት የሚባል እሴት አይጋራም። አንድ የሚጋራው ነገር ቢኖር በገዢው ፓርቲ ላይ ያለው የጠለቀ ጥላቻ ነው። ሆኖም፤ ጥላቻ ለአለው ችግር መፍትሄ ነው የሚል ግምት ጎጂና የተሳሳተ ነው። በኃይማኖት ዙሪያም ያለው ልይኑነት ጠቃሚነቱ ለገዢው ፓርቲ ነው። የሶስት ሽህ አምስት መቶ አመታት ተከታታይ ታሪክ የሚያሳየው ኢትዮጵያ የህብረ-ብሄር፤ የተለያዩ ሃይማኖቶች አገር መሆኗን ነው። ፍትህ ነበር ለማለት አይደለም። ይህን ተከታታይ ታሪክ የውጭ ጠላቶቿ ተቀብለው አያውቁም። የምእራብ መንግሥታት፤ በተለይ ቅኝ ገዢዎች ይህን የሚያኮራ ታሪክ በጠላትነት አይተውታል። የአረብ አገሮች አሁንም የኢትዮጵያን ሕዝብ ማደግ አይፈልጉም። የሚፈልጉት አገሪቱንና ሕዝቧን ለመቆጣጠር ነው። ለዚህ ህወሓት/ኢህአዴግ መሳሪያ ሆኖ አገልግሏል። "ኑ፤ ግቡ" ብሏል። ዛሬ እንደ አል ሸባብ ያሉ አክራሪና ሽብርተኞች የሚጠቀሙበት መሳሪያ የሰብአዊ መብቶች፤ በተለይ የእስልምና ኃይማኖት ነጻነት መገፈፉን ነው። ለገዢው ፓርቲና ለሃገሪቱ የሚበጀው ፖሊስ ተከታታይና አይነ-ጭፍን የሆነ የሰብ አዊ መብቶች አፈና አይደለም። በኃይማኖትና በሌሎች ብሄራዊ ችግሮች ላይ የሰላም፤ የእርቅ፤ አብሮ የመኖር ወዘተ ውይይትና ድርድር ነው።

የህወሓት አመራር አማራውን የተለየ ጠላት ያደረገው፤ ከብሄሩ በላይ ኢትዮጵያዊ ስለሆነ ነው። ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት፤ ለሃገሪቱ ነጻነት ከማንም የበለጠ ስለተዋጋ ነው። ዋጋ ስለከፈለ ነው።  አብሮ መኖርን በጋብቻ፤ በባህል፤ በሃይማኖት፤ በትምኅርት፤ በስልጣን ስለተጋራ ነው። አማራን ማጥፋት ዋና አላማ ከሆነ ኢትዮጵያን ማጥፋት ዋና ግብ ሆኗል። ነፍጠኛ ተብሎ ከቀዬ ውጣ ሲባል፤ ኢትዮጵያ አገርህ አይደለችም። ወራሪ ነህና ወደ መጣህበት ሂድ ማለት ነው። እኛ የምናየው፤ ይህ ዘዴ ተቀናቃኝ የሆነን ሁሉ በማሳደድ ህወሓት ለመጭው መቶ አመታት ለመግዛት ያስችለኛል ብሎ የተቀበለው መመሪያ ነው። ሰብአዊ መብቶችን የሚያፍንበት የአገዛዝ መሳሪያ ነው። የአማራውን ሰብአዊ መብት በመግፈፍ፤ የጥቂቶችን እድል ማመቻቸት፤ የአብዛኛውን እድል መዝጋት ያስችላል የሚል ጠባብ ግብ ስላለው ነው። ለዚህ፤ የአፈናውን ኢላማ ከአማራው ላይ ያደረገው አያስደንቅም። "የትግራይ ተቀናቃይ" አማራው ነው የሚል ጊዜ ያለፈበት ርእዮት ስለሚከተል ነው። እኛ ማጤን ያለብን፤ በአማራው ላይ የሚደረገው "እልቂት" የመሰለ ዘመቻ በሁሉም ላይ ደርሷል። ካልደረሰ ይደርሳል። "ነግ በኔ" እንበል። ህወሓት ደፍሮ ለፍትህ የቆመን ሁሉ አይለይም። በቅርቡ ትግራይ፤ አማራ፤ ኦሮሞ፤ ጉራጌ ሳይለይ አስሯል። ዘዴው ከፋፍለህ ምታው መሆኑ ነው። በእርጋታ መስፈርት ሲታይ የሚዘገንነው ደሃው የአማራ ክልል ከትግራይ ክልል ጋር ሲነጻፀር በነፍስ ወከፍ ገቢ፤ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ፤ መንገድ፤ የጤና አገልግሎት፤ ጥራት ያለው የትምኅርት ቤት መሰረተ ልማት፤ ንጹህ ውሃ፤ ፋብሪካ፤ ወዘተ አልተሰራለትም። እንዲያውም፤ ከአጀማመሩ፤ አማራውን ሙሉ በሙሉ ለማዳከም፤ ህወሓት፤ የማምረቻ ምንጮቹን ለራሱ ክልል አዘዋውሯል። አገርን እመራለሁ የሚል መንግሥት ያለፉ መንግሥታት የሰሯቸውን ልማቶች አያፈርስም። ህወሓት አፍርሷል። አንድ ምሳሌ።

ህወሓት ጣና በለስን ለምን አፈራረሰ?

የህወሓት መስራቾች፤ መሪዎችና ደጋፊዎች የሚመሩበት እርዮት ጥላቻና ቂም በቀልነት ነው። ኢትዮጵያዊ የሆኑ ተቋሞችን የሚያፈሱበት ምክንያት ለዚህ ነው። ተከታታይነትን በጥላቻ ያዩታል። ደርግ ለግብርናውና ከግብርና ጋር

ለተያያዘ ኢንዱስትሪ ትኩረት ሰጥቶ ነበር። ዛሬ ዓባይን እገድባለሁ ብሎ የተነሳው ገዢ ፓርቲ ወደ ስልጣን አፋፍ በደረሰበትና ስልጣን በያዘበት ወቅት ብዙ ተቋሞችን አፈራርሶ ወደ ትግራይ ክልል አዛውሯል። ከእነዚህ ውስጥ በጣም የሚዘገንነው የኢትዮጵያ ደሃ ሕዝብ በጉልበቱን በገንዘቡ የመሰረተውን የጣና በለስ ማፈራረሱ ነው። የጣና በለስ የመስኖ እርሻና የመብራት ኃይል አቅርቦት ስራ ዓለም ባንክ በውስጥ ጥናቶቹ አስፈላጊ ነው ያለው የደርግ መንግሥት ያሰራው ከፍተኛ የማህበረሰብና የኢኮኖሚ ልማት ጥቅም ያለው ነበር። ይህ የእርሻና ኢንዱስትሪ ስራ ሁለት ዓላማዎች ነበሩት፤ አንድ፤ ለምግብ የሚውሉ ሰብሎችን ማምረትና ለገበያ ማቅረብ፤ ሁለት የውሃ መብራት ኃልይ ለኢንዱስትሪና ለሕብረተሰብ አገልግሎት ማቅረብ። ሁለቱም አስፈላጊዎች ናቸው። በተጨማሪ፤ ስራው እየተስፋፋ ሲሄድ ልዩ ልዩ የምግብ አይነቶች ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ፍላጎትና እምቅ ችሎታ ነበር። የግብፆችን ጠላትነትና ተቃውሞ በማጤን የጣና በለስ ስራ በጣና ኃይቅ ዙሪያ (ከፍተኛው የዓባይ ወንዝ መነሻ) የዓባይን ወንዝ ገድቦ የኃይቁን ውሃ ከፍ በማድረግና ውሃውን በቦይ እንዲያልፍና ተሽከርካሪዎች ተጠቅሞ የሚወርደውን ውሃ ለመስኖ እርሻ መጠቀም ነበር። እቅዱ ሙሉ ስራ ላይ ሲውል በዚህ አካባቢ ብቻ አንድ ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለመስኖ እርሻ ለማዋል ይቻል ነበር። ጥቅሙ ብዙ ዘርፎች አሉት፤ የአካባቢውን የደሃ ገበሬ ቤተሰቦች ከደሃነት ነጻ አውጥቶ ወደ መካከለኛ መደብ ያስተላልፋቸዋል፤ ለምግብ ዋስትና ከፍተኛ አስተዋፆ ያደርጋል፤ ከእርሻ ጋር የተያያዘ እንዱስትሪ ያስፋፋል፤ የስራ እድሎች ይፈጥራል፤ የአገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ የሚችል ሕብረተሰብ ይፈጥራል፤ ኢትዮጵያ በዓባይ ላይ ያላትን የመጠቀም መብት ያመቻቻል። በወቅቱ የደርግ መንግሥት ባለስልጣን የነበረ በመጽሃፉ ያቀረበው በበለጠ ያብራራዋል።

የጣና በለስ “በአስደሳች ሁኔታ ተጀመረ። ከጣልያን አገር አግሮኖሚስቶች (የእርሻ ባለሞያዎች)፤ የተለያዩ የቴክኒክ እውቀት ያላቸው በለሞያዎች መጡ። ኢትዮጵያውያን የእርሻ ባለሞያዎችና በሺህ የሚቆጠሩ ሠራተኞች ከጣልያኖች ጋር ተቀናጅተው እንዲሰሩ ተደረገ። የአፈር ምርመራ፤ የመስኖ መሥመር ዝርጋታ፤ የሙከራ ጣቢያዎች ግንባታ፤ የውሃ፤ የኤሌክትሪክና የቴሌፎን ዝርጋታ ስራ ተጀመረ። የእርሻው አካባቢ ተቀየሰ። ወደፊት ከተማ ሊሆኑ የሚችሉ ጣቢያዎች ተቆረቆሩ። የመንገድ ግንባታ በየአቅጣጫው ተጀመረ። ከድህነትና ከረሃብ የመገላገል ተስፋችን ለመለመ። ኢትዮጵያ የምስራቅ አፍሪካ የውሃ ምንጭ እየተባለች በመስኖ መጠቀም ተስኗት ለዘመናት በረሃብ መጠበሷ ያከትማል የሚል ተስፋ አደረብን።” አስደናቂ ዘመናዊና የተያያዘ የልማት ስራ መካሄድ ጀመረ ማለት ነው። በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ይኼን የሚመስሉ እቅዶችና ጅምሮች ነበሩ። የጣናን ኃይቅና የዓባይን ወንዝ በጥናትና አግባብ ባለው እቅድ በስፋት ሲሰራ የመጀመሪያው መሆኑ ነው። ከዚያስ ምን ተከተለ? “እኛ እንደሰት እንጅ ጠላቶቻችን (ግብፆች፤ ሻቢያ፤ ህወሓት) በጣና በለስ ፕሮጀክት ቅሬታ ተሰምቷቸዋል። በዚህም የተነሳ ህወሓት አካባቢውን በያዘበት ጊዜ እንዳልሆነ አድርጎ ፕሮጀክቱን አፈራረሰ። ለፕሮጀክቱ ስራ ይጠቅማሉ ተብለው የመጡትን የግንባታና የእርሻ መሣሪያዎች በሙሉ እየጫኑ ወደሚፈልጉበት አካባቢ አጓጓዙ። ጠቃሚ መስሎ የታየውን ማንኛውንም እቃ እየነቀለ ወሰደ። ዘመናዊ የሕክምና መሣሪያዎች ተደራጅቶ የተቋቋመውን ሆስፒታል አፈራረሰ። የኤክስሬይና ዘመናዊ የምርመራ መሠራሪያዎችን ነቃቅሎ አጓጓዘ። የተዘርጉ ቧንቧዎች ሳይቀሩ ተነቃቀሉ። በኢትዮጵያ ላይ ከጠላቶቿ ጋር በመተባበር ታላቅ ወንጀል ተፈፀመ።” 9/

እንደዚህ ያለ ወንጀል በነጻ የአፍሪካ አገሮች ተደርጎ አያውቅም። በኢትዮጵያና በአካባቢው ነዋሪዎች ህይወት ላይ የተፈፀመ “ወንጀልና” ከህደት የውጭ ወራሪ ጠላት ከሚያደርገው የባሰ ነው። ሆስፒታል ሲፈራርስ ሴቶች በወሊድ ይሞታሉ፤ እንክብካቤ የሚደረግላቸው ህፃናት መድሃኒት ስለማያገኙ ይሞታሉት። በአካባቢው የመስኖ ስራ የተሰማሩ ኢትዮጵያውያን እድል ይበከላል፤ ወዘተ። ህወሓት ጣና በለስን ሲያፈራርስ ያስከተለው በደል ከዚህ አንፃር መታየት አለበት። በጥላቻ የተመረዘው አመራር ኩረቱ የአማራውን ሕዝብ ዘመናዊነት ለመደምሰስና መንፈሱን ለማድከም ነው የሚል ግምት አለን። የውጭ ጠላት፤ ቢያንስ የሚገዛውን ሕዝብ ለማባበል ሲል እንደዚህ ያለ በደል አይፈፅምም። ህወሓት ከጅምሩ የኢትዮጵያን ሃብትና ጥሪቶች አባክኗል፤ አጥፋቷል። እኛን ያስገረመንና ያሳሰበን የህወሓት ወንጀለኛነት አይደለም። ወንጀል የተፈፀመበት ሕዝብ ተከፋፍሎ ለዚህ አረመኔ አገዛዝ ታዛገርና አጎብዳጅ መሆኑ ነው። ተነቅሎ የተዘረፈ መሳሪያ ተጭኖ የተወሰደው ወደ ክልል አንድ፤ ትግራይ ነው። በወቅቱ የቤጌምድር/ሰሜንና ጎጃምን የጣና በለስ ፕሮጀክት አፈራርሶ ዛሬም መብቱን ገፎ ለሚቀጥሉት መቶ ዓመታት እገዛለሁ ይላል። ተገዦዎቹ ለመብታቸው ካልቆሙ የተሃድሶ ግድብ ለእነሱ ህይወት ማሻሻያ፤ ለመስኖ እርሻ መስፋፋት ወዘተ አይውልም። ህወሓት በለመደው ባህርይ የተሃድሶን ግድብ ለራሱ ጥቅም ያውለዋል። የጣና በለስን አፈራርሶ “ያለፈውን እርሱት፤ ዓባይን እገድባለሁ፤ ለእናንተ ጥቅም አውላለሁ” ሲል አመኔታ መስጠት ሞኝነት ነው። ኢትዮጵያ ዓባይን የመገደብ መብት አላት፤ ህወሓት የሚሰራው ግድብ ለነዋሪዎቹ ከፍተኛ ጥቅም የሚል ይሰጣል የሚለው ግን አያዋጣም።

የጣና በለስና ሌሎች የቀድሞ መንግሥታት የመሰረቷቸው መፈራረስና መውደም የምዝበራ፤ የአድልዎና የሙስና ዋቢ ነው። ገዢው ፓርቲ ለግልና ለጠባብ ቡድን ሲል የኢትዮጵያን የተፈጥሮ ሃብት ወደራሱ ኮርፖሬሽንነት ለውጦታል።

ለሃገሪቱ የወደፊት ደህንነትና ለመላው ሕዝቧ የኑሮ መሻሻል ተቆርቋሪነ የማያሳዩ ተግባሮችን በተከታታይ ፈጽሟል። መሬት ለሱዳን መንግሥት ሲሰጥና የጣና በለስን ተቋም ሲያፈራርስና መሳሪያ ጭኖ ወደ ፈለገው ቦታ ሲወስድ አላማ አለው። አማራው በድህነት፤ በበሽታ፤ በኋላ ቀርነት ተበክሎ፤ እንዲሰደድ ነው። ቢቻል እንዲጠፋ ለማድረግ ነው። የአማራው ሕዝብ ቁጥር ከሃያ አምስት ሚሊዮን ወደ አስራ ሰባት፤ አስራ ስምንት ሚሊዮን ኢንዴት ወረደ ብለን የመጠየቅ መብት አለን። ጠይቀን መልስ መፈለግ አለብን። የአማራውን ቁጥር መቀነስ፤ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ "የብሄር ማጽዳት ሴራ" ይባላል። በአንድ በኩል አማራው ውጣ እየተባል በሌላ በኩል ልዩ ልዩ ከተማዎች በተመረጡ የትግራይ ተወላጆች "ቁጥጥር" የዋሉ የሚመስሉ ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል። በጣም የተበሳጩ አገር ቤት የሚገኙ ግለሰቦች "የውስጥ ወረራ ይመስላል" የሚሉት ለዚህ ነው። "የውስጥ ወረራ" ከሆነ ጣሊያን ከዚህ የበለጠ ሊሰራ አይችልም ነበር። ባጭሩ፤ የአማራው ሆነ የኦሮሞው። የአ፟ኡ ሆነ የሶማሌው። የክርስቲያኑ ሆነ የእስላሙ ሰብአዊ መብቶች መገፈፈ የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ መብቶች መገፈፍ መሆኑን መቀበል ያስፈልጋል። የሰብአዊ መብቶች ገፈፋ ወይንም ሰለባ፤ ከዚህ ጀምሮ ከዚያ ላይ ይቆማል የሚባል አይደለም። አፈና ዘር ወይንም ኃይማኖት አይለይም። መከፋፈል ይቁም የምንልበት ዋና ምክንያት ለዚህ ነው። የተከፋፈለ ሕብረተሰብ ደካማና ተጠቂ ነው።

የህወሓት የበላይ አናጺዎች በአማራ ላይ የደመደሙትን ፍልስፍናና ኢላማ አልፈጠሩም። ተውሰውና አጠናክረው ወደ መንግሥት አመራር ለውጠውታል። ዋናዎቹ ፈጣሪዎች- የጣሊያን፤ የእንግሊዝና ሌሎች ቅኝ ገዥዎች ናቸው። የግራ ክንፉ ትርጉም የሰጡት በአዲስ አበባ የንጉሡን አገዛዝ ይቃወሙ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ናቸው። ቀስ በቀስ እየተገለፀ የምናየው፤ የኢትዮጵያ ጠላቶች መሳሪያ ያደረጉት ኢትዮጵያውያን እርስ በእርሳቸው እንዲጨራረሱ፤ በተለይ አገር ወዳዱ እንዲጠፋ ነው። ለምሳሌ፤ አማራው ዋለልኝ መኮንን፤ "The Roots of Political Dysfunction: on the question of nationalities in Ethiopia," HSU, 1969 የጻፈው ከስታሊን የተቀዳ መሰረተ ሃሳብ ክብሪት ሆኖ የብሄር ጥላቻን በማቀጣጠል ለኢትዮጵያ መፈራረስ አስተዋጾ አድርጓል። የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ማንን ያቅፋል የሚለውን ጥያቄ፤ "ኢትዮጵያዊነት የንጉሳዊ ገዢ መደብ በውሸት የፈጠረው። ጥቂት አቢጋዞች የወለዱት ነው" ብሎ ለሻቢያና ለህወሓት ፈጣሪዎች ዘመናዊ መሳሪያ አቅርቦላቸዋል። አባባሉ ከመለስ ፍልስፍና ጋር ይዛመዳል። አቀራረቡ የመደብ ትንተና አልነበረም። ያተኮረው በአማራው የበላይነት ነበር። "ባጭሩ፤ ኢትዮጵያዊ ለመሆን፤ የአማራ ሽፋን መልበስ ግዴታ ነበር።" የኢትዮጵያና የቅኝ ገዥዎች ፍልስፍና አንድ ነው ለማለት ነው። ፈረንሳዮች፤ በገዟቸው አገሮች ሁሉ፤ ፈረንሳይኛ ተማሩ። እንደ ፈረንሳዮች ልበሱ። ብሉ፤ ይሉ ነበር። ፖርቱጋሎች እኛን ለመምሰል ከፈለጋችሁ ተጋብታችሁ ነጭ ሁኑ ይሉ ነበር። አማራው ባህላችሁን አልቀበልም። አልጋባም። ከአማራ ውጭ ሚኒስትር፤ ጀኔራል፤ የክፍለ ሃገር አስተዳዳሪ ለመሆን አይቻልም አላለም። ንጉሡ፤ የአንድ ብሄር ዘር አልነበሩም። ድብልቅ ነበሩ፤ ኦሮሞኛ ይናገሩ ነበር ይባላል። የትምኅርት እድል የከፈቱት ለአማራ ብሄረሰብ ብቻ አልነበረም። ተቀዳሚነት የሰጡት ለኤርትራ ክፍለ ሃገር ነበር። ጸሃፊው፤ "ብሄር፤ ብሄረሰቦች ከተጨቆኑ የመገንጠል መብታቸው መደገፍ አለበት" ብሎ ነበር። ይህን ለማጠናከር፤ "የብሄር ነጻ አውጭ ግንባሮችን፤ ለምሳሌ፣ የኤርትራ ነጻ አውጭ ግንባር፤ ተገንጣይ በመሆናቸው አልደግፍም አልልም። ምክንያቱም፤ <u>የዲሞክራሲ ባህልን ያራምዳሉ"</u> ብሏል። የህወሓት/ኢህአዴግ ህገመንግሥት አቀራረጽ አንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝ ከተባለው ጋር ግንኙነት አለው። ኤርትራ ተገንጥላ ዛሬ ወጣቱ ወደ ውጭ ይጎርፋል።

ባለፉት ሃያ ሶሳት አመታት በቀጥታ ያየነው የህወሓትና የሻቢያ መንግሥታት ለዲሞክራሲ ጸር መሆናቸውን ነው። ሰብአዊ መብቶች ከተከለከሉባቸው ሃገሮች መካከል ኢትዮጵያና ኤርትራ ዝቅተኛ ቦታዎችን በተከታታይ ይዘው እናገኛቸዋለን። የብሄረሰቦች እኩልነት ጥያቄ ዲሞክራሳዊ በሆነ መንገድ እንዲፈታ መጣር አስፈላጊ ነው። በብሄረሰቦች እኩልነት አመካኝቶ ሰብአዊ መብቶችን ሙሉ በሙሉ ማፈን ከዚህ ተጻራሪ ነው። ኢትዮጵያን እንድትፈራርስ ማድረግ ከዲሞክራሲ ጋር ግንኙነት እንደሌላቸው እያየን ነው። የተሰጠው መሰረተ ሃሳብ አንዱ ውጤት ኤርትራ ከእናት አገሯ፤ ከኢትዮጵያ መገንጠሏ ነው። ታሪክ በማያሻማ ደረጃ የሚያስተምረን ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል እንደነበረች ነው። ህወሓት ይኼን ሃቅ ስለካደ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ የባህር በሯን ተነጥቃለች። አሰብ የኤርትራ እንድትሆን ተደርጓል። ሁለተኛውና አሁን ለብሄር ማጽጃ (Ethnic cleansing) በኢህአዴግ ባለስልጣናትና አፈቀላጤዎቻቸው የሚነገረው፤ በብሄር ልዩነቶች ላይ የተመሰረተው፤ የክልል አስተዳደር ህጋዊ መሆኑ ነው። የኤርትራን ፈለግ ተከትሎ ማለት ነው። ኢትዮጲያ የወደብ መብቷን ማስመለሷ የማይቀር ነው የሚል ግምት አለን። ምክንያቱም የኢኮኖሚው ፈጣን እድገትና የአገሪቱ ደህንነት በምርኩዝ እየተራመዱ ነው።

ሶስተኛው አገርን የማፈራረስና ሠብአዊ መብቶችን የሚያፍን አገዛዝ ዘዴ የኢትዮጵያን የውስጥና የውጭ ድንበር ሊመለስ በማይችል መንገድ መለወጥ ነው። ይህ ድርጊት የነዋሪዎችን መንፈስ ያደክማል። የወደፊት ትውልድን የእድገት እድል ይወስናል። አገሪቱን ለአደጋ ያጋልጣል። ሕዝብ ከሕዝብ ያናክሳል። የህወሓት መሪወች በትግል ወቅት ለአረቦች የገቡትን ቃልና ከድጋፍ የተገኘ "ስምምነት" ለማክበር ብዙ አድርገዋል። የኢትዮጵያ መንግሥታት አስበውት

የማያውቁትን፤ የሱዳንና የኢትዮጵያን ወሰን ውሎች በማፍረስ ወይንም በመጣስ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይመካከርበት፤ በምስጢር፤ እርዝመቱ አንድ ሽህ ስድስት መቶ፤ ጥልቀቱ ከሰላሳ እስከ አርባ ኪሎሜትር የሚሆን የለም መሬት፤ በመሬት ውስጥ ያለ የተፈጥሮ ሃብት፤ ወንዝና ተራራ ለሱዳን መንግሥት አስተላልፏል። ይህ፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እድገት ጎጅ። ለነጻነቷ አስጊ። ለሰላምና ለእርጋታ ቀውስ። ለውጭ ተከታታይ ጠላቶቿ ጠቃሚ የሆነ ውሳኔ ነው። ተከታታይ ትውልድ ሊረሳው አይችልም። ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም የቆመ መንግሥት ሲተካ፤ ሊከራከርበትና ሊያስመልሰው ይገባል። ተቃዋሚ ፓርቲዎች፤ ልክ በባህርና በየብስ መብት ላይ የወሰዱት አቋም፤ በድንበሮች ላይም መወሰድ አለበት። የኢትዮጵያ የድንበር ጉዳዮች ስብስብስ የጻፋቸው ዘገባዎች ለዚህ ይጠቅማሉ። በአንጻሩ መነሳት ያለበት የአማራ ህብረተሰብን ፍጹም ለማስንብደድ በደቡብ ክልል፤ ጉራ ፈርዳ ወረዳ፤ በቤኒ ሻንጉልና ሌሎች ክልሎች የአማራ ብሄረሰብ ክብርና መብት ተገፏል። ህጻናት፤ በወሊድ ላይ የነበሩ ሴቶች፤ ሽማግሌዎችና ገበሬዎች ከመሬታቸው፤ ከቤታቸው፤ ከእርሻቸው ተባረዋል። ሃብታቸው ተወርሷል። ዜግነታቸው ተከዷል። ማንም ኢትዮጵያዊ የጉራ ፈርዳውን አማራ ዜግነትና ሰብአዊ መብቶች መገፈፍ በተናጠል ሊያየውና ችላ ሊለው አይችልም። እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ አማራው ሰብአዊ መብት አለው። ህወሓት/ኢህአዴግ ይህን የሚያደርግበት ምክንያት ከላይ ቀርቧል። በተደጋጋሚ የምናየው ክስተት ህወሓትና ደጋፊዎቹ ዛሬ አማራውን፤ ነገ ኦሮሞውን፤ ከነገ ወዲያ ትግሬውን በየተራ እንደሚጎዳ ነው። ነግ በኔ ብሎ አብሮ መነሳት ብልሃት ነው እንላለን።

አማራው ሕዝብ የተፈጥሮ ሃብት እንዳይኖረውና እንዳያድግ በማሰብ፤ የመለስ መንግሥት ከወሎና ከጎንደር ክፍለ ሃገሮች "ሕዝቡ አቤት፤ ተውን" እያለ፤ በእብሪተኝነት የአማራውን አንጡራ መሬት ለትግራይ ክልል ሰጥቷል። ይህ ሕዝብ ያልፈቀደው በሃይል የተደረገ የመሬት ነጠቃ የውስጥ ወረራ ነው። በሰቲት ሁመራና በሌሎች የአማራ "ክልል" ተብለው በሚጠሩ ቦታዎች ትግሬዎችን አስፍሯል። የአማራ ሴቶች ትግሬዎችን እንዲያገቡ ተገደዋል። አላማው የአማራውን ቁጥር ለመቀነስ፤ የትግሬውን ለመጨመር ነው። በጎንደር ከተማ፤ የንግድና የማምረቻ ተቋሞችን ለምርጥ የትግራይ ተወላጆች አስረክቧል። "ጎንደሬ የት ሄደ" የሚባል ሁኔታን ፈጥሯል። ይህ፤ "የውስጥ ወረራ" የሚመስል የመሬትና የሌላ ተፈጥሮ ሃብቶች ንጥቂያ አማራውን ለማዳከም ከተደረገው ሴራ ጋር አብሮ የተያያዘ ነው። በደቡብ ክልል፤ ቤንች ማጂ ዞን፤ ጉራ ፈርዳ ወረዳ፤ በቤኒ ሻንጉል ወዘተ አማራው ከሚኖርበት፤ ከሚያርስበት፤ ለኑሮው ከሚመካበት ቀይ ተባሯል። ተዋርዷል። ዜግነቱ ተገፏል። ይህን ያደረገው "ተአምራዊ እድገት" አምጥቻለሁ። ኢትዮጵያን ዲሞክራሳዊ አድርጌያለሁ። ለሁሉም እድል ከፍቻለሁ ከሚል መንግሥት ነው። እኛ ለማሳየት የምንፈልገው፤ በጋምቤላና በኦሞ ሸለቆ፤ በኦሮሚያና በቤኒ-ሻንጉል፤ በአማራና በኦጋዴን፤ የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ጥያቄ የሰብአዊ መብቶችና የመኖር አለመኖር ጥያቄ መሆኑን ነው። የሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 40 (3) እንዲህ ይላል። "መሬት የኢትዮጵያ ብሄሮች፤ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ኃብት ነው፤ ሊሸጥ፤ ሊለወጥ አይችልም"። ባለፉት ዓመታት፤ ገዢው ፓርቲ ነዋሪዎችን ሳያማክር፤ እንዲያውም እያባረረ፤ ከአራት ሚሊዮን ሄክታር በላይ ለውጭ ኢንቬስተሮች እስከ መቶ ዓመታት ድረስ አስረክቧል። ይኼ ታላቅ የመሬት ስጦታ ተከታታይ ትውልድን ይጎዳል፤ የሃገሪቱን የምግብ ዋስትና ይበክላል።

አንቀፅ 40 (4) እንዲህ ይላል። "የኢትዮጵያ ነዋሪዎች፤ ገበሬዎች መሬት የመያዝ፤ የመጠቀም መብታቸው በሕግ የተጠበቀ ነው። ከቀያቸው ያለፈቃዳቸውና ያለ ተመጣጣኝ መተኪያ ካሳ ሊወገዱ አይችሉም"። የኦሞ ሸለቆ፤ የአፋር፤ የጋምቤላንና ሌሎች ክልሎች ነዋሪ ይህ ሕግ ሊያገለግለው አልቻለም። ነዋሪዎች ከቆቻቸው እየተገደዱ በልማት ስም ወደ አዲስ መንደሮች ያለ ምንም ጠቃሚ መተኪያ እንዲሰፍሩ ተገደዋል። ገዥው ፓርቲ መመሪያ ያደረገው የመሬትን ወላዊነት፤ የነዋሪዎችን መብት ትኩረት በመስጠትና ዝቅተኛ አምራቾችን በማፎልመስ አይደለም ማለት ነው። እኛ የምንመክረው የኢትዮጵያ የጀርባ አጥንት የኢትዮጵያ አምራቾች ናቸው። ማንኛውም ማእከላዊ መንግሥት የእድገት ዓመራሩን ስልት የመቀየስ ሃላፊነት አለበት። የባጀት፤ የእርዳታና የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም እቅዶችንና ተግባሮችን ትኩረቶች አውጥቶ ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነት ይጠበቅበታል። የነጻ ገበያ አባትና አለቃ የሆነው አሜሪካ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ልማት ያለው አስተዋፆ ከፍተኛ ነው። ለምሳሌ፤ በሳይንስ፤ በጤና፤በደህንነት ወዘተ ቴክኖሎጂ ምርምርና አመራር። የፌደራል መንግሥቱ ከክፍለ ሃገሮች የበለጠ የመዝናኛ መሬቶችን ይመራል፤ ለተፈጥሮ እንክብካቤ ከፍተኛ አስተዋፆ ያደርጋ። የደህንነትና የመእከላከያ ክፍሉን ሙሉ በሙሉ ይቆጣጠራል ወዘተ። ስከሆነም፤ በመሬት፤ ወንዝ፤ ተራራ፤ የብስና ሌሎች ላይ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው። ለወል ለሆነው ሃብት ትኩረት ይሰጣል ማለት ነው። ስለዚህ፤ በኢትዮጵያም የፌደራል መንግሥቱ ለወል ሃብቶች ተንከባካቢነት፤ ለህብረተሰቡ አገልግሎትና ለብሄራዊ ባጀት አጠቃቀም ተመሳሳይ ሚና እንዲኖረው ያስፈልጋል። ዋናው ከሚዛኑ ላይ ነው። የግሉና የፓርቲ/መንግሥቱ።

በተፈጥሮን ሃብት አጠቃቀም መስፈርት ሲታይ፤ገዢው ፓርቲ ትኩረት የሰጠው ለአንቀፅ 40 (6) ይመስላል። "መንግሥት ነዋሪዎችን ሳይጎዳ መሬት ለልማት ሊያውል ይችላል" ለሚለው። በከተማ ሆነ በገጠር የችግሩ መንስኤ ይህ

ነው። ግልፅነትና የሕግ የበላይነት በሌለባት ኢትዮጵያ መንግሥስት ከነዋሪዎች መሬት ሲነጥቅ ማንን አማክሮ፤ ምን ያህል ተገቢ መተኪያ ሰጥቶ፤ ምን አይነት ውል ተስማምቶ፤ ማንን ጠቅሞና ማንን ጎድቶ እንደሆነ አይታወቅም። ውሳኔዎች ሁሉ የፖለቲካ ሆነው ይታያሉ። ነዋሪዎች ጠበቃ የላቸውም። ለሙብታቸው ለመከራከር አይችሉም። የችግሮቹ እምብርቶች እነዚህን ይመስላሉ።

የመሬት አመራርንና አጠቃቀምን ይዘት ስናይ፤ መንግሥት ህገመንግሥቱን እንደፈለገ ተርጉሞታል። በአንድ በኩል አማራውንና አፏኩን፤ ኦሮሞውና ሶማሌውን፤ ወዘተ "ለራስህ ልማት ስትል ውጣ" ይላል። በሌላ በኩል የትግራይ ተወላጆችን "አዋሳ ሆነ ጎንደር፤ ጋምቤላ ሆነ ሃረር፤ ባህር ዳር ሆነ ጅማ ወዘተ" ለመስፈርና ሃብት ለመያዝ መብታችሁ ነው ይላል። የህግና የዜግነት መብቶች በፖለቲካ የሚወሰኑ መሆናቸውን ያሳያል። የጠባብ ጎሰኛነት አድልዎ የሚከሰተው በፖለቲካ የበላይነት ብቻ አይደለም። በተፈጥሮ ሃብትና በኑሮ መሻሻል ጭምር ነው። ከሚኖርበት መሬት የተባረረውና መብቱ የተገፈፈው የአማራ ብሄረሰብ በህዳር 3, 2005 ዓም ለአዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር፤ ለአቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝ የጻፈው አቤቱታ የሰብአዊ መብቶች መገፈፍ ያመጣውን በደል በበለጠ አስቀምጦታል። የኢትዮጵያ መንግሥት፤ በተደጋጋሚ፤ የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ የተቀበላቸውን ሰብአዊ መብቶች ጥሷል። ከጉራ ፈርዳ፤ ከቤኒ ሻንጉል ጉሙዝና ሌሎች ቦታዎች የተባረረው የአማራ ብሄረሰብ ሕዝብ የሚጠይቀው ዓለም የተቀበለውን፤ ህገመንግሥቱ በግልጽ ለዓለም ህብረተሰብ ያስታወቀውን የዜግነት መብት ነው።

- "በህገመንግስቱ መሰረት፤ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሃገሪቱ ውስጥ፤ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደሪያው የመረጠውን ስራ ለመስራት መብት አለው (አንቀጽ 43/1)።
- ሁሉም ኢትዮጵያዊ መተዳደሪያውን፤ ስራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው (አንቀጽ 43/2)።
- መንግሥት ለስራ አጦችና ለችግረኞች ስራ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ ይከተላል (አንቀጽ 42/6)።
- መንግሥት ዜጎች ጠቃሚ ስራ የማግኘት እድላቸው እየሰፋ እንዲሄድ ለማድረግ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል (አንቀጽ 43/7)" ይላል።

ሕግ በወረቀት ላይ መቀመጡ ሳይሆን በተግባር ያለ ፖለቲካ ተፅእኖ ከስራ ላይ መዋሉ ነው ተቀባይነት የሚሰጠው። እአንባቢው መፍረድ ያለበት ቀላል ነው። የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት ስራ ለሌላቸው በተፈለገው መጠን ስራ ለመፍጠር ችሏል ወይንስ አልቻለም። መልሱ አልቻለም። መንግሥት የራሱን ህገመንግሥት አላከበረም። ካላከበረ፤ በመጀመሪያ ለምን የሚዳኝ ሕግ ነው ብሎ ተቀበለ? አማራው ከሚኖርበት የሚባረርበት የሕግ ልዩኑነት ግልጽ የሚሆነው አማራው "ጠላት ነው" ተብሎ ስለተፈረደበት ከአማራ ክልል ውጭ ካሉ ክልሎች ማባረር ለማዳከመም ከሚደረግ ሴራ ጋር አብሮ የሚሄድ ነው። እናወዳድር። በአንጻሩ፤ ትግሬዎች ጎንደር ለመስራት፤ በጎንደሬዎች መሬት ለመስፈር፤ ሰባ አምስት በመቶ የሚሆነውን የጋምቤላ ለሃገር ኢንቬስተረች የተሰጠ የእርሻ መሬት ለመያዝ መብት እንዳላቸው ተደርጓል። (Oakland Institute, International Rivers). በትግሬነታቸው በየትኛውም የኢትዮጵያ መሬት ለመሰማራት ይችላሉ። ስለዚህ፤ ህገመንግሥቱ ሙሉ በሙሉ የፖለቲካ መሳሪያ ሆኗል። በሰብአዊ መብት መስፈርት ሲታይ፤ ህገመንግሥቱ ከስራ ላይ ያዋለው ሁሉን አስተናጋጅ የሆነ የማህበረሰብ አመራር አይደለም። የዓለምን ህብረተሰብ ድጋፍ በማጭበርበር ለማግኘት የተጸነሰ መሳሪያ ነው። ይኼን ስንል የትግራይ ሕዝብ በሙሉ የአድሎዎው ተጠቃሚና ደጋፊ ነው ማለታችን አይደለም።

ከፕሬዘደንት ሬገን አስተዳደር ጀምሮ፤ የአሜሪካ መንግሥት ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር፤ ደጋፊ መንግሥት ለመፍጠር ፍላጎት ነበረው። ዚቢነው ብሬዥንስኪ፤ የአሜሪካ የደህንነት አማካሪ፤ ሶቭየቶችን በመጥላት፤ ለሶቭየቶች አጎብዳጅ የሆኑትን፤ "ኩባን፤ አንጎላን፤ ኢትዮጵያን፤ ወዘተ ማድከም" አለብን ብሎ ነበር። ሻቢያና ህወሓት ለዚህ አመች የነበሩ ወንፊቶች መሆናቸውን አይተናል። ፕሬዚደንት ክሊንተን፤ በአፍሪካ እያበቡ የሚገኙት "አዲስ የዲሞክራሲ ኮከቦች ሙሰቨኒ፤ መለስ፤ ካጋሚ ወዘተ ናቸው" ሲል በይፋ ነበር። "ዲሞክራቱ መለስ አምባገነናዊ" ሆኖ ተገኝቷል። ዋለልኝ መኮነን ያሰበው፤ ኢትዮጵያ የምትባል አገር ትርጉም የሚኖራት "አማራ፤ ትግሬ፤ ኦሮሞ፤ አደሬ፤ ሶማሌ፤ ወላሞ፤ ጉራጌ ወዘተ በእኩልነት የሚኖሩባት ኢትዮጵያ ስትፈጠር" ነው ያለውና እኛም የምንጋራው በስራ አልተተረጎመም። እኩልነት ከሌለ ግጭት አይቀርም። ዩጎስላቪያ የሆነውን ማስታወስ ይጠቅማል። አማራን ማባረር እኩልነት፤ ፍትህ፤ እድገት አይፈጥርም። አፏኩን ከቅድመ አያቶቹ መሬት ማስወጣት እኩልነትና እድገት አይደለም። ለትግሬዎች አድልዎ ማድረግ እኩልነትን ማጠናከር ሳይሆን ለጠባብ ብሄር አድሎ ማድረግ ነው። ቂም በቀል ፈጣሪ አመራር ነው። የበለጠ እድል መስጠት ማለት ነው። እነዚህ ሁሉ፤ የሰብአዊ መብቶችን መደምሰስ ያሳያሉ።

አራተኛው ቁልፍ የአገዛዝ መንገድ እርጋታ እንዳይኖር ጠብ መጫር የሚል ነው። በባድሜ ምክንያት የተካሄደው ጦርነት በውስጡ፤ “የወንድማማቾች ጦርነት” ነው ለማለት ይቻላል። መለስ፤ የቅርብ ግብረ አበሮቹና ኢሳይያስ አፈወርቂ ጠላቶች ነበሩ ለማለት ምንም ማስረጃ የለም። በጠባብ ብሄርተኛነት፤ በውጭ ጠላቶች የተቀነባበረ፤ ኢትዮጵያን የማፈራረስ ዘመቻ የተካሄደው በሻቢያና በህወሓት ህብረት ነው። በቂም በቀልነት የተዋቀረ አመጽና ለውጥ፤ ከጠባብ ብሄርተኛነቱ ነጻ ለመውጣት አልቻለም። ስልጣን ይዞ ለመቆየት የሚችለው፤ የኢትዮጲያን ሕዝብ በመከፋፈል ብቻ ነው። በነጻነት፤ በዲሞክራሳዊ፤ በሕዝብ እኩልነትና ስልጣን አይደለም። በትጥቅ ስልጣን ይዣለሁ፤ በትጥቅ አውርዱኝ የሚል አገዛዝ ነው። የባድሜ ጦርነት፤ ብዙ ቢሊዮን ብር ጠፍቶበታል። ከሰማንያ ሽህ በላይ ሕዝብ አልቋል። የዚህ ዋጋ የተከፈለበት ጦርነት ውጤት የአልጀርሱ፤ የተቻቸሎ ለጊዜው መኖር የሚመስል ስምምነት ብቻ ነው። የማይተካ ዋጋ ተከፍሎ፤ ህወሓት/ኢህአዴግ የመራው የኢትዮጵያ መከላከያ ሊገፋና የባህር በር ለማስመለስ ሲችል፤ የህወሓት የበላይ አመራር፤ አሰብን ለማስመለስ ፈቃደኛ አልነበረም። ጦርነቱ የተካሄደበትን ምክንያት መለስ ለሕዝብ በሚገባ ለማስረዳት አልፈለገም። ባጭሩ ለመናገር የሚቻለው፤ ዋጋ ከፋዩ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ነው። ሰላሙና እርቁ የረዳው ጠባቡን የህወሓት የበላዮች ነው። ግብግቡ፤ የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት ትግል ነው። የኢትዮጵያንና የመላው ሕዝቧን ዘላቂ ጥቅም ለማስከበር አልነበረም። ባድሜ፤ አሁንም “የተቀበረ ቦምብ” የሚመስለው ለኢትዮጵያ ጠቃሚ ውጤት ባለማሳየቱ፤ ጠባብ የትግርኛ ተናጋሪዎች፤ የስልጣን የበላይነት ግብግብ በመሆኑ ነው። የኤርትራ ተወላጆች ከፈተኛ ስልጣን ይዘው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰሩበት ምን ኢትዮጵያዊ ምክንያት አለ? የለም። በባድሜ ጦርነት የተጎዳው፤ የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝብ ነው። የሁለቱም ህብረተሰቦች መሪዎች ለምን ወደ ጦርነት እንደሄዱ ተጠያቂዎች አልሆኑም። የኢሳይያስ አፈወርቂ አምባገነን መንግሥት አንዳለ ነው። የህወሓትም እንደዚሁ። ሁለቱም፤ ሰላምን፤ እኩልነትን፤ ፍትህን፤ የህግ የበላይነትን፤ ዲሞክራሲን፤ የሰላም ጉርብትናን አይፈልጉም፤ ቆይታቸውን የሚያረጋግጡት፤ ሰብአዊ መብቶችን በመከልከል ነው።

አምስተኛው የአገዛዝ ቆይታ ዘዴ በአፍሪካ ታሪክ፤ ገቢና ሃብት የሚገኘው የፖለቲካ ስልጣን በመያዝ ብቻ ነበር የሚልው መሰረተ ሃሳብ ነው። ህወሓት በዚህ ከፖለቲካ ስልጣን ጋር በተያያዘ የገቢ ማደግ፤ የሃብት ክምችት፤ የብሄር ማጽዳት (Ethnic cleansing)፤ የግልና የቤተሰብ ኑሮ መሻሻል፤ ከሙስና የመነጨ፤ ከሕግ ውጭ ሃብት የማሸሽ ልምድ የተካነ ሆኗል። የመለስን መንግሥት “ተአምራዊ እድገት ያስገኘ፤ እንደነ ሌኒንና እንደነ ማኦ ሴቱንግ ታሪክ የተመዘገበለት፤ የእድገት ጀግና” ብለው የሚጠሩት ተጠቃሚ ግለሰቦችና ድርጅቶች የረሱት ጎሳዊ አድልዎና ሙስና፤ አገሪቱንና ህብረተሰቡን እያደቀቃቸው የሄደ መሆኑን ነው። የኢትዮጵያ ሃገራዊና ብሄራዊ <u>ምሰሶ እየተናደ ነው።</u> ይህ ምሰሶ ከወደቀ ኢትዮጵያ የምትባል አገር አትኖርም። ጎሳዊ አመራር ዙሮ ዙሮ ይኼን ምሰሶ እንደሚንደው አያከራክርም። ሁሉን በፍትህ ለማስተናገድ የማይችል ልክ እንደ ዓለም የኳስ ጨዋታ “የኔ ቡድን ብቻ ያሸንፍ” የሚል የፖለቲካ ግብ ግብ አጥፊ ነው። የኔ ቡድን ወይንም መደብ ብቻ መብት አለው የሚለው አጥፊ አስተሳሰብ እንኳን ኋላ ቀር በሆነች ኢትዮጵያ፤ የዓለም መሪ በሆነው አሜሪካም እያየነው ነው። አንድ ከመቶ የተባለው መደብ ስልጣኑን፤ ጥቅሙን ለመካፈል አይፈልግም። ህወሓት የስግብግቦችን የነጻ ገበያ የሚመስል ብልጣብልጥ ፈለግ ተከትሏል። የፖለቲካ ስልጣን ያባልጋል። በብልግና ኑሮን ያሻሻለ፤ ሃብት ያካበተ፤ ፍትሃዊነትን አይቀበልም። ለመቀበል የሚያስገድደው አንድም ነገር የለም። አድልዎና ሙስና፤ ህብረተሰቡን እያደቀቁት መሆኑን ለማወቅ መጠየቅ የሚገባቸው የገዢው ፓርቲ አለቃዎች፤ ሰላዮች፤ ደጋፊዎች አይደሉም። ተራው ህዝብ ነው። ለመቶ ኪሎ ስንዴ ከዘጠኝ መቶ እስከ ሽህ ብር። ለመቶ ኪሎ ገብስ ከዘጠኝ መቶ አምሳ እስከ ሽህ ብር። ለመቶ ኪሎ ጥቁር ጤፍ ከዘጠኝ መቶ ሰማንያ እስከ አንድ ሽህ ሰማንያ ብር። ለአንድ ኪሎ ሽሮ ሃያ አራት ብር። ለአንድ ኪሎ ስኳር፤ አምሳ ብር። ለአንድ ዶሮ መቶ ሰማንያ ብር ወዘተ የሚከፍለው ሕዝብ ነው። የዋጋ ግሽፈት፤ ላለው የህወሓት አዲስ ሃብታም አይሰማውም። ህወሓት፤ ድምጽን፤ ነጻ ፕሬስን፤ የሚፈራው፤ ሃቁ ስለሚጎዳው ነው። የዋጋ ግሽፈት ውሸት የእድገት ውጤት ነው ተብሎ ተደጋግሞ ሲነገር እውነት ይመስለዋል። የማይካደው አንኳር ነገር፤ የዋጋ ግሽፈት፤ጎሳዊ አድልዎና ሙስና ህብረተሰቡን እየጎዳው ነው። እድገቱን እየገታው ነው። በመንግሥት ያለውን እምነት በሙሉ እየበለው ነው። ይህ አደጋን ያመጣል። መንግሥት እነዚህ ሁሉ ችግሮች እንዳይታወቁ ጸረ-ሽብርተኛ ህግ ተጠቅሞ ማንም አንዳይናገር አድርጓል። ተቃዋሚውን እያደኑ ማሰር ፖሊሲ ወለድና መዋቅራዊ የሆነው የኑሮ ችግር አይፈታም። Oxfam, 2014, “Ethiopia is 123rd of 125 worst fed countries in the world.” The UN World Food Progarm 2014 Assessment, “14 million Ethiopians are at risk; and the heart of the looming catastrophe (hidden) is Ethiopia where 10 million are in need of emergency food.” የውጭ አገር መንግሥታት፤ በተለይ አሜሪካ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት የተቻላቸውን የሚያደርጉ መሆኑን እናምናለን። ችግሩ መሰረታዊ የሆነው የግብርና ስራ እቅድና የዓምራቾችን አቅም የማጎልመሱ ተግባር አመርቂ በሆነ መንገድ አለመካሄዱ ነው።

ስድስተኛው የአገዛዝ ብልሃት አብዮታዊ ዲሞክራሲን፤ ማለትም፤ የአንድ ጎሰኛ ፓርቲንና የጎሰኛ ተባባሪዎችን የበላይነትን ከዘመናዊ ካፒታሊስት የኢኮኖሚ አመራር ጋር ማያያዝ ነው። ለዚህ ራስን አገልጋይ ለሆነ ፍልስፍና ከኢትዮጵያውያን ምሁራን የበለጠ እውቀት ያለው አሜሪካዊ ምሁር ትምህርት ሰጥቶናል። ቴወድሮ ቬስታል፤ "የማርክሲስት-ሌኒንስት አለቃ መለስ ዜናዊ፤ የካፒታሊስት ጠበቃ" (Meles Zenawi: the Marxist-Leninist Master of "Capitalist" Speak" በሚል ጽሁፉ በ2012 መጨረሻ፤ የመለስን እልፈት አያይዞ ያቀረበው እድገታዊው መንግሥት ያመጣውን ጣጣ በሚገባ ገልጿል። "መለስ ጥቂት አወዳሾች፤ ብዙ ተቃዋሚዎች" የነበሩት፤ የአፍሪካ አምባገነን ("Bigman) በመሰረተ ሃሳቡ የአልባኒያ አይነት ሌኒኒስት ነበር። ኤሪትራን ከኢትዮጵያ ያስገነጠለ። የብሄር አስተዳደርና አገዛዝ በህግ ያቋቋመ ነበር" ይላል። መለስ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ብሎ በህብረተሰቡ ላይ የጫነው እርዩተዓለም፤ "ከዲሞክራሳዊ አገዛዝ-ስልጣን መከፈፋል/መጋራት--ጋር ምንም ግንኙነት የለውም።" የመለስ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ሌኒን ዲሞክራሳዊ ማእከል፤ "ተወያይቶ ወደ ተግባር መጓዝ" የሚለውን በስራ አልተረጎመውም። ቬስታል ይቀጥልና፤ የአንድ ፓርቲ አምባገነን አመራርና ህገመንግሥቱ በቀጥታ የተያያዙ ናቸው ይላል። እአአ በ 1995 ሕዝብ ሳይወያይበት የጸደቀው ህገመንግሥት የኢትዮጵያ የበላይ ሕግ ነው (Supreme Law of the land) የተባለው፤ ሙሉ በሙሉ ያጠናከረው የህወሓት/ኢህአዴግን ፍፁማዊ የበላይነት ነው። "እንደውነቱ ከሆነ፤ የመለስ ኢትዮጵያ ፌደራል ዲሞክራሳስዊ ሪፐብሊክ፤ <u>የአንድ አምባገነን ፓርቲ መንግሥት ነው"</u> ብሏል።

የፖለቲካ ሆነ የኢኮኖሚ የበላይነቱን ያጠናከረው ህገመንግሥቱን ተጠቅሞ ነው። የግለሰብ መብት የገፈፈውና የብሄር ማጽዳት ዘመቻ የሚያካሂደው ህገመንግሥቱን ተጠቅሞ ነው። መድብለ ፓርቲ እንዳይኖር ያደረገው ህገመንግሥቱን ተጠቅሞ ነው። "አንድ ለአምስት" የተባለ የስለላ ሰንሰለት የፈጠረው ህገመንግሥቱን ተጠቅሞ ነው። ህገመንግሥቱ ዲሞክራሲ፤ የሕግ የበላይነትና እኩልነት፤ የሰብአዊ መብት መከበር፤ የፕሬስ ነጻነት፤ ለስልጣን የመወዳደር፤ የመነጋገር፤ የመሰብሰብ፤ የግል ሃብት ዋስትና የማስጠበቅ መብት አለ የሚለው ሁሉ ፕሮፓጋንዳ "ለጋስና አበዳሪ ድርጅቶችን" ለማታለል ነው" በማለት ደምድሟል። ያልጨመራቸው ሁለት ነጥቦች አሉ። አንድ፤ መንግሥቱ የተመሰረተው በጎሳ ስብስቦች/ፓርቲዎች መሪዎች የበላይነት ነው። ሁለት፤ አበዳሪዎች መንግሥቱን የሚደግፉት የራሳቸውን ጥቅም የሚያገለግል መሆኑን ስላወቁ ነው። "ጀርባየን እከክልኝ፤ አክልሃለሁ" በሚል። ባጭር አባባል፤ ህወሓት/ኢህአዴግ ህገመንትሥቱንና ተቋሞችን "እንደ ማጥቂያ መሳሪያዎች" ተጠቅሞባቸዋል። ህገመንግሥቱን ለሰብአዊ መብቶች አፈና ይጠቀምበታል።

ሰባተኛው የአገዛዝ ብልሃት ኋላ ቀርና ደሃ ሕዝቦችንና ክልልሎችን ለራሳቸው ሲባል፤ በውሳኔ ላይ ሚና ሳይሰጡ፤ ከድህነት ነጻ ማውጣት አለብን የሚል ብልሃት ነው። ህገመንግሥቱ መሬትና ሌላ የተፈጥሮ ሃብት የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አንጡራ ሃብት ነው ይላል። ይህ ጥበብ ለህወሓት መሪዎች ልቦና የ(Intelligence) የበላይነት ይሰጣል። ኋላ ቀር ክልሎችን ተከታይ ያደርጋል። የህወሓት የበላዮች፤ "መሬት የሚሸጥ/የሚለወጥ በመቃብራችን ላይ ነው" ብለው ነበር። ዛሬ በተፈጥሮ ሃብት የሚያዘው የኢትዮጵያ ሕዝብ አይደለም። በተለይ፤ የህወሓት የበላይ ባለስልጣኖችና ታማኝ ደጋፊዎቻቸው ናቸው። በደጋፊዎቻቸው የእድገት "ጀግና" የሚል የተለየ መጠሪያ የተሰጠው መለስ፤ በሃገራችን ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ፤ እስካሁን ብቻ፤ ከአራት ሚሊዮን ሄክታር በላይ የሆነ ለም መሬት፤ ወንዞችና ጅረቶች ከሰላሳ ድስት አገሮች ለመጡ ከበርቴዎች እስከ ዘጠና ዘጠኝ አመታት ድረስ እንዲጠቀሙበት አብርክቷቸዋል። ምርቱንም ለውጭ ገበያ እዲሸጡ ራሱ ፈቅዷል። የዚህን ለም መሬት ለውጭ ኢንቬስተሮች ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታና የማህበረሰብ ጥቅም ውሎች ማስረከብ አደጋ በአንድ ምሳሌ እናብራራለን። የሞዛምቢክ መንግሥት የምግብ ዋስትና፤ የስራ እድልና የደሃውን ኑሮ ማሻሻል በሚል እምነት ብዙ ለም መሬት ለውጭ ኢንቬስተሮች አከራየ። አንድ ሰፊ ጥናት ያሳየው ሆዮ ሆዮ በተባለ ቦታ ሃያ አምስት ሺህ ኤከር መሬት ለአንድ የፖርቹጋል ኩባንያ ያከራያል። ነዋሪዎች ይጠቀማሉ፤ የስራ እድል ይፈጠራል፤ ገቢ ያድጋል፤ የምግብ ዋስትና ይኖራል፤ የቴክኖሎጅ ልምድ ይስፋፋል ወዘተ የሚለው እምነት ወና ሆነ። ትምህርት ቤቶች፤ የጤና ጣቢያዎች ወዘተ እሰራለሁ ያለው የግል ድርጅት የገባውን ቃል ለማሟላት አልቻለም። እንዲያውም፤ ልክ ጋምቤላና የኦሞ ሸለቆ እንደሆነው፤ ነዋሪዎች ከመሬታቸውና ከለመዱት የስራ ልምድ ተባርው የበለጠ ደሃና ስደተኛ ሆኑ። ትምህርቱ የእርሻ መሬትና ውሃ እየጠበበ በሄደበት በአሁኑ ዓለም እንደ ኢትዮጵያና ሞዛምቢክ የመሳሰሉ ደሃና ኋላ ቀር አገሮች ለኢንቬስተሮች መሬታቸውን በሚያሳፍር ዋጋ፤ ግልፅነት በሌለው ማህበራዊ ጥቅም ማከራየት "በአገርና በወገን ላይ የሞት ፍርድ መፍረድ ነው" የሚል ድምዳሜ በሰፊው ይነገራል። መሰረታዊው ጥያቄ መሬቱን ማን ይረሰው፤ ማን ያልማው፤ ማን ይጠቀምበትና እንዴት የሚሉት ናቸው። በእኛ ግምት ቁልፉ የኢትዮጵያን ዝቅተኛ አምራቾችና የኢትዮጵያን ኢንቬስተሮች አቅም ማጎልመስና ባለቤትነታቸውን ሕጋዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው። (Out of Africa: the next breadbasket, National Geographic, July 2014).

የኢትዮጵያ መንግሥት፤ ለህብረተሰቡ አገልግሎትና አቅርቦት ግዴታ የሌለበት ውል ተፈራርሟል። የከተማና የገጠር መሬት ለገዢው ፓርቲ ፖለቲካ ስልጣን መቆያ፤ ለውጭ ኢንቬስተሮች ወዳጅ መግዣ፤ ለውጭ ምንዛሬ ማጠናከሪያ፤ ለውስጥ ወዳጆች መሳቢያ፤ ለምርጥና ታማኝ ግለሰቦች ገቢና ሃብት ማካበቻ፤ ለጎሳዊ አድልዎና ሙስና ዋና መሰረት ሆኖ ያገለግላል። መሬትንና ከመሬት ስር ያለ የተፈጥሮ ሃብት የያዘ ይገዛል። ይከብራል። ወዳጅ ያፈራል። ህወሓት፤ በተቀጣይነት፤ ኢህአዴግ የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሃብት፤ በተለይ ለም መሬትንና ውሃን የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚ የበላይነት ማቆያ፤ የዲፕሎማቲክ ወዳጅ መግዣ አድርጎታል።

የቀረው ተራው ሕዝብ፤ መኖሪያ ቤት ለማግኘት ህልም የሆነበት መሆኑን ለማወቅ በአዲስ አበባ ብቻ፤ ከአንድ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን በጠለላ፤ በመንገድ የሚኖሩ መሆናቸውን ማጤን ያስፈልጋል። መሬቱን ተነጥቆ፤ ለስደት የተዳረገውን የጋምቤላን፤ የቤን ሻንጉልን፤ የደቡብ ኦሞን ሕዝብ ሁኔታ ማጤን ያስፈልጋል። ሕዝብ ቀን በቀን የሚያስፈልጉት ቁሳቁሶች፤ ምግብ፤ መጠለያ፤ ልብስ፤ ውሃ፤ በኢትዮጵያ ብርቅ ናቸው። በአዲስ አበባ፤ የመኖሪያ ቤት እጥረት ከየትም አፍሪካ አገሮች የባሰ ነው። አንድ የኮሌጅ ምሩቅ፤ አንዲት ክፍል ለመከራየት ደመወዙ ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ከሚበላው ምግብ ቀሪ የለውም። ተዳብሎ መኖር አለበት። የመንግሥት ዝቅተኛ ሰራተኛ፤ ታክሲ ነጅ፤ የትንሽ ሱቅ በደረቴ ባለቤት፤ ቤት መግዛት፤ ወይንም መስራት ቀርቶ፤ መከራየት ከማይችልበት ደረጃ ደርሷል። ገንዘቡ ረክሷል። የሚገዛው ሁሉ ውድ ሆኗል።

ህወሓት በስራ ላይ ያዋለው የመሬት ፖሊሲ ተራውን ሰው ቤትና መሬት አልባ የሚያደርግ ነው። ደሞዝተኛውና ሱቅ ያለው፤ ሁለት ምግብ በቀን ለመብላት እየተቸገረ ነው። የሚያስደነግጠውና የሚያስቆጣው፤ "ተአምራዊ እድገት" ታሳያለች በምትባለው ኢትዮጵያ፤ በከተማ፤ በተለይ፤ በአዲስ አበባ የሚኖሩ ደሃ ቤተሰቦች ቤታችሁ "የእናንት አይደለም። ሰፋሪዎች ናችሁ። መሬቱ የመንግሥት ነው" እየተባሉ፤ መሬቱ ለባለስልጣናት ኪራይ ሰብሳቢዎች፤ "የኮንትራት ሃብታሞች" ሲሰጥ ይታያል። በሚሊዮን የሚቆጠረው በመጠለያ የሚኖረው ለዚህ ጭምር ነው። መኢአድ በአንድ መግለጫ ያወጣው ዘገባ እንዲህ ይላል። ህወሓት/ኢህአዴግ "ሕዝቡን (በራሱ አገር፤ በራሱ ከተማ) ባሪያ አድርጎ የሚያኖር መንግስት ሆኗል።" በሌሎች የቅኝ ግዛት የነበሩ የአፍሪካ አገሮች እንኳን፤ የዚህ አይነት አፈና፤ ጫና፤ በደል፤ ግፍ፤ ከአፓርታይድ ደቡብ አፍሪካ ውጭ አልተደረገም። ለምን እንደዚህ ይሆናል ብሎ ለመጠየቅ ሙብት የለም። መሬት ከኢትዮጵያ ተራ ሕዝብ መነጠቅ ከጀመረ ቆይቷል። ምክንያቱም፤ መሬት ለህወሓት/ኢህአዴግ የበላይ ባለስልጣናት፤ ታማኞች፤ ወዳጆች፤ የውጭ ደጋፊዎች በእጅ የተያዘ የኪራይ መሰብሰቢያ (Rent Extraction) የትርፍ ምንጭ፤ የስልጣን ማጠናከሪያ፤ የጠላት ማድከሚያ፤ ለጉቦ፤ ለአድልዎ፤ ለሙስና የዋለ ሆኗል።

ማስረጃ ካቀረቡት መካከል፤ የሮጀር ካሎው፤ የአለን ማክኖዶላንድና የፔፒርስ ክሮስ አከራካሪ ሊሆን አይችልም። "የመሬት ባለቤትነቱ የታገድው ደሃ ገበሬ፤ ቤት እሰራለሁ ብሎ ተስፋ የሚያደርገው የመንግሥት ሰራተኛ፤ ፋብሪካየን አስፋፋለሁ ብሎ የሚጥረው ነጋዴ፤ ወዘተ፤ ግራ የገቡበት ምክንያት አለ። ህንዶች፤ ሳውዲዎች፤ ምርጥ የህወሓት ደጋፊ የትግራይ ተወላጆች፤ የፓርቲው የበላዮች መሬት ሲሰጣቸውና የግል አድርገው ሲጠቀሙበት፤ ተራው ኢትዮጵያዊ የመሬቱ ባለቤት ለመሆን ህልም የሆነበት ለምንድን ነው" የሚለው ነው። የመሬት ሃብት ዋስትና የሌለው ግለሰብ የኑሮ ዋስትና የለውም። ዜግነቱ ተገፏል። ለሃገሩ ቀርቶ ለራሱ ቤተሰብ ለማሰብ ያዳግተዋል። ከድህነት ነጻ ለመውጣት አይችልም። አስተማማኝ ነው የሚለው ዋስትና ያለው ሃብት አይኖረውም። የመሬት ጥያቄ፤ የኢኮኖሚ መብት፤ የሰብአዊ መብት፤ የዜግነትና የሰው ክብር፤ የማንነትና የተከታታይ ትውልድ እድገት ወይንም ድህነት ጥያቄ ነው። መንግሥትን የማመን ወይንም ያለማመን ጥያቄ ነው። ከሁሉም በላይ የአመራር በደል፤ የአገዛዝ መጥፎነት ምልክት ነው። በህ-ገመንግሥቱ መሰረተ ቢሰራ ኖሮ፤ መሬት አሁንም የአንድ የገዢው ፓርቲ ሃብት አይሆንም ነበር። የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ጥሪት ነው። መለስ ትቷቸው ካለፈው የፖሊሲ ግድፈቶች አንዱና ዋናው የመሬት ጥያቄ የሚሆነው ኢትዮጵያውያን "ታዝዥና ጭሰኛ፤ ጥገኛ፤ ቤት አልባ፤ በጠለላ ኗሪ" ስላደረጋቸው ነው። በህይወታቸው፤ በተፈጥሮ ሃብታቸው፤ በሚኖሩበት መሪትና ቤት ለማዘዝ አልቻሉም። ሌላው ቀርቶ ቤተክርስቲያን ወይንም መስጊድ ለመስራት የፓርቲውን ፈቃድ መጠየቅ አለባቸው። " እድገት አለ የሚባለው" ትርጉሙ ምንድን ነው የሚለው ሕዝብ እየጨመረ የሄደው በዚህ ምክንያት ነው። ጥያቄው ተጠቃሚው ማነው? መልሱ፤ እድገት ያለ ነጻነት ፍትሃዊና ስኬታማ አይሆንም ነው። ነጻነት ከሌለ እድገቱ ትርጉም የለውም። ነጻነት ከሌለ፤ ይገባኛል ብሎ በህግ ለመከራከር አይቻልም። ስለዚህ፤ ዛሬ፤ የኢኮኖሚውና የማህበረሰብ አመራር ፖሊሲው ከሰብአዊ መብቶች መገፈፍ ጋር አብሮ ሄዷል። ለሰብአዊ መብቶች እገዳና አፈና መሳሪያ ሆኗል። ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት ያወጧቸውን የሰብአዊ መብቶች ደንቦች፤ ህጎችና መመሪያዎች ፈርማለች። በ1948 የታወጀው Universal Declaration of Human Rights አንቀፅ አንድ፤ ሁለት፤ አራትና ሰባት እንዲህ ይላሉ። "ሁሉም የሰብአዊ ፍጥረት በክቡርነቱና በሙብቱ ነጻና እኩል ነው...ማንኛውም ግለሰብ በሕግ በኩል ሙብቱና ነጻነቱ የማይከፋፈልና አንድ ወይንም ተመሳሳይ ነው..All human beings are born free and equal in

dignity and rights...Everyone is entitled to all the rights and freedoms contained in the Declaration...No one should be subjected to torture or to cruel, inhuman or degrading treatment or punishment....All are equal before the law," etc. ማንኛውም መንግሥት እነዚህንና ሌሎችን የሰብአዊ መብቶች የማክበረና የማስከበር ሃላፊነት አለበት። በአምባ ገነንነት የሚገዛው ህወሓት/ኢህ አዴግ ምንም እንኳን እነዚህንና ሌሎች የሰብአዊ መብቶች በሕገ መንግሥቱ ቢያያፀድቅም፤ በተከታታይ በድርጊት ያሳየውና የሚያሳየው ከዚህ የተለየ ነው፤ ፍፁም አፈናና የፍርሃት ዓለም (an environment permeated with fear። ስለዚህ፤ ይኼን ዓለም የተቀበለውንና የሚያከብረውን መብት ማስከበር ያለበት የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በተለይ ወጣቱ ትውልድ ነው።

ስምንተኛው የአገዛዝ ቆይታ ብልሃት ህወሓት ህገመንግሥቱን "ከጭቁኖች መብቶች" ጋር ማቆላለፉ ነው። የዚህን ሁኔታ ውጤት የአንድነት ፓርቲ ሲተች፤ "የፍትህ ተቋሞች ለአገዛዞች እነደማጥቂያ መሳሪያዎች ሁነው ያገለግላሉ" ብሏል። እውነት ነው። የህወሓት ፓርቲ የቀረጸው አገዛዝ ከጅምሩ በጥላቻና በፍርሃት ላይ ነበር። የሚፈራው የስልጣን ተቀናቃኞችን ነው። የሚጠላው በጠላትነት የፈረጀውን የአማራውን ብሄረሰብ ነው። በእኛ ስሌት፤ ጥላቻችን በጥላቻ መመለስ አደገኛ ነው። ለጥላቻ የሚበጀው ሰላም፤ እርቅ፤ መግባባትና ፍቅር ነው። ጥላቻ ጥሪት አይደለም፤ አድካሚና ጠብ ጎታች ነው። ይህ ጥላቻ እንደ "ሃብት፤ እንደ ጥሪት" ሊቆጠር የማይችልበትን ምክንያት በዚህ መጽሃፍ አያሳየን ነው። ህወሓት/ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘበት ጀምሮ፤ ሶስት የተያያዙ ችግሮችን ወልዶ ለተከታታይ ትውልድ አውርሷል።

አንደኛ፤ የትግራይ ኮሙኒስት ሊግ ፈጣሪ የነበሩት የአልባኒያን አርአያ (Model) በአብዮታዊ ዲሚክራሲ አወቃቀር ከስራ ላይ አውለውታል። ማለትም፤ ሁሉም ግለሰብ እኩል መሆን አለበት ብለው የጀመሩት የርእዮት መሪዎች በእኩልነት ፋንታ በኢትዮጵያ ያልታየ፤ በሃብታምና በድሃ መካከል የገቢና የሃብት ልዩነት (unparalled gap between the few rich and the vast majority poor)፤ በሕዝቡ መካከል የጥላቻ ዓለም ፈጥረዋል። አብዮታዊ ዲሞክራሲን ተጠቅመው ሰብአዊ መብቶችን አፍነዋል። አደገኛውን ልዩነት ሲገልጽ፤ ቴድ ቬስታል፤ እንዲህ ብሏል። "መለስ የፈጠረው ስትራተጂ ለጋስ አገሮችን፤ አበዳሪዎችን ለማታለል ነው። ህወሓት በአንድ በኩል የአንድ ፓርቲን በጠባብ ብሄር የበላይነት የተመሰረተ አገዛዝ ፈጥሯል። በሌላ በኩል፤ ውሸትን እንደ እውነት አድርጎ ለማሳመን የቻለው "አለቃው ማርክሲስቱ መለስ" ለዲሞክራሲ፤ ለካፒታሊዝም፤ ለገበያ ውድድር ቆሚያለሁ የሚል መልእክት አቅርቧል። "የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ሪፐብሊክ፤ የሃገሪቱን የመንግሥትና የግል የኢኮኖሚ ክፍሎች ለመቆጣጠር ችሏል።" እንዴት ይህን ለማድረግ ቻለ የሚለውን ሲመልስ፤ "የአፈና፤ የማንበርከክ፤ የማሸበር የበላይነትን (Monopoly of Terror) የሚያስችሉ--የስለላ፤ የፌደራል ልዩ ፖሊስና የመከላከይ--ተቋሞችን መሳሪያ አድርጓል" በሚል አጠቃሎታል። 10/

ሁለተኛ፤ ይህን ለማድረግና በተከታታይ እያፈኑ ለመግዛት አቅም፤ ገንዘብና መሳሪያ ያስፈልጋል። "ለጋስ መንግስታትንና አበዳሪ ድርጅቶችን ማሳመን ግድ ይሆናል። ቆራጥነትን፤ የአገዛዝ ብልሃትን፤ የመገናኛ ብዙሃን አፈናን፤ በአንድ ድምጽ መናገርን፤ በአንዳንድ በሚታዩ ዘርፎች እድገት ማሳየትን አሰራር ይጠይቃል" ይላል። መንግሥት የሚያቀርበው ምክንያት እድገት እንዲቀጥል ከተፈለገ እርጋታ፤ ሰላም፤ ግዛታዊ አንድነት፤ "የህግ የበላይነት" መከበር አለበት የሚል መሪ ያስፈልጋል። "ሽብርተኛነት" አለ። መቆጣጠር አለብን የሚለው ዘዴ ለዚህ ይጠቅማል። ይህ ሁሉ ለዓለም ህብረተሰብ  መነገር አለበት። ስለሆነም፤ መገናኛ ብዙሃንን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር የመቆያ ቁልፍ መሳሪያ ሆኗል። ነጻ ፕሬስን ማጥፋት ከበላይነት ጋር አብሮ ይሄዳል።  መንግሥት የመቆያውን መሳሪያዎች ሁሉ ለሕዝብ  አገልግሎት የሚውሉ ናቸው በሚል ዘዴ ማንም እንዳይከራከረው አድርጓል። "ኢትዮጵያ በመገናኛ ብዙሃን ስርጭት፤ ዘመናዊ የሆኑ የመገናኛ መሳሪያዎችን--ኢንተርኔት፤ ትዊተር፤ ሞባይል--በመጠቀም በዓለም ዝቅተኛ ከሆኑ አገሮች አስረኛ ናት።" መንግሥት "የግል መገናኛ እንዳይኖር፤ እንዳይሰራጭ አድርጓል። ጋዜጠኞችን፤ የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን፤ የሰብአዊ መብት ታጋዮችን አስሯል። ከአገር አባሯል።" የኢኮኖሚና የፖለቲካ የበላይነትን ስለፈለገ፤ በነጻ የመገናኛ ብዙሃን፤ በዘመናዊ የመገናኛ ቴክኖሎጂ ስርጭት ላይ ጦርነት ካወጀ ቆይቷል ማለት ነው። ለዚህ ሁኔታ ዋጋ የሚከፍለው አዲሱና ተከታታይ ትውልድ መሆኑ አያጠራጥርም። 11/

ሶስተኛ፤ የገዢው ፓርቲ ታይቶ የማይታወቅ እድገት እያሳየሁ ነው የሚለውን መርህ ለማስተጋባት ማስረጃዎችን ይፈጥራል። ሎቢስቶችን ይከፍላል። ድህረገጾችን ያባብላል። በቅርቡ አይኤምኤፍ ያወጣው ዘገባ በእጥፍ እድገት አለ የሚለውን ሊሆን አይችልም ብሎ ምክንያቶች አቅርቧል። የእድገት አስደናቂነት ፈጠራው ማስረጃ የቀጠለው፤ አበዳሪዎችን፤ ለጋሶችን ለማባባል ጭምር ነው። ታዛቢ ኢኮኖሚስቶች "መረጃዎች ከእውነቱ የራቁ መሆናቸውን በተደጋጋሚ" አቅርበዋል። ለዚህ ዋና ማስረጃ የሆነው በግልጽ የሚታየው "አጠቃላይ የህብረተሰቡ ፍጹም የሆነ (Absolute Poverty Level) ድህነት ነው" ይላሉ። ይህን ዘገባ ያደረጉ ታዛቢዎች፤ በአንድ በኩል የጥቂት ጠባብ

ብሄርተኛ አገዛዝ "ሚሊኒየሮች" ስርአቱ ፈጥሮ ሲከብሩ፤ በሌላ በኩል አብዛኛው ሕዝብ ምስኪን እየሆነ መሄድ ያስደነገጣቸው ናቸው። 12/

የእነዚህ የሶስት ፍጹማዊነት ያላቸው--ከአገዛዙ ፖሊሲ የመነጨ በግልጽ የሚታዩ የሃብታምና ደሃ የኑሮ ልዩነት ውጤት- የመንግሥት በደሃው ስም ተከታታይ ብድርና ድጎማ ማግኘትና እድገትን ለማሳየት ማስረጃን መደለዝ-- ችግሩን ደብቆታል። የህብረተሰብ ሙሉ ተሳታፊነትና ፍትሃዊ እድገት እንዳይኖሩ አድርጎታል። ረሃብ፤ ድንቁርና፤ ስራ አጥነት፤ የሞራል ብቁነት፤ ሃቀኝነት፤ ታታሪነት፤ ለወገን፤ ለአገር አሳቢነት እንዳይኖሩ ባህሉን በርዞታል። አንዱ የችግሩ ዋና ቁልፍ ይህ ነው። የፖለቲካ ተሳትፎ በሌለበት አገር፤ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ኑሮ አጋርነት፤ ተሳታፊነት ሊኖር አይችልም። ተሳትፎ ካልኖረ፤ ለአብዛኛው የነፍስ ወከፍ ገቢ ሊያድግ አይችልም። ድህነት ሊወገድ አይችልም። ደሃው ለመሸመት አይችልም። ሸማቹ ሃብታሙ ብቻ ይሆናል። ባጭሩ፤ ስርአቱ ሙሉ በሙሉ "የኪራይ ሰብሳቢ" አገዛዝ እስከ ቀጠለ ድረስ በጥቂት ሃብታሞችና በአብዛኛው ደሃ መካከል ያለው ልዩነት እየሰፋ ይሄዳል። የመካከለኛ መደብ አይሰፋም። ከአስተዳደር ጉድለት የመነጨው ጉቦ፤ አድልዎና ሙስና ይቀጥላል። አቤቱታ ለማቀረብ የሚችል አይኖርም። አቤቱታ አቅራቢ ከሌለ፤ የሃብት ሽሽቱ ይቀጥላል። ይህም፤ የሰብአዊ መብቶችን በሙሉ መገፈፍ፤ አገዛዙ አፋኝ መሆኑን ያሳያል።

<u>እአአ ከ 2000-21012 $18 ቢሊዮን</u> ከህግ ውጭ ከኢትዮጵያ ደሃ ሕዝብ ተዘርፎ በልዩ ልዩ የውጭ ባንኮችና ሌሎች ድርጅቶች የተደበቀው ለዚህ ነው። ከዚያ ወዲህ በዓመት ከሶስት ቢሊዮን ዶላር በላይ ከሃገር እየተሰረቀ ይሸሻል። ሃቀኛው ተራ ነጋዴ የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት የተቸገረው ለዚህ ነው። አገዛዙ በሕዝብ፤ ለሕዝብ ተሳታፊነት፤ ሃላፊነት፤ ተጠሪነት፤ እኩልነት፤ የተመሰረተ አይደለም። ከአገዛዝ መጥፎነት የመነጨ ሙስና አዲስ ለጥቂቶች አገልጋይ የሆነ፤ ያልተጠበቀ ጎጂ ሃገራዊ ባህል ሆኗል። ህብረተሰቡን እንደ ነቀርሳ እየበላው፤ ባህሉን እየናደው ነው። የአገርና የባህል ምሰሶዎች እየተናዱ ነው። ተተኪው ትውልድ እንዲከተል የተገደደው የሞራል ብቃት፤ አገር ወዳድነት፤ የሕዝብ አገልጋይነት አይደለም። እኔስ እንዴት ሌቦቹ ከደረሱበት እደርሳለሁ የሚል ይመስላል። ከዚህ ደረጃ የደረሰውንና <u>መቆሚያ የሌለውን ዘረፋ በተናጠል ማየት አይቻልም። በሠብአዊ መብቶች መገፈፍ በህብረተሰቡ ላይ</u> ያመጣውን ጉዳት አብሮ ማጤን አስፈላጊ ነው። የእድግት ጥቅሙ ወይንም ጉዳቱ መመዘን ያለበት ከህብረተሰቡ የኑሮ መሻሻል አንጻር ብቻ ነው። በዚህ መስፈርት ሲታይ፤ በአንጻሩ ሲታይ፤ ከትግራይ ክልል ውጭ፤ የዛሬ አርባና አምሳ አመት- ደራሲው በትምህርት ገበታ ላይ ወይንም የመጀመሪያ ስራ በያዘበት ወቅት--ያለው የኢኮኖሚ መዋቅር አሁንም እንዳለ ይታያል። እድገታዊው መንግሥት "ታይቶ የማይታወቅ ለውጥ አምጥቷል" እየተባለ ሲነገር ይህ ለፈፋ ከጥቂት ተጠቃሚዎች ውጭ መዋቅራዊ የሆነ፤ የአብዛኛውን ሕዝብ ህይወት የለወጠ እድገት አይታይም። ድህነት ስራ ሰደዷል ለማለት እንደፍራለን።

የወጣቱ ትውልድ እድል ተምሮ መሰደድ መሆኑ ለዚህ ዋና ማስረጃ ነው። ጠባብና ጎሰኛው አገዛዝ በመጀመሪያ ደረጃ ሰብአዊ መብቶችን አፍኗል። ሆኖም፤ ለሕዝቡ የሚናገረው፤ ለመጀመሪያ ጊዜ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የብሄር/ብሄረሰብ፤ የሃይማኖት፤ የጾታ እኩልነት ተቀዳጅቷል ይላል። የጭቁን ብሄሮች እኩልነት ከሠብአዊ መብቶች ጋር የሚኖረውን ግንኙነት አይናገርም። እኩልነት ቋንቋን መናገር ብቻ አይደለም፤ የመወሰን መብትም ጭምር ነው። የጋምቤላ፤ የኦጋዴን፤ የቤኒ-ሻንጉል ጉሙዝ፤ የአሞ ሸለቆ፤ የኦሮሞያ፤ የአማራ፤ የአፋር፤ የደቡብ ወዘተ ሕዝብ በየጊዜው የደረሰበትን የመብቶች አፈና እንድሌሉ ይከዳል። የኦጋዴንና የጋምቤላ ሕዝብ እኩልነት አለ ብሎ የሚቀበለው በመሬቱ፤ በቤቱ፤ በታሪኩ፤ በባህሉ፤ በዜግነቱ፤ በኑሮው ወዘተ ባለቤትነና ዋስትና ሲኖረው ነው። በክልል ኢንቬስትመንት ሲታይ ከትግራይ ክልል ውጭ አስደናቂው እድገት ለአብዛኛው ሕዝብ አልደረሰም የምንለው ለዚህ ነው። የትግራዩም አገልጋይነቱ ለታማኞች ነው የሚሉ ብዙ ናቸው።

በሚከተለው ሰንጠረዥ እንደሚታየው፤ "አስደናቂው እድገት" ለየአብዛኛው ሕዝብ የኑሮ ሁኔታ መሻሻል የሚታይ መሰረታዊ ለውጥ አያሳይም። ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር ሲነጻፀር እንደዚህ ዝቅተኛ ከሆነ፤ ለአገሪቱና ለተራው ሕዝብ ደህንነት ማን ቆሚል? ማን ይጠየቃል? ማን ሃላፊነት ይወስዳል? ብለን መጠየቅ የእኛ የሞራል ግዴታ ነው። በግልና በጠባብ ጎሰኛነት ደረጃ ሲታይ፤ የገዢው ፓርቲ የሚሰራውን ያውቃል። ለማን እንደቆመ ያውቃል። እንዴት እነደሚገዛ የተገነዘበ ድርጂት ነው። በአንጻሩ፤ የተቃዋሚው ክፍል እያንቀላፋ ነው። ከላይ ባጭሩ እንደቀረበው፤ ከሁሉም አደገኛ የሚሆኑት፤ ሁለት ሸሽቶች (two critical capital flights at the same time) ናቸው። በአንድ ላይ ህብረተሰቡን እየጎዱት ነው። አንደኛው የተማረ፤ በተለይ <u>ወጣት የሰው ሃይል ስደትና ፍልሰት ነው።</u> ሁለተኛው ከህግ ውጭ የሃብት ወይንም የገንዘብ ሽሽት ነው። እነዚህ ጥሪቶች የኢትዮጵያን ህብረተሰብ ካላገለገሉ፤ ዘላቂነት ያለው፤ ፍትሃዊና አገር ወለድ የሆነ ዘላቂ ልማት አይኖርም። ገዢው ፓርቲና ተቃዋሚው ክፍልና አገር ወዳድ ነን የምንለው ሁሉ፤ በግልም ሆነ በጋራ የታሪክ ተጠያቂዎች ሆነናል የምንለው ለዚህ ነው። የመጀመሪያውን የታሪክ ተጠያቂ በጥልቀት

እንየው።ገዢው ፓርቲ ለአብዛኛው ሕዝብ አስደናቂ የኑሮ መሻሻል አምጥቻለሁ ቢል አያስደንቅም። ራሱን መደገፍ የስርአቱ መቆያ ስልት ነው። እኛ ለማሳየት የምንፈልገው ሃቁን በሚከተሉት ስምንት የህብረተሰብ ደህንነት ወይንም ድህነት ቅነሳ መስፈርቶች በ 2011-2012 በተገኘ ማስረጃ ስንጠረዥ ነው።

| መለኪያ | ደረጃ --ከመቶ ሰባ ዘጠኝ አገሮች |
|---|---|
| የህብረተሰቡ እድገት/የኑሮ መሻሻል | 169ነኛ |
| ንጹህ ውሃ የሌለው ሕዝብ | 66ነኛ |
| መጸዳጃ የሌለው ሕዝብ | 89ነኛ |
| ፍጹም ድሃ የሆነው ሕዝብ | 44ነኛ |
| አማካይ የነፍስ ወከፍ ገቢ በአመት | $490 (የአፍሪካ መካከለኛ $1,700) |
| ሰድሳ በመቶ የሚሆነው ህዝብ የቀን ገቢ | ከ$1.25 በታች |
| በባንክ የሚሰራ ኢትዮጵያዊ የወር ገቢ | ከአምስት መቶ ብር በታች |
| የስራ እድል የሌለው ወጣት (ከመቶ) | 70-80 |

"እድገታዊው መንግሥት" ሁሉንም የታሪክ ተጠያቂ አድርጓል

የህወሓት/ኢህአዴግን አስከፊ አገዛዝ ስናማርር ሃያ ሶስት አመታት ቆይተናል። ይህ የጠባብ ብሄርተኛ ቡድን ከተጠነሰሰበት ወቅት ጀምሮ ሆነ ብሎ የሚያደርገው ሰላማዊ ሕዝብ ማሰቃየት፤ ሰብእነት መግፈፍ፤ ማሳደድ፤ መግደል፤ ከአገር ማሰወጣት ወዘተ ነው። ማን ገኘ፤ ማን ተገኘ እንደሆነ ለማሳመን ሞክሩል። ማንን ማጥቃት እንዳለበትም ደንግጓል። በተለይ ኢላማ አድርጎ የተነሳው፤ የአማራው ህብረተሰብ ሰብእነትና ክብር እንዲገፈፍ፤ በራሱ ባህልና ታሪክ እንዲያፍር ማድረግ። ራሱን እንዲጠላና አግባዳጅ እንዲሆን ማስገደድ። አስተዋጽኦው ቀፎ ነው ብሎ እንዲቀበልና ራሱን እንዲጠራጠር ማሳመን ይገኙበታል። ለቀጣይና ተሳትፏዊ እድገት መሰናከል ሆኖ የሚታየው ኢትዮጵያ "የሕዝቦች እስር ቤት" ተብላ እንድትጠራ መሆኑና ከዚህ ጋር ተያይዞ የእድገት መዛባት መከሰቱ ነው። በህወሓትና በተመሳሳይ ጠባብ ጎሰኛ ክፍሎች ትብብር፤ ኢትዮጵያን፤ የአማራ ህብረተሰብ ለጭቆናና ለዘረፋ ዳርጓታል ብለው በማሳመን የሞራል ክስ በአማራ ህብረተሰብ ላይ ለማቅረብ ተሞክሯል። ይህ፤ ለአገር ነጻነት መከታ የነበረ ህብረተሰብ የታሪክ ሃላፊነትና ተጠያቂነት እንዳለበት ዓለምን ለማሳመን ተጥሯል። ይህን መሰረት የሌለው ክስ በማቅረብና በማስጠላት፤ አማራው ቀስ በቀስ ከሃብቱ፤ ከማሳውና ከንብረቱ፤ ከአገሩና ከወገኖቹ እየወጣ ቁጥሩ እንዲቀንስና ለስደት እንዲዳረግ ተደርጓል። በጉራ ፈርዳ፤ ደቡብ ክልል ወዘተ በሚኖሩ በሰላማዊ ህጻናት፤ እናቶች፤ አባቶችና በማሳቸው በግብርና ሙያ በሚተዳደሩ አማራዎች ላይ፤ "ከሰሜን የመጣችሁ ናችሁ፤ ወደ "ሃገራችሁ ተመለሱ" በተባለ፤ ህገመንግስቱን በሚጥስ ትእዛዝ ከመኖሪያቸው ተገደው ወጥተዋል። አሁንም ይወጣሉ። ለወደፊትም ዋስትና የላቸውም። ዛሬ በአማራው ላይ የሚካሄደው የጎሳ ማፅዳት ወደ ሌሎች፤ ትግሬዎችን ጨምሮ እንደሚዛመት መገመት አለብን። በእነዚህ፤ ኢትዮጵያውያን ላይ የሚያካሂደው ኢሰባዊ መፈናቀልና ለዘር ጽዳት ዳራጊ ተግባር ታሪክ እየመዘገበው ያለው የህወሓትንና ተባባሪ ዋና ዋና መሪዎች በህግ የሚያስጠይቃቸው ወንጀል ነው። አሁን በሚደረገው ሽግግር፤ የመንግሥቱ የበላይ አመራር የኢትዮጵያን ሕዝብ መምሰል አለበት የሚለውን የአሜሪካኖች ጫና በመቀበል፤ አዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር፤ በሶስት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴሮች---አማራ፤ ኦሮሞ፤ ትግራይ እንዲወከል ተደርጓል። ሆኖም፤ ይህ ሽግግር መሰረታዊ የሆነውም አገዛዝ አያስተካክልም። ህወሓት አሁንም አለቃ ነው። ሁለት መንግሥታት አሉ የምንልበት ለዚህ ነው።

ግለሰብ ወይንስ ስርአት?

ይህ አዲስ የመንግሥት አመራር ሊፈታው ያልቻለው የውስጥ የፖለቲካ ሽግግር ውጥረት- ህወሓት አዲሱን አወቃቀር ይቀበል እንጅ-- በድብቅ እንደ ሽምቅ ተዋጊ ሆኖ አገሪቱን በበላይነት የሚመራው የህወሓት የበላይ ነው። ቁልፍ የሆኑ፤ የመከላከያ፤ የፌደራል ፖሊስ፤ የስለላ፤ የውጭ ጉዳይ ወዘተ፤ ድርጅቶችን የሚቆጣጠረው ህወሓት ሆኖ ይቆያል የሚሉ ብዙ ታዛቢዎች አሉ። የበላይ አመራሩ "ኢትዮጵያን ይመስላል" ቢባልም ፖሊሲው አይለወጥም። ችግሩ ከመለስ ተተኪዎችና ከበላይ ባልስልጣናት ጋር አይለይም። ከመንግሥቱ አቀራረጽና ከ ፖሊሲው ጋር ነው። የኦሮሞ ሆነ የአማራ

ተወላጅ ከፍተኛ ቦታ ቢይዝ፤ የህብረተሰቡን ችግሮች ሊፈታቸው አይችልም። ሊፈታቸው የሚችል <u>ስርአቱን ለማሻሻል የተዘጋጀ አመራርና የስልጣን ክፍፍልና አጋርነት ነው።</u> ለምሳሌ፤ አዲስ አመራር የአኟኩን ለም መሬት ባለቤትነት ያረጋግጣል። አማራው በዜግነቱ የትም ለመኖር፤ ለመስራት፤ ለመምረጥና ለመመረጥ ይችላል የሚሉትን የፖሊሲ ጥያቄዎች ለመመለስ መቻል አለበት። እነዚህ የሰብአዊ መብት ጥያቄዎች ናቸው። ተከታታይ ትውልድ ማወቅ ያለበት፤ አንጋፋ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ አካል የሆነው የአማራ ብሄረሰብ፤ ለዚህ አሰቃቂ የመፈንቀልና የዘር ማጽዳት ድርጊት ኢላማ የሆነበት ዋና ምክንያት ወንጀል ስለሰራ አይደለም። ላለፈው "ወንጀልና ጥፋት" ወደፊት ነጻ ኮሚሺን አቋቁሞ ለመመርመር ይቻላል፤ መሆንም አለበት። አሁን ያለው ዋናው ምክንያት ብሄራዊ ተቀናቃይ ለማጥፋት ነው። አማራውና ኦሮሞው፤ ትግሬውና አፋሩ ወዘተ ለኢትዮጵያ የተሰበጣጠረ (Tapestery) ሕዝብ ኩታገጠምነት፤ አብሮ በሰላምና በመከባበር ለመኖርና ኑሮን ለማሻሻል፤ ለኢትዮጵያ አንድነትና ሉአላዊነት ምሰሶ ናቸው። ምሰሶውን አፍርሶ መልሶ ለመተካት አይቻልም። ሁሉም በተለያዩ ወቅቶች አገራቸውን አገልግለዋል። አሁንም በመንግሥታቸው መገልገል አለባቸው። መብታቸው ነው። ደሃው የአማራ ገበሬ ሌላውን ጎድቷል። ጨቁኗል የሚለው፤ የጣሊያን፤ የአረቦች፤ የሻቢያ፤ የህወሓት ከፋፋይ ፍልስፍና ነው። ምሰሶውን ያፈረሰ። ከጅምሩ፤ የህወሓት ጠባብ ብሄርተኛ፤ የዘር ፖለቲካ ፈጣሪዎች በኢትዮጵያ "የማይታረቁ የብሄረሰብ ልዩነቶች" አሉ በሚለው "የከፋፍለህ ግዛው፤" የፖለቲካ አደረጃጀት ስልት የተጠቀሙትና በዚህ ላይ የተመሰረተ የክልል ስርአት ከስራ ላይ ያዋሉበት መሪ ምክንያት ሕዝብን ከሕዝብ ጋር አጋጭቶ ገቢና ሃብት ለመሰብሰብ ነው። ሊቆች ይህን አይነት አገዛዝ "የፖለቲካና የኢኮኖሚ መማረክ" ይሉታል። "መማረክ" የሚቻለው ሌላውን በማግለልና በማዳከም ነው። አማራ፤ አፋር፤ አኟክ፤ ሶማሌ፤ ኦሮሞ ወዘተ አይለይም።

የዝምታ ትውልድ

የኪራይ ሰብሳቢው ቡድን በእኩልነት ወይንም አብሮ በማደግ፤ወይንም በፍትህ፤ ወይንም በህግ የበላይነት አያምንም። በሠብአዊ መብቶች መጠበቅ ሊያምን አይችልም። ምክንያቱም ተቀናቃኝና ተወዳዳሪዎች ካሉ ምዝበራን ለራሳቸው ሲሉ መከላከል ይጀምራሉ። ቢያንስ አድልዎና ሙስና ያለልክ እንዲስፋፋ አያደርጉም። ኪራይ ሰብሳቢው ጠባብ ጎሰኛ ከሆነና ፓርቲውን፤ መንግሥቱንና ተቋሞችን ሙሉ በሙሉ ከተቆጣጠረ ሌላው ምንም መፈናፈኛ አይኖረውም። እስካሁን በሚገባ ያልመረመርነው አበይት ነገር የጠባብ ዘረኛነትን አደጋ የማንቀበል፤ስርአቱን የምንቃወም፤ የሕዝቡን ስቃይና መከራ በየቀኑ የምናይ፤ ይህ የሰውን ክቡርነት የተፈታተነ ሰቆቃ ከራሳችን ድክመት ጋር የተያያዘ መሆኑን ነው። "ኢህ አፓ፤ መኤሶን፤ ኢጫት፤ ኢሰፓ፤ ኢዲዩ፤ ቅንጂት" ወዘተ እያልን ከዚህ ደርሰናል። ልዩነቶቻችን ለራሳችን ቀንበር ሆነው ቆይተዋል። ይህን "እያወቁ ዝምታ" በተከታታይ አይተነዋል። አሁን አደገኛ ደረጃ ላይ ደርሷል። የኢትዮጵያ ታሪክ ተከልሶ በውሸት ሲጻፍ ዝም አልን። ህብረ-ብሂራዊ ስርአት ቀስ በቀስ ሲናድ ዝም አልን። የአገር ሉአላዊይነት እየተቦረቦረ ስናይ ችላ አልን። ምትክ የማይገኝላቸው አድባራት-እንደ ዋልድባ ያሉና-ሌሎች ተቋሞች እየተናዱ ስናይ ድምጻችን ጠፋ። ህወሓት የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን መንግስት በምስጢር ሲሰጥ አንዳልሰማን ዝም አልን። ለም መሬት፤ ማሳዎችና ወንዞች ለውጭ መንግስታትና ድርጅቶች፤ ለምርጥ ግለሰቦች በጅምላ ሲሰጡ ድምጽ ሳናሰማ ቆየን። መንፈሳዊ አባቶች የሚጠቀሙበት፤ መተኪያ የማይገኝለት የገዳማት ምድርና ደን--ተከታታይ መንግሥታት ያከበሩት የዋልድባን ገዳም የሚደግፍ--ለህወሓት ደጋፊ ድርጅቶችና ለትግራይ ተወላጆች ለስኳር ማምረቻና ፋብሪካ ሲቆፈር በፍርሃት ድምጽ ሳናሰማ ቀረን። አኟኮች ሲጨፈጨፉ፤ አማራዎች ከቀያቸው ሲባረሩ፤ የኦሮሞ ወጣቶች ሲጨፈጨፉ፤ እን እስክንድር ነጋ፤ አንዱዓለም አራጌ ወዘተ ሲፈረድባቸው ለአንድ ቀን ጨኸን ወደ ቤታችን ገባን፤ ወዘተ፤ ወዘተ። አፈናው ወደ ውጭ ተዛምቷል፤ አሁንም አመርቂ የአንድነት አማራጭ አልመሰረትንም።

የህወሓት አመራር በተከታታይ ያፈረሰው ኢትዮጵያዊ ተቋሞችን ብቻ አይደለም። ለመለወጥ የወሰነው የሕዝቡን የብሄርና የሃይማኖት ስርጭት ጭምር ነው። (The TPLF core leadership is committed in transforming Ethiopia's demographics). የአሞ ሸለቆ ሕዝብ ከሚኖርበት ተገዶ ሲወጣ የወደፊት መኖር አለመኖሩ ያጠራጥራል። ሴሰደድ ተመልሶ ወደ ቅድመ አያቶቹ መሬት የመመለስ እድሉ ዜሮ ነው። ሌላ ምሳሌ እንይ። የአማራ ሕዝብ--ልክ ለእርሱ ብቻ በመጣ የወረርሽኝ በሽታ እንዳለቀ ሁሉ---ቁጥሩ እንደቀነሰ፤ ወይንም፤ በፈቃዱ ማንነቱን እንደለወጠ ተደርጎ በሚያስደነግጥና በሚያናድድ ደረጃ ቁጥሩ ከሰላሳ ሚሊዮን ወደ ሃያ ሰባት ሚሊዮን፤ በዚህ አመት፤ ከዚህ በታች እየቀነሰ እናያለን። ማንነትክን ለውጥ ሲባል፤ ቁጥርህ መቀነስ አለበት እንደማለት ነው። ተራው ምሁርና ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ይህን እያዩ ዝም ብለዋል። የዚህ ሕዝብ ቁጥር የቀነሰው ወደ ጨረቃ ስለተጓዘ እንዳልሆነ የታወቀ ነው። ብዙ ታዛቢዎች የአማራ ምሁራን የት ደረሱ እያሉ ይጠይቃሉ። ሌሎች "ድፍረት ስለሌለው ነው" ይላሉ። ለህሊና እንተወው። ሃቁ ከአማራ ክልል ውጭ ይኖር የነበረውና አሁንም በኢትዮጵያዊነቱ የሚኖረው አማራ እንዲጠፋ የተፈረደበት ይመስላል። የብሄር እልቂት ወይንም ጀኖሳይድ ማለት ይኼው ነው። በዘዴ ማጥፋት። የህወሓት የበላዮችና አጋፋሪዎች "አማራ እንጅ ኢትዮጵያዊ" አይደለህም፤ መብት የለህም ብለው የደነገጉበት ሕዝብ ሆኗል። ማንነቱን

እንዲለውጥ፤ ቀስ በቀስ የመጥፋት እድሉ ጠለቅ እንዲል ለማስገደደ መሆኑ አያጠራጥርም። በሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን፤ብሄረሰብን ለማጥፋት ከተፈለገ በዘመናዊ ዘዴና በረቀቀ መንገድ መሆን አለበት። የረቀቀና የሠብአዊ መብቶች አፈና ስለሆነ በመጀመሪያ፤ አማራውን ከጥፋት ማዳን ያለበት አማራው ነው። አማራው፤ በተለይ የአማራው ምሁር የውስጥ ልዩነቱን ካላስወገደ፤ ከጥፋት፤ ከስደት፤ ከድህነት፤ ከክብር ማጣት ሊድን አይችልም። እንዳለፈው ታሪኩ፤ አማራው ራሱንና ኢትዮጵያን ለማዳን ከሌሎች ጋር መተባበርና የሌሎችን እኩልነት መቀበል ግዴታው ነው። ዛሬ "ኢህ አፓ፤ መኤሶን፤ ኢሴፓ፤ ግንቦት ሰባት፤ ሸንጎ፤ አንድነት፤ መድረክ፤ ሰማያዊ፤ አሬና" የምንልበት ወቅት አይደለም። በአንድ ላይ፤ ለአንድ ብሄራዊ አላማ፤ ለሰላን፤ ለእርቅ፤ ለፍትህ፤ ለእውነተኛ እኩልነትና ለዲሞክራሲ የምንሰራበት ወቅት ነው። አለበለዚያ ሁላችንም እናልፋለን፤ "ለዘላለም ትኑር" የምንላት ኢትዮጵያ ትበታተናለች፤ ትጠፋለች።

በብሄር ስርጭት መስፈርት ሲታይ የህወሓት አላማ አንድና ወሳኝ ነው። የአማራው ቁጥር ሲቀንስና ደሃ ሲሆን ወይንም ሲሰደድ የሚያስከትለው ውጤት አለ። የአማራው አቅምና ጉልበት፤ የለመደው አገር አቀፍ ሚና ይለወጣል። "የካሊሸንኮቭ" ቀረርቶው የመጣው በዚህ ነው። ቀስ በቀስ፤ የአማራው ሕዝብ ቁጥር ወደ ንኡስነት ይቀየራል፤ ልክ እንደ ትግራይ ብሄረሰብ ይሆናል የሚል ዘገባ ነው። የሚያሰጋው፤ የሻቢያና የህወሓት እቅድ አንድ ነው። ቢቻል የአማራውን ህልውና ጭራሽ እንዲጠፋ አድርጎ በኩታ ገጠም ክፍለ ሃገሮች ተቀናቃኝን ማጥፋት የሚል ነው። ሆኖም፤ ሻቢያም ሆነ ህወሓት ቢወድም ባይወድም አመራሩ ሊለውጠው የማይችለው ሃቅ፤ አማራ በምንም አይጠፋም። ህወሓት ለማጥፋት የሚፈልገው አማራን ብቻ አይደለም። ሌላው ሕዝብ በአማራ የደረሰው በራሱ ላይ እንደሚደርስ ያውቀዋል። ኦሮሞው ይረዳዋል። እየደረሰበት ነው። አኟኩ ይገባዋል። አፋሩ አይቶታል። በአሁኑ ወቅት፤ ቢያንስ፤ ከዘጠና አራት ሚሊዮን ህዝብ፤ ሰባ አምስት ሚሊዮኑ አማርኛ ተናጋሪ ነው። ቢያንስ ሰባ በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቅይጥ ወይንም ድብልቅ ነው። ከማንም ብሄረሰብ የበለጠ፤ ከኦሮሞው ጋር በጋብቻ የተቀላቀለ አማራው ነው። አንደ አማራ ህብረተሰብ ከሁሉ ህብረተሰብ ጋር አብሮ የሚኖር፤ የሚጋባ፤ የተደበላለቀ አለ ለማለት አስቸጋሪ ነው። የህወሓት ጠባብ ብሄርተኛ ቡድን ይህን ሃቅ በምንም ሊቀይረው አይችልም። የሕዝብ ቁጥርና ስርጭት ተፈጥሮ ውጤት ነው። አገዛዝ ሊለውጠው አይችልም። የአዲስ አበባን ሕዝብ በቋንቋህና በብሄርህ መኖር አለብህ ቢባል "እሽ" እንደማይል መገመት አያዳግትም። ሆኖም፤ አማራውና አማርኛ ተናጋሪው በያለበት፤ የራሱን ህልውናና መብት የመጠበቅ ስልት መቀየስ አለበት። በአርመኖች ላይ፤ በአይሁዶች ላይ፤ በጥቁር ላቲኖች ላይ የደረሰውን ማስታወስ ይጠቅማል። ይህን ማለት፤ አማራው የታወቀበትን መለያ፤ ኢትዮጵያዊነቱንና የኢትዮጵያን ግዛታዊ አንድነትን ወደ ጎን ይተው ማለት አይደለም። እንዲያውም ከመቸውም በበለጠ ደረጃ ለሰባዊ መብቱ፤ ለክብሩ፤ ለነጻነቱ መነሳትና ለብሄራዊ አንድነቱ ከሌሎች ጋር አብሮ መታገል አለበት፤ ለህወሓት ርእዮት መንበርከክና ህወሓት ለቀየሰው የቋንቋ መለያ ሰለባ መሆን የህወሓትን አላማ ያራምዳል እንላለን። አንጋፋዎቹ የኦሮሞና የአማራ ጎሳዎች በአንድ ላይ ቆመው ከታገሉ የሚያግዳቸው ኃይል አይኖርም። ከሁሉም ክፍሎች የሚጮሁ አክራሪዎችን ወደ ጎን ትቶ ወደ ማእከል መጓዝ የሚጠቅመው ለዚህ ነው።

የኢኮኖሚ ስደት የመንፈስ ስደት መሆን የለበትም

ከጉራ ፈርዳ የተባረረው የአማራ ብሄረሰብ ለጠቅላይ ሚንስትር ኃይለማሪያም ያቀረበው ማስረጃ እንዳለ ሆኖ አሁንም የምናየው ተከታታይ ድክመት የእኛው፤ የተማርነው፤ በተለይ በስደት የምንኖር ኢትዮጵያውያን ነው። ለማስተማር አልሞከርንም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዙ የወል እሴቶች እንዳሉት ከተቀበልን፤ ሕዝቡን ከሚያራርቁት ንኡስ ነገሮች ላይ ማተኮር ለዚህ ጨቋኝ አገዛዝ ሴራ ምርኮኛ መሆንን ያሳያል። ተስማምተን ለመስራት ካልቻልን፤ ይህ አሰቃቂ ስርአት ይቀጥላል። ጥሩው ነገር፤ በአሁኑ ወቅት የራሳችን ድክመት ለወገኖቻችን ሆነ ለኢትዮጵያ አስከፊ ጉዳት ማምጣቱን ከልባችን ለማመን ሙከራ የምናደርግ እየበዛን ሄደናል። ይህ ጥሩ ጅምር ነው። በቂ አይደለም። ብዙ ስራዎች ከፊታችን ይጠብቁናል። አሁንም ካሉ ችግሮቻችን መካከል የባህርይ ለውጥን ጠቃሚነት በሚገባ አለማስቀመጥ ነው። አለመተማመን፤ ለጥቅም መገዛት፤ መጠላለፍ፤ ሃሜት፤ እውነትን በድፍረትና በጨዋነት አለማሳየት፤ ራስ ወዳድነት፤ ፍርሃትና መከፋፈል ይገኙበታል። የመንፈስ መሪዎች ፖለቲከኞች ሲሆኑና ከእውነት ሲርቁ ማየታችን የችግሩን ጥልቀት ያሳየናል። የህወሓት አመራር ተቋሞችን ሁሉ ወደ ፖለቲካ ሲለውጣቸው በመተባበር አልተነሳንም። ፓትሪያርክ በህይወት እያሉ የፖለቲካ ፓትርያርክ መሾም ፖለቲካ ነው። አሁንም ሌላ በፖለቲካና በብሄር መስፈርት የተመለመለ ፓትሪያርክ ተሾሟል። ይህ ሲሆን በስደት የሚገኘው ምእመናንና አመራር በምንም መዘንጋት የሌለበት "ክፍፍሉ" ሆነ ተብሎ የሚሰራ መሆኑንና በስደት ያለው በመንፈሱ አገር ቤት ካለውጋር የበለጠ አንድ መሆኑን ማስተማር ነው።

የህወሓት መንግሥት የአንድ ክልል፤ እንዲያውም የአንድ መንደር ቡድን የበላይነት መንግሥት መሆኑን አሁን ሳይሆን ስልጣን ከያዘበት ጀምሮ እንዳሰመረበት አይተናልል። ለዚህ ሃገራዊ ችግር መፍቻ ተባብረን ለመስራት የተነሳን ጥቂቶች ነን። ይህን ድክመት አለመገንዘብ የዋህነት፤ ወይንም አውቆ የስርአቱ ተባባሪ መሆን ነው። የችግሩን ክብደት በሚገባ

የማመዛዘኑን ጥበብ ካላወቅንበት፤ መፍትሄ ለመጠቆም አንችልም። የኢትዮጵያን ሕዝብ ለመርዳት፤ ታሪክ ያላትን ኢትዮጵያን ካለችበት ፈተና ለማዳን አንችልም። የሚበጀው፤ ልዩነቶችን ወደ ጎን አድርጎ፤ በመተባበር መስራት ነው። የአረብ አገሮች በሕዝብ የተመሩ ለውጦች፤ የሚያሳዩን አቅጣጫ ይህን ነው። ኢትዮጵያውያን የራሳቸው የሚያኮራ ልምድ አላቸው። ገንቢ ለውጥ ለማምጣት የሚቻለው የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በተለይ ወጣቱ ትውልድ ለሙብቱ ቆርጦ ለመነሳት ሲወስንና ተባብሮ ለጥላቻ ሳይሆን፤ ለፍትህ፤ ለርትእ፤ ለእኩልነት፤ ለሰላም፤ ለዲሞክራሲ፤ ለህግ የበላይነት ወዘተ ከአንድ ላይ ሲነሳ ብቻ ነው። የመነሳት ልምድ አለው። ለመነሳት እንደሚፈልግ ብዙ ምልክቶች አሉ። ውጭ ያለው ብዙ ያልተፈተነው የሰው፤ የገንዘብና የእውቀት ሃይል፤ ለአገር ዘላቂ ጥቅም፤ ለሕዝብ ሰብአዊ መብቶች ለመቆም መቻልና መወሰን አለበት። በማንኛውም መንገድ አገር ቤት ለፍትህ ለሚታገሉ ሁሉ የማያቋርጥ ድጋፍ መስጠት ግዴታ ነው። የሚጎድለው ገንዘብና እውቀት አይደለም። ፈቃደኛነት፤ አገር ወዳድነትና ቁርጠኛነት ነው። የገንዘብ እርዳታ ሳንሰጥ "ተነሱ፤ ለሙብታችሁ ቁሙ" ለማለት አንችልም።

ህወሓት የኢትዮጵያን ሕዝብ ከፋፍሎ ለመግዛት ያጠመደው ወጥመድ (Political trap) እየሰራለት ነው። በኢትዮጵያ የሚኖሩ"ብሄረሰቦች የማይታረቁ ልዩነቶች" አሏቸው በሚል ያጸደቀው፤ በክልል አስተዳደር የተመሰረተ ህገመንግሥት፤ ለተፈጥሮ ሃብት መሻማት፤ "ከውጭ መጡ" የሚባሉ የብሄረሰብ አባላትን ከመሬታቸው ለማባረር፤ የአንዱን መሬት ወደሌላ ለማሸጋገር የመንግሥት መሪዎች እየተጠቀሙበት ነው። በግልጽ የሚታየው፤ አስተዳደሩ፤ ለሃገራዊ የኢኮኖሚና የማህብረሰብ ውህደት ወጥመድ እየሆነ ነው። ከጅምሩ፤ ለብዙ ሽህ አመታት፤ የብዙ ብሄርና ብሄረሰቦች መኖሪያ የሆነች አገር፤ በዘር ስትከፋፈል እያየን፤ ለሃያ ሶስት አመታት ችላ ብለናል። ካለንበት ደረጃ ደርሰናል። የምሁራንና የፖለቲካ ድርጅቶች ድክመት፤ መበታተን፤ እርስ-በእርስ መኮራረፍ፤ የፖለቲካ ስልጣን ዉድድር፤ ራስ ወዳድነት፤ ትእቢተኛነት፤ ፍርሃትና ስንፍና፤ ህወሓት ላጠመደው ወጥመድ ሰለባ አድርጎናል። ድክመታችን ለተሳሰረው ህብረተሰብ መፈራረስ አስተዋጾ እያደረገ ነው። ህወሓት እየነጣጠለ፤ አንድ ቀን አፏኩን። ሌላ ቀን ኦሮሞውን። ሌላ ቀን ሶማሌውን ወዘተ ሲመታ አደጋው "ከእኛጋ እስከሚደርስ" የምንጠብቅ ብዙ ነን። ምንም እንኳን ኢትዮጵያ በምንም ትጠፋለች ብለን የማናምን ብዙ ብንሆንም የኢኮኖሚው ችግር፤ የሰብአዊ መብቶች መገፈፍ፤ ሁኔታውን ከዱሮው ባመዘነ ደረጃ አባብሶታል። አገር የማጣት እድል ያመዝናል የሚለው ትንተና ቁም ነገር እንዳለው መገንዘብ መፍትሄ ለመፈለግ ይረዳል። ኢትዮጵያ የሶማልያ፤ የሩዋንዳ፤ የላበሪያ፤ የኮንጎ ኪንሻሳ አይነት እድል ሊገጥማት ይችላል። ለኢትዮጵያና ለመላው <u>የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚበጅ ሁሉን የሚስተናግድ የአላማ አንድነት</u> መቅረጽና ከስራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል። ካለፈው የምንማረው፤ የወደፊቱ አገዛዝ የሁሉም ጥቅም የሚገለገልበት አማራጭ ዋና መመሪያ መሆን ይኖርበታል። ይህ በባዶ ሜዳ አይሆንም። መጀመሪያው፤ ኢትዮጵያ የምትባል፤ ታሪክና እውቅና ያላት አገር የሁላችንም ናት ማለትን ይጠይቃል። ዋናውና መሪው እሴት ይኼው ነው። ካልሆነ፤ ህወሓትን ከመቃወም በስተቀር፤ ለአንድ ሃገራዊና ሕዝባዊ አላማ የሚሰበስብ አበይት ጉዳይ አይኖርም። "ጎረቤት" ለመሆን ውይይት አያስፈልግም። ሁሉም በእየቤቱ ይኖራል። አብሮ ለመኖር ውይይት ቁልፍ ነው። ኢትዮጵያ የጋራችን ናት። ተባብረን መድረስ የሁላችንም ሃላፊነት ነው። "እኛ ጎረቤቶች ሆነን ለመኖር እንችላለን" ማለት የተለየ ሃሳብ ነው። ጎረቤት ለመሆን መወያየት አያስፈልግም። በተለይ፤ "ምሁራን ነን" የሚለው ኢትዮጵያዊ እንደገና ለመማር ፈቃደኛ መሆን ይኖርበታል። ከሌሎች ጋር አብሮ መኖር። አብሮ መስራት። አብሮ አገርንና ሁሉን ሕዝብ ማገልገል ልምዱ አይደለም። ባህሪውን መለወጥ የሚኖርበት ዛሬ የሚታዩ ችግሮች በግል ሊፈቱ ስለማይችሉ ነው። በመተባበር ይፈታሉ።

ምሁራንና የፖለቲካ መሪዎች ራሳቸውን ካልለወጡ ለማንም የለውጥ ሃዋርያ ለመሆን አይችሉም። አፍራሾች ናቸው። ስርአቱ ባስቀመጠው የብሄርተኛነት መርዝ አዙሪት ታውኮ ለውጥ ለማምጣት አይቻልም። እንዲያውም የችግሩ አካል መሆንን ያስከትላል። በቋንቋ ብቻ ተለያይቶ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የደማላትን፤ የሰው ፍጥረት መነሻ አኩሪ አገር ማጣት ውርደት ለሁሉም ነው። ማንኛውም የውጭ ጥናት የሚያሳየው፤ ህወሓት፤ ከትግራይ ውጭ፤ ቋንቋን ዋና መለያ አድርጎ የህብረተሰቡን እድገት አንቆታል። ህገመንግሥቱን ለሠብአዊ መብቶች ማፈኛ ተጠቅሞበታል። ይህን የሚያደርገው ኢትዮጵያን ለማጠናከር አይደለም። ህብረተሰቡን ከፋፍሎና አዳክሞ ለመቶ አመታት ለመግዛት ነው። ጣሊያን ካደረገው "ከፋፍለህ ግዛው" አይለይም። ተቆላላፊነት (National cohesion and integration) አብሮና ተከባብሮ የመኖር ምልክት ነው። ማንንም ብሄረሰብ ማባረርና ማጽዳት ኢ-ሰብአዊ ከመሆኑም በላይ፤ ለዘላቂና ፍትሃዊ እድገት መሰናከል ነው። ተገንጣይነት የሚጠነክረው ፍትህ ሲጓደል ነው። በተጻራሪው፤ በሰላም፤ በመከባበር፤ በእኩልነት፤በጋራ አገርን መጠበቅ፤ የተፈጥሮ ሃብቷን በጋራ መጠቀም፤ ዘላቂነትና ፍትሃዊነት ያለው ማህበረሰብን ይፈጥራል። ህወሓት፤ በጠባብነቱ፤ በህብረ-ብሄራዊነት አያምንም። ከተሜነትን አይፈልግም። ምክንያቱም፤ ከተሜነትና ህብረ-ብሄርነት አብረው ይሄዳሉ። (Urbanization creates social pluralism and contributes to greater integration). የኢትዮጵያ ከተሜነት (Urbanization) አስራ ሰባት በመቶ ነው። የሌላው አፍሪካ አርባ በመቶ ነው። የዛሬ ሃያ አመት አብዛኛው የአፍሪካ ሕዝብ የሚኖረው በከተማ ነው። ህወሓት ገጠሩ ገጠርና ኋላ ቀር ሆኖ እንዲቆይ

የሚያመቻች ፖሊሲ ይከተላል። ለምን እንደሆነ ብንጠይቅ፤ ደሃና ያልተቆላለፈ፤ የመገናኛ ብዙሃን የማይጠቀም ህብረተሰብ ለአምባገነን አገዛዝ አመች ስለሆነ ነው። ደሃውን በድህነቱ እንዲኖር የሚያደርግ አገዛዝ የህብረተሰቡን የኢኮኖሚ መብት የሚገድብ ነው። የሁሉም ኢትዮጵያውያን የኑሮ መሻሻል ህብረ-ብሄራዊነትን ያጠናክራል።

ለዚህ ህብረ-ብሄራዊነት አላማ ጸር የሆነው የህወሓት መንግሥት የራሱን ህገ መንግሥት አንቀጾች ሙሉ በሙሉ ጥሶ ተቃዋሚ የሆነውን ሁሉ ያስራል። በድብቅ ይገድላል። ያሳድዳል። እነደዚህ ባለ፤ ህግ በማይከበርበት አገር፤ በሰላም ለመኖር፤ ኑሮን ለማሻሻል፤ለማደግ፤ የግል ስራ ለማቋቋም፤ ንብረት ለማፍራት አይቻልም። የተዛባ እድገት አይቀርም። ዛሬ በትግራይና በሌሎች ክልሎች መካከል የሚታየው የህብረተሰብ ኑሮ ልዩነት የመጣው ከዚህ አድሏዊ ከሆነ የባጀት አጠቃቀም፤ የእርዳታ አወራረድ ስልት ነው። የምናየው ሃቅ፤ ኢትዮጵያዊ የሆነ ተወላጅ መብት ሲከበር አይደለም። ሃቁ፤ መብትና ሃብት፤ ህወሓት እንደፈለገ የሚሰጠው። አንደፈለገ የሚነጥቀው ሆኗል። ማንም በኑሮው፤ በማሳው፤ በሃብቱ፤ በሰብእነቱ ሊመካ ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። ማንም በአገሩ በነጻነት ሊኖር አይችልም። “አገርህ ክልል ነው፤ ወደመጣህበት ተመለስ” እየተባለ ነው። ጉዞው ከቀጠለ፤ አዲስ አበባን መልቀቅ አይቀርም። ማንኛውም መብት ከመቅጽበት ሊወሰድ እንደሚችል ደጋግመን አይተናል። የመናገር፤ የመሰብሰብ፤ የመንቀሳቀስ ወዘተ መብቶች ሁሉ እንደ ችሮታ፤ በህወሓት ፈቃድ የሚሰጡ፤ እንደቅጣት የሚነሱ ሆነዋል። የሕዝብን ሰቆቃ ከህገመንግስቱ አንጻር ብናየው ይህ ጸረ ፍትህ፤ ጸረ- ርትእ፤ ጸረ- እርጋታ፤ ጸረ-ኢትዮጵያዊነት፤ ጸረ-ዘላቂነትና- ጸረ-ተሳትፎአዊነት ያሳያል። ሰው በአገሩ ሃብት ለመያዝ፤ ለመኖር፤ ለመንቀሳቀስ፤ ማሳ ኑሮት ለማረስ፤ ራሱን ለማሻሻል ካልቻለ ዜግነቱ የት ላይ እንደሆነ ለማወቅ ከማንችልበት ደረጃ ደርሰናል። የበላይ አለቃዎችን ባህርይና ተግባር የሚያሳይ ሰእል ከፊታችን ተደቅኖ የሚታይ ለዚህ ነው። የመለስ ማለፍ ይህን አፋኝ ስርአት አባብሶታል።

የህግ የበላይነት በብሄር መሪዎች የበላይነት ተተክቷል

አንድን ህብረተሰብ ዘመናዊ የሚያደርገው ዋና መለያ፤ በሕግ ፊት እያንዳንዱ ግለሰብ እኩልነቱ ሲከበር ነው። ታላቁ የአሜሪክ ፕሬዘደንት አብራሃም ሊንከን፤ “ባርነትን” ሲያጠፉ፤ አብሮ መሰረት የጣለው የሕግ እኩልነትን ነበር። ዛሬ፤ ኢትዮጵያ በጨለማ ዘመን የምትኖር አገር ትመስላለች። የሕግ የበላይነት ፍጹም የለም። ሕገመንግሥት መጻፍና ማስከበር የተለያዩ ናቸው። ሕጉ የሚለውን አይቶ ማነው ወንጀለኛ ብሎ ማመዛዝን የሁላችንም አጣዳፊ ተግባርና ሃላፊነት ነው። “ማንም ኢትዮጵያዊ ወይንም በሕግ በኢትዮጵያ የሚኖር ሁሉ በአገሩ ለመንቀሳቀስና ለመኖር መብቱ ነው” የሚለውን ሕግ ወደስራ የሚተረጉመው የፖለቲካ ስልጣን ያለው ወይንም ወኪሉ ብቻ ነው። ስለሆነም፤ ሌሎች ዲሞክራሳዊ የሆኑ አገሮች “የሕግ እኩልነት” ብለው የሚጠሩት ኢትዮጵያ አይሰራም። የሰብአዊ መብት ድርጅቶች በተደጋጋሚ የሚጽፉት የኢትዮጵያ ሕገመንግስት የፖለቲካ መሳሪይ መሆኑን ነው። የ Freedom House 2012: Freedom in the World Report፤ ኢትዮጵያ ነጻ ካልሆኑ አገሮች መካከል አንዷ ናት ብሏል። ከዚህ ድምዳሜ በድጋሜ የደረሰበት ዋና ምክንያት የፖለቲካና የማህበረሰብ መብቶች በሙሉ ስለተረገጡ ነው። አገዛዙ፤ የኢኮኖሚ ተሳትፎ አፋኝና አድሏዊ ነው። የግል ስራ ለማቋቋም ብዙ ማነቆዎች ፈጥሯል። የኢትዮጵያ መንግሥት፤ በተባበሩት መንግስታት ስብሰባዎች የሰብአዊ መብት አፈና ጥያቄዎች ሲነሱ አይሚገትም። ብዙ ጊዜ አይሳተፍም። የሰብአዊ መብቶችን በጣሱ መንግስታት ላይ አቋም አይወስድም። በ November 2012 የተባበሩት መንግስታት ለሰብአዊ መብት ካውንስል(UN Human Rigts Council) በየጊዜው የሚተኩ አባላትን ምርጫ ከማድረጉ በፊት፤ ፍሪደም ሃውስ በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ጠናካራ አቋም ወስዷል። ተቃውሞውን ያቀረበው የተባበሩት መንግስታት ያጸደቀውን መመሪያ መለኪያ በማድረግ ነው። ይህ፤ አብዛኛው የዓለም ህብረተሰብ የተቀበለው፤ 60/251 እንዲህ ይላል። “አባል የሆኑና አባል ለመሆን የሚፈልጉ መንግስታት በከፍተኛ ደረጃ ሰብአዊ መብቶችን መንከባከብና መጠበቅ አለባቸው። ተወዳዳሪዎች የሚለዩበት፤ ለሰብአዊ መብቶች እድገትና ጥበቃ የሚታይ አስተዋጽኦ ለማድረጋቸው ማስረጃ ሲኖር ነው። ለእነዚህ መብቶች መጠበቅ ቃል ሲገቡ ነው”። በመለኪያው መሰረት፤ የኢትዮጵያ መንግሥት አባል ለመሆን አይችልም።

ፍሪደም ሃውስ ባደረገው ጥናት፤ አይቮሪ ኮስት፤ ኢትዮጵያ፣ ጋቦን፤ ፓኪስታን፤ ካዛክስታንና ቬኔዙዌየላ፤ የተባበሩት የአረብ ኤምሬትስ፤ ነጻ ያልሆኑ፤ ለነጻነት ያልቆሙ፤ ሰብአዊ መብቶችን ያፈኑ ናቸው። የኢትዮጵያ መንግሥት፤ <u>በተደጋጋሚ ሰብአዊ መብቶችን ገፏል።</u> ተቃዋሚዎችን አስሯል። ገድሏል። አገር ለቀው እንዲሄዱ አስገድዷል። ዘገባው እንዲህ ይላል “መለስ ዜናዊ ከ 1995 ጀምሮ ከዚህ ዓለም እስከተለየበት ድረስ የመራው ብቸኛው የፖለቲካ ፓርቲ ኢህአዴግ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ የፖለቲካ ህይወት በሙሉ <u>ይገዛዋል። ያዘዋል። መብቱን ገፎታል።</u> በ May 2011 የተካሄድውን አገር አቀፍ ምርጫ ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥሮ፤ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዳይንቀሳቀሱ አድርጓል። መሪዎቻቸውንና አባሎቻቸውን አስሯል። ስብሰባዎችን በትኗል። ስለሆነም ለማሸነፍ በቅቷል። የኢትዮጵያ መንግሥት፤

ጸረ-ሽብርተኛን ለመቆጣጠር ተብሎ የወጣው አዋጅ ማንኛውን ተቃዋሚ በማሰር፤ በማሳደድ፤ ከስራ በማባረር፤ ተጠቅሞበታል። ገዢው ፓርቲ የሚቆጣጠረው ፓርላማ፤ ማንኛውም ተቃዋሚ ሽብርተኛ (Terrorist) ነው ብሎ አውጇል። ነጻ ጋዜጠኞች በሽብርተኛነት ለፍርድ እንደሚቀርቡ ተስማምቷል። "ህጉ ተቃዋሚ የሆነውን ሁሉ ለማቀብ፤ ለማፈን፤ ለማስፈራራት የታቀደ ነው" ብሏል። ስለሆነም፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ለነጻነትና ለሰብአዊ መብት ሁሉ የሚታገልን ሺብርተኛ ነው ይላል። "በተደጋጋሚ መብቶችን የገፈፈ ነው" በማለት የተባበሩት መንግስታት የህወሓት/ኢህአዴግን መንግሥት አባል እንዳይሆን ጠንካራ ተቃውሞ አቅርቧል። የኢትዮጵያ መንግሥት አባል ሆኖ ከተመረጠ፤ የተባበሩት መንግስታት አመኔታን እንደሚያጣ አሳስቦ ነበር። ውሳኔው የፖለቲካ መሆኑን የሰብአዊ መብት ድርጅቶች በሙሉ እንደሚያስተጋቡት፤ ለአፍሪካ ዲሞክራሳዊ እንቅስቃሴ መጥፎ ምልክት እነደሚሆን አስጠንቅቋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕገ መንግስቱ የሰጠውን መብት ለመጠቀም አትችልም ተብሏል። የህብረተሰቡ ተሳታፊነት የሚካሄደው በፓርቲ ካድሬዎች ትእዛዝ ነው። ማንኛውም ዜጋ በሃይል ተገዶ ከሚኖርበት/ከሚሰራበት ሊባረር ይችላል። ገበሬውንና ዘላኑን ከማሳው ማስወገድ ተከታታይ እርምጃ ሆኗል። የተፈጥሮ ሃብት የሚዳረሰው በፖለቲካ ውሳኔ ነው። የፖለቲካ ውሳኔ ለክልል የበላይ መሪዎች ዱሮ ያላገኙትን ስልጣን አበርክቶላቸዋል። ክልሎች የአዲስ መሳፍንት አምባዎች ሆነዋል ብንል ከሃቁ የራቅን አይመስለኝም። የመንግሥት ባለስልጣናት ከውሳኔው ይጠቀማሉ። ከኅሰኛ መሪዎች መቆላለፍ የመጣ አዲስ የባለጠጋነት ጥቅም ያልነው ይኼን ነው። የተፈጥሮ ጸጋ ባላቸው የአፍሪካ ሃገሮች የዚህ አይነቱ፤ የፖለቲካ ስልጣን ተጠቅሞ ራስን ሃብታም የማድረግ አገዛዝ፤ <u>"የተፈጥሮ ጸጋ እርግማን" (The Resource Curse)</u> ይባላል። የሚጠቀመው ህብረተሰቡ ሳይሆን የፖለቲካ ስልጣን ያለው፤ ወይንም ከባለስልጣኑ ጋር የተቆራኘ ነው። እንደ ቦትስዋና ያሉ አገሮች፤ ከተፈጥሮ ሃብት ሊመጣ የሚችለውን ሰቆቃ ለማስወገድ እንቁና ሌላ የተፈጥሮ ጥሪታቸውን በሕግ ለህዝባቸው ኑሮ መሻሻል በመጠቀም ላይ ናቸው። እርግማኑን ወደ ምርቃት ለውጠውታል። የጋና መንግሥት ተመሳሳይ ፖሊሲ ይጠቀማል። በአጠቃላይ ሕጋዊ የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ጉቦን፤ አድልዎን፤ ሙስናን ይቀንሳል። በኢትዮጵያ የወንዝ፤ የለም መሬት፤ የከተማ ቦታ፤ ልክ እንደ "ተፈጥሮ ጸጋ እርግማን" የፖለቲካ ስልጣን መጠቀሚያ ሆኗል። ነዋሪዎች ካሉበት ሲባረሩ የሚነገረውን እንይ።

አይጋ የተባለው የህወሓት (ድህረገጽ) እና በአዲስ አበባ ነዋሪ የሆነች የፓርቲው ደጋፊ፤ ወይዘሪት ሚሚ ስብሃቱ ያሉትን ስናይ የገጠር መሬት አጠቃቀም፤ ልክ እንደ ከተማው፤ አስከፊ ደረጃ ላይ መድረሱንና የህወሓት ፕሮፓጋንዳ እንደ እውነት የሚገልጸው መሆኑን ያስምርልናል። ሁለቱም፤ የፖለቲካ እንጅ የህግ አስተዳደርን ለማሳየት አልሞከሩም። አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚለው፤ በአሁኑ ወቅት፤ ያለምንም ገደብ፤ የትም ቦታ ለመኖር፤ ለመስራት፤ ለመግዛት፤ ቦታና ማሳ ለመመራት፤ ቤት ለመስራት፤ ስራ ለማግኘት፤ የከፍተኛ ትምኅርት እድል ለማግኘትና ሃብት ለመያዝ የሚችሉ የፓርቲው ባለስልጣናት፤ ቤተሰቦቻቸውና ከፍተኛ አባላት፤ ሁነኛ ደጋፊዎች፤ ምርጥ የትግራይ ተወላጆች፤ የውጭ ባለሃብቶች ብቻ ናችው የሚል ነው። በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን፤ በአንድ አገር ውስጥ፤ በዜግነት ሳይሆን፤ በቋንቋ ብቻ እድል ሲወሰን የመጀመሪያ መሆኑ ነው። አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ እዚህ ግንዛቤ ላይ ደርሷል። ለዚህ የሕዝብ አስተሳሰብ ዋና ምክንያት የሆነው ስርአቱ በይፋ የሚያደርገው፤ አይን ያወጣ የበላይ ባለስልጣናት ብልግናና የማእከላዊ መንግሥት ባለስልጣናት ፍጹም የሆነ የተፈጥሮ ሃብት፤ የገንዘብ እርዳታ ምዝበራና ጎሳዊ አድልዎ ነዉ፡፡ ሁለቱ ከላይ የተጠቀሱት የህወሓት ደጋፊዎች ያሉት እንደሚከተለው ነው።

ካሉበት ተገደው የወጡት፤ ሰብእነታቸውን ህወሓት የሚቆጣጠረው የራሳቸው መንግሥት የገፈፈው አማራወች "ከሕግ ውጭ ባልተፈቀደላቸው ቦታ ስለሚኖሩ" ነው ይላል። በአገራቸው "ህገ-ወጥ" በአሜሪካኖች አነጋገር (Illegal Aliens) ናቸው። የሚያጠያይቀው፤ የአማራ ህብረተሰብ፤ ህገ-ወጥ ከሆነ፤ የትግራይ ተወላጆችን ከትግራይ ውጭ ለመኖር፤ ለመስራት፤ የከተማ ቦታና ማሳ የትም ክልል ለመያዝ፤ ሃብት ለማከማቸት፤ የትም ቦታ ለመነገድ ወዘተ ማን ሕጋዊ አደረጋቸው ብሎ አንድ ታዛቢ ቢጠይቅ መልሱ እንቆቅልሽ ነው። የቅኝ ገዥዎች፤ የአፓርታይድ መሪዎች፤ ዜጎችን ከቤታቸው፤ ከመንደራቸው፤ ከእርሻቸው ሲያባርሩ የተጠቀሙበት ዘዴ ተመሳሳይ ነበር። "ነጭ ከሆንክ የትም ለመኖር ትችላለህ። ጥቁር ከሆንክ ወደ ባንቱስታን መሄድ አለብህ" የሚል በዘር የሚለያይ መመሪያ ይከተሉ ነበር። አፓርታይድ እንዳደረገው፤ የህወሓት መሪዎችም የፈለጉት የተፈጥሮ ሃብቱን ለራሳቸው ማድረግ ነው። የዜጎችን መብት ህጋዊ ማድረግ አይደለም። አኟኮች፤ የኦሞ ሕዝብ፤ አማራ ከያለበት ሲባረር፤ የሚፈለገው መሬቱ ነው። ወደ ኋላ ሄደን ብንመለከተው፤ "ተጨቆንን" ይል የነበረው የህወሓት መስራች አመራር፤ ስልጣን ከያዘ በኋላ፤ ራሱ አይን ያወጣ ጨቋኝ ሆኗል።

የኦሮሞ ሕዝብ፤ በቁጥሩና በመሬት ስፋቱ፤ በኢትዮጵያ አንደኛውን ደረጃ የያዘ ነው። የአማራው ሕዝብ ሁለተኛውን ደርጃ ቢይዝም ህወሓት በሁለት ሚሊዮን ተኩል ቀንሶታል፤ የዚህን ሕዝብ ከጉራ ፈርዳ መባረር የተቃወመ፤ ታሪክ

የሚመዘግበው፤ የኢትዮጵያዊነት መለኪያ የሚሆን ጋዜጣዊ መግለጫ ከሰጡት የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል አንዱ፤ የኢትዮጵያን በእኩልነት የተመሰረተ ብሄራዊ አንድነት የሚደግፍ በጄኔራል ከማል ገልቹ የሚመራው የኦነግ ክፍል ነው። ስለአማራው መባረር ያቀረበውን ተቃውሞ እንደዚህ በሚል ገልጾታል። “ህወሓት በሰላማዊው የአማራ ህብረተሰብ ላይ የሚያደርገው ኢ-ሰብአዊ ፍንቀላ፤ ከህግ ውጭ በሃይል ከማሳና ከኑሮ አስገድዶ <u>ማባረር፤ ወንጀል ነው”</u> ያለው እንከን የለውም። ይህ ኢ-ሰብአዊ የሆነ፤ በህጻናት፤ በእናቶች፤ በአባቶች፤ በገበሬዎች ላይ የተደረገ ህገወጥ ጥቃት ለነዋሪው ህብረተሰብ ኑሮ መሻሻል የታሰበ አይደለም። የፖለቲካ ውሳኔ ነው። “ከፋፍለህ ግዛው” በሚለው የክልል አገዛዝ መሰረት፤ ሆን ተብሎ፤ ሕዝብን ከሕዝብ ጋር ለማጋጨት፤ ብሎም፤ የህወሓትንና የደጋፊዎቹን የፖለቲካና የተፈጥሮ ሃብት የበላይነት አገር አቀፍ በሆነ ደረጃ ለማስተላለፍ ነው። ገዢው ፓርቲ የሰውን ስሜት በመቀስቀስ፤ በኃይማኖት ሆነ በመሬት ነጠቃ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ እርስ በእርሱ ሲያተራምሰው ለማንኛውም ህብረተሰብ ክፍል የኑሮ መሻሻል አይበጅም። ተጠቃሚው ጠባብ፤ የፖለቲካ ስልጣን በሃይል የያዘ፤ በሃይል የሚቀጥል ክበብ ወይንም ኮርፖሬሽን ነው። የትግራይ ሕዝብም ሆነ፤ ተቃዋሚ ክፍሎች፤ ኦነግ የሰጠውን መግለጫና አቋም ፈለግ ተከትለው ህወሓትን/ኢህአዴግን መኮነን ያልፈለጉበት ምክንያት ግልጽ አይደለም። ህገወጥ ድርጊቶች ሲፈጸሙ አቋም መውሰዱ፤ ህብረተሰቡን ያስተባብረዋል። ከብሄርተኛነት ወጥመድ ነጻ እንዲሆን ይረዳዋል። ለሰብአዊ መብቶች ያለውን አቋም ይገልጻል። በማንኛውም የኢትዮጵያ ህብረተሰብ የሚመጣውን የሰብአዊ መብቶች መገፈፍ አለማውገዝ ለስርአቱ እውቅናና ብርታት ይሰጠዋል።

የፖለቲካ ስልጣን የሌለው “አዲስ ከበርቴ” ለመሆን አይችልም

የአይጋ የሚዘገንን ፕሮፓጋንዳ፤ “የአማራው ሕዝብ የአካባቢውን ነዋሪዎች አንጡራ የተፈጥሮ ሃብት ወሰዷል። ይህ ማራቆትና ማደህየትን አምጥቷል” የሚል ነው። አዲስ የፖለቲካ ድንጋጌ ማለት ነው። መሰረተ ቢስ የሚሆነው፤ ላለፉት ሃያ ሶስት አመታት ኢትዮጵያን ለጎሳዊ አድልዎና ለሙስና የዳረጋት ህወሓት/ኢህአዴግ ነው። በጋምቤላ የመሬት ምሪት ተጠቃሚ የሆነው፤ ኦሮሞ፤ ጉራጌ፤ አፋር፤ አማራ፤ ሶማሌ አይደለም። ለም መሬት ከተመራው ሰባ አምስት በመቶው የትግራይ ተወላጅ ነው። በአይጋ አነጋገር ምርጥ ትግሬዎች ወራሪዎች ናቸው ማለት ነው። ይኼን አባባ አንጋራም። አባባሉ በሚዛናዊ እድገት ሲመረመር መሰረት የለውም።  የትም አገር፤ ማንኛውም የሃገር ተወላጅ በዜግነቱ፤ አገሩ ውስጥ ሰርቶ መኖር የአካባቢ ሕዝብ ይጎዳል ሲባል የመጀመሪያ መሆኑ ነው። እንዳባባሉ ከሆነ፤ ተሰዶ የሚኖርውም ኢትዮጵያዊ የአካባቢውን ህብረተሰብ ጥቅም ይጎዳል። ይህ ከሆነ፤ ሁላችንም ወደ ኢትዮጵያ መመለስ አለብን። ስንመለስም፤ መግቢያችን ኢትዮጵያ ሳትሆን ክልላችን ነው። ህወሓት/ኢህአዴግና ደጋፊዎቹ ኢትዮጵያን እንደ ግል ሃብት ቆጥረዋታል። እንደ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሃገርና ሃብት ናት ብለው ለማየት አልቻሉም። አገሪቱን የግል ሃብት ስላደረጓት፤ ማን የት እነደሚኖር ይወስናሉ። “የተፈጥሮ ጸጋን እርግማን” የሚያሳየው፤ አምባገነኖች ስልጣን ሲይዙ ከሁሉም በላይ ለመቆጣጠር የሚወስኑት፤ ማእደን፤ የከተማና የገጠር ቦታ፤ ከእርዳታ የሚገኝ ገንዘብ ወዘተ ነው። ቁጥጥሩ፤ ለምዝበራ፤ ለጉቦ፤ ለሙስና ለአድልዎ ይረዳል። ያለ አግባብ በአመት፤ ከሶስት ቢሊዮን ዶላር በላይ ወይንም ከአምሳ አምስት ቢሊዮን  የኢትዮጵያ ብር በላይ ከአገር ህገ-ወጥ በሆነ መልክ ለማሸሽ ሙሉ የፖለቲካ፤ የተፈጥሮ ጸጋ፤ የኢኮኖሚ፤ የውጭ ግንኙነት፤ የጉምሩክ፤ የባንክ፤ የመገናኛ፤ የፍርድ ወዘተ የበላይነትንና ተቃዋሚን በእያለበት ማንበርከክን ይጠይቃል።

ስልጣንና ሃብት፤ ከባለስልጣናት ጋር የቅርብ ግንኙነት የሌለው ሙሰኛ ሊሆን አይችልም። በቅንነት የሚያገለግል የመንግሥት ባለስልጣን አይሰርቅም። ገንዘብ አያሸሽም። የማምረትና የቁጠባ አቅሙ ዝቅተኛ የሆነ፤ በውጭ እርዳታ የሚኖር፤ ስደተኛው በሚልከው ገንዘብ የሚመካ ግለሰብ ንዘብ ለማሸሽ ችሎታ የለውም። በአብዛኛው፤ ለመስረቅ፤ ለመዝረፍና ገንዘብ ከአገር ለማሸሽ የሚችሉ፤ የፖለቲካ ስልጣን ተጠቅመው፤ አዲስ ሚሊኒየር የሆኑ የስርአቱ ፍጥረቶች ናቸው። በተጨማሪ፤ ሰርተው፤ አትርፈው፤ በአገራቸው ለመስፋፋት የፖሊሲ መስናክል ያጋጠማቸው፤ በመንግሥቱ እምነት የሌላቸው ገንዘብ ያሸሻሉ። የውጭ ኢንቬስተሮችም ከባለስልጣናት ጋር በመደጋገፍ የማሸሽ እድል አላቸው። አላሙዴ የሚያመርተውና ለውጭ ገበያ የሚያቀርበው የኢትዮጵያ ወርቅ ተቆጣጣሪ የለውም፤ አይፈተሺም፤ አግባብ ያለው ቀረጥ መክፈሉን እንጠራጠራለን። የአገር ውስጥ አዲስ ሃብታሞች፤ የትም ለመኖር። የትም ሃብት ለማካበት፤ ታከስ ላለመክፈል፤ ከጉምሩክ ውጭ እቃ ለማስገባት፤ አየር ባየር  ለመነገድ ወዘተ መብት አላቸው። የትም ለመንቀሳቀስ። የትም የተፈጥሮ ሃበት ለመያዝ። እነደፈለጉ ለመዝረፍ። እንደፈለፉ እቃና ገንዘብ ለማሸሽ። እንደፈለጉ በማላየዢያ ወዘተ ብዙ መቶ ሚሊዮን ዶላር ለመደበቅ ችለዋል። ባጭሩ፤ የፖለቲካ የበላይነት፤ ለምዝበርና ገንዘብ ለማሸሻ፤ ወዘተ እየረዳ እናየዋለን። የስልጣን ብልግና (Abuse of Public Trust and Authority) ማለት እንደዚህ ነው። ባጭሩ፤ የፖለቲካ ስልጣኑን በሃይል የያዘው ህወሓት ከፍተኛ ባለጸጋነትን ያስረከበው ለራሱና ለመረጣቸው፤ በአብዛኛው፤ ተባባሪ ለሆኑ የብሄር ፖለቲካ ፓርቲ አለቃዎችና ደጋፊዎቻቸው ነው።

አድልዎና አዲስ ባለጠጋነት የባለስልጣን መከታ ያስፈልገዋል

የህወሓት መሪዎች አይን ያውጡ ኪራይ ሰብሳቢዎች ሆነዋል። በአሁኑ ወቅት አዲስ አበባ፤ ቦሌ ሰፈር፤ የምርጥ ትግራይ መኮንኖች በርካታ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች፤ ግምታቸው እያንዳንዳቸው ከ 45 እስከ 90 ሚሊዮን ብር (ከባንክ የመጣ፤ የሕዝብ ገንዘብ በመበደር) የተሰሩ ስለተደረደሩበት ይህን አካባቢ ሕዝቡ "ክልል አንድ" ብሎታል። ስሙ፤ የትግራይ ክልል መለያ መሆኑን አንባቢ ይረዳዋል፡፡ የህወሓት ደጋፊዎች የማይቀበሉት ነገር አለ። የስልጣንና የሃብት ክምችት መብት ለትግራይ ገዢ ቡድንና ታማኝ ደጋፊዎች ብቻ ነው የሚለውን። የህወሓት አለቃዎች "ኢኮኖሚውን ለጠባብ ቡድን መስጠት የትግሉ ውጤት ነው" ብለዋል። የትግራይ ክልል ፈጣን ልማት "በጦር የተጎዳው የክልሉ ሕዝብ" ካሳ ነው የሚሉ ይመስላል። ነጻ ጋዜጠኞችን ማሰርና ማባረር እውነቱ እንዳይነገር ለማድረግ ይረዳል። ተቃዋሚ ፓርቲ እንዳይኖር ማድረግ ለህብረተሰቡ ሌላ አማራጭ እንዳይቀርብ ይረዳል። ህወሓት፤ ለስሙ፤ ግራ ክንፍ ነበርኩ ቢልም፤ አሁን ማህበራዊ አይደለም። በምዝበራ የተበከለና ጎሳዊ ነው። ራሱን አገልጋይ ከበብ ፈጥሯል። ማህበራዊ ስርአት የመላው ህብረተሰብ አገልጋይ ሲሆን፤ የህወሓት ስርአት በግልጽ የሚታይ የጎሳ አድልዎ እያደረገ ነው። በዚህ ፍልስፍና መሰረት፤ ይህ ቡድን ስልጣን ላይ ለመቆየት የተገኘውን ሃብት ለመጠበቅና ሌላም ለማካበት፤ የግድ ተወዳዳሪ የሆኑ ወይንም ሊቀናቀኑ ይችላሉ የሚላቸውን አገር ወለድ ጠበቃዎች ሁሉ ማቀበ/ማገብ ወይንም ማስወገድ አለበት። የሰብአዊ መብቶች መታፈን፤ ለኢኮኖሚ የበላይነት፤ ለአድልዎ፤ ለጉቦ፤ ለሙስና ይጠቅማል። የሕዝብ ጠበቃ አይኖርም። ቁልፍ የሆኑ ህወሓት የፈጠራቸው የተቋም መሪዎች- ከደሞዛቸው በላይ- ግልጽና አሳፋሪ በሆነ መልክ የፍጆት እቃዎች እንዲያስገቡ። የቅንጦት አኗኗር እንዲኖሩ ያደርጋል። የህወሓት ጀኔራሎች፤ ታላላቅ ፎቆችን ለመግዛት ወይንም ለመገንባት የቻሉት በራሳቸው ደሞዝና ሃብት አይደለም። "ደግፊኝ፤ እደግፍሃለሁ" በሚል የስልጣን ማቆያ ስልት ነው። ይህን አመለካከት የሚያጠናክረው፤ የፖሊሲ ወሳኝና አስፈጻሚዎቹ፤ እስካሁን፤ የአንድ ብሄረሰብ ስብስቦች መሆናቸው ነው። የትግራይ ክልል በሚያስደንቅ ሁኔታ ሌሎቹን ክልሎች--በከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች፤ በሆስፒታሎች፤ በዘመናዊ ፋብሪካዎች፤ በውሃ ግድቦች--አልፏቸው የሄደበት ዋና ምክንያት የፌደራሉ መንግሥት ከፍተኛውን የውጭ

እርዳታና የፌደራል ባጀት ወደ ክልሉ ስላስተላለፈው ነው። ወሳኞቹ የኢትዮጵያን ሕዝብ አይወክሉም። የፌደራል አገዛዙ ለሙሉ ቁጥጥር ይረዳል። ባጀት እንደ ልብ ለማሸጋገር ይረዳል። ወጭውን በምስጢር ለመጠበቅ ይረዳል።

የህወሓት ደጋፊዎች ለመቀበል የማይፈቅዱት፤ የሃይልና የሃብት ሁኔታው ሲመዛዘን፤ አማራ ሆነ፤ ኦሮሞ፤ አፋር ሆነ፤ ሶማሌ ወዘተ በአገሩ ያለገደብ፤ ሊወዳደር፤ የግል ሃብት ለማቋቋም አቅምና ዋስትና የለውም። የህወሓት አመራር ፈቃድና ታማኝነት ያስፈልገዋል። ጉቦ፤ ኮሚሽን መከፈል አለበት። ከበቡ፤ እድገትን የሚያየው ከጥቂቶች ጥቅምና ታማኝነት አንጻር ነው። ከማህበራዊ መሻሻል አይደለም። ለዚህ ነው፤ የእድገት ጥቅሙ ለማንና እንዴት እንደሆነ መታየትና መገምገም ያለበት። ማንኛውም ማስረጃ የሚያሳየው የተዘረጋው የኢኮኖሚ የበላይነት ፍጹም የትግራይ ምርጥ ቡድንና ታማኝ ደጋፊዎቹ መሆኑን ነው። ግልጽነት (Disclosure) የለም። ማን የመንግሥት ስልጣን አደራ ይዞ ሃብት እንደሚያካብት ለማወቅ ግልጽነት ቁልፍ ነው። ይህ ያለመንግሥት ፈቃድ አይቻልም። እስካሁን ህብረተሰቡ በሹክሹክታ የሚነጋገርበት፤ ሃብት የጥቂት ቤተሰቦች መሆኑን ነው። ይህም ሊሆን የቻለው የፖለቲካውና የኢኮኖሚው ዘርፎች የተቆላለፉ በመሆናቸው ነው። ተወዳዳሪነት የለም። አስተዳደሩ ክልላዊ ነው። ክልላዊነት ሃብት ለመደበቅ አመቺ ነው። ሌላው የሚነገረው፤ አገር ወለድ ኢኮኖሚ ለማደግ ያልቻለው አገዛዙ ስላፈነው የሚል ነው። አባባሉ፤ በአምባገነናዊ አገዛዝና በሃብት ዘራፊነት ያለውን ግንኙነት ያመለክታል። በብዙ የአፍሪካ አገሮች ታሪክ እንደታየው፤ የፖለቲካ ስልጣን መያዝ፤ ለሃብት ክምችትና ለጎሳዊ አድልዎ ቁልፍ ነው። ተጠያቂነት ከሌለ፤ ሙስናና አድልዎ ገደብ አይኖረውም። የኢትዮጵያን ለየት የሚያደርጉት ብዙ ምክንያቶች አሉ። ጥቂቶቹ።

የህወሓት ምርጥ ቡድን የሃብት ክምችት በቃኝን አያውቅም። ይሉኝታን አያውቅም። ከተሳትፎ የሚመጣውን የህብረተሰብ ጥቅም አይቀበልም። የግለሰብ መብትን አያውቅም። በሕግ የመዳኘትን ምንነት አያውቅም። አይቀበልም። በህግ የበላይነት አያምንም። አብሮ መኖርንና ነጻ ውድድርን ይፈራል። የሚያውቀው ዋና እምነት፤ ሕግን ለአፈና መጠቀም። ፍጹም በሆነ፤ በዘርና በጠባብ ቡድን የተደራጀ የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነትን ብቻ ነው። የተፈጥሮ ሃብትን ሙሉ ቁጥጥር ማየት ለዚህ ይጠቅማል። የኦክላንድ ተቋም (ኦክላንድ-ኢንስቲቱት) ያለውን ማየት በቂ ነው። ቢጋምቤላ ብቻ 75 በመቶ የሚሆነው ለም መሬት ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች የተሰጠው፤ በምሪት መልክ ለትግራይ ተወላጆች መሆኑን መዝግቧል። ኤፈርት የተባለው የፓርቲው ፈጠራ፤ ስንት ቁልፍ የሆኑ ድርጅቶችን፤ በአገር ደረጃ እንደያዘ ማሰብ ይረዳል። ዛሬ ካፒታሉ ከዜሮ ጀምሮ አምሳ ቢሊዮን ብር እንደደረሰ ይገመታል። በኢኮኖሚው ዘርፍ የሚታየው፤ ይህንን የሚመስል ፍጹም የበላይነት፤ የውጭ ታዛቢዎችን ለብዙ አመታት ሲያነጋግር ቆይቷል። "ትግራይ የግላችን፤ ኢትዮጵያ የጋራችን" የሚለው የኢትዮጵያውያን አባባል ከዚህ የበላይነት የመነጨ ትዝብት ነው። ለምርጥ

የትግራይ አዲስ ሃብታሞች አገልጋይ እስከሆነ ድረስ፤ ማንኛውምን የስራ ዘርፍ መንጠቅ ህጋዊነት አለው። የትግራይ ተወላጅ ላልሆኑ- በአብዛኛው ማለታችን ነው--የግል ሃብት የሕግ ዋስትና የለውም። መንግሥት በፈለገ ጊዜ፤ በፈቃድ፤ በቀረጥ፤ በሽብርተኛነት አሳቦ ሊወስደው ይችላል። ቡድኑ እንደፈለገ፤ (በልማት ስም) ህገመንግሥቱን ጠምዝዞ፤ አገር ሊቸረችር ችሏል። ግድያም አድርጓል። የራሱ ታማኝ ደጋፊ ካልሆነ፤ አንድ ሰው ባልሰራው ነገር፤ ህገወጥ ነህ ለማለት ይችላል። ፓስፖት ሳይቀር ይቀማል። ህጉን ጠምዝዞ ለማሰር ወደኋላ ብሎ አያውቅም። አዙሮ፤ ሰው ባልፈጸመው ወንጀል "ይቅርታ ጠይቅ/ጠይቂ" ለማለት ይችላል። ባጭሩ፤ በኢትዮጵያ የመኖር/አለመኖር። የመስራት አለመስራት። የመከበርና መደኸየት ሁኔታ በጠባብ ጎሰኛነት መነፀር የሚታይ እየሆነ ሄዷል። እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን አበይት ነገር አለ። ይኼ ሁሉ ግጭት ፈጣሪ መሆኑን።

ባለፉት ሃያ ሶስት አመታት፤ በተለይ መለስ ይመራው የነበረው መንግሥት፤ Freedom House እንዳቀረበው፤ ሕጉን ሲጠመዝዝ፤ ድርጊቱ፤ አብዛኛዎቹ የዓለም መንግስታት ከተቀበሏቸው የህግ፤ የሚዛናዊ እድገት መስፈርቶችና የሰብአዊ መብቶች መለኪያዎች እጅግ የተራራቀ መሆኑ ታይቷል። በህገ መንግሥቱና በሰብአዊ መብቶች መረገጥ መካከል ያለው ሜዳ ለምን እንደተራራቀ እናውቃለን። ምክንያቱ፤ የፖለቲካ የበላይነትን ከኢኮኖሚ የበላይነት ጋር ለማቆየት ነው። የብድር ሊጋሶች፤ ህገ መንግሥቱ ሲጣስ፤ ለምን ዝም እንዳሉ እናውቃለን። ምክንያቱም፤ የራሳቸው ጥቅም እስከተጠበቀ ድረስ፤ የሰብአዊ መብቶች መረገጥ አያስጨንቃቸውም። ሶሪያ በራሷ የውስጥ ጦርነት ፈራርሳለች። የምእራብ መንግስታት፤ በሶሪያ ከመቶ ሺህ በላይ የተገመተ ንጹህ ሰው ሲሞት ሊቢያ እንዳደረጉት ለተቃዋሚው የሚሊተሪ ድጋፍ ያልሰጡበት ምክንያት፤ ጥቅሙን ከጉዳቱ ስላመዛዘኑ ነው። የሚዳኘው የራሳቸው ጥቅም ነው። ለአሜሪካም ሆነ ለሌች መንግስታት፤ አምባገነናዊ መንግስት ጥቅም አለው። በውድድር እናምናለን የሚሉ ሊጋስ መንግስታትና አነደ ዓለም ባንክ ያሉ አበዳሪ ድርጅቶች፤ ለምን በድፍረት ውድድር አልባ አመራር ዘላቂነትና ፍትሃዊነት ያለው እድገት አያመጣም ብለው  እንደማይናገሩ እናስብ። የራሳቸው ጥቅም እስካልተነካ ድረስ፤ አንድን አገር "ስይጣን" ወይንም "ዝንጀሮ" ቢገዛው ግድ የላቸውም። የፊሊፒንሱን ማርቆስ፤ የችሌውን ፒኖቸ፤ የዛየሩን ሞቡቱ፤ የግብጹን ሞባረከ፤ ወዘተ ደግፈዋል። የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሆነ፤ የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ድርጅት የህወሓትን ኢ-ሰብአዊ ድርጊቶች ተጠያቂ ባለስልጣናት ማንነት ያውቃሉ። ዝም ብለው የሚመለከቱበት ዋና ምክንያት፤ ጥቅማቸው ስላልተነካ ነው። የምእራብ መንግስታትን፤ በተለይ፤ የአሜሪካን ፈለግ ስለሚከተሉ ነው። ገዢው ፓርቲ ከምእራብ አገሮች ጋር ቁልፍ ግንኙነት አለው። ተቃዋሚው ደካማ ስለሆነ፤ ለኢትዮጵያና ለመላው ሕብረተሰብ መብቶችና ጥቅም ቆሞ ከገዢው ፓርቲ የበለጠ አማራጭ ስላላቀረበ ጭምር ነው። የተቃዋሚው ክፍል ደካማነት ለሰብአዊ መብቶች መገፈፍ አስተዋጽኦ አንዳለው መካድ አይቻልም። ጠንካራ የተቃውሞ አለመኖር ክፍተት ባስቸኳይ መፈታት አለበት። አለበለዚያ፤ የፈለገውን ደብዳቤ ብንጽፍ፤ ሰልፍ ብናደርግ፤ በፓልቶክ ብንነጋገር ዋጋ የለውም። የጎሳና የቋንቋ ስርአትና አስተዳደር በምንም ሰላምና ፍትሃዊ እድገት አያመጣም የሚለውን መንግስታትና አበዳሪዎች ያውቁታል። የዓለም ባንክ የውስጥ ዘገባ እንዲህ ይላል። "የሕዝብ ተሳትፎ የሌለበት የልማት አመራር ድህነትን አያጠፋም። የአብዛኛውን ኑሮ አያሻሽልም። በደሃና በሃብታም መካከል ያለውን ልዩነት ያባብሳል።"  ይህን ካለ በኋላ ብድሩን ጨምሯል። ወደፊትም፤ አሜሪካኖች ድጋፍ እስከሰጡ ድረስ ብድር ይሰጣል። ሁኔታው እንዳሁኑ ከቀጠለ፤ እንኳን  ለቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮ መሻሻል ቀርቶ ለኢህአዴግ ስድስት ሚሊዮን አባላትም አያዋጣም። ኢኮኖሚው ምርታማ ካልሆነ ጥገኛ ሆኖ ይቆያል። ምጽዋተኛ የሆነ ኢኮኖሚ በውጭ ለመደገፍ ዋስትና የለውም።

ከላይ የቀረበው እንደሚያሳየው፤ ለጥቅምና ለፖለቲካ ፍጹማዊ የበላይነት የቆመው ህወሓት በበላይነት የሚያዘው የኢህአዴግ መንግሥት፤ ለአገር ዘላቂ ጥቅም፤ ለሏአላዊነትና ለነጻነት፤ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላም፤ ለሰው ክብር፤ ለሰብእነት፤ ለእኩልነት፤ ለሁሉም የኑሮ መሻሻል፤ ለፍትህ ወዘተ ደንታ የለውም። ኢኮኖሚው እንዳያመርት ማነቆ ሆኖበታል። የአብዛኛው ሕዝብ ኑሮ የሚያሳየው የገዢው ፓርቲ ቆይታ አደጋ ውስጥ እንደገባ ነው። ለዚህ ጨለማ ለሚመስል የአገዛዝ-በደል፤ ስፋትና ጥልቀት ያለው ችግር፤ ፓርቲው ብቻውን የማይፈታው መሆኑን ያሳያል። የአገዛዙ ችግሮች በዱብዳ የመጡ አይደሉም። ታስበው የተጸነሱ፤ የውጭ ድጋፍ ያላቸው ናቸው። ድጋፍ ስላላቸው፤ የሰብአዊ መብት ድርጅቶች ደጋግመው አደጋውን ቢያስረዱም፤ አዳማጭ አላገኙም።

የጠባብ ጎሰኛነት/ብሄርተኛነት አገዛዝ፤ ከጽንሰ ሃሳብ ወደ ተግባር

የህወሓት ፍልስፍና ከአጀማመሩ በዘር ጥላቻ ልዩነቶች የተበከለ መሆኑን መካድ አይቻልም። ስሙ ራሱ፤ እስካሁን ያልተለወጠ፤ በትግራይነቱ የሚያምን ነው። ለትግራይነቱ የቆመ ነው። ለዚህ የዘር አገዛዛዝ ግንባታ፤ ሆነ ብሎ ኢትዮጵያዊ የሆኑ ተቋሞችን እየለወጠ ወይንም በሙሉ እያጠፋ በምትካቸው በክልልና በጠባብ ዘረኛነት የተቀረጹ፤ በስልት የተደራጁ፤ የትግራይን ህብረተሰብ ከሌላው ለመለየት፤ "ትግራይ የራሳችን ኢትዮጵያ የሁላችን" ብሎ የተነሳ፤

አገር ከፈረሰ “ታላቋን ትግራይ” አገነባለሁ ብሎ ያቀደ ነው። አሁንም፤ የበላይነቱን ካጣ ለመገንጠል የሚከጅል መሆኑን የሚያመለክቱ ብዙ ማስረጃዎች አሉ። ግልጽ ለማድረግ የምንፈልገው፤ በትግራይ ሕዝብ ስም ለጠባብ፤ እንዲያውም፤ ለመንደር ቡድኑ አገልጋይ ሆኗል። ለክልሉ ብዙ ቢሊዮን ብር አፍስሷል። አካባቢውን አሻሽሏል። ዘመናዊ ከተሞች መስርቷል። ሆኖም፤ አብዛኛውን የትግራይ ህብረተሰብ ከድህነትና ከስደት ነጻ አላወጣውም። የትግራይን ሕዝብ በሙሉ አይወክልም። አብዛኛው የትግራይ ህብረተሰብ ከሌላው ሰፊ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር የሚጋራው ያደላል። ይህ ጠባብ ቡድን፤ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያደረሰውንና የሚያደርሰውን በደል የትግራይ ህብረተሰብ ያውቃል። እየቆየ፤ እንደሚታገለው ማመን ይኖርብናል። ለመታገል ካልደፈረ፤ አሁን ያለው የአስተዳደር፤ የሙስና፤ የሰብአዊ መብቶች ናዳ ወዘተ በደል እየባሰ ይሄዳል። የህወሓት አመራር የብሄርና የሃይማኖት ጥላቻውን ያባብሰዋል። ኢትዮጵያ ደከማ ህብረተሰቧም ይደከማል።

የፖሊሲ ጥፋትና ድክመት

ዋናው ከርክርና ልዩነት የፖሊሲ ነው። የግል ጥላቻ አይደለም። ብሄራዊ /ኢትዮጵያዊ አለመሆኑ። ታሪክ የመዘገበውን እንይ። ኢሳይያስ አፈወርቂና ቡድኑ፤ ከኢትዮጵያ ለመለየት ያዘጋጁትን፤ አረቦችና ሌሎች የኢትዮጵያ ጠላቶች ይመኙት የነበረውን እቅድ ከስራ ያዋለው ይህ መለስ ዜናዊ የመራው ጠባብ ብሄርተኛ ቡድን፤ ህወሓት ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ የባህር፤ የንግድ፤ የሃሳብ፤ የስልጣኔ፤ የሕዝብ እንቅስቃሴ ታሪክ ነው። ባህረ ነጋሽ (በኋላ ኤርትራ የተባለችው) የዚህ ታሪክ አካል ነበረች። ስለሆነም፤ ኢሳይያስ የመራው ሻቢያና እነ ስብሃት ነጋ ያቋቋሙት የጠባብ ጎሰኛ ነጻነት አውጭ ግንባር፤ የዚህ ቡድን ሴራ ስራ ላይ ውሎ ኢትዮጵያን ወደብ አልባና ጥገኛ አድርጓታል፡፡ ይህ ብሄራዊ ክህደት የኢትዮጵያ መፈራረስ መሰረት ሆኗል። ምስሶው እየወደቀ ነው ያልንበት ለዚህ ነው። ደህንነቷንና የረጅም ጊዜ ጥቅሟን ከአደጋ ላይ ጥሏል። ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በወደብ አገልግሎት ጥገኛ በመሆኗ የምትልከውና የምትሸምተው እቃ ውድ ሆኗል። የእድገቱ መዋቅር ካለመለወጡ ሌላ ወደብ-አልባ መሆኗ እድገቷን ቀንሶታል። ከመለስ እልፈት በኋላ በህወሓት ውስጥ የሚካሄደው የስልጣን ሹኩቻ የኤርትራን ጥቅም ለመጠበቅ በሚፈልጉ--ስብሃት ነጋ፤ በረከት ሰምኦንና ሌሎች በአንድ በኩል እና በሌላ በኩል ህወሓት የትግራይ ተወላጆችን ጥቅም ማገልገል አለበት በሚሉ-መካከል የሚካሄድ ትግል ይታያል። የትግሉ ዋና አላማ ብሄራዊ/ኢትዮጵያዊ ጥቅምን ለማጠናከር አይደለም። ቢሆን፤ ቢያንስ ውይይቱ የፖሊሲ፤ ማለትም፤ የኢትዮጵያን የባህር በር ችግር እንዴት እንፍታው የሚል ይሆን ነበር። ስላልሆነ ግብግቡ የጠባብ ጎሰኞች የስልጣን ሽሚያ ሆኖ ይታያል።

የህወሓት የስልጣን ሽሚያ ተወዳዳሪዎች አሁንም የማይቀበሉት አለ። የኢትዮጵያን ብሄራዊ አንድነትና ደህንነት፤ የአክሱም፤ የጎንደር (ፋሲለደስ)፤ የላሊበላ፤ ወዘተ ስልጣኔዎች ከመከሰታቸው በፊት ኢትዮጵያ የምትባል የታወቀች አገር ነበረች። የኦሮሞ ሕዝብ ከደቡብ ወደ ሰሜን እየተንቀሳቀሰ የራሱን አስተዋጾኦ አድርጓል። ከሌሎች ጋር ቢጋብቻ፤ በባህል፤ በንግድ ተያይዟል። የትግራይ ሕዝብ ከሚኖርበት--በድርቅና ረሃብ የተነሳ- እየፈለሰ በመላው ኢትዮጵያ ተሰራጭቷል። ከሌላው ጋር ተጋብቷል። ሃይማኖቱና ስራው ከአማራውና ከኦሮሞው ጋር አቆራኝቶታል። በብሄር ደረጃ ሲታይ የትግራይ ሕዝብ በመላው ኢትዮጵያ ተሰራጭቷል። ተመልሰህ ወደ ክልልህ ግባ የሚለው ሃይል የለም። መኖርም የለበትም። በጎንደር ክፍለ ሃገር ታናናሽ መንደሮች የትግራይ ተወላጆች ከነዋሪው ጋር ተጋብተው ይኖራሉ። የአክሱም ስልጣኔ የአንድ ብሄር ስልጣኔ ሊሆን የማይችለው ሕብረተሰቡ ህያውና ተንቀሳቃሽና ሌሎች ወደ ክፍለ ሃገሩ እንዲገቡ ይፈቅድ ስለነበረ ነው። ይህ የኢትዮጵያውያን እንቅስቃሴ የሚያሳየው “የትጋራይ ሕዝብ” ከሌሎች ኢትዮጵያውያን የተለየ ምርጥና  የበላይነት (Priviledge) ይገባኛል ለማለት እንደማይችል ለመግለጽ ነው። የትግራይን ሕዝብ ብቻ እወክላለሁ የሚለው ህወሓት ሕዝብ ከሕዝብ የሚለያይ ፖሊሲ የጠባብ ጎሰኛ አምባገነን ፖሊሲ ነው። ህወሓት ኢትዮጵያን እንደ-ሸቀጥ ለመቸርቸር ሙብት የሰጠው ሕዝብ የለም።

በፖለቲካ የበላይነት ሆነ በኢኮኖሚ አመራር መንግሥት የሚመራ ፓርቲ ጎሳዊ አድልዎ ሲያደርግ የሚጎዳው አገር ውስጥ ባለጠጋ ለመሆን ምኞትና ችሎታ ያላቸውንና ህብረተሰቡን ነው። የባህር በሩ የተዘጋው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚቀጣው ከብዙ አቅጣጫ ነው። ለምሳሌ፤ ሼክ አላሙዲ ከራሱ ካፒታል በላይ ተወካይ ሆኖ የሚያንቀሳቅሰው የአረቦችን ካፒታል ነው። በተለይ፤ የሳውዲወችን። ህወሓት የሚነግረን፤ ሼኩ ለሰው ስራ እድል ፈጥሯል። ዘመናዊ ተቋሞች መስርቷል ወዘተ ነው። እኛ የምንጠይቀው ይህ ባለጠጋ ትርፍ ካላገኘ፤ በጀርባ ያሉትን ወዳጆቹን ካልጠቀመ፤ ሚና ይኖረው ነበር ወይ የሚል ነው። ጥቂት ወጭ አውጥቶ፤ ከኢትዮጵያ ባንኮች ገንዘብ ተበድሮ፤ የኢኮኖሚ መሰረቶችን-- የወርቅ መአደን፤ ለም መሬት፤ ኢንዱስትሪ፤ ሆቴል ወዘተ--ለመያዝና ለማስፋፋት ከቻለ፤ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ሊሰሩት የሚችሉትን ወሰደባቸው ማለት ነው። ከአረቦች፤ በተለይ ከሳውዲዎች ጋር ያለው የጥቅም ግንኙነት የኢትዮጵያን የተፈጥሮ ሃብት፤ ምሰሶ የሆኑ የኢኮኖሚ ክፍሎች፤ የውስጥና የውጭ ገበያ ከህወሓት አዲስ

ባለጠጋዎች ጋር በመቆራኘት እንዲቆጣጠር ረድቶታል። አረቦች ሳይዋጉ በኢትዮጵያ የዘረጉት ታይቶ የማይታወቅ የተፈጥሮ ሃብት፣ የንግድ፣ ቁልፍ የሆኑ የኢኮኖሚ ክፍሎች ቁጥጥር ስኬታማ የሆነው በህወሓትና በሼኩ አስተናጋጅነት ነው። ይህ የበላይነት ኢትዮጵያውያን በግል ሆነ በጋራ ሊያቋቁሙት የሚችሉትን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በር ዘግቶባቸዋል። ዛሬ ሌሎችም ይኼን ዘዴ ተጠቅመው የእንጀራ ፋብሪካ ሰርተው ለስደተኛው ለማቅረብ ይጣጣራሉ። የኢትዮጵያውያንን እንጀራ እየወሰዱት ነው ማለት ነው። ይኼና ተመሳሳይ በግብዣ የመጣ ኢንቬስትመንት አገሪቱን የበለጠ ጥገኛ አድርጓታል። ለም መሬቷና ወንዞቿ ለውጭ አገር መንግስታትና ኩባንያዎች በመሸጋገር ላይ ይገኛሉ። የዚህ ውጤት በሚቀጥሉት አምሳና መቶ አመታት የሳውዲ ሕዝብ በልቶ ሲያድር አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ በረሃብ ሊሰቃይ ይችላል የሚል ግምት አለን።

ቢቀበልም ባይቀበልም፣ ጠባብና ጎሰኛው ህወሓት ጸረ-ኢትዮጵያዊ ሆኗል። እስካሁን ያገለገለው ራሱን፣ የአረቦችንና የሌሎችን የኢትዮጵያን የተፈጥሮ ሃብት ቁጥጥር ነው ለማለት ይቻላል። የሳውዲዎች ስትራተጂ በመስራት ላይ ይገኛል። ባለፉት ሃያ ሶስት አመታት ያለውን የእድገት ውጤት ስናይ፣ የህወሓት የኢኮኖሚ አመራር ፖሊሲ አንዱ ከሌላው ጋር የተያያዘ አይደለም። ለምሳሌ፣ የአጭር ጊዜው ከረጅም ጊዜው ጋር። የግል ክፍሉ ከኢትዮጵያውያን ከበርቴዎች ካፒታልና ሚና ጋር። የተፈጥሮ ሃብት ልማት ከአካባቢው ዘላቂነት ጋር። ትምኅርት ከስራ መፍጠር ጋር ወዘተ። አላሙዲ በመካከል ሆኖ ያመቻቸው አገር ወለድ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ካፒታሊስቶች የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ እንዲቆጣጠሩ አይደለም። ድልድይ ሆኖ የሚያገለግለው የሳውዲ አረቢያን ሃብታሞችና ራሱን ነው። ለማስታወስ የምንፈልገው፣ የውጭ ካፒታል ወደ ኢትዮጵያ የገባው በመንግሥት ግብዣ መሆኑን ነው። ለዚህ ሁሉ የውጭ ሃገሮችና ኩባንያዎች የበላይነት አስከባሪው የህወሓት የበላይ አመራር ነው። "እድገት በመንግሥት ግብዣ" የምንለው ለዚህ ነው። ችግሩ ዘላቂነትና ፍትሃዊ የሆነ እድገት በግብዣ የተካሄደበት አገር የለም። አጋርነት፣ ለምሳሌ፣ አምሳ አንድ በመቶ የኢትዮጵያ፣ አርባ ዘጠኝ በመቶ የውጭ የሚል ቢሆን ያዋጣል። ጎረቤት የሆኑ ኬንያውያን በአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ጊዜ ሲናገሩ፣ "ኢትዮጵያውያንን ከሌሎች የሚለያቸው፣ የተፈጥሮ ሃብታቸውን፣ ቁልፍ የሆኑ ተቋሞቻቸውን የሚቆጣጠሩት ራሳቸው በመሆናቸው ነው" ይሉ ነበር። ዛሬ፣ ኢትዮጵያውያን (አብዛኛውን ማለታችን ነው) በአገራቸው አያዙባታም። አይኮሩባትም። የተፈጥሮ ሃብቷን ተጠቅመው ኑሯቸውን አላሻሻሉባትም።

የሠብአዊ መብቶች መታፈን  ኑሮን አላሻሻለም

አምባገነኖች የሚሉት ቅልጥፍና ያለው አመራር ወደተሻለ ኑሮ ያመራል ነው። እኛ በምርምር የደረስንበት መብቶች ታፍነዋል። የተራው ሰው ኑሮ አልተሻሻለም ነው። ስለዚህ ህብረተሰቡ በሁለት ጎን ተጎድቷል። ባጭሩ፣ በመብቱና በኑሮው። የተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅት በተደጋጋሚ በ2010 እና በ2013 ያቀረባቸውን የሠብአዊ እድገት መስፈርቶች ስናይ የኢትዮጵያ መንግሥት የተባበሩት መንግስታት የተስማማባቸውን ዝቅተኛ የእድገት መለኪያዎች ሊያማሏ አልቻለም። ዋናው ምክንያት፣ መንግሥት ያተኮረው ትርፍ ከሚያስገኙ ኢንቬስትሜንቶች ላይ ነው። የተባበሩት መንግስታት Millinnium Development Goals (MDGS) ያተኮሩትድህነትን፣ ረሃብን፣ በሽታን፣ መሃይምነትን፣ ስራ አጥነትን፣ የሴቶችን ሁኔታ፣ የአየር ጠባይን ወዘተ ከሚያሻሽሉ መስፈርቶች ላይ ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት የእድገቱን እቅዶች ድህነትን ለማጥፋት መደረግ ባለበት ጥረት ላይ አላዋለውም። ለይስሟላ ያድረጋቸውን መካድ አይደለም፤መሰረታዊ ለውጦች የሉም ማለታችን ነው።

ኢንቬስትሜንቱን ከአቅም ግንባታ ላይ ስላላዋለው፣ የድህነት ጥልቀትና ስፋት እየባሰ ሄዷል። ትምኅርት መስፋፋቱ ባይካድም ጥራት የለውም። አንድ አስተማሪ ከአምሳ ጎልማሳዎች በላይ ያስተምራል። ደብተር፣ መጽሃፍ፣ መጸዳጃ ወዘተ የለም። በብዙ ሺህ የሚገመቱ ወጣቶች ተስፋ ቆርጠው ትምኅርታቸውን ያቆማሉ። ወደ ሶስት ሚሊዮን የሚገመቱ ወጣቶች በጭራሽ ትምኅርት ቤት ለመግባት አልቻሉም። ወጣቶች ተምረው የስራ እድል የላቸውም። በጤና በኩል ሲታይ፣ መሻሻል አለ። ሆኖም በወሊድ የሚሞቱ እናቶችና በረሃብ የሚሞቱ ህጻናት ቁጥር አድጓል። ኢትዮጵያ "ጤናማ ካልሆኑ ደሃ አገሮች መካከል" የመጨረሻ ደረጃ ይዛ ትገኛለች። ኢኮኖሚው መዋቅራዊ ለውጥ ለመፍጠር አልቻለም። ከትግራይ ክልል ውጭ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ስርጭት ከዓለ ዝቅተኛ ነው። ስለሆነም ወጣቱ ስራ የለውም። ከገጠር ወደ ከተማ የሚሄደው ሕዝብ ቤት፣ መጸዳጃ፣ ምግብ ለማግኘት ተቸግሯል።

ደሃነት ካልቀነሰ፣ እርዳታው ወደ ማን ኪስ ገባ?

የውጭ እርዳታ የሚሰጠው የተሻሻለ ኑሮ መቀዳጀት የማንኛውም ዜጋ መብት ነው በሚል መመሪያ ነው። ከውጭ የመጣው እርዳታ ከመቸውም በላይ አድጓል። ባለፉት ሶስት አመታት የኢትዮጵያ መንግሥት በቀጥታ የተሰጠው የልማት ማጎልመሻ ቼክ ሰላሳ አምስት ቢሊዮን ዶላር ደርሷል ሲል ዓለም ባንክ አስታውቋል። በኛ ግምት አርባ ቢሊዮን

ዶላር አልፏል። ሃላፊነት የሚሰማው መንግሥት ይህን ታይቶ የማይታወቅ እርዳታ ድህነትን ለመቀነስ፤ የአገር ውስጥ የማምርት ችሎታን ለማሳደግ ጥረት ያደርግበታል። አልሆነም፤ በ2012 መጨረሻ፤ University of Massachussets በምርምር የደረሰበት ዘገባ ያሳየው ባለፉት ሰላሳ አመታት ሃያ አምስት ቢሊዮን ዶላር ከኢትዮጵያ ተሰርቆ እንደወጣ ነው። ባለፉት አስራ ሶስት አመታት ብቻ አስራ ስምንት ቢሊዮን ዶላር ከአገር ወጥቷል። የመንግሥት ባለስልጣናት በየቦታው የራሳቸውን የግል የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከመንግሥት ሃላፊነታቸው ጋር አብረው ማካሄድ ከጀመሩ ሃያ አንድ አመታት አልፏል። የመጀመሪያዎቹ የመመቻቸት ዓመታት ነበሩ። የዚህ አይነት የግል ጥቅም ከመንግሥት ሃላፊነት ጋር ሲቆራኙ አድልዎ፤ ጉቦና ሙስና በምንም ሊወገዱ አይችልም ። የኢትዮጵያ መንግሥት ሰላሳ አምስት ቢሊዮን ዶላር በአፍሴል የተሰጠ የልማት ገንዘብ በሙሉ ሂሳብ የት እንደዋለ የጠየቀው የለም። ስለሆነም፤ አገሪቱ የተባበሩት መንግስታት ያወጣውን የድህነት መቀነሻ አላማ በሚቀጥሉት ሁለት አመታት ስኬታማ ለማድረግ አትችልም። ገዢው ፓርቲ የውጭ እርዳታ ለግል ባለጠጋነት ሲውል ለህብረተሰቡ ቀጥተኛ የሆነ ዘገባ አላቀርበም። እንዲያቀርብ ያልተገደደበት ምክንያቶች አሉ። Human Rights Watch በተከታታይ እንዳቀረበው፤ ዋናው ምክንያት ነጻ ፕሬስ፤ ነጻ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ፤ ነጻ የማህበረሰብ ድርጅት ወዘተ ስለሌሉ ነው። ለዚህ አስጊ ሁኔታ አስተዋጽኦ ያደረጉት ፖሊሲዎች የሚከተሉት ናቸው።

- ግጭቶች ወላጅ የሆነው የጎሳ ፖለቲካ አደረጃጀትና አመራር።
- የጎሳ-ነክ ህገ-መንግሥትና የክልል አስተዳደር።
- ፖለቲካዊ የሆነ በችሎታ የማይመራ የፌደራልና የክልል አገዛዝ።
- የሠብአዊ መብቶች መታፈን።
- የተማረ የሰው ሃይል ወደ ውጭ እንዲሰደድ መገደድ።
- ከህግ ውጭ የሚሸሸው የውጭ ምንዛሬ።

ከሁሉም በላይ ለድህነት ችግር አለመፈታት ማነቆ የሆነው የሠብአዊ መብቶች ሙሉ በሙሉ መታፈን ነው የሚል ግምት አለን። ኢትዮጵያ ያላትን የተፈጥሮ ጥሪት ተጠቅማ፤ አገር ወለድ ኢኮኖሚ ለመፍጠር ትችላለች። ለዚህ ዋናው መሰረት የገጠሩ ህብረተሰብ ነው። ገበሬው፤ ዘላኑ፤ ነጋዴው ወዘተ የፖሊሲ ለውጥ ያስፈልገዋል። መንግሥት ደጋፊውና አበረታቹ ካልሆነ ማነቆ ሆኗል ማለት ነው። በሌላ አነጋገር፤ መንግሥት ከቁጥጥር አገዛዝ ወጥቶ ለህብረተሰብ ክፍሎች ሙሉ ድጋፍ ቢሰጥ፤ ህብረተሰቡ የተፈጥሮ ሃብቱ ባለቤት ቢሆን፤ አብዛኛው እርዳታ በቀጥታ ወደ አምራች ሃይሎች እጅ (እንደ ሁኔታው) በጋራና በግል ቢገባ፤ ወጣቶች ተምረው በጋራና በግል ዘመናዊ እርሻ እንዲጀምሩ ብድርና ሌላ ድጋፍ ቢሰጣቸው፤ የኢትዮጵያ የግል ክፍል በእየ ቁልፍ ኢኮኖሚው ገብቶ እንዲሰራ ቢደረግ፤ ወዘተ፤ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ የማምረትና ለገበያ ምርት የማቅረብ አቅሙ ወደላይ እንደሚያድግ አንጠራጠርም። ይህ የቀጣይነትና የፍትሃዊነት ልማት መሰረት ነው እንላለን።

የፖለቲካ፤ የማህበረሰብ፤ የኢኮኖሚ ውድድር፤ የእርሻ ልማት መስኮች ከተዘጉ ከላይ ያቀረብነው ሊሆን አይችልም። ዝግ የሆነና ለጥቂቶች የሚያገለግል የኢኮኖሚ አመራር ምርቱን ለማሳደግ አይቻልም። ምርት ካላደገ ገቢ በአስተማማኝ ደረጃ አያድግም። ገቢ ካላደገ፤ ድህነትን አይቀንስም። የመሬት ይዞታ ፖሊሲ በአንድ ፓርቲና በሚመራው መንግሥት ቁጥጥር ከቀጠለ የገጠሩን ኢኮኖሚ ወደ ዘመናዊነት ለመለወጥ አይቻልም። ሕጋዊ የመሬት ባለቤትነት ለምርት እድገት ቁልፍ ነው። ባለቤትነትና ከባለቤትነት የሚመጣ ሃላፊነት፤ አሁን ያለውን ከምግብ ጋር የተያያዘ የዋጋ ግሽበት ሊቀንሰው፤ ቀስ በቀስ፤ ሊያጠፋው ይችላል። በአንጻሩ፤ የአንድ ፓርቲ ቁጥጥርና የመንግሥት ባለቤትነት የእርሻና የሌሎች ምርቶችን እድገት ይቀንሰዋል።

የተመዛዘነ የኢኮኖሚ አመራርና እቅድ፤ በተለይ፤ ለገጠሩ አምራች አጎልማሽ የሆነ የመሬት ስሪት ከሌለ፤ ከጥቂቶች በስተቀር መዋቅራዊ የሆነ ለውጥ አይኖርም። ይህን የልማት አመራር የበከለው፤ ሕዝብ ሳይወያይበት፤ ባለሞያዎች ሳያጠኑት፤ ገዢው ፓርቲ አዲስ፤ ወደ ውጭ ያተኮረ የእርሻ ልማት ፖሊሲ ማውጣቱ ነው። ይህ ፖሊሲ ለም መሬት ከኢትዮጵያውያን እየነጠቀ ለውጭ መንግስታትና ኩባንያዎች፤ በአገር ውስጥ፤ ግልጽነት በሌለው ሁኔታ፤ ለምርጥ ደጋፊዎች አስተላልፏል። ይህ የተፈጥሮ ሃብት ከኢትዮጵያውያን ነጥቆ ለውጭ ኩባንያዎች ማስተላለፍ ተከታታይ--ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍና አደገኛ የተፈጥሮ ሃብትና የገንዘብ ዝውውር ወይንም ሽግግር በመፍጠር ላይ

ይታያል። የተፈጥሮ ሃብት ሽግግር ለተከታታይ ትውልድ አደጋ ያስከትላል። ለሰደትና ለእርስ በእርስ ጦርነት ይዳርጋል። (Multigenerational transfer of real resources from Ethiopians to foreigners and selected domestic individuals that will impact peace and stability).

የአገሪቱን መሬት ለሳውዲ ስታር፤ ለካሩቱሪ መስጠት የምግብ ዋስትና አያመጣም። ድህነትን አይቀንስም። የስራ እድል አይፈጥርም። መጋቢ እንዱስትሪ እያስፋፋም። የዋጋ ግሽበትን አይቀንስም። ፖሊሲው ነዋሪዎችን በማስገደድ ከመሬታቸውና ከኑሯቸው እያባረራቸው ነው። ይህ ፖሊሲ ሰላምና እርጋታ አይፈጥርም። ለተገንጣዮች ዓላማ መጋቢ መሳሪያ እየሆነ ነው። ለአገሪቱ ግዛታዊ አንድነት አደገኛ ነው። የተለያዩ ጥናቶች የሚያመለክቱት፤ የተፈጥሮ ሃብት ያላቸው አገሮች በተቻለ መጠን ያላቸውን ሃብት ለራሳቸው እድግትና ለሕዝባቸው ዘላቂነት ያለው የኑሮ መሻሻል መጠቀም አለባቸ የሚል ነው። ይህን መሰረተ ሃሳብ እኛም እንጋራለን።

የአፍሪካ ታሪክ ያስተማረን፤ ሰፊው የአፍሪካ የተፈጥሮ ሃብት ለአፍሪካውያን ኑሮ መሻሻል እንዳልዋለ ነው። "የተፈጥሮ ሃብት" እርግማን የተባለው ተብሎ የተጠራው ለዚህ ነው። ስለዚህ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተፈጥሮ የለገሰውን ጸጋ በጥንቃቄና ለተከታታይ ትውል በሚጠቅም መንገድ መጠቀም አለበት። ይህን ስንል፤ ከውጭ ኢንቬስተሮች ጋር ድርድር አይደረግ ማለታችን አይደለም። ድርድሩ ለነዋሪዎች፤ ለመላው ሕብረተሰብና ለአገሪቱ ዘላቂነት ማገልገል አለበት። ነዋሮዎችና መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተፈጥሮ ሃብቱ ባለቤትና አዛዥ መሆን አለበት። አለበለዚያ፤ ዘላቂነት አይኖርም። ነዋሪዎችና የኢትዮጵያ ሕዝብ የተፈጥሮ ሃብቱ ባለቤት ከሆነ፤ ቢያንስ የምግብ ዋስትና እንዲኖረው አድርጎ ሊደራደር ይችላል።

የሰብ አዊ መብቶች መታፈን ብዙ ጉድ እንዳወጣ ይረዳል። ከእንዚህ መካከል በአናሳ ጎሳዎች ላይ የሚደረገው በደል አንዱ ነው---በአዋሽ ሸለቆ የሚገኙ እትዮጵያውያን መሬት መነጠቁን የነዋሪዎች ኑሮ መሰናከሉ፤ በጋምቤላ በልማት ስም ሕብረተሰቡ ከቀዩ እንዲባረር፤ የሚኖርበት መተኪያ ሳይሰጠው፤ ለጤና፤ለትምህርትና ሌሎች መሰረታው ፍላጎቶች የተሟሉ ስራዎች ሳይካሄዱ "በአዲስ መንደሮች" ስፈር መባሉ ምሳሌ ነው። ሌላው አብዛኛውን ሕዝብ ያስመረረው የዋጋ ግሽበት፤ የአቅርቦት እጥረት ነው። ጥሮ ግሮ የሚኖረው ሕዝብ ገቢ በፍጥነትና በአስፈላጊው መጠን አያድግም። በገጠር የሚኖረው ገበሬ ምርቱና ገቢውም ቢጨምር የሚፈልገው እቃ ዋጋ ከፍተኛ ስለሆነ የመግዛት አቅም የለውም። የአገሪቱ ኢንዱስትሪ ለፍላጎት የሚሆነውን እቃ ለገጠሩና ለከተሜው ሕዝብ በተመጣጠነ ደረጃ ለማቅረብ አልቻለም።

ባጭሩ፤ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የምግብ ዋጋ ግሽበት መሮታል።

የሚከተለውን የ2012 የምግብ ዋጋ ግሽበት ሰንጠረዥ እንይ፤

| አይነት፤ | ዋጋ፤ በብር |
|---|---|
| ንጹህ ስንዴ ለመቶ ኪሎ | 900-1000 |
| ገብስ ለመቶ ኪሎ | 950-1000 |
| ጤፍ ለመቶ ኪሎ | 980-1080 |
| ሽሮ ለአንድ ኪሎ | 24.00 |
| በርበሬ ለአንድ ኪሎ | 900 |
| ሽንኩርት ለአንድ ኪሎ | 10.00 |
| ስኳር ለአንድ ኪሎ | 50.00 |
| ቅቤ ለአንድ ኪሎ | 180.00 |
| ዶሮ (አንድ) | 180.00 |
| የከብት ስጋ ለኪሎ | 100.00 |

በስደት የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ክብደቱን አያየውም። በውጭ በዶላር ከሚያስብና ደልቶት ከሚኖረው ሕዝብ አንጻር ሲታይ፤ ዋጋው ቀላል ይመስላል። አይደለም። ማየት ያለብን ከተራው ሰው ገቢና ወጭ አንጻር ነው። "ምን ቀን አመጣህብን፤ መቼ ይሆን ደህና ኑሮ የምንኖረው" የሚለው፤ የመሸመት አቅሙ ስላልቻለ። የእድገቱ ተካፋይና ተጠቃሚ ስላልሆነ ነው። በሽራተን ዊስኪ የሚቀያይረው አዲስ ሃብታም አይሰማውም። የተለየ ዓለም ውስጥ ይኖራል። እድገቱ ገቢውን ጨምሮለታል። አብዛኛው ሃሁ የቆጠረ ሁሉ ከአገር መሰደድ የሚመርጠው ወዶ አይደለም። እድልና ሰላም ስለሌለ። የኑሮ ውድነቱን ስላልቻለው ነው። ይህ አስቃቂ የኑሮ ሁኔታ ሊቀየር የሚችለው፤ አገር ወለድ ኢኮኖሚ ሲፈጠርና ሁሉም የእድገቱ ተካፋይ ሲሆን ነው። ምርት ሲያድግ ነው። በሁሉም አገሮች የተፈተነ የእድገት መለኪያ የሚያሳየው፤ መልካም የህብረተሰብ አመራር፤ ገንቢና ውጤታማ የሆነ ማህበረሰብ ይፈጥራል። ሰው እፎይ ብሎ፤ በልቶ ያድራል። ለዚህ ውጤታማ ለሆነ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ኑሮ መሻሻል፤ የመንግሥቱ አመራር አጎልማሽ፤ ጸረ አድልዎ፤ ጸረ-ሙስና መሆን አለበት። ለኢትዮጵያውያን በሙሉ እንክብካቤ ማድረግ አለበት። ባጭሩ፤ ለጥቂቶች አገልጋይ የሆነ ኢኮኖሚ ውጤቱ የተዛባ ይሆናል። የምርት ሃይሉን ያደከማል ወይንም በጭራሽ ያፍነዋል። በገጠር ያለው ኢኮኖሚ እንዲሻሻል ከተፈለገ፤ የዝቅተኛ አምራቾችን አቅም ከፖለቲካ ቁጥጥር ውጭ ማድረግና ማጎልመስ ያስፈልጋል። ለም የእርሻ መሬት ለውጭ መንግስታትና ሃብታሞች፤ ለውስጥ ምርጥ ተጠቃሚዎች በመስጠት የእርሻ እድገት ውጤት ስኬታማ አይሆንም። አራሹ የመሬቱም፤ የምርቱም ባለቤት መሆን አለበት የሚለውን በጥናት የተደገፈ አመለካከት ያቀረቡ አዋቂዎች ብዙ ናቸው። ፖሊሲው ሲለወጥ፤ ገበሬው የመሬት ሃብት ዋስትና ሲኖረው፤ የጥቂቶች ሳይሆን፤ የአብዛኛው አምራቹ ክፍል አቅም ሲጎለምስ፤ ኢትዮጵያውያን የአገራቸው የተፈጥሮ ሃብት ባለቤት ሲሆኑ ፍትሃዊ ልማት መሰረት ይይዛል። በየትም ቦታ ያለገደብ ሲንቀሳቀሱ፤ የማምረት ሃይል ይሻሻላል። መዋቅሩ እየተለወጠ ይሄዳል። የእርሻው ክፍል ወደ እንዱስትሪነት ይለወጣል። ምርቱ ለኢንዱስትሪ መጋቢ ይሆናል። ለዚህ የፌደራሉ መንግሥት የማዳበሪያ ኢንዱስትሪ ማስፋፋት ግዴታው ነው።

አሁን ያለው ኢኮኖሚ እነደዚህ አይሰራም። ባጭሩ—የአሁኑ ጠባብ የጎሰኛ ቡድን ኢትዮጵያን በኢትዮጵያውያን በማልማት ፋንታ፤ "ዘርፎ ለዘራፊ" ዳርጓታል። ችግር የለም። የውጭ ምንዛሬ እጥረት የለም ይላል። የሚሰደደው አዲስ ትውልድ ከአገር የሚወጣው ወዶ ነው። ያስገደደው የለም ይላል። ችግሩን ከሕዝብ እድገት ጋር፤ ከእድገት ጋር አያይዞ እንደ ተፈጥሮ ሂደት ያቀርበዋል። ሂደቱ ፖሊሲውና መዋቅራዊ ከሆነ ገዢው ፓርቲ ሊለውጠው አይችልም። መዋቅሩ እንዳለ ይቆያል ። ፖሊሲንና መዋቅርን ለመለወጥ፤ ለለውጥና ለመሻሻል የተዘጋጀ የፖለቲካ አመራር ያስፈልጋል። አንዳንዶች የውስጥ አዋቂዎች እነደሚሉት፤ "ህወሓት የራሱ ጠላት ሆኗል። ለመለወጥ አይፈልግም።" የምግብ ዋስትና፤ የእርሻ ምርት እድገት ምስጢር አይደለም። መሰረት የሆነውን ለም መሬት ለውጭ ኢንቬስተሮች ለዘጠና ዘጠኝ አመታት በማከራየት ስኬታማ አይሆንም ። የኢትዮጵያውያን ድምጽ ታፍኖ፤ የህንዱ ካሩቱሪ፤ ሳውዲ ስታር የሚያዙባት አገር የሆንችው ኢትዮጵያ፤ በቅኝ ገዥዎች ወረራ ምክንያት አይደለም። በህወሓት ባለስልጣኖች ግብዣ ነው። በግብዣ የመጣ የውጭ የበላይነት ፖሊሲ፤ "farmland colonization by invitation" ብለን ሰይመነዋል። ይህ ሁኔታ ካልታረመ፤ ከመሞቱ በፊት መለስ ዜናዊ እንዳለው "ኢትዮጵያን የማጣት እድላችን ከፍ ያለ ነው፤ እንደ ሶማሊያ የመሆን አዝማሚያችን ከፍ እያለ ይሄዳል"። የተፈጥሮ ሃብትን መነጠቅ፤ ዜግነትን መነጠቅ ነው። አገርን ለአደጋ መጋበዝ ነው። አገርን ማጣት ነው። መለስ፤ በዚያ ጊዜ የተናገረው እውነት ነው፤ በሕይወት ቢቆይ ኢትዮጵያን ይለውጣት ይሆን ብለው አንዳንድ ግለሰቦች የሚጠይቁት ወደው አይደለም። ሆኖም፤ እውነተኛ ሃገራዊ የሆነ የፖሊሲ ለውጥና ለውጡ ሊያመጣ የሚችለውን ውጤቱ ለማየት አንችልም። ሃያ አንድ አመታት በበላይነት ሲገዛ፤ ፖሊሲ የመለወጥ አቅም ነበረው። አላደረገውም። ሆኖም፤ማስጠንቀቂው አግባብ አለው።

የከተማ ወይንስ የገጠር ድህነት?

የህወሓት/ኢህአዴግ የበላዮችንና ደጋፊዎችን የእድገት ወሬ ስናዳምጥ፤ ድህነት በከተማ አለ። በገጠር ግን የለም የሚል ነው። እኛ የምንለው ድህነት ዲካ/ወሰን የለውም። ድህነት አገር አቀፍ ነው። የገጠሩ የማይሰማው ገዢው ፓርቲ ሙሉ በሙሉ ስለሚቆጣጠረው ነው። አሁን በየቦታው የምናየው የማህበረሰብ ህይወት ቀውስ፤ ህወሓት ከውጭ አማካሪዎች ጋር ተባብሮ፤ የፖለቲካ ስልጣን እንደያዘ ከቀረፀው ህገመንግሥት አስተዳደር ጋር የተያያዘ የአገዛዝ ውጤት ነው። ስልጣን በያዘበት ወቅት የነበረው ኢላማ፤ የሕዝብን መብት ማጎልመስ አልነበረም። ይህ ቢሆን ኖሮ፤ ፍትሃዊ እድገት እናይ ነበር። ቢያንስ፤ የገጠሩ አርሶ አደር የመሬቱ ባለቤት ሆኖ በልቶ ያድርና ኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና ትጎናጸፍ ነበር። ገዢው ፓርቲ ያደረገው፤ ህብረተሰቡን ለመቆጣጠር፤ ብሄረሰቦችን እርስ በእርሳቸው ለማጣላትና እርጋታ እንዳይኖር ለማድረግ (Permanent Societal Tension and Suspense)፤ በፖለቲካ ማደራጀት ነበር። ዱሮ በሰላም የመኖር

ልምድና ባህል የነበረውን ሕዝብ አሁን አንዱ በሌላው ላይ ሰላይ እንዲሆን ተገዷል። የቁጥጥር የፍርሃት ምልክት ነው። ጎጅ፤ ግልጽነት የሌለው፤ በተቆጣጣሪነቱ ዘመን ያለፈበትን የሶቭየት ህብረትን አብዮታዊ ዲሞክራሲ የተባለ ተከሏል። በጽሞና ጉዳቱን ላላየው፤ አብዮታዊ ዲሞክራሲ“ማር የተቀባ መርዝ” ነው። ማርነቱ ለጭቁን ብሄረሰቦች ቆሜያለሁ ማለቱ ነው። መርዝነቱ በጭቁን ብሄረሰቦች ስም፤ ለጥቂቶች የበላይነትን ማስተላለፉ ነው። ዋና ተጠቃሚዎች የብሄረሰብ ባለስልጣናትና የሃብት ጥመኞች ናቸው (Ethnic Political and Social Elites). የዚህ አገዛዝ ውጤት የፖለቲካ ስልጣን ተጠቅሞ ለግል ጥቅም አገልጋይ መሆን የሚለውን ወልዷል። (This is known as ethnic elite economic and social capture). ስለዚህ የአገዛዝ አይነት ጉዳቶች የተጻፉ ብዙ ማስረጃዎች አሉ። የታወቀው ኢኮኖሚስት ዊሊያም ኢስተርሊ “የብዙ ብሄረሰቦች መኖሪያ በሆኑ አገሮች የሚታየው የፖለቲካ መሬዎች ሆነ ብለው፤ በሕዝብ መካከል ያለውን “ጥላቻ” በስሜት እየቀሰቀሱ፤ እያባባሱ፤ የብሄረሰብ መሪዎችን ስብስብ በመገንባት ለሃብት ማከፋፈያ መሳሪያ አድርገውታል። ገጠሬው ገቢው አድጓል ቢባልም፤ የብሩ ዋጋ እየቀነሰ እስከሄድ ድረስ፤ የአገሪቱ ምርት ነዋሪዎች የሚፈልጉትን ቁሳቁስ በዝቅተኛ ዋጋ ለማቅረብ እስካልቻለ ድረስ የሚገኘው ብር ቢትረፈረፍ ፍላጎትን ለማሟላት አይችልም። ሆኖም፤ ኢስተሪ እንዳለው የጎሳ አለቃዎች የሚናገሩት እድገት አለ፤ አገሪቱ ከሙቸውም በበለጠ እያደገች ነው ይላሉ። (“Politicians often exploit ethnic animosities to build coalitions that seeks to redistribute income to “us from them”) በማለት አደጋውን አሳይቷል። 13/

የብሄር መሪዎች ስብስብ (Elite ethnic coalition) የፖለቲካ ስልጣን ይዞ ራሱን ሲያከብር “ማር ነው ወይንስ መርዝ” የሚለውን ጥያቄ አንባቢ በህሊናው እንዲመልሰው እንተወዋለን። አንባቢው፤ የብሄረሰብ ስብስብ ለአገር ጉዳት አይኖረውም ብሎ ለመከራከር ሙብት አለው። ችግሩ ከመሰብሰቡ ላይና ሙብቶቹ ይከበሩ ከማለቱ ላይ አይደለም። ፖል ኮሊየር፤ ዓለም ባንክ ሲሰራ በነበረበት ወቅት፤ ስለ ብሄረሰብ ልዩነቶችና የፖለቲካና የኢኮኖሚ ግብግብ ባደረገው ጥናት፤ የስራ እድል፤ የገቢ፤ የተፈጥሮ ሃብት አያያዝ ልዩነቶች፤ ምዝበራ፤ ቀስ በቀስ ወደ የእርስ በእርስ ጦርነት እንድሚያመራ አሳይቷል። በአፍሪካ፤ በብሄር የፖለቲካ አወቃቀር፤ አድልዎና ሙስና ያለውን አደጋ በጥናት ያቀረበችው ሚኪየላ ሮንግ ከኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር ሰለሚመሳሰል፤ በአጭሩ እናቀርበዋለን። በኬንያ የነበረው አድሏዊ አገዛዝ፤ በብሄር የተመሰረተ ነበር። ገዢው ፓርቲ፤ የብሄርና የፓርቲን የጥቅም ዘዴ ለማጠናከር ከመንግስቱ ጋር አያይዞ፤ ህጉን፤ ደንቡን፤ የስለላና የመከላከያ ድርጅቶችን፤ ፍርድ ቤቶችን አቆራኝቶ፤ አንዱ የሌላው ደጋፊ ሆነ። ፓርቲው የህብረተሰቡ አገልጋይ በመሆን ፋንታ፤ የአንድ ፓርቲ፤ የአንድ ብሄረሰብ አገልጋይ ሆነ። “ችግሩ፤ ተጠቃሚው ብሄረሰብ፤ ለአገሩ በማሰብ ፋንታ፤ ለራሱ ብሄረሰብ ብቻ ማሰብ ጀመረ።” ኬንያዊ መሆኑ ተረስቶ፤ ኪኩዩ፤ ሉኦ፤ ማሳይ መባል ተመረጠ። መንግስት ህብረተሰቡን ማገልገሉ ተረስቶ ራሱን ማገልገል ተመረጠ፤ “የህብረተሰቡ ገንዘብ (ባጀት፤ የተፈጥሮ ሃብት) ወደ ተወሰነ የብሄር ጥቅም፤ ክልል ተዘዋወረ። ከጥቅሙ ያልተካፈለው ዋጋ ከፈለ።” የህብረተሰቡ ሞራል እየተበረዘ ሄደ። ጉቦ፤ ሙስና፤ ወዘተ፤ ከህብረተሰቡ ህይወትና የኑሮ ሁኔታ ተለይቶ ሊታይ አይችልም። በጠባብ ብሄርተኛነት በሚመራ ሃገር፤ ሌላው ቀርቶ አንድ ግለሰብ የመኖር ተስፋ የሚኖረው (hope for mere survival)፤ ስልጣን ከያዘው ብሄረሰብ ጋር ቁርኝት ሲኖረው” ብቻ ነው ካለች በኋላ ስለ ናይሮቢ የጻፈችው አዲስ አበባን ይመስላል። 14/

“በማር የተቀባ መርዝ” ኢትዮጵያን ገላጭ ነው። የደላው ስደተኛ አዲስ አበባ ደርሶ ሲመለስ የሚናገረው ስለለውጡ ጥሩ ጎን ነው። ስለተራው ህብረተሰብ አሰቃቂ የኑሮ ሁኔታ አይደለም። እንደ ኢስተርሊ ያሉ ሠብአዊነት ያላቸው ግለሰቦችና ሌሎች ህይወታቸውን ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች እየሰሩ የቆዩ ባለሞያዎች ናይሮቢና አቢጃን ሲመላለሱ በመጀመሪያ የሚያዩት ብልጭልጩን ነው። ከዚያ ወጣ ብለው የውስጡን ጉድ ሆነ ብለው ይመራመራሉ። ሃቁን በጽሁፍ ያቀርባሉ። የኢኮኖሚስት ማጋዚን ከሁለት አመታት በፊት፤ አዲስ አበባ የሚታየው “የብልጭልጭ እድገት” ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን አሰቃቂ ድህነት አይገልጸውም” ያለው፤ ኢስተርሊ ስለ ኢትዮጵያ ድህነት፤ ሚቸላ ሮንግ ስለ ናይሮቢ ከጻፉት አይለይም። ሮንግ ያለችውን እንጥቀስ። “በናይሮቢ ከተማ አጠገብ የነበረው ባዶ መሬት አሁን የለም። መንገድ የሌለበት መንገድ ተሰርቶበት፤ አሁን አፓርትሜንት፤ ቪላ፤ ሱቅ....ተደርድሮበታል። የናይሮቢን ዘመናዊነት ለማወቅ የፈለገ በትራፊኩ ሊገነዘበው ይችላል- በእኔ አመለካከት፤ እድገቱን” በትራፊኩ፤ በቪላው መመዘኑ ትክክል አይደለም-ታላላቆቹ የመንግስት መሪ ሙሰኞች የመስረቂያ መሳሪያቸው፤ ታላላቅ መሰረተ ልማቶች መስራት፤ ኮንትራቱን ለራሳቸውና ለታማኞቻቸው መስጠት...ይህን የመሰረተ ልማት ስራ ሲሰሩ፤ አገር እናለማለን በሚል ዘዴ፤ ዘረፋቸውን ዘመናዊ በሆነ መንገድ ይቀጥላሉ፤ የአበዳሪዎችን አድናቆት ያገኛሉ። ሙሰኞች ሁልጊዜ ሌላውን ቀድመው የህብረተሰብ አገልጋይ መስለው መቅረብ አለባቸው” ብላለች። እንደዚህ ያለ አገርን በማልማት አሳቦ መዝረፍ፤ የራስንና የታማኞችን የግል ጥቅም ማገልገል “በማር የተቀባ መርዝ” መሆኑን ያየነው የኬንያ ሕዝብ ተነስቶ አራፐ ሞይን፤ በነጻ ምርጫ፤ ከስልጣን ሲያባርር፤ ሞባረክን ወደ እስር ቤት ሲሰድ ነው። የኢትዮጵያ ሁኔታ የባሰ ነው። 15/

አብዮታዊ ዲሞክራሲ ማህበረሰባዊ (Social) ወይንም ዲሞክራሳዊ (የህዝብ ድምጽና መብት) ይዘት የለውም። በህብረተሰብ ስም፤ የግል ኪራይ ሰብሳቢ ሆኗል። ህብረተሰቡ በውሳኔ ላይ ምንም ድምጽና መብት የለውም። ስለዚህ ዲሞክራሳዊ ሊሆን አልቻለም። "በማር የተቀባ መርዝ" ነው የሚባልበት ሌላው ምክንያት ማለታችን ነው። የህወሓትን አገዛዝ ከሌሎች በአብዮታዊነት፤ በዲሞክራትነት አምባ ገነን ሆነው ከገዙ፤ አሁንም ከሚገዙ የሚለየው፤ ጎሳዊ፤ ክልላዊ፤ የኢኮኖሚ አመራሩ ነው። የኢኮኖሚው አመራር ሲታይ፤ "በሌሊት ጨለማ እንደሚጓዝ" መንገደኛ ይመስላል። ወደ የት እንደሚሄድ። ለማን እንደሚሄድ። ማንን እንደሚያቅፍ። ማንን ትቶ እንደሚጓዝ አይታወቅም። ገንዘብ የሚሸሸበት አንዱ ምክንያት ሆነ ብሎ "ደንባራ" ስለሆነ ነው። ምስጢረኛ ስለሆነ፤ ሂደቱና አቅጣጫው አይታወቅም። ጥቅሙ የማይታይ፤ ከብልጭልጩ በላይ የማይዳሰስ፤ ተሳትፎ የሌለበት፤ ሰው የሚበላው ያጣበት፤ ቢያንስ የሚጨነቅበት፤ ብዙ ሚሊዮን ሕዝብ በረሃብ አለንጋ የሚገረፍበት፤ ወጣቱ ትውልድ የሚሰደድበት ማህበረሰብ ፈጥሯል። ይህ በግልጽ እየታየ፤ ገዢው ፓርቲ አገሪቱ በአመት አስራ አንድ በመቶ እያደገች ነው እያለ ማስረጃ ያቀርባል። ይህን ተደጋጋሚ የሆነ የፈጠራ ማስረጃ የሚያቀርብ መንግሥት የት ላይና በምን እንደሚታመን ማስረጃ ለማግኘት ያዳግታል። ለምሳሌ፤ ዓለም ባንክ፤ ኦክስፎርድ ዩንቨርስቲ፤ ሌጋተም፤ ሞ ኢብራሂም፤ የተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅት፤ ያወጧቸው ዘገባዎች፤ የነፍስ ወከፍ ገቢ አሁንም፤ አሜሪካ ዶላር ሶስት መቶ አርባ ሰባት በታች መሆኑን ያሳያሉ። የእርሻ እድገት ውጤት ከሕዝብ እድገት ጋር ሊራመድ እንዳልቻለ፤ የዋጋ ግሽበት መካከለኛ መደብ ውስጥ ለሚገኙ ዜጎች ኑሮ አስቃቂ እንደሆነ። ከስምንት እስከ አስራ አንድ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን አሁንም በውጭ አገሮች የምግብ ድጎማ እንደሚኖሩ። አምስት ሚሊዮን የሚገመቱ ቤተሰቦች በስደተኞች ገንዘብ እንደሚደገፉ። ቢያንስ፤ ሰባ ስድስት በመቶ የሚሆነው ወጣት አገሩን ለቀ ለመሰደድ እንደሚመኝ። ሰማንያ በመቶ የሚሆነው ስራ እንዳጣ በጥናት ያሳያሉ። በሰው የኑሮ መሻሻል መለኪያና ደስታ ሲታይ፤ መንግሥት ማስረጃ እንደፈጠረ ያመለክታል።

ዓለም የሚጠቀምባቸው የእድገት መለኪያዎች አሉ። ከተሳትፎ የሚገኝ ፍትህ አንዱ ነው። ገዢው ፓርቲ፤ የኢኮኖሚ ተሳትፎ እንዲስፋፋ በማድረግ ፋንታ፤ ዝግና ለጥቂት ግለሰቦችና ቤተሰቦች የሚጠቅም ኢኮኖሚ ፈጥሯል። ስግብግብነት፤ ራስ ወዳድነት፤ ለአገር አለማሰብ፤ አድልዎና ሙስና፤ ለነገ አለማሰብ ባህል ስር እንዲሰድ አድርጓል። ከምርጥ ግለሰቦችና ቤተሰቦች ውጭ ሌላው ሰነፍ ነው የሚል የውስጥ ክስ ያካሂዳል። ማን ሰነፍ እነደሆነ አይናገርም። ማን ኪራይ ሰብሳቢ እንደሆነ ተናግሯል። ፓሪቲውና ደጋፊዎቹ አይደሉም። ተቃዋሚውና የግል ክፍሉ ነው ይላል። በሰላም አብሮ የመኖር ባህል እንዲጠፋ ሆን ብሎ ሲገፋበት ይታያል። በሌሎች አገሮች እንደታየው፤ አምባገነናዊ አገዛዝ ሆን ብሎ "አለመረጋጋትን" (Instability) ይፈጥራል። ለምን? ለሙስና፤ ለጉቦ፤ ለአድልዎ ይጠቀማል። የምእራብ አገሮች ለህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት ድጋፍ የሚሰጡት መረጋጋትን ስለመረጡ ነው። የአጭር ጊዜ መረጋጋት የረጅም ጊዜ ሰላም አይፈጥርም። የረጅም ጊዜ መረጋጋት የሚፈጥረው የአብዛኛው ሕዝብ ኑሮ ሲሻሻል ነው። ገዢው ፓርቲ ሕዝብ ለሕዝብ እንዲያስብ፤ ፖለቲካውንና የእድገት መሰላሎችን ፍትሃዊ፤ ተሳትፎያዊ እንዳይሆኑ፤ ልማት በዘላቂነትና በተሳትፎነት፤ እንዳይመሰረት ህጉን፤ ደንቡን በጮሌነት ሲመራው ይታያል። ልክ ኬንያ እንደሆነው። በታሪክና በልምድ የተገኘው የህብረ-ብሄር አገራዊ ትሥሥር፤ በዘመናዊ መልክ ስር እንዳይሰድ ተደርጓል። ለዘር ፖለቲካ ቀደምትነት በመስጠት፤ ህብረተሰቡን ዘርፎ ለዘራፊ ዳርጎታል። መደጋገም ያለበት መሰረተ ሃሳብ፤ በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያውያን በአገራቸው የተፈጥሮ ሃብት ቀርቶ፤ በህይወታቸው ለማዘዝ አይችሉም። በውሳኔ ላይ ሚና መጫወት ቀርቶ መጠነኛ ድምጽ የላቸውም። አደጋው ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፋል የሚል ግምት ያቀረብነው ለዚህ ነው።

ሆኖም፤ ህብረተሰቡ በግል ደረጃ፤ አስተሳሰቡን ካልለወጠ፤ በህብረተሰብ ደረጃ፤ የጎሳና የኃይማኖት ርእዮት አውልቆ፤ በኢትዮጵያዊነቱ አብሮ መረረኝ ብሎ በጋራ ካልተነሳ፤ የህወሓት/ኢህአዴግ አምባገነናዊ አገዛዝ፤ አስር ጊዜ ሸሚዙን ቢቀይር አይለወጥም። የተናጠል ሃሳብና ጀግንነት፤ ንዴትና አቤቱታ፤ ትግል፤ በራስ ሳይሆን በውጭ መንግስታት መመካት ከአርባ አመታት በላይ ተሞክሮ አላዋጣም። ግብጾች፤ ሶሪያኖች፤ የበርማ ሕዝብ፤ ወዘተ፤ ሙጥኝ ብሎ የአሜሪካን መንግስት "ነጻ አውጣኝ" ብሎ ቢጠብቅ ኖሮ ለውጥ አይመጣም ነበር። የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት በልመና አይለወጥም። ልመናን እንደ ድክመት ያየዋል። የግል፤ የቡድን፤ የአንድ ብሄረሰብ ወዘተ ንዴት፤ ወደ ህብረተሰብአዊ የለውጥ አመጽ መቀየር አለበት። ካልሆነ፤ አንችልም ብሎ መቀመጥ። ሕዝቡን በውሸት ተስፋ አለመቀስቀስ ይሻላል። የሰላም አመጽ በተከታታይ አልተሞከረም። በቅርቡ የእስልምና ተከታዮች የሚያደርጉት አይነት ማለታችን ነው። የሰላም ለውጥ ሲባል፤ አንዳንዶቹ አሁንም አያዋጣም ይላሉ። ለምን እንደማያዋጣ ሲጠየቁ የሚሰጡት መልስ የህወሓት/ኢህአዴግን ሃይለኛነት ይጠቅሳሉ። የዘጠና ሰባቱን ምሳሌ ይደጋግማሉ። የማይናገሩት፤ በዘጠና ሰባቱ ምርጫ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማሸነፉን፤ ህወሓት ስለተሸነፈ፤ ወደ ከፍተኛ ሽብርተኛነት መለወጡን አይደለም። የቅንጅትን አመራር ወደ ቃሊቲ እስር ቤት ማስገባቱን፤ ብዙ ሺህ ኢትዮጵያውያን መታሰራቸውን፤ የቅንጅት አመራር ሆን ተብሎ መከፋፈሉን አይደለም። አመራሩ በግልና በቡድን ሹክቻ መከፋፈሉን አይደለም። ሕዝቡ በፖለቲካ መሪዎች ያለው እምንት መድከሙን ወዘተ ነው። ሕዝቡ የህወሓትን አመራር አለመቀበሉን በድምጹ አሳይቷል። ለዲሞክራሲ

በህይወቱ ዋጋ ከፍሏል። አንዳንድ ተመልካቾች የቅንጅት አመራር ፓርላማ መግባት ነበረበት ይላሉ። ውጤቱን አናውቅም። ህወሓት/ኢህአዴግ ፓርላማ የገቡትን ነጻነት አልጠበቀም። ደሞዝ አግኝተው ለገዢው ፓርቲ እንዲታዘዙ የሚፈልግ አገዛዝ ነው። ስለሆነም፤ የመግባታቸው ጥቅምና ጉዳት ዛሬ አከራካሪ መሆን የለበትም። ቢገቡ ኖሮ አቋማቸውን የሚገልፁበት እድል ይኖራቸው ነበር የሚለው ያዋጣል። አከራካሪ መሆን ያለበት፤ የፈለገው ፈተና ቢመጣ የቅንጅት አመራር ልዩነቶችንና የግል ወይንም የቡድን ጥቅምን ወደ ጎን ትቶ ለኢትዮጵያና ለመላው ሕዝቧ በአገር ደረጃ፤ ከሕዝቡ ጋር ሆኖ መከራከር ነበረበት የሚለው ነው። የአመራሩ የስልጣን ግብግብ፤ ሽሽትና መበታተን ህብረተሰቡንና ተተኪውን ትውልድ ጎድቶታል። ይህ ትልቅ ትምኅርት ሆኗል።

ለውጥ ለሚፈልግ ህብረተሰብ፤ ዘዴው ብዙ ነው

በኢትዮጵያ፤ ከየካቲት አብዮት ወዲህ በጋራና በአገር አቀፍ ደረጃ፤ በዘላቂነት፤ ሰላማዊ የሆነ፤ "አልገዛም፤ ፍትህ ይስፈን፤ ዲሞክራሳዊ ስርአት ይመስረት፤ አምባገነናዊ አገዛዝ ይፍረሰ" የሚል፤ ተከታታይ የሕዝብ የሰላም አመጽ ገና አልተሞከረም። ብዙ ምክንያቶች ልንደረድር እንችላለን። አጥጋቢ ሊሆን አይችልም። ሁለት እንጥቀስ። አንድ፤ ህወሓት/ኢህአዴግ ሕዝቡን ንቆታል። አገር ወዳዶችን አስሯል፤ ከሃገር አሰውጥቷል። ከሕዝብ አገልግሎት በላይ የፈለገው፤ የሚገዛው፤ ለጠባብ የጎሳ ቡድንኖች መሆኑን ህብረተሰቡ ያውቃል። በየቀኑ የሚደረገው አፈና በቂ ነው። ሁለት፤ በመግቢያና በዚህ ክፍል እንዳሳየነው፤ ገዢው ፓርቲ በተደጋጋሚ፤ የራሱን ህገመንግሥት የሙብት አንቀጾች አፍኗቸዋል። አንቀጽ ሃያ ዘጠኝ። አንቀጽ ሰላሳና ሰላሳ አንድ። አንቀጽ ሰላሳ ስምንት። የሚመለከተው ስልጣኑን ማራዘም ነው። "ስልጣን ወይም ሞት" የሚለውን። ህገመንግሥቱን መጣሱን አይደለም። ሲጀመር፤ ህገመንግሥቱን የነደፈው ለቁጥጥር ነበር። በተግባር ሲታይ የአፈናና የስልጣን ማረጋገጫ መሳሪያ ሆኗል። ሆኖም፤ ገዢው ፓርቲ አፈና ቢያካሂድም፤ ከሕዝቡ የበለጠ ሃይል የለውም። ሙባረክ እንዳልነበረው አይተናል። መንግሥቱ ኃይለማሪያም እንዳልነበረው አይተናል። ሕዝቡ በአንድ ላይ፤ በመላው ኢትዮጵያ ቢነሳ፤ ገዢው ፓርቲ ሊያቆመው አይችልም። ሰው አይሞትም ማለት አይደለም። ሶሪያ፤ በሶስት አመታት ከመቶ ሺህ በላይ ሰላማዊ ሰው ሞቷል። ወደፊትም ብዙ ሽህ ይሞታል ተብሎ ይገመታል። የሶሪያ ሕዝብ፤ ነጻነት፤ ዲሞክራሲ፤ ፍትህ ዋጋ ሳይከፈል እንደማይገኝ በህይወቱ እያስመሰከረ ነው። ኢትዮጵያውያን፤ በልባቸው፤ ከልባቸው መወሰን ያለባቸው፤ የፈለገውን ያህል ጊዜ ቢወስድ፤ የፈለገውን ያህል መስዋእት ቢከፈል፤ የፈለገውን ያህል ሰው ቢያስር፤ ሰላማዊ አመጽ መካሄድ አለበት ማለት መብታቸው ነው። ሕዝቡ መብታችን ታፍኗል ካለ፤ ይህን መብት ያፈነ መንግሥት አንቀበልም ማለት ይከተላል። አቅማችን የሚችለው መንገድ ምን ይመስላል ብሎ መጠየቅ አግባብ አለው። የህንድ፤በጋንዲ ዘመን፤ የደቡብ አፍሪካ፤ በማንዴላ ዘመን፤ የአሜሪካ፤ በማርቲን ሉተር ኪንግ ዘመን፤ የፖላንድ በሌክ ቫሌንዛ ዘመን፤ ወዘተ የተደረጉ ዓለም ያደነቃቸው ለውጦች፤ የሰላማዊ ፖለቲካና፤ የሰብአዊ መብቶች መከበር ሂደቶች ናቸው። የቱኒሲያ፤ የሊቢያ፤ የግብጽ፤ የየመን፤ የባህሬን ወዘተ ለውጦች የህብረተሰብ አመጽ ለውጦች ናቸው።

በማንኛውም ለውጥ በሚፈልግ አገር፤ የትግሉ ዋና አላማ፤ መጥፎውን አገዛዝ በተሻሻለ አገዛዝ መለወጥና ማሻሻል ነው። ቂም በቀልን ለመወጣት አይደለም። የተሰራውን ሁሉ ማፈራረስ አይደለም። ይህን ለማድረግ በመጀመሪያ በራስ መተማመን። በህብረተሰቡ ማመን ያስፈልጋል። የጎሳ ፖለቲካ ኪሳራ አስገብቶናል ከተባለ፤ ከኪሳራ የሚያዋጣው መንገድ የብሄር ጥላቻና ቂም በቀል አይመስለንም። የሁሉንም ፍላጎት የሚያስተናግድ አማራጭ ማቅረብ ነው። ከዘዴዎቹ መካከል ጥቂቶቹን እንይ።

1. ለጥቂቶች አገልጋይ የሆነው የህወሓት/ኢህአዴግ የኢኮኖሚ አመራር አብዛኛውን ወደ ጎን ትቶታል። ፓርቲው የያዛቸው ድርጅቶች በኢትዮጵያ ህጻናት፤ ልጃገረዶችና እናቶች ይነግዳሉ። እንጀራ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ተጠቅመው በአሜሪካ ለሚኖረው ስደተኛ ሸማች በየቀኑ ያቀርባሉ። የኢትዮጵያን አየር መንገድ፤ የሚያገለግለው ለሃገር ጥቅም ሳይሆን፤ ለገዢው ፓርቲ ከፍተኛ አባላትና ቤተሰቦች ሆኗል። በኢትዮጵያ፤ የንግድ፤ የመገናኛ፤ የትምኅርት፤ የአገልግሎት፤ የእርሻ፤ ወዘተ ተቋሞችን በበላይነት እየተጠቀመ፤ መልሶ ለህብረተሰቡ ይቸረችራል። ቤቶችና ህንጻዎችን ከባንክ ተበድሮ ሰርቶ ያከራያል። የምርት ሆነ የአገልግሎት ተቋም ባለቤትነቱ፤ የህወሓት/ኢህአዴግና የደጋፊዎች ከሆነ፤ ማንኛውንም ተቋም ማገብ (Boycott) ይገባል። ይቻላል። ጀምሮ መተው አያዋጣም። እነጀራውን እፈልጋለሁ። በኢትዮጵያ አየር መንገድ መሄድ እፈልጋለሁ ከተባለ ስኬታማ አይሆንም። ፓርቲውን ለማድከም የሚደረግ እገባ ዳር ድንበር ሊኖረው አይገባም። አለበለዚያ አለመጀመሩ ይሻላል።

2. እገባ በቁሳቁስ አይወሰንም። ትምኅርት ቤት መሄድን ማቆም እገባ ነው። ስራ አልገባም ብሎ መቅረት እገባ ነው። ታክሲ አልነዳም ብሎ ማቆም እገባ ነው። ከዚህ ሱቅ አትግዙ እኔም አልገዛም ማለት እገባ ነው። ቤተክርስትያን ሄዶ

ከጸሎት በኋላ ለለውጥ ፀሎትና አድማ ማድረግ እገባ ነው። የህወሓት የበላዮች ከህግ ውጭ በአድልዎ ያገኙት ተቋም ሁሉ የእገባ ኢላማ ሊሆን ይችላል። በሙስና ክስ መመስረት እገባ ነው።

3. የገዢው ፓርቲ፤ ከሰደተኛው ቢያንስ በአመት፤ አራት ቢሊዮን ዶላር ያገኛል። ዘመድ ወገን መርዳት አስፈላጊ መሆኑን ማንም አይክድም። እርዳታው መቀጠል አለበት። ሆኖም፤ ዶላር ለገዢው ፓርቲ በባንኮች የሚላክበት ምክንያት የለም። ህወሓት ተዋጊ በነበረበት ጊዜ የተጠቀመበትን ዘዴ፤ ማለትም፤ ከህግ ውጭ ገንዘብ ማንቀሳቀስን ተቃዋሚው ህብረተሰብ የማይጠቀምበት ምክንያት የለም። ይቻላል። አንዱ የእቀባ ዘዴ ነው።

4. ህወሓት/ኢህአዴግ በኢትዮጵያና በመላው ህብረተሰብ ላይ የሚያደርገው አፈና ካበሳጨን፤ ለተወሰነ ጊዜ፤ ሁኔታው አስገዳጅ ካልሆነ---ለምሳሌ፤ የዘመድ እልፈት፤ ብርቱ ህመም---ኢትዮጵያ አንሄድም ብሎ ለዓለም ህብረተሰብ ማስታወቅ የእቀባ ዘዴ ነው። ለመጠቀም ይቻላል።

5. የከተማው ሕዝብ በያለበት፤ በሳምንት አንድ ቀን መርጦ፤ በእየቤቱ ለሃያ አራት ሰአት፤ አንቀሳቀስም፤ ስራም፤ ሱቅም፤ ሌላም ቦታ አንሄድም። በየቤታችን ለለውጥ ጸሎት እናደርጋለን ለማለት ይችላል። ይህ የድምጽ ማሰሚያ መሳሪያ ነው። ከተቀነባበረ፤ ሰሚ አያጣም። ወጣቱን ያበረታታል። ተቃዋሚው ክፍል በአንድ ላይ እንዲሰራ ይገፋዋል። የውጭ መንግስታት ማዳመጥ ይጀምራሉ። የሰጡትን ድጋፍ ሊለውጡ ይችላሉ። በውጭ ያለው ስደተኛ ተቃዋሚ የሃገር ቤቱን መደገፍና መለወጥ ይጀምራል።

6. የክርስትናና የእስልምና ኃይማኖት አባቶች አብረው በመነሳት የኃይማኖት መብቶች ይከበሩ በማለት በዘላቂነት የሚሰራ አንድ ሁለቱን የሚያቅፍ የነጻነት፤ የመብት፤ የእኩልነት፤ የሰላም፤ ካውንስል አቋቁመው ለተባበሩት መንግስታት፤ ለሰብአዊ መብቶች ድርጅቶች፤ ለዓለም ቤተክርስቲያኖች ካውንስል ወዘተ፤ በተከታታይ አቤቱታ ሊያሰሙ ይችላሉ። የሚከለክላቸው ሃይል የለም።

7. በውጭ ያለው ተቃዋሚ ክፍል፤ ጥቃቅን ልዩነቶችን ወደጎን ትቶ ለሰብአዊ መብቶች፤ ለፕሬስ ነጻነት፤ ለመድብለ ፓርቲ ውድድር የተቀነባበረ፤ ዘላቂነት ያለው የዲፕሎማሲ ስራ ሊጀምር ይችላል። በየቦታው የሚገኙ ለመምረጥ የሚችሉ ስደተኞች የመምረጥ መብታቸውን እንዲጠቀሙ። ለኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጠበቃ እንዲሆኑ ለመቀስቀስ፤ ለማደራጀት ይቻላል።

8. እስከ ዛሬ የታየው የፖለቲካ ስብስብ ውጤት አልባ መሆኑ አያከራክርም። ሆኖም፤ በፖለቲካ አመራር መቆጣት፤ ከሃላፊነት መሸሽ መሆን የለበትም። በተለያየ መንገድ ተደራጅቶ ለፍትህ መሟገትን አይከለክልም። ፖለቲካ ኮረንቲ ነው ብሎ እጅን አጥፎ መቀመጥ ለታሪክ ተጠያቂ ያደርጋል። ስለሆነም፤ ባለፈው የፖለቲካ ድክመት የተቆጡ ግለሰቦች የፈለገውን አማራጭ ተጠቅመው፤ ለዲሞክራሳዊ ለውጥ፤ አገርን ከከፋ አደጋ ለማዳን መነሳት አለባቸው። ከፈቀዱ ይችላሉ።

9. ከዚህ ጸሃፊና ከጸሃፊው በፊት የተወለደው ትውልድ በደርግና በህወሓት/ኢህአዴግ የተወለደውን ትውልድ ወሳኝነት አላሰተዋለውም። ከዚህ ትውልድ በፊት የነበረው አሁን የእድሜ ባለ ፀጋ የሆነው ትውልድ በውቅቱ ባለው እውቀት፤ ችግር፤ ፍላጎትና ራእይ አስደናቂን ለውጥ ለማድረግ ሞክሯል። የር እዮት፤ የትግል ዘዴና ሌላም ልዩንት መኖሩ ባያከራከርም፤ ያ ትውልድ የተታገለውና የማይተኩ ወገኖች የሞቱበት ዋና ዓላማ ለማህበረተሰቡ ህይወት መሻሻል ነበር። ለራሱ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጥቅም አልነበረም። ወጣቱ ትውልድ የወደፊቱን ፈለግ ሊቀርጽ የሚችል፤ ከጎሰኛነት በላይ ለማህበረሰባዊና ለህብረተሰባዊ ደህንነት ለውጥ ለማሰብ የሚችል ሃይል ሊሆን ይችላል። የፖለቲካና የማህበረሰብ መሪዎች ሃላፊነት ወጣቱን ትውልድ ለመሪነት ማብቃት ታሪካዊ ግዴታቸው ነው። በአገር ቤትና በውጭ ይህ ትውልድ በታሪኩ እንዲኮራ አቅሙን ማበርታት። እንዲደራጅ ማዘጋጀት። ከፊት ሆኖ እንዲመራ መቀስቀስ ያስፈልጋል።

10. ከአምሳ በመቶ በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሴቶችን የያዘ ነው። ሴቶች የሌሉበት ለውጥ የትም አይደርስም። የእኛ (እድሚያችን ከሃምሳ በላይ የሆነው) ትውልድ በስብሰባና በአመራር ሴቶችን አላሳተፈም። ወጣቶችን አላጎለመሰም። ይህ ክፍተት ካልተዘጋ ስር ነቀል ለውጥ አይቻልም። የሰሜን አፍሪካና የሶሪያ ለውጦች የተካሄዱት በወጣቶች። በሴቶች ደፋርነት፤ ተባባሪነትና ቆራጥነት ነው። የፖለቲካና የማህበረሰብ ስብስቦች በአስቸኳይ ሴቶችና ወጣቶች በስብሰባና በአመራር ቦታቸውን እንዲይዙ ማበረታታት ተገቢ ጥያቄ ሁኗል። ማንኛውም እገባ ያለ ሴቶችና ወጣቶች ተሳትፎ ውጤት አይኖረውም።

11. ዛሬ ኢትዮጵያ ሃገራችን ከፍተኛ አደጋ እያንዣበባት ነው። ሕብረተሰቡ የማህበራዊ ኑሮው ተናግቷል። የሚኖረው ከእጇ ወደ አፍ የሆነ ኑሮ ነው። እነዚህ ችግሮች መሆናቸውን ከተጋራን፤ የአሁኑ ትውልድ ዋና አደራ በብዙ መስዋእት የተረከብናትን ኢትዮጵያን መታደግ፤ የመላውን ሕብረተሰብ ኑሮ ለማሻሻል ቆርጦ መነሳት ነው። ሑለቱም መስ ዋእትነት ይጠይቃሉ፤ ካለፈው ታላላቅ ትውልዶች የወረስነው ቅርስ ይኼው ነው። አገር ከሌለ ፍትህ፤ እውነተኛ እኩልነትና ዲሞክራሲ ትርጉም የላቸውም።

የተከፋፈለ ታማኝነት (Divided Loyalty)

የህወሓት/ኢህአዴግ የፖለቲካና የማህበረሰብ ባህል የተከፋፈለ ታማኝነት ባህል ነው። አንድ ጊዜ ለኢትዮጵያ ቆሚያለሁ። ሌላ ጊዜ ለኤርትራ። ሌላ ጊዜ ለትግራይ ወዘተ የተከፋፈለ ታማኝነት ነው። የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስትያን አመራር የሚታመሰው ለዚህ ነው። ስርአቱ ከፋፍሎ መግዛት ስላለበት ታማኘነቱ ቀን በቀን ይለወጣል። ታማኝነቱ ለማን እንደሆነ ግልጽ መመሪያ ለመስጠት አይችልም። ራሱ ተደናብሮ አዲሱን ትውልድ አደናብሮታል። የታማኝነት መደናበር የተደናበረ የኢኮኖሚና የማህበረሰብ ባህል እየፈጠረ ነው። የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ አመራር ባህል አገር ወለድ፤ ዘመናዊና ሁሉን-አቀፍ እንዳይሆን ህወሓት/ኢህአዴግ አዲሱን ትውልድ በምቀኝነት፤ በራስ ወዳድነት፤ በፍርሃት፤ በውጭ ባህል ወዳድነት፤ በጎጅ-ባህል፤ በውሸት፤ በማጭበርበር፤ በስደት ወዘተ ባህል እንዲያምን አስገድዶት ይታያል። የሕዝቡን ኑሮ ለማሻሻል የፖለቲካው ባህል መለወጥ አለበት ብለን የምንከራከረው ለዚህ ነው። ለአገርና ለወገን በማሰብ ፋንታ በስሜት ተገዝቶ ለዘር፤ ለገዢው ፓርቲ ታማኝነት፤ ለራስ ጥቅም እንዲገዛ፤ በአባቱና በእናቱ፤ በወንድሙና በእህቱ፤ በጓደኛው ላይ ጀሮ ጠቢ እንዲሆን ተገዷል። ይህ የተከፋፈለ ታማኝነት ፈጥሯል። ዛሬ፤ ገዢው ፓርቲ አንዱ፤ በሌላው ላይ እንዲቀናና እንዲሰልል እያደረገ ነው። በአመት፤ ከግማሽ ቢሊየን ብር በላይ፤ ለስለላ፤ ለማስታወቂያ፤ ለልዩ አስተዳደር ያፈሳል። ፈሰሱ  ሕዝብን ለማቀራረብ፤ አገርን ለመላው ዓለም ለማስተዋወቅ፤ አዲስ እውቀትን ለመሸመት፤ ሰላምና እርጋታን ለማጠናከር አይደለም። ቁጥጥርን ለማስፋትና ጥልቀት ለመስጠት ነው። በፍርሃት የተበከለ፤ ለራሱ ነጻነትና ክብር የማያስብ፤ ለታዛዥነት ቅድሚያ የሚሰጥ ትውልድ እንዲፈጠር የተደረገበት ዋና ምክንያት ወጣቱ ትውልድ ሙሉ ታማኝነቱ ለኢትዮጵያና ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዳይሆን ነው። አንድ ልሂቅ ይኼ ክልል "የኔ ብቻ ነው፤ አማራውና ትግሬው ከዚህ መውጣት አለበት" ለማለት የሚደፍረው ስርዓቱ ስለፈቀደለትና ስላበረታታው ነው። ሰው ተነስቶ ሌላውን በሉት፤ ግደሉት፤ ቤቱን አቃጥሉት አይልም። የትምኅርቱ ስርአት በኢትዮጵያዊነቱ የማያምን፤ ራሱን ከድህነት ነጻ አውጥቶ አገሩንና ወገኑን፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ የሚሰራ አዲስ ትውልድ እንዳይፈጠር አድርጎታል። የህወሓት/ኢህአዴግ  መንግሥት ስደትን ለመነገጃ ተጠቅሞበታል። ይህን ለማድረግ የቻለው፤ የትምኅርት ስርአቱን ኢትዮጵያዊ በማድረግ ፋንታ፤በጎሳ፤ በቋንቋ፤ በፓርቲ ታማኝነትና፤ በዘር ልዩነቶች ላይ በመመስረት፤ የስራ እድልን በታማኝነት በመወሰን ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ ትምኅርት እንዳይሰጥ የሚከለክል መንግሥት አገር ወዳድ ሊሆን አይችልም። የትምኅርት አወቃቀሩና ውጤቱ፤ ለተሳሰረ ህብረተሰብ አመሰራረትና ጥንካሬ አይሆንም። ኢትዮጵያ አቀፍ የሆኑ ተቋሞች፤ አገራዊ የህብረተሰብና የኢኮኖሚ እሥስር፤ መቆላለፍ፤ መደጋገፍ እንዳይኖሩ አድርጓል። አገራዊ ወይንም ኢትዮጵያዊ ተቋሞች ከሌሉ፤ የፖለቲካ ሆነ የኢኮኖሚ ጥቅሞች ፍትሃዊና ተሳትፏዊ ሊሆኑ አይችሉም። የተዛባ እድገት ይወለዳል። ተከታታይ ትውልድ፤ አንዱ የበላይ፤ ሌላው ታዛዥ። አንዱ ደሃ ሌላው ሃብታም። አንዱ በልቶ አዳሪ፤ ሌላው ጦም አዳሪ ይሆናል። ከተፈጠረው አዙሪኝ ለመውጣት ቀላል አይሆንም።

የህወሓት/ኢህአዴግ ባለስልጣናት፤ ስለ እድገት የሚያቀርቡት ማስረጃ የኢትዮጵያ ሕዝብ የማይቀበለው መሆኑን አንባቢው ያውቃል የሚል ግምት አለን። ለማንሳት የምንፈልገው፤ የማንኛውም የህብረተሰባቸውን ህይወት የለወጡ ታዳጊ አገሮች--ቦትስዋና፤ ሞሪሽየስ፤ ቤትናም፤ ታይላንድ፤ ብራዚል ወዘተ--የሚያሳየው ገጽታ የክልላዊ ሳይሆን የብሄራዊ እድገት ነው። ክልላዊ ነው ካልን በባንቱስታን ደቡብ አፍሪካም እድገት ነበር። ያደጉት አገሮች ያሳዩት ሂደት ሁሉም አገራዊ መሆናቸውን ነው። አገራዊ ለሆነ የእድገት ሂደት፤ አገራዊ የሆኑ ተቋሞችና አገራዊ የሆነ የሕዝብ ተሳትፎ ቁልፍ ናቸው። ወጣቱ በሚማርበት ጊዜ፤ "እድገትህ ለክልልህ" ከተባለ ለብሄራዊ ልማት እንዳያስብ ይገደዳል። እድገት በመላው ሕዝብ ጥቅም ላይ ካልተመሰረተና በሕግ ካልተዳኘ፤ የእድገቱ ጥቅም ለጥቂቶች ብቻ ይሆናል። ኢትዮጵያ የምናየው ይህን ነው። እድገት ከሕዝብ ጥቅምና የኑሮ መሻሻል ጋር ካልተሳሰረ፤ ዘመናዊነትና ዘላቂነት፤ ፍትህና ርትእ እውን አይሆኑም። ከጥገኛነት ነጻ የሆነና ራሱን የቻለ፤ የውስጥ የማምረት ሃይሉ--የፍጆት፤ የማምረቻ ሃይሎችን የሚያቀርብ፤ ቀስ በቀስ፤ ከውጭ አቅራቢዎች ጋር ተወዳዳሪ የሆነ-- ጠንካራ ኢኮኖሚ ለመገንባት አይቻልም። የአሁኑን ቅጥ ያጣ የፖለቲካና የኢኮኖሚ አገዛዝ፤ እንደ ነጻ የገቢያ አሰራር (Free and competitive market economy) አድርጎ ማቅረብ ከእውነቱ የራቀ ነው። ልክ፤ የሰብአዊ መብት አለ እንደሚባለው። ገዢው ፓርቲ ነጻና ውድድር ያለበት ኢኮኖሚ የሚለው፤ በፓርቲና በጥቂት የፓርቲው አጋር ድርጅቶች የሚንቀሳቀስ፤ ለአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ዝግ የሆነውን

ኢኮኖሚ ነው። ወጣቱ ትውልድ ይህን ዝግ የሆነ የኢኮኖሚ አመራር ሲያይ ተስፋ ይቆርጣል። ከመንግሥት ድጋፍ ካላገኘሁ ተስፋ አይኖረኝም ይላል። ሙብቱን አሳልፎ ይሰጣል። ስለዚህ፤ ዝግ የሆነ የኢኮኖሚ አመራር አገልግሎቱ፤ ለጠባብ ክበብ ነው ለማለት ያስችላል። አገር ወለድ ኢኮኖሚ ለመፍጠር፤ አገራዊ የሆነ አመራር ቁልፍ የሚሆነው ለዚህ ነው። የቦትስዋናን እድገት ምሳሌ እንጠቀም። የነፍስ ወከፍ ገቢዋ በዓመት፤ <u>$15,800፤ የኢትዮጵያ ከ $498 (2014 ግምት)።</u>

ራሷን ያስመሰገነችውን ቦትስዋና--ሕዝቧን ያበለጸገች አገር ስናይ--እድገቷ ምስጢር ሳይሆን የአገዛዝና የብሔራዊ አመራር ጥሩነት ውጤት ነው ለማለት ያስደፍራል። እአአ በ 1966 ነጻነቷን የተጎናጸፈችው ቦትስዋና፤ በዚያ ወቅት 22 (ብቻ) ዩንቨርስቲ የጨረሱ ዜጎች ነበሯት። የድህነት ምሳሌ ነበረች ማለት ነው። ከዚህ ዝቅተኛ ደረጃ ተነስታ እንዴት የአፍሪካ የእድገት አርአያ ልትሆን ቻለች ብለን እንጠይቅ። በመጀመሪያ፤ ሁሉን አቀፍ የሆነ አገራዊ ህገ መንግስት፤ ተቋሞችና የመንግስት አስተዳደር (Civil Service)፤ ስራ ላይ አዋለች። ህወሓት የኢትዮጵያን የሚያኮራ ተቋም አፈራርሶ በካድሬዎች ተክቷል። ቦትስዋና ነጻና ተሳትፏዊ ምርጫዎችን በግልጽነትና በተደጋጋሚ አካሄደች። የግል ሃብት ዋስትናን በሕግ እንዲረጋገጥ አደረገች። ማእከላዊ አስተዳደር፤ ከሚዛናዊ የክፍለ ሃገር ተሳትፎና የሕዝብ ድምጽ ጋር ጎን ለጎን ተደጋግፈው እንዲሰሩ አደረገች። እንቁ (diamond) በብዛት ሲገኝ ሁሉም የአገሪቱ ሕዝብ እንዲጠቀም አደረገች። ከኢንቬስተሮች ጋር ተደራደረች። ጥቅሟን አስከበረች። የሚገኘው ትርፍ የበላይ ስልጣን ለያዙ ጥቂት ሰዎች ጥቅም እንዳይሆን፤ ለአገሪቱ ዘላቂ እድገትና ለመላው ሕዝብ ኑሮ መሻሻል ስራ ላይ አዋለች። ስግብግብነት፤ ራስ ወዳድነት፤ ሙሰኝነት ተወገዱ። በሕግ የበላይነት የሚመራ፤ ከሙሰኝነት ነጻ የሆነ፤ ለሕዝብ ሃላፊነትና ተጠሪነት ያለው አመራር ተፈጠረ። ተቋሞች ሁሉ ለሕዝብ አገልጋዮች እንዲሆኑ አደረገች። የትምኅርቱ ስርአት ወጣቱ ትውልድ ለራሱና ለሃገሩ እንዲያስብ ረድቶታል።

ቦትስዋናና በፍጥነት በማደግ ላይ ያለችው ጋና፤ የሚያሳዩት፤ አገራዊ ተቋሞች፤ አገራዊ አመራር፤ የሕዝብ ተሳትፎ፤ ለሕዝብ ተጠሪነት፤ የህግ የበላይነትና የሰው ህይወት ክቡርነት፤ ተከታታይ ነጻ ምርጫ፤ የግል ንብረት በሕግ ታዋቂነት፤ የተፈጥሮ ሃብት ለሃገርና ለሕዝብ ጥቅም መዋል፤ ወዘተ ለልማት ቁልፍ መሆናቸውን ነው። እነዚህ ስኬታማ <u>የሚሆኑት ሁሉን-አቀፍ የሆነ የመንግሥት ስርአትና ሁሉን-አቀፍ አገራዊ ተቋሞች ሲኖሩ፤</u> መሪዎች የሕዝብ አገልጋዮች ሲሆኑ ብቻ ነው። ዘላቂነትና ፍትሃዊነት ያለው እድገት በአዋጅ አይመጣም። የሚገኘው እንደ ቦትስዋና፤ እንደ ጋና፤ እንደ ሞሪሽየስ ባሉ፤ ለሕዝብ ተጠሪና ሃላፊነት ባለባቸው፤ የአገዛዝና የአመራር መንገዶች ነው። እድገት የትም አገር ሊኖር ይችላል። በተለይ፤ እንደ ኢትዮጵያ ባለ፤ ከአርባ ቢሊየን ዶላር በላይ ለልማትና ለበጎ አድራጎት የሚውል በእርዳታ ባገኘና በአመት፤ ቢያንስ አራት ቢሊዮን ዶላር የባጀት ድጎማ በሚያገኝ መንግሥት። ችግሩ፤ የገንዘብ እጥረት አይደለም። የገንዘብ አጠቃቀምና ስርጭት ጉዳይ ነው። ስለሆነም፤ እድገት ቢታይም፤ የአብዛኛው ሕዝብ ኑሮ ሊሻሻል አልቻለም። በዚህ ከቀጠለ፤ ለአብዛኛው ሕዝብ፤ የዛሬ አምስት አመት ህይወት ለዋጭ እድገት አይታይም። በእርዳታ የሚገኘው ገንዘብ ለጥቂቶች ሃብት ማካበቻ፤ ታይቶ የማይታወቅ የድሎት ኑሮ መኖሪያ፤ የገንዘብ ማሸሻ መንገድ እየሆነ ነው። በአንድ አመት ሶስት፤ ነጥብ ሶስት ቢሊየን ዶላር ከአገር ያለአግባብ መውጣት የሚያሳየው፤ በዲሞክራሳዊዋ በቦትስዋናና በአንድ ፓርቲ አምባገነንነት በምትመራ ኢትዮጵያ መካከል ያለውን ሰፊ ልዩነት ነው። በዚህ አይነት፤ ቦትስዋና ከደረሰችበት፤ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ለመድረስ፤ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ምን ማድረግ እንዳለበት ያመለክታል። ቦትስዋና ዛሬ ከኮስታሪካ ጋር እንጅ ከኢትዮጵያ ጋር አትነጻጸርም። ሁለቱም መካከለኛ ገቢ የደረሱ፤ ህብረተሰባቸው ተደስቶ በሰላም የሚኖሩባቸው አገሮች ናቸው። ፍትሃዊ እድገት ሰላምና ደስታን ፈጥሮላቸዋል።

በቦትስዋና፤ በኮስታሪካ፤ አሁን፤ በጋና የሚታየው እድገት የሚመስክረው አበይት ነገር አለ። ይህም፤ ለሃገር ሃላፊነት የሌላቸው ተቋሞች፤ ለመላው ህብረተሰብ ተጠሪነት የሌለው አመራር፤ በዘላቂነትና ፍትሃዊነት ደረጃ ሲታይ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያይላል። ለዚህ ማስረጃው በቱኒዥያ፤ በግብጽ፤ በየመን፤ በሊቢያና፤ አሁን በሶሪያ የሚጠፋው በሕዝብ የሚመራው ለውጥ ነው። እነዚህ ለውጦች፤ ከኑሮ ውድነት፤ ከስራ ማጣት፤ ከጭቆና፤ ከኪራይተኛነት ባህል (rent-seeking culture)፤ ከሙስና፤ ከአድልዎ፤ ከህገ ወጥነት፤ ከስልጣን ብልግና፤ ከሰባዊ ሙብቶች አፈና፤ ከተስፋ መቁረጥ፤ ወዘተ የመነጩ ናቸው። ጊዜ ቢወስድም፤ ነጻነቱንና ሙብቱን የተከለከለ ሕዝብ ለማስብ፤ ለመፍጠር፤ ለማደግ፤ ራሱን ረድቶ አገሩን ለመርዳት ከፈለገ፤ ከሁሉም በላይ ለፍትህ ቆርጦ መነሳት አለበት። ለራሱ ሙብት መሞት አለበት ብለው፤ በመተባበር የተነሱ በሰሜን አፍሪካ፤ በኤገርያና በሌሎች ብዙ ሕዝቦች እናያለን። እነዚህ ህብረተሰቦች የሚፈልጉት የቦትስዋናና የኮስታሪካ አይነት የኑሮ ደረጃ ነው። የሚያውቁት፤ ከዚህ ደረጃ ለመድረስ አምባገነናዊ አገዛዝ እንደማያዋጣቸው ነው። የሚያደርሳቸው ስርአት፤ ሁሉን አቀፍ፤ ለሁሉ እድል ከፋችና አመቻች የሆነ፤ በእኩልነት፤ በፍትህ፤ በሕዝብ ድምጽ የሚያምን፤ ለሕዝብ ተጠሪ አማራጭና ይህን የሚመራ ለሕዝብ ተገዥና ችሎታ ያለው አገራዊ አመራር ነው። በግብጽ እንደምናየው፤ የዲሞክራሳዊ አገዛዝ ምስረታ ቀላል አይደለም፤ ትእግስትና መቻቻል ይጠይቃል።

ሆኖም፤ ሌላ አማራጭ የለም። አሜሪካ የደረሰችበት ታላቅነት በቀላል መንገድ አይደለም። በመደራጀት፤ በመስራት፤ ለሙብቶች በመቆም፤ የህግ የበላይነትን በመንከባከብ፤ ለሁሉም እድል ከፋች የሆነ የትምኃርትና የኢኮኖሚ አመራር በመከተል ወዘተ ነው። ፍትሃዊ ስርአት በቀላሉ አይገነባም።

የማይሸፈን የገጠር ድህነት

በፍጥነት ዘላቂነትና ፍትሃዊ የሆነ እድገት የተጎናጸፉ፤ ወይንም ለዚህ መንገድ የከፈቱ አገሮችን ስናይ፤ የሚለያቸው መልካም ወይንም ጥሩ አገዛዝ፤ ፈረንጆች (Good Governance) የሚሉት ነው። ባህሉ ሲታይ፤የመንግስት አስተዳደሩና አመራሩ የተለየ ነው። መንግሥት ድልድይ ሆኖ ያገናኛል፤ ያስማማል፤ ሕዝብን እርስ በእርስ አያናክስም። ሕዝቡ ታሪኩንና ማንነቱን እንዲጠራጠር አያደርግም። በብሄርና በቋንቋ ልዩነቶች የተመሰረተው የክልል አስተዳደር በግል ሙብትና በኢትዮጵያዊነት በሚገለፅ ማንነት አያምንም። እንዲያውም ኢትዮጵያዊነትን እያከሸፈ ይታያል። በመከፋፈል የሚገዛ መንግሥት ለህብረተሰብ መደጋገፍ ጸር ነው። ለገዢው ቡድንና ደጋፊዎች ግን አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ጊዜያዊ ጥቅም ያስገኛል። የአጭር ጊዜ ጥቅምን ብቻ የሚፈልጉ ግለሰቦችና ቡድኖች ድርጊታቸው ለኢትዮጵያና ለአብዛኛው ሕዝብ እድገት ጎጂ መሆኑን አያውቁም ለማለት አይቻልም። አንድ ሚሊዮን የአዲስ አበባ ሕዝብ “በመጠለያ” እንደሚኖር አያውቁም ማለት ለህሊና ይቀፋል። ሆኖም፤ አዲስ ባለጠጋዎች የገቢና የኑሮ ልዩነትን “የዘመናዊነትና የሕዝብ ቁጥር መጨመር ውጤት (an outcome of modernization and increase in population)” ነው ብለው ያልፉታል። የተዛባ ገቢና ባለጠጋነት ውጤት ነው ለማለት አይችሉም። ከሰሜን አፍሪካ እንዳየነው፤ በገቢ ልዩነት የተከፋፈለን፤ የስራ እድል የሌለውን፤ በዋጋ ግሽበት የሚሰቃየውን፤ ባጭሩ፤ ምስኪኑና ደሃውን ሕዝብ ለመግዛት ቀላል የነበረበት ጊዜ አልፏል። ጥያቄው የመኖር አለመኖር ሆኗል። ዜና ይሰራጫል። ሌሎች የሚያደርጉት ይሰማል። ስለሆነም፤ የቁጥጥር፤ የአፈና መንገድ ዲሞክራሳዊ ለውጥን ለዘላለም አይገታውም። የገዢው ፓርቲ ደጋፊዎች የከተማ ነዋሪው በኑሮ ውድነትና በስራ አጥነት እንደሚሰቃይ ያምናሉ። የሚሉት ሰማንያ ሶስት በሙቶው የሚኖረው በገጠር ነው። የገጠሩ ሕዝብ ኑሮ ተሻሽሏል የሚል ነው። በመሰርተ ልማት መሻሻል እንዳለ አያከራክርም። የአብዛኛው የገጠር ሕዝብ ኑሮ ተሻሽሏል የሚለውን አንቀበልም። በጎጆ፤ ያለ ሙብራት አገልግሎት፤ ያለ መፀዳጃ፤ ያለ ንጽህ ውሃ፤ ያለ ዘመናዊ የጤና አገልግሎት ከመሳፍንት ዘመን የሚለይበት ግልፅ አይደለም። ብዙ ህይወት የተከፈለበት ምኞት ኑሮን ለማሻሻል፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከሚዘገንን ደሃነትና የጨለማ ዘመን ለማውጣት ነበር።

ዓለም ባንክ በተደጋጋሚ የኢትዮጵያን ሕዝብ ኑሮ አጥንቷል። ሰማንያ ሁለት ሚሊዮን የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በገጠር ይኖራል። ከዚህ ሃያ በሙቶ (አስራ ዘጠኝ ሚሊዮን) የሚሆነው በቂ መሬት ስለሌለው የሚፈልገውን ምግብ ግማሽ ብቻ አርሶ ያገኛል። ሌላውን ከለጋሶች ይጠብቃል። ኑሮው ተሻሽሏል በሚባልበት ኢኮኖሚ አንድ በሙቶ የሚሆኑ የግብርና ቤተሰቦች ብቻ አምስት ሄክታር መሬት ያርሳሉ። አምሳ በሙቶ የሚሆነው ከግማሽ ሄክታር በታች ያርሳል። መሬቱ የተበላ በመሆኑ የመሬት ድህነት ብቻ ሳይሆን፤ የአካባቢ መበላሸት በየጊዜው አስከፊ ረሃብ ይፈጥራል። በምግብ እጥረት የሚሞቱ ህጻናት ቁጥር አልቀነሰም። በአጠቃላይ ሲታይ የገጠሩ ሕዝብ ኑሮ ከእጅ ወደ አፍ ነው ለማለት ይቻላል። ደርግ ያወጀውን፤ ኢህአፓና መኤሶን ያመቻቹትን የመሬት ይዞታ አዋጅ ፓርቲው የሚቆጣጠረው መንግሥት ለፖለቲካ ቁጥጥር ማዋሉ ሁኔታውን አባብሶታል። አካባቢን ማን ባለቤት ሆኖ ይንከባከብ። ገዢው ፓርቲ የገጠሩ ሕዝብ ኑሮ አለመሻሻሉን የሚሸፍንበት መንገድ አለው። ቁጥጥርና ስለላ ይባላል። ሆኖም የቁጥጥር ስርአት፤ ድህነትን አይሸፍንም። የስራ እድል ለአብዛኛው አይፈጥርም። የዚህ ሁሉ፤ ጨለማ የሚመስል፤ የጥቂቶች ባለጠጋነትና ለጥቂቶች ቁጥጥር የዋለ የኢኮኖሚና የተፈጥሮ ሃብት አመራር ዘላቂነት አይኖረውም። ህብረተሰቡ የሚያውቀው፤ የቁጥጥሩ አገዛዝ ዋና አላማ፤ ኢትዮጵያዊነትን በጎሰኝነት መታወቂያ ተክቶ፤ የገዢውን ፓርቲ ስልጣንና ጥቅም ለማጠናከር መሆኑን ነው። የኢትዮጵያዊነት መታወቂያ እየተናደ ሲሄድ፤ የሚተካው የማህበረሰብ አንድነት መናድ ነው። ሁሉም የሚገደደው፤ በአገር ደረጃ ማሰብ ሳይሆን፤ በጥቅም፤ በመንደር፤ በጎሳ፤ በክልል ጎጆ መዋጥ። ለቀኑ ኑሮ መሯሯጥ ነው። ለዚህ ዋና ዋና የተቋም መለኪያዎች እንዴት እንደተለውጡ ማየት ይበጃል። ሁለት ምሳሌዎች።

የህወሓት ተቋሞች የኢትዮጵያን ሕዝብ አይመስሉም

ህወሓት በበላይነት የመራው መንግሥት፤ የኢትዮጵያን ተቋሞች ገርስሷል። በምትኩ፤ የጎሰኛ ተቋሞችን አደራጅቷል። የኢትዮጵያ የጦር፤ የፖሊስ፤ የስለላ ወዘተ ተቋሞች ማንን ይመስላሉ፤ ማንን ያገለግላሉ? የበላይ እዛዦቻቸው ምን ይመስላሉ? አገራዊና ኢትዮጵያዊ ናቸው ወይንስ ጎሳዊ/ ህወሓታዊ? የማይካደው፤ በማንኛውም ቁልፍ ቦታ፤ አብዛኛዎቹ የበላዮች/ወሳኞች/አዛዦች የትግራይ ወይንም የኤርትራ ሰዎች መሆናቸው አያከራክርም። ለይስሙላ፤ ትግራይ ያልሆነ ሃላፊዎች ፊት ለፊት ተሹምው ቢቀመጥ፤ ከጀርባ ወሳኙ ታማኝ የሆነ የትግራይ ተወላጅ ነው። ሌላውን አያምንም ማለት ነው። ከዚሁም ብሶ፤ “ከአንድ መንደር” የመጡ ተብሎ ይነገራል። እነዚህና አገር ያገለግላሉ የተባሉ ድርጅቶች፤

የኢትዮጵያን ሕዝብ ይመስላሉ። ኢትዮጵያን ያገለግላሉ ብሎ ለመቀበል ምንም ማስረጃ የለም። የቦትስዋና አገዛዝ ከኢትዮጵያ የሚለየው በዚህ ነው። የኢትዮጵያ ተቋሞች መሪዎች አገሪቱን አይመስሉም። በንጉሡና በደርግ ስርአቶች፤ የኢትዮጵያ የመከላከያ፤ የፖሊስና የስለላ ተቋሞች አገራዊ ነበሩ። የአንድ ጎሳ ወይንም ፓርቲ የስልጣን ምሰሶ አልነበሩም። ለመንግሥቱ ታማኝነት አልነበራቸውም ማለት አይደለም። ይህ የተቋሞች ልዩነት በደንብ መታወቅ አለበት። የኢትዮጵያን ሕዝብ ካልመሰሉ፤ ህወሓት ለራሱ ጠባብ ቡድን የበላይነት ይጠቀምባቸዋል። ተቋሞች የመላውን ሕዝብ ገጽታ የሚወክሉ ካልመሰሉ፤ መላውን ሕዝብ ካላገለገሉ ኢትዮጵያዊነታችው የት ላይ ሊሆን ይችላል ብሎ መጠየቅ አግባብ አለው። የጋና ጀኔራል የሚታወቀው በጋናዊነቱ ነው። የሚያገለግለው ጋናን ነው። ስለሆነም፤ የአሁኑ የወታደር/ፖሊስ/ስለላ አወቃቀር አመራር፤ የሚመስለው ገዢውን ፓርቲ። የሚያገለግለው ገዢውን ፓርቲ ነው። ዋና ሚናው የህወሓትን የበላይነት መጠበቅ ነው። ጀኔራሎች ሰማይ ጠቀስ ፎቅ የሚሰሩት በደሞዛቸው አይደለም። በሚያገኙት ልዩ ድጎማ ነው። ጡሮታ ሲወጡ የኤፈርት ወይንም የሌላ ድርጅት መሪ ወይንም የቦርድ አባል የሚሆኑት ታማኝነታቸውን ለማረጋገጥ፤ ውለታቸውን ለመክፈል ነው። የኢትዮጵያን ሕዝብ ደህንነት፤ ያለ አድልዎ ለመጠበቅ፤ አገሪቱን ከጥቃት ለማዳን፤ መከላከያ ሃይሉ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ሕዝብ መምሰል አለበት። ካልሆነ፤ የሰብአዊ መብቶችን አብሮ ያግባል። የችግሩ አካል ይሆናል።

ሆኖም፤ ይህ ስራዊት ከሕዝብ የተወጣጣ እንደመሆኑ መጠን፤ አንድ ቀን ወደ ሕዝብና ወደ ዋናው አገርን የመከላከል ተግባሩ መመለሱ አይቀርም። ቢያንስ፤ ለማን፤ ለምን፤ እንደቆመ ራሱን መጠየቁ አያጠራጥርም። አሁንም እንደሚሰማው ራሱን እየጠየቀ ነው። በኢህአዴግ ስብሰብ ውስጥ ያሉ አባላትም፤ መለስ ካለፈ በኋላ፤ ቀስ በቀስ፤ ራሳቸውን መጠየቅ ጀምረዋል። ኢትዮጵያውያን ለዚህ የተደበቀ፤ ግን ያልጠፋ ለአገር የማሰብ ባህል፤ የሚያኮራ ታሪክና የአስተዋይነት ቅርስ አለን። ምንም አይነት አገዛዝ ሕዝቡን ቢያማርረው፤ በጠባብ ብሄርተኛነት የተነሳ፤ እርስ- በእርሱ በጅምላ የመገዳደል ባህል፤ ልምድ፤ ጸባይና፤ አዝማሚያ የለውም። የኢትዮጵያን ሕዝብ ልዩ የሚያደርገው አንዱ ይኸ ነው። ጠቅላይ ሚንስትር መለስ የተሳሳተው እዚሕም ላይ ነው። በዘጠና ሰባት ምርጫ፤ ሕዝቡ ያለውን ትእግስት፤ መቻቻልና ታላቅነት ቢያይም፤ መለስ፤ ሳያዘው ጨዋነቱን አስመስከሯል። እንደ ሩዋንዳ፤ በትግራይ ተወላጆች ላይ እልቂት ይመጣል ተብሎ የተሰጠው ፕሮፓጋንዳ ሊሆን አለመቻሉን የኢትዮጵያ ሕዝብ አሰምሮበታል። የበደለውን ቡድን/ግለሰብ ከሰላማዊው ሕዝብ መለየት የሚችል ህብረተሰብ ነው። የጦር ሃይሉን ለሰላም፤ ለመቻቻል፤ ለእርቅ ወዘተ ይመራዋል ብሎ ለመገመት ይቻላል። በሕዝብ እምነት ሊኖረን የሚገባን ለዚህ ነው። ስለዚህ፤ ጦሩ፤ አገር አቀፍ በሆነ ደረጃ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቢነሳ፤ ድርጅትና አመራር ቢኖር፤ ወገኑ እርስ በርስ እንዲፋጅ ያደርጋል ብሎ ለመገመት ያስቸግረናል። የሚፈልገው እኩልነትን የሚያቅፍ አማራጭ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በዘር የተመሰረተውን የህወሓት ቡድናዊ አገዛዝ፤ ከደቡብ አፍረካ አፓርታይድ አገዛዝ አይለይም ይላል። ስንመረምረው፤ ህወሓት፤ ራሱን ያጋልጣል። በዘር የተቀነባበረው ክልል የተባለ የአገዛዝና የአስተዳደር ዘዴ፤ በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ ሲተከልበት አላማው ምን ነበርና ለማን ሲባል? ማነንን ለማድከም? ማንን ለማሳደድ? ማንን ለማክበር፤ ሲል የቀየው፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ መልሱን አግኝቷል። ህወሕት ለዓለም ያቀረበው ፕሮፓጋንዳ፤ የሕዝብን መብት ለማጠናከር፤ ለማጎልመስ፤ ኢትዮጵያን ለመታደግ። ሕዝብ ወሳኝ እንዲሆን ለማድረግ። ፍጥነት ያለው እድገት እውን ለማድረግ። ኢትዮጵያ እንዳትፈራርስ ለማድረግ የሚሉ ናቸው። የመወሰን መብትን እንደመለኪያ ወስደን፤ ለሕዝብ አገልጋይነቱን ብንመረምር ክፍተቱን ያሳየናል። የዲሞክራሲ ዘመን መጣልህ የተባለው ሕዝብ ተጠቂና ታዣዥ ከሆነ የዲሞክራሲ ትርጉም ቀፎ ነው። በተለይ፤ ለአርሶ-አደሩ ሕዝብ። አርሶ-አደሩ፤ በመወሰን ደረጃ፤ ምንም መብት የለውም። የፓርቲው ገባር ሆኗል። የእርሻ መሬቱን ሆነ የእርሻውን ውጤት አያዝበትም። ባለቤትነት የለውም። እንዲያውም ነጠቃው ባለበት ሁሉ ከእርሻው መሬት እንዲፈናቀልና ያለ መኖርያ እንዲሰደድ እየሆነ ነው። ነጠቃው በማን ትእዛዝ፤ ለማን ጥቅም፤ እንደሚደረግ ብዙ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ዘግበውታል። ከቦትስዋና ጋር ስናወዳድር፤ የቁጥጥር አገዛዝ ባለበት፤ እነደ ኢትዮጵያ ባለ አገር ሁሉ የተፈጥሮ ሃብትን እንደተፈለገ ለመስጠት፤ ለመሸጥ፤ ሃብት ለማካበት፤ ለአድልዎና ሙስና ስርአቱን ለማራዘም ይረዳል። የገጠሩ ህብረተሰብ ለቁጥጥር የተዳረገው ለዚህ አመች እንዲሆን ነው። የከተማ ሆነ የገጠሩ ሕዝብ ስልጣን አለው ብሎ ለመናገር አይቻልም። አርሶ አደሩ የሚኖርበትን ቀርቶ፤ የሚያመርተውን ሊያዝበት አልቻለም። ህወሓት፤ የደርግን የመሬት ይዞታ አዋጅ ለቁጥጥር ተጠቅሞበታል። ትርፍ ያገኘበታል። የሚያስደንቀው እሴት፤ ኦሮሞው በጅምላ አማራውን አልጨፈጨፈም፤ ትግሬውን ከክልሌ ውጣ አላለም። የኦሮሞ ሆነ የአማራ፤ የትግራይ ሆነ የአፋር ወዘተ ሕዝብ የሚያኮራ አብሮ የመኖር ባህል እንዳለው አስመስከሯል። አክራሪዎች ይኼን ዋጋ አልሰጡትም።

የጋምቤላ፣ የአፋር፤ የኦጋዴን፤ የደቡብ፤ የኦሮምያ፤ የአማራ፤ የቤኒ-ሻንጉል ጉሙዝ ለም መሬት፤ ከ 36 አገሮች ለመጡ፤ የህንድ ኩባንያዎች፤ ለምሳሌ፤ ካሩቱሪ፤ የአረብ-አገሮች ጥቅል ድርጅቶች፤ ለምሳሌ፤ ሳውዲ-ስታር፤ የግብጽ ማእከላዊ

ባንክና ከ 8,000 በላይ ለሚሆኑ ኮንትራት ያቀረቡ የውጭ ኢንቬስተሮች፤ ለህወሓት ምርጥ ደጋፊዎች፤ በጅምላ እስከ ዘጠና ዘጠኝ አመታት ድረስ፤ በዝቅተኛ ኪራይና ያለምንም ገደብ ተላልፏል። የጋርዲያን ጋዜጣ፤ በኢትዮጵያ የታየውን የተፈጥሮ ሃብት ለጋስ ስጦታ "በዓለም ያልታየ የተፈጥሮ ሃብት ማስተላለፍ፤ ማስረከብ" ብሎ ደምድሞታል። ገዢው ፓርቲ ይህን የተፈጥሮ ሃብት ሲያስረክብ የተጠቀመበት ዘዴ፤ የክልልን አስተዳደር መብት ጠቅሶ ነው። ፖሊሲውን በመአከልነት ወስኖ፤ ፍጻሜውን ለክልል አስተዳደር አስተላልፏል። የኢትዮጵያን መሬት ለሰሜን ሱዳን ሲሰጥ የተጠቀመበት ዘዴ ተመሳሳይ ነው። በመአከላዊ መንግሥት ሆነ፤ በክልል አስተዳደር፤ ጥቅሙን ማጋነን እንጅ ጉዳቱን ከሁሉ አቅጣጫ የሚያሳይ አንድም መመዘኛ አልተሰጠም። የመሬት ነጠቃን ከአጠቃላይ የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀምና እድገት ጋር አብሮ የሚያመዛዝን እቅድ አልወጣም። የዚህን "ወረራ" የሚመስል የፖሊሲ ጥፋት፤ ጥልቀት ያለው ትንተና ያስፈልገዋል። በውጭ ተቋሞች የቀረቡ ጥናቶች የሚያሳዩት፤ በኦሮምያ ክልል ብቻ የብዙ ቢሊየን ብር መዋእለንዋይ ፈሶበታል። ሰፊ የእርሻ ልማት ይካሄዳል። የስራ እድል ተፈጥሯል የሚል ነው። ጥያቄው፤ የኢንቬስትሜንቱ ዋና ተጠቃሚ ማነው የሚለው ነው። ባጭሩ፤ አብዛኛው የኦሮሞ ህብረተሰብ አይደለም። በሌሎችም ክልሎች የሚካሄደው የመሬት ነጠቃ፤ ከህብረተሰቡ፤ ከኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና፤ ከድህነት ቅነሳ (Poverty Reduction) ከአካባቢ ጥበቃ፤ ከተከታታይና ፍትሃዊ እድገት አንጻር አልታየም።

እስካሁን የታየው፤ የመሬት ነጠቃና ቅርሚት ውጤታማ ከሆነ መራብ የሌለባት አገር ለምን ትራባለች? ረሃብ በገጠር ለምን ይስፋፋል? የምግብ ዋጋ ግሽበት ለምን እየባሰ ይሄዳል? ነዋሪዎች ለምን ይሰደዳሉ? ማን ተጠቃሚ፤ ማን ተጎጂ እየሆነ ነው? ብሎ መጠየቅን ያስገድዳል። ባጭሩ፤ የክልል አስተዳደር፤ ለገጠር ሆነ ለከተማ ሕብረተሰብ ጥቅም፤ ለእድገት ዘላቂነት፤ ለተሳትፎ፤ ለድህነት ቅነሳ ጥረት ይረዳል ለማለት አስቸጋሪ ነው። በአብዛኛው አይቻልም የሚል። የሕዝብ ተሳትፎና መብት ያልተከበረበት፤ የከተማ ሆነ የገጠር ኢኮኖሚ አመራር ፖሊሲ፤ የማህረሰብ ስርአትና እድገት፤ ድህነትንና ኋላ ቀርነትን አላጠፋም። በበለጠ ስልጣን ያጠናከሩት፤ ሃብት የሰጡት ለገዢው ፓርቲና በበላይነት ለሚያገለግሉ የክልል መሪዎች ነው። ይህ አድሏዊና አፋኝ አገዛዝ ከቀጠለ በገጠርም ሆነ በከተማ፤ ስደት፤ የኑሮ ውድነት፤ስራ አጥነት፤ ግጭት፤ ረሃብ፤ የሕዝብ እጣ ሆነው ይቀያሉ። ከተፈጥሮ ሃብት የሚነሳ ግጭት አይቀርም። ገዢው ፓርቲ የፖለቲካ፤ የተፈጥሮ ሃብትና የኢኮኖሚ የበላይነትን በተከታታይ ለማረጋገጥ፤ የፖለቲካ፤ የማህበረሰብ፤ የመገናኛና ሌሎች ሰብአዊ መብቶች ሙሉ በሙሉ አፍኗል። ማፈኑ መፍትሄ ሊሆን አይችልም። የውጭ ለጋስና አበዳሪ የሆኑ መንግስታትና ድርጅቶች፤ የገዢውን ፓርቲ ፈለግ ተከትለው፤ በአፍ ብቻ፤ መብቶች ይከበሩ ይላሉ።

ከመሸንገል ውጭ፤ የሚሰጡትን እርዳታ ከሰብአዊ መብቶች፤ ከገጠሩ ህብረተሰብ የኑሮ መሻሻል ጋር ለማያያዝ ፈቃደኛነት አላሳዩም። ከሁሉ በላይ የመረጡት እርጋታን ነው። የራሳቸው ጥቅም መጠበቁን ነው። የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ዋና መመኪያ የሆነው የእርሻ መሬት አጠቃቀም ፖሊሲ አሁንም ኋላ ቀር ነው። ተከታታይ ረሃብ ሊወገድ የሚችለው የኢትዮጵያን የእርሻ መሬት ለውጭ ድርጅቶችና መንግስታት በመስጠት ሊሆን አይችልም። ዝቅጠተኛ አምራቾችን በማጎልመስ፤ አገር ወለድ የግል ክፍል እንዲጎለምስ በማድረግ ነው። ሆኖም፤ ባለፉት አመታት ገዢው ፓርቲ ብዙ ሚሊዮን ሄክታር መሬት፤ በርካሽ ዋጋ፤ ግልጽነትና ሃላፊነት በጎደለው መልክ ሲሰጥ እያዩ፤ ለጋሶች ይህ ፖሊሲ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝንናል በማለት በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ምንም ጫና አላደረጉም። በአንጻሩም፤ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎች ደካማ መሆናቸው፤ በአንድ ድምጽ፤ ለአንድ አገር፤ ለአንድ ህብረተሰብ ፍትህ አለመስራታቸው የችግሩ አካል አድርጓቸዋል። ድክመቱ ለተፈጥሮ ሃብት ከኢትዮጵያ ሕዝብ መነጠቅና ወሳኝ የሆኑ የኢኮኖሚ ምሰሶዎች (Pillars of the economy) ከህብረተሰቡ እጅ እየወጡ፤ ወደ ውጭ ኢንቬስተሮችና ወደ ጥቂት የህወሓት ደጋፊዎች እንዲሸጋገሩ ረድቷል።

ምእራፍ ሶስት፤ የጎሳ-ተኮር ፌደራሊዝም፤ የብሄራዊነት ናዳ ለብሄራዊ ምዝበራ ያመቻል የሚል ነው። ከልዩ ልዩ አንኳር ከሆኑ የፖሊሲ ጥያቄዎች ጋር በማያያዝ የጠባብ ጎሰኛነትን ጉዳት ያቀርባል። ጎሳ-ተኮር ፌደራሊዝም አድሏዊ ሆኗል። የተዛባ ገቢና ልማት ፈጥሯል። የህብረተሰቡን ግንኙነት ከስሩ እየናደው ሄዷል። የወጣቱን ትውልድ የኑሮ መሻሻል መሰረት አድክሞታል።

## ምእራፍ ሶስት

## የጎሳ-ተኮር ፌደራሊዝም ኢትዮጵያዊነትን እየናደ ነው

"ከሁሉ በላይ አከራካሪ የሆነው የህወሓት/የኢህአዴግ ሕገ-መንግስት አቢይ አንቀጽ፤ የተፈጥሮ ሃብትን፤ በተለይ፤ መሬትን፤ መንግስቱን ለሚመራውና ለሚቆጣጠረው፤ ለኢህአዴግ ማስረከቡ ነው" 16/

ቲኦዶር ቬስታል

"የብሄር ብሄረሰቦችን የራስን እድል በራስ መወሰን እስከመገንጠል የሚል አንቀጽ አጽድቀን የመሰረትነው ፌደራሊዝም ምን ያህል ከማእከላዊ መንግሥት ቁጥጥር ነጻ ነው?" 17/

ተመስገን ደሳለኝ

"ኢህአዴግ የፈጠረው የብሄር ፌደራሊዝም በብሄረሰቦችና በሕዝቦች መካከል ያለውን ግጭት አላቀዘቀዘውም። እንዲያውም ለመሬት፤ ለተፈጥሮ ሃብት፤ ለባጀትና ለአስተዳደር የበላይነት ያለውን ጤናማ ያልሆነ ውድድር አባብሶታል፤ ....ክልሎች ራሳቸውን ለማስተዳደር አልቻሉም" 18/

ኢንተርናሽናል ክራይሲስ ግሩፕ

እነዚህ ሶስት ታዛቢዎች የሚጋሩት አንድ መሰረተ ሃሳብ አለ። ህወሓትና የተለያዩ የጎሳ ስብስቦች ተወያይተው በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የጫኑት የብሄር ፌደራሊዝም የህብረተሰብ መብቶችን፤ በሕግ የሚገኝ እኩልነትን፤ ፍትህን እያጠፋ ነው። <u>የዚህ ክፍል አስኳል ሃሳብ አረቦች፤ ጣሊያኖች፤ በተለይ መሰሪ የሆኑት የጎሳ ከፋፋይነት አለቃ ሆነው የአፍሪካን ሕዝብ እርስ በርሱ እንዲናከስ ያደረጉት እንግሊዞች ቅኝ ገዢዎች በነበሩበት ወቅት የአገሮችን ሕዝቦች በማዳከምና በማጣላት ለመገዛት እንዲያመቹ፤ ተባብረው ለማደግ እንዳይችሉ በጎሳና በኃይማኖት ከፋፍለው ያበረከቱት ቅርስ ነው። በኢትዮጵያ ይኼን ዘዴ በስራ ላይ ያዋሉት ጣሊያኖች ናቸው። የኢትዮጵያው ግራ ክንፍ ጥልቀት ያለው ጥናት ሳያደርግ፤ የሶቭየት ሕብረትን እርዮት ገልብጦ በኢትዮጵያ እንዲያስተጋባ አድርጎ ነበር። ብልጣ ብልጦቹ የሻቢያ መሪዎችና በጀርባቸው ደጋፊ የነበሩ የኢትዮጵያ ጠላቶች የኤርትራን ክፍል ሃገር ችግር "የቅኝ አገዛዝ (Colonial Question) ነው" ብለው የተዋሱትን አስተሳሰብና የኢትዮጵያው ግራ ክንፍ ያበረከታቸውን መሰረተ ሃሳብ ወደ ፖሊሲ ቀየሩት። የኢሳይያስ አፈወርቂ ቡድንና የህወሓት መስራቾች ይኼን በብሄረሰቦች ልዩነቶች ላይ፤ በአማራው ሕዝብ ቅኝ ገዢነት ላይ የተመሰረተ አገርና ሕብረተሰብ ለዋጭ አስተሳሰብ የራሳቸው መመሪያ አድርገው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲናንከስ፤ እንዲበታተን፤ ለመግዛት እንዲያመች አድርገው ተጠቀሙበት።</u> የህወሓት መስራቾችና የመለስ "እምላኪዎች" የሚሰሩትን ያውቃሉ። ከጅምሩ ከሻቢያ መሪዎችና ከውጭ ደጋፊዎቻቸው ጋር ሆኖ ያሰላው ኢትዮጵያን ለመግዛትና ለመመዝበር ኢትዮጵያውያንን እርስ በርሳቸው ማነታረክ አለበት። በሰላምና እርጋታ ስም፤ ፍትህን የሚፈልጉትን ሁሉ በፀረ-ሺብርተኛነት መክሰስና በቁጥጥር ውስጥ ማስገባት አለበት። የብሄር ስብስቦች ያልተገነዘቡት ይኼን ክስተት ነው። "ተባበሩ ወይንም ተሰባበሩ" የሚለውን አበይት ምክር አልሰሙም። ኢህአፓ፤ መኤሶን፤ እሴፓ፤ ኦነግ፤ ቅንጂት፤ መድረክ፤ አንድነት፤ መኤአድ፤ አሬና፤ ሰማያዊ ወዘተ ወዘተ እያሉ የህወሓትን መሰሪነት አለማወቅ ቂልነት ነው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ኦነግ ነው። የኦነግ መስራቾች ከሃጢያቱ ንፁህ አይደሉም። ጎሳዊውን ስርዓት አብረው መስርተዋል፤ ኤርትራን አስገንጥለዋል።

የኦነግ መስራቾችና መሪዎች ለዚህ ሕዝብን ከሕዝብ የሚያጋጭና ተከታታይ ትውልድ እርስ በርሱ እንዲጋጭ የሚያደርግ የቋንቋ ፌደራሊዝም ተገገር አደረጉት። ኤርትራ ከእናት አገሯ ተገነጠለች። የኢትዮጵያ የባህር በር ተዘጋ። ህወሓት በገባው ቃል መሰረት ኤርትራን ካስገነጠለ በኋላ በበበለጠና መሰሪነት በሚያሳይ ደረጃ ተደራጅቶ ራሱ የሚለውንና የሚፈልገውን ቋንቋ ሌሎች እንዲጠቀሙበትና እንዲፋተጉበት ያደርጋል። "የራሳችን ቋንቋ ተጠቅሞ ራሳችን ያዘናል፤ ያባላናል፤ ይገዛናል" የሚሉ ኢትዮጵያውያን ትክክል ናቸው። በመንደር ደረጃ የሚጠቀመው ዘዴም መንግሥት የሚሰራው ሁሉ ጥሩ ነው የሚል፤ እርስ በርሳችን እንድንጋጭ የሚያደር አመራር ነው። ለአማራው "ኦሮሞው መጣብህ ተጠንቀቅ፤ ለኦሮሞው ኢሰፓና አማራው መጡብህ ወዮልህ" ወዘተ የሚል። ህወሓት እንደፈለገው የኢትዮጵያ መልክአ ምድር እንዲከፋፈል፤ ስር ነቀል በሆነ ደርጃ መሰረት እንዲይዝ፤ ለእድገትና አብሮ ለመኖር በማያስችል መንገድ እንዲመሰረት አድርጓል። "ኢትዮጵያ ሃገሬ ናት፤ ዜግነቴ ኢትዮጵያዊ ህወሓት የበላይነት ስልጣኑ ይዞ ዘላቂነቱን በሕዝብ መከፋፈል ስሌት (Strategic calculation) ሕጋዊነት ሰጠ። የፖለቲካ "ቡዳነት" (የሮፌሰር መረራ ጉዲና ቃል መፈታተግ፤ መካሰስ፤ ለአገር ሳይሆን ለስልጣንና ለጥቅም መካሰስ መሰረት ያዘ። እንደሚታወቀው፤ የአብዛኛውን

የኦሮሞ ሕዝብ ፍላጎትና ምኞች ለማሟላት ያልቻለው አነግ፤ ቀስ በቀስ የህወሓት "ጠላት" ሆኖ በ "ሽብርተኛነት ተወነጀለ"። ህወሓት በፈለገው መንገድ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በጎሳ እንዲደራጁ አመቻቸ። ስለሆነም፤ የጎሳ አገዛዝና አመራር ከሁሉም በላይ የጠቀመው ለህወሓት የበላዮች ነው። ያለው ሁሉ ማስረጃ የሚያመለክተው "የፖለቲካው ቡዳ" ህወሓት እንጅ ለፍትህ የሚታገሉ ኃይሎች አይደሉም። ህወሓት ተቃዋሚውን

የዚህ ሕዝብን ከሕዝብ የሚናከስ፤ የሕዝብ እልቂትን በከፍተኛ ደረጃ ላይ ለማስከተል የሚችል ስርዓትና የኢትዮጵያን ግዛታዊ አንድነትና ህልውና ወደ ጥያቄ አስገብቶታልልል። የቋንቋ ፌደራሊዝም ሲመሰረት የቀረበው "መሰረተ ሃሳብ ወይንም ዋና አላማ፤ "ሃብታም፤ ፍትሃዊና ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ያለ አድልዎ የሚወከሉበትን" ስነስርአት መፍጠር የሚል ነበር። በተግባር የታየው፤ በራሱ መለኪያ ፈተናውን አላለፈም። ለዓለም የተገለጸው አላማ ዲሞክራሳዊና ፍትሃዊ ሲሆን፤ "በመለስ ዜናዊ ሊቀመንበርነትና ጠቅላይ ሚንስትርነት የተመራው ኢህአዴግ፤ የኢትዮጵያን ፖለቲካ ስነስርአት በማይመለስበት ደረጃ ለውጦታል። የዜግነት፤ የፖለቲካና የማንነትን ትርጉም ከኢትዮጵያዊነት ወደ ጠባብ ጎሰኝነት/ብሄርተኝነት እንዲሻገር አድርጎታል። ለምን? ቢያንስ የሚከተሉት ምክንያቶች ይገኙበታል።

አንድ፤ የክልል አገዛዝ ዋና አላማው አንጋፋ የሆኑትን የኦሮሞና የአማራ ብሄረሰቦች ለመከፋፈልና ቢቻል አናሳ ለማድረግ ነው። (To balkanize majorities into minorities; and to leverage TPLF's minority status better).

ሁለት፤ የአናሳውን የትግራይ ብሄረሰብ የበላይነት ሕጋዊይና ተቋማዊ መሰረት ለመጣል::

ሶስት፤ የክልል አስተዳደርን ተጠቅሞ የመንግስት ባጀትና የውጭ እርዳታ ለጥቂት ባለስልጣናት ለማሺጋሸግና ወደ ክልል አንድ (ትግራይ) ለማሽጋገር፤ የዚህን ክልል አቅም ከፍተኛ ደረጃ ላይ ለማድረስ:: አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የመገንጠል እድልን ለማመቻቸት፤ ከሰሜን ሱዳን ጋር የሚደረገው የጠነከረ ግንኙነት ይኼን ሃሳብ አጠናክሮታል።

አራት፤ የተከፋፈለ አስተዳደር ለአፈናና ለድብብቆሽ ስለሚያመች፤ የጦር፤ የቁሳቁስ፤ የመሰረተ ልማት፤ የምርትና ሌሎች ግብአቶችን በረቀቀ መንገድ ለማዘዋወር እንዲያመች:: ዛሬ አንዱን፤ ነገ ሌላውን ወዘተ ለመምታት፤ ለማድከምና ተስፋ ለማስቆረጥ አመቻች ሁኔታዎችን ለመፍጠር አስችሏል።

አምስት፤ እያንዳንዱ ክልል ለይስሙላ ራሴን አስተዳድራለሁ በሚል መልክ ከጎሳ የበላዮች ጋር (Ethnic elites) የግል ጥቅም መረብና ሰንሰለት ለመፍጠርና "አዲስ የብሄር የበላዮች ለመፍጠር"። የዛሬይቱ ኢትዮጵያ የመሳፍንት ዘመንን የምትመስለው ለዚህ ነው። የክልል አለቃዎች ከጀርባ በህወሓት በሚሰጣቸው መመሪያና ትእዛዝ መሰረት ሕገ-መንግሥቱን በመጣስ ነዋሪዎችን ከቀያቸው ለማባረር ችለዋል (ጋምቤላ፤ የአሞ ሸለቆ)፤ ዜጎችን በቋንቋ ሰበብ ከሚኖሩበት አስወግደዋል (ቤኒ ሻንጉል ጉሙዝ፤ ጉራ ፈርዳ ወዘተ)።

ስድስት፤ በድምሩ ህብረተሰቡ በጋራ እንዳያስብ፤ በጋራ ችግሮቹን እንዳይፈታ፤ በጋራ መብቱን እንዳያስከብር ለማስገደድ ነው። ስለሆነም፤ ህብረተሰቡ ብሄራዊ የሆነ እንባ ጠባቂና ተከራካሪ የሌለው አድርጎታል። የህወሓት መሪዎች የስልጣን የበላይነትና ቆይታ ዘዴዎችን ሲመረምሩ፤ አናሳ ጎሳ የሚወክል ቡድን አላማውን ስኬታማ ለማድረግ ከፈለገ ኢትዮጵያን በቋንቋ መከፋፈልና ሁሉንም ብሄር/ብሄረሰቦች አናሳ ማድረግ ነበረበት:: በተግባር አሳይቷል። ኢትዮጵያን በጎሳና በቋንቋ መከፋፈል ለራስ አስተዳደር አስፈላጊ ነው የሚል የስልጣን መያዣ አቋራጭ መንገድ በማጤን ነው። ጎሳዊው ፌደራሊዝም ለጭቁን ሕዝቦች የመወሰን ስልጣን ይሰጣል የተባለው ዘይቤ በድርጊት አልተሳካም። የፌደራል መንግሥቱ ዋናው የተፈጥሮ ሃብት፤ የውጭ እርዳታና የባጀት አጠቃቀም መሪ ወሳኝ ነው። ሆኖም፤ የፌደራሉ መንግሥት ተግባሮቹን ስኬታማ ለማድረግ የተገደደው የሕዝቡን ሳይሆን የክልል አለቆችን ጥቅምና ስልጣን በመጠበቅ መሆኑ ይታያል።

አስቀድመን ለማለት የምንፈልገው፤ ሁሉን ብሄር/ብሄረሰቦች፤ እምነቶች ወዘተ የሚያስተናግድ አስተዳደር ለኢትዮጵያ አስፈላጊና ጠቃሚ መሆኑን እናምናለን። ሆኖም፤ ኢትዮጵያን እንደ ደቡብ አፍሪካ ባንቱስታን የመከፋፈል መነሻና መድረሻ በጣም አደገኛ ነው። አወቃቀሩ በጥላቻ እንጂ በመፈላለግ፤ በእኩልነት፤ በሰብአዊ መብት ወሳኝነት፤ በዲሞክራሳዊ ስርአት አስፈላጊነት አይደለም። ይህን በሚገባ ያላጤነው የህወሓት አመራር ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ምሁርና ተቃዋሚ ክፍልም ጭምር ነው። አሁንም ያጤነው አይመስልም። ይህን የምንልበት አንዱ ምክንያት፤ ክልሎች እንደ "ነጻ ሪፑብሊክ፤ የዘመናዊ መሳፍንት ስርዓት" ሆነው ከተመሩ፤ የሚያያይዟቸው የወል እሴቶች እየተናዱ ሄደው ከማይመለሱበት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ። የተዛባ ገቢ፤ ሃብትና ልማት የሚታየው ለዚህ ጭምር ነው። ለኢትዮጵያ ግዛታዊ

አንድነትና ደህንነት፤ ለመላው ሕዝቡ አብሮ ማደግ መሰናክል ይሆናሉ። ደሃ፤ ደካማና ኋላ ቀር ኢትዮጵያ ለውጭ ጠላቶቿ በረከት ትሆናለች በሚል ነው። አንድ ምሳሌ።

የዓባይ ቀናተኞች

በታሪካቸው ኢትዮጵያዊያንን ከሌሎች በቅኝ ከተገዙ አገሮች የሚለያቸው ብዙ ማስረጃዎች አሉ። ዋናው፤ በጎሳና በሃይማኖት ሳይበከሉ፤ ለነጻነታቸውና ለብሄራዊ አንድነታቸው አስፈላጊውን መስዋእት መክፈላቸው ነው። ኢትዮጵያ ኢላማ የሆነችበትና በተከታታይ ለመልማት ያልቻለችበት ዋና የኢኮኖሚ ምክንያት፤ የዓባይ (የናይል) ዋና ምንጭ ወይንም መነሻ መሆኗ ነው። እንደመሆኗ መጠን፤ ከፈርኦኖች ጀምሮ እስከ ጣሊያን ወረራ ድረስ፤ የውጭ ጠላቶች የማይናጋ ብሄራዊ አንድነት፤ የጠነከረና ዘላቂነት ያለው እድገት እንዳይኖራት የውስጥ ደጋፊዎችን በመንከባከብ ሊያፈርሷት እንደነበር ይታወቃል። ተከታታይ ጦርነት የሰው ኃይልና የሃብት ዋጋ ተከፍሎበታል። ግዛታዊ አንደነቷንና የሕዝቧን ማህበራዊ ትሥሥር የማናጋት እቅድ፤ ከውጭ ጠላቶች ጥቅምና ጣልቃ ገብነት፤ ከውስጥ ተባባሪዎች ፍላጎት ጋር ተያይዘው አብረው ሰርተዋል። የአረብ መንግስታት፤ በተከታታይና በተቀነባበረ ዘዴ ኢትዮጵያን አድምተዋታል። የእስልምናን ኃይማኖት ተጠቀመው (Political Islam as an instrument of policy) አረባዊ አላማቸውን ለመቀዳጀት ሞክረዋል። አሁን እየሞከሩ ነው። አገሪቱን ከውድቀት ያዳናት፤ ከኃይማኖትና ከጎሳ በላይ፤ ሕዝቡ አብሮ መሰለፉና ለአገሩ መዋጋቱ ነው። አሁንም የሚፈለገው ተመሳሳይ አቋም ነው። የኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ቤተክርስትያንና የእስልምና ኃይማኖቶች "የተለየና ኢትዮጵያዊ የሆነ" አመጣጥ፤ ባህል፤ የውስጥ አስተዳደር፤ ጎን ለጎን ተከባብሮ የመኖር ልምድ አላቸው። ከሁሉም በላይ የኢትዮጵያን ግዛታዊ አንድነትና ጥቅም ይጋራሉ። ይህ ልምድ መቀጠል አለበት። የኢትዮጵያ የእስልምና ኃይማኖት የአረብ መንንግሥታት ተቀጥላ መሆን የለበትም። በእኛ እምነት ሁለቱ አንጋፋ ኃይማኖቶች ነጻነታቸውን ጠብቀው፤ ተከባብረው፤ ለሃገራቸው ግዛታዊ አንድነት፤ ለሕዝቡ ሉዓላዊነት፤ ፍትህና ዲሞክራሳዊ ስርዓት ቅድሚያ ሰጥተው ጠንካራና ሃብታም ኢትዮጵያን ለመፍጠር ይችላሉ። ገዢው ፓርቲ በኃይማኖት ሙብትና ነጻነት የሚያደርገው አፈና እንዲቆም ተባብሮ ለፍትህ ከመቆም ሌላ አማራጭ እንደሌለ እናምናለን።

አጼ ምኒልክ ኢትዮጵያዊያንን አስተባብረው በአፍሪካ፤ በጥቁር ሕዝቦችና በቅኝ አገዛዝ ስር በነበሩ አገሮች ታይቶ የማይታወቅ ድል ሲቀዳጁ የተከሰተ የማይካድ ነገር አለ። ድልን ለመቀዳጀት አገር ወዳድ የሆነ ብሄራዊ አመራር፤ ለነጻነቱ ለመሞት የተዘጋጅ ሕዝብ ያስፈልጋል። ንጉሱ አንድ ብሄር አሰልፈው የአድዋን ድል አልተጎናጸፉም። ኦሮሞው፤ አማራው፤ ጉራጌው፤ ትግሬው፤ ሶማሌው፤ እስላሙ፤ ክርስትያኑ ወዘተ መስዋእት ሆኗል። ድሉ የሁሉም ነበር። ገበሬው ጎጆውን፤ ቤተሰቡንና፤ እርሻውን ትቶ ወታደር የሆነባት አገር ኢትዮጵያ ናት ለማለት የሚያስደፍሩ ምሳሌዎች አሉ። በተከታታይ፤ አጼ ቴዎድሮስ፤ አጼ ዮሃንስ፤ አጼ ምኒልክና አጼ ኃይለ ሥላሴ ያስመሰከሩት የኢትዮጵያን ብሄራዊነት (Ethiopian nationalism) ተቀዳሚነት ነው። አገር ከሌለ የኃይማኖት ሆነ ሌላ ነጻነት ትርጉም አይኖረውም። አፄ ምኒልክ ያሰለፉት የአንድ ብሄር/ብሄረሰብ ወታደር አልነበረም። ኢትዮጵያዊያን ለአገራቸው በምንም ሳይበገሩ፤ ሳይደለሉ በህይወታቸው ዋጋ የከፈሉት በውጭ እርዳታ ተመክተው አልነበረም። ነጻነታቸውንና ክብራቸውን የጠበቁት በራሳቸው ተማምነው ነው። የሙሶሎኒ ወረራ ለዚህ ዋና ማስረጃ ነው። ይህን የኢትዮጵያውያን ንጹህ ደም የፈሰሰበትን ወረራ አስመልክቶ፤ የቼክ ተወላጁ የሆነው፤ ከኢትዮጵያ አርበኞች ጎን የተዋጋው ጀግና፤ አዶልፍ ፓርለሳክ ያቀረበልን መንፈስ የሚቀሰቅስ፤ <u>የሃበሻ ጀብዱ፤</u> የዚህን ኩሩ ሕዝብ ታሪክና የከፈለውን ዋጋ መስክሮለታል። ከመጽሃፉ የተማርኩት፤ ነጻነትና ፍትህ ዋጋ ሳይከፈል የማይገኙ መሆናቸውን ነው። የሚያመለክቱት አገር ወለድና ፍትሃዊ የሆነ እድገት ከማህብረሰብ ሰንሰለትና (National cohesion) ከነጻነት ጋር የተያያዙ መሆናቸውን ነው። ይኼ ከጎሳ ፌደራሊዝም ይለያል።

አንዳንድ ኢትዮጵያውያንና የውጭ ተመልካቾች፤ እንደዚህ ብሄራዊ አመራርና የህብረተሰብ ትሥስር የነበራት ነጻዋ ኢትዮጵያ ለምን ኢኮኖሚዋን ዘመናዊ ለማድረግ አልቻለችም ይላሉ። ዛሬ ለጥቁር አፍሪካና ለመላው የዓለም ጥቁር አኩሪ አስተዋፆ ያደረገች ኢትዮጵያ እንዴት ወደ ታች ዘግጣ የጎሳኞች የፖለቲካ መጫዎቻ ሆነች የሚሉ ብዙ ናቸው። መጠራጠር የሌለብን፤ የኢትዮጵያ ጠላቶች ለአገሪቱና ለሕዝቧ ሰላም ሰጥተዋት አያውቁም። አሁንም፤ወደፊትም ጣልቃ ገብነታቸውን አያቆሙም። የኢትዮጵያ ታሪክ የጦርነትና የጀግንነት ታሪክ ነው። ሌሎችም ምክንያቶች አሉ። አንዱ የውጭ መንግስታት ጫና ነበር። ሰላምና እርጋታ የሌለበት አገር ከእድገት ላይ ለማተኮር ይቸገራል። የኢትዮጵያ ተከታታይ መንግሥታት ድል ከተጎናጸፉ በኋላ የውጭ ጫናው ቀጥሎባቸው ነበር። የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘመናዊ ህብረተሰብ እንዳይገነባ፤ ከውጭ የሚመጣው ሴራ ማለታችን ነው። አጼ ምኒልክ፤ በኋላም አጼ ኃይለ ሥላሴ፤ አባይን ለመስኖና ለኤሌክትሪክ ሃይል ለመጠቀም ሲሞክሩ ብዙ መሰናክሎች ገጥመዋቸው ሳይሳካ ቀርቷል። ዛሬ ህወሓት እገድበዋለሁ ያለውን "የተሃድሶ ግድብ" ጽንሰ ሃሳብ ያስጠኑት አጼ ኃይለ ሥላሴ ናቸው። የደርግ መንግሥት ህወሓት

ያፈራረሰውን አስደናቂ የጣና በለስ ልማት ጀምሮ ነበር። መፈራረስ ያልነበረበት የኢትዮጵያ ሃብት። በአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ዓባይን ያጠናው የአሜሪካ ተቋም ነበር። ሆኖም፤ የግብጽ መንግስትና ሌሎች እንዳይሰራ ብዙ መሰናክሎች ፈጥረዋል። ዓለም ባንክ ግድቡ ቢሰራ ብድር አልሰጥም ብሎ ነበር። ሊካድ የማይችለው፤ እነዚህ መንግስታት ብሄራዊ/ኢትዮጵያዊ ነበሩ። ለአጭር  ጊዜ ጥቅም ሲሉ ለማንም የውጭ መንግስት የአገርን ጥቅም አላስረከቡም። ስለሆነም፤ በተከታታይ አገርን ከውጭ ጠላቶች የመጠበቅ ተቀዳሚነት የኢትዮጵያን ፈጣን እድገት ጎድተውታል። የአጼ ምኒልክ ድል የኢትዮጵያን ታሪክ ሂደት የተከተለ ነው። ይህን ስንል፤ በኢትዮጵያ ውስጥ በብሄር ሆነ በሃይማኖት ችግር አልነበረም ማለት አይደለም። ችግር ያልገጠመው አገር ካለ ፈልገን ልናገኝ አልቻልንም። የኢትዮጵያ ታሪክ እንደሌሎች ረጅም ታሪክ ያላቸው አገሮች ውጣ ውረድና እልቂት ነበረበት። አሜሪካኖች ከወረራ በፊት ነዋሪዎች የሆኑትን ህንዶችን አጥፍተዋል። ጥቁሮችን በባርነት ገዝተዋል። በእርስ በእርስ ጦርነት ተላልቀዋል። ፕሬዘደንት ሊንኮን የመራው ጦርነት ለስድስት መቶ ሺህ ነጮች መጥፊያ ምክንያት ሆኗል። ይህ ሁሉ ሆኖ አሜሪካኖች እርስ በእርሳቸው ሲናከሱ፤ መጥፎ ታሪካቸውን ለማናጋት ሲጠቀሙበት፤ መሪዎቻቸውን ሃውልት ሰርተው ሲያዋርዱ አናይም።

የኢትዮጵያ ታሪክና የሕዝቧ ጀብዱ የሚያኮራ ሆኖ ሳለ፤ ሻቢያ፤ ህወሓትና እነሱ ሆነ ብለው ለጎሰኝነት ፖለቲካ የፈጠሯቸው ስብስቦች፤ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አኩሪ የሆነውን ታሪክ  አሳፋሪ ነው ብለው ሰርዘውታል። መሰረዛቸው ለአሁኑ የጎሰኝነት አገዛዝ መሰረት ሆኗል። ለኢትዮጵያ መጠቂያ በር ከፍቷል። ታሪክ የሌለው ሕዝብ ታሪክ ለመስራት እንደማይችል ታስቦ የተደነገገ ይመስላል። የዚህን ክስተት የእድገት ጫናነት በሚቀጥለው ምእራፍ የተፈጥሮ ሃብት ምዝበራን አስመልክቼ አቅርቤዋለሁ። ጣሊያኖች ኢትዮጵያን ለመከፋፈል፤ ለማዳከምና ዘመናዊነቷን ለመግታት የተጠቀሙበት ዋና ዘዴ፤ ህብረተሰቡን በጎሳና በሃይማኖት መከፋፈል ነው። ያጤኑት፤ በተለይ የምሁሩን ክፍል ሃላፊነት የጎደለው ነው ተብሎ የሚያስወቅሰው--ለሃቅና ለአገር ታሪክ አለመቆም--ዛሬ፤ በጎሰኝነት የተከፋፈለች ኢትዮጵያ አንድነቷን ለመጠበቅ የማትችል መሆኗን፤ በጎሳ በመከፋፈሏ፤ የተፈጥሮ ሃብቷን ተጠቅማ አገር ወለድ የሆነ ዘመናዊ ኢኮኖሚ ለመገንባት የማትችል መሆኗን ለማስተማር ፈቃደኛነትና ብቁነት አለማሳየቱ የታሪክ ተጠያቂ አድርጎታል። የጎሰኝነት አገዛዝ እንዲሁ ከሰማይ የወረደ አይደለም። ሂደት አለው። ደጋፊዎች ነበሩት። አሁንም አሉት። ዋናው ምንጭ ከውጭ የመጣ ነው። ጣሊያኖች ኢትዮጵያን የወረሩበት ዋና ምክንያት ለማሰልጠን አልነበረም። ማንም ቅኝ ገዢ ማንንም አላሰለጠነም። ዋናው አላማ የኢኮኖሚ ቁጥጥር ነበር። “ሙሶሊኒ ኢትዮጵያን የፈለገበት ዋና ምክንያት፤ የተፈጥሮ ሃብቷን ለመቆጣጠር። የምግብ ዋስትና ለማግኘት። የጣሊያኖች መስፈሪያ ለማድረግ ነበር። (Mussolini hoped to develop Ethiopia as a granary, for Italy, a source of raw materials, and a colony of settlement).” 19/

እንደማንኛውም ወራሪ፤ ጣሊያኖች ኢትዮጵያን ለመቆጣጠርና ግባቸውን በስራ ለመተርጎም፤ መንገድ፤ ድልድይና ሌላ መሰረተ ልማት ማስፋፋት ነበረባቸው። የዚህ አይነት መሰረተ ልማት ወታደር በፍጥነት ለማጓጓዝ፤ ሕዝቡን ለመቆጣጠር አስችሏል። እድገቱ ሊለውጠው ያልቻለው የሕዝቡን አልገዛም ባይነት ነበር። በነጻነት የኖረ ኩሩ ህዝብ አልገዛም ሲል ሌላ ዘዴ መፈለግ ግዴታ ሆነ። የጎሳ አቀራረጽ እቅድ መሰረተ ሃሳብ የመጣው ከዚህና የኢትዮጵያ ግራ ክንፍ ተውሶ ካዛመተው የብሄር/ብሄረሰብና ሕዝቦች ነጻነት እስከ መገንጠል ድረስ የሚለው ፍልስፍና ነው። ልክ እንደ ደቡብ አፍሪካ ባንቱስታን በጎሳ መከፋፈል። የኢትዮጵያ ግራ ክንፍ ሌሶና የተባለውን የጣሊያን ተወላጅ በመጥቀስ፤ “ኢትዮጵያ የሕዝቦች ሙዚየም (Ethiopia is a museum of peoples) ናት” ያሉት የተቀዳው ከጣሊያን ቅኝ ገዥዎች የጽንሰ ሃሳብ መሪዎች ነው። ብዙ ብሄር/ብሄረሰቦች እንዳሉባት አይካድም። ሆኖም፤ የተለያዩ ብሄር/ብሄረሰቦች አብረው መኖራቸው የማይታረቅ ግንኙነት ፈጥሯል። አንዱ ጨቋኝ፤ ሌላው ተጨቋኝ። አንዱ ቅኝ ገዥ ሌላው ተገዥ። አንዱ መሪ ሌላው ተመሪ ነው የሚለውን መሰረተ ሃሳብ ለግባቸው የተጠቀሙበት ጣሊያኖች ናቸው። ሻቢያና ህወሓት፤ሌሎች የጎሳ ስብስቦችም በአቀንቃኝነትና በአድር ባይነት፤ ለግል ወይንም ለጠባብ ጥቅም አውለውታል። ለምሳሌ፤ አማራ ትግራይን በቅኝ ገዢነት ሃብቷን አሟጧል። ደሃ አድርጓታል። ሕዝቡን ለስደት ዳርጎታል ተብሏል። የትግራይ ብሄረሰብ ገዢ እንደነበረ ተክዷል (አክሱም) ። ትግራይ የኢትዮጵያ አካል እንደነበረች፤ አሁንም እንደሆነች ተክዷል። ታላቋን የትግራይ ሪፑብሊክ እናቋቁማለን የሚለው ሃሳብ የመነጨው ከዚህ ነው። ይህ ሂደት፤ የጎሳ ፖለቲካ አገዛዝን የጎሰኛ እሴቶች መገልገያ መሰረት ሆኗል። ኤርትራዊው ጆርዳን ገብረመድህን፤ ኢትዮጵያን ለማፈራረስ፤ የኤርትራን ነጻነት በእውቀት ለመደገፍ፤ “ስለ ኤርትራ ሬፈረንደም” በ 1993 በኢትዮጵያ ሪቪው የጻፈው እንዲህ ይላል። “አጼ ምኒልክና አጼ ኃይለ ሥላሴ በአሸዋ ላይ የገነቡት የሸዋ-አማራ ግዛት፤ በጭቁን ሕዝቦች አመጽ ይፈረካከሳል። ነጻዋ ኤርትራ ታብባለች”። የጭቁን ሕዝቦች ነጻ አውጭዎች ብሎ የሰየማቸው የሚደግፋቸውን ሻቢያንና ህወሓትን ነበር። የተመኘው ደርሶለታል። የኤርትራ ኤርትራ በታሪኳ የኢትዮጵያ አካል ነች። የኢትዮጵያ ታሪክ ከኤርትራ ታሪክ ተለይቶ አያውቅም ነበር። ህወሓት አመቻችቶ ኤርትራን ከናት አግሯ ሲያስገነጥል፤ ሕዝብ ጠባብ ጎሰኞችን አልደገፈም። ድምፁ አልተጠየቀም። ጠባብ ጎሰኞች ስልጣን የያዙት የኤርትራና የኢትዮጵያ ሕዝብ ድጋፍ ስለሰጡ አይደለም። መረሳት

የሌለበት የወንድማማቾች ግጭትና መከፋፈል አሁን ላለው ጎሳ-ተኮር ፌደራሊዝም የኤርትርያና የትግራይ ምሁራን ከፍተኛ አስተወጽኦ ማድረጋቸው ነው። የጠባብ ጎሰኞች የበላይነትና የመገንጠል ፖለቲካ ግብ ግብ እየጠነከረ የሄደው ህወሓት ኤርትራን እንድትገነጠል አመቻች ስለሆነ ነው።

የጣሊያን መንግስት የኢትዮጵያን ሕዝብ ከፋፍሎ ለመግዛት የተጠቀመባቸው መስፈርቶች ነበሩ። ከእነዚህ ዋናዎቹ፤ የሃይማኖት (ክርስቲያንና እስላም)፤ የቋንቋና የመልክአ ምድር፤ በተለይ የጎሳ ልዩነቶች ናቸው። ቅኝ ገዢዎች፤ "የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚሻለው አስተዳደር በጎሳ (አሁን ክልል) ወይንስ በኢኮኖሚና በንግድ" የሚለው ጥያቄ ጣሊያኖችን አከራክሯቸው ነበር። በጎሳና በመልክአ ምድር አስተዳደር ቀይሶ፤ የአማራውን ክልል ለይቶ በሚሊታሪ እንዲተዳደር አድርጎት ነበር። ለምን እንደሆነ አንባቢው ያውቀዋል የሚል ግምት አለኝ። የሸዋ ሆነ ሌላው አማራው ከኢትዮጵያ ብሄራዊ አንድነት ጋር ስለተያያዘ፡ አልገዛም ባይ ስለነበር። በየቦታው ለጣሊያኖችን ሰላም ስለነሳ ነው። አማራውን በሃይል መቆጣጠር፤ ስነልቦናውን መቅሰፍና ብሄራዊነቱን፤ አገር ወዳድነቱን ማዳከም ለቅኝ ገዢው ሃይል ጠቃሚ ነበር። ህወሓት አሁን ከሚያደርገው የተለየ አይደለም። ዘዴው እንዳልሰራ የጣሊያን ጸሃፊዎች መዝግበውታል። "የኢትዮጵያ ሁኔታ ያሳየው፤ ኢትዮጵያን በጎሳ/በብሄር መከፋፈል ጉዳቱ ከፍተኛ መሆኑን ነው።" ኢትዮጵያ የሚለው መሰረተ ሃሳብ ዳኘ ማለት ነው። በጎሳ የመከፋፈሉ ጉዳት አመዝኗል የሚለው አስተሳሰብ የመጣው፤ ሕዝቡ ለከፋፍለህ ግዛው አመች ሆኖ ስላልተገኘ ነው። ለዚህ አስተዋጽኦ ያደረጉት ከሁሉም ብሄር/ብሄረሰቦች ይታገሉ የነበሩ አገር ወዳድ አርበኞች ናቸው። አንገዛም ብለው ትግላቸውን በየ አቅጣጫው ስለቀጠሉ ብቻ ነው። ይህ፤ ለአሁኑ ትውልድ ትምህርት አለው-- "የጣሊያን ቅኝ ገዦች ያልገባቸው፤ ማንኛውንም መስዋእት ቢከፍሉ፤ ኢትዮጵያውያን የአገራቸውን ጥቅም ለማስከበር አስፈላጊውን መስዋእት በመክፈል በሚያኮራ ደረጃ አሳይተዋል…ጣሊያኖች የኢትዮጵያ ጀግንነት ታሪክ፤ ባህልና ልምድ ፈጽሞ አልገባቸውም ነበር።" 20/

ከዚህ ላይ ማስታወስ ያለብን አንድ ነጥብ አለ። ጣሊያኖች በአማራና በኦሮሞ ሕዝብ ያለውን ልዩነት ለመጠቀም ያልሞከሩት ነገር አልነበረም። የኦሮሞ ሕዝብ ይህን የዘር መከፋፈል ዘዴ አውቆ ነበር። የፈለገው ጠላትን አስወግዶ በእኩልነት የተመሰረተ አገዛዝን መመስረት ነበር፤ አሁንም ነው። ዛሬ፤ ህወሓት፤ በአማራውና በኦሮሞው መካከል የእርስ በእርስ ግጭት ሲጭር፤ የኦሮሞው ህብረተሰብ የህወሓትን የበላይነት ይመርጣል የሚል-- ልክ ጣሊያኖች የተጠቀሙበት "የከፋፍለህ ግዛው"--ስልት ነው። ኦሮሞው ለአማራ ጥላቻ አለው የሚለው ሰው ሰራሽ፤ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ነው። ይህን ስል፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ፤ የብሄር/ብሄረሰብና የሃይማኖት ልዩነቶች፤ በደሎች፤ የሉም ማለቴ አይደለም። አሉ። የሚፈቱት በጎሰኝነት ፖለቲካና በጥላቻ ሳይሆን በፍትህ፤ በውይይት፤ በእውነተኛ እኩልነት ነው። የጣሊያን ሆነ የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት የመረጡት ፍትሃዊ ለውጥን አይደለም። የጣሊያኖች የጎሳ አስተዳደር የተመሰረተው ብሄራዊ ስሜትን ለመደምሰስ ነበር። ጸረ- አማራ የሆነ ፖሊሲ ከስራ ላይ የዋለው ይህን ብሄረሰብ በሌሎች ለማስጠላት ብቻ አይደለም። የአማራውን ኢትዮጵያዊነት ከስሩ ለመመንጠር ነበር። ጣሊያን በዚህ አላቆመም። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንና በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ያደረገው መከፋፈል የህብረተሰቡን አንድነት ለማጥፋት የታሰበ ነበር። "ጣሊያኖች የእስልምና ተከታዮችን በበለጠ ያምኑ ነበር። በሃይማኖታቸው ጣልቃ አይገቡም ነበር። በአንጻሩ፤ ጣሊያኖች የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ለመቆጣጠር ሞክረዋል። ነጻና ኢትዮጵያዊ ስለሆነ። ሃይማኖቱን ከአማራና ከኢትዮጵያዊነት ጋር አያይዘው ያዩት ነበር።" አርበኞት በግራዚያኒ ላይ የግድያ ሙከራ ካደረጉ በኋላ የሆነው እልቂት ያሳየው የጣሊያን ዋና ኢላማ አገር ወዳድ የሆኑትን፤ ጾታ፤ ጎሳና ሃይማኖት ሳይለይ ተተኪ አገር ወዳድ ትውልድ እንዲጠፋ አድርጎ መቅጣት የሚል ነበር። በዚህ ስልት፤ ፋሺስቶቹ "ቆራጡና ኩሩው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመጨረሻ ጊዜ የሚንበረከከው የማይረሳው እልቂት ሲፈጸምበት ብቻ ነው" አሉ። ሰላማዊውን ሕዝብ ጨምረው እልቂት አደረሱበት። የመጀመሪያው የብሄር ማጥፋት ዘመቻ (Ethnic Cleansing) የተካሄደው በጣሊያኖች ነበር። ሆኖም፤ የአርበኛው ትግል በዚህ አላቆመም። "ግድያው ቢካሄድም፤ ኢትዮጵያዊያን በቁርጠኛነትና በድፍረት(determination and courage) በአንድ ላይ ሆነው የኢትዮጵያን ነጻነት ጠብቀው ለተተኪ ትውልድ ለማስተላለፍ አስችሏቸዋል." 21/

ጣሊያን ለምን ከዋና ዋና ተቋሞች ላይ አተኮረ?

በህይወትና በቁሳቁስ ሲታሰብ፤ በተከታታይ ከፍተኛ ዋጋ የተከፈለባትን የጥቁር ሕዝቦች የነጻነት አርአያ፤ ኢትዮጵያ፤ ጠባብና ትምክህተኛ ጎሰኞች ወይንም ብሄርተኞች--ከዚህ በኋላ ጠባብ ጎሰኛ የሚለውን ቃል እጠቀማለሁ--ለምን አፈራረሷት ወይንም ከስሯ እያፈራረሷት ነው? ይህ፤ ከኢትዮጵያዊነት/ ከብሄራዊነት ወደ ጠባብ ጎሰኝነት ያመራ ፖለቲካ ከየት መጣ? ለምን? ማን አስተዋፆ አድርጓል? የደህንነት፤ የእድገት ጉዳቱስ ምንድን ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ለተከታታይ ትውልድ ማቅረብ ግዴታ ነው። በጠባብ ጎሰኝነት የተጸነሰውና በስራ የተተረጎመው በጣሊያን ወራሪዎች

መሆኑን ገልጸናል። ጉዳቱን አሳይተናል። በፋሽስት ወረራ ብቻ፤ የአንድ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ህይወት ጠፍቷል። በግራዚያኒ ላይ በተደረገው የነፍስ ግድያ ሙከራ ብቻ፤ በሶስት ቀኖች ሰላሳ ሽህ ህይወት ጠፍቷል። ፋሽስቶች ያጠፉት ህይወት ብቻ አልነበረም። ኢላማቸው ተቋሞችን ማጥፋት ነበር። ሁለት ሽህ ቤተክርስቲያኖች፤ ግማሽ ሚሊዮን ቤቶች አቃጥለዋል። የፈለጉት የኢትዮጵያን መታወቂያ ሁሉ ማጥፋት ነበር። የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስትያን በተለያዩ አስጨናቂ ወቅቶች ብሄራዊ ግዴታዋን ተወጥታለች። ጣልያን ሊያጠፋት አልቻለም ነበር። ይህችን የአገር መታወቂያ በኃሳ በመከፋፈል የማጥፋት ዘመቻ፤ የብሄር/ብሄረሰብ ልዩነቶች የማይታረቁ ናቸው በሚል በተሳሳተ ጽንሰ-ሃሳብ ለሻቢያና ለህወሓት መሳሪያ እንዲሆን ያደረገው የግራ ክንፍ ነኝ ባዩ፤ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ጭምር መሆኑን ብዙ የኢትዮጵያ ደራሲዎች ተችተውታል።

ኢትዮጵያ ዋርካ ናት

ምስሶው በብል የተበላ ቤት ይረርሳል። ሙስና እንደ ብል ወይንም እንደ ተስቦ በሽታ ነው። አገርን ያፈርሳል፤ ህብረተሰብን ያደከማል፤ ያደሄያል። ደራሲው ጎንደር ተማሪ በነበረበት ጊዜ፤ አንድ ትልቅ ዋርካ እንደ ሃውልት መሰብሰቢያና መገናኛ መሆኑን አይቶ ይገረም ነበር። ከትውልድ ትውልድ የተላለፈ፤ መንግሥት ቢቀየር የማይነካ ምስል ነበር። ዋርካው ኢትዮጵያ የማትበገር ሆና መቆየቷን ያስታውሰናል። ዋርካው ቅርንጫፎች ነበሩት። የኢትዮጵያ ብሄር/ብሄረሰቦች ዋርካው እንደ ቤት ሆኖ የሚደግፋቸው ቅርንጫፎች ናቸው። አንዱ አጭር። ሌላው ረጅም ሊሆን ይችላል። ለዋርካው ልዩነት የለውም። ዋርካው ለዘላለም ይቆያል። ለቅርንጫፎቹ ሁሉ መጠጊያ ሆኖ ያገለግላል። ዋርካው እንክብካቤ ካላገኘ ለቅርንጫፎቹ ህልውና ያሰጋል ማለት ነው። ዛሬ የኢትዮጵያ "ዋርካነት" በፈተና ላይ ይገኛል። ዋርካው በምስጥ እየተቦረቦረ ጠውልጎ ይታያል። ኢትዮጵያ የገጠማትን፤ ከጠባብ ጎሰኛነት አገዛዝ የመነጨ አስጊ ሁኔታ ከውጭና ከውስጥ ከመጣ የመለያየት ትኩረት መለየት አይቻልም። ባጭሩ፤ የኢትዮጵያ ምሁርና "ግራ ክንፍ" ፖለቲካ እንቅስቃሴ፤ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ፤ ለጠባብ ጎሰኛነት ፖለቲካ አስተዋፆ አድርጓል። ኢትዮጵያ ለደረሰባት አደጋ ሁሉም ተጠያቂ ነው ለማለት ይቻላል። ሁላችን ተጠያቂ ከሆንን መፍትሄውንም በጋራ መሻት ይኖርብናል። የመጀመሪያው ተግባር ኢትዮጵያ የምትባል አገር ዘላለም መኖር አለባት ብለን ደፍረን በአንድ ላይ መነሳት አለብን። ገሪቱ ከጠፋች ማንም ሰላም አያገኝም። የማንም የወደፊት ህይወት (ከመሰደድ ውጭ) አስተማማኝ አይሆንም። ሆኖም፤ የህወሓት አመራር የፈጸመውን ግፍ በጥልቀት ካላወቅንና ካላስተናገድን መፍትሄውን ለማቅረብ አንችልም።

ምን ሰለባ ተደረገ፤አስር የፖሊሲ ግድፈቶች

የህወሓት የጠባብ ጎሰኛነትን ፖለቲካ ሰለባ ወይንም ብሄራዊ ጉዳት ጥልቀት በሚከተሉት አስር ጸረ-ኢትዮጵያ የፖሊሲ፤ የተቋምና የምዋቅር ለውጦች እናሳያለን።

1. የመጀመሪያው ታሪክ የሚፈርደው የህልውናና የኢኮኖሚ እድገት ጉዳት ያመጣው፤ ሻቢያና ህወሓት ተመሳጥረው፤ የኤርትራና የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምጽ ሳይሰጥበት፤ ኤርትራ ከእናት አገሯ እንድትገነጠል ማድረጋቸው። የኢትዮጵያን የባህር በር መዝጋታቸው ነው። ይህ የኢትዮጵያ አቢይ ጠላቶች ይፈልጉት የነበረ አላማ ነው። ግብጾች፤ ሳውዲዎችና ሌሎች በቀይ ባህርና በአባይ ላይ ታላቅ ሚና እንዲኖራቸው ያመቻቸው የሻቢያና የህወሓት የበላይ አመራር ነው። ኢትዮጵያ ወደብ አልባ በመሆኗ፤ ለምትሸምተውና ለምትልከው እቃ ከአራት እስከ አምስት እጅ በበለጠ ትከፍላለች። ምንም አይነት ወደብ አልባ አማራጭ (ጅቡቲ፤ ኬንያ፤ ሱዳን) ግድፈቱን ሊያሟላው አይችልም። ከፈርኦኖች ዘመን ጀምሮ፤ ዓባይን ለመቆጣጠር ያልተደረገ ሴራ የለም። ግብጾች፤ ቱርኮች፤ ጣሊያኖች፤ እንግሊዞች፤ ፈረንሳዮችና ሌሎች በየጊዜው የኢትዮጵያን ጥቅም ለመጉዳት ሞክረዋል። ይህን ያደረጉት የውስጥ ተባባሪዎች በመፈለግ፤ የገንዘብ፤ የመሳሪያ፤ የዲፕሎማሲ ድጋፍ በመስጠት ነው። ይህ ሁሉ ሲሆን ኢትዮጵያ ከራሷ አገር ወዳዶችና ሕዝብ ውጭ አንድም ደጋፊ እልነበራትም። ሻቢያና ህወሓት ግባቸውን ለመቀዳጀት የቻሉት በራሳቸው አቅም ብቻ አይደለም። ከውጭ በተደረገላቸው ድጋፍ ጭምር ነው። አገር ወዳዶችን በመጨፍጨፍ፤ የደርግ አመራር ለድክመቱና ለክፍተቱ አስተዋፆ አድርጓል።

2. አፍሪካዊውንና ሌሎች የጥቁር ሕዝቦች በሙሉ ያደንቁት የነበረው የኢትዮጵያ ታሪክ ሂደት የልዩ ልዩ ብሄር/ብሄረሰቦችና ሃይማኖቶች መሆኑን፤ ኢትዮጵያውያን ከሁሉ በላይ በኢትዮጵያዊነታቸው እንደሚለዩና እንደሚታወቁ፤ ለነጻነታቸው ተባብረው መስዋእት እንደከፈሉ ነበር። የህወሓት መስራቾች ይህን ብሄራዊ ቅርስ ደምሥሰውታል። ዋርካው እየፈረሰ ነው። በምትኩ፤ ጠባብ ጎሰኛነት መመሪያ እንዲሆን በህብረተሰቡ ላይ ጭነውብታል። ከሁሉ በላይ ለኢትዮጵያ ደህንነትና ፍትሃዊ እድገት ጫና ያደረገው ይህ ከአፓርታይድ የማይለይ አገዛዝ ነው። በማንኛውም አገር፤ ሃላፊነት የሚሰማው አመራር፤ በህግ "ዋርካውን ለማፈራረስና" ለመገንጠል ይቻላል ብሎ

መበታተንን እንደ መመሪያ በህገመንግስቱ አያስገባም። ታሪኩን የካደ፤ የወደፊቱን ጠንካራነት ለመመስረት ያልፈለገ ካልሆነ በስተቀር። በሃገሩ መናድ ላይ፤ በመላው ሕብረተሰብ ሰብ አዊ መብት ላይ ተከታታይ አፈና የሚያደርግ ገዢ ፓርቲ አገርና ሕዝብ ወዳድ ነው ለማለት አስቸጋሪ የሚሆነው ለዚህ ነው። የህወሓት አመራር ለራሱ ጥቅምና አገዛዝ ዘላቂነት ብሎ የኢትዮጵያን ዘላቂነት ለአደጋ ዳርጎታል። ጠባብ ጎሰኞነት ስለሚገዛው፤ ህወሓት በአዲስ አበባና ሌሎች ከተሞች "የእንግሊዝኛ አማርኛ" ስር እንዲሰድ እያደረገ ነው። ምክንያቱም፤ አማርኛን ከአማራ ብሄረሰብ ጋር ስላያያዘውና ጉዳቱን ስላላወቀው። ለምሳሌ፤ የላሊበላ "ሬስቶራንት፤ የሜሪ ስፓ" የሚባሉ ስሞች በየቦታው ይታያሉ። ቻይና የማይደረገው ኢትዮጵያ ተራ ነገር ሆኗል። እነዚህን፤ የላሊበላ ምግብ ቤት። የማሪያም መጸዳጃ ወይንም መዝናኛ ብሎ ለመሰየም ይቻላል። ለአገር ባህል የሚቆረቆር አመራር ፈቃድ ሲሰጥ፤ የአማርኛ፤ የኦሮሞኛ ወይንም ሌላ የአገር ቋንቋ መለያ ተጠቀሙ ሊል ይችል ነበር። ወላጆች ልጆቻቸውን በራሳቸው ቋንቋ ከመጠቀም ይልቅ፤ እንግሊዝኛ ተናገሩ ብለው ሲያስገድዱ፤ ኢትዮጵያዊ መለያ አስፈላጊ አይደለም የሚል መልእክት እንደሚያስተምሩ ዘንግተውታል። ጥገኛነት በራስ ባህልና ታሪክ ካለመመካትም የሚመጣ ነው። የሚያዘጋጇቸው ለስደት ይመስላል።

3. የህወሓት ጠባብ ጎሰኞች የክልል አስተዳደርን መስርተው፤ 'በሌለ ዲሞክራሲ' የፖለቲካ የበላይነትን ይዘዋል። <u>የፖለቲካ ስልጣኑን ለኢኮኖሚ የበላይነት</u> መሳሪያ አድርገውታል። በኢትዮጵያ ታሪክ ብቻ ሳይሆን፤ በሌሎች አፍሪካ አገሮች ያልታየ ከአድልዎና ከሙስና ጋር የተያያዘ ምዝበራ እያካሄድባት ነው። በማንኛውም የኢኮኖሚ ዘርፍ የህወሓት ባለስጣናት፤ ታማኞችና የውጭ ኢንቬስተሮች የበላይነት ያልያዙበት ክፍል የለም። የሚዘገንነው የህወሓት አለቆች የዘረጉት የጠባብ ጎሰኛ ምዝበራ አይን ያወጣ የገቢ፤ የባለ ጠጋነት፤ የሃብትና የኑሮ ልዩነቶችን ፈጥሯል። "ታማኝና ምርጥ የትግራይ ተዎላጆች" የዚህ ምዝበራ ዋና ተጠቃሚዎች ሆነዋል። በግልጽ እየታየ የሄደው የጉቦ፤ የሙስና፤ የአድልዎ ባህል ስርአቱ በህግ የማይዳኝ መሆኑን ያሳያል። በኢትዮጵያ አየር መንገድ መብት ሆኖ ቴኬት የገዛው ሰው አውሮፕላን ሞልቷል ተብሎ ባለስልጣን ወይንም የባለስልጣን ዘመድ ለመጓዝ የፖለቲካ ግንኙነት ተጠቃሚ መሆን፤ የአገልግሎት ዋጋዎች በፖለቲካ መወሰናቸው፤ ህግ ዋጋ ቢስ መሆኑን ያሳያሉ። አገዛዙ በአድልዎና በሙስና ከቁንጮው ስለገማ፤ ማንኛውም ግለሰብ እኔም በሕግ አልገዛም ቢል አያስደንቅም። ሕግን የማያከብር መንግሥት ሌሎች ሕጉን እንዲያከብሩለት ለማድረግ ይሞክራል። የሚከፈለኝን ዋጋ የምወስነው እኔው ነኝ ቢል አያስደንቅም። ሕግ የማያከብር መንግሥት፤ ሌሎች ህግ እንዲያከበሩ ሊጠይቅ አይችልም። ስለዚህ፤ አገዛዙ 'በማፊያ" የሚመራ መስሏል። ማፊያ ሕግ አያከብርም፤ የሕግ የበላይነትን አይቀበልም።

4. ለጭቁን ብሄር/ብሄረሰቦች ዲሞክራሳዊ መብትና እኩልነት ቆሜያለሁ የሚለው የጠባብ ጎሰኛ ስርአት የሁሉንም ብሄር/ብሄረሰቦች <u>ሰብአዊ መብቶች</u> በተከታታይ ጥሷል። በዛሬይቷ ኢትዮጵያ እንኳን በሃገር ቤት የሚኖር/ይምትኖር ተቃዋሚ፤ በውጭ አገሮች የሚኖሩ የፍትህ ታጋዮች አስተማማኝ ህይወት አይኖሩም። በሰው ህይወት ላይ ለህሊና የሚዘገንን ወንጀል ፈጽሟል። በአኟክ፤ በሶማሌ፤ በኦሮሞ፤ በአማራ፤ በጉራጌ፤ በኦሞ ሸለቆ ሕዝብ ላይ የተካሄደውና የሚካሄደው ወንጀል በዓለም ፍርድ ቤቶች የሚያስጠይቅ ሆኗል። ማቆሚያ ያለው አይመስልም። ጠባብ ጎሰኛው ቡድን ይህን የሚያደርገው፤ ጠባብ ብሄርተኛነትን፤ ፓርቲን፤ መንግስትንና ተቋሞችን በማቆላለፍ ነው። የፌደራል ፖሊስ፤ የመከላከያ፤ የስለላ፤ የምርጫ፤ የፍርድ፤ የጉምሩክ፤ የውጭ ጉዳይ ተቋሞች ሁሉ በትግራይ ተዎላጆች እጅ የተያዙበት ዋና ምክንያት ለፖለቲካ የበላይነትና ለምዝበራ እንዲያመቹ ነው። በJuly 14, 2014, የእንግሊዝ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አንድ የጋምቤላ ተወላጅ መብቴ ተረግጧል፤ ወገኖቸ ከቀያቸው ተባረዋል፤ ተደብድበናል፤ ተዋርደናል፤ መሬታችን ተቀምተናል፤ ተሰደናል፤ የሚገባን ካሳ አልተከፈለንም፤ ለዚህ የሰብአዊ መብት ጥሰት ዓለም ባንክ፤ የአሜሪካ ተራድዖ ድርጂት፤ የኢንግሊዙ የውጭ ልማት ርዳታ ተቋም ተባብረዋል። የራሳቸውን መመርሪያ ጥሰዋል በሚል ክስ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ክሱን ተቀብሎታል። የታወቀው የስብአዊ መብት ጠበቃ እንዲህ ብሏል። "The UK High Court rulng is just a first step, but it should be a wake-up call for the government of the UK and other donors that they need rigorous monitoring to make sure their development programs are upholding their commitments to human rights." ይኼ የመጀመሪያ እንጂ የመጨረሻ አይደለም የሚለውን እንቀበላለን። በቀጥታ ለገዢው ፓርቲ የሚሰጥ እርዳታ ድህነትን ሊያጠፋ አይችልም፤ ለድሃው ህይወት ለዋጭ ግብአቶችን ለመስጠት ስላልቻለ። ቁጥጥር ስለሌለበት ያጠናከረው አፈናን ነው። የጥቂቶችን ኪስ መሙላትን ነው። እነደ ኢትዮጵያ እርዳታ በአድልዎ የሚካሄድበት አገር ያለ አይመስለንም።

5. ጠባብ ጎሰኛው አመራር፤ በረቀቀ ሁኔታ፤ <u>የኢትዮጵያን የተፈጥሮ ሃብት ከኢትዮጵያ ሕዝብ</u> ወደ <u>ፓርቲው፤ ወደ ፈጠራቸው ተባባሪ ድርጅቶች</u> ማዘዋወሩን ቀጥሏል። ለምሳሌ፤ ኤፈርትና ጉና፤ ወደ ታማኝ ደጋፊዎችና ወደ ውጭ ኢንቬስተሮች አዘዋውሯል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በራሱ አገር በተፈጥሮ ሃብቱ ላይ ማዘዙ በሙሉ አቁሟል። በአዲስ አበባ ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን ለብዙ አመታት ከያዟቸው መሬታቸውና ከቤታቸው እንዲወጡና ለኢንቬስተሮች ቦታ

እንዲለቁ ተደርጓል። አይን ያወጣ በደል መሆኑን መካድ አይቻልም። በጋምቤላ ለሳውዲ ስታር (የሳውዲዎች) ፤ ለካሩቱሪ (የህንዶች)፤ በዋልድባ ለጎሰኛው ፓርቲና ለምርጥ የትግራይ ተወላጆች ወይንም ለክልሉ መሬት ይለቀቅ ሲል፤ የኢትዮጵያዊያንን ባለቤትነት ለማጥፋት ነው። ይህ ከኢኮኖሚ ወንጀል የማይለይ ድርጊት ነው። ዜግነትን፤ ኢትዮጵያዊነትን በሙሉ ይገፋል። የሚደረገው "በእድገት" ስም ነው። ጥያቄው ለማን እድገት። ለማን ጥቅም የሚለው ነው።

6. ጠባብ ጎሰኛነት <u>ለወጣቱ ትውልድ የስራና የመስራት</u> እድል አልፈጠረለትም። ስለሚራብ፤ ስራ ስለሌለው፤ ወገኖቹ በረሃብ ሲሰቃዩ ስለሚያዩ፤ በአገራቸው ያላቸውን ኩራት ቀንሶባቸዋል። በመንግስቱ ምንም እምነት የላቸውም። ይባስ ብሎ፤ ህወሓትና ደጋፊዎቹ ህጻናትን፤ ልጃገረዶችንና ሌላውን ወጣት ትውልድ "እንደ ሸቀጥ" ወደ ውጭ እንዲጎርፍ፤ መልሶ የውጭ ምንዛሬ እንዲልክ አስገድደውታል። በአሁኑ ወጣት ትውልድ የሚደረገው "ንግድ" የመሰለ ፖሊሲ የምዝበራን እውነተኛ ኢ-ሰብአዊይነት ያሳያል። አመራሩ ለአዲሱ ትውልድ ህይወት፤ ደህንነት፤ በአገሩ ኮርቶና ሰርቶ እንዳይኖር ዋና ማነቆ ሁኗል። ኢትዮጵያ ዋና ወደውጭ የምትልከው የሰው ሃይል ነው። ስርአቱ እስካለ ድረስ፤ ይህ ጎርፍ ሊያቆም አይችልም። ኢትዮጵያ የተማረ ሰው እጥረት አለባት ተብሎ ሲነገር አብሮ የማይነገረው ለእጥረቱ የህወሓት አመራር ፖሊሲ ምክንያት መሆኑ ነው። ሰባ አምስት በሙቶ የሚሆነው የጤና ጥበቃ ትምህርትና ልምድ ያለው ይሰደዳል። በዚህ ደረጃ <u>ከተሰደደ፤ እጥረቱ ስርአታዊ (Systemic)</u> ነው። የኢትዮጵያ ደሃ አስተምሮ ጥቅሙን የውጭ መንግስታት ያገኛሉ። ይህ ለህወሓት የፖለቲካ ስልጣን ባለ ጠጋዎች ክፍተት ፈጥሯል። ብሄራዊ ተወዳዳሪ የለባቸውም።

7. ገዢው ፓርቲ በተግባር ያሳየው፤ የጠባብ ጎጠኛው አመራር፤ <u>የመንግሥትን መለዋወጥ አስፈላጊነትና የአገርን ተከታታይነት</u> የለየ አይደለም። በአብዛኛው አገሮች፤ መንግስትን መለወጥ የተለመደ ነው። አገርን (ዋርካውን) መለወጥ የተለመደ አይደለም። ህወሓት ስልጣን ከያዘ በኋላ የታየው ልምድ አገሪቱን እንደ ተራ እቃ ወይንም ሸቀጣ ሸቀጥ አይቷታል። ወሰኗን የሚቸረችረው አመራሩ ለአገር ዋርካነት ስላልቆመ ነው። መልክአ-ምድሩን እንደፈለገ ለውጦታል። የጎንደርንና የወሎን ሕዝብ መሬት ነጥቆ ከትግራይ ክልል ጋር አቀላቅሏል። የህወሓት አመራር የአገሪቱን ድንበር ለውጦታል። ከአንድ ሽህ ስድስት መቶ ኪሎሜትር በላይ የሆነ ለም መሬት ለወዳጁ ሰሜን ሱዳን አስረክቧል። የጎንደርን፤ የወሎን መሬት ወደ ትግራይ አዘዋውሯል። ታሪክን፤ የግዛቶችን አቀማመጥ በፈለገው መንገድና መጠን ይቀይራል። የጎዳው የአማራውን ሕዝብ ሙብት ብቻ አይደለም። የሚኖረውን ሕዝብ ሰላም ነስቶታል። ህይወቱን አናግቶታል። እንዲያምጽ አስገድዶታል።

8. ጠባብ ጎሰኛው መንግሥት፤ <u>አሁንም ጥላቻን እንደ ፖሊሲ ይከተላል</u>። ጥላቻ ለፍትሃዊ እድገት ጸር ነው። የማምረት ኃይል ይቀንሳል። የህወሓት "አባት ነኝ" የሚለው ስብሃት ነጋ፤ በስልጣኑና ባገኘው ከበርቴነት ደልቶት የሚኖር የስልጣን ባለጠጋ፤ በጥላቻ የፍልስፍና ዲግሪ ያገኘ ይመስላል። "የአማራውንና የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን ጀርባ አድቅቀነዋል" ሲል ራሱን ሹሞ የኢትዮጵያ መታወቂያ የሆነውን ሁሉ ማጥፋት አቋማችን ነው ማለቱ ነው። ተቋሞችን ማድቀቅ ኢትዮጵያን ማድቀቅ ነው እንላለን። እያየነው ነው። የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የአገራችን መታወቂያ ነው። ከስድሳ በሙቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ነው። ክርስትና የአማራ ወይንም የትግሬ፤ ወይንም የኦሮሞ ወዘተ መታወቂያ አይደለም። የእስልምናም ሃይማኖት ኢትዮጵያዊነት አለው። እነዚህ ሃይማኖቶች ኢትዮጵያዊነታቸውን ከሳቱ ለውጭ ጠላት መሳሪያ እንደሚሆኑ አያጠራጥርም። ዛሬ ለጠባብ ጎሰኛ መንግሥት ቆይታ ብቻ የሚደረግ የዘርና የቋንቋ መከፋፈል--ትግሬ ከሆንክ የትግሬ ቤተክርስቲያን ሂድ ወይንም አቋቁም፤ የሸዋ አማራ ከሆንክ እንደዚሁ፤ አንድ ቤተክርሲያን፤ አንድ ሲኖድ፤ አንድ ፓትሪያርክ፤ አንድ አመራር አያስፈልግም፤ አመራሩን እኛ ባልነው ብቻ እንዲመረጥ እናደርጋለን--ወዘተ፤ ማለት አደጋ መጋበዝ መሆኑን ስብሃት ነጋ አልተረዳውም። አንድ ቤተክርስቲያን ሊመሰረት የሚችለው በፖለቲካ አመራር አይደለም። የሃይማኖት ነጻነት ሲኖር ብቻ ነው። በማሊ፤ በናይጀሪያ፤ በግብጽ፤ በሶማሊያ፤ በየመን የሚካሄደውን አደጋ የህወሓት አመራር ያየው አይመስልም። አገርን በጎሳ፤ በቋንቋ፤ በሃይማኖት መለያየት፤ ብሄራዊነትን ያዳከማል። አገርን ፈጽሞ ያጠፋል። ህወሓት ካለፈ በኋላ ለተከታታይ ትውልድ <u>ትቶት የሚሄደው ጠንቅ አሁን ስር እንዲሰድ አድርጎታል።</u> ይህን የጠባብ ጎሰኛነት ፖለቲካን የመሰረቱትን የበላዮች በታሪክ ሲያስጠይቃቸው ይኖራል። በማንም ብሄርና በማንም ሃይማኖት ላይ እንደዚህ መረን የለቀቀ መከፋፈል ሲደረግ አደገኛ አመራር መሆኑን ወደፊት ታሪክ ያነሳዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህ መርዝ ጎጂ መሆኑን ሲገነዘብ ጥላቻን በፍቅር እንደሚለውጠው እንገምታለን።

9. አገራዊ ተቋሞች የዋጋ ተመን <u>የሌላቸውም (Priceless) መታወቂያዎች ናቸው። ከፈረሱ አይተኩም።</u> የዋልድባ ገዳም አንዱ የኢትዮጵያዊያን መታወቂያ ነው። ልክ እንደ አክሱም፤ እነደ ላሊበላ ወዘተ። አክሱምን መስራት ቀላል

አልነበረም። አክሱምን ማፍረስ ቀላል ነው። ዋልድባን መስራትና ማጥፋትም እንደዚሁ። ለትግራይ ክልል ስኳር ለማቅረብ ሲባል፤ የገዳሙ መተዳደሪያ የሆነውን መስክ፤ የማይተካ ዛፍና ደን ጨፍጭፎ፤ ሌላውን አፍርሶ ማረስ ታሪክ የማይረሳው በደል ነው። ለተፈጥሮ ሃብት ምንም ግምት አለመስጠት ነው። ለም መሬት ለሳውዲዎችና ለህንዶች እየተሰጠ፤ የመታሃራን የስኳር ፋብሪካ ለመስራትና ለማስፋፋት ሲቻል፤ የስኳር ምርት ያስፈልጋል ብሎ ዋልድባን በግሬደር ማረስ ዋናው አላማ በወልቃይት የሚገኘውን የጎንደር ሕዝብ የባህልና የኢኮኖሚ መብት ለመክልከል ነው። “ጠላት” የተባለውን የዘላለም ደሃ ለማድረግ ነው። የለየለት ማን አለብኝ የሚል የጠባብ ጎሰኞች ተግባር ነው። የስኳር ኮርፖሬሽን ሃላፊው አባይ ጽሃየ፤ ሌላው የህወሓት አለቃ፤ በልማት ስም ዋልድባን በበላይነት ሲያስቆፍር የሕዝቡን፤ የአባቶችንና የምእመናንን መብትና ተቃውሞ ጥሶ በሃይል የሚያድርገው ነው። የታወቀው ጋናዊ ኢኮኖሚስት ጆርጅ አይቴ፤ “ደም መጣጭ ስነ-ስርአት ብሎ የጠራው (Vampire State)” የዚህን አይነት የአጭር ጊዜን የበላይነት ጥቅም የሚያስቀድም መንግስትን ነው። ደም መጣጭ ስርአት አርቆ የማያስብ፤ ጥላቻን ፈጣሪ መሆኑን ያሳያል።

10. <u>የጠባቡ ጎሰኛ አመራር በሃይማኖት ነጻነት የሚያደርገው አፈና ኢትዮጵያን ለባሰ አደጋ ዳርጓታል።</u> ሳውዲዎች እንደ-ወራሪ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡና ለእስልምና ኃይማኖት መሰራጨት ብዙ መቶ ሚሊዮን ዶላር ፈሰስ እንዲያደርጉ፤ የእስልምና ተከታዮች በሌሉበት መስጊዶች እንዲሰሩ ከፈቀደ በኋላ የእስልምና ኃይማኖት መሪዎችን አፍኗል። በሽብርተኛነት ከሷቸዋል። በሰላም፤ በጉርብትና  ይኖር የነበረውን የሁለቱን ኃይማኖቶች ተከታዮች ለማጋጨት እየሞከረ ነው። የአረቦች ተቃውሞ እንዳይመጣበት በማጤን፤ ለእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች የተቃውሞ መብት ሰጥቷል። ለክርስቲያኖች ተመሳሳይ እድል አልሰጠም። እራሱ ለፖለቲካና ለኢኮኖሚ ጥቅም ሲል የፈጠረውን ችግር ሌሎች እንዳመጡት ያስተጋባል። በጎሳ ሆነ በኃይማኖት፤ በፖለቲካ ሆነ በሰብአዊ መብቶች፤ አመራሩ ለአደጋ ያመቻቸው መሆኑን ህብረተሰቡ ገብቶታል።

እነዚህ አስር ታሪክ የመዘገባቸው የአመራር ድህነቶች (The Poverty of Poor and Repressive Governance) “የለውጥ ሃዋሪያ” መለኪያዎች አይደሉም። ሙሶሎኒ ኢትዮጵያን በጎሳ መለያ ከፋፈላት። አማራ፤ ሃረር፤ ኦሮሞ-ሲዳሞ እና ሸዋ ብሎ። እነዚህ የጎሳ ክልሎች ልክ እንዳሁኑ የክልል ስርአት፤ የገንዘብ፤ የህግ፤ የአስተዳደር መብት አላችሁ ተብለው ነበር። ዋናው ውሳኔ የሚመጣው ግን ከላይ ከሚቆጣጠረው ከፋሺአቱ አመራር ነበር። የጣሊያን ክልሎች በአንድ ኢትዮጵያ ስም ይተዳደሩ እንጅ፤ በጣም የተለያየ መልክ መያዝ ጀምረው ነበር። “እያንዳንዱ ክልል ነጻ የሆነ ሪፐብሊክ ነበር። አንዱ አስተዳደር ከሌላው ጋር የሚጋራው ምንም አልነበረም። መረዳዳትና መተባበር ፍጹም ጠፍቶ ነበር። ሌላው ቀርቶ የክልሉን ደህንነት ለመጠበቅ ልዩነት ነበረ” ወዘተ። ልክ እንደ ዛሬው፤ በቋንቋና ጎሳ የተቋቋመው አስተዳደር የጣሊያኖችን አላማ ቀላል አላደረገውም ነበር። ጣሊያን እርጋታን ለማረጋገጥ የሞከረው ሃይል በመጠቀም ነበር። ዛሬ፤ ህወሓት/ኢህአዴግ ሰላምን ለማረጋገጥ የሚጠቀመው የሕዝብ ፈቃድ አይደለም። ሃይልና አፈና ነው። ኢትዮጵያ ከሚያስፈልጋትና አቅሟ ከሚችለው በላይ በሆነ በመከላከያ፤ በፌደራል ፖሊስና በስለላ መዋቅር መረብ ትገዛለች። የሻቢያና የህወሓት መስራቾች ኢትዮጵያን ለማፈራረስና ለመቆጣጠር የተጠቀሙት ዘዴ በራሳቸው ጭንቅላት የተፈጠረ አይደለም። በቅኝ ገዢዎች መሰረተ ሃሳብ፤ በአረቦች አባይን የመቆጣጠር አላማ ነው።

የህወሓት መስራቾች “አክሱም ለኦሮሞው፤ ላሊበላ ለጉራጌው ምን ትርጉም አለው” ሲሉ፤ ኢትዮጵያዊያን ምንም የሚጋሩት ታሪክ የላቸውም ማለት ነው። ዓባይስ ለሶማሌው ምንድ ነው? ዛሬ ስብሃት ነጋ፤ “የአማራውንና የተዋህዶ ቤተክርስቲያንን ጀርባ አድቀነዋል” ሲል--ልክ ዘላለም እንደሚኖር ትምክህተኛ--ኢትዮጵያ ታሪክ የላትም። አዲስ ታሪክ ተሰርቷል ማለቱ ነው። አማራው ነጻነቷን ለማስጠበቅ ያደረገው መስዋእትና አስተዋጽኦ እንደሌለ ለማሳመን ነው። ይህ የብሄር ጥላቻ ይባላል። ጆርዳን ገብረመድህንና ሌሎች ደጋግመው “ምሁራዊ አስተዋጽኦ” ያደረጉበትና ሌሎቻችን የተከራከርንበት፤ የፖለቲካ ሂደት ነው። በአንድ ወቅት፤ የአማራ ምሁራንም ይህን የጥላቻ ባህል መሰረት አስምረውበት ነበር። “የአማራው ብሄረሰብ ለፖለቲካና ለኢኮኖሚ የበላይነት ሌላውን ጨቁኗል። የባርነትን ባህልና ተግባር የፈጸመውና ለትግራይ ኋላ ቀርነት ምክንያት የሆነው አማራው ነው” ወዝተ የሚል የጥላቻ ፖለቲካ ያደረሰውን አደጋ እያየን ነው። ምሁራንም ሆኑ የጎሳ ፖለቲከኞች  አማራውን ሲያዋርዱ ያሉት ተመልሶ አገሪቱን እንደሚጎዳት አላሰቡም ነበር። አጼ ቴዎድሮስን፤ አጼ ምኒልክን፤ አጼ ኃይለ ሥላሴንና ሌሎችን ያወገዙት በምርምር፤ በሃቅ በተገኘ ትንተና አልነበረም። በጥላቻ ነበር። ህወሓት፤አነግና ሻቢያ አሁንም የሚመሩት በዚሁ የአማራ ጥላቻ የፖለቲካ ስልት ነው። ኢትዮጵያን ለማስተባበር፤ ዘመናዊ የወታደር ተቋም ለመመስረት፤ የውጭ ጠላትን ለመቋቋም ታግለው የሞቱትን ጀግና፤ አጼ ቴዎድሮስን ከመንግስቱ ሃይለማሪያም በላይ “ክፉ፤ ጨካኝ፤ ሙሰኛ፤ ወዘተ ወዘተ” ብሎ የትግራይ ተወላጅ የሆኑትን አጼ ዮሃንስ እንደ ወርቅና እንደ እንቁ ማቅረብ ይሉኝታ የሌለው። ጠባብ ጎሰኛነትና የታሪክ ክህደት መሆኑን አብዛኛው አንባቢ እንደሚጋራ እናምናለን። አዲስ ታሪክ የተፈጠረው በዚህ የጠባብ ጎሰኛነት ዘይቤ ነው። ይኼ ሁሉ ሕዝብን ለመከፋፈል የሚደረግ የጥላቻ መርዝ ነው።

የክርስቲያን ሆነ የእስልምና ተከታዮች ይህን የብልጣ ብልጥ ታሪክ ተከታታይ ተሃድሶ አንቀበልም ማለት አለባቸው። አገር የጋራ ናት። ሃይማኖት የግል ነው። አገር ከሌለች የሃይማኖት ነጻነት አይኖርም። ፍትሃዊ እድገት አይኖርም። የጋራ አገርን ዘላላማዊነት ለማደስ ከተፈለገ፤ አገዛዙ የሚያደርገውን ማንኛውንም ልዩነት በድፍረትና በአንድነት መቃወም ተገቢ ነው። በቅርቡ የሚታየው ከሃይማኖት በላይ በኢትዮጵያዊነት መሰብሰብና አብሮ መታገል አዝማሚያ ለዚህ ይበጃል። ህወሓት የተዋህዶ ቤተክርስቲያንን በኀሳ በመለያየት፤ ለሁለተኛ ጊዜ የትግራይ ተወላጅ ፓትሪያርክ በፖለቲካ ውሳኔ መርጧል። ስለዚህ፤ አንድ ሲኖዶስ፤ አንድ አስተዳደር፤ አንድ ፓትሪያርክ የሚለውን መርህ ደምስሷል። የኢትዮጵያን ተዋህዶ ቤተክርስትያንና ምእመናን ጎድቷል። ህወሓት በሃይማኖት ነጻነት ላይ ጣልቃ መግባቱ የአገሪቱን ደህንነት ወደ አደጋ አምርቶታል። በተለይ በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች አፈና ዙሪያ። ለዚህ አፈና የሚበጀው ክርስቲያኑና እስላሙ ለአንድ አገር፤ ለሃይማኖት ነጻነት አብሮ መቆምና የጠባብ ጎሰኛነትን አመራር ማጋለጥ ነው። ሌላው የህብረተሰብ ክፍል ማድረግ ያለበት እነዚህ ሃይማኖቶች አብረው ተባብረው ለአገር፤ ለፍትሕ፤ ለእኩልነት፤ ለእውነተኛ የሃይማኖት ነጻነት እንዲቆሙ ድጋፍ መስጠት ነው።

ጎሰኛነት አድልዎን አመቻችቷል

የጠባብ ጎሰኛነት ፖለቲካና አመራር ለሃገር መክሸፍ (መበታተን) ቀዳዳ ከፋች ነው። ሶስት ተጨማሪ ምሳሌዎች እንይ።

አንድ፤ የብሄር/ብሄረሰብ እኩልነት አለ የሚለው የህወሓት ፕሮፓጋንዳ ቀፎ ነው። አንጋፋ የሆኑት የኦሮሞና የአማራ "ክልሎች" ከትግራይ ጋር ሲነጻጸሩ፤ በሕዝብ ዘገባ፤ የኦሮሞው ቁጥር ከትግራዩ ቢያንስ ስድስት ጊዜ የበለጠ፤ የአማራው ከትግራዩ ቢያንስ አምስት ጊዜ የበለጠ ነው። ሆኖም፤ የትግራይ ክልል እንደ አንጋፋ ተወክሏል። አወቃቀሩ ለምዝበራና ለጎሳዊ አድልዎ ያመቻል።

ሁለት፤ በባጀት አመዳደብና ክፍፍል (Federal Budgetary Allocation and Distribution) ላይ የታየው አስተዋጽኦ በቅድሚያ ታስቦ ነው። ከሁሉም በላይ፤ የትግራይ ክልል በጦርነት ተጎድቷል በማለት፤ ለሃያ ሶስት አመታት፤ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የተሰበሰበ፤ ከውጭ ለጋሶች የተገኘ ብዙ መቶ ቢሊዮን ብር ድጋፍ አግኝቷል። አመራሩ ይህን ሲያደርግ፤ የጦር አውድማ የነበረውን የጎንደርን ሕዝብ እድል በማገዠ ነው። የክልል አንድ (ትግራይ) መሰረተ ልማት ከአማራውና ከኦሮሞው የተሻለ መሆኑ ማስረጃ ነው። ጥራት ያለው የዘመናዊ መገናኛ፤ የመሃንዲስነት፤ የህክምና፤ የእርሻ ወዘተ ትምህርትና ስልጥንና የሚሰጠው ለዚህ ክልል ተወላጆች ነው። በአንጻሩም ለውጭ ትምህርት እድል አድሏዊ በሆነ መንገድ የሚሰጠው ለዚሁ ክልል ተወላጆች ነው። አፋሩስ፤ አፗኩስ፤ ሶማሌውስ፤ ደቡቡስ፤ ኦሮሞውስ፤ አማራውስ????

ሶስት፤ የፌደራል አስተዳደር ለሕዝብ ብዛት ምንም ክብደት አልሰጠም። የሕዝብ ብዛት ክብደት ያልተሰጠበት ምክንያት ግልጽ ነው። በቁልፍ ተቋሞች የትግሬዎችን የበላይነት ለማጠናከር። በአብዛኛው፤ የውሳኔና የባጀት አጠቃቀም አገልጋይነቱ ለአንድ አምባገነናዊ ፓርቲ የፖለቲካ፤ የማህበረሰብ፤ የኢኮኖሚና የተፈጥሮ ሃብት መያዣ አመች እንደሆነ አመልካች ነው። በአንጻሩ፤ ተራው የማንኛውም የብሄር፤ ብሄረሰብ አባል በግል ሆነ በጥቅል ዲሞክራሳዊ መብቱ አልተጠበቀም። የእድገት ፍላጎቱ አልተሟላም። አብዛኛው ከፍጹም ድህነት ነጻ

አልሆነም። እድገት መኖሩ ባይካድም፤ በአብዛኛው፤ የእድገቱን ጥቅም በይበልጥ (The Lion's Share of Ethiopia's Growth) ያገኘው የተወሰነ የፖለቲካ ባለስልጣን፤ ፓርቲው፤ ታማኝ የሆኑ የፓርቲው ደጋፊዎችና የውጭ አገር ኢንቬስተሮች፤ ክልል አንድ ናቸው። ይህን፤ ከእድገቱ ማን ተጠቀመ፤ ማን ተጎዳ የሚለውን ጥያቄ በጽሞና ለማጤን፤ ለየትኛውም ብሄር ቢሆን፤ የህብረተሰቡ የኑሮ ሁኔታ መሻሻል ዋናው የእድገት መለኪያ መሆኑን እንቀበል። አለበለዚያ፤ ቪላ፤ ሰማይ ጠቀስ ፎቅ፤ መንገድ፤ የሃይል ማመንጫ ግድብ፤ ወዘተ መሰራቱ ብቻ እድገት ነው ተብሎ ሊፎከርበት ይችላል። የእድገት ዋና መለኪያው የህብረተሰቡ ኑሮ መሻሻሉ ከሆነ- የእኛ እምነት ነው- አንድ ለህይወት አስፈላጊ የእድገት መለኪያ፤ ማለትም፤ የምግብ አቅርቦት (Staple food supply) ሁኔታውን እንመርምር። 22/

የእርሻን ቁልፍነት፤ በብልጭልጩ የእድገት ውጤት ማየት ብቻ አያዋጣም። በ2014 84 በመቶ የሚሆነው ወይንም 79 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን (ከ94 ሚሊዮን ሕዝብ)፤ የሚመካው በእርሻና ከእርሻ ጋር በተያያዙ የኢኮኖሚ ክፍሎች ነው። ስለሆነም፤ እርሻ ለህብረተሰቡ ህይወት ወሳኝ ነው። የኢትዮጵያን የእድገት ደረጃ ለማመዛዘን፤ በእርሻ በኩል ያለውን ውጤት መመርመር አስፈላጊ ነው። በአጠቃላይ ሲታይ፤ ኢትዮጵያ ያለ ውጭ ድጋፍ፤ ሕዝቧን ልትመግብ አልቻለችም። የእርሻው መሬት ተበልቷል። የሕዝቡ ቁጥር አድጓል። ሌላ የገቢ አማራጭ በተፈለገው መጠን አልተሰራም ወዘተ። ከእልፈቱ በፊት፤ ጠቅላይ ሚንስተር መለስ፤ ከታወቀው ሃብታምና ለጋሽ፤ ቢል ጌትስ ጋር ስለ ብዙ ሚሊዮን የኢትዮጵያ

ዝቅተኛ አምራቾች አቅም ማጎልመስ ጉዳይ የተነጋገሩትና የእርሻ ምርትን ለማሳደግ የተዋዋሉትን ማጤን ይጠቅማል። ቢል ጌትስን ያሳሰበው የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ "ከማንኛውም የዓለም ሕዝብ በበለጠ፤ የምግብ ዋስትና የሌለው፤ ጥገኛ መሆኑ" ነው። ይህን የተናገረው የገጠር ኢኮኖሚው የገዢው ፓርቲ እንደሚለው በማደጉ አይደለም። የህወሐት አመራር የካደው፤ ትግራይ በድርቅ የተሰቃየ፤ ብዙ ሕዝብ ከትጋራይ ተሰዶ ወደ ሌሎች ክፍለ ሃገሮች እንደሄደ መቀበልን ነው። ላለፉት ሃያ ሶስት አመታት፤ ህወሐት በበላይነት የመራው መንግሥት፤ በእርሻ  የተመሰረተ የኢንዱስትሪ ልማት አመራር ነበር። ሌላው ቀርቶ የምግብ ዋስትና ሊያስገኝ አልቻለም። ረሃብን ሊፈታ አልቻለም። እራሱ በግብዣ ያመጣውን የሽብርተኛነትን ዋና መንስኤ አላወቀም።

የገዢው ፓርቲ መሪ ቢጨንቀው፤ ለም መሬት ከክልሎች በማስገደድ እየወሰደ፤ በተፈጥሮ ሃብት ባንክ እያስገባ፤ ወደ መሬት ችርቻሮ ስራ ገብቷል። ካሩቱሪ፤ ሳውዲ ስታር ወዘተ ተጠቃሚ ሆኑ። እነዚህ የውጭ ኢንቬስተሮች ያሞሉት የራሳቸውን ኪስና የወከሏቸውን መንግስታት የምግብ ፍላጎት ነው። እነዚህ ሁለት ምሳሌዎች፤ በእርሻ ልማት ላይ የተመሰረተው የእድገት አመራር ከቁጥጥር ባሻገር፤ አጥጋቢ ውጤት አለማሳየቱን ያመለክታሉ። አጥጋቢ ውጤት ቢገኝ ኖሮ፤ የምግብ ድጎማው ባላስፈለገ ነበር። ከሃያ ሶስት አመታት የህወሐት መንግሥት በኋላ፤ አሁንም ለማኝ መሆን የእድገት ምልክት ሊሆን አይችልም። በሰፋፊ የንግድ እርሻ ላይ የተሰማሩት የውጭና የውስጥ ተጠቃሚዎች፤ የገዢው ቡድን ምርጥ የትግራይ ተወላጆች አዲስ ሃብታሞች፤ በግብዣ የመጡ ትርፍ ፈላጊ የውጭ አገሮችና ድርጅቶቻቸው፤ ረሃብን፤ የምግብ ጥገኝነትን ሊያስወግዱ አለመቻላቸውን ያሳያል። ሁሉም የተሰማሩት፤ ለትርፍ እንጅ ድህነትና ረሃብን ለማስወገድ፤ የምግብ ዋስትናን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለማስገኘት አይደለም። የመሬት ነጠቃና ቅርሚት ጉዳት በሁሉም ኢትዮጵያውያን ላይ እነደሚሆን ብዙ ምርምሮች ያሳያሉ። ለዚህ ነው የመሬት ይዞታ ፖሊሲው መለወጥ ያለበት። የገዢው ፓርቲ በኢትዮጵያ ሕዝብ አማካይነት መሬትና ሌላ የተፈጥሮ ሃብት ይዣለሁ፤ ህብረተሰቡ እንዲገለገልበት እያደረግሁ ነው የሚለው የፖለቲካ ጨዋታ ጊዜው አልፎበታል። ከተጠቃሚው ንኡስ ክበብ ውጭ ማንም አይቀበለውም። ባጭሩ፤ የጎሳ-ተኮር ፌደራሊዝም፤ ኢትዮጵያዊያን በራሳቸው አገርና በራሳቸው የተፈጥሮ ሃብት ላይ አዛዥ እንዳይሆኑ መሰናክሎች ፈጥሯል። ሌላው ቀርቶ፤ በግል ህይወታቸው ያዝባቸዋል። ውጡና አልቅሱ ከማለት በላይ ምሳሌ የለም።

በቅርቡ የኦክላንድ ተቋም የተባለው ያቀረበው ዘገባ እንዲህ ይላል። "በአሁኑ ወቅት ከኢትዮጵያውያን ይልቅ የውጭ ባለሃብቶችና የመንግስት ባለስልጣናት የበለጠ ሃይልና ስልጣን አላቸው።" የኢትዮጵያ ሕዝብ በአገሩ ምንም ድምጽ፤ ሃይልና ተሳትፎ የለውም። ይህ፤ ስርአቱ ያመጣው ማነቆና አፈና ነው። ስርአቱን ስለሚረዳው፤ የገዢው ፓርቲ አለቆች ኢትዮጵያዊያን በራሳችው አገር ቢናቁ፤ ቢባረሩ፤ ቢያፍሩ፤ ታዛዥና አጎብዳጅ ቢሆኑ፤ ከአገር ቢሰደዱና በአረብ አገሮች ቢዋረዱ፤ ቢራቡ፤ ምንም አይሰማቸውም። የራሣቸው ኪስና ሆድ ሞልቷል። ለዚህ ነው፤ በጥላቻ የተመሰረተው የጠባብ ጎሰኛ ፌደራሊዝም ለጠባብ ጎሰኞች ጥቅም አለው በማለት የምከራከረው። የጎሳ ፌደራሊዝም ዋናው ተግባር "ለከፋፍለህ ግዛው" መሳሪያ ሆኖ ማገልገል ነው። ጥላቻን ወልዷል፤ ጥላቻን ማጠናከር ክፍተት ይፈጥራል። ተወዳዳሪ እንዳይኖር ያደርጋል። በጥላቻ የተመሰረት አገዛዝ ኢትዮጵያዊያን ከድህነት፤ ከኋላ ቀርነት፤ ከረሃብ፤ ከጥገኝነት ሊያወጣት የሚያስችል አይደለም ለማለት ያስደፍራል። ጎሰኛው አገዛዝ የተመሰረተው ለፍትህ፤ ለእኩልነት፤ አብሮ ለመኖር፤ አብሮ ለመልማት አይደለም። ሲጀመር፤ ህወሐት ታላቋን ትግራይ ለመመስረት ነበር። እየቆየ ሲያየው፤ መላው ኢትዮጵያን መቆጣጠር ለትርፍ እንደሚያመች ተገነዘበው። የለም እርሻ ሃብትና ወንዝ፤ ማእድንና የኢኮኖሚ አውታሮች፤ ቀስ በቀስ፤ ከአገርና ከኢትዮጵያውያን እጅ እየተነጠቁና እየተገለሉ (Alienation)፤ ለፈረንጆችና ለጥቂት የትግራይ ተወላጆች ተላልፈዋል፤ እየተላለፉ ነው። የህወሐት አሰራር አያስደንቅም፤ ለማንም ተመልካች የሚያስደንቀው፤ ተቃዋሚው ክፍል ይህን በብሄረሰቦች ነጻነትና እኩልነት ተመስርቷል የተባለ ከሃቁ የራቀ የአገዛዝ ስልትና አገራዊ ምዝበራ ዝም ብሎ ተመልክቷል። አሁንም ይመለከታል። ቁሞ ተመልካችነት ከታሪክ ተጠያቂነት ነጻ አያወጣም። ሃብት፤ ጥሪት፤ ተሳትፎ፤ የመወሰን እድል የሌለው ሕዝብ ደሃ መሆኑን፤ ተከታታይ ትውልድም ድሃ እንደሚሆን ያውቃሉ። ገዢው ፓርቲ ጥቅሙን አስቦ የጸነሰው ስርአት ስለሆነ፤ ተቃዋሚው ክፍል ከጎሳው ፌደራሊዝም መብቶች ማግኘቱ በጣም አከራካሪ እየሆነ ሂዷል። ዋና ደጋፊዎቹ የጥቅም ተካፋዮች ናቸው። የሚያዋጣው ተኮራርፎ፤ ተጠራጥሮ መኖር አይደለም። የሚያዋጣው ለሁሉም የሚያገለግል የፖለቲካና የማህበረሰብ ማእከል መፍጠር ነው። የአማራውና የኦሮሞው ልሂቃንና የፖለቲካ ስብስቦች ዋና ተግባር ተፈላልገውና ተፈቃቅደው ይኼን ለወደፊቷ ዲሞክራሳዊ እትዮጵያ የሚያገለግል ማእከል መፍጠር ነው። አክራሪነት፤ ለህወሐት አጎብዳጅነት፤ ተጠላፊነት፤ ደሞዝ ፈላጊነት ምንም አያዋጣቸውም። የሕዝብ ብዛት ስላላቸው በምርጫ ተወዳድረው ስልጣን ለመያዝ የሚያግዳቸው ኃይል አይኖርም።

በጎሳ ፌደራሊዝምና በእድገት አሳቦ፤ የህብረተሰቡን መብት፤ ሰብእነት፤ ክብር መግፈፍ፤ ከገንዘብ ድህነት የባሰ ጉዳት አለው። የመንፈስ ድህነት ፈጥሯል። ማእከል ለመፍጠር አለመቻል የመንፈስ ድህነት መስፈርት ነው። ሕዝቡ በራሱ

መተማመን አቅቶታል። ተራውን ደሃ እንተወውና፤ ሰባ ስድስት በመቶ የሚሆነው ወጣት ትውልድ (እድሚው ከሰላሳ አምስት በታች የሆነው) ያለው ስርአት አማሮት፤ ብሰደድ ይሻለኛል የሚለው፤ በተደጋጋሚ ለማለት የምገደደው። አገሩን ጠልቶ ሳይሆን በአገሩ ሰርቶ፤ ኮርቶ ለመኖር ስለማይችል ብቻ ነው። በተቃዋሚው ክፍልም ያለው እምነት እየቀዘቀዘ ስለሄደ ነው። ህብረተሰቡ የሚለው፤ ቅንጅትን ያፈረሰ ተቃዋሚ የህብረተሰቡን እምነት ቀብሮታል የሚል ነው። የጎሳ ፖለቲካ፤ የጎሳ ፌደራሊዝም፤ የጎሳ የስራ ድልድል፤ የጎሳ ምርጫ፤ ወዘተ፤ ለስደት አስተዋጽኦ አድርጓል። ወደፊትም ያደርጋል። በኢትዮጵያ የሚቆየው አዲስ ትውልድ፤ ቢማርም ባይማርም፤ ደሃ ሁኖ የመቆየት እድሉ ከፍ እያለ የሚሄድ እንጅ የሚቀንስ አይመስልም። የተማረም ሆነ ያልተማረ፤ ከተሜ ሆነ ገጠሬ፤ ድህ ሕዝብ መከታ የለውም፤ በሰላም ተኝቶ አያድርም። ደሃው ለጉርሻ ሁለት ብር ከአምሳ ሳንቲም እየከፈለ በአገሩ ሊኮራ አይችልም፤ ሰውነቱም መንፈሱም ስለተጎዳ፤ መብቱን ለማስከበር አቅም አይኖረውም። ከመሬትህ ለቀህ ውጣ ሲባል መውጣት እድሉ ሁኗል። ገዢውን መንግሥት ለመቃወም መብትም፤ አቅምም የለውም። ህወሓት የሚያዘው የጎሳ ስብስብ፤ ኢህአዴግ፤ ለም መሬት፤ ሌላ የተፈጥሮ ሃብት፤ዉሃ፤ ማእድን፤ ፋብሪካ፤ ከኢትዮጵያውያን እና ከአገር ወደ ራሱ ተቋሞችና ደጋፊዎች፤ ወደ ውጭ ባለ ሃብቶች ሲያዘዋውር የሚጠቀመው የጎሳውን ህገመንግስትና አስተዳደር የበላዮች ነው። ጠቅሞ ይጠቀማል። ይህ፤ በኢትዮጵያ የነጻነት ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ የሃብት ምዝበርና ዝውውር፤ ለገዢው ፓርቲ ቆይታ ያገለግለዋል። ለምሳሌ፤ ድጋፍን ከኢንቨስተሮች ያመጣለታል፤ ይህን እንደ ድል ይቆጥረዋል። የህወሓት የበላዮች ድል ግን ብሄራዊ ውርደትን፤ ድከመትን፤ ጥገኝነትን ወልዷል። ህገመንግስቱን፤ ክልሎችን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር ለሃብት ዝውውር ጣምራዊ አገልግሎት ሰጥተዋል። ከገንዘብ ጥቅሙ ሌላ፤ የዲፕሎማሲ ጥቅሙ ከፍ ያለ ነው፤ ህንዶች፤ አረቦች፤ ቻይኒሶች ወዘተ ይደግፉታል። ገዢው ፓርቲ የሚሰጠው መልእክት፤ "እኛኮ የውጭ ኢንቬስተሮችን እንደግፋለን፤ ከካፒታሊዝም ጋር ምንም ልዩነት የለንም" የሚል ነው። ከአድሏዊ ካፒታሊዝም (Crony Capitalism) ሊጣላ አይችልም። ከቻይና የተማረው አንዱ ይህ ነው። ቬስታል፤ መለስን "የካፒታሊዝም ጠቨቃ ማርክሲስት-ሌኒኒስት" ያለው ለዚህ ነው። 23/

ጠለቅ ብሎ ላየው፤ የጎሳ ፌደራሊዝም በመርዝ የተቀባ ማር ነው። መርዝነቱ ለድሃው፤ ለወጣቱ ትውልድ፤ ለአገር ወዳዱ፤ ለኢትዮጵያ ሲሆን፤ ማርነቱ ለፖለቲካ ባለስልጣኖች፤ ላፈሯቸው ጥቂት ተጠቃሚዎችና ለእነሱ ልጆችና የልጅ ልጆች ነው። <u>ስርአቱ ለአብዛኛው ተከታታይ ትውልድ ጉዳት አለው። አሁን የሚያጎለምሳቸው ግለሰቦች የወደፊት የበላዮች ይሆናሉ በሚል ሂሳብ ነው። ምሳሌ፤ በሌሎች አገሮች እንደሆነው ሁሉ፤ የፖለቲካ ስልጣን በሃይል መያዝ (Elite Political Capture) ቀስ በቀስ የሚመራው ወደ ገንዘብ፤ ሃብትና የተፈጥሮ ሃብት ጠለፋ ነው (Economic and Social Capture)</u> ነው። ዛሬ፤ በኢትዮጵያ ደሃ የሆነ ከፍተኛ ባለስልጣን የለም፤ ስብሃት ነጋ፤ አባይ ጸሃይ፤ ሳሞራ ዩኑስ፤ አዜብ መስፍን፤ ስዩም መስፍን፤ ወዘተ ድሃ አይደሉም፤ ያገኙት ጠጋ (ሃብት) ፋብሪካ ሰርተው፤ ነግደው፤ ጥረው ግረው አይደለም። ልጆቻቸው የዚህ ከፖለቲካ ስልጣን ጠለፋ የመጣ ውጤት ተጠቃሚ እንደሚሆኑ አልጠራጠርም። ባለስልጣን አባቶቻቸው፤ የድህነትን ጫና ከትከሻቸው አውርደውላቸዋል ማለት ነው። የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ አለቃዎች፤ የቻይናን ኢኮኖሚ እንደለወጡት አልጠራጠርም። በአይኔ አይቸዋለሁ። ድህነት ቀንሷል። የሚራብ የለም። መካከለኛው መደብ አድጓል....ይህን ተአምራዊ ለውጥ ያመጡት የቻይና መሪዎችና የቻይና ሕዝብ ነው። አገር ወዳድ አመራር ስላለ። ችግሩ፤ የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ አለቃዎች ለህግ፤ በህግ አይገዙም፤ ልክ እንደ ህወሓት የበላዮች። ነጻ የሆነ ተቆርቋሪ ተቋም የለም። ነጻ የመገናኛ ብዙሃን አይፈቀድም።

የአድልዎና ሙስና ባህል ከፖለቲካ ስልጣን ጋር የተያያዘ ነው

አንጋፋና ዘላለማዊ ናቸው ተብለው የሚጠሩት የዘመናዊዋ ቻይና መስራቾች (The 8 Immortals) ዴንግ ዚያወኦፒንግን ጨምሮ፤ ለቤተሰቦቻቸው ዘላቂነት ያለው የበላይነት አውርሰዋል። አገዛዙ የህወሓት አመራር አሁን ከሚያደርገው ተመሳሳይ ነው። የቻይና ባለስልጣናት ለልጆቻቸውና ለልጅ-ልጆቻቸው ታይቶ የማይታወቅ የገቢና የሃብት የበላይነት ድልድይ ፈጥረዋል። እነዚህ የባለስልጣናት ልጆች እንዴት ከዚህ ደረሱ። ህወሓትስ የሚያደርገው አድሎ ተመሳሳይ እድልና የገቢ ልዩነት ይፈጥራል ወይ ብለን እንጠይቅ። መልሱ ፈጥሯልና እየፈጠረ ይቆያል የሚል ነው። እንዴት?

1. የባለስልጣን ልጆችና ዘመዶች ለትምህርት፤ ለስራ፤ ለግል ባለ ጠጋነት መነሻ እድል ከፈተላቸው። ህወሓት አሁን የሚያደርገው ይህን ነው።

2. እነዚህ ልጆችና ዘመዶቻቸው ከሌላው በተለየ ሁኔታ መሬት፤ ብድር፤ ፈቃድ፤ ኮንትራት ለማግኘት ያላቸው መብት ከፍተኛ ነው። ውሳኔ ከሚሰጡት የመንግሥት ሰራተኞች ጋር ተቆላልፈዋል። የጠየቁትን ያገኛሉ። ልክ ቻይና እንደሆነው።

3. የከፍተኛ ባለስልጣናት ልጆችና ዘመዶች የሚሰሩት ከህጉና ደንቡ ውጭ ነው። በኮንትሮባንድ ይሰራሉ። ከጉምሩክ ቀረጥ ውጭ ናቸው። ህጉና ደንቡ አይመለከታቸውም። ህገወጥ ስራ ቢሰሩ ፖሊስና ዳኞች በሃላፊነት አይጠይቋቸውም። ህግ በኢትዮጵያ ዋጋ የሌለው ለዚህ ነው።

4. ከህግ ውጭ ለመስራት ስለሚችሉ፤ የባለስልጣናት ቤተሰቦችና የቅርብ ወዳጆች የውጭ ምንዛሬ እንደልባቸው ሊሰበስቡና ሊያሸሹ ይችላሉ። ማንኛውንም የሚሸጥ እቃ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደውጭ ሊልኩ መብት አላቸው። ኤምባሲዎችን ለግል አገልግሎት መሰብሰቢያቸው የማድረግ መብት አላቸው። በጎሳቸውና በቋንቋቸው ብቻ ቢሰበሰቡ ማንም አይቃወማቸውም። የመንግሥት ሃብት የህወሓት ሃብት ነው ብለው ተቀብለውታል።

ብሉምበርግ ዜና ባደረገው ጥናት፤ በቻይና አንድ መቶ ሶስት የሚሆኑ የባለስልጣናት (Public Authorities) ቤተሰቦች የተለየ ግንኙነታቸውን ተጠቅመው የባንኮችና ፋይናንስ፤ የኢንዱስትሪ፤ የመገናኛ፤ የቤት ስራ፤ የመሬት ባለጸጋዎች ሆነዋል። በኢትዮጵያ ከአስራ ሁለት በላይ የማይሆኑ የፓርቲ፤ የመንግሥት ከፍተኛ ባለስልጣኖችና ቤተሰቦቻቸው፤ በአዲስ አበባ ብቻ ታላላቅ ፎቆችን፤ ኢንዱስትሪዎችን ወዘተ ይቆጣጠራሉ። ምን ያህል ገቢና ሃብት እንዳላቸው በምስጢር የተያዘ ነው፤ የባለስልጣናት ልጆች ልዩ እንክብካቤ እየተደረገላቸው በቻይና፤ በጃፓን፤ በህንድና በሌሎች አገሮች ከፍተኛ ትምህርት ይከታተላሉ። ወደፊት አባቶቻቸውን እንደሚተኩ ይጠበቃል። አንድ ምሳሌ፤ የጃፓን መንግሥት አስራ ሁለት ኢትዮጵያውያን በችሎታቸው ተመርጠው ለከፍተኛ ትምህርት በስኮላርሽፕ እንዲሄዱ ይወስናል። ፈተናውን ይወስዳሉ፤ ለመሄድ ሲዘጋጁ ከአስራ ሁለቱ አራቱ ብቻ እድል ይደርሳቸዋል። በስምንቱ ምትክ ህወሓት የመረጣቸውን የትግራይ ተዎላጆች ይልካሉ። ፈተና ያለፉት ይቀራሉ። ለምን ብለው ለመጠየቅ ፈርተው እድሉ ያመልጣቸዋል። የወደፊቱን ተተኪ የበላዮች ህወሓት ለማዘጋጀት ሲል፤ የሌሎችን እድል ያቅባል ማለት ነው። የጎሳ-ተኮር ፌደራሊዝምን ጥቅም የሚያዩ ሁሉ ማየት ያለባቸው፤ የስልጣን ብልግና የወደፊቱን ትውልድ እየጎዳው መሆኑን ነው። ስርዓትዊ ችግር ተከታታይ ትውልድን ይጎዳል የምንለው ለዚህ ነው።

በቻይና እንደሚደረገው፤ የስኳር፤ የቴሌኮሙኒኬሽን፤ የታላላቅ ባንኮች፤ የመገናኛ፤ የአንጋፋ የመንግሥት ተቋሞች ግንባታ ኮንትራቶች፤ የአስመጭና ላኪ፤ የጉምሩክ ወዘተ ተቋሞችን በቦርድ አባልነት፤ በስራ አስኪያጅነት ወዘተ በበላይ የሚቆጣጠሩት የህወሓት አባላት የትግራይ ተወላጆች ናቸው። ጡሮተኞች፤ ቤተሰቦችና ታማኝ ዘመዶች። በ1990s በዓለም ባንክ ሥሰራ ያየሁት ዘገባ፤ በመለስ ትእዛዝ ብዙ የመንግሥት አምራችና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች የግል ሲሆኑ ተጠቃሚ የሆኑት የትግራይ ተዎላጆች እና ወዳጆቻቸው ናቸው። በአጭሩ፤ ህወሓት፤ የጎሳ ፌደራሊዝም አገዛዝን በግልጽ ለራሱና ለቤተሰቦቹ እድገት እየተጠቀመበት ነው። በጎሳ የመከፋፈልን ክፍተትና የፖለቲካ ስልጣን መማረክ (ነጣቂነትና የበላይነት) ተጠቅሞ ሃብትን አሸጋግሮበታል። ሞኙ የአማራና የኦሮሞ አዲስ ትውልድ እርስ በርሱ ሲጋጭ በራሱ መንደር አዛዡ የህወሓት ካድሬ ሆኑላ ማለት ነው። ይህ ሽግግር የጎዳው የፖለቲካ ስልጣንና ተካፋይነት የሌለውንና ሃገሪቱን ነው። የማንኛውም ብሄር አባል ቢሆን፤ የተራው ኢትዮጵያዊ እድል ተዘግቷል፤ ቢበዛ፤ ባለህበት ቁም ተብሏል። በገቢና በባለጠጋነት ክምችት መመዘኛ ሲታይ፤ እድገቱ ያጎለመሰው የህወሓትን ቤተሰቦችንና ደጋፊዎች ነው። ህወሓት፤ የባለጠጋነትን ዘዴ ለማስፋፋትና ታማኝነት ለማጠናከር፤ የከበርቴነትን ደረጃ (Ranking of who is well to do, rich and super-rich) የሚወስነው በታማኝነትና በመቆያ አስፈላጊነት ነው። ሌላው፤ ከውጭ ኢንቬስተሮች፤ አበዳሪዎችና ለጋስ መንግስታት ጋር ቁርኝት በማድረግ ነው። ግሎባላይዜሽን (Globalization) ለቡድኑ አይቶት የማያይታወቅ ጥቅም አበርክቶታል። የጊዜው ባለ ጠጋዎች የፖለቲካ የበላይነት ፍጥረቶች ናቸው የምንለው ለዚህ ነው።

"የአባትህ ቤት ሲሰረቅ አብረህ ስረቅ፤ የምዝበራ ዘዴ"

ወደ ውስጥም ብናይ፤ ይህ ስርአት በራሱ ብቻ የሚሺከረከር አይደለም። ብሄራዊና አገር ወዳድ ስላልሆነ፤ ተቃዋሚ ስላልፈቀደና ተቀናቃኝ ስለሌለው በህግ የሚከሰው የለም። ተቀባይነቱን የሚያረጋግጠው፤ በተቻለ መጠን የደጋፊዎቹን ኑሮ በማሻሻል ነው። ስለሆነም፤ ምርጥና ጥቂትም ቢሆኑ፤ የጎሳዊ ፖለቲካ የሃብት ተጠቃሚዎች አፍርቷል። ብዙ ደጋፊዎችን በጥቅም፤ በጉቦ፤ በማስፈራራት ያቀፈ ነው። ከፍተኛውን የአገር ምዝበራ ለራሱ ይዞ፤ ዝቅተኛውን ወይንም ፍራፋሬውን ለሌች እየለቀቀ ይገኛል። መስሎት፤ ፍርፋፌ ያገኘ ሁሉ መብት እንደሌለው ተካፋይ ነኝ የሚል ስሜት አድሮበታል። ዘዴኛው ህወሓት ምዝበራውን በትንሹም ቢሆን አካፍሏል። ስለዚህ ስርአቱን በሙሉ ማየት ይገባል። ተጠቃሚዎችን ባይሰበስብ ኖሮ እስካሁን ባልቆየም ነበር፡፡ በየቦታው፤ በየሕብረተሰቡ፤ ደመወዝ ተከፍሏቸው አገልጋይና አንባዳጅ የሆኑ ደጋፊዎችንና ትእዛዝ አስፈጻሚዎችን በጥቅም ሰብስቧል። በመደለል ሆነ በማስፈራራት ወዘተ ሰፋት ያለው ድርጅታዊ መረብ አለው። ገዢው ፓርቲ ከመንግሥት ደሞዝ እየከፈለ፤ ስድስት ሚሊዮን አባላት

ሰብስቧል። አንድ ለአምስት በሚል የስለላ ሰንሰለት የበላይነቱን ያስጠብቃል። ግምገማ እያደረገ ራሱን ማደስ ስልጣን ላይ የመቆያ ማረጋገጫ ሆኗል። የመለስን እልፈት ምክንያት በማድረግ፤ በትግራይ ብቻ ከመንግስት ባጀት የወጣ የአበል ክፍያ በመስጠት፤ የህወሓትን የበላይነት ተከታታይ ለማድረግ ብዙ ሚሊዮን ብር ማፍሰሱ አመልካች ነው። ሖኖም፤ በግድ፤ በድኅማ፤ በጥቅምና በማስፈራራት የተደራጀ፤ በኅሰኝነት የተበከለ ድርጅት "የእምቧይ ካብ" ነው። የትግራይንም ሆነ ሌላውን ሕዝብ በማታለል፤ በማስገደድና በማስፈራራት አባል ሁን ሲል ሊኖር አይችልም። የአብዛኛው ኑሮስ? የወጣቱ ብዛት ብቻ ስርዓቱን ሊያንበረክከው ይችላል፤ ላወቀበት።

ምዝበራ ያጋለጠው የኅጠኛ ስርአት

ህወሓትን ያጋለጠው፤ ጥቂቶች በአብዛኛው ሕዝብ "ጭቁን ስም" ተጠቅመው የስልጣን ነጋዴና ባለ ጠጋ መሆናቸው ነው። ይህን ግልጽ በደል፤ ሕዝብ እያወቀ ሄዶ ከተነሳ፤ የገዢው ፓርቲ የኅሳ ስነስርአት በቀላሉ ይናዳል። አይበገርም የተባለው የደርግ መንግስት ወድቋል። የሙባርክና የጋዳፊ መንግስታት ወድቀዋል። የአሳድ መንግስትም ይወድቃል። ይህን፤ የህወሓት በኅሳ መከፋፈል የተዘረጋ ስልት ራሱ የፈጠረው ነው ለማለት አይቻልም። ከበፊቶቹ የቀዳው መጥፎ ልምድም የለም ለማለት አይቻልም፤ ግድያን ተከታታይ ያደረገው በደርግ እያመካኘነት ነው። የማይካደው በንጉሱ ሆነ በደርግ ዘመናት ከሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች የተመለመሉ ስርአት አስከባሪዎችና አገልጋዮች ነበሩ። በእነዚህ፤ በደልና አድሎ አልነበረም ማለት አይቻልም። የአሁኑን የኅሳ ስርአት የሚለየው ዋናው መለኪያ መነሻው፤ ሂደቱና አሰራሩ ሁሉ ለጠባ ቡድን በዘር፤ ለዘር ጥቅም መሆኑ፤ ለጥቂቶች ቡደን ጥቅም መቆሙ ነው። ይህን የስልጣን ብልግና ሃብታምነት እንለዋለን። የኅሳ ስርአት አደጋ ሁለ ዘርፍ፤ ሁለ ገብ መሆኑን እናያለን። ስልጣኑን ለማኅልመስ፤ ግለሰቦችን፤ የብሄር አለቃዎችን እየመረጠ አለሁልህ፤ ይላል። 'ድጋፍ ከሰጠህ ትበላለህ፤ ትኖራለህ፤ ትሰራለህ፤ ትማራለህ፤ ካልሰጠህ ወዮልህ' የሚል ነው። የሰውን ስነልቦና ገምቶ "ለከፋፍለህ ግዛው" አሰራሩ የብሄር ጥላቻን ይጠቀምበታል ማለት ነው። ተባባሪነት፤ ዘር፤ ሃይማኖት፤ ጾታ፤ አይለይም። የበላይ ወሳኞች ይህን ስልት ነው የሚጠቀሙት።

ወደኋላ ሄደን ስናይ፤ የንጉሱን ስርአት ለመጣል፤ ብዙ የተማሩ ኢትዮጵያውያን፤ ከጀርባ ያለውን ኃይል ሳይመረምሩ ለጠባብ ኅሰኛ/ብሄርተኛ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ድጋፍ ሰጥተው አሁን ለደረሰው ከኅሳ ፖለቲካ ለመጣ ቀውስ አስተዋፆ አድርገዋል። ህወሓት ደርግን ተቃውሞ በተሰማራበት ወቅት ያን አሰቃቂ መንግሥት ለመጣል ሲባል ብዙዎቻችን ከጠባብ ኅሰኞች ጋር አብረን ተሰልፈናል። ደርግ አገር ወዳድና ትውልድ የማይተካቸውን መሪዎች፤ የሰራዊት እዝ አባላት፤ ምሁራንና ወጣቶች ገድሏል። በጀርባ የመጣ በኅሳ፤ በጠባብ ብሄርተኛነት ርእዮት የተበረዘ ቡድን በቀጥታም ሆነ በድብቅ አጠናከሯል። ይህ ያላሰብነውም ሆነ ያሰብነው ድጋፍ የእርስ በእርስ ቂመኝነትንና አለመግባባትን እንደ ጠቃሚ ፖለቲካ ባህል ተከሎብናል። የመንፈስ ሽባ አድርኅናል። ከላይ እንዳቀረብነው፤ ህወሓት ኢትዮጵያን የሚፈታተን እቅድ ያወጣው ጣሊያኖች፤ አረቦች፤ ሻቢያና ሌሎች ሲያስተጋቡት የነበረውን የኢትዮጵያን ግራ ክንፍ የከፋፈለውን የብሄረሰቦች ጥያቄ አወላግዶ በህገመንግሥት በመቅረጹ ነው። ከበፊቶቹ መንግሥታት በጣም የተለየና አስከፊ ነው። "የአሁኑ የወያኔ ሥርአት ከሶሻሊዝም ተቃራኒ.. ኅሳን መሰረት ያደረገ፤ ሌሎችን ኅሳዎች በኢላማነትና በተጠቂነት መድቦ ፋሽዝምን ወደ መገንባቱ ሂደት መሸጋገሩና ይህም ለሁሉም እያሰጋ መምጣቱ ግልጽ ነው።" እየለየ የአማራውን ብሄር የሚያጸዳ አገዛዝ ብዙም ከፋሽስቶች አይለይም። ይህን የሚያደርገው "በቅጥፈት፤ በውሸት" ሌላውን በመዝለፍና በማዋረድ ነው። "ህዝባዊ ሓርነት ትግራይ አማራዎች ከድሮ፤ ከጥንት ጀምሮ የትግራይ ሕዝብ ጠላቶች ናቸው፤ እነኚህ አህዮች ከአገራችን ይውጡ፤ ትግራይ የራሳችን ነጻ አገር ነች"። 24/

አጼ ቴዎድሮስ የለውጥ ሃዋርያ ነበሩ

"አማራ የትግራይ ሕዝብ ዋና ጠላት ነው" የሚለው የህወሓት አርማ በ1991 የተገበየ አይደለም። ከጣሊያን ቅኝ ገዢዎች ፈለግ የመጣ የኢትዮጵያውያን ምሁርና ነን ባይ ፍጥረት ጭምር ነው። "ባርነትን ለማቆም" ጥረት ያደረጉትን አጼ ቴዎድሮስ "ጨካኝ፤ ክፉና ሙሰኛ" ይሉ የነበረ የኢትዮጵያ፤ የኤርትርያ፤ የትግራይ ምሁራን ያባባሱት የብሄር ጥላቻን ነው። ሃቁ፤ ከማንኛውም የኢትዮጵያ መሪዎች በላይ፤ የኢትዮጵያን አንድነት፤ የመሬት ስሪት አግባብነት፤ የሃይማኖት ዘመናዊነት አስፈላጊነት፤ የጦር ሃይል ብሄራዊነትንና ዘመናዊነት፤ የፍትህን አስፈላጊነት" ያስተጋቡት አጼ ቴዎድሮስ ናቸው። እኒህን አገር ወዳድ መሪ እንደ "ጭራቅ" አድርጎ ማቅረብ የተፈለገበት ዋና ምክንያት አማራውን ለመኮነን፤ የትግራይን የበላይነት በአዲስ መልክ ለማቅረብ ነው። የኢትዮጵያን ታላቅነት በዘመናዊ መንገድ ለማመቻቸት የፈለገጉትንና ታላቅ ትእይንት የነበራቸውን ንጉሠ ነገሥት ማዋረድ ኢትዮጵያን ለማዋረድ የታሰበ የጠባብ ኅሰኞች ምሁራን እቅድ ነበር። ህወሓት የዚህ እቅድ ሸማችና ተጠቃሚ ሆኗል። ከሁሉም በላይ፤ አጼ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምኅርትና እውቀት ያስፈልጋታል የሚሉ ታላቅ መሪ ነበሩ። ታላቅነታቸውንና ታሪክ ለዋጭነታቸውን ለማወቅ ኅንደሬ መሆን አያስፈልግም። የትግራይ ጠባብ ኅሰኞች ለመቀበል ያልቻሉት፤ አማራ የሆኑት አጼወች ከሁሉም በላይ

የፈለጉት የኢትዮጵያን ታላቅነት፤ ግዛታዊ አንድነት ነው። አጼ ዮሓንስ ኢትዮጵያዊ መሪ እንደሆኑ እናምናለን። ኢትዮጵያን ከውጭ ጠላቶች ለመከላከል ከታገሉ መሪዎች መካከል አንዱ ናቸው። ከእንግሊዞች ጋር የምስጢር ውሎች መዋዋላቸው ታላቅነታቸውን አይፍቀውም። የትግራይ ምሁራንና ህወሓት ይህን ሲክዱ ከመገረም በላይ ለነሱ ተከታይ ትውልድ ማሰብ ያስፈልጋል። የኢትዮጵያን ነገሥታት የሚያዋርዱ ምሁራንና የጠባብ ጎሰኛ የፖለቲካ መሪዎች የተከሉት ባህል በልዩ ልዩ መልክና ጠባይ መንጸባረቁን ቀጥሏል። የትግራይ፤ የኦሮሞ፤ የወላይታ፤ የአጋዴን፤ ወዘተ የበላዮች (Elites)የሚጋሩት አማራውን መጥላት ሆኗል። የማይረዱት ቁም ነገር አለ። በማንም አገር የጥላቻ ፖለቲካ የትም እንዳላደረሰ ነው። የዩጎስላቪያን፤ የሱዳንን ወዘተ መፈራረስ ማየት ይበቃል። የጥላቻ ፖለቲካ የሚመራው ወደ መበታተን ብቻ ነው። መበታተን ድህነትን ይፈጥራል።

የብሄር ጥላቻ ፈላስፋዎች የሚጋሩት፤ ደሃው አማራ እንደ ጨቆናቸው፤ እንደ ገዛቸው፤ ጥቅማቸውን እንደ ከለከላቸው ነው። ወዳጀ ዶር ተኮላ ሃጎስ አጼ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት መሆን የለበባቸውም ነበር ሲል የሰጣቸው ምክንያቶች አስደንቀውኛል። ያስደነቁኝ ከአንድ ምሁር ስለማይጠበቁ ነው። "አካለ ጎደሎ ነበር፤ ጽዳት የለውም፤ ከመደበኛ ጋብቻ ውጭ የተወለደ ነበር።" ዘመናዊ ትምኅርት ካገኘ ምሁር የሚጠበቅ አይደለም። የአሜሪካ ፕሬዘደንት ሮዝቬልት ሽባ ሆኖ አሜሪካን ገዝቷል። አጼ ምኒልክ የትግሬ ተወላጅ ባለመሆናቸው ታላቅነታቸውን መግፈፍ ድንቁርና ነው። ለጠላቶች መሳሪያ ይሆናል። አጼ ዮሓንስ የትግራይ ተወላጅ በመሆናቸው፤ ስለሳቸው ደካማ ጎን ጎንደሬ ወይንም ሌላ አማራ፤ የፈጠራ ታሪክ አይናገርም። የትግራይ ረሃብተኞች--ብዙ በህይወት ያሉ ጎንደሬዎች ህጻን በነበሩበት ወቅት--ጎንደር መጥተው ስለለመኑ፤ ትግሬዎች "ሰነፎች፤ ደሃወችና ስደተኞች ናቸው" አላሉም። ጊዜው "የፈጠራቸው ችግርተኞች" እያሉ የተቻላቸውን ድጋፍ አድርገዋል። በእውነተኛ እኩልነት እምነት ያለው ምሁር ሌላውን አያዋርድም። ታሪክን ለጠባብ ጎሰኛነት ጥቅም አይበርዝም። ከፍተኛ ትምኅርት ለከፈተኛ አስተሳሰብ ቁልፍ ነው። አጼ ቴዎድሮስ፤ አጼ ዮሓንስ፤ አጼ ምኒልክ፤ አጼ ኃይለ ሥላሴ ችሎታ ባይኖራቸው ስልጣን አይዙም ነበር። አጼ ምኒልክ በችሎታቸው ብቻ ከልዩ ልዩ ብሄረሰቦች የተመለመሉ ሃላፊዎችን መሰብሰባቸው አስደናቂ ነው። ህወሓት ይህን አያደርግም። የአማራ ተወካይ የማይባለው አይሁዲ፤ ሃጋይ ኤርሊክ የመዘገበው፤ አጼ ምኒልክ፤ የችሎታ መሰፈርት ተጠቅመው (On the basis of individual merit) ከሁሉም ጎሣዎች ተቀባይነት ያላቸው መሪዎች እንደሰበሰቡ ነው። ዘመናዊ ኢትዮጵያን ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች የሚለያት፤ መሪዎቿ በአንድነት፤ በችሎታ፤ በሁሉን- አቀፍነት መምራታቸው ነው። ህወሓት/ኢህአዴግ በችሎታ አያምንም። የጎሳ ፌደራሊዝም በችሎታ አያምንም።

ጆርዳን ገብረ መድህን፤ በረከት ሃብተሥላሴና ሌሎች ጠባብ ጎሰኛ ምሁራን የሚጋሩት አንድ ነገር አለ። ኤርትራያን ከእናት አገሯ መነጠልና ኢትዮጵያን ለመጀመሪያ ጊዜ የባህር በር አልባ ማድረግ። ሌላው የሚጋሩት በጭቁን ብሄረሰቦች ስም ጎሳ-ተኮር ፌደራሊዝም እንዲቋቋም አስተዋጾ ማድረጋቸው ነው። ጆርዳን ገብረ መድህን "ኤርትርያዊያንና ውሻዎች ከዚህ ሆቴልና መመገቢያ ሊገቡ አይችሉም" የሚለውን የጣሊያን ዘረኞች ማስታወቂያ ያየው አይመስልም። ሌሎችን ኢትዮጵያውያን ከእንደዚህ ያለ ውርደት ነጻ ያደረጓቸው ደፋርና አገር ወዳድ መሪዎች እነ አጼ ቴዎድሮስ፤ እነ አጼ ዮሓንስ፤ እነ አጼ ምኒልክ፤ እነ አጼ ኃይለ ሥላሴ መሆናቸውን እረስቶታል። ድህነትና የአገር ኋላ ቀርነት አገር ወዳድነትንና ጀግንነትን አይበርዝም።

ለትግራይ ሆነ ለሌሎች ክልሎች፤ በአንድ በኩል፤ በእኩልነትና በፍትህ የተመሰረተ ዲሞክራሳዊ አገዛዝ መገንባት፤ በሌላ በኩል፤ የጎሳ ጥላቻን መሳሪያ አድርጎ አገርን መከፋፈል፤ ስልጣን ተጠቅሞ መዝረፍ የተለያዩ ሂደቶች ናቸው። አገርን የሚወድ፤ ታሪኩን የሚያከብር አመራር በጥላቻ አይገዛም። የህወሓት አመራር፤ መለስን ጨምሮ፤ ስለአገሩ ታሪክና ጀብዱ ከሚያውቀው የበለጠ፤ የአሜሪካ ስለላ ድርጅት የሚያውቀውን መማር የመረጠ ነው። የህወሓት አለቆች አሁንም በጭፍን ከጥላቻዎች ላይ ያተኩራሉ። ተተኪውን ትውልድ ጥላቻ ያስተምሩታል። የአገሩን ትክክለኛ ታሪክና ልምዶች እንዳያውቅ፤ በውጭ ባህል እንዲበከል ይመሩታል። ስርቆት፤ ቅጥፈት፤ አድልዎና ሙስና እንደ ዘመናዊ ባህል አድርገው ያስተምሩታል። "የህወሓት መሪ መለስ ዜናዊ በኤርትራ ሕዝብ ታሪክና ትግል በርካታ ጽሁፎችን አቅርቧል። በተለይም ሁለት ትልልቅ መጽሃፍቶች--አንዱ ስለ ኤርትራ ሕዝብ ትግል። ሌላው ስለ ቻይና፤ ሩሲያ/ቬትናምና አልባኒያ ሕዝብ ታሪክና ትግል። "አገሬ ናት ብሎ ስለ ኢትዮጵያ አንድ ቀንም ጽፎ ሲያስተምር አናውቅም"። እንዲያውም፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ መሰዋእት የሆነውን፤ ከትግራይ ሕዝብ ጋር ሆኖ በተከታታይ የውጭ ጠላትን የታገለውን አማራ አዋርዷል። የኢትዮጵያ የአንድነት ታሪክና የአማራው ሕዝብ ታሪክ አንድ መሆናቸውን ክዷል። የራሱንም ጎሳ እውነተኛ ታሪክ በርዟል። ለሃያ አንድ አመታት ኢትዮጵያን በአምባገነንነት የገዛው መለስ የኢትዮጵያን "ሰንደቅ አላማ ጨርቅ ነው፤" ኢትዮጵያዊያን የሚኮሩበትን "የአክሱም ሃውልት ለከምባታውና ለኦሮሞው ምኑ ነው" የሚለውን አዲስ ፍልስፍና ተጋርቷል። ስልጣን ተጠቅሞ ሁሉን አውቃለሁ ባይ የጠባብ ብሄር ትምክህተኛ ነበር። ይህ ሁሉ ተደምሮ የሚያሳየው፤ ልክ እንደ ጣሊያንና እንደ ሻቢያ፤ የህወሓት የበላይ አመራር ፀረ ኢትዮጵያና ፀረ አማራ፤ ፀረ አንድ የተዋህዶ

ቤትክርስቲያን መሆኑን  አሳይቷል። አንድ የትግራይ ተናጋሪ ኢትዮጵያዊ ጸሃፊ ያለው ተገቢ ነው። "የወደብ ማጣት፤ ውድቀት፤ ውርደት፤ ሞትና ጦርነት በሃላፊነት የሚጠየቁት የህወሓት መሪዎች ቢሆኑም በመለስ ሳምባ ለሚተነፍሰውና በመለስ ጭንቅላት ለሚንቀሳቀሰው ለህወሓት መኖርና ውድቀት ወሳኙ መለስ ዜናዊ መሆኑን ለክርክር የሚቀርብ አይደለም። የህወሓት ፀረ ኢትዮጵያዊነትና ፀረ አማራነት በስፋትና በመረጃ አስደግፌ ወደተከራከርኩበት መጽሃፌ ይዣችሁ ልግባ" እያለ ማስረጃ አቅርቦልናል። 25/

ጸሃፊው እንዳለው፤ እኔ እስከማስታውሰው ድረስ፤ ህወሓት እወክለዋለሁ የሚለው የትግራይ ሕዝብ በጎሳ፤ በቋንቋ፤ በሃይማኖት ልዩነቶች የተበከለ አልነበረም። የመንደረኛነት ባህሪይ አልነበረውም። በመላው ኢትዮጵያ ሰፍሮ፤ ተጎራብቶ፤ ከሌላው ጋር ተጋብቶ፤ ትምህርት ቤት ገብቶ፤ ነግዶ፤ አርሶ፤ ጸልዮ በኢትዮጵያዊነቱ ኮርቶ የሚኖር ሕዝብ ነበር። ይህን ያፈረሰው የህወሓት ጠባብ ጎጠኛ አመራር ነው። የጎሳ ፌደራሊዝም አገርን በመከፋፈል፤ ብሄራዊነትን በማድከም፤ ሌላው ቀርቶ ለኢትዮጵያ አንድነት ኢጋር የሆነችውን ትግራይ "ቅኝ ግዛት ናት" በማለት ራሱን ከድቶ የትግራይን ሕዝብ እንዲከዳ ያስገደደ አመራር ነው። ይህን ሁሉ ያደረገው ለእኩልነት አይደለም። ለጠባብ ጎሰኛ ለሆነ ቡድን የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት ነው። ይህ አደጋ የሚመጣ መሆኑን ያወቁ ኢትዮጵያውያን ለምን ሻቢያን፤ ህወሓትን ኦነግንና ሌሎችን የጠባብ ጎሰኛ ድርጅቶችና አመራሮች ደገፉ፤ አሁንስ ለምን ይደግፋሉ ብለን መጠየቅ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም፤ አደጋው እየከረረ እንጅ እየቀነሰ አልሄደም። "ሁሌም የሚከነክነኝ ነው። እኛ ትግሉን ስንጀምር ትኩረታችን በትግራይ ሕዝብ ትግል ብቻ ነበር…ዲሞክራሳዊት ኢትዮጵያን ከመሰረትን ችግሩ ይፈታል ብለን ገምተን ነበር፤ ሆኖም የብሄር ጥያቄ እስስታዊ ጠባይ አለው…ማንም ሰው ለሥልጣን መወጣጫ ለማድረግ ወደፈለገው አቅጣጫ ሊጠመዝዘው የሚችል የትግል መርሆ ነው።" አብሮ የሚጎዳው ቆመንልሃል የሚሉት ሕዝብ መሆኑ አልታወቀም ነበር ። "ይኼውና የትግራይ ሕዝብ ባደገበት መንደር በገዛ አገሩ በፍርሃት የሚጨነቅበትና የሚሰጋበት ኀይወት ከመምራቱ ባሻገር፤ በተቀረው ኢትዮጵያዊ ወንድሙና እህቱ እንደ ባእድ፤ እንደ ፀረ-ኢትዮጵያዊ ሆኖ የሚታይበት የባህር ወደቦቹና ዳር ድንበሩ ለጠላት አሳልፎ የሚሰጥ ከሃዲ ተደርጎ እንዲታይ አድርጎታል።" የህወሓት አመራር፤ ከጅምሩ፤ "አማራን በማእከላዊ ጠላትነት በመፈረጅ፤ የራሱን ጎሳ በማስቀደም" አገሪቱን አድክሚታል። "የማያጠራጥረው፤ በአጠቃላይ ሲታይ፤ ትግሬዎች ጠባብና ትምክህተኛ፤ ራስ፤ ገንዘብ፤ ቁሳቁስና ስልጣን ወዳዶች ናቸው።" የህወሓት አመራር ያጠነከረው ይህን ጠባብ ከጥቅም ጋር የተያያዘ የበላይነትን ነው። የዚህ የጠባብ ብሄር ትምክህተኛነት ጥቅም ከፍተኛ ስለሆነ የህወሓት አመራር ጥላቻውን ይቀጥልበታል። 26/

ሆኖም፤ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ መከፋፈሉን ካልፈለገ ስርአቱን ለመቀበል አልችልም ለማለት መድፈር አለበት። የተከፋ ሕዝብ ቅጣትን ሁል ጊዜ ተቀብሎ ሊኖር አይችልም። ክብር አይኖረውም።  የተቃዋሚው ክፍል አሁንም የተበከለበት ወጥመድ የጎሳ ፖለቲካ ነው። አብዛኛዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተቋቋሙት በኢትዮጵያዊነት መለያ ሳይሆን በጎሳ መለያ ነው። ይህ የፖለቲካ አደረጃጀትና አመራር ከፍተት ባይኖር ጠባብ ብሄርተኛው ቡድን፤ ህወሓት፤ የፖለቲካ የበላይ፤ የኢኮኖሚ ሙሉ-በሙሉ ተቆጣጣሪ ሊሆን አይችልም ነበር። አገር ወዳዶችን በጋራ አጥፍተን በከፈትነው ክፍተት የገባውና የተጠቀመው ጎሰኛው ህወሓት ነው። አሁንም ቢሆን ይህ የመከፋፈልና የቂም በቀል ባህል የኢትዮጵያን ሕዝብ እያደማው ነው። ለዚህ ድክመት ገና ብልሃት አልነደፍንለትም። የጎሳ ፖለቲካ አለማዋጣቱን እያየን አሁንም በጎሳ የፖለቲካ ዓለም የምንኖር ብዙ ነን። ችግሩ ሁሉን የሚመለከት መሆኑ እየገባን የምናተኩረው ከልዩነቶቻችን ላይ እንጅ በጋራ ከምንጋራቸው እሴቶች ላይ አይደለም። አገር ውስጥና ውጭ የተቋቋሙ ከዘጠና በላይ የሚሆኑ የብሄር ፖለቲካ ድርጅቶችን ማየት በቂ ነው። ዘጠና ፓርቲ ማለት ዘጠና ጊዜ ተከፋፍለናል ማለት ነው። በብሄረሰብ እኩልነት ተመካኝቶ፤ ዘፈኖች ስለተዘፈኑ፤ በዓሎች ስለተከበሩ፤ ልብሶች ስለተለበሱ፤ ቋንቋዎች ተከብረው ወጣቶች በቋንቋቸ ስለተማሩ፤ እኩልነት አለ የምንል ብዙ ነን። እነዚህ የእኩልነት መስፈሪያዎች መጠበቅ፤ መቀጠል አለባቸው። ጠባብ ጎሰኛው ህወሓት የእውነተኛ የብሄረሰብ እኩልነት አርአያ ሊሆን አይችልም። በአጼ ኃይለ ሥላሴና በደርግ መንግሥታትም የቋንቋና የባህል እኩልነት ተከብረው ነበር። ደርግ የብሄረሰቦች ተቋም አደራጅቶ ነበር። ታዲያ የህወሓት/ኢህአዴግ ታርካዊ ለውጥ የት ላይ ነው? የፌደራል አስተዳደርን ጥቅም ዲሞክራሳዊ በሆኑ አገሮች የምንኖር ሁሉ አይተናል። ዘጠና ዘጠኝ በሙቶ የሚሆኑት የጎሳ አደረጃጀት አይጠቀሙም። ፌደራላዊ አስተዳደር የሚከተሉ ዲሞክራሳዊ አገሮች፤ በአብዛኛው፤ ቋንቋ ተጠቅመው፤ በማይታረቁ ልዩነቶች ላይ ትኩረት አያደርጉም። የሚጋሯቸውን ያጠናክራሉ። የአናሳ ብሄረሰቦችን መብት በሕግ ይጠብቃሉ። ካናዳዊው እንግሊዘኛ ተናጋሪ በፈረንሳይ ተናጋሪዋ ኩቤክ ስለኖረ ካናዳዊ አይደለም ማለት ቅዠት ነው። ካናዳውያን ፌደራላዊ ስርአት የፈጠሩት፤ ከፈለግህ ልትገነጠል ትችላለህ ብለው አይደለም። አብሮ መኖር ከመገንጠል በላይ ዋጋና ጥቅም አለው ብለው ነው። በማንም ፌደራላዊ አገዛዝ፤ ማንም ፓርቲ፤ የአንድ ብሄረሰብን ቁጥር ሆን ብሎ ለመለወጥ የሞከረ የለም። ህወሓት የአማራውን ቁጥር ሆን ብሎ ቀንሷል። የብሄር ማጽዳት በረቀቀ ሁኔታ የሚያካሂድ መንግሥት ህወሓት የመጀሪያው መሆኑ ነው። የበላይነት ይዞ የዘር ማጥፋት

ዘመቻ ለማካሄድ የቻለው ብቻውን አይደለም። ሌሎችን በማንበርከክ፤ አጎብዳጂና ደሃ በማድረግ ነው። አማራን ማዋረድና ማዋከብ የኢኮኖሚ ጥቅም አለው። መረሳት የሌለበት፤ በተከታታይ መዋረድ ያደክማል።

ይህን የሚገልጽ አንድ ተረት አለ። አይጥ በክረምት ጉድጓዷን ቆፍራ ትገባለች። ሲርባት ወጣ ትላለች። እባብ ከፊቷ ታያለች። "ለምን ወጣሽ" ሲላት፤ "ምግብ ለመሰብሰብ" ትላለች። "በይ ሰብስቢ" ብሏት ባለበት ይቆያል። ሰብስባ ስትመጣ ድንጋዩ ወደቤቷ እንዳትገባ ያግዳታል። እባብን "እባክህ እርዳኝ፤ ድንጋዩን አልቻለውም" ትለዋለች። አስገርሞት "አንች ቂል፤ ከመጀመሪያውም እባብ መሆኔን ረስተሽ ነው" ብሎ እራት አደረጋት። ዛሬ ሁሉም የህወሓት ራት እየሆነ ነው። አፈናውን ያልቀመሰ ጎሳ የለም። ህወሓት በአማራ ሕዝብ ላይ የሚያደርገው ግፍ አስፈጻሚዎች አሉት። አነግ አንዱ መሳሪያ ነው፤ አብዛኛው የኦሮም ሕዝብ የማይጋራውን የአማራ ጥላቻ አስፈፃሚነት። ህወሓት የሚያፍነው አጎብዳጅ የሆነውን የአማራ ጎሳ የፖለቲካ ድርጅት ተጠቅሞም ነው። ኦሮሚያም የሚያደርገው በተመሳሳይ ነው። ይህን አወቃቀር የዲሞክራሳዊ መብት ይለዋል። የጎሳ አጎብዳጅ አደረጃጀት ሊለው አይችልም። የአይጥና የእባብ ታሪክ ይመስላል። አጎብዳጁ ነጻነት ያገኘ መስሎት አሜን ይላል። ቀስ በቀስ ይበላል።

ህወሓት፤ ለራሱ ጥቅም ሲል፤ የፈጠረውን የአማራውን ብአዲየንን ስናይ፤ የአማራን ህብረተሰብ ማገልገል ቀርቶ የራሱን፤ የአባላቱን ጥቅምና ስልጣን ለማስከበር አልቻለም። አይችልም። ለምሳሌ፤ መለስ የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን መንግሥት ስጥ ሲለው፤ የክልሉ አመራር "እሽ" ብሎ ፈርሟል። አብዛኛው መሬት የአማራ ክልል ነው። አጎብዳጅና ታዛዢ እንዲሆን የተፈጠረ ድርጅት፤ የክልሉን ጥቅም፤ የህብረተሰቡን መብት ለማስከበር ነጻነት የለውም። ወልቃይት ጠገዴ፤ ወዘተ ለትግራይ ክልል ሲሰጥ፤ በህወሕት አባላትና የትግራይ ተወላጆች ተደፍሮ ሲታረስ፤ የአማራ ህብረተሰብ ነህ ተብሎ ብዙ ሽህ አማራ ከሚኖርበት ሲሰደድ፤ ቤቱ ሲቃጠል፤ ንብረቱ ሲወድም፤ ኑሮው ሲናጋ ይህ የጎሳ ድርጅት የት ነበር ተብሎ የሚጠየቀው ለዚህ ነው። ዋልድባ የአማራ ብቻ አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ መታወቂያ እንቁ የሆነ ጥሪት ነው። መተኪያ የለውም። እንደለመደው፤ ህወሓት በልማት ስም ሲያርሰው፤ ፓርቲው የህወሓት ፍጥረት አጎብዳጅ ሆኖ ተገኝቷል። ይህ የሚያሳየው አንድ ነገር ቢኖር፤ የትም ቦታ፤ የብሄር የፖለቲካ ድርጅቶች የመወሰን መብት የላቸውም። የሚያገለግሉት የፈጠራቸውን ህወሓትን  ነው። ህወሓት ከሌለ እነሱን አይኖሩም። እንዲኖር ማገልገል አለባቸው ማለት ነው። እንወክልሃለን የሚሉትን ህብረተሰብ አያገለግሉም። በጋምቤላ፤ በኦሮሚያ፤ በአማራ፤ በደቡብ፤ ወዘተ የሚታየው ሰእል ተመሳሳይ ነው። ስለዚህ፤ አገር ውስጥና ውጭ ያለው የጎሳ ፖለቲካና የክፍፍል አስተሳሰብና ስነልቦና፤ ለህወሓት ጠቃሚ መሳሪያ ነው። የተቃዋሚ ክፍል ትርጉም ሊኖረው የሚችለው ይህን "የከፋፍለህ ግዛው" ጠቢብ አንቀበልም፤ ቀፎ ነው ብሎ፤ ከጎሳ በላይ የፖለቲካ ባህልን ሲፈጥር፤ ከጎሳ በላይ በእውነተኛ ዲሞክራሲ፤ በእውነተኛ እኩልነት የተመሰረተ አማራጭ ለህብረተሰቡ ሲያቀርብ ነው። ለዚህ አማራጭ  አለመተባበር የድክመትን ጥልቀትና ስፋት ያሳያል።

የቋንቋ ልዩነት ለባለ ጠጋነት (ከበርቴነት) ማካበቻ ምንጭ ሆኗል

ማንም ኢትዮጵያዊ በራስ ቋንቋ መናገርን ይቃወማል የሚል ግምት የለኝም። የረሳነው ህወሓት ራሱን አጠንክሮ ለማቆየት ቡድኑና ደጋፊዎቹ ሃብት የሚያካብቱበትንና የሚጠቀሙበትን መንገድ የሚያቃና፤ ደንቡን የሚያመቻች፤ ሕጉን የሚጠመዝዝ፤ በቋንቋ ልዮነቶች የመሰረተውን የክልል አስተዳደር በከፍተኛ ደረጃ ለራሱ ጥቅም ያዋለ ነው። ከራሱ ቡድን ውጭ የሆኑ ወይንም የሚቃወሙ፤ ወይንም ተፎካካሪ የሆኑ ሁሉ መድረሻና መወዳደሪያ መስክ የላቸውም። አይፈቀድላቸውም። ከተፈቀደላቸው በህወሓት ማመንና ደጋፊ መሆን አለባቸው። የመስራት ነጻነት የላቸውም። የህወሓት አመራር ብልሃቱን አውቆበታል። የበላይነትን ለመጠበቅ ተወዳዳሪን አጎብዳጅና ደካማ ማድረግ ያስፈልገዋል። የቋንቋን ልዩነት የሚጠቀመው አ፟ኩን ስለወደደ አይደለም። ቢወደው ከአንጡራ መሬቱ አያባርረውም ነበር። አቅሙን አጎልምሶ እንዲያመርት ይረዳው ነበር። ነጻነቱን በተግባር ለማሳየት የሚሞክር የአ፟ክ ህብረተሰብ ኢትዮጵያዊ ዞሮ ዞሮ ዋጋ ይከፍላል። በታከስ፤ በጉምሩክ፤ በመሬት ነጠቃ ወዘተ። ህወሓት፤ በቋንቋ የተሳሰረ፤ የግል ኩባንያ የመሰለ መዋቅር፤ ግልጽነት የሌለው አመራር፤ የምስጢር ባህል ልክ እነደማፊያ ወደ ሳይንስ የለወጠ ኮርፓሬሽን ነው። የዚህ አይነት ከቋንቋ ክፍፍል የመጣ የበላይነት ባህል ስር እንዲሰድ ያደረገውና ሁሉን አጎብዳጅ ያደረገው ፍትህ፤ እኩልነትና ዲሞክራሲ እንዲሰፋፋ፤ ስልጣን በያዘበት ጊዜ የገባውን ቃል ስራ ላይ ለማዋል አይደለም። የገባው ቃል ምን ነበር? እኩልነትን፤ ፍትህን፤ ዲሚክራሲን ለመገንባት ነበር። "በመለስ ዜናዊ የተመራው ኢህአዴግ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ባህል ከመሰረቱ ለውጦታል።" ("The EPRDF, led by its chairman and prime minister, Meles Zenawi, has radically reformed Ethiopia's political system…redefined citizenship, politics and identity on ethnic grounds.")  ይህ እምርታዊ ለውጥ የታሰበው ለአናሳ የትግራይ ብሄረሰብ የፖለቲካ የበላይነት ብቻ አይደለም። የኢኮኖሚ፤ የተፈጥሮ ሃብት የበላይነት ለማመቻቸት ነው። ግጭት ፈጣሪ መሆኑ አያከራክርም። የተዛባ የገቢ፤ የሃብት

ልዩነቶች ፈጣሪ መሆኑን አይተናል። ይህ ጸረ-ፍትህ፤ ጸረ-እኩልነት የሆነ አገዛዝ ካልተለወጠ፤ የአገር ውስጥ አለመረጋጋት እየተባባሰ ይሄዳል። መድብለ-ፓርቲ አስፈላጊ የሚሆነው ለዚህ ነው። **"Without genuine multi-party democracy, the tensions and pressure in Ethiopia's politics will only grow, greatly increasing the possibility of a violent eruption that would destabilize the country and the region." 27/**

ጎሳ-ተኮር የቋንቋ ፌደራሊዝም ለፍትሃዊ እድገት ጥቅም አለው የሚሉ አሉ። ሃሳባቸውን እናከብራለን። የማያዩት ለፍትሃዊ እድገት ማነቆ መሆኑን ነው። በጎሳዊ ስርአት ግልጽነት ያለው የኢኮኖሚ ውድድር የለም። ለገዢው ፓርቲ ታዛዥ ያልሆነ ጎሳዊ ፓርቲ ከበላዮች ውጭ ገቢንና ጥቅምን የማዳረስ ሚናው የተወሰነ ነው። የህወሓት መሪዎች ለታዛዢነትና ለአጎብዳጅነት ትልቅ ዋጋ የሚሰጡት የኢኮኖሚ ዋጋ ስላለው ነው። አጎብዳጅ ድርጅት ወይንም ግለሰብ የመንቀሳቀስ፤ የማንቀሳቀስ ነጻነት እንደሌለው ያውቃሉ፡፡ ነጻነቱ የተከለከለ፤ በራሱ አይተማመንም። ስርአቱን ቢቃወምም በግሉ፤ በሆዱ፤ በወዳጅና ታማኝ ዘመዱ ዙሪያ ብቻ ነው። በምእራፍ ሁለት እንዳሳየነው የሰብአዊ መብቶች ሙሉ በሙሉ መከልከል ለዚህ የኢኮኖሚ ገደብ ያገለግላል። "በነጻነትና በእድገት መካከል ምንም ግንኙነት የለም" ብሎ የህወሓት አመራር ያወጀው ሌሎችን ከኢኮኖሚው ውድድር ለማስወገድ፤ ውድድርን ለመቀነስ፤ የበላይነትን ለማረጋገጥ ነው። በትምክህተኛነት የታነጹት የትግራይ መሪዎች ከእኛ ሌላ አገሪቱን ለማልማት ችሎታ ያለው የለም ብለው ያምናሉ። አባባሉ ለራሳቸው ጥቅም ያገለግላል። የኢትዮጵያን ነጻነት ያቆዩት ስግብግብ ትምክህተኞች አይደሉም። የመጀመሪያውን ሃዲድ የዘረጉት ትምክህተኞች አይደሉም፤ የኢትዮጵያን አየር መንገድ ኢትዮጵያዊ ያደረጉት ትምክህተኞች አይደሉም። ጠባብ ትምክህተኛነት የሚያገለግለው ስግብግብ የሆኑ ጠባብ ጎሰኞችን ነው ለማለት የምደፍረው ለዚህ ነው። እስኪ ህወሓት በአንደኛነት፤ ከጽንሰ ሃሳብ እስከ ተግባር የሰራውን ነገር ይናገር። እስኪ በግልጽነት ማን የምን ባለጠጋ እንደሆነ ለሕዝብ ይግለጽ። እስኪ እያንዳንዱ አዲስ ሃብታም ያለውን ካፒታልና ከየት እንደመጣ ለሕዝብ ይፋ ያድርግ። እስኪ ኤፎርት ምን ያህል ካፒታል እንዳለውና ምን ያህል ቀረጥ እንደከፈለ ይፋ ያድርግ፤ ወዘተ። ወደ ኋላ ሄደን ስናይ ሃቁ የመሰረተ ልማት እቅዶች በአብዛኛው የተጸነሱት በአጼ ምኒልክ፤ በአጼ ኃይለ ሥላሴና በመንግስቱ ሃይለማርያም መንግሥታት አመራርና በኢትዮጵያ ጠበብቶች (Experts) ነው። ጉቦ መኖሩ ባያከራክርም እነዚህ መንግሥታት፤ በአብዛኛው፤ በአድልዎ፤ የመንግሥትን ካዝና እንደ ግል ካዝና በመጠቀም፤ ሙልጭ ባለ ምዝበራ አልታወቁም። ህወሓት እድለኛ ሆኖ "ተአምራዊ እድገት" አሳየ የተባለው የምእራብ አገሮች ስለደገፉትና ከአርባ ቢሊዮን ዶላር በላይ የእርዳታ ፈሰስ ስለለገሱት ነው። የበፊቶቹ መንግሥታት ይህ ስጦታ አልደረሳቸውም። ከፍተኛ እርዳታ ሙስና እንደሚፈጥር አንጠራጠር።

ጎረቤት የሆኑት ኬንያውያን እንደሚሉት፤ ከአሁን በፊት የነበሩት የኢትዮጵያ መንግሥታት ለአገራቸው ቀና ነበሩ። የተፈጥሮ ሃብትና የአገር ቁልፍ ኢኮኖሚ ክፍሎችን ለውጭ መንግሥታትና ኩባንያዎች አላስረከቡም። ዝቅተኛም ቢሆን በውስጥ ውድድር ያምኑ ነበር። የህወሓት ቡድን በመወዳደር አያምንም። በመስማማትና ተቻችሎ ሰርቶ ትርፍን በመካፈል አያምንም። በፖለቲካው ሲታይ አመራሩ፤ በኢትዮጵያዊነቱ ኮርቶ፤ ተባብሮ፤ ተቻችሎ፤ የሁሉም ጥቅም በሕግ ተከብሮ፤ የሚኖርባትን ኢትዮጵያ ለመገንባት የተነሳ አይደለም። የስለላ መረቡ የሚያሳየው ልክ የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ የዘርጋውን <u>ተቋማዊ ፍጹም የሆነ የቁጥጥር መዋቅር ይመስላል</u> (Absolute Command and Control of the Society)። ምን ማለት ነው? በቻይና፤ ኮሙኒስት ፓርቲው ፍጹም የበላይነት አለው። ብሄራዊ ደህንነትን፤ ስለላን፤ ፖሊስን፤ መከላከያን፤ መንግሥትን፤ መገናኛ ብዙሃንን አጣምሮ ይቆጣጠረዋል። ህወሓት የቀዳውና በስራ ላይ ያዋለው ተመሳሳይ ነው። በቻይና ህገመንግሥቱ የአንድ ፓርቲን የበላይነት ያገለግላል። በኢትዮጵያም ተመሳሳይ ነው። በቻይና ተወዳዳሪ ፓርቲ አይፈቀድም። በኢትዮጵያም ተመሳሳይ ነው። በቻይና የፖለቲካ ስልጣን ለባለጠጋነት (ከበርቴነት) ቁልፍ ሆኖ አገልግሏል። በኢትዮጵያም ተመሳሳይ ነው። በቻይና በመንግሥትና በፓርቲው መካከል የሚለይ ገደብ የለም። የኢትዮጵያን የሚለየው፤ በጠባብ ጎሰኛነት፤ በፓርቲ፤ በመንግሥትና በተቋሞች መካከል ምንም ወሰን አለመኖሩ ነው። በአብዛኛው የሚለየው፤ በቻይና የኢኮኖሚ ውድድር አለ። የግል ክፍሉ ቀስ በቀስ ከመንግስትና ከፓርቲው ኢኮኖሚ ጋር ይወዳደራል። በቅርቡ ድህነት ይጠፋል፤ አገር ወዳዶች ስለሚመሩት።

በኢትዮጵያ ስግብግብነቱ (Greed) ያየለው በህወሓት አባላትና ቤተሰቦች ዙሪያ ነው። ስለሆነም፤ ምዝበራው ጎሳዊ ሆኗል። የበላይነትን ለመጠበቅ ብዙሃኑን በፍርሃት በክሎታል። ከፋፍሎታል፤ በቂም በቀል በማሰር፤ በመግደል፤ ያላጠፋውን በሃይል እያስገደደ አጥፍተሃል ብሎ እንዲያምን በማድረግ፤ በማሳደድ፤ ከስራ በማስወጣት፤ አገር ለቆ እንዲወጣ በማድረግ ወዘተ ስልጣኑንና የኢኮኖሚ የበላይነቱን አረጋግጧል። ስርአቱ ህይወቱን የሚያራዝመው በዚህ መልክና የጎሳ አስተዳደር በሰጠው ጥበብና ህገመንግሥታዊ የበላይነት ነው። የሚያስደንቀው፤ በትግሬዎች መካከል ያዳላል-የአድዋን ትግሬ ከሌላው። ሌሎች አሁንም በጎሳ መደራጀት ጥቅም አለው የሚሉት ለዚህ ይመስላል። የማይሉት፤ ጥቅሙ ለተራው ጉራጌ፤ አፋር፤ ሶማሌ፤ አማራ፤ ኦሮሞ አለመሆኑን ነው። ጥቅሙ ከላይ ሆነው

ለሚያሽከረክሩት መሪዎች (Political Elites) ነው። የጎሰኛ ፌደራሊዝምና አገዛዝ የቁጥጥር መሳሪያዎች መሆናቸው መታየት ያለባቸው ከበላይነት በሚገኝ ጥቅም ነው። ለምሳሌ፤ በደሃና ጥገኛ አገር፤ በብዙ ሚሊዮን ብር የሚገመት የመንግሥት ባጀት ለስለላ፤ ለአስተዳደር፤ ለድጎማ፤ ለጉቦ የሚያወጣው የበላይነትን ለማጠናከር ነው። ፍልስፍናው፤ ማንም <u>ሰው ለጥቅሙ ይገዛል የሚል</u> ነው። የግለሰቦችንና የሚፈልጋቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች መብቶች (Groups) በማቀብ የራሱን ጎሳዊ ቡድን መብትና ጥቅሞች አገር አቀፍ በሆነ ደረጃ ያጠናከራል። የበላይነቱን ያራዝማል። የትግራይን ክልል እስካፍንጫው አስታጥቆ፤ አማራውን ጎራዴ አትያዝ ይላል። ስልጣኑ እንዲራዘም ከሚጠቀምባቸው ዘዴዎች መካከል የክልሎች መብት፤ ሰላም፤ እርጋታ ይጠበቅ የሚል ሰው ሰራሽ ታሪክ ያስተናግዳል። ለዚህ እነ ሄርማን ኮህን "ጸጥታ እንዲኖር ከተፈለገ፤ ኢትዮጵያ በጎሳ መለያየት አለባት" ብለው ያወጡት የአሜሪካ አመራር ደግፎታል። መሳሪያ፤ እርዳታ ሰጥቶታል። ስለዚህ፤ ከአገር ግዛታዊ አንድነት፤ ከሕዝብ ሉአላዊይነት፤ ከህብረተሰብ እኩልነት የበለጠ ዋጋ የሚሰጠው ለስግብግብነት፤ ለሙስና፤ ለልዩነት፤ በአፈና ለሚገኝና ለተከበረ እርጋታ ነው። ከብሄራዊ አንድነት ይልቅ ጠባብ የቋንቋ ልዩነትን ያስቀድማል። የሚገዛው የጥቅም አንድነት ነው። አንዱ ማስረጃ በፓርቲው፤ በጦር ሃይሉ፤ በስለላው፤ በፌደራል ፖሊሱ፤ በአስተዳደር፤ በውጭ ግንኙነት ስራዎች የተሰማሩትን ባለስልጣናት በጠባብ የግል ጥቅም ማቆላለፉ ነው። በአገር ቤትና በውጭ ያሉትን የግልና የመንግሥት ተጠቃሚዎች የጥቅም እትብት የሚንጸባርቅ መተሳሰር አደራጅቷል። ለምሳሌ፤ በኢንቬስተሮች፤ በህወሓት ባለስልጣናትና ድርጅቶች መካከል ያለው መቆላለፍ የሚያመለክተው ይህን የጥቅም ግንኙነት ነው። በ March 2013 Guangdong Chuan Hui የተባለው የቻይና ኩባንያ በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ Chuanhui Industrial Zone የሚል ስያሜ ያለው የኢንዱስትሪ ማእከል እንደሚያቋቁም አስታውቋል። ይህ ስድሳ ሄክታር መሬት የሚይዝ ማእከል፤ የሲሚንቶ፤ የብረታ ብረት፤ የዲዝል፤ የመዝናኛና 99 ፎቅ የያዘ በሃየት ስም የሚጠራ ሆቴል ይኖረዋል። ስራው ሲጠቃለል የቻይናውን ስም ትቶ "የመለስ ዜናዊ ዓለም አቀፍ ሴንተር" ይባላል። ቻይና በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከፍተኛ ሚናዋን ታጠናክራለች። ህወሓት እንደ ተመኘው፤ የመለስን "አምልኮ" ዘላለማዊ ያደርጋል፤ ከኮንትራቱና ከሌላው ትርፍ ያገኛል። የማይታበለው፤ ውድድር የሌለበት የኢንዱስትሪ ማእከል ለመስራት የውሳኔ ቅልጥፍና ያስፈልጋል። ለዚህ ጠቃሚ ሆኖ ያገኘነው የጠባብ ብሄርተኛ ፓርቲ፤ መንግሥትና ተቋሞች የተሳሰሩ መሆናቸው ነው። መቆላለፉ ብዙ ጥቅሞች አሉት። አንዱ ቅልጥፍናና ስልጣን ተጠቅሞ ባለጠጋነትን ለማስፋፋት ረድቷል። ለፍትህ የሚታገሉትን ሁሉ ለመቆጣጠር፤ ለማሰር፤ ከአገር ለማስወጣት ያስችላል። ተቋሙ መሬት ያስፈልገዋል። ነዋሪው እንዲባረር የሚደረገው ለዚህ ነው። ሲባረር ግጭት መፈጠሩ ተከታታይ ይሆናል።

ይህን ገልብጠን ብናየው፤ ለአንድ አገር የቆመ መንግሥት፤ ሃላፊነቱ ለአንድ ጎሳ ወይንም የበላይ ፓርቲ ባልሆነም ነበር ከሚል ዘገባ ላይ እንደርሳለን። ለአንድ አገርና ህብረተሰብ የቆመ መንግሥት፤ የአገሩን የተፈጥሮ ሃብት አሳልፎ ለግል ጥቅምና ለስልጣን ሲል ለወጭ ሃይሎች አይሰጥም ከሚል ድምዳሜ እንደርሳለን። ይህን ያጭር ጊዜ ለጥቅም የተዘጋጀ እስስር በአገርና በሕዝብ ዲሞክራሳዊና ተሳትፎ መነጸር ስናየው አደጋው ጎልቶ ይታያል። በጠባብ ጎሳዊ የበላይነት የተደራጀ ተቋም ለምዝበራ ያመቻል። ዘላቂነት ግን አይኖረውም። ምክንያቱም፤ ስልጣንና ሃብት ያገኘው አብዛኛውን ህብረተሰብ በማግለል ነው። የታገበው ድሃ ያሰረውን ስርአት ተቀብሎ አይኖርም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘላቂ ጥቅም የሚጠበቀው በእውነተኛ ዲሞክራሲ፤ በሕዝብ እኩልነት፤ በፍትህ-ርትእ የተመሰረተ የፖለቲካ ስርአት ሲኖር ነው። ተገንጣዮች ከስሜት በመነሳት፤ ዲሞክራሳዊ ያልሆነ ስርአት ጉዳት አለው አይሉም። ኤርትራ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ በሆነች ነበር። ኦሮሞዎች "መሃይም ሁሌም የሚያውቀውን ይናገራል" እንደሚሉት፤ ተቃዋሚ ነን የሚሉ የብሄር ድርጅቶች አሁንም የሚመሩት በራሳቸው ፈጠራ አይደለም። ጣሊያኖች፤ አረቦች፤ ሄርማን ኮህን፤ ሻቢያና ህወሓት ባመጡት የጎሳና የቋንቋ ልዩነቶች ላይ ነው። እንደገና የጎንደሩን ዋርካ ምሳሌ ልጠቀም። የሁላችንም የዘር አመጣጥ ቢመረመር፤ ማንም ንጹህ ነኝ የሚል የለም። ድብልቅ ነን። የኦሮሞ ሕዝብ እንደ አማራው ድብልቅ ነው። ዋርካው አንድ ነው። ስለሆነም፤ የኦርሞ ሕዝብ ከራሱ ይገንጠል ሲባል ትርጉም አይኖረውም። አንድ አንጋፋና ታሪክ ያለው ሕዝብ ከራሱ ጋር ተጣልቶ አፍርሱኝ፤ ምንቅርቅሬን አውጡት አይልም። የሚጎዳው ራሱም ጭምር ነው። ተገንጣዮች ስሜታቸው ከሕዝብ ጥቅም በላይ ስለሆነ፤ ከግለሰብ መብት የሚመጣን ዲሞክራሲና እውነተኛ እኩልነት ዋጋ አልሰጡትም። ተሳትፏዊ ዲሞክራሲ ዜግነትን፤ የፖለቲካ ውድድርን፤ ማንነትን፤ እኩልነትን ከጎሳዊነት ወደ ኢትዮጵያዊነት ይለውጠዋል። እያንዳንዱ ኢትዮጵያ በሕግ ፊት እኩል ከሆነ ብዙ ችግሮች ይፈታሉ። ሁሉም ድምጽ ይኖረዋል። ኑሮውን ለማሻሻል የሚገታው አይኖርም። በአንጻሩ፤ በነ ሄርማን ኮህን ድጋፍ ህወሓት የቀረጸው የጎሳ ፌደራሊዝም፤ ኢትዮጵያዊነትን፤ ማንነትን የሕግ የበላይነትን አጣብቂኝ ውስጥ አስገብቷል። "ግጭትን ያባብሳል፤ አለመረጋጋትን ያመጣል" የተባለው ለዚህ ነው። በቋንቋ ልዩነቶች ላይ የተመሰረተው የጎሳ ፌደራሊዝም ተቀባይነት ያገኘው፤ የኢትዮጵያን ታሪክ በመደለዝና በማጥፋት፤ "የምኒልክ አገዛዝ" የቅኝ አገዛዝ ነበር በማለት፤ አዲስ ሰው ሰራሽ ታሪክ በመፍጠር ነው። ታሪክን አፈራርሶ በአዲስ ታሪክ መተካት ለጠባብ ጎሰኛ ቡድን ዋና መሳሪያ ሆኖ እያገለገለ እናየዋለን። የኢኮኖሚ ጥቅም አለው ማለት ነው።

አብዛኛዎቻችን፤ በኢትዮጵያ ህብረተሰብ መካከል ሲወርድ፤ ሲዋረድ የቆየ የማይካድ --ከጋብቻ፤ ከሃይማኖት፤ ከባህል፤ ከእውቀት፤ ከኢኮኖሚ ግንኙነት ወዘተ፤ የወረስናቸው ሃረጎችና የኢትዮጵያዊነት መስፈርቶች አሉን። አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን መሰረተ ሃሳብ ይቀበላል። የሚጋራው ታሪክ እንዳለው ያምናል። ኢትዮጵያ የቅኝ ገዥዎች ፍጥረት እንዳልሆነች ያምናል። የህወሓት ፈጣሪዎች አዲስ ታሪክ እንሰራለን በሚል የጮሌነት ፖለቲካ፤ የኢትዮጵያን ታሪክ እንዳልነበረ አድርገዋል። ተመሳሳይ የሆነ የአፍሪካ ታሪክ ቅልበሳ ምሳሌ ለማግኘት አልቻልኩም። "ነጠላና ጋቢ" በሚል እርእስት ዳንኤል ክብረት፤ የጎሰኛን ፖለቲካና የጠባብ ብሄርተኛ አመራር ቀፎነት ለታሪክ አስቀምጦታል። አንድ የትግራይ ተወላጅ አባት ያሉትን ሲጠቅስ፤ "እዚህ አክሱም ያልኖረ፤ ያልሰራ፤ ያልተቀበረ፤ የሰው አይነት የለም። እስኪ የአክሱምን ነገሥታት ስም ተመልከት፤ የትግሬ ይሁን፤ የአማራ፤ የኦሮሞ ይሁን፤ የአገው፤ በምን ታውቃለህ?" የጠባብ የብሄርተኛነትን አዲስ የፈጠራ ታሪክ ባዶ አድርገውታል። 28/

የህወሓት መስራቾች የኢትዮጵያ ታሪክ የሁሉም ታሪክ አይደለም፤ የአክሱም ስልጣኔ የአንድ ጎሳ ስልጣኔ ብቻ ነው ወዘተ የሚል ኢትዮጵያ እንዳልነበረች ለማረጋገጥ የሚያስችል የታሪክ ቅልበሳ ለማድረግ ያልሞከሩት ነገር የለም። የኦሮሞ ሕዝብ ከደቡብ ወደሰሜን ተንቀሳቅሶ ያደረገውን አስተዋጽኦ ንቀውታል። አላማው ጥላቻን ለማስፋፋት፤ መከፋፈልን ለማጠናከር፤ የአማራውን ብሄረሰብ ከሌሎች ጋር ጠላትና ኢላማ ለማድረግ ነበር። ስብሃት ነጋ "የአማራውንና የተወህዶ ቤተክርስቲያንን" መሰረቶች በማይመለስ ደረጃ ንደናል ሲል የሚያጠናክረው ጥላቻን ነው። እሱም ሰው ስለሆነ ያልፋል። የቀበረው የጥላቻ ቦምብ ብልሃት ይጠይቃል። በኛ ግምት፤ አማራውና የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በምንም አይፈርሱም። ከፈረሱ ኢትዮጵያም ትፈርሳለች። አማራው በምንም አይጠፋም። ራሱን ይጠብቃል። የህወሓትና የሌሎች ጠባብ ጎሰኞች ፖለቲካ ለምን ተከታታይ ሆነ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ሞክረናል። ባጭሩ የምንደግመው ለትግራይ ሕዝብ ኋላ ቀርነት፤ ለረሃቡ ሁሉ ተጠያቂ የሚሆነው አማራ አይደለም። አባባሉ የራስን ጎሳ እነደ "መላክ" የማቅረብ ባህል የፈጠረው ህወሓት የአክሱምንም ታሪክ ኢትዮጵያዊነት ዋጋ አልሰጠውም። አላማው ሌላ ስለነበር። "አክሱም ተወልደው እንደ ዩዲት ጉዲት አክሱምን ያጠፉ ሞልተዋል።" አክሱምን የገነቡ ትግራይ ያልሆኑ ሞልተዋል። "እስኪ እነዚህን የአክሱምን ቤተክርስቲያኖች ተመልከት፤ ያንን የጥንቱን ያነጸው ፋሲል ነው፤ ከጎንደር ነው፤ ይህንን ህንጻ ያነጸው ተፈሪ ነው፤ ከኦሮሞም፤ ከሸዋም ነው የመጣው፤ እነዚህ ሁሉ አክሱማዊያን ናቸው። ታቦት ያለችበትን መቅደስ ያነጸችው የሸዋ መነን ናት"። ህወሓት የሸዋ አማራ አንጋፋው ጠላታችን ነው ብሎ የተነሳው የራሱን ታሪክ በማርከስ ጭምር ነው። ቀጥለው፤ "ይህን ሃውልት ማን እንደሰራው ታውቃለህ? ትግሬ ነው፤ አማራ ነው፤ ኦሮሞ ነው፤ አገው ነው፤ ወላይታ ነው ሶማሌ ነው?" የሚሉ ጥያቄዎችን ካቀረቡ በኋላ፤ "የአክሱም፤ የላሊበላ፤ የጎንደር፤ የሓረር፤ የሸዋ ስልጣኔ የኢትዮጵያውያን እንጅ የአንድ ዘር/ጎሳ/ብሄረሰብ አይደለም" ሲሉ መክረዋል። አባቢው ይኼን ትኩረት እንዲሰጥ አደራ እንላለን። 29/

ህወሓት፤ ይህን የመሰለ፤ ከሄሮዶተስ (ግሪክ) ጀምሮ የታሪክ ጠበብቶች የመዘገቡትን፤ መጽሃፍ ቅዱስ ደጋግሞ የመዘገበውን ታሪክ የለም ብሏል። አላማው፤ ታሪክን ሰርዞ፤ አዲስ የጎሳ አገዛዝ ለመፍጠርና የበላይነት ለመተግበር ነው። ሌላውን በማርከስ፤ የጠባብ ጎሰኛውን ቡድን የበላይነት ለማጠናከር ነው። መለስ የኢትዮጵያ ባንዲራ "ጨርቅ ነው ወዘተ ሲል፤ እኛን እንደ ኢትዮጵያዊያን የሚያይዘን የታሪክ ሃረግ የለም፤ የተለያየንና የማንታረቅ፤ ቋንቋ የሚለያየን "ሕዝቦች" ነን ማለቱ ነበር። ህወሓት አሁንም የሚከተለው ጥላቻን ያዘለ የቋንቋ ልዩነት ፖለቲካ የሆነው ለዚህ ነው። የኢትዮጵያን ታሪክ የካደ፤ አብሮ የካደው የራሱን ታሪክም ነው። "አክሱምን ከትግራይ፤ ላሊበላን ከአገው፤ ጎንደርን ከአማራ፤ ሃረርን ከሃረሬ፤ አዲስ አበባን ከኦሮሞና ከአማራ ጋር ብቻ አያይዘን የምናያቸው ከሆነ፤ በኢትዮጵያ ታሪክና ጉዞ ውስጥ ይቅር የማይባል ስህተት እንሰራለን።" ይህን "ይቅር የማይባል ስህተት" የሰራው የህወሓት ፈጣሪ መንግሥት አሁንም በትምክህተኛነት ይገዛል፤ ስልጣን ተጠቅሞ ይዘርፋል። አማራው "ጭራቅ ነህ" ተብሎ ሲበየንበት የተሰጠው ምክንያት ኢትዮጵያን የገዛት ይህ ጎሳ ብቻ ነው በሚል የፈጠራ ታሪክ ነው። ራስ ጉግሳ፤ ራስ ወሌ ጎንደርን ገዝተዋል፤ ሁለቱም ኦሮሞዎች ነበሩ። ራስ ሚካኤልና ራስ ውቤ ጎንደርን ገዝተዋል። ጎንደሬው፤ ትግሬ ስለሆናችሁ አንፈልጋችሁም አላለም። በኢትዮጵያዊነታቸው ተቀብሎ አስተናግዷቸዋል። አጼ ዮሓንስ ማህዲስቶችን ሲዋጉ አብሯቸው የቆመው አማራ፤ ጉራጌ፤ ሃረሬ፤ ኦሮሞ ነው። የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት እንጅ የትግራይ ብቻ አልነበሩም። 30/

ይህን የሚያኮራ የኢትዮጵያ ሕዝብ መቆላለፍ፤ መደጋገፍ፤ አብሮ መኖር፤ አብሮ ታሪክ መስራት፤ አብሮ ኢትዮጵያን እውቅና መስጠት እንዳልነበረ ያደረገበት ዋና ምክንያት የጎሳ አስተዳደር አቋቁሞ የበላይነትን ለሙቶ አመታት ለመያዝ ነው። የኢትዮጵያ ተማሪዎች "ልዩነቶችን አስወግደን ፤ አዲስ ሁሉን አቀፍ የሆነ ድርጅት አቋቁመን፤ ለመላው ኢትዮጵያ የሚበጅ ዴሞክራሳዊ አገዛዝ እንመስርት" ብለው ነበር። አንዱ የመረጡት የትንተና ዘዴ የመደብ ጭቆና ነበር። ሌላው የብሄረሰብ ጭቆናን መንገድ መረጠ። ህወሓት ሁለተኛውን መንገድ መርጦ የጎሳ ፖለቲካ መሰረት እንዲሆን አደረገ። የጎሳ ፌደራሊዝም የመደብ ልዩነቶችን ለማስወገድ አልተነሳም። የገቢ፤ የሃብትና የኑሮ ልዩነቶችን አጠንክሯል። ህወሓት

የተነሳው መሰረታዊ የሆኑ፤ ከላይ የተጠቀሱ የወል ወይንም የጋራ እሴቶች ለመደምሰስ ነበር። ኤርትራን ከእነ ሄርማን ኮህን ጋራ በመደራደር ያስገነጠሉት ሻቢያና ህወሓት ናቸው። ህወሓት ስልጣን ከያዘ በኋላ አገር ማድማቱን ቀጥሎበታል። ተወዳዳሪዎችን በማጥፋት ተከስቷል። የወል እሴቶችን ባይንዳቸው ኖሮ የጎሳው ፖለቲካ ስር አይሰድም ነበር። የጎሳ ፖለቲካ ደጋፊዎች ማጤን ያለባቸው፤ለሕዝብ እኩልነት፤ ለፍትሃዊ እድገት ቆሚያለሁ ያለው ህወሓት አስጊ የሆነ የመደብ ልዩነትና በጎሳዎች መካከል እልቂት የሚያስከትል ሁኔታዎችን መፍጠሩን ነው። ይህ፤ የጎሳ አገዛዝ ውጤት ነው። አደጋው ግልጽ እየሆነ ለሄደ ክስተት ዋናው ተጠያቂ የህወሓት አመራር ነው። የእርስ በእርስ ትርምስ፤ ቆይታውን ያረጋግጥለታል።

አመራሩ በደል ሰርቷል። ሃላፊነት አለበት ማለቱ ሁልጊዜም ቀላል ነው። አስቸጋሪ የሆነው፤ የተቃዋሚው ክፍልና ሌሎቻችን ለዚህ ለምናየው አደጋ በታሪክ በሙሉ ተጠያቂዎች መሆናችን አልተቀበልንም። የሕዝብ የበላይነትን የሚያንፀባርቅ ዲሞክራሳዊ ስርአት ማለትም--የሕዝብ ድምጽ መከበር፤ ነጻ ምርጫ፤ የመንግሥት ለሕዝብ ሃላፊነትና ተጠሪነት፤ እውነተኛ እኩልነት፤ የህግ የበላይነት፤ የሰብአዊ መብቶች ያለገደብ በህግ መከበር፤ ማንኛውም ግለሰብ በህግ ፊት እኩልነት ወዘተ--ለዋጭ የሆነ አማራጭ ነው። ለዚህ አይነት ስርአት መታገል ለሁሉም እንድሚጠቅም አምናለሁ። አስቸጋሪ የሆነው፤ ገዢውን ፓርቲ የሚያገለግለው፤ በተቃዋሚው ክፍል አሁንም ያለው ጠባብ ጎሰኛ የፖለቲካ መሪዎች የሚከተሉት ሻቢያና ህወሓት የፈጠሩትን፤ እነ ሄርማን ኮህን የሚደግፉትን የጎሳ ርእዮት መከተላቸው ነው። መጠንቀቅ ያለብን፤ ጥቅሙ እስከተከበረ ድረስ፤ ከአሁን በኋላ የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት ኢትዮጵያ እንድትበታተን የሚመርጥ አይመስለንም። ተገንጣዮችና የጠባብ ጎሳ አክራሪዎች ዙረው ዙረው የሚያገለግሉት የስርአት ቆይታ ነው ለማለት የምንገደደው ለዚህ ነው። ለፍትህ መታገል ሁሉን ያገለግላል። ይኼም ስኬታማ የሚሆነው ትንንሽ አንጎችን፤ትንንሽ ቅንጅቶችን፤ ትንንሽ ኢሰፓዎችን ወዘተ በመፍጠር አይደለም። አንጋፋ ሕብረ-ብሄር ድርጅቶችን በመመስረት ብቻ ነው።

ህወሓትን መቃወም ብቻ በቂ አይደለም?

የቀድሞውን ሁሉ ሳያመዛዝኑ ማፈራረስ የፖለቲካ ባህል መሆን የለበትም። ህወሓትን/ኢህአዴግን መቃወም ብቻ የጎሳ ፖለቲካ ያመጣውን ሁለ-ገብ ችግር ሊፈታ አይችልም። ከባድ የሆነውና የማንነጋገርበት፤ የራሳችንን ድክመት ነው። የምንደጋግመው የምናውቀውን ብቻ ሆኗል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ያጣው እውነተኛ የሕዝብ መብቶች፤ የፍትህ፤ የእኩልነት፤ የህግ የበላይነት ጠበቃ ነው። ሊገዛው የሚፈልግ አይደለም። ተቃዋሚው ክፍል አርአያ በመሆን ፈንታ፤ ጠብና ጥላቻ ማሰፋፋት፤ መከፋፈል፤ ችግሮችን በመመካከር፤ በእርጋታ፤ በውይይት፤ በመረዳዳት ለመፍታት አለመቻላችን ህብረተሰቡን ተስፋ አስቆርጦታል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጎሳ በላይ አገሩን እንደሚወድ፤ ዲሞክራሳዊ ስርአትን እንደሚመርጥ በቅንጅት ጊዜ አይተናል። ቅንጅት ድጋፍን ያገኘው ህብረ-ብሄር ስለነበረ ነው። ከብሄር/ብሄረሰብ የፖለቲካ ድርጅቶች ይልቅ ቅንጅት አንጋፋ ድጋፍ ያገኘው በኢትዮጵያዊነት ስለተደራጀና ሕዝቡን ስለቀሰቀሰ ነው። በአዲስ አበባና በሌሎች ከተማዎች ቅንጅት ከፍተኛ ድጋፍ ነበረው። ለምን? አንድ፤ ከተሜው ከሁሉም ብሄረሰቦች የተወጣጣ፤ አንድ ብሄረሰብ የማይዳኘው ሆኗል። ሁለት፤ ከተሜው በልዩ ልዩ ዘዴ ዜና ያገኛል። ለመንግሥት ፕሮፓጋንዳ አይታለልም። ሶስት፤ ከተሜው ማን ምዝበራ እንደሚያካሂድ፤ ማን በስልጣን እንደባለገ፤ ማን ስልጣን ተጠቅሞ እንደ በለጸገ ወዘተ ያውቃል። አራት፤ ከተሜው ከውጭ ካለው ስደተኛ ጋር ቀጥታ ግንኙነት አለው። እውቀት ሸማች ነው። በአንጻሩ፤ ህወሓት/ኢህአዴግ የገጠሩን ሕዝብ ሙሉ በሙሉ አፍኖታል። ለበላይነቱ አገልጋይ አድርጎታል። ዜና እንዳያገኝ መሰናክሎች ፈጥሮበታል ወዘተ። ድህነትን ለፖለቲካ መሳሪያ ተጠቅሞበታል።

የቅንጅትን አመራር መንግሥት በቀላሉ የከፋፈለውና ያጠፋው ብሄራዊነቱን ስላወቀና አመራሩ ደካማና ራስ ወዳድ ስለነበረ ነው። የቅንጅት አመራር ግለሰባዊነትና ግትርነት፤ ልክ ትእዛዝ እንደተሰጠው መከፋፈሉ ነው። የገዢው ፓርቲ ሃላፊዎች በተከታታይ የሚፈጥሩትና የሚደግፉት በጎሰኛነት የሚደረገውን የፖለቲካ አደረጃጀትና የሚያመጣውን ክፍተት ሰርገው በመግባት ነው ። በህገመንግሥቱ መሰረትና ከዚያ ውጭ በአገር ደረጃ አለመዋቀር አገሪቱን ጎድቷታል። ገዢው ፓርቲ ይህን ክፍተት ተጠቅሞ ተቃዋሚውን ሁሉ ለማሳደድ፤ ለማሰር፤ ወጣቱ ትውልድ አገሩን ለቆ በገፍ እንዲሰደድ ረድቶታል። ይህን በጎሳ የመደራጀት ድክመት ቀን በቀን እያየን፤ አሁንም በብሄራዊ ደረጃ ለአገር/ለወገን አለመነሳታችን የታሪክ ተጠያቂ አድርጎናል። ይህ ድክመት የስርአቱ ጥፋት በደልና ሰቆቃ ብቻ አይደለም። የራሳችን ችግሩን በሚገባ አለማየት፤ መበታተን፤ መዘላለፍ፤ አገር ሳይኖር ለስልጣን መወዳደር ወዘተ ጭምር ናቸው። ስለዚህ ድክመት በግልጽና በሰፊው ስንወያይ አይታይም። አንድ የውጭ ታዝቢ የተቃዋሚው ድክመትና መከፋፈል አስገርሞት እንዲህ አለ "እንደ ኢትዮጵያ ስደተኛ የሚያወራ፤ የሚሰበሰብ የለም፤ ግን፤ ምን ቁም ነገር ለአገራችሁ ሰራችሁ ብየ ስጠይቅ አጥጋቢ መልስ አላገኘሁም።" ለዚህ አባባል መልስ መስጠት የሁላችንም ሃላፊነት ነው። ገዢው ፓርቲ

ድክመታችን ስላየ በምንኖርበት አገር ሁሉ ያሳድደናል። በታወቀው ጋዜጠኛ፤ በአበበ ገላው ላይ የግድያ ሙከራ አሜሪካ የተደረገው ድክመታችን ስለታየ ነው። አንዳርጋቸው ጽጌ በየመን የመረጃ ክፍል ተይዞ ለህወሓት የመረጃ ክፍል የተሰጠው በአንድ ላይ ባለመስራታችን ጭምር ነው። አገር ያለውን ህገወጥ ግድያ፤ ህወሓት ወደ ውጭ እያሰራጨው ነው። ይህ የቂም በቀል አፈናና የግድያ ሙከራ ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ ለዋጭ መሆን አለበት። በአበበ ገላው ላይ የተሞከረው በያንዳንዳችን ላይ እንደተደረገ ማየት ያስፈልጋል። ይህን አረመኔ ቡድን በዓለም ፍርድ ቤቶች ማቅረብ ያስፈልጋል። ነፍሰ ገዳዮች ከህወሓት መንግሥት ሸሽተው ወደ ሌላ አገር ሲሄዱ በፍርድ ለማቅረብ ይቻላል። የአሜሪካ መንግስት በራሱ ምድር ላይ የተፈጸመውን ሴራ አይቶ ለኢትዮጵያ መንግሥት የሚሰጠውን እርዳታ ሁሉ እንዲያቆም መቀስቀስ ያስፈልጋል። እድሉን መጠቀም የሁላችንም ሃላፊነት ሆኗል። ለዚህ የሚረዳን፤ ቢያንስ አንድ የምንስማማበት አገራዊ ነገር አለ። ይህም፤ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሚደረገው የማያቆም ፤ኢ-ሰብአዊነትና ለህሊና የሚቀፍ ፍጹም የሆነ አፈና ነው። መፈክሩ "ፍትህ ለሁሉም" ነው። በተጨማሪ፤ የመሬት ነጠቃ፤ ቅርሚት፤ አድልዎና ሙስና ሕብረተሰቡን ሊሰበስቡ ይችላሉ የሚል ግምት አለን።

አገርና ነጻነት ከሌለን በምን የፖለቲካ መስከ እንደምንታገል ማሰብ የተሳነን ይመስላል። የምንጋራቸው እሴቶች ካሉ፤ በጋራ ለመስራት መቁረጥ አለብን። ቢያንስ፤ ዘላቂነትና በእቅድ በተደገፈ መንገድ ይህን ጠባብ ጎሰኛ ቡድን ለዓለም፤ ለአፍሪካ፤ የፍርድና የሰብአዊ መብት ጥበቃ ድርጅቶች ለማቅረብ እንችላለን። የጎደለው መረጃው አይደለም። ገዢውን ፓርቲ ለመክሰስ፤ በአሜሪካ የግድያ ሙከራ ከማድረግ በላይ ማስረጃ አያስፈልግም። አስፈላጊው የአስተሳሰብ ለውጥ ነው-- ከፍርሃት ነጻ መውጣት፤ በራስ መተማመን፤ ጉልበትን፤ እውቀትን፤ ገንዘብንና ሃይልን መስብሰብ፤ አብሮ በዘላቂነት ለመስራት ቆርጦ መነሳትንና ሃሳብን ወደ እቅድና ተግባር መተርጎም ናቸው። የተለመደ ባህላችን፤ አንድ አስቃቂ ነገር ስንሰማ ብቻ ብቅ ጥልቅ ማለት አያዋጣንም። ከገዢው ፓርቲና ታማኝ ተጠቃሚዎቹ ውጭ፤ ማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል፤ የሰብአዊ መብቱ ተገፏል። ህወሓት/ኢህአዴግ "በቋንቋህ ለመናገር ትችላለህ። የራስህ ቴሌቢዥን አለህ። የራስክን ሙዚቃ ልትጫወት ትችላለህ" ወዘተ፤ እያለ ስሜት ቀስቅሷል። ይህ ስለሆነ፤ የአኘክ፤ የአፋር፤ የኦሮሞ፤ የጉራጌ፤ የአማራ፤ የሶማሌ ህብረተሰብ ነጻነት አለው ማለት አይደለም። በድንቁርና ዓለም ውስጥ ካልኖርን በስተቀር፤ የለውም። የቋንቋ ልዩነት ግፉን አያጠፋውም። በእነዚህ ህብረተሰቦች የተፈጥሮ ሃብትና የግል ንብረት መያዝ መብቶች ተወግደዋል። ስለሆነም፤ ተቆርቋሪ ነኝ የሚል ሁሉ ለራሱ ጎሳ ሳይሆን፤ ለሁሉም ኢትዮጵያዊያን የሰብአዊ መብቶች አምባሳደር ለመሆን ቆርጦ መነሳት አለበት። ጊዜው ነገ ሳይሆን ዛሬ ነው። በአበበ ገላው ላይ ሊደረግ የተሞከረውን ጥቃት ወደ ጥንካሬ መለወጥ አስፈላጊ ነው። እስከምናውቀው ድረስ ይሕ ጋዜጠኛ የሚታገለው ለፍትህ፤ ለዲሞክራሲና ለነጻነት ነው፤ ሁሉም የሰላም እሴቶች። አንዳንድ ኢትዮጵያዊያን፤ ከጎሳ ባሻገር፤ ለፍትህ የሚያደርጉት ትግል ለተከታታይ ትውልድ ምሳሌ ነው።

ህወሓት በበላይነት የሚመራው የጎሰኛ አገዛዝ በቀላሉ ሊለወጥ አይችልም። ለአባላቱ የሚሰጠው ጥቅም ያየለ ስለሆነ። መለስ ከማለፉ በፊት፤ አንዳንድ የታወቁ ግለሰቦችና ድርጅቶች ለሰላማዊ የለውጥ ሽግግር ያላቸውን ሃሳብና ምክር ለመለስ አቅርበው ሳይሳካላቸው ቀርቷል። አሁን ህወሓት ራሱን በበለጠ ለማጠናከር የሚያደርገው ዘመቻ <u>ከመቻቻል ጋር አብሮ የሚሄድ</u> <u>የማይመስለው አብሮ አገርን የማሳደግ፤ አብሮ ስልጣንና የእድገት ውጤትን መጋራት</u> ልምድ ስለሌለው ነው። አገዛዙ አሁንም የሚመራው በጠባብ ጎሰኛነትና በጦርነት ስነልቦና ነው። መለስ አገራዊ ተቋሞችን አፍርሶ አልፏል። ተከቶት ያለውፈው የጠባብ ጎሰኛ የበላይነትን ባህል፤ በጦር የተመሰረተ አገዛዝን እንደተቋም አድርጎ ነው። በኃይማኖት ዙሪይ እየተስፋፋ የሄደው ችግር የሚያሳየን፤ መለስና ቡድኑ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ተቋሞች ሲያጠፉ ወደፊት የሚመጡትን አደጋዎች አላሰቡም። አሁንም ጭፍኖች ናቸው። እአአ በ 1995 ቲኦዶር ቬስታል ለመለስ የሰጠውን ምክር ለአንባቢው አቀርባለሁ። "አንተ (መለስ)፤ የኢትዮጵያን ታሪክ ሂደት ገንቢ ወደ ሆነ አቅጣጫ ለመለወጥ ስልጣን አለህ። ይህን ስልጣን ተጠቀምበት። ታሪክ ያመሰግንሃል፤ ካላደረግህ ታሪክ ይወቅስሃል። የምመክርህ፤ የፖለቲካውን ሜዳ ክፈትና የዲሞክራሲ መለኪያ የሆነ መሰረት ጣል። ለመድብለ ፓርቲ ጨቅላነትና መጥፋት፤ለስብአዊ መብቶች መገፈፍና መረገጥ ሃላፊነት ውሰድ። የኢትዮጵያ ሕዝብ የበላይ የሚሆነውና በታሪኩ የሚኮራው፤ እውነተኛ የራስ አስተዳደር (Self-Rule) ሲኖረው ነው። አንተንም እንደ ታላቅ መሪ አድርጎ ተከታታይ ትውልድ የሚያከብርህ፤ ደፍረህ ህይወትን የሚለውጥ አዲስ ምእራፍ ስትከፍት ነው። የፖለቲካ ስልጣን ከተወዳዳሪዎች ጋር መጋራት ለለውጥ ዝግጁ መሆንክን ያሳያል" በማለት ምክሩን አቀረበ። 31/

ስልጣን እውቀት ሰጥቶኛል ብሎ በሁሉም ነገር ላይ የበላይነት ይሰማው የነበረው መለስ ምክሩን አልተቀበለም። የማንንም ተቃዋሚ ወይንም የለውጥ ጠበቃ ምክር ሰምቶ አያውቅም። በቬስታል ዘገባ፤ እንዲያውም፤ አምባገነንነቱ እየጠነከረ ሄደ። "የመለስ መንግሥት ጨካኝ፤ ጨቋኝ፤ አፋኝ፤ አምባገነን መሆኑ ተባባሰ። ጸረ-ሽብርተኛ የሚል ህግ አወጣ። ተቃዋሚውን ሁሉ፤ በጸረ-ሽብርተኛነት መክሰስ፤ ማሰርና ማሳደድ ቋሚ መመሪያው ሆነ።" ቬስታል ድክመቱን

እንዲህ ሲል ገልጾታል። "መለስ ከማርቲን ሉተር ኪንግ፤ ከኔልሰን ማንዴላ፤ ከጋንዲ አልተማረም። ለመማር አልፈለገም። ያለፈው የትምህርት ፈተና፤ የስታሊንን፤ የሌኒንን፤ የማኦን፤ የአልባኒያውን ሖሳን" የግራ ፖለቲካ መስመር መተግበር ነው። ተጻራሪ የሆነው፤ የግራ ፖለቲካ ተማሪው የቀረጸው የፖለቲካ አመራር አሳታፊ ሳይሆን አምባገነናዊ ፓርቲ የፈጠረው እድገታዊ መንግሥት፤ ኢኮኖሚው ፍትሃዊ ሳይሆን ለጥቂቶች የተለየ ገቢና ባለጠጋነት ምዝበራ የተደራጀ ነው። የጎሳ ፖለቲካ ባለስልጣናት (Ethnic Elites) የፖለቲካ የበላይነቱን ይዘው፤ የገቢና የሃብት ምንጮችን ለራሳቸው ያደረጉበትን አገዛዝ የፈጠረው መለስ ነው። ("Ethiopian ethnic elites have a chokehold on the economy, whose ideological underpinnings were articulated by Meles….In the massive transfer of wealth, non-Tigrean elites are considered second class or not Ethiopian worthy of the same status." የቬስታል ድምዳሜ፤ የጎሳው ፖለቲካና አስተዳደር ያጠናከረው ህወሓትን መሆኑን አሳይቷል። 32/

ማነህ ባለ ሳምንት?

ከቬስታል የቀዳሁት ትምህርት፤ የህወሓት የበላይ አመራር አዲስ ፍትሃዊ የሆነ ህብረተሰባዊ ታሪክ የፈጠረ አይደለም። የሚለወጥ አለመሆኑን አጠናካሪ ነው። ስለዚህ፤ ፍትህ የሚፈልግ ተቃዋሚ በአቤቱታና በአማላጅ ለውጥ አያመጣም። ለለውጥ ፈቃደኛ ፈላጊ፤ (the will and determination to change the status quo)፤ መስዋእት ከፋይ ለመሆን መዘጋጀት አለበት። ይህ ድምዳሜ የሚያስገድደው። መተባበራን፤ መወያየትን፤ መተማመንን፤ አብሮ መስራትን፤ ከጎሳና ካኃይማንቶ በላይ ለአገር ማሰብን ነው። አለመስማማት ለመጥፊያ ዋና ምክንያት ይሆናል። ይህን ክስተት አለመረዳት በአገርና በወገን ላይ ወንጀል ሲፈጸም ዝም ብሎ እንደማየት ይቆጠራል። ለአገርና ለወገን አለመቆም ዋጋ ይከፈልበታል፤ ተጠያቂ ያደርጋል። ህወሓት/ኢህአዴግ፤ የክልሎች የቋንቋ መብትን ተጠቅሞ፤ በእድገት አመካኝቶ፤ በአኝዋክ ሕዝብ፣ በኦሮሞ ሕዝብ፣ በአፋር ሕዝብ፣ በአማራ ሕዝብ፤ በኦሞ ዙሪያ ሕዝብ፤ በሶማሊ ሕዝብ፤ በአስተማሪዎች፤ በተማሪዎች፤ በእናቶች፤ በወጣት ሴቶች፤ በህጻናት፤ በተለያየ ወቅት፤ አሰቃቂ በደል ሲያደርግ ቆይቷል። በያንዳንችን ላይ ስላልደረሰ፤ በሩቅ ተመልክተነዋል። አሁን ደረጃውና ስፋቱ ለህሊና በሚዘገንን ሁኔታ ጭቅናና በደል በአማራ ሕዝብ ላይ በተቀናጀ መልክ እየተደረገ እናየዋለን። አንዳዶቻችን ድምጽ ስናሰማ ሌሎቻችን እንደተለመደው ዝም ብለናል። ሒትለር በአይሁዶች ላይ አሰቃቂ በደል ሲያደርስ ዝም ብለው ያዩትን ይመስላል። ነገ በራሳቸው ላይ እንደሚመጣ አላወቁትም ነበር። ኢ-ሰብአዊ በደል ለአማራ ህብረተሰብ የቂም በቀል ማሳያ ብቻ ነው ብሎ ማለፍ ይህን አፍራሽ የሆነ የጠባብ ጎሰኛ ቡድን አለማወቅ ነው። አማራው ተከታታይ በደል ደርሶበታል። ሆኖም በታሪክ የተፈተነ ስልሆነ አይጠፋም። ራሱን ለመጠበቅ መነሳቱ የማይቀር ነው። አይሁዶች እንዳደረጉት። የአማራው ህልውና ከፈተና ላይ የወደቀውና በደል የተፈጸመበት ብሄራዊ ድርጊት ነው። በአማራ ህብረተሰብ ላይ ብቻ አይደለም። የዜግነት መብት የሚነጣጠል አይደለም። የአማራ፤ የኦሮሞ፤ የሶማሌ፤ የአፏከ መብት አይደለም፤ የመላው ኢትዮጵያዊያን መብት ጥያቄ ነው። ነጻነትና አፈና ብሄር፤ ሃይማኖት፤ እድሜና ጾታ አይለይም።

ከጅምሩ፤ ሻቢያና ህወሓት ያደረጉት ኢትዮጵያዊ የሆኑ ተቋሞችን ሁሉ ማጥፋት ነው። አፈናው የሚካሄደው በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ መሆኑን ማወቅ ከተከታታይ አደጋ ሊያድን ይችላል። የአክሱምን ታሪክ እናስታውስ። ይህ ጠባብ ብሄርተኛ ቡድን ሲቋቋም ጀምሮ ዋና ኢላማ ያደረገው የአማራ ተወላጆችንና ተናጋሪዎችን ነበር። ከዚያም መሰሎችን በማሳደድ/ በመግደል፤ ለድህነት በመዳረግ ሲሆን ፤ ዋናው አላማ ለስልጣንና ለሃብት ተወዳዳሪ እንዳይኖር ማድረግ መሆኑን ብዙ ምርምሮች ዘግበውታል። የበላይነት ካልፈለገ፤ የኦሮሞ ሕዝብን ባላገለለ ነበር። በብዛቱ፤ በነጻ ምርጫ ተወዳድሮ የማሸነፍ መብት አለው። ማንም የኦሮሞ ተወላጅ ተቃውሞ ሲያሳይ፤ የኦነግ አባል ነህ ተብሎ ይታሰራል። የኦሮሞን ባለስልጣናት "አማራውን በሉት፤ ግደሉት" ሲል የሚልከው መልእክት፤ እኔ የማንም ብሄረሰብ ጠላት አይደለሁም፤ ኦሮሞው ግን ጠላትህ ነው ለማለት ይመስላል። የዘር ማጥፋትና ማጽዳት ዘመቻው አሁን የተጀመረ አይደለም። ኢላማው የታወቀ ይሁን እንጅ ፤ በዘሩ ብቻ በግልጽ ቅጣት ያልደረሰበት ቢኖር የባለስልጣኑ ክፍል ጎሳ ነው ለማለት የሚያስገድዱ መረጃዎች ብዙ ናቸው። የትግራይ ወጣት በጅምላ ሲገደል፤ ሲሳደድና ሲሰደድ አላየንም። በግልጽ፤ በትግራይ ሕዝብ ላይ ፍጹም የሆነ አፈና፤ የብሄር ጽዳት (Ethnic cleansing) አልተካሄደም። ሆኖም፤ በክልል አንድም ቢሆን-- ልክ እንደ ሰሜን ኮሪያ፤ "የተዘጋ ክልል" መስሎ በሚገዛው--ብዙ ሰላማዊ ሰዎች እነደሚሰቃዩ መገመት አያዳግትም። በአሬና ፓርቲ ላይ የሚደረገው አፈናና ጫና፤ አገራዊ የሆነ የትግራይ ተንቀሳቃሽ ተቃዋሚ ከጅምሩ እንዲደመሰስ የሚደረግ እቅድ ነው። ብዙ የትግራይ ሕብረተሰብ አባላት ስርአቱን ይቃወማሉ። ተሰደዋል፤ ተገድለዋል። አብዛኛዎቹ በኢትዮጵያዊነታቸው ያምናሉ። ስለሆነም፤ አብዛኛው የትግራይ ሕዝብ የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ አጋር ነው።

የጎሳ ክልልና መንግሥት የተቋቋመው፣ የቋንቋ ልዩነቶችን መለያ በማድረግ አንዱን ከሌላው ጋር ለማጋጨት ነው። የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥንካሬን ለማድከም የተጸነሰ የስልጣን ስልት ነው። አንባቢውን የምጠይቀው፣ የአክሱም ታሪክ የኢትዮጵያ ታሪክ ከሆነ፣ የፋሲል ታሪክ የኢትዮጵያ ታሪክ ከሆነ፣ ወዘተ፣ ህወሓት ለምን የቋንቋ ልዩነትን ተጠቅሞ የክልል አስተዳደር መሰረተ የሚለውን ነው። ሌላ አይነት የፌደራል ስርአቶች አሉ። በእኛ ምርምርና በሌሎች አስተያየት፣ የቋንቋ ልዩነት የተጠቀመው፣ ህብረተሰቡን በመከፋፈል፣ ላልተወሰነ ጊዜ የበላይነትን ጭብጥ ለማድረግ ነው። ህገመንግሥቱ ለዚህ ቁልፍ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል። የሕግ የበላይነት ሳይሆን፣ የጠባብ ጎሰኛ ቡድን የበላይነት ነው። ክልል አንድ ወይንም ትግራይ። ለዚህ የበላይነት መሳሪይ ሁኖ እንዲያገለግል ተገዷል።ብዙ የመንግሥት ባጀት ወደ ትግራይ የሚፈሰው ለዚህ ነው። እስከ አፍንጫው በጦር የተዘጋጀው እንደ ምሽግ እንዲያገለግል ነው ። እንደማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል፣ የትግራይ ተቃዋሚዎች ሃብት፣ ዘመድ፣ ግንኙነት አላቸው። በጎሳቸው፣ በቋንቋቸው ብቻ በጅምላ፣ መኮነንና ማግለል፣ መጠራጠር ተገቢ አይደለም። በእነሱም ውስጥ ፍርሃት፣ ጭንቀት፣ ተቃውሞ፣ መጠራጠር አለ። ይህን በመቀራረብ እንጅ በመራራቅ፣ በመጠራጠር፣ በጂምላ በመኮነን መጠቀም አይቻልም። በኦሮሞ ህብረተሰብም ዙሪያ ሊኖረን የሚገባው አመለካከት ተመሳሳይ መሆን አለበት።

እኛ እስከምናውቀው ድረስ፣ ደራሲው-- ከተማሪዎች እንቅስቃሴ ዘመን የጀመረ--ከልዩ ልዩ ብሄረሰቦች አባላት ጋር ጓደኝነት አለው። ጎንደሬዎች ትግሬዎችን እነደሚያቀርቡና እነደሚያስተናግዱ ሁሉ፣ ኦሮሞዎችንም ይቀበላሉ። እንደ ወዳጅ፣ እንደ ዘመድ ይቆጥራሉ። እንዲያውም፣ በአጠቃላይ ሲታይ፣ እንደ ጎንደር ሕዝብ ማንንም ተቀባይ፣ አስተናጋጅ አለ ብየ ለመገመት አልችልም። ይህ አስተናጂነቱ አስጠቅቶታል። ክፍለ ሃገሩ ከትግራይ ክልል የበለጠ በእርስ በእርስ ጦርነት ወድሟል። ይህን የሚነቅፍ፣ እስኪ ተመሳሳይ ማስረጃ ያቅርብ ብለን እንጠይቃለእን። ጎንደር የጦር አውድማ ሆኖ ያገለገለው፣ ጎንደሬ አትምጡብኝ የሚል ባህል ስለሌለው እንግዳ ተቀባይ ስለሆነ ነው። መረሳት የሌለበት ጎንደሬ አማራና ኢትዮጵያዊ ነው። በራሱ ቆሞ ለመሄድ የሚያስችሉ፣ ሁሉም የተፈጥሮ፣ የባህል፣ የታሪክ፣ የህዝብ ጥሪቶች አሉት። የኦሮሞ ህብረተሰብ፣ እንደ ጎንደሬው፣ እንደሌላው፣ መከበርን፣ እኩልነትን፣ የራሱን እድል መምራትን፣ የጥቅሙን መከበር ይፈልጋል። መብቱ መደገፍ አለበት። እውነተኛ እኩልነት የምደግፈው ለዚህ ነው። ልክ እንደ ጎንደሬውና ሌላው፣ የኦሮሞ ሕዝብ ለኢትዮጵያ ህልውናና ታሪክ አስተዋጽኦ አድርጓል። ወደፊትም ያደርጋል። ለተቆላለፈ፣ በፍትህ/በርትእ፣ በእኩልነት፣ በተሳታፊነት ለሚመሰረት ህብረብሄራዊ ስርአት አቀራረጽ ሚና ወሳኝ እንደሚሆን መቀበል ብልሃት ነው። የአፋር፣ የሶማሊ፣ የቤን ሻንጉል፣ የጋምቤላ፣ የትግራይ፣ የአማራ ወዘተ ህብረተሰብ ሁሉ በጋራ ተቻችሎ፣ ተፈቃቅዶ፣ ተስማምቶ፣ በነጻ ምርጫ፣ በተሃድሶ፣ ለተሃድሶ ሊፈጥራት የሚችላትን ኢትዮጵያ ማየት የሁሉም ፍላጎትና ተስፋ እንደሆነ እተማመናለሁ። ለዚህ የተቀደሰ፣ የጎሳ አገዛዝን ለሚተካ ግብ ሁላችንም አስተዋጾ ማድረግ የታሪክ ግዴታችን ነው። የታሪክ ግዴታ፣ የጎንደሬ፣ የሶማሌ፣ የኦሮሞ ወዘተ አይደለም። የሁሉም ኢትዮጵያዊያን ግዴታ ነው። አክሱምን፣ ጎንደርን፣ ወዘተ፣ የፈጠሩ ሁሉም ኢትዮጵያዊያን ከሆኑ- እኔ በዚህ አምናለሁ-- የወደፊቷን ኢትዮጵያ የሚፈጥሩት ሁሉም ኢትዮጵያዊያን በእኩልነት ተመካክረውና ተባብረው ነው። የህወሓት ፈጣሪዎች ያልተገነዘቡት ይህን አንኳር ቁም ነገር ነው። የስሜት ተገዥዎች መሆናቸውን በዚህ የበላይነት ጸባይ ለማየት ይቻላል። ሌሎች በጎሳ መደራጀታቸው ለዚህ አላማ መሰናክል ሆኗል።

ማየት የሚገባን፣ ይህ ሁሉ ከጠባብ ጎሰኝነት የመጣ፣ በድምሩ ከፊታችን የተደቀነው የአመራር በደል ስእል የህወሓት ቡድን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ሆነ ብሎ በመከፋፈል ለማድከም፣ ከዚያም በላይ፣ ለማጥፋት፣ ቢያንስ ለመፈታተን እንደቆረጠ ያሳያል። የበላይነቱ ካልተረጋገጠ አገሪቱ እንድትፈራርስ ያደርጋል። ግድ የለውም። ሕዝብ እርስ በእርሱ እንዲተላለቅ ይገፋል። ያላቋረጠ፣ በሰላማዊ ሕዝብ ላይ የሚደረግ ቅጣት፣ ስፋቱና ጥልቀቱ ሲታይ ለአገሪቱ ደህንነትና ዘላቂነት ጠንቅ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ለልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች አብሮ መኖርና አብሮ ማደግ አደገኛ ነው። አደጋው በሃይማኖት፣ በጎሳ ልዩነት፣ በስግብግብነት፣ በሙስና እየተከሰተ ነው። "እዚህ ጋ እቆማለሁ፣ አንተን አልነካም" አይልም። ስለሆነም፣ ይቆያል እንጅ ማንም የህብረተሰብ አካል ከቅጣቱ አያመልጥም። የህወሓት/ኢህአዴግ አመራር የመርዝ ፖለቲካ፣ የአጼ ምኒልክን ታሪክ በማንቋሸሽ፣ "ከኔ ጠባብ ጎሳ በላይ ለኢትዮጵያ የሚያስብ የለም" በማለት፣ የበላይነቱን በመሳሪያና በመሰለያ መረብ ተደግፎ የሚያጠናክር፣ የሕዝብን ፍቅርና ብሄራዊ አንድነት የሚያዳክም መሆኑን አይተናል። የመለስ ማለፍ ጥላቻውን አልለወጠውም። ይህን መሰረተ ሃሳብ ለማጠናከር የኢትዮጵያን የአንድ የጠባብ ጎሰኛ ስብስብ መንግሥትና ጋናን በማወዳደር አሳያለሁ። ጋና፣ ከሌሎች የአፍሪካና ከራሷ መጥፎ የፖለቲካ ታሪክ ተምራ ሁሉን የሚያስተናግድ ማህበረሰብ በማቋቋም ላይ ናት።

የኢትዮጵያና የጋና የአገዛዝ ልዩነቶች

የኢትዮጵያ ታሪክ፤ የአፍሪካን አገሮች፤ የዓለምን ጥቁር ሕዝብ የሚያበረታታ፤ የሚቀሰቅስ፤ የሚሰበስብ ነበር። የጋና መሪዎች፤ ከዋሜ ንክሩማን ጨምሮ፤ ኢትዮጵያን እንደ አፍሪካ ነጻነት ምሳሌ አድርገው ተጠቅመውባታል። የብዙ አፍሪካ አገሮች ባንዲራዎች ከኢትዮጵያ ጋር ተመሳሳይነት አላቸው። አርአያ ስለነበረች። በአርአያነቷ፤ ከገቢ አቅሟ የበለጠ፤ ለአፍሪካ ነጻነት አስተዋጽኦ አድርጋለች። የአፍሪካን አንድነት ማህበር፤ ሌሎችን በማበረታታት፤ መስርታለች። መሰብሰቢያ ቦታና አዳራሽ ሰጥታለች። መሪዎቿ ታሪክ ያላት አገር መሆኗን አስመስክረዋል። ዛሬ ያለችበት ደረጃ ካለፈው ታሪኳ ጋር አብሮ የሄደ አይደለም። በ1956 ከእንግሊዞች ነጻነቷን ያገኘችው ጋና፤ ከተከታታይ አምባገነን አገዛዝ በኋላ፤ በራሷ ታጋዮች ፍላጎት፤ ጥረትና ህብረት ነጻ ከሆኑ ጥቂት አገሮች መካከል የክብር ቦታዋን ይዛለች። እድገቷ፤ የዘላቂነትና የፍትሃዊነት መሰረት ጥሏል። ለምንና እንዴት? ጋና ከኢትዮጵያ በምን መሰረታዊ ክስተቶች ትለያለች?

1. አይኤምኤፍ የአፍሪካን አገሮች በማወዳደር፤ ጋና በ2012፤ 14.6 በመቶ እንዳደገች አመልክቷል። በጥቂት አመታት ብቻ በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ጋናውያን ወደ መከካለኛ መደብ እንደተሸጋገሩ ማስረጃ ሰጥቷል። የኢትዮጵያ እድገታዊ መንግሥት እንዳወጀው በእጥፍ እንዳላደገ አመልክቷል። የኢትዮጵያ የመካከለኛው መደብ በኑሮ ውድነት ገቢውና የመሸመት አቅሙ እየቀነሰ መሄዱን አስምሮበታል።

2. ኢትዮጵያ፤ የገንዘብ ሚኒስትር እንዳስታወቀው፤ የውጭ እዳ ተሸካሚ ሆናለች። እዳዋ፤ በ2012 $12 billion ደርሷል። በአንጻሩ፤ ጋና ከውጭ እዳ ነጻ ናት። እንዲያውም፤ በማእከላዊ ባንኳ፤ ለክፉ ቀን የሚሆን ሁለት መቶ ሚሊዮን ዶላር ተቀማጭ አላት። ኢትዮጵያ፤ አይኤምኤፍ እንዳሳሰበው፤ የሁለት ወር ተኩል ብቻ ሸቀጥ የሚያስገዛ የውጭ ምንዛሬ አላት።

3. የጋና መንግሥት የገጠር እድገት አላማ፤ አንስተኛ የጋና አምራቾችን ማጎልመስ፤ የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ መስጠት፤ የተፈጥሮ ሃብታቸው ባለቤት እንዲሆኑ ማድረግ ነው። የውጭ ኢንቬስተሮች ሚና የሚኖራቸው የሚለካ ጥቅም ለጋናውያን ለማቅረብ ሲችሉ ነው የሚል አመራር በስራ ላይ ውሏል። በአንጻሩ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት፤ ህንዶችን፤ ሳውዲዎችን፤ ቻይናዎችን፤ ቱርኮችን፤ ግብጾችን ጋብዞ ታላላቅ የእርሻ መሬቶችን እንዲጠቀሙ አድርጓል። የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች የበላዮች የውጭ ኢንቬስተሮች ናቸው፤ቱርኮች፤ ፓኪስታኖች፤ ህንዶች፤ ቻይናዎች። ምርታቸውን ለውጭ ገበያ እንዲያቀርቡ ፈቅዷል። አብዛኛው የኢትዮጵያ ዝቅተኛ አምራች ገበሬ በራሱ እንዲንቀሳቀስ ግብአቶች ከፈለገ የፓርቲው አባልና ደጋፊ እንዲሆን ያስገድደዋል። ህወሓት የውጭ ኢንቪስተሮች ከኢትዮጵያ መንግሥት ወይንም የግል ክፍል ጋር፤ አምሳ አንድ በመቶውን ኢትዮጵያ ወይንም ኢትዮጵያውያን፤ አርባ ዘጠኝ በመቶውን ኢንቬስተሮች እንዲይዙ መመሪያ ማውጣት ግዴታ አለበት፤ እንደማንኛውም ደንብ ግልፅነት የለም።

4. የኢትዮጵያ መንግሥት፤ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት እድል አስፋፍቻለሁ። የተባበሩት መንግስታትን እቅድ-Millinnium Development Goals (MDGS)--አሟላለሁ ብሏል። አስተማማኝ ማስረጃ ለማግኘት አይቻልም። በአንጻሩ ጋና የአንደኛ ትምህርት እድልን ለሁሉም ያዳረሰችው በ2007 ነው። ግማሹ የጋና ወጣት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጨርሷል። ጋና ኢትዮጵያን በብዙ አመታት ቀድማለች።

5. የጋና መንግስት የመብራት ሃይል ስርጭት መመሪያ ሁሉም ጋናዊያን የዛሬ ስምንት አመት የኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዲኖረው የሚል ነው። በአንጻሩ፤ የኢትዮጵያ የሃይል ማመንጫ ግድቦች፤ በአብዛኛው፤ ለውጭ ምንዛሬ ምንጭ እንዲሆኑ ማድረግ ነው። የኢትዮጵያ መንደሮችና ከተሞች መብራት ከማግኘታቸው በፊት ሱዳኒሶች የተሃድሶ መብራት ተጠቃሚ የሚሆኑበት ማህበሰባዊና እድገታዊ ምክንያት የለም። በዚህ አመራር፤ ህብረተሰቡ፤ ለብዙ አመታት በኩራዝ አገልግሎት እንዲኖር ይገደዳል ማለት ነው።

6. የጋና ሕዝብ የዘመናዊ መገናኛ ተጠቃሚ ሆኗል። ኢንተርኔት፤ ሞባይል፤ ቴሌቪዢን፤ ኤፍ ኤም ሬዲዮ፤ ወዘተ ተስፋፍተዋል። በቅርቡ ጋና ከማይክሮሶፍት ጋር በመተባበር፤ ለገጠርና ለከተማው ሕዝብ የሚያገለግሉ፤ ለማደስ የማያስቸግሩ፤ ዋጋቸው ዝቅተኛ የሆኑ ኮምፒውተሮችና ሌሎች መሳሪያዎች እንዲሰሩና እንዲሰራጩ ተደርጓል።ጋና የህንድ አይነት የቴክኖሎጂ ማእከል ትሆናለች። ለኢትዮጵያ መንግሥት፤ የዘመናዊ መገናኛ ስርጭት ጠላቱ ነው። የሞባይል ስርጭት ሁለት በመቶ ነው። ህወሓት መገናኛ ከእድገት ጋር ያለውን ግንኙነትና ጥቅም አያይም። ለነጻነት፤ ለመተባበር፤ ለፍትህ አገልጋይ ይሆናል የሚል ፍራቻ አለው። የህወሓት መንግሥት የዘመናዊ መገናኛ ብዙሃን አመራር መሰረት ቁጥጥር ነው። ደህንነትን፤ ጸረ-ሽብርተኛነትን፤ ፖሊስንና መከላከያን፤ ስለላን ከቴሌ አጠቃቀም ጋር ማቆራኘት። ይህ የፍጹም ቁጥጥር መረብ ወጣቱን ትውልድ ጎድቶታል።

7. ጋና አገር ወለድ ኢኮኖሚን፤ ከአገር ወለድ አሳታፊ የፖለቲካ አስተዳደር ጋር ታካሂዳለች። ኢትዮጵያ በአንድ ፓርቲ የበላይነት ትገዛለች። ቻይናዎችን ና ሌሎችን በመማጸን፤ "ኑና አገሬን አልሙልኝ" የሚል ፖሊሲ ተከትላለች። ይህ የባእዳን አምልኮ ለአገሪቱ በጣም አደገኛ ነው። የኃይማኖቱ አፈና ዋና መሰፈርት ነው። ሳውዲዎችን "ኑ፤ ግቡ፤ በየቦታው መስጊድ ስሩ፤ ኢትዮጵያ ለእናንተ ክፍት ናት" ካለ በኋላ አሁን የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮችን ማፈን ጀምሯል። የእስልምና ኃይማኖት ኢትዮጵያዊ የሆነ ታሪክ አለው። አረባዊ አይደለም። ይህን ኢትዮጵያዊ ታሪክ ያጠፋው ህወሓት/ኢህአዴግ ነው። ጣልቃ ገብነቱ የተጀመረው ኢትዮጵያን "ዘመናዊ ለማድረግ" ነበር።

8. አንዳጋጣሚ ሆኖ፤ የጋና ፕሬዘደንትና መለስ ዜናዊ ያረፉት እአአ በ2012 አጋማሽ ላይ ነው። የጋና ሽግግር ያለምንም እንከን፤ በህገመንግስቱ መሰረት ዲሞክራሳዊ በሆነ፤ ግልጽነት ባለበት ሁኔታ ተካሂዷል። በኢትዮጵያ አገራዊና ዲሞክራሳዊ ተቋሞች ስለሌሉ፤ አሁንም አቅጣጫው አልለየለትም። ለስልጣን የሚደረገው ሹኩቻ ህብረተሰቡን አሰልችቶታል። ጋና፤ ሰላማዊ የሆነ፤ እርጋታ ያለው፤ ወደየት እንደሚጓዝ የታወቀ፤ አስተማማኝ ህብረተሰብ ለመመስረት ችላለች። የፖለቲካ ለውጥ ነጻና አስተማማኝ በሆነ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ውድድር ይካሄዳል። አገዛዙ ጎሳዊ ፖለቲካ አደረጃጀት አይፈቅድም። ህገመንግስቱ፤ በብሄር መደራጀትን ከልክሏል። ጋናና ጋናዊ መታወቂያ፤ መለያ መሆናቸው በሕግ ተደንግጓል። ህወሓት/ኢህአዴግ ከጋና ለመማር አልቻለም። ውድድር ለሌበት ምርጫ ይዘጋጃል። የአገር ውስጥ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ለማነጋገር ፈቃደኛ ያልሆነው ኢህአዴግ ከልዩ ልዩ አገሮች የሚወከሉ ግራ ክንፍ ነክ የሆኑ ፓርቲዎችን በባህር ዳር ከተማ ለማስተናገድ ሽር ጉድ ብሎ ነበር። ለዚህ አግላይ ፖለቲካ ፓርቲ ድጋፍ መስጠት "እያወቁ መበላት" ነው።

9. ጋና፤ ከ1992 (ህወሓት/ኢህአዴግ) ስልጣን በያዘ አንድ ዓመት በፊት ጀምራ፤ ተከታታይ ነጻና ግልጽ የሆነ፤ ተወዳዳሪዎች ያለገደብ አቋማቸውን ለሕዝብ ያሰሙበት ምርጫዎችን አካሂዳለች። ለዚህ ቁልፍ ሆነው ያገለገሉ ተቋሞች አሉ። የኢትዮጵያ ገዢ ፓርቲ፤ የምርጫ ውጤትን አይቀበልም። ተወዳዳሪ እንዲኖር አይፈልግም። የሚፈልገው በተከታታይ ምርጫ ማሸነፍ ነው። የጎሳ ፖለቲካ ጠቃሚ ሆኖ ስላገኘው በህገመንግሥቱ አውጀታል። ስርአቱ ለህብረተሰቡ አገልግሎት የቆመ አይደለም።

10. ጋና ለዲሞክራሳዊ መብቶች መሳሪያ አድርጋ የምትጠቀምበት ዋና ተቋሞች አሏት። የፕሬስ ነጻነት ዋናው ነው። ይህ ተቋም፤ በስፋትም በጥልቀትም ብሄራዊ ነው። ኤፍኤም ራዲዮ በየመንደሩ ይሰማል። ኢንተርኔት ተስፋፍቷል። መንግሥት አይቆጣጠረውም። በኢትዮጵያ፤ አንድ መንግሥት የሚቆጣጠረው ቴሌቪዢን፤ አንድ ፓርቲው የሚቆጣጠረው ቴሌኮሚውኒካሺን፤ ለዘጠና አራት ሚሊዮን ህዝብ ያገለግላሉ። በኢትዮጵያ ተቃዋሚው ክፍል የሜዲያ መጠቀም መብት የለውም። ህብረተሰቡ የሚሰማው የመንግሥቱን ፕሮፓጋንዳ ብቻ ነው። ከጋና ጋር ለመወዳደር አልቻለም። በኢትዮጵያ፤ ጋዜጠኞች "ሺብርተኞች" ተብለው ይታሰራሉ። ይሰደዳሉ። በጋና፤ ጋዜጠኞች የህብረተሰብ ታጋዮች፤ እውነተኞች፤ ጀግኖች ተብለው በክብር ይኖራሉ።

11. ጋና፤ የህብረተሰብና የመንግስት ያልሆኑ ድርጅቶች እንዲስፋፉ ድጋፍ ሰጥታለች። እነዚህ ድርጅቶች ነጻነታቸውን ተጠቅመው፤ የልዩ ልዩ፤ አገራዊ፤ ህብረተሰባዊ፤ ግለሰባዊ አገልግሎቶች ይሰጣሉ። አድልዎንና ሙስናን ከሚያጋላጡት መካከል የመጀመሪያ ደረጃን ይዘው ይገኛሉ። ሲያጋልጡ፤ የፖለቲካ መሪዎችና ጠበቃዎች ወንጀለኞችን ለፍርድ ያቀርባሉ። ፍርድ ቤቶች ከማንኛውም ፓርቲ ቁጥጥር ውጭ ስለሆኑ ፍትሃዊ ፍርድ ለመስጠት ችለዋል። እነዚህ ድርጅቶች የመሰብሰብ፤ የመደራጀት፤ የመንቀሳቀስ፤ ገንዘብ በህግ የመሰብሰብ መብታቸው የተጠበቀ ነው። የኢትዮጵያ፤ እነዚህ ሁሉ፤ በመንግሥት የተከለከሉ ናቸው። መንግሥት የሕዝብ ድምጽና ድጋፍ የሚጠይቀው ሲወጠር ብቻ ነው። "በሳውዲዎች አማካይነት የእስልምና ኃይማኖት በኢትዮጵያ እንዲስፋፋ" ያደረገ የህወሓት መንግሥት ነው። "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ሪፓብሊክ የብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት የምክር ቤት ቃለ ጉባኤ" የተባለ በ 15/10/2004 ዓም የተጻፈማስታወሻ የእስልምና ኃይማኖት ሰላማዊ አመፅ አስጊ ደረጃ ላይ መድረሱን አስምሮበታል። ይህ አያስደንቅም። ያመጣው ራሱ ገዢው ፓርቲ ነው። አስደናቂው፤ መብቱን ያፈነውን የክርስቲያን ኃይማኖት ተከታይ "እባካችሁ፤ ደግፉን" ማለቱ ነው። ዋልድባን አርሶ መልሶ ደግፉን ብሎ ሲጠይቅ ንቀቱን ያሳያል። መልሱ "እሺ" ማለት አይደለም። ተቃዋሚው ማለት ያለበት "እንዴት ክርስትያኑን ብትንቅ ነው። ራስህ የፈጠርከውን ችግር እራስህ ተወጣው። አትከፋፍለን። የሁሉንም ማህበረሰብ ክፍሎች መብት አክብር። ፍትህ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን በሙሉ" የሚል መልስ መስጠት ብቻ ነው። ኢትዮጵያ ጋናን መሆን አለባት።

12. የጋና ስደተኛ በጎሳ፤ በሃይማኖት፤ በሚአሳስብ የገቢ ልዩነት ወዘተ የተከፋፈለ አይደለም። ከሁሉም በላይ፤ በጋናዊነቱ ያምናል። ለጋና ዲሞክራሳዊ ስርአት አብሮ ቆሟል። ተሟግቷል። ለለውጥ የሚያኮራ አስተዋጽኦ አድርጓል። በአንድ ላይ ስለሰራ፤ ፖሊሲና አመራር እንዲለወጡ ጠበቃ ሆኖ አገልግሏል። የውጭ አገር መንግስታትን አክብሮትና ድጋፍ

አግኝቷል። ስደተኛው ያደረገው ለኢትዮጵያውያን ቆንጆ ምሳሌ ነው። ይህ ትጉህ፤ ለአንድ አገራዊ አላማ ጠበቃ የሆነ፤ ልዩ ልዩ ጥናቶችን አድርጓል። የነጻ ፕሬስ እንዲከበር። የፖለቲካ ውድድር እንዲካሄድ። አምባገነኖች ከስልጣን እንዲወርዱ ብቃትና ዘላቂነት ያለው አስተዋጽኦ አድርጎ፤ ጋና ካለችበት ደርሳለች። ለሌሎች አገሮች ምሳሌ ሆናለች። የጋና ስደተኛ በአመት ወደ አገር ከሚልከው $14.5 billion (2012) በላይ የሚመሰገነው፤ ሁሉን አቀፍ የሆነ የፖለቲካ ውድድርና ዲሞክራሳዊ አገዛዝ፤ ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች እድል የሚከፍት ስርአት (Governance that offers political and social opportunities for all stakeholders) በጋና እንዲቋቋም ማድረጉ ነው። የጋና ስደተኛ የታሪክ ግዴታውን ተወጥቷል። የኢትዮጵያ ስደተኛ ብዛት ቢኖረውም፤ እንደዚህ ያለ ውጤት አላስገኘም። አገር ቤት ካለው በባሰ የተከፋፈለ ነው። የአምባገነኑ ፓርቲ የውጭ ምንዛሬ መጋቢ ሆኗል። የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት ስደተኛውን የሚፈልገው፤ ገንዘቡን እንዲልክ ነው። የፖሊሲ ሃሳቡን እንዲሰጥ አይደለም። የኢትዮጵያ ስደተኛ ማድረግ ያለበት፤ ጋናዊያን እንዳደረጉት፤ ቆርጦ፤ ዲሞክራሳዊ ለውጥ ያስፈልጋል ብሎ ሌት ተቀን መስራት ነው። ፋላጎቱ ካለ የሰውና የገንዘቡ ሃይል ከጋና ስደተኛ የላቀ ነው። ብዛት ወደ ጥራት መለወጥ አለበት።

ሰላምና፤ መቻቻል፤ ነጻነትና ፍትህ፤ የፖለቲካ ውድድርና ነጻ ምርጫ እውን ካልሆኑ፤ ዘላቂነትና ተሳትፏዊ ልማት አይኖርም። ጋናንና ኢትዮጵያን ማወዳደር ከሕዝብ ጥቅም አንጻር ከሆነ የዲሞክራሳዊ ስርአት ከፍተኛ መሆኑን ለመካድ አይቻልም። አብሮ ለሰላም፤ ለእርቅ፤ ለመመካከር፤ ለጋራ እድገት፤ ለብሩህ አማራጭ አቅርቦት ሳይሰለቹ መግፋት፤ የሕዝብን አቅም መገንባት፤ የመተማመንን ባህልን ማስተጋባት ወዘተ አስፈላጊ ሆነዋል። አሳታፊ የሆነ አገዛዝ ባይቋቋም ምን አለ። ሌሎች አምባገነን ፓርቲ የመሯቸው አገሮች እድገት አሳይተዋል የሚሉ ታዛቢዎች አሉ። አምባገነን ፓርቲ ፍትሃዊ እድገት እንደማያመጣ በተደጋጋሚ አይተነዋል። በዘጠና ሰባቱ ምርጫ፤ ከሁለት መቶ በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያዊያን ተገድለዋል። ከአርባ ሺህ በላይ ሰላማዊ ኢትዮጵያዊያን ታስረዋል። በየወሩ ብዙ ሺህ ወጣቶች ይሰደዳሉ። የኢትዮጵያ ዋና ኤክስፖርት የሰው ሃይል ሆኗል። ሙስና እንደነቀርሳ ተስፋፍቷል። ሰብአዊ መብቶች ሙሉ በሙሉ ታፍነዋል። ይህ አገዛዝ ከቀጠለ፤ ኢትዮጵያ፤ ላይበሪያ በ 1990፤ እንደሆነው፤ ሶማሊያ በ 1991 እንደሆነው፤ ሩዋንዳ በ 1994 እንደሆነው፤ ሴራ ሊኦን በ 1998 እንደሆነው፤ አይቮሪ ኮስት በ 2008 እና በ 2011 እንደሆነው፤ ቱኒዚያ፤ ሊቢያና ግብጽ በ2011 እንደሆነው፤ አሁን በሶሪያ እንደሚጦፈው የእርስ በእርስ ጦርነት መካሄዱ አይቀርም። የኢትዮጵያን የባሰ የሚያደርገው የውጭ ጣልቃ ገብነት ስላለበት ጭምር ነው። አረቦች የእስልምና ኃይማኖትን ተጠቅመው በአባይ ላይ ያላቸውን ጥቅም ለማስከበር እንደሚሞክሩ አንጠራጠርም። ቢያንስ ህብረተሰቡ፤ ለሙብቱ የመነሳት እድሉ ከፍ ያለ ነው። በተያያዘ መልክ መታየት ያለበት፤ የመገንጠልም እድል ከፍ ያለ ይሆናል። በጎሳ ፖለቲካ የተበከለ፤ አድሏዊ፤ ሙሰኛ አገዛዝ፤ ቀስ በቀስ የራሱን ማጥፊያ ሁኔታዎች መፍጠሩ አይቀርም። ሆኖም፤ ለጎሰኛው ስርአት የመጣ አደጋ ለኢትዮጵያም አደጋ ይፈጥራል። ጋና፤ የነጻ ምርጫን መንገድ ተጠቅማ፤ ህብረተሰቧን ከእርስ በእርስ ጦርነት አደጋ አድናለች። ከአስር ሙሉ በሙሉ ነጻ ከሆኑ የአፍሪካ አገሮች አንዷ ሆና፤ ዘላቂነትና ፍትሃዊ ወደ ሆነ የእድገት ጎዳና ታመራለች። ስለሆነም፤ የህወሓት/ኢህአዴግ አምባገነናዊ መንግሥት ከፍተኛ ዋጋ እየተከፈለበት ነው። ለሁሉም ፍትህ፤ ሰላምና የኑሮ መሻሻል ማነቆ ሆኗል።

በአጠቃላይ ሲታይ፤ ጎሳ-ተኮር ፌደራሊዝም ለፍትሃዊ እድገት ማነቆ ሆኗል። ጠባብ ጎሰኛነትን፤ ፓርቲን፤ መንግሥትንና ተቋሞችን አወቃቅሮ፤ መብቶችን አፍኖ ስለያዘ፤ በእድገቱ ላይ ጫና የሚያደርገው እንደሚከተለው ነው።

- አገር-ወለድ የሆነ፤ ለሁሉም ተወዳዳሪነት የሚረዳ የግል ክፍል እንዳያድግ ማነቆ ሆኗል። የሚያዳላው ለህወሓት ባለስጣናት፤ ድርጅቶችና ታማኝ ግለሰቦች ነው። ኪራይ ሰብሳቢ ነው።

- ጠንካራ አገር ወለድ የግል ክፍል ኢኮኖሚ እንዳያድግ ጫናና አድልዎ ስለሚያደርግ፤ የኢትዮጵያን ተወዳዳሪነት አንቆ ይዞታል። ኢኮኖሚውን ያለምንም ገደብ ለጥቂት የአገር ውስጥ፤ ለመከላከያና ለውጭ ኢንቬስተሮች ከፍቶ ሰጥቶታል።

- አገዛዙ የህብረተሰቡን በራስ የመመካት፤ ራስን ጠቅሞ አገርን የማሳደግ ባህል ነስቶታል። ፍርሃትን ለአገዛዝ በሚጠቅም ዘዴ ተቋማዊ አድርጎታል። ይህን የፖለቲካ ፍርሃት ወደ ኃይማኖት አስፋፍቶታል። ስለሆነም፤ የኃይማኖት ግጭት የጊዜው የተቀበረ “ቦምብ” ሆኗል።

- አገዛዙ ከአብዛኛው ሕዝብ እምነት ውጭ ሆኖ ብቻውን ይንሳፈፋል። ህገመንግሥቱ የቁጥጥር መሳሪያ ሆኗል። የሕግ የበላይነት በሙሉ ጠፍቷል። የጥቁር ገበያ ተስፋፍቷል።

- አገዛዙ የራሱን ጥንካሬና ጥቅም ብቻ በመምረጥ፤ የመንግሥት ባጀት እየተጠቀመ የፓርቲውን አባላት ቁጥር አስፋፍቷል። ስለሆነም፤ የአስተዳደሩ ዋጋ ህብረተሰቡን እየጎዳው ሄዷል። (The administrative burden of running the state outweighs the benefits).

- የብሄር/ብሄረሰቦች ልዩነቶች ለአናሳ-ጠባብ ጎሰኛ ፓርቲ የበላይነት መሳሪያ ሆነዋል።

- ብሄራዊ የሆኑ ተቋሞች ሙሉ በሙሉ በመፍረስ ላይ ይገኛሉ። መፍረሳቸው ለአገሪቱና ለመላው ሕዝብ አደጋን እየፈጠረ ነው። ለአገር ተቆርቋሪ ተቋም የለም።

- አገዛዙ አድሏዊ ስለሆነ ታይቶ የማይታወቅና አደገኛ የሆነ የገቢ፤የባለጠጋነት፤ የኑሮ ልዩነቶች ፈጥሯል። (Grosss disparities and inequities in income, wealth and standard of living). ስለሆነም፤ ገዢው ፓርቲ ጥቅሙን ለማስከበር ሰብአዊ መብቶችን መግፈፉን ይቀጥላል።

- አገዛዙ ሕግ አውጭ፤ ሕግ ተርጓሚ፤ ሕግ አስተዳዳሪና ሕግ አስፈጻሚ ሆኗል። ስለሆነም፤ ሚዛናዊ የሆነ ፍርድ ለማግኘት አይቻልም። (No checks and balances in the system).

- ብሄራዊ ተቀናቃኝና ተቆርቋሪ ስለሌለ፤ የተፈጥሮ ሃብት-የእርሻ መሬት፤ ወንዝ፤ መአደንና ሌሎች ኃብቶች-ለጠባብ ጎሰኛው ፓርቲ እንደ ግል ሃብት መሸቀጫ ሆነዋል።

- የኢኮኖሚው አመራር ሙስናን፤ አድልዎን፤ የገንዘብ ሽሽትን፤ ስደትን አጠናክሯል። የውጭ እርዳታ፤ በአብዛኛው፤ ለፖለቲካ ስልጣን ጡንቻና ለግል ባለጠጋነት መገልገያ ሆኗል።

- አገዛዙ ለጥቂት የፓርቲው ባለስልጣናት፤ ቤተሰቦች፤ ልጆች፤ ወዳጆችና ድርጅቶች ታይቶ የማይታወቅ የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት አትርፎላቸዋል። ኤፎርትና ሌሎች ህወሓት የፈጠራቸው ድርጅቶች አገር አቀፍ በሆነ ደረጃ የበላይነቱን ለትርፍ ተጠቅመውበታል። ይህ ፍጹም የበላይነት (party and endowment monopoly) ለአገራዊ ምርት እድገት፤ ለስራ ፈጠራ፤ለገቢ እድገት፤ ረሃብንና ድህነትን ለማጥፋት ወዘተ ማነቆ ነው። የሃገሪቱ የምርት እድገት ታፍኗል፤ የስራ እድል ተበክሏል።

እነዚህ ብሄራዊ ችግሮች የአገዛዝ መጥፎነት ውጤት ናቸው። ስልዚህ፤ አገር ወዳድ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ማሰብና መተግበር ያለባቸው፤ ጋናውያን እንዳደረጉት፤ ለዚህ ሁሉን አቀፍ ሰቆቃ፤ ሁሉን አቀፍ መፍትሄ ይጠይቃል ብለው መነሳት ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ህወሓት እንዳቀደው፤ ተነጣጥሎ ሊወጣው የማይችለው ሰቆቃ ውስጥ እንደገባ ተጨማሪ ማስረጃ አያስፈልግም። ህብረተሰቡ፤ በህይወቱ፤ በኑሮው ዋጋ እየከፈለ ነው። የህጻናት፤ የልጃገረዶችና የሌሎች ወጣቶች አሰቃቂ ኑሮ የአገዛዙን በደል ገልጸውታል። የኢትዮጵያ ሁኔታ፤ ልክ እንደ ላይበሪያ፤ ሶማሊያ፤ ሩዋንዳ ወዘተ፤ ሰቆቃው ሁሉን የህብረተሰብ ክፍሎች፤ ሁሉን ጎሳዎች ነክቷል። ለዚህ ማስረጃ ካስፈለገ ለማመልከት ያህል፤ (Illustrative Samples) በሰብአዊ መብቶች ላይ የደረሰውን ወንጀል ለማሳየት ጥቂቶቹን ከዚህ በታች አቅርበናል። አንባቢውን አሁንም የምናሳስበው፤ አገር ቤትም ሆነ ውጭ፤ ኢትዮጵያውያን የጎደላቸው ማስረጃ አይደለም። ለውጥ ለማምጣት ያላቸው ፈቃደኛነት፤ ችሎታ፤ ድፍረት፤ ውሳኔ፤ አብሮ መስራት፤ ለአንድ አገርና ለመላው ሕዝብ ፍትህ መታገል አለመኖሩ ነው። (The deficiency of will to change and the lack of capacity and readiness to move beyond words has direct correlation with the persistence of dictatorial governance in Ethiopia). ከግድያ፤ ከዘር ማጥፋት፤ ከትምክህተኛነት፤ ከመሰደድ፤ ክብርን ከማጣት፤ ወዘተ በላይ ለአገዛዙ አፋኝነት ምን ማስረጃ ያስፈልጋል?

ማስርጃ ሞልቷል፤ ለጋራ ፍትህና ብልጽግና የሚያስብ ደፋር ጠፍቷል

ከምርጫ ዘጠና ሰባት ጀምሮ ያሳሰብኩት፤ የኢትዮጵያ ችግር የመለስ አምባገነናዊይነት ብቻ አይደለም የሚል ነበር። አምባገነን መሪ ለአገዛዙ የሚበጀውን ተቋሞችና አመራር ይፈጥራል። መለስ የፈጠረው አገዛዝ አሁን እንዳለ የቀጠለው ለዚህ ነው። ግለሰቡ ከዚህ አለም አልፏል። ስርአቱ ግን በተባባሰ ሁኔታ ቀጥሏል። ተተኪ የሆነው ጠቅላይ ሚኒስተር ሃይለማሪያም ደሳለኝ፤ ተገዶም ሆነ በፈቃዱ የመለስን "መንፈስና ርእየት" አጠንክሮ ለማራመድ ይጥራል። ምንም እንኳን በሃይማኖቱ እውነትን መናገር ያደገበት ቢሆንም፤ ከዱሮው በባሰ ሁኔታ እውነቱን ከዷል። በፓርላማ መደበኛ ስብሰባ የተናገራቸው ሁለት ፍጹም ከጠቅላይ ሚንስትሩ የማይጠበቁ ክህደቶች የኢትዮጵያን ሕዝብ "የባሰ መጣ"

እንዲሉ አስገድዷቸዋል። አንዱ በኢትዮጵያ "አንድም የፖለቲካ እስረኛ የለም" ማለቱ ነው። ሁለተኛው፤ ኢትዮጵያ "የውጭ ምንዛሬ እጥረት የለባትም" ያለው ነው። ሁለተኛውን አከራካሪ ነው ብለን እንተወው። የመንግሥትን ካዝና ማንም አያውቅም። እነ እስክንድር ነጋ፤ አንዷአለም አራጌ፤ ቁጥራቸው ብዙ ነው ተብሎ የሚገመተው፤ "የአነግ አባሎች ናችሁ፤ ሽብርተኞች ናችሁ" ተብለው በተፈጠረ ማስረጃ የታሰሩትን ኢትዮጵያውያን ቤት፤ ልጅ፤ ዘመድ፤ ወዳጅ እንደሌላቸው አድርጎ የፖለቲካ "እስረኞች የሉም" ማለት ለህሊና የሚቀፍ ነው። በውድቀት ላይ ትገኛለች ለምትባል አገር ውሼት ጠንቅ ነው። ከአንድ መሪ የሚጠበቅ አይደለም። በውሼት ከሶ በውሼት መፍረድ የለመደው አገዛዝ ጠበቃ አግኝቷል ማለት ነው። ተቃዋሚ ስለሌለ ውሼትና ክህደት እንደ እውነትና ሃቅ ሆነው ይነገራሉ። የጎሳዊ ስርአት አንዱ ጉዳት ይህ ነው። አምባገነናዊ አገዛዝና ክህደት አብረው እየተጓዙ እያየን ነው።

ጎሳዊ በሆነ በቋንቋ ልዩነቶች የተመሰረተ ህገመንግሥትና አስተዳደር፤ የዜግነትን መብት ትርጉም አጥፍቶታል። ማንነትን ከኢትዮጵያዊነት ወደ ጎሰኛነት ለውጦታል። የፖለቲካ ስልጣን የጠባብ ጎሰኛና የቋንቋ አቅጣጫ እንዲወስድ አድርጎታል። ምን ማለት ነው? በትግራይ ውስጥ፤ ትግሬ የሆነ የበለጠ መብት አለው፤ በኦሮሚያ፤ ኦሮሞ የሆነ የበለጠ መብት አለው ወዘተ ማለት ነው። ሌላው "መጤ" ስለሆነ አገርህ ተመለስ እየተባለ ነው። የመኖር አለመኖር መብት በቋንቋ ከተመራ፤ ትግሬ የሆነ ግለሰብ ኦሮሚያ ለመኖር፤ ለመስራት፤ ለመወዳደር አይችልም ማለት ነው። ኦሮሞ የሆነ በትግራይ ክልል እንደዚሁ፤ አማራ የሆነ ከአማራ ክልል ውጭ መኖር፤ መስራት፤ ሃብት መያዝ አይችልም ወዘተ። በአሜሪካ ሆነ በካናዳ አንድ ግለሰብ የትም ክፍለ ሃገር ሰርቶ ለመኖር ይችላል። ባለበት ለመመረጥና ለመምረጥ ይችላል። ኢትዮጵያ አይችልም፤ ብዙ ገደብ አለበት። ይህ በዜግነት፤ በብሄራዊ አንድነትና በህይወት፤ በአብሮ መስራትና በአብሮ መኖር፤ በስልጣን ክፍፍል፤ በተለይ በተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ላይ ህይወት ለዋጭ የሆነ ክስተት አለው። የተፈጥሮ ሃብት መቆጣጠር እየቆየ እንደሚባባስ አንጠራጠር። በተለይ ውሃና ለም መሬት። ማንም ኢትዮጵያዊ በዚህ ክልል የመኖር መብት የለህም ከተባለ፤ ውሳኔውን ካልተቀበልክ "ወንጀለኛ ነህ " ተብሎ ኢትዮጵያዊነቱ ይናዳል ማለት ነው። በጉራ ፈርዳ የሆነው "ከሕግ ውጭ የሚኖር፤ የሚሰራ፤ ሃብት የያዘ ሁሉ" ካለበት መውጣት አለበት የሚል፤ ህገመንግሥቱን የሚጻረር ድርጊት ነው። የህወሓት አመራር "የክልል አስተዳደር በክልሉ" የመኖር/አለመኖር መብቶችን ለመንጠቅ መብት አለው የሚል ነው። በግልጽ የማይነገር፤ በድርጊት የሚታይ አመራር ነው። በሌሎች አገሮች ፌደራል ስርአቶች፤ ህገመንግሥቱ የመላው ህብረተሰብ የሆነ፤ ማንም የማይጥሰው ህግ ነው። (Supreme law of the land). ሕጉ እንደተፈለገ የፖለቲካ መሳሪያ አይሆንም። የሕግ የበላይነት ተብሎ የሚነገረው ለዚህ ነው። ፕሬዘደንት አባማ የህገመንግስቱ አገልጋይ ነው። ወንጀል ከሰራና ከተመሰከረበት ከፕሬዘደንትነቱ ይለቃል፤ እንደ ኒክሰን።

በኢትዮጵያ፤ ማእከላዊ መንግሥቱን የሚያሽከረክረው ህወሓት ሲፈልግ በየትም ክልል የውስጥ አስተዳደር ጣልቃ ይገባል። ሲፈልግ የክልል አስተዳደር ውሳኔ ነው ይላል። ህገመንግሥቱን ለፖለቲካ ውሳኔ ይጠቀምበታል ማለት ነው። በሕግ የማይመራና የማይዳኝ አገዛዝ መዘዙ ከዚህ ላይ ነው። ማንም የሚከራከረው የለም። በሁለቱም አንጻር ቢታይ፤ ለመካድ የማይቻለው ውሳኔው ከገዢው ፓርቲና ከተባባሪዎቹ የበላዮች ሊወጣ አይችልም። የሕግ አጽዳቂዎችና አስፈጻሚዎች ነጻነት የላቸውም። (checks and balances do not exist). የፓርቲው ደጋፊ ናቸው። የዚህ አይነት የጎሳና የቋንቋ ልዩነቶች አወቃቀር፤ አስተዳደርና አወሳሰን፤ ለገዢው ፓርቲና ለተባባሪዎቹ ህገመንግሥቱ ከሚፈቅደው በላይ ስልጣን ስጥቷቸዋል። ስልጣን አለን ብለው ስለሚገምቱ፤ ሰብአዊ መብቶችን በተደጋጋሚ ለመጣስና ከሃላፊነት ነጻ ለመሆን ይረዳቸዋል። "የፖለቲካ እስረኞች የሉም" ለማለት ይረዳቸዋል። ወሳኙ የፌደራል መንግሥት እኔ ከጥፋቱ የለሁበትም ሊል ይችላል። ጋምቤላና ጎንደር እንደሆነው። የክልሉ አስተዳደር እኔ የተከተልኩት የፌደራል መንግሥቱን ትእዛዝ ነው (የመለስን) ይላል። በጋምቤላ፤ "እኔ ወንጀለኛ ከሆንኩ መለስም ተጠያቂ ነው" እንዳለው። የፌደራል መንግሥቱና የክልሉ ስልጣን የት ላይ እንደሚጀምር፤ የት ላይ እንደሚለያይ፤ የት ላይ እንደሚያበቃ ግልጽ ያልሆነ አገዛዝ መኖሩ አይካድም። በምእራፍ ሁለት እንዳሳየነው፤ ለሰብአዊ መብቶች መረገጥ ማንም ሃላፊነት የለውም ማለት ነው። ይህ ሆን ተብሎ የተዘጋጀ አገዛዝ ነው። ተቃዋሚ ፓርቲዎችና የማህበረሰብ ድርጅቶች ማጤን ያለባቸው ነጥብ አለ። የትም ቦታ ቢሆን የትም፤ በፌደራል ትእዛዝ ይወሰን ወይንም በክልል አስተዳደር፤ በሰው ህይወትና በንብረት ላይ የተደረገ ወንጀል በሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወደ ተጠያቂነትና ሃላፊነት ያመራል። በክልል ስልጣን አሳቦ ወንጀልን ለመደበቅ አይቻልም። ስርአቱ የወለደው አገዛዙ የተቆላለፈ ሆኖ እንዲሰራ ስለሆነ፤ ወሳኙ ተጠያቂነት አለበት። የሰረቀውና ያሸሸው ገንዘብም ተደብቆ አይቆይም። መመለስ አለበት፤ ለማስመለ ይቻላል። ማስረጃ መሰብሰብ የሚጠቅመው ለዚህ ነው።

የተባበሩት መንግስታት የሚቀበለው የሕዝብ ማጥፋት (ጀኖሳይድ) ትርጉም፤ "በከፊል ሆነ በጥቅል፤ አንድ ህብረ-ሕዝብ ክፍል/ነገድ/ህልውናው የታወቀ ሕዝብ ወይንም ዘር፤ ወይንም የሃይማኖት ተከታይ፤ ሕዝብን ለማጥፋት ወይንም በማጥፋት የተሰራ ማንኛውም ወንጀለኛ ተግባር ነው። ወንጀሉ፤ በሕግ ያስጠይቃል፤ ያስከስሳል።" ይህን ሕግ ብዙ

አገሮች ተቀብለውታል። የአፍሪካ አንድነት ማህበርም ሙሉ በሙሉ ከስራ ላይ ባያውለውም ያምንበታል። "አንድ ማንነቱ/ምንነቱ በሕግ የታወቀ፤ በኑሮ/ባህል/ዘር/ቋንቋ ወዘተ የተሳሰረ ሕዝብን ከሚኖርበት ምድር ሆነ ብሎ ያለፈቃዱ በሃይል በማስፈራራት፤ በማስገደድ፤ በማሰር፤ በማባረር፤ በመግደል፤ ከሚኖርበት በማስወጣት የተፈጸመ ድርጊት፤ የዘር ወገዳ ወይንም የዘር ጽዳት ይባላል።" በዚህም መለኪያ፤ የህወሓት/የኢህአዴግ ባለስልጣናት ፍርድ የሚቀርቡበት ብዙ ማስረጃ አለ። ሰላማዊ ሕዝብ ማጥፋት ወይንም ሆነ ብሎ ያለ ጥፋትና ያለ ፍርድ መግደል ወይንም ማስገደል (ጀኖሳይድ)፤ ማሰርና፤ ያለፈቃዱ አስገድዶ ከሚኖርበት ማባረር፤ ሕዝብን በሰላም ከሚሰራበት፤ ከኑሮው፤ ከንብረቱ ወዘተ ማባረር ወይንም ማሳደድ፤ "በሕዝብ ወይንም በሰባዊ ፍጡር ላይ የተደረገ ኢ-ሰብአዊ ወንጀል Crime Against Humanity" ነው ይላል።

ዓለም አቀፍ የሆነውን ኢንተርናሽናል ክሪሚናል ኮርት (የዓለም የወንጀለኛ ፍርድ ቤት) የተባለውን የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ሲመሰርት ዋና አላማው ስልጣን ተጠቅመው በግለሰቦች ወይንም፤ ሕዝቦች ላይ ወንጀል የፈጸመ/የፈጸሙ መሪን/መሪዎችንና የሚመለከታቸውን ግለሰቦች ለፍርድ ለማቅረብ ነው። የዚህ ተቋም አዋጅ የሚለው "በሮም ደንብ (ስታቹትስ) መሰረት፤ ይህ ድርጅት የመጀመሪያው ዘላቂነት ያለው ዓለም አቀፍ ተቋም ሲሆን፤ አላማው፤ በሰላማዊ ሰው/ሰዎች ላይ ወንጀል የሰሩትን መሪዎች ሁሉ ለፍርድ ለማቅረብ" ነው። እአአ በ1998 አንድ መቶ አገሮች ይህን ተቋም አጸደቁ፤ 90ዎቹ ሰለፈረሙ፤ መተግበር ጀምሯል። ምንም እንኳን የሱዳን መንግሥት ህጉን ባይቀበልም፤ ፕሬዘደንት ባሽር ከተከሳሾቹ አንዱ ነው። የዱሮው የዩጎስላቪያ ፕሬዘደንት ሚሎሶቪችና የላይበሪያው ታይለር እንደዚሁ ለፍርድ ቀርበዋል። እነዚህ የሚያመለክቱት የጎሳ ፌደራሊዝም ከክስ ሊያድን አለመቻሉን ነው። አንዱ በሌው አመካኝቶ ወንጀል ከሰራ አልሰራሁም ለማለት አይችልም። ማንም ባለስልጣን በሰላማዊ ግለሰብና በህብረተሰብ ላይ፤ ያለ አግባብ፤ ያለ ሕግ፤ ያለ ፍርድ ወዘተ ግድያ የፈጸመ፤ ትእዛዝ ሰጥቶ ያስገደለ ወይንም በሰው/ሰዎች ላይ ማናኛውንም ወንጀለኛ ተግባር ያካሄደ ሁሉ በዚህ የዓለም ፍርድ ቤት ሊከሰስ ይችላል። ያለፉትን ክሶች መሰረት በማድረግ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ የተካሄዱና አሁንም በመካሄዱ ወንጀሎች ላይ ያሉ የሚከተሉት፤ በንጹህ ኢትዮጵያዊያን ላይ የተደረጉና ወደፊትም የሚደረጉ ግድያዎች ሁሉ ሊያስከስሱን ይችላሉ። የህወሓት አመራር ጎሳዎችን በመከፋፈልና አንዱ በሌላው እትዮጵያዊ ላይ እልቂት እንዲያካጊድ በማድረግ ወንጀሉን ከራሱ ለማራቅ ይሞክራል። ለማለት የምንገደደው ህወሓት የሌለበትና የማይደግፈው ወንጀል አይፈፀምም። የሰብአዊ መብት ተቋሞች የሚመሰክሩቱ የምንለው ሃሳብ ተደጋፊነት እንዳለው ነው። ግድያዎቹ ማንንም በሃላፊነት አያስጠይቁም በሚል ዘዴ ስለተካሄዱ፤ ለውይይትና ለመተግበር ያመቹ ዘንድ የማያሻሙት መረጃዎች በሚከተለው ሰንጠረዥ ቀርበዋል።

የግድያ ናሙና ለፍትሕ ለቆሙ ሁሉ ይረዳል

1. እአአ በ1991፤ በአርሲ (ዲቡና ጂጋን) ፤ በህወሓት መንግሥት ታጣቂዎች፤ 150 ሰላማዊ የአማራ ተዎላጆች ናችሁ ተብለው ተገድለዋል።

2. በዚሁ አመት በአርባ ጉጉ/ሐረር ("ኦነግ ነን") የተባሉ ታጣቂዎች የህወሓት የበላይ አመራር እያወቀ 1000 የአማራ ተወላጆች ገድለዋል። ብዙ ንብረት አውድመዋል፤ አቃጥለዋል።

3. እአአ 1992፤ የህወሓት ታጣቂዎች ሰላማዊ የሆኑ 92 የኦሮሞ ተወላጆችን የኦነግ ደጋፊዎች ናችሁ ብለው፤ እራሳቸው ፈርደው ገድለዋል።

4. እአአ 1992፤ በዲኖ/ሃረር 140 የአማራ ተወላጆች ናችሁ ተብለው ተገድለዋል።

5. እአአ 1992፤ የህወሓት መንግሥት ታጣቂዎች አንዲት እናትና ወንድሟን በገመድ አንቀው ገድልዋል።

6. እአአ 1993/1994፤ የህወሓት ወታደሮች 18 ሰላማዊ ኢትዮጵያውያን ገድልዋል።

7. እአአ 2001፤ የህወሓት ታጣቂዎች 40 ሰላማዊ የአዲስ አበባ ዩንበርስቲ ተማሪዎች ገድለዋል።

8. እአአ 2002፤ በተፒ የህወሓት ታጣቂዎች 200 ሰላማዊ ኢትዮጵያውያን ገድለዋል።

9. እአ.አ 2002፤ በሲዳማ የህወሓት ታጣቂዎች 25 ሰላማዊ ኢትዮጵያውያን ገድለዋል።

10. እ.አአ 2003፤ በኦጋዴን የህወሓት ወታደሮች 47 ሰላማዊ የሶማሌ ተወላጆች ገድለዋል።

11. እ.አ.አ 2003 የህወሓት እዝ 424 ሰላማዊ አኝዋኮችን ገድለዋል። ከዚህ በኋላ ጀኖሳይድ ወች እንዳረጋገጠው እስከ 2005 ድረስ 1500 ተገድለዋል። ይህ ብቻ ለከስ ይበቃል።

12. እአአ 2005 ከ 193 በላይ ሰላማዊ ወጣቶች፤ እናቶች፤ አባቶች ለሙብታቸው በህገመንግሥቱ መሰረት ለሰላማዊ ሰልፍ ሰለወጡ ብቻ በህውሓት ልዩ ኢጋዚ በተባለና ሌላ የፖሊስና ልዩ ለባሽ ሃይል ተጨፍጭፈዋል።

13. እአአ 2006፤ በጅማ/ኦሮምያ ክልል 50 ክርስትያኖች፤ በሃይማኖታችው ምክንያት ብቻ ተገድለዋል፤ መንግሥት ወንጀሉን አልመረመረም።

14. እአአ 2008፤ 300 የቤኒ ሻንጉል-ጉሙዝ ሰላማዊ ነዋሪዎች ተገድለዋል።

15. እአአ 2008፤ 18 የአፋር ተወላጆች የሆኑ ሰላማዊ ሰዎች ተገድለዋል።

*ወንጀለኛ መለየት ተገቢ ነው*

*መጠንቀቅ ያለብን ይህን ያደረገውን አመራር ከሕዝቡ ከመለየቱ ላይ ነው። ቀደም ሲል እንዳሳየሁት፤ የትግራይ ወይንም የኦሮሞ ወይንም የሶማሌ ሕዝብ ሌላውን በጥላቻ አያይም። በአብዛኛው፤ የትግራይ ሕዝብ፤ አገሩን ወዳድ፤ ለታሪኩ፤ ለኃይማኖቱ፤ ለባህሉ ተቆርቋሪ ነው የሚል እምነት አለኝ። ወደፊት የምናየው የትግራይ ተቃዋሚ ለተከበረች፤ አንድነቷ ለጸና፤ እኩልነቷ በሕግ ለታወቀ ኢትዮጵያ እንደሚነሳ አልጠራጠርም። ታሪኩ ያስገድደዋል። ኦሮሞውም እንደዚሁ ሌላውን ፈልጎ አብሮ ፍትሃዊነት፤ እኩልነት የሰፈነባትን ኢትዮጵያ ለመገንባት እንደሚነሳ አምናለሁ። ሌሎቻችን ማበረታታት ያለብን ህብረተሰቡ በጋራ ለጥላቻ ሳይሆን ለፍትህ እንዲነሳ ነው። ሁሉም ማወቅ ያለበት፤ በአጠቃላይ ሲታይ፤ ህወሓት/ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘበት ጀምሮ በተከታታይ የታወቀና ገና ያልታወቀ ከአፋኝ አገዛዝና አመራር የመጣ ወንጀል ፈጽሟል። ለእነዚህና በብዙ ሽህ ለሚቆጠሩ ሌሎች ስማቸው ለታወቀና ላልታወቀ፤ በዱር፤ በገደል፤ በእስር ቤት ኢሰብአዊ በሆነ መንገድ ለተጨፈጨፉ ሰላማዊ ኢትዮጵያውያን ሁሉ የመንግሥት፤ የፓርቲውና የክልል ከፍተኛ መሪዎች፤ እዞችና ስራ አስፈጻሚዎች በዓለም የፍርድና የሰብአዊ መብት ጠባቂ ድርጅቶች፤ በተለይ ኣይሲሲ ለሰሩት ወንጀል በሃላፊነት፤ በተጠያቂነት፤ በተጠሪነት መቅረብ አለባቸው። ከሌሎች አገሮች ልምድ ለመቅሰም የምንችለው ሰላማዊና ሕጋዊ አማራጭ ይህን ይመስላል። ዋናው ቁም ነገር፤ በሰብአዊ መብቶች መረገጥና መጣስ የሚያምኑ ሁሉ፤ በጎሳ፤ በሃይማኖት፤ በሌላ ሳይገቱ፤ በድፍረት፤ በዘመናዊ ዝግጅት፤ አሰራርና ስልት፤ በዘላቂነት፤ መረዳዳትና ሃይልን መሰብሰብ ይኖርባቸዋል። ይህን ማድረግ ከታሪክ ተጣያቂነት ሊያድን ይችላል። ለህብረተሰብ፤ በተለይ ለወጣቱ ትውልድ ድፍረት ይሰጠዋል።*

ከዚህ ባሻገር፤ የህወሓት/ኢህአዴግ አዛዥዎች ፈቃደኛ ቢሆኑ ኖሮ፤ ወንጀለኞችን ለዓለም ፍርድ ቤት ከማቀረብ ይልቅ፤ ለእርቅ፤ ለሰላም፤ ለድርድር፤ ጥፋትን አምኖ ይቅርታ ለመጠየቅ አመቻች የሚሆን የፖለቲካውን ሜዳ ክፍት ማድረግ ነው። ከመቸውም በላይ ዛሬ፤ አገር አቀፍ የሆነ የእርቅ ድርድር ያስፈልጋል። አገርን ከአደጋ የሚያድን የይቅር ባይነት ውይይት፤ የሚል የፍትህ ተሃድሶ (Restorative Justice) ድርድር ማካሄድ ይመረጣል። የፍትህ ተሃድሶ ሁሉን የህብረተሰብ ክፍሎች የሚያሳትፍ (All Stakeholders)፤ ያለፍርሃት የሚያነጋግር፤ የሃይማኖት መሪዎች፤ አዛውንቶች፤ እናቶች፤ ወጣቶች፤ የማህበረሰብ መሪዎች፤ ምሁራን፤ የፖለቲካ ተቃዋሚዎችና የህወሓት/ኢህአዴግ ባለስልጣናት የሚሳተፉበት መሆን ይኖርበታል። የደቡብ አፍሪካው ዴዝመንድ ቱቱ፤ ልምድ ስላላቸው፤ የስብሰባው አመቻች (Expert facilitator) ሊሆኑ ይችላሉ። ለሁሉም የሚጠቅም፤ ገደብ የሌለው ተሃድሶን ሊያመጣ የሚችል ውይይት ጥሩ አማራጭ ነው። ሆኖም፤ በራሱ የሚፈጠር አይደለም። ጠበቃ ያስፈልገዋል። የገዢው ፓርቲ አመራር አሁንም በክህደት አዙሪኝ የተበከለ ነው። ደቡብ አፍሪካ፤ ሩዋንዳ፤ ላይቤሪያ፤ በቅርቡ በርማ ያሳዩትን አማራጮች መዝኖ ከስራ ላይ ማዋል ድክመት አይደለም። ጥበብ ነው እንላለን። ይህ አማራጭ በጠባብ ጎሰኛነት ለተበከለው ለአሁኑና ለተከታታይ ትውልድ አኩሪ ይሆናል። ግብጾች እንዳደረጉት፤ ጋናውያን እንዳደረጉት፤የደቡብ አፍሪካ ሕዝብ እንዳደረገው፤ ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን ችግሮች ራሳቸው ለመወጣት እንደሚችሉ ያሳያል። በጋር መደራደር መተማመንን፤ እርቅንና መቻቻልን ያመጣል። ሆኖም የህወሓትን/ኢህአዴግን የበላዮች አስተዋይነትና ፈቃደኝነትንና ለፍትህ መቆምን ይጠይቃል። ከእለት ስልጣንና ጥቅም ይልቅ ለረጅም ጊዜ የህብረተሰብ ጥቅም ማሰብን ይጠይቃል። ይህን ያልተለመደ አማራጭ ጎዳና አለመቀበል፤ አደገኛ ነው። እንደገና ኢትዮጵያንና፤ እርጋታን እርቅን ናፋቂ የሆነውን ህብረተሰቧን ከአዙሪኝ ችግር ውስጥ ያስገባቸዋል። **(the vicious cycle of instability, injustice, inequality, corruption and nepotism will persist and this will lead to the probability of a failed state).** ይህ ለማንም አያዋጣም።

የህወሓት የአፈናና የምዝበራ አገዛዝ ህብረተሰቡን ወደ እርስ በእርስ እልቂት እየመራው መሆኑን ከሌሎች አገሮች ታሪክና ልምድ ለማየት ሳይንቲስት መሆን አያስፈልግም። ድርጊቱ ያሳያል።

ብሄራዊ ችግሮችን በጋራ አለመፍታት መታወቂያችን አይሁን

የጎሳ-ተኮር ፌደራሊዝምን የፈጠረውን ከፋፋይነትና ድክመትን ለመደምደም፤ በኢትዮጵያ ባህልና የፖለቲካ ታሪክ፤ ጠበብት የሆነውን ዶክቶር ዶናልድ ለቪንን ልጠቅስ እፈልጋለሁ። በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩንበርስቲ በማስተማር ላይ ሳለ አንድ ተማሪ እንዲህ ብሎ ጠየቀኝ ይላል፤ ለቪን። "መቸ ይሆን፤ እኛ ኢትዮጵያውያን ተስማምተን አንድ አገራዊ ችግር በጋራ የምንፈታው?" ጥያቄው ሁላችንም የሚመለከት ስለሆነ አንባቢው መልሱን እንዲሰጥበት አሳስባለሁ። ላለፉት አምሳ አመታት ደጋግመን ያየነው፤ ዛሬ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ማነቆ የሆነው ችግር የህወሓት ጥንካሬ ብቻ አይደለም። በአብዛኛው ድክመቱና ክፍተቱ የተቃዋሚው የፖለቲካ፤ የማህበረሰብ ስብስብ፤ የምሁራንና ሌሎች አብሮ ለአንድ ኢትዮጵያዊ አላማ፤ ለፍትህ፤ ለእውነተኛ እኩልነት፤ ለዲሞክራሲ አለመቆም ነው። በመከባበር፤ በመተማመን፤ በመረዳዳት አብሮ ችግሮችን ለመፍታት አለመቻል ለገዢው ፓርቲ ጥንካሬ ሰጥቷል። የኢትዮጵያን ሕዝብ ከምርጫ ዘጠና ሰባት በኋላ ተስፋ አስቆርጦታል። የውጭ ታዛቢዎች ሊገባቸው ያልቻለው፤ የኢትዮጵያ ስደተኞች በግለሰብ ደረጃ ሲታዩ ለአገራቸው ተቆርቋሪዎች ናቸው። ራሳቸውን ችለው ልጆቻቸውን ለማስተማር፤ ቤተሰቦቻቸውን ለመርዳት ጊዜ አይወስድባቸውም። በያሉበት የግል አገልግሎት፤ የጸሎት፤ የመመገቢያና ሌሎች ተቋሞችን ለመመስረት ችሎታ እንዳላቸው ይናገራሉ፤ ያደንቃሉ። በግል ደረጃ ሲታይ አብዛኛው በየቤቱ ትቷት ለመጣው አገሩና ወገኑ የፖለቲካ ሃኪም ሆኗል። ይህ የግል ጸጸት ወደ ማህበረሰብ ጥንካሬ አልተለወጠም። እንዲያውም እየባሰ የሄደ ይመስላል። ከላይ የቀረቡትን የሰብአዊ መብቶች ገፈፋና አገራዊ ምዝበራ በጋራ ሆነው ለዓለም ሕዝብ ለማሳወቅ፤ ክስ ለማቅረብ ሲሰሩ አይታይም። የኛ ድክመት ለአፋኙ አገዛዝ ጥንካሬ ሆኗል።

የፖለቲክ ሃኪሞች ሆነናል

ከአርባ አመታት በኋላ፤ በጋራ ሆኖ የኢትዮጵያን ህብረተሰብ ችግር ለመፍታት ያለመቻል ጥያቄ እንዳለ ነው። ኢትዮጵያ ብዙ የፖለቲካ ሃኪሞች አሏት። እነዚህ ሃኪሞች ችግሩን ያወቁት አይመስለኝም። በአብዛኛው፤ የጎሰኞች ሰለባ ሆነዋል። በተለይ፤ በኢትዮጵያዊነት፤ ለአንድ ጠንካራ፤ ሃብታምና ለሁሉም ቤት ለምትሆን ኢትዮጵያ በአንድ ላይ አለመሰብሰባቸው። ችግሩን በሚገባ ካላወቁት፤ በሽተኛውን ለማከም አይችሉም። እነዚህ የፖለቲካ ሃኪሞች፤ ከመጻፍ፤ ከመናገር፤ ከመሰብሰብ ባሻገር፤ ለህብረተሰቡ በአንድ ላይ ሆነው መፍትሄ ሲፈልጉ አይታዩም። አገር ቤት ያለው ተቃዋሚ ክፍል ውጭ ካለው አይሻልም። ውጭ ያለው ከአገር ቤቱ አይሻልም። የተማረው ካልተማረው አይሻልም። በወሬ ደረጃ ሁሉም ለኢትዮጵያ ሃኪም ነኝ ይላል። ሃኪም ከሆነ በመጀመሪያ ችግሩን መዳሰስና ማወቅ ይገባዋል። ሆኖም፤ ልክ እንደ ህወሓት የበላዮች የምናውቀው እኛ ብቻ ነን የሚል ትውልድ ተፈጥሯል። ጎሰኛ እያለ ራሱ ከጎሰኛነት ነጻ አልወጣም። ዲሞክራሲ እያለ ከአምባገነንነት አስተሳሰብ ራሱን ነጻ አላወጣም። ለዚህ ተደጋጋሚ ችግር መልሱን መስጠት ያለበት በመጀመርያ ደረጃ ተቃዋሚው ክፍል ነው። የህወሓት የበላዮች አሁንም የወደፊቱን የሚያዩት "በመለስ ራእይ" ተከታታይነት ነው። ህወሓት/ኢህአዴግ ተቃዋሚውን የሚያየው እንደ ጠላት ነው። እንደ አጋር አይደለም። ይህ ግትር (Inflexible) አመለካከት ለኢትዮጵያና ለአብዛኛው ሕዝቧ አደገኛ ሆኗል።

በተለይ አሳሳቢ የሆነው፤ ከፍጹም ድህነት ወጥቶ በባዶ ኪስ የተሰደደው በነጻ፤ በድሎት፤ በሰላም  የሚኖረው ስደተኛ ኢትዮጵያዊ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመማር እድል እንደከፈተለት እየረሳው መሄዱ ነው። ለሁላችንም እድል የተከፈተልን፤ ከአገር ተሰደን የወጣን ሁሉ የኢትዮጵያ ጉዳይ እንቅልፍ ነሳን ብለን የምናወራው (The talking heads) ሁሉ ትተነው ለመጣነው ህብረተሰብ ገንቢ አስተዋጽኦ አላደረግንም። ወገን ካለበት ተገዶ ከልጁና ከሚስቱ ጋር እንደ ተራ ወንጀለኛ ሲሰደድ እናያለን። ልጅ ከአባቱ ሲለያይ እንመለከታለን። በአገር ውስጥ ለመሰደድ የተገደዱ ወገኖቻችን እንዳይሞቱ ተብሎ የሚሰጣቸው የምግብ መጠን ለህይወት ማጎልመሻ እንደማይሆን እናያለን ፡፡ ሆነ ተብሎ የአማራው ሕዝብ ቁጥር ሲቀነስ እናያለን። አንዳንድ ጊዜ፤ለአንድ ሳምንት "እግዚኦ" ከማለት በላይ የምናስብበትና የምንሰራበት አሁን ካልሆነ መቸ እንደሚሆን ራሳችን መጠየቅ አልቻልንም። ስለሆነም፤ ሁኔታው በታሪክ አስጠያቂ መሆኑን መቀበል የሰብአነታችን መለኪያ ሆኗል። ራሳችን ለመስራት ለምንችላቸው፤ ሁላችንም ለምንጋራቸው ጉዳዮች፤ በተለይ፤ ለሰብአዊ መብቶች የቆምን ሁሉ አብረን እንደምንነሳ ተስፋ እናደርጋለን። መቀበል ያለብን፤ እርምጃዎች ስንወስድ ብቻ ነው "እኛ ኢትዮጵያውያን ተስማምተን፤ በጋራ አንድ ሃገራዊ ችግር ለመፍታት የምንችለው መቼ ይሆን" የሚለውን ጥያቄ የምንመልስ። ኢትዮጵያን ከሌሎች አገሮች የሚለያት ከጎሳ በላይ አገርን በአንድ ላይ ለአንድ አላማ ቆሞ ከውጭ ጠላት ነጻ ማውጣት ነው። ባሁኑ ክፍለ ዘመን ከፊታችን የተደቀነው ችግር ቀጥተኛ የሆነ የውጭ ወረራ አይደለም። "ዘመናዊ ወራሪዎች" የኢትዮጵያን የተፈጥሮ ሃብት፤ እንዱስትሪና ሌሎች የእድገት መሰረቶች (Pillars of the national

economy) የያዙት፤ አጋር በሆነው በአምባገነኑ መንግሥት ግብዥያ ነው። (Invasion by invitation). ዘዴው ይለያይ እንጂ፤ ካሪቱሪና ሳውዲ ስታር ጋምቤላን ሲቆጣጠሩ የሚኖረው ውጤት ተመሳሳይ ነው። ኢትዮጵያውያን በአገራቸው ጥሪት ለማዘዝ አይችሉም። አብዛኛው የውጭ እርዳታ ለጥቂት ግለሰቦችና ቤተሰቦች የባለጠጋነት መሳሪያ ሆኗል።

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሃኪሞች ከሁሉ በላይ ቀረብ ብለው መመርመር ያለባቸው የራሳችውን አለመለወጥ ጉዳት ነው። ራሳችን ሳንለውጥ የፖለቲካ ሃኪም ነን ብለን፤ ልክ መንግሥቱ ሃይለማሪያምና መለስ ዜናዊ እንደተከተሉት ፈለግ-- ከስልጣን  የሚገኝ እውቀት አጠቃቀም ብንለፈልፍ-- ጠቃሚ ያለው አስተዋጽኦ ለማድረግ አንችልም። መረጃው እስካሁን የትም አለመድረሳችን ነው። የፖለቲካ ሃኪሞች ደጋግመው የማይወያዩበት ሃቅ አለ። የህወሓት/ኢህአዴግ አፈና ለመቀጠል የቻለው በፓርቲው ድርጅታዊና አመራር ጥንካሬ ብቻ አይደለም። ጅምሩንና ተከታታይነቱን ስኬታማ ያደረጉት ቁልፍ ክስተቶች መረሳት የለባቸውም። አንድ፤ መንግሥቱ ኃይለማሪያም አገር ወዳድ፤ የአስተዳደር ልምድና ጥልቅ እውቀት የነበራቸውን፤ ከሁሉም ብሄረሰቦች የተወጣጡ መሪዎችና አዛውንቶች ህዳር 14, 1967 ዓም በጭካኔ መግደሉ መሰረታዊ ክፍተት ፈጠረ። ጭካኔ የሚባል። (This is a turning Point in Ethiopia’s modern history). ሁለት፤ እርህራሄ ያልነበረው ደርግ፤ የጦር መኮንኖች መንግሥቱ ሃይለማሪያምን ለመተካት የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ ሲያደርጉ መተኪያ የሌላቸውን፤ ለአገራቸው አንድነትና ለሕዝብ ደህንነት ቀን ከሌት ይሰሩ የነበሩትን ጀኔራሎች “ሳይቀድሙኝ መቅደም አለብኝ ” በሚል የስልጣን ሽሚያ ጨፈጨፋቸው። ለተገንጣዮችና ለጠባብ ጎሰኞች የማይረሳ <u>ሁለተኛ ክፍተት ፈጠረላቸው። በ1975 ዓም የተደረገው ግድያ የኢትዮጵያን ታሪክ በማይመለስ ደረጃ ለውጦታል። BBC የመዘገበው ታሪካዊ ነው። “ኢትዮጵያ የጦር መሃንዲሶቿን ገደለች። (Ethiopia killed her war engineers)</u>.” አገር ወዳድ መሪዎችና “የጦር መሃንዲሶች” ሲጨፈጨፉ የተከተለው ብሄራዊ ክፍተት ለጠላት አመችቷል። ለመጨመር የምፈልገው፤ ጀኔራላቹ ከመገደላቸው ከዘጠኝ አመታት በፊት የተደረገው ግድያም “ኢትዮጵያ አገር ወዳድ መሪዎቿን ገደለች። ራሷን በራሷ አደከመች”። በተከታታይ አገር ወዳድ የሆኑት መገደላቸው ለውጭ ጠላቶች፤ ለሻቢያና ለህወሓት ተዋግተው የማያገኙትን ድል አጎናጽፏቸዋል። የጎሳ-ተኮር ፌደራሊዝም መሰረት ሊይዝ የቻለው በዚህ ብሄራዊ ክፍተት ነው። አገር ወዳዶች ሁሉ ስለሞቱ ወይንም ለእስር ቤት ስለተዳረጉ፤ ወይንም ሸሽተው ስለወጡ፤ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች የማያገኙት ድል አገኙ። የምእራብ መንግስታት የሚፈልጉትን አገልጋይ መንግሥት ምኒልክ ቤተመንግሥት አስገቡ። የእርዳታ ጎርፍ ያገኘው የውጭ ተጠቃሚዎች ስላገለገለ ነው።

ሻቢያና ህወሓት አዲስ በብሄር/ብሄረሰብ ልዩነቶችና የማይታረቅ ግንኙነት መሰረተ ሃሳብ የያዘ ህገመንግሥት ሲመሰርቱ የኢትዮጵያን ታሪክ እነደገና “ሃሁ” ብለው ጽፈዋል። የጻፉት ከራሳቸው ጭንቅላት የመነጨ አለመሆኑን ስለ ጣሊያን ፋሽስቶች ያቀርብኩት ዘገባ ያመለክታል። የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ይፈልጉት የነበረውና የምእራብ መንግስታት ይመኙት የነበረው መከፋፈል ደረሰ ማለት ነው። ሻቢያና ህወሓት ከኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶችና ከምእራብ መንግሥታት አስፈላጊ ድጋፍ (Critical Support) ባያገኙ ኖሮ ስልጣን ለመያዝ አይችሉም ነበር። በዚያ ጊዜ የነበረው የግራ ክንፍ ትውልድ ጥበብ ስለጎደለው በአንድ ላይ ለመራር አለመቻሉ ከፍተኛ አስትዋፆ እንዳደረገ ቀደም ስል አሳይቻለሁ። ሻቢያና ህወሓት ከውጭ ድጋፍ ባያገኙ ስልጣን ለመያዝ ይችላሉ የሚል ግምት የለንም። ለዚህ ማስረጃው የአሜሪካ መንግስት ሰላይ ድርጅቶች ያወጡትን ዘገባ ነው። ክፍተቱን ያመቻቸው የደርግ አምባገነን መንግሥት አገር ወዳዶችን በጅምላ መጨፍጨፉ ነው። ግራ ክንፉ ለዚህ አስተዋጽኦ አድርጓል። ገዢው ፓርቲ  ይህን የውጭ ሴራና ድጋፍ ክዷል። በራሱ ጀብዱ ድል እንደተጎናጸፈ ይናገራል። ለውለታ የተከፈለው የአሜሪካ መንግሥትና የዓለም ባንክ እርዳታ ባይጎርፍ ህወሓት የት ይደርስ ነበር? አመራሩ የረሳው የአጭር ጊዜ የፖለቲካ ስልጣን ጥቅም የረዥም ጊዜ አደጋዎችን መውለዱን ነው። አንድ አገር ለማኝ ሆኖ አይኖርም። ለማኝ ታዛዢ ለመሆኑ ማስረጃው እንደ አፈር ነው።

ወደኋላ ስናይ የህወሓት አመራር የካደው “በአገራችን የተለያዩ ብሔሮች አገራችን ማስተዳደራቸውን ነው። “አማራ፤ ኦሮሞ፤ ትግሬ፤ ሃረሬ (አዳል) ወዘተ ወዘተ...ክርስትና፤ እስልምናና ካቶሊክም ብሄራዊ ሃይማኖት ሆነው ተፈራርቀዋል።” የህወሓት አመራር ክህደት ለማለት የሚያስደፍረው፤ ኢትዮጵያውያን፤ ከሚለያቸው የሚጋሯቸው ስለሚያመዝኑ ነው። የጎሳ ተኮር ፌደራሊዝም እንደ ታሪካዊ ለውጥ የቀረበው ፍትህን፤ እኩልነትን፤ ተሳታፊነትና የህብረተሰብ የመወሰን ስልጣንን ከማእከል ወደ ክልልና ነዋሪ ስላዛወረ አለመሆኑን አሳይቻለሁ። ታላቁ የአባይ የተሃድሶ ግድብ የሚሰራው የቤኒ ሻንጉል-ጉሙዝ ሕዝብ ምክርና ተሳትፎ ተጠይቆ አይደለም፤ ወዘተ። ህወሓት/ኢህአዴግ የሚወስነው በምስጢር ነው። ማንኛውም ፕሮጀች ጠቃሚነቱ ከህብረተሰቡና ከአገሪቱ ፍላጎት አንጻር አይደለም፤ ከገዢው ፓርቲ የበላይነት አንፃር ነው። ከአገሪቱ ታሪክና ልምድ፤ ከዘመናዊ ዲሞክራሳዊ አስተዳደር ጋር ከተያያዘ ፌደራሊዝም በጣም ይለያል። ዱሮም ቢሆን፤ “የአካባቢ ገዥዎች አካባቢያቸውን (ጎሳቸውን) እያስተዳደሩ ለማእከላዊ መንግሥት ግብር እያስገቡ በሰላም ውለው ያደሩበት ደጉ ዘመንንም ማስታወስ ይቻላል። የአጼ ዮሓንስ የአስተዳደር ዘይቤም ለፌደራሊዝም በእጅጉ የቀርበ እንደሆነ መናገር ይቻላል”። 33/

ባጭሩ፤ የህወሓት/ኢህአዴግ ጎሳ ተኮር ፌደራሊዝም በአብዛኛው ያጠነከረው--በጭቁን ብሄር/ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ስም--የገዢውን ፓርቲ አምባገነንነት ነው። የአንድ አናሳ ብሄር የበላይነት ጎልቶ የሚታየው ለዚህ ነው። በጭቁኖች ህይወትና መብቶች መሻሻል መነጽር ሲሰላ፤ዲሞክርሳዊነቱ ቀፎ እየሆነ ሄዷል። የእባቡንና የአይጢቱን ታሪክ ያቀረብኩበት ምክንያት ለዚህ ነው። ብልጡ የህወሓት የበላይ አመራር ጭቁኖችን ለማባበል ጎሳ ተኮር ፌደራሊዝም እንደ አሜሪካ፤ እንደ ካናዳና እንደ ሌሎች ዲሞክርሳዊ መንግሥታት አይሆንም ብሏል። ለምን ብለን ብንጠይቅ የብልጦች መልስ ይሰጠናል። ኢትዮጵያ እንዳተፈራርስ፤ የኢትዮጵያ ጎሳዎች ልዩነታቸው የማይታረቅ ስለሆነ። "የአፍ መፍቻ" የሆነው የቋንቋ ልዩነት ዋና መለኪያ ግዴታ ስለሆነ በማለት አንጋፋ ብሄረሰቦች ( ኦሮሞውና አማራው) የበላይነት እንዳይዙ ስለሚፈለግ ወዘተ ወዘተ የሚሉ መልሶች ይሰጣል። የትግራይን ምርጥ ጎሰኛ ባለስልጣናት ማን ወሳኝ አደረጋቸው ብለን እንጠይቅ። "በመሳሪያ ሃይል፤ በውጭ ድጋፍ" የበላይነት እውን ከማድረግ ውጭ አጥጋቢ መልስ አናገኝም። ደርግን ያጠፋው የአምባገነን አገዛዝና የውጭ መንግሥታት ሴራ ነው። የሶብየቶች ታዛዥ ሆኖ ብሄራዊ ነኝ ማለት የማያዋጣ መሆኑን አላወቀም ነበር። አገር ወዳዶችን እየጨፈጨፈ ለብሄራዊ አንድነት ቆሚያለሁ ማለት ድንቁርና መሆኑን አላወቀም ነበር። የህወሓት አመራር ፉከራው በሃይል ስልጣን ስለያዝን በሃይል አስወግዱን የሚል ነው። በነጻ፤ በውይይት፤በመመካከር፤ በነጻነትና በነጻ ምርጫ አሸንፉ የሚል አይደለም። ከስሜቱ ባሻገር ሲታይ፤ ጎሳ ተኮር ፌደራሊዝም "...በአፍ መፍቻ ቋንቋ በመከፋፈል" የተመሰረተና የሚመራ አምባገነናዊ መንግሥትን ለስልጣን መገልገያ፤ ለአፈና፤ ለገቢ፤ለሃብትና ለጥሪት ማጎልመሻ መሳሪያ ሆኖ የሚያገለግል ስርአት አድርጎታል። 34/

በኢትዮጵያ ታሪክ ሂደት፤ በልምዷና በባህሏ፤ በመላው ሕዝብ ፍላጎት፤ ተሳትፎና እኩልነት በጥናት የተመሰረተ የሕዝብን የበላይነት የሚያንጸባርቅ እውነተኛ ዲሞክራሳዊ የሆነ ፌደራላዊ ስነስርአት መመስረት ሙሉ በሙሉ እደግፋለሁ። እውነተኛ እኩልነት የሌለባት ኢትዮጵያ ለማንም አትበጅም። የጠባብ ጎሳ- ተኮር ፌደራሊዝም እነዚህንና ሌሎችን ዲሞራሳዊና ፍትሃዊ ተመክሮዎች አያካትትም። ያጠናከረው፤ ራሱን አገልጋይ የሆነውን የጠባብ ጎሰኞች የበላይነት ነው። ይህን ሃቅ በበለጠ የሚያሳየው የቋንቋዎች መከበር አይደለም። እውነተኛ ነጻነትና እኩልነት አይደለም፤ ስለሌለ። የገቢ፤ የሃብትና የንብረት ልዩነት እየሰፋ መሄዱ ነው። ከባዶ ተነስቶ ሚሊዬኔር የሆነ የህወሓት ባለስልጣን ከአኟክ ድሃ ጋር አይወዳደርም። ሆኖም፤ የህወሓት ባለስልጣናትና ደጋፊዎች የጋምቤላ ለም መሬት ተሰጥቷቸዋል። አኟኩ ምን ደረሰው፤ የት ይግባ፤ በምን ይተዳደር?

በፍጠነት እድገት አሳይተዋል የተባሉ አገሮች-የምስራቅ ኤዢያና ፓሲፊክ (ሆንግ ኮንግ፤ ኮሪያ፤ ታይዋን፤ ሲንጋፖር ወዘተ)፤ በአፍሪካ ከነጻነት በኋላ በፍጥነት ያደጉ-ቦትስዋና፤ ሞሪሺየስ፤ ኬፕ ቬርዲ፤ ደቡብ አፍሪካ፤ እነዚህን መብለጥ ትችላለች ተብላ የምትገመተውጋና ወዘተ- የተከተሏቸው ብሄራዊ ፖሊሲዎች አሉ። የመጀመሪያ የእድገት መመሪያ ያደረጉት የተፈጥሮ ሃብታቸውን ተጠቅመው፤ የሕዝባቸውን የማምረት አቅም ማሻሻል ነው። ስለዚህ፤ አገር ወዳድ አመራር መሰረቱ። አስፈላጊ አቅርቦቶችና አገልግሎቶችን ለአብዛኛው ሕዝብ አቀረቡ። ከእነዚህ አቅርቦቶች ምግብ ዋናው ነው። የአገዛዝ መመሪያቸው <u>ይለያያል። ሆኖም ሁሉም የሚጋሩት አገር ወዳድነት ነው።</u> ለኔ፤ አገር ወዳድ ማለት አገርንና ሁሉን ሰው አፍቃሪ፤ ከጎሰኛነት በላይ የሁሉን መብት አስከባሪ ማለት ነው። በፍጥነት ባደጉ አገሮች የትምህርት፤ የጤና፤ የመጠለያ፤ የንጹህ ውሃ፤ የመጸዳጃ፤ የመንገድ አገልግሎቶች፤ የስራ እድል ፈጠራ፤ የሴቶች ተሳታፊነት ወዘተ፤ አድሏዊና ጎሳዊ ባልሆነ መንገድ አብረው ሄደዋል። መሰረተ-ልማት (Infrastructural investment and growth)--ትምህርት፤ ጤና ጥበቃ፤ ንጹህ ውሃ፤ መጸዳጃ፤ መጠለያ፤ መንገድ፤ ድልድይ፤ የውሃ ግድብ ወዘተ-- ድህነትን ለመቀነስና ዘላቂነት ያለው እድገት መሰረት ለመጣል ቁልፍ መሆናቸው አያከራክርም። ሆኖም፤ ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎች ዘላቂነትና ፍትሃዊነት ያጣመረ የእድገት አመራር የተከተሉ አገሮች ፖሊሲ መሰረተ ልማትን ከሌሎች ዘርፎች ነጥለው አላዩም። ከማምረት፤ አገር-ወለድ ከሆነ የግል ኢኮኖሚ እንቅስቃሴና ለብዙ ሚሊዮን ዜጎች የስራ እድል ከሚፈጥሩ ተግባሮች፤ ከግል ባለጠጋነት፤ ከብሄራዊ እድገት ማለታችን ነው። ሁሉም ዘላቂነትና ፍትሃዊነት ያለው እድገት መሰረት ሊይዝ የሚችለው ብሄራዊ የግል ኢኮኖሚ ያለምንም ተጽእኖና አድልዎ ሲያድግ ነው ብለዋል። ይህ ሲሆን፤ ትምሕርት ወደ ስራ ያመራል። መንገድንና የወንዝ ግድብ ለምርት ያገለግላል። የገጠሩ ኢኮኖሚ ከከተማው ጋር ይቆራኛል ወዘተ። ህወሓት ይህን ሚዛናዊ አመራር አይከተልም።

በፍጥነት ያደጉ አገሮች የእድገት መለኪያቸው የህብረተሰቡን አስፈላጊዎች (Basic needs) ማሟላት ነው። እነዚህ ለህይወት አስፈላጊ የሆኑ አቅርቦቶች እየተሟሉ ሲሄዱ ሕዝቡ በራሱ ይተማመናል። የህብረተሰቡ የመፍጠር፤ የማምረት፤ ለውጥን የመቀዳጀት አቅሙ እያደገ ይሄዳል። አገር ወለድ የሆነ እድገት መሰረት ይጥላል። ድሃው ራሱን ችሎ ልጆቹን ያስተምራል። ለአገሩ መንግሥት ግብር ይከፍላል። ለወደፊቱ ያስባል። እንደዚህ እያለ ዘላቂና ፍትሃዊ እድገት ያስተጋባል። በዚህ መለከያ፤ የህወሓት/ኢህአዴግ የጎሳ ተኮር ፌደራሊዝምና መንግሥት የኢትዮጵያን ሕዝብ ፍላጎት አላሟላም።

ምእራፍ አራት የሚያቀርበው የህወሓት/ኢህአዴግ የፖለቲካ-ኢኮኖሚ አመራር ታላቅ አስተዋጽኦ ያደረገው ከፖለቲካ ስልጣን ጋር ለተቆራኙ፤ በተለይ የህወሓት ባለስልጣናት፤ ታማኝ ወዳጆች፤ ቤተሰቦች፤ ምርጥ የትግራይ ተወላጆች፤ ህወሓት የፈጠራቸው ድርጅቶችና የውጭ ኢንቬስተሮች ባለጠጋነት/ሃብታምነት ሆኗል የሚል ነው። ስለዚህ፤ በፖለቲካ ስልጣን የበላይነትና በምዝበራ መካከል ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት ተፈጥሯል።

## ምእራፍ አራት

## ጎጠኛ ባለጠጋዎች የፈጠረ የፖለቲካ-ኢኮኖሚ

"ጥበበኛ መሪ ማለት ለሌሎች (ለሁሉም) በተከታታይና በተግባር፤ የትምህርትና የማህበረሰብ መሻሻል እድል የሚከፍት ነው"

ጆን ኩይንሲ አዳም፣ አሜሪካዊ

"አባይን ያላየ ምንጭ አይቶ ይደነቃል"

የኢትዮጵያውያን ተረት

ችግሩ የፌደራል ስር ዓት አይደለም፤ በፌደራል ስርዓት የሚደረገው አፈናና የተፈጥሮ ኃብት ቁጥጥርና ምዝበራ ነው። የህወሓት አገዛዝ ሰውን ህይወት እንደ እንስሳ ህይወት እንደሚያይ በምእራፍ ሁለትና ሶስት አሳይቻለሁ። በዚህ ክፍል፤ የህወሓት የፖለቲካ-ኢኮኖሚ አመራር የአገሪቱን የተፈጥሮ ሃብትና ቁልፍ የሆኑ የኢኮኖሚ ዘርፎች ለአንድ የጠባብ-ጎሰኛ አመራር ባለጠጋነት መገልገያ እንዳደረጋቸው አሳያለሁ። የፖለቲካ ስልጣን ተጠቅሞ ብሄራዊ ሃብትን ለባለስልጣኖችና ለሌሎች ታማኞች፤ አግባብና ግልጽነት በሌለው መልክ ለውጭ ኢንቬስተሮችና የግል ጥቅም ማሸጋገር ከሰብአዊ መብቶች አፈና ጋር ቀጥታ የሆነ ግንኙነት አለው። ዛሬ፤ ኢትዮጵያ የምትታወቅበት አበይት መለኪያ፤ የነጻነት መዲና፤ የመላው ጥቁር ሕዝቦች የነጻነት መኩሪያ፤ የአፍሪካ አንድነት ማህበር ዋና መናገሻ፤ የክርስቲያንና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በሰላም ተቻችለው መኖሪያ አይደለም። ህወሓት ሆነ ብሎ በጎሳ የከፋፈላት፤ የሕግ የበላይነት የሌለባት፤ ከአስር እስከ አስራ-ሶስት ሚሊዮን የሚሆኑ ኢትዮጵያዊያን በለጋስ ሃብታም አገሮች የሚመገቡባት አገር መሆኗ ነው። ዋናው ወደ ውጭ የምልከው የሰለጠነ፤ የተማረ፤ በአብዛኛው ወጣት የሰው ጉልበትና እውቀት ኃይል ነው። ከላይ ያስቀመጥኩት የመጀመሪያ የአመራር መለኪያ ጥቅስ፤ ብሄራዊና የሁሉን ጥቅም የሚያስተጋቡ መሪዎችን ገላጭ ነው። ይህን መለኪያ የሚያሟላ የአገር መሪ፤ በጠባብ ጎሰኛነት አያምንም። በሕዝብ እልቂት አያምንም። ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች የመማር፤ ራስን የማሻሻል፤ ከድህነትና ከጭቆና አገዛዝ ነጻ መውጣት ቀን ከሌሊት ይሰራል። በኢትዮጵያ ተከታታይ ታሪክ፤ ዓለምና አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያደነቃቸው መሪዎች አሉ። መለያውን በመጠቀም ምሳሌች እንሰጣለን። አጼ ቴዎድሮስ፤ የኢትዮጵያን አንድነት መሰረት ለመጣል፤ ታሪክ የመዘገበው አስተዋጽኦ አድርገዋል። እውቅናቸው ጎንደሬ በመሆናቸው አይደለም። አገር ወዳድ፤ ደፋርና ጀግና ኢትዮጵያዊ በመሆናቸው ነው። ለጠላት አልተንበረከኩም።

ታላቁ መሪ፤ አጼ ዮሓንስ፤ የማህዲስቶችን፤ የግብጾችንና የሌሎችን አድማና ሴራ ተዋግተዋል:: የሚታወቁት ትግሬ በመሆናቸው ሳይሆን እውነተኛ፤ ቆራጥ ኢትዮጵያዊ፤ ክርስቲያን መሪ በመሆናቸው ነው። አጼ ምኒልክ፤ በአገር ላይ ያንዣበበውን የጣሊያን ቅኝ ገዥዎች ወረራ ለመቋቋም ብልሃት ባለው አመራር አማራ፤ ጉራጌ፤ ትግሬ፤ ሃረሬ፤ አፋር፤ ሶማሌ፤ ኦሮሞ፤ ክርስቲያን፤ እስላም ወዘተ ሳይሉ ዓለምን ባስደነቀ ሁኔታ፤ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለመላው ጥቁር ሕዝብ የሚያኮራ ድል ተጎናጽፈዋል። ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ የተለየ እውቅና አበርክተው አልፈዋል። ዘመናዊ መገናኛና ትምህርት መስርተዋል። አጼ ኃይለ ሥላሴ፤ የጣሊያንን ወረራ ለመቋቋም፤ በአገር ቤትና በስደት፤ በድልና አዲሲቱን ኢትዮጵያ በመገንባት ታሪክ የማይረሳው አስተዋጾ አድርገዋል። ከሁሉም በላይ፤ የእኔ ትውልድ ሊረሳው የማይችለው፤ በጎሳ ሳይለዩ፤ የዘመናዊ ትምህርት መሰረተ የጣሉት እሳቸው ናቸው። መለስ ዜናዊና ሌሎቻችን እየተከፈለን የተማርነው፤ ከጎጆ የወጣነው እኚህ መሪ ኢትዮጵያ የተማረ ሰው ያስፈልጋታል የሚለውን መርህ ስራ ላይ ስላዋሉት ነው። ስብሃት ነጋም ሆነ እኔ፤ ይህ እድል ባይደርሰን ድህነት እጣችን ይሆን ነበር። የሻቢያና የህወሓት አለቆች ሊረሱት የማይገባቸው፤ ከጎንደሬው ወይንም ከመንዜው አማራ የበለጠ የትምሕርት እድል የተከፈተለት የኤርትራ ወጣት ነበር። በዊንጌትና በመነን ትምሕርት ቤቶች በስኮላርሽፕ ይማሩ የነበሩ ሁሉ ታዛቢዎች ናቸው። እነዚህና ሌሎች የተለያዩ የአገር መሪዎች ተመሳሳይ የሚያደርጋቸው ዋና መለኪያ ኢትዮጵያዊነታቸው፤ ከሃይማኖትና ከጎሳ በላይ፤ በተቻላቸው አቅም፤ በነበረው የዓለም ሁኔታ፤ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን እድል መክፈታቸው ነው።

አገር ወዳድ የሆነ መሪ፤ ለስልጣን ሽሚያ ብሎ የባህር በር አይዘጋም፤ ሰብአዊ መብቶችን አይገፍም፤ በእድገት ስም፤ አገርን መዝበሮ ለዘረፋ አይዳርግም። የአጼ ምኒልክን ታሪክ በራዥ የሆኑ፤ የህወሓት ጎሰኞች ዛሬ የሚያካሂዱት መርዝ የለበሰ ጥላቻ፤ ዓለም ከሚያውቀው የተለየ ነው። ጠባብ ጎሰኛ ከመሆኑ በላይ፤ የአማራንና የኦሮሞን ሕዝብ እርስ በእርሱ ለማጋጨት የሚሰራ ሴረኛ ነው፤ አደጋው ማንንም አይምርም። የጎሰኛ ፖለቲካ አመራር ቀርጾ፤ ህብረተሰቡን

የሚያባላው፤ አጼ ምኒልክ ያነጹት ስርአት አይደለም። በአኟክ፤ በአሞ ሸለቆ፤ በኦሮሞ፤ በአማራ ህብረተሰብ ላይ ታይቶ የማይታወቅ እልቂት የሚያካሂደው የህወሓት/ኢህአዴግ አመራር ነው። የዛሬውን የኢትዮጵያን የፖለቲካ አመራር ስናይ፤ በልማት ስም፤ ለም መሬቷና ወንዞቿ በሳንቲም የሚሸጡባት፤ እስከ ዘጠና-ዘጠኝ አመታት ለውጭ መንግስታት፤ ለግል ሃብታሞች፤ ለተወሰኑ ታማኝ ለሆኑ የትግራይ ተወላጆች የሚቸረቸርባት አገር መሆኗ እውቅና ሰጥቷታል። ጋርዲያን የተባለው የእንግሊዝ ጋዜጣ፤ የመሬት ነጠቃንና ቅርሚትን፤ “የሃያ አንደኛው መቶ የዘረፋ ድርድር” ያለው የአመራሩን ጠባብነትና ጉድለት ያሳያል። ህወሓትና ደጋፊዎቹ ይህን የአመራር ጉድለት ይክዳሉ። የሚሉት፤ የገጠር ኢኮኖሚው፤ በታሪክ ያልታየ፤ አስደናቂ መዋቅራዊ ለውጥ አሳይቷል። የገጠር ሚሊኒየሮች ተፈጥረዋል ነው። እምርታዊ የሆነ ለውጥ ቢካሄድ፤ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ይኮራበታል፤ ሁሉም በልቶ ያድራል። እኔ ይህን መጽሃፍ ለመጻፍ አልገደድም ነበር። ሁኔታው ከዚህ በጣም የተለየ ነው። ለምሳሌ፤ በ2012 የአፍሪካ ኢንቴሊጀንስ፤ ቁጥር 1343 የሚከተለውን ዘገባ አቅርቧል። “የመለስ ዜናዊ ፓርቲ የሚመራው ኢኮኖሚ፤ ወደ ቁልቁለት እያመራ ነው። እንደዚህ ያለ፤ ያልታሰበ ሁኔታ ባለፉት ጥቂት አመታት አልታየም። ኢትዮጵያን ይለውጣል የተባለው፤ የአባይ ተሃድሶ ግድብ፤ (Renaissance Dam) የአገሪቱን የውጭ ምንዛሬ አሟጦታል። (The Ethiopian economic situation is in the worst state it has been for many years...The Great Renaissance Dam has drained liquidity... Meles Zenawi's economic legacy (the area where he is considered a hero) could turnout to be less than his partisians are claiming).”

አባባሉ፤ የእድገቱን ጠባብነት ያሳያል። “አባይን ያላየ ምንጭ አይቶ ይደነቃል” ያሉት ለዚህ ትንታኔ ተገቢ ነው፤ ብልጭልጭ ህንጻዎች ወዘተ ስለተሰሩ አስደናቂና ህይወት ለዋጭ እድገት ተካሂዷል ተብሎ ይነገራል። ተሳትፎ የሌለበት እድገት እያደረ ይደክማል። ይህ ሊካድ አይችልም። ባለስልጣናትና ደጋፊዎቻቸው በሚሉትና በአብዛኛው ሕዝብ መካከል ያለው አመለካከት ሊገናኝ አልቻለም። ህወሓት በበላይነት የሚመራው የኢህአዴግ መንግሥት  ባለስልጣናት፤ “በሬ ወለደ ብለው” አብዛኛውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን፤ ዓለምን ለማሳመን ይሞክራሉ። ለውጭ ታዛቢዎች አስደናቂ የሆነው፤ የገዢው ፓርቲ ሊታመኑ ወይንም በሰው ህይወት ለውጥ ማስረጃ ሊደገፉ የማይችሉ ማስረጃዎች እንደ እውነት ማቅረባቸውና አማኞች ለመግዛት መቻላቸው ነው። ባለስልጣናትና ደጋፊዎቻቸው እድገቱ ፍትሃዊ ነው፤ ዲሞክራሲዊ አለ፤ ረሃብ የለም ይላሉ። ደሃው ሕዝብ የሚያየውን ሌሎች ለማየት አልቻሉም። አዲሱ ገዢዎች ደሃነት እየጠፋ ነው ብለዋል። የአዲስ አበባን ብልጭልጭ ህንጻዎች፤ ምግብ ቤቶችና ሆቴሎች ስላዩ ነው። እርግጥ የደላው በቪላ ይኖራል፤ ሸራቶን አገሪቱ የማታመርተውን የውጭ መጠጥ ይጠጣል፤ ዱባይ ይሄዳል። አሳዛኙ በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጋዎች በጠለላ እንደሚኖሩ፤ በተመሳሳይ ቁጥር ምግብ ከቆሻሻ መጣያ እየለቀሙ እንደሚመገቡ አልተረዱትም። መለስ “የዋጋ ግሽበት፤ የብር ዋጋ መቀነስ” የእድገት መለኪያ ነው ብሎ ተከራክሯል። እድገት ካለ አቅርቦትም ማደግ እንዳለበት የተከራከረው የለም። እነዚህን፤ ለእድገቱ አድናቆትና እውቅናን የሚሰጡ ግለሰቦች፤ አንድ ጥያቄ ራሳቸውን ቢጠይቁ ያስመሰግን ነበር። ድህነት ከጠፋ ለምን እንሰደዳደለን፤ ወጣቱ በጅምላ ለምን ከአገር ይወጣል። ይህን ስንል፤ ያለፉት መንግሥታት አላጠፉም የሚል አስተያየት የለንም።ጥፋት ባያደርጉ ኖሮ እልቂትና ለውጥ ባላስፈለገም ነበር። ሆኖም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የተመኘው አንዱን ጨቋኝ በሌላ መተካት አልነበረም። የዜጎች ስብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ ነበር።

ኢትዮጵያ፤ ከምርጫ ዘጠና ሰባት በኋላ፤ በተከታታይ፤ በአመት አስራ አንድ በመቶ አድጋለች ተብሏል። እድገት እንዳለ አልከራከርም። አብዛኛው የመዋቅር ግንባታ እድገት የተካሄደው ከምርጫ ዘጠና ሰባት በኋላ ነው። ምርጫ ጥቅም አለው ማለት ነው። የምከራከረው፤ ይህ እድገት የአብዛኛውን ሕዝብ ኑሮ እንዴት አልለወጠውም ብለው የሚከራከሩ ኢትዮጵያውያን መኖራቸውን ገዢው ፓርቲ ይክዳል። ገዢው ፓርቲና ደጋፊወቹ በጭፍን ህይወት ለዋጭ እድገት አለ ይላሉ። ሌሎቻችንም  ይህ እውነት እንደሆነ፤ የብልጭልጭ እድገቱ “አባይን ያላየ” የሚባለው፤ (ቪላ፣ ህንጻ፤ መንገድ፤ ሆቴል፤ የምግብ ቤት፤ የዘፈን ቤት፤ ሸራቶን፤ ወዘተ መሰራታቸውን) እንደ ፍትሃዊ ልማት ማየታችን ቀጥሏል። አይቮሪ ኮስት፤ በአፍሪካ ተወዳዳሪ የሌለው የብልጭልጭ እድገት አሳይታ ነበር። ዓለም ባንክና ሌሎች እድገቱን በአፍሪካ ታይቶ የማይታወቅ ይሉት ነበር። የእድገቱ ተጠቃሚዎች ፈረንሳዮችና ጥቂት የፕሬዘደንት ሁፉት ቧኘ ቤተሰቦችና ወዳጆች ነበሩ። የእርስ በእርስ ጦርነት ሲመጣ፤ ብልጭልጩ የአይቮሪ ኮስት እድገት ጨለማን ወልዷል። ዛሬ፤ በኢትዮጵያ ውሸቱንና እውነቱን ለመለየት አይቻልም። አስደናቂ እድገት ካለ፤ ማንን ጠቀመ፤ ማንን ጎዳ፤ ማን ተሰደደ፤ ማን ታሰረ?

ኢትዮጵያዊያን አገራዊ መሪዎቻቸውን በአገር ደረጃ እንዳያከብሩ ተከልክለዋል

ህወሓት በበላይነት የሚመራው መንግስት ያለፈ ታሪክ፤ የእድገት ውጤት አይቀበልም። የኢኮኖሚ ቀውስ የሚያስከትለውን ችግር አያየውም። ሰላምንና እርቅን አይፈልግም። የመረጠው አለመረጋጋትን (Permanent Suspense) ነው። ለምን ብለን  መጠየቅ ተገቢ ነው። የኢኮኖሚ የበላይነት ጥቅም ስላለው። እንዴ አማራውን፤ ሌላ

ጊዜ ኦሮሞውን፤ ሌላ ጊዜ ሶማሌውን ወዘተ፤ ማነህ ባለ ሳምንት በሚል መልክ ያሳድዳል። ያለፉ መሪዎችን ታሪክ ያንቋሽሻል። የራሱን ጠባብ ታሪክ ከፍ ያደርጋል። ለማጠናከር የሚፈልገው የጠባብ ቡድኑን የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት ነው። በአንጻሩ፤ ጋናውያን ታድለዋል። በውጭ ያለው ስደተኛ ከጎሳ በላይ ያስባል። ከእርስ በእርስ ጥላቻ ነጻ ሆኗል። የጎሰኛነትን ጉዳት በሌሎች አገሮች አይቶታል። የጋና ስደተኛ፤ ለዲሞክራሳዊ ለውጥ ታሪክ የመዘገበው ተገቢ አስተዋጽኦ አድርጓል። ጋና፤ የተማረ የሰው ሃይሏን ለአገራዊ እድገት እየተጠቀመችበት ነው። ኮፊ አናን ተሰሚነት አለው። እኛ ያደረግነውን ጥፋት ተከታታይ ትውልድ ማወቅ አለበት። እንደ ኮፊ አናን ያሉ መሪዎቻችንን አጥፍተናል። ደርግ የማይተኩ መሪዎችን በአንድ ሌሊት ገደለ። ህወሓት፤ የተረፉትን ሽባና ዱዳ አድርጓቸዋል። ከጥቂቶች በስተቀር፤ ስማቸውን፤ ድምጻቸውን አንሰማም። አሉን ብለን አንከባከባቸውም። የእንጀራ ልምድ በዓለም ቢስፋፋም፤ በሃገሩ ራሱን ያላከበረ ህብረተሰብ ሌላው አያከብረውም። የሚያኮሩ ኢትዮጵያውያን ከዚህ ዓለም ሲያልፉ እናለቀሳለን። በህይወታቸው እያሉ ምክራቸውን አንጠቀምም። በዚህም፤ ጋናዊያን ይበልጡናል። ኮፊ አናን ተደማጭነት አለው። ይህ፤ የተባበሩት መንግስታት ዋና ጸሃፊ ሆኖ ያገለገለ ጋናዊ፤ ስለ ለም መሬት አጠቃቀምና ስለ መንግስት መሪዎች ሃላፊነት ምክር ሰጥቶ ነበር። "የአፍሪካ መንግስታት መሪዎች፤ ሁለተኛ የቅኝ አገዛዝ፤ የአፍሪካን የተፈጥሮ ሃብት ተጠቅሞ፤ አፍሪካውያንን ገባር እንዳያደርጋቸው መጠንቀቅ ያስፈልጋል። የአፍሪካ መንግስታት መሪዎች የመጀመሪያ ሃላፊነታቸው፤ ያላቸውን የእርሻ መሬት ተጠቅመው፤ ለሕዝባቸው የምግብ ዋስትና ማስገኘት ነው"። የኢትዮጵያ ገዢ ፓርቲ ይህንን መርህ ለማሟላት አልቻለም። እድገቱ ማንን እንደጠቀመ፤ ማንን እንዳለፈ ማየት ተገቢ ነው። ሃብታም መሆን የምትችል ኢትዮጵያ አሁንም ደሃና ጥገኛ የሆነችው ስርዓት ወለድ ችግር ስላለ ነው። ይኼ ችግር ገለሰቦችን በማሰረና በማሳደድ አይፈታም።

የእድገቱ ውጤት ለማን ጠቃሚ፤ ለማን ጎጅ መሆኑን ለማገናዘብ የተራውን ህዝብ ኑሮ ማየቱ ብቻ ይበቃል። ለሕዝብ ታዛዥና አገልጋይ በሆኑ አገሮች ተራው ዜጋ ሰርቶ፤ በልቶ ያለፍርሃት ያድራል። በኢትዮጵያ፤ የዋጋ ግሽበት ጥሩ ኑሮ ይኖሩ የነበሩትን ወደ ድህነት እያመራ ነው። የዛሬይቱ ኢትዮጵያ መገለጫ፤ፍትህ፤ ነጻነት፤ የህግ የበላይነት፤ የሕዝብ ድምጽና ተሳትፎ የሌለባት ነው። ሃቁ፤ በአንድ ጠባብና ትምክህተኛ የንኡስ ብሄርተኛ የበላይነት የሚመራ ፓርቲ የሚገዛት፤ ለሃያ አንድ አመታት ጠቅላይ ሚኒስቴሯ መለስ ዜናዊ የተባለ አምባ ገነን እንደ መንደሩ ያዘዘባት አገር መሆኗ ነው። ተተኪዎቹ የመለስን ፈለግ ተከትለው፤ ከእርሱ የባሱ ሆነዋል። የችግሩ እምብርት የአገዛዝ በደል ነው። መለስ፤ ይሄም እንደሌለ ተናግሮ አልፏል። ባለስልጣናት የማይቀበሉት፤ የኢትዮጵያ እድገት ለጥቂቶች እየታየ ድህነት የሚሰፋባት፤ የእርሻ እድገት አለ እየተባለ፤ ረሃብ በጥልቀት የሚታይባት አገር መሆኗን ነው። ሌላም የማይቀበሉት አበይት ጉዳይ አለ። ህወሓት በበላይነት የሚያዘው መንግስት፤ በተከታታይ ምርጫን በግድም ሆነ በውድ አሸንፋለሁ ብሎ ሲነሳ፤ በኢኮኖሚው በኩል ውጤት ማሳየት እንዳለበት የተገነዘበው ከምርጫ ዘጠና ሰባት በኋላ መሆኑ አይካድም። ከምርጫ ዘጠና ሰባት በፊት፤ በመዋእለ ንዋይ መልክ በብዙ ቢሊየን ብር የፈሰሰው ክልል አንድ፤ ትግራይ ነበር። ክልሉ በጦርነት ተጎድቷል የሚል ተቀዳሚነት ነበረው። ሃቁ የተለየ ነው። በጦርነት ያልተጎዳ ክልል የለም። የአማራው ክልል፤ በተለይ የጦር አውድማ የነበረው ጎንደር። ገዢው ፓርቲ ከክልል አንድ ውጭ መሰረተ ልማት ያሰፋፋው ከምርጫ ዘጠና ሰባት በኋላ ነው። ይህም የሆነው በለጋሶች ግፊት ነው። ዓለም ባንክ ቦርድ ወስጥ፤ ድህንነትና ረሃብን ለመቀነስ ልማት ሁሉን አሳታፊ መሆን አለበት የሚል ግፊት ነው።

የዚህን አዲስ አቅጣጫ ጥቅም፤ ቢያንስ ከሁለት አንጻር እንየው። አንዱ፤ ስልጣንን ለማቆየት ነው። ሌላው፤ ሃብትን አገር አቀፍ በሆነ መንገድ ለገዢው ፓርቲና ለደጋፊዎች ለማስፋፋት ነው። መሪዎቹና ደጋፊዎቻቸው ያካበቱት ሃብት ከትግራይ ብቻ ሊገኝ እንደማይችል አውቀውታል። የመሰረተ ልማት መስፋፋት ለይስሙላም ቢሆን፤ ሌሎችን ማቀፍ ነበረበት። ከታቀፉት መካከል በግልጽ የሚታየው የውጭ ባለ ሃብቶችና ምርጥ፤ ታማኝ፤ የትግራይ አዲስ ሃብታሞች አገር አቀፍ ሚና ማግኘታቸው ነው። (National capitalist class) በመንግሥት አድልዎ በኮንትራት ያልደከሙበትና የማይገባችው ሃብት መጎናጸፋቸው ነው። የጥቅም ሰንሰለት እየጠነከረ የሄደው በዚህ ነው። ይህ ሰንሰለት፤ ህወሓት በሚፈልገው ደርጃ የሚያስተጋቡ ተጠቃሚዎችን አስፍፍቷል። ይህ የመሰረተ ልማት መስፋፋት ግን መዋቅራዊ ለውጥ አላመጣም። ግብርናን እንይ።

የቁጥጥር ፖለቲካ የቁጥጥር ኢኮኖሚ ወልዷል

የቁጥጥር ፖለቲካ፤ ገቢ፤ ሃብት፤ የተፈጥሮ ጥሪትና የኑሮ መሻሻል ለማን እንደሚረዳ ይወስናል። ጎሳ ተኮር ፌደራሊዝም አድሎውን ያባብሰዋል። ይህ መጽሃፍ የሚያሳየው እድገት አለመኖሩን አይደለም። እድገቱ ለጥቂት ቤተሰቦች ገቢና በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ የሃብት ክምችት (Concentration of unprecedented wealth for a few) መፍጠሩን ነው። እድገቱን የመዘነው የአብዛኛው ድሃ ሕዝብ ገቢ እያደገና ኑሮው እየተሻሻለ (Human Development)

ከመሄዱ ወይንም ካለመካሄዱ አንጻር ነው። አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ በእርሻ ይመካል። ሁሉም ምግብ መብላት አለበት። የእድገቱን ደረጃና በተፈጥሮ ሃብት ማን ተጠቃሚ እንደሆነ ለማየት የገጠሩን እድገት መመርመር አስፈላጊ ነው። የእርሻ እድገት አስደናቂ ነው በሚባልባት ኢትዮጵያ፤ 2011-12 ህወሓት፤ ስምንት ሚሊዮን ቶን እህል ሸምቷል። ህወሓትና ደጋፊዎቹ ይህን የሸመታ ጥገኝነት ይክዳሉ። የሚሉት፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ጨምሯል። ቢሆንም የሚራብ ኢትዮጵያዊ የለም ነው። ነገሩን ያባባሰው እድገትንና ዲሞክራሲን ከተጎናጸፈ ቆይቷል ማለታቸው ነው። ዲሞክራሳዊ ስርአት ቢኖር የተራብ ከመንግሥት ሃላፊነት ሊጠይቅ በቻለ ነበር። የታወቀው የህንድ ሎሬት አማሪትያ ሴን፤ "ዲሞክራሳዊ በሆኑ አገሮች ከድርቅ የመጣ ረሃብ (Famine) የለም" ያለውን እናስታውሳለን። መንግሥት ሊከደው የማይችለው የምግብ <u>አቅርቦት ከፍላጎት (supply and demand)</u> ጋር ሳይስማሙ መሄዳቸውን ነው። ባለስልጣናት ለዚህ ምክንያት ሲሰጡ ሕዝብ እየጨመረ፤ፍሎጎት እያደገ ሄዷል ነው። በዚህ አይነት አመለካከት፤ ኢትዮጵያ ረሃብተኛ ሆና ትቆያለች ማለት ነው። ወይንም ሕዝቡ እንዳይጨምር ዘዴ መፈለግ ማለት ነው። መለስ ክፍተቱንና የዋጋ ግሽበቱን የእድገት ምልክት ነው ብሏል። በእድግትና በውጭ እርዳታ ግንኙነት ሲታይ፤ ኢትዮጵያ በአመት አራት ቢሊየን ዶላር ታገኛለች። ስለሆነም፤ በመሰረተ ልማትና በፍጆት ላይ የፈሰሰው መዋእለንዋይ ውጤት ሲታይ ለጥቂቶች ገነት የፈጠረ እድገት መኖሩ አያስደንቅም። ባይኖር ያስደንቅ ነበር። ቁም ነገሩ፤ የእድገቱ ውጤት የሚያሳየው ፍትሃዊ አለምሆኑን ነው። ይሕብረተሰቡን ፍላጎር ለማሟላት አልቻለም። ሃቁ፤ የቁጥጥር ፖለቲካው፤ የቁጥጥር ኢኮኖሚን ወልዷል። የተወለደው የምጣኔ ሃብት የሚያደላው ለፈጠረው ለህወሓትና ለደጋፊዎቹ ነው። ፍትሃዊ ለመሆን አይችልም። አብዛኛው የእርዳታ ገንዘብ በልዩ ልዩ ዘዴ ይሰረቃል። ከአገር ህገወጥ በሆነ መንገድ ይወጣል። Global Financial Integrity እንዳሳየው፤ በ2000-2008 ብቻ 12 ቢሊዮን ዶላር ተሰርቋል። ቢያንስ፤ በአመት ሶስት ቢሊየን ዶላር ከአገር ይውጣል። በንጥር (Net inflow) ሲታይ፤ ከእርዳታው የሚገኘውና ወደ ውጭ ከሚላከው የእቃ ገቢ ከሚገኘው አብዛኛው ይሰረቃል ወይንም ከሕግ ውጭ በተለያየ መንገድ ይወጣል።

*መዋቅራዊ ለውጥ የእድገት መለኪያ ነው*

ስርቆቱና ሙስናው ቢኖር ባይኖር፤ የምርት ሃይሎችን በማጎልመስ መለኪያ ሲታይ፤ እርዳታ ያለ ሕዝብ ተሳትፎ፤ ያለ ነጻ ተቋማዊ ቁጥጥር (Independent Oversight) ያለ የህግ የበላይነት፤ ያለ ምርት እድገት፤ ለአገርና ለህብረተሰብ አገልግሎት ሊውል አይችልም። እነደ ኢትዮጵያ መዋቅራዊ ችግር ባለበት አገር--እርሻ ዘመናዊ አለመሆኑ፤ ኢንዱስትሪ በስፋት አለመቋቋሙ፤ የገጠሩና የከቴሜው ኢኮኖሚ በእቅድ አለመቆራኘታቸው፤ የግል ክፍሉ ግልጽና ተወዳዳሪነትን በሚያጠናክር ሁኔታ አለመተዳደሩ፤ የገበያ አመራር ለጥቂት የበላዮች አገልጋይ መሆኑ ወዘተ--የአገሪቱን የማምረት አቅም ጎድቶታል። ነጻ ሜዲያና ህያው የሆነ የማህበረሰብ ድርጅት ጠበቃ የለም። ክፍተቱ ለሙስና አመች ሆኗል። በእርዳታ የሚገኘው ሁሉ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣትና የህብረተሰቡን የማምረት አቅም ለማጠናከር አልዋለም። የዓለም ለጋሽ አገሮች የእድገት መለማመጃ የሆነችው ኢትዮጵያ፤ አሁን እንደ ቦትስዋና፤ ሞሪሺየስና እንደ ምስራቅ ኤዥያ አስደናቂ እድገት ያሳዩ አገሮች ለመሆን ብዙ ጊዜ ባልወሰደባትም ነበር። ቢያንስ ሕዝቧ የምግብ ዋስትና ይኖረው ነበር። የሚታየው ሃቅ ግን የውጭ እርዳታ ሙስናን፤ ስርቆትን፤ የሃብት ሽሽትን፤ ኪራይ ሰብሳቢነትን፤ የሃብት ክምችን (concentration of incomes and assets) ጥገኛነትን አጠንክሯል። ይህን ስል፤ በጎ አድራጊዎች የሰው ህይወት አላዳኑም ማለቴ አይደለም። አድነዋል። ዜጎችን ከረሃብ፤ ከበሽታና ከሌሎች ችግሮች ማዳንና ዘላቂነት ያለው አምራችነት ያለው እድገት መሰረት እንዲይዝ ማድረግ የተለያዩ ናቸው። በኢትዮጵያ የሚታየው የእርዳታ አቅርቦት ጥገናዊና ጥገኛነት ወላጂ እየሆነ ሄዷል። ለዚህ ማስረጃው ድህነት ጥልቀትና ስፋት እየያዘ መሄዱ ነው። ተከታታይ ሙስና፤ ስርቆት፤ አድልዎ፤ የአስተዳደር ብልሽት፤ ጥገኛነት የእርዳታን ገንቢነት አያሳዩም። አንዳንድ ግለሰቦች መጥፎ አገዛዝ ህወሓትን አይገልጸውም ይላሉ። እኛ ደግሞ መጥፎና አፋኝ አገዛዝ ህወሓትን በበለጠ ይገልጸዋል እንላለን። መጥፎ አገዛዝ ለሰብአዊ እድገት ማነቆ ሆኗል እንላለን። ሰብ አዊ ሙብቶችን ማፈን የመጥፎ አገዛዝ ዋና መለኪያ ነው።

*ህወሓት የጎዳው በራስ መተማመንን ነው*

በቅኝ አገዛዝ ዘመን እንደታየው ተከታታይ ጥገኛነት ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል፡፡ ከሁሉም በላይ፤ ህብረተሰቡ በራሱ አይተማመንም። አገር ወለድ የሆነ ኢኮኖሚ ለመፍጠር ይቸግረዋል። ቬስታልና ሌሎች ታዛቢዎች እንዳሉት፤ መለስ የመራው መንግሥት የታወቀው በፍትህ፤ በአገር ወለድ እድገትና በሌሎች የነጻነት መለኪያዎች አይደለም። በጠባብ ጎሰኛነት፤ በተበቃይነት፤ በስግብግብነት፤ በሙስና ወዘተ ነው። "የመለስ አምልኮ" አማኞች የሚሉት መለስ የመራው ህወሓት አስደናቂ እድገት አካሂዷል ነው። እድገት እንዳለ ባይካድም፤ በአብዛኛው ሲታይ፤ የመለስ መንግሥት ፖሊሲና አመራር የፈጠረውና ያስተላለፈው የአገዛዝ ባህል የሚከተለው ነው። አፈና፤ ፍርሃት፤ <u>አድልዎ፤ ሙስና፤ ኪራይ ሰብሳቢነት፤ ስርቆት፤ ግጭት፤ የተዛባ እድገት፤ ጥገኛነት፤ የህብረተሰቡን ሃብት በፖለቲካ ውሳኔ ወደ ፓርቲው</u>

ባለስልጣናት፤ ምርጥ ግለሰቦችና ቤተሰቦች ማዘዋወር። (Unprecedented, politically-driven suffocation of dissent and massive transfer of incomes and assets from the public to private entities). ይህን ከፖለቲካ ስልጣን ብልግና የመጣ የአገዛዝ በደል አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያውቀዋል። ግራ የተጋባው ስደተኛው ነው። ሕዝቡ "እድገት አለ ብለው የሚያመሰግኑት ተጠቃሚዎች ናቸው" ይላል ። ለጋስ የሆኑ የውጭ መንግስታትና አበዳሪ ድርጅቶችም እድገት አለ ብለው ሲናገሩ ማስረጃውን የሚያገኙት ማስረጃን ከሚፈጥረው ከህወሓት ነው። ለጋሶችና አበዳሪዎች ተጠቃሚወች በመሆናቸው ለጠፋው ገንዘብ ተጠያቂ እንዳይሆኑ፤ ታክስ የሚከፍለው ሕዝባቸው እርዳታ ጥቅም አለው ብሎ ማሰቡን እንዲቀበል፤ እርዳታ ድህነትን እየቀነሰ ነው ማለታቸውን ቀጥለዋል። እድገት ከአብዛኛው ሕዝብ አስቃቂ ኑሮ ተለይቶ ቀርቧል። አስከፊው ኑሮ ተደብቋል። በአብዛኛው፤ አበዳሪ ድርጅቶች ፖለቲካ ነክ የሆኑ ችግሮችን ደፍረው አይናገሩም። በዓለም ባንክ የአድልዎና ሙስና ችግር ጀምስ ወልፎንሶህን ፕሬዘደንት ከመሆኑ በፊት ቀጥተኛ የሆነ ውይይት ተደርጎበት አያውቅም። ዛሬ ከአገዛዝ አርእስቶች ተቀዳሚ ሆኖ ወደ አመራር ተለውጧል። ወደ ኢትዮጵያ ገና አልገባም። በእድገት ላይ የሚነገረውም ከደሃው ኑሮ መሻሻል አንጻር አይደለም። ዓለም ባንክ ባለፉት ሁለት ዓመታት ብቻ ስለ ሙስና ባስደረገው ጥናት ኢትዮጵያ በማንኛውም የኢኮኖሚና የማህብራዊ አገልግሎት ዘርፎች በሙስና እንደ ተበከለች ነው።

ፍትሃዊ እድገት ካለ ሰሜን አፍሪካ አይለወጥም ነበር

የቱኒሲያና የግብጽ አመጽ በተካሄደበት ወቅት ዓለም ባንክና አይኤምኤፍ፤ በእነዚህ አገሮች እድገት አለ ይሉ ነበር። እያወቁ፤ ሙስና ህብረተሰቡን እንደጎዳው አይከራከሩም ነበር። ይህ "እያወቁ ድንቁርና" ክብራቸውን ቀንሶታል። ፍትሃዊ እድገት ቢኖር ኖሮ፤ የብዙ ሰላማዊ ሰዎች ህይወት የተሰዋበት ለውጥ ባላስፈለገ ነበር። ዛሬ በአበዳሪ/ለጋስ አገሮች/ድርጅቶችና በኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል ያለው የአመለካከት ልዩነት ሰማይና ምድር ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ አበዳሪዎችን የሚያያቸው ልክ ገዢውን ፓርቲ እንደሚያየው ነው። "ምግብ የታል፤ ስራ የታል" ወዘተ። በሁለቱም ላይ እምነት የለውም። Human Rights Watch ያወጣውን ዘገባ ማየት ይበቃል። የኢትዮጵያ መንግሥት፤ እርዳታን ለፖለቲካ የበላይነት ተጠቅሞበታል። የእርዳታ ዋና ሚና አቅምን መገንባት ነው። ሰብአዊ መብቶችንና ክብርን ማጠናከር ነው። በፖለቲካ የተበከለ እርዳታ ችግር ፈጣሪ ነው። ለአፈና ስለሚውል። በኢትዮጵያ አገራዊ እድገትን ሊያጠነክር አልቻለም። ስለዚህ ነው ህብረተሰቡ እርዳታ ጥቅሙ የትላይ ነው? የሚለው። 35/

ጎጂ የሆነው የአበዳሪዎችና የውጭ እርዳታ ሚና

ከብሄራዊ አቅም ግንባታ ላይ ያተኮረ እርዳታ ድህነትን ለመቀነስ ሚና እንዳለው አምናለሁ። በሌሎች አገሮች አይቸዋለሁ። ኢትዮጵያዊያን በደንብ መገንዘብ ያለባቸው መሰረታዊ ሃሳብ አንድ ነው፤ ድጋፉ የሚሰጠው የራሳቸውን (የለጋሶችን) ጥቅም ለማጠናከር እየሆነ መሄዱን ነው። አሜሪካ ታላቅ እየሆነ በሄደበት ዘመን--ማለትም፤ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ-- አሜሪካኖች አስበውበት የሚከተሉቱ የውጭ አመራር ወይንም ፖሊሲ፤ እርዳታን፤ የትምሕርት ቤት ተቋሞችን፤ የሰላም ልኡካንን፤ ተቃዋሚ መንግስታትን ገልብጦ፤ ለነሱ ጥቅም የሚያገለግሉ መሪዎችንና መንግስታትን አቋቁሞ ጥቅማቸውን ማስከበር የሚል ነው። አብዛኛዎቻችን የምናስበው፤ የአሜሪካ ፕሬዚደንት፤ የውጭ ጉዳይ ሚንስቴር የአመራር ውሳኔ ያደርጋሉ የሚል ተራ አስተሳሰብ ነው። ውሳኔው ከየትና እንዴት እነደሚደረግ አናውቅም። በ2012 ስለ ሱዛን ራይስ ሲደረግ የነበርውን ትንተና ስናይ የውሳኔ ማእከሉ የት ነው የሚለውን ጥያቄ በመጠየቅ እንጀምር። "የአሜሪካ የብሄራዊ ደህነነት አማካሪና የሚመራው ወይንም የምትመራው፤ ብሄራዊ የደህንነት ካውንስል፤ ዋናው የመመሪያ ጸናሽና ለፕሬዘደንቱ ውሳኔ አቅራቢ ነው።" ይህ ምስጢረኛ የሆነ፤ ለአገሪቱ ሕዝብ ያልታወቀ የውስጥ ክበብ፤ ዓለምን ያካሂዳል። በኢትዮጵያ ላይ የሚደረገው የአሜሪካ ውሳኔ፤ እነ ኪሲንጀር፤ እነ ኮንዶሊዛ ራይስ፤ እነ ብሬዚንስኪ ወዘተ የመሩት ተቋም ነው። "The National Security Advisor has now achieved cabinet-level status..." The National Security Counci (NSC) that the Advisor leads is "in charge of running the world...it is a world unto itself." 36/

ህወሓት ሆን ብሎ ህብረተሰቡን ከኢትዮጵያዊነት መለያው ወደ ብሄር/ብሄረሰብ መለያ በመደገፍ በውሸት ፕሮፓጋንዳ የለወጠው ጎሳዊ በሆነ የከፋፍለህ ግዛው አስተዳደር ቅርጽ የውጭ ተባባሪ መንግስታትም--በተለይ እንግሊዞችና አሜሪካኖች-- ስላመኑበት ነው። አገሪቱን የጎዳት አመራሩ የሰጠው የአገዛዝና የባህል ዘይቤ ብቻ አይደለም። ጠባብ ጎሰኛነት ቀስ በቀስ መላውን የተማረና ተቃዋሚ ነኝ ባይ፤ ብዙ የውጭ ታዛቢዎችን በክሏል። በተለይ የተቃዋሚና የማህረሰብ ክፍሎች ከውጭ የመጣውን አደጋ ፈጽሞ የተረዱት አይመስሉም። የህወሓት አመራር ከምእራብ አገሮች እርዳታ ሌላ ስልጣን በያዘበት ማግስት የአረብ አገሮችን፤ በተለይ፤ የሳውዲ አረቢያን መንግስትና ኢንቬስተሮች፤ በእድገት ስም፤ "ኑ፤ ግቡ፤ ኢትዮጵያ ለእናንተ ክፍት ናት" ብሎ ጋበዛቸው። ባለፉት ሃያ ሶስት አመታት ሳውዲ አረቢያ

በኢትዮጵያ፣ የኢኮኖሚ የበላይነት ይዛለች። በተለይ በሰፋፊ እርሻዎች ኢንቬስትመንት። ኦሮሚያ በውጭ ኢንቬስተሮች በሽ በሽ ብሏል ሲባል የሚመለከተው ኦሮሞ ወይንም ሌሎች ኢትዮጵያዊያን ሃብታሞችን አይደለም፣ አረቦችንና ህንዶችን ነው። ይህ የረቀቀ "ዘመቻና ወረራ" የሚመስል "የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ" ብቻውን አይሽከረከርም። አብሮ የሚመጣ መዘዝ አለ። የአረቦች ባህልና ሃይማኖት። በተለይ፣ ሳውዲዎች የሚከተሉት የእስልምና አይነት ሰፋትና አደገኛ የሆነ ሚና ይጫወታል። ይህ በመንግሥት ግብሣ የመጣ ሁለገብ ጣልቃ ገብነት፣ ዋናው ሚና የኢትዮጵያን የተፈጥሮ ሃብት፣ በተለይ፣ ለም የእርሻ መሬትና ታላላቅ ወንዞች፣ ማእደን፣ ባህል፣ ሃይማኖት፣ የሰው ሃይል ለመቆጣጠር ከሚደረግ የታሰበ እቅድ ጋር የተያያዘ ነው። ሰፋቱንና ጥልቀቱን የጋበዘው ህወሓት ነው። ከህወሓት ባለስልጣናት ጋር በአመቻችነት (Facilitator) የሚሰራው ሼክ ሞሃመድ አላሙዲ ነው። የሼኩ አመቻችነት የኢትዮጵያን ሃብታሞች፣ ወይንም ነዋሪዎች ካፒታላቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ እውቀታቸውን ሰብስበው እንዲወዳደሩ ማድረግ አይደለም። ዋናው ሚና ለአረብ ኢንቬስተሮች የፖለቲካውን ሁኔታ ከገዢው ፓርቲ የበላዮች ጋር በመመካከር ማመቻቸት ነው። አዛዥነትና ጥቅም የሚሰጠው ለሳውዲ አረቢያ መንግስትና ሃብታሞች ነው።

የታወቀው አይሁዳዊ ምሁር፣ ሃጊ ኤርሊች፣ Saudi Arabia and Ethiopia: Islam, Christianity and Politics Intertwined በተባለው የምርምር መጽሃፉ፣ የመለሰ መንግሥት የፈጠረውን የሳውዲ አረቢያ መንግሥት የተቆላለፈ ሚናና አደጋ በሚገባ አቅርቦታል። "የሳውዲ መንግስት፣ በሃይማኖት ስም፣ ታላቅ ከሃይማኖት ክፍፍል የመጣ አደገኛ ሚና ይጫወታል።" ምንም እንኳን ጸሃፊው፣ የዋሃቢን መስፋፋት የሚያየው ከእስራኤል ጥቅም አንጻር ቢሆንም፣ ትንተናውና መሰረተ ሃሳቡ ለኢትዮጵያዊያን ተቆርቋሪዎች ከፍተኛ ጥቅም አለው። ባጭሩ ኤርሊች የሚያሳየው፣ ተከባብሮ፣ ተሳስቦ፣ በኢትዮጵያዊነቱ አምኖ በሰላም የሚኖረው የክርስቲያንና የእስልምና ተከታይ ህብረተሰብ እየታመሰ መሆኑን ነው። ከእርስ በእርስ ንትርኩ የሚመነጨው የኢኮኖሚና የተፈጥሮ ሃብት የበላይነት ከኢትዮጵያውያን ወደ ጥቂት ተጠቃሚዎችና ወደ ኢንቬስተሮች መሸጋገሩን በማያሻማ ጥብብ አሳይቶታል። መተርጎሙ የራሳችን ሃላፊነት ነው። 37/

የምዝበራ ስርአት የሳውዲ አረቢያን ተጠቃሚነት ተከሏል

ሳውዲ አረቢያና ተመሳሳይ የአረብ መንግስታት ከኢትዮጵያ የሚያገኟቸው ጥቅሞች ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ይለያሉ። ከምክንያቶቹ ጥቂቶቹ።

አንድ፣ አስተማማኝ የሆነ በርካሽ የሚሸመት የምግብ አቅርቦት ይሰጣታል። (To establish and secure cheap and reliable food supply for the Saudi Market).

ሁለት፣ተግቶ የሚሰራ፣ በዝቅተኛ ደሞዝ የሚሸመትና መብቱ ያልተከበረ የሰው ሃይል ታገኛለች። (To ensure cheap, hardworking and docile labor force).

ሶስት፣ አስተማማኝ የሆነ የውጭ ገበያና ትርፍ መሰረት ትጥላለች።

አራት፣ ህወሓት በአፋኝነት የከፈተው የባህልና የሃይማኖት ሜዳ፣ በተለይ የሳውዲ መንግስት ለደገፈው ሞሃቢነትን መሰራጨት የበላይነትን "በማይመለስ መንገድ" ማረጋገጡና በአፍሪካ ቀንድ ተወዳዳሪነት የሌለው ጫና መጨበጡ ይገኙበታል። በአብዛኛው፣ የምእራብ መንግስታት ይህ ሂደት ለነሱም ጭምር አደጋ እንደሚያመጣ የተገነዘቡ አይመስልም። የፈለጉት ሮስኮፍ ባደረገው ጥናት እንዳሳየው፣ የአጭር ጊዜ ጥቅማቸውን ነው። ሽብርተኝነትን መቆጣጠርና የቻይናን መስፋፋት መቋቋም። ከኢትዮጵያ ምዝበራ፣ ሰብአዊ መብቶች አፈናና ከሃይማኖት ነጻነት ላይ አላተኮሩም። ስለዚህ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የውጭ ተቆርቋሪና ጠበቃ የለውም። የራሱን መብት በራሱ መታደግ ይኖርበታል።

የምእራብ አገሮች አገልጋይነት ያስገኘው ጥቅም

የሳውዲ መንግስት፣ ልክ እንደ አሜሪካና እንደሌሎች የውጭ መንግስታት፣ አበዳሪዎችና በጎ አድራጊዎች የሚመሩት በራሳቸው ጥቅም፣ ለራሳቸው ጥቅም እንጅ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላም፣ አቅም-ግንባታ፣ ነጻነት፣ ፍትህ-ርትእ፣ ሉአላዊነት፣ ሁለ-አቀፍ ልማት አይደለም። ለዚህ ነው የአሜሪካው ፕሬዚደንት፣ ባራክ አባማ፣ መለስ ዜናዊ ይመራው የነበረውን፣ አሁን፣ ሃይለማሪያም ደሳለኝ የሚመራውን መንግሥት ግፎች አውቆ ዝም ያለው። ይህ አውቆ ድንቁርና ጊዜ እስከሚፈታው ድጋፉ የሆነውን አመራር መርዳቱን ይቀጥላል። <u>የአሜሪካን-ኢትዮጵያ ፖሊሲ ሊለውጠው የሚችለው፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ መረረኝ ብሎ በመተባበር ከዳር እስከ ዳር ሲነሳ ብቻ ነው።</u> ሁለተኛ ቅንጅት ማለት ነው። ሁኔታው

ተደጋጋሚ ስለሚሆን ወደኋላ ሂዶ ማየት ይጠቅማል። በ2012፤ የኦባማ መንግስት በኢትዮጵያ የሚሆነውን ግፍ እያወቀ፤ መለስ ዜናዊ የስምንቱ ሃብታም አገሮች ስብሰባ ተካፋይ አድርጎ፤ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ያላገኘውን ማእረግ ሰጥቶ፤ በዋሽንግተንና በካምፕ ዴቪድ እንዲገኝ የጋበዘው። ይህ ክብር፤ ከሶስቱ፤ የጋና፤ ታንዛኒያና ቶጎ መሪዎችጋር ሲነጻጸር የመለስ ዜናዊ መሳተፍ፤ ለምእራብ አገሮች፤ በተለይ ለአሜሪካ መንግስት፤ ለውጭ ኢንቬስተሮች፤ መለስ የመራው መንግሥት፤ በአፍሪካ ቀንድ ጠቃሚነቱን የሚያሳይ እንጅ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ታዛዥ መሆኑን ገላጭ አልነበረም። በዘጠና ሰባቱ ምርጫ ከሁለት መቶ በላይ ወጣቶች፤ እናቶችና ሌሎች የገደለ፤ ከአርባ ሽህ በላይ ያሰረ፤ ቅንጅት ያሸነፈውን ድል አልቀበልም ያለ መሪ አምባገነን መሆኑን አጥተውት አይደለም። የጋና ፕሬዚደንትና የኢትትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር የሚመሯቸው መንግስታት ተጻራሪ መሆናቸውን ያውቃል። ጋና፤ የሕዝብ ድምጽና የሕግ የበላይነት የተከበረባት ስትሆን፤ ኢትዮጵያ አንድ ንኡስ፤ ጠባብ ብሄርተኛ ቡድን የሚገዛት ናት። ይህ ቡድን፤ የፖለቲካ ስልጣን ተጠቅሞ የአገሪቱን ወሳኝ የኢኮኖሚ ክፍሎች (Pillars of the national economy)፤ ከውጭ ኢንቬስተሮች ጋር በመጋራት ተቆጣጥሯል። ለውጭ መንግስታትና ድርጅቶች አስተላልፏል። ከአብሮ መኖርና ማደግ በላይ የሚፈልገው የበላይነትን ነው። ለኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነት፤ ለሕዝቡ ፍትህ ደንታ የለውም። ከመለስ እልፈት በኋላ፤ የህወሓት አመራር፤ ጥላቻን እንደ በትር መጠቀሙን ቀጥሎበታል። መለስ፤ ጓደኞቹና የውጭ ደጋፊዎቹ የፈጠሩት፤ የደቡብ አፍሪካን ባንቱስታን (Bantustan) የሚመስል የጎሳ አስተዳደር ያዋቀሩት ለአናሳ ጠባብ ብሄርተኛ ከበብ አገልጋይ እንዲሆን ነው። የበላይነት ለመቀጠል የሚችለው፤ መላው ህብረተሰብ እርስ በእርሱ ሲጋጭ፤ ተቃዋሚ ክፍሉና የማህበረሰብ ድርጅቶች በጎሳ ፖለቲካ ሲታመሱ ነው። እርስ በርሳቸው ሲናከሱ። መለስ ካለፈ በኋላ በሚዘገንን ደረጃ፤ ጠባብ ብሄርተኝነት፤ ዘረኝነት፤ እየተስፋፋ ሲሄድ የምናየው፤እንዲያውም ከመለስ በላይ አገሪቱ ለባሰ አደጋ እንድትወድቅ፤ በሰበቡም፤ ያለው ጠባብ ጎሰኛ ስነስርአት እንዲቀጥል ታስቦ ነው። ሁለ-ዘርፍ የሆነ ጭቆና አፈናና የእርስ-በእርስ ግጭት ቢከሰት፤ ዋጋ የሚከፈልባቸው ውጤቶች እንደሚኖሩ አያጠያይቅም። ከጎሳ በላይ የግድ አሰባሳቢ ከሚሆኑ ክስተቶች መካከል፤ የሚከተሉት አሉ።

አንደኛ፤ የኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነትና ህልውና አስተማማኝ አለመሆኑ። ሁለተኛ፤ የተራው ሰው በህይወት በልቶ በሰላም መኖር አስተማማኝ አለመሆኑ። ሶስተኛ፤ የሰብአዊ መብቶች በልዩ ልዩ ምክንያቶች በተባባሰ ደረጃ የሚረገጡ መሆናቸው ይገኙበታል። የመጨረሻው ችግር ሁሉን ያካትታል፤ አንድ ምሳሌ። ህወሓት ከጅምሩ ህገመንግሥቱን ለአፈና ተጠቅሞበታል። ይህ አፈና በተለይ ያተኮረው ከብሄራዊ ተቋሞች፤ አገር ወዳድ ግለሰቦችና ስብስቦች ከማድከም ላይ ነው። የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አስተማሪዎችን ሲያባርር አስቦበት ነው። ተቀናቃይ፤ ለአገርና ለወገን የሚያስብ እንዳይኖር። በውጭ ለሚኖረው ስደተኛ ልዩ የአመራር እቅድ (ስትራተጅ) ሲያወጣ፤ በተለይ አገር ወዳድ የሆኑ ተቋሞችንና ግለሰቦችን ለመከታተል፤ ለመከፋፈልና ለማዳከም ነው። የኢትዮጵያን ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሲኖድ ሲያፈራርስ፤ የኢትዮጵያ መታወቂያ የሆነውን ሁሉ በቁጥጥር ለማዋል ነው። ባለፉት አመታት አፈናውን ለማጠናከርና የኢኮኖሚ የበላይነትን በተረጋገጠ መልክ ተቋማዊ ለማድረግ፤ የህወሓት አመራር በተለይ ያተኮረባቸው አንጋፋ ድርጅቶች አሉ። የስለላ፤ የመከላከያ፤ የባንኮችና ገንዘብ፤ የተፈጥሮ ሃብት፤ የንግድ፤ የትምሕርትና ስልጠና፤ የውጭ ግንኙነት ወዘተ። አጼ ምኒልክ የዛሬ መቶ ሃያ አመት ያቋቋሙት ዘመናዊ መገናኛ፤ቴሌኮሙኒኬሽን ከኢላማዎቹ አንዱ ነበር። ለምን? ጥቅሙ ሁለ-ዘርፍ ስለሆነ፤ ላም እንደሚታለብ ሁሉ፤ የሚታለቡ የትርፍ፤ የሙስና፤ የአድልዎ ተቋሞችን ወደ ህወሓትና ቤተሰቦች ማዘዋወር ከጠባብ ጎሰኝነት አገዛዙ ጋር አብሮ የሚሄድ ነው። ይህን ለማድረግ፤ ቀስ በቀስና በዘዴ አገር ወዳድ ሰራተኞችን ማባረር ያስፈልጋል። አባሯል። ጥቅሙ ቢያንስ ሁለት ነው። አንድ፤ ትርፍ ይገኝበታል። ሁለት፤ ለስለላ ያመቻል። ይህን ያደረገው ዘመናዊ በሆነ መንገድ ነው (Business Process Reengineering) በሚል ዘዴ። "አዲሱ ቴሌና የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ" ተብሎ የሚጠራው የስለላ መረብ እነዚህን ሁለት አላማዎች በአንድ ላይ ያስገኛል።

የጠባብ ጎሰኛ ፓርቲ የበላይነት (Monopoly) ጸረ-ወጣት ትውልድ አገዛዝ

አፋኝ የሆነ አገዛዝ ጸረ-ወጣት ትውልድ ነው። ህወሓት የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በተለይ ወጣቱ ትውልድ በዘመናዊ የመገናኛ ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ ህይወቱን እንዲያሻሽል አልፈቀደለትም። በኢትዮጵያ የዘመናዊ መገናኛ ከአፍሪካ አገሮች፤ ሶማሊያን ጨምሮ ዝቅተኛ ነው። ሆኖም፤ ጎጠኛ ፓርቲ የቴክኖሎጂን የትርፍ ጠቃሚነትና ለአፈና ቁልፍነት አልዘነጋውም። አጼ ምኒልክ የጀመሩትን፤ በአጼ ኃይለ ሥላሴ እየተስፋፋ ሂዶ የነበረውን አፍርሶ በምትኩ ለትርፍና ለአንድ ፓርቲ የበላይነት የሚያገለግል ቴሌኮሙኒካሽን ዘርግቷል። ሲዘረጋ አገሪቱ ያወጣችውን ፈሰስ ዋጋ ቢስ አድርጎታል፤ እንደ ሌላው ማለት ነው። የቀድሞውን በማሻሻል ፋንታ ማፈራረስ ዋጋ ይከፈልበታል። የተደረገው ማፈራረስ ሃላፊነት የጎደለው የኢኮኖሚ ወንጀል ነው ለማለት ያስደፍራል። ህወሓት ያየው የበላይነትን እንጅ ጉዳቱን አይደለም። የበላይነት (Monopoly) ለእድገት መጥፎ ነው። አጼ ምኒልክ ለአንድ የእንግሊዝ ኩባንያ ያለ ምንም ውድድር የንግድ ፈቃድ (Concession)

ሲሰጡ አንድ ኢቶዮጵያዊ ምሁር የውሉን ጎጅነት በትንተና አቅርቦ ነበር። የዛሬ መቶ አመት ማለት ነው። ውሉ "ዘረፋ ነው" ያለው የመረመራቸው፤ የላስቲክ ዛፍ-አሁን ጠፍቷል፤ የፍራ ፍሬ ዛፎች፤ ቆዳ፤ የጎንደርና የሸዋ የምግብ አዘገጃጀት ልዩነቶች ወዘተ ነበሩ። ሊቁ ያሳየው እነዚህና ሌሎች የተፈጥሮ ሃብቶች ለገቢ እድገት፤ ለአገር ልማት ቁልፍ መሆናቸውንና ኢትዮጵያውያን የበላይነቱን መያዝ እንዳለባቸው ነበር። የአሁኑ ትውልድ የእነዚህን ጠበብቶች ጥልቅ እውቀት ዋጋ አልሰጠውም።

በቅርቡ በአዲሲቱ ኢትዮጵያ የጋራ እንቅስቃሴ በጥናት የቀረበ ዘገባ ከህወሓት የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት ጋር የተያያዘ ጥናትና ተመክሮ ላወቀበት የማንም ድርጅት ካቀረበው በላይ ጊዜያዊ ነው። የህወሓት የበላይ አመራር ድርጊቱ ለማንም ኢትዮጵያዊ ሆነ ለውጭ ድርጅቶችና መንግስታት እንደሚዘገንን ያሳያል። በሰብአዊ መብቶች መገፈፍ ላይ ያሳየቱን ያጠናክራል። ህወሓት ዘላቂነት ያለው አፈና ያካሄደው፤ የምእራብና እንደ ሳውዲ አረቢያ ያሉ መንግስታት የሚጋሩትን ጸረ-ሽብርተኛነትን ያካተተ ብሄራዊ የመረጃና የደኅንነት አገልግሎት ሰጭ የተባለ ዘመናዊ መገናኛ መረብ (Information Infrastructure and network) ዘርግቷል። ዋናው ኢላማ በደህንነት ስም፤ ዓለም አቀፍ ስለላን ለማጠናከር ነው። የዚህ ውጤት (Effect and Impact) ፍጹም የሆነ የግለሰብ ነጻነት አፈና ነው። ይህ አፈና ብሄር፤ ጾታ፤ የውስጥ፤ የውጭ፤ እድሜና ሃይማኖት፤ ኢትዮጵያዊ ወይንም ፈረንጅ አይለይም። የቻይናን ቅጅ ይመስላል። ህወሓት ከዚህ ውሳኔ ላይ ሲደርስ የዛሬ መቶ አመት ያስጠነቀቀውን ኢትዮጵያዊ የኢኮኖሚ የበላይነት (Monopoly) አደጋ በአናቱ በማስቀመጥ ነው። ጥናቱ እንደሚያሳየው፤ የውጭ ቴክኖሎጂ አቅርቦት ጠቃሚነቱና ጥራቱ የሚታየው የተለያዩ አቅራቢዎች ግልጽነት ባለው መልክ ተወዳድረው ያሸነፈው ሲመረጥ ነው። ቁልፉ መስፈሪያ ኢትዮጵያውያን ተሳታፊዎች መሆናቸው ነው። ህወሓት በግልጽነትና በነጻ ውድድር ስለማያምን ውሳኔው የፖለቲካ ሁኗል። ለምሳሌ፤ እውቅና ያላቸው እንደ ጀርመኑ ሲመንስ፤ እንደ ኖሪዲኩ ኖኪያ፤ እንደ አሜሪካው ኤቲና ቲ ወዘተ እንዲወዳደሩ አልተደረገም። ለምን? ውድድር አለመኖሩ አራት ችግሮችን ወልዷል።

አንድ፤ ኢትዮጵያ የምትከፍለው ዋጋ ከፍ ብሏል።

ሁለት፤ የቴክኖሎጂው ጥራት አልተረጋገጠም።

ሶስት፤ በኮሚሽንና በጉቦ ወዘተ የሚከፈለው ለሙስና ዋና መንገድ ጠራጊ የሆነውን አደጋ ለመከላከል አላስቻለም።

አራት፤ ዱሮ ከነበረው የቴሌ መሳሪያ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ልምድ ያለውን ሰራተኛ ለመጠቀም አልተቻለም። አገሪቱ የበለጠ ዋጋ ትከፍላለች። የአገሪቱን ልምድና እውቀት ተጠቅሞ ኢትዮጵያዊ የሆነ ኢንዱስትሪ ለማመቻቸት አላስቻለም።

በብዙ አገሮች ፈጣን የቴክኖሎጂ አቅርቦት ከግል የኢኮኖሚ ውድድር ጋር አብሮ የሚሄድ ነው፤ በኢትዮጵያ ይህ ያልሆነበት ምክንያት ግልጽ ነው። የህወሓትንና የፈጠራቸውን ድርጅቶች የበላይነት ለመስጠት፤ሌላው፤ በቴክኖሎጂ እድገት ስም፤ "የመረጃ መረብን ለማጠናከር ነው።" ይህ ስለሆነ፤ በማንኛውም ኢትዮጵያዊ ላይ ስለላ ለማድረግ አመች አድርጎታል። ሞባይል ሆነ መደበኛ ቴሌፎን፤ ኢንተርኔት ሆነ ፌስቡክ ወዘተ ለመከታተል ያመቻል። የግል ከሆነ ለስለላ አያመችም። የበላይነቱ በቀጥታ ከትርፍና ከምዝበራ ጋር አብሮ ይሄዳል። የህወሓትን ረጅም ጡንቻ አጠናካሪ የሚሆነው የበላይነቱን ፍጹም በሆነ ደረጃ ለመያዝ በመቻሉ ነው። "ብሄራዊ የመረጃና የድህንነት አገልግሎት" ሆነ፤ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ተጠሪነታቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ አይደለም፤ ለህወሓት የበላዮች ነው። በጸረ-አሸባሪነት (Counter-Terrorism) የተመሰረቱት ተቋሞች ስራቸውን ሲሰሩ፤ ነጋዴዎችን፤ ተማሪዎችን፤ ስደተኞችን፤ የማህበረሰብና የፖለቲካ ድርጅቶችን በሙሉ ሰርገው ገብተው ነው። አንዱ በሌላው ላይ እንዲሰልል ያደርገዋል። የአሁኑን የስለላ ረጅም እጅ በአስጊ ሁኔታ ያጠናክረዋል ማለት ነው። ከህንጻዎች ላይ የተተከሉት ካሜራዎች ለጌጥ አይደለም፤ ስለላውን፤ በተለይ የሕዝብ እንቅስቃሴን ለመከታተል ነው። 38/

የህወሓት የፖለቲካ ውሳኔ፤ የቻይናው ዚቲኢ ለምን ተመረጠ?

የቁጥጥር ኢኮኖሚ አመራርና የስለላ መረብ የተቆላለፉ ናቸው፤ ለአድሎና ለሙስና መሳሪያ ሆነው ያገለግላሉ። አጼ ምኒልክ ለሕዝብ አገልግሎት ብለው ያቋቋሙት ዘመናዊ መገናኛ በሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዋናው ተግባሩ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ዘመናዊ ማድረግ ነበር። አልሆነም። የስለላና የአፈና መሳሪያ የሆነው ለአድልዎና ለሙስና ጭምር የማይገኝ ጥቅም ስለሚሰጥ ነው። የቻይናው ዚቲኢ የተመረጠበት ዋና ምክንያት ቴክኖሎጂው ለስለላ አመች ስለሆነ ነው። ሁለት ግንዛቤዎችን እንይ። አንድ፤ ውድድር ሳይኖር ኮንትራቱ በፖለቲካ ውሳኔ ለቻይና ዚቲኢ መሰጠቱ። ሁለት፤

ትምህርትና ልምድ ያላቸውን ኢትዮጵያውያን ከስራቸው አባሮ በምትካቸው ታማኝ የሆኑ ለስለላው መረብ የሆኑ የህወሓት፤ በተለይ የትግራይ ተወላጆችን መተካቱ። አንባቢው እንዲያየው የምንጠይቀው፤ ጠባብ ጎሰኛነት፤ መንግሥት፤ ተቋሞችና የፖለቲካ አመራሩ መረብ አላቸው የሚለውን ነው። (Highly networked and integrated). ለአገሪቱና ለህብረተሰቡ ተከራካሪ የላቸውም። በመንገድ፤ በግድብና በሌሎች ታላላቅ ስራዎች፤ መንግሥት ማንም በማይቆጣጠረው ደረጃ ብዙ ቢሊዮን ዶላርና ብር በሚያፈሰው ተጠቃሚውን ይመርጣል። የቻይና መንግስት ለዚህ ጠቃሚ ሚና ይጫወታል። የኢትዮጵያ የመከላከያ ዘርፍ በተሃድሶ ግድብ የሚቻወተው ሚና ከዚህ የተያያዘ ጥቅምና ቁጥጥር ጋር መታየት ይኖርበታል። ቻይና የምትታወቅበት አንዱ ሚና የውጭ ምንዛሬ እንደልብ ማቅረብ ነው። ህወሓት የሚፈልገውን አቅርቦት በሻጭ አበዳሪነት (Supplier's Credit, Vendor Financing) ስታመቻች ቆይታለች። ጥናቱ እንደሚያሳየው የአዲሱን ቴሌ እቃ ለመግዛት ቻይና አንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ዶላር አበድራ ህወሓት ያለምንም ውድድር እቃውን ከቻይና ገዝቷል። ቻይና ያለምንም ተቀናቃኝ የበላይነት ተሰጣት። ይህ ግልጽነት የሌለው አቅርቦት በኮሚሽን፤ በጉቦና ሌላ ዋጋ ይከፈልበታል። ቴክኖሎጂው ጥራት ይኑረው አይኑረው አይታወቅም። በመንገድ፤ በድልድይ፤ በግድብና ሌሎች ስራዎችም ኮንትራቶች በግልጽና በውድድር አይሰሩም። ዋጋውን የሚሸከመው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ውድድር ከሌለ ሶስት ነገሮች በማያከራክር ሁኔታ መከሰታቸው አይቀርም። አንድ፤ ዋጋውን ለመቆጠጠር አይቻልም። ውድድር ካለ እውነተኛ ዋጋ ይከፈላል። ሁለት፤ አድልዎና ሙስንና ለመከላከል አይቻልም። ሶስት፤ የቴክኖሎጂው ጥራትና ዘላቂነት አስተማማኝ ይሁን/አይሁን አይታወቅም። ዋጋ የሚከፍለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ቻይና ብድሯን ትከፈላለች።

የግል ኢኮኖሚ ለእድገት ቁልፍ ነው የሚሉት የምእራብ መንግስታትና አበዳሪ ድርጅቶች ግልጽነትና ውድድር የሌለበት ንግድ ጉዳት እንዳለው ያውቃሉ። "የምእራብ አገሮች የቴሌኮሙኒኬሽን ኩባንያዎች የሚዘረጉት ቴክኖሎጂ ከስለላና ከደኅንነት ጋር ተቆራኝተው ስለማይዘረጉ መረጃዎች እንዳያፈተልኩበት የሰጋው አገዛዝ ከደህንነት የመረጃ መረብ ጋር ተቆራኝቶና ተገምዶ የሚዋቀረውን የቻይናን የቴሌኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ለመጠቀም እንደወሰነ ያገኘነው መረጃ ያሳያል።" ጥናቱ የሚያጠናክረው የፖለቲካ ውሳኔ መሆኑን ነው። የህወሓትና የቻይና መንግስት የጥቅም ግንኙነታቸው በጣም የጠነከረ መሆኑን ያመለክታል። ቻይናዎች ኮንትራቱን ለማግኘት ኮሚሽን ለህወሓት ባለስልጣን ቢከፍሉም መልሰው ከሚያበድሩት ገንዘብ ላይ ስለሚደምሩት ከኪሳቸው ወጭ አይኖርም። ባለ እዳው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ኮሚሽን የተከፈለበት የሚመስለውን የንግድ ክፍያ ዶላር እቃውን ስላቀረቡ መልሰው ይወስዱታል። ኮሚሽኑ ለህወሓት የበላዮች የምዝበራ መሳሪያ ይሆናል። "እከክልኝ አክልሃለሁ።" 39/

የህወሓት የታማኝነት ችሎታ መለኪያ

ምዝበራው በዚህ አያቆምም። ቴሌ "የምትታለብ ላም" ማለት ነው። ገቢው አያቆምም። የሚቆጣጠረው ሁልጊዜ ኪሱ እንዳበጠ ይኖራል። ቁጥጥሩን በበለጠ ለማጠናከር የሚያስችለው የእለት ከእለት ስራውን የሚያካሂደው የሰው ሃይል ነው። በሽህ የሚቆጠሩ ልምድ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ከስራቸው እንደተባረሩ ተነግሯል። የወጡም ምስክሮች አሉ። ህወሓት የውጭ ሊቆችን እውቀት ይፈልጋል በሚል ዘዴ፤ ድሮ ኢትዮጵያውያን ያካሂዱት የነበረውን የቴሌ አመራር ለፈረንሳዮች ሰጠ። ይህ ህወሓት በጀርባ ሆኖ ለማመቻቸትና ለማዘዝ ረድቶታል። ቁም ነገሩ፤ ኢትዮጵያውያንን አባሮ ህወሓት ከተካቸው ላይ ነው። ከሁለት ሽህ በላይ ሰራተኞች አባሯል። በሁለት ሽህ ታማኞች፤ በተለይ የትግራይ ተወላጆች ተክቶታል። እንደዚህ ያለ አይን ያወጣ የጎሳ አድልዎ የትም አገር አይደረግም። በኢትዮጵያ ታሪክ ተደርጎ አያውቅም። ህወሓት የመረጣቸው ከአዲስ አበባና ከመቀሌ ከፍተኛ ውጤት አገኙ የተባሉት ቁልፍ ቦታዎች ተረከበዋል። ዋናው መለኪያ ለህወሓት ታማኝነት ነው። "በአንድ አገር ውስጥ የሚታመኑ፤ የማይታመኑ፤ ቢታመኑም ሃላፊነትና ነጻነት የማይሰጣቸው ፍጹም ባይታወር የሆኑና በጠላትነት ተፈርጀው የሚማቅቁ ዜጎች ይኖራሉ"። ጥናቱ አጠናክሮ ያቀረበው ሌላ ማስረጃ የፖሊስ፤ የመከላከያ፤ የደኅንነትና የስለላ ተቋሞች መቆላለፋቸውን ነው። ይህን ለማድረግ ታማኝ አገልጋዮች ያስፈልጋሉ። ግማሹ ኤሪትሪያዊ፤ ግማሹ ትግሬ የሆነው ጌታቸው አሰፋ የበላይ ሆኖ ይሰራል። የቴሌኮሙ ቦርድ ሊቀመንበር ትግራዩ ዶር ደብረጽዮን ገብረሚካኤል ነው። የቤተሰብ ድርጅት ይመስላል። "አዲሱ ቴሌና የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ (ኢንሳ) እየተመጋገቡ እንዲሰሩ ተደርጎ በሚዘረጋው መረብ ውስጥ ተጠቃሚ የሆነ ሁሉ የሚቀያየሩባቸው መረጃዎች ምስጢርነታቸው እንዲጠበቅ ኢንሳ ውስጥ በአመራር ላይ ያሉት ሰዎች የትግራይ ተወላጆች እንዲሆኑ ተደርጓል። "በትምህርትና ልምድ ውጤት ወይንም ሳይታሰብ የተቀረጸ ድርጊት ነው ለማለት አያስደፍርም።" 40/

ይህ አዲስ ክስተት አይደለም። እውቀትና ችሎታ የነበራቸው የዩኒቨርስቲ አስተማሪዎች ተባረዋል። በጋምቤላ የእርሻ መሬት ምሪት ሰባ አምስት በመቶ የሚሆኑት ተጠቃሚዎቹ የትግራይ ተወላጆች ናቸው። የጎንደርና የወሎ መሬት ተቆርሶ

ለክልል አንድ ሲሰጥ ተጠቃሚዎቹ የትግራይ ተወላጆች ናቸው። ወደ ጃፓን አስራ ሁለት ኢትዮጵያውያን ተመርጠው፤ ስምንቱ ቀርተው በምትካቸው የተላኩት የትግራይ ተወላጆች ናቸው። ማለቂያ የለውም። የአድልዎ በደል ፍጹም ሆኗል። ለማሳየት የምፈልገው፤ የታማኝነቱ የስራ ድልድል ውጤት የሚያጠናክረው ስለላውን ጭምር መሆኑን ነው። ግለሰብ ስልክ ሲጠራ ወይንም ስልክ ሲመልስ፤ በራሱ ሞባይል ሆነ በሌላ ስልክ ክትትልና ጠለፋ ይደረግበታል። የግልም ሆነ የቤተሰብ የስልክ ውይይት ክትትል ይደረግበታል። ኢሜይል፤ ኢንተርኔት፤ ፌስ ቡክ ከስለላ ነጻ አይደሉም። የበጎ አድራጊ ድርጅቶች፤ ኤምባሲዎችና ሌሎች የጠለፋው ጫና ይደርስባቸዋል። ህወሓት የመረጣቸው ካድሬዎች ኢትዮጵያን በመወከል በልዩ ልዩ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ለስለላ ተመልምለው ይላካሉ። ዓለም ባንክ ለልምምድ (Internship) እንደገቡ ደራሲው ያውቃል። "የቅንጅት ፖለቲካ በተሰፋፋበት ወቅት፤ ከአረብ አገራት ተቀጥረው የመጡ የመረጃ ሰራተኞች" ነበሩ። ዛሬ ኢትዮጵያውያን ያሉበት ሁሉ በስለላ ተበክሏል። የፖለቲካና የማህበረሰብ ስብስቦች ይህን አውቀው ራሳቸውን ለመጠበቅ ቆርጠው መነሳት አለባቸው። 41/

ካልፈለጋችሁ ከኢትዮጵያ የመውጣት መብት አላችሁ ብሎ የሚያሰናብተው ህወሓት፤ በስደተም ነጻነት ለመከልከል እንደሚሞክር መካድ አይቻልም። በታወቀው ጋዜጠኛ በአበበ ገላው ላይ በአሜሪካ ምድር የተደረገው የኑብስ ግድያ ሙከራና የአንዳርጋቸው ጽጌ ጠለፋ ለዋጭ አስተሳሰብን ማምጣት አለበት። ህወሓት የዕኛን ድክመት ስላወቀው፤ "ፍለሱ፤ ሂዱ፤ ተሰደዱ" ድምጽ አታሰሙ። አትወዳደሩ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሃብትና ንብረት የራሴ ብቻ ነው" ብሏል። የህወሓት የበላይ አመራር እስካሁን የመዘበረው አልበቃውም። "እንዲማሩ፤ እንዲሰለጥኑ፤ ልምድ እንዲያገኙ ልዩ ትኩረት" ለልዩ ጎሳ የሚሰጠው ተተኪውን ለማዘጋጀት ነው። እድልዎ "የተሰጣቸው በተለይ የትግራይ ተወላጆች ናቸው።" የፖለቲካ ታማኝነት የሌላቸው በእድላቸው መኖር አለባቸው የሚል አመራር ነው። ይህ የአገዛዝ በደል የሚቀጣው አዲሱንና ተከታታዩን ትውልድ ነው። የንግድ፤ የአገልግሎትና የአምራች ተቋሞችን ለራሱ በሚጠቅም ሁኔታ የሚመራው ከዚህ ተለይቶ አይታይም። ቴሌን መቆጣጠር ፍጹም ያደርገዋል። "የህወሓት የንግድ ተቋም ኤፈርት ትግራይን ለማቋቋም ተፈጥሮ ነበር"። መልሶ ማቋቋም ወደ ኢኮኖሚ፤ የገቢ፤ የኑሮና የሃብት የበላይነት አምርቷል። ኤፈርት አምሳ ቢሊዮን ብር ካፒታል ለመድረስ የቻለበት ዋና መሳሪያ የፖለቲካ የበላይነት ነው። ዛሬ አገር አቀፍ የሆነ የበላይነት ሚና ይጫወታል። ብዙ ሚሊኔየሮች ፈጥሯል። የንግድ፤ የምርት፤ የአስመጭና ላኪ፤ የባንክና ፋይናንስ፤ የአገልግሎት ወዘተ ወዘተ ተቋሞች አገር አቀፍ በሆነ ደረጃ ያንቀሳቅሳል። አገራዊ የሆነ እንቅስቃሴ የሚያደርገው አትራፊ ኤፈርት፤ አሁንም ጠባብ ጎሰኛነቱን በመከተል፤ የልማት ሚና የሚጫወተው ትግራይ ውስጥ ነው። ትርፍ የሚሰበሰበው አገር አቀፍ በሆነ ደረጃ ነው። የአዲሱ ቴሌ ልማት ሲዘርጋ አንዱ ተጠቃሚ ኤፈርት ነው፤ ይህ የበላይነቱን ያጠናክራል፤ ውድድርን ይጎዳል። 42/

ባጭሩ፤ የደህንነትና የዘመናዊ ቴሌ መቆራኘት አድሏዊ የሆነ ገቢን፤ የህወሓትና ተባባሪ ድርጅቶችን የኢኮኖሚ የበላይነት፤ የማፈንና የስለላን አቅም፤ ጉቦን፤ ሙስናን፤ ወደ ውጭ የሚጎርፈውን የውጭ ምንዛሬ ሽሽት ያባብሰዋል። ለዚህ የሚበጀው ከጎሳ ባሻገር ማሰብን፤ ለሰብአዊ መብቶች፤ ለእውነተኛ እኩልነትና ዲሞክራሳዊ ስርአት አብሮ ተባብሮ መነሳትን ነው። ለፍጹም አፈና መልሱ ተባብሮና ደፍሮ በአንድ ላይ መነሳት ነው።ከጠባብ ጎሰኛነት፤ ከሃይማኖት፤ ከስልጣን ሺሚያ በላይ ማሰብ የሚያስፈልገው ለዚህ ነው። አገርና የህብረተሰቡ ጥቅም መቅደም አለበት። ስሜታዊ የሆነው የጎሳ ፖለቲካ ያዋጣል ብለው ለጊዜው የተሰበሰቡ ቢኖሩም፤ በጎሳ በመደራጀታቸው፤ ደካማ ናቸው። ኢትዮጵያን ማጥፋት ለሁሉም መጥፊያ ይሆናል ብሎ መገመት ጥቅም አለው። የአገዛዙ አጥፊነት አገራዊ፤ ህብረተሰብአዊና ግለሰባዊ ነው። <u>ዋናው የመሻሻል (Reform) ኢላማ አፋኝ የሆነው ስርአቱ ነው።</u> መተካት ያለበት። ለውጡ ማካተት ያለበት የፖለቲካ ድርጅቶችን ብቻ አይደለም። ማንኛውንም የህብረተሰብ አባላት፤ የፖለቲካ፤ የማህበረሰብ፤ የሞያ፤ የሃይማኖት፤ የግለሰብ፤ የከተሜ፤ የገጠሬ፤ የአገር ውስጥ፤ የአገር ውጭ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ይመለከታል፤ ስርአታዊና መሰረታዊ ስለሆነ። ሁሉም ድርሻውን ማቅረብ ያለበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ከውስጥ ብቻ ሳይሆን፤ ከውጭ ያንዣበበውን አደጋ አለመገመት ሞኝነት ነው። በማንኛውም አንጻር ሲታይ፤ ይህ የመጥፎ አገዛዝ ሁኔታ ከቀጠለ፤ ማን ሃብታም፤ ማን ደሃ፤ ማን ገዥ፤ ማን ተገዥ፤ ማን ስደተኛ፤ ማን ተቀጣሪ፤ ማን አዲስ ተጠቃሚ እንደሚሆን ለመተመን አያስቸግርም። የዘር ማጥፋት ዘመቻን፤ የሃይማኖት ነጻነት ገፈፋን፤ ወዘተ፤ የማየው ከዚህም ከገዢው ፓርቲና ከውጭ ደጋፊዎች ድርጅቶችና መንግስታት የተሳሰር ጥቅም አንጻር ነው። ህወሓት፤ የቻይናን፤ የደቡብ ኮሪያን፤ የታይዋንን፤ የቬትናምን አይነት እድገታዊ አመራር (developmental state model) እከተላለሁ ሲል ምክንያት አለው። እነዚህ አገሮች የሚመሩት በአገር ወዳዶች ነው። ህወሓት ለራሱ ሃይል፤ ሃብት ከምችትና ቁጥጥር ነው። ወገናዊ ስለሆነ (Partisan) ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ህይወት ለዋጭ አይደለም። በልማትና በብሄራዊ እርጋታ ስም፤ የኦጋዴንን ሰላማዊ ህብረተሰብ ይገድላል። የአኗክን ሕዝብ ያባርራል። የኦሮሞውን ሕዝብ "በአማራ ላይ ተነሳ፤ አጼ ምኒልክ የተከለብህን የቅኝ አገዛዝ አፍርስ" ይላል። የእስልምና ሃይማኖት ኢትዮጵያን ሊያፈራርሱ ተነስተዋል ይላል። ይህን ሁሉ ፈጥሮ የሚያስተጋባው፤ ስልጣንን፤ የበላይነትን ለማረጋገጥ ነው። እድገታዊ መንግሥት ነኝ ሲል፤ የእነ

ኮሪያን፤ የእነ ታይዋንን አስደናቂ ህይወት ለዋጭ ውጤቶች ሳያሳይ ነው። ለምሳሌ፤ እነዚህ አገሮች በአምባገነኖች በተገዙበት ወቅት፤ ተቋሞቻቸው ሆኑ መሪዎቻቸው አገር ወዳድ፤ ታሪክና ባህል አክባሪ፤ መላውን ሕዝብ ያቀፉ ነበሩ። የግል ክፍሉ፤ ጎሳዊ ወይንም ክልላዊ አልነበረም። በውጭ "ወራሪዎች" አልተያዘም። በእድል እኩልነት፤ በጋራ ጥቅም የተመሰረተ ነበር። ለሁሉም በር ከፋች ነበሩ። የህወሓት ጭልጥ ያለ ጎሳዊ ነው። በጠባብ ጎሰኛነት የታነፀው የህወሓት የፖለቲካ፤ የማህበረሰብና የኢኮኖሚ ስርአት (Governance) ከማንም አገር ጋር ሊነጻጸር አይችልም።

የህወሓት ዋና መለያዎች፤ ጠባብ ጎሰኛነትና በይፋ የሚታይ አድሏዊይነት፤ ከዚህ ጋር የተያያዘ አገራዊ ምዝበራና ሙስና ናቸው። በማንኛውም መለኪያ፤ ጠባብ ጎሰኛነት ለሌላው እድል ይዘጋል። እነ ኮሌየር፤ ኢስተርሊ፤ ሮንግና ሌሎች በምርመራ ያገኙት፤ የጎሰኛነት አመራር እድል ይዘጋል። የእርስ በእርስ ንትርክና ጦርነት ይፈጥራል የሚል ነው። ጠባብ ጎሰኛነት እድልን ማጥበቡ አያከራክርም ። አንባቢው ማሰብ ያለበት፤ እየቆየ ሲሄድ፤ ለራሱ ደጋፊዎች እድል እያሰፋ፤ ተተኪዎች እያሰለጠነ፤ የመግዛት ሃይሉን በሚያገኘው ገንዘብና በሚገዛው የሰውና የመሳሪያ ሃይል እያጠነከረ ለመቆየት ይሞክራል። ሃያ ሶስት አመታት ከገዛ፤ ህብረተሰቡና ተቃዋሚዎች ከጎሳ በላይ አስበው በአንድ ላይ ካልተነሱ ሌላ ሃያ፤ አምሳ፤መቶ አመታት ለመግዛት የሚያስችለውን ሁኔታ እየፈጠረ ይሄዳል። ሆኖም፤ ህብረተሰቡ ካልፈቀደ በስተቀር፤ የመሳሪያና ፍጹም የሆነ የስለላ መረብ ብቻውን አገርን አይገዛም። የታፈነ፤በድህነትና በስደት የሚሰቃይ ሕዝብ ነጻነቱን፤ መብቱን፤ ህልውናውን ለመጠበቅ ይነሳል። የሰሜን አፍሪካና የመካከለኛው ምስራቅ አገሮች ዋና ምሳሌዎች ናቸው። ጋና፤ ደቡብ አፍሪካ፤ በርማ፤ ወዘተ ምሳሌዎች ናቸው።

እድገታዊ መንግሥት በነፍስ ወከፍ ገቢ መለኪያ ሲታይ

ወደ ካምፕ ዴቪድ ከመምጣቱ ቀደም ብሎ የሰብአዊ መብቶች ተቋም (Human Rights Watch) ያደረገውን ትችት መለስ ፕሮፓጋንዳ ነው ሲል ያጠናከረው ነጥብ አለ። "ለእድገት፤ ዲሞክራሲ አያስፈልግም" የሚል ነበር። ይህ ከእውነቱ የራቀ መሆኑን እንመልከት። አስቸጋሪ ሆኖ ያገኘሁት፤ ሊጋስ የሆኑ መንግሥታት፤ እንደዚህ አይን ያወጣ፤ በእድገትና በሰብአዊ መብቶች መካከል ግንኙነት የለም የሚል መንግስት ለምን ደገፉ የሚለው ነው። የሳውዲ መንግስት ቢያደርገው አያስደንቅም። የሳውዲ ሴቶች ተምረው ስራ የላቸውም። አብዛኛው ወጣት ስራና የራሱ ቤት የለውም። መብት የለውም። መብቱን ሊጠይቅ አይችልም። የሳውዲ መንግስት የዲሞክራሲ መለኪያ ሊሆን አይችልም። አስቸጋሪ የሆነው የአሜሪካ መንግሥት የተከተለው ፖሊሲ ነው። አሜሪካ በኮሪያ፤ በቬትናም፤ በኢራቅ፤ ወዘተ፤ የበላይነቱን ያሳየው፤ ዲሞክራሳዊ ስርአት መመስረት ከማንኛውም የበለጠ ነው በሚል አመራር ነው። ፕሬዚደንት ኦባማ በሄደበት የሚያስተጋባው፤ የሰብአዊ መብቶችን መከበር አስፈላጊነት ነው። በጋና የተናገረው መድብለ ፓርቲ ያላቸው የአፍሪካ አገሮች ፈጣንና ፍትሃዊ እድገት እንደሚያሳዩ "የአይን ምስክር ነኝ" የሚል ነው። ናይጀሪያ፤ ደቡብ አፍሪካ፤ ጋና፤ ማሊ(ከመፈራረሷ በፊት) ፤ ኒጀር፤ ቤኒን፤ ሴኔጋል፤ ሴራሊኦን፤ የመካከለኛው አፍሪካ፤ ሞዛምቢክ፤ ታንዛኒያ፤ ቦትስዋና፤ ናሚቢያ፤ ሞሪሸየስ፤ ኬፕ ቬርዲ፤ ሌሶቶ፤ ኮሞሮስና ሴየሸልስ ዲሞክራሳዊ መንግስታት አሏቸው። ይህን መጽሃፍ በምንጽፍበት ወቅት፤ የእነዚህ አገሮች መካከለኛ የነፍስ ወከፍ ገቢ በአመት $4,000፤ ከፍተኛ የመካለኛ ገቢ የደረሱት፤ የሞሪሸየስ፤ ቦትስዋና፤ ሴየሸልስ፤ በአመት የነፍስ ወከፍ አማካይ ገቢ $10,000 በላይ መሆኑን አይኤምኤፍ መዝግቦታል። ሃያ ስድስት የአፍሪካ አገሮች የነፍስ ወከፍ ገቢያቸው በአመት ከ$1,000 እስከ $3,999 ነው። በአንጻሩ፤ የእርዳታ ተቀዳሚ የሆነችው ኢትዮጵያ፤ የነፍስ ወከፍ ገቢ አሁንም የአፍሪካ መጨረሻ ከሆኑ አገሮች መካከል ነው። በአመት በከፍተኛ የተገመተው $498 ነው።

አስደናቂ እርዳታ ዝቅተኛ ምርትና የስራ እድል

የኢትዮጵያን እድገት ከራሷ ከኢትዮጵያ ጋር ማነጻጸሩ የአግሪቱን እድገትና የሕብረተሰቡን የኑሮ መሻሻል አያሳይም። ከዝቅተኛ ደረጃ ጀምሮ በተከታታይ እድገት ማሳየት የሚጠበቅ ነው፤ በተለይ ለኢትዮጵያ። ምክንያቱም፤ ባለፉት ሃያ ሶስት ዓመታት የምእራብ አገሮች፤ በተለይ እንግሊዝ፤ አሜሪካ፤ ካናዳና የአውሮፓ የጋራ ማህበር ኢትዮጵያን ከሌሎች የጥቁር አፍሪካ አገሮች ለይተው የእርዳታ ትኩረት ሰጥተዋታል። የእርዳታው መጠን አስደናቂ ነው ለማለት ይቻላል። በኦፊሴል ደረጃ በ1997 $605 ሚሊዮን የነበረው የእርዳታ መጠን በአስራ ስድስት ዓመታት እያደገ ሄዶ በ 2013 $4 ቢሊዮን ደርሷል፤ ከአፍሪካ አንደኛውን ደረጃ የያዘ፤ ከዓለም አራተኛውን ደረጃ የያዘ--ከኢራክ፤ አፍጋኒስታንና ኢንዶኔዢያ ቀጥሎ። ይህ በአፈርካ ተወዳዳሪ የሌለው የእርዳታ መጠን በጣም የጨመረው የኦሳማ ቢን ላደን አመፀኞችና ሸብርተኞች በአሜሪካ ላይ ታይቶ የማይታወቅ ጥቃት ካደረሱ በኋላ ነው፤ ናይን ኢለቨን የሚባለው ጥቃት። ከዚያ ወዲህ በኢትዮጵያና በአሜሪካ መካከል ያለው የደህንነት ትብብር ጥልቀትና ስፋት ይዟል። አልኬይዳን በየቦታው ለመከላከል። የኢትዮጵያ መንግሥት የአሜሪካን ጥቅም ማስተጋባቱን በይፋ ማካሄድ ጀመረ፤ አሜሪካ ለኢትዮጵያ መንግሥት ከፍተኛ ድጋፍ መስጠቷን ተከታታይ አደረገች። እንደ ዓለም ባንክ ያሉ የምትቆጣጠራቸው አበዳሪዎች

ለኢትዮጵያ ትኩረት እንዲሰጡ መመሪያ ሰጠች። የመሰረተ ልማትና ሌሎች የእድገት መስፈርቶች የተስፋፉት ከዚያ ወዲህ ነው ብንል የተሳሳትን አይመስለኝም። ምርጫ ዘጠና ሰባትም ለእድገቱ ስፋትና ጥልቀት የሚያስመሰግን አስትዋፆ አድርጓል። በግልፅ የሚታየው ክስተት አሜሪካ ነጻነት፤ ፍትህ፤ እኩልነትና ዲሞክራሲ ሁለተኛ ደረጃ የያዘ ነው ከሚል ድምዳሜ መድረሷ ነው። እርጋታና ፀረ-ሺብርተኛነት የፖሊሲ ማእከል ሆኗል። ይኼን ወደ ጎን ትተን የነፍስ ወከፍ ገቢን እንይ። በተራው ኢትዮጵያዊ ኑሮ መሻሻል መስፈርት ስናየው ይህ በኢትዮጵያ ታሪክ ተመሳሳይ የሌለው የእርዳታ መጠን አስተማማኝነት እንዲኖረው ከተፈለገ እድገታዊ የሆነው አመራር፤ ዝቅተኛ ገቢ ያላትን አገር ወደ ከፍተኛ ደረጃ (እንደ ሌሎቹ በፍጥነት ያደጉና በማደግ ላይ ያሉ አገሮች) ለማድረስ አልቻለም። እርዳታው የተራውን ኢትዮጵያዊ ኑሮ አላሻሻለም። ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዢ እንዳሳየነው ሰላሳ አምስት የአፍሪካ አገሮች ኢትዮጵያን ቀድመዋታል። ጥያቄው መቅደማቸው አይደለም፤ ገዢው ፓርቲ የተራውን ኢትዮጵያዊ ገቢ ለማሳደግና ኑሮውን ለማሻሻል ምን ተአምር እያደረገ እንደሆነ አጥጋቢ መረጃ ላገኝ አለመቻሌ ነው። ሌላው አስቸጋሪ የአየር ጠባይ ለውጥ ነው። የአየር ጠባይን ችግር ለመከላከል (በእርሻ ምርት በኩል) እቅድ ያስፈልጋል። የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ስልት ያስፈልጋል፤ ባለቤትነትና ሃላፊነት ያስፈልጋል። እርጋታ አለመኖርና በተፈጥሮ ሃብት ዙሪያ የእርስ በእርስ ግጭት ሁኔታውን አባብሶታል። በአንጻሩ፤ አንባቢው እንዲያጤን የምፈልገው ፍትሃዊ፤ በህግ የሚዳኝ፤ መላው ሕዝብ የሚሳተፍበት ስርአት ቢመሰረት፤ ኢትዮጵያ ሌሎች ከደረሱበት ደረጃ ለመድረስ ወይንም ለማለፍ ትችላለች። ለመድረስ የፖሊሲና መዋቅራዊ ለውጦች ማድረግ ግዴታ ነው። አለያ፤ እነዚህና ሌሎች አገሮች ይቀድሟታል፤ ከነሱ ለመድረስት አስርት ዓመታት ይወስዱባታል። ችግሩ ስርአት የፈጠረው፤ማለትም ሰው ሰራሽ ነው። በኢትዮጵያና በሌሎች የጥቁር አፍሪካ አገሮች መካከል ያለውን የገቢ ልዩነት ከታች በሚታየው ሰንጠረዥ አቅርበናል። የአገሮችን ስም በትክክል ለማስቀመጥ ስለፈለግን እንግሊዝኛ ተጠቅመናል። ከዚህ ሰንጠረዥ ጋር አብሮ መታየት ያለበት የኢትዮጲያ የአገዛዝና የኪራስ ሰብሳቢነት ተደጋጋፊ ወይንም የተቆላለፈ ስርዓት ነው። በእኛ ጥናትና ግምት የህወሓት አገዛዝ የተቆላለፍና የተደጋገፈ ባይሆን በቀላሉ ይወድቃል።

<u>የመካከለኛ ገቢና ወደ መካከለኛ ገቢ የሚጓዙ የጥቁር አፍሪአክ አገሮች የነፍሥ ወከፍ ገቢ (2014) በሚቀጥለው ገጽ አቅርበናል።</u>


ማስረጃው የሚያመለክተው ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ከፍተኛ እርዳታ የሚለግሷት ኢትዮጵያ በማንኛውም መስፈርት ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር ለመወዳደር አልቻለችም። አስገራሚው ክስተት በነፍስ ወከፍ ግቢዝቅተኛ፤ በስደተኞች ከፍተኛ በሆነችው ኢትዮጵያ The Guardian, የተባለው የእንግሊዝ ጋዜጣ April 28, 2014 ባወጣው ዘገባ ኢትዮጵያ የአዲስ ሚሊየኒሮች አገር መሆኗን ገልጿል። ቁጥራቸው በሚያስደንቅ ሁኔታ በ2007 1,300 የነበረው በ2013 ወደ 2,700 ጨምሯል፤ ከእጥፍ በላይ። በዚሁ ወቅት የደሃው ሕዝብና አገሩን ለቆ የሚወጣው ወጣት ቁጥር ጨምሯል። ኢትዮጵያ የግል ትርፍ በቀላሉ ከሚገኝባቸው አገሮች መካከል ከፍተኛ ደረጃ ይዛለች። ሰርቶና አምርቶ ሚሊየኔር መሆን አግባብ አለው፤ ግልፅነትና ውድድር በሌለባት ኢትዮጵያ ሚሊየኔር ለመሆን የሚችሉ እንደማን እንደሆኑ አቅርበናል። ከዚህ በታች ያለው ሰንጠረዥ የሚያሳየው በሰብአዊ ልማት፤ በተለይ ደሃነትንና ስራ አጥነትን ለማጥፋት፤ የነፍስ ወከፍ ገቢን በፍጥነት ለማሳደግና ኢትዮጵያውያን የተሻለ ኑሮ ለመኖር እንዲችሉ ያልተቆጠበ ጥረት በማድረግ መስፈርቶች ኢትዮጵያ አሁንም ኋላ ቀር ሆና እናያለን።




The rest of SSA falls below $480. Niger, Ethiopia and Malawi at bottom.

**አዲስ ባለጠጋዎች እንዴት ገቢያቸውን፤ ሃብታቸውንና ኑሯቸውን አሻሻሉ ለሚለው ቁልፍ ጥያቄ የአገዛዙን የተቆላላፊ አቀራረጽና ተደጋጋፊነት በሚከተለው ሰንጠረዥ እናሳያለን። ጠባብ ጎሰኝነትን የአገዛዝ ስልት አድርገው የያዙት የመንግሥት ባለስልጣናትና ከእነሱ ጋር የተቆራኙ ታማኝ ግለሰቦች ተደጋጋፊ የጥቅም እትብት መስርተዋል። በፓርቲው፤ በሕግ አውጪና በሕግ አስፈጻሚው፤ በፍርድ ቤቱ፤ በፀጥታና በመከላከያ የተያያዘና ተደጋጋፊ የጥቅም ግንኙነት አለ። መንግሥትና ገዢው ፓርቲ እጇና ጓንቲ ናቸው። ነጻ የሆነ የመንግሥት ተቋም የለም። ይኼ ትሥስር ለድርጅታዊ ምዝበራ አመቻችና ስኬታማ አድራጊ ነው።**


የህወሓት የተቆላለፍና የአዙሪኝ አገዛዝ ስልት




ለማስመር የምፈልገው ነጥብ፤ አፋኝና ራሱን አገልጋይ ሌላውን አፋኝ የሆነ አገዛዝ፤ ቁንጽል የሆነ የነፍስ ወከፍ ገቢ ይወልዳል ነው። የተዛባ የገቢና የሃብት ስርጭት ፈጥሯል። አደገኛ ሁኔታን ወልዷል። ለፈጣንና ፍትሃዊ እድገት ስኬታማነት ተሳትፎ፤ የሕግ የበላይነት፤ ውድድር፤ ግልጽነት፤ አብሮ መኖርና ዲሞክራሳዊ ስርአት፤ ለተፈጥሮ ሃብት ተቆርቋሪነት የሚያስፈልጉ ለመሆኑ የጠቀስኳቸው የአፍሪካ አገሮች ጥሩ አርአያ ናቸው። ቢያንስ የሕዝባቸውን ኑሮ ለማሻሻል እየጣሩ ነው። በአብዛኛዎቹ የምግብ ዋስትና አለ። የአሜሪካ መንግስት፤ ዋናው ለጋስ፤ ከዚህ ከዲሞክራሲ ስርአት የሚገኙ ጥቅሞችን ያውቃል። ከእያንዳንዳችን በላይ ኢትዮጵያን፤ ያላትን የተፈጥሮ ሃብት፤ ታሪኳን፤ የህብረተሰቧን ጥንካሬ፤ ያንዣበባትን አደጋ ሁሉ ያውቃል። የሃጊ ዕርሊቹን መጽሃፍ የአሜርካ ወሳኝ ግለሰቦች እንደሚያውቁት አልጠራጠርም። በጸረ-ሸብርተኛነት አመካኝቶ የግለሰቦችን መብት ሙሉ በሙሉ የሚያፍን፤ የአገርን አንጡራ ሃብት የሚያባክን፤ የግል ውድድርን የሚከለክል ዘራፊ አገዛዝ "እድገታዊ" ነው ለማለት አይቻልም። በሰንጠረዡ እንዳሳየነው፤ የተዛባ የገቢ፤ የኑሮና የሃብት ስርጭት፤ አፈና ወዘተ መፈራረስን ይወልዳል።

ለሁሉም ህብረተሰብ ክፍሎፍች አገልጋይና ተገዢ ያልሆነ መንግሥት ዙሮ ዙሮ ውድቀትን ያመጣል። ሰፊ ጥናት ያደረጉ ተቋሞች የሚሉትን ወስደን ስናይ ኢትዮጵያ ወደ ወዳቂነት እያመራች ነው። ይኼን በሚከተለው ሰንጠረዥ እናሳያለን።

አፈናና የኢትዮጵያ የምርኩዝ ጉዞ (Failed and failing states: a worldwide picture)




ለውድቀት መጋቢ ክስተቶችና ምሳሌዎች

የሰብአዊ መብቶች መታፈን፤

የተፈጥሮ ሃብት፤ በተለይ የለም መሬት ሺሚያ፤ ጉቦና ሙስና፤

የጎሳዊ ይገባኛልነት ግብግብና የብሄራዊ አመለካከት መናድ፤

ጎሳዊ አድልዎ፤ የስራ እድሎች ፖለቲካዊና ጎሳዊ መሆን፤

የአገር ሃብት መባከን፤

የገቢ፤ ሃብትና ኑሮ መዛባት፤ የኑሮ ውድነት፤

የሕግ የበላይነት አለመኖር፤

ፍላጎት ከአቅርቦት ጋር አለመጣጣም፤

ገበሬው “ገባር” ሆኖ የምግብ ዋስትና እንዴት ይታሰባል?

ከጅምሩ ህወሓት ራሷን ያጠናእከረው በመዝረፍና በማታለል ነው። አባካኝና አድካሚ መሆኑን በጣና በለስ ምሳሌ አሳይተናል። ሲያባከን ወነጀል ይፈጽማል። የሆስፒታል ማሳሪያዎች ከጣና በለስ አወላልቆ ወደ ሌላ ቦታ ሲወስድ እናቶች በወሊድ ሞተዋል፤ ህፅናታ ህክምና በማጣት ሞተዋል። ገበሬዎች በመስኖ የሚተዳደር መሬት አጥተዋል ወዘተ። ወንጀሉ ማህበራዊ ነው። የህዝብ ቁጥር እያደገ ሲሄድ የእርሻና ሌላ መሬት አጠቃቀም አግባብና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ መቀየስ ይኖርበታል። የጣና በለስን ተንከባክቦና አስፍቶ በመያዝ ፋንታ ማፍረሱ ከኢትዮጵያ ፍላጎትና ምኞት ጋር አብረው አይሄዱም። አገዛዙ ሁሉን አስተናጋጅ ካልሆነ ውጤቱ ግጭትን ደሃነት ይሆናል። በምርኩዝ የተደገፉ ወይን የወደቁ አገሮች ስርዓታዊ በደልና ችግር ያለባቸው ናቸው። በስልጣን ክፍፍል፤ በተፈጥሮ ሃብት ፍትሃዊነት ክፍተት፤ በኑሮ ውድነት፤ በስራ አጥነት፤ በገቢ ልዩነት ወዘተ የተበከሉ አገሮች ይወድቃሉ፤ ያልወደቁት በምርኩዝ ያዘግማሉ። መፍትሄ ካልተገኘ እንደ ሶማሊያ ይወድቃሉ። በማንኛውም መስፈርት ብናየው የእርስ በእርስ ግጭት ወደ ውድቀት ማምራቱ የጊዜ ጉዳይ ነው። ኑሮው ያልተበከለ ሕዝብ ግጭት አይፈልግም፤ በልቶ ማደረ ወሳኝ ሚና አለው። አብዛኛው የአፍሪካ ሕዝብ ኑሮውን የሚያሟላው በእርሻ ስራ ነው። የመሬት ባለቤትነት ዋስትና ወሳኝ ሚና ይጫወታል። የግብርና ኢኮኖሚ ዘመናዊይነት፤ የግለሰብን፤ የህብርተሰብን፤ የአገርን ህይወትና እድገት ለዋጭ ሊሆን ይችላል። በቻይና፤ በህንድ፤ በቬትናም፤ በብራዚል፤ ወዘተ አይተነዋል። የማንኛውም አገር እድገት የተለያየ ቢሆንም፤ በአብዛኛው፤ ቁልፉ፤ ለአምራቾች የመሬት ዋስትና መስጠት፤ የግል ንብረታቸው የህግ እውቅና እንዲያገኝ ማድረግ፤ እንዲጎለምሱ ያልተቆጠበ ድጋፍ ማቅረብ ነው። ከሁሉም በላይ፤ የባለቤትነት ዋስትና ለእድገት ቁልፍ ነው። ቻይናዎችና ህንዶች ያደረጉት ምሳሌ ነው። በራሱ ሕዝብ ስልጣን የሚነግድ መንግሥት የምግብ ዋስትና ተቀዳሚነትን ብሄራዊ ትኩረት አይሰጥም፤ ጣና በለስን ያፈርሳል፤ አጇኮችን ከቀያቸው ያባርራል።

ኮፊ አናን፤ ስለመሬት ነጠቃ (Land grab) አስተያየት ሲሰጥ፤ “የአፍሪካ መንግስታት፤ አዲስ የቅኝ አገዛዝ በልዩ መልክ ተመለሶ አፍሪካ እንዳይገባ መታገል አለባቸው፤ የመጀመሪያ ሃላፊነታቸው፤ ለዝቅተኛ አምራቾች (Smallholders) ግብዓቶችን በመለገስ፤ ለህብረተሰባቸው የምግብ ዋስትና ማስገኘት ነው” ያለው ለኢትዮጵያ ሁኔታ ተገቢ ነው። ፕሬዘደንት ኦባማ፤ መለስ ዜናዊይን፤ በ2012 ለታላቅ ስብሰባ የጋበዘበትን ምክንያት ከሌላው ጊዜ ለየት የሚያደርገው አቢይ ጉዳይ <u>የምግብ ዋስትና (food security)</u> ውይይት፤ መሆኑ ነው። ችግሩ፤ አርእስቱ አይደለም። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስለ ምግብ ዋስትና ኢትዮጵያን ለመወከል፤ በእየቀኑ ለሚራቡት፤ በኑሮ ውድነትና የምግብ ዋጋ ግሽበት ለሚሰቃዩት ድምጽ ለመስጠት የሞራል ብቃት የለውም ነበር የሚለው ነው። የመራው መንግሥት፤ በሃያ አንድ አመታት አገዛዝ ያሳየው ተግባር ደሃውን ሕዝብ፤ ከድህነት ሰቆቃ ነጻ በማውጣት ፋንታ፤ በስለላ ሰንሰለት፤ ለቁጥጥር አደራጅቶታል። ነጻነቱን ገፎ ከድህነት ነጻ አወጣሃለሁ የሚል መሪ በሕዝብ ሙብቶች የሚቀልድ ነው። የዚህን አደጋ ከላይ አሳይቻለሁ። አፍኖ ማጎልመስ የሚል የእድገት መንገድ የለም። ስርአቱ የተዋቀረው ደሃውን ለማጎልመስ አይደለም።

ህወሓት በግምገማና በማጎልመስ ያምናል፤ ስልጣኑን ለማጠናከርና አስተማማኝ ለማድረግ። በኛ ግንዛቤና በሌሎች አገሮች ልምድ ማጎልመስ (Capacity development and empowerment) ከነጻነት፤ ከመድብለ ፓርቲ ውድድር፤ ከባለቤትነት፤ ከተወዳዳሪ ኢኮኖሚ አመራር ጋር አብሮ የሚሄድ ነው። ፕሬዚደንት ኦባማ በወጣቶች እንደሚያምን አውቃለሁ። ሲወዳደር የደገፍኩበት ዋና ምክንያትም ለዚህ ነው። ሆኖም፤ መለስ ያነጸውና የመራው መንግስት፤ ለወጣቱ ትውልድ በአገሩ ጥሩ እድል ሊከፍትለት አልቻለም። ለስደት ዳርጎታል። <u>ትምህርት የእድል ቤት ከፋች መሆኑ የታወቀ ነው። ለእድገት አስፈላጊ መሆኑ አያከራክርም። ሆኖም፤ ትምህርት ወደ ስራ ካላሸጋገረ፤ ብቃት ካላሳየ፤ ጥራት ከሌለው በፍጥነት ካደጉ አገሮች ጋር ለመወዳደር አይቻልም። ውጤቱ፤ ተምሮ መሰደድ ይሆናል።  ከላይ ከጠቀስኳቸው ከሶስቱ አበይት ችግሮች አንጻር እንየው፤ የህወሓት ትምህርት ወጣቱን ትውልድ ለስደት</u> እየዳረገው ነው። ከሁሉ በላይ፤ የሚሰቃዩት የኢትዮጵያ ወጣት ሴቶች ናቸው። ሳውዲ አረቢያ እንደ ሸቀጥ የሚላኩት፤ ተዋርደው በጅምላ ወደ ሃገራቸው የሚላኩበት ዋና ምክንያት በሃግራቸው እድል ስለሌላቸው ነው። በኢትዮጵያ፤ ድህነት በወለደው በሴት አዳሪነት የሚኖሩት፤ ገና በአስራ አራትና በአስራ አምስት አመት እድሚያቸው ለውርደት፤ ለተስቦ በሽታ የሚዳረጉት፤ በድህነታቸው ነው። ያለውን አሰቃቂ ሁኔታ በቅርብ ለማየት፤ Half the Sky፤ የተባለውን የምርምር መጽሃፍ ማንበብ ብቻ ይበቃል። <u>የህወሓት አመራር የሚሰራው ለራሱ የፖለቲካ ስልጣንና የኢኮኖሚ፤ በተለይ የገንዘብ ጥቅም የበላይነት እንጂ ለኢትዮጵያ ሴቶችና ወጣቶች ደህንነት ደንታ የለውም። ከዚህ የምንደመድመው ህወሓት ቀጭ ስርዓት ፈጥሮ</u>

የተቀጣና “የተረገመ” የሚመስል ትውልድ አምርቷል። ህወሓት ወጣቱን ትውልድ ሺባ ለማድረግ በሃገሩ ጉዳይ ላይ ከመነጋገር ፋንታ የእንግሊዞችን ፉትቦል ማየት፤ የአረቦችን ሺሻ ማዘውተር፤ሽሙጥን እንደ ቁምን ነገር መቀበል፤ የትምሕርት ውጤትና ዲግሪ በማጭበርበርና በገንዘብ ሲገዛ እንደ ተራ ነገር መቀበልን እንዲመርጥ አሳምኖታል። ሆን ተብሎ ወጣቱን ትውልድ ሺባ ለማድረግ የሚደረግ ዘዴ።

የወጣቱ ትውልድ ‘ዋጋ ቢስነት’ የስርአቱ ነጸብራቅ ነው

የህወሓት አመራር ለሰው ልጅ ክቡርነት ዋጋ የሰጠበት ጊዜ ለማግኘት አልቻልኩም። ሰውን የሚያየው እንደ እንስሳ፤ እንደ ሸቀጥ ነው ለማለት ይቻላል። የወጣቱ ትውልድ ህይወት፤ ልክ ዋጋ እንደሌለው እንደ ጤዛ እየረገፈ ነው። የደርግ መንግሥት ወጣቱን እርስ በእርሱ እንዲናከስ፤ እንዲገዳደልና እንዲገደል አደረገ። ግራ ክንፉም ግራ ተጋብቶ እርስ በእርሱ እልቂት አካሄደ። ህወሓት ፈለጉን ተከትሎ የመናገር፤ የማሰብ፤ የመንቀሳቀስ፤ እንደልብ ሃብት፤ ጥሪት የመያዝ መንገዶች ዘጋበት። ማንም ኢትዮጵያዊ ለሙብቱ ሲነሳ እያሰሩት፤ እያሳደዱት ነው። ፕሬዝደንት ኦባማ የቁጥጥር መንግስት የአምባገነነት መለኪያ መሆኑን ያውቃል። የደህንነት ተቋሙ የሚከታተለው ይህን ነው። የኢትዮጵያን አምባገነን መንግሥት፤ ከግብጽ፤ ከሊቢያ፤ ከየመን፤ ከቱኒሲያ፤ ከሶሪያ፤ ከዝምባብዌ፤ ከበርማ የሚለይ መለኪያ ሊኖር አይችልም። የኢትዮጵያ ወጣት ትውልድ ህይወት እንደሌላው ዋጋ አለው። እንደሌላው ክቡር ነው። በህወሓት የሚካሄደው  የጭካኔ፤ የመለየት፤ የአድልዎ፤ የጎሰኛነት መጠን፤ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን፤ ለአፍሪካ ቀንድ አደጋ እንደሚያመጣ የአሜሪካ ተቋሞች አስምረውበታል። የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት በእያመቱ ያወጣው ዘገባ፤ መለስ ዜናዊ ይመራው የነበረው መንግሥት የበላይ ባለስልጣናት፤ በዓለም ፍርድ ቤት፤ እንደ ላይብሪያው ታይሎር፤ እንደ ሱዳኑ ባሽር፤ እንደ ግብጹ ሙባረክ (በቅርቡ የእድሜ-ልክ እስራት በሃገሩ የተፈረደበት) ወዘተ፤ ለማቅረብ የሚያስችሉ “ወንጀሎች” እንዳሉ ያውቃሉ። መለስ በህይወት በነበረበት የአምባገነንነት ዘመን፤ የህወሓት/ኢህአዴግ ባለስልጣናት በሰላማዊ ሕዝብ ላይ፤ በተከታታይ ወንጀል የፈጸሙ መሆናቸውንና ተጠያቂነት እንዳለባቸው አያጠራጥርም። በምእራፍ ሶስት እንዳሳየነው፤ ወንጀል አልፈጸምኩም ለማለት አይችሉም። ከጀርባ ትእዛዝ በመስጠት፤ የህወሓት የበላይ አዛዦች፤ በግልም ሆነ በቡድን ያልገቡበት ወንጀል፤ ትእዛዝ ያልሰጡበት አቢይ ውሳኔ ከስራ ላይ እንደማይውል ፕሬዘደንት ኦባማ ያውቃል። እነዚህን የወንጀል መሰረቶችና ማስረጃዎች በበለጠ ለማጠናከር ምሳሌዎች በመስጠት ወደ ዋናው የምግብ ዋስትና ትንተና እገባለሁ።

በከተማ ሆነ በገጠር፤ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም፤ የፖለቲካ መሳሪያ ሆኗል። የመሬት ስሪት፤ ዋና የጉቦ፤ የአድልዎ፤ የሙስና ምንጭ ነው። አብዛኛው በአገር ውስጥ የሚካሄደው አድልዎ፤ ጉቦና ሙስና በቀጥታ ከተፈጥሮ ሃብት ጋር የተያያዘ ነው። በተለይ፤ ከመሬትና በመሬት ሥር ከሚገኙ ሃብቶች ጋር። ልክ ዱሮ በሌሎች የአፍሪካ፤ የላቲን አሜሪካና ካሪብያን አገሮች ይደረግ እንደነበረው፤ አሁንም በአንዳንድ አገሮች እንደሚሆነው። የምዝበራና የኪራይ ፈላጊነትና ሰብሳቢነትን ባህል፤ ጥቅምና ተግባር ከተፈጥሮ ሃብት አስተዳደር ጋር ተያይዟል። ህወሓት የሚመራው መንግሥት፤ ለራሱ የሞራል የበላይነት ለመስጠት፤ ከገዢው ፓርቲ ውጭ፤ ሌላውን “ኪራይ ፈላጊና ሰብሳቢ ነው” ብሎ  ወንጅሏል። ይህ፤ የጠባብ ጎሰኛ አመራር የሚጠቀምበት ዘዴ ነው። ጠቅላይ ሚንስትር መለስ ሃያ አንድ አመታት የመራው፤ የአንድ አናሳ፤ ጠባብ ጎሰኛ ቡድን መንግሥት በእርሻ-ላይ የተመሰረተ የኢንዱስትሪ ልማት የአብዛኛውን የደሃ ሕዝብ ኑሮ አላሻሻለም። ድርጅታዊ አቅሙን አገር አቀፍ በሆነ መንገድ አስፋፍቷል። ከመንግሥት ባጀት ፈሰስ እያደረገ፤ ስድስት ሚሊዮን አባላት ሰብስቧል። እነዚህ አባላት ፓርቲውን እንዲደግፉ ድጎማ ያደርጋል። በስለላ ሰንሰለት ይቆጣጠራል። የአሜሪካ መንግስት ይህን ሙሰኛ የሆነ የፖለቲካ አመራር ታሪክ ያውቃል። ዓለም ባንክ በነበርኩበት ወቅት፤ አንድ የውስጥ ዘገባ ያየሁት፤ መንግሥት ከምርጫ ዘጠና ሰባት በኋላ፤ ባጀት ተጠቅሞ፤ የአባላትን ብዛት ወደ አራት ሚሊዮን መጨመሩን ነበር። ከዚያ ወዲህ ቁጥሩ ወደ ስድስት ሚሊዮን አድጓል። መለስ፤ እድገታዊ መንግሥት ብሎ የጠራው ስርአት፤ የፖለቲካ ሆነ የመዋእለንዋይ የበላይነትን ከያዘ መቆየቱን የአሜሪካ መንግስት ሰላይና አመራር ድርጅቶች ያውቃሉ። ጥቅማቸውን አገልጋይ ስለሆነ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮና ሙብት ደንታ የለም።

ሃብታም ለመሆን የፖለቲካ ስልጣን ያዝ፤ መረብ ፍጠር

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ፤ እንደ ሌላው አመራር በምስጢር የሚሰራ ነው። የገበያው ስርአት ግልጽነት የለውም፤ በህግ አይተዳደርም፤ ኮንትራቶች ዋና የሃብት ምንጮች ሆነዋል። የሚሰሩት አድሏዊ በሆነ መንገድ ነው፤ በኮንትሮባንድ የሚንቀሳቀሰው ዘርፍ በህግ ከሚንቀሳቀሰው ያላነሰ፤ አንዳድ የውስጥ ተመልካቾች እንደሚሉት፤ አመዛኝ የሆነ ነው። አምራችና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶችን፤ ከመንግስት ቁጥጥር ነጻ እናውጣ በሚል ዘይቤ (so-called Washington Consensus based privatization) ህወሓት ስልጣን ከያዘበት ጀምሮ እስካሁን፤ ቀስ በቀስ የአገር ንብረት የነበሩ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ድርጅቶችን ወደ ፓርቲውና ወደ ምርጥ ባለስልጣኖች፤ ቤተሰቦች፤ ታማኝ የትግራይ ተወላጆች፤ ሌሎች

ተባባሪዎች፤ እንደ አላሙዲ ላሉ የውጭ ተወካዮች አስተላልፏል ። (The biggest transfer of assets in Ethiopian history). በሚያስገርም ሁኔታ፤ ምንም በስማቸውና በስራቸው ጥረት ካፒታል የሌላቸው፤ “ምስኪን የነበሩ” ግለሰቦችና ፓርቲው የሚቆጣጠራቸው እንደ ኤፈርት ያሉ ድርጅቶች ነጥረው ሃብታም የሆኑበት ምስጢር ከዚህ የመነጨ ነው። የፖለቲካ ስልጣን ለግል ባለጠጋነት መሰብሰቢያና ማጠራቀሚያ ከሆነባቸው በእጅ ከሚቆጠሩ አገሮች መካከል፤ ኢትዮጵያ ከፍተኛ ደረጃ ይዛለች። ይህ የአገዛዝ ዘዴ፤ የኢሊቶች (ምርጦች) የበላይነት (Elite political and economic capture) ተብሎ ይጠራል። የህወሓት ባለስልጣኖች ይህን ታሪክ የመዘገበው ምዝበራና ዘረፋ የሚያካሂዱት በሚስት፤ በልጅ፤ በዘመድ፤ በወዳጅ፤ በድርጅት፤ በበጎ አድራጊ፤ በውጭ ኢንቬስተሮች ስም ነው። ሁለ ገብ ምዝበራ፤ ሁለ ገብ አደረጃጀት፤ መረብና አሰራር ያስፈልገዋል። ስፋቱንና ጥልቀቱን ለማጤን አገር ውስጥ የሚፈሰውን መዋእለንዋይ ብቻ ማየት አይበቃም። በዱባይ፤ በደቡብ አፍሪካ፤ በምእራብ አፍሪካ፤ በአሜሪካ፤ በደቡብ ሱዳን ወዘተ የሚፈሰው፤ የሚሸሸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሃብት ሰፊ ነው። ምርምርና ክትትል ይፈልጋል። ይህ ካፒታል በድብቅ የማዘዋወር ዘመቻ የሚደረገው በዘዴና በምስጢር ነው። በአጭሩ፤ የፖለቲካ የበላይነት፤ ስልጣንና ቁጥጥር ለኪራይ ሰብሳቢነትና ሳይሰራ ለሚገኝ ሃብታምነት አመችቷል። የመንግሥት የነበሩ አትራፊ የምርት፤ የአገልግሎት ድርጅቶች ለግለሰቦች፤ ለከፍተኛ ባለስልጣኖች፤ ለበጎ አድራጊው ኤፈርትና ለፓርቲው ሲተላለፉ (Transfer of real resources from Ethiopian society to TPLF core and supporters) ኪሳራውን የተሸከመው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። “እድገታዊ መንግሥት” ለሃገሪቱ መኪታና አገልጋይ ከሆነ የመንግሥት የሆኑ ድርጅቶችን ለግል ማስረከቡ አግባባ አልነበረውም። ገዢው ፓርቲና መንግሥት አሁን ከፍተኛውን የኢኮኖሚና የአገልግሎት ክፍል (ከአምሳ በመቶ በላይ የሚሆነውን የዘመናዊ ክፍል ማለታችን ነው) ከተቆጣጠረ የመንግሥት የሆኑ ድርጅቶችን “የግል” አድርጊያለሁ ሲል የገዢው ፓርቲ፤ የኤፎርትና የመንግሥት አድርጊያለሁ ማለቱ ነው። በግል ስም ሆነ ብግል ትርፉን የሚያገኙት የህወሓት ባለስልጣኖች፤ ታማኝ ግለሰቦች፤ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች፤ የውጭ ኩባንያዎችና መንግስታት እንደሆኑ አያከራክርም።

አይን ያወጣ ጎሳዊ ዘረፋ

በ1990ዎቹ የተዘዋወረውን የባለጠጋነት (የሃብት) ስእል ትተን፤ በቅርቡ የተደረገውን ስናይ፤የምዝበራውን ቀጣይነት ያስምርልናል። ቀጣይነቱ ቁም ነገር ስላለው ህወሓት ስልጣን ከያዘበት ጀምሮ፤በ1990ወቹ አመታት-ዌቭስ በተባለው መጽሃፍ- ከኢትዮጵያ ታዛቢዎች ባገኘነው ማስረጃ እንዳሰየነው፤ ህወሓት ብቻ የተረከባቸው ዱሮ የመንግሥት የነበሩ ድርጅቶች ብዛት ሰማንያ ደርሶ ነበር። ባንኮች፤ አበዳሪ ድርጅቶች፤ የመንግስትና የግል አናጺ ተቋሞች (Construction companies) የእርሻ፤ የአግልግሎት ሰጭ፤ የአስመጭና ላኪ፤ የአማካሪ ኩባንያዎችና ሌሎች ያካትታል። ተጠቃሚዎቹ ፓርቲውና ባለስልጣናት ናቸው። ይህ በቀጥታ ከፖለቲካ ከስልጣን ጋር የተያያዘ ባለጠጋነት በይፋ ስር የሰደደው የህወሓት ስልጣን ከተረጋጋ በኋላ ነው። የዚህን አድሏዊ ተጠቃሚዎች እንደገና በማስረጃ እናቀርበዋለን። በ1995 ብቻ ከሃያ ሚሊዮን ብር በታች ካፒታል አላቸው የተባሉ በትግራይ ተወላጆች የተቋቋሙ ድርጅቶች ብዛት አስራ አንድ ነው። ሰላም፤ ሰገል፤ ሜጋ፤ ብርሃን ወዘተ። በዚሁ አመት ካፒታላቸው ከሃያ እስከ አምሳ ሚሊዮን ብር የተገመተ አስራ አንድ ተቋቁመዋል። ሼባ፤ አዲስ መሃንዲስ፤ በርሄ ኬሚካል፤ ሂወት እርሻ ወዘተ። በወቅቱ፤ ከአምሳ ሚሊዮን ብር በላይ ካፒታል ያላቸው አስር በትግራይ ተወላጆች ባለቤትነት ተቋቋሙ። መስፍን ኢንዱስትሪ፤ መሶብ ሲሚንቶ፤ ደበቢት ቁጠባና አበዳሪ፤ ጣና ንግድ፤ አለሜዳ ጨርቃ-ጨርቅ፤ አዲስ ፋርማሲ ወዘተ። ሌሎች የትግራይ ተወላጆች ባለቤትነት ያላቸው ካፒታላቸው ከስድሳ እስከ ብዙ መቶ ሚሊዮን ብር የሆነ ኩባንያዎች አለሜዳ፤ ሱር፤ ዳሽን፤ መሶብ፤ወጋገን ባንክ፤ ዘለቀ ፋብሪካ፤ ጉና ንግድ፤ ብሩህ፤ አፍሪካ ኢንሹራንስ፤ ሂዮት ኮንስትራክሽን፤ መስከረም ኢንቬስትሜንት፤ ሜሳ ኮርፖሬሽን፤ አለሜዳ ማኑፋክቸሪንግ፤ ትራንስ-ኢትዮጵያ፤ ዳሽን መጠጥ ፋብሪካ ወዘተ። ዋና መስሪያ ቤታቸው ትግራይ ክልል የሆኑ--አምባሰል ንግድ፤ ዳሽን ቢራ፤ አማራ መልሶ ማቋቋም፤ ሳባ፤ አድዋ የዱቄት ፋብሪካ፤ ሰብሃት ነጋ የግል ድርጅት፤ ዲማ ማር፤ አብደሌ የእንስሳ ኤክስፖርት ወዘተ ተቋቁመዋል። በወቅቱ፤ እነዚህ በዝቅተኛ ግምት ከባዶ ውይንም ዜሮ ካፒታል ተነስተው ወደ አራት ቢሊዮን ብር ካፒታል ነበራቸው። አንባቢው መገንዘብ ያለበት፤ ይህ ካፒታል ከዚያ ወዲህ ሊያመጣ የሚችለውን የባለጠጋነት ደረጃ ማጤን ነው። የኤፈርት አምሳ ቢሊዮን ከደረሰ የሌሎቹ አምስት፤ ስድስት፤ አስር እጂ ቢያድግ አያስገርምም። ህወሓት፤ በተለይ መለስ ዜናዊ የመራው መንግስት ለፓርቲውና ለጥቂት የትግራይ ተወላጆች በህልማቸው አስበውት የማያውቁትን የገቢና የባለጠጋነት የበላይነት አበርክቶላቸዋል። ዝቅተኛ ገቢ ያለው፤ ከባለስልጣናት ጋር ቀጥተኛ ቁርኝት የሌለው ኢትዮጵያዊ ከእነዚህ ጋር ለመወዳደር አይችልም። በአሁኑ ወቅት አንድ ግለሰብ የራሱን ኩባንያ ለማቋቋም ቢፈልግ በሚሊዮን እንጅ በመቶ፤ በሁለት መቶ ሺህ ወዘተ ለማሰብ አይችልም። ለጉቦም አይበቃም። ሰዎች ስለግል ኩባንያ ሲነጋገሩ ቃላቱ ተለውጧል። ስንት ሚሊዮን ብር አለህ እንጅ፤ ስንት ሽህ ብር አለህ የሚል የለም። ደሃ በሆነ አገር እንደዚህ ያለ የዋጋ ግሽበትና የብር ዋጋቢስነት በጣም ይጎዳል። ይህ ከፖለቲካ ስልጣን የመነጨ ምዝበራ ሌላውን ኢትዮጵያዊ እንደጎዳው ለማየት አይቸግርም።

ይህ ከፖለቲካ የበላይነት ጋር የተያያዘ ባለጠጋነት አላቆመም። በቅርቡ የተደረገውን የጥሪት ሽግግር (Transfer of real assets) ለማሳየት የፈለግንበት ስርአቱ አለመለወጡን ለማጠናከር ነው።

የምዝበራ ናሙና

1. የጣይቱ ሆቴል፤ ያለ ምንም ወጭ፤ ከሕዝብ ሃብተነት ወደ ምርጥ/ታማኝ ግለሰብ ተሸጋገሯል።

2. የጉለሌ የሳሙና ፋብሪካ፤ ከመንግስት ባንክ ሃያ ሚሊዮን ብር ብድር በመውሰድ፤ ፋብሪካው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ወደ ግለሰብ ተሸጋግሯል። ይህ ፋብሪካ በአመት ሃያ ሚሊዮን ብር ትርፍ ያስገኝ ነበር። ትርፍ የሚያስገኝ ተቋም ለግል ተጠቃሚ ለምን እንደተሰጠ ምስጢር ሊሆን አይችልም። ሃብትን ለማሸጋገር ነው። የህወሓት አርአያ የሆነችው ቻይና ይህን አላደረገችም።

3. የጉለሌ ልብስ ስፌት ፋብሪካ–አስራ ሰባት ሺህ ካሬሜትር - በአንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ብር ተመን ለታማኝ ግለሰብ ተሸጧል። ከኢትዮጵያ ሕዝብ ወደ ህወሓት ባለስልጣናት ደጋፊ ግለሰብ ያለ ውድድር ተዘዋውሯል። በ1990ዎቹ የተደረገውን የጅምላ (Wholesale) የሃብት ዝውውር ይመስላል።

4. ታሪክ ያለው፤ የባህር ዳር ጊዮን ሆቴል፤ ለአንድ የህወሓት ደጋፊ፤ ታማኝ ግለሰብ ተዘዋውሯል።

5. የጎንደር ጎሃ ሆቴል፤ በሳንቲም ሂሳብ፤ ለአንድ በውጭ ለጥቂት ወራት ለቆየ የትግራይ ተወላጅ ግለሰብ፤ ካፒታል ለሌለው ታማኝ፤ እንደ ስጦታ ተዘዋውሯል። ሌሎች እንዲወዳደሩ አልተጋበዙም።

6. በቻይና ኢንቬስተሮች የተደገፉ፤ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች (ሞጆ) ፤ የጫማ ፋብሪካ፤ ሌሎች ከኢትዮጵያ ሕዝብ ሃብትነት ወደ ህወሓት ደጋፊዎች/ታማኞች ተዘዋውረዋል። ህወሓት ይህን ሲያደርግ፤ በመንግስትነት ስልጣኑን ተጠቅሞ፤ የሕዝብ ሃብት ወደ ግለሰብ ማዘዋወር ለእድገት ይጠቅማል በሚል ዘዴ ነው። ከቻይና ጋር ሊወዳደር አይችልም። ቻይና፤ በአብዛኛው፤ የሕዝብ ሃብት ለሕዝብ ጥቅም ትጠብቃለች። የግሉ ክፍል እንዲስፋፉ እያደረገች ነው። ህወሓት፤ በገበያ ውድድር ስም የግል የሃብት ክምችትን አጠናክሯል።

7. የደንበል ሕንጻ-የሚያወጣው በግምት ከሰባ እስከ ሰማኒያ ሚሊዮን ብር-ሲሆን ገዢው ፓርቲ ለደጋፊ ግለሰብ፤ ህንጻውን መያዣ አድርጎ (collateral) እንደ መንግሥት ካዝና ከሚቆጠር ባንክ ከሁለት መቶ አምሳ እስከ ሶስት መቶ አምሳ ሚሊዮን ብር አግኝቶ ባለቤትነቱን ይዟል። ወጭ ተደርጎ፤ ገንዘቡ የት እንደደረሰ አይታወቅም። ሁነኛ ግለሰቦች የነገሩኝ፤ ይህ ገንዘብ በጥቁር ገበያ ወደ ውጭ ምንዛሬ ተለውጦ ከአገር ወጥቷል። የጥቁር ገበያ የደመቀበት መርካቶ፤ በአሁኑ ወቅት በቀን ብዙ መቶ ሚሊዮን ብር ወደ ዶላር ይለወጥበታል። የተለወጠው አገር አይቀርም። ፋብሪካ አይሰራም፤ ዘመናዊ እርሻ አይሰራም። የካፒታል መሳሪያ አይገዛም። አብዛኛዎቹ ለዋጮች ገንዘብ በሚሊዮን ብቻ የሚቆጥሩ የህወሓት ባለስልጣናት፤ የቅርብ ቤተሰቦች፤ ወዳጆች፤ ታማኞች ናቸው። ሕጉ፤ ደንቡ አይመለከታቸውም። እነዚህ የሙስና፤ የስርቆት፤ የአድልዎ፤ የዘረፋ፤ የህገ ወጥነት ማስረጃ ናቸው።

8. ህንጻዎች፤ ቪላዎች፤ ኮንዶሚኒየሞች፤ የግል ቤቶች በአሜሪካ፤ በዱባይ ወዘተ መሰራታቸው፤ ዛሬ ከፍተኛ ባለስልጣናት፤ ታማኝ ግለሰቦች፤ የፓርቲው ሃላፊወች፤ ስልጣንና የረቀቀ ግንኙነት በመጠቀም፤ ኢምባሲዎችን ለግል አገልግሎት አውለዋል። በብዙ መቶ ሚሊዮን ዶላር የኪራይ መሰብሰቢያ፤ የማረፊያ፤ የልጅና የቤተሰብ፤ የወዳጅ መገልገያ የሆኑ ተቋሞች በእየቦታው እንዳሉ ይነገራል። ገንዘብ ካልሸሸ፤ እነዚህ ሃብቶች አይቋቋሙም፤ ገንዘብ ሲሸሽ የሚጎዳው ደሃውና የወደፊቱ ትውልድ ነው። በኢትዮጵያ አየር መንገድ የሚጓጓዘው የምግብ እና ሌላ እቃ በአመት ብዙ ሚሊዮን ዶላር ትርፍ እንደሚያስገኙ ይገመታል። የህጻናት ንግድ ለህወሓት መቶ ሚሊዮን ዶላር ገቢ እንደሚያስገኝ በውጭ ታዛቢዎች በማስረጃ ቀርቧል፤ በአብዛኛው፤ የሚነግዱትና ተጠቃሚዎቹ የህወሓት ባለስልጣናት፤ ታማኝ የሆኑ የትግራይ ተወላጆችና ደጋፊዎች ናቸው። እቃ ከቀረጥ ውጭ ለማጓጓዝ፤ ቤቶችን ሆነ ሌላ የቁሳቁስ ሃብት ለማቋቋም የፖለቲካ ስልጣን፤ ግንኙነት፤ ገንዘብ ቁልፍ ናቸው። ገንዘቡ የሚመጣው ከሰማይ አይደለም። በመጀመሪያዎቹ የህወሓት ስልጣን አመታት የተቋቋሙት የፓርቲውና የትግራይ ተወላጆች ኩባንያዎች ከውጭ በመጣ ወይንም ከቁጠባ ከተገኘ ካፒታል አይደለም። ከኢትዮጵያ ደሃ ሕዝብ፤ ከአገሪቱ ባንኮች የተገኘ ወዘተ ነው። ይህ እንዴት እንደሚሰራ በስፋትና በጥልቀት ለማሳየት የዚህ መጽሃፍ ሚና አይደለም። የኢትዮጵያ ባንኮች በፖለቲካ ውሳኔ አበድረዋል። ብር በጥቁር ገበያ እየተለወጠ ወደ ውጭ እንደሚጎርፍ የአደባባይ ምስጢር ነው። ስልቱ በሚስት፤ በልጅ፤ በቅርብ ዘመድ፤ በሰራተኛ፤ በወዳጅ፤በኤምባሲ ሰራተኞች፤ በፈረንጆች፤ በውጭ አገር ተወካይች አማካኝነት ከስራ ላይ ይውላል። የፖለቲካ ስልጣን

መያዝ፤ የፕሬስ ነጻነት ማገድ፤ የማህበረሰብና የፖለቲካ ድርጅቶችን ሽባ ማድረግ እስከዚህ ድረስ ለግል ባለጠጋነት ጠቃሚ ሆኗል።

ጠቅላይ ሚንስትር መለስ ሲናገር በመንግሥት ውስጥ “ሌቦች አሉ። እናውቃቸዋለን። ነገር ግን፤ ኪራይ ሰብሳቢዎች የህወሓት መሪዎች፤ ትግሬዎች፤ አይደሉም። እኔ ወይንም ባለቤቴ አይደለንም” ብሏል። እሱ ሊሆን፤ ላይሆን ይችላል። የማውቀው ማስረጃ የለኝም። ሆኖም፤ የስርአቱን ችግር ክህደቱ ሊሸፍነው አይችልም። አጼ ኃይለ ሥላሴ የወሎን ረሃብ የለም ሲሉ ያላጤኑት፤ እሳቸው ማለታቸው ሃቁን ሊሽረው አለመቻሉን ነበር። መለስ “የመንግሥት ሌቦች እንዳሉ” ካወቀ ፤ የፖሊቲካ ስልጣን ብልግና፤ ሙስና፤ ገንዘብ ማሸሽ የተያያዙ መሆናቸውን ያውቅ ነበር። አጼ ኃይለ ሥላሴን፤ መንግስቱ ሃይለማሪያምን ለፍትህና ለሃቅ አልተገዙም ካልን መለስ ከትችቱ ነጻ ሊሆን አይችልም። ከፍተኛውን የመንግሥት ስልጣን የያዙት የህወሓት አባላት ናቸው። ማን ሌባ እንደሆነ ያውቃሉ። ሕጉም፤ ፍርዱም። ፍርድ ቤቱም። ፈራጁም። እስር ቤቱም በመለስ እጂ ነበሩ። ለምን መንግሥት ሌቦችን ለፍርድ አያቀርብም ብለን መጠየቅ መብታችን ነው። እቅጩ፤ ከማንም በላይ የስልጣን ተጠቃሚው የህወሓት ከፍተኛ ባለስልጣናት። ቤተሰቦች። ከፍተኛ የጦር መኮንኖች። ታማኛ የትግራይ ተወላጆችና ሌሎች ግለሰቦች መሆናቸውን ተራው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያውቃል። በ1990ዎቹ የሕዝብ ኩባንያዎችን የግል ማድረግ ያስፈልጋል ተብሎ ዋናውን ጥቅም ያገኙት የትግራይ ተወላጆች ናቸው። ጠቅላይ ሚንስትሩም ዘዴውን ያውቅ እንደነበር አንጠራጠርም። ስብሃት ነጋ የራሱ ኩባንያ ሲያቋቁም ስልጣኑን ተጠቅሞ ነው። አለያ፤ ከየት ያመጣዋል። በወቅቱ፤ እነደ ጠቅላይ ሚንስትሩ፤ ይህን ማስረጃ የሚሰጡኝ ግለሰቦች የሚኖሩት ኢትዮጵያ ነው። ሁኔታው ሰለዘገነናቸው፤ ባይሆን ለታሪክ ይጻፍ በማለት በየጊዜው የሚሰጡኝ ማስረጃ ነው። ከላይ ስለስለላ መረብ የቀርበው ማስረጃ ከተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን የተገኘ ነው።

9. የከተማ ቦታና የገጠር ለም መሬት አሰረጫጨትን ስናይ፤ ኪራይ አልሰበሰብም የሚለው እድገታዊው ህወሓት ቢፈቅድም፤ ባይፈቅድም በምዝበራ ከሚታየው ደሙ ንጹህ ለመሆን አይችልም። ለዚህ ጥሩ ማስረጀው የከተማ ቦታና የለም መሬት ስርጭት/ቅርሚት፤ አስተዳደር ነው። መሬት የባለጠጋነት  ማከማቻ መሰረት ሆኗል። በቦሌ፤ በዱከም፤ በቡራዩ፤ በሰንዳፋ፤ በሱሉልታ፤ በናዝሬት፤ በደብረዘይትና በአዲስ አበባ ዙሪያ ያለውን የመሬት ስርጭት ማየት፤ ማን ምን ተጠቃሚ እንደሆነ በገሃድ ያመለክታል። በክልል ርእሰ-ከተማዎችም ያለው አጠቃቅም ይህን ይመስላል። ታላላቅ የፓርቲውና የመንግስት ባለስልጣናት፤ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች፤ ታማኝ የትግራይ ተወላጆች፤ የሹማምንት ሚስቶች፤ ከሶስት እስከ አስር ቁልፍ ቦታዎች ተመርተርው፤ የራሳቸው አድርገውታል። ታላላቅ ፎቆች ሰርተዋል። በዋሽንግተን የህወሓት አምባሳዶር የሆነው “የህንጻ ባለጸጋ ነው” የሚል ማስረጃ አንድ ግለሰብ በቅርቡ አሳይቶናል። አምባሳደሩም ሆነ ሌሎች ህንጻ በማስያዝ ከመንግሥት ባንኮች ብዙ ሚሊዮን ብር አግኝተዋል። ባለስልጣናት ህንጻ ሲሰሩ በራሳቸው ገንዘብ አይደለም። ከየት ያመጡታል። የትኛውን ፋብሪካ ሰርተው? ሃብታም የሆኑት የፖለቲካ ስልጣናቸውን ተጠቅመው ነው። ከሰባ እስከ ሰማኒያ ሚሊዮን ብር ለጀኔራሎች ታላላቅ ፎቆች መስሪያ፤ እስከ ዘጠና ሚሊዮን ብር የሚፈጀው የህንጻ መስሪያ ገንዘብ የሚገኘው ከመንግስት ባንኮች ነው። የመንግስት ባንኮችና ባጀት የፓርቲው ካዝና፤ የግል ጥቅም ማካበቻና መገልገያ የሆነባት አገር ኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን <u>አትቀርም። ቴሌ እንደ ላም ይታለባል። ባንኮችም ታልበዋል።</u> ስልጣንና የብድር ዋስትና (Political power as collateral)፤ የሃብት ክምችት የተቆላለፉ መሆናቸውን ይጠቁማል። የከፍተኛ ፎቆችና ህንጻዎች ባለቤቶች ተራ፤ ወይንም ከስልጣን ጋር ያልተቆራኙ ኢትዮጵያን አይደሉም። ሊሆኑ አይችልም። እነሱ ድምጽ፤ ስልጣን የላቸውም። የበይ ተመልካቾች ናቸው። ባጭሩ ሲታይ፤ የጎሰኛ የፖለቲካ ስልጣን፤ ፓርቲ፤ መንግሥትና ተቋሞች በደንብ ተሳስረዋል። በጥቅም ይደጋገፋሉ። አሁን ደግሞ ፖሊስ፤ መከላከያ፤ ደህንነት፤ ምዝበራ በዘመናዊ ክትትልና ስለላ ተቆላልፈዋል። የ<u>ሚዘገንን አፈና ተቋማዊ የሆነበት አንዱ ምክንያት ይኼው ነው።</u>

10. የኮንትሮባንድ ንግድ የሚስፋፋው በገበያው እምነት በሌለበት አገር ነው። የዚህ አይነት ንግድ ለትርፍና ለኪራይ ፈላጊዎች መሳሪያ ነው። በህግ የማይተዳደር ስርአት ከቁጥጥር መውጣቱን ያሳያል።  የሚያበሳጨው “የመንግስት ሰራዊት መኪናዎች የኮንትሮባንድ ንግድ ማንቀሳቅሻ” መሆናቸው ነው። አገራዊ አገልግሎት በመስጠት ፋንታ፤ የግል መክበሪያ መሳሪያ ሆነዋል። ማንም አይፈትሻቸውም። አይቆጣጠራቸውም። ኬላ እንደልብ ያልፋሉ። በብዙ መቶ ሚሊዮን ዶላር የሚታሰብ ሸቀጥ ከሕግ ውጭ ያዘዋውራሉ። ከአገር ያወጣሉ። “የጦር መሳሪያ ይነግዳሉ።” ትርፍ ለግል ያከማቻሉ። በአንጻሩ፤ በዚህ መለኪያ፤ በአምባገነኑ የደርግ ዘመን የጦር ሃይሉ፤ የዚህ አይነት የግል ሃብት መሳሪያ አልነበረውም። በዊስኪ ይከሰስ እንደሁ እንጂ፤ አብዛኛው የደርግ መንግሥት አባላት ብሙስና ሊከሰሱ አይችሉም። በህወሓት፤ መኮንኖች ስርአቱን ስለሚያገለግሉ መንግስት ሊቆጣጠራቸው አይችልም፤ ከህግ በላይና ውጭ ይሰራሉ ማለት ነው። ከፍተኛ የጦር፤ የስለላ፤ የፌደራል ፖሊስ ወዘተ መኮንኖች እንደ ሌላው የድርጅታዊ ምዝበራ አካል ናቸው።

የግብር (ቫት) አድሏዊነት

11. ብዙ ሰው የማያውቀው ህወሓት የቀረጥ ጫና እንደሚያደርግ ነው። የአገር ውስጥ ገቢን አስተዳደር ስንመለከት፤ ይህን ተቋም ሙሉ በሙሉ የሚመሩት የህወሓት ታማኝ የሆኑ የትግራይ ተወላጅ ባለስልጣናት ብቻ ናቸው። ግንኙነታቸው በቀጥታ ከፓርቲው፤ ከቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ባለቤት፤ ከስለላ ድርጅቱ ጋር ነበር። ሁኔታው ይለወጥ አይለወጥ ማስረጃ የለም። የኢኮኖሚ የበላይነትን ለመያዝ፤ የአገር ውስጥ ገቢን መቆጣጠር አስፈላጊ ነው። ትርፍ ይገኝበታል፤ የማይፈለግን ግለሰብ ለመቅጣት ያስችላል። ህወሓት ድርጅቱን አንደ አይን ብሌን ያየዋል። ለምን? አሸናፊውን ይመርጣል። መገለል ያለበትን በዘዴ ያባርራል። ይጎዳል። መድረሻ ያሳጣል። ያደከማል። የአመራሩን ዘዴ ብናይ፤ ጎጅነቱን እንረዳለን። አብዛኛው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዘመናዊ አይደለም። የሚሸከረከረው በዝቅተኛ ነጋዴዎች ነው። ሴቶች፤ አናቶች ይተዳደሩበታል። <u>ከአስራ- አምስት በመቶ በላይ ቀረጥ (Value added tax)</u> የሚደነገገው በእነዚህ ታታሪዎች ላይ ነው። አምባገነኑ የደቡብ ኮሪያ ፕሬዘደንት ፓርክ በገዛበት ወቅት አንስተኛ ድርጅቶችን ታላቅ እንዲሆኑ ድጋፍ ሰጥቶ ነበር። ትላንት አንስተኛ የነበሩት ሂውንዳይ፤ ሳምሱንግና ሌሎች ያለመንግስት እንክብካቤ ዛሬ ካሉበት ደረጃ አይደርሱም ነበር። ፕሬዘደንቱ አገር ወዳድ ስለነበረ ነው። ባንጻሩ፤ ህወሓት ለመጠጥ፤ ለቡና፤ ለሻይ፤ ለዳቦ፤ የሚከፈለውን ቫት ስናይ ጎጅነቱን ለመረዳት ይቻላል። ማነጻጸር የሚገባን፤ የህወሓትና ታማኞች ጥሪት፤ ከቀረጥ ነጻ የሆኑትን፤ እንደ ኤፈርትና ጉና፤ በኮንትሮባንድ የሚሰሩትን የመከላከያና የስለላ ድርጅቶች፤ በህግ ያልታወቁ፤ ከቀረጥ ውጭ የሆኑ ሌሎች ድርጅቶችን ነው። ቀረጥ የቅጣት መሳሪያ ሆኗል የሚሉ ብዙ ናቸው። የህወሓት ድርጅቶች ባት የማይከፍሉበት ምክንያት ለምንድን ነው ብሎ ለመጠየቅ የማይችለው የግሉ ህብረተሰብ፤ “ወይ ጉድ” እያለ ሁኔታውን ተቀብሎታል። የህወሓት ምርጥ ድርጅቶች ቀረጥ እንዳይከፍሉ የተደረገው ከስርአቱ ጋር የጥቅም ግንኙነት ስላላቸው ብቻ ነው። በሕግ አይገዙም።

በአገር አቀፍ ደረጃ ሲታይ፤ ዋና ዋናው የንግድ ስራ በሙሉ ለፖለቲካ ባለስልጣናትና፤ ታማኞች ተዳርጓል። ዝቅተኛ ነጋዴዎች ከፍተኛ ግብር እንዲከፍሉ ይገደዳሉ። አቅማቸው ስለማይፈቅድ፤ ቀስ፤ በቀስ ስራቸውን ይዘጋሉ። ሃብት ያላቸው፤ አገር ወዳድ የሆኑ ሲብስባቸው አገር ለቀው ይወጣሉ። ከቻሉ፤ ገንዘብ ያሸሻሉ። የህወሓት ዋና አላማ የፖለቲካ ስልጣኑን ተጠቅሞ የንግዱን፤ ቁልፍ የማምረቻና የማከፋፈያ ክፍል፤ ባንክ፤ መገናኛ፤ ማጓጓዣ ሙሉ በሙሉ፤ የህወሓት የበላይ ባልሰልጣናት፤ ታማኝ የትግራይ ተወላጆች፤ ተባባሪ የሆኑ፤ የውጭ ባለሃብቶች እንዲይዙት ማድረግ ነው። ይህ ሁሉ አፈና በሃቅና በትጋት የሚሰራው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሃብት የበላይነት እንዳይኖረውና  አንዳይወዳደር ለማድረግ ነው። የበላይነት ከተረጋገጠ ህወሓት በተከታታይ ለብዙ አመታት ወይንም ከትውልድ- ትውልድ ለመግዛት ይችላል፡፡ ይህ፤ በምዝበራ ላይ የተመሰረተ እቅድ፤ ትርፍን፤ ሃብትን እንደሚያስገኝ አንጠራጠርም። ሰላምን አይፈጥርም። ችግሩ፤ የጠባብ ጎሰኛ የፖለቲካ አመራ፤ የመስራት፤ ሃብት የመያዝ፤ የመንቀሳቀስ፤ የተፈጥሮ ሃብት ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የማግኘት እድል ከሌለ ዘላቂነትና በእኩልነት የተመሰረተ እድገት ሊኖር አይችልም። ባለጠጋዎች፤ የዛሬ ተጠቃሚዎች የነገ ኢላማዎች ሊሆኑ ይችላሉ። የጠባብ ጎሰኛ ኢኮኖሚው እንደ ቦትስዋና ሊሆን አይችልም።

12. የለም መሬት አያያዝ፤ የዘመናዊ ግብርናውን ክፍል እንደ ሌላው፤ ህወሓትና ታማኞች በኢትዮጵያውያን ስም እየተቀራማቱት ነው። ለውጭ አገር ታዛቢዎች የሚሉት፤ አብዛኛውን ለም መሬት ጠፍ ነው። የተመሩት ኢትዮጵያዊያን ናቸው ነው፡፡ ይህ ከእውነቱ የራቀ መሆኑን፤ (Oakland Institute, Human Rights Watch, the Guardian, Survival International, Desalegn Rahamato, etc)፤ ማስረጃ አቅርበውበታል። ለውስጥ ኢንቬስተሮች ተሰጠ የሚባለው እርግጥ ነው። ሆኖም፤ ሰባ አምስት በመቶው ለምርጥ የትግራይ ተወላጆች፤ ለከፍተኛ የጦር መኮንኖች፤ ለፓርቲው ከፍተኛ ሃላፊዎች የተሰጠውን ነው። በግልጽ መመሪያ ለሁሉም ኢትዮጵያዊያን ቢሰጥና ወገኖቻቸውን ሳይጎዱ፤ ተጠቅመው ጥቅም ቢሰጡ ለመቃወም አይቻልም። ሰባ አምስት በመቶ የተመራው ተጠቃሚ ትግሬ ከሆነ፤ ሌሎች ኢትዮጵያዊያን የሉብትም። ወይንም አያገባቸውም እንደማለት ነው፤ የአድሎውን ጨካኝነት ያመለክታል። ግልጽነት በሌለባት አገር፤ የፓርቲው ባለስልጣኖች፤ ታማኝ የትግራይ ተወላጆች፤ የህንድን፤ የፓኪስታንን፤ የሳውዲ አረቢያን ወዘተ፤ ኢንቬስተሮች በውስጥ ድርድር ተካፋይ እንዲሆኑ አድርጓል። በውሳኔው ላይ፤ ነዋሪው ሚና የለውም፤ ይህ የጥቅም ውል የኢትዮጵያን ለማደግ የሚችሉ ከበርቴዎች፤ ዝቅተኛ አምራቾች፤ ወጣቶች ወደ ጎን እየተወ፤ ኢትዮጵያዊያን በአገራቸው ለም መሬትና ወንዝ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ እያደረጋቸው ነው። ልክ እንደ ቴሌው ኩንትራት፤ በአጭሩ፤ የንሳ አስተዳደር፤ የከተማ ሆነ የገጠር መሬት አመዳደብን ከኢትዮጵያዊያን እየነጠቀ ለውጭ መንግስታት፤ የፓርቲውና ታማኝ ደጋፊዎቹ አስተላልፉል። ሆኖም፤ የመሬት ነጠቃውን በተናጥል አላየውም። ከንግዱ፤ ከዘመናዊ ምርቱ፤ ከማጓጓዣው፤ ከቴሌው፤ ከመከላከያ እዙ፤ ከሰብአዊ መብቶች መገፈፍ ወዘተ ጋር አጣምሬ አየዋለሁ። አንዱ ሌላውን ይደግፉል።

በፍጥነት ያደጉ አገሮች ታሪክ የሚያስተምረን፤ እኔ በአይኔ ያየሁት፤ የታይዋን፤ የደቡብ ኮሪያ፤ የሲንጋፖር፤ የማላይዚያ፤ የኢንዶኔዝያ፤ የቻይና፤ የህንድ፤ የሞሪሺየስ፤ የብራዚል፤ የኮስታ ሪካ እድገት ከኢትዮጵያ በጣም ይለያል። በእነዚህ አገሮች ሕዝብ አይራብም። እነዚህ አገሮች የአገር ውስጥ ታዳጊ የሆኑትን የኢኮኖሚ፤ የአገልግሎት፤ የንግድ ክፍሎች በተቻለ መጠን ከውጭ አገር አትራፊዎች ተንከባክበው እንዲጎለምሱ አድርገዋል። ህወሓት፤ ሌላ ቀርቶ፤ የቻይና አትራፊዎች በችርቻሮ ተግባር ገብተው ኢትዮጵያውያንን እየጎዱ ቆሞ ያያቸዋል። የምስራቅ ኤዥያ አገሮች ከተወላጆች ውጭ የማይፈቅዱትን፤ የሞባይል ስርጭት፤ የምግብ አቅርቦት፤ የንግድ ወዘተ፤ ተግባሮች፤ ህወሓት ፈቅዶ በማስረከብ ኢትዮጵያውያንን እየጎዳ ነው። ስርጭቱን ለራሱ ኤፈርት እያስተላለፈ ነው። አንባቢው እንዲገነዘብ የምፈልገው መልእክት ይህ ነው። ሃላፊነት የሚሰማው መንግስትና አመራር "ኑ ብሎ" የውጭ ኢንቬስተሮችን ወደ አገሩ የሚያስገባው የአገሩ ሕዝብ ለመስራት የማይችለውን እንዲሰሩ፤ አቅም ገንብተው ቶሎ እንዲወጡ ለማድረግ ነው። የአገሪቱን አምራቾች፤ ነጋዴዎች፤ ለመፍጠርና ለማምረት የሚችሉ ኢትዮጵያውያንን እንዲተኩ አይደለም። በእርሻም በኩል ታናናሽ ገበሬዎች ሆኑ ፍላጎትና፤ ችሎታ ያላቸው ኢትዮጵያውያን መሬቱን፤ ወንዙን፤ ምርቱን፤ ገበያውን እንዲቆጣጠሩት ማድረግ የማእከላዊ መንግስት ሚናና ተግባር ነው። ሃላፊነትና ተጠያቂነት አለበት። ህወሓት የሚያደርገው ከዚህ አገራዊ አመራር የራቀ ነው። ስለዚህ፤ አመራሩ የኪራይ-ሰብሳቢነት፤ የትርፍ አመቻችነት ተግባር ፈጻሚ ሆኖ ይታያል። አብዮታዊ ዲሞክራሲ የተወሰነ መደብ የበላይነት አመራር ስልት ነው። ለዚህ ነው፤ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመወከል "የሞራል ብቃት የለውም" የሚሉ ብዙ ኢትዮጵያን ድምጻቸውን ያሰሙት።

ከሁሉም በላይ፤ 'እድገታዊው' የህወሓት አስተዳደር ያበለጸገው እራሱን። ምርጥና ታማኝ የትግራይ አዲስ ከበርቴዎችን። ከፍተኛ የጦር መሪዎችን። ለይስሙላ ሌሎች ደጋፊዎችን መሆኑን ፕሬዘደንት ኦባማ ያውቃል። በአሁኑ ወቅት፤ ኢትዮጵያ "ዘርፎ ለዘራፊ" ተዳርጋለች ቢባል ከሃቁ የራቀ አይሆንም። የኢትዮጵያን ስብጥር ህብረተሰብ የሚያንጸባርቅ አገር ወለድ ከበርቴ ገና መሰረት መያዝ ያልቻለው አመራሩ አገራዊና ህብረተሰባዊ ስላልሆነ ነው። የዓለም ባንክ ዘገባ እንደሚያሳየው የግል ክፍሉ በህወሓትና ደጋፊ ተቋሞች፤ በወጭ ከበርቴዎች ታንቋል። ይህን የግል ክንፉ ለእድገት ዋና ሚና መጫወት አለበት የሚሉት የአሜሪካ ባለስልጣናት ያውቃሉ። ደንቡ፤ ህጉ፤ አስተዳደሩ አድሏዊና አፋኝ ከሆነ አገር ወለድ ከበርቴ በስፋት ሊፈጠር አይችልም። እንደ ቦትስዋና፤ ናይጀሪያ፤ ጋና መካከለኛ መደብ ሊስፋፋ አይችልም። የኮሪያ፤ ጃፓን፤ ቬትናም፤ እድገት ጎዳናዎች የሚያሳዩት ተመሳሳይ ክስተት፤ አድሎ የሌለበት አገራዊና ህብረተሰባዊ የሆነ የኢኮኖሚ ስርአት፤ ለሁሉም እድል ከፋች መሆኑን ነው። ለሴቶች፤ ለወጣቶች እድል ይከፍታል። በጋና፤ በሴኔጋል፤ በታንዛኒያ የሚታየው አገር ወለድ እድገት ኢትዮጵያን እንደሚለያት አሳይቻለሁ። ህወሓት አዲስ የግል ሃብታሞች ተፈጥረዋል የሚለው እውነት ነው። ችግሩ፤ የተወሰኑ፤ የተመረጡ፤ አብዛኛዎቹ የትግራይ ተወላጆች መሆናቸውን የኦባማ መንግስት ያውቃል። <u>በኢትዮጵያ የተዛባና ትግራያዊ በሆነው፤ የመከላከያ እዝ ላይ</u> የአሜሪካ መንግስት ተወካይ ጀኔቫ ያደረገውን ወቀሳ አባማ፤ ከሊንቶን፤ ራይስ አያውቁትም የሚል ታዛቢ አናገኝም። የመከላከያ የበላይነቱ፤ ፖለቲካውና ከኢኮኖሚው የበላይነት አብረው የተቆራኙ ናቸው።

የህወሓት ባለስልጣናት እንደሚሉት ከሆነ፤ የዚህ አንዱ የተዛብ የእድገት ውጤት የገጠር ሚሊኒየሮችን መፍጠሩ ነው። ከምሳሌ ውጭ ግን፤ እነዚህን የገጠር የህወሓት እድገት አመራር ውጤት የሆኑ ሃብታሞች ፈልገን የት እነደሚኖሩ፤ የት እንደሚገኙ ልንደርስባቸው አልቻልንም። የአሜሪካ ተራድኦ ድርጅት የእርሻ ምርት አለማደጉን ያውቃል። አብዛኛው የምግብ መደጎሚያ የሚጎርፈው ከአሜሪካ መንግስት ነው። የዓለም ባንክ የውስጥ ዘገባ፤ "Poverty and well-being in Ethiopia: the role of agriculture agency" ያሳየው የህወሓት መሪዎች ከሚሉት የገጠር ልማት፤ የምርት እድገት የኑሮ መሻሻል ይጻረራል። ጥናቱ የሚለው፤ የገጠሩ ሕዝብ የሚተዳደርበት መሬት ባለቤት አይደለም። መሬት፤ ምርጥ ዘር፤ ብድር፤ ማዳበሪያ፤ ሌላም የአገልግሎት ግብአቶች (input) ለማግኘት የገዢው ፓርቲ ታዛዥ መሆን አለበት። የሚታረስ መሬት እየጠበበ ሄዷል። በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን መሬት አልባ ሆነዋል የሚል ነው። የሰብአዊ መብት ድርጅቶች፤ በተለይ፤ (Human Rights Watch) እንዳረጋገጡት ህወሓት የውጭ እርዳታ የሚያዳርሰው በታማኝነት መለኪያ ነው። ከፖለቲካ ቁጥጥር ውጭ ሄዶ፤ የሕዝብን ችግር ለመፍታት፤ የግል ክፍሉን አገራዊ ለማድረግ፤ አቅምን ለማጎልመስ፤ ድህነትን በሙሉ ለማጥፋት፤ በተግባር ያሳየው የለም። የአሜሪካኖችን እርዳታ ተጠያቂ የሚያደርገው፤ የገጠሩ የእርሻ ኢኮኖሚ ዘመናዊ አለመሆኑ ጭምር ነው። የግል ክፍሉ ያለምንም አድልዎና ተጽእኖ ካላደገ ዘላቂነት፤ ፍትሃዊነት፤ ያለው እድገት አይኖርም። መዋቅሩ አይለወጥም። አለመረጋጋትና ስደት ይቀጥላል። ይህ ከቀጠለ፤ የምእራባዊያን ጥቅም ይጎዳል።

የዓለም ባንክ፤ ባለሞያዎች፤ ስቴፋን ዴርኮንና ሌሎች ከአንድ አመት በፊት ያቀርቡት ትንተና፤ ኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና ስኬታማ ለማድረግ የፖሊሲና የመዋቅር ችግሮች እንዳሉባት ነው። "ኢትዮጵያ በእርሻ ምርት አስደናቂ እድገት

አሳይታለች የሚለው የመንግሥት ዘገባና ወሬ በምንም ማስረጃ፤ ከህብረተሰቡ ወይንም፤ ኢትዮጵያዊ ከሆኑ ነጻ ተቋሞች ወይንም ምሁራን የተደገፈ" አይደለም። በሚታመን ማረጋገጫ ካልተመሳከረ፤ እድገቱ የፈጠራ ወሬ ነው። "Ethiopia is 123rd of 125 worst fed countries in the world," Oxfam, 2014. በፈጠራ ወሬ ህወሓት በበላይነት የሚመራውን አስተዳደርና አመራር የሚወዳደር የትም አይገኝም። ዓለም ባንክ በሰፊ ጥናቱ እንደሚለው ከሆነ፤ በገጠር በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን መሬት አልባ ናቸው። (Rural landless and landpoor). የሚያርሱት መሬት የተበላ፤ የተቦረቦረ፤ የተቆራረጠ፤ ከእጅ ወደ አፍ የሚሆን መሬት ነው በማለት አስምርበታል። በተጨማሪም፤ በገጠር ብዙ ሰዎች ይራባሉ፤ አማራጭ ስራ የላቸውም ብሏል። ለዚህ ዘገባ ዋና ማስረጃ የሆነው፤ ከስምንት እስከ አስራ-ሶስት ሚሊዮን የሚሆኑት በውጭ የምግብ ድጎማ ይኖራሉ። በአለፉት ሃያ አንድ አመታት፤ ደጓሚዎቹ አቅምን በመገንባት ፋንታ፤ "ምግብ ለስራ" በሚል የእድገት አመራር፤ ጥግኛነትን የመረጡ ይመስላል። የህንድ "አረንጓዴ አብዮት" የተካሄደው፤ "ምግብ ለስራ" በሚል የጥገኝነት እቅድ አልነበረም። ኢትዮጲያ የሚያስፈልጋት፤ ለአገሪቱ ተስማሚ የሆነ አዲስ የገጠር አረንጓዴ ለውጥ ነው። ከመለስ እልፈት በፊት፤ ቢል ጌትስ "የኢትዮጵያ ሕዝብ ከየትኛውም አገር የበለጠ የምግብ ዋስትና የሌለው (The most food insecurity on the planet) እርዳታ የሚያስፈልገው" ነው ብሏል። ይህ የማያሻማ ድምዳሜ የመንግሥቱን የገጠር ኢኮኖሚ አመራር ድክመት አጋልጦታል። ይህ ሲባል፤ የእርሻ የአይነት ውጤት ልዩነት አላሳየም ማለት አይደለም። አበባ ተመርቶ ወደ ውጭ ይላካል። ስንዴ በሳውዲ ስታር ተመርቶ ለአረቦች ገበያ ይቀርባል። ስለዚህ፤ ወደ ውጭ የሚላከው የእርሻ ውጤት ከበፊቱ አድጓል። ዋናው ጥያቄ፤ የምግብ አቅርቦትስ ነው። በተከታታይ፤ በአመት ከአስራ-አንድ በመቶ ባላነሰ አድጋለች፤ አሁንም፤ እያደገች ነው የሚለውም የመንግሥት ፕሮፓጋንዳ ከዚህ አንጻር መታየት ይኖርበታል። የዚህ ነጥብ አላማ አለው። መንግሥት እድገቱ እውነተኛ ነው ብሏል። እኛ ደግሞ ነጻ መገናኛ ፍቀድና ለሕዝብ የሚጠቅም ሪፖርት ይቅረብ እንላለን። ነጻ መገናኛ ብዙሃን ካለ፤ እውነቱን፤ ከህብረተሰቡ ኑሮ መሻሻል አንጻር አይቶ ለመደምደም ይቻላል።

ዓለም ባንክ እድገት አለ ሲል ምን ማለቱ ነው?

ህወሓት ያመጣው እድገት መኖሩ አያከራክርም። ሊያከራክር ይችል የነበረው እድገት በፍጹም ባይኖር ነበር። ወደፊትም እድገት ይኖራል። ሆኖም፤ እድገቱ የአብዛኛውን ህይወት እንዳልለወጠው ማስረጃው ብዙ ነው። አግባብ የሌለውና የተዛባ የኢኮኖሚ አመራር ተከስቷል። ምስና ተቋማዊ ሆኗል። Transparency International 2012 Assessment, "Ethiopia is 133rd out of 176 countries." Freedom House 2013 ASSEMENTS/CONCLUSIONS በሕግ የበላይነት ሲታይ፤ 30 percent out of 100. የሰራተኛ መብት 46.9 percent out of 100; የንግድ መብት 64 out of 100 percent፤ የኢኮኖሚ ነፃነት 134th of 179 countries፤ ስራ በቅልጥፍና የመስራት ልምድ 127th of 185 countries. የተቋሙ ዋና ድምዳሜ ኢትዮጵያ በዓለም ነጻ ካልሆኑ አገሮች መቶ አርባ ስድስተኛ ናት ብሏል። "Regulatory efficiency remains poor, creating an unfavorable climate for entreprunial activity...The fundations of economic freedom are fragile, particularly because of pervasive corruption and a deficient judicial system further undermines the foundations of economic freedom" for the Ethiopian private sector. ሁኔታው፤ ምንም እንኳን ጥቂት ሃብታሞች "ቃተኛ ለመግዛት" ቢሰለፉም፤ የግል ክፍሉን የማምረትና የስራ እድል የመፍጠር ኃይልና አቅም አግቦታል። "The investment regime lacking transparency and efficiency, remains unfavorable" for productivity and domestic private sector initiative. ይኼ አፋኛና ጎታች ሁኔታ የውጭ ምንዛሬ ለማሸሽና አገሪቱን ለማድማት አስከፊ አስተዋፆ እያደረገ ነው። በ 2012, The International Crisis Group had concluded the same. "Meles engineered one party rule in effect for the TPLF and his Tigray inner circle, with the complicity of other ethnic elites that were coopeted into the ruling alliance, the EPRDF...Ethiopia's much praised economic development is not as robust or cost free...as the international community believes...the system was entirely dependent on central authority or command and control." ከመለስ እልፈት በኋላ ሁኔታው ብሷል። በቅርቡ ሪኔ ሌፎርት ያቀረበችው ትንተና አግባብ አለው። የመለስ እልፈት የህወሓትንና የኢህአዴግን አመራር አናግቶታል። የአስተዳደና የህብረተሰቡን ሰላምና ጥቅም ለማስከበር አስቸጋሪ ሆኗል። ሁለት ተወዳዳሪ መንግሥታት በአንድ አገር የሚሰሩ ይመስላል ያለችው ጠቃሚ አስተያየት ነው። Rene' Lefort, Open Democracy, Ethiopia: a leadership in disarray, July 5, 2014. "The party's pinnacle is at least in disarray...the state economy is no longer adequate for driving growth; the private sector needs the scope to take the slack." እስማማለሁ። የኢትዮጵያ የግል ክፍል በኢትዮጵያውያን ተይዞ በፍጥነት ካላደ የኢትዮጵያ መሰረታዊ ችግሮች በምንም አይፈቱም። ይኼ ስኬታማ ለመሆን የሚችለው የፖለቲካ፤ የማህበራውና የኢኮኖሚው ሜዳ ሁሉን አቀፍ፤ ለሁሉም አገልጋይ ሲሆን፤ ይኼም በሕግ ሲረጋገጥ ብቻ ነው። እድገቱም መበየን ያለበት ከዚህ አንጻር ነው፤ እድል ከፋች፤ አጎልማሽ፤ ፍትሃዊ ከመሆኑ አንጻር። አለያ፤ በያመቱ እድገት

አለ ቢባል የአብዛኛውን ሕዝብ ህይወት አይለውጥም፤ በእየ ዓመቱ ለሁለት ሚሊዮን ተኩል ወጣቶች የስራ እድል አይፈጥርም። የሰው ኃይል መፍለስና መሰደድ አያቆምም። የእርስ በእርስ ግጭት ይስፋፋል። አፈናውም ይብሳል።

ዓለም ባንክ ሆነ አይኤምኤፍ እድገት አለ ቢሉ፤ አንባቢው መገረም የለበትም። ስራቸው ማበደርና እድገት አለ ማለት ነው። የሚያበድሩት ፈሰስ ውጤት ካላሳየ፤ ለአለቆቻቸው ተቀባይነት አይኖረውም። ስለዚህ እድገት አለ ማለት አለባቸው። ስለቱኒዚያ ያሉት ተመሳሳይ ነበር። ቱኒዚያ ለውጥ የተካሄደው የምግብ ዋጋ ግሽበት እያደገ በመሄዱ፤ የስራ እድል ባለመኖሩ፤ ሙስና በመስፋፋቱ፤ ህብረተሰቡ በነጻ የመንግስትን ሃላፊነት ለመግለጽና ይገባኛል ለማለት ባለመቻሉ ነው። ያለፈው አመት የተባበሩት መንግስታት የሠብአዊ እድገት መለኪያ (Human Development Index 2012)፤ ኢትዮጵያን ከመቶ ሰማንያ አገሮች መቶ ሰባ አምስተኛ ያደረጋት መሆኑን ማስታወስ ይበጃል። ዘገባው አልተለወጠም። ገዢው ፓርቲ ሲፈልግ እየመረጠ ዓለም ባንክን፤ የተባበሩት መንግስታትን የእድገት ድርጅቶችን እድገታችን አመሰገኑ ሲል የሚፈልገውን ዘገባ መርጦ፤ የማይፈልገውን ትቶ፤ ዋናውን የህብረተሰብ ኑሮ መሻሻል የእድገት መለኪያ እንደሌለ አድርጎ ነው። የማህበረሰብ ድርጅቶችና ነጻ የመገናኛ ብዙሃን በሌለበት አገር፤ (a Society that is totally closed to independent groups) መንግሥት የሚያቀርበው ማስረጃ ብቻ ለዓለም ሕዝብ እንደ እውነት ሆኖ ይቀርባል። ዝግ በሆነ አገር በማስረጃ መዋሸት ይቻላል። የሌለውን ማቅረብና ተቀበሉ ማለት የህወሓት ልዩ ተሰጦ ሆኗል ለማለት የሚያስደፍረው ለዚህ ነው። መፍትሄው፤ የፖለቲካ ውድድር መኖር፤ የማህበረሰብና የመገናኛ ብዙሃን ነጻ መሆን ናቸው። ቻይናዎች፤ ቱርኮች፤ ህንዶች ወዘተ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች መከፈታቸው ኢትዮጵያውያን እስከ ተሳተፉበት ድረስ፤ ቀስ በቀስ የበላይ እስከሆኑ ድረስ አግባብ ይኖረዋል። የኢትዮጵያን ባለቤትነትና የኢትዮጵያውያንን አቅም ከጎዱት ዘላቂነትና ፍትሃዊነት ያለው የዘመናዊ ኢንስትሪ መሰረት ለመጣል አይቻልም።

እውነቱን በግልጽ ለማስቀመጥ የሚቻለው ሁል ጊዜ ከህብረተሰቡ የኑሮ መሻሻል ጋር አብረን ስናየው ብቻ ነው። እድገታዊ መንግስት የሚመራበት ስርአት የአንድ አናሳ ጎሰኛ ፓርቲን የበላይነት ብቻ የሚያንጸባርቅ ነው። የታወቀው ተመራማሪ ደሳለኝ ራማቶ እንዳለው፤ ከህወሓት ውጭ ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ሁሉ በእድገት ላይ የመናገር፤ አማራጭ የማቅረብ፤ የመሳተፍ፤ የመተቸት፤ መብት የላቸውም። አብዮታዊ ዲሞክራሲ አይፈቅድም። መለስ በህይወት በገዛበት ዘመን፤ እነዚህን ከገዢው ፓርቲ ውጭ ያሉ ሁሉ "ኪራይ ሰብሳቢ ስለሆኑ፤ አልሚ  ለመባል የሞራል ብቃት የላቸውም።" ይህ ድንጋጌ እንደመመሪያ ሆኖ አሁንም ያገለግላል። ኪራይ ሰብሳቢ ማን እንደሆነ በማስረጃ ገልጨዋለሁ። ስለሙስና የቀረበው ምእራፍ የበለጠ ያብራራዋል።  ይህ "ሌሎች ኪራይ ፈላጊዎችና ሰብሳቢዎች ናቸው" የሚል ድንጋጌ ዋጋ እየተከፈለበት ነው። አገር ወለድና ኢትዮጵያዊ የሆኑ ሁሉ የመፍጠር፤ የማምረት፤ የመንቀሳቀስ፤ የመወዳደር፤ ሃብት አግኝተው አገራቸውን የማልማት ሚና እንዳይጫወቱ ተደርጓል። ስርአቱ አገራዊ የሆነ የሃብታምና መካከለኛ መደብ ለመፍጠር እንዳይችሉ ማነቆ ሆኗል። ኢትዮጵያ ለመላው ኢትዮጵያውያን የኑሮ መሻሻያ፤ ተግተው ለሚሰሩ ሁሉ፤ የገቢና የሃብት ማሻሻያ፤ ለራሳቸው ሰርተውና አትርፈው፤ አገራቸውን መርጃ መሰረት ካልሆነች እድገቱ ቢኖርም፤ በአብዛኛው ተጠቃሚዎቹ ስልጣን ያላቸው፤ ቤተሰቦቻቸውና የውጭ ኢንቬስተሮች ይሆናሉ። በ December 2012 ባወጣው የኢትዮጵያ እድገት ዘገባ፤ ዓለም ባንክ የተጠቀመው በኢትዮጵያ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ የቻይና ድርጅቶችን ሚናና የእድገት ግምት፤ የትርፍ ሁኔታ፤ በመመርመር ነው። በኢትዮጵያውያን ባለቤትነት የተያዙት የአምራችና የአገልግሎት ድርጅቶች የት አሉ ብሎ መጠየቅ አስፈለጊ ነው። አገር ወለድ እድገት ከተፈለገ የምርምሩ መሰረት ኢትዮጵያውያን የሚያንቀሳቅሱት የግል የኢኮኖሚ ዘርፍ መሆን አለበት። ቻይናዎች፤ ህንዶችና ሌሎች አይደሉም። እነሱ የሚፈልጉት ትርፍን ነው፤ ለማህበረሰብ ደህንነት ደንታ የላቸውም።

የውጭ ኢንቬስተሮች ሚና የላቸውም ማለት አይደለም። ችግሩ፤ የውጭ ኢንቬስተሮች ኢትዮጵያውያንን እንዲተኩ መሆኑ ነው። ከኢትዮጵያውያን ጋር ተባብረው፤ የአገሪቱ ኢኮኖሚ ራሱን እንዲችል ያድርጉ የሚል ብሄራዊ አመራር የኢንቬስተሮችን ሚና ጠቃሚ ያደርገዋል። ኢንቬስተሮች የኢኮኖሚ አውታሮችን እንደልባቸው ይያዙ የሚለው አመራር አገሪቱን ይጎዳታል። በተለይ፤ የግሉን ክፍል እድገት ያፍነዋል። የጠቃሚ አጋርነት ምሳሌ እንይ። የኢትዮጵያ አየር መንገድ በውጭ ድጋፍ እንደተመሰረተ እናውቃለን። በጥቂት አመታት ኢትዮጵያውያን የበላይነቱን ይዘው አሁን ለአገር የሚያኮራ ሆኗል። ቴሌና ሌሎች ምሳሌዎችም ነበሩ። የጎሰኛው ስርአት ያጠፋቸው። በእድገት ስም ጥገኛነትን መጋበዝ ዞሮ ዞሮ ህብረተሰቡን ይጎዳል። የገዢው ፓርቲ የበላዮች የሚመለከቱት አገር ወለድ፤ ሁሉን የሚያስተናግድ የእድገት መሰረት መፈጠሩን አይደለም። ቁጥሩ ከፍ ማለቱን፤ ጥቂቶች ትርፍ ማግኘታቸውን ነው። የስልጣን ቆይታን ያጠናክራል። ህወሓት በበላይነት የሚገዛው መንግሥት የደነገገውን አመራር ባለመቀበል፤ ተቃዋሚዎች "እድገቱ አገር ወለድና ፍትሃዊ  አይደለም። አድሏዊ ነው። ሌሎች የሚያገባቸው ሁሉ ታፍነዋል። ህብረተሰቡ ተቆርቋሪ የለውም። ባለመኖሩ፤ ስርአቱ ምዝበራን፤ አድልዎንና ሙስናን አጠናክሯል" የሚል አቤቱታ ይሰነዝራሉ። ሕዝቡ፤ "ስርአቱ ሰው በአገሩ ሰርቶ እንዲኖር አያበረታታም፤ እድገት አለ፤ ዳቦ የለም" ይላል። ሰሚ የለውም።

እውነቱን መናገር ግን ወንጀል ሆኗል። እነ እስክንድር ነጋ፤ እነ አንዷአለም አራጌና በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሌሎች በእስር ቤት የሚማቅቁት ለፍትህ ሰለቆሙ ነው። በተደጋጋሚ ይህን ካሉ ምርጫቸው ወይ ከርቸሌ፤ ወይ ስደት ሆኗል። ተስፋ የቆረጡ በስርአቱ ፍትሃዊነት እምነት ስለሌላቸው አማራጭ ሆኖ የሚያዩት፤ ከአገር መሸሽ፤ ያላቸውን ሃብት ማሸሽ፤ ወዘተ ሆኗል። እድገታዊ መንግሥት ተብሎ የሚጠራው ወሳኝ አመራር ጥቅሙ ለአንድ ጠባብ ጎሰኛ ቡድን መሆኑን የሚያጠነክረው የፖለቲካ ሆነ የኢኮኖሚ ተወዳዳሪ መከልከሉና የመንቀሳቀስ መብት አለመኖሩ፤ እድገቱን አዳክሞታል። የሕዝብ ጠበቃና ተወዳዳሪ ቢኖር አድሏዊ የሆነው አመራር ያስከተላቸውን ጎጅ ውጤቶች ማሳየትና የኢትዮጵያን የእድገት መስመር ወደተሻለ አቅጣጫ መምራት ይቻል ነበር። ይህ ያለመሆኑ ጉዳት ለወጣቱ ትውልድ፤ በተለይ ለሴቶች መሰደድ፤ ለአገር ወለድ እድገት እየታፈነ መዳተት፤ ለሰብአዊ መብቶች መረገጥ አስተዋጽኦ አድርጓል። ስርአቱ በውስጡ ህብረተሰብአዊ አደጋን ፈጥሯል። ይህን የአደጋ መኖር ከውጭ መንግስታትና ከአበዳሪ ድርጅቶች አመኔታ መጠበቅ ስህተት ነው። ህብረተሰቡ አውቆ መብቱን ማስከበር አለበት። በቸልተኝነት ሆነ በፍርሃት፤ በጨዋነት ሆነ ነገ ይፈታል በማለት ግድ የለሽ ሆኖ ማየት "በሽታን እንደመደበቅ" ይሆናል። የውጭ ኢንቬስተሮች ያለምንም ገደብ ሲያርሱ፤ አበባ ተክለው ለውጭ ገበያ ሲያቀርቡ፤ ማእደን ቆፍረው ወርቅ ሲያመርቱ ወዘተ የሚኖረውን ዘላቂ ጉዳት የሚያመጣ የአካባቢ አደጋ ህብረተሰቡ መገንዘብ አለበት። ኢንቬስተሮች ሆኑ የውስጥ ለትርፍ ብቻ የሚስገበገቡ ተጠቃሚዎች የአካባቢውን አደጋ ይቆጣጠሩልናል ማለት የዋህነት ነው።

የአካባቢው ውድቅት (massive environmental degradation and social dislocation that threatens sustainability) እየሰፋ ሄዷል። በሃብታምና በደሃ መካከል ያለው የገቢ፤ የሃብትና የኑሮ ልዩነት እጅግ በጣም በሚያስደነግጥ ሁኔታ እየሰፋ ሄዷል። የጎሳዊ አድልዎና የሙስና ጥልቀት አስከፊ ደረጃ ላይ ደርሷል። የወጣቱ ትውልድ በመንግስትና መሪዎቹ ያለው አመኔታ ተንዷል። በየክልሉ ሲታይ መልካም የሆኑ የባህል እሴቶች እየጠፉ ነው። በምትካቸው፤ ህብረተሰቡ የማያውቃቸው ባህሎችና ልምዶች ተስፋፍተዋል። የመንግሥት ሌቦች መኖራቸውን ያወቀ ትውልድ፤ ስርቆትን እነደ ብልጠት ማየት ከጀመረ ቆይቷል። መንግሥት ለታላላቅ የቤተክርስቲያን ተቋሞች ያለውን ዝቅተኛ አመለካከት--ለምሳሌ የዋልድባን ገዳም አካባቢ ማረስ--ሲመለከት፤ የጥንት ቅርሶች የኢኮኖሚ ጥቅም እንደሌላቸው ያያቸዋል። በፔሩ፤ በግብጽ፤ በቻይና፤ በጃፓን፤ በተርኪ ወዘተ የጥንት ባህላዊ፤ ሃይማኖታዊ ቅርሶች ከአገራዊ መታወቂያቸው በላይ ብዙ ሽህ ሰራተኞች ይቀጥራሉ። ወጣቱ ለአገር ዘላቂነት ያለው (Sustainable) ገቢ እንደሚያመጡ አይማርም። መንግሥት ዋጋ ስላልሰጠው ወይንም፤ የባህል ቅርሶችን የፖለቲካ መሳሪያ ስላደረጋቸው። ገዢው ፓርቲ፤ እነዚህንና ሌሎችን የልማት መሰረተ ሃሳቦችንና ፖሊሲዎች ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ትችት እንደ ጠላትነት ይቆጥራል። የሰብአዊ መብቶችን የረገጠበት አንዱ ምክንያት የህብረተሰቡ አሰቃቂ ኑሮና ሌሎች አማራጮች እንዳሉ እንዳይታወቅ ነው። መለስ በህይወት በገዛበት ዘመን፤ ቢፈልግ ኖሮ፤ የመንግሥቱን ፖሊሲ ከግለሰቦች ጥቅም ነጻ ለማውጣት ችሎታና ብቃት፤ ሃይልና ተቋማዊ ድጋፍ ነበረው። አሁን ያለው አመራር የሚመራው በአፋኝ ርእዮት ነው። ባለፈው የነበረው፤ "ተቀናቃይ ሁሉ ጠላት ነው" የሚለው ፍልስፍና አሁን በባሰ ሁኔታ እየተካሄደ ነው። በመለስ ዘመን፤ የህወሓት ደጋፊወች በያሉበት፤ ተቃዋሚዎችንና ጥያቄ አቅራቢዎችን በጅምላ፤ "ግለሰብ (መለስን ማላታቸው ነበር) ስለጠላችሁ እንጅ፤ ተቃውሟችሁ ፍትሃዊ እድገት ስለሌለ አይደለም" ይሉ ነበር። ይህ ጭፍንና ግትረኛ አስተሳሰብ፤ በመለስ እልፈት አልተለወጠም። "የመለስን አምልኮት" በመከተል፤ የጠነከረ፤ ጠባብ ጎሰኛነት የሚያስተገባ ፕሮፓጋንዳ በመካሄድ ላይ ነው። ባጭሩ፤ የመለስ እለፈት፤ ስርአቱን የኢምንት ያህል አልለወጠውም።

መለስ በስልጣን ላይ በነበረበት ወቅት፤ በጠባብ ጎሰኛነት ዙሪያ የመጣውን አዲስ ከፖለቲካ ስልጣን የመነጨ የባለጠጋነት አደጋ የተመለከተው ዓለም ባንክ አንድ የውስጥ መሰረታዊ ጥናት አድርጎ ሶስት ግንዛቤዎችን አቅርቧል። የአገዛዝ፤ የሕዝብ አመኔታና የችሎታ ብልሽቶችና ድክመቶች የሚሉ። Sahr Kpundeh and Gilbert Khadiagala, Information Access, Governance and Service Delivery in Key Sectors: Ethiopia and Kenya, 2008 የተገነዘቡት የኢትዮጵያ መንግሥት ባለስልጣናት ሆነ ብለው "ዜናና ማስረጃ ለህብረተሰቡ እንዳይደርስ የከለከሉት አድልዎና ሙስና እንዳይታወቅ ስለፈለጉ ነው" ይላል። የድርጊቱን ኢ-ሰብአዊይነት በማስረጃ ሲያቀርቡ ያተኮሩት ለመኖር/አለመኖር ወሳኝ በሆኑ ለተሰቦ በሽታ፤ ለወባ፤ ኤችዓይቪ/ኤድስና ሌሎች መከላከያ መድኃኒቶችና አገልግሎቶች የተደረገውን አድልዎና ሙስና ነው። ህወሓት ለበሽተኞች ተብሎ የተላከውን "እርዳታ ከልክሏል። የውሸት መድሃኒት አስራጭቷል። ለተጠቃሚዎች እንዳይደርስ አድርጓል። ከሞት የሚያድን አገልግሎት ነስቷል። ገንዘቡን በሚያስደንግጥ ሁኔታ ለሌላ ጥቅም አውሎታል። ወዘተ ወዘተ።" ስለሆነም፤ ጥናቱ ያሳየው ህብረተሰቡ በመንግሥት ላይ ምንም አመኔታ የለውም የሚል ነው። አገልግሎት ይሰጣሉ ተብለው "ስልጣን የተሰጣቸው ግለሰቦች ከታማኝነታቸው ሌላ ችሎታ የላቸውም" ከሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል። ይህ ዘገባ ለመንግሥት ባለስልጣናት ቀርቧል። እንደሌላው ጥናቱ የውሃ ሽታ ሆኗል። መድኃኒትና ተገቢ አገልግሎት መከልከሉና መድሃኒቱ አግባብና ጥቅም የሌለው መሆኑ የመንግሥት ሃላፊዎች በማህበረሰቡ ላይ ወንጀል እንደሰሩ ያስጠይቃቸዋል።

ዓለም ባንክ በውስጥ ያቀረበውን ትችት ወደጎን ትተን ከመለስ እልፈት በፊት፤ አዲስ አበባ በተካሄደ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ስብሰባ፤ አንድ የቻይና ባለስልጣን ለመለስ የተናገርው "ለውጥ አስፈላጊ ነው" የሚል መልእክት የሰጠውን እንይ። አባባሉ፤ ከእኛ ስህተት ተማሩ፤ ህብረተሰቡን አስቀድሙ፤ እድልዎ አታድርጉ የሚል ነበር። "ተማሩ፤ በጭፍን ቻይናን፤ ቻይና አትበሉ፤ ችግሮችን ተገንዝባችሁ ሌላ ውብ (beautiful) አማራጭ ተከተሉ።" ውብ አማራጭ ማለት፤ አገር ወለድ፤ ጥሩ ምሳሌ ከሚያሳዩ አገሮች ሁሉ ተምራችሁ ለኢትዮጵያ የሚስማማ፤ ኢትዮጵያዊ የሆነ የኢኮኖሚ አመራር ተከተሉ ማለቱ ነበር። የቻይና ኮሙኒስት ፖርቲ በ2012 እና ከዚያ በኋላ ባደረገው ስብሰባና የአመራር መተካት ምርጫ የሰማውም፤ የፓርቲው የበላይነት ህይወት ሊኖረው የሚችለው ሙስናን፤ መጥፎ አስተዳደርን፤ አድልዎን ሲያስወግድ ነው የሚሉ መልእክቶች ነበር። የቻይና ሕዝብ ድምጹን ማሰማት ጀመረ ማለት ነው። ቻይናዊው ግለሰብ አዲስ አበባ ሆኖ የሰጠው ምክር፤ ለህወሓት ጥቅም አልነበረውም። የህወሓት አመራር፤ ኢትዮጵያውያን፤ በኢትዮጵያዊነታቸው መታወቂያ፤ በመላው ኢትዮጵያ መስራት፤ መሬት መያዝ ይችላሉ በሚል መሰረተ ሃሳብ አያምንም። የቻይና የግል ክፍል እድገት ገደብ የለውም። በንግግርና በውይይት ደረጃ፤ የቻና አመራር፤ ችግር እንዳለበት፤ ችግሩ ለፓርቲውና ለቻይና አደገኛ እንደሆነ ህብረተሰቡ ይነጋገርበታል። እመርታዊ ለውጥ ይመጣል ተብሎ ባይገመትም፤ ፓርቲው ለመቆየት ከፈለገ ለሕዝቡ ታዛዥ መሆን እንዳለበት ተቀብሏል።

በአንጻሩ፤ ህወሓት የሚመራው መንግሥት ስኅተት ሰራሁ ብሎ ለመቀበል በምንም አይችልም። ስህተት ሰራሁ ማለት ለፓርቲው የበላዮች ድክመት ነው። አመራሩ የለመደው፤ ሌላውን ማንበርከክ፤ ሰብእነቱን መግፈፍ ነው። ከስህተቱ የማይማር የመንግሥት አመራር የሚያምነው በፈላጭ ቆራጭነት ነው። ስለዚህ፤ የገዢው ፓርቲ መሪዎች ካለፈው ስህተት ለመማር የማይችሉ፤ ለሕዝብ ንቀት ያላቸው፤ የሌለውን ከተሳትፎ የሚመጣ ፍትሃዊ እድገት የሚያፍኑ፤ ሕዝብ እየተራበ አልተራበም የሚሉ፤ ወዘተ ናቸው። ጠባብ ጎሰኛ የነበረው፤ ለሃያ አንድ አመታት ሰብአዊ መብቶችን የረገጠ መሪ በዓለም መሪዎች የምግብ ዋስትና ውይይትና ድርድር ላይ ለመገኘት የሞራል ብቃት አልነበረውም የሚሉ ኢትዮጵያዊያን ትክክል አይደሉም ለማለት የማይቻለው ለዚህ ነው። አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆዱ ሞልቶ አያድርም። አመራሩ በሃያ አንድ አመታት ያላሳየውን የምግብ ዋስትና አምባገነኑ ፓርቲ እንዴትና በምን ተአምር በሚቀጥሉት አምስት አመታት እንደሚጎናጸፍ ለእኔና ለሌልች የቅርብ ተመልካቾች እንቆቅልሽ ነው። ሌላው፤ አመራሩ ከአገሩ ሕዝብ የበለጠ እምነቱ፤ በውጭ ለጋሶችና ሃብታሞች (donors and investors) ድጋፍ ነው። በአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የመስራትና የማምረት ችሎታ ኢያምንም። ለዚህ ነው የዓለም ባንኩ ዘገባ ህብረተሰቡ በመንግስት እምነት የለውም ያለው።

በሕዝብ የመስራት፤ የመፍጠር፤ የማምረት ሃይል የሚያምን መንግሥት፤ የአገሩን አምራች ገበሬ አቅም ይገናባል። ህወሓት በትግራይ ክልል የሚያደርገው ማለታችን ነው። ሳውዲ ስታር፤ ካሩቱሪ ወዘተ፤ አርሰው ይመግቡኛል ብሎ፤ በውጭ የትርፍ አምራቾች አይመካም። አገሩን ዘርፎ ለዘራፊ አይዳርግም። መለስ በህይወቱ በነበረበት ወቅት "እኛ ኢትዮጵያውያን ካልተጠነቀቅን፤ የኢኮኖሚ ምሰሶ የሆኑትን ክፍሎች ለውጭ እንቬስተሮች አስተላልፈን፤ አገራችን እናጣለን ያለው" ትክክለኛ ነበር። ፖሊሲውን ለመለወጥ እድል ነበረው። ይህን እድል አልተጠቀመበትም ። የአሁኑ አመራርና ፖሊሲ እንዳለ ከቀጠለ እድገት ይኖራል። ነገር ግን፤ ድሃው ሆነ መካከለኛ መደብ፤ ብሄራዊ ከበርቴ ሆነ ኑሮውን የማሻሻል እድሉ የተወሰነ ነው። የሚጎዳው የአሁኑና ተከታታይ ትውልድ ነው። የስራ እድል የሌለው ወጣት መብቱን የሚያስከብርበትን መንገድ ተባብሮ ራሱ መፈለግ አለበት። ከእድገቱ ተካፋይ ያልሆኑ ኢትዮጵያውያን እጃቸውን አጥፈው ከተቀመጡ ማንንም ለመውቀስ አይችሉም። ማንም የውጭ ሃይል መብታቸውን፤ ነጻነታቸውን፤ ክብራቸውን በሳህን አቅርቦ አይሰጣቸውም። ክብሩን፤ መብቱን የሚፈልግ ትውልድ ራሱን ማደራጀትና ለለውጥ ደፍሮ መነሳት አለበት። ያለፈ ታሪኩ የሚያስተምረው ይህን እሴት ነው። ለውጥን ለማምጣት አብሮ መስራትን ይጠይቃል። አብሮ ለመስራት ከጎሳ፤ ከሃይማኖት ልዩነት በላይ ማሰብን ይጠይቃል። የጠባብ ጎሰኛው አመራር የጫነውን፤ "የብሄር ልዩነት ባርኔጣ" አንግቦ ዲሞክራሳዊ ለውጥ ይመጣል ብሎ መመኘት ህልም ነው። አይቻልም። ለውጥ ሊመጣ የሚችለው አገራዊ በሆነ ስልት፤ ለአንድ አገር ዘላቂነት፤ ለአንድ ለተሳሰረ ህብረተሰብ ፍትህ፤ ለእውነተኛ እኩልነት ተቻችሎ በተግባር ለማሳየት ብቁነትና ድፍረት ሲኖር ነው። ወጣቱ ትውልድ ስሜት እንዳለው ይታያል። ይህ ትውልድ አብሮ ተባብሮ ከቆመ፤ ዛሬ የኢትዮጵያ መታወቂያ የሆኑትን፤ ማለትም፤ጥገኝነት፤ ኋላ ቀርነት ወዘተ የመጥፎ አገዛዝ እሴቶች ናቸው ብሎ ሊለውጥ መነሳት አለበት። መነሻው፤ ኢትዮጵያ ሃብታምና ዘመናዊ ለመሆን፤ የተፈጥሮና የሰው ሃይል እንዳላት ማመን ነው። ደሃ ነን ብለን ካመንን፤ ከድህነት ነጻ አንወጣም። ብሄራዊ እምነት የሌለው ተከታታይ ትውልድ፤ የትምህርት እድል ቢኖረውም፤ አማራጩ ስደት ይሆናል። ስደቱ ተደጋጋሚ (Recurring) ሲሆን፤ አገር ቤት የሚቀረውን ህብረተሰብ ለአምባገነናዊ አገዛዝ ይዳርገዋል። ትውልዱ በታሪክ ተጠያቂ ይሆናል።

የምግብ ዋስትና የመላው ኢትዮጵያዊ መብት ነው

የስራ እድል፤ የራስን ድርጅት ማቋቋም፤ የምግብ ዋስትና፤ የመናገርና የመንቀሳቀስ፤ በሃገር ውስጥ የትም ቦታ የመኖር መብቶች በአብዛኛው ዓለም የተከበሩና በሕግ የተጠበቁ ናቸው። ቀደም ሲል እንዳሳየሁት፤ ህወሓትና ደጋፊዎቹ ሙሉ በሙሉ የሚቆጣጠሩት መንግስት ኢትዮጵያዊ መታወቂያ የነበራቸውን ተቋሞች አፍርሷቸዋል። በምትካቸው ጎሳዊ የሆኑ፤ ቁልፍ ውሳኔዎችን የሚያስተጋቡ ፈጥሯል። ጎሳዊ አድርጓል። በማድረጉ፤ ባለጠጋንት ለራሱና ለደጋፊዎቹ አካብቷል። የመከላከያ፤የህግ፤ የውጭ ግንኙነት፤ የጉምሩክ፤ የባንክ፤ የማዘጋጃ ቤት፤ የአስተዳደር፤ የተፈጥሮ ጥሪት አጠቃቀም፤ የስራ ፈቃድ፤ የትምህርት ድርጅቶችን በሙሉ ጎሳዊ አድርጓቸዋል። እድገት አለ ቢባልም፤ የዚህ አይነት ከልካይ (Restrictive) አገዛዝ በምንም መለኪያ ዘላቂነትና ፍትሃዊነት ሊኖረው አይችልም። አሁን ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ በልዩ ልዩ ዘርፍ የችግሩን ክብደትና ስፋት ያሳያል። አመራሩ ያልተቀበለው፤ መንግሥት ብቻውን ችግሩን ሊፈታው አይችልም የሚለውን ነጥብ ነው። ብሄራዊ ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉት ሌሎችን በማቀብ፤ በማሳደድ፤ በማሰር፤ በመግደል፤ አያገባችሁም በማለት አይደለም። ሊፈቱ የሚችሉት በአገራዊ አሰራር ስርአት፤ በመላው ሕዝብ ተሳትፎ፤ መብትና እኩልነት ነው። የምግብ አቅርቦትና ዋስትና ለህብረተሰቡ ፍላጎቶች ዋና ከሆኑት መካከል የመጀመሪያውን ደረጃ ይዞ ይገኛል።

የምግብ ዋስትና ባለቤትነት ይጠይቃል

በ2012 ዋሽንግተን፤ ካምፕ ዴቪድና ሜክሲኮ የተደረጉት የG-8ና የG-20 ስብሰባዎች ያልተገነዘቡት የህወሓትን የአፈና አገዛዝ ሃቅ ነው። የገበሬውን የመሬት ባለቤትነት ዋስትና የገፈፈ፤ የመናገር፤ የመሰብሰብ፤ የመንቀሳቀስ፤ የመምረጥ/የመመረጥ፤ ወዘተ መብቶችን ያቀበ አገዛዝ ለተራበ፤ ስራ ላጣ ሕዝብ ደንታ የለውም። የጎሰኛ አስተዳደር ተጠቅሞ፤ የብሄር ጽዳት መሳሪያ የሆነውን የክልል ስርአት ዘላቂነት ለመስጠት የሚሞክረው ለቁጥጥር እንዲያመች ነው። በጎሳ የተከፋፈለ ህብረተሰብ፤ በአንድ ላይ ተነስቶ መብቴ ይከበር አይልም የሚል ሂሳብ አለው። የገጠሩን አምራች የሚቆጣጠረው በተመሳሳይ ስልት ነው። የዚህን በአይነቱ የተለየ ክፉ አገዛዝ ውጤት በህሊና ለመቅረጽ፤ ከራሳችንና ከመንረዳቸው ቤተሰቦች ወጥተን በፍጹም ደሃ ከሆኑ ሴቶችና የልጆቻቸው ኑሮ ብናይ ይዘገንናል። በDecember 19, 2012, ማርሲ ኤሪክሰን የምትባል በጎ አድራጊ፤ (Grace Center, Bahir Dar, Amhara Region)፤ ያቀረበችውን ዶክመንተሪ ሳይ፤ እራሴን የጠየቅሁት "ይህን ያየ እንዴት እንቅልፍ ይወስደዋል" የሚል ነው። ወጣት እናቶች ተርበው፤ ልጆቻቸውን የሚያጠቡት ወተት ከጡታቸው አይወጣም። አጽማቸው ብቻ ቀርቷል። እነሱም ረሃብተኞች ናቸው። ህጻናቱ ልክ እንደታላቁ የወሎ ረሃብ፤ አጽማቸው ብቻ የቀረ ይመስላል። በባህር ዳር ሆስፒታል የተገኙት ህጻናት የመትረፍ እድላቸው አስተማማኝ አይመስልም። ስንቶቹ እንደሚሞቱ አይታወቅም። ባጭሩ፤ ተአምራዊ እድገት ታሳያለች በምትባለው ኢትዮጵያ፤ በአብዛኛው የሚታየው ስእል፤ የድሃ እናቶችና የወለዷቸው ልጆች በሞት አፋፍ ላይ የሚታይ ስእል ነው። ይህ በደል በተወሰኑ ክልሎች የሚታይ ብቻ ከሆነ፤ ግፉ በደረሰበት ህብረተሰብ ላይ በገዢው ፓርቲ አመራር የታሰበ፤ ሊወገድ የሚችል የሞት ፍርድ እንደተፈረደበት ይቆጠራል። የእኔ ግምት፤ በገጠር ውስጥ በደሃ ቤተሰቦች ላይ፤ በተለይ፤ በወጣት ሴቶችና በልጆቻቸው ላይ የሚታየው የረሃብ አለንጋ አጠቃላይ ይመስላል። እውነቱን ለማጣራት፤ ከጥቂት ማስረጃ ለመሰብሰብ ከቻሉ ፈረንጆች በስተቀር የሚያውቀው የለም።

የመገናኛ ብዙሃን ነፃነት ቁልፍ ነው

የመገናኛ ብዙሃን ቁልፍ የሚሆነው ለዚህ ነው። ህብረተሰቡና የዓለም ህዝብ እውነቱን እንዲያውቅ፤ ሕዝብ ለሕዝብ እንዲገናኝ፤ ለመብቱ እንዲታገል ከተፈለገ መገናኛ ብዙሃን ያለተጽእኖ ሚና መጫወት አለበት። የብሄር ማጽዳቱን ዘላቂ ጉዳት (Systematic ethnic cleansing and reduction) ያወቀ ሕዝብ ለመብቱ አብሮ ይታገላል። የትግሉን ሜዳ ያሰፋዋል። ማን እንደሚጎዳው፤ ማን እንደሚረዳው ያውቃል። በነጻነት የሚያገለግል የዜና ስርጭት ለመብት፤ ለፍትህ፤ ለእውቀት፤ ለመደጋገፍ፤ ለእድገት፤ ለሕዝብ አመጽ፤ ለገበያ ስፋት፤ ለድፍረት ቁልፍ ነው። በሰሜን አፍሪካ የተካሄደው የሕዝብ አመጽና ለውጥ ያለ ዜና ስርጭት ከግቡ አይደርስም ነበር። ለብዙ አስርት አመታት የግብጽ ሕዝብ "እርግብ ነው፤ ሰነፍ ነው፤ ለመብቱ አይነሳም፤ ያዘዙትን ይቀበላል፤ መብትና ግዴታን ለይቶ አያውቅም፤ ዲሞክራሲ ምን እንደሆነ አይገባውም ወዘተ" እየተባለ በምእራብ ተመልካቾች ይተረክ ነበር። አባባሉ የአሁኑን የኢትዮጵያን ይመስላል። ግብጾች፤ የዓለም ህብረተሰብ ሳያስበው፤ በሚያስደንቅ ሁኔታ የአገራቸውን የፖለቲካ ታሪክ ለውጠውታል። በአንጻሩ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ከግብጾች የበለጠ የታፈነ፤ ድህነት ያጠቃውና በጎሳ-ተኮር ፖለቲካ የተከፋፈለ ነው።

የግብጽ ሕዝብ ለመጀመሪያ ጊዜ መሪውንና ህገመንግስቱን ያለ ተጽእኖ ለመምረጥ የቻለው የህዝብ አመጽ ውጤት ነው። ውጤቱ እውን የሆነው፤ በወጣቱ ትውልድ መሪነትና አስተባባሪነት፤ በመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም፤ በሕዝብ ሰንሰለትና አብሮ መነሳት ስልት ጭምር ነው። አሜሪካ ወይንም ሌላ የውጭ ሃይል አልቀሰቀሰውም። ኢትዮጵያውያንም ልምዱ፤ ባህሉና ወኔው አላቸው። አሁን የጎደለው ድፍረትና አብሮ መነሳት አለመቻል ይመስላል። የህወሓት ዋና መስራችና

የፍልስፍናው ዋና ሊቅ የነበረው መለስና ግብረ-አበሮቹ ነጻ መገናኛ ብዙሃንን ፈርተው ያጠፉት ለዚህ ነው። የውጭ አገር ተወላጅ የሆነችው ኤሪክሶን ያቀረበችውን ሲኒማ መሰል ዘገባ አንድ ነጻ ኢትዮጵያዊ ቢያወጣ፤ ሽብርተኛ ነህ ተብሎ ይታሰር ነበር፡፤ ህወሓት፤ ሌላው ቀርቶ በውጭ የምንገኘውን አገር ወዳዶች ሁሉ ለማንበርከክ ይሞክራል። አንዳንዶቻችን ለፍረሃት ተገዢ የሆንነው ለዚህ ነው።

ሰርቶና በልቶ ለማደር ነጻነት ወሳኝ ነው

የሕዝብ ተሳትፎ የሌለበት እድገት በምንም ፍትሃዊ ሊሆን አይችልም። በሞት አፋፍ ላይ የሚገኙ ወጣት እናቶች፤ ገና በአስራ አምስት አመታቸው የሴት አዳሪ የሆኑ ልጃገረዶች፤ በድህነታቸው ብቻ ተገደው ለሳውዲ ሃብታሞች ግርድና የሚላኩ ሴቶች የመናገር መብታቸው ተገፏል። በአገራቸው "የኢኮኖሚ መብት" እንደሌላቸው ማጤን ይገባል። የG-8 የምግብ ዋስትና ስብሰባ የተካሄደው ኢትዮጵያ መብቶች በሙሉ በተከለከሉበት ወቅት ነው። ትውልድ እንዲያስታውሰው የፈለግሁት፤ በአሜሪካ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ይህን አጋጣሚ በመጠቀም፤ እአአ፤ በተከታታይ፤ May 14, 2012 ሁዋይት ሃውስ ሕንጻ ፊት ለፊት፤ ከዚያም በህንድ ኤምባሲ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ በሚያኮራ አሰላለፍ፤ ሁሉም ለሙብቱ፤ ለነጻነቱ፤ ለአንድ አገር፤ በአንድ ድምጽ የሚነሳበትን መፈክሮች አንግቦ ጠበቃ ለሌለው ሕዝብ ሲሟገት ዉሏል። በስብሰባው አዳራሽ የታወቀው ጋዜጠኛ፤ አቶ አበበ ገላው ለነጻነት በመቆም ድምጹን አሰምቷል። ሰልፉና የጋዜጠኛው ድምጽ ያስተማረኝ ስደተኛው በቆራጥነትና  በተከታታይ የዚህ አይነት መተባበር ቢያሳይ አዳማጭ እንደሚያገኝ እንገምታለን። በMay 18, 2012, ከጥዋቱ ሰባት ሰአት ተኩል ጀምሮ በሬገን ህንጻ የተካሄደው ሰላማዊ ሰልፍ የኢትዮጵያን ሕዝብ አወቃቀር ያንጸባረቀ፤ በወጣቶች የተመራ፤ መልእክት ያስተላለፈ ነበር ለማለት እችላለሁ። ከውጭ ያለው ድምጹን ለፕሬዘደንት ኦባማ፤ ለአሜሪካ ሕዝብ፤ ለተጠሩ እንግዶች በስሜት አሰምቷል። ከውጭ ያለው ሰላማዊ ሰልፍ እያካሄድ በነበረበት ጊዜ፤ በአዳራሹ ውስጥ የነበረው የታወቀው ኢትዮጵያዊ ጋዜጠኛ፤ አበበ ገላው፤ የአሁኑና የወደፊቱ ትውልድ ምሳሌ የሚያደርገው፤ ለፍትህ-ለርትእ የቆሙ ሁሉ "አገራችን ሰው አላት" ብለው ሊነሳሱበት የሚያስችል መልእክት ለተሰበሰቡ መሪዎችና ጋዜጠኞች አስተላለፈ። ቀረብ ብሎ ለሰማው በአዳራሹ ያለው ሁሉ አይኑና ሃሳቡ በሙሉ ያረፈው ከተናጋሪው ላይ ነበር። አንባቢው እንዲያስታውስ የምመኘው ጋዜጠኛው ያስተላለፈው መልእክት የዘር ጥላቻ አልነበረም። የፖሊሲ ለውጥ አስፈላጊነት መልእክት ነበር። "መለስ ዜናዊ አምባገነን ነው። እስክንድር ነጋ ይፈታ። የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ። ምግብ ያለ ነጻነት ዋጋ የለውም። መለስ ሰላማዊ ሕዝብ በመግደል ወንጀል ፈጽሟል። እኛ የምንፈልገው ነጻነት ነው። ነጻነት፤ ነጻነት፤ ነጻነት" ብሏል።

በመለስ ዘመን፤ የህወሓት መሪዎች ሰብእነትን በእየቦታው ገፈዋል። በግል ደረጃ፤ መለስ የራሱን ጎሳ "እንቁ፤" አማራውን "እህያ" ብሎ ተሳድቧል። ተቃዋሚዎቻቸውን ሁሉ አዋርዷል። ግለሰቦችን ባልሰሩት ወንጀል ይቅርታ ጠይቁኝ ብሏል። ስለዚህ፤ ሌላ ሰው "መለስ አምባገነን ነው--የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገው ነጻነት ነው" ቢል የተናገረው አግባብ አለው። ለራሱ የበላይነት ማንም እንዲንበረከክ የሚያደርገው መለስ ከቆመበት የሰመጠው ሰእል በታሪክ ይታወሳል። ያሳየው የአመራር ውርደትን ነው። መልእክቱ ግን በመለስ አያልቅም። የስርአት በደል አንድ ግለሰብን በመጥላት፤ በይፋ በማዋረዱ የሚነሳ አለመሆኑን በመጽሃፎቸ አቅርበናል። ለእኛ፤ መልእክቱ የስርአት መጥፎነት መልእክት ነው። "ነጻነት"፤ ሙብት፤ ፍትህ፤ የህግ የበላይነት፤ እኩልነት፤ የመላው ሕዝብ ድምጽና ተሳትፎ ይከበር የሚል፤ የአንድ ጠባብ ጎሰኛ ጠቅላይ ሚኒስትር መሆነክን አቁም፤ መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለ አድሎ አገልግል ወዘተ የሚል ነበር። ያስመሰግናል እንጅ አያስወነጅልም። ማንም ኢትዮጵያዊ ቢሆን ለአገሩ፤ ለመላው ህብረተሰብ የቆመን መሪ በማንኛውም ቦታ አያዋርድም። መለስ ብሄራዊ መሪ (Ethiopian nationalist instead of narrow ethnicist) ቢሆን ኖሮ፤ ውርደቱ ለሁሉም ነበር። ጠቅላይ ሚንስትሩ የመራው መንግሥት "የእነሱ ፓርቲ፤ የእነሱ መንግሥት" ተብሎ እንደሜጠራ ያውቅ ነበር። በምርጫ ዘጠና ሰባት እልቂት አንድ የእንግሊዝ ጋዜጠኛ መለስን "አንተኮ የመላው ኢትዮጵያ መሪ ነህ እንጅ የአንድ ጎሳ መሪ አይደለህም። ሆኖም፤ የምታሳየው ጎሰኛነትን ነው" ያለው ለዚህ ነው። አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ህወሓትንና የሚመራውን መንግሥት "የኔ ፓርቲ፤ የኔ መንግስት" ናቸው ብሎ አለመቀበሉን ጋለፐ ፓል በማስረጃ አቅርቦታል። የጠቅላይ ሚንስትሩ በዓለም መሪዎች ፊት እነደዚህ  መዋረድ (humiliation)፤ የታሪክ ሙሉ ለምጽ መሆኑ አያጠራጥርም። ይህን ሁኔታ የፈጠረው ብቻውን አይደለም። ፓርቲውን አደራጅቶ፤ ተቋሞችን ፈጥሮ፤ ታማኞቹን ቁልፍ ቦታ አስይዞና ኃብታም አድርጎ ነው። ይህ ደራሲ ብዙ ጊዜ ከተቃዋሚዎች ጋር የማይስማማበት አንዱ ነጥብ መለስ ብቻውን አገር ይመራል፤ ያስተዳድራል፤ እሱ ከሌለ፤ አመራሩ ይናዳል በሚል ግምት ነበር፤ እኛ የምንለው፤ ከስርአቱ ውጭ አንድ ግለሰብ ብቻውን አገር አይገዛም ነው። ለጊዜውም ቢሆን፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ "ጉድ"፤ አልፎ፤ "እሰይ" ማለቱ አልቀረም። ወዲያው ወደ ኢትዮጵያ የተላለፈው ቪዲዮ ብዙ መቶ ሺህ ሕዝብ በሞባይል እየተቀባበለ አሰራጭቶታል፤ ቪዲዮው ሲጠቀስ ይኖራል።

ከዚህ ባሻገር፤ አበበ ገላው፤ እንደ አብዛኞቻችን "ምሁራን" በፍርሃት አልተጠመደም። ለግል ጥቅም አልተገዛም። ታሪካችንና ባህላችን የሚያስተምረን፤ ፍርሃትን ሳይሆን ድፍረትን፤ በጎሳና በሃይማኖት መከፋፈልን ሳይሆን አብሮ መኖርን፤ራስ ወዳድነትን ሳይሆን ተካፍሎ መብላትን፤ አገር ማስቀደምን ነው። ደፍረን መነሳት የነጻነት መለኪያችን ነበር። ከግብጾች የበለጠ የነጻነት ታሪክ አለን። ግብጽን የፈጠረች ኢትዮጵያ ናት። አባይ ባይኖር ግብጽ አትኖርም። አብዣኞቻችን ከዚህ የጠባብ ጎሰኛው ስርአት መሪዎች ካዘጋጁልን የፍርሃት ወጥመድ ነጥቀን አልወጠነም። ብንወጣ፤ ኢያትዮጵያ እንደ ግብጽ፤ እንደ ሊቢያ፤ እነደ ቱኒሲያ የፍትሃዊ ስርአት መሰረት ለመጣል ትችላለች። ጋዜጠኛው የሰራው ከነ እስክንድር ነጋ፤ አንዱአለም አራጌና ሌሎች ተመሳሳይ ነው። ለአንድ ቡደን አልተናገረም። የተናገረው በኢትዮጵያዊነቱ ኮርቶ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ነው። ያሳየን፤ የነጻነት ጥቅም በሳንቲም የሚታሰብ አለመሆኑን ነው። ነጻነት፤ በቤት፤ በመሬት፤ በገንዘብ ድጎማ፤ የማይለወጥ መሆኑን አሳይቷል። ነጻነት የሌለው ሰው በራሱ አይተማመንም። አንዳንዱ፤ በሆዱ፤ ለሆዱ ይገዛል። ለፍትህ፤ ለነጻነት፤ ለሰው ክብር፤ በረሃብ ለሚሞቱ ህጻናት መታገል በዶላር ሊተመን አይችልም። ነጻነት ካለ  ለመስራት፤ ለመፍጠር፤ ለመንቀሳቀስ፤ ሃብት ለማግኘት፤ ለመምረጥ፤ ባለ ስልጣናትን "ሃላፊና ተጠያቂዎች ናችሁ" ለማለት ይቻላል። የስልጣን ብልግና የሚያሳዩትን ከስልጣን ለማውረድ፤ ሙሰኞችን በሕግ ለመጠየቅ ይቻላል። ጠባብ ብሄርተኞችን፤ ትምክህተኞችን፤ ለማዋረድ አቅም ይኖራል። የንጹህ ደም አፍሳሾችን፤ ለም መሬት፤ ሴቶች፤ ህጻናት እንደ ተራ ሸቀጥ ቸርቻሪዎችን በሕግ ለመሚገት ይቻላል።

ለህግ የበላይነት የቆመ አገር ወዳድ መሪ፤ ጠቅላይ ሚንስትር መለስ ይለው እንደነበረው፤ "የመንግስት ሌቦች አሉ፤ እናውቃቸዋለን" ብሎ በዛቻ አያልፍም። "በውጭ ሁለት ቢሊየን ዶላር ያስቀመጡ መኖራቸውን እናውቃለን፤ ብዙ ሺህ ቶን ቡና ሲሰረቅ ማን አንደሰረቀ፤ እናውቃለን፤ የእኛም እጅ ስላለበት አንከታተለውም" ማለት ሃላፊነት የሌለው አመራር ነው። ሃላፊነቱን የማይወጣ መሪ "እኔም፤ ፓርቲየም ከህግ በላይ ነን" የሚል ነው። ስለሆነም፤ ችግሩን የፈጠረው የህወሓት አገዛዝ ነው። ሙስናን ለይተን ስናይ የቻይና ጠበብት አንዳለው፤ "አሳ የሚገማው ከራሱ" የሚለው ለህወሓት አዛዦች አግባብ አለው። የህወሓት ስርአት የገማው ከቁንጮው ነው። በመለስ ዘመን፤ መንግሥት ለፍርድ የሚያቀርበው ዝቅተኛ ሙሰኞችን ነበር። "ከቁንጮው ለገማው ስርአት ተጠያቂ መሆን የሚገባቸውን የመንግሥትና የፓርቲ ሌቦች፤ የበላይ ባለስልጣናት አልነካቸውም። ስርአቱ ለቁንጮው መለወጥ አለበት የምንለው ለዚህ ነው።

አገር ወዳዶች በህብረት ያለመነሳት አደጋ

ኢትዮጵያውያን አገራቸውንና መላውን ሕብረተሰብ በጋራና በመፈላለግ የመታደግ ሃላፊነት አለባቸው እንላለን። ዛሬ ኢህ አፓ፤ መኤሶን፤ ኢሴፓ፤ መድረክ፤ ግንቦት ሰባት፤ ቅንጂት ወዘተ የምንልበት ወቅት አይደለም። በኢትዮጵያና በመላው ታታሪ ሕዝቧ ዙሪያ ለፍትህ፤ ለእውነተኛ እኩልነት ለዲሞክራሳዊ ተተኪ ስርዓት በአንድ ላይና በአንድ ድምፅ የምንሰራበት ወቅት ነው። ማንኛውም ፓርቲ በተናጥል ከታገለ የትም አንደርስም። ለህወሓት የበላዮች ሰለባ ክፍተት እየፈጠርን በሆነ ባልሆነው አንስማማም ካልን የትም አንደርስም። የውጭ አገር መንግሥታት ቁም ነገር አይሰጡንም። አበበ ገላው ታሪክ በሰራበት ሳምንት፤ May 19, 2012፤ በካምፕ ዴቪድ፤ ከምርጫ ዘጠና ሰባት ወዲህ ያልታየ አስደናቂ የሆነ ሰላማዊ ሰልፍ ተካሂዷል። የሚዲያ ሽፋኑ ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ መሆኑን አይቻለሁ። የኢትዮጵያን ሕዝብ ሰቆቃ ፈረንጆች እንደመዘገቡት፤"በብዙ መቶ የሚቆጠር"፤ እኔ እንዳየሁት ከሽህ በላይ የልዩ ልዩ የሃይማኖት፤ ፖለቲካና ማህበራዊ ስብሰብ ተወካዮች ድምቀት ባለው ሁኔታ ሰላማዊ ሰልፍ አካሂደዋል። በአንድ ላይ የሰበሰባቸው አበይት ጉዳይ የህወሓት አሰቃቂና አፋኝ ስርአት ነው። የነጻነት፤ የሕግ የበላይነት፤ የሰው ክብር ወዘተ መረገጥ ናቸው። ኢትዮጵያውያንና ደጋፊዎች በደመቀ ሁኔታ ለፍትህ ሲታገሉ፤ የአሜሪካ ፕሬዘደንት ኦባማ፤ ለG-8፤ ስለ ምግብ ዋስትና አስፈላጊነት ያቀረበውን ሃሳብና እቅድ ማጤን አስፈላጊ ነው። በ May 18, 21012 ስብሰባ ላይ እንዲህ ብሏል። "ተከታታይ ረሃብ ጸረ-ፍትህ ነው። (Recurring hunger is unjust). መንግስታት ሁሉ ረሃብን ማጥፋት ተቀዳሚ ተግባራቸው ነው። የምግብ ዋስትናን ጭብጥ ማድረግ የጥበባዊ እድገት አመራር መለኪያ ነው። ሰው ክብሩን የሚጎናጸፈው በእርዳታ ሲኖር አይደልም። ራሱን ሲችል ብቻ ነው። ሰውን በምግብ ለመደጎም የምናደርገው እርዳታ ዘላቂ መልስ ሊሆን አይችልም" ብሏል። በዚህ መጽሃፍ የተከራከርኩት ተመሳሳይ ነው። የቀድሞው የብራዚል ፕሬዘደንት ሉላ ያለውን ያስታውሰናል። "ከሁሉም በላይ ለህሊና የሚዘገንን ጥፋት፤ (the worst of all mass destructions) ረሃብ ነው። የብዙ ሰዎችን ህይወት ያጠፋል። የእድገት ዋና አመራር መሰረት መሆን ያለበት በመጀመሪያ፤ ረሃብን ማጥፋት ነው። ይህ ካልሆነ፤ በማንኛውም ኅብረተሰብ፤ ሰላም ሊታሰብ አይችልም" ብሏል። ፕሬዘደንት ሉላ በአእምሮየ የቀረጸው ሁለት ትዝብቶችን ነው። አንድ፤ ረሃብ ያለንጋ ገረፋ ከሆነ የህወሓት መንግሥት ለምን ይህን ገረፋ አላሰወገደውም። ሁለት፤ የኢትዮጵያ ምሁራን የት ተደበቁ፤ የመጡበትን አገርና በረሃብ አለንጋ የሚገረፉትን ህጻናት፤ እናቶችና አባቶች እንዴት ረሷቸው የሚሉ። ሰላማዊ ሰልፍ ያደረጉት ምን ተከታታይ ስራ ሰሩ?

*ገዢው ፓርቲ የኢትዮጵያን የተፈጥሮ ሃብት ተቆጣጥሮታል*

የኢትዮጵያን የተፈጥሮ ሃብት የሚቆጣጠረው ገዢው ፓርቲ ነው። ፕሬዘደንት ኦባማ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ እንደ ኢስተርሊ ያሉ ምሁራን፤ የእድገት ባለሞያዎች፤ ተቋሞች ሲሉት የቆየውን በመቀበሉ፤ የአሜሪካ እርዳታ በመጨረሻ፤ አሰራሩን የለወጠ ይመስላል። ለምሳሌ፤ ከስብሰባው በኋላ፤ ጀኔራል ሚልስ የተባለው የምግብ አቅራቢ ድርጅት፤ ከአሜሪካ ተራድኦ፤ ከተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅትና ከሌሎች ጋር ሆኖ ለዝቅተኛ አምራቾች የጉልመሳ ድጋፍ መስጠት ጀምሯል። በታንዛኒያና በዛምቢያ ለመቶ ሺህ ገበሬዎች ድጋፍ ሰጥቷል። የአሜሪካ መንግስት ተራድኦ የጀመረው አመራር ደሃውንና የአገር ከበርቴውን እራሱን እንዲችል ማጎልመስ ይመስላል። እኛ በጀርባ ያለውን አላማና እቅድ እንጠራጠራለን። የምንጠራጠረው የኢትዮጵያን ታናናሽ ገበሬዎችና ብሄራዊ ከበርቴዎች በዘመናዊ እርሻ ተሳትፎ ለማጠናከር ከተፈለገ የአገዛዙ አመራር፤ ማለትም መንግስቱ፤ ከጎሳዊ አድሏዊነት ወደ ኢትዮጵያዊነት መለወጥ ይኖርበታል። ይህን የአገዛዝ መሰናክል የአሜሪካ መንግስት በድፍረት አላቀረበውም። በአሁኑ የጎሳዊ መንግስት፤ ኢትዮጵያውያን የአገራቸው የተፈጥሮ ሃብት ባለቤት አይደሉም፤ ካልሆኑ፤ መዋቅራዊ ለውጥ አይቻልም፤ ለአካባቢው ደህንነት ለመጣር አይቻልም። የባለቤትነት ሙብትና ነጻነት የተያያዙ ናቸው። ባለቤትነት ከታገደ፤ ዘላቂነትና ፍትሃዊ ያለው እድገት ሊኖር አይችልም። ከአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግስት ጀምሮ፤ በተለይ በመለስ መንግስት፤ የአሜሪካና የሌሎች ሰብአዊ እርዳታ (Humanitarian aid)፤ ከአስር እስከ አስራ ሶስት ሚሊዮን የሚሆኑ ኢትዮጵያውያንን በምግብ ድጎማ እንዳይሞቱ ማድረግ ነበር። ይህ እርዳታ ከሞት አደጋ ቢጠብቅም ከጥገኛነት ነጻ አላወጣም። ተከታታይ ድጎማ የጥገኛነት መለኪያ ነው። የእድገት መላኪያ አይደለም። የገጠሩን ህብረተሰብ ከድህነትና ከጥገኝነት ነጻ ለማውጣት ፍላጎት ካለ፤ መንግስት ለምን አመራሩን (Policy) ለመለወጥ አልቻለም ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው። በእኛ ግምት፤ ገዢው ፓርቲ ያልለወጠበት ምክንያት ድሃውን ለመቆጣጠር ስለመረጠ ነው። የአመራር ስልት ቢለወጥ፤ ገበሬው የመሬቱና የምርቱ ሙሉ ባለቤት ይሆናል። ሌሎች አገሮች እንዳደረጉት ድጋፍ ቢሰጠው፤ ምርት ያደጋል። የኑሮ ሁኔታ ይሻሻላል። ኢትዮጵያ በምግብ እራሷን ከመቻል አልፋ ምግብ ወደ ውጭ ትልካለች። ገቢ ታገኛለች። ለምርት ያመቸ ለም መሬትና ወንዝ ባይኖር የመሬት መሻማት፤ ነጠቃና ቅርሚት አይኖርም ነበር። ኢንቬስተሮች በዳ ወደሆነው ወደ ሳውዲ አረቢያ ሄደው መሬት አይቀራመቱም። በረሃው ለእርሻ ዋጋ የለውም። የእርሻውን ውጤት ለማሳደግ ከተፈለገ፤ የኢትዮጵያ አምራቾች አቅም መገንባትና ድሃው ሕዝብ የእድገቱ አጋር መሆን አለበት። አምራቹ የመሬቱ ባለቤት መሆን አለበት።

የግል ሃብት ባለቤትነትና ተሳትፎነት ለፍትሃዊና ዘላቂነት ላለው ልማት ቁልፍ ናቸው። ተሳትፎ የሌለበት ኢኮኖሚ የተዛባ እድገት ወልዷል። በሌሎች አገሮች እንደታየው፤ ፍትሃዊ እድገት (equitable development) ከአምባገነን ስርአት ጋር አብሮ አይሄድም። የኢትዮጵያን አስጨናቂ ረሃብንና ድህነትን ለማጥፋት ምኞት ካለ መጀመሪያ የፖለቲካው ስርአት ችግር መፈታት አለበት። አሁን የምናየው ፖሊሲውና መዋቅሩ ከስርአቱ ጋር የተቆራኙ መሆናቸውን ነው። የመንግስት አመራር ችግር ካልተፈታ የምግብ ዋስትና ሊገኝ አይችልም። የG-8ና የG-20 ስብሰባዎች ሲካሄዱ፤ አገዛዝ መሰረት እንደሆነ ውይይት አይደረግም። ለምሳሌ፤ ከአጠቃላይ አነጋገር ውጭ፤ <u>በነጻነት፤ በመልካም አገዛዝና በምግብ ዋስትና ያለውን ቀጥተኛ ግንኙነት</u> ፕሬዘደንት ኦባማ አልነካውም። የዲፕሎማቲክ ፕሮቶኮል አይፈቅድም። በግል ግን ሊያነሳው ይችላል። ዋናው ነጥብ፤ ህወሓት የአሜሪካ ጥቅም አስከባሪ እስከሆነ ድረስ፤ እርዳታው ይቀጥላል። መለስ በህይወት በነበረበት ዘመን የክብር እንግዳ ሆኖ ይጋበዝ የነበረው፤ እንደ ጋና ፕሬዘደንት መድብለ ፓርቲ፤ የህግ የበላይነት፤ የፕሬስ ነጻነት ወዘተ ስላከበረ አልነበረም። ይህ የአሜርካ መለኪያ ቢሆን ኖሮ፤ እንደ ካስትሮ፤ እንደ ሻቬዝ ይኮነን ነበር።

የምግብ ዋስትናን አሰፈላጊነት ካቀርበ በኋላ፤ ፕሬዘደንት ኦባማ፤ አዲስ እቅድ እንደታሰበ ተናግሯል። ኢትዮጵያን፤ ጋናን፤ ታንዛንያን፤ ያቀፈ “A New Agriculture Alliance” ትብብር ተመስርቷል። አላማው፤ የእነዚህን አገሮች ጦም አዳሪ፤ አምሳ ሚሊዮን ሕዝብ እራሱን ለማስቻል ነው። ለዚህ አላማ፤ ሃብታም አገሮች ሶስት ቢሊዮን ዶላር ወጭ ያደርጋሉ። “ዘላቂነት እንዲኖረው ስለሚፈለግ፤ መንግስታት፤ ሊጋስ ድርጅቶች፤ አርባ-አምስት የሚሆኑ የግል ባለ ሃብቶችና ኩባንያዎች፤ ተቋሞች፤ የአካባቢ ስብስቦች፤ ይሳተፉበታል። የዝቅተኛ አምራቾችን ማጎልመስ ያስፈልጋል በሚለው አላማ እንስማማለን። ችግሩ፤ በቤኒ ሻንጉል-ጉሙዝ፤ በደቡብ፤ በአማራ፤ በጋምቤላ፤ በኦጋዴን፤ በአፋር፤ በኦሮሚያ በኦሞ ሸለቆ፤ በዋልድባ የሚካሄደው የውስጥና የውጭ ኢንቬስትሜንት ከዚህ የተለየ ነው። በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ለመብታቸውና ለጥቅማቸው የቆመ አጋር መንግስት የላቸውም። አቅማቸው ካልተገነባ (empowerment and engagement) በውጭ አገሮች ኢንቬስተሮች ይዋጣሉ። ከባለቤትነታቸው ይወገዳሉ። ጋምቤላ እንደሆነው። ለጥቅማቸው ሲታገሉ፤ በመንግስት ይታሰራሉ። የመንግስት፤ የክልል፤ የአካባቢ ተቋሞች ብሄራዊ መሆናቸው አከትሟል። የህወሓት/ኢህአዴግ ተቋሞች ለአካባቢው ነዋሪ አቅም ግንባታ የተመሰረቱ

አይደሉም። እውቀቱ፤ መሳሪያው፤ ገንዘቡ ያለው ከጥቂት የግል ባለ ሃብቶች፤ ከውጭ መንግስታትና ኢንቬስተሮች፤ ከአበዳሪዎች ጋር ነው። አቅም ካልተገነባ፤ ዘላቂነትና ፍትሃዊነት ያለው እድገት አሁንም እውን አይሆንም። ለም መሬቱና ወንዙ ለሃብታሞች። የምግብ ዋስትናውና ትርፉ ለእነሱ። የውጭ ምንዛሬው ለህወሓት ይሆናል። በመጀመሪያ ደረጃ፤ ዋጋ ከፋዩ የአካባቢው ሕዝብ ነው። በተያያዘ ደረጃ፤ የኢትዮጵያ ሸማችና ኢትዮጵያ ይሆናሉ። ተሻሽለዋል ቢባልም፤ ውሎቹ ከጥቅማቸው ጉዳታቸው ያመዝናል። ለገበሬዎች፤ ለኢትዮጵያ ሸማቾች፤ ለአገር ከበርቴዎች ቅድሚያ አይሰጡም። ገዢው ፓርቲ እስካሁን ለብሄራዊ ጥቅም ቀናተኛነት አላሳየም። የአባይ ግድብ ስኬታማነት አመለካከቱን ያሻሽላል የሚሉ መኖራቸው አይካድም። ዋናው ችግር ነዋሪው ሕዝብ በራሱ ለም መሬትና ወንዝ አዛዥ አይደለም። ጠበቃ የሚሆኑት ማህበራዊ ድርጅቶች ታግደዋል። ከመንግስት ቁጥጥር ነጻ የሆነ መገናኛ ብዙሃን የለም። ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች እንዳሉ አይቆጠርም። ቢኖሩም ታፍነዋል። ስደተኛው ለአገሩ ያለው ቁራጥ አቋም ተበታትኗል።

ፕሬዘደንት አባማ ባንግላደሽ፤ ሃይቲ የዝቅተኛ አምራቾች ውጤት እጥፍ አድጓል ያለው ትክክል ነው። በቬትናምም አስደናቂ እድገት ታይቷል። ነገር ግን፤ እነዚህ አገሮች በጠባብ ጎሰኛ ቡድን አይመሩም። በባንግላደሽ ዘመናዊ የመገናኛ ስርጭት ዓለም ያደነቀው ሆኗል። በኢትዮጵያ፤ ህወሓት መገናኛ ብዙሃንን እንደጠላት ይቆጥረዋል። ሊጋሱ የአሜሪካ መንግስትና መሪው ፕሬዘደንት አባማ የኢትዮጵያን ደሃ፤ ዝቅተኛ አምራች (smallholder) ለማጎልመስ ከፈለገ የህወሓት/ኢህአዴግ መንግስት መገናኛ ብዙሃንን ነጻ እንዲያደርግ፤ የመሬት ይዞታ እንዲሻሻል ጫና ማድረግና መምከር አለበት። እርዳታው ሁሉ ለአቅም ግንባታ እንዲውል ማድረግ ይችላል። ከማንኛውም በላይ ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት የሕዝቧ ነጻነት፤ ተሳትፎና የተፈጥሮ ሃብቱ ባለቤትነት ነው። የእርዳታ ፖሊሲው ጥያቄ አስቸኳይ የሆነበት፤ የገዢው ፓርቲ ለቁጥጥር ስለሚጠቀምበት ነው። ኢትዮጵያ ያለ ውጭ ድጋፍ ሕዝቧን ልትመግብ አትችልም በሚል ዘዴ እርዳታውን እየተቀበለ ለስልጣኑ ማቆያና ለምዝበራ ተጠቅሞበታል። እንደ ገና ለማሣሰብ የምፈለገው፤ ከልፈቱ በፊት፤ ጠቅላይ ሚንስተር መለስ፤ በራሱ ጋባዥነት ከታወቀው ሃብታምና ለጋስ ቢል ጌትስ ጋር ስለ ዝቅተኛ 15 ሚሊዮን የኢትዮጵያ አምራቾች አቅም ማጎልመስ ተነጋግረዋል። በሃያ አንድ አመታት የህወሓት አመራር ያልፈታውን የምግብ ዋስትና ጥያቄ ለመፍታት ነው። እርዳታ መጠየቁ አያስደንቅም። አቅም ግንባታ አስፈላጊ ነው። በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ሰቲት ሁመራን፤ አዋሽን፤ አርሲን ወዘተ ያለሙት የውጭ መንግሥታትና ለጋሶች አይደሉም። ኢትዮጵያውያን ናቸው። ሁለት ሚሊዮን ገበሬዎች በልዩ ልዩ መልክ ተሳትፈዋል። ገዢው ፓርቲ ኢትዮጵያውያን ሊሰሩት የሚችሉትን የዘመናዊ እርሻ ስራ ለውጭ መንግሥታትና ኩባንያዎች ሲሰጥ ኢትዮጵያ ምንም ልምድ የላትም ብሎ ነው። ይህ ውሸት ነው።

የመሬት ነጠቃ በጦፈበት ወቅት፤ ብዙ ዓለም አቀፍ ባለሞያዎችና ተቋሞች አደጋውን ሲያስታውሱ፤ መለስ እንዲህ ብሎ ነበር። “እኛ እየተራብን ጠፍ መሬት እይተን ለመደሰት አንፈልግም። መሬታችን ተጠቅመን ራሳችን መመገብ አለብን።” አባባሉ ምንም አያከራክርም። አከራካሪው፤ “እኛ መሬታችን ተጠቅመን” የሚለው ነው። “እኛ” ማለት ነዋሪው ሕዝብ ነው። ለመመራትና ለማረስ የሚፈልጉ፤ ችሎታ ያላቸውን ኢትዮጵያዊያንን ነው? አይደለም፤ የውጭ በግብዣ የገቡ ኢንቬስተሮችንና ምርጥ የትግራይ ተወላጆችን ነው። አንባቢው በጥንቃቄ እንዲመለከተው የምፈልገው፤ የሳውዲ አረቢያን ሚና ነው። ቀደም ሲል፤ የሳውዲ መንግስት ሆነ ብሎ፤ በህወሓት አመራር አማካኝነት ኢትዮጵያ መስፋፋቱን አቅርበነዋል። አሁን ወደ ዋናው ስትራተጅ ልግባ። የሳውዲ አረቢያ የምግብ ዋስትናና የአባይን ወንዝ ለአረቦች ጥቅም ለመቆጣጠር የሚደረገው እሽቅድምድም የወቅቱ መሪ ጥያቄ ሆኗል። ከፈርኦኖች ጀምሮ ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር የተደረገው ወረራ፤ የእርስ በእርስ ጦርነትና ዛሬ የተከሰተውን የውጭ አገሮች የበላይነትና “የይገባኛልነት ፖሊሲ” የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት ብቻውን ሊወጣው አይችልም። የኢትዮጵያን ሕዝብ እምነትና ድጋፍ ማግኘት አለበት። የሳውዲ መንግሥት የዘተበት ራሱ ባመጣው ጣጣ ነው።

የሳውዲ አረቢያ የኢኮኖሚ ዘመቻ በኢትዮጵያ

አረቦች በኢትዮጵያ ላይ ያላቸው የማድከም፤ የማፈራረስና የመቆጣጠር ዘመቻ ከአባይ ወንዝና ከለም መሬት የበላይነት አላማቸው ተለይቶ አይታይም። አንዱ ለአላማቸው የሚጠቀሙበት ዘዴ የኢትዮጵያን የእስልምና ኃይማኖት መሪዎችና ተከታዮች መከፋፈልና ገንዘብ እየሰጡ መቆጣጠር ነው። ሳውዲ አረቢያ የዘይት ባለጸጋ ናት። በተቀማጭ ብቻ ከግማሽ ትሪሊዮን ዶላር በላይ አላት። ብዙ ነገር ለመግዛት ትችላለች። ሆኖም፤ የፈለገው ዘይት ብታመርት ዘይቱን አትበላውም። ምግብ ለማምረት ብትፈልግ ወንዝና ውሃ የላትም። የነበራትን አሟጣዋለች። አንድ ሰሞን ሳውዲ ስንዴ ታመርት ነበር። አሁንም ትንሽ ታመርታለች። ማቆም አለባት። ከብት ታረባ ነበር። የውሃ ችግር ስላለ ማርባቷ እየቀነሰ ይሄዳል። የሳውዲን ሕዝብ የምግብ ፍላጎት እቅድ ማሟላት የሞት የሽረት ጥያቄ እየሆነ ሄዷል። ሃቁን ለማወቅ የሚከተሉቱን ማስረጃዎች እናቀርባለን።

1. ሳውዲ አረቢያ ሊታረስ የሚችል መሬት ያላት፤ ከጠቅላላው፤ አንድ በመቶ ብቻ ነው። የቀረው በረሃ ነው።

2. የሳውዲ መንግስት የሕዝቡ መኖር አለመኖር የሚወሰነው በሌሎች አገሮች ወንዝና ለም መሬት በመግዛት ወይንም በመከራየት ነው ብሎ ወስኗል።

3. ንጉስ አብዱላህ በጥናት ተደግፎ ወንዝና መሬት የሚገኘው አፍሪካ ነው። ኢትዮጵያ ተቀዳሚነት ከሚሰጣቸው አገሮች አንዷ መሆን አለባት ብሎ ወስኗል።

4. ለሳውዲ ኢንቬስተሮች አመራረጥ ጠቃሚ ሆኖ የተገኘው ዋና መለኪያ የተመራጩ አገር የጂኦግራፊ አቀማመጥ (መልክአ ምድር) (Geographical proximity) እና ተሰማሚ ወይንም ተባባሪ የሆነ መንግሥትና በስራ ላይ የሚያውል ጠበቃ ናቸው ብሏል።

5. የሳውዲ ሕዝብ የነፍስ ወከፍ ገቢ $20,000 (2012) ነው። አስተማማኝ እህል እንደሚያስፈልገው፤ በቂ አቅርቦት ከሌለ ሰላም እንደማይኖር ገምቷል።

6. በገልፍ ከሚገኙ አገሮች ሰባ አምስት በመቶ የሚሆነውን የምግብ ሸመታ (Food import) የሚጠቀመው የሳውዲ ሕዝብ መሆኑን በጥናት ደርሶበታል።

7. ቢያንስ፤ ሳውዲ አረቢያ አንድ ሚሊዮን ቶን ሩዝ፤ አንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ቶን ስንዴ በአመት እንደምትሸምት ታውቋል።

8. ሳውዲዎች መዋእለንዋይ በሚያፈሱበት አገር ቢያንስ አምሳ በመቶ የሚሆነው ምርት ለሳውዲ ገበያ መዋል አለበት ብለው ወስነዋል። የህወሓት መንግሥት ግዴታ ገብቷል።

9. ለዚህ እቅድ ደጋፊ የሆነ የሳውዲ የእርሻ ኢንቬትሜንት የሚል በ2008 ተቋቁሟል። ብድር፤ ካፒታል፤ የፖለቲካና የዲፕሎማቲክ ድጋፍ ይሰጣል።

10. ከ2008 እስካሁን፤ ሳውዲዎች በአፍሪካ 800,000 ሄክታር ለም መሬት ተረክበዋል። ከዚህ፤ በጋምቤላ ብቻ የኢትዮጵያ መንግስት 290,000 ሄክታር እነደሚሰጥ ተስማምቷል።

11. የሳውዲን ሰፊ መሬት ነጠቃ በኢትዮጵያ የሚያካሂደው ሼክ ሞሃመድ አላሙዲ ነው። እርሻውን የሚያለማው ድርጅት የሳውዲን መለያ በመጠቀም ሳውዲ ስታር ይባላል። በስምምነቱ መሰረት የመጀመሪያውን የስንዴ ምርት ለንጉስ አብደላህ እንደ ክብር ዋንጫ የሰጠው አላሙዲ መሆኑ ተረጋግጧል። ልክ የዱሮዎቹ ፊርአኖች እንደሚያደርጉት ይመስላል።

12. እስካሁን በጋምቤላ በተሰጠው ለም መሬትና ወንዝ የተነሳ፤ የጋምቤላ ህብረተሰብ ኑሮ በሙሉ ተቃውሷል። የመሬቱን መታወቂያ ከመቀማቱም በላይ አማራጭ አልተሰጠውም። በአዲስ መንደሮች እንዲሰማራ ተገድዷል። ለጋስ መንግሥታትና ድርጅቶች ይኼን ነጠቃ ደጉመዋል። የኢንግሊዝ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የእንግሊዝ እርዳታ የጋምቤላን ሕዝብ ሰብ አዊ መብቶች ገፏል፤ ይኼ መቆም አለበት ያለው ለዚህ ነው። ሕዝቡ በመማረር መዋጋትና መሟገት ጀምሯል። ሰላምና እርጋታ ጠፍቷል። በApril, 2012, ነዋሪዎቹ አዳማጭ ስላጡ፤ በትጥቅ፤ በሳውዲ ስታር መስሪያ ቤት ገብተው አምስት የድርጅት ሰራተኞች ገድለዋል። ነጠቃው ካላቆመ ሰላም እንደማይኖር አስጠንቅቀዋል። 43/

ኢትዮጵያ በታሪኳ ሰላም አግኝታ አታውቅም። የዚህ ዋና መነሻው የአባይን ወንዝ ለመቆጣጠር የሚፈለጉ፤ የቀይ ባህርን በር ለኢትዮጵያ ጥቅም ለመዝጋት የተመኙ፤ አገሪቱ በእርስ በእርስ ጦርነት እርጋታ እንዳይኖራት የሚጥሩ መንግስታት ጣልቃ ስለገቡ ነው። እድገቷን፤ ብሄራዊ አንድነቷን፤ ህብረተሰብአዊ ቁርኝቷን ሲፎካከሩት ቆይተዋል። የኢትዮጵያ መሪዎች ለአገራቸው ቀና በመሆናቸው የመጣባቸውን ጠላት ሁሉ ተቋቁመው ለአሁኑ ትውልድ አስተላልፈዋል። ዛሬ፤ ይህ ብሄራዊ ወኔና ህብረት በፍጥነት እየተናደ ነው። የሳውዲ አረቢያ የመሬትና የወንዝ ነጠቃ (Massive land grab) ከዚህ የብሄራዊ ስሜት መናድ ጋር የተያያዘ ነው። ሳውዲ አረቢያና ሌሎች የአረብ አገሮች በዘይት ሃብት የተመረቁ ቢሆኑም፤ ዝናብና ወንዝ የላቸውም። የእርሻ መሬትና ውሃ ከሌላቸው፤ አማራጭ መፈለግ ብሄራዊ ግዴታቸው ነው። ምግብ ካላገኙ ህልውና አይኖራቸውም። አሸዋና ዘይት ሊበሉ አይችሉም። የሚሸጡትን ዘይት ተጠቅመው የእርሻ መሬት መግዛት ወይንም መከራየት አለባቸው። የእነሱ የምግብ ዋስትና የአከራዮችን ሕዝብ ኑሮ ቢያናጋ፤ ለእነሱ ፋይዳ የለውም። ጋምቤላ የዚህ፤ ኢሰብአዊ የሆነ ከዘመኑ ካፒታል ስርጭት ጋር የተያያዘ በደል የተከሰተበት ነው። ክልሉ፤

ከኢትዮጵያ ክልሎች በጣም ወደኋላ የቀረ፤ በድህነት የሚሰቃይ ክፍለ ሃገር ነው። ሆኖም፤ ያለው የተፈጥሮ ሃብት ድህነትን ለማጥፋት የሚያስችል ነው።

*ለተፈጥሮ ሃብት ምዝበራ የመንግሥት ድጋፍ ቁልፍ ሆኗል*

ባለፉት ሶስት ሺህ አምስት መቶ አመታት ያልተደፈረው የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሃብት እንዴት ለሳውዲ አረቢያና ለሌሎች በቀላሉ ሊተላለፍ ቻለ? የሳውዲ አረቢያ መንግስት ከኢትዮጵያ የሚፈልገው ውሃ፤ ወንዝና ለም መሬት ነው። ይህን ለማድረግ የህወሓትን የበላዮች፤ በተለይ የመለስ ዜናዊይን ወዳጅነት ተንከባከቦ አጠነከረ። የኢትዮጵያ ጅኦግራፊያዊ አቀማመጥ ረዳው። የንግድ ግንኙነት፤ የሳውዲ መንግስት ለኢትዮጵያ ነዳጅ ማቅረቡ ወዘተ ግንኙነቱን አጠነከረው። በየትኛውም አገር እንደሚደረገው፤ የሳውዲዎችን ኢንቬስትመንት ለማጠናከር ወዳጅ፤ አስተባባሪ፤ ተሰሚነትና ታማኝነት ያለው ግለሰብ አስፈለገ። ሞሃመድ አላሙዲ ለዚህ ተስማሚ ሆኖ ተገኘ። በኢትዮጵያ የሚያንቀሳቅሰው የራሱን ካፒታል ብቻ አይደለም። የአረቦችን ካፒታል ጭምር ነው። በጋምቤላ በቀላሉ መጀመሪያ አስር ሺህ ሄክታር መሬት ሲረከብ፤ በሳውዲ አረቢያ ስም ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት በጋምቤላ ብሄራዊ የሆነ፤ የሚጠበቅ መዝናኛ ለትውልድ እንዲተላለፍ፤ ነዋሪዎችም አሳ በማጥመድ፤ ጎብኝዎችን በማስተናገድ ይጠቀሙበታል ተብሎ የተቋቋመውን የጋምቤላ ናሺናል ፓርክ፤ ሳውዲ ስታር የተባለው ድርጅት ለሳውዲዎች ምግብ ማምረቻ ወደ ትልቅ የእርሻ መስክ ለውጦታል። የናሽናል ጂኦግራፊክ ዜና አቀባይ፤ ፍሬድ ፒርስ እንዳስቀመጠው፤ በጋምቤላ የሚካሄደው የተፈጥሮ ጥሪት ውድመትና የነዋሪዎች መፍለስ፤ "ለውሃና ለእርሻ መሬት ጥቅም ነው። ሳውዲዎች፤ ምንም ይምጣ፤ ሕዝባቸውን ለመመገብ ወስነዋል። ዘይት ለሙብላት አይችሉም። <u>የሚችሉት፤ ከዘይት የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬ ተጠቅመው፤ እንደ አባይ ያሉ ወንዞችንና ለም መሬቶችን መቆጣጠር ነው።</u>" 44/

የሳውዲው ንጉስ አብደላህ፤ በጥናት የተመሰረተ የሕዝብ ምግብ ዋስትና እቅድ ለተከታታይ ትውልድ ቀርጿል። ያለውን ገንዘብ ተጠቅሞ ወዳጅ መንግስታት እንደሚያገኝ አስቦ ነው። መለስ ዜናዊ ከወዳጆቹ አንዱ ነበር። "እኛ ጠፍ መሬት እያየን መደሰት አንፈልግም፤ መሬታችንን አልምተን እራሳችን ለመመገብ እንጠቀምበታለን" ብሎ ነበር። ሆኖም ዋና ተጠቃሚዎች የሚሆኑት የውጭ አገር ኢንቬስተሮችና ወገኖቻቸው መሆኑን አልተናገረም። የሳውዲ መንግስት የተዋዋለው፤ ቢያንስ አምሳ በመቶ የሚሆነው ምርት ለሳውዲ ገበያ እንደሚቀርብ ነው። የኢትዮጵያ መንግስት የተዋዋለው የሳውዲን ህብረተሰብ የምግብ ዋስትና የተረጋገጠ ለማድረግ ነው። በጣም አስጊ የሆነውን የለም መሬትና ወንዝ ዘላቂነቱ አስተማማኝ የሚሆነው ተቆርቋሪ ባለቤት ሲኖረው ነው። የአዲስ "ቅኝ ገዥነትን" አደጋ የተረዳው የደቡብ አፍሪካ ስታንዳርድ ባንክ ልዩ ጥናት አድርጎ ያቀረበውን ከመለስ አባባል ጋር እናመሳክረው። ይህ ለታሪክ አስፈላጊ ነው። ማን ተጠቃሚ፤ ማን ተጎጂ እንደሆነ ለማወቅ የምንችለው እውነቱን ከውጭ ታዛቢዎች አንጻር ስንመረምር ብቻ ነው። እኛ ያደረግነውን ህወሓት እና ደጋፊ መንግስታት አልተቀበሉትም። "የአፈሪካ አገሮች ሳይመረምሩና ለራሳቸው ህብረተሰብ የሚያገለግል ውል ሳይፈራረሙ የሳውዲ አረቢያን የእርሻ ድርጅቶች መጋበዝ የተፈጥሮ ሃብትን ጥቅም አለማወቅና በእውቀት ያልተዘጋጀ ድርድር ነው። መሬቱ ያረፈበት አፈር ለእድገትና ለሰው ህይወት እጅግ አስፈላጊ ነው። ከሳውዲዎች ጋር የሚደረግ ተመሳሳይ ውል በጣም አደገኛ ነው። (Inability on the part of government leaders to understand "agricultural assets --both land, and perhaps more critically, water--remains a profound threat)." 45/

ፍሬድ ፒርስ፤ ሰርቫይቫል ኢንተርናሺናል፤ ሂዩመን ራይትስ ወች፤ ኦክላንድ ኢንስቲቲዩት በተደጋጋሚ በጥናት ያመለከቱት የሳውዲዎች ሆነ የሌሎች ጥቅም፤ አፍሪካዊያንን ይጎዳል። አገሮችን ለእርስ በእርስ ጦርነት ይዳርጋል። ረሃብን ያባብሳል። የአካባቢውን አየርና ተፈጥሮ በማይመለስ ደረጃ ይለውጠዋል የሚል ነው። ሳውዲ ስታር ለንጉስ አብደላህ አገር አንድ ሚሊዮን ቶን ሩዝ፤ ተጨማሪ ገብስ፤ ቦቆሎ፤ የስኳር አገዳ ወዘተ ሲያመርት ለነዋሪው ሕዝብ ግልጽና ህይወት አሻሻይ የሆነ አስተዋጽኦ ምን እንዳቀረበ አይታወቅም። ነዋሪውን "መሬትክን ልቀቅና አዲስ መንደር ስፈር" ማለትና ከበፊቱ የተሻለ ኑሮ ትኖራለህ፤ ልጆችህ ያልፍላቸዋል፤ ክልሉ ዘመናዊ እድገት ይቀዳጃል፤ አካባቢው ይጠበቃል፤ ለተከታታይ ትውልድ ያገለግላል ማለት የተለያዩ ናቸው። የሳውዲ መንግስት የኢትዮጵያን ለም መሬትና ወንዞች በመንግስት ድጋፍ በመረከብ ላይ ያለበት የኢኮኖሚ እና የማህበረሰብ ምክንያት ግልጽ ነው። የእርሻ መሬትና ውሃ የለውም። የማያልቅ የሚመስል የውጭ ምንዛሬ ስላለው ተባባሪ መንግስታትን "ለመግዛት" እችላለሁ የሚል ግምት አለው። ለዚህ፤ የኢትዮጵያ ድህነት፤ ኋላ ቀርነትና መከፋፈል፤ የጠባብ ጎሰኛ አገዛዝ የማይገኝ እድል ከፍቶለታል። በናይል አካባቢ ሰፋት ያለው የመሬት ነጠቃ እድል ቢያገኝ አያስደንቅም። የሚያስደንቀው፤ የኢትዮጵያ መንግስት ግብዣና "እልል" ብሎ ያለ ምንም ገደብ መቀበሉ ነው። የሳውዲዎች የምግብ ዋስትና፤ ለነዋሪዎች ድህነት መነሻ ሆኗል። ያልለማ መሬት አለ የተባለው የመንግስት ወሬ እውነት ነው ብለን ብንቀበል፤ እስካሁን ባለው ዘገባ፤ የለማው መሬት

የምግብ ዋስትና የሚሰጠው ለሳውዲዎች፤ ለህንዶችና ለሌሎች ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ የምግብ ዋስትናስ የት ደረሰ? ነዋሪዎቹስ የት ይድረሱ፤ እንዴት ይኑሩ? ማን ለነሱ ሃላፊነት ይውሰድ?

ፍሬድ ፒርስ ስለጋምቤላ መሬት ነጠቃና ስለ ነዋሪዎች ስቃይ ሲመራመር እንዲህ ብሏል። “መለስ ዜናዊ፤ ለምን ግልጽነት በሌለው፤ አድሏዊና ጎጂ በሆነ መንገድ ለም መሬትና ወንዝ ለወዳጅህ ለሼክ አላሙዲ ሰጠህ” ተብሎ ተጠይቆ ነበር። “ሁልጊዜ ለማንኛውም ጥያቄ በፍጥነት መልስ የሚሰጠው መለዝ ዜናዊ (Meles Zenawi who had an instant answer to those who criticized his largesse to his Saudi friend, Sheikh Al-Amoudi)” ያለምንም ማመናታት፤ “የምግብ ዋስትና” ለማግኘት ነው አለ። ሌሎች በምርምር የደረሱበት ዘገባ፤ ይህ ስጦታ አደጋ ያለው መሆኑ ሲነሳ፤ መለስ ለዚህም መልስ ነበረው። ቢያንስ ሶስት ሚሊዮን ሄክታር ለውጭ ኢንቬስተሮች እንደሚሰጥ፤ ካስፈለገ ልገሳው እንደሚጨምር ተናግሮ ነበር። ግልጽ ያልሆነልኝ፤ የእድገቱ መሰረተ ሃሳብ ምንና የት ላይ እንደሆነ ነው።” 46/

ሼክ አላሙዲ ለንጉስ አብደላህ የጋምቤላን ስንዴ ሲያበረክት ከጀርባው የመለስና የህወሓት ሙሉ ድጋፍ እንደነበረው አረጋግጦ ነው። ለገዢው ፓርቲ ማሸነፍ ገንዘብ ያወጣበት፤ ፓርቲውን ሙሉ በሙሉ የሚደግፍበት ዋናው ምክንያት የራሱንና የሳውዲ መንግስትን ዋና ግብ ለመፈጸም ስላስቻለው ነው። በአንጻሩ፤ ልዩ ልዩ ጥናቶች የሚመክሩት፤ አብዛኛው (A generous portion of crops produced by foreign owned firms--should be guaranteed for the local market). በኢትዮጵያ “በውጭ ኢንቬስተሮች የሚመረተው እህል ለነዋሪውና ለሕዝቡ መቅረብ አለበት” የሚል ነው። 47/

እኛም የምንከራከረው ለዚህ አላማ ነው። ኢትዮጵያውያን የተፈጥሮ ሃብረታቸውና የምርታቸው ባለቤትና ተጠቃሚ መሆን አለባቸው የሚል እምነት አለን። መብታቸው ነው። በአላሙዲ የሚመራው ሳውዲ ስታር አንድ ሚሊዮን ቶን ሩዝና አንድ ሚሊዮን ቶን ስንዴና ሌላ ጥራጥሬ አምርቶ ለሳውዲ ገበያ ለማቅረብ ውል ገብቷል። ውሉ ለነዋሪዎችና ለኢትዮጵያ ሕዝብ የምግብ ዋስትና እንደማያስገኝ ያሳያል። ለሁሉም መልስ ስላለው፤ ህወሓት የሚለው “የውጭ ምንዛሬ ስናገኝ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በዓለም ገበያ ሽምተን ምግብ እናቀርባለን” ነው። አንባቢው የዚህን አይነት የኢኮኖሚ አመራር፤ የእንግሊዙ ኢኮኖሚስት እንዳለው “ድንቁርና” ለማየት ይችላል። የተባበሩት መንግስታት የምግብ ፕሮግራም ( World Food Program) ለኢትዮጵያ ረሃብተኛ በአመት የሚያወጣው በገንዘብ ሲተመን፤ ሳውዲዎች በጋምቤላ ለማምረት ከሚያወጡት ኢንቬስትሜንት አያንስም። በኢትዮጵያ ከውጭ ምግብ ለመግዛት የሚወጣው ገንዘብ በጋምቤላ ወዘተ ዘመናዊ እርሻ ልማት ቢውል ነዋውሪዎች ይጠቀማሉ። ኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና ይኖራታል። አካባቢዋ ሃላፊነት ባለው መንገድ ከጥቅም ላይ ይውላል። ስለሆነም፤ ችግሩ የገንዘብ እጥረት አይደለም። የመንግሥት ስህተተኛ የፖሊሲ አመራርና የገንዘብ አጠቃቀም ፈሰስ ነው። የህወሓት አመራር በፍጹም የሳተው፤ በእድገት ስም፤ የአካባቢውን ደህንነት አለመንከባከቡ ነው። የአክላንድ ኢንስቲቱት ደጋግሞ እንዳሳሰበው፤ የኢትዮጵያ መንግሥት፤ በማንኛውም ልማት፤ አንድም አይነት “የአካባቢና የህብረተሰብ ደህንነት ጥናት አድርጎ አያውቅም።” ለአካባቢው ማን ሃላፊነት ይወስዳል? ለተከታታይ ትውልድ ጥቅምስ?

ሪኔ ሌፎርትና ሌሎች እንዳሉት፤ የተፈጥሮ ሃብት ሽሚያ የጎሳዊ ጥላቻን እያስፋፋና አገሪቱን ወደ አደጋ እየወሰዳት ነው። በክልል ከሚመራ አስተዳደር የመጣው አደጋ የሚያሳየው ለነዋሪዎችና ለአካባቢው ብሄራዊ አመራርና አገር አቀፍ ተቆርቋሪ አለመኖሩን ነው። የሳውዲ አረቢያ የበላይነት ማህበረሰባዊ ስርአቱን እየጎዳ የሚሄድ መሆኑን ያሳያል። ብሄራዊ ተቋሞች ቢኖሩ፤ቢያንስ አደጋውን ይቀንሱታል። ለጋስ አገሮችና አበዳሪዎች ሊያዩት ያልቻሉት ከላይ የተጠቀሰውን የመሬት ነጠቃ አደገኛነት ነው። ኢትዮጵያውያን ለማሟላት የሚችሉትን፤ ግን ያልተፈቀደላቸውን፤ የህንዱ ካሩቱሪ፤ የሳውዲው ሳውዲስታር ያሟላሉ ማለት በሕዝብ ህይወት ላይ መቀለድ ነው። እስካሁን፤ ለቁጥጥር የተዘርጋው በእርሻ ልማት ላይ የተመሰረተ ልማት ውጤት አላሳየም። የምግብ ዋስትና በውጭ ኢንቬስተሮች ይገኛል ብሎ አዲስ መንገድ መሻት ሌላ በፍጹም ያልተሰበ አደጋ እያመጣ ነው። ዘላቂነት ያለው አማራጭ የኢትዮጵያን ገበሬዎች ከአንድ ፓርቲ ቁጥጥር ነጻ ማውጣት ነው። የመሬታቸው ባለቤት እንዲሆኑ የመሬት ይዞታን ፖሊሲ መለወጥ ነው። አቅማቸውን በዘላቂነት መገንባት ነው። ይህ ከሆነ፤ ምርት እያደገ ይሄዳል። ኢትዮጵያ ምርቷን ለሳውዲ ገበያ ለማቅረብ ትችላለች። ቢል ጌትስ፤ ጄኔራል ሚልስ ወዘተ፤ በቀጥታ አምራቹን ካጎለመሱ ውጤት ይገኛል። በሰፋፊ የንግድ እርሻ ላይ የተሰማሩት የውጭና የውስጥ ተጠቃሚዎች፤ በአብዛኛው፤ ስራቸው ትርፍ ነው። የምግብ ዋስትና አይደለም። ወጣቱንና ደሃውን ቀጥረው ጥሩ ደመወዝ መክፈል አይፈልጉም። ትርፍ ስለሚቀንስ። የገዢው ቡድንና የትግራይ አዲስ ሃብታሞች፤ በግብዣ የመጡ ትርፍ ፈላጊ ኢንቬስተሮች፤ ከነዋሪው ሕዝብ ተሳትፎ ውጭ የሚሰሩት ድህነትንና ረሃብን ሊያስወግዱ የማይችሉ መሆናቸውን አንጠራጠር። የሚሰሩት ለትርፍ ነው። የሚያመርቱት ለውጭ ገበያ መሆኑን

አሳይተናል። Guardian, Human Rights Watch, Suvival International, Friends of the Earth, Oakland Institute ወዘተ የደረሱበት ድምዳሜ ተመሳሳይ ነው።

ከኢትዮጵያ ሕዝብ ባለቤትነትና ቁጥጥር ውጭ የሆነው የዚህ አይነት የኢኮኖሚ አመራር ጉዳቱ ከፍተኛ ነው። በቀጥታና ወዲያው የሚጎዱት፤ ነዋሪዎች ናቸው። ሆኖም፤ ችግሩ ብሄራዊ ነው። ፖሊሲው እንዳለ ከቀጠለ፤ የምግብ ዋስትናን ችግር ለማስወገድ የአሜሪካ መንግስት ያቀረበው የመንግስትና የግል ትብብር ያለውን ስርአታዊው ችግር ሊያስወግደው አይችልም። ችግሩ ፖሊሲና መዋቅራዊ ስለሆነ። ምክንያቱም፤ መንግስት የችግሩ አካል ነው። የውጭ ሃብታሞች ከፖለቲካ አገዛዝ የመነጨን የፖሊሲና መዋቅራዊ ማነቆዎች ለመለወጥ አይችሉም። ለዓለም ገበያ የምግብ ዋስትና መፍጠር አስፈላጊ መሆኑ አያከራክርም። ክርክሩ ማን ዋጋ ይከፍላል። ጥቅሙን ማን ያገኛል የሚለው ነው። በምግብ ዋስትና የሚደረግ ኢንቬስትመንት ለትርፍ ፈላጊወች በጣም ይጠቅማል። ስለዚህ የግል ኢንቬስተሮች ቢደግፉት አያስገርምም። የእኔ ነጥብ፤ ፖሊሲው ነዋሪውን ሕዝብ ማሳተፍና የበላይነት እንዲኖረው ማድረግ አለበት ነው። ለመሬት ላራሹ ብዙ ትግል የተደረገውና ብዙ ዋጋ የተከፈለበት ኢትዮጵያውያን የመሬታቸው ባለቤት እንዲሆኑ ነው። መሬቱና ከመሬቱ ስር ያለው የነዋሪውና የሃገሪቱ አንጡራ ሃብት መሆናቸው በሕግና በውሎች ግልጽ መሆን አለበት። በG-8 and G-20 ስብሰባዎች፤ ፕሬዘደንት ኦባማ የነዋሪዎችን መብትና ተሳትፎ ከቃላት ባሻገር ዋጋ አልሰጠውም። የሳውዲና ሌሎች ኢንቬስተሮች በአፍሪካ የሚያደርጉትን የተፈጥሮ ሃብት የበላይነት ፈጽሞ አልጠቀሰውም። ኢትዮጵያውያን በራሳቸው አገርና የተፈጥሮ ሃብት ላይ ለማዘዝ አለመቻላቸው ያመጣውን አደጋ የተመለከተው የለም። ከላይ እንዳቀረብነው፤ የባለቤትነት ጥያቄ የመኖር አለመኖር ጥያቄ ሆኗል። መሰረታዊ የሆነ የመብት ጥያቄ ነው። ለዚህ አደጋ (National Threat) ተቀዳሚ ተጠያቂ የገዢው ፓርቲ የበላይ መሪዎች ናቸው። ይህን ስርአት የዓለም መንግስታት በስብሰባ ሊለውጡት አይችሉም። ለመለወጥ የሚችለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። እንዴት፤ መብቱ ይከበር በማለት። በውጭ ያለው ስደተኛ ለማድረግ የሚችለው ድምጽ ማሰማት፤ ገዢው መንግሥት ፖሊሲውን እዲለወጥ ማጋለጥ። ጥናታዊ ዘገባ አያዘጋጁ የዓለምን ህብረተሰብ ማስተማር። ለውጥ እንዲመጣ መቀስቀስ ናቸው። የተፈጥሮ ሃብት ነጠቃ የመኖር አለመኖር ጥያቄ ነው።

ፕሬዘደንት ኦባማ ስለ ኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና ሲናገር ከ2008-2012 በተከታታይ የወጡትን የተፈጥሮ ሃብት፤ በተለይ የእርሻ መሬትና ውሃ አጠቃቀም ዘገባዎች ያቀረበለት ያለ አይመስልም።  ለምሳሌ፤ ኦክላንድ ኢንስቲቱት ያለውን "በአሁኑ ወቅት ከኢትዮጵያውያን ይልቅ የውጭ ባለሃብቶችና ባለስልጣናት በተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም በራሳቸው አገር የበለጠ ሃይልና ስልጣን አላቸው" ያለውን ድምዳሜ። ስርአቱ ያመጣው ዋናው የአገዛዝ ማነቆ ነው። የውጭ አገር ባለሃብቶችና ታማኞች አፈናውን ተጠቅመውበታል። ስርአቱን ስለሚረዳው የገዢው ፓርቲ አለቆች ኢትዮጵያውያን በራሳችው አገር ቢናቁ፤ ቢራቡ፤ ታዛዥና አጎብዳጅ ቢሆኑ፤ ወጣት ሴቶች በአረብ አገሮች ቢዋረዱ፤ ምንም አይሰማቸውም። ተቃዋሚወች ያለው አመራር ኢትዮጵያውያን ከድህነት፤ ከረሃብ፤ ከጥገኛነት ሊያወጣት የሚችል አይደለም የሚሉት ለዚህ ነው። የእርሻ መሬት ሃብትና ወንዝ፣ ማእደንና ሌሎች የኢኮኖሚ አውታሮች ቀስ በቀስ ከአገርና ከኢትዮጵያውያን እጅ ወደ ሳውዲዎችና ሌሎች ፈረንጆች፤ ወደ ጥቂት የትግራይ ተወላጆች ተላልፈዋል። ይህ ለተከታታይ ትውልድ አደጋ አለው። ለተማረው ክፍል በታሪክ ያስጠይቃል። የተፈጥሮ ሃብትና ጥሪት ለመያዝ፤ ተሳትፎና የመወሰን እድል ምንም የሌለው ሕዝብ፤ ደሃ ነው፤ ደሃ ሆኖ ይቆያል። በአገሩ ሊኮራ አይችልም። በተፈጥሮ ሃብቱ ስለማያዝበት፤ ከገንዘብ ድህነት የባሰ የመንፈስ ድህነቱ ያጠቃዋል። ሰባ ስድስት በመቶ የሆነው የተማረ ክፍል፤ ብሰደድ ይሻለኛል የሚለው አገሩን ጠልቶ አይደለም። ስርአቱ ስላፈነው፤ በአገሩ ሰርቶና ኮርቶ፤ ተከብሮ ለመኖር ስላልቻለ ነው። ስደት ዋጋ ይከፈልበታል። በአብዛኛው ሲታይ፤ ስደት የኢትዮጵያውያን እጣ ሆኗል። የአብዛኛው ወጣት ትውልድ ደህ ሆኖ የመቆየት እድሉ ከፍ ያለ ነው።  ገዢው ፓርቲ የእርሻ መሬትና ወንዝ፤ ማእደንና ፋብሪካ ከኢትዮጵያውያንና ከማህበረሰቡ ወደራሱ ተቋሞችና ደጋፊዎች፤ ወደ ውጭ ኢንቬስተሮች ሲያዘዋውር የሚያገኘውን አዲስ ባለጠጋነት ያውቃል። ባለጠጋነት ለማዘዝ ይረዳል። ይህ የሃብት ዝውውር ድጋፍን ከኢንቭስተሮች ያመጣለታል። የሳውዲ መንግስት የገዢው ፓርቲ መሪዎች ወዳጅ የሆነው በጥቅም ግንኙነት ነው። ከውጭ መንግስታትና ድርጅቶች ጋር የቀረበ ግንኙነት መፍጠር፤ ገንዘብ እንደልብ ለማሸሽ ያመቻል። ገዢው ፓርቲ ይህ የገንዘብ ዋጋ ስላለው እንደ ድል ይቆጥረዋል። የጠባብ ጎሰኛው ስብስብ፤ፓርቲ፤ የመንግስት ተቋሞች መቆራኘት ለቁጥጥርና ለዝውውር ጣምራዊ ሆነው ይደጋገፋሉ። የመሬት ሊጋስ መሆን ከገንዘብ ጥቅሙ ያላነሰ የዲፕሎማሲ ጥቅሙ ከፍ ያለ ነው።

ወደ ውስጥ ገባ ብለን ብናይ ይህ ስርአት በራሱ ብቻ የሚሺከረከር አይደለም፤ ብዙ ደጋፊዎችን በጥቅም፤ በጉቦ፤ በማስፈራራት ያቀፈ ነው። ስለዚህ ስርአቱን ከግለሰብ ባሻገርና በሙሉ ስእሉ ማየት ይገባል። የውስጥና የውጭ ተጠቃሚዎችን ባይሰበስብ ኖሮ እስካሁን ባልቆየም ነበር፡፡ በየቦታው፤ በየሕብረተሰቡ፤ ለገዢው ፓርቲ አገልጋይና አጎብዳጅ የሆኑ የጎሳ ደጋፊዎችንና እዝ አስፈጻሚዎችን በጥቅም በመሳብና በመግዛት፤ በመደለል፤ በማስፈራራት ወዘተ

ሰፋ ያለ ድርጅታዊ አቅም አለው። ፍርሃቱና ያለፈው ፕሮፓጋንዳ በጣም ጥልቀት አለው። ግለሶብችና ስብስቦች ከጎሳ-ተኮር አገዛዙ ጥቅም አግኝተናል የሚሉ አሉ። ለሰሚው ግራ የሚሆነው፤ ጥቅም አገኘን የሚሉት ሙብታቸውን እንደ ስጦታ ማየታቸው ነው። ስለሆነም፤ ለለውጥ የሚታገለውን ክፍል አዳክመውታል። በአገር ውስጥ ተገቢ ጥቅም ማግኘት የፓርቲ ስጦታ ወይንም ችሮታ አይደለም። ሙብት ነው። የስራ ውጤት ነው።

በግብጽ፤ በሊብያ፤ በቱኒሲያ፤ በየመን፤ አሁን በሶሪያ እንደምናየው፤ በጥቅምና በማስፈራራት የተደራጀ፤ በጎሰኝነት ወይንም በሌላ አምባገነንነት ቡድን የተበከለ ድርጅት “የእምቧይ ካብ” ሊሆን ይችላል። ሕዝብ አገር አቀፍ በሆነ ደረጃ ከተነሳ በቀላሉ ይናዳል። ይህን በጎሳ መከፋፈል የተዘረጋ “በረከት ሰጥቸሃለሁና ተገዛ” የሚል ስልት እራሱን ለማቆየት፤ መሪዎቹንና ታማኞቹን ሃብታም ለማድረግ የተፈጠረ ነው ለማለት ይቻላል። አንዱ ጎኑ በስልጣን ሃብት ማካበት ሲሆን፤ ከበፊቶቹ የቀዳው መጥፎ ልምድ አለ። የማይካደው፤ በንጉሱ ሆነ በደርግ ዘመናት ከሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች የተመለመሉ የስርአት አገልጋዮች ነበሩ። ሆኖም፤ በእነዚህ አስተዳደሮች በደልና አድሎ አልነበረም ማለት አይቻልም። የአሁኑ አገዛዝ በማንም አገር ታይቶ የማይታወቅ ጎሳዊ አድሎ አለበት። የመውደቂያው አንዱ ዋና ምክንያት አድሎና ሙስና ሆኗል።

ብሄራዊ፤ ሁሉን የሚያስተናግድ አገር ወዳድ አመራር አለመኖሩ ያስከተለውን ጉዳት በአጭርም ቢሆን አቅርቤዋለሁ። የህወሓትን/ኢህአዴግን ስርአት ከማንም የሚለየው ዋናው መለኪያ መነሻው፤ ሂደቱና አሰራሩ ሁሉ ከፋፋይ ነው። በጎሳ ለጎሳ መሆኑ፤ ያተረፈው የኢኮኖሚ ውጤት ለጥቂት ቡደን ጥቅም መሆኑን አሳይተናል። የጠባብ ጎሰኛ ስርአት አደጋ ሁለ-ዘርፍ፤ ሁለ-ገብ መሆኑ በተፈጥሮ ሃብት ጠለፋ ቀርቧል። በጠባብ ጎሰኝነት የተመሰረተው ስርአት የበላይነትን ለማረጋገጥ፤ ብሄረሰቦችን እየከፋፈለና እየመረጠ፤ አንዱን ዛሬ “አለሁልህ፤ ጥቅም አግኝተሃል፤ ድጋፍ ከሰጠህ ትበላለህ፤ ትኖራለህ፤ ትሰራለህ፤ ትማራለህ፤ መሬት ትመራለህ፤ መሬትህን ካልሰጠህ፤ እንደ ጋምቤላና ሌሎች ሕዝብ ወዮልህ” የሚል አገዛዝ ነው። “ፍርፋሬ ማግኘት” ይህን ስእል አይለውጠውም። የሰውን ስነልቦና ገምቶ ብሄራዊ የነበሩትን ተቋሞች ያጠፋበት ምክንያት ክፍተት ለመፍጠር ነው። በአገር ደረጃ ተቆርቋሪ እንዳይኖር ለማድረግ ነው። አገዛዙ ይህ ብቻ እንደማይበቃ አውቋል። ስለሆነም፤ ከእየብሄረሰቡ አዲስ ተጠቃሚዎች መፍጠር ግዴታው ነው። ይህ ከፓርቲው በቸርነት የተሰጠ የሚመስል ድጋፍ ፈጥሮለታል። ሆኖም፤ አዲስ የመጠቃቀም መረብ መዋቅራዊ የሆኑ ችግሮችን ሊፈታ አልቻለም። አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚኖረው “ከእጅ ወደ አፍ” ነው። በአብዛኛው ሲታይ ስርአቱ አገሪቱንና ህብረተሰቡን ለምዝበራ ዳርጎታል። አንባቢው መገንዘብ የሚገባው፤ የተቃዋሚው ክፍል መከፋፈልና መዳከም፤ ህብረተሰቡ ያለውን በሙስናና በአድልዎ የተበከለ አገዛዝ እንደ ተፈጥሮ ህግ እንዲቀበለው አስገድዶታል። የተቃዋሚው ክፍል አብሮ አለመቆም ጥቃት እየፈጠረ ነው። በተፈጥሮ ሃብት ምዝበራ የሚታየው አደጋ የሚያመለክተው፤ አገዛዙ በጭሌነት፤ የጣልያን “ከፋፍለህ ግዛው” የመሰለ የጎሳ ልዩነት ፖለቲካ ባህል ተከሏል። ይህ አደገኛ የአገዛዝ ባህል፤ ያስከተለው ውጤት የተቃዋሚው ክፍል በሃይማኖት፤ በጾታ፤ በእድሜ፤ በዱሮ ታሪክ ችግሮች አዙሪኝ ውስጥ ገብቶ እንዲዋለል አድርጎታል። ኢትዮጵያ እንደ ማንዴላ ያለ ለሁሉም ሙብት፤ ለሁሉም ተስፋ ሰጭ፤ ለሁሉም ዲሞክራሳዊ ሙብት የሚታገል ድርጅትና መሪ ያስፈልጋታል።

ለማጠቃለል፤ የሳውዲ አረቢያንና የሌሎችን አገሮች የመሬት፤ የባህልና ሌላ የኢኮኖሚ የበላይነት ያየሁት ከሶስት አንጻር ነው። አንድ፤ ህወሓት የብሄራዊ ተቋሞችን ከማፈራረሱና ለሰብአዊ ሙብቶች፤ ለፍትህና ለዲሞክራሲ ሁሉ የሚታገለውን ማፈኑ። ሁለት፤ የተቃዋሚው ክፍል ከመድከሙና ከመከፋፈሉ። ሶስት፤የብሄራዊነት፤ ኢትዮጵያዊ ማእከል ለመፍጠር አለመቻሉ፤ ሁሉም በጎሳው ዙሪያ መደበቁ፤ በኢትዮጵያዊነት የመሰብሰብ ባህልና ልምድ መናድ በጅምላ ለውጭ ጠላቶች አመቻች ከመሆኑና ከፈጠሯቸው ብሄራዊ አደጋዎች አንፃር። እነዚህን ብሄራዊ አደጋዎች በቀላሉ ማየት ለብሄራዊ ናዳው አስተዋጾ እንደሚያደርግ አመልክተናል። ሳውዲዎች ነጻ ኮርታ በነበረች አገር ሰፊና አደገኛ የሆነ የእርሻ መሬት፤ የወንዝሮችና የባህል የበላይነት እየያዙ ነው። ህንዶችም እንደዚሁ። እነዚህና ሌሎች ለአገራቸው ሕዝብ የምግብ ዋስትና ሲያገኙ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለማኝና ጥገኛ ሆኖ ይቆያል። የኢትዮጵያ የግል ዘርፍ ሜጩትና በውጭ ኢንቬስተሮች ጫና መበከሉ ለብዙ ሚሊዮን ወጣት ኢትዮጵያውያን የስራ እድል ለመፍጠር አስቸጋሪ ሆኗል። ለዚህ ሁሉ ችግር ገዢውን ፓርቲ ብቻ መውቀስ አያዋጣም። ሌሎቻችን፤ በተለይ ተቃዋሚው ክፍል ይህ ብሄራዊና ማህበራዊ ችግር አሁን ካልተፈታ “ሊለወጥ የማይችል” አደጋ ሊሰበስበው ይገባል። በጋራ ከተሰበሰበና ከሰራ ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ተስፋ ይኖረዋል የሚል ድምዳሜ ደርሰናል።

ምእራፍ አምስት፤ ህወሓት “እድገታዊ መንግሥት” ብሎ የሰየመው አገዛዝ ለአሁንና ለተከታታይ ትውልድ ሊፈታ የማይችል የሚመስል “ደዌና” የመኖር አለመኖር ችግር መፍጠሩን በማስረጃ ያቀርባል። ኢኮኖሚው በአሰደናቂ ሁኔታ አድጓል በሚባልባት ኢትዮጵያ የስራ አልባነት ቁጥር እየበዛና እየባሰ ሄዷል። የወጣቱ እድል ተምሮ መሰደድ ሆኗል።

ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው፤ በመካከለኛው መደብ የታቀፉ ጥረው ግረው የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በቀን ሶስት ምግብ ከመብላት ወደ ሁለት ተሸጋግረዋል። ወጣት ሴቶች እድላቸው ወደ አረብ አገሮች መሄድ ወይንም በአገር ውስጥ ራሳቸውን አዋርደው፤ ሰውነታቸውን ሸጠው፤ በመንገድና በጠለላ፤ ቢበዛ ተዳብለው መኖር ወዘተ ልምድ ሆኗል። ይህ ለኩሩና ለጥቁር ሕዝቦች ሁሉ የነጻነት አርአያ ለነበረች ኢትዮጵያና ለታታሪው ሕዝቧ አሳፋሪ ሆኗል።

## ምእራፍ አምስት

### የህወሓት ማሕበረ ኢኮኖሚ ከባዶ አልጀመረም፤"ሃሰትና ስንቅ እያደረ ያልቅ"

"አምላካችን ያበረከተላትን ይህን ኃብቷን (አባይን) ለሕዝቦቻቸው ሕይወትና ደህንነት በማዋል እንዲጠቀሙበት ከጎረቤት ወዳጅ አገሮች ጋር በሊጋሥነት በጋራ ለመካፈል ዝግጁ ብትሆንም፤ ይህን የውሃ ንብረቷን በቁጥር እየጨመረ ለሚሄደው ሕዝቧና፤ በማደግ ላይ ላለው ኢኮኖሚ ጥቅም እንዲውል ማድረግ የኢትዮጵያ ተቀዳሚና የተቀደሰ ግዴታዋ ነው።"

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፤ ጥቅምት 1957 ዓም

"ረሃብን ለማስወገድ ከተፈለገ፤ ሰብአዊ ሙብቶች መከበር አለባቸው"

The Guardian UK, September 2012

"ልማት የፈለገ ሕዝብ በጥቂት "ቀላዋጮች" ወደ ኋላ መጎተት የለበትም። በተመሳሳይ፤ ለልማት የተሻሻለ መንገድ እፈልጋለሁ የሚል ሕዝብ እጣውን ለጥቂት ሰዎች በአደራ አያስረክብም"

ነጋድራስ ገብረህይወት ባይከዳኝ

አበው ሲቀልዱ "ሃሰትና ስንቅ እያደር ያልቅ" ይላሉ። ህወሓት በበላይነት የሚመራው "እድገታዊ መንግሥት" ለዓለም ህብረተሰብ ያቀረበው ታሪክ የኢትዮጵያ ልማት የጀመረው ከህወሓት/ኢህአዴግ ስልጣን በኋላ ነው የሚል አጠቃላይ ይዘት አለው። ይህ ከእውነቱ የራቀ ነው። የማንም ሃገር እድገት የሚያሳየን ልማት ከትውል ትውልድ ተከታታይ መሆኑን ነው። አጼ አምደጽዮን በ1342 ዓም ግብጾች የሚያደርጉትን አሻጥር በመቃወም "አባይን እገድባለሁ" ብለው ነበር። አጼ ኃይለ ሥላሴም ደጋግመው የአባይ ወንዝ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ኢኮኖሚ መዋል አለበት ብለው እቅዶች አውጥተው ነበር። የአባይንና የሌሎችን ወንዞች ወደ ኃይልና የመስኖ እርሻዎች ማዳበሪያ ልማት ማዋል እርምጃ በመውሰድ ፖሊሲ ህወሓት የመጀመሪያው መንግሥት አይደለም። ኢትዮጵያ ልምድ አላት። ቻይና ዘመናዊ የካፒታሊስት እድገቷን የያዘችው ካለፈው የልማት ታሪኳ ጋር አያይዛ ነው። ኢትዮጵያ ይህን አመልካች የሆነ ታሪክ አላት። የትምሕርት ታሪኳ ከአንድ ሺህ አምስት መቶ አመታት ይልቃል። የአክሱም፤ የጎንደር፤ የላሊበላ፤ የሓረር ወዘተ የታሪክ ቅርሶች የልማት ምልክቶች ናቸው። የአገር ውስጥና የውጭ ንግድ፤ ከከፋ ጀምሮ እስከ ምጽዋ፤ ከሓረር እስከ አድዋና አስመራ፤ ከጂቡቲ እስከ ጎንደር፤ በውጭ እስከ መካከለኛው ምስራቅና ሰሜን አፍሪካ ሲካሄድ ቆይቷል። የቅመም፤ የወርቅና የዝሆን ጥርስ ንግድ የተስፋፋ መሆኑን ታሪክ ይመሰክራል። የውጭ ንግድ የብዙ ሺህ አመታት ታሪክ አለው። ይህን ልምድና ባህል እንደማይጠቅም አድርጎ ማጥፋት ለልማት አይበጅም። ዘመናዊይነት ባህልን፤ ልምድን፤ ታሪክን፤ የህብረተሰብ መቆራኘትን ማስወገድ አይደለም። ባህላዊ የሆኑ ቅርሶች የኢኮኖሚ ጥቅም አላቸው። የጥፋት ፖለቲካ ባህል አብሮ የሚያጠፋው የማይተካ ጥሪትን ነው።

የኢትዮጵያ ዘመናዊ ልማት (Modern Development) ቅድመ-ህወሓት/ኢህአዴግ መሆኑን የሚያመለክቱ ማስረጃዎች አሉ። ይህ ታሪክ ባለፉት ሃያ ሶስት አመታት ለተደረገው እድገት መሰረት ሆኗል። ህወሓት/ኢህአዴግ ከባዶ ወይንም ከዜሮ አልጀመረም። በአንዳንድ የልማት መለኪያዎች ሲታይ፤ እንዲያውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደኋላ ተጎትቷል። ለምሳሌ፤ በማይመለስ ደረጃ ጎሳዊነት ምስፋፋቱ። ባለፉት ሃያ ሶስት አመታት የተደረገውን እድገትና ልማት ለማወዳደር የሚቻለው ከደርግ የጦር/የዘመቻ ኢኮኖሚ ጋር በማነፃፀር አይደለም። አይነፃፀሩም፤ ደርግ የአገሪቱን ህልውና ለመጠበቅ፤ "የእናት አገር" ጥሪ እያለ ያደረገው የገንዘብ ወጭ ከልማት ላይ ቢውልና ፖሊሲው የግል ክፍሉን ባያቀረቁዘው ኖሮ በብዙ ዘርፎች አስደናቂ ልማት ይካሄድ ነበር። በተለይ በመሰረተ ልማት። ለምሳሌ ትምህርት። የተባበሩት መንግስታት ዮኔሥኮ (UNESCO) በ 1984 ለኢትዮጵያ ሽልማት የሰጠው የትምኅርት ሽፋን ስለሰፋ ነው። ማንበብና መጻፍ የሚችለው ስድሳ በመቶ ደርሶ ነበር። አሁን ወደኋላ ተመልሷል። ለዚህ መሃይምነትን ለማጥፋት አስደናቂ አስተዋጾ ያደረገው "ለእድገት በህብረት" የዘመተው ወጣት ትውልድ ነበር። ሕዝብ ለአገሩ ሲንቀሳቀስ አስደናቂ ውጤት ያመጣል ማለት ነው።

### የልማት መሰረት መቼ ተጣለ?

አጼ ቴዎድሮስና አጼ ዮሓንስ ያተኮሩት የኢትዮጵያን ግዛታዊ አንድነት ለመጠበቅ ነበር። የኢትዮጵያ ደህንነት ከዘመናዊ ልማት ጋር አብሮ መሄድ አለበት ብለው ዘመናዊ የጦር ሃይል ለማቋቋምና በዘመናዊ አገር ወለድ መሳሪያ መረዳት አለበት ብለው የሞከሩት አጼ ቴዎድሮስ ናቸው። አጼ ቲዎድሮስ የአገር አንድነት ያለ ዘመናዊ የኢኮኖሚ ልማት የማይቻል መሆኑን የተረዱ መሪ ነበሩ ለማለት ይቻላል። ከእነዚህ መንግሥታት በፊት የሆነውን ሙከራና ታሪክ ወደ ጎን አድርገን፤ የልማት ግስጋሴን ታሪክ ሂደትና ውጣ ውረድ ለማየት እንችላለን። አጼ ምኒልክ ለኢትዮጵያ ካደረጉት የአድዋ ድል ሌላ የሚያስመሰግነው፤ ዘመናዊ መገናኛ (ቴሌና ሃዲድ)፤ ትምህርት፤ ባንክ፤ ዘመናዊ ከተማ (አዲስ አበባ) ወዘተ ማቋቋማቸው ነው። ከሁሉም <u>መንግሥታት በተቀዳሚ ለኢትዮጵያ ዘመናዊ ልማት የማይናቅና የማይረሳ አስተዋጽኦ ያደረጉት አጼ ኃይለ ሥላሴ ናቸው።</u> እሳቸው የቀጠሉት ያለፈውን ብሄራዊ ልማት በማጥፋት አልነበረም። የዚህ ምእራፍ ዋና አላማ የሳቸውን መንግሥት የልማት አስተዋጽኦ ለማቅረብ አይደለም። ከህወሓት/ኢህአዴግ በፊት የማይናቅ ልማት እንደነበረ፤ በአንድ አንድ ዘርፎች ቀዳሚነት እንደነበረው ለማሳየት ብቻ ነው። ችግሮች አልነበሩም አንልም። ችግሮች የሌሉበት የእድገት ዓለም የለም። ለመጠየቅና ለመመለስ የምንፈልገው፤ ለመሆኑ ንጉሱ ምን ሰሩ የሚል ነው? የደርግና የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥታት ይህን አስተዋጽኦ እውቅና አልሰጡትም። ያለፈውን እንደ ድንቁርና ዘመን አይተውታል። ስላዩትም ብዙ ቢሊዮን ብር ጥሪት ወድሟል። የሰቲት ሁመራ፤ የአዋሽ ሸለቆ፤ የአርሲ፤ አስደናቂው የጣና በለስ ልማትና ሌሎች ሰፋፊ ዘመናዊ እርሻዎችና ዘመናዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ውድመት "ከጥላቻና ከፖሊስ ስህተቶች" የመጣ ዋጋ የተከፈለበት ጥፋት ናቸው።

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ልማት ዘመን መቼ ተጀመረ?

ልማት የሚመሰረትባቸው ምሰሶዎች የአገራዊ አቀማመጥና የተፈጠሮ ስጦታዎች አሉ። የኢትዮጵያ አቀማመጥ፤ ታሪክ፤ ባህል፤ ልምድ፤ የአየር ጠባይ፤ ወንዞች፤ ዝናብ፤ ለም መሬትና ጠንካራ የመስራት ልምድ ያለው ሕዝብ ይገኙበታል። ከጥንት ጀምሮ ጥናት ያደረጉ ተቋሞችና ግለሰቦች የሚቀበሉት፤ ኢትዮጵያ የአፍሪካና የመካከለኛው ምስራቅ "የዳቦ ቅርጫት"ለመሆን እንደምትችል ነው። ስለሆነም፤ ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ሃብትና በሕዝብ አንጻር ሲታይ፤ ደሃ አይደለችም። መራብ የለባትም። ራሷን ችላ የእርሻ ምርት ለውጭ ገበያ በተወዳዳሪነት ለማቅረብ የምትችል አገር ናት። ለዚህ ጥሩ የሆነ፤ ብሄራዊና አሳታፊ አገዛዝ ያስፈልጋታል። መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት በተቀዳሚ የተማረና የሰለጠነ የሰው ሃይል አስፈላጊ ነው። ዛሬ ይኬ ታላቅ ጥሪት እየባከነ ነው ለማለች ይቻላል። ያልባከነው አገሩ ለቆ ሌሎችን ያገለግላል፤ ኑሮውን ያሻሺላል። በገጠር ሆነ በከተማ ያደገው የእኛ ትውልድ ይገነዘባል ብለን የምንገምተው ህይወቱን ለዋጭ የሆነ የትምሕርት እድል ያገኘው አጼ ኃይለ ሥላሴ ባደረጉት ብሄራዊ ልማት ነው። "ከኲራዝ ወደ እሌክትሪክ፤ ከጭቃ ቤት ወደ ዘመናዊ ቤት ወዘተ " መሸጋገር ልማት ነው በሚል እንጀምራለን። አጼ ኃይለ ሥላሴ አምሳ ሰባት አመታት አገሪቱን በአምባገነንነት የመግዛታቸው መጥፎ ጎን ብዙ አነጋግሯል። ያላነጋገረው መንግሥታቸው ያበረከተው መልካም የእድገት ጎን መኖሩ ነው። ሮበርት ካለደሪሲ የተባለው በዓለም ባንክ ያገለገለ፤ ኢትዮጵያን በጥልቀት የሚያውቅ ካናዳዊ፤ The Trouble with Africa በተባለው መጽሃፉ የአገሪቱን የአስተዳደር ዘመናዊነት አቅርቦታል። ይህ ደርግ የጠበቀው፤ሆኖም ህወሓት/ኢህአዴግ ያፈራረሰው ብዙ መቶ ሚሊዮን ዶላር የፈሰሰበት ዘመናዊ የመንግሥት አስተዳደር አገልግሎት (Modern civil service) የሚያኮራ ነበር ብሏል። በአፍሪካና በመካከለኛው ምስራቅ ተወዳዳሪ የነበረ የመከላከያ ሃይል፤ የባህር በር፤ የተሻሻለ ህገመንግሥት፤ አገር አቀፍ የሆነና ጥራት ያለው የትምሕርት ስርአት፤ ዘመናዊ የባንክ አሰራር፤ የመንግሥት የሆኑ አምራችና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች፤ አገር ወለድ የሆነ የግል ክፍል እንደ ነበሩ አሳይቷል። ከእነዚህ አንዱን አስተዋጾ ወስደን ብናይ፤ የአስተዳደር ቅልጥፍና ለልማት ወሳኝ ነው። ገዢው ፓርቲ የአስተዳደር ቅልጥፍናን ወደ ፖለቲካ ቁጥጥር ለውጦታል። የፖለቲካ ቁጥጥር የማስተዳደር ዋጋውን በጣም ከፍ አድርጎታል። (Administrative management efficinency has been traded for political control thereby raising the costs of governing the country). ኬንያውያን በኢትዮጵያ ይደነቁ ነበር። አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ተቋሞች ቅልጥፍና ያላቸው ናቸው ይሉ ነበር። የግል ክፍሉን የሚመሩትና በባለቤትነት የያዙት ኢትዮጵያውያን ስለነበሩም ነው። በኬንያ ፈረንጆችና ህንዶች ቁልፍ የሆኑ ተቋሞችን ስለያዙ። ብሄራዊ አመራር ከጎሳዊ አመራር የበለጠ መሆኑን አመልካች ነው። ጎሰኛነት ይህን አፈራርሷል። ከሁሉም በላይ ችሎታ ይከበር ነበር።

የንጉሠ ነገሥቱን የኢኮኖሚ አመራር የምንመለከተው በብሄራዊነቱና በመስራችነቱ ጥቅም፤ በአስተዳደሩ ያለው የሰራተኛ ስብጥርና ቅልጥፍና ነው። ልማቱ፤ አገሪቱ ከነበረችበት ደረጃና የጣሊያን ፋሽስቶች ካደረሱት እልቂት አንጻር መታየት አለበት። መንግሥት ከባዶ ጀመረ የሚል አመለካከት ካለ፤ የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ጣሊያኖች ኢትዮጵያን ካደቀቋት በኋል ከባዶ ወይንም ከዜሮ መጀመሩ ይሆናል። ጣሊያን የተወው በቅልጥፍና የሰራውን መንገድ፤ ድልድይ፤ ቤትና ሌሎች ህንጻዎች ነው። ሌላው ከብሄራዊ ልማት ጋር አብሮ የሚሄደው ንጉሠ፤ ኤርትራን ከእናት አገሯ ጋር ማቀላቀላቸውና አገሪቱ የባህር በር እንዲኖራት ማድረጋቸው ነው። ለዚህ አግባብ ስለሌለው የግለሰቦችን ስም መዘርዘሩ

አያስፈልግም። ሆኖም፤ አገር ወዳድና ብቁነት የነበራቸው ኢትዮጵያውያን ኤርትራ ወደ እናት አገሯ እንትቀላቀል አድርገዋል። ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያ አካል የነበረው ኦጋዴንን ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለስ አድርገዋል። የአፍሪካን አንድነት ማህበር ለማቋቋም ቁልፍ ሚና ተጫውተዋል። ኢትዮጵያ በዓለም ሁሉ እንድትታወቅ አድርገዋል። እነዚህ ሁሉ በድምራቸው ለኢትዮጵያ ህልውናና ብሄራዊ ዘመናዊነት አስተዋጾ አድርገዋል። እነዚህ የኋላ ቀርነት መስፈርት አይደሉም።

ቻይናዎች የሚያስደንቁን፤ ታሪካቸውንና ታሪክ ሰሪዎቻቸውን አያዋርዱም። ጀንጅስ ካን በዘመናዊቷ ቻይና ታላቅ ሚና አለው። ማኦ የተከበረ ነው። የቻይና የልማት ምልክት መንገድ፤ ትምሕርት ቤት፤ ፎቅ፤ ወዘተ ስለተሰራ ብቻ አይደለም። ታሪክን፤ የተፈጥሮ ሃብትን፤ አካባቢን፤ የልዩ ልዩ ብሄር/ብሄረሰቦችን ባህል በማክበር ጭምር ነው። ኢትዮጵያ ከቻይና ጋር ተወዳዳሪ የሆነ ጥንታዊነት አላት። ታሪኳን፤ ባህሏን ጠብቃ፤ ከዛሬ የበለጠ ኢትዮጵያ በዓለም፤ በተለይ በአፍሪካ እውቅና ያገኘችው በአጼ ኃይለ ሥላሴ ጥበባዊና የማያቋርጥ ብሄራዊ አመራር ነበር። የእኛ ትውልድ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት ሲከታተል፤ እሳቸው ቤልጅግ፤ አሜሪካ፤ ሳውዲ አረቢያ፤ ህንድ፤ ብራዚል ወዘተ ሲጎበኙ፤ ለአፍሪካ ነጻነት ሲታገሉ፤ ለአፍሪካ ተማሪዎች ከአገሪቱ ዝቅተኛ ባጀት ተጠቅመው በያመቱ ከመቶ በላይ ስኮላርሺፕ ሲሰጡ በትምሕርት ገበታ ላይ የነበርን ሁሉ ትዝ ይለናል የሚል እምነት አለኝ። ይህ ሁሉ በድምሩ ኢትዮጵያ በዓለም ህብረተሰብ ታላቅና የሚያኮራ ዕውቅና እንድታገኝ አድርጓት ነበር። ይህን እውቅና በማስረጃ ያቀረበው፤ የኢትዮጵያ ወዳጅ የነበረው ጆን ስፔንሰር ነው።

ካቀረባችው ልንጠቅሰው የምንፈልገው፤ አጼ ኃይለ ሥላሴን ያስደስታቸው የነበረው ልማትን በየቦታው ማየት ነበር። "ጎንደር፤ ሃረር፤ ጎጃም፤ ወላይታ፤ ትግራይ ወዘተ" የሚል የልማት ፈለግ አልተከተሉም። " አገር ወዳድነት፤ ታታሪነት፤ የማስታወስ ችሎታ፤ የስራ ዲሲፕሊን፤ የወደፊቱን የማየት ተሰጦ፤ ሃቀኛነት" አስደናቂ ነበር ያለውን ተከታታይ ትውልድ ለራሱ ሲል ማወቅ ይኖርበታል ። በልማት መለኪያ ሲታይ፤ መንግሥታቸው ምን አደረገ የሚለውን ባጭሩ ለታሪክ እናስቀምጥ። አንባቢ የልማትን ታሪክ ማየት ያለበት ማንም መንግሥት ከባዶ እንደማይጀምር ነው።

የዘመናዊ ባንክ አስፈላጊነትና እድገት

ቅድመ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ የውስጥ ንግድ የተካሄደው በልውውጥ ነበር። (Trade was primarily barter). በአብዛኛው ኢኮኖሚው በገንዘብ አልተተመነም። ስለሆነም፤ ዘመናዊ ባንኮች ማቋቋም ለልማት ቁልፍ ሆኖ ተገኘ። የመጀመሪያው ባንክ፤ የአቢሲኒያ ባንክ ተብሎ በአጼ ምኒልክ እአአ (ከዚህ በኋላ የምንጠቀምበት አቆጣጠር) በ1905 ተቋቋመ። በ1931 ስሙ ተለውጦ የኢትዮጵያ ባንክ ተባለ። የሚጠቀምበት የገንዘብ አይነት ወርቅና ብር (Gold and Silver) ነበር። ይህ ለዘመናዊ ኢኮኖሚ የማይሰራ መሆኑ ታውቆ በ1942 የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ተቋቋመ። የኢትዮጵያ ብር የተባለው ተሰየመ። ይህ ሃያ ሁለት ቅርንጫፎች የነበሩት ባንክ የማእከላዊይና የንግድ ባንክ ሚናዎችን በአንድ አድርጎ ከሰራ በኋላ ዘመናዊ በሆነ መልክ በ1963 ሕግና ደንብ ተለውጦ ሁለት የባንክ አገልግሎቶች ተመሰረቱ። አንድ፤ ማእከላዊ ባንክ (State Bank of Ethiopia). የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ድልድይ የሆነው። ሁለት ለኢትዮጵያ ዘመናዊነት አስደናቂ አስተዋጾ ያደረገው የንግድ ባንክ። እነዚህ ብሄራዊ ተቋሞች ሲመሰረቱ፤ መንግሥትና ባለሞያዎች የተገነዘቡት ባስቸኳይ አመራራቸውና ሰራተኛው ኢትዮጵያዊ እንዲሆን ማድረግ ነበር። በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያ የማእከላዊ ባንክ ተጠባባቂ መሪ ሆነው ያገለገሉት አቶ ምናሴ ለማ ናቸው። የተኩት አሜሪካዊውን ጆርጅ ሪን ነበር። ኢትዮጵያዊ የሆነ- ከዚህ በኋላ አገር ወለድ ልማት- የምንለው፤ ቁልፍ መሆኑን ደጋግመን የምናሳየው ለዚህ ነው። ነጋድራስ ገብረህይወት ባይከዳኝ "ለልማት የተሻሻለ መንገድ የሚፈልግ ሕዝብ ልማቱን ለጥቂት ግለሰቦች (የውጭ ማለታቸው እንደሆነ አልጠራጠርም) አያስረክብም" ያሉት ለዚህ ነው። የልማት ቀጣይነት ቁልፍና የማይናጉ ብሄራዊ ተቋሞችን መመስረትና እነዚህን ተቋሞች በችሎታ፤ በቅንነት፤ በሃቅነት የሚያገለግሉ ኢትዮጵያውያንን ማጎልመስ አለበት። ቀጣይነት ያለው ልማት ያለብሄራዊ ተቋሞችና ያለ ቀልጣፋ፤ አገር ወዳድ፤ ብቁና ስብጥር የሰው ሃይል አይቻልም። ስደት ያመጣውን ጉዳት ከዚህ አንጻር ማየት ይቻላል። ብንወድም ባንወድም፤ ብንቀበልም ባንቀበልም፤ በአቅማቸውና አገሪቱ በነበራት <u>ገንዘብና አቅም፤ አጼ ኃይለ ሥላሴ ይህን የመሰለ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ለአገር ቀናተኛ መሆን ልማትን ይወስናል።</u>

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ አመራር ከአሁኑ የሚለይበት ዋና ምክንያት የአገሪቱን የገንዘብ መጠንና ዝውውር (Money in circulation) የሚወስነው ከኢኮኖሚው እድገት ጋር በማያያዝ ነበር። እድገቱ፤ ማለትም የምርትና የአገልግሎት ውጤቱ ከፍ ሲል፤ ማእከላዊው ባንክ የገንዘብ አቅምን ከፍ ያደርጋል። የዋጋ ግሽበት ኢኮኖሚውንና ህብረተሰቡን እንዳይጎዳው ይቆጣጠራል። በዘፈቀደ፤ የምርት ውጤት ሳያድግ ገንዘብ ቢታተም የዋጋ ግሽበት ያስከትል ነበር። የገንዘብ ብዛትና አጠቃቀም በቀጥታ ከምርት እድገት ጋር መያያዝ አለበት የሚለው የልማት ሂደት ቁልፍ እንደሆነ ግንዛቤ ነበር።

የኢትዮጵያ ብር ከአሜሪካ ዶላር ጋር መያያዙ፤ ዋጋው አንድ ዶላር ሁለት ብር ከአምሳ መሆኑ፤ መንግሥት በባንኩ የቀን በቀን አመራርና አስተዳደር ጣልቃ አለመግባቱ አገልግሎታል። አጼ ኃይለ ሥላሴ ለባጀቴ ተዛቦት/መዛባት ማሟያ ወይንም ማስተካከያ (Deficit Financing) ይህን ያህል ሚሊዮን ብር ማተም አለብህ ቢሉ አያትምም ማለት ነው። የንግድ ባንክ አመራርም በዘመናዊ መለኪያ (Loan Criteria) ያበድር ነበር። መያዣ መኖሩ፤ ተበዳሪው ለመክፈል መቻሉ፤ ብድሩ ለምን አይነት ተግባር እንደሚውል፤ እንዴት እንደሚከፈል ለማወቅ አስችሎታል። በአብዛኛው፤ አድልዎ በሌለበት መንገድ ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል። ይህን የባንክ አጠቃቀም አመራር በመከተል፤ አስደናቂ የሆነ እድገት እንዲካሄድ በ1970ዎቹ አመታት የንግድ ባንክ ለታላላቅ ዘመናዊ እርሻዎች፤ ለእኒዱስትሪዎችና ሌሎች አምራች ድርጅቶች ብድር አስፋፍቶ ነበር። ለዚህ እንዲረዳው ቅርንጫፎች በየቦታው ዘርግቶ የቁጠባ ልምድ እንዲለመድ አድርጓል። ይህ ዘመናዊ የባንክ አገልግሎት አጠቃቀም ስፋት ያስገኘው ውጤት (Monetization of the economy) በአመት ሃያ በመቶ እንዲያድግ ማድረጉ ነው። ሃያ በመቶ ቀላል አሃዝ አይደለም። ወደ ኋላ ለቀረች ኢትዮጵያ የዚህ አይነት ለውጥ እመርታዊ ልማት ሊባል ይችላል።

የግራ ክንፉ ይህን ሁሉ ጠቃሚ ለውጥ እንዳልነበረ ቆጥሮታል። ያተኮረው በመንግሥቱ ጥንካሬ ላይ ሳይሆን በደካማ ጎኑ ነበር ማለት ነው።

## ልማትና የተፈጥሮ ሃብት ብሄራዊነት

የኢትዮጵያ ልማት ከተፈጥሮ ሃብቷ ጋር አብሮ የሚሄድ ነው። ከሁሉም በላይ በወንዞቿና በለም መሬቷ ያለው የማደግ ተስፋ ወደ ተግባር የሚለጠው የመንግሥት ፖሊሲ አጎልማሽ ሲሆን ነው። የባንክ አገልግሎት መስፋፋት ሂደት እንዲሁ በምኞት የመጣ አልነበረም። የኢኮኖሚው አመራር ድክመቶች እንደነበሩት ባያከራክርም (በተለይ ጉልታዊ ስር አቱ)፤ ጥንካሬዎችም ነበሩት። ከእነዚህ ልንጠቅሳቸው የምንገደደው፤ብሄራዊና አገር ወዳድ የሆነው አመራር መንግሥት ቁልፍ ሚና መጫወት አለበት የሚለውን መርህ መቀበሉ ነው። የልማት ዋና መመዘኛ የነፍስ ወከፍ ገቢን ከምርት ውጤት ጋር አያይዞ ሕብረተሰቡ በስራ እድል፤ በገቢና ሌላ የእድገቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ሞክሯል። የኢንዱስትሪ አቅም ግንባታ መስፋፋት ከመሰረተ ልማት ጋር ተያይዞ ህብረተሰቡ የሚፈልገውን አቅርቦት ለመግዛት በሚችልበት ደረጃ ስኬታም ለማድረግ ሞክሯል። በተቻለ መጠን ኢትዮጵያውያን ባለቤትነት እንዲኖራቸው የውጭ ኢንቬስተሮች እንዲጋሩ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ተቀብሏል። አምሳ አንድ ለአርባ ዘጠኝ (ኢትዮጵያዊያን የበላይነት እንዲይዙ) ለማድረግ መሞከሩ ይገኙበታል። አንባቢ እንዲገነዘበው የምንፈልገው፤ በልማትና እድገት (Development and Growth) አንድ የማይካድ መሰረተ ሃሳብ አለ። የፈለገው ያህል የተፈጥሮ ሃብት ቢኖር ባለቤትነትና አዛዥነት የሌለው ሕዝብ የተፈጥሮ ሃብቱንና ህይወቱን አይቆጣጠርም። እንዲያውም፤ የተፈጥሮ ሃብቱ መገዣው ሊሆን ይችላል። ባለቤትነትን መካድ "ዘመናዊ ባርነት" ፈጣሪ እንለዋለን። ወጣቱ ትውልድ በአገሩ እድል ስለሌለው አገሩን ለቆ ለውጭ "ባርነት" ይዳረጋል። አገር ቤት ያለው በዝቅተኛ ደሞዝ እንዲሰራ፤ወይንም ስራ አልባ እንዲሆን ይገደዳል። የተሰደደው፤ ከስድስት ሚሊዩን በላይ የሚገመተው--በአረብ አገሮች ሁለት ሚሊዮን፤ በሰሜንና ደቡብ ሱዳን ሁለት ሚሊዮን፤ በምእራብና ሌሎች አገሮች ሁለት ሚሊዮን ስደተኛ--በአብዛኛው የዘመኑ "ባርነት" የጉልበት ሰራተኛ ሆኗል። ኢትዮጵያውያን ብዙ ጊዜ የራሳቸውን ችግር ወደ ጎን ትተው ሃያ አምስት በመቶ የሚሆነው የኤርትራ ሕዝብ ተሰዷል ይላሉ። ስድስት ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን መሰደዳቸውን የረሱት ይመስላል። ማንም ሰው በኢኮኖሚ ወይንም በፖለቲካና በፍትህ ጉድለት ምክንያት አገሩን የሚለቅ ስደተኛ ነው።

## የማእከላዊ መንግሥት ሚና

በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ኢትዮጵያ የተከተለችው የልማት አመራር "አሃዳዊ መንግሥት ካፒታሊዝም" ነበር። ይህ መጽሃፍ አሃዳዊ ስርአት ያስፈልጋል ብሎ አልተከራከረም። አይከራከርም። አቀራረጹ የሕዝብ ውሳኔ መሆን አለበት። ክርክሩ አገሪቱን ለቀጣይ ልማት የሚያረጋግጥላት የተማረ ሰው ማስለጠንና መጠበቅ አስፈላጊ መሆኑን የተቀበለ መሆኑ ነው። ብዙ ብሄራዊ የሆኑ የአገልግሎትና የምርት ድርጅቶችን ያቋቋመ ነበር። የማእከላዊ መንግሥት ቁልፍ ሚና እንደነበረው የሚያረጋግጠው ከ1957-1973 የተካሄድው የአምስት አመት ዕቅዶች አመራር ነው። አመራሩ ከሁሉ በላይ ያተኮረው የምርት ውጤትን፤ በተለይ፤ የእርሻንና ከእርሻ ጋር የተያያዘ የኢንዱስትሪ ምርትን ማሳደግ ነበር። በእቅዱ መሰረት ከ1957-1968 የተደረገው ጥረት ያተኮረው ከመሰረተ ልማት ላይ ነው። ትምሕርትና ጤና፤ መንገድና መገናኛ፤ ግድብ ወዘተማስፋፋት። በ1960ዎቹ መጨረሻ አመታት ልማቱ ያተኮረው ከኢንዱስትሪና ከእርሻ ምርት እድገት ላይ ነበር። ታላላቅ ከውጭ ኢንቬስተሮች ጋር በመጋራት የተቋቋሙት የአዋሽ ሸለቆ የስኳር አገዳ እርሻና የስኳር ፋብሪካ፤ የቅዱስ ጊዮርጊስና የመሎቲ የቢራ ፋብሪካዎች፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወዘተ። እነዚህ በተቋቋሙበት ዘመን፤ ደቾች፤ አሜርካኖች፤ ጣሊያኖች፤ ዓለም ባንክ የተሳተፉባቸው የልማት ሂደት ምሳሌዎች ናቸው። ተከታታይ

ባይሆንም፤ ኢኮኖሚው በአመት ስድስት በመቶ (6 percent per annum) ያደገበት ወቅት ነበር። ጣሊያን ያደቀቃትን ኢትዮጵያ ከባዶ ጀምሮ በዚህ ደረጃ ማሳደግ ቀላል አልነበረም። የአገር ውስጥ ገቢና ቁጠባ፤ የውጭ እርዳታ ዝቅተኛ ነበር። በተለይ አንባቢው በአእምሮው እንዲቀርጽው የምንፈልገው በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ይገኝ የነበረው የውጭ እርዳታ በጣም የተወሰነ መሆኑን ነው። ስደተኛ ስለሌለ ከኢትዮጵያውያን የሚመጣ የውጭ ምንዛሬ አልነበረም። ኢትዮጵያውያን ውጭ ሄደው ትምሕርታቸውን ሲጨርሱ ወዲያው ወደ አገር ይመለሱኑ ነበር። የአገርን የሰው ሃይል ተንከባክቦ መጠቀም ለተከታታይ አገር ወለድ ልማት ወሳኝ  መሆኑን አሳይተዋል። በራስ ጥረት ለማደግ መሞከር አገር ወዳድነትን፤ ታታሪነትን፤ በራስ መተማመንን ወዘተ ያሳያል።

ዘመናዊ እርሻና ልማት

በቅርቡ አንድ አገር ወዳድ ተመልካች ስለ ህወሓት/ኢህአዴግ ኢኮኖሚ ውጥንቅጥነት ልብን የሚቀሰቅስ ድርሰት አቅርቦ ነበር። "እኛ የመጨረሻዎቹ" የተባለው ድርሰት የዱሮውን በማስታወስ "እኛ የመጨረሻዎቹ፤ በ15 ሳንቲም አውቶቡስ የሄድንበት። በ35 ሳንቲም ታክሲ የወሰድንበት። በ50 ሳንቲም የቀበሌ ቤት የተከራየንበት። በ10 ሳንቲም ዳቦ የበላንበት። በ15 ሳንቲም ሻይ የጠጣንበት። በመቶ ብር መቶ ኪሎ ጤፍ የገዛንበት። በአስር ብር አንድ ደሮ የበላንበት። በሃያ ብር አንድ ቤት የተከራየንበት። ወደ ውጭ ለመሄድ ለኢሚግሬሽን ገንዘብ ያስያዝንበት። እኛ የመጨራሻዎቹ።" ይህ አለም አልፏል የሚል ነው። የገዢው ፓርቲ የበላዮች እንደሌሎቻችን በዚህ ተበልቶ በሚታደርበት ህብረተሰብ አድግዋል። ማደጋቸውንም ጭምር የካዱት ይመስላል። አሁን የሚታየው የኢኮኖሚ ሁኔታ ለጥቂቶች፤ ኪሳቸው ለሞላው ከብደታቸው ለጨመረው ገነት ነው። ለአብዛኛው ጨለማ ነው። በተለይ፤ የምግብ አቅርቦት ሁኔታ ሲታይ።

በእኛ ግምትና ጥናቶች በሚያመለክቱት፤ ዘመናዊ የንግድ እርሻ የተጀመረው በ1950ዎቹ ነው። ደቾች በአዋሽ ሸለቆ የስኳር ምርጥትና ፋብሪካ አቋቋሙ። እንግሊዞች በተንዳሆ የጥጥ ፋብሪካ በ1960ዎች ተጋርተው አቋቋሙ። እነዚህ ጅምሮች ኢትዮጵያ ወደ ዘመናዊ የእርሻና የተያያዘ እርሻ ወጥ ኢንዲስትሪ ለማቋቅም የምትችልና የአገር ውስጥ ፍላጎት አሟልታ ለውጭ ገበያ አቅርቦት ተወዳዳሪ ለመሆን እነደምትበቃ አመልካች ሆኑ። ማንም ሳይጠይቃቸው የግል ባለጠጋዎች ያላቸውን ገንዘብና እውቀት፤ ከባንክ የሚያገኙትን የተወሰነ ብድር ተጠቅመው ወደ ዘመናዊ እርሻ ስራ ገቡ። የእርሻ ውጤት የሆኑ የታሸገ ስጋ (Canned food)፤ ፍራ ፍሬ፤ ቅጠላ ቅጠል፤ ስኳር፤ የምግብ ዘይት፤ አሳ፤ ወተትና ቅቤ፤ የተዘጋጀ ቆዳ ወዘተ ለአገርና ለውጭ ገበያ ማቀርብ ጀመሩ። በተለይ መገለጽ ያለበት፤ በግል ኢትዮጵያውያን ትጋት፤ ጥረት፤ ጉልበትና አቅም አገር ወለድ የእርሻ ምርት እድገት የተካሄድውና የገጠር ባለጠጋዎች በብዛት የታዩበት ከ1970 በኋላ የተከሰተው የኢትዮጵያ "አረንጓዲ ልማት" ለሚል መለኪያ የሚያሟላ ወቅት ነው። እነዚህ ታታሪዎች፤ የሳውዲና የህንድ ብድር አልጠየቁም። ኢንቤስተሮችን "ኑና የአገራችን እርሻ" አልሙልን አላሉም። አስደናቂ ውጤት ያሳየውን የሰቲት ሁመራን የእርሻ ልማት ማየት ይጠቅማል። ከተከዜ ወንዝ በታች በሚገኘው በሰቲት ሁመራ የታየውን አስደናቂ ዘመናዊ እርሻና የምርት እድገት በ1960ዎቹ መጨረሻ አመታት ያካሄዱት ማንም ሳያስገድዳቸው፤ የኢትዮጵያ የግል ኢንቬስተሮች ነበሩ። የአለም ማያ ኮሌጅ ምሩቆች፤ ተራ ገበሬዎች፤ የመንግሥት ሰራተኞች፤ የጦር መኮንኖች ወዘተ በብዛት ገብተውበት ነበር።

ዘመናዊ እርሻ በልዩ ልዩ ዘርፍ ሁለት ሚሊዮን ኢትዮጵያውያንን ያሳትፍ ነበር። በሰብል ጊዜ ከአምሳ ሽህ በላይ ደሃ ገበሬዎችን ቀጥረዋል። ብዙ ሽህ ሰራተኞች ቀጥረው፤ ትርፍ አግኝተው፤ ለሃገራቸው የሚያኮራ የውጭ ምንዛሬ አስገኝተዋል። የውጭ ምንዛሬ ሰርቀው ወይንም አታለው አላሸሹም።  እንደዚህ ያለ ነውር ባህል በአእምሯቸው አይታሰብም ነበር። ምን አመረቱ? ጥጥ፤ ሰሊጥ፤ ማሽላ፤ ገብስ ወዘተ። እነዚህ የእርሻ ምርት ውጤቶች ለኢንዱስትሪ መጋቢ ሆኑ። የጨርቃ-ጨርቅ ፋብሪካ ተስፋፋ። ረሃብንና ድህነትነትን ለመቀነስ አስተዋጽኦ አደረጉ። የሰቲት ሁመራ አርአያነት ወይን ሞዴል በሌሎች ክፍለ ሃገራት ዘመናዊ እርሻ እንዲስፋፋ አድርጓል። ከሁሉ በላይ አስደናቂ ሆኖ ያገኘነው፤ ኢትዮጵያውያን የመንግሥት ጫና ከሌለባቸው፤ በራሳቸው ተነስተው፤ የራሳቸውን ጉልበትና ገንዘብ ተጠቅመው ዘመናዊ እርሻና ሌላም ኢንዱስትሪ ለማቋቋም ችሎታ እንዳላቸው ስላስተማሩን ነው። ሰቲት ሁመራ በልማት ታሪክ ውስጥ የማይናቅ አስተዋጽኦ እንዳደረገ የተረዱ የውስጥ አዋቂዎች አሉ። "The demonstrative effect of Setit-Humera for mechanized agriculture in other regions was enormous. Private commercial farms began to be established in the Awash Valley, the Billatae plains, Gibe valley (where the controversial Gibe III Dam is located) and other promising locations with a good climate and ample water." 48/

የዝቅተኛ ገበሬዎች ቁልፍነት

የሰቲት ሁመራና የሌሎች ዘመናዊ እርሻና ተመጋቢ እንዱስትሪ መስፋፋት ያሳያቸው የልማት ምልክቶች ብዙ ናቸው። አንድ፤ ኢትዮጵያዊያን በትንሽ ካፒታል ተነስተው ከበርቴ ለመሆን ይችላሉ። ሁለት፤ መንግሥት ጫና ካላደረገባቸው የግል ክፍሉን ለማሳደግ ይችላሉ። ሶስት፤ ለውጭ ገበያ አቅርቦት ተወዳዳሪ ለመሆን ብቃት አላቸው። አራት፤ ተጠቃሚ እስከሆኑ ድረስ በሙስና አይበከሉም። አምስት፤ በአገራቸው አገዛዝ እምነት እስካላቸው ድረስ የውጭ ምንዛሬ አያሸሹም። በሰቲት ሁመራ የተገኘው የእርሻ ምርት እድገት አስደናቂ የልማት ሂደት ነው የምንልበት ዋና ምክንያት፤ ብዙ የመንግሥት ሰራተኞች፤ የተማሩ ወጣቶችና የጦር መኮንኖች ስራቸውን ትተው የዘመናዊ እርሻ ስራ በገፍ ጀምረው ስለነበረ ነው። የገታቸው የመሬት ይዞታው መሳፍንቶችን አገልጋይ መሆኑ፤ ገበሬው የመሬቱ ባለቤት አለመሆኑ ይገኙበታል። ከስተቱ ነዋሪው ሕዝብ ከመሬቱ እንዲባረር ማድረጉና መሬታቸውን ያጡ ወደ ከተማ እንዲሰደዱ መገደዳቸው ነው። የመሬት ይዞታ ኋላ ቀርና በገባርነት የተመሰረተ መሆኑ በፍጥነት ለማደግ የሚችለውን የእርሻ ውጤት አድክሞታል። የገጠር ከበርቴ በፍጥነት እንዳያድግ ማነቆ ሆኖበት ነበር። የመሬት ይዞታ እድገቱን አቅቦታል። የግል ክፍሉ ለማምረት ስላልፈለገ አይደለም። የመንግሥቱ "የገባርነት ስርአት ፖሊሲ" ከእድገቱ ጋር አብሮ ስላልተለወጠ ነው። የስድሳ ስድስቱን አብዮት ያስከተለው አንዱ የመሬት ይዞታ ጥያቄ ነው። የተማረው ክፍል "መሬት ላራሹ" ብሎ ተነሳ። የሚያቆመው ሃይል አልነበረም። መረሳት የሌለበት ዋናው የልማት ቁም ነገር በየቦታው የተካሄደው የግል ዘመናዊ እርሻ ውጤት ዓለም ያደነቀው ነበር። ስለተደነቅም ለጋሶች ድጋፍ ሰጥተውታል።

እርዳታ ከምርት ጋር ሲያያዝ ህይወት ይለውጣል

የውጭ እርዳታ ዋና ሚናው አገሮች ከእርዳታ ነጻ እንዲሆኑ ነው። አሊያ፤ እርዳታ ጥገኝነት ይባላል። ኮሪያና ቻይና እርዳታ ያገኙ ነበር፤ ዛሬ ከእርዳታ ነጻ ናቸው። በእኛ ትውልድ ራሳቸውን ችለዋል። እርዳታ አቅምን ሲያሳድግና የማምረት ሃይልን ሲያዳብር ጥቅም አለው። የስዊድን መንግስት የጭላሎን የእርሻ ጥረት በአሪሲና በወላሞ ሶዶ አጠንክሯል። ዓለም ባንክ፤ የአሜሪካ ተራድኦ ድርጅት፤ በአዳና በሌሎች ቦታዎች የተጣመረ ድጋፍ ሰጥተዋል። የገጠሩን የእርሻ ኢኮኖሚ ለማሳደግ፤ ድህነትን ለመቀነስና ለማጥፋት ከተፈለገ ዝቅተኛ ገበሬዎችን (Smallholders) ማጎልመስና የመሬት ባለቤትነታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑን መንግሥትና የውጭ እርዳታ ሰጭዎች ተገንዝበው ነበር። ሆኖም፤ የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት አጥጋቢ ለውጥ አላደረገም። ስላላመጣ የራሱን ስርአት ለማውረድ አስትዋጾ አድርጓል። "የኢትዮጵያን ፍጹም ድህነት፤ ተሰፋ መቁረጥና ረሃብ ለመቀነስ ከተፈለገና ስፋትና ጥልቀት ያለው ልማት እንዲመሰረት ምኞት ካለ፤ የዝቅተኛ አምራቾችን ጉልምስና ማስቀደም ዋና የመንግሥት ተግባር መሆን አለበት። "የእርሻ ምርት ሊያድግ የሚችለው፤ ገበሬዎች ከፖለቲካ ቁጥጥር ውጭ የሆነ ማዳበሪያ፤ የተሻሻለና ተስማሚ ዘር፤ ዝቅተኛ ወለድ ያለው ብድር፤ የመሬት ዋስትና፤ የገበያ እድልና ተወዳዳሪነት፤ ከእርሻ ጋር የተያያዘ የኢንዱስትሪ ልማት" በእቅድ ሲካሄድ ነው። በኢትዮጵያ፤ የመሬት አዋጁ ጥቅም በአንድ ፓርቲ የበላይነት ተተክቷል። አብዛኛው በግብርና የሚመካ ኢትዮጵያዊ የመሳፍንት ስሪትን አስወግዶ አሁን ለአንድ የጠባብ ጎሰኛ ፓርቲና አጋሮቹ "ጭሰኛ" ሆኗል። የፓርቲውና የመንግሥት "የበላይነት አዲስ ጭሰኝነትን"ፈጥሯል። 49/

በውጭ እርዳታ የተደገፈው ማጎልመስ ምን ማለት ነው? ማንም የእድገት ባለሞያ ማጎልመስ ለፖለቲካ ስልጣን መቆያና መቆጣጠር አለመሆኑን በማስረጃ ያቀርባል። ሰቲት ሁመራን ከበዳነት ወደ ዘመናዊይነት የለወጡት ኢትዮጵውያን ማንም አጎልምሷቸው አይደለም። ልምድና ባህል አላቸው። ስለሆነም፤ አገር ወለድ ልምድንና እውቀትን (Indiginous culture and knowledge) ማጥፋት ለልማት በደል ይፈጥራል። የሰቲት ሁመራና ሌሎች የእርሻ ልምድ ለዋጮች መንግሥት ስለተቆጣጠራቸው አይደለም። መሰናከል ስላልሆነባቸው ነው። አዲስ ባለጠጋ ለመሆን የወሰኑና ዝቅተኛ አምራቾች የነበሩት የፈለጉት፤ማዳበሪያ፤ ምርጥ ዘር፤ መሳሪያ፤ ገበያ፤ የቴክኒክ ድጋፍ፤ ብድር ወዘተ ናቸው። እነዚህ ግብአቶች ስለተገኙ የእርሻ ውጤት በጣም አደገ። የሰቲት ሁመራና ተመሳሳይ ምርቶች፤ የመንግሥት እርሻዎች፤ ዝቅተኛ አምራቾች በጠቅላላው ኢትዮጵያ በምግብ አቅርቦት ራሷን እንድትችልና ወደ ውጭ የምትልከውን የእርሻ ውጤት በጣም እንዲጨምር አደረገው። ከእርሻ ጋር የተያያዘ ኢንዱስትሪ እንዲስፋፋ አስተዋጾ አደረገ። አንባቢ፤ ምርት ካደገ ለምን ታላቁ የወሎ ድርቅ ተከሰተ ይል ይሆናል። ተገቢ ጥያቄ ነው፤ የወሎ ሆነ ከዚያ በኋላ የተከሰቱ ከድርቅ ጋር የተያያዙ ረሃቦች (Drought Driven Famines) የተፈጥሮ ብቻ አይደሉም። ዋናው የአገዛዝና የአስተዳደር ችግሮች ናቸው። ለምሳሌ፤ አምራች የሆኑና ትርፍ (Surplus) የነበራቸው ክፍለ ሃገራት በድርቅ ከተጎዱ ክፍለ ሃገራት ጋር አለመቆራኘታቸው አንድ ምክንያት ነው። መንግሥት በከህደት አዙሪኝ ውስጥ መግባቱና ድርቅን የፖለቲካ መሳሪያ ማድረጉ። የአገሪቱ የመገናኛ ልማት አለመዳበሩ መሰረታዊ ለውጥ እንዳይኖር ማነቆ ነው። የድርቅ ረሃብ የፖሊሲና የአገዛዝ ውድቀት አመልካች ነው። ወንዝ፤ በመስኖ የሚለማ መሬትና ዝናብ ያለው አገር የሚራብበት ዋና ምክንያት አገዛዙ አጎልማሽና ፍትሃዊ ስላልሆነ ነው። ድርቅ የኢትዮጵያን ለማምረትና እራሷን ለመቻል፤ ላለመቻል አመልካች

አልነበረም። አሁንም አይደለም። የአገዛዝ አጎልማሽነት አስፈላጊ መሆኑን አመልካች ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ፤ ቻይናና ህንድ አሁንም በረሃብ ይሰቃዩ ነበር።

ስዊድን፤ ሆላንድ፤ ዓለም ባንክ፤ የአሜሪካ ተራድኦ ድርጅት በዘመናዊ እርሻ እድገት ላይ ያደረጉት አስተዋጽኦ ስለ ውጭ እርዳታ ሚና አጎልማሽነት ወይንም ጥገኛነት ጥያቄ ይወስደናል። የአሜሪካ እርዳታ በሰፊው መካሄድ የጀመረው ከ1952 በኋላ ነው። የካናዳ ከዝያ አራት አመት በኋላ። በዚህ ዘገባ የምናሳየው እአአ ከ1952-1974 የነበረውን ብቻ ነው። ፖይንት ፎር፤ በኋላ የአሜሪካ ዓለም አቀፍ እርዳታ ድርጅቶች ታላቅ ሚና ተጫውተዋል። በኢትዮጵያ ልማት ሊጠቀሱ የሚችሉት የህብረተሰቡን ጥንካሬና አጎልማሽ የሆኑ የሰው ሃልይና ብሄራዊ ተቋሞች ለመገንባት ሚና የተጫወቱት ናቸው። የእርሻ ልማት ለማጠናከር አለማያ ኮሌጅ፤ ከፍተኛ ትምሕርት ለማጠናከር ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ፤ የጤና አገልግሎት ለማጠናከር ጎንደር ኮሌጅ፤ የመንገድ፤ የየብስና የአየር መገናኛ ለማጠናከር ወዘተ። ትራንስ ወርልድ ኤርላይንስ ለኢትዮጵያ አየር መንገድ የሰጠው የቴክኒክ ድጋፍ አቅም ገንብቷል። በተለይ ሊጠቀስ የሚገባው አሜሪካ ለብዙ ሽህ ኢትዮጵያውያን የከፍተኛ ትምሕርት ስኮላርሽፕ መስጠቷ ነው። በኢኮኖሚ ግንባታ በኩል የአሜሪካ የግል ክፍል ወሳኝ የሆነ ሚና አልነበረውም። ቴኔኮና ሲንክሌር በኦጋዴን ዘይት ፍለጋ ቁፈራ አድርገው ሳይሳካ ቀርቷል። ፓርሰንስ የተባለው የግል ድርጅት በአፋር የፖታሽ (ለማዳበሪያ) ቁፋሮ አድርጎ ነበር። አሁን የካናዳ የግል ድርጅት ምርት ጀምሮበታል።

በነገራችን ላይ ለማጠናከር የምንፈልገው ኢትዮጵያ የዝቅተኛ ገበሬዎችን የምርት ውጤት ለማሳደግ ከፈለገች፤ ልክ ህንዶች እንዳደረጉት ብዙ ዝቅተኛ ካፒታል የሚያወጡ የአገር ውስጥ ማዳበሪያ አምራች ፋብሪካወች ማቋቋም አለባት። ገበሬዎች የመሬታቸው ባለቤት እንዲሆኑ አዲስ ፖሊሲ ማውጣት አለባት። ኢትዮጵያውያን ወደ ዘመናዊ እርሻ እንዲሰማሩ የፖሊሲ ገደቦችን ማስወገድ አስፈላጊ ነው። ፖታሽ ተጣርቶ ለዓለም ገበያ ማውጣትና መልሶ ማዳበሪያ መግዛት አያዋጣም። ኢትዮጵያ የራሷ ኢንዱስትሪና የተፈጥሮ ሃብት ባለቤት መሆን አለባት።

ግዙፍ ተቋምና እውቀት አይሰረቅም

በኢትዮጵያና በአሜሪካ መካከል የነበረው ጥሩ ግንኙነት ቀጥተኛ የሆነ የንግድ ጥቅም ነበረው። አብዛኛው የኢትዮጵያ ቡና የሚሸጠው ለአሜሪካ ነበር። በየካቲት አብዮት ዘመን የግራ ክንፉ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በበላይነት የያዙት አሜሪካኖች ናቸው የሚል ክስ እናስታውሳለን። ይህ ከእውነቱ የራቀ ነበር። አሜሪካኖች "በጋራ ( Joint) በሆነ መንገድ የያዟቸው፤ የኢትዮጵያ እንሥሳ እድገት፤ የኢትዮጵያ የቅመማ ቅመም ድርጅት፤ የኢትዮጵያ የግንባታ ድርጅትና አዲስ ባንክ ነበሩ። እነዚህ ድርጅቶች አገር ለዋጭ የሆነ ሚና አልተጫወቱም። የአሜርካ የግል ክፍል ካደረገው ጥቅም ይልቅ የአሜሪካ መንግስት ለኢትዮጵያውያን የሰጠው የትምሕርት እድል ይበልጣል። ከግማሽ በላይ ውጭ የተማረው ኢትዮጵያዊ--ከሶብየቶች በፊት-- ይላክ የነበረው አሜሪካ ነበር። ግራ ክንፉ "የሲአይኤ" ሰላዮች እያለ ይከሳቸው የነበሩት የሰላም ልኡካን ብዙ መቶ ሽህ ኢትዮጵያውያን አስተምረዋል። ውለታ የማያውቀው ግራ ክንፍ ያስተማሩትን ሁሉ በጅምላ ሲ አይ አኤ ማለት ይቀናው ነበር። አብዛኛው ወደ ምእራብ አገሮች የሚሰደደው ኢትዮጵያዊ ወደ አሜሪካ ለመምጣት የፈለገው የሕዝብ-ለሕዝብ ግንኙነት የመቶ አመታት ታሪክ ስላለውና አጼ ኃይለ ሥላሴ ይህን ግንኙነት ስላጠናከሩት ነው። ባጭሩ፤ የውጭ እርዳታ መጠነኛ ቢሆንም ሙሉ በሙሉ ከልማት ላይ ውሏል ለማለት ይቻላል። ተቋም ለመገንባት የተሰጠ እርዳታ አልተሰረቀም። የኢትዮጵያ የተማረ የሰው ሃይል እውቀት ሊሰረቅ አይችልም። ላወቀበት መንግሥት ይህ የማይሰረቅ ጥሪት ለልማት ቁልፍ ነው።

አጼ ኃይለ ሥላሴ ሙሰኛ ነበሩ?

አገርን ለመዝረፍና ሙሰኛ ለመሆን የሚዘረፍ መኖር አለበት። አጼ ኃይለ ሥላሴን ከስልጣን ያወረደው ደርግ ንጉሱ "ሌባ ናቸው፤ በስዊስና በሌሎች ባንኮች ብዙ ቢሊዮን ዶላር ከአገር ዘርፈው አስቀምጠዋል" የሚል ነበር። የንጉሡን ሃቀኛነት፤ ፈርሃ እግዚአብሄርና አገር ወዳድነት ብንተወው--ብዙ ቢሊዮን ለመስረቅ እድሉ መኖር አለበት። ከአዶላ ወርቅ፤ ከመንግሥት ባጀት፤ ከእርዳታ፤ ከውጭ ንግድ፤ ከየት ይመጣል ብለን እንጠይቅ። አብዛኛው የሚለው ከአዶላ ወርቅ ማእደን ነው። አሁን ሁሉም የወርቅ ማእደን ለአላሙዲ ተሰጥቷል። በእስር ቤት ሳሉ፤ አጼ ኃይለ ሥላሴ የዘረፉትን ሃብት አጣሪ ኮሚቴ ተቋቁሞ የብሄራዊ ባንክ ዋና አዛዥ የነበሩት አቶ ተፈራ ደገፌና ሻለቃ ዮሃንስ ምትኬ አነጋገሯቸው። በስዊስ ባንክ "በሳንቲም የሚቆጠር ገንዘብ" እንዳለ አረጋገጡ። "በለንደንና በኒው ዮርክ፤ በልጅ ልጆቻቸው ስም ሂሳብ አለ" ብለው አስረዱ። ከዚህ ሌላ "ምንም የተደበቀ የለም" ብለው ቃላቸውን ሰጡ። ያመናቸው ስለሌለ የደርግ መንግሥት በየቦታው ተከታትሎ ውጤት አላገኘም። እኝህ ንጉሥ ከአምሳ አመታት በላይ ገዝተዋል። ሙሰኛ ቢሆኑ ለመስረቅና ብዙ መቶ ሚሊዮን ዶላር ለማሸሽ እድል ነበራቸው። በእኛ እምነት በራሳቸው ስም

የተቀመጠ፤ ለራሳቸው መጦርያ የሚሆን ገንዘብ አለ ለማለት በምንም አንችልም። ለምን? ይህ ጸሃፊ-ባልሰራው ወንጀል ተከሶ አንድ ቀን ብቻ በፊታቸው ቀርቦ "ይቅርታ" ጠይቋል። ከዚያ በላይ አያውቃቸውም። ደራሲው የሚያስታውሰው አገር ወዳድና ይቅር ባይነታቸውን ነው። የንግድ ባንክ ዋና ስራ አስኪ ሃጅ በነበርኩበት ወቅት መዝገቦችን አጣርቸ የግል ገንዘብ ማሸሻቸውን የሚያሳይ አንድን መረጃ አላገኘሁም። የልቅ የሚጠቅመው እሳቸውን ከመለስ ጋር ማወዳደር። መለስ አስሮ ያዋርድ ነበር። እሳቸው አስረው ማስረጃ ሳቀርብ እኔን ፈተውኛል። በቅርብ የሚያውቋቸው ስለነበሩና አሁንም በህይወት ስላሉ፤ ምስክር ይሆናሉ የሚል ግምት አለን። እኛ በሙስናና በስርቆት ሊከሰሱ አይችሉም የምንልበት ምክንያት የሚከተለው ነው። አጼ ኃይለ ሥላሴ ከሁሉ በላይ አገር ወዳድ፤ በጣም ኩሩ፤ ለታሪካቸው ቀና ነበሩ። ለግል ጥቅምና ለባለጠጋነት የኖሩ አይደሉም። ለአገራቸውና ለክብራቸው የማያጠራጥር ክብደት ይሰጡ ነበር። ታሪክ እንዲያስታውሳቸው ይፈልጉ ነበር። አጣሪ ልኡካንን ሳይሆን መንግሥቱ ሃይለ ማሪያምን ፊት ለፊት የጠየቁት ያልነውን ያጠናክራል። <u>"ምን ያህል ገንዘብ የደበቅን ይመስልሃል? ብዙ ቢሊዮን ? አስራ አራት ቢሊዮን? ከየት ይመጣል። ለምን ጥቅም እናውለዋለን። በስደት ደልቶን እንድንኖርበት?"</u> 50/

ከስልጣን የሚመጣ ምዝበራ የግልና የጎሳዊ ቡድን እሴት ነው

የአገር ገንዘብ ለመስረቅና ለመደበቅ የሚሰረቅ ገንዘብ በገፍ መኖር አለበት። ሌባው ኩራትና ክብር የሌለው፤ ለአገሩና ለህብረተሰቡ ደንታ የሌለው መሆን አለበት። ለታሪኩና ለክብሩ ሳይሆን የሚኖረው ለራሱና ለቤተሰቡ መሆን አለበት። ከላይ የተጠቀሰውን ለመንግስቱ ሃይለ ማሪያም ካሉ በኋላ "ያላቸውንና የሌላቸውን ሁሉ ለኢትዮጱያ ሕዝብ እንዲመለስ ፈርመው አልፈዋል። ምዝበራና ለምዝበራ ያለውን እድል የሚለውን ለማመዛዘን የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ከመገልበጡ በፊት ምን ያህል እርዳታ ያገኝ ነበር? ለአፍሪካ አገሮች የሚሰጠው እርዳታ በጣም ያደገበት ወቅት አብዛኛወቹ ነጻ ከሆኑ በኋላ፤ የሶቭየት ህብረት ተወዳዳሪነት በጦፈበት ወቅት ነበር። ኢትዮጵያ ከማንኛውም የአፍሪካ አገሮች ዝቅተኛ እርዳታ ታገኝ ነበር። አብዛኛው እአአ ከ1974 በፊት የተሰጠው እርዳታ በአይነት ነው። ተቋሞች መገንባት፤ የቴክኒክ እርዳታ መስጠት፤ የትምሕርት እድል መክፈት ወዘተ። ለሙስና መንቀሳቀሻ ቀዳዳ አይሰጥም። <u>እአአ በ1970 ዎቹ በተለይ በ1974/75 የተሰጠው</u> የኦፊሴል እርዳታ በአመት ከመቶ ሚሊዮን ዶላር ያነሰ ነበር። ከእድገቱ ባጀት አስተዋጽኦ አስራ አምስት በመቶ በታች ነው። ይህ ዝቅተኛ ጥገኝነትን ያሳያል። ቢፈልጉም እንኳን፤ አጼ ኃይለ ሥላሴና ሌሎች ባለስልጣናት ከእርዳታ ለመስረቅ አያስችላቸውም። የተተካው የደርግ መንግሥት ለሙስና አላፈናፈነም። መንግስቱ ሃይለማሪያም በድሎት ለመኖር የቻለው በሰረቀው ገንዘብ አይደለም። አሜሪካኖች ስልጣኑን ለቅቆ እንዲሄድ በሰጡት ድጎማ ነው። ሌላው መመዝገብ ያለበት፤ በቅድመ ህወሓት/ኢህአዴግ የተገኘው እድገትና ልማት የውጭ እርዳታ ውጤት አልነበረም። የአገሪቱና የህብረተሰቡ ታታሪነት ውጤት ነው። ህብረተሰቡ እየተረዳዳ መንገድ፤ ትምኅርት ቤት፤ የጤና ጣቢያ፤ ድልድይ ወዘተ ይሰራ ነበር።

ከ1957-61 በነበረው የአምስት አመት የልማት እቅድ፤ መንግሥት ያተኮረው በመሰረተ ልማት ላይ ነበር። ከ1962-67 ያተኮረው በኢንዱስትሪ፤ በተለይ ከእርሻ ምርት ጋር በተያያዘ የፋብሪካ ስራ ላይ ነበር። ከ1968-73 ትኩረቱ ከትምሕርት መስፋፋትና ከዝቅተኛ የእርሻ ልማት ላይ ነበር። ከ1974-75 የመገናኛና ቴሌ ተቀዳሚነት አገኙ። በሶስተኛው እቅድ የእድገት ባጀቱ ሶስት ቢሊዮን አንድ መቶ አስራ አምስት ሚሊዮን ብር ደርሶ ነበር። ማነቆ ሆኖ የተገኘው የተማረ የሰው ሃይል እንደተፈለገው አለመገኘቱ ነው። በዚያ ወቅት እድገቱ በአመት ሶስት ነጥብ ሁለት በመቶ ደርሷል። ከ1970-1974 እድገቱ በአመት 3.6 በመቶ አስመዝግቧል። በአንጻሩ ህወሓት/ኢህአዴግ ከ1995-2000 ያስመዘገበው 3.0 በመቶ ነው። ለማነጻጸር በ1970ዎቹ የሱዳን እድገት በአመት አንድ ነጥብ ሶሥት በመቶ፤ የዩጋንዳ አምስት ነጥብ ስድስት በመቶ ነበር። ሌላው የእድገት መለኪያ ወደ ውጭ የሚላከው እቃ በአመት ሶስት ነጥብ አምስት በመቶ እድገት ማሳየቱ ነው። ኢትዮጵያ ስንዴ፤ ማሽላ፤ ገብስ፤ ሰሊጥ፤ የተዘጋጀ ቆዳ፤ ቡና ወዘተ ለውጭ ገበያ ታቀርብ ነበር። አበባና ወርቅ ከመጨመሩ በስተቀር የአሁኑ የንግድ መዋቅር በአጼ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ከነበረው እምብዛም አይለይም። ዛሬ በአመት አራት ቢሊዮን ዶላር የደረሰው እርዳታ መዋቅሩን አልለወጠውም። በአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት በጣም የሚያስደንቅ ከአመት አመት እድግት ያሳይ የነበረው መጓጓዣና ቴሌ ነው። በአመት 9.3 በመቶና 15.6 በመቶ እድገት አሳይቷል። ተከታታይ መንግሥታት፤ የኢትዮጵያን ወንዞችና ጅረቶች ለመገደብና የሃይል ማመንጫ፤ የመስኖ እርሻ ማስፋፊያና የኢንዱስትሪ ምርት ማሳደጊያ አውታር ለማድረግ ሞክረው ነበር። ግራሃም ሃንኮክ፤ The Sign of the Seal: the quest for the lost ark of the covenant በተባለው መጽሃፉ ጀምስ ብሩስን በመጥቀስ እንዲህ ብሏል። "አጼ ላሊበላ ላሊበላን ሲሰሩ፤ ግብጽን ለመቆጣጠርና አገራቸውን ለማልማት የአባይን ግድብ ለመስራት አስበው ነበር።" ይህ የሚያሳየን፤ ቢችሉ ኖሮ የኢትዮጵያ መሪዎች አባይን ለልማት ያውሉት ነበር። በግብጽና በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል ያለው ግጭትና ጥርጣሬ ዛሬ የመጣ አይደለም። የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት የአሜሪካኖችን ቴክኒካል ተራድኦ ተጠቅሞ ሰፊ ጥናት አደረገ። ግድቦችን ለመስራት አማራጮች አቀረበ። ሆኖም፤ አበዳሪ ድርጅቶች ለግብጽ ተቀዳሚነት

በመስጠት እቅዱ ወደ ተግባር እንዳይለወጥ አድርገዋል። ዛሬ ገዢው ፓርቲ የጀመረው የተሃድሶ ግድብ ሃሳቡ የተጸነሰው በአጼ ላሊበላ መንግሥት ነበር።

ሊካድ የማይቻለው፤ እአአ በ1970ዎቹ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ፤ በኢንዱስትሪ ውጤት አቅርቦት፤ በምግብ ምርት ከፍተኛነት፤ በአገልግሎት መስፋፋት አገር ወለድ የሆነ አይነታዊ ለውጥ አሳይቶ ነበር። ዶክተር አለማየሁ ገዳ ባደረገው ጥናት "አጠቃላይ የአገር እድገት ውጤት ሲታይ (GDP) ከፍተኛ እድገት ያስመዘገበውና የሰውን ህይወት የለወጠው የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ነው። እድገቱ በአመት አራት በመቶ (4 percent) ነበር።" ለማነጻጸር እንዲረዳ፤ በ1970 GDP per capita $645 የተመዘገበው በ2000 ወደ $572 GDP per capita ወርዶ ነበር። የውጭ እርዳታው መጉረፍ ሲጀምር በፍጥነት ወደ ላይ ሄዷል። በ2010 ወደ $995 ተሸጋገረ። በዚያ አመት የእርዳታ መጠን አንድ ቢሊዮን ዶላር ነበር። አንባቢ እንዲመዘግበው የምንፈልገው የአጠቃላይ ገቢና የውጭ እርዳታው የተመጣጠኑና የተያያዙ መሆናቸውን ነው። የእርዳታው መጠን እያደገ ሲሄድ፤ የአገሪቱ ጠቅላላ የምርታና የአገልግሎት ውጤት ያድጋል። የእድገቱ ባጀት--በውጭ እርዳታ ምክንያት--በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ከነበረው ድጎማ--ከልማቱ ባጀት አስራ አምስት በመቶ--በህወሓት/ኢህአዴግ ወደ አርባ በመቶ ደርሷል። የላቱ ባጀት ከዚህ በላይ። ይህ ልማት ወላጅ የሚመስል ጭማሬ አሳሳች ነው። ጠቅላላ የአገር ምርትና አገልግሎት ውጤት (GDP) የግለሰቦችን የኑሮ መሻሻል አያሳይም። የእድገቱ ተጠቃሚዎች ጥቂት ግለሰቦችና ቤተሰቦች ናቸው። በኢትዮጵያ የገቢና የኑሮ ልዩነት በጣም የሰፋው ለዚህ ነው። በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በአፈሻል ደረጃ የተገኘው የውጭ እርዳታ በአመት ከመቶ ሚሊዮን ዶላር አልፎ አያውቅም። ህወሓት/ኢህአዴግ ስልጣን ይዞ አስር አመት ሳይሞላው በአመት አንድ ቢሊዮን ዶላር ደረሰ። ከአጼ ኃይለ ሥላሴ <u>አስር ጊዜ ጨመረ</u>። አሁን አርባ ጊዜ ጨምሯል። እርዳታ ሰጭዎች ለአጼ ኃይለ ሥላሴና ለደርግ ንፉግ ነበሩ። ለህወሓት/ኢህአዴግ ለጋስ ናቸው።

ለህወሓት/ኢህአዴግ እነደጎርፍ የፈሰሰው እርዳታ እያደገ መሄድ (በዶላር/ቢሊዮን)

| አመት | 2001 | 2003 | 2005 | 2008 | 2010 | 2012 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ዶላር (በቢሊዮን) | 1.1 | 2.0 | 2.0 | 3.0 | 3.4 | 4.0 |

ለስምንት አመታት ለጋስ መንግስታትና ድርጅቶች ለህወሓት/ኢህአዴግ በአመት በአማካይ አንድ ቢሊዮን ስድስት መቶ ሰማንያ ስምንት ሚሊዮን ዶላር በቀጥታ ለመንግሥት ካዝና አስተላልፈዋል። አምሳ ሶስት በመቶ የሚሆነው እርዳታ ወለድ የማይከፈልበት ስጦታ ነው። አብዛኛው የዓለም ባንክ አይዳ የተባለው ድርጅት የሰጠው ነው። በተጨማሪ፤ ህወሓት/ኢህአዴግ ከባጀቱ ውጭ (Off Budget) በአመት ግማሽ ቢሊዮን ዶላር ($500 million) እንደሚያገኝ አስተማማኝ የሆነ መረጃ አኢሲዲና አንድ የካናዳ ጥናት አቅርበዋል። አንድ ቢሊዮን አንድ መቶ ሚልዮን ዶላር ሲባል አንድ ቢሊዮን ስድስት መቶ ሚሊዮን ብሎ መተርጎም ያስፈልጋል። ቁም ነገሩ ሁለት ነው። አንድ፤ የኢትዮጵያ አስደናቂ እድገት የተባለው ውጤት በውጭ እርዳታ መሰረተ ልማትና የፍጆት ኢኮኖሚ (ህንጻ፤ ቪላ፤ ሆቴል፤ መዝናኛ ወዘተ) አስደናቂ በሆነ ፍጥነት ያንቀሳቀሰ ነው። ሁለት፤ ይህ እርዳታ ብዙ ቀዳዳዎች ይታዩበታል። ጥቅሙን የሚቆጣጠር ነጻ ተቋም የለም (There is no independent oversight at all). ቀዳዳ ሲኖር የመስረቅ፤ የአዲስ ባለጠጋነት፤ የሙስናና የመደበቅ እድል ይሰፋል። ይህ ወንፊት ለጥቂቶች አቅምን አጠናክሯል። ሶስት፤ በሕዝብ ኑሮ መሻሻል መለኪያ ሲታይ፤ ለህወሓት/ኢህአዴግ የተሰጠው አርባ ቢሊዮን ዶላር (ከባጀት ውጭ ያለውን ጨምሮ) እርዳታ የአብዛኛውን ህብረተሰብ ህይወት አላሻሻለም። እንዲያውም አባብሷል የሚሉ ብዙ ናቸው። አራት፤ በአገር ደረጃ ሲታይ፤ እርዳታ የወጣቱን፤ የሴቶችን፤ የድሃውን አቅም አላጠናከረም። አርባ ስድስት በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተጠይቆ "እድል ስለሌለ አገሬን መልቀቅ "እፈልጋለሁ" ብሏል። ከወጣቱ ትውልድ ሰባ ስድስት በመቶ የሚሆነው "ከመሰደድ ሌላ አማራጭ የለም" ይላል። ማስረጃው የሚያመለክተው "እድገታዊው መንግሥት" እድል ፈጣሪ አለመሆኑን ነው። ችግሩ የአገዛዝና የፖሊሲ ችግር ነው። ኢኮኖሚው መወቅራዊ ለውጥ ስላላመጣ፤ የምርት ሃይሎች እአአ በ1970ዎቹ ማሳየት የጀመሩትን የአገር ውስጥ እንዱስትሪና የእርሻ ምርት እድገትና የስራ እድል መፍጠር ከህብረተሰቡ የአቅርቦት ፍላጎት ጋር አብሮ አላሳደገውም። ባለማሳደጉ፤ ሃብት ያላቸው ግለሰቦችና ሌሎች ያለውን የተመጠነ አቅርቦት (Limited supply) ይሻሙታል። ለመግዛት የሚችለው የገቢ አቅም ያለው ሆኗል። አቅርቦት ከፍላጎት (Supply and Demand) ጋር አብረው ለመሄድ ስላልቻሉ የዋጋ ግሸበት ህብረተሰቡን ያስቃየዋል። ህወሓት/ኢህአዴግ ለልማት አዲስ ትርጉም

በመስጠት ላይ ነው። "እድገት ለጥቂቶችም ቢሆን ልማትን ያመጣል። ከድህነት ነጻ ያወጣል። ስደት ዓለም አቀፋዊይነት (Globalization) ያመጣው ነው። የሌለው በእድሉ ይኑር። የዋጋ መናር የልማት ምልክት" ነው ወዘተ የሚሉ።

የኢትዮጵያ እድገት የሚመራው በአንድ ፓርቲ የበላይነትና እራሱ በመረጣቸውና በሚፈጥራቸው አዲስ ባለጠጋዎች ባለቤትነት ነው። ከቻይና ጋር ይመሳሰላል የሚባለው ለዚህ ነው። ሆኖም፤ ሁለቱ በጣም የተለያዩ ናቸው። የቻይና ብሄራዊ ነው። የውስጥ የግል ውድድር የጦፈበት፤ የገጠሩና የከተማው ኢኮኖሚ የተሳሰረበት፤ መካከለኛ መደብ በፍጥነት እያደገ የሚታይበት ነው። በቻይና የነፍስ ወከፍ ገቢ እያደገ ሄዷል። በኢትዮጵያ ፍንከች አላለም። የአብዛኛውን ገቢ የመግዛት አቅም የዋጋው ግሽበት ቀንሶታል። በቻይና የስራ እድል እንደልብ ነው። በኢትዮጵያ የተማረው ምርጫው መሰደድ ነው። በቻይና ከተሜነት (Urbanization) በሚያስደንቅ ሁኔታ እያደገ ነው። ቻይናዎች ሮምን የሚያህል ከተማ በወር ይሰራሉ ይባላል። ለገጠሩ ያልተማረ ከሁለት መቶ ሚሊዮን በላይ ለሚገመት ሕዝብ በከተማ የመስራት እድል ፈጥሯል። የኢትዮጵያ ከተሜነት ከአስራ ሰባት በመቶ በላይ አላደገም። የገጠሩ ደሃ ወደ ከተማ ሲያመራ የሚገጥመው የስራ፤ የምግብና የመኖሪያ ችግር አስከፊ ደረጃ ላይ ደርሷል። ይህ የሚያሳየው የገጠሩ ኢኮኖሚ መሰረታዊ በሆነ መንገድ አለመለወጡን ነው። ገጠር ሲባል "ጨለማ" ማለት አይደለም። የገጠሩ ኢኮኖሚ ወደ ዘመናዊይነት ይለወጥ ሲባል የገጠሩን ህብረተሰብ ባለበት አቅሙን ማሳደግና ገቢውን ከፍ ማድረግ ማለታችን ነው።

የእርዳታ ስኬታማነት መለኪያ፤ ለጋስ የሆኑ ድርጅቶች የገጠሩን ህብረተሰብ አቅም ሲያጠነክሩት ነው። የገጠሩ ሕዝብ ኑሮ ተሻሽሎ ወደ ዘመናዊነት ሲለወጥ፤ የገጠር ከበርቴዎች በብዛት ያብባሉ። የቁጥጥር አመራር ይህን ለማድረግ አይችልም። ሃቁ፤ የኢንዱስትሪ ስራ ለማግኘት አማራጭ የለም። ከገጠር የሚፈልሰው ደሃ ሕዝብ የከተሜውን ችግር አባብሶታል። የምግብ ዋጋ ከመግዛት አቅም በላይ ሆኗል። መኖሪያ ቤት ህልም ነው ወዘተ። እኛ "የዱሮዎቹ" የምናውቀው የመግዛት አቅም አሁን የለም። ዘጠና አራት ሚሊዮን የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ የመብላት ወይንም የመራብ፤ የመስራት ወይንም የመሰደድ፤ ቤት ውስጥ የመኖር ወይንም መንገድ ላይ የመኖር እድሉ ሆኗል። ሁሉን የሚያካትት አገዛዝ ካልተፈጠር የአገሪቱ ሕዝብ እየጨመረ ሲሄድ ምን ሁኔታዎች ሊከሰቱ ይሆን ብለን ማሰብ ግዴታ ነው። የሕዝብ እድገት ችግር አይደለም። ለእድገት አስፈላጊ ነው። ሆኖም፤ የሕዝብ ጭማሬ ጠቃሚ የሚሆነው የመስራት፤ የማምረት፤ የግል ሃብት የመያዝ እድል ሰፊ ሲሆን ነው። የሌሎችም አፍሪካ አገሮች ሕዝብ ቁጥር ይጨምራል። በኢትዮጵያና በሌሎች የአፍሪካና ሌሎች በፍጥነት ያደጉና በማደግ ላይ ያሉ አገሮች የሚታየው የማህበረሰብና የኢኮኖሚ እድል ክፍትነት ትኩረትና ስፋት ነው። የማህበረሰብ ትኩረት ያለው አገር ለሰብአዊ ህይዎትና ክቡርነት ከፍተኛ ዋጋ (Value Premium is socially oriented) ይሰጣል። ለምሳሌ፤ ይኼ ዋጋ ያለው ትኩረት ሁሉም ወጣት ሴቶች የትምሕርት እድል እንዲኖራቸው ያደርጋል። የተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎች፤ በተለይ በትምኅርት እድል፤ በስራ፤ በመሰረተ ልማት ኋላ ቀርና የተጎዱ ጎሳዎችና ክልሎች (ጋምቤላ፤ አፋር፤ ኦጋዴን፤ ቤኒ ሻንጉል ጉሙዝ ወዘተ) አስቸኳይ የመንግሥት ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል። እነዚህ የሃገር ክፍሎች ሰላምና እርጋታ እንዲኖራቸው ከተፈለገ የሕብረተሰቦቻቸው ህይዎት መሻሻል አለበት።

የሕዝብ ቁጥር እያደገ መሄዱ አያከራክርም፤ የተፈጥሮ ሕግ ነው። የፖሊሲው ትኩረት እየጨመረ የሚሄደውን ሕዝብ፤ በተለይ የወጣቱን ትውልድ አቅም ማጎልመስ ነው፤ ጥራት ያለውና ወደ ስራ የሚያመራ የትምህርት አቅርቦት ወሳኝ ነው። የቻይናና የሕንድ ሕዝብ ቁጥር (የእያንዱ) ከአንድ ቢሊዮን በላይ ነው። የሕዝባቸውን ቁጥር ወደ ጥንካሬ እየለወጡት ነው። ስለዚህ፤ የሕዝብ ብዛት ችግር አይደለም፤ ጥሪት ነው። ሆኖም፤ ለሃገርና ለመላው ሕዝብ የሚቆረቆርና ቀን ከሌት የሚሰራ የመንግሥት አመራር ከሌለው የሕዝብ ብዛት ችግርን፤ ብጥብጥን፤ እልቂትን፤ የተፈጥሮ ሃብት ሽሚያን ወዘተ ያስከትላል። ፓኪስታን እንደተከሰተው።

የሕዝብ እድገት በአራት የአፍሪካ አገሮች ሲታይ

| የአገር ስም | ስምና በ2012 የሕዝብ ቁጥር (በሚሊዮን) | የህዝብ ቁጥር ብዛት በ2050 (በሚሊዮን) |
|---|---|---|
| ኢትዮጵያ | 94 | 278 |
| ጋና | 23 | 39 |
| ኬንያ | 38 | 65 |

| | | |
|---|---|---|
| ናይጀሪያ | 146 | 281 |

የዛሬ ሰላሳ ሰባት አመት የኢትዮጵያ ሕዝብ የዛሬውን ሶስት ጊዜ ይሆናል። በቀላሉ ስናየው፤ መመገብ ይኖርበታል። መኖሪያ ያስፈልገዋል። ጤናው መጠበቅ ይኖርበታል ወዘተ። በተፈጥሮ ሃብት፤ በተለይ በእርሻ መሬትና በውሃ ላይ የሚደርሰው ሽሚያ ከፍተኛ እንደሚሆን ታላቅ ልቦና (Intelligence) አይጠይቅም። አስከፊ ረሃብ ቢከሰት--አገዛዙ ካልተለወጠ መከሰቱ የማይቀር ይመስለናል--የሕዝብ አመፅና መፍለስ ወሰን አያግደውም። የፖሊሲ መሰረቱ ዛሬ ካልታነጸና ወደ ብሄራዊይነት ካልተቀየረ አደጋው ቁልጭ ብሎ ይታያል። መርሊን የተባለ የመንግሥት ያልሆነ ድርጅት በ2012 ያቀረበውን ዘገባ ባጭሩ እንመልከት። ሰማንያ በመቶ (80 percent) የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚኖረው ዓለም ባንክ አስፈላጊ ነው ብሎ ከገመተው ዝቅተኛ ገቢ በቀን ከ$1.25 በታች ነው። ሁለት ዶላር በቀን ብንጠቀም፤ ዘጠና በመቶ የሚሆነውን ኢትዮጵያዊ ይሸፍናል። "የጤና አገልግሎት ከአለም የመጨረሻ ነው። 0.22 ሃኪም አንድ ሺህ ኢትዮጵያውያን ያክማል። (A ratio of 0.22 physician per 1,000). ምግብ በማጣት እድገታቸው የተበከለ (malnourished) ህጻናት ቁጥር ሰላሳ አምስት ከመቶ ደርሷል። አስራ ሁለት ሚሊዮን የሚሆኑ (15 percent of the population) ኢትዮጵያውያን በውጭ የምግብ እርዳታ ይኖራሉ። የንጽህና አገልግሎት አለው የሚባለው ቤተሰብ አስራ ሰባት በመቶ ነው። ንጹህ ውሃ ማግኘት እንደ ምኞት ይቆጠራል። በገጠር የሚኖረውን ደሃ ሕዝብ ስናይ፤ የመሬት ይዞታ መጥበብና መበላት ኑሮውን አባብሶታል። ህወሓት/ኢህአዴግ አዲስ ጭሰኞች ፈጥሯል። ይኼ ምንም አያስደንቅም። ከላይ እንደ ጠቀስነው ኢትዮጵያ የምትደማው ከገንዘብ ሺሺት ብቻ አይደለም፤ ከተማረና ከሰለጠነ የሰው ሃብት ሺሺት ጭምር ነው። የካናዳው CUSO International ተቋም እንደመዘገበው ከ1990-2006 ኢትዮጵያ 3,700 ሃኪሞች ከፍላ አሰልጥና 3,000 ከሃገር ተሰደዋል/ወጥተዋል። የኢትጵያ ሕዝብ ባስተማረውና ባሰለጠነው የሰው ሃብት ሊጠቀምና ሊመካ አልቻለም ማለት ነው። የሕዝብ ቁጥር እያደገ ሲሄድ ሁኔታው መፍትሄ ካላገኘ ችግሩ እየከፋ እንዲሚሄድ አንጠራጠርም። የሕብረተሰቡን ደህንነት ወደፊት የሚመጣውን በጠቅላላ የአገር ገቢ መመዘኛ ብቻ ለማየት አይቻልም። አጠቃላይ ሁኔታን መመዘን አስፈላጊ ነው። የነፍስ ወከፍ ገቢ፤ እኩልነት (Equality of opportunity) ፤ ፍትህ-ርትዕ፤ ሰላም፤ እርጋታ ወዘተ ለመተንበይ አንችልም። ሆኖም በመተንበይ ስራ ልምድ ያላቸው ድርጅቶች የሚያቀርቡትን መናቅ አደገኛ ነው። ካርኔጊ ኢንዳውሜንት--The World in 2050: technological catch-up ያቀረበው ለኢትዮጵያ አግባብ አለው። "ኬንያ የተሻሻለ የቴክኖሎጂ እድገት" ታሳያለች ይላል። ምክንያቱም፤ "የመንግሥት በበለጠ ደረጃ ግልጽነትና ለግል ክፍሉ አጋዥነት፤ የመሰረተ ልማት (Physical Infrastructure) በተለይ የዘመናዊ መገናኛ ቴክኖሎጂ መስፋፋት፤ የፕሬስ ነጻነት" ይገኙበታል። በእነዚህ መስፈርቶች ሲታይ፤ የኢትዮጵያ አስተማማኝ አይደለም የሚል ግምት ሰጥቷል። ግምቱን ባንቀበል ኢትዮጵያ ዛሬ የት ደርሳለች፤ እንዴትስ ሌሎች ከደረሱበትና ከሚደርሱበት የተሻሻለ ልማት ትደርሳለች ብለን መጠየቅ ተገቢ ነው። በ2012 መጨረሻ ሶስት የመሰረት ልማት ክፍሎችን እናወዳድርና በ2030ና በ2050 ጠቅላላ የአገር ገቢን እንይ።

መሰረተ ልማት---ዘመናዊ መንገድ (Paved) የኢንተርኔት ስርጭት የሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት (ከመቶ)


| የአገር ስም | ዘመናዊ መንገድ | ኢንተርኔት ስርጭት | ሁለተኛ ደረጃ |
|---|---|---|---|
| ኢትዮጵያ | 12.7 ሺኪሜ | 0.4 በመቶ | 24.0 (በመቶ) |
| ጋና | 14.9 ሺኪሜ | 3.8 በመቶ | 45.0 (በመቶ) |
| ኬንያ | 14.1 ሺኪሜ | 8.0 በመቶ | 43.0 (በመቶ) |
| ናይጀሪያ | 15.0 ሺኪሜ | 6.8 በመቶ | 32.0 (በመቶ) |

መሰረተ ልማት ለቀጣይነት እድገት ቁልፍ ነው። ኋላ ቀር የሆኑ ክልሎች፤ አፋር፤ ኦጋዴን፤ ጋምቤላ፤ ቤኒ ሻንጉል ጉሙዝ ወዘተ ከፍተኛ መሰረተ ልማት ያስፈልጋቸዋል፤ የሌሎችም ሚዛናዊ በሆነ መንገድ መስተካከል አለበት። ኢትዮጵያ አስደናቂ መሰረተ ልማት አካሂዳለች ቢባልም ከሌሎች አገሮች ጋር ስትነጻጸር በማኛውም መሰረተ ልማት ኋላ ቀር ናት፤ ከአየር መንገድ አገልግሎት በስተቀር። ኢትዮጵያ በመንገድ ስራት ስፋትና ጥራት በኩል ኢትዮጵያ ኋላ ቀር መሆኗን

ከላይ ባለው ሰንጠረዥ አሳይተናል። ቁም ነገሩ ኋላ ቀር መሆኗ አይደለም። የተመዘዘነ የመንገድ መረብ ያስፈልጋታል የሚለው ነው። ይኼ ብቻ አይደለም። ለዘመኑ እውቀትና ኑሮ ማሻሻል ቁልፍ በሆነው በኢንተርኔት ስርጭት ከሶማልያና ከሌሎች “ደሃ” ናቸው ከሚባሉ አገሮች እጅግ በጣም ወደኋላ ቀርታለች። አንባቢው እንዳይረሳ፤ እንዳትረሳ የምንፈልገው መንገድ መስራት፤ ዘመናዊ መገናኛ ማስፋፋት ብቻቸውን ዋግ አይኖራቸውም። መንገድ ምግብ፤ ውሃ፤ ቤት ወዘተ አይሆንም። ቻይና መንገዶችንና ሌሎች መሰረተ ልማቶችን በቀጥታ ከምርትና ከአገልግሎት ጋር አያይዛለች። የከተሞች ልማት በቀጥታ ከመካከለኛውና ከደሃው ህይወት ጋር የተቆራኘ ነው።

እትዮጵያ በዘመናዊ መገናኛ የምትከተለው ፖሊስ ለወጣቱ ትውልድ የወደፊት አደጋ ሆኖበታል፤ እውቀትና አቅም እንዳይኖረው ማነቆ ስለሆነ። በመላው ዓለም የሚታየው ሃቅ፤ መንግስታት የዘመናዊ መገናኛ ቴክኖሎጂን ለህብረተሰባቸው ጥቅም ቅድሚያ ሰጥተውታል። የባንግላደሽ ገጠር ሴቶችና ወጣቶች ድህነትን እያሸነፉበት ነው። ከዚህ በታች እንዳለ ያቀረብነው ሰንጠረዥ፤ የዓለም አቀፍ ቴሌኮም ዘገባ በ2012 የሚያሳይ እውነተኛ ገጽታ ነው። ገዢው ፓርቲ ከቻይና የሸመተውን ቴክኖሎጂ ለወጣቱ ትውልድ ኑሮ ማሻሻያ አላዋለውም። የሚጠቀምበት ለስለላ፤ ለክትትል፤ ለአፈና ነው። በአፈና የተወለደ፤ ያደገና የተማረ ትውልድ ለራሱ ለማሰብ፤ በራሱ ተፍጨርጭሮ አዲስ ስራ ለማቋቋም፤ በራሱ ለመተማመን፤ ራሱን ረድቶ ህብረተሰቡንና አገሩን ለመርዳት አይችልም። አብዛኛው እድሉን የሚፈልገው በውጭ ይሆናል። የዘመናዊ ቴክኖሎጂ አፈና የእድል አፈና ነው።

የዘመናዊ መገናኛ ስርጭት በአፍሪካ አገሮች (ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ)




የኢትዮጵያ ተሳታፊነት ከመካከለኛው አፍሪካ ያንሳል፤ አይታይም። ህወሓት የዘመናዊ መገናኛን አፍኖ የያዘበት ዋና ምክንያት ሕዝቡ፤ በተለይ ወጣቱ ትውልድ ዜናና እውቀት እንዳያገኝ፤ ማለትም፤ ለቁጥጥርና ለአፈና እንዲያመች ነው። የመገናኛ ብዙሃን የሌለው ሕዝብ ለመብቱ ለመታገል የሚችለውን እውነተኛ ዜና አያገኝም። ነጻ የሆነ ፕሬስ ለነጻነት ቁልፍ ነው፤ ለልማት አስፈላጊ ነው። መሰረተ ልማት ከዜጎች ህይወት ጋር መያያዝ አለበት። የኢኮኖሚውና የማህብረሰቡ መሻሻል አብረው ስላልተያያዙ። አስደናቂ እድገት ታይቷል በሚላቸው፤ ብዙ መቶ ሚሊዮን ዶላር በፈሰሰባቸው በመንገድና በሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት ስፋት በውጭ እርዳታ በአፊሪካ አንደኛ፤ በዓለም ሶስተኛ የሆነችው

ኢትዮጵያ ከዝቅተኛ ደረጃ ላይ መሆኗን ልንክድ አንችልም። የእንግሊዙ ሳሴክስ ዩኒቨርሲቲ ባደረገው ጥናት ደሃውን "መንገድ፤ ትምህርት ቤት፤ የጤና ጣቢያ ወዘተ ተሰራልህ። ስለዚህ ድህነት እየቀነሰ ነው" ሲሉት አብዛኛው፤ "እንዲያውም ከባሰ ድህነት ደርሰናል። ሶስት ምግብ ለመብላት አንችልም" የሚል መልስ ተሰጥቶታል። የተማረው ስለ ኢንተርኔት ቢጠየቅ የሚሰጠው መልስ ምን እነደሚሆን መገመት አያዳግትም። ለየካቲት ስድሳ ስድስት አብዮት መነሻ የሆነው የወሎ ሕዝብ ሲጠየቅ፤ "ድህነትና ረሃብ ጨምሯል" ይላል። ይህን ድምዳሜ ያቀረቡት ተቋሞች የህወሓት ጠላት አይደሉም። የፖለቲካ ጥቅም የላቸውም። የእድገት ባለሞያዎች በመሰረተ ልማትና በአጠቃላይ የአገር ገቢ ግንኙነት አለ ይላሉ። ከእነዚህ፤ በፈጣን እድገት፤ በጠቅላላ ገቢና በኑሮ መሻሻል ግንኙነት እንደሌለ የሚናገሩ ብዙ ናቸው። (There can be rapid growth without fair and equitable income distribution). አንድ ደሃ ገበሬ የአባይን "ተሃድሶ" ግድብ በማየት ሊኮራ ይችላል። ሆኖም፤ ግድቡ በመስኖ እንዲያርስና ገቢውን እንዲያሻሽል ካልረዳው እድገቱ ያመጣለት ህይወት ለዋጭ ነገር የለም። ይህን መሰረተ ሃሳብ በየቦታውና በየ ኢኮኖሚ ክፍሉ ለማየት ይቻላል። እድገት እኩልነት ማለት አይደለም። በህግ ካልተዳኘ፤ እድገት በቀጥታ የእድል እኩልነት የሌለበት ህብረተሰብ ይፈጥራል። የእድል እኩልነት የፖለቲካ ውሳኔ ነው። ምንም ሳንቲም ሳይኖራቸው በፖለቲካ ስልጣን <u>ሚሊኒየርና ቢሊኒየር የሆኑ ኢትዮጵያውያን</u> ባለጠጋነት ያገኙት በፖለቲካ የበላይነት ነው። ይህን መሰረተ ሃሳብ ይዘን የአራቱን አፍሪካ አገሮች--ኢትዮጵያ፤ ጋና፤ ኬንያና ናይጀሪያ--ስናይ፤ በ2050፤ በቢሊየን ዶላር ሂሳብ ጠቅላላ የአገር ገቢ የኢትዮጵያ $380፤ የጋና $350፤ የኬንያ $400፤ የናይጀሪያ $1,650 ይደርሳል የሚል ግምት ካርኔጊ የተባለው ድርጅት አቅርቧል። በዚያ ጊዜ ሕዝቧ ሁለት መቶ ሰባ ስምንት ሚሊዮን የሚሆነው ኢትዮጵያ፤ ሕዝቧ ስድሳ አምስት ሚሊየን ከሚሆነው ከኬንያ አትደርስም ። ናይጀሪያ ትሪሊዮን አልፋ በአፍሪካ የመጀመሪያ የኢኮኖሚ እድገት ትጎናፀፋለች። በጠቅላላ የምርትና የአገልግሎት ውጤት አንጻር ሲታይ፤ የአንጋፋዋ ናይጀሪያ $6,500፤ የጋና $8,500 (ከሁሉም ከፍተኛ)፤ የኬንያ $4,500፤ የኢትዮጵያ (ከሁሉም መጨረሻ) $1,500 ተገምቷል። ይህ የሚያሳየው፤ አሁን የገቢና የኑሮ ልዩነት እየሰፋ ስለሄደ በ2050 የገቢና የኑሮ ልዩነት እየተባባሰ ይሄዳል። የአብዛኛው ሕዝብ ኑሮ ድህነት ይሆናል። ጥቂት ባለጠጋዎችና ቤተሰቦቻቸው ታይቶ የማይታወቅ ሃብት በአገር ቤትና በውጭ ይኖራቸዋል። የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ለወጣቱ ትውልድ እንደልቡ አለመድረሱ ለዚህ ኋላ ቀርነት አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ አንጠራጠርም። ወጣቱ ትውልድ ምን አይነት ዓለም እንደሚገጥመው ከአሁኑ ማሰብ አለበት እንላለን።

የብሄራዊ ልማትና ሃብት ጭማሪ ምስጢሩ ምንድን ነው?

ድህነትን ለማጥፋት ተብሎ የተቋቋመው ዓለም ባንክ ከማበደርና ከለጋስነት (Grants) ተግባሩ የበለጠ የሚጠቅመው በሚያበረክተው ጥልቀት ጥናትና የሌሎችን አገሮች ልምድና እውቀት አበርካችነቱ ነው። ከጥቂት አመታት በፊት ባደረገው ሰፊ ጥናት ቀጣይነት ወይንም ተከታታይነት ያለው የልማት ሂደት ምን እንደሚመስል አሳይቷል--Where is the Wealth of Nations--ከሌሎች ሰፊ ጥናቶች ለፖሊሲ አቀራረፅ ተገቢ የሆነበትን ምክንያት በአጭሩ እናቀርባለን። መሰረቱ የእሴትና የተቋሞች የበላይነት ነው። ሕዝብ በአገዛዙና እርስ በእርሱ ያለው እምነት፤ ድምጽ (ነጻ ምርጫ፤ የመሪዎች ተጠያቂነትና ሃላፊነት) ፤የህብረተሰብና የሃገር ሰላምና እርጋታ (Peace and Stability) ፤የአገዛዙ ቀልጣፋነትና ፍትሃዊይነት፤ የደንቦች ግልጽነትና አሳታፊነት፤ የህግ የበላይነት፤ የመንግስቱ ፀረ-ሙሰኛነት ናቸው። ራቅ ብሎ ለሚያያቸው፤ እነዚህ የተከታታይና የፍትሃዊ ልማት (Development) መለኪያዎች አንድ ሁለት ተብለው እንደ ገንዘብ የሚቆጠሩ አይደሉም። ሆኖም ወሳኞች ናቸው። ብሄራዊ ልማት ተከታታይነት የሚኖረው ቅድመ ሁኔታዎች ዝግጁና ግልጽ ሲሆኑ ነው። በማንም አገር ህግ መኖሩ አያከራክርም። አንዱን ከሌላው የሚለየው፤ዲሞክራሳዊ በሆኑ አገሮች ህገመንግስት ከማንም ፓርቲና ባለስልጣን፤ ከማንም ደንብና፤ ከማንም ተቋም በላይ ከፍተኛነትና ተከባሪነት ያለው ሲሆን ነው። ሁሉም የሚቀበለውና የሚዳኝበት የሕዝብ የበላይነት አመልካችና መመሪያ በመሆኑ ነው። በህግ ፊት ሁሉም እኩል ነው። ይህ በኢትዮጵያ ታሪክና ባህል የተለመደ ነበር። ዜጋ "በህግ አምላክ" ሲባል የሚቆመው ለህግ አክብሮት ስላለው ነው። ህግ "ከተመለከ" ተከብሯል ማለት ነው። ለመከበር ሁሉንም በእኩልነት ማስተናገድ አለበት። የህወሓት/ኢህአዴግ መሪዎች ከህግ በላይ ናቸው።

የህወሓት/ኢህአዴግ ህገመንግስት ራሳቸውን በትጥቅ ትግል ቤተመንግስት አስገብተው በህብረተሰቡ ላይ የጫኑት የጥቂት ቡድኖችን የፖለቲካ ስልጣንና የኢኮኖሚ ጥቅም አገልጋይ ነው። አንቀፅ አምሳ ሁለት እንዳስቀመጠው፤ በዚህ ህገመንግስት ስልጣን ሊከፋፈል አይችልም። ህግ አውጭው፤ ህግ ፈጻሚውና ህግ አስፈጻሚው አንድ ወጥ ነው (Unity of Power) ይላል። ስልጣን፤ ሃላፊነትና ተጠሪነት ከላይ ወደ ታች ነው። የፖለቲካ፤ የማህበራዊይና የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችና አፈጻፀም ከገዡው ፓርቲና ከበታቾቹ ውጭ ሊታሰቡ አይችሉም። የገዢው ፓርቲ የበላዮች ካልፈቀዱ ማንኛውም ውሳኔ በአቤቱታ ሊመለስ አይችልም። በተግባር፤ የትግራይ ተወላጆች የትም ቦታ ለመኖር፤ ለመስራት፤ ባለጠጋ ለመሆን፤ ለመግዛትና ለመዳኘት ይችላሉ። ሌላው ተወላጅ ተመሳሳይ መብት የለውም። የፖለቲካና የህግ

ውሳኔው አንድ ነው። ስርአቱ ለማፈንና ለማነቅ ያስችላል (Strangulation is legally enabled). ስለሆነም፤ መንግሥት አንድን ግለሰብ "ሽብርተኛ ነህ" ብሎ የፖለቲካ እስረኛ ሲያደርገው የማይመለስ ውሳኔ ነው። የፈለገውን ያህል ቢከራከርና የዓለም ሰብአዊ ድርጅቶች ቢጮሁ አቤቱታው አይሰማም። በዚህ ስርአት የህግ የበላይነት ሊኖር አይችልም። ስርአቱ በልማት ላይ ያለው ጫና ከፖለቲካው አይለይም። የዓለም ባንክ ጥናት ተከታታይነትና ፍትሃዊ ልማት ሊለካ የሚችለው "ለአሁኑና ለተከታታይ ትውልድ አስተማማኝ የሆነ ተቋማዊና ህጋዊ መሰረት መጣሉ ሲታይ" ነው ይላል። ምን ማለቱ ነው? 51/

የበለጸጉ አገሮች ታሪክ ያሳያል ያለው፤ የዘይት ሃብትን ወደ ጎን ትቶ (የሚያልቅና የማይተካ ስለሆነ) የተፈጥሮ ሃብት--ለም መሬት፤ ወንዝ፤ የሰው ሃይል--ከአገር ጠቅላላ ሃብት ሃያ በመቶ የሚሆነውን ያጠቃልላል። ስለሆነም፤ የተፈጥሮ ሃብት ባለቤትነት ለተከታታይ ትውልድ መንከባከብ ተለዋጭ የሌለው መንገድ ነው። ይህ የልማት መሰረተ ሃሳብ ሠብዓዊ ካፒታልን (Human Resource Capital) ያካትታል። ትምሕርት ለልማት ወሳኝ የሆነ አስተዋጽኦ አለው የሚባለው ለዚህ ነው። ሠብዓዊ ሃብትን ተንከባክቦ ያልያዘ አገር ዋጋ ይከፍላል። የተማረው አገር ለቆ ይወጣል። የአገር አጠቃላይ ገቢና ጠቅላላ ሃብት ይቀንሳል። የተማረ የሰው ሃይልን ተንከባክቦ መያዝ፤ የተፈጥሮ ሃብትን--ወንዝና ለም መሬት፤ ዛፍና ደንን፤ እንስሳዎች ወዘተ--በጥንቃቄ ማልማት ገቢንና ጠቅላላ ሃብትን ይጨምራል። ከሁሉ በላይ ወሳኝ ሆኖ የተገኘው የማህብረሰብ ካፒታል (የሰው ኀይል) ከጥሩ አገዛዝ ጋር አብሮ ሲራመድ ገቢንና ሃብትን የሚጨምር፤ ድህነትንና ረሃብን የሚቀንስ መሆኑ ነው። በሰብአዊ መብቶች መከበርና በህግ የበላይነት በአንድ በኩል፤ በሌላ በኩል፤ በነፍስ ወከፍ ገቢ፤ በኑሮ መሻሻልና በአገር አጠቃላይ ሃብት መጨመር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለ። ስደት፤ ልማትን ይቀንሳል። ሰብአዊ መብትና የህግ የበላይነት ለተከታታይና ለፍትሃዊ ብሄራዊ ልማት አማራጭ የሌለው መንገድ ነው። ("The preparatory form of wealth worldwide is intangible capital--human capital and the quality of formal and informal institutions" in any country). 52/

በሌላ አነጋገር፤ ሠብአዊ ካፒታሉን ያፈነ መንግሥት የሚጎዳው ግለሰቦችን ብቻ አይደለም። የአገሪቱን ልማት ጭምር ነው። የፍርድ፤ የማህበረሰብ አገልግሎት፤ ግንባታና አጎልማሽ ተቋሞች ለፖለቲካ የበላይነት መሳሪያ ከሆኑ፤ ለህብረተሰቡና ለአገሪቱ ተጨማሪ ሃብት ፈጣሪ አይሆኑም። ከእጅ ወደ አፍ የሆነ የነዋሪዎች ህይወት ቁልፍ ለሆነው ለብሄራዊ ቁጠባ ወይንም ተቀማጭ ገንዘብ (Stock of Savings) አስተዋጽኦ ለማድረግ አይችልም። ምክንያቱም፤ ካፒታሉ ታፍኗል። ኑሮ ከእጅ ወደ አፍ ከሆነ ለመቆጠብ የማይታሰብ ነው። ቁጠባ ከሌለ የወደፊቱ ትውልድ ዋጋ ይከፍላል። በውጭ ብድርና ድጎማ ሲተማመን አይኖርም። ጥናቱ ሲደመድም፤ የልማት ተከታታይነት የሚረጋገጠው ከተፈጥሮ ሃብትና ከሠብአዊ  ሃይል ጥረት የሚገኘው ሁሉ ገቢ (Rent) ተመልሶ ለህብረተሰቡ የኑሮ መሻሻል ሲውል ነው ይላል። ይህን ገልብጠን ስናየው፤ ገቢው ወይንም ከኪራይ የሚገኘው ለጥቂቶች ባለጠጋነት ከዋለና በሙሰኛነት ተሰርቆ ወደ ውጭ ከሸሸ ወይንም ለቅንጦት ኑሮ አገልጋይ ከሆነ የሚያስከትለው ውጤት የገቢ አቆልቋይነት ነው። ዘላቂነት ያለው ድህነትና፤ ስራ አልባነት፤ ስደትና ጥገኝነት ነው። ብሄራዊ ቁጠባ አይኖርም፤ ቢኖርም ይቀንሳል። ገቢ በሙስና ወደ ግል ሃብትነት ሲዘዋወር ዋጋ የሚከፍሉት ህብረተሰቡና አገሪቱ ይሆናሉ። የህግ በላይነት ቢኖር ይህን ችግር ሊቀንሰው ወይንም ሊያጠፋው ይችላል። ከላይ የተጠቀሰውን የልማት መሰረት በመጠቀም ዓለም ባንክ አገራዊ የነፍስ ወከፍ አጠቃላይ ገቢ ሲዳሥስ፤ እአአ በ2000 የማዳጋስካር "wealth per capita $5,020 ፤ የኢትዮጵያ $1965" እንደነበር ያሳያል። ይኼ የነፍስ ወከፍ ገቢ አይደለም። ሁሉ ነገር ተደማምሮ የአገር ጠቅላላ ሃብት ቢከፋፈል የሚኖረው ስእል ነው። የወደፊቱ ትውልድ ምን አይነት የልማት መሰረት ይወርሳል የሚለውን ጥያቄ መልሷል። በ2003 ጋና ሃያ በመቶ የደረሰ የአገር ውስጥ ቁጠባ እንዳላት (more than 20 pecent of domestic savings) መዝግቧል። በአንጻሩ፤ በአንድ ፓርቲ በምትገዛ፤ የህግ የበላይነት በማይከበርባት ኢትዮጵያ፤ የግል ጥሪትና ሃብት አስተማማኝነት እንደሌለባት፤ የአገር ውስጥ ቁጠባ ሃያ ሰባት በመቶ ወደ ታች የወረደ መሆኑን አሳይቷል። (A domestic savings gap of–27 percent-negative."  ወደታች ማቆልቆል የልማት ምልክት ሊሆን አይችልም። የሚያመጣው ችግር ለማን ይሆናል ብለን እንጠይቅ። ለአገሪቱና ለተከታታይ ትውልድ የሚል መልስ እናገኛለን። አንባቢ "እኔ ከሞትኩ" የሚል ሃሳብ ይሰጥ ይሆናል። ትክክል ነው። ማየት ያለብን ከራስ በላይ ነው። ተከታታይ ትውልድ በአንድ ላይ ለመኖር አለመኖር መቻሉ አስተማማኝ ሁኔታ አይታይም። የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ የሚከተለው የኢኮኖሚ አመራር ለኢትዮጵያ ብሄራዊ እርጋታና ደህንነት፤ ለህብረተሰቧ ሰላም፤ አሳታፊ ልማትና የኑሮ መሻሻል መሰናክል ሆኗል። 53/

የዓለም ባንክን ግንዛቤ መሰረት አድርጎ ተመሳሳይ ዘገባ ያደረገው አሜሪካዊ ሮናልድ ቤይሊና፤ ስለ ገቢና ባለጠጋነት ስብሰብ የበላይነት (Concentration of wealth) አደጋ የታወቀው ብዙ የጻፈው ዴቪድ ሮዝኮፍ የሚያስተጋቡት በጥቂቶችና ለጥቂቶች አገልጋይ የሆነ የኢኮኖሚ ስርአት ቀጣይነቱ አጠራጣሪ መሆኑን ነው። እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ደሃና ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው አገሮች የጥቂቶች ከልክ ያለፈ፤ ከፖለቲካ ስልጣን ጋር የተቆራኘ ባለጠጋነት አደጋ እንደሚፈጥር

ይናገራሉ። ሮናልድ ቤይሊ "ማንኛውም ግለሰብ ሰርቶ፤ ፈጥሮ፤ ደክሞ ያገኘው ሃብት ባለቤትነት እውቅና የህግ የበላይነት አመልካች ነው።" ሆኖም፤ "የግል ሃብት ባለቤትነት ከሌለ ፍትህ የሚባል ነገር በፍጹም አይኖርም።" በሌላ በኩል፤ፍትሃዊይነት ባለበት አገር "የመማር፤ የስራ እድል ፤ የግል ድርጅት የማቋቋም፤ ካፒታል የማንቀሳቀስ እድል ከመንግሥት የሚሰጥ ሳይሆን ሰብአዊ  መብት" ነው ይላል። ይህ ከሠብአዊ መብት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው የማህበራዊይና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በብሄር፤ በኃይማኖት፤ በፆታ፤ በርእዮት፤ በእድሜ አይወሰንም። መብቶች በስራ ሲተረጎሙ እውነተኛ ገቢ፤ ብሄራዊ ቁጠባ፤ ምርትና የተሳሰረ አገልግሎት እያደጉ ይሄዳሉ።" 54/

ከዚህ የሚከተለው፤ ሠብአዊ መብቶችና የግል ሃብት ባይከበሩ፤ የህግ የበላይነት ባይኖር ምን ችግር አለ የሚል ነው። እድገት ይኖራል። ጥቂት የሚጣጣሩ ግለሰቦችና ድርጅቶች ባለጠጋ ይሆናሉ። የአገሪቱ ጠቅላላ ገቢ እያደገ ይሄዳል። ቀስ በቀስ ሌሎች ከእድገቱ ተጠቃሚ ይሆናሉ። (Ripple Effect) ወዘተ ወዘተ የሚል ነው። ለዚህ አስተሳሰብ መልስ የምንፈልገው ከተጠቃሚዎች አይደለም። ከባለሞያዎች ነው። የህግ የበላይነት መመዘኛ (Rule of Law Index) መልሱን ይሰጠናል። ከማንኛውም መለኪያ የበለጠ የህግ የበላይነት መለኪያ የአገዛዙን ባህርይና የህብረተሰቡን አኗኗር ይገልጻል። ለፖለቲካ መቆያ ተብሎ የተመሰረተ የትምሕርት ስርአት ጥራትና ነጻነት ባይኖረው ነጻ የሆነ ሂስ ለማቅረብ የሚችል የለም። ህወሓት ሰላሳ ዩኒቨርሲቲዎች አቋቁሟል። የትምሕርት እድል ለአብዛኛው ወጣት አቅርቧል። ሁለት መሰረታዊ ጥያቄዎችን ለማቅረብ የሚደፍር፤ መብቱ በህግ የተጠበቀ ግለሰብ ወይንም ተቋም አልፈጠረም። የከፍተኛ ትምኅርት ጥራት ምን ያህል ነውና ትምኅርቱ ወደ ስራ ይመራል ወይንስ አይመራም? አብዛኛው ለትምኅርት የደረሰ ወጣት እድል ካለው ሁለት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን የሚሆኑ ኢትዮጵያዊ ህጻናትና ወጣቶች የመማር መብት ለምን የላቸውም? የትምኅርት ደረጃ ከተስፋፋ የሁለተኛ ደረጃ ትምኅርት ከኬንያ፤ ጋናና ሌሎች ጋር ለምን አልተነጻፀረም? የሚሉ እናቀርባለን። ይህን ዘገባ እኛ የፈጠርነው አይደለም። ሞ-ኢብራሂም ፋውንዴሽን በዳካር ስለወጣት አፍሪካዊያን የወደፊት እድል በ2012 ያደረገው አቅርቦት ነው። ድምዳሜው፤ የተማሩ አፍሪካውያን (ኢትዮጵያዊያን አፍሪካዊ ናቸው) ወላጆቻቸው ያገኙትን ገቢና የኖሩትን ኑሮ ሊያገኙ አይችሉም ይላል። ይህ ለልማት ባለሞያዎች አሳሳቢ የሆነበት ምክንያት አለ። ኮሪያ፤ ታይዋን፤ ሲንጋፖር፤ ቻይና፤ አሜሪካ ወዘተ ሃብታም የሆኑት ገንዘብ በማተም አይደለም። ሃብታምነታቸው የሠብዓዊ ሃይላቸው ስለንለመሰና ለመፍጠር፤ ለማምረት፤ ለማሻሻል፤ የግል ሃብት ለመያዝ ስለቻሉ ነው። የትምኅርት፤ የአስተዳደር፤ የህግ፤ የኢኮኖሚና የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀምና አመራር (Management) በጥራት ስለተስተናገዱ ነው። ተቋሞች የማህበረሰብና የኢኮኖሚ ጉልምስናን ስለደገፉ ነው። ልምዳቸው የሚያሳየው አንዱ መስፈርት፤ የህግ የበላይነት አውራ ሆኖ ለአጠቃላይ ሃብታምነት ከመቶ አምሳ ሰባት ድርሻ ይዞ ይገኛል። ትምኅርት ሰላሳ ስድስት በመቶ ድርሻ አለው። ሁለቱ፤ የህግ የበላይነትና ጥራት ያለው ትምኅርት ለብሄራዊ ሃብት ዘጠና ሶስት ከመቶ ድርሻ ይዘዋል። በህግ የበላይነት ዘገባ ብቻ ሲታይ አሜሪካ ዘጠና ሁለት በመቶ (91.8 percent) ነው። ኢትዮጵያ አስራ ስድስት ነጥብ አራት በመቶ (16.4) ነው። የኢትዮጵያ ወጣት ትውልድ ከችግሩ ለመውጣት የማይዘለቅ የአገዛዝ ተራራ ከፊቱ ተደቅኗል። የዘመናዊ መገናኛን ጥቅም የምናየው ከዚህ የአገር ልማትና ሃብት አንጻር ነው። 55/

"የተደራጀ ምዝበራ"

ህወሓት የጣና በለስን አፈራርሶ፤ መሳሪያዎችን ነቅሎ ሲወስድ ምዝበራና ወንጀል ነው። ከላይ እንዳቀረብነው፤ የህግ የበላይነት በሌለበት አገዛዝ ባለጠጋነት በጥቂቶች መከማቸቱ ወይንም መሰብሰቡ፤ አድልዎና ሙስና መፈጠሩ አያከራክርም። የህወሓት/ኢህአዴግ አመራርና ደጋፊዎች የሚሉት እንኳን ደሃ በሆነች ኢትዮጵያ፤ በአሜርካም ቢሆን "ከላይ ያለው አንድ በመቶ የሚሆነው ባለጠጋ፤ ከታች ያለውን ዘጠና በመቶ የመካከለኛና የደሃ መደብ አጠቃላይ ገቢና ሃብት ይበልጠዋል" ነው። በአሜሪካ ያለው የገቢና የሃብት ክምችት ልዩነት አከራካሪና አደገኛ ነው። አብዛኛው ሃብት የተሰበሰበው በስራ ነው። ግለሰቦች ሲሰርቁና ሙሰኛ ሲሆኑ ህጉ እንደሚከታተላቸው፤ የተፈረደባቸው እስር ቤት እንደሚገቡ ይታወቃል። ኢትዮጵያ የሚታየውና አሜሪካ የሚታየው የተለያየ መሆኑን ረስተውታል። ኢትዮጵያ የሚታየው ከአገዛዝ ጋር በቀጥታ የተያያዘ ልዩነት ከምዝበራ የመጣ መሆኑን ከደውታል። ክርክሩን ወደ ጎን ትተን ስንመረምር አስቸጋሪ ሆኖ የምናገኘው ግልፅነት አለመኖሩ ነው። በነጻነት የሚንቀሳቀሱ ተቋሞች የሉም። የፖለቲካ ስልጣን ማንን እንዳከበረ በማያሻማ ለማወቅ አስቸጋሪ ነው። ለማለት የሚቻለው ከከፍተኛ የፖለቲካ ሃላፊዎች፤ ከመከላከያ እዝና የፖሊሲ ወሳኞች ውስጥ ደሃ ለማግኘት አይቻልም። ይህ የፖለቲካ ስልጣን ተጠቅሞ ከፍተኛ ባለጠጋ መሆን ተባብሶ የሚገኘው በህወሓት ቁንጮ የበላዮችና ቤተሰቦቻቸው መካከል ነው። ሁኔታው ሴይንት አገስቲን ያለውን ያስታውሰናል። "ፍትህ በሌለበት ህብረተሰብ የፖለቲካ ሉአላዊይነት የተደራጀ ምዝበራ ነው።" ("In the absence of of justice, what is sovereignty but organized robbery?")

ግፈኛና አምባገነናዊ የፖለቲካ ስልጣን

ስግግብነትና ሙስና፤ የባህል ቀውስና የሃብት አመራር ብልሽት ወዘተ ይፈጥራል። በልማት ሞያ የታወቀው የቬኔዙዌላ የገንዝብ ሚኒስተር ሞኢሲስ ናየም፤ በደሃ አገሮች ለሕዝብ ሃላፊና ተጠያቂ ያልሆኑ ባለስልጣናት "ለህብረተሰቦቻቸው ችግሮች ፈጣሪዎች፤ ተጠያቂዎችና ሃላፊዎች ናቸው" ብሏል። ዋናው ምክንያት፤ ስልጣን ተጠቅመው ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ስለሚያከብሩ፤ ሌሎችን ደሃ ስለሚያደርጉ ነው። ራሳቸውን ሲያከብሩ በህብረተሰቡ ላይ የሚከሰቱ ችግሮች አሉ። የተባበሩት መንግስታት ልዩ ጥናት፤ ዛሬ "ኢትዮጵያ ከበፊቱ እኩልነት የሌለባት ሆና ትገኛለች" ብሎ ደምድሟል። እነዚህ ዘገባዎች እንዴት ይደገፋሉ። ምን ማስረጃ አለ ብለን እንጠይቅ። በ January 8, 2013, ብራያን ዋርነር የተባለ የዘመናዊ መገናኛ ቴክኖሎጂ ባለሞያ፤ ሴሌብሪቲ ኔትወርዝ (Celebrity Networth) በተባለው መድረክ፤ "መለስ ዜናዊ፤ የቀድሞው የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስተር፤ የ$3 ቢሊዮን ባለጠጋ መሆኑን አሳውቋል። ዘገባው ዌልዝ አፍሪካ (Wealth Africa) በተባለ ድህረገጽም ተደግሟል። ዌልዝ አፍሪካና ኢትዮጵያን ሪቪው በተከታታይ፤ የህወሓት ከፍተኛ ባለስልጣናት፤ ከፓርቲው ጋር የቅርብ ግንኙነት ያላቸው የግል ነጋዴዎችና ደጋፊዎች ከአስር ቢሊዮን ዶላር በላይ የቤተሰብ ሃብት እንዳከማቹ አስታውቀዋል። እኛ የማንጠራጠርበት የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት አድሏዊ የሆነና በሙስና የተበከለ መሆኑን ነው። It is one of the worst forms of ethnic-based crony capitalism in the 21st century. የፖለቲካ ስልጣን ተጠቅሞ የሚሰበሰብ ሃብት ግልጽነት ሊኖረው አይችልም። አንባቢን የምናሳስበው የኢትዮጵያ ጠቅላላ የአገር ውጤት ገቢ (Ethiopia's gross domestic product in 2012) ከሰላ እስከ ሰላሳ አንድ ቢሊዮን ዶላር ነው። የነፍስ ወከፍ ገቢ ከሶስት መቶ ሰባ ዶላር፤ ዛሬ ወደ አምስት መቶ ዶላር ደርሷል የሚባለውና ከላይ ያሳየነው። ሴሌብርቲ ኔት ወርዝ ለዓለም ያስታወቀውን ብነወስድና ብናጤን የመለስ ኃብት ብቻ ከአገሪቱ ጠቅላላ ገቢ አስር በመቶ ነው።

አዲስ ባለጠጋነት በግለሰቦች የተወሰነ አይደለም። ከህወሓትጋር የተቆራኙ ድርጅቶች የኢኮኖሚ የበላይነት ጡንቻ እያሳዩ ነው። ኤፈርት የተባለው ከመቶ በላይ የሚሆኑ ድርጅቶች ይቆጣጠራል። አንድ አንድ ታዛቢዎች ይህ ድርጅት ብቻ "ብዙ መቶ ቢሊዮን ብር ሃብት እንዳለው" ይገምታሉ። በግለሰብ ደረጃ ሆነ በድርጅት፤ በኢትዮጵያ ማን ምን ያህል ካፒታል እንዳለው ለማወቅ አስቸጋሪና አከራካሪ መሆኑን አንክድም። ግልፅነትና ለሕዝቡ ማስረጃ የማቅረብ ህግ፤ ደንብና ልምድ በሌለበት አገር (Honest and Transparent Reporting and Disclosure) የባለጠጋነትን መጠን ለማወቅ አስቸጋሪ ነው። በሙስና አልተሳተፍንም። ያካበትነው ሃብት አግባብ ባለው ስራ የተገኘ ነው የሚሉ ካሉ ይህን ለኢትዮጵያ ሕዝብ በማስረጃ ማቅረብ ያለባቸው "የሚታሙት" ናቸው። በኢትዮጵያ ማን ምን አይነት ሃብትና ኑሮ እንዳለው ለማየት አስቸጋሪ አይደለም። ህብረተሰቡ ያየዋል። ይነጋገርበታል። አስተማማኝነት ያለው የውጭ ዘገባዎች ስርአቱ ግድፈት እንዳለው ደጋግመው ያወጡትን መመርመር ያስፈልጋል። ግድፈቶቹን እንደ ገና በግልፅ ለማስቀመጥ፤ አምስት አመታት ወስደን ሞ-ኢብራሂም በተከታታይ ስለ ህግ የበላይነት፤ ስለ ሰብዓዊ መብቶች፤ ስለ ሕዝብ ተሳትፎና ያወጣውን እንይ። እአአ ከ2007-2011 በደህንነትና በህግ የበላይነት ከሌሎች አምሳ ሁለት የአፍሪካ መንግስታት አገዛዝ ጋር ሲነጻደር፤ የኢትጵያ መንግሥት ያገኘው በአማካይ አርባ አምስት ከመቶ ነው። ከ200-2011 ባለው ዘገባ ኢትዮጵያ ሰላሳ ሶስተኛ ነበረች። ሁኔታው እየባሰ መሄዱን ለማሳየት አገዛዙ ሁለት ነጥብ አንድ (-2.1 በመቶ) ወርዷል። የባሰ የአገዛዝ አፋኝነት የሚታየው በሕዝብ ተሳትፎና (ምርጫና ድምጽ) አርባኛ፤ በሠብአዊ መብቶች መከበር አርባ አምስተኛ መሆኑ ነው። አሳሳቢ ነው ተብሎ የሚገመተው፤ የአሜሪካ የደህነት ክፍል ካወጣው ጋር የሚመሳሰል የኢትዮጵያ በብሄራዊ ደህንነት አምሳኛ መሆኗ ነው። አገዛዙ ብሄራዊ ደህንነትን ወደ አስጊ ሁኔታ እየመራው ነው። አመራሩ ደጋግሞ የሚለው ኢትዮጵያ ቀጣይነት ወዳለው የሠብአዊ ልማት ጎዳና ታመራለች ነው። ታዛቢዎች የሚሉት አስቸኳይ የሆነ በቀጥታ ከሕዝቡ ኑሮ ጋር የተያያዘ ዘገባ "ዘጠና በመቶ የሚሆነው የገቢ ዋስትና የለውም (Income insecure and vulnerable) ነው። ዋስትና ያለው ደሞዝተኛ ከአስር በመቶ በታች ነው። ከጠቅላላ ሕዝቡ ሰላሳ በመቶ የሚሆነው ስራ የለውም። ወጣቶች የራሳቸውን ስራ ለመጀመር አቅም የላቸውም። ለመበደር አይችሉም።

የኦክስፎርርድ ዩኒቨርስቲ ሁለ-አቀፍ የድህነት መለኪያ፤ ዘጠና በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በየጊዜው የረሃብ አደጋ እነደሚገጥመው በማስረጃ ገልጿል። የህጻናትን ህይወት በየጊዜው የሚፈትሸው ዩኒሴፍ (UNICEF) መንግሥት ለጤና ካለው ባጀት አንድ በመቶ ብቻ ያወጣል። ወላጅ የሌላቸው ህጻናት ሰባት ሚሊዮን ናቸው። የህጻናት ሞት ከፍጹም ረሃብ ጋር የተያያዘ ነው። ሴቭ ዘ ችልድረን ኢትዮጵያ "ለህጻናት ሲኦል ናት" ብሎ ደምድሟል። አገር ቤት ያሉ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚስቶች ሰባ በመቶ የሚሆነው ወጣት ስራ እነደሌለው ይናገራሉ። የፖለቲካ አፈናና የስራ እድል አለመኖር በወር ከኢትዮጵያ ለሚሰደደው ብዙ ሺህ ወጣት ዋና ምክንያት እንደሆነ ይናገራሉ። ሞ-ኢብራሂም ከሚሰደዱት አምሳ በመቶ እድሜያቸው ከ15-29 የሆነ፤ ከእነዚህ ሃያ አምስት በመቶ ወደ ሰሜን አሜሪካ፤ ሃያ አምስት በመቶ ወደ ሱዳን (ሰሜንና ደቡብ)፤ አብዛኛው ወደ አረብ አገሮች፤ ሌላው ወደ ሌሎች የአፍሪካ አገሮች እንደሚጎርፍ ይገልጻል። የሚሰደደው ተምሮ የስራ እድል የሌለው ጎልማሳ ብቻ አይደለም። ሃያ አምስት በመቶ ሃኪሞች፤ አምሳ

በመቶ ነርሶች፤ ስድሳ ሰባት በመቶ ሌላ ትምኅርት ያላቸው ኢትዮጵያውያን ይሰደዳሉ። ስደት፤ የሰው ሃይል ናዳ ብቻ ሳይሆን፤ የመንፈስ ናዳም አስከትሏል።

በእርዳታ የተደገፈ እድገት ጣጣ

ገዢው ፓርቲ እድገትና ባለጠጋነት የተቀዳጀው በውጭ እርዳታ ነው። አጠያያቂ ሆኖ የምናገኘው የውጭ እርዳታ እንደ ማንኛውም የግል ስራ ሆኖ መገኘቱ ነው ። (Aid as any other business). የግል ወይንም የመንግሥት ጥቅም ስራ ከሆነ ማለቂያ የለውም። ይህ የችግሩ ብልት ነው። በአፊሴልና ከባጀት ውጭ አርባ ቢሊዮን ዶላር እርዳታ ከተገኘ ያስመጣው የሠብአዊ ልማት፤ የእርሻና የኢንዱስትሪ ምርት እድገት የት ላይ ይታያል የሚል፤ ኢኮኖሚስት የተባለው ጋዜጣ ከሁለት አመታት በፊት የደመደመው "ኢትዮጵያ ከብዙ ቢሊዮን ዶላር እርዳታ በኋላ የዛሬ ሃያ አምስት አመት በፊት ከነበረችበት ድህነትና ኋላ ቀርነት አልተሻሻለችም" ያለወን የሚያጠናከር ነው። እርዳታ ድጎማ እንጅ የብሄራዊ ጥረት መተኪያ አይደለም። ቢል ኢስተርሊ እንዲህ ይላል፤ "ትንሽ የሆነው የውጭ እርዳታ በዓለም ደሃ የሆኑ አገሮችን ኋላ ቀርነት፤ ድህነት ችግሮች አይፈታም።" ድህነት ሊወገድ የሚችለው የህብረተሰቡን የመስራት፤ የማምረት፤ የመፍጠር ሃይል ማጎልመስ ነው። የኢትዮጵያ እድገት በአብዛኛው የሚመራው የውጭ ሽመታን በተከተለ ንግድና ኢንቬስትመንት ነው። መዋቅራዊ ለውጥ አያሳይም። አገሪቱ ለማምረት የምትችለው ስኳር ይሸመታል። ለኢትዮጵያ የሚያስቡ ባለሞያዎች ዛሬ የኢኮኖሚው ምርት ውጤት ዘጠና አራት ሚሊዮን ሕዝብ ለመደገፍ ካልቻለ፤ ከሰላሳ አመት በኋላ ምን ሊሆን ነው የሚል በሃቅ የቀረበ የፖሊሲ ጥያቄ ነው?

እርዳታ ለማፈኛ ውሏል

የእንግሊዝ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያስተማረን ዋና ነገር፤ ቁጥጥር የሌለበት እርዳታ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማፈኛ መሆኑን ነው፤ ጋምቤላ በተፈጥሮ ሃብት፤ በተለይ በለም መሬት የደረሰውን በደል ያሳያል። አዲሱ የኢትዮጵያ ትውልድ ከወላጆቹ ያነሰ ኑሮ ይኖራል ከተባለ ሁኔታውን የፈጠረው ወይንም ያባባሰው ስርአት ወለድ ችግር አለ። ሊጋሶች ይህ የአገዛዝ ችግር መኖሩን ቀደም ብለው ተገንዝበውት ነበር። ከምርጫ ዘጠና ሰባት በኋላ ዓለም ባንክ ለሊጋሶች ያቀረበው የእርዳታ እቅድ፤ አብዛኛውን ገንዘብ በቀጥታ ለመሰረታዊ አገልግሎት (Basic needs) እናውል የሚል፤ Protection of Basic Services የተባለ ፕሮግራም አወጣና ከስራ ላይ አዋለ። ይህ ፕሮግራም ከተጀመረበት ወዲህ ገዢው ፓርቲ በቀጥታ አስራ ሶስት ቢሊዮን ዶላር እርዳታ ተቀብሏል። ከዚህ ከሁለት ቢሊዮን በላይ የሚገመተው የዓለም ባንክ ነው። የድርጅቱ የውስጥ ዘገባ በተደጋጋሚ ያመለከተው፤ ድህነትን፤ ረሃብን፤ በሽታን፤ ወዘተ ለመቀነስ የሚሰጠው እርዳታ ከተፈለገው ስራ ላይ አለመዋሉን ነበር። እንዲያውም፤ ለም መሬትን በሚመለከት የውጭ እርዳታ ለአፈና ዋና መሳሪያ ሆኑል። ሆኖም፤ እርዳታው በመቀነስ ፋንታ፤ ያለምንም ቁጥጥር ጨምሯል። እአአ በ September, 2012, ዓለም ባንክ ለዚሁፕሮግራም ስድስት መቶ ሚሊዮን ዶላር ለገሰ። ያለ ምንም ክትትልና ቁጥጥር። እንደተለመደው የኢትዮጵያ መንግሥት እርዳታውን ለልዩ፤ ልዩ አፈናና ቁጥጥር አውሎታል። ከዚህ አፈና ውስጥ የዘመናዊ እርሻ ለውጭና ለምርጥ የውስጥ ኢንቬስተሮች የለገሰው መሬት፤ ለሃይል ማመንጫ የሚገደቡ ግድቦች፤ ለስኳርና ለሌች የተመድቡ መሬቶችና ከዚህ ጋር የተያያዙ የሕዝብ ሰፈራና መቆጣጠር ተግባሮች ይገኙበታል። ከዚህ ሁሉ አስቃቂ የሆነው በነዋሪዎች ላይ የሚደረገው የሠብአዊ መብቶች ገፈፋ ነው። የፖሊስ፤ የወታደርና የስለላ ሃይል ማጠናከር፤ አፈና፤ ማስፈራራት፤ሽሸት፤ ሴቶችን አስገድዶ መድፈር፤ ተጠቃሚዎች መግዛት ወዘተ ይገኙበታል። ለነዋሪዎች ድህነት የተሰጠው እርዳታ፤ ከዚህ በፊት Human Rights Watch, Oakland Institute, Guardian, Survival International, International Rivers ያሳሰቡት አሁን በከፋ ሁኔታ ለገዢው ፓርቲና ለጥቂት ተጠቃሚዎች እየዋለ ነው። ጉቦን፤ አድልዎንና ሙስናን ከማስፋፋቱ በላይ፤ የህብረተሰቡን ኑሮ እያናጋው ይገኛል። Inclusive Development International ባደረገው ጥናት፤ እርዳታ "ሰለባን" እንዳስከተለ ያሳያል፤ መሪው ጥያቄ፤ዋናዎቹ ሰላቢዎች እነማን ናቸው? መንስኤው ምን አይነት አገዛዝ ነው? የሚሉ ናቸው።

ዓለም ባንክ የሰጠው $600 million የለገሰው ገንዘብ ከጅምሩ አጠያያቂ ነበር። ይህን የምንልበት ምክንያቶች፤ የሠብአዊ መብቶች ከበፊቱ በባሰ ሁኔታ መታፈናቸው፤ የመሬትና ሌላ የተፈጥሮ ሃብት ሽሚያው አደገኛ ከሆነ ደረጃ መድረሱ፤ ነዋሪዎች እንዲሸሹ መገደዳቸው፤ ከዘረፋ ጋር የተያያዘው ሙስና ከቁጥጥር ውጭ መሆኑ፤ ህብረተሰቡ በስለላ፤ በፖሊስና በመከላከያ ቁጥጥር ስር መዋሉ (The militarization of the society) ይገኙበታል። የዓለም ባንክ ብድር በቀጥታ ለመንግሥት ስለሚሰጥ፤ ባለስልጣናት እንደፈለጉ ይጠቀሙበታል። ዓለም ባንክ የሚገኙ፤ ስማቸውን ለመግለጽ የማይፈልጉ እውቅና ያላቸው ግለሰቦች እንደሚሉት ከሆነ ብድሩ ለአፈናና ለሌላ መዋሉ ለድርጅቱ ዝና መጥፎ ይሆናል የሚል ግምት እንዳለ ተረድተናል። (reputational risk). እንደሚሰማው የድርጅቱ ነጻ የሆነ የክትትል ተቋም፤ Inspection Panel ምርምር አድርጎ ውጤቱን ለቦርዱ ካቀረበና ቦርዱ ከተስማማ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ከዓለም

ባንክና ከሌሎች የሚሰጠው ብድርና ስጦታ (both loans and grant) ሊቆም ይችላል። ይህን የሚያጠናክረው፤ በጋምቤላ ሕዝብ ስም ለዓለም ባንክ ፕሬዝደንትና ለድርጅቱ ነጻ የምርምር ክፍል በ International Development Institute (IDI), October, 09, 2012 የተጻፈ ጠንካራ ደብዳቤ ነው። ዓለም ባንክ፤ በማስረጃ የተደገፈ፤ ዝናውን የሚያኮላሽ ደብዳቤ ደርሶት ዝም እንደማይል እንገምታለን። ሆኖም፤ የአሜሪካ መንግሥት ገዢውን ፓርቲ ከደገፈ እርዳታው አይቆምም። ይህ አንጋፋ ድርጅት የሚለግሰውን የልማት እርዳታ "አቁሜያለሁ" ቢል ለኢትዮጵያ ሕዝብ አስተዋጾ ያደርጋል የሚል ግምት አለን። ሆኖም፤ ከዚህ በፊት፤ ማለትም፤ የነጻው ምርምር ፓነል ከመቋቋሙ በፊት የወጡ ተመሳሳይ ዘገባዎች የውሃ ሽታ እንደሆኑ እናውቃለን። "ለተባሰው ማጭድ አታውሰው" እንደሚሉ፤ ለጋሶች የችግሩ አጋር ሆነዋል።

"እጥፍ ድርብ እድገት" ምን ማለት ነው?

ገዢው ፓርቲ "እጥፍ ድርብ እድገት አለ" ይላል። ሆኖም፤ መዋቅራዊ ለውጥ የለም። ከሕዝቡ ሰማኒያ ስድስት በመቶው የሚመካው በእርሻና ከእርሻ ጋር በተቆራኘ ኑሮ ነው። ዘመናዊ እንዱስትሪ የሚባለው ከአራት እስከ ሰባት በመቶ ነው። በአጼ ኃይለ ሥላሴ ከነበረው ፈቀቅ አላለም። አርባ አንድ በመቶ የሚሆነው "ዘመናዊ ኢኮኖሚ" አንቀሳቃሽ በዝቅተኛ ንግድ ራሱን ችሎ የሚኖር የቤተሰብ ኢኮኖሚ ነው። አርባ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ለኑሯቸው ይመኩበታል። በሌሎች ጥሩ ልማት ባሳዩ አገሮች እነዚህን አገር ወለድ የምርትና የአገልግሎት ድርጅቶች አጎልምሰው ወደ ከፍተኛ ደረጃ አድርሰዋቸዋል። የውጭም ሆነ የአገር ውስጥ ኢኮኖሚ የበላይነት የያዙ ድርጅቶች ጥቃቅኖቹን እንዳያፍኗቸውና እንዳያጠፏቸው ድጋፍ አድርገዋል። ደቡብ ኮሪያ ጥሩ ምሳሌ ናት። የመካከለኛ መደብ እያደገና እየሰፋ የሚሄደው መንግሥት ያልተቆጠበ ድጋፍ ሲሰጥ፤ ከማነቆነት ሲቆጠብ ነው። ገዢው ፓርቲ ዲሞክራሲን ተቋማዊ ለማድረግ ፈጣን እድገት ያስፈልጋል ይላል። ሰው ለነጻነቱና ለመብቱ ከማሰቡ በፊት በልቶ ማደር አለበት የሚል መልእክት ይሰጣል። ችግሩ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሁለቱም በኩል ዋጋ እየከፈለ ነው። ሰው ጠግቦ በልቶ አያድርም። ነጻነትና መብቱም ታፍኗል። የኦሞ ሸለቆ ሕዝብ የሚገለገልበት መሬት ያለምንም ውይይት እቅድ እየተመነጠረ፤ እየታረሰ፤ የኦሞ ወንዝ እየተገደበ ነው። ሕዝቡ ከተፈጥሮ ጋር አብሮ ይኖር ነበር። ይህን እያጣ ነው። በልቶ ለማደር ከፈለገ መብቱን መጠየቅ አይችልም። ቁጥጥሩ እንዴት እነደሚሰራ ስናይ፤ በከተማ የቀበሌ መሪዎች ልዩ ልዩ የኑሮ ድጎማ ያገኛሉ። በገጠር የተወሰኑ ገበሬዎች ዝቅተኛ ብድር (Micro-credit) ይሰጣቸዋል። ይህ በድጎማ የተጠናከረ ቁጥጥር የመንግሥቱን የአስተዳደር ዋጋ ጨምሮበታል። አፈና አጠናክሯል።

የብሄራዊ ባህልና እሴቶች ናዳ

የምስራቅ ኤዢያ አስደናቂ ልማት ውጤት ያሳየው በትምኅርት አቅርቦት ጥራት ነው። የታየው የትምኅርት አቅርቦት ቁጥርን መጨመር ብቻ አለመሆኑን ነው። ትምህርት የወጣቱን ትውልድ ሞራል አንጿል። የሚያንፀው፤ ወጣቱን ትውልድ በስነልቦና፤ በባህል፤ በራስ መተማመን፤ ራሱን አክብሮ ሌላውን በማክበር፤ ህብረተሰቡን በሚያወቃቅሩት አበይት ጉዳዮች፤ በአገር ወዳድነትና ሌሎች ገንቢ በሆኑ እሴቶች ማዘጋጀት፤ ምርትንና የስራ እድልን በማሳደግ ነው። በሌሎች አገሮች፤ ህብረተሰቡ በመቀራረብና በመተሳሰብ በጋራ ማደግ ቁልፍ የሆነ የልማት መስፈርት ሆኖ ይገኛል። ብሄራዊ መተባበር (National Solidarity) ውጤታማ የሆነው ባለስልጣናት የመንግሥት ሃላፊነት ትምኅርት የግለሰቦች መብት መሆኑን ተቀብለው የሚያቀራርቡ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ስለነደፉ ነው። በፖለቲካ የበላይነት የተመሰረተና የሚመራ፤ ጠባብ ጎሰኛ የሆነ የትምኅርት ፈለግ ይህን ለማድረግ እንዳልቻለ በይፋ እያየን ነው። የኢትዮጵያን ህብረተሰብ በዘላቂነት የማያገለግለው የወጣት ትውልድ አደረጃጀት ድክመት በግልጽ የሚታየው ብሄራዊ ማንነት (National identity, retention of human capital, appreciation of past history and own indigenous culture and aspiration to be great) ቀስ በቀስ መናዳቸው ነው። ይህ ናዳ የአማራ፤ የተዋህዶ ክርስቲያን፤ የእስልምና ኃይማኖት፤ የኦሮሞ፤ የትግራይ ወዘተ አይደለም። ብሄራዊ ነው። አንዳንድ ባህሪና እሴቶች ለተወሰነ ብሄረሰብ ያገለግላሉ። መታወቂያ ናቸው። ሌሎች ብሄራዊ ናቸው። ሁለቱም ለልማት ጥቅም አላቸው። የዲሞክራሲ እሴቶች የኦሮሞ ሊሆኑ ይችላሉ። የእርሻ ችሎታ የአማራ ሊሆን ይችላል። የጥንት ባህል ቅርሶች የትግሬ ሊሆኑ ይችላሉ። የንግድ የሃረሬ ወይንም የጉራጌ ሊሆኑ ይችላሉ። የዘላንነት የአፋር፤ የሶማሚሌ ሊሆን ይችላሉ። የአሣ አጠማጅነትና ከተፈጥሮ ጋር አብሮ መኖር የአኟክ ሊሆን ይችላል ወዘተ። ይህ ሁሉ ጥሪት ለመላው ህብረተሰብ ሊያገለግል ይችላል። ትምኅርት እነዚህን ሁሉ ያከብራል። ቁም ነገሩ ተደጋጋፊ የሆነ ሕብረተሰብን ከመመስረትና አብሮ መከበርን ተቋማዊ ከማድረጉ ላይ ነው።

ትምኅርት ብቻውን ግለሰብንና አገርን አይገነባም። ግለሰቡን ከህብረተሰቡ ፍላጎትና ልማት ጋር አብሮ ሊያያዝ ወይንም ሊያለያይ የሚችለው ስልጣን የያዘው ፓርቲና መንግሥት ነው። በፍጥነት ያደጉ አገሮች ታሪክ የሚያስተምረን የጋራ ግንዛቤ ሁሉም በየፊናው ብሄራዊ የሆነውን አብሮ የማደግ አላማ ሲጋራ ነው። የተፈጥሮ ኃብት ለመላው ህብረተሰብ

እንዲያገለግሉ የሚሞከረው በዜጎች መካከል የጠነከረና አድልዎ የሌለበት ህብረተሰብ እንዲፈጠር ስለሚፈለግ ነው። ተባብሮ የሚሰራ የበለጠ ጥንካሬ ይኖረዋል። በመካከሉ የሚደጋገፍ ህብረተሰብ (ጃፓን፤ ቬትናም፤ ቻይና፤ ቦትስዋና ወዘተ) ከሱዳን፤ ከኢትዮጵያ ወይንም ከሶማሊያ የሚለየው ለዚህ ነው። ትምኅርት የመተባበርን ባህል፤ እሴቶችና ልምድ ሲያጠናክር ሃብታም የሆነ ህብረተሰብ ይፈጠራል። የሁሉም ኑሮ ይሻሻላል። አንዱ በይ ሌላው ተመልካች፤ አንዱ አለቃ ሌላው ሎሌ አይሆንም። ለዝህማ ቅኝ ገዢዎች ምን አጠፉ። ቁም ነገሩ፤ ስርዓቱ ጎሰኛና አግላይ፤ አፋኝ ከሆነ የኑሮ ልዩነቶችና የተዛባ እድገት ይፈጥራል። ማህበረሰብአዊነትን ይንዳል።

የግል ሆነ የህብረተሰብ (Public Education) ትምኅርት ከታሪክ፤ ባህልና ልምዶች ጋር ጥቅም ያለው መሆኑን በአጭሩ አቅርበናል። ኢትዮጵያ ህብረተሰቡን የሚያጋራውን የሚሰበስበው የትምኅርት ፈለግ መናድ ከጀመረ ቆይቷል። በትግራይ ክልል የሚካሄደው ትምኅርት ቀደምትነት የሚሰጠው ለክልሉ ጎሳ ሆኗል። ልክ እንደሚገነጠል ህብረተሰብ ይመስላል። ይህ ጠባብ ጎሳዊነት በሩቅ ሲታይ ብሄራዊ ችግር እንዳለው ማሰብ አያስቸግርም። የህጻናትና ከዚያ በላይ የሆኑ የግል ትምህርት ቤቶች እንደ ኪዮስክ ተስፋፍተዋል። መስፋፋታቸው ጠቃሚ ነው። ሆኖም፤ የሚያስተምሩት ትውልድ ለውጭ ገበያ የሚዘጋጅ ይመስላል። ስሞቹ ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ፤ የሚያስተምሩበት ቋንቋ እንግሊዝኛ፤ አስተማሪዎቹ ፈረንጆች፤ የሚጠቀሙት መጽሃፍ የፈረንጅ፤ ወዘተ ነው። ብሄራዊ መታወቂያው ምንድን ነው? ስሞቹን እንይ። Gibson Academy, School of America Academy, Horizontal Academy, Cambridge, Oxford, MacMillan, Majic Carpet, Hillside, Mercy, Paradise, Sunshine, Britain, etc academy. ኢትዮጵያዊ ስም ለምን አሳፈረ? በዓለም የሚደረገውን የህጻናት ትምኅርት አሰጣጥ ስናይ፤ የኢትዮጵያ ብቻ ተለይቶ ወደ ፈረንጆች ባህል ለዋጭ ሆኖ እናገኘዋለን። እነዚህ ህጻናት ማንነታቸውን እንዲክዱ ወይንም እንዳይቀበሉ ይገደዳሉ። ልጆች “አባየ፤ እማየ፤ እትየ” በማለት ፋንታ “ዳዲ፤ ማሚ፤ አንቲ” ሲሉ ልክ የቅኝ ገዢዎች በአፍሪካዊያን ላይ ይጭኑት የነበረውን ባህል ይመስላል። የታወቀው ሯጭ “ሃይሌ ገብረ ሥላሴ ልጆቹን በአማርኛ መናገር አትችሉም፤ ተረት፤ ተረት ነውር ነው፤ ባርኒና ስፓይደርማን ጥሩ ነው” ይላል። በሃገሩ ባህል አፍሮ ልጆቹንም አሳፍሯቸዋል።

የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት ናዳውን ያውቃል። የትምኅርቱን ካሪኩለም፤ ትምኅርት ቤቱ እንዲከፈት ካልፈቀደ ይህ ናዳ አይመጣም ነበር። ፈረንጆች የኢትዮጵያ ባህልና ልምድ ቢጠፋና የራሳቸው ቢተካ ደስ ይላቸዋል። እንግሊዝኛ መማር ከአማርኛ የተሻለ ነው በሚባልበት ጊዜ፤ እንግሊዝኛ ተናጋሪው ከአማርኛ ተናጋሪው የበለጠ እውቀትና እድል አለው የሚል መልእክት ይሰጣል። ቻይና፤ ጃፓን፤ ብራዚል፤ ቬትናም የማይታሰበው ኢትዮጵያ እንደ ፖሊሲ አመራር ሆኖ ያገለግላል። በአፍሪካ አማርኛ ብቻ ነው ረጅም የፊደልና የማስተማሪያ ልምድ ያለው፤ መጻህፍት፤ ድርሰቶች፤ ታሪኮች፤ ዘፈኖች፤ ሙዚቃዎች፤ ውሎች፤ ወዘተ የተጻፉበት ብሄራዊ ቋንቋ ነው። ቢያንስ ሰባ በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚናገረው የጋራ ቋንቋ ሆኗል። ይህን ቋንቋ በጥላቻ ምክንያት ማድከምና ማጥፋት፤ ወይንም እንዲጠፋ ማድረግ ለጋራ ልማት፤ ለማንነት፤ ለእውቅናና ለታሪክ የማይረሳ በደል ነው። ህወሓት የናደው የህብረተሰቡን በቋንቋና በሃይማኖት መቆላለፍና መተባበር ብቻ አይደለም። በራሱ ልምድ፤ ባህልና ታሪክ አለመተማመንን ጭምር ነው። የአክላንድ ኢንስቲቱት “በዛሬይቱ ኢትዮጵያ፤ የውጭ አገር ዜጎች ከኢትዮጵያውያን የበለጠ መብትና ሃይል አላቸው” የሚሉትን እናስታውሳለን። ቻይናዎች እንደልባቸው ኢትዮጵያውያንን “እንደ እንሰሳ ይደበድባሉ። “የልጃገረዶችን ክብር ይደፍራሉ።” ህንዶች  ለቀን ሰራተኞች የፈለጋቸውን ደሞዝ ይከፍላሉ። አረቦችና ሌሎች ቱሪስቶች አዲስ አበባን ወደ “ሴቶች መደሰቻ ” ከተማ (Sex Paradise) ለውጠዋታል። የውጭ ባህል የኢትዮጵያዊያንን ባህል እየተካ ሄዷል። ኢትዮጵያዊ እውቅና ባላቸው የክርስትናና የእስልምና ኃይማኖቶች መዲና በሆነች ኢትዮጵያ “የእራቁት መዝናኛ” ቦታዎች (Nude Night Clubs) ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል። የኢትዮጵያ የባህልና የኃይማኖቶ በአሎች በፈረንጆች እየተተኩ “የኮለምበስና የእናት ቀን፤ ታንክስጊቪንግ ወዘተ” ተቀባይነት እያገኙ ነው። ወላጆች ልጆቻቸውን በእንግሊዝኛ ማነጋገርና ስማቸውን “ጆንና ጆኒ” ማለት ከጀመሩ ቆይቷል። ኮሪያና ጃፓን፤ ቻይናና ኢንዶኔዢያ የማይታሰበው ኢትዮጰያ ተራ ነገር ሆኗል። አዲስ ነገር የተባለው ድህረ-ገፅ፤ “የኤደን፤ የቤቲና የሜላት አማርኛ” በሚል አርእስት ከሁለት አመት በፊት ያቀረው ትዝብት የሚመስል ምሳሌ የብሄራዊ ባህል ናዳን ያስተጋባል። ይህ “ከልማት ጋር ምን አገናኘው” ብለን ብንጠይቅ:: ታሪክና ባህል የሌለው ህብረተሰብ ማንነት የለውም። በራሱ አይተማመንም የሚል መልስ እንሰጣለን።

በኢትዮጵያ የሚኖሩ ከፍተኛ ትምኅርት ያገኙ ኢትዮጵያውያን ኑሯቸውን ለማሻሻል ደሞዛቸው ዝቅተኛ ሆኗል። ብዙዎችን የሚያበሳጫቸው፤ በትምኅርት ያለውን ዋጋ ስናየው፤ አንድ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው ፈረንጅ በግል ትምኅርት ቤት ሲያስተምር የሚያገኘው ደሞዝ ተመሳሳይ ዲግሪ ካለው ኢትዮጵያዊ አምስት ጊዜ ይበልጣል። ልምድ ያለው፤ ባህሉንና አገሩን የሚያውቅ ኢትዮጵያዊ ሶስት ሺህ ሲከፈለው ፈረንጁ በወር ከአምስት ሽህ እስከ አስራ አንድ ሽህ ይከፈለዋል። በቋንቋ የሚለያይ የደሞዝና የልዩ ድጎማ ባህል ተስፋፍቷል። ከፈረንጆች ቀጥሎ ከፍተኛ ደሞዝ

የሚከፈላቸው ህንዶች ናቸው። ከዚያ ቀጥሎ ከሌላ አፍሪካ አገር የመጡ ናቸው። የመጨረሻው ኢትዮጵያዊ ነው። የአገር ትምኅርት፤ ባህል፤ ታሪከና እውቀት የማያከብር ስርአት ለስደት ምክንያት ሆኗል። ወጣቶች በኢትዮጵያዊነታቸው ኮርተው፤ ቋንቋና ባህላቸውን እንዳይማሩ ብዙ የቤተሰብና የስርአት ጫና እንደሚደረግባቸው ከላይ አሳይተናል። ገዢው ፓርቲ ይህን ጎጅ የእሴት ወረራ፤ በሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተቀባይነት የሌለው የደሞዝ ልዩነት "የችሎታ ልዩነትና የወላጆች "መብት" ይለዋል። የብሄራዊነት ናዳ ገዢውን ፓርቲ ይጠቅመዋል። ይህ ሁሉ ብሄራዊ ናዳ የሚካሄደው አገር ቤት ብቻ አይደለም። ከመቸውም የባሰ የባህልና የሥብአዊ መብቶች አፈና አገር ውስጥና ውጭ በተቀነባበረና ሴራ ይካሄዳል። የፍሪደም ሃውሱ ሊኦናርዶ አሪዮላ ይህን ፍጹም የሆነ አፈናና የመንፈስ ናዳ ሲገልጽ እንዲህ ብሏል። "ለረጅም ጊዜ ሲጠበቅ የቆየው የኢትዮጵያ ዲሞክራሲ ባለፉት ግማሽ አሥር አመታት ሙሉ በሙሉ አከትሟል።"

ብሄራዊው የግል ክፍል የት ሄደ?

ባህልና ታሪከ ለልማት ቁልፍ መሆኑን ካሳየን በኋላ አገር ወለድ ልማት ምን ጫና ገጥሞታል የሚለውን ጥያቄ እንመልስ። ለባህል ሊቆረቆር የሚችለው ጠንካራ ብሄራው የግል ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ሲኖር ነው፡፡ ባህልና ልምድ ጥቅም አለው። የጉራጌ ክትፎ ወግና ማ እረግ ስላለው በአገር ቤትም በውጭም ገቢ ያስገኛል። እነጀራም እንደዚሁ። የቡና ማፍላት ስነ ስር ዓት በዓለም የታወቀና የተከበረ እውቅና እያገኘ ሄዷል። የኢትዮጵያ የተዋህዶ ቤተ ክርስትያን ባህል፤ ልምድና በዓሎች በዓለም እውቅና አግኝቷል። ዋጋና ጥቅም አላቸው። እነዚህ ሁሉ በግል ወይንም በጋራ የሚሰሩ ገቢና ስራ የሚፈጥሩ ጥሪቶች ናቸው። ገዢው ፓርቲ የአገሪቱን እድገት ለማፋጠን መንግሥትና ፓርቲው ወሳኝ ሚና መጫወት አለባቸው በሚል የበላይነት ዘዴ ኢትዮጵያዊ ከበርቴዎች እንዳያብቡ ከሌሎች በፍጥነት ካደጉና በማደግ ላይ ካሉ አገሮች የተለየ የአስተዳደር ደንብና መሰናከሎች (Administrative and Regulatory Burden) ጭኖባቸዋል። ሽከሙን የማይቀበሉ ካፒታላቸውንና ልምዳቸውን ወደ ውጭ ማሸሽ ጀምረዋል። ስለሆነም፤ የአገሪቱ የምርትና አገልግሎት አቅም ተጎድቷል። ይህ ያሳሰበው የዓለም ባንክ ዲሬክተር ኬን ኦሃሺ፤ "ህወሓት/ኢህአዴግ ክፍት፤ ግልፅና አግባብ ያለው ውድድር እንዳይኖር መሰናከሎች ፈጥሯል። እነዚህ መሰናከሎች የኢኮኖሚውን የማምረት ሃይልና የውስጡን የገበያ ውድድር ጎድተውታል። ፓርቲው የፈጠራቸው ለተወዳዳሪዎች ቀዳዳ ነስተዋል። የአምስት አመቱ እቅድ አስተማማኝ አይደለም" የሚል ምክር ሰጥቷል። ዓለም ባንክ ስለ ግል ክፍሉ ሚና ባወጣው የውስጥ ዘገባ "የምርት ኢንዱስትሪዎች በመንግሥትና በፓርቲ መያዛቸው ቀጣይነትና ፍትሃዊ የሆነ ልማት ያመጣል የሚል እምነት የለንም። በዚህ ሁኔታ ከቀጠለ መዋቅራዊ ለውጥ ሊኖር አይችልም" ከሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል። ምሳሌ አድርጎ የተጠቀመባቸው አስደናቂ ልማት ያሳይቱን የምስራቅ ኤዢያ አገሮች ነው። አንባቢ እንዲገነዘበው የምንፈልገው አንድ ለኢኮኖሚና ለኑሮ የሚጠቅም፤ ገቢ የሚያስገኝ ሃቅ አለ። ጥንታዊ ባህል፤ ልምድና ጥሪት የሚባል። ኬንያ ለብዙ ሰው የስራ እድል የፈጠረችበትና የውጭ ምንዛሬ የምታገኝበት ከተፈጥሮ ሃብት ጋር የተያያዘ ቱሪዝም ነው። የጋምቤላ፤ የኦሞ ሸለቆ ወዘተ የተፈጥሮ ሃብት የስራ እድል ይከፍታል። ነዋሪዎች ከተፈጥሮ ሃብታቸው ይጠቀማሉ። ለመንግሥት ገቢ ያስገኛል፤ የኦሞ ሸለቆ ሃብት የማይተካ ነው። የነዋሪዎቹ ባህልና ልምድ፤ የተፈጥሮው ሃብት፤ ወንዙና ሸለቆው ለልማት ቁልፍ ነው። አንድ የውጭ ቱሪስት ይህን በዓለም የማይገኝ ሃብት ለመጎብኘት አስራ ስድስት ሽህ ዶላር ከፍሏል። አስፋፍቶና ዘመናዊ አድርጎ መጠቀም ብልሃት ነው። ነዋሪው ክብሩን ጠብቆ ይኖራል፤ የግል ክፍሉ ዘመናዊ የቱሪስት መስተንግዶ አገልግሎት ያስፋፋል። ሁሉም ይጠቀማል። ገዢው ፓርቲ ያተኮረው ከሃይል ማመንጫና ከስኳር ፋብሪካ ላይ ነው። ሌላውን የልማት መንገድ ፈጽሞ ንቆታል። የነዋሪዎችንና የተፈጥሮውን ዘላቂነት ለአጭር ጊዜ ጥቅም ለውጦታል።

የገጠሩን አምራች ክፍል ማን አፈነው?

ገና ኋላ ቀርና ድሃ በሆነ አገር የገጠሩ ኢኮኖሚ ፈጣን እድገት ወሳኝ ነው። ገዢው ፓርቲ የገጠሩን አምራች ገበሬ ህገመንግስቱን ተጠቅሞ በሙሉ ተቆጣጥሮታል። ዓለም ባንክ፤ ኤፍኤኦ፤ ኢፍፐሪና (International Food Policy Research Institute) ሌሎች የእርሻው ምርት ከሕዝብ ብዛት ጋር አብሮ ሊራመድ አለመቻሉን በመገንዘብ የስራ አፈጻፀም ፖለቲካዊ እንደሆነ፤ ከውጤት ጋር ግንኙነት እንደሌለው ካስጠነቀቁ ቆይተዋል። ጥናቶቹ የሚያሳዩት፤ በእርሻና ሌሎች የስራ አፈፃፀምና ምርታምነት ሲነፃፀር የኢትዮጵያ እድገት ካሳዩ አገሮች አራት ጊዜ ዝቅተኛ መሆኑን ያመለክታል። ምክንያቱም ኢኮኖሚው የሚመራው እንደ ፖለቲካው ነው። ፓርቲው ባለፉት ጥቂት አመታት "አርባ አራት በመቶ ተጨማሪ ለም መሬት ታርሷል፤ የጥራ ጥሬ ምርት ጨምሯል፤ የገጠር ሚሊኒየሮች ተፈጥረዋል" ያለውን ዓለም ባንክ ባደረገው ሰፊ ጥናት ጥያቄ ውስጥ አግብቶታል። "የመሬት ይዞታ ፖሊሲ አለመሻሻል፤ የእርሻ ቴክኖሎጂ ኋላ ቀርነት፤ የተቋማዊ ድጋፍ ደካማነት ፤ የመሬት መቦርቦር፤ የመስኖ ምርት አለመስፋፋት፤ የማዳበሪያና የብድር

እጥረት፤ አግባብ ያለው ጥናትና ምርምር አለመኖር" ወዘተ "የእርሻ ምርት ውጤትን ወስኖታል። የገጠር ድህነትና ረሃብ እንዳይቀንስ ማነቆ ሆነዋል። ከስድስት እስከ ሰባት ሚሊዮን የሚሆኑ የገጠር መሬት አልባና ድሃ ገበሬዎች ሌላ አማራጭ ስለሌላቸው በዘላቂነት በውጭ የምግብ እርዳታ ይኖራሉ" ብሏል። "Agriculture has failed to keep up with population growth resulting in zero growth in agriculture GDP per capita." አገሪቱ ተፈላጊውን ምግብ ለህብረተሰቡ ለማቅረብ ስላልቻለች በያመቱ ብዙ መቶ ሚሊዮን ዶላር እየከፈለች ስንዴ፤ የምግብ ዘይት፤ ስኳር ወዘተ መሸመቷን ቀጥላለች፤ ዓለም ባንክ ይህን ብሎ ድጋፉን ቀጥሏል።

የዓለም ባንክ የህሊና ጫና (Reputational Risk)

ለአምባገነን መንግስታት እርዳታ የሚሰጡ ለጋሶች የታሪክ ተጠያቂ እንደሚሆኑ አንጠራጠርም። ከሁሉም በላይ ለኢትዮጵያ የሚያሰጋት ከነጻነት መታፈን የመነጨ ድህነት ነው። በአፍሪካ የልማትና የሃብታምነት አውራ ለመሆን የምትችል አገር በአገዛዝና በአመራር ብልሽት የመጨረሻ መሆን የለባትም እንላለን። የታወቀው የህንድ ኢኮኖሚስት አማርትያ ሴን ደጋግሞ የሚያስተምረን ረሃብ ከአገዛዝ ጨለማና ከአመራር ድንቁርና የመጣ መሆኑን ነው። "በአፍሪካና በሌሎች አገሮች ተከታታይ ረሃብን ለማስወገድ አስፈላጊው የአገዛዝ ለውጥ ዲሞክራሲንና ያልተገደበ የፕሬስ ነጻነት ተቋማዊ ማድረግና በጠላትነት የሚካሄድ ፖለቲካን በሙሉ ማስወገድ ነው" ያለው የኢትዮጲያን መንግሥትና ተቃዋሚውን በአንድ ላይ ይመለከታል። በእኛ ግምት፤ የጥላቻ ፖለቲካ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እድገትና ታላቅነት ፀር ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት ህብረተሰቡን ሆነ ብሎ በቋንቋና በጎሳ ክልል ሲያዋቅርና የፈለገው ክልል ለመገንጠል ይችላል ሲል፤ የአገሪቱን ከድህነት ወጥታ ታላቅ የመሆን እድል ዘግቶታል። ቢያንስ ገድቦታል። "እውነተኛ ዲሞክራሲ፤የፕሬስ ነጻነትና ከጥላቻ የፀዳ ፖለቲካ" ረሃብን ለማጥፋት፤ ለቀጣይነትና ፍትሃዊ እድገት አስፈላጊ ነው የሚለውን መሰረተ ሃሳብ እንቀበላለን። በዚህ መሰረት የውጭ እርዳታ እነዚህን እሴቶች ለማንፀባረቅ አለመቻሉ ያጠያይቃል። አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ የሡብአዊ መብት "ጠበቃዎች" ና ለጋሶች፤ በተለይ ዓለም ባንክ የሚሰጠው ቁጥጥር የሌለበት እርዳታ አምባገነናዊ መንግሥት አጎልምሷል ይላል። በኢትዮጵያ የዓለም ባንክ ዲሬክተር የነበረው ኬን ኦሃሺ ቀጣይነት ያለው ልማት ሊኖር የሚችለው "የፓርቲ፤ የመንግሥት፤ የጥቂት ግለሰቦችና ፓርቲው የፈጠራቸው ድርጅቶች የበላይነት ተወግዶ እውነተኛ ውድድር ሲፈጠር ነው" ያለውን የድርጅቱ የውስጥ የጥናትና ምርምር ክፍል አረጋግጦታል። የደመደመው፤ "በአጠቃላይ ሲታይ፤ ዓለም ባንክ ለኢትዮጵያ መንግሥት የሚሰጠው እርዳታ ውጤት አጥጋቢ አይደለም" የሚል ነው። ከዚህ የበለጠ የህሊና ወቀሳ--አብዛኛውን የውጭ እርዳታ (the bulk of official development assistance) ለሚሰጥ ድርጅት በራሱ ሰራተኞች ደርሶበት አያውቅም። ከባንኩ ቋንቋ ወጣ ብለን ብናየው፤ የውጩ እርዳታ ቀጣይነት ያለው አገር ወለድ ልማት አልፈጠረም። በተለይ አጥጋቢ ሆኖ ያላገኘው መንግሥት "ደሃውንና ማህበረተሰቡን አላጎለመሰውም። ከመንግሥት አገልግሎት ውጭ የስራ እድል አልፈጠረም። ሡብአዊ መብቶችን አላከበረም። አካባቢውን አልተንከባከበም" በሚሉ ወሳኝ በሆኑ የአገዛዝ ግድፈቶች ዙሪያ ነው። 56/

ለዓለም ባንክ አገልግሎት የሰጠን ሁሉ የምናስታውሰው፤ እርዳታ ውጤታማ የሚሆነው የአገር ወለድ ልማት መሰረት ሲጥል ብቻ ነው። ኮሪያ፤ የምስራቅ ኤዢያ አስደናቂ ልማትና ሌሎች የሆነውን ማስታወስ ተገቢ ነው። በነዚህ አገሮች ሙስና መኖሩ አከራካሪ ባይሆንም። በአብዛኛው፤ እርዳታው የዋለው የጥቂቶችን ኪስ ለመሙላት አልነበረም። የባንኩ ዋና ራእይ "ድህነት የሌለበት አለም" የሚል ነው። June, 2007, Economist እንዳለው "የባንኩ ዋና ስራ አገር-ወለድ የሆነ የድህነት ዘመቻ ማጠናከር...ትንሽ ገንዘብ መስጠት አንድ አንድ ጊዜም ገንዘብ መንሳት። ሌላ ጊዜ እውቀት" ማስተላለፍ። ይህ ምክር ኢትዮጵያ አልተሰራበትም። የባንኩ እርዳታ ከአመት ወደ አመት አድጓል። አብዛኛው በ2012 መጨረሻ ከሰባት ቢሊዮን ዶላር በላይ የደረሰው ፖርትፎሊኦ የዋለው ለመሰረተ ልማት--መንገድ፤ ትምኅርት፤ ጤና ጥበቃ፤ ሡብአዊ አገልግሎትና ምግብ ላይ ነው። የመንገድ ስራ ዋና ሙስና ፈጣሪ ነው። ዘገባዎች ማድረጉ ጠቃሚ ቢሆንም፤ ዓለም ባንክ ሙስናንና አድልዎን እንደ ነቀርሳ አልቆጠረውም።

ትምኅርት ጥራት የለውም። ዓለም ባንክ የሰጠው እርዳታ ጥራት ያለው የሡብአዊ ጉልምስና እንዳላበረከተ አላየውም። የጤና አገልግሎት ከዓለም የመጨረሻ መሆኑን አይቶ መንግሥት የፖሊሲ ለውጥ እንዲደረግ አላስገደደም። በቻይና፤ ቬትናም፤ ህንድና ሌሎች ዓለም ባንክ የሰጠው እርዳታ ዝቅተኛ አምራቾችን ከድህነት ነፃ አውጥቷቸዋል፤ የብዝዎችን ጤና አሻሽሏል። በኢትዮጵያ ተከታታይ የምግብ እርዳታ ድሃውን የበለጠ ድሃና ጥገኛ አድርጎታል። ለጋስ መንግስታትና ሌሎች አበዳሪዎችና ለጋሶች እርዳታ አጥጋቢ ውጤት ያላስገኘበት ምክንያት እንዳለ ያውቃሉ። የምንጠይቀው ለውጥ ያልገቱበት ምክንያት ምንድን ነው የሚል ነው።

ከ1998-2005 (ምርጫ ዘጠና ሰባት) ሃያ ስምንት መንግስታት፤ አስራ ስድስት ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ቁጥራቸው በብዙ መቶ የሚገመቱ የግልና የመንግስት ያልሆኑ ድርጅቶ ኢትዮጵያን የድህነት ማጥፋት ላቦራቶሪ አድርገዋታል።

በያመቱ የሚሰጡት እርዳታ ከ$660 ወደ $2 ቢሊዮን ወጣ፤ አሁን አራት ቢሊዮን ዶላር ደርሷል። እስከዚህ ወቅት ዓለም ባንክ ከስራ ላይ ውሏል ያለው (Total Disbursement by the government) $8.5 billion ደርሶ ነበር። ዛሬ እርዳታው በአመት አራት ቢሊዮን ($4 billion) አልፏል። ይህን ለማንሳት የተገደድንበት፤ አብዛኛው የኢትዮጵያ መሰረተ ልማት የጦፈበት ከምርጫ ዘጠና ሰባት በኋላ መሆኑን ለማሳየት ነው። ምርጫ ለውጥ ያመጣል። ተከታታይ ነጻ ምርጫ ህይወት ይለውጣል። ከዚያ በፊት ያለው አገራዊ መሰረተ ልማት በጣም የተወሰነ ነበር። ዓለም ባንክ “ፀጥ ያለ ወይንም የታፈነ ረሃብ” (The Silence of Hunger)” ብሎ በሰየመውን የምርምር ጽሁፉ ይፋ ያደረገው ድርጅቱና ሌሎች ለጋሶች በተከታታይ ያሳዩት ድክመትና ግድፈት “ደሃውን በቀጥታ ድምጹን አዳምጠው የደረሰበትን ብሶትና የኑሮ ችግር ተምረው” የእርዳታውን አሰጣጥ ዘዴ ማስተካከል አለመቻላቸው ነው። መንግሥት የሚሰጠውን የኑሮ መሻሻል መረጃ እንደ እውነት ሲወስዱ ቆይተዋል። ተጠቃሚው በተቋሞች ይደገፋል ማለት አይቻልም። የገዢው ፓርቲ የፖለቲካ መሳሪያ ሆነዋል። “Institutional development is particularly weak, with the country in no better position than it was 10 years ago to make efficient allocation of resources….Political power is frequently used to create rents for members of the ruling coalition.” እኛ የኪራይ ሰብሳቢ ስርዓት የምንለውን ያንፀባርቃል። እድገታዊው መንግሥት ከሚለው ጋር ይጻረራል። ገዢው ፓርቲ ኪራይ ሰብሳቢው የሚለው ተቃዋሚው ነው። እኛ የምንለው ከዓለም ባንክ አይለይም፤ የፖለቲካ ስልጣን “የተደራጀ ምዝበራ” ወልዷል ነው። 57/

የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ችግር ድህነት ብቻ አይደለም። ድህነት ሊወገድ ይችላል። ዋናው የአስተዳደር ጫና፤ ጭቆና፤ ቁጥጥርና አፈና፤ ከላይ ወደታች የሆነ የመንግሥት ባጀትና የውጭ እርዳታ አከፋፈል ዘይቤ ነው። separate the party from the state, and to influence government through established institutional mechanisms such as cabinet and parliament. One issue is the seemingly pervasive presence and influence of the party in public administration.” 58/

በግልጽ ቢቀመጥ ኖሮ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት የህግ አውጭነት፤ የህግ አስፈጻሚነትና የሕግ ተርጓሚነቱንና ተቆጣጣሪነቱን ስልጣን አደራርቦ ይዞታል። (There are no checks and balanances or separation of powers in the system). ነጻ የሆነ ተቆጣጣሪና ተቆርቋሪ ተቋም የለም። 59/

በገጠር የሚኖረው ሕዝብ ግብአቶችን ለማግኘት የተቀላለፈውን ስርአት ማገልገል አለበት። ግብአቶችን የሚያስተዳድረው የቀበሌው ፖለቲካ ካድሬ ነው። በ2005 ሂዩማን ራይትስ ወች እንዳሳየው፤ አንድ ገበሬ ማዳበሪያ በብድር ተሰጥቶት አቅሙ ስለማይችል ባይከፍል እስር ቤት ይገባል። “የእርሻ አገልግሎት ባለሞያዎችና የማህበረሰብ ተመልካቾች እንዳሉት፤ ለመክፈል አቅም የሌላቸው ብዙ ገበሬዎች ታስረዋል። ቅጣት እንዲከፍሉ ተገደዋል። አንድ ገበሬ ሁለት መቶ አምሳ ብር ለመክፈል ስላልቻለ እስር ቤት ገብቷል።” ገጠርም ሆነ ከተማ፤ በጎ አድራጊዎች አርባ ቢሊዮን ዶላር አፍስሰው የህወሓት/ኢህአዴግ ማህበረሰብና የኢኮኖሚ ልማት አመራር በድህነት፤ በረሃብ፤ በተስፋ መቁረጥ ወዘተ ለሚንገላታው አጋር፤ ጠበቃና ደጋፊ እንዲሆን ለማድረግ አለመቻላቸውን ያሳያል። “Ethipia faces a challenge larger than poverty: it is a combination of extreme deprivation, chronic hunger and famine… a million children are stunted (60 percent in the Amhara region) from chronic undernourishment…millions are constantly at risk of starvation, including subsitence farmers….every three to five years the number of vulnerable people rises substantially, to 13 million in 2013…and increase each year there after… with no end in sight.” መንግሥት የሚለው ይህ ሁሉ የተቃዋሚ ትችት ነው። እድገቱ “የብዙ ደሃ ኑሮ አሻሺሏል” ነው። ችግሩ ይህ ድምፅ የደሃው አይደለም። “ማህበረሰቡ ታይቶ የማይታወቅ እድል አግኝቷል” ብሎ የበየነው መንግሥት ነው። 60/

ይህ ስእል የሚያሳየው ለጋስ ድርጅቶች መንግሥቱ እጥፍ ድርብ እድገት አለ የሚለውን ፕሮፓጋንዳ ይዘው የምንሰጠው እርዳታ ውጤት አሳይቷል ማለታቸው ይገልጻል። ለአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ አጥጋቢ አይደለም። በጥቂት አዲስ ባለጠጋዎችና ዘጠና በመቶ በሚሆነው የነፍስ ወከፍ ገቢው ከእጅ ወደ አፍ በሆነው መካከል ያለው ልዩነት ቀን በቀን እየተባባሰ ሄዷል። ገዢው ፓርቲ ለዚህ የፈጠረው መንገድ ሠብአዊ መብቶችን በበለጠ ማፈን ነው። የስለላ መረብ ማጠናከር የስርአቱ ዋና መሳሪያ ሆኗል። “Communites are under perpetual surveillance by kebele officials who report any subversive activities to higher authorities…the formal structure of local government in Ethiopia has remained unchanged since the overthrow of the Derg dictatorship in 1991.” ገዢው ፓርቲ ከቻይና በብድር የሸመተውን የመገናኛ ቴክኖሎጂ የስለላን መረብ አጠናክሮበታል..ቀደም ሲል ጋሬ (ሰላሳ ቤተሰቦች፤ ጎጥ (ሶስት ጋሬዎች የሚጠቀልል) ብሎ ያወጣውን የስለላ መረብ አሁን አንድ ለአምስት አድርጎታል።

ሂዩማን ራይትስ ወች ይህን የስለላ መረብ "ኦርዌሊያን ይመስላል (Voice in Orwellian Villages)" ብሎታል። ፍፁም ግፈኛና አፋኝ ማለቱ ነው። 61/

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሚመኘው "የሚዘገንን አፈና፤ ምስኪንነት፤ ድህነትና ረሃብ" እንዲጠፋ ነው። አብዛኛው የማይቀበለው ይህ ሁኔታ ተለውጧል የሚለውን የመንግሥትና ደጋፊዎች ከእውነት የራቀ "በሬ ወለደ" የሚል የኑሮ መሻሻል አለ የሚል ታሪክን ነው። የማይካደው ከደርግ ጋር ሲነጻጸር ብዙ መንገድ፤ ህንጻ፤ ቤት፤ ትምኅርት ቤት ወዘተ ተሰርቷል። ይህ የእርዳታ ውጤት ነው። ዓለም ባንክና ሌሎች የሚሰጡት እርዳታ የአንድ ፓርቲን የበላይነት አጠናክሯል። በጥቂት የኢኮኖሚ ዘርፎች የጦፈው እድገት በጥቂት አዲስ ሃብታሞችና በዘጠና በመቶው ሕዝብ መካከል ያለውን የገቢና የኑሮ ልዩነት በደርግ ጊዜ ከነበረው አባብሶታል። ለጋሶች ቢቀበሉም ባይቀበሉም ለተጠቃሚው ድምፅና መብት፤ ለፕሬሱ ነፃነት፤ ለተቃዋሚው ተሳታፊነት፤ ለማህበረሰብ ድርጅቶች ቦታ ወዘተ የማይሰጥ አገዛዝ፤ በመሰረቱ ዝግና ራሱን አገልጋይ ነው (a closed order) ለማለት ይቻላል። ሰሜን ኮርያ ሆነ ኢትዮጵያ ዝግ የሆነ አገዛዝ ለጥቂቶች መብት ይሰጣል። ለአብዛኛው እድል ይነሳል። ለዚህ ነው ኪራይ-ሰብሳቢነትና አድሎ የጦፈው። ለዚህ ነው የአገር ውስጥ ገበያ ቅጡን ያጣው፤ የዋጋ ግሽበት ከቁጥጥር ውጭ የወጣው፤ የወጣቱ ትውልድ ከአገር የሚሰደደው። ከልማት አንጻር ሲታይ፤ ይህ ለጥቂቶች አገልጋይ የሆነ ፖለቲካ ኢኮኖሚ እድገት ቢያሳይም ቀጣይነትና ፍትሃዊይነት ሊኖረው አይችልም ። ጠባብ ጎሰኛነት፤ ፓርቲ፤ መንግሥትና ተቋሞች ተቆላልፈው ተደራጅተዋል። የሚጎዳው ተራው ህብረተሰብ ነው። ዓለም ባንክ ይህን ችግር ካየው ቆይቷል። የኢትዮጵያ የተቆላለፈ የአንድ ፓርቲ አገዛዝ ድህነትን ለማጥፋትና ብሄራዊ የግል ክፍሉን ለማስፋፋት ማነቆ ሆኗል ብሎ ፖሊሲውን አልቀረም። "There is also a significant unfinished agenda in Ethiopia of transforming the political party system for improved economic governance."

የዓለም ባንክ የአገር ኢኮኖሚ ጥናት "የገቢ ድህነት (Income Poverty) ከዱሮው ሊወርድ አልቻለም። ኢኮኖሚው መዋቅራዊ ለውጥ አላሳየም። በገጠር ያለው ሁኔታ ሲታይ፤ በጥቂት ምርጥ ገበሬዎችና በአብዛኛው ገበሬ ያለው የኑሮ ልዩነት እየተባባሰ ሄዷል። የዚህ ዋና መነሻ የመንግሥት ፖሊሲ ነው" ብሏል። እንደዚህ ከሆነ የአገዛዙ ጥራት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ ሄዷል። የእርሻ ምርት እድገት ከሕዝቡ ብዛት ጋር አልተመጣጠነም። የግል ክፍሉ አልተስፋፋም። እንዱስትሪ አላደገም። ቁልፍ የሆነውን የሠብአዊ ልማት ከለጋሶች አንፃር እንየው። ብዙ ትምኅርት ቤቶች ተሰርተዋል። ኮሌጆች ተከፍተዋል። ሆኖም የተማሪዎች መብዛት በራሱ ውጤትን አያሳይም። አንድ አስተማሪ ለአምሳ አራት ተማሪዎች፤ መጽሃፍና እርሳስ፤ መፀዳጃና በቂ ምግብ ለሌላቸው ተማሪዎች አገልግሎት ይሰጣል። ይህ የሠብአዊ ልማት መሻሻል መለኪያ መለኪያ አይደለም። የተጨማሪ እርዳታ ማካበቻ ነው። "A massive number of new schools have built, but the student-to-teacher ratio, already among the highest, is rising and shortages of textbooks are severe...main social indicators, such as poverty rate and human development index (mentioned earlier), show no significant improvements over the review period...Ethiopia ranked 170 of 177 countries in 2006 (in 2011/2102, its rank was 171 of 178 countries, the same as in 2006)...there was no perceptible change in the following 8 years...Life expectancy at birth was also little changed." በአብዛኛው ሰው ኑሮ ሲታይ ምንም አጥጋቢ ውጤት የለም የሚል ነው። "Thus, based on indicators provided by external sources, there has been little or no improvement in living standards." 62/

በተራው ኢትዮጵያዊ ህይወት ሲታይ ከደርግ ወዲህ "ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ መሻሻል ይታያል"፤ በአንድ አንድ የኢኮኖሚ ክፍሎች "የተሻሻለ ሁኔታ አይታይም።" ከዚህ ግንዛቤ ላይ ከተደረሰ "አስደናቂው እድገት" ለማን አሰደነቀ? ማንን አከበረ? ማንን አደኺየ? እርዳታው ወደ የት ተሸጋገረ? ማንን አከበረ? ወጣቱ ትውልድ ምን ይበጀዋል? ብለን እንጠይቃለን።

ለመንግሥት በቀጥታ የሚሰጥ እርዳታ አምባገነንነትን አጠናክሯል

ይህ በተከታታይ የሚታይ የኢኮኖሚ አገዛዝ ማነቆ እየተባባሰ ሄዷል። ለጋስ መንግስታትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የአገዛዙን አመራር ጮሌነት በሚገባ አላወቁትም። ቢያውቁትም ፖለቲካዊ ስለሆነ በድፍረት አልነኩትም። ህወሓት/ኢህአዴግ ህገመንግሥቱን ሲቀርፅ ፍጹም የሆነ ሁለ-ገብ የበላይነቱን በሚያረጋግጥ መንግድ ነው። አንቀጽ አምሳ አንድ (2) የፌደራል መንግሥት ስልጣን በኢኮኖሚ አመራር የሚኖረውን ሚና ገልጾታል። "የሃገሪቱን አጠቃላይ የኢኮኖሚ፤ የማህበራዊይና የልማት ፖሊሲ፤ ስትራተጂና እቅድ ያወጣል፤ ያስፈፅማል።" ሕጋዊ የበላይነት ካለ የውጭ እርዳታና የፌደራል ባጀት ወሳኞች እንድሚፈልጉት በፖለቲካ ውሳኔ ይመራሉ። "ክልል አንድ ቅድሚያ ያገኛል ከተባለ" ስራ ላይ ይውላል። ጋምቤላ መሬት ለሳውዲዎችና ለህንዶች ይሰጣል ከተባለ የክልሉ አስተዳደሩ ምርጫ የለውም። የወርቅ ማእደን ለምርጡ የፓርቲ ደጋፊ ለአላሙዲ ይሰጣል ከተባለ ሌላ ምርጫ የለም ። የአገዛዝ ጮሌነት ውይንም

“እራዳነት” ነው። ለጋሶች “ክልሎች የመወሰን ስልጣን አላቸው” (The myth of decentralized decision-making) የሚል የበላይ ፕሮፓጋንዳ ስነልቦናቸውን ማርኮት ነበር። ህገመንግሥቱ ስለ ክልል ስልጣንና ተግባር በአንቀጽ 52 (ሃ) የብሄር/ብሄረሰቦችን ታሪክ፤ ባህልና ኑሮ የሚያስከብር አውጆ ነበር። እንዲህ ይላል፤ “የክልሉን የኢኮኖሚ፤ የማህበራዊ ልማት ፖሊሲ፤ ስትራተጂና እቅድ ያወጣል፤ ያስፈጽማል።” የፌደራሉና የክልሉ ስልጣኖች ሲጋጩ የትኛው ወሳኝ ይሆናል? ስታሊኒስት በሆነው ህገመንግሥት፤ ወሳኝ ሊሆን የሚችለው ማእከላዊው፤ የፌደራሉ ነው። አቤቱታም ለማቅረብ አይቻልም። ህወሓት በበላይነት ለመግዛት የቻለው ለዚህ ነው። አቤት የሚባልበት ከፓርቲው ቁጥጥር ውጭ የሆነ ብሄራዊ ወይንም ማህበራዊ ተቋም የለም። “ኦርዌልያን” የተባለው ለዚህ ነው። በኦሞ ሸለቆ፤ በጋምቤላና በሌሎች ክልሎች የሚኖሩ “አናሳ” ብሄር/ብሄረሰቦች ባህል፤ ታሪክ፤ ልምድና ኑሮ በህግ መከበር አለበት።

ለለጋሶች አስቸጋሪ የሆነባቸው፤ በአንድ በኩል ድህነትን ማጥፋት ይፈልጋሉ። በሌላ በኩል ፖለቲካውን መንካት አይፈልጉም። የዚህ ውጤት፤ ቀስ በቀስ ለጋሶች (All Donors) የመረጡት ያለውን መንግሥት መደጋፍ (Pro-Incumbency or against political reform) ሆኗል። የአምባገነኑ መንግሥት ደጋፊ ከሆኑ፤ ለገዢው ፓርቲ ቆይታ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። በጥናት የደረስንበት የሚያመለክተው፤ የተራው ተጠቃሚ መብትና ድምጽ አይከበርም። በዚህ አገዛዝ እርዳታ መጨመሩ የሞራል ውድቅት ያሳያል። ለጋሶች ድህነትን ከማጥፋትና አገር ወለድ አቅምን ከመገንባት የበለጠ እርጋታን መርጠዋል። (Donors prefer stability over alleviation of poverty). ሂውማን ራይትስ ወች “Development without Freedom” ባቀረበው ማስረጃ የውጭ እርዳታ የፖለቲካ መቆጣጠሪያ መሳሪያ መሆኑን ገልጿል። የዓለም ባንክ የውስጥ ጥናት፤ የኢትዮጵያ የግል ክፍል ለመወዳደር አለመቻሉን አስምሮበታል። መለስ ዜናዊ የውጭ መንግስታትንና ኢንቬስተሮችን ለማባበል በ2006 መጀመሪያ እንዲህ ብሎ ነበር። “የእኛ ከዓለም ባንክና ከአይኤምኤፍ ጋር ተመካክረን ያወጣነው የኢኮኖሚ ለውጥ ከፓርቲና ከመንግሥት የበላይነት ወደ ክፍት የካፒታሊስት ገበያ ኢኮኖሚ የሚያመራ ነው።” በቃላት መጫወት ችሎታ የነበረው መለስ፤ ይህን ለውጥ “ዲሞክራሳዊ ልማት (democratic developmentalism” ብሎ ሰየመው። የበላይነቱን የያዙት አዲስ ባለስልጣናት፤ ፓርቲው፤ የፈጠራቸው ድርጅቶችና ታማኝ የሆኑ “ሁሉን ብሄር/ብሄረሰቦች” እንዲወክሉ በብልሃት የተመረጡ “የፖለቲካ ስልጣን ጌቶች” (Elites) ናቸው። በተግባር ሲታይ፤ አባባሉ ከዓለም ባንክና ከሌሎች የምእራብ መንግስታት እሴቶች ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። አንድ ጠባብ ጎሰኛ ፓርቲ የሚመራው መንግሥት ዲሞክራሲንና የካፒታሊሥት ውድድራዊ ኢኮኖሚን ሊፈጥር አይችልም። የትም አገር አልታየም። ስም መቀየሩ ስርዓቱን አይቀይረውም።

በሕግ አንጻር ስናየው፤ ዲሞክራሳዊ አገዛዝ ገጠር፤ ከተማ አይለይም። በቀበሌ ጋሪ የሚነዳ ግለሰብ የሚሊዮን ዶላር ቤት ካለው አይለይም። በገጠር የሚኖር መሬት የሌለው የቀን ሰራተኛ ከህወሓት ባለስልጣንና አዲስ ከበርቴ አይለይም። በአግባብ የሚሰራ ህገመንግሥት ቢኖር፤ በሕግ ፊት እነዚህ የእኩሉነት መብት አላቸው። ከአርባ ቢሊዮን ዶላር በላይ እርዳታ ሲሰጡ ለጋሶች የሳቱት በሕግ ፊት እኩልነት የሌለበት አገዛዝ መኖሩን ነው። የማህበረሰብ ልማት፤ የገቢና የባለጠጋነት መግቢያ (Access Equity) እኩልነት አይቀበልም። በተለይ፤ የአገዛዝ የበላዮች የማህበረሰብና የኢኮኖሚ “ወንጀለኞች” የሚያስብላቸው አድሏዊዊና ጠባብ ጎሰኛ መሆናቸው ነው። አገዛዝን ለግል ጥቅም ማዋላቸው ነው። የዓለም ባንክ ዘገባ መደምደሚያ እንዲህ ይላል። “የመንግሥት ክፍሉ ለክልል ነዋሪወች ስልጣንና መብት አልሰጠም። ሠስብአዊ መብታቸውን አልጠበቀም። አድልዎ ያደርጋል። የአብዛኛውን የመሻሻል እድል ዘግቶታል።” ባይናገረውም፤ የተደራጀ ምዝበራ እንዳለ ያመለክታል። ዓለም ባንክና ሌሎች ለጋሶች ይህን “የጨለማ ኢኮኖሚ አመራር ስእል” ካዩ ገዢው ፓርቲ “የድህነት ማጥፋት ጠበቃ (Pro-Poor)” ሊሆን አይችልም ከሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ ነበረባቸው። ምክንያቱም፤ ፓርቲው “በኑሮ መሻሻል መለኪያ” ያገኘው ውጤት “ፍጹም አጥጋቢ አይደለም” የሚል ነው። 63/

ባጭሩ፤ የውጭ እርዳታ ከጥቅሙ ጉዳቱ እያመዘነ ሄዷል። ዋናው ጉዳት አምባገነኑ ፓርቲ እርዳታውን ለግል ጥቅም አውሎታል። አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከእርዳታው የሚመጣ እድገት ተጠቃሚ አልሆነም። ለጋሶች ይህን በሚገባ ያውቁታል። የቻይና መንግሥት ህወሓት/ኢህአዴግን መደገፉ አስገራሚ አይደለም። የምእራብ መንግስታትና ለጋስ ድርጅቶች የሚሰጡት እርዳታ ከራሳቸው እሴቶችና የአገዛዝ እምነቶች ጋር አብረው አይሄዱም። አሜሪካ በፀረ-ሽብርተኛነት መደጋገፍ ለኢትዮጵያ መንግሥት የሚሰጠው እርዳታ አብዛኛውን የኢትዮጵያ ሕዝብ አልረዳውም። በግልጽ የረዳው አምባገነኑን መንግሥት ነው። በዘላቂነት ሲታይ አገር ወለድ የሆነ፤ በራሱ ተወላጆች የሚመራ፤ መላውን ህብረተሰብ ከድህነት፤ ከረሃብ፤ ከሃፍረት፤ ከጥገኛነትና ከስደት ነጻ የሚያወጣ ማህበረሰብ ለመመስረት አላስቻለም። የእርዳታ ፖሊሲ መለወጥ አለበት ከሚል ድምዳሜ ደርሰናል።

ከተሜው የቤቱ ባለቤት አልሆነም። የእድገትና ልማት ዋና መለኪያ ዜጎች የራሳቸው የቁሳቁስና ሌላ ሃብት የበላይነት በህግ ሲከበር ነው። ፍሪደም ሃውስና ሌሎች ዘገባዎች እንዳሳዩት፤ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የግል ሃብት ባለቤትነት የለም።

ገዢው ፓርቲ የከተማ ቦታና ቤት የፖለቲካ መቆያ፤ የስደተኛው ማባበያ፤ የደጋፊዎች መደጎሚያና የምዝበራ ሃብት መንስኤ አድርጎታል። ደርግ ለሕዝብ ጥቅም ብሎ ያወጀው ብዙ ኢትዮጵያዊያን የታገሉለት የመሬት ይዞታ የህወሓት/ኢህአዴግ ፖለቲካ ስልጣን መሳሪያ ሆኗል። በአዲስ አበባ ብቻ አንድ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን "ዘመናዊ" የሚባል ቤት የላቸውም። መንግሥት የቤት ችግር አጠፋለሁ ብሎ ቃል ከገባ ቆይቷል። ያለፈው እቅድና ተግባር አመልካች ከሆነ ለ500,000 ቤተሰቦች የቤት ፍላጎት መንግሥት ያቀረበው 80,000 ነው። አብዛኛው የከተማ ነዋሪ በህይወቱ በዘመናዊ ቤት ለመኖር አይችልም። ብዙ መቶ ሺህ ኢትዮጵያውያን የሚኖሩት በሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተቀባይነት በሌለው፤ ፈረንጆች Slum በሚሉት አኗኗር ነው። አሁንም መንግሥት የሚሰራቸው ቤቶች ለመካከለኛውና ለደሃው ፍላጎት አልደረሱለትም። በአብዛኛው ኮንዶ ለመግዛት አቅም ያላቸው በስደት የሚኖሩና አዲስ ባለ ፀጋ የሆኑ ግለሰቦች ናቸው። ይህን አኗኗር ከአዲስ ሚሊኒየሮች ቪላና ሰማይ ጠቀስ ፎቅ ሲነፃፀር የገቢና የኑሮ ደረጃ የሰማይና ምድር ያህል መራራቅ እንዳለ እናያለን።

የእድገቱ ውጤት ለማን ጠቀመ?

ገዢውፓርቲ በሁሉም ሠብአዊ እድገት መለኪያዎች ኢትዮጵያ አይታው የማይታወቅ እድገት አሳይቻለሁ ይላል። የተባበሩት መንግስታት ልማት መለኪያ ስንመረምር ከላይ ያሳየነውን ያጠናክራል። በመሰረተ እድገት--ጤና፤ ትምኅርት፤ ንፁህ ውሃ፤ መፀዳጃ፤ ምግብ፤ የስራ እድል-- በተከታታይ ኢትዮጵያ ከመቶ ሰማንያ አምስት አገሮች ከሰባ አራተኛነት ወይንም ከሰባ አምስተኛ ከፍ ብላ አታውቅም። በሞ-ኢብራሂም የአገዛዝ መለኪያ ከአምሳ ሁለት የአፍሪካ አገሮች ከሰላሳ አምስተኛነት ከፍ ብላ አታውቅም። የወል ስትሪት ጆርናል በተከታታይ ያወጣው ዘገባ፤ "ነጻነትና ተሳትፎ የለም። ተሳትፎ ስለሌለ የግል ስራ ለማቋቋም ችግር አለ። እድገቷ ዝቅተኛ ነው" ብሏል። የሠብአዊ መብቶች ተቋም፤ "ኢትዮጵያ የሠብአዊ መብቶች በሙሉ የታፈኑባት ናት" ብሎ ደምድሟል። የኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ምርምር፤ "ኢትዮጵያና ኒጀር በአፍሪካ የመጨረሻ ድሃ አገሮች ናቸው" ብሏል። ህወሓት/ኢህአዴግ በሚሰለች ደረጃ የተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅት (UNDP) "ፈጣን እድገት አለ" ብሎናል ይላል። ይህ ድርጅት ያለው "የነፍስ ወከፍ ገቢዝቅተኛ፤ የእርሻ ምርት ከሕዝብ እድገት ጋር ያልተመጣጠነ፤ ከቁጠባ የሚገኝ የልማት ገቢ ዝቅተኛ፤ የስራ እድል ዜሮ፤ የሴቶች እኩልነት ከሌሎች አፍሪካ አገሮች የማይወዳደር" የሚል ነው። በ2011 ኢትዮጵያን ከመቶ ሰማንያ አምስት አገሮች መቶ ሰባ አራተኛ ነበረች። በ2011/2012 ከመቶ ሰባ ስምንት አገሮች መቶ ሰባ አንደኛ ። እነዚህ ዘገባዎች በተከታታይ ያሳዩት የገቢና የባለጠጋነት ክፍተት እየባሰ መሄዱን ነው። ይህ የባለጠጋነት ልዩነት የእርስ በእርስ ጦርነት ከሚካሄድባት ከዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኦፍ ኮንጎ የባሰ ሆኗል።

ለደሃው፤ የብር ጥቅም ዋጋ ቢስ ሆኗል

ለተሜም ሆነ ለገጠር ነዋሪ የገቢ የመግዛት አቅም ውድቀት ያሳያል። አማካይ የአመት የነፍስ ወከፍ ገቢ ስናይ፤ በ2012 መጨረሻ፤ ምንም እርዳታ የማያገኘው፤ አምባገነን የሆነው የሰሜን ኮሪያ መንግሥት $1,900 ነው። በዓለም ሶስተኛ ከፍተኛነት ያለው እርዳታ የሚያገኘው የኢትዮጵያ መንግሥት $370 ነበር፤ አሁን ትንሽ አድጓል ይባላል። ደጋግመን የምንጠይቀው መሰረታዊ ጥያቄ ከእርዳታው ተጠቃሚ የሆነው ማን ነው። ባለፉት አስራ ስምንት አመታት ብቻ፤ መንግሥት ለልዩ ልዩ ስራዎች ብሎ ወደ ውጭ ያስተላለፈው ገንዘብ (Capital outflow) $8.3 ቢሊዮን። ከ2000-2009 ከህግ ውጭ ከአገር የሸሸው የውጭ ምንዛሬ $12 ቢሊዮን ደርሷል። እስካሁን ከሃገር የወጣው ሃያ አምስት ቢሊዮን ዶላር ነው። የተራው ዜጋ ኑሮ በዋጋ ግሽበት መናር ተናግቷል። ኢትዮጵያ ወደ ውጭ የምትሸጠው እቃ እመርታዊ ለውጥ አላሳየም። ባያሳይም፤ ገዢው ፓርቲ በእድገት ስም የብሩን ዋጋ በተከታታይ ቀንሶታል። ልቦና የሚጠይቀው ይህ ተከታታይ የብር ዋጋና ጥቅም መውረድ በገቢና በመግዛት አቅም ያለውን ጉዳት ጭምር ነው። የአንድ ዶላር ዋጋ በ2007 8.96 ብር፤ በ2008 9.57 ብር፤በ 2009 11.78 ብር፤ በ2010 14.41 ብር፤ በ2011 16.9 ብር ሆኗል። የዚህ ውጤት ገቢያቸው ከፍተኛ ለሆነው አያስቸግርም። የሚያስቸግረው ለተራው፤ ደሞዙ ወይንም ገቢው ለማይጨምረው ነው። ለመግዛት አቅም ያላቸው አዲስ ኃብታሞች ናቸው።

የኢትዮጵያን እዳ ማን ይከፍላል?

መንግሥት የአገር ውስጥ ሆነ የውጭ ብድርን እንደ ሸክም አያየውም። ምርትና ገቢ እያደጉ ካልሄዱ እዳውን ለመክፈል መበደር ግዴታ ይሆናል። እዳውን ተሸካሚው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንጅ ገዢው ፓርቲ አይደለም። ማንኛውም መንግሥት መሰረተ ልማት ተበድሮ መስራቱ የሚጠበቅ ነው። ሆኖም፤ ብድሩ የምርትና የስራ እድል መፍጠር ውጤት ማሳየት አለበት። የኢትዮጵያ ጠቅላላ እዳ ከጠቅላላ ገቢዋ አርባ አምስት በመቶ ደርሷል። (45 percent of GDP estimated at $31 billion at the end of 2012 and a per capita GDP of $370). የቻይናን ብድር ሳይጨምር፤

የውጭ እዳ $15 ቢሊዮን አልፏል። የውስጥ እዳ 60 ቢሊዮን ብር አልፏል። መንግሥት ለምን ይበደራል አይደለም። ተበድሮ ምን ሰራበት፤ የአገሪቱ የምርት ውጤት ጨመረ አልጨመረም? የስራ እድል ፈጠረ? የተራውን ዜጋ ህይወት ለወጠ? አገር ወለድ ከበርቴና ኢኮኖሚ ፈጠረ? ወዘተ የሚሉት ናቸው። በአንድ በኩል መበደር በሌላ በኩል፤ ብሩን በጥቁር ገበያ ወደ ዶላር እየለወጡ በልዩ ልዩ መልክ ወደ ውጭ ማሸሽ የሚያስከትለው ችግር ለአሁኑ ትውልድ ብቻ አይደለም። ለተከታታይ ትውልድ ነው። የውጭ ምንዛሬ በገፍ ከአገር ሲወጣ ተመልሶ የአገሪቱን እዳ አይከፍልም። የሚከፍለው ህብረተሰቡ ነው። ይህ ብቻ፤ ገዢውን ፓርቲ "ለአደራ ያልበቃ"ና ችሎታ የሌለው አገዛዝ ያስብለዋል። ለብሄራዊ አደራ በቂነት ያለው አገዛዝ ሳንተምም ብትሆን እንዲሰረቅ አይፈቅድም። ባለስልጣናት የተደራጀ ምዝበራ አካሂደው ባለጊዜ ሃብታሞች እንዲሆኑ አይፈቅድም። ይህ ሁሉ ብሄራዊ ችግር እየታየ ገዢው ፓርቲ የውጭ የንግድ ሚዛን ችግር እንዳለ አያምንም። ስቲትፋንድ (2012 Stitfund Transformative Index) ኢትዮጵያ በተከታታይ የውጭ ንግድ ሚዛን ለማሟላት ያልቻለች መሆኗን አሳይቷል። ከውጭ የምትሸምተው ከሰባት ቢሊዮን ዶላር በላይ ነው። ወደ ውጭ የምትልከው በተከታታይ ከሁለት ቢሊዮን አያልፍም ይላል። ባለፈው አመት መጨረሻ አንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ነበር። ከእልፈቱ በፊት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ " እኛ ኢትዮጵያውያን ምሰሶ (ቁልፍ) የሆኑ የኢኮኖሚ ዘርፎችን ለመያዝ ጥረት ካላደረግንና የአገር ምርት ካላሳደግን አገራችንን እናጣለን" ያለው ልክ ነው። ኢትዮጵያውያን በግል ኢኮኖሚው ሚና ስለሌላቸው በውጭ ንግድና ሽመታ ተመክተዋል። ይህ የንግድ ሚዛን ቀውስ ፈጥሯል። የተጎዳው ተራው ዜጋ ነው። ችግሩ ስርአታዊ ስለሆነ፤ አበው እንደሚሉት "ያልተዘራ አይበቅልም። በብድር ሆነ በታክስ ወይንም በቁጠባ የሚገኘው የመንግሥት ገቢ ከሁሉ በላይ ማተኮር ያለበት ለአብዛኛው ዜጋ ራስን የመቻል እድል መፍጠርና ማመቻቸት ነው። እዳ እየጨመረ፤ ገቢን ለማሳደግና ኑሮን ለማሻሻል ያለው እድል እየቀነሰ፤ የምርት ውጤት እንዳለ እየቆመ ከቀጠለ ኢትዮጵያን ወደ መካከለኛ ገቢ አገሮች እናሸጋግራልን የሚል አመራር በስደተኛው ተማምኖ ነው ወይንስ የማይታይ መካከለኛ ገቢ ያለው መደብ (Invisible Middlle Class) እየፈጠረ ስለሆነ ነው? ብለን መጠየቅ ተገቢ ነው። ሕብረተሰቡ በሁሉ ዘርፎች ካልተሳተፈ አይቻልም።

የጠባብ ጎሰኛነት ቡድን የኢኮኖሚ ጉዳት ገጽታ

በብሄርዊ የማምረት አቅም፤በኢትዮጵያ ዜጎች የገቢና የኑሮ መሻሻል ፍትሃዊነት ያልተደገፈ የውጭና የውስጥ እዳ መሰብሰብ ለህብረተሰቡ ችግር እንደሚያስከትል አሳይተናል። ሌላው መነገር ያለበት ግልጽነትና ተወዳዳሪነት በሌለበት ጎሳዊ ኢኮኖሚ አድልዎ የተፈጠረው ቀውስ (Economic and social distortion) እየተስፋፋ መሄዱ ነው። ለምሳሌ፤ ከሠብአዊ እርዳታ በተገኘ ትንሽ ካፒታል የጀመረው ኤፈርት የተባለው መቶ ድርጅቶች የሚቆጣጠረው የህወሓት ሞኖፖሊ ዛሬ ካፒታሉ ወደ $40 ቢሊዮን እንደደረሰ ይነገራል ።ችግሩ መድረሱ አይደለም። ምን አምርቶ፤ እንዴት ደረሰና ማንን አፍኖ የሚለው ነው። የሚያነጋግረው ይህ ድርጅት በሃያ አንድ አመታት ብሄራዊ የበላይነት የያዘው የፖለቲካ ስልጣን በያዙ፤ የፌደራል መንግሥቱ ባጀትና የእርዳታን ስርጭት በሚወስኑ ባለስልጣናት አማካይነት ነው። የበላይነቱ የተገኘው በራስ የማምረት ስራ ችሎታ፤ በደሞዝ፤ በቤተሰብ ውርስ ወዘተ ካፒታል አይደለም። በቋንቋና በብሄር የተደራጀ የፖለቲካ አመራር የሚያስከትለውን ቀውስ (Crisis) የዓለም ሠብአዊ መብቶች ካውንስል (International Council on Human Rights--The persistence and mutation on racism, 2000) በተባለ በማስረጃ የተደገፈ ጽሁፍ ለተባበሩት መንግስታት አቅርቦ ነበር። "ጠባብ ጎሰኛነት ከዘረኛነት አይለይም። ጠባብ ዘረኛነት ማለት ገቢን፤ የኢኮኖሚ ምሰሶዎችንና የተፈጥሮ ሃብትን ከተገለለው ሕዝብ ወደ ተመረጠው ጎሳ ወይንም ቡድን ማሸጋገር ማለት ነው።" የኢኮኖሚ አመራሩ በምርጥ "ጎሰኞች" ከተያዘ፤ በአብዛኛው፤ ራሱ ከብሮ ሌላውን ደሃ ያደርጋል። የፖለቲካ ስልጣን የያዘው ቡድን የሚፈጠረውን መዛባት በሃይል ያስተዳድረዋል። የገቢና የኑሮ ልዩነት እየሰፋ የሚያመጣውን አደጋ ለማስተናገድ የሚመርጠው የመሳሪይ ሃይል መጠቀም ነው።" ፖል ኮሊየር የተባለው የታወቀ ኢኮኖሚስት በ Understanding Civil War, Volume One: Africa, The World Bank, 2005 የጠባብ ጎሰኛነት አገዛዝ ራሱን የሚያበለጽገው ሌሎችን በማግለል ነው ብሏል። ኢኮኖሚው ካልተሰተካከለ የእርስ በእርስ ጦርነት እንደማይቀር ያስጠነቅቃ። የተገለሉ ክፍሎች "ፍትህ ይፈልጋሉ።" መሬታቸው የተነጠቀ ኑሯቸው ተነጠቀ ማለት ነው። "የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት የያዘው ቡድን አድልዎ ስላየለባቸው ነው።" በራሱ ቃል። "The perception is that the dominant group will seize the opportunity to exploit"....pushing those who are excluded or discriminated "to rebellion...Ethnic polarization, combined with authoritarianism , may increase the risk of civil war." ጎሳ-ተኮር ፌደራሊዝም ለዚህ አደጋ አስተዋጽኦ እያደረገ ነው።

በሌሎች አፍሪካ አገሮች የታየውን የጎሳ ፖለቲካ አደጋ ከሌላ አንጻር ያቀረበው የአሜሪካ "የልቦና ክፍል የሆነው የደህንነት ኤጀንሲ" ነው። ትንተናውና ድምዳሜው ሊያከራክር ይችላል። ሆኖም አሳሳቢ መሆኑን አንጠራጠር። ኢትዮጵያ በ2030 የከሸፈች አገር (Failed State) የመትሆንባቸው ሁኔታዎች እንደተፈጠሩ ነው። እነዚህን ሰብሰብ

አድርገን የችግሮቹን መንስኤዎች እናስቀምጥ። ለአገር መክሸፍ ዋናው ምክንያት የሥብአዊ መብቶች መታፈን ነው። ጎሳ-ተኮር የሆነው ፌደራልዝም ብሄራዊነትንና አብሮ ማደግን ደምስሶ ቀብሮታል። ህወአሓት/ኢህአዴግ በተከታታይ ያደረገው ከብሄር ጥላቻ የተነሳ የስነልቦና ለውጥ ህብረተሰቡን በክሎታል። ለአገሪቱና ለመላው ህብረተሰብ ደህንነት በአንድ ላይ ሆኖ የሚያስብ ተቃዋሚ አልተፈጠረም። ሰብሳቢ የሆነው ለግል ጥቅምና ለጠባብ ጎሰኝነት መደራጀትና መታገል ሆኗል። የፖለቲካ ተቀናቃኞች ያላዩት ወይንም ወደ ጎን የተውት የእርስ በእርስ ግጭት መንስኤ የፖለቲካ ስልጣን ተቀዳሚነት ሆኖ እናየዋለን። ይህ ህብረተሰብ ወለድ አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጎሳና ከኃይማኖት በላይ በማሰብ፤ በምርጫ ዘጠና ሰባት የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ በቃኝ ብሎ በአንድ ድምፅ ለአገሩ ግዛታዊ አንድነትና ለራሱ የኑሮ መሻሻል ቅንጅትንና ህብረትን መርጧል። የገዢውን ፓርቲ አልቀበልም ብሏል። ከዚያ ወዲህ ገዢው ፓርቲ፤ የማህበረሰብና የፕሬስ ነጻነት፤ የህግ የበላይነት፤ የሰብአዊ መብቶች መከበር ፍጹም በሆነ ደረጃ አጥፍቷል። የውጭ አገር መንግስታትና ሌሎች ለጋሶች፤ በተለይ የአሜሪካ መንግስት፤ ለዚህ የብሄራዊነት ናዳ፤ አፈናና የፍትሕ ጥቃት አስተዋጽኦ አድርገዋል። ፀረ-ሽብርተኛነት (Anti-Terrorism)--የመኖር ያለመኖር ጥያቄ--አስፈላጊና ብሄራዊ ግዴታ መሆኑን እንቀበላለን። ኢትዮጵያ የነገይቱ ሶማሊያ፤ ወይንም ሩዋንዳ፤ ወይንም ማሊ፤ ወይንም ናይጀሪያ ወይንም አፍጋኒስታን የመሆን እድሏ ከፍ ያለ ነው። በማህበረሰብ የኑሮ ሁኔታ ሲታይ፤ ጎሳዊው የኢኮኖሚ አመራር ለባለስልጣናት ገቢና ሃብት አዘዋዋሪ ሆኖ ሌሎችን አግልሏል። አብዛኛውን ሕዝብ አበሳጭቶታል። አምባገነኑ ህወሓት/ኢህአዴግ ለፍትህ-ርትዕ፤ ለእውነተኛ እኩልነት፤ ለህግ የበላይነት፤ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ፤ ለሰብአዊ መብቶች ደንታ አያሳይም። በፀረ-ሽብርተኛነት ዘመቻ የአሜሪካን ድጋፍ ተጠቅሞ ራሱ ሽብርተኛ ሆኗል። ፀረ-ሽብርተኛነት ለህወሓት/ኢህአዴግ መቆያና ባለጠጋነት ቁልፍ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል። ይህ መሰረታዊ ችግር ለሰላም፤ አብሮ ለመኖርና አብሮ ለመሻሻል፤ ለእርጋታና ለደህንነት ጠንቅ ነው።

በጠባብ ጎሰኛነት የተደራጀው ህወሓት ከጅምሩ፤በየካቲት 1968 ዓም "የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጭ ድርጅት (ተ.ሃ.ህ.ት)" ብሎ ራሱን የሰየመውና ህወሓት የሆነው ያወጣው የፖለቲካ ፕሮግራም፤ "ትግርኛ ተናጋሪዎች፤ አፋር፤ አገው፤ ሳሆ፤ኩናማ" ወዘተ መሆናቸውን አረጋግጧል። ይህን የጎሳ መስፋፋት እንለዋለን። "የትግራይ መሬት...ወልቃይትንና ፀለምትን እንደሚያጠቃልል" አውጇል። አማራውን ከአማራው የሚያጋጭ፤ መሬቱን ብብሄር ስም የሚያስነጥቅና የኢኮኖሚ ሽባ የሚያደርግ ስልት ነው። ቀጥሎም፤ ዛሬ ለአገሪቱ ህልውና ፈተና የሆነውን "የብሄሮች የራስን እድል ራስ መወሰን--ተጨቋኝ ብሄር ከጨቋኝ ብሄር የፖለቲካ መገንጠል ይችላል ብሎ ማወጁ ነጻ የሆነ የራስ መንግሥት ማቋቋም ማለት" መሆኑን በግልጽ አስቀምጧል። ቡድኑ ስልጣን ከያዘ በኋላ ጎሳ-ተኮር ፌደራሊዝም አቋቁሟል። አንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝ ግዛታዊ አንድነት እንዲዳከምና የህብረተሰቡ ሉአላዊይነት እንዲፈራርስ አድርጎታል። በምእራፍ ሶስት እንዳሳየነው ይህ የአንድ አናሳ ብሄር ቡድን የበላይነት ኤርትራን ከእናት አገሯ አስገንጥሏል። ለመጀመሪያ ጊዜ፤ ኢትዮጵያ የባህር በሯ ተዘግቷል። ደህንነቷ አደጋ ላይ ወድቋል። የኤርትራ መገንጠል ለኢትዮጵያ መበታተን መሰረት ሆኗል። የአሜርካና ሌሎች ተቋሞች ያወጡትን ዘገባ እንይ። በብሄራዊ አደጋ የጀመረ መንግሥት በተከታታይ አደጋን እንደሚፈጥር መረዳት አለብን። ከድህነቱ ዘገባ እርዳታ ሰጭዎች እንዳሳዩት፤ በጠባብ ጎሰኛ ቡድን የሚመራው ብሄራዊ ምዝበራ ጥልቀት ይዟል። ጥቂት የህወሓት/ኢህአዴግ የበላይ አዛዦችና ቤተሰቦቻቸው፤ የስለላና የመከላከያ ባለስልጣናት በሚዘገንን ደረጃ ባለሃብትነት አግኝተዋል። ሃብትና ገንዘብ ይደብቃሉ። ከአገር ያሸሻሉ። ከውጭ ድርጅቶች ጋር ይሻረካሉ። አገሪቱን ለግል ባለጠጋነት የሚጠቀመው ህወሓት/ኢህአዴግ የኢኮኖሚ የበላይነትንና እድሜውን ለመቶ አመታት ለማረጋገጥ በአዲስ ዘዴ ቁልፍ አጋር እየፈጠረበትና የእድገት ምሰሶ የሆኑትን የምርት ክፍሎች ለመከላከያ ሃይሉ በማስረከብ ላይ ይገኛል። የኢኮኖሚ ምሰሶዎችን የተረከበ ሃይል ስንል በሃገርና በህብረተሰቡ ህይወት ላይ ወሳኝ የሆኑ ኢንዱስትሪዎችንና የተፈጥሮ ሃብቶችን (Strategic industries and natural resourcs) መቆጣጠር ማለታችን ነው። ይህ የበላይነት ከትውልድ ወደ ትውልድ ይሸጋገራል። በተከታታይ ትውልድ ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር ያስችላል የሚል ስሌት አለን። አንባቢ እንዲረዳው የምንፈልገው፤ የአገሪቱ ኢኮኖሚ በመከላከያ እዝ ውስጥ እየገባ መሆኑን ነው። ይህ እዝ ጥቅሙን ለማስከበር ስርአቱን እንዳለ ይጠብቃል:: (It is and will continue to be pro-incumbency).

የመለስ እልፈት ለውጥ (reform) ያመጣ ይሆናል ይሉ የነበሩ የውጭና የውስጥ ታዛቢዎች አገዛዙ በግልና በቡድን ጥቅም ላይ የተመሰረተ መሆኑን የዘነጉት ይመስላል። The Economist, February 16, 2013, Ruling Ethiopia: long live the king ያወጣውን እንጋራለን:: ለሃያ አንድ አመታት፤ መለስ ያለውን ትምኅርት፤ ልቦናና ችሎታ ተጠቅሞ አዲስ ኢትዮጵያ፤ አዲስ የፖለቲካ አደረጃጀትና አመራር፤ አዲስ የልማት ፈለግ ፈጥሮ ነበር። ጎሳ-ተኮር ፌደራሊዝም፤ አብዮታዊ ዲሞክራሲና "እድገታዊ መንግሥት" የሚሉ::  አንዱ ከሌላው ጋር የተያያዘ፤ ማእከላዊነትን መሰረት ያደረገ ስርአት ነው። ይህ የአገዛዝ ስልት "እንከን በሌለበት" መልክ ሰርቷል የሚሉ የአገር ውስጥና የውጭ አድናቂዎች እንዳሉ አንክድም። አጼ ኃይለ ሥላሴም ከአምሳ አመታት በላይ ገዝተዋል:: ለመለስ አድናቆት የተሰጠው ኋላ ቀርና ደሃ

የሆነችውን ኢትዮጵያን በፍጥነት አሳድጓታል የሚል ግንዛቤ ስላለ ነው። በመሰረተ ልማት በኩል እድገት እንዳለ ማንም አይክድም። ሆኖም፤ እድገቱ የአብዛኛውን ሕዝብ ኑሮ አልለወጠውም። እድገቱ የተገኘው በመሪዎች እውቀትና ጥራት አይደለም። በውጭ እርዳታ ነው። ኢንቬስትሜንቱ መለስ ብቻውን በተለመው መንገድ ነው። ከአብዛኛው ሕዝብ ኑሮ መሻሻል ጋር ግንኙነት የለውም። የችግሩ መሰረት ይህ ነው። Meles "planned meticulously for everything-from road building to oppressing the opposition-except, that is, for his own demise…he had grabbed so much power that many feared his death would spark political chaos.." ባጭሩ፤ መለስ የመሰረተው አምባገነናዊ ህብረተሰብ ነው። በፖለቲካ ስልጣንና በኢኮኖሚ ጥቅም የተሳሰረ አገዛዝ ፈጥሮ አልፏል። ይህ አገዛዝ በቀላሉ አይፈርስም። ምክንያቱም፤ አዲስ ተጠቃሚዎች ስርአቱ እንዳይፈርስ ማንኛውንም ዘዴ ይጠቀማሉ።

ጋዜጣው ያስተወሰን አምባገነኑ ስርአት አሁንም አምባገነን መሆኑን ነው። "The old guard that once surrounded Meles, who hailed from the northern region of Tigray, remains in power…the Tigrayans have held on to top security jobs…Meles' widwow, Azeb Mesfin…still controls a state-affiliated conglomerate, EFFORT…key posts remain in the hands of ageing loyalists, many of whom fought along side Meles. Talk of "generational change" over the past few years was seemingly a charade…The government is dominated by Tigrayans." The Economist provides the rationale for Hailemariam Desalegn's choice as a successor to Meles; he pre-selected a non-Tigrayan "either to weaken ethnic divisions or perhaps to guarantee that ultimate power remains with his northern brothers-in-arms." በእኛ ግምት፤ የሃይለማሪያም ደሳለኝ መተካት የዲሞክራሲ ጭላንጭል አይደለም። ስርአቱን እንዳለ ለመጠበቅ የታቀደ የአገዛዝ ቀጣይነት ዘዴ ነው። እስካሁን ያየነው፤ አዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር "የመለስን አምልኮ" ተከታይ መሆኑን ነው። የአገሪቱ አበይት የፖለቲካ፤ የማህበረሰብና የኢኮኖሚ ውጥረቶች አይለወጡም። "They govern on autopilot, following the blueprints he left behind. Conformity of thought is common and new ideas are seemingly unwelcome…Meles was so central to the Ethiopian state that his followers are trying to keep him alive with a Mao-style cult of personality." "በመለስ መንፈስ" መመራት አለብን ማለት ማንኛውም ለውጥ አያስፈልግም ማለት ነው። ተቃዋሚ የሆነ ሁሉ የህገመንግሥቱንና የመለስን ራእይ "ይጻረራል" ማለት ነው። ተጻራሪ ከሆነ "ሽብርተኛ" ይሆናል። የአዙሪኙ ፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት ይቀጥላል።

ማን የኃብት የበላይነት ያዘ፤ ምን ማስረጃ አለ?

ኢትዮጵያን ሪቪው (Ethiopian Review, January 19, 2013) አገር ውስጥ ባገኘው መረጃ መሰረት ያቀረበውን ከሌሎች ምርምሮች ጋር በማገናዘብ እንይ። ህወሓት በበላይነት የሚቆጣጠረው የመከላከያ ሃይል፤ በልማት ስም፤ ኢኮኖሚውን ሚሊታሪያዊ በማድረግ ላይ ነው። (The TPLF core is militarization the Ethiopian Economy). ይህ አዲስ የባለጠጋነትና የበላይነት ዘዴ የትግራይ ተወላጅ የሆኑት የጦሩ አዛዦች ከፖለቲካና አዲስ ከበርቴ ከሆኑ ባለጠጋዎች ጋር የጥቅም መረብ ይዘረጋል:: የገዢውን ፓርቲ የበላይነት ጠብቆ፤ የአዲስ ባለ ጠጋዎችን ጥቅም አብሮ ያስከብራል:: በልማት ስም ስለሆነ የምእራብ መንግስታት አይቃወሙትም። የመከላከያ ሃይሉ የአስራ አምስት ኢንዱስትሪዎች ባለቤት ነው። መቶ ፋብሪካዎች ያንቀሳቅሳል። የዚህ አስተባባሪ "ብሪጋዴር ጀኔራል ክንፉ ዳኛቸው" እንደሆነ ያሳያል። ይህ የበላይነት (Monopoly) የጠበበውን የኢኮኖሚ ውድድር በበለጠ ያጠበዋል። አቅም የሌላቸው ታናናሽ አገር ወለድ እንዱስትሪዎች ይጠፋሉ። ለማምረት ፍላጎትና ችሎታ ያላቸው ኢትዮጵያውያን አቅም አይኖራቸውም። ተወዳዳሪነት በጣም ይጎዳል። ገበያው በጥቂቶች ቁጥጥር ስር ወድቋል። አዜብ መስፍን አርባ ቢሊዮን ብር ካፒታል ያለውን ኤፈርትን ማንቀሳቀሷን ትቀጥላለች። ያላቸው ይጨመርላቸዋል። የሌላቸው ድሃ ሆነው ይቆያሉ፤ ወዘተ።

ህወሓት በበላይነት የሚቆጣጠረው፤ ዘጠና በመቶ የሚሆነው (ከላይ ወደ ታች የተዘረጋው) እዝ የትግራይ ተወላጅ የሆነው የመከላከያ ተቋም ወደ ኢኮኖሚው በሰፋትና በጥልቀት ገብቷል። ግልጽነት ስለሌውና ብሄራዊ ውድድር ስለሌበት፤ ለአገሪቱና ለህብረተሰቡ ችግር ይፈጥራል። ዋናው ምክንያት ጦሩ በኢኮኖሚው መሳተፉ አይደለም። በሌሎች አገሮችም ይደረጋል። የኢትዮጵያን አከራካሪ ያደረገው ብሄራዊ አመራር ስለሌለው ነው። የኢትዮጵያን ሕዝብ አይወክልም። እዙ የሚቆጣጠረው ለአገሪቱ እድገት ምሰሶ የሆኑትን ክፍሎች ነው። ደጀን አቪየሽን፤ ቢሾፍቱ ኦቶሞቲቭና ሎኮሞቲቭ፤ ህብረት ማሽን ቱልስ እንጂኔሪንግ፤ ጋፋት አርማሜንት ኢንጂኔሪንግ፤ ኢቲአ ፕላስቲክ፤ ሂተች ኢንዱስትሪያል አንድ ሜታል ፋብሪኬሽን፤ ፖወር እንጂኔሪንግ፤ ናዝሬት ትራክተር አሴምብሊ፤ አዳማ ጋርሜንት ኢንዱስትሪ፤ አስር የስኳር ምርት ፋብሪካዎች (አንዱ ዋልድባ ይሰራል የተባለው)፤ ሁለት የማዳበሪያ ፋብሪካዎች

ወዘተ። የኢትዮጵያ ሕዝብ የእነዚህንና የሌሎች እንዱስትሪዎች ባለቤት መሆን አለበት። ከሁሉም ብሄረሰቦች የተወጣጡ ችሎታ ያላቸው ኢትዮጵያውያን መምራትና ተባብረው በባለቤትነት መያዝ አለባቸው። ይህ ከሆነ፤ ኢንቬስትሜንቱ አያጠያይቅም። የመለስ መንግሥት የኢትዮጵያ ሕዝብ በባለቤትነት ይቆጣጠራቸው የነበሩትን ተቋሞች አጥፍቷል። ዛሬ የመንግሥትና የመከላከያው የበላይነት ያላቸው ኢንዱስሪዎች በአንድ ወገናዊ በሆነ ክፍል ባለቤትነት በማቋቋም ላይ ነው።

ለዚህ ክስተት የተለየ ምክንያት ካለ፤ ለሕዝብ መገለጽ አለበት። አለበለዚያ አደጋው ግልጽ ነው። The merger of military and ethnic elite merger is dangerous for the country. ይህ አዲስ ብሄራዊይነት ከሆነ ከየት መጣ? ለምን? ለማን ጥቅም? ተመልካቾች "የመለስ አምልኮ" አመራር ሲቀጥል ተጨማሪ ኃብት ለማካበት የሚችሉት ከፖለቲካ ስልጣን ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያላቸው ናቸው ይላሉ። የሚሊታሪ እዙን የኢኮኖሚ ተሳትፎ ከግል ጥቅም ውጭ ለማየት የሚያስቸግረው ለዚህ ነው።

በህወሓት አመራር የወሬና ተግባር ልዩነት አለ

ህወሕት ባወጣው የመጀመሪያ እቅድ ያለውን እንይ። "ነጻ ብሄራዊ ኢኮኖሚ ማቆም፤ የመሬት ይዞታውን ሥርዓት ማስተካከልና ከበርቴያዊ ምርት ተቆጣጥሮ የምርት ሃይሎችን በህብረተሰቡ ቁጥጥር ሥር ማድረግ። መሰረታዊ ችግሮችን፤ ማለትም፤ መሃይምነትን፤ ረሃብን፤ በሽታን፤ የኑሮ ውድነትን፤ ስራ አጥነትን ወዘተ" የሚያስወግድ የኢኮኖሚ አመራር መፍጠር የሚሉ ነበሩበት። ባለፉት ሃያ አንድ አመታት እየታየ የመጣው፤"ብሄራዊ ኢኮኖሚ ማቆምና ከበርቴያዊ ምርት መቆጣጠር" ማለት ለህወሓትና ተጠቃሚ ለሆኑ የኢህአዴግ የበላዮችና ቤተሰቦቻቸው ማለት መሆኑ አያጠራጥርም። ሁሉም የሚደረገው በልማት ስም ነው። የመከላከያ የበላዮች በኢኮኖሚው ላይ ያላቸው ሚና ታስቦበት፤ የአገሪቱን የገንዘብና የተፈጥሮ ሃብት ለማሸጋገር ነው። ይህ ሲሆን ህወሓት የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነቱን ለተከታታይ አመታትና ትውልድ ያስተላልፋል። በአንጻሩ የምንከራከረው፤ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ከመሰረታዊ ችግሮች ሊላቀቅ የሚችልበት የልማት መንገድ ከህወሓት/ኢህአዴግ እቅድ የተለየ መሆኑን ነው። የእድገት ሊቆች የሚቀበሉት ፍትሃዊ የሆነ የልማት መንገድ ከጥቂቶች ባለጠጋነት የተለየ ነው። ህብረተሰቡ በመንግሥቱና በራሱ፤ አገራዊ በሆነ ደረጃ መተማመንና መጠቃቀም መኖሩ ሲታይ ነው። የተፈጥሮና ሌላ ቁሳቁስ ባለቤትነት የእድገት መለኪያ ከመሆኑም በላይ የማንነትና የዜግነት መለኪያ ነው። ባለቤትነት በህግ ያልታወቀ ከሆነ ዜግነት ትርጉም ያጣል። ህወሓት/ኢህአዴግ ባለቤትነትን ከራሱና ከበላዮች ውጭ በረቀቀ ዘዴ እያጠፋ ነው። የመንግሥት ሚና ከላይ ሆኖ የተፈጥሮ ሃብትንና የማምረቻ ሃይሎችን በፈለገው ሁኔታ ለመረጠው ብቻ ካስተላለፈ አብዛኛው ኑሮውን የማሻሻል እድሉ የተወሰነ ይሆናል። የህግ የበላይነት ባለበት አገር የገቢ፤የባለጠጋነት፤ የከፍተኛ ትምሕርትና የስራ እድል ወዘተ እኩልነት ህጋዊ ነው። በኢትዮጵያ ይህ መሰረታዊ የባለጠጋነት (Wealth and Wellbeing) መብት በህግ የተከበረ አይደለም። የሕግ የበላይነትና ለትምሕርት ያለው ፍትሃዊ እድል ለባለጠጋነት፤ ለኑሮ መሻሻል፤ ለገቢ እድገት ወሳኝ ነው።

የልማት ትብብር ወይንስ የልማት ማነቆ?

የፖል ኮሊየር ጥናት በሌሎች አገሮች እንዳሳየው ስብጥር ሕዝብ (In diverse societies) ባለበት አገር በቋንቋና ጎሳ የተመሰረተ የሃብት ምዝበራ ግጭት መፍጠሩ አይቀርም። ምክንያቱም፤ አገዛዙ የልማት ትብብርን (Social and Economic Solidarity) በማጠናከር ፋንታ፤ የበላዮች ምዝበራን (Elite Economic Capture) አጠናክሯል። አገዛዙ የፖለቲካ የበላይነቱን ተጠቅሞ የተፈጥሮ ሃብት ወገናዊ በሆነ መንገድ ለጥቂቶች አስተላልፏል። ከአጀማመሩ የጎንደርን፤ የወሎን፤ የጎጃምን ለም መሬት ለራሱ ክልልና ለሌሎች መስጠቱ መሰረታዊ ችግር ፈጥሯል። ለተወሰደበት ህብረተሰብ አማራጭ ነስቶታል። ፈለጉን ተከትሎና በልማት ስም፤ በጋምቤላ፤ በቤኒ-ሻንጉል-ጉሙዝ፤ በደቡብ ኦሞ፤ በደቡብ ክልል፤ በአማራ፤ በኦሮሚያ ለም መሬትና ወንዝ ከሰላሳ ስድስት አገሮች ለመጡ የውጭ ኢንቬስተሮች አስተላልፏል። በውስጥ ከተመሩት ኢትዮጵያውያን ሰባ አምስት በመቶ የትግራይ ተወላጆች ናቸው። ይህ ግጭትን ጠባብ ጎሰኛነትን ወይንም ዘረኛነትን ያመለክታል። ፖሊሲው ግጭት ፈጥሯል። የኢትዮጵያን ለም መሬትና ወንዞች ለሰሜን ሱዳን መንግስት በምስጢር አስተላልፏል። አድሏዊይነቱ በኃይማኖት ዙሪያም ተከስቷል። ከጅምሩ የህወሓት አመራር ፈጽሞ ለማጥቃት የሚፈልጋቸውን ብሄራዊ ተቋሞችና የተቀናቃኝ ክፍሎች በሁሉም መልክ፤ ግልጽ ባልሆነና ግልጽ በሆነ መንገድ አፍኗቸዋል። አንዳንዶቹን ፈጽሞ አጥፍቷቸዋል። (Socio-economic strangulation).

በጠቅላላው ሲታይ፤ ህወሓት በበላይነት የሚቆጣጠረው ስርአትና መንግሥት፤ በማንኛውም የህብረተሰብ ኑሮና ህይወት መሰረታዊ የሆኑ (Systemic) ችግሮች ፈጥሯል። አጋርና ደጋፊ የሆነው የአሜሪካ መንግስት ተቋም "የኢትዮጵያ መክሸፍ" እየተጠናከረ ነው ብሎ አደጋውን አስምሮበታል። ሃላፊነት የሚሰማው አመራር ቢኖር ራሱን ገምግሞ ሁሉን

ለሚያሳትፍ ዲሞክራሳዊ አገዛዝ በር ይከፍት ነበር። ግትርነቱ በግልጽ ይታያል። አገዛዙ እየተሻሻለ ሄዷል ወይንም ሊሄድ ይችላል የሚሉ አሉ። ይህን ሲሉ ለጥቂቶች ታይቶ የማይታወቅ ባለጠጋነትንና ከዚህ ጋር አብሮ የሚሄድ የበላይነትን ጡንቻ ያበረከተው የኢኮኖሚ ፈለግ ቀስ በቀስ ወደ ተራው ሰው ይወርዳል በሚል ተስፋ ነው። (Trickle down economics). ዓለም ባንክ እንዳሳሰበው፤ ተራው ዜጋ የሚጠይቀውን ባለስልጣናትና ደጋፊዎች አያዳምጡም። ከኑሮው ብሶት እንየው። አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ በቀን ሶስት ጊዜ ሙብላት እንደ ቅንጦት መቁጠር ከጀመረ ቆይቷል። በድሎት የምንኖረው ስደተኞች ማጤን ያለብን በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ቢጨንቃቸው ቁርስና ምሳን ደርበው "ቁምሳ" የሚል ቃል ፈጥረውለታል። በብዙ ሙቶ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን፤ በተለይ ወጣቶች የመግዛት አቅም ስለሌላቸው ከምግብ ቤቶች የሚጣለውን ምግብ እየለቀሙ ይበላሉ። ገቢያቸው ዝቅተኛ የሆኑ ኢትዮጵያውያን አንድ ጉርሻ ገዝተው በልተው ያድራሉ። በማንኛውም መለኪያ ብናየው፤ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ "ተአምራዊ እድገት ባስመዘገበችው ኢትዮጵያ" ችግሩ በርትቶበታል።

በተለይ አሳሳቢ የሆነው፤ አዲሱ ትውልድ "ነገን" የሚመለከተው እንደ እድል መለወጫ አለመሆኑ ነው። እንደማይበገር ጨለማ ነው። ነገ ብርሃን ይሆናል ብሎ ለማሰብ የተሳነው አዲስ ትውልድ ኑሮውን ለማሻሻል አይችልም። እድሉ ወደ ውጭ መሰደድ መሆኑን ያምንበታል። ስለሚሰደድ፤ ራሱን ጎድቶ አገሩንም ይጎዳል። በዚህ መጽሃፍ ደጋግመን በማስረጃ ያቀረብነው ግንዛቤ የውጭ አገሮችና ድርጅቶች የእርዳታ "ደሃ" የነበረውን የደርግንና የእርዳታ "ሃብታም" የሆነውን፤ አፍሪካ ውስጥ ተወዳዳሪ የሌለውን፤ የህወሓት/ኢህአዴግ አመራር ማወዳደር አይደለም። መሆንም የለበትም። ሁለቱ የተለያዩ መሆናቸውን አሳይተናል። ለማነጻፀር የምንገደደው፤ በህወሓቷ ኢትዮጵያና በሌሎች ቀጣይነት ያለው እድገት በሚያሳዩ የአፍሪካ አገሮች መካከል ያለውን የኑሮ ልዩነት ነው።ጋናን እንደ ምሳሌ አቅርበናል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሙብላት ላለሙብላት፤ ሰርቶ ለማደር ወይንም ለመሰደድ ዋናው መነሻው የኢኮኖሚው መዋቅሩ ጠባብ፤ ጎሰኛ፤ አድሏዊና ሙሰኛ መሆኑ ነው። አገዛዙ የሚያገለግለው ራሱን ነው። ስለዚህ፤ ቁልፉ መፍትሄ ሰብአዊ መብቶችን፤ ፍትህን በህግ የሚያስከብር የፖለቲካ ለውጥ ነው። የሁሉን ጥቅም የሚያስተናግድ ዲሞክራሳዊ አማራጭ ከተመሰረተ፤ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ታላቅና ሃብታም የሆነ ህብረተሰብ ለመመስረት እነደምትችል አንጠራጠርም።

የእድገት ጥርጣሬ ለምን መጣ?

ቀጥተኛ መልሱ እድገት ጥርጣሬ ከፈጠረ ቆይቷል ነው። ልክ በሌሎች የአፍሪካ አገሮች እንደሚታየው፤ በኢትዮጵያም እድገት መኖሩ አያከራክርም ብለናል። ዓለም ባንክ፤ አይኤምኤፍ፤ ጎልድማን ሳክስ፤ የአፍሪካ ልማት ባንክ፤ ዕርንስት ያንግና ሌሎች አፍሪካ በፍጥነት ከሚያድጉ አህጉሮች ቀደምተኛ ሆናለች ሲሉ ቆይተዋል። የተፈጥሮ ሃብት--ማእደን፤ ዘይት፤ ለም የእርሻ መሬት ወዘተ--ያሏት ኋላ ቀር አህጉር እድገት ማሳየቷ ደስ የሚያሰኝ ነው። ኢትዮጵያ ከእነዚህ በፍጥነት በማደግ ላይ ካሉ የተለየ የአብዛኛውን ሕዝብ ህይወት ለዋጭ እድገት አላሳየችም። ብታሳይ ሁላችንም እንደሰታለን። በአጠቃላይ ሲታይ፤ በመሰረተ ልማት የተደረገው እንቅስቃሴ ሊታበል አይችልም። መንገድ፤ ግድብ፤ ትምሕርት ቤቶች፤ የጤና ጣቢያዎች በብዛት ተሰርተዋል። ቤቶች፤ ቪላዎች፤ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች፤ ሆቴሎች፤ የምግብ መገልገያዎች፤ ከተሞች፤ ወዘተ ተስፋፍተዋል። ይህ እድገት ብቻውን ተለይቶ ሲታይ አስደናቂና ታይቶ የማይታወቅ ይመስላል። ጠለቅ ብሎ ሲያዩት ለአብዛኛው ያመጣው ጥቅም ባዶ ሆኖ ይገኛል። በአገር ደረጃ መዋቅራዊ ለውጥ አለመኖሩን ያመለክታል። ገዢው ፓርቲና ደጋፊዎቹ የሚሉት ከዚህ የተለየ ነው። በጥናት የተገኘው ጥቅስ እንደሚያመለክተው፤ ከሁሉ በላይ ተጠቃሚ የሆኑት የጎሳ የበላዮች ናቸው። ሚዛናዊ ትንተና ለማድረግ በመጀመሪያ ህወሓት/ኢህአዴና ደጋፊዎች የሚጠቅሱትን የእድገት መለኪያ እንመርምር። ለዚህ መመዘኛና መለኪያ ያስፈልጋል። ደህንነትና ፀጥታ፤ የሕግ የበላይነት፤ ግልፅነትና ሙስና፤ ሕዝባዊ ተሳትፎና ሰብዓዊ መብቶች መከበር፤ ቀጣይነትና ፍትሃዊነት ያለው የኢኮኖሚ እድል፤ ሰብዓዊ ልማት (Human Development)፤ ጤናና ንፅህና፤ የትምሕርት እድልና ጥራት የገኙበታል። ሞ-ኢብራሂም፤ አክሶፎርድ ዩኒቨርስቲ፤ የተባበሩት መንግስታት የእድገት ፕሮግራም፤ ወርልድ ፒስ ፋውንዴሽንና ሌሎች በተለያየ መንገድ የሚጠቀሙት እነዚህን ከሠብዓዊ ህይወት መሻሻል ጋር የተያያዙ የእድገት መለኪያዎች ነው። ከእነዚህ በተለይ ለአርአስቱ አግባብ ያለው የታወቀው ሱዳናዊ ባለጠጋ ያቋቋመው በስሙ የሚጠራው የሞ-ኢብራሂም ተቋም የአፍሪካ መንግስታት የአገዛዝ መለኪያ ነው። ዘገባው ሁሉን የአፍርካ መንግስታት ወስዶ ከአመት አመት የሚያድርጉትን የአገዛዝ መሻሻል ይለካል። ከፍተኛና አርአያ የሆነ ውጤት በተከታታይ ያሳየ መሪ/መሪዎች ልዩ ሽልማት ይሰጠዋል። ተቋሙ በየጊዜው አጣዳፊና ፖሊሲ ነክ በሆኑ ሁሉን የአፍሪካ መንግስታት በሚመለከቱ አርእስቶች ጥልቀት ያለው ጥናት ያካሂዳል። በመላው አፍሪካ ህብረተሰብ <u>ለዋጭ ከሆኑት ሂደቶች መካከል ( Transformative Trends) የወጣቱ ትውልድ እየተማረና እያደገ መሄድ ነው።</u> በ2012 ትኩረት የተሰጠው የአፍሪካ ወጣት ትውልድ ነበር። ጥናቱ ሲያመድም፤ "የአፍሪካ ወጣት ትውልድ ካለፈው ትውልድ የበለጠ ትምህርት አለው።

ነገር ግን የገቢውና የኑሮው ሁኔታ ሲመረመር ከወላጆቹ ያነሰ ነው።” ተቋሙ አደጋውን በመገመት ለመንግስታት ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል። የኢቶጵያን ወጣት ትውልድ ሁኔታ እንደሚገልጽ ከላይ በቀረበው አንረዳለን።

የገዢው ፓርቲና ደጋፊዎች የእድገት መለኪያዎች

በመሰረተ ልማት ሰፊ ለውጥ እንዳለ ተቀብለናል። ገዢው ፓርቲና ደጋፊዎች የሚሉት ከመሰረተ ልማት በላይ ህይወት ለዋጭ እድገት ይታያል ነው። ለአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ እድገቱ የተሻሻለ የህይወት ለውጥ እንዳላመጣ አሳይተናል። የገዢውን ፓርቲ ማስረጃዎች ቀረብ ብሎ ማየት ተገቢ ነው። አይኤምኤፍና ዓለም ባንክ መስክረውልናል የሚል ማሳመኛ ሲቀርብ-- እስከምናውቀው ድረስ እነዚህ ድርጅቶች የሚደግፉት መንግሥታትን ነው--የዓለም ባንክ ዘገባ እንዳሳየው፤ ለጋሶች ነጻ በሆነ መንገድ፤ ማህበረሰቦችን፤ ደሃውን፤ ተራውን ዜጋ፤ ተቃዋሚዎችን ጠይቀው ማስረጃ አቅርበው አያውቁም። ለጋሶችና አበዳሪዎች እንደመሆናቸው መጠን የሰጡትን ገንዘብ ጥቅም ለማሳየት የመንግሥት ማስረጃ መጠቅምና የሚለውን ማስተጋባት ግዴታ ሆኖባቸዋል። ቱኒዚያና ግብጽ፤ ፊሊፒንስና ችሌ ወዘተ ያደርጉት የነበረው ተመሳሳይ ነው። ለአይቮሪ ኮስት መንግሥት “እድገታዊ አመራር” አድናቆት ሰጥተው ነበር። ሙስና እየባሰ ሲሄድ አማካሪ (ኮንሰልታንት) ቀጥረው ዘገባ እንደሚያደርጉ እናውቃለን። በአብዛኛው የመንግሥት ድክመቶች ሲያዩ በውስጥ ይነጋገራሉ አንጅ የመንግሥቱን አመራር በይፋ አይገስጹም። በልዩ ልዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች ነጻ ጥናት እንደሚያካሂዱ አንጠራጠርም። ጥናቱ ወደ ፖሊሲ አልተለወጠም። መንግሥት የሚያወጣው መረጃ ሙልጭ ያለ ውሸት ሆኖ ሲያገኙት ራሳቸውም እንዳይዋረዱ ችግሩን ለዓለም ያስታውቃሉ። ልክ አይኤምኤፍ ስለ ኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሬ እጥረት እንዳሳሰበው። የዓለም ባንክ ዲሬክተት ኬን ኦሃሺ ስለ ህወሓት የኢኮኖሚ መማረክ/ነጥቆ መውሰድና (Elite Economic Capture)ና ስለፓርቲው የበላይነት አደጋ ፤ ስለግል ክፍሉ መታፈን ወዘተ እንደገለጸው ፖሊሲው ከቀጠለ ኢትዮጵያ እንደ ምስራቅ ኤዢያ ያለ ልማት ለመጎናጸፍ አትችልም። ይህን ድምዳሜ እንጋራለን። ለጋሶች በሁለት አፍ የሚናገሩትን አባባል ሲደጋግሙና በተግባር እርዳታ ያለምንም ቁጥጥር ሲለግሱ እውነተኛ አላማቸው “ድህነትን ማጥፋት” መሆኑን ከጥርጣሬ ውስጥ ያስገባል። ታዛቢዎች ለጋሶች ታማኝ ምስክሮች ለመሆን አይችሉም የሚሉበት ለዚህ ነው። ዓለም ባንክ በአንድ በኩል “የፖለቲካው ስርአት ለቀጣይ እድገት ማነቆ” ሆኗል አለ። በሌላ በኩል ምንም የፖለቲካ ለውጥ ሳይታይ ድጋፉን አስፋፋ። የእንግሊዝ መንግሥት ሙስና እንዳለ ተቀብሏል። እርዳታውን አላቆመም ወይንም ዘዴውን አልለወጡም። የአሜሪካ ተራድኦ ድርጅት ለመሬት ነጠቃ ድጋፍ ሰጥቷል። ነዋሪዎች ከመሬታቸው እንዲወገዱ ደግፏል የሚል ወቀሳ ደርሶበታል። ባጭሩ፤ ለጋሶች ያጠናከሩት ግፈኛውን መንግሥት ነው የምንለው ለዚህ ነው። መንግሥትና ደጋፊዎቹ ቢያንስ ሶስት የእድገት መስፈርቶች አሉ ብለው የሚከራከሩባቸው ሃሳቦች አሉ።

አንድ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ባጀት እያደገ ሂዷል የሚል። ባጀት እያደገ መሄዱ አያከራክርም። አንባቢው መገንዘብ ያለበት፤ ባጀቱ የጨመረው ቁጠባ እያደገ ስለሄደ፤ አገር ወለድ ከበርቴዎች እየተስፋፉ ስለሄዱ፤ መንግሥት ከህብረተሰቡ የሚሰበስበው ታክስ የልማት ፍላጎትን ለማሟላት ስለቻለ፤ ወጣቱ ስራ ስላገኘ ወዘተ አይደለም። ህወሓት ደርግ በአስራ ሰባት አመታት ያገኘውን እርዳታ አሁን በአንድ አመት ስላገኘና ባንኮችን ተቆጣጥሮ ገንዘብ ለማተምና ብድር ለማግኘት ስለቻለ ጭምር ነው። ስደተኛ ከፍተኛ አስተዋፆ እንደሚያደርግ አመልክተናል። ህወሓት የሚቆጣጠረው መንግሥት ስልጣን ከያዘበት ወቅት ጀምሮ አብዛኛው ለእድገት የሚውለው ፈሰስ የሚገኘው ከውጭ እርዳታ ነው። እድገቱ በብድርና በለጋሶች ድጋፍ የተገኘ ነው።  ስደተኛው ለፍጆት ኢኮኖሚው ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ ነው። ቤት ይሰራል፤ ቱሪስት ሆኖ ብዙ መቶ ሚሊዮን ብር ያወጣል። የውጭ ምንዛሬ ይልካል። በንጥር ሲታይ፤ ስደተኛው የሚልከው ገንዘብ ከአመት ወደ አመት እያደገ ከእርዳታ ከሚገኘው በልጧል። በዓለም ባንክ ዘገባ ባለፈው አመት አራት ቢሊዮን ዶላር ደርሷል። ገዢው መንግሥት የብር ዋጋን በተከታታይ ቀንሶ የብር ጥቅም ከመቸውም እየቀነሰ ሄዷል። ባንኮችን እንደላም ማለብ ከጀመረ ቆይቷል። ብሄራዊ ባንክ ገንዘብ እያተመ የመንግሥት ባጀት ማሟያ ሆኗል። ከሃምሌ 1, 1998 እስከ ሰኔ 30, 1999 ዓም ብቻ መንግሥት 23.2 ቢሊዮን ዶላር ከእርዳታና ከብድር አግኝቷል። አስራ ስድስት ቢሊዮን ብር በስጦታ የተገኘ ነው። ከዚያ ወዲህ መንግሥት በአመት የሚያገኘው እርዳታና ብድር በሚያስደንቅ ሁኔታ ጨምሯል። ባለፈው አመት አራት ቢሊዮን ዶላር ወይንም ሰባ ሁለት ቢሊዮን ብር ደርሷል። የውስጥ እዳ ስድሳ ቢሊዮን ብር ደርሷል። በእኛ ግምት፤ የኢትዮጵያ ችግር የገንዘብ ማነስ አይደለም። የአገዛዝ ግፍ (Tyranny) ነው። ያለፉት ሃያ ሶስት አመታት የሚያሳዩን ገንዘብ ብቻውን የዘላቂነትና ፍትሃዊ ልማት ወሳኝ (Massive pouring of foreign aid and deficit financing is not a determinant of sustainable and equitable development in Ethiopia) አለመሆኑን ነው።

ሁለት፤ ኢትዮጵያ የሚያስደንቅ እድገት አስመዝግባለች የሚል ነው። የመሰረተ ልማት እድገት እንዳለ ተቀብለናል። የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት ካለፉት መንግሥታትና ከሌሎች በፍጥነት ካደጉ አገሮች የሚለየው ኢትዮጵያ እድገቷን የምትደግፈው ወደ ውጭ ገበያ ልካ በምታገኘው የውጭ ምንዛሬ ወይንም ከቁጠባ በሚገኝ ካፒታል አይደለም። በሁሉም የመሰረተ ልማት ዘርፎች የምትመካው ከውጭ በሚገኝ፤ መንግሥት በሙሉ በሚቆጣጠረው እርዳታ ነው። ለጋሶች ገንዘብ የሚሰጡት በቀጥታ ለመንግሥት ነው። (The money is fungible and can be used in any manner the party chooses). የፌደራሉ አስተዳደር ገንዘቡን እንደፈለገ ያሰራጨዋል። ነጻ የሆነ እንባ ጠባቂ የለም። ገንዘቡ ወደ የትና ለምን እንደዋለ ለማወቅ ያስቸግራል። መንግሥት ያለውን መቀበል አስፈላጊ ነው። የምናውቀው በለጋሶች የተደገፈው የእድገት ባጀት ከአመት ወደ አመት እያደገ መሄዱን ነው። ማደጉ ምንም አይደል እንበል። መጠየቅ ያለብን የአብዛኛው ሕዝብ ኑሮ ለምን አልተሻሻለምና የአገሪቱ የምርት ሃይሎች ለምን በፍጥነት አላደጉም ነው። የዛሬ ሶስት አመት ኢኮኖሚስት በትክክል ያስቀመጠውን "ከብዙ ቢሊዮን ዶላር እርዳታ በኋላ ኢትዮጵያ ከዛሬ ሃያ አመታት በፊት ከነበረችበት የድህነት አዙሪኝ ነጻ አልወጣችም። ኢህአዴግ አስመዘገብኩት የሚለው ድርብ የሆነ የኢኮኖሚ እድገት የሕዝቡን ከቀን ወደ ቀን የሚታይ የኑሮ ቁልቁለት አልለወጠውም። የተራው ዜጋ ሕይወትና ልክ ያጣው የዋጋ ግሽበት ተጨባጭነቱን ወትሮውንም ጥያቄ ውስጥ አስገብቶታል።" በአዲስ አበባ ከሚታየው "የፍጆት እድገት ከብልጭልጭ በላይ የተራውን ሰው ህይወት ለውጦ አናየውም።" ሁሉን የሚያሳትፍ፤ በሕግ የበላይነት የተመሰረተ የአገዛዝ አማራጭ ከሌለ አብዛኛው እርዳታና አገር ውስጥ በልማት ስም የሚገኘው ብድር፤ በአብዛኛው፤ የጥቂቶች መክበሪያ ሆኗል።

ሶስት፤ የገዢው ፓርቲና ደጋፊዎቹ ነጥብ ፍትሃዊ እድገት የለም እያሉ "ታላቁን የለውጥ ሃዋርያ" መለስን የሚተቹትን ይመለከታል። ደጋግሞ ከዋሸ ውሸቱ እውነት የሚመስለው አመራርና ደጋፊዎቹ፤ ሂስ አቅራቢ ለሆኑ የውጭና የአገር ተቆርቋሪዎችን ስም ያወጡላቸዋል። "የኢሰፓ ርዝራዦች፤ የአጼ ኃይለ ሥላሴ ስርአት ናፋቂዎች፤ የአማራ ትምክህተኞች፤ የሻቢያ ቅጥረኞች፤ የሊበራል ዲሞክራሲ ተላላኪዎች፤ ሽብርተኞች" የሚሉ። ህወሓትን የሚቃወሙ ሁሉ እድገት መኖሩን ይክዳሉ የሚል ነው። ማስረጃው የሚያመለክተው ስድቡ ሃቁን ሊሸፍነው እንደማይችል ነው። ለመካድ የማንችለው የተራውን ኢትዮጵያዊ የኑሮ ሁኔታ ነው። የዓለም ባንክ የውስጥ ዘገባ፤ የሞ-ኢብራሂም ፋውንዴሽን፤ የተባበሩት መንግስታት የእድገት ድርጅት ወዘተ፤ ወዘተ የማንም አቀንቃኝ ድርጅቶች አይደሉም። ህወሓት ሆነ ተቃዋሚው በገንዘብ ሊገዛቸው አይችልም። አንባቢው ማጤን ያለበት፤ ስደተኛው በዚች የመጨረሻ ደሃ አገር "የመጠሪያ ሆነ የግል ቤት" መስሪያ መሬት ለመከራየት ወይንም ለመግዛትና ለመስራት መቻሉ የአብዛኛውን ሕዝብ አሰቃቂ ኑሮ ሊፈርጀው አይችልም። በ Whiteman's Burden፤ የታወቀው አሜሪካዊ ኢኮኖሚስት፤ ቢል ኢስተርሊ ስለ ኢትዮጵያ ፍጹም ደሃነት ያለውን እንጨምር። "ከአዲስ አበባ ወጥቼ ስመለስ፤ እድሜያቸው ከዘጠኝ እስከ አምሳ ዘጠኝ የሚሆኑ ወጣትና እናት ሴቶች ወገባቸው በማገዶ እንጭት ሸክም ክብደት ታጥፎ፤ ልክ ከኋላ ሆኖ "የማይታይ ባሪያ ነጅ" እንደሚያዛቸው ሲጓዙ የኢትዮጵያን ሕዝብ ደሃነትና ምስኪንነት አስከፊነት አሳይቶኛል። እኔ ይህን ጉድ እያየሁ ስሄድ፤ ሌሎች ፈረንጆች የደሃነቱን አስከፊነት አይተው ወደሚያድሩብት ሆቴል ተመልሰው ክፍላቸው ገብተው አልቅሰዋል።" ኤስተርሊ "የማይታይ ባሪያ ነጅ" ያለው አሰከፊውን ደሃነት (Utter deprivation and poverty) ነው። ባርነት በኢትዮጵያ ጠፋቷል። በተከታታይ፤ በፍጹም ደሃነት መኖር ከዱሮው ባርነት አይለይም። በብዙ መቶ ሺ የሚቆጠሩ ሴቶች ወደ አረብ አገሮች ተሰደዋል። አሁንም ይሰደዳሉ። በተለይ ወጣት ሴቶች የሚኖሩበት ሁኔታ "ዘመናዊ ባርነት ነው"። ለዚህ "ዘመናዊ ባርነት" የዳረጋቸው በአገራቸው የመስራትና የመኖር እድል አለመኖር ነው። የሰብአዊ መብቶች አፈና ለዚህ መጋቢና አጠናካሪ ነው። ህጻናት ለውጭ አገር ልጅ ፈላጊዎች በኮሚሽን የሚሰጡት ወላጆቻቸው ደሃ ስለሆኑ ነው። ፍትሃዊ እድገት ቢኖር እነዚህ የዘመኑ "ባርነት" መግለጫዎች ከኢትዮጵያ ምድር ይጠፉ ነበር። በአብዛኛው ኢትዮጵያ የሚታየው እውነተኛ ገጽታ የማህበረሰብ ችግሮች እየተስፋፉና ጥልቀት እየያዙ መሄዳቸውን፤ የተማረውና የሰለጠነው የሰው ኃይል በገፍ የሚሰደድ መሆኑን ነው።

ምእራፍ ስድስት የጠባብ ጎሰኛ አገዛዝ የፈጠረውን ስርአት ወለድና ሁለ-ገብ ሙስና ያቀርባል። ዋናው መሰረተ ሃሳብ፤ አምባገነናዊው አገዛዝ የህብረተሰቡን ባህል፤ ስነምግባርና ግንኙነት በክሎታል የሚል ነው። ስር የሰደደ ከጠባብ ጎሰኛነት ጋር የተያያዘ የእድል አድልዎ፤ የአስተዳደር ብልግና፤ ሌብነት፤ ጉቦና ሙስና አደገኛ በሆነ ደረጃ መዋቅራዊና ተቋማዊ ሆነዋል። ይኼ ለሃገር ሰላምና እርጋታ፤ ለብሄራዊ አንድነት፤ ለአብዛኛው ሕዝብ ኑሮ መሻሻል ማነቆ ሆኗል።

# ምእራፍ ስድስት

## በደሃነት የተሸመተ ሁለ-ገብ ሙስና

“እኛ እንደፈለግን እንዳንሰርቅ፤ እንደፈለግነው ሙብት እንዳናፍን፤ በሌላ አነጋገር አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ባህሪያችንን እንድናጠፋ ቀፍድዶ የሚይዘን ሃይል የለም”

መለስ ዜናዊ

“እአአ በ2009 ብቻ፤ ኢትዮጵያ ሶስት ቢሊዮን ሶስት መቶ ሚሊዮን ዶላር ተሰርቆባታል። በድምሩ አገሪቱ በተባለው አመት ለልማት የደረሳት ከእርዳታና ወደ ውጭ ከሚላክ ያገኘችው የውጭ ምንዛሬ ተሰርቆ ሸሽቷል ማለት ነው”

ጃነስ ዊይንተር፤ the Daily Maverick

“የኢትዮጵያ ሕዝብ በራሱ መንግሥት እየደማ ነው። የፈለግውን ያህል “ከፍጹም ምስኪንነትና ደሃነት” አዙሪኝ ነጻ ለመውጣት ቢሰራና ቢታገልም፤ ወደላይ እንደ መዋኘት ሆኖበታል። የገጠመው ማእበል ከህግ ውጭ የሚዘረፈውና የሚሸሸው ገንዘብ (ካፒታል) ነው።” (The people of Ethiopia are being bled dry. No matter how hard they try to fight their way out of absolute destitution and povety, they will be swimming upstream against the current of illicit capital leakage”

Global Financial Integrity

“ኢትዮጵያ በዓለም ከፍተኛ እርዳታ ከሚለገሳቸው አገሮች መካከል አንዷ ናት። በአፍሪካ የመጀመሪያውን ደረጃ ይዛ ቆይታለች። ሆኖም፤ ከኢትዮጵያ ሕዝብ አምሳ በመቶው በቀን የሚያገኘው ለኑሮ አስፈላጊ ነው ተብሎ ከተገመተው ከአንድ ዶላር ከሃያ አምስት ሳንቲም በታች ነው። ለመንግሥት በቀጥታ የሚሰጠው የገንዘብ እርዳታ የሚደግፈው የአንድ ፓርቲ የበላይነትን ነው። ገዢው ፓርቲ እርዳታውን የቁጥጥር መሳሪያ አድርጎታል”

Human Rights Watch: Development without Freedom, October, 2010

### ሙስና ምንድን ነው፤ ጉዳቱ ከየት ይመጣል?

በዚህ መጽሃፍ የተጠቀምንበት የሙስና ትርጉም ሰፊ ነው። ምክንያቱም፤ የህወሓት/ኢህአዴግ ሙስና ሁለ-ገብ ነው። የፖለቲካ ስልጣን የበላይነትን ለማጠናከር የሚደረግ የምርጫዎች ማጭበርበርና ተቃዋሚዎችን ማፈን፤ ጋዜጠኞችንና የሰብ አዊ ሙብት ጠበቃዎችን ምስረጃ ፈጥሮ ማሰርና ማሳደድ፤ የፀረ-ሺብርተኞች መከላከያና የማህበረሰብ (ሲቪል ድርጅቶች) ማቀቢያ ሕጎችን አውጥቶ ሠብአዊ ሙብቶችን በማያሻማ መልክ ማፈን፤ የክልል አስተዳደርን ተጠቅሞ የጎጠኞች ባለጠጋነት ማጠናከር በጎጠኛ፤ አስተዳደርን ተጠቅሞ ጉቦ፤ አድልዎና ሙስኛነትን ተቋማዊ ማድረግ፤ በልማት ስም የነዋሪዎችን ሙብት መግፈፍ፤ ሕገ መንግሥቱን የፖለቲካ መሳሪያ ማድረግና የሕግ የበላይነትን ዋጋ ቢስ ማድረግ ወዘተ ይገኙበታል። ስለዚህ፤ በእኛ አመለካከት ሙስና ገንዘብ በመስረቅ፤ ሳይሰሩ በመሰብሰብና ከሕግ ውጭ ከሃገር በማውጣት ብቻ አይወሰንም። ሙስና “ማሰነ” ከሚለው የግእዝ ቃል የመነጨ ነው። ተራው ሰው ይህን ቃል የሚተረጉመው በስርቆት፤ በማጭበርበር፤ በጉቦ፤ በገንዘብ ወይንም በሌላ ቁሳቁስ መጥፋትና ጉድለት ነው። ይኼም ስርአት ወለድ ሙስናን ስለሚገልጽ ካቀረብነው ትርጉም ጋር ይዛመዳል። የህወሓት/ኢህአዴግ የእድገት ፍልስፍና የካፒታሊዝምን ትርጉም በጭንቅላቱ የደፋ ነው። ከሁሉም በላይ ትኩረቱ የገንዘብ ወይንም ኪራይ መሰብሰብ ጥቅምን ነው። የማህበረሰብ ሙብት፤ ለምሳሌ እንደ ጀርመኒ፤ ስዊድን፤ ደንማርክ፤ ፊንላንድ፤ የሰራተኞችንና የገበሬዎችን፤ የወጣቶችንና የሴቶችን ሙብትና ጥቅም አያስተናግድም። አብዛኛውን የአገር ኃብት ለጥቂት የበላዮችና ለቤተሰቦቻቸው ባለጠጋነት ያስተላለፈ የኢኮኖሚ አመራር ነው። የህወሓት መንስኤ እርዮት የግራ ክንፍ ቢሆንም የሶሻል ዲሞክራሲን አግባብነት ፈጽሞ ትቶታል። “የመለስ ራእይ” ተከታዮች ባይቀበሉትም፤ ኪራይ ሰብሳቢና ሙሰኛ መሆኑ በግልፅ ይታያል። ከሶሻል ዲሞክራሲ፤ ማለትም የሰራተኞችን፤ የገበሬዎችን፤ የአናሳ ብሄረሰቦችን፤ የሴቶችን፤ የወጣቶችን ፍላጎትና ምኞት ለማሟላት አልቻለም። በመንግሥት የሚመራ ካፒታሊዝም (Development state capitalism) እድገት መመሪያችን ነው ይላል። የመንግሥት ዋና ትርጉሙ ለማህበረሰቡ ከአድልዎ ነፃ የሆነና የተመዛዘነና ፍትሃዊ የሆነ አገልግሎት መስጠት ነው። የህወሓቱ መንግሥት “በብሄር ክልል” በተዋቀረ አገር ፍጽም የሆነ የበላይነት ይዟል። ይህ የእድገት ፍልስፍና፤ “በጭቁኖች” ስም የተመሰረተ ነው። የማህበረሰብ አገልግሎት ከማይሰጣቸው መካከል የጋምቤላ፤

የቤኒ ሻንጉል ጉሙዝ፤ የአሞ ሸለቆ፤ የኦጋዴን፤ የአፋርና ሌሎች ደሃና ወደ ኋላ የቀሩ የአገር ክፍሎች ይገኙበታል። ስለሆነም፤ ህወሓት የፈጠረው የካፒታሊዝም ውጤት ብሄራዊ ሃብትን አብሮ መካፋፈልንና ሚዛናዊ በሆነ መንገድ አብሮ ማደግን አያሳይም። ተቃራኒውን ነው። ስርቆትን፤ ሃሰትን፤ ራስ ወዳድነትን፤ ስግብግብነትን፤ የአገር ኃብት ማሸሽን ወዘተ። ትርፍ ገንዘብ ማግኘትና መሰብሰብ የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ ልዩ መታወቂያ ሆኗል። አሳሳቢ ሆኖ ያገኘነው ከትርፍና ከኪራይ ሰብሳቢነት ውጭ ሕብረተሰቡ እንዴት ይሻሻል፤ የአገሪቱን ሃብትና ጥሪት እንዴት ፍትሃዊ በሆነና ሁሉን በሚያስተናግድ መልክ እናሰራጨው የሚል ትኩረት የለም። መቶ አምሳ ሺህ ወጣት ኢትዮጵያውያን ከሳውዲ አረቢያ ተገደው ወደ ሃገር ሲመለሱ የተማርነው የስራ፤ የገቢና የሃብት ስርጭት አደገኛ ደረጃ ላይ መድረሱን ነው። የጥቂቶች ኢኮኖሚ የበላይነት የአብዛኛውን ሕዝብ፤ በተለይ ወጣት ትውልድ እድል እየዘጋው ነው። ይህ የግል ጥቅም አገልጋይ የፓርቲና መንግሥት የኢኮኖሚ አመራር ፍልስፍና፤ "በጥቂቶች፤ ለጥቂቶች" ሊባል ይገባል። ካፒታሊዝም ዘላቂነትና ተቀባይነት የሚኖረው ከማህበራዊ ወይንም ሶሻል ፍላጎቶች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ሲኖረው ነው። የህወሓት ካፒታሊዝም ጥቂት ግለሰቦችንና ቤተሰቦችን የሚያገለግል የኢኮኖሚ አመራር "ባዶ ወይንም ቀፎ" የሆነ፤ የአገሪቱን ሃብት የህብረተሰቡን ጠቅላላ የኢኮኖሚ ውጤት ለራሱ አድርጎ አብዛኛውን ከጥቅሙ ውጭ ያደረገ የሚሉት ለዚህ ነው። (The economics of zero sum game). ለተጠቃሚዎች፤ በዚህ ፍልስፍና አብዛኛውን የህብረተሰብ ክፍል ወደጎን ትቶ ኢኮኖሚውን ማሳደግና ባለጠጋ መሆን ምንም አያሳፍርም። ማንኛውም ገንዘብ፤ ኪራይ፤ ትርፍ ወዘተ ለመሰብሰብ የሚያስችል መንገድ ተቀባይነት አለው። ጉቦ፤ ስርቆት፤ ማጭበርበር፤ ሙሰኛነት፤ ዋጋን መደለዝ፤ ያልተገዛውን ተገዛ ማለት፤ ያልወጣውን ወጣ ማለት፤ ገንዘብና ሌላ ሃብት ወደ ውጭ ማሸሽ ተቀባይነት አግኝቷል። አብዛኛውን ሕዝብ ማግለልና በደሃው ትከሻ ሃብት ማካበት ትልቅ አደጋ እንደሚፈጥር እናሳያለን። አደጋው ቀላል አይደለም። ወደሚወድቅ አገር፤ ወደ የእርስ በርስ እልቂት (Failed State) ሊያመራ ይችላል።

የገዢው ፓርቲ  አመራርና አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ--ምሁሩን ጨምሮ--ሙስና ሲባል በገንዘብ ብልግና የሚወሰን ይመስለዋል። ሙስና ከዚህ የባሰ ነው። ጀምስ ወልፎንሶህን፤ የዓለም ባንክ ፕሬዘደንት ሆኖ ባገለገለበት ወቅት በደሃው ላይ የሚፈጸመው ምንም ይቅርታ የሌለው "በደል" ደሃ አገሮች ከለጋሶች የሚያገኙትን ገንዘብ ከተፈለገው አላማ ላይ ማዋል ግዴታቸው ነው ብሎ ነበር። ፍጹም ደሃነትን፤ መሃይምነትን፤ የተስቦ በሽታን፤ ረሃብን፤ ስራ አጥነትን፤ የሴቶችን የጾታ ጭቆና ወዘተ መቀነስ ማለቱ ነው። አፋኝና ሙሰኛ መንግሥታት ይህን በማድረግ ፋንታ ስልጣን ተጠቅመው እርዳታውን ለቤተሰቦቻቸው ሃብት ማካበቻ አድርገውታል። ከእርዳታና ከውስጥ የተፈጥሮ ሃብት የሚገኘው ገቢ ከሕግ ውጭ ወደ ግል ኪስ ሲገባ በህብረተሰቡ ላይ የሚያስከትለው በደል የከፋ ነው።  ወልፎንሶህን ሙስናን "የተስቦ በሽታ ወይንም ካንሰር" ብሎ ሰይሞታል። ለተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅት፤ ለዓለም ባንክና ለሌሎች ለጋሶች አማካሪ ሆኖ ያገለገለው ዝነኛ ኢኮኖሚስትና፤ ሮበርት ክሊትጋርድ (Robert Klitgaard) ለሙስና የሰጠው ትርጉም ዓለም አቀፋዊ እውቅና አግኝቷል። በዚህ መጽሃፍ የምንጠቀመው የክሊትጋርድን ትርጉም ነው። "ሙስና በመንግሥትና <u>በኅብረተሰብ አገልግሎት የተሰማራ ግለሰብና ቡድን ሕጉን፤ ደንቡንና ሌሎችን የሰለጠነው</u> ዓለም የሚመራባቸውን ልምዶችና ባህሎች ጥሶ ያለበትን ሃላፊነት ለግል፤ ለቤተሰብ፤ ለቡድን፤ ለፓርቲ፤ ለራስ ጎሳ/ብሄር ወዘተ የግል ጥቅም ሲያውል ነው። በአብዛኛው ጥቅሙ የገንዘብ፤ የሌላ ቁሳቁስና የስልጣን አጠቃቀም አመራርና በደል ሊሆን ይችላል።" የስልጣን አጠቃቀም፤ የምርጫ መዛባት ክስተቶች ከሙስና ጋር አብረው ይሔዳሉ። የፖለቲካ ስልጣን ብልግና ዋና ዓላማው የግልና የቡድን ጥቅምን ለማጠናከር ነው።

ወልፎንሶህን፤ ሴን፤ ክሊትጋርድ፤ ኢስተርሊ፤ ኮሌር፤ ሮንግና ሌሎች ባለሞያዎች የሚጋሩት "የስልጣን ብልግና ለግል ጥቅም ሲውል" መንግሥት ለህብረተሰቡ የገባውን ቃል ለግል ጥቅም አውሎታል የሚል ነው። ለግል የሚለው ትርጉም አከራካሪ መስሎ ይታያል። ሙሰኞች ለመንግሥት አገልግሎት የሚሰጡ ግለሰቦችና ድርጅቶች ብቻ አይደሉም። በግል ስራ የሚተዳደሩ፤ የውጭ ኢንቬስተሮችና ሌሎች፤ በተለይ ስልጣን ከያዙ ጋር የቅርብ ግንኙነት ያላቸው ሙሰኛ ለመሆን ይችላሉ። ዋናው መነሻ፤ በተለይ ደሃ በሆኑ አገሮች፤ አገዛዙ ለህብረተሰቡ ሃላፊነትና ተጠያቂነት ያለው ወይንም የሌለው መሆኑ ነው። ነጻ ተቋሞች ከሌሉ፤ ለምሳሌ መግናኛ ብዙሃን፤ ጋዜጠኞች፤ የህግ ተቋሞች፤ የማህበረሰብ ስብስቦች፤ ምሁራኖች ወዘተ ጠበቃ ሊኖር አይችልም። ተጠያቂነትና ሃልፊነት የሌለው የኢኮኖሚው አመራር ለሙስና ያመቻል። ዲሞክራሳዊ ከሆኑ ስርአቶችጋር ሲነጻጸር፤ አምባገነናዊ አገዛዝ ሙስናን ይፈጥራል። ባለስልጣናት በቅርብ የሚያገለግሉት "ራሳቸውን፤ ቤተሰባቸውን፤ ወዳጆቻቸውን፤ ብሄረሰባቸውን" ነው። ይህ የባለሞያዎች አስተሳሰብ በብዙ አገሮች ከታየ ልምድ ጋር ይመሳሰላል። ባለሞያዎች፤ እንዴት ተብለው ሲጠየቁ፤ በአምባገነናዊ አገዛዝ ባለስልጣናት "ሃቁን" አይናገሩም። የመናገር ግዴታም የለባቸው፤ የሚከራከሯቸውን ያስራሉ ወዘተ። ሠብአዊ መብት ይገፋሉ። ነጻ ፕሬስ አይፈቅዱም። ያታልላሉ። ጉቦና ኮሚሽን በድብቅ ይቀበላሉ። ለሚፈልጉት ኮንትራት ይሰጣሉ። ዋጋን ከሌሎች ጋር ተመሳጥረው ይደልዛሉ። የውጭ ምንዛሬ ለመጓጓዣና ለሌላ የሃላፊነት ስራ ነው ብለው ከአገር ያወጣሉ። የአገራቸውን ገንዘብ በልዩ ልዩ መልክ በውጭ አገር እየመነዘሩ ያሸሻሉ ወዘተ። ለሚፈልጉት ግለሰብ የውጭ ምንዛሬ ለስራ ነው

ብለው ይፈቅዳሉ። (In the words of Robert Klitgaard, "public officials of tyrannical governments deceive, misrepresent and conceal facts, doctor data, pay and receive bribes and are always prone to break the law for private ends....predator elites retard economies and cause political instability...where there is corruption, there is more poverty." 64/

ዓለም ባንክ የተመሰረተው ደሃነትን ከዓለም ማጥፋት ለሰላምና ለሰብዓዊ መብቶች ወሳኝ ነው በሚል መሰረታዊ ፍልስፍና ነው። በአፍሪካ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1950ዎቹ አመታት ለኢትዮጵያ እርዳታ የሰጠው ዓለም ባንክ ሙስናን እንዲህ የሚል ትርጉም ሰጥቶታል። "ሙስና የመንግሥት አስተዳደር ቁንጮ ይዞና ሌሎችን አግልሎ፤ ስልጣንን ለግል ጥቅም ማዋል ነው። ይህ የሚከሰተው አስተዳደሩ (the bureaucracy) ሰራዎችንና አገልግሎቶችን በአድልዎ፤ በጉቦ፤ በሙስና፤ በውስጥ ድርድር ሲያካሂድና የተሰጠውን አደራ በረቀቀ መንገድ ለግል ጥቅም ሲያውል ነው"። በአደራ የሚያስተዳድረውን የህብረተሰብ ገንዘብና የተፈጥሮ ኃብት ለግልና ለቡድን ጥቅም ስለሚያውለው ሙስና ለኢኮኖሚ፤ ለማህበራዊ እድገትና ለዜጎች የኑሮ መሻሻል ዋና መሰናክል ይሆናል። ("Corruption is widely seen as one of the biggest impediments to economic growth, investments and poverty reduction)." የፖለቲካ ስልጣን ብልግና ሙስናን እንደሚያስከትልና ፀረ-ማህበረሰብ፤ ፀረ-ፍትህ፤ ፀረ-ርትእ፤ፀረ-ደሃነት ቅነሳ እንደሆነ አያከራክርም። ከሁሉም በላይ ጉቦ፤ አድልዎና ሙስና ድህነትን ለመቀነስ ለሚደረግ ጥረት ዋና ማነቆ ነው። ህወሓት የሚመራው መንግሥት ሙስናን ልዩ ትርጉም ሰጥቶታል። ከላይ ያቀረብነውን ሰፋ ያለ ትርጉም በአገዛዝ ስሌት ስናየው ሙስና የፖለቲካ፤ የማህበረሰብና የኢኮኖሚ ዘርፎችን ያካትታል። አምባገነናዊ የሆነው የገዢው ቡድን የበላዮች ምዝበራን ተግባራዊ አድርገውታል። (Predator Elites). የየበላዮች ምዝበራ፤ "ዘራፊ ወይንም ምዝበራን የሚያካሂድ በጥቅም የተሳሰረ ቡድን" ማለት ነው። ቡድኑ እንዴት ለግልና ለቤተሰብ የሚጠቅም ብሄራዊ ምዝበራ ለማካሄድ እንደሚችል ስንመረምር ገዢው ቡድን የፈለገውን ሲያደርግ ማንም እንደማይቆጣጠረው በምእራፍ ሁለት-- የሠብአዊ መብቶችን መታፈን አስመልክተን-- አቅርበናል። አፈና ለምዝበራ ዋና መሳሪያ ነው። በፖለቲካ ሲታይ፤ ሁኔታው የተሻለ ሊሆን አይችልም። በምርጫ ዘጠና ሰባት የሕዝቡን ድምጽ አልቀበልም ብሎ የቅንጅትን አመራር ቃሊቲ እስር ቤት አስገብቷል። ይህ አገር አቀፍ ድርጅት እንዲከፋፈልና እንዲፈራርስ አድርጓል። ከአምስት አመታት በኋላ፤ ማንም ለመወዳደር ባልቻለበት ዝግ የፖለቲካ መስክ ዘጠና ዘጠኝ ነጥብ ስድስት በመቶ አሸንፊያለሁ ብሎ የበላይነቱን አረጋግጧል። በመጭው ምርጫ፤ ማለትም የዛሬ ዓመት ተመሳሳይ ውጤት እንደሚያገኝ አንጠራጠርም። የምርጫ ውጤት፤ የፖሊሲ፤ የባጀትና የኢንቬስትሜንት ምርጫዎችን ለራሱ እንዲያደርግ ረድቶታል። በፖለቲካው መስክ ገዢው ፓርቲ ሁልጊዜ ማሸነፍ መብቴ ነው ይላል። ከላይ መለስ እንዳለው፤ "እኛ እንደፈለግነው መብትን" ለማገብ "የሚያግደን" ኃይል የለም ትርጉም ይኼው ነው። ተቃዋሚው ሃይል ለመወዳደር መፈናፈኛ ቀዳዳ የለውም። ቁም ነገሩ የአንድ አምባገነን ፓርቲ ተከታታይ የፖለቲካ የበላይነት የፖለቲካ ሙስና ነው። ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ አይፈቅድም። የበላይነቱን በቀጥታ ስኬታማ የሚያደርገውና የሚያጠናክረው የቁጥጥር ተቋሞችን (ፍርድ ቤት፤ ፖሊስ፤ ስለላ፤ መከላከያ፤ አስተዳደር ወዘተ) ስለያዘ ነው። ስለ ኢትዮጵያ መንግሥት በተደጋጋሚ የምትጽፈው ፈረንሳዊት ጋዜጠኛ ሪኔ ለፎርት የሙስናውን ጥልቀትና ስፋት በሚገባ ገልጻዋለች። "ሙስና በኢትዮጵያ፤ ከመንግሥት የበላዮች ጀምሮ በክልልና በቀበሌ ደራጃ ስር ሰዷል። ማንኛውም የመንግሥት አገልግሎት ያለ ጉቦ፤ ያለ ጎሳዊ አድልዎና ያለ ሙስና አይሰራም"።

ዓለም ባንክ የኢትዮጵያን ሙስና በተመለከተ ባለፉት አስራ ስምንት ወራቶች ሁለት ጥናቶች አካሂዶ የደረሰበት ድምዳሜ የችግሩን ስፋትና ጥልቀት አሳይቷል። Diagnosing Corruption in Ethiopia-2012 and 2013. የችግሩን ስፋትና ጥልቀት ያሳዩት ጥናቶች የሸፈኗቸው የኢኮኖሚና የማህበራዊ አገልግሎት ክፍሎች "የስራ ፈቃድ፤ መአድን፤ ኩንትራቶች፤ የመሬት ኪራይ (ሊዝ)፤ መሰረተ ልማት፤ አቅርቦት፤ የአስተዳደር ግድፈትና ጉቦ፤ መገናኛ፤ የመብራትና የውሃ አገልግሎት፤ የፍርድ አሰጣጥ፤ ፖሊስና ትራፊክ፤ ታክስ፤ የውጭ ምንዛሬ" ወዘተ። አዲስ ፎርቹን የተባለው ጋዜጣ በ1/29/2014 ዓለም ባንክን ጠቅሶ እንዲህ ብሏል። "ጥናቱ ያሳየው ዝቅተኛ ሙስና በሁሉም የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ተሰፋፍተው ተቋማዊ ሆነዋል...ሕዝብ አገልጋዮች በሙሉ ሌቦች፤ ጉቦኞችና ሙሰኞች ሆነዋል"። ለሃገሪቷን ለሕብረተሰቡ አገልጋይ የለም። የመብራት፤ የውሃና የቴሌፎን አገልግሎቶች በተደጋጋሚ ይቆረጣሉ፤ ይቋረጣሉ። ለተራ አገልግሎት የሚከፈለው ድጎማ/ጉቦ ከሕዝቡ አቅም በላይ ደርሷል"። ለምሳሌ፤ የሚሰጠው ጉቦ ለአንድ ጊዜ ከአምስት ሺህ እስከ ሰባት ሺህ ብር (ዝቅተኛ)፤ አምሳ ሺህ ብር (ከፍተኛ) ተጠቅሰዋል። በገጠርና በከተማ አገልግሎት ለማግኘት ወይንም ፍርድ ለማግኘት ያለ ጉቦ አይቻልም። ራቅ ብሎ ለሚያየው አገሪት በማፊያ የምትዳደር ትመስላለች። እንዲህ ባለ ሁኔታ ሕብረተሰቡ እንዴት እንደሚሰቃይ፤ እንዴት እንደሚጉላላ ለማሰብ አያስቸግርም። አማራጭ ስለሌለው ጥርሱን ነክሶ ይኼን የአስተዳደር በደል ተሸክሞ ይኖራል። ይኼን ስር ሰዓታዊ ሸክም (Systemic administrative burden) ስናይ፤ የተማረውና የሰለጠነው የሰው ኃይል አገሩን ለቆ በነርፍ ቢሰደድ አይፈረድበትም።

የሕግ የበላይነት የሚገዛውና የሚያስተናግደው ሕብረተሰብ ከጉቦ፤ ከአድልዎና ከሙስና ነጻ የሆኑ ተቋሞች ሲኖሩት ነው። እነዚህ በኢትዮጵያ አይታሰቡም፤ የሉም። ባጭሩ የዓለም ባንኩ ጥናት የፍርድ፤ የፖሊስ፤ የመገናኛ ብዙሃን፤ ወዘተ መርምሮ ሶስት መቶ አምሳ የውጭ ድርጂቶችን አሳትፎ የደረሰበት ግንዛቤ እንዲህ የሚል ነው። "አስራ ስድስት በመቶ የሚሆኑት በአማካይ ለአንድ ስራ ስድስት ጊዜ ጉቦ እንዲከፍሉ ይጠየቃሉ። ዳኞች፤ የፍርድ ቤት፤ የደህንነት፤ የመዘጋጃ ቤት፤ የጉምሩክ፤ የቀረጥ፤ የውሃ፤ የመሬት አስተዳደር፤ የፈቃድ፤ የመንግሥት አቅርቦት (ፕሮኪውርሜንት) የመብራትና የመገናኛ አገልግሎት ሰራተኞች፤ጉቦ እንዲከፈላቸው ይጠየቃሉ"። ታዲያ ከጉቦ፤ ከአድልዎና ከሙስና ነጻ የሆነ የሕብረተሰብ አገልጋይ ማነው ብለን የመጠየቅ ሃላፊነት አለብን። <u>ጉቦና ሙስና የተራውን ዜጋ የመግዛትና የመኖር አቅም ቀንሶታል።</u>

አድልዎ፤ ጉቦና ሙስና የቁሳቁስ ብቻ አይደለም። በሃሳብ፤ በምርጫ፤ በትምኅርት፤ በጤና አገልግሎት፤ በፈቃድ፤ በቀረጥ ወዘተ ይከሰታል። ለፎርት እንዲህ ስትል አስቀምጣዋለች። "No institution was able to escape this corrupt-ridden dominance. It is a monopoly of ideas" and actions. "The TPLF holds the key positions in the nationalized companies and in "the privatized" firms that, in reality, the TPLF controls. So-called parastatal companies that dominate 2/3rds of the economy are dominated by the TPLF and its affiliates." የህወሓት መንግሥት የአገር የነበሩትን ኩባንያዎች "የግል" ያደረገበት ዋና ምክንያት ሃብትና ጥሪት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ወደ ራሱና ወደ ታማኝ ደጋፊዎቹ ለማሸጋገር ነበር። ይህ ድርጊት የሙሰኛነት አካል ነው። የዚህ ከፍተኛ ጎሳዊ አድልዎ ውጤት፤ የተዛባ እድገት፤ የተዛባ አስተዳደር፤ የተዛባ የገቢና የኑሮ ልዩነት ነው። የህወሓት አገዛዝ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ወደ ታች የጎተተው ከመንደር ጀምሮ እስከ ፌደራሉ መንግሥት የራሱን ታማኝ፤ በተለይ የትግራይ ተወላጆችን፤ የአካባቢ ግለሰቦችን በመደለል፤ በመደጎም፤ በማስፈራራትና በሌልች ዘዴዎች ታማኝ አገልጋይ እንዲሆኑ በማድረግ ነው። ለመፍረድ የማይቻለው ኑሯቸውን ለመደገፍ ሌላ አማራጭ የሌላቸው ኢትዮጵያውያን ስርዓቱን ቢያገለግሉና "ቢደግፉ" የማያስገርም መሆኑን ነው። አማራጭ ቢኖራቸው እነዚህ ግለሰቦች ፍትሃዊና ዲሞክራሳዊ ምትክ አይፈልጉም ለማለት አንችልም። ይፈልጋሉ። የጦር ኃይሉ በሕዝቡ ላይ የሚደርሰውን አፈናና በደል አያውቅም ለማለት የማንደፍረው ከሕዝቡ አብራክ ስለወጣና የሕዝቡን ምሬት ቀን በቀን ስለሚሰማው ነው። ስለሆነም፤ የመንግሥት ሰራተኞች በሙሉ ጉቦኞች ናቸው ለማለት አንችልም።

እርዳታ የፈጠረው እድገት

የኢትዮጵያ የልማት ባጀት የሚመካው በለጋሶች (ለጋሾች ሊባል ይችላል) የገንዘብ እርዳታ ነው። የመንግሥት ባለስልጣናት እርዳታውን ሙሉ በሙሉ ለተፈለገው ብሄራዊና ማህበራዊ ማጎልመሻ ማዋል የመጀመሪያ ተግባርና ሃላፊነት መሆኑን ለጋሶችና የልማት ባለሞያዎች ይጋራሉ። ይህ በወረቀት የሰፈረ ስምምነት ከስራ ላይ አልዋለም። የዛሬ አምስት አመት ዓለም ባንክ ለኢትዮጵያ መንግሥት የሚሰጠውን እርዳታ በመፈተሽ እንዲህ ብሎ ነበር። "የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር ሲወዳደር፤ አሁንም ወደኋላ የቀረ፤ የነፍስ ወከፍ ገቢ ከአፍሪካው አማካይ አንድ አምስተኛ የሆነ፤ ሰባት ሚሊዮን የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን አሁንም በውጭ የምግብ እርዳታ የሚመኩበት አገር ነው።" ይህ ከብዙ ቢሊዮን ዶላር እርዳታ በኋላ የቀረበ ዘገባ ነው። ባንኩ በተደጋጋሚ ያቀረበው ማሳሰቢያና ምክር የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ቀጣይነትና ፍትሃዊነት የሚኖረው፤ <u>"ለህብረተሰቡ ተጠሪነትና ሃላፊነት ያለው ዲሞክራሳዊ</u> አገዛዝ፤ ማህበረሰቡን በፌደራል፤ በክልልና በቀበሌ ደረጃ የሚያገለግል ችሎታ ያለውና ከሙስና የራቀ የሰው ሃይል፤ ጠንካራ የግል ኢኮኖሚ፤ ነጻ የሆኑ የማህበረሰብ ስብስቦች፤ ጥራት ያለው ከፍተኛ ትምኅርት ተቋማዊ ሲሆኑ ነው" ብሏል። 65/

እነዚህ የልማት መስፈርቶች በስራ አልተተረጎሙም። ሆኖም እርዳታው፤ በአመት አራት ቢሊዮን ዶላር ደርሷል። ሙስናው ጥልቀትና ስፋት እንዳለው ዓለም ባንክ በተደጋጋሚ አሳይቷል። የተራው ሰው ኑሮ በመሻሻል ፋንታ ተባብሷል። የኮሌጅ ዲግሪ ያለው ግለሰብ፤ የኮሌጅ አስተማሪ፤ የመንግሥት ሰራተኛ፤ በራሱ/በራሷ ስራ የሚተዳደር ግለሰብ፤ ወዘተ ለህይወት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን--ምግብ፤ ልብስ፤ መድኃኒት--ለመግዛት አቅሙ/አቅሟ እየቀነሰ ሄዷል። አዲሱ ትውልድ ወላጆቹ ከኖሩት ኑሮ በታች እንዲኖር እየተገደደ ነው። ቤት መግዛት አይታለምም። ብዙ ወጣት ቤተሰቦች እየተዳበሉ ወይንም ከወላጆቻቸው ጋር አብረው መኖር ከጀመሩ ቆይተዋል። መንግሥት ይህን ሁሉ እንደሌለ ይናገራል (ክሊትጋርድ አምባገነኖች ይዋሻሉ የሚለው ለዚህ ነው)። በአስተማማኝ ለመናገር የምንችለው የሚጎርፈው እርዳታ የወጣቱን ህይወት ለማሻሻል አልቻለም። የእርዳታው መሰረታዊ አላማ አከራካሪ እየሆነ ሄዷል። በሌላ አነጋገር፤ ለጋሶች መሰረታዊ የሆነውን የአገዛዝ ችግር ሊፈቱት አልቻሉም። የአገሪቱ "የውስጥ ጉዳይ ነው" ይላሉ። ገንዘቡን የሚሰጡት እነሱ ስለሆኑ፤ "የውስጥ ጉዳይ ነው" የሚለው የሞራል ወቀሳ እንደሚያስከትልባቸው አንጠራጠርም። ይህን የምንልበት ዋና ምክንያት፤ ከሚለግሱት ገንዘብ በያመቱ ብዙ ቢሊዮን ዶላር ለባለስልጣናት

ቤተሰቦች፤ ለወዳጆቻቸውና የግል ተባባሪዎች የግል ጥቅም እየዋለ ስለሚገኝ ነው። ከአገር የሚሸሸውን ማለታችን ነው። የአገሪቱ ኢኮኖሚና የህብረተሰቡ የኑሮ መሻሻል ስለተጎዳ ነው። ጥቂት የፖለቲካ ስልጣን የበላዮችና ቤተሰቦቻቸው ደሃ፤ ረሃብተኛና ጥገኛ በሆነች አገር የማይጠበቅ የድሎት ኑሮ መኖራቸው ይታያል። አገዛዙ የፈጠረው በአመት ከሶስት ቢሊዮን ዶላር በላይ እየተሰረቀ ከአገር መሸሹን ያውቃሉ። ለእርዳታ የሚሰጠው ገንዘብ ለሠብአዊ መብቶች አፈና መዋሉን ያያሉ። አንባቢውን የምናሳስበው አንድ መሰረታዊ የህሊና ቀስቃሽ ሃሳብ የሚከተለው ነው። እያንዳንዱ ከሕዝብ የሚሰረቀው፤ የሚሸሸውና ለግል ጥቅም የሚውለው-ለህዝብ አገልግሎት የተለገሰ- ዶላር በቀን አንድ ደሃ ህጻን ይመግባል። ያስተምራል። ለአንዲት በወሊድ መሞት ለሌባት እናት መድሃኒት ይገዛል። በአጠቃላይ ሲታይ የሚሰረቀውና ከአገር የሚሸሸው የሕዝብ ሃብት የሕዝቡን ኑሮ ሊያሻሽል ይችል ነበር። ስርቆት፤ ጉቦና ሙስና ወንጀልና የሕብረተሰብ ከሃዲነት ነው። ለወጣቶች የስራ እድል በመክፈት፤ ለገበሬዎች የተሻለ መሳሪያ በማቅረብ፤ የግል ስራ ለማቋቋም ለሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን በዝቅተኛ ወለድ ብድር በመስጠት ፋንታ ገንዘብ ማሸሽ፤ መደበቅ የኢኮኖሚውን የማምረትና የስራ እድል የመፍጠር ችሎታ ጎድቷል። የማህብረሰቡን ኑሮ መሻሻል የማያሳይ እርዳታ ከጥቅሙ ጉዳቱ አመዝኗል። ጠባብ ጎሰኛው ቡድን ፓርቲውን፤ መንግሥቱንና ተቋሞችን ከመንደር ጀምሮ ስለተቆጣጠረ እርዳታውንም እንደፈለገው የፖለቲካ ስልጣን ማቆያ አድርጎታል። ሰብአዊ መብቶች ቀጥታ በሆነ መንገድ ታፍነዋል። ይህም የሙስና መለኪያ ነው። ሰብዓዊ መብቱ የታፈነ ሕዝብ ለመደራደርና አቤቱታ ለማቅረብ ይቸገራል። አቤቱታ ለማቅረብ ዳኛውም፤ ፖሊሱም፤ የመንግሥት መስሪያ ቤት ሰራተኛውም በቅሺሺ ይጠይቃል። ማን ይችለዋል?

ፍፁም የሆነው ታይቶ የማይታወቅ በደልና ሸክም የሚያስታውሰን በFebruary 8, 2014, ብንያም ከበደ ያቀረበውን ነው። "ኢህአዴግ እባክህ ለራስህ ስትል ከብደትህን አቁም" ያለውን። ገዢው ፓርቲ እንኳን የተቃወመውን የመረጠውን ሕዝብ አያዳምጥም። ታዛቢው በአጭሩ ያስቀመጠው በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብና በገዢው ፓርቲ መካከል ያለውን ጨለማ የሚመስል ግንኙነት ነው። ፓርቲው አገዛዙን ለማቆየት የኢትዮጵያ ሕዝብ በማይችለው ደረጃ ታማኝነትንና ታዛዢነትን ለመግዛት ጉቦና ማባበያ ይሰጣል፤ "በአዲስ አበባ ከተማ ሶስት መቶ ሁለት ቶዮታ መኪናዎች ከባጀት ወጭ አድርጎ ለታማኝ ሰራተኞች ሰጥቷል" ይላል። ይኼ የታወቀ ሲሆን ያልታወቀው በያመቱ ብዙ መቶ ሚሊዮን እንደሚሆን መገመት አያዳግትም። ለሰርግም፤ ለቀብርም፤ ወዘተ መደጎሚያ ይከፈላል። በገዢው ፓርቲ ጫንቃ ላይ ሆኖ ራስን ማገልገል ሙስና ነው። ፀሃፊው እንዳለው አንድ ቀን የነጻነት እንደምታ ሲከሰት ይኼ ሁሉ በደል ይፋ መሆኑ አይቀርም የሚል ግምት አለን።

እርዳታ የሠብአዊ መብቶች ማፈኛ መሳሪያ ሆኗል

የዓለም ባንክን ስድስት መቶ ሚሊዮን ዶላር እርዳታ በተመለከተ እንዳሳየነው፤ ገዢው ፓርቲ እርዳታን የፖለቲካ መሳሪያ አድርጎታል። የሠብአዊ መብቶች መታፈን፤ አድልዎ፤ የአስተዳደር ግፍና ሙስና አብረው ሄደዋል። ለዚህ በተደጋጋሚ የህብረተሰቡን ብሶት በማስረጃ ያቀረቡ ብዙ ናቸው። ከእነዚህ ምርምር አድርጎ ሃቁን ሳይበርዝ ያቀረበው Human Rights Watch ነው። የሁለት ጥናቶች ድምዳሜ ጭማቂዎችን ከሙስና ጋር አብረን እናቀርባለን። "የኢትዮጵያ መንግሥት በአፍሪካ የለጋሶች ምርጥ ወይንም ኮከብ ሆኗል። በ2008 ብቻ ከሶስት ቢሊዮን ዶላር በላይ እርዳታ ተቀብሏል። ይህ እርዳታ ለገዢው ፓርቲ ቁልፍ የሆነ የአንድ ፓርቲ መቆጣጠሪያ መሳሪያ ሆኗል። ከመቆጣጠሪያነቱ በላይ፤ ለራሱና ለደጋፊዎቹ የግል ባለጠጋነት ማካበቻ፤ ለሚመርጣቸውና ታማኝነት ለሚሰጡት መኖሪያ፤ ለሚቃወሙት መቀጣጫ አድርጎታል። የውጭ እርዳታ አንዱ የበላይነት መሳሪይ ሆኗል።" ላለፉት ሃያ ሶስት አመታት በአምባገነንነት አገሪቱን የመራውና አሁንም የሚመራው ፓርቲ (Ethiopia is an authoritarian state) በደሃው ስም የሚያገኘውን ሰፊ እርዳታ ደሃውን ለማፈን ተጠቅሞበታል። ከላይ ዓለም ባንክ ያቀረበው መንግሥት ለሕዝቡ ያለው ሃላፊነት ለቀጣይነትና ለፍትሃዊ እድገት ወሳኝ ነው የተባለው ዋጋ ቢስ ሆኗል። መንግሥት ባለበት ሃላፊነት ህብረተሰቡን ከደሃነት፤ ከረሃብና ከመሃይምነት ነጻ አላወጣም። የፖለቲካ ድጋፍ የማይሰጡትን እየመረጠ፤ የቤት፤ የስራ፤ የትምኅርት፤ የጤና፤ የማዳበሪያ፤ የምርጥ ዘር፤ የብድር፤ የገበያ፤ የግል ስራ ፈቃድ፤ የእርሻና የግል ቤት መስሪያ መሬት ይከለክላል። በፀረ-ሽብርተኛነት የሚከሳቸውን ግለሰቦች የግል ሃብት ይቀማል ወዘተ። ለህሊና የሚቀፈው፤ ዓለም ባንክ በረሃብ ለሚሰቃዩ ኢትዮጵያውያን ያቋቋመውን የደህንነት ፕሮግራም (Safety-net Program) ለገዢው ፓርቲ ታማኞች ይገዛበታል። ደሃ ሰው ብዙም አማራጭ የለውም። በልቶ ማደር አለበት። ድጋፍ መስጠት በልቶ ለማደር ይረዳል። የማይደግፍ ምርጫው ጦም አደር ይሆናል። ("The government is routinely using access to aid money as a weapon to control people and to crush dissent…it is able to do this because the ruling party controls all the aid programs." 66/

በሂሳብ ማጭበርበር

የተሳሳተና ከእውነቱ ውጭ የሆነ ማስረጃ የማህበረሰብ ጉዳት ያመጣል። ችግሮች እንዳይፈቱ ይደብቃል። ህወሓት/ኢህአዴግ የፖለቲካ ድጋፍ በገንዘብ የሚሸምት ፓርቲ ነው። የፖለቲካ ድጋፍ አገር ውስጥ በሚሰበሰብ ባጀት ወይንም ከውጭ በሚሰጥ እርዳታ የሚደገፍ ፕሮግራም የሚገዛ መሆኑን አሳይተናል። የፓርቲ አባልነትና የምርጫ ድጋፍ በገንዘብ ሆነ በሌላ ቁሳቁስ ሲገዛ የሙስናን ትርጉም ያሟላል። የፖለቲካ ድጋፍ በመንግሥት ባጀት መግዛት ሙስና ነው። በተጨማሪ የሙስናን ባህል ያጠናክራል። የተዛባ ኢኮኖሚ ይፈጥራል። ስለ ገዢው ፓርቲ አድሏዊነት፤ ሙስኛንትና ስለ መንግሥት ሰራተኞች ብልግና የቴክኒካል ኮሌጅ፤ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች፤ ሌሎች ወጣቶችና የመንግሥት ሰራተኞች ተጠይቀው የሰጡት አስተያየት የህብረተሰቡን ችግር ጥልቀት ያሳያል። ቢያንስ "ሃያ ሁለት በመቶ የሚሆኑ የኮሌጅ ተማሪዎች ዲግሪያቸውን ለማግኘት ጉቦ እንዲከፍሉ ተገደዋል። ከተማሪዎች አርባ ሁለት በመቶ የሚሆኑት የትምኅርት ቤት ሃላፊዎች፤ ጉቦ ተቀብለው የተማሪ ፈተና ውጤት እንደሚለውጡ ተናግረዋል። ዘጠና ዘጠኝ ከመቶ (99 percent) የፌደራል መንግሥት ሰራተኞች፤ ባለፉት ሁለት አመታት፤ የመንግሥት ገንዘብ ያለ አግባብ "ለግል ጥቅም" እንደዋለ ገልጸዋል። ስድሳ በመቶ የሚሆኑ የመንግሥት ሰራተኞች (Public Officials ) የመንግሥት ባጀት ለልዩ ልዩ "የግል ጥቅሞች ይውላል" ብለዋል። ይኼ ሀሉ ኦዲት አይደረግም። በየቦታው የመንግሥት እጅ እንደሚገባበት ለማስታወስ፤ የጃፓን መንግስት ለአስራ ሁለት ኢትዮጵያውያን ስኮላርሽፕ ሲሰጥ ባልታወቀ ምክንያት፤ አራቱ ብቻ ጃፓን ሲሄዱ፤ ሌሎቹ በፖለቲካ ውሳኔ ቀርተው ህወሓት የመረጣቸውን ሌሎች ስምንት ልኳል። ይህን ሲያደርግ የፈተና ውጤት እንደቀየረ እንገምታለን። ይኼም ሙስና ነው። ሌሎች "ወሳኝ የሆኑ የመንግሥት ባለስልጣናት ኮንትራት ለመስጠት የሚጠቀሙበት ዋና መለኪያ (The sole criteria) ኮሚሽንና ጉቦ ነው። የውጭ ምንዛሬ፤ ብር ወይንም ሌላ ሊሆን ይችላል" ብለዋል። ይህን በጥልቀት "ኅሰኛ ባለጠጋዎች የፈጠረ የፖለቲካ ኢኮኖሚ" በተባለው ምእራፍ አቅርበነዋል። ባጭሩ፤ በኢትዮጵያ ከከፍተኛ የፓርቲና የፌደራል መንግሥት ሃላፊዎች ውስጥ ባለጠጋ ያልሆነ፤ ለአገሩ በሃቅ የሚሰራ ለማግኘት ተቸግረናል። ይህ አዲስ ባለጠጋነት ዛሬ የመጣ አይደለም። ህወሓት/ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘበት ቀን የጀመረ ነው። ለብዙ አመታት፤ ኢትዮጵያ በድብቅ ሲካሄድ የነበረው አድልዎና ሙስና "እንደ ተራ ነገር እየታየ ይታለፍ ነበር። አሁን ለእድገትና ለልማት ዋናው ማነቆ ሆኗል።" 67/

ከላይ ከሕዝብ የተሰበሰበ ማስረጃ ያቀረቡት ባለሞያዎች ያጠኗቸው የኢኮኖሚና የማህበረሰብ አግልግሎት ክፍሎች ለጋሶች የገነዘብ ድጋፍ የሚሰጧቸው ናቸው። የትምኅርትና ጤና፤ የንጹህ ውሃና መጸዳጃ፤ የግንባታና መሬት አጠቃቀም፤ የመገናኛና የማእደን፤ የደህንነትና የፍትህ–አገልግሎቶች ይገኙበታል። እነዚህን ክፍሎች (Sectors) በጥልቀት ተመራምረው የደረሱበት መደምደሚያ የበደሉን ደርጃ ያሳያል። በተለይ፤ "በኢትዮጵያ አስጊ የሆነ ከአገዛዝ ግፈኛነት የመጣ ችግር" መኖሩን። (A high level of risk). ሮጀር ካሎው፤ አለን ማክዶናልድና ፒየርስ ክሪስ "የገጠር ውሃ አጠቃቀምን" በሚመለከት ያቀረቡት ጥናት ያሳየው የለጋሶች እርዳታ "ለጉቦና ለሙስና ክፍት" መሆኑን ነው። "ኢትዮጵያ ከመላው ዓለም ንጹህ ውሃና ዘመናዊ መጸዳጃ ከሌለባቸው አገሮች" አንዷ ናት። በያመቱ፤ ቢያንስ 250,000 ህጻናት ንጹህ ውሃና ዘመናዊ መጸዳጃ ስለሌላቸው ይሞታሉ። The study highlights a number of "vulnerable areas such as participation at the lowest level, procurement and construction (end of the value chain) and stakeholder perception of corruption." ምን ማለታቸው ነው? የሕዝብ ተሳትፎና ለማንኛውም ተግባር ተወዳዳሪነት የሌለበት የግንባታ አገልግሎት ለጉቦና ለሙስና ወንፊት ሆኗል። ("Water corruption can be either grand …misuse of public sector funds by larger inter-connected elite or petty abuse of public funds by a smaller circle of public officials; in either case abuse of public trust in carrying out public service for private gain)." 68/

ዝቅተኛና ከፍተኛ ጉቦና ሙስና በህብረተሰብ አገልግሎቶች ስም ይመጣል የሚለውን በጥናት የተገኘ ድምዳሜ እንቀበላለን። ጥያቄያችን እንዴት ይሆናል የሚል ነው። ያገኘነው ግንዛቤ፤ የፖለቲካ አመራር ፖሊሲ፤ የውሳኔና የበላይነት፤ የፌደራል መንግሥት የባጀት አመዳደብና አጠቃቀም ይዘት፤በተለይ ለመሰረተ ልማት የሚመደበው ገንዘብ፤ ግልጽነትና ውድድር አለመኖር ለሙስና አስተዋጽኦ አለው። ከመንግሥት ውጭ ተወካይ ወይንም ተቆጣጣሪ (Independent oversight) አለመኖሩ ሙስናውን አጠናክሮታል። ጥናቱ ያመለከተው፤ የማንኛውም የመንግሥት መሰረተ ልማት (Public Construction) ስራ ከእውነተኛው የገበያ ዋጋ ስድሳ አራት በመቶ ይጨምራል። ዋጋው በጉቦና በሙስና ምክንያት ከሚገባው በላይ 64 percent (በመቶ) ይጨምራል። የዋጋ ልዩነት እንዲፈጠር ያደረገውና፤ መዝብሮ የሚያታልለው ወይንም የመንግሥት ሃላፊነት ይዞ የሚሰርቀው ከፍተኛ የመንግሥት አመራር ሃላፊነት ያለው ወይንም ከሃላፊ ጋር ቁርኝት ያለው ሰው ነው። ይህ አይነት የመንግሥት ኮንትራት ኢትዮጵያ የተለመደ ሆኗል። ሁኔታው የተባባሰው በከተማና በገጠር የመሬት አስተዳደር ነው። Land sector findings show "capture of assets by the elite and senior officials. Elite capture is facilitated by a weak policy and legal framework and procurement systems to implement policies and laws. Corruption in the implementation of land

policy and laws, particularly, the institutionalizations of informal fees, such as bribes, permit, and fraudulent actions of officials to allocate land to themselves both in urban and rural areas." ሙስና መዋቅራዊ ሆኗል። ስርአቱ መዋቅራዊ ሙስና ሲፈጥር የፖለቲካ ድምጽና ሃይል የሌላቸው ይጎዳሉ። ከጥንት ጀምሮ የተጠቀሙበት መሬት አይገባችሁም ከተባሉ አቤቱታ ለማቅረብ አይችሉም። ምርጫቸው መሬቱንና ቤቱን ለቀው ወደ ጠለላ መግባት ነው። ጎሳ-ተኮር አስተዳደር ሁኔታውን አባብሶታል። 69/

የከተማና የገጠር መሬት አመዳደብ ለጉቦና ለሙስና ቁልፍ ነው። ከማንኛውም የተፈጥሮ ሃብት መሬት ከፍተኛ ዋጋ አለው። ቤት ይሰራበታል፤ የመንግሥትና የግል ኢኮኖሚ ማንቀሳቀሻ ህንጻ ይሰራበታል። ኪራይ ይገኝበታል። ለቻይናዎች ፋክተሪ ማቋቋሚያ ይሆናል። ምግብ ይመረትበታል። ማእደን ይቆፈርበታል ወዘተ። ማንም ዜጋ ያለ መሬትና ውሃ አይኖርም። ሕዝብ እየጨመረ ሲሄድ የመሬት ዋጋም ይጨምራል። ዛሬ የመሬትና የቤት ባለቤትነት ያገኘ ነገ ለልጆቹና ለልጅ ልጆቹ አስተማማኝ የሆነ መሰረት ይጥላል። የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት የመሬትን ዋጋና ጥቅም በሚገባ ተረድቶታል። ያመልክበታል ለማለት እንችላለን። ዋና የኪራይ መሰብሰቢያና የፖለቲካ ስልጣን መቆጣጠሪያ አድርጎ ይጠቀምበታል። አገር ወዳድ ያልሆነ፤ መንግሥት የሚመራ ኪራይ ሰብሳቢ ቡድን፤ ጉቦኛና ሙሰኛ የሚሆነው ለዚህ ነው። በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች የመንግሥት ሰራተኞች ከከፍተኛ ባለስልጣናትና ከመዘጋጃ ቤቶች ጋር በመመሳጠር (Collusion) "የመሬት ባለቤትነት መዝገቦች በጉቦ፤ በቋንቋ አድልዎ፤ በማጭበርበር (Fraud)፤ በቀረጥ ወዘተ" እንደሚቀይሩ ታውቋል። "የመንግሥት ፀረ-ሙስና ድርጅት በአምስት የአዲስ አበባ ቀበሌዎች ባደረገው ጥናት ጉቦና ሙስና ከቁጥጥር ውጭ እነደሆነ" አረጋግጧል። "የመሬት ክፍሉ ለኪራይ ሰብሳቢነትና ለሙስና ዋና መሰረት ሆኗል። እአአ በ2008 የቀረበው የ Transparency International Bribe Payers Index ከአስራ ዘጠኝ የኢኮኖሚ ክፍሎች የከተማ ቦታና አመራር፤ ባለቤትነትና ስራ ለባለስልጣናት ዋናው የጉቦና የሙስና ምንጭ" መሆኑን ገልጿል። ማን አዲስ ባለጠጋ እንደሆነ ስንመረምር የሚከተሉት ይገኙበታል።

1. "ከፍተኛ የመንግሥት አገልግሎት ድርጅቶች፤ ለምሳሌ ቴሌኮሙኒኬሽንና አውራ ጎዳና።

2. ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣናትና የመምሪያ ሃላፊዎች፤ የመከላከያ ኃይሉን የበላዮች ጨምሮ፤

3. የቀበሌ፤ የመዘጋጃ ቤትና የክልል ሃላፊዎች።

4. የግል አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶችና ኮንትራተኞች።

5. የግል ኢንቬስተሮች፤ የውጭ አገር ኩባንያዎች፤ ስደተኞች፤ አገር ውስጥ ያሉ ሃብታሞች።"

ሙስናው ሰፊና ጥልቀት ያለው መሆኑ ያስደነገጣቸው ተመራማሪዎች ደጋግመው ተማሪዎችን ጠይቀው የተማሩት እንዲህ ይላል። "የትምኅርት ቤት ህንጻዎችና ሌሎች አቅርቦቶች (school construction and inputs such as computers and books)፤ ፈተናዎችና ውጤቶች በኮሚሽን፤ በጉቦና በአድልዎ" እንደሚሰሩ አረጋግጠዋል። በጤና አገልግሎት ያለው ከትምኅርቱ፤ ከመሰረተ ልማትና ከሌላው ስራ አይለይም። "የመድኃኒት ቤት ፈቃድ፤ የሆስፒታል አገልግሎት፤ የውሃ፤ የኤሌክትሪክና የቴሌፎን አገልግሎት፤ የፍርድ ቤት አገልግሎት ወዘተ" በሙስና የተበከሉ ናቸው። መንግሥት በፍርድ ቤቶች የውስጥ ስራ በተደጋጋሚ ጣልቃ ይገባል። "ፍትሃዊ የሆነ የሕግና የፍርድ አስተዳደር" እንደሌለ አረጋግጦ እንዲህ ሲል ደምድሟል። "The overview emerging from this study is that the full range of anticipated corruption risks exist within the education sector…it is difficult to ensure the integrity of procurement process in any sector." 70/

ትምኅርት ለጉቦ ሰለባ ከተዳረገ፤ ሌላው ክፍል ምንም አያጠራጥርም። ለሃያ ሶስት አመታት ይታይ የነበረው የባለስልጣናትና የሌሎች የተደራጀ ብሄራዊ ምዝበራ እየባሰ ሲሄድ ድህነትን ለማጥፋት የሚሰጠው እርዳታ ስኬታማ አይሆንም። እንዲያውም ለሰላምና ለእርጋታ አደገኛ ነው። የተዛባ የገቢና የኑሮ ልዩነት ፈጥሯል ወዘተ በማለት ሊጋሶች በዓለም ባንክ የሚደገፍና የሚመራ ጥናት አካሂደዋል። ከአደጋው ጋር ለመጨመር የምንፈልጋቸው የገዢው ፓርቲና ደጋፊዎች የሚከራከሩባቸው የእድገት ውጤት ናቸው የሚባሉ ሊደገፉ የማይችሉ ሁለት ክስተቶች አሉ። አንዱ፤ በታዳጊ አገሮች የገቢና የኑሮ ልዩነት የሚጠበቅ ነው የሚል። የጀርመኖች፤ የስካንዲናቪያ አገሮችና ሌሎች ይዚህ አመለካከት አይጋሩም። ሌላው አገርን በፍጥነት የሚያሳድጉት የተወሰኑ ግለሰቦችና ቤተሰቦች ናቸው የሚል ነው። ሌሎች ቀስ በቀስ ገቢያቸው እያደገ ስለሚሄድ በእምነት መቆየት አለባቸው። የመጀመሪያው ትክክለኛ የእድገት ሂደት አያሳይም። ከላይ እንዳቀረብነው፤ በኢትዮጵያ ጥቂት ባለስልጣናትና ቤተሰቦች የተሳሰረ የኢኮኖሚ የበላይነት የያዙት የፖለቲካ ስልጣን

ተጠቅመው እንጅ ጥረው፤ ግረው የሃገሪቱን ምርት አሳድገው፤ ፋብሪካዎች ሰርተው፤ ብዙ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ቀጥረው አይደለም። ያገኙት ንብረት በኩንትራትና በሌላ ዘረፋ ነው። ለዚህ ኪራይ ሰብሳቢነት ወሳኝና እድል ከፋች ሆኖ ያገኘነው የውጭ እርዳታ እንደ ልብ ለመንግሥት ባለስልጣናት በቀጥታ መለገሱ ነው። ሁሉም የውጭ ጥናቶች የሚያመለክቱት የመንግሥት እጅ በማንኛውም የምርትና የአገልግሎት ዘርፎች እንደገባበት ነው። እጅ ሲገባ ባዶውን አይደለም። ያስከተለው ከፖለቲካ ስልጣን ጋር የተሳሰረ ሌብነትን ነው። ሌብነት የሚጋራ ያስፈልገዋል፤ ተጠቃሚና ምስጢር ጠባቂ። የማያከራክረው የመንግሥት ሌቦች በየቦታው አሉ። ከዚህ የምንደመድመው የፖለቲካ መማረክ፤ የኢኮኖሚ መማረክን ፈጥሯል። የኢ አዴግ አለቃዎች ከብደት ከድርጂታዊ ዘረፋ ጋር ቀጥታ ግንኙነት አለው። መንግሥትና ደጋፊዎቻቸው የሚሉት፤ "አሜሪካም ያደገችው በጥቂት ግለሰቦችና ቤተሰቦች ጥረት ነው።"

በአንጻሩ፤ አሜሪካ ሲመሰረት፤ የኢኮኖሚ የበላይነት ይዘው ከፍተኛ ባለጠጋ የሆኑ ጥቂት ቤተሰቦች (The so-called Robber Barons) ነበሩ። አሁንም አሉ። እነ ፎርድ፤ ቤተልሄም የብረት ፋብሪካና ሌሎች ሃብታም የሆኑት አዲስ ነገር በመፍጠር፤ ለሌሎች እድል በመስጠት፤ መካከለኛ መደብ በማስፋፋት፤ ራሳቸው ተጠቅመው አገራቸውን ስላሳደጉ ነው። የገዢው ፓርቲ ከአሜሪካ ካፒታሊዝም የወረሰው የተለየ ነው። ህወሓት የጎሳ አድልዎ አድርጎ ትግራይ፤ በተለይ፤ መቀሌ ከተማ ካፈሰሰው ብዙ ቢሊዩን ብር ካፒታል ውጭ-- በአገር ደረጃ፤ የምርት ሃይሎች ማሳደግን፤ የመካከለኛ መደብ ማስፋፋትን ወዘተ አናይም። በአገር ደረጃ ስናየው፤ እንደ እርኢያ የተቀበለው የካፒታሊዝምን መጥፎ ጎን ነው። ስግብግብነት፤ ኪራይ ሰብሳቢነት፤ የገንዘብና የትርፍ አምልኮ ይባላል። ባለፉት ጥቂት አመታት አብዛኛውን የአሜሪካ ሃብት ከላይ የያዘው አንድ በመቶው ነው። የኢትዮጵያም ከዚህ ይብሳል፤ ሳያመርት ትርፍ ያገኘ። የኢትዮጵያ ሁኔታ ከዚህ የባሰ ነው የሚሉ ብዙ ናቸው። ዘጠና በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ የነፍስ ወከፍ ገቢው በቀን ከሁለት ዶላር በታች ነው። ይህን በብዙ ሚሊዮን ዶላር የሚገመት ገቢ ካላቸው አዲስ የአገሪቱ ሃብታሞች ጋር ማነጻጸር ያስፈልጋል። አንድ ኢትዮጵያዊ ተመልካች የተናገረው አግባብ አለው። የኢትዮጵያ "አዲስ ሃብታሞች በድህነት ባለጠጋ ሆነዋል። ስልጣን ያላቸውና ከባለስልጣናት ጋር ግንኙነት ያላቸው አዲስ ኃብታሞች ለሽርሽር የሚሄዱት ዱባይ ነው። ቀረጥ ሳይከፍሉ እህል፤ እንሰሳና ሌላ የሚሸጡት በርበራ ወይንም ደቡብ ሱዳን ነው። እንጀራ በአየር መንገድ ልከው የውጭ ምንዛሬ የሚያገኙት አሜሪካ ነው። ወደ ውጭ የሚላከውን እቃ የውጭ ምንዛሬ ገቢ እንዳለ አሸሽተው ካይመን ደሴት፤ ሲንጋፖር፤ ማላየዥያ፤ ሆንግ ኮንግ ወዘተ የሚደብቁት ያላቸው ናቸው።" ባጭሩ፤ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ኢኮኖሚ የሚያሳየው፤ ከላይ በጣም ሃብታም የሆኑ ጥቂት ቤተሰቦች፤ ከመካከል ሊሰፋ ያልቻለ የመካከለኛ መደብ፤ ከታች አብዛኛው ከደሃነት፤ ከጎጆ ኑሮ፤ ከኩራዝ መብራት፤ ከረሃብ ነጻ ያልወጣ ህብረተሰብ ነው። ከላይ ሃብታም የሆነው መደብ፤ ሙሉ በሙሉ ባይባልም፤ አብዛኛው፤ ባለጠጋ የሆነው ከገዢው ፓርቲ ጋር በመቆራኘት ነው። የሌሎች የበለፀጉ አገሮች ልምድ እንደዚህ አይደለም። ለአብዛኛው እድል ከፋች ነው። ምስራቅ ኤዢያና ቻይና ለዚህ ምሳሌ ናቸው። የመካከለኛ መደብ የኢትዮጵያን ሕዝብ ስርጭት በሚያንፀባርቅ መልኩ ቢስፋፋ የኢትዮጵያ እኮኖሚ ይፋፋል። አንጠራጠርም።

ይህን የተዛባ፤ ጸረ-ፍትህ፤ ጸረ-ርትእ፤ ፀረ-ማህበረሰብ የሆነ የኢኮኖሚ አመራር በመገንዘብ ለጋሶች ታንዛኒያ የሚገኝ ኪሊማንጃሮ ኢንተርናሽናል ኮርፖሬሽን የሚባል የግል ድርጅት ስለ ሙስና ጥናት እንዲያደርግ ወሰኑ። ጥናቱ ያተኮረው ከላይ በጠቀስነው በውጭ አገር ኢንቬስተሮችና ድርጅቶች ሳይሆን በአገር ቤት ባለው ሁኔታ ነው። በሕግና ፍትህ አስተዳደር፤ በህግ አፈጻጸም፤ በአገር ውስጥ ገቢና ጉምሩክ፤ በመዘጋጃ ቤቶች አስተዳደር ነው። ሙስና በእነዚህ የኢኮኖሚ ክፍሎች እንደማይወሰን በማጤን፤ ጥናቱ መገናኛን፤ የመሬት ይዞታን፤ ማእድንን፤ ግንባታን (Construction) ዳሰሰ፤ ዳሰስ አድርጓል። እነዚህ የመንግሥት ተቋሞች በዜጎች ህይወትና ኑሮ ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው። መመረጣቸው አያከራክርም። የሚያከራክረው ጥናቱ ጥልቀትና ድፍረት የሌለው መሆኑና ለዓለም ባንክና ለኢትዮጵያ መንግሥት ያቀረባቸው ተመክሮዎች "ጡንቻ" የሌላቸው መሆኑ ነው። በማንኛውም የኢኮኖሚ ክፍል የሚታየው የግልሰብና የክልል አድልዎ፤ ጉቦ፤ ሙስናና የአስተዳደር በደል ስርአታዊነት ነው። ተራው ሕዝብ የሚኖረውን ማለታችን ነው። ጥናቱ ያለውን አምባገነናዊ አገዛዝ በጭራሽ አልነካውም። ሆኖም ዘገባውና ትኩረቱ ከጥናታችን ጋር አብሮ ይሄዳል። ባጭሩ የሚከተሉትን አሳይቷል።

አንድ---የሕግ የበላይነት የለም

የሕግ የበላይነት በሚከበርበት አገዛዝ፤ ቢያንስ፤ በጉቦና በሙስና የተከሰሱ ወይንም በሚጠረጠሩ ባለስልጣናትና ሌሎች የፖለቲካ ጥበቃ አይደረግላቸውም። ማንም ግለሰብ ከሕግ በላይ ሊሆን አይችልም። በኢትዮጵያ "ሙስና ሁለት መልክ አለው። አንደኛው፤ የፖለቲካ ባለስልጣናት በፍርድ ቤቶች ተግባር ጣልቃ ይገባሉ። ዳኞች ይህን ስለሚያውቁ ሊከታተሉ የሚችሉት ዝቅተኛ "ወንጀለኞችን" ውይንም የፖለቲካ መቀጣጫ የሆኑ ግለሰቦችን ነው። የገዢው ፓርቲ

ጣልቃ ገብነት፤ የሕግ ሂደቶች በፖለቲካ እንዲመሩና በውሳኔ ልዩነት ለማድረግ እንዲችሉ አድርጓል።" ሁለተኛ፤ ዳኞችና ሌሎች የፍርድ አገልግሎት አስከባሪዎች ራሳቸው "ጉቦ ይጠይቃሉ። ይከፈላቸዋል። ፍርዳቸው ከግል ጥቅም ጋር ተያይዟል።" ስድሳ ደመወዝተኞች ተጠይቀው በአንድ ድምጽ፤ መንግሥት በፍርድ ስራ ጣልቃ እንደሚገባ፤ "ዳኞችና ፍርድ ቤቶች በሙስና እንደተበከሉ" ገልጸዋል። ከላይ ወደታች የሆነው የገዢው ፓርቲ የፖሊሲና የውሳኔ አስተዳደር ለሙስና መጠናከር አስተዋጽኦ አድርጓል። የፍትህ ስነስርአት የሚባል ነገር ፈጽሞ የለም። "The judiciary system is willing to make decisions in politically sensitive cases in accordance with the perceived wishes or actual instructions of political actors (elites)....Observers noted that kinship, friendship, ethnic and political ties might have a stronger impact" in the administration of law. ይህን የፍርድ ጉድለት ያጠናከረው የገዢው ፓርቲ የፖለቲካ አመራርና የፍርድ ተቋሙ (Judiciary) ቀጥተኛ የሆነ የመደጋገፍ ግንኙነት ስላላቸው ነው። ጥናቱ ያሳየው "ባለስልጣናት በማንኛውም ዘርፍ የተቆጣጣሪነት ሚና ይጫወታሉ" የሚል ነው። "A specific finding that spans a number of sectors points toward widely held concerns about members of the ruling party involvement." 71/

ሁለት፤ የባጀትና የእርዳታ አጠቃቀም የተዛባ ሆኗል

በመንግሥት ባጀት የተደገፈውና በኮንትራት የሚሰራው የግንባታ ስራ ዋና የጉቦ፤ የኮሚሽንና የሙስና ምንጭ ሆኗል። "በኢትዮጵያ በኮንትራት የሚሰራ፤ ወይንም መንግሥት ራሱ የሚሰራው የመሰረተ መዋቅርና ሌላ ስራ" ለሙስና እድል ከፋች ነው። ጥራት የሌለው ስራ በከፍተኛ ዋጋ (inflated prices) ይሰራል። በስምምነቱ መሰረት አያልቅም። ኮንትራት የሚሰጠው ግልጽ ባልሆነና አድልዎ በሚታይበት ሁኔታ ነው። ጥናቱ ያሳየን፤ የግንባታ፤ በተለይ የመንገድ ስራ፣ "የመሬት አስተዳደርና የማእደን ተግባሮች ሙስና የሰፋባቸው" ሆነው ይገኛሉ። እነዚህና ሌሎች የእድገትና የለውጥ ምሰሶዎች ተብለው የሚጠሩ ክፍሎች 'የጉቦ፤ የኮሚሽንና ሙስና' እድል ከፋቾች ሆነዋል። "In late 2009, risks in the construction, land and mining sectors were on an upward trajectory." መንግሥት ለመንገድና ለሌሎች መሰረተ ልማት ነክ ተግባሮች በአመት $1.2 ቢሊዮን ያወጣል። የመንገድና ተመሳሳይ ኮንትራት ለሙስና ጥርጊያ መንገድ ሆኗል። "On the basis of responses received, the construction sector in Ethiopia appears to show most of the classic warnings of the risks of corruption." ኢትዮጵያውያን በተደጋጋሚ ይናገሩት የነበረውን በይፋ አወጣው ማለት ነው። የመንግሥት ኮንትራት የባለስልጣናት ቤተሰቦችን፤ ወዳጆቻቸውን፤ አቅራቢዎችን አዲስ ባለጠጋ አድርጓል። ቴሌም እንደዚሁ ነው። ገዢው ፓርቲ የቻይናን የቴሌ ድርጅት የመረጠበትን ዋና ምክንያት ጠቅሰናል። ቻይና የኢትዮጵያ ገዢ ፓርቲና በበላይነት የያዘውን ኢኮኖሚ አትቃወምም። የሙስና ባህል አያስደነግጣትም። ሙስና በቻይና መንግሥት የበላዮች የተለመደ ሆኗል። የቻይና ድርጅቶች የሚጫወቱት ሚና ጠቅሟቸዋል። "በቴሌኮሙኒኬሽን፤ HIV/AIDS፤ በመድኃኒት አገልግሎት" ያለው ተመሳሳይ ነው። "የአውራ ጎዳና መስሪያ ቤት" እንደ ላም የሚታለብ የኪራይ መሰብሰቢያ ሆኗል። "በአጠቃላይ ያገኘነው ስእል፤ ከፍ እያለ የሄደ የሙስና ባህል ነው።" በእነዚህ የኢኮኖሚ ክፍሎች ከፍተኛ አድልዎ፤ ወገናዊነትና (Nepotism and fraud) ማጭበርበር በመቀነስ ፋንታ ከፍተኛ እድገት አሳይቷል። "The overall 'profile' of corruption along the value chain is not dissimilar to other countries or to other sectors." የማእደን ስራ የሚሰጠው በአድልዎ፤ ግልጽነትና ውድድር በሌለበት የውስጥ ውል መሰረት ነው። የመገናኛውን ዘርፍ ዘመናዊ ለማድረግ የሚደረገው ኢንቬስትሜንት ኮንታራት ፍጹም ግልጽነትና ጥራት የለውም። "In the pharmacy and health subsectors, and in new investment sectors (such as dams), the opportunity for and risk of corruption seized at all stages of investment, and service delivery chain is high. In the education sector, corruption is widespread and that a ruling party (TPLF) affiliated transaction resulted in the lack of fairness, most notably in the selection of teachers for employment and in the selection and grading of students." በአስተማሪዎች አመራረጥ፤ በተማሪዎች ፈተና ማለፍ አለማለፍ የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት እንዳለ ይታያል። የደሃ ወጣቶች የመማር እድላቸው በፖለቲካ ይወሰናል። እንደዚህ ያለ በትውልድ ላይ የሚደረግ ተመሳሳይ በደል በየትም አገር ለማግኘት አልቻልንም። 72/

ሶስት፤ ገዢው ፓርቲ ማን ባለጸጋ እንደሚሆን ይመርጣል

መንግሥት ከለጋሶች የሚያገኘውን ገንዘብ ለመሰረተ ልማት እንደሚያውል አያከራክርም። ግዴታው ነው። ለማሳየት የምንፈልገው ኢንቬስትሜንቱ ለማን በሚጠቅም ሁኔታ ይደረጋል የሚለውን ነው። በግንባታ ስራ በችሎታ ተማምኖ ኮንትራት ለማግኘት ከባድ ነው። ወሳኙ የመንግሥት ሃላፊ ነው። ሃላፊው ተወዳዳሪውን በችሎታ ሳይሆን "በግንኙነትና በታማኝነት" ይመርጣል። "Favoritism determines market entry; there is hardly any competition among

suppliers; decisions are consistently top-down. In the water sector, there is a perception that state (read party) owned drilling companies benefit from favoritism, in part resulting from relatively high entry barriers (closed market due to monopolistic practices)...In most regions (kilil) corruption in these and other sectors permeates the entire system." ይህ ነጥብ ከህብረተሰቡ ባህል ጋር ይጋጫል። "በአብዛኛዎቹ ክልሎች ህብረተሰቡ አዲሱን ከፖለቲካ አመራር ጋር የመጣ የጉቦና የሙስና ባህል" አልተቀበለም። ሆኖም ከላይ ወደ ታች የሚደረገው የገዢው ፓርቲ የበላዮች ውሳኔ የበታቾች "ጉቦና ኮሚሽን" እንዲቀበሉ፤ አድልዎ እንዲያደርጉ የአመራሩ ባህል ረድቷቸዋል። ከላይ ያለው ሙሰኛ ከሆነ "እኛስ ለምን አዲስ ሃብታም አንሆንም" የሚል ስሜት አለ። ጥናቱ ደጋግሞ የጠቀሰው ሙስና በገጠር፤ በከተማ፤ በቴሌ፤ በመንገድ ስራ ጉቦና ሙስና ተስፋፍተዋል። 73/

አራት፤ የተፈጥሮ ሃብት የበላይነት ለጉቦና ለሙስና ቁልፍ ሆኗል

በገጠሩ ኢኮኖሚ የሚታየው አድልዎ፤ ጉቦና ሙስና በቀጥታ የተያያዘው ከመሬት፤ ከወንዞች፤ ከግድብና ከማእደን ልማት ጋር ነው። መሬት፤ በየደረጃው ላሉ ባለስልጣናት (political and social elites) ሁለት የተያያዙ ጥቅሞች ሰጥቷል። አንድ፤ ብዙ ትርፍ የሚያስገኝ የኪራይ መሰብሰቢያ ሆኗል። ሁለት የገጠሩን ህብረተሰብ መቆጣጠሪያ መሳሪያ ሆኗል። መለስ የፈጠረው አምባገነናዊ አገዛዝ ተከሎት ያለፈው የኢኮኖሚ አመራር ገዢው ፓርቲ የመላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ የተፈጥሮ ሃብት እንዲቆጣጠር አድርጎታል። አገር አቀፍ የሆነ የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀምና የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ፖሊሲ የለም። ከሕዝቡና ከነዋሪዎች ጋር ውይይት አይደረግም። መሬት ለውጭና ለውስጥ ኢንቬስተሮች ሲሰጥ ማንንም አያማክርም። ውሳኔው ሁሉ የፖለቲካ ነው። የፖለቲካ አድልዎና ሙስና እንደሌላው የኢኮኖሚ ክፍል በገጠሩም ኢኮኖሚ ስር ሰዷል። ("Capture of assets by the elites and senior officials is widespread....Corruption practices in land management and administration are common." ግልጽና ፍትሃዊ የሆነ ፖሊሲ፤ መመሪያና ደንብ (Regulatory Framework) የለም። የገጠርና የከተማ መሬት ምሪት፤ ባለቤትነት፤ ይገባኛል ባይነት፤ ፈቃድ ወዘተ አስተዳደር የሚወስኑት በፖለቲካና በጉቦ ነው። በአዲስ አበባ ዘጠና በመቶ የሚሆኑ የቤት 'ባለቤቶች'በሕግ የተረጋገጠ ባለቤትነት የላቸውም። የመሬት ባለቤትነት በሕግ የታወቀና በሕግ የሚከበር አለመሆኑ ለጉቦ፤ ለአድልዎና ለሙስና አመች ሁኔታ ፈጥሯል። "Lack of formal tenure offers opportunity for asset capture by elites and senior officials; inevitably, this leads to corruption. Corrupt practices take the form of "institutionalized fees such as bribes and kickbacks in allocating lands." More critical, elites and officials at all levels allocate "prime lands to themselves or to developers who pay kickbacks or co-own buildings; they routinely issue forged land documents and transfer properties forcibly." የዚህ ሁሉ ጠቅላላ ውጤት ያሳየው የሕግ የበላይነት አለመኖሩን ነው። ኢትዮጵያውያን በራሳቸው አገር "የኔ ነው" የሚሉት የግል ሃብት እንዳይኖራቸው እየተደረገ ነው። 74/

አምስት፤ ገዢው ፓርቲ ዘመናዊ መገናኛ ቴክኖሎጂ ከልክሏል

በሰለጠነው ዓለምና በፍጥነት በሚያድጉ አገሮች ዘመናዊ መገናኛ ለነጻነትና ከድህነት ነጻ ለመውጣት ቁልፍ መሳሪያ ሆኗል። ባለፉት አስር አመታት፤ የኢትዮጵያ መንግሥት የቴሌኮሙኒኬሽንን አገልግሎት ዘመናዊ ለማድረግና ለማስራጨት አስራ አራት ቢሊዮን ዶላር ፈሰስ አድርጊያለሁ ብሏል። ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር ሲወዳደር፤ የሞባይልና ሌላ ዘመናዊ መገናኛ ቴክኖሎጂ ስርጭት አሳፋሪ ነው። ሞባይል ሁለት በመቶ ነው። መንግሥት ለዚህና ለሎች ቴክኖሎጂ ስርጭት ካፒታል ቢያወጣ ያስመሰግናል። አልሆነም። ገንዘቡ የት እንደገባ ከተጠቃሚው አንጻር እንመርምር። እአአ በ2012 የኢትዮጵያ የቴሌኮሙኒኬሽን ስርጭት ከአፍሪካ አገሮች የመጨረሻ ነበር። ልክ እንደ ግንባታው ስራና እንደ መሬት አሥተዳደር፤ ቴሌ እንደሚታለብ የኪራይ መሰብሰቢያ ድርጅት ሆኗል። መንግሥት ከቻይና ለሚገዛ መሳሪያ የሚበደረው ወይንም የሚያወጣው ገንዘብ ዋና ጥቅሙ ለገዢው ፓርቲ የስለላና የመቆጣጠሪያ አገልግሎት ነው። በ2008 Transparency International concluded that "Ethiopia's Telecommunications Corporation (ETC) was the tenth corrupt in the world." እንዴት ሊሆን ቻለ ብለን እንጠይቅ። ምክንያቱም ይህን እንደ አይን ብሌን የሚታይ ተቋም እንደ ግል ሃብቱ የሚቆጣጠረው የገዢው ፓርቲ ነው። ባለስልጣናት ከፍተኛ የግል ገቢ ያገኙበታል። ለቁጥጥር እንዲያመቻቸው፤ እውቀትና ልምድ ያላቸውን አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ከስራ አባረው በምትካቸው ታማኝ የሆኑ፤ በአብዛኛው የትግራይ ተወላጆችን አስገብተውበታል። ታማኞችን በየቦታዝው መሰግሰግ የህወሐት ዋና መለያው ሆኗል። ይህ አይን ያወጣ አድልዎ የፖለቲካ የበላይነት ሙስና ነው። "It is a matter of public record in Ethiopia that there are problems with management of ETC equipment supply

contracts;" a Chinese firm was selected; and "undisclosed sum of money transferred to key officials in the form of kickback and commission." ጥናቱና ሌሎች ታዛቢዎች የጠየቁት፤ ይህ የአገርን ጥቅም የሚጎዳ ወንጀል ሲሰራ እንዴት ኢትዮጵያውያን ዝም አሉ የሚል፤ የፓርቲውን አፋኝነት የሚያጋልጥ ጥያቄ ነው። አፋኝ በሆነ አገዛዝ ነጻነት የለም። ነጻነት ስለሌለ፤ የፖለቲካ ስልጣን ያለውን ከፍተኛ ሙሰኛ ማንም ደፍሮና በህይወቱ ፈርዶ ለማጋለጥ አይችልም። ካጋለጠ በራሱ፤ በቤተሰቡና በንብረቱ ፈረደ ማለት ነው። ሌላው የሚዘገንነውና ህወሓትን ከሌሎች አምባገነን ፓርቲዎች የሚለየው አይምሬ መሆኑ ነው። የተወነጀለ ግለሰብ አብሮ የሚወነጀልበት መላው ቤተሰቡ መሆኑ ይኼን ፓርቲ ከሌሎች ይለየዋል። ዘዴው ከጭካኔው በላይ ፍርሃትን መሳሪያ ለማድረግ ነው። ባጭሩ፤ የሰለላው መረብ የሚያሳየው፤ በማንኛውም የኢኮኖሚና የማህበረሰብ እንቅስቃሴ ፍርሃት ተስፋፍቷል። ይህ ፍርሃት ማነቆ ከመሆኑም በላይ ለሙስና ጠቃሚ ወንፊት ነው። "<u>The study identified among respondents a marked sense of fear that is not observed in other countries.</u> The conclusion here is that there are indeed significant corruption risks." ገዢው ፓርቲ ህብረተሰቡን የሚቆጣጠረውና ሊካድ የማይቻል ምዝበራ የሚያካሂደው በዘረጋው የስለላ፤ የአፈና፤ የማሳደድና በጸረ-ሽብርተኛነት የማሰር ወይንም ከአገር የማባረር መረብ ነው። በሙስና የተደረገው ጥናት "የተደራጀ ምዝበራ" የሚለውን መሰረተ ሃሳብ ይደግፋል። 75/

ስድስት፤ የኢትዮጵያ የውጭ ንግድ ለሙስና ወንፊት ሆኗል

የዛሬ ሁለት ዓመት ኢትዮጵያ ወደ ውጭ የምትልከው የእቃ አይነት ለውጥ እንዳሳየ ተመልክተናል። አንዱ ለውጥ የወርቅ የውጭ ገበያ መስፋፋቱ ነው። ወደ ውጭ የሚላክ የእቃ አይነት (Export Diversification) ለውጥ ለአገሪቱና ለህብረተሰቡ ጥቅም እንዳለው እናምናለን። ጥያቄው ምን አይነት ለውጥና ለማን ጥቅም የሚለው ነው። ህወሓት/ኢህአዴግ ስልጣን በያዘ በማግስቱ የመንግሥት የነበሩ የምርትና የአገልግሎት ድርጅቶችን፤ ያተርፉና ብዙ ኢትዮጵያውያን ይቀጥሩ የነበሩትን ጨምሮ፤ ግልጽነት በሌለው መልክ የግል አድርጓል። "የግል" ማለት የህወሓት፤ የፈጠራቸው ድርጅቶችና ታማኞች ማለት ነው። የዚህ አይነት የግል ክፍል አጎልማሽ (Privatization Scheme) እድል የከፈተው ለህወሓትና ለደጋፊዎቹ ነው። ከዚያ ወዲህ የማእደን ፍለጋና ምርት ፈቃድ በምስጢርና በተዛባ መንገድ ተካሂዷል። ከምርቱ የሚገኘው ልዩ ልዩ ገቢ ስንት እንደሆነና ከምን ብሄራዊ ስራ ላይ እንደዋለ አይታወቅም። የወርቅ ማእደን ለሼክ አላሙዲ ለምን እንደተሰጠ፤ ምን ያህል ገቢና ትርፍ እነደሚገኝ፤ እንደዚህ ያለ ለሃገሪቱ የውጭ ምንዛሬ ሊያስገኝ የሚችል ሃብት ለምን በኢትዮጵውያን (በሕዝብ) እጅ እንዳልቆየ ወዘተ የሚታወቅ ነገር የለም። "There is rapid and ongoing expansion in the sector that could increase both the risk of corruption and the amounts of money potentially lost (to the society)...licensing, operations and minining <u>revenues are unknown and opaque...</u>bribes are paid to get licenses...officials collude with mining companies. At least 37 percent of respondents willing to share data were aware of bribery....The actual risk in Ethiopia are that mining companies are breaking the conditions under which they were expected to operate." ወርቅ ሆነ ሌላ ሲቆፈር ለአካባቢው ሃላፊነት ያስፈልጋል። ዋናው ትርፍ ማግኘት ከሆነ ለአካባቢውና ለወደፊቱ ትውልድ ማንም ሃላፊነት አይወስድም። መንግሥት ለአገሪቱና ለህብረተሰቡ ሃላፊነት ከሌለው ጥናቱ እንዳሳየው "ምርቱ፤ ትርፉ፤ የት እንደሚሄድ አይታወቅም። ወርቅ ከህግ ውጭ ከአገር ይወጣል። በፌደራል መንግሥት ደረጃ ጉቦ፤ ማጭበርበር፤ ኮሚሽን የተለመደ ሆኗል"። ማእደን መስፋፋቱ ለአገሪቱና ለህብረተሰቡ የሚያስገኘው ጥቅም ሊታይ አልቻለም። ለአካባቢው ያመጣው ጠንቅ አስከፊ እንደሚሆን ይገመታል። አትራፊዎች ትርፍ ካገኙ በኋላ ችግሩን የሚረከበው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። 76/

ሰባት፤ አገዛዝና ሙስና ተቆላልፈዋል

ይህን ክፍል ለማጠቃለል፤ መሰረታዊ ጥያቄ እናቀርባለን። ጉቦን፤ አድልዎን፤ ስርቆትን፤ ማጭበርበርንና ሙስናን ወሰን በሌለው ሁኔታ ከዚህ አደገኛ ደረጃ ያደረሰው ምን አይነት የአገዛዝ ክፍተት ነው? ዋናውና የመጀመሪያው ከገዢው ፓርቲ ሙሉ ነጻነት ያለው፤ ለአገርና ለመላው ህብረተሰብ ጥቅም የቆመና የሚቆረቆር ተቆጣጣሪ ተቋም መከልከሉ ነው። ("There is no independent oversight" to speak of). ሁለተኛ፤ የኢኮኖሚ አመራሩ ምንም ግልጽነት አይፈቅድም። አብዛኛው ውል፤ ኮንትራትና ስራ የሚካሄደው በምስጢር ነው። ሶስተኛ፤ የፌደራሉ መንግሥት ሁሉንም የውጭ እርዳታና ብሄራዊ ባጀት ስለሚቆጣጠር፤ ለመሰረተ ልማት (Infrastructural work) የሚያወጣው ገንዘብ፤ የግዥና የአቅርቦት ድርድር የሚካሄደው በበላዮች ቁጥጥር ነው። አሸናፊውን አስቀድመው ይመርጣሉ። የመቀሌ ከተማ ከሌሎች ከተሞች የበለጠ የመሰረተ ልማት፤ የከፍተኛ ትምኅርት፤ የሆስፒታል፤ የስራ እድል ፈጣሪ የሆኑ የፋብሪካ ተቋሞች፤ የከተማ አረንጓዴነት (the greening and environmental sustainability of the city) የተስፋፉት

ከከተማው ነዋሪ በሚገኝ ባጀት ብቻ አይደለም። አብዛኛው ከፌደራሉ መንግሥት ከሚገኝ ባጀት ነው። የመንግሥት ባጀት ፈሰስ ግልጽነት ስለሌለ ለጎሳዊ አድልዎ፤ ለጉቦ፤ ለኮሚሽን ወዘተ የሚከፈለው ገንዘብ ብዙ ነው። ለአቅርቦት እውነተኛ ዋጋ አይከፈልም። በአብዛኛው ዓለም አቀፍ ወይንም ብሄራዊ የሆነ መስፈርትና ውድድር የለም። አራተኛ፤ በሌሎች አገሮች የሚደረገው በሕግ መዳኘትና አስቀድሞ ደንቦችንና መመሪያዎችን ለህብረተሰቡ ማስታወቅ የለም። ውሳኔው የፖለቲካ ነው። አምስተኛ፤ ብዙ ብሄራዊና ማህበረሰብአዊ ተግባሮች በምስጢር ይካሄዳሉ። የኢትዮጵያ የግል ኃብታሞች አገራቸውን ለቀው፤ ከቻሉ፤ ካፒታላቸውን የሚያሸሹት በመንግሥቱ ምንም እምነት ስለሌላቸው ነው። ካፒታላቸውን ሲያሸሹ ድምጽ መስጠታቸው ነው። ይህን መንግሥት “አንፈልግም፤ አገዛዙን አንደግፍም” የሚል። በአመራሩ እምነት ስለሌለ ሁሉም የሚያስበው በፍጥነት ትርፍ ማግኘትና ራሱን መጠበቅ ሆኗል። ስድስተኛ፤ ልምድ ያላቸው፤ አገር ወዳድ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ከስራቸው ተባረዋል። ያሉትም ለመኖር ሲሉ ፈርተው ይሰራሉ። ብሄራዊ የሆነ አቅም ደክሟል። የተዛባ ባህል፤ የተዛባ ኢኮኖሚ፤ ከፍትህ-ርትእ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው እድገት በማካሄድ ላይ ይገኛል። እነዚህ ክፍተቶች ለሙስና ዋና መሳሪያዎች ሆነዋል። “A standard export shipment of goods from Ethiopia requires 7 documents and takes an average of 42 days at a cost of $1,760 per container, compared to import of the same container that takes 44 days and costs $2,660.” የግል ክፍሉ ይህን የዋጋ ሸክም አይችልም። ኢኮኖሚውን ለማንቀሳቀስ የሚከፈለው ዋጋ ከሌሎች አገሮች ጋር ሊወዳደር አይችልም። የባህር በር የዘጋው ህወሓት ሕብረተሰቡን ከፍተኛ ዋጋ እያስከፈለው ነው።የዚህ ሁሉ የአገዛዝ ማነቆ ውጤት ምን ይሆን ብለን ስንጠይቅ ቀጣይነትና ፍትሃዊነት ያለው ልማት የማይቻል መሆኑን እንረዳለን። “If left unchecked, corruption could undermine the nation’s development efforts.” አገዛዙ እውነተኛ ዲሞክራሳዊ ካልሆነ፤ አደጋ ላይ የሚወድቀው የአገሪቱ ቀጣይና ፍትሃዊ እድገት ብቻ አይደለም። የአገሪቱ ህልውና፤ የህብረተሰቡ ኑሮ መሻሻል፤ አብሮ በሰላም ተደጋግፎ መኖርና እርጋታም ይናዳሉ። 77/

ጸረ-ሽብርተኛነት ለሙስና አገልግሏል

የሺብርተኛነት አደጋ መኖሩን እናምናለን። አስቸጋሪ ሆኖ ያገኘነው ገዢው ፓርቲ ሺብርተኛ መሆኑን ጭምር ነው። ሙሰኛ አመራር ሌሎችን መክሰስ ይወዳል። የማንኛውንም ፍትህ ፈላጊ “ሽብርተኛ” ብሎ መክሰስ ይጠቀማል። ይህን ከባድ ግንዛቤ ስናቀርብ በቀላሉ አይደለም። በቅርቡ የአሜሪካ የልቦና ተቋም ያሳሰበውን መሰረት በማድረግና ሌሎች በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ የተሳሰረ የአገዛዝ ግፍ የሚያስከትለውን ችግር በመከታተል ጥልቀት ያለው እውቀት ያቀረቡትን ግንዛቤም በማጤን ነው። በቅርቡ በሰሜን አፍሪካና በመካከለኛው ምስራቅ የሕዝብ አመጽ የተካሄዱባቸውንና በማካሄድ ላይ ያሉባቸውን አገሮች አለመረጋጋት መንስኤዎች ደጋግመው ገልጸዋል። <u>ቀስቃሹ የህብረተሰቡ የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚና የማህበረሰብ የኑሮና የህይወት መናጋት ነው።</u> ኬንያ፤ አይቮሪኮስት፤ ዝምባብዌ፤ ላይበሪያ፤ ሴራሊኦን፤ ሶማልያና ሌሎች አገሮች የሆኑት ውድቀቶች በሌሎች ይደገማሉ የሚል ግንዛቤ ቀርቧል። Freedom House በተደጋጋሚ ያቀረበው ኢትዮጵያ “ምንም ነጻነት ከሌለባቸው” አገሮች መካከል አንዷ ናት። ገዢው ፓርቲ ማንኛውንም ሰላማዊ ተቃውሞ “ወንጀል” አድርጎታል። ለህብረተሰቡ የቆመና የሚቆም ግለሰብ ወይንም ድርጅት ወንጀለኛ ነው። ይህ አፋኝ የሆነ ስርአት እስከ ቀጠለ ድረስ አራት ክስተቶች ይኖራሉ። አንድ፤ ኢኮኖሚው ይናጋል። ሁለት፤ ዲሞክራሳዊ መብት አይኖርም። ሶስት፤ ምዝበራው አያቆምም። አራት፤ እርጋታና ሰላም አይኖርም። ፓርቲው የበላይነቱን የቀጠለው ተራውን ዜጋ በማገልገል አይደለም። “ብሄራዊ ደህንነት መረጋገጥ አለበት” በሚል ከሕዝቡ መብት ተለይቶ በቀረበ ዘዴ ነው። “The Ethiopian government framed its interests around terrorism and national security…” It receives enormous amounts of money from Western countries to finance this goal while suppressing dissent. The party exercises “complete dominance of local and national governmental institutions, a number of large businesses linked to the party either directly or through family members, party affiliated nongovernmental organizations such as the Relief Society of Tigray.” የውጭ እርዳታ ለማግኘት ገዢው ፓርቲ ሁለት ዘዴዎች ይጠቀማል። አንድ፤ ብሄራዊ ደህንነትና ፀረ-ሽብርተኛነትን። ሁለት አስቃቂ ድህነትንና ረሃብን። ሁለቱም ለግል ሃብት ማካበቻ ቁልፍ መሆናቸውን ከላይ አይተናል። እርዳታው እንዲጨምር ውጤት ማሳየት አስፈላጊ ነው። ለዚህም መንግሥት መልስ አለው። የእርሻ ውጤት በጣም አድጓል ብሎ ነበር። የዓለም ባንክ ባለሞያዎች ስለደነገጡ ጥናት አድርገው “የኢትዮጵያ የእርሻ እድገት መንግሥት እንደሚያወራው ከሆነ አገሪቱ በዓለም የሚያስደንቅ ‘የአረንጓዴ አብዮት አካሂዳለች።” ይህ ከእውነቱ የራቀ መሆኑን በማስረጃ አቅርበውታል። በሌላውም የኢኮኖሚ ዘርፍ ያለው የእድገት ሂሳብ አስተማማኝ አለመሆኑን አሳይተናል። 78/

የገዢው ፓርቲ ደጋግሞ የሚያስተጋባው ክልሎች ለመጀመሪያ ጊዜ በተፈጥሮ ሃብታቸው ላይ የባለቤትነትና የመወሰን መብታቸው ተከብሮ በፍጥነት እያደጉ ነው የሚል ነው። ክልሎች ካደጉ የህብረተሰቡም ኑሮ ተሻሽሏል። ሁሉም

የህብረተሰብ ክፍሎች ካደጉ የአገሪቱም የምርት ሃይል ጨምሯል። እነዚህ ሁሉ ከሆኑ የነፍስ ወከፍ ገቢ አድጓል። ተራው ዜጋ በልቶ ያድራል። ይህን ለአንባቢ ህሊና እንተወውና ሊከሰት ይችላል የሚባለው እንደምታ ምን ይመስል ይሆን ወደሚለው እንሂድ። ያለው የዋጋ ግሽበት፤ የስራ አጥነት፤ የአስተዳደር በደል፤ ጉቦ፤ አድልዎ፤ ሙስና፤ ከሃገር እየተሰረቀ የሚወጣው ብዙ ቢሊዮን ዶላር ካላቆመ--ጥናታችን የሚያሳየው እነደማያቆም ነው የእርጋታ መዛባትና ሌሎች ያልታሰቡ ችግሮች ይከሰታሉ። "If urban disturbances occurred simultaneously in Addis Ababa and several cities (Dire Dawa, Nazret, Mekele, Gondar and Awassa are the next largest cities, and Jimma is an important university town), then the ability of the regime to manage the crisis would be in question." በምእራፍ ሶስት እንዳሳየነው፤ ጎሳ-ተኮር ፌደራሊዝም ለእርስ በእርስ ትርምስና ግጭት አስተዋጽኦ እያደረገ ነው። "Ethnically defined federalism has created potentially powerful interests in the regions with their own institutions, generating potential for centrifugal forces to undermine national unity in the event of a crisis." የምግብና የሌሎች አስፈላጊዎች ዋጋ ጨምሯል። እንዲያውም ተፈላጊ ቁሳቁሶች አይገኙም። የስራ እድል የለም። ወጣቱ እየተሰደደ ነው። ሰብአዊ መብቶች በሙሉ ታፍነዋል። ቢያንስ ከሰማንያ ሽህ በላይ የፖለቲካ እስረኞች አሉ። የሃይማኖት ነጻነት ታፍኗል። ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሽባ ሆነዋል ወዘተ ወዘተ። ይህ ሁኔታ ለኢትዮጵያ ብሄራዊ አንድነትና ለአብዛኛው ሕዝብ ኑሮ መሻሻል አሰጊ መሆኑን በግልጽ ያሳያል። ጥናቶች የሚያሳዩት ሃቅ፤ ግፈኛ መንግሥታት ጥቅማቸውን ለመጠበቅ የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። ከእነዚህ መካከል "ዲሞክራሲ አለ ወይንም እየተገነባ ነው። እድገት እየታየ ነው። ሰላምና እርጋታ አለ" ወዘተ የሚሉ ይገኙበታል። 79/

የተቋማዊ ክፍተት ያስከተለው ውጤት

ለሙስና ጥልቀት ምክንያት የሆኑ ሁለት ክፍተቶች እንጠቅሳለን። አንድ፤ ለአገር ተቆርቋሪ፤ ከመንግሥት ቁጥጥር ነጻ የሆነ ተቋም አለመኖሩ። ሁለት፤ የተፈጥሮ ሃብት አስተዳደርና ባለቤትነት በሕግ አለመከበሩ። ገዢው ፓርቲ ያፈነው መብቶችን ብቻ አይደለም። ብሄራዊ ተቋሞችንና ሃቁንም ጭምር ነው። እውነቱና ውሸቱ አይታወቅም። መንግሥት ብሄራዊ ተቋሞችን እንደ ጠላት ያያቸዋል። ድህነትን ለማጣፋት የሚሰጠው እርዳታና ውጤቱ በሰፊው ተጠንቷል። በአጠቃላይ፤ ሕግ በሚከበርበት አገር፤ መንግሥታትና ድርጅቶች የሚቀበሉት እርዳታ በቀጥታ ለመንግሥት መሪዎች በባለቤትነት "በአደራ" ሲሰጥ ባለስልጣናት ሃላፊነታቸውን አይረሱም። አብዛኛውን ገንዘብ ለተጠቃሚዎች ያስተላልፋሉ። በቀበሌና በክልል የሚገኙ የማህበረሰብ አባላት ይጠቀማሉ። ይህ ሲሆን ገቢ ያድጋል። ደሃነትና ረሃብ ይቀንሳል። በኢትዮጵያ ይህ እንዳልሆነ አሳይተናል። በ2012 ጋዛላ ማንሱሪና ቪጃያንዴራ ራኦ የተባለ ኢኮኖሚስቶች ስለ ዓለም ባንክ እርዳታ ያደረገው ጥናት ያሳየው፤ ነዋሪዎችን ለማጎልመስ ለመንግሥት የሚሰጠው ገንዘብ ለውጥ አለማምጣቱን ነው። ለተጠቃሚዎቹ አልደረሰም። ከሰላሳ እስከ አርባ በመቶ የሚሆነው የማንኛውም ሊጋስ እርዳታ የታሰበው ገጠሩን ለማልማት ነው። ጥናቱ ያሳየው የማእከላዊና የክልል፤ የቀበሌና የሌሎች ሃላፊዎች በመመሳጠር አብዛኛውን የእርዳታ ገንዘብ ለግል ጥቅም ያውሉታል። "በዩጋንዳ ሰማንያ ሰባት በመቶ የሚሆነው ለገጠር ትምህርት ማስፋፊያ የተሰጠ እርዳታ ተሰርቋል። በካሜሩን፤ ዘጠና በመቶ የሚሆነው የእርዳታ ገንዘብ ለመከላከያ ሃይሎች ተዘዋውሯል። የተረፈው አድሏዊ በሆነ መንገድ ለፓርቲው ታማኝ ለሆኑ ክልሎችና ድርጅቶች ተሰጥቷል"። ለዚህ ሁሉ ምክንያት የሆነው ሙስና ነው። አንድ የዓለም ባንክ የውስጥ ጥናት፤ ቢያንስ ሰላሳ በመቶ የሚሆነው እርዳታ ይሰረቃል ይላል። የእኛ ግምት ከዚህ በላይ ነው፤ ቢያንስ አምሳ በመቶው። የዩጋንዳውና የካሜሩኑ ምሳሌዎች ከኢትዮጵያው ጋር ተመሳሳይ ናቸው። የዓለም ባንክ "የውስጥ ታዛቢዎች የኢትዮጵያው አድልዎና ሙስና ከሰላሳ እስከ አርባ በመቶ ነው" ይላሉ። ከመንግሥት ቁጥጥር ውጭና ነጻ የሆነ ብሄራዊ የቁጥጥር ተቋም ከሌለ የሙስናውን መጠን ከፍ ያደርገዋል። ለኢትዮጵያ HIV/AIDS የሚሰጠው ገንዘብ እንደሚሰረቅ የዓለም ባንክ ማስረጃ ያሳያል። በመጀመሪያዎቹ የህወሓት/ኢህአዴግ የአገዛዝ ዓመታት፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የትምህርት እድል ይዳረሳል ተብሎ የተለገሰ ገንዘብ ለክልል አንድ--ለትግራይ መሰጠቱን እናውቃለን። የጋምቤላና የአፋር ሕዝብስ ለምን አልደረሰውም ብለን ስንጠይቅ መልስ አላገኘንም። ፕሬዝደንት ክሊንተን የዩጋንዳውን አምባገነንና የሙሰኛ ስርአት የሚገዛውን፤ ሙሴቬኒን፤ የኢትዮጵያውን መለስን የአፍሪካ ዲሞክራት "ኮከቦች" ብሏቸው ነበር። አምባ ገነኖችና ሙሰኞች ከሆኑ "ኮከብነታቸው" በምን መለኪያ ነው ብለን ብንጠይቅ፤ ለምእራብ መንግሥታት ታማኝ ከመሆናቸው ውጭ የሕዝብ አገልጋይነታቸው አይታይም። "The report paints a grim picture of how some groups are undermined by local elites. The most marginalized are often minority ethnic groups and women." 80/

ሙሰኛ የሆነ ተቋም ሙሰኝነትን ሊቆጣጠር አይችልም

ገዢው ፓርቲ የቁጥጥር ተቋሞች ይፈጥራል። ነጻነትና ሙብት የላቸውም። ስብጥር ሕዝብ በሚኖርበት አገር ማንኛውንም ክፍል አለማገልገል ወይንም ለይቶ ማግለል ዘላቂ ጉዳት ያመጣል። የህብረተሰብ ክፍሎች ሲገለሉ የኢኮኖሚው የማምረት አቅም ይጎዳል። ከዚህ ጋር ሠብአዊ ሙብቶች ሲታፈኑ፤ ሙስና መዋቅራዊ ሲሆን፤ ወጣቱና አገር ወዳዱ ለስደት ሲዳረጉ ወዘተ ቀስ በቀስ የአገር ውድቀት ይከተላል። የኢኮኖሚው መዋቅር--ከጥቂት የኪራይ መሰብሰቢያ ክፍሎች በስተቀር--እንደ ረጋ ወተት ባለበት ይቆማል ወይንም እንደ አይሾሪኮስት ይወድቃል። ገዢው ፓርቲ ሲጋሶችን ለማባበል፤ የጸረ-ሙስና ኮሚሽን አቋቁሟል። የሕግ የበላይነትና የመገናኛ ነጻነት ባለበት አገር የስነምግባርና የጸረ-ሙስና ተቋም ያገለግላል። በኢትዮጵያ ሊያገለግል አይችልም። ተቋሙ ራሱ በፖለቲካ የበላይነት ሙስና የተበከለ ነው። የተቋሙ ሃላፊዎች ራሳቸው "በጉቦ፤ በአድልዎና በሙስና" የሚጠረጠሩ ናቸው። ለቁጥጥርና ለዳኝነት ብቁነት የላቸውም። ከላይ ባቀረብነው ዘገባ፤ ገዢው ፓርቲ፤ በተለይ ህወሓት፤ ያልገባበት የምርት ወይንም የአገልግሎት፤ ወይንም የተፈጥሮ ሃብት አስተዳደር ክፍል የለም። ሁሉም ክፍሎች ለግል ጥቅም ቁልፍ ናቸው። መንግሥት ራሱን የሚቆጣጠረውንና ለሕግ የሚያቀርበውን ብሄራዊ ተቋም አይፈቅድም። በሌሎች የበለጸጉ አገሮች የተለመደው ሚዛናዊ የአገዛዝ ልምድ (Checks and Balances) በኢትዮጵያ አይታሰብም። የፖለቲካው አመራር ይህን ተቋማዊ መዋቅር ከፈቀደ ራሱን እንደሚያጋልጥ ይገምታል። በቀላሉ ለማስቀመጥ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉም የመንግሥትና የገዢው ፓርቲ ባለስልጣናት ያከማቹትን ሃብት ለሕዝብ ማስታወቅ አለባቸው ብሎ ቢጠይቅ አዳማጭ አያገኝም። ሆኖም፤ መጠየቅ አለበት። ሙብቱ ነው። የህወሓት ባለስልጣናትና የፈጠሯቸው ድርጅቶች፤ ከዜሮ ካፒታል ተነስተው፤ የብዙ ቢሊዮን ዶላር ባለጠጋዎች ሆነዋል። በደሃነት ነግደዋል ። አግባብ ያለው ጥያቄ፤ እያንዳንዳቸው ለኢትዮጵያና ለዓለም ሕዝብ ያላቸውን ኃብት እንዴት እንዳገኙት፤ የት እንዳስቀመጡት ግልጽ ለማድረግ ይፈልጋሉ ወይንስ አይፈልጉም የሚል ነው። (Are they willing and ready to disclose what they own and where?) የፓርቲ ወይንም የመንግሥት ስልጣን የያዘ ኢትዮጵያዊ በደሞዙ ቢሊዬኔር ለመሆን አይችልም። ሃብቱን ይፋ ለማድረግ አይፈቅድም።

በፈረንሳይ (ከፈረንሳይ አብዮት በፊት) በፊሊፒንስ፤ በደቡብ ኮሪያ፤ በኬንያ፤ በደቡብና በሰሜን አፍሪካ፤ በመካከለኛው ምስራቅ ወዘተ ያየነውና የምናየው ሁኔታ መንግሥትን የሚመሩ ኪራይ ሰብሳቢ ፓርቲዎችና ባለስልጣናት ግትር መሆናቸውን ነው። ዘዴው፤ ማንኛውንም መገናኛ መዝጋት ነው። ችግሩ ከቁጥጥር ውጭ ካልሆነ ለመለወጥ ፈቃደኛ ሆነው አያውቁም። የገንዘብና ሌላ ቁሳቁስ "ያሰክራቸዋል" የሚባለው ለዚህ ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት በተከታታይ ነጻ የሆኑ የመገናኛ ብዙሃንንና ጋዜጠኞችን የሚዘጋበት፤ የሚያስርበትና የሚያሳድድበት፤ ሁሉን ተቃዋሚ "በሽብርተኛነት" የሚወንጅልበትና የሚያስርበት ምክንያት የአገሪቱን ግዛታዊ አንድነት ለማስከበር አይደለም። የደሃውን ሕዝብ ህይወት ለማሻሻል፤ ለወጣቱ ትውልድ እድል ለመክፈት አለመሆኑ አይተናል። ገበሬውን የመሬቱ ባለቤት ለማድረግ አይደለም። የኢትዮጵያ ወጣት ትውልድ ራሱን ረድቶ አገሩን ለማጠናከር የሚችለው በመደጋገፍ ብቻ መሆኑ ይታወቃል። ህወሓት/ኢህአዴግ መደጋገፍን በጎሳ ወስኖታል። የሚያደርገው በፍጥነት ከሚያድጉ አገሮች ተጻራሪ ነው። ወጣቱን በጎሳ፤ በሃይማኖትና በስራ አቀጣጠር ከፋፍሎታል። የኬንያ ወጣቶች "በጎሳ መከፋፈል ለሁላችንም ይጎዳል" ይላሉ። የኢትዮጵያ ወጣቶች ለመነጋገር አይችሉም። በሚቀጥሉት ሙቶ አመታት፤ በአገሩ፤ የትኛው ወጣት የራሱን እድል ወሳኝ እንደሚሆን ለመገመት አያዳግትም። የኬንያ ወጣት የተሻለ እድል እንዳለው አንጠራጠርም። የህወሓት የበላዮች የወደፊቱን የሚያዩት ከመደጋገፍ በሚመጣ ጥቅም መነጸር አይደለም። እአአ በ July, 2012 "የትግራይ ሰማእታት ቀን" ሲከበር፤ ህወሓት ያቀረበው "ዘገባ ዘጠና በሙቶ የሚሆነው የትግራይ ገበሬ ዘመናዊ የውሓ አጠቃቀም መሰረት እንዳለው ተናግሯል። ሶስት ሙቶ ሺህ ወጣቶች ስራ እንዳገኙ አውርቷል። መንግሥት ለደሃ ገበሬዎችና ለወጣቶች ብድርና ጉልምስና" እንደሚሰጥ ገልጿል። መስጠቱ አያከራክርም። የሚያከራክረው በቋንቋ የተመሰረተው አድልዎ ነው። የአፋር፤ የኦሞ ሸለቆ፤ የቤኒ ሻንጉል፤ የጋምቤላ ወዘተ ገበሬና ወጣት ተመሳሳይ ድጋፍ ያስፈልገዋል። ለፖለቲካ ስልጣን እድሜ የትግራይን ክልል ለይቶ "ዘመናዊ ማድረግ" የተዛባ ኢኮኖሚ ፈጥሯል። ሌላው ወደ ኋላ ከቀረ፤ የትግራይ ክልል እየቆየ ይጎዳል። ገበያ አይኖረውም። አንዱ የህወሓትን አመራር ከሌላው ዓለም በጣም የተለየ የሚያደርገው ይህ <u>አይነቱ የጎሳ፤ የግልሰብና የክልል እድገት አድልዎ ነው።</u> የፖለቲካ ስልጣን ቁንጮ ይዞ ለራስ ጎሳ ወይንም ብሄር በተከታታይ ከፍተኛውን እርዳታና የአገር ባጀት ፈሰስ ማድረግ አይን ያወጣ ጠባብ ጎሰኛነት ነው። በህብረተሰቡ መካከል እያደገ የመጣውን ቂም ያባብሰዋል። አብሮ ለማደግና በሰላም ለመኖር የሚደረገውን ጥረት ያዳከመዋል።

<u>በግልጽና በሕግ የበላይነት</u> የሚገዛ የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም አለመኖሩ ህብረተሰቡን ጎድቶታል። ይህ ከነጻ ተቋሞች አለመኖር ጋር ግንኙነት አለው። ዓለም ባንክ ስለ ኬንያና ስለ ኢትዮጵያ የአገዛዝ ክፍተቶች ያወጣው ዘገባ፤ "የመንግሥት አመራር እምነት፤ የዘመናዊ ኢኮኖሚ አስተዳደር ችሎታና ብቃት አለመኖር" ይገኙበታል። እነዚህ ክፍተቶች የተባባሱበት ዋና ምክንያት የሕግ የበላይነት ስለሌለ ነው። አምባገነን እንደመሆኑ መጠን፤ ገዢው ፓርቲ የነዚህን

ከፍተቶች አስፈላጊነት አይቀበልም። የሕግ የበላይነት፤ የማህበረሰብና የኃይማኖት ነጻነት፤ የፐሬስ ነጻነት፤ የመናገር፤ የመሰብሰብ፤ የመንቀሳቀስ፤ የመቃወም ወዘተ ነጻነቶች በሙሉ ከልከሏል። እነዚህን ሠብአዊ መብቶች መከልከል የግል ኢኮኖሚ ባለ ኃብትነት ጥቅም አለው። የተፈጥሮ ሃብት እንደልብ "ለመሸጥ፤ ለመለወጥና ለማከራየት" ያስችላል። "ነጻ የሆነ ብሄራዊ ተቋምና የህግ የበላይነት" ወዘተ አለመኖራቸው የተፈጥሮ ሃብት በተፈለገው፤ ግልጽነትና ሃላፊነት በሌለው መንገድ እንዲሽከረከሩ ይረዳል። ጉቦ፤ አድልዎና ሙስና ተቋማዊ (Institutionalized) ሆነዋል። ይህን በግልጽ የምናየው በተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀምና በባጀት አስተዳደር ነው። በተለይ ለኪራይ ሰብሳቢነት፤ ለአድልዎ፤ ለጉቦና ለሙስና መባባስ እድል ከፋች ለሆነው የከተማና የገጠር መሬት ግልጽ አመራር የለም። የኢትዮጵያ የመሬትና የውሐ ጥሪት ለዘላቂና ለሁሉ-አቀፍ ልማት ቁልፍ ነው። ኢትዮጵያ የብዙ ሰው ኃይል፤ ባህል፤ ቅርሶች፤ ማእደን፤ ለም መሬትና ውሃ ባለፀጋ መሆኗን ማንም አይክድም። ሁሉም ለአገሪቱና ለመላው ሕዝብ ጥቅም ከዋሉ ረሃብና ድህነት ይጠፋሉ። አገሪቱ ለከፍተኛ እድገትና ልማት መሰረት ትጥላለች። ኢትዮጵያ ደሃና ረሃብተኛ መሆን የለባትም። ደሃ ያደረጋት የአገዛዝ ግፈኛ ስርአት ነው። የተፈጥሮ ሃብት መኖሩ ብቻ አንድን አገር ከድህነትና ከረሃብ ነጻ አያደርገውም። ነጻ የሚያደርገው የአጠቃቀሙ ስልት ነው። ተጠንቅቆ መጠቀም ለተከታታይ ትውልድ የተሻለ ህይወት ወሳኝ ነው። የማህበረሰባዊና አካባቢያዊ (Social and Environmental Sustainabiltiy and Value added) ዘላቂነት የአገዛዝን ተጠሪነትና ሃላፊነት ይጠይቃል። በሕግ የማይዳኙ አትራፊዎች ለዘላቂነት ግድ የላቸውም። በአንጻሩ፤ ባለቤትነቱ በሕግ የተረጋገጠለት ኢትዮጵያዊ የተፈጥሮ ሃብቱን ተንከባክቦ እንደሚይዝ አንጠራጠርም። ፒተር ጊልስ የተባለ የኢኮኖሚ መብቶች ጠበቃ፤ ስለ ኢትዮጵያ ለም መሬት፤ ዝናብና ወንዝ፤ በሌላ በኩል አስከፊና ተደጋጋሚ ረሃብ ሲናገር እንዲህ ብሏል። "የተከታታይ ረሃብ መነሻ የዝናብ አለመኖር ሳይሆን የገዢዎች/መሪዎች ደካማነትና አፋኝነት ነው።"

ደሃነትና ረሃብ ሊወገድ ባለመቻሉ፤ ዛሬ በኢትዮጵያ ከሃያ ሽህ በላይ የውጭ በጎ አድራጊ ግለሰቦችና ድርጅቶች አገሪቱን ወደ "ልማት ላቦራቶሪ" ለውጠዋታል። ሆኖም ፍጹም ደሃነት፤ ረሃብና ስደት ገብደድ አላሉም። ፒተር ጊልስ (Famine and Foreigners and Human Rights Watch, Development without Freedom) እንዳሳዩት የኢትዮጵያ ደሃና ሌላ ክፍል የባለቤትነት፤ የመወሰን፤ የመምረጥና የመመረጥ መብት አለመከበር ለአገሪቱ ኋላ ቀርነትና ለአብዛኛው ሕዝብ ድህነት ምክንያት ሆነዋል። የታወቀው የልማት አኪኖሚስት፤ አማርትያ ሴን "ዲሞክርሳዊ አገዛዝ ባለበት አገር የረሃብ ሰቆቃ የተለመደ አይደለም።" አስቃቂ ረሃብ የተለመደው የዜጎች መብት በሕግ ባልተከበረባቸው አምባገነናዊ አገዛዞች ነው። በዚህ መጽሃፍ እንዳሳየነው፤ በእነዚህ አገዛዞች የፈለገው እርዳታ ቢሰጥ፤ የፈለገውን ያህል ሊጋሶች ቢንቀሳቀሱ፤ በአብዛኛው የሚያጎለምሱት የጥቂቶችን ኪስ ነው። ለዚህ የእርሻ መሬት አጠቃቀምን እንይ።

የመሬት አስተዳደር የሙስና ምሰሶ ሆኗል

የተፈጥሮ ሃብት ቁጥጥር ለአምባገነናዊ ስርአት ዋና መሳሪያ ነው። የኢትዮጵያን ለም መሬት፤ ወንዝ፤ ጅረቶችና ሌላ የተፈጥሮ ሃብት ጥቅምና አጠቃቀም ከአገዛዙ ለይተን ለማየት አንችልም። ባለፉት አምስት አመታት፤ ገዢው ፓርቲ ጥናት ሳያደርግ፤ የማህበረሰብና የአካባቢ እቅድ ሳያወጣ፤ ሕዝብ ሳይማከርበት ብዙ ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለውጭና ለአገር ውስጥ ኢንቬስተሮች አስተላልፏል። ያስተላለፈበት የእድገት ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

- የኢትዮጵያን እርሻ ዘመናዊ ለማድረግ (The technology transfer argument).
- ለአገሪቱ የምግብ ዋስትና ለመፍጠር (The food self-sufficiency and security argument).
- ለድሃው የስራ እድል ለመፍጠር (The employment generation argument).
- ለመንግሥት አስተማማኝ የውጭ ምንዛሬ ፈሰስ ለመመስረት (The foreign exchange inflow argument) እና፤
- ኢትዮጵያን ወደ መካከለኛ መደብ አገርነት ለማሸጋገር (The middle income country (MIC) status argument).

የእርሻ መሬትና የወንዝ ውድድር መነሻ

ገጠሩን ማልማት አለብን የሚለው አስተሳሰብ የሚደገፍ ነው። አሁን የተያዘው ገዢው ፓርቲ ባለፉት ሃያ ሶስት አመታት ከሞከረው የልማት እቅድ አይለይም። የገጠሩ ኢኮኖሚ የማምረት ሃይል ካልጨመረና ለሌላው መጋቢ ካልሆነ፤ የገጠሩ ሕዝብ ኑሮ በፍጥነት አይሻሻልም። ለጋሶች የዛሬ ሃያ አመት "ምን አደረግን፤ ለምን ድህነትና ረሃብ" አልጠፋም ማለታቸው አይቀርም። አብዛኛው እርዳታ የሚሰጠው ደሃውን ከድህነት ነጻ ለማውጣት ነው። የውጭ ኢንቬስተሮች የእርሻ መሬት የፈለጉበት የራሳቸው ምክንያት አለ። ትርፍ ለማግኘትና ለራሳቸው ሕዝቦች የምግብ ዋስትና ለማመቻቸት ነው። በ2007-2008 በብዙ አገሮች የምግብ ዋጋ ግሽበት ወደ ሰማይ ነጥሮ ነበር። ለአምራች አገሮች ገፀ-በረከት፤ ለሸማቾች ጨለማ የሆነበት ጊዜ ነበር። በባንግላደሽ፤ በግብፅ፤ በሃይቲ፤ በሜክሲኮ፤ በቱኒዚያ ወዘተ የምግብ ሰላማዊ ሰልፍ ጦፈ። በሃይቲና በማዳጋስካር መንግስታት ተገለበጡ። ይህ ክስተት ሸማች አገሮችን ውጥረት ውስጥ አስገባቸው። የሳውዲ፤ የቻይና፤ የህንድ፤ የደቡብ ኮሪያ ወዘተ መንግስታትና ኩባንያዎች የለም መሬት ፍለጋ ጀመሩ። ዋናው መወዳደሪያ የአፍሪካ አህጉር ሆነ። ሁኔታውን ያባባሰው የዓለም ሕዝብ ቁጥር ዛሬ ካለው ሠባት ቢሊዮን ከአርባ አመት በኋላ ወደ ዘጠኝ ቢሊዮን ይሸጋገራል። በከተማ የሚኖረው ሕዝብ ቁጥር እየጨመረ ይሄዳል የሚሉ ይገኙበታል። የሕዝብን ቁጥርና ወደ ከተማ መንቀሳቀስ ማንም መንግስት ሊቆጣጠረው አይችልም። አምሳ በመቶ የሚሆነው የዓለም ሕዝብ ዛሬ ከተሜ ነው። በታዳጊ አገሮች በቀን መቶ ሰማንያ ሽህ ሰው ወደ ከተማ ይሰደዳል። በአፍሪካ አርባ በመቶ የሚሆነው ሕዝብ ከተማ ይኖራል። የተባበሩት መንግስታት ጥናት፤ የዛሬ አርባ አመት፤ አንድ ቢሊዮን አፍሪካውያን ከተሜ ይሆናሉ ይላል። ኢትዮጵያ ከዚህ የሕዝብ እንቅስቃሴና ስርጭት ውጭ ልትሆን አትችልም። ከተሜነትና የሕዝብ ስርጭት የማይቀር የዘመናዊነት ምልክት ሆኗል። ስለዚህ የገጠር ኢኮኖሚው ዘመናዊ መሆን ለከተሜነት ቁልፍ ነው። መዋቅራዊ ለውጥ ያስፈልጋል፤ እንዱስትሪ መስፋፋት አለበት የምንለው ይኬን በማጤን ነው። ከተሜነት ምግብ ያስፈልገዋል። ውሃ ያስፈልገዋል ወዘተ። የከተማው ኢኮኖሚ ዘመናዊነት ከገጠሩ ጋር አብሮ መራመድ አለበት። በከተማ የስራ እድል ከፋች የሆነ ኢኮኖሚ ካልተመሰረተና ይህን ኢኮኖሚ የሚደግፍ መሰረተ ልማት--መንገድ፤ ቤት፤ መጸዳጃ፤ መጓጓዣ፤ የውሃ ግድብ ወዘተ- አሁን ካልተሰራ ችግሩ እየተባባሰ ይሄዳል። ኢትዮጵያ ገና አልተዘጋጀችም። የተሃድሶን ግድብ የምናየው ከዚህ አንፃር ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ችግር ገጠሬ ወይንም ከተሜ አይለይም። ሁሉም የምግብና የሌሎች እጥረቶች ሰቆቃ ይታዩበታል። ቢያንስ አብዛኛው ደሃ በቀን አንድ ምግብ ለማግኘት ይቸገራል። ልዩ ልዩ የዓለም ባንክ ጥናቶች የሚያሳዩት፤ የገጠር ደሃነትና ረሃብ ጥልቀት እንደያዘ ነው። (Poverty and Well-being is one the most exhaustive studies on rural poverty in Ethiopia.) ከሰባት ሚሊዮን የበለጠ የገጠር ሕዝብ በውጭ የምግብ እርዳታ ይኖራል። የገጠሩ ነዋሪ ኑሮውን ሊያሻሽልና ከረሃብ ነጻ ሊሆን የሚችለው በተከታታይ እርዳታ አይደለም። የመሬቱ ባለቤት ሆኖ ምርቱንና ገቢውን ሲያሳድግ ብቻ ነው። ከገጠር ወደ ከተማ የሚንቀሳቀሰው በያመቱ ብዙ መቶ ሽህ ሕዝብ በከተማ የስራና የገቢ አማራጮች ያስፈልጉታል። ህወሓት መቀሌ እድል የፈጠረው ይህን ችግር ለመወጣት ነው። ለቀረው ኢትዮጵያዊ ወጣት ለአዲስ ኃብታሞች ቤት ለመስራት ወዘተ "ድንጋይ መፍለጥ" ብቻ አማራጩ ሊሆን አይችልም። በገጠር ሆነ በከተማ አዲስ እድሎች ሊስፋፉ የሚችሉት የመሬትና የሌላ ቁሳቁስ ባለቤትነት በህግ ሲረጋገጥ፤ ሕዝብ እንደልቡ ለመንቀሳቀስ ሲችል፤ መንግሥትና ባንኮች ብድር፤ የውጭ ምንዛሬና ሌሎች ግብአቶች ያለ አድልዎና ሙስና ሲሰጡ፤ የግሉ ክፍል በፍጥነት እያደገ ብዙ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ሲቀጥር ነው።

ይህ፤ በሕዝብ ህይወትና ኑሮ ላይ የተመሰረተ ሌሎች አገሮች የሚጠቀሙበት የልማት መንገድ ነው። በገጠር ያለው የእርሻ ኢኮኖሚ በሌሎች አገሮች የምግብ ምርትን ያሳደገው አይነት የአረንጓዴ አብዮት (Green Revolution) ድጋፍ ያስፈልገዋል። ይህ አብዮት ከሕዝብ ተሳትፎ ጋር አብሮ የሚሄድ ነው። የገዢው ፓርቲ ለፖለቲካ የበላይነት የሚጠቀምበት መንገድ ባለፉት ሃያ ሶስት አመታት ተሞክሮ መዋቅራዊ ለውጥና የምርት ውጤት አላመጣም። ያተኮረው ከፖለቲካ ቁጥጥር ላይ ነው። የእርሻ ምርት አለመጨመሩና በአገር ውስጥ የሚሰራው የፍጆት እቃ ከሕዝብ ፍላጎትና የመግዛት አቅም ጋር ተመጣጥኖ አለመሄዱ አያከራክርም። የአብዛኛው ሕዝብ የነፍስ ወከፍ ገቢ ከኑሮው ጋር አልተመጣጠነም። እድገት አለ ቢባልም፤ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የገቢ ደሃ ነው። ለሕዝብ፤ በተለይ፤ ለአምራቹ ክፍል ያልተቆጠበ የፖሊሲና የግብአቶች ድጋፍ በመስጠት ፋንታ፤ የምርት መሬትና ውሃ የሚገኝባቸው ቦታዎች እየተቸረቸሩ ለህንዶች፤ ለሳውዲዎች፤ ለቻይናዎች፤ ለግብጾች፤ ለአርባና ለዘጠና ዘጠኝ አመታት፤ በዝቅተኛ ዋጋና ኪራይ ተሰጥተዋል። ይህ ጨካኝ ፖሊሲ ደሃነትን፤ ስራ አጥነትን አያስወግድም። የምግብ ዋስትና፤ የስራ እድል፤ የቴክኖሎጂ ማስፋፋትና የመካከለኛ ገቢ አገር ዋስትና አላስገኘም። ዋስትና ያስገኘው ለአንዱ የመንግሥት አላማ ነው። ለገዢው ፓርቲ የውጭ ምንዛሬ አላማ ስኬታማ አዳርጎለታል። አንድ፤ በስራ እድል በኩል አንድ ሄክታር መሬት ሲሸጥ የሚያስገኘው የስራ እድል 0.005 ሰራተኛ ነው። በዚህ አይነት ለብዙ ሽህ ኢትዮጵያውያን የስራ እድል ለመክፈት "ኢትዮጵያን በሙሉ መሸጥ"፤ ቢያንስ ብዙ ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለሳውዲዎችና ለህንዶች መቸርቸር ያስፈልጋል። ሁለት፤ እስካሁን በጋምቤላና በቤኒ-ሻንጉል-ጉሙዝ የሚያመርቱት የውጭ ኢኒቬስተሮች አንድ ዘመናዊ መሳሪያ ለደሃ

ገበሬ አልሰጡም። አንድ ፋብሪካ አልከፈቱም። አንድ የዘመናዊ እርሻ ማሰልጠኛ ተቋም አልሰሩም። ብዙ ቢሊዮን ዶላር ለገዢው ፓርቲ አስገብተዋል። ይህ ከደሃው መሬት ሽያጭ የሚገኝ የውጭ ምንዛሬው ለምን ብሄራዊና ማህበረሰብአዊ ጥቅም እንደዋለ አይታወቅም። ደጋግመን የጎሳ አድልዎ ለፍትሃዊ ልማት ማነቆ ነው የምንልበት ዋና ምክንያት፤ የስራ እድል ለአብዛኛው ወጣት አለመድረሱን በማየት ጭምር ነው።

የኢትዮጵያ መንግሥት ከደሃው የበለጠ የውጭ ኢንቬስተሮችን መርጧል

ለውጭ ኢንቬስተሮች፤ እነደ ኢትዮጵያ መንግሥት ያለ ተስማሚና ጋባዥ የለም። የፈለጉትን ሁሉ በቀላሉ ያገኛሉ። ማድረግ ያለባቸው ኪራይ መክፈል ነው። ኪራይ ለሚከፍል ማንኛውም ነገር ይሸጣል። የተፈጥሮ ሃብት ልክ እንደሚተካ ሃብት በጅምላ ይሸጣል። አገዛዙ ይህን የሚያደርገው በምዝበራ ዓለም ውስጥ ስለሚኖር ነው። የታወቀው ኮሪያዊ ኢኮኖሚስት፤ ሃ-ጁን ቻንግ፤ (The Bad Samaritans) "አምባገነናዊ አገዛዝም ቢሆንም--እንደ ኮሪያ ማለት ነው--አመራሩ አገር ወዳድ ከሆነ "ለመጀመሪያዎቹ የእድገት አስርት አመታት ታዳጊ አገሮች የውስጥ እድገት ምሰሶ የሆኑትን የተፈጥሮ ሃብትና የምርት መሰላሎች ለማንም የውጭ ኢንቬስተር አያስረክቡም። ደቡብ ኮርያ፤ ፊንላንድ፤ ብራዚል። መንግሥት የአገር ውስጥ አምራቾችን (ገበሬዎችን ይጨምራል) መንከባከብና እንዲያድጉ ማድረግ ዋናው ስራው ነው" ይላል። ሌሎችም የእድገት ምሁራን ይህን ይጋራሉ። ዴቪድ ሮዝኮፍ The Global Power Elite and the World they are Making በተባለው መጽሃፉ ያቀረበው ትምህርታዊ ነው። በኢትዮጵያ በጥቂት የጠባብ ጎሰኛ የበላዮችና በኢንቬስተሮች መካከል ያለውን የጥቅም ግንኙነት እንዲህ ሲል ገልጾታል። "የውጭ ከበርቴዎችና ትርፍ ፈላጊዎች የትርፍ ሥራ ሊሰሩ የሚችሉት አገር ውስጥ ካሉ ኪራይ ፈላጊዎች ጋር የትርፍ ስራ ተጋርተው እንዲሰሩ አገር ውስጥ ያሉ ሁኔታዎች ስለተመቻቹ ነው" ብሷል። መለስ ያዋቀረው ስርአት ለውጭ ኢንቪስተሮችና መንግሥታት አገልጋይ ሆኖ አግኝተነዋል። ይህ የተያያዘና የተደራጀ የኪራይ ሰብሳቢነት ተግባር አዲስ የሃብታምና የመደብ ልዩነቶች ፈጥሯል። ኃብታም የመንግሥት ባለስልጣናት በተባባሪነት ለለም መሬትና ወንዞች መሸጋገርያ ቁልፍ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛሉ። የሳውዲ አረቢያ መንግሥት ምሳሌ ነው።

የገዢው ፓርቲ የበላዮች ከካፒታሊዝም ጋር ያለውን ቁርኝነት የግል ጥቅም ካወቁበት ቆይቷል።  የኢትዮጵያ ኋላ ቀርነት፤ ደሃነትና ረሃብ ያለ ውጭ መዋእለ ንዋይ ፍንከች አይልም ይላሉ። ጥያቄው በምን አይነት ውል፤ ለማን ጥቅም፤ በምን የመሻሻል መለኪያ? የጀርመን መጽሄት፤ ስፒግል በሚገባ አስቀምጦታል። "የምግብ አቅርቦት እየቀነሰ ሲሄድ ባለፀጋዎች በጣም ደካማና በአምባገነኖች የሚገዙ ደሃ አገሮችን መፈለግ አለባቸው። እነዚህ ባለፀጋዎች (ኢንቬስተሮች) የሚዳኙት በሕግ የበላይነት፤ በበጎ አድራጊነት አይደለም። በሁለት ነገሮች ነው። "አንድ፤ የራሳቸውን ህብረተሰብ የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ። ሁለት፤ ለራሳቸው ትርፍ ማግኘት። የአካባቢው መበላሸትና መውደም ጉዳያቸው አይደለም። የነዋሪው ህይወት መናጋት አያሳስባቸውም።" በኢትዮጵያ፤ ለነዋሪው ሕዝብ የሚታገል መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት የለም። ሕዝቡ የመንግሥትን ውሳኔ ላለመቀበል መብት የለውም። የነጻ ፕሬስ የለም። ገዢው ፓርቲና የውጭ ባለኃብቶች እጅና ጓንት ሆነው ለመስራት የቻሉት ለዚህ ነው። የጋምቤላ ሕዝብ መሬት እየተሸነሸነ፤ ዛሬ ህንዶች ስድስት መቶ ሽህ ሄክታር መሬት ተረክበዋል። የኢትዮጵያ መንግሥት እስካሁን ብቻ ፈረንሳይን የሚያህል ለም መሬትና ውሃ ለኢንቬስተሮች አስረክቧል። የመቃወም መብት የለም። ለጋሶችም የመንግሥት ቃል ተቀብለው መጓዝ ልምዳቸው ሆኗል። የአሜሪካና የዓለም ባንክ ድርጅቶች ነዋሪዎችን ሌላ ቦታ "በመንደር" ለማቋቋም ድጋፍ ይሰጣሉ። ሁኔታውን አባብሰውታል። ባለፈው አመት የደቡብ ሱዳን ነጻ አውጭ ግንባር መሪ የነበሩ እንዲህ ብለዋል። "ይህ የመሬት ድለላና ድርድር እኮ የሚካሄደው አፍሪካ ነው። መልክዓ ምድሩ ልክ ማፍያ የሚያስተዳድረው አገር ይመስላል። እኔም እንደ ማፍያ አለቃ እቆጠራለሁ። የችግሩ ተባባሪ ነኝ።" በኢትዮጵያ እንደዚህ ብሎ ደፍሮ የሚናገር የመንግሥት መሪ የለም።

አገዛዙና የጥቂት የበላዮች የኢኮኖሚ የበላይነት ያመጣውን ብሄራዊ ችግር በሁለት መጽሃፎች አቅርበናል። "Endemic Poverty in Ethiopia that Globalization won't tackle but Ethiopians can and 'The Deal of the Century-land grab in Ethiopia." በለም መሬት የሚታየው ድለላና የምስጢር ድርድር ሌላ ተባባሪ ጥሪትን፤ ማለትም ውሃን ለመቆጣጠር መሆኑን አሳይተናል። ለም መሬትና ውሃ አብረው የሚታዩ የአገርና የሕዝብ እድገት መሰረቶች፤ የኑሮ ማሻሻያ ምሰሶዎች ናቸው። ሰው ያለነዚህ ጥሪቶች ለመኖር አይችልም። ኢትዮጵያ የምስራቅ አፍሪካ የውሓ ክምችት መነሻ ናት። የመሬት፤ ውሃና ሌሎች የተፈጥሮ ጥሪቶች ለማን ይጠቅማሉ፤ ማንን ይጎዳሉ ብሎ ማሰብ ለአገሪቱ ደህንነትና ለአብዛኛው ሕዝብ የኑሮ መሻሻል መሰረት መሆናንቸውን መገንዘብ አስፈላጊ ነው።  ቀጣይነትና ፍትሃዊነት ያለው ልማት ሊመሰረት የሚችለው የተፈጥሮ ሃብት ተጠቃሚው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲሆን ነው። የምግብ ዋስትና ሊገኝ የሚችለው መንግሥት የአገር ውስጥን ኢኮኖሚ በሕዝብ ተሳትፎና አጋርነት፤ ፈጣሪነት፤ ባለቤትነትና አምራችነት ሲመራ ነው። ፓል ኮሊየር፤ The Bottom Billion በተባለው መጽሃፉ እንዲህ ይላል። "የገጠር ገበሬዎች ራሳቸውን

ሊመግቡ የሚችሉት በፖለቲካ ቁጥጥር አይደለም። ብድር፤ ቴክኖሎጂ፤ ዜና፤ ገበያ፤ አገልግሎት፤ መሰረታዊ ልማትና የመሬት ባለቤትነት ሲያገኙ ነው።” በቬትናም፤ በታይላንድ፤ በፔሩና በሌሎች አገሮች፤ ዝቅተኛ አምራቾች ምርታቸውን ያሳደጉት መንግሥት ሁኔታዎችን ስላመቻቸ ነው። ማነቆነቱን ስላስወገደ፤ ጉቦን፤ አድልዎንና ሙስናን ስለተቆጣጠረ ነው። ይህም ሆኖ፤ የገጠር አምራቾች በተናጠል አገርን ሊያለሙና ደሃነትን ሊያጠፉ አይችሉም። ደጋፊ የሆነ እርሻን ከኢንዱስትሪ፤ ትምኅርትን ከስራ፤ መንገድንና ሙብራትን ከምርት ጋር የሚያያይዝ የኢኮኖሚ እቅድና ግብ ያስፈልጋል። ይህን ለማንቀሳቀስና ተከታታይነት ለመመስረት የሚቻለው አገር ወለድ የሆነ ብሄራዊ ከበርቴ ሲፈጠር ነው። ብሄራዊ ከበርቴው በመንግሥት እምነት ከሌለውና ከአገር ከወጣ ኢትዮጵያ የውጭ ኃይሎች መጫወቻ ትሆናለች። ካሩቱሪ፤ ሳውዲ ስታር ብሄራዊ ተቋሞች አይደሉም።

የኢትዮጵያ መንግሥት ለምርትና ለአገልግሎት ፍጥነት የፖሊሲና የመዋቅር ችግሮች ፈጣሪ ሆኗል። ሙስና ከፈጠራቸው ችግሮች አንዱ መሆኑን አሳይተናል። በመሬት አጠቃቀም ሰፊና በምስጢር የሚካሄድ አድልዎና ሙስና አለ። የውጭ መንግሥታትና ኩባንያዎች ምሰሶ የሆኑትን፤ የኢንዱስትሪ፤ የማእደን፤ የዘመናዊ እርሻ ተቋሞች ተቆጣጥረዋል። ቻይና የኢንዱስትሪ ማእከል--ያለ ኢትዮጵያውያን ተሳትፎ--አዲስ አበባ ስታቋቁም አዛዥ መሆኗን አስመስክራለች። የውጭ ኩባንያዎች አገር ወለድ ለሆኑ ድርጅቶችና ለማደግ ለሚፈልጉ ከበርቴዎች ማነቆ ይሆናሉ። የኮሪያና የሌሎች አገሮች እድገት እንዳሳየው፤ የውጭ ኩባንያዎች የበላይነት በአገር ውስጥ አንስተኛና ሊያድጉ የሚችሉ የግል ክፍሎችን ጫጩት እንደሆኑ እንዲቆዩ፤ አንዳንዶቹም እንዲጠፉ ያደርጋሉ። ይህ የዘመኑ የካፒታሊስት አስተዳደግና የበላይነት ሕግ ነው። ሊቆጣጠረው የሚችል ለአገርና ለወገን የቆመ አገር ወዳድ መንግሥት ብቻ ነው። የቬኔዝዌላው ሂውጎ ቻቬይ ያደረገው ይህን ብሄራዊ የበላይነት ነው። አገር ወለድ የሆነ ሃብታም፤ አገር ወለድ የሆነ የምርት ክፍል ወዘተ አስፈላጊ ነው። ደጋፊ የሆነ አመራር፤ የውጩ የውስጡን እንዳይጎዳውና እንዳያጠፋው መከታ ይሆናል። ለም መሬትንና ውሃን በከፍተኛ ደረጃ መንከባከብና ለውስጥ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ማዋል አማራጭ የሌለው ፖሊሲ ነው። እአአ Financial Times ስለ ሞዛምቢክ የዳቦ ዋጋ ሰላሳ በመቶ መጨመር ያወጣው፤ የዋጋ ግሽበት ብጥብጥና ሞት እንደሚያስከትል አሳስቧል። ልክ እንደ ኢትዮጵያ ሞዛምቢክ በአመት አስር በመቶ አድጋለች። የስኳር፤ የጥራ ጥሬ፤ የስጋ፤ የመድኃኒት እጥረት አብዛኛውን ሕዝብ አስቆጣውና አስነሳው። ብዙ ሰዎች ሞቱ። ተመልካቾች የደመደሙት፤ የሞዛምቢክ የፖሊሲና የመዋቅር ችግር “የመጭውን ጊዜ የሚጠብቅ ቦምብ ነው” የሚል ነው። በዚች በፍጥነት በምታድግ አገር ችግሩ በምግብ አልተወሰነም። የውሃ፤ የመብራት፤ የመገናኛ፤ የመጓጓዣ ወዘተ ዋጋ ሶስት ጊዜ ጨምሯል። ዓለም ባንክና አይኤምኤፍ “የሞዛምቢክ ኢኮኖሚ በአመት ከሰባት በመቶ በላይ አድጓል። በአፍሪካ አገሮች ፈጣን እድገት ከሚያሳዩ አንዷ ናት። ሌላዋ ኢትዮጵያ ናት” ወዘተ ብለው ነበር። ችግሩ እድገቱ የሕዝቡን አስፈላጊ ፍላጎት አላሟላም።

ኢትዮጵያና ሞዛምቢክ የምግብና የሌላ ዋጋ ግሽበትንና እጥረት እንወጣለን ብለው የጀመሩት የአገዛዝ ቅዥየት የተፈጥሮ ሃብታቸውን ለውጭ አገር መንግስታትና ኩባንያዎች መስጠታቸው ነው። በማንኛውም መስፈርት ይህ አመራር “ዘመናዊ ቅኝ ገዥዎችን መልሶ እንደመጋበዝ” ነው። ህንድ፤ ሳውዲ አረቢያ፤ ግብፅ ወዘተ ስለሆኑ ከቅኝ ገዢ የሚለያቸው የለም። ሞዛምቢክ መቶ ሽህ ሄክታር ለም መሬት አስረክባለች። ልክ እንደ ኢትዮጵያ አገር ወለድ ትናንሽና አንጋፋ የሆኑ ዘመናዊ እርሻዎችን ለማቋቋም ትችል ነበር። የሞዛምቢክን ለጊዜው ወደጎን ትተን የኢትዮጵያን እንመርምር። ገዢው ፓርቲ የሚጠቀምበት ዘዴ ሕገ-መንግሥቱን ነው። መሬቱን ሕዝብ አይኖርበትም ይልና መዓከላዊው መንግሥት መሬቱን ለአገር ልማት ቅድሚያ እሰጣለሁ በማለት ለመሸጥ፤ ለመለወጥ፤ ለማከራየት ያለውን ስልጣን ይጠቀማል። የተፈጥሮ ሃብትን የሕዝብ ያደረገው አዋጅ አሁን አንድ ጠባብ ጎሰኛ ፓርቲ-የከተማ ሆነ የገጠር መሬት-ለመቸርቸር እንደፈለገ ይጠቀምበታል። ለጥቂቶች ኃብት ማካበቻ ሆኗል። ብሄራዊ አላማው አገሪቱ አቅም ስለሌላት የውጭ ካፒታል ያላቸውን ጋብዞ ቴክኖሎጂ ለማስለመድ፤ የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ፤ ወዘተ የሚሉት በማስረጃ ስኬታማ አልሆኑም። የሚታወቁት የልማት ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

1. መሬቱን ሕዝብ አይኖርበትምና አይጠቀምበትም የሚለውን ኦክላንድ ኢንስቲቱት፤ጋርዲያን፤ ግሬይን፤ ሰርቫይቫል ኢንተርናሽናል፤ ወዘተ አስተባብለውታል። ሁለት ሚሊዮን የሚሆን የጋምቤላ፤ የኦጋዴን፤ የቤኒ-ሻንጉል ጉሙዝና የአፋር ሕዝብ ከመሬቱ ተወግዶ በአዲስ መንደሮች እንዲሰፍር እየተደረገ ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት ከህንዶችና ከሳውዲዎችጋር የተለየ ስምምነት እንዳለው እናውቃለን። የህንድ ኩባንያዎች የሃገራቸው ህብረተሰብ የማይደግፈውን የመሬትና የሰው ሃይል አጠቃቀም በኢትዮጵያ አጥቂ በሆነ ደረጃ ይጠቀማሉ። ከአምስት ቢሊዮን ዶላር በላይ በማፍሰስ ከስድስት መቶ ሽህ ሄክታር በላይ ለም መሬት ይዘዋል። ሶስት መቶ ሽህ ሄክታር በጋምቤላ ካሩቱሪ የተባለው ድርጅት ይዟል። ለያንዳንዱ ሄክታር በከፍተኛ የከፈለው አንድ ዶላር ከአስር ሳንቲም ነው። በ February 7, 2013, የጋርዲያኑ ጆን ቪዳል፤ ህንዶችና ሌሎች የውጭ ኢንቬስተሮች ለጋምቤላና ለሌሎች የመሬት ነጠቃ ክልሎች “ቅስፈት” ሆነዋል፤ አምባገነኑ መንግሥት የኢንቬስተሮችን ጥቅም ለመጠበቅ ሲል፤ “የነዋሪዎችን ኑሮና የአካባቢው ሁኔታ በሚያስፈራ ደረጃ

እንዲደመሰስ" እያደረገ ነው ብሏል። (The Ethiopian government "promotes the sale of the country's prime lands through repression, detention, rapes, beatings and evictons of indigenous people, and imprisonment of journalists and political opponents." ብዙ ታዛቢዎችን ያስደነገጣቸው፤ ገዢው ፓርቲ "አስራ አምስት በመቶ የሚሆነውን ለም መሬት ለውጭ ኢንቬስተሮች ለመሸጥ" መወሰኑ ነው። ሌላው፤ የወጣቱ ትውልድ ሽባነት ነው። አገር ውስጥና ከአገር ውጭ የሚኖረው ወጣት ትውልድ አደጋውን በቀላሉ ያየው ይመስላል። የሚጎዳው ራሱ ነው። በአንጻሩ፤ ኢንቬስተሮች ቢያንስ በአመት ሃያ አምስት በመቶ ትርፍ ያገኛሉ። የህንድ ሕዝብ ዝቅተኛ ዋጋ የሚከፈልበት ጥራ ጥሬና ሌላ ሰብል ይቀርብለታል። የኢትዮጵያ ሕዝብ መሬቱን አስረክቦ ይራባል። ይህ የኢኮኖሚ ወንጀል ነው። ሰላምና እርጋታ ሊፈጥር አይችልም። ነዋሪው ሕዝብ "መሬትህ ተወስዷል፤ ለአስቃቂ ረሃብ ትጋለጣለህ" የሚል ፍርድ በራሱ መንግሥት ሲበየንበት ቁጭ ብሎ የሚያይ አይመስለንም። ለጋሶች ለእውነተኛ እድገትና ለሰላም ከቆሙ "ለመሬት ልማት አዲስ መንደሮች ማቋቋም" የሚሰጥ እርዳታ ማቆም አለባቸው። አለበለዚያ የእርስ በእርስ ግጭት አይቀርም። ዓለም ባንክ "ለመንደረኝነት" የሚሰጠውን ድጋፉን ማቆም አለበት።

2. በስራ እድል በኩል ከመሬቱ የተፈናቀለው ዜጋ የቀን ሰራተኛ ሆኗል። የስራ ዋስትና የለውም። የሚከፈለው የቀን ደሞዝ ቢበዛ አንድ ዶላር ከሃያ አምስት ሳንቲም ነው። በዚህ ደሞዝ ቤተሰብ ለመደገፍ ያስቸግራል። ልጆች ለማስተማር አይቻልም። ከመሬታቸው የሚፈናቀሉት ድጋፍ አያገኙም።

3. ኢንቬስተሮች ለኢትዮጵያ ሕዝብ የምግብ ዋስትና እንዲያረጋግጡ የሚል ግዴታ የለም። ህንዶች፤ አረቦችና ሌሎች ምርታቸውን ለውጭ ገበያ ለማቅረብና ትርፋቸውን ለመውሰድ ሙሉ መብት አላቸው። የኢትዮጵያ መንግሥት የውጭ "ምንዛሬ ስለምናገኝ የሕዝቡን ምግብ ፍላጎት ከዓለም ገበያ እንሸምታለን" የሚል የተሳሳተ አመራር ተከትሏል። ልቦና የሚያስገድደው፤ አምርቶ ለአገሪቱ የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ፤ የተረፈውን ለህንዶች፤ ለአረቦችና ለሌች መሸጥ ነው። ካፒታል የለም ከተባለ ከኢንቬስተሮች ጋር በጋራ ሰርቶ ነዋሪዎችንና ኢንቬስተሮችን ለመጥቀም ይቻላል። ለም መሬቱና ውሃው የተሰጠው ምንም ጥቅም እንደሌለው ነው። ከጥቅሙ ጉዳቱ አመዝኖ ይታያል።

4. የገዢውፓርቲ፤ ሃላፊነት በጎደለው መልክ፤ እንደ "በረከት" የሰጠውና አሁንም የሚሰጠው መሬትና ውሃ፤ ዜግነትንና ክብርን ገፏል። ሙስናን፤ ድህነትንና ስደትን አስፋፍቷል። የረጅም ጊዜ የአካባቢ አደጋ በመፍጠር ላይ ነው። በጎሳ የተመሰረተ አድልዎና ጥላቻ አስፋፍቷል። የአገሪቱን ብሄራዊ አንድነት፤ እርጋታና ሰላም በመናድ ላይ ነው። ከገዢው ፓርቲ ቁጥጥር ነጻ የሆነ ለተፈጥሮ ሃብትና ለነዋሪዎች የሚቆረቆር "እንባ ጠባቂ" ተቋም የለም። ስለዚህ ግፉና በደሉ ተባብሷል። የአሁኑ ትውልድ ተቆርቋሪነት አያሳይም። በእኛ ግንዛቤ ይህ ሁሉ ተደምሮ አሰቃቂ ውጤት ያሳያል። የነዋሪዎች ህይወት መዛባቱ፤ የማይመለስ የአካባቢ ውድመት የሚካሄድ መሆኑ (catastrophic environmental and social destruction)፤ የወደፊቱ ትውልድ የኑሮው መሰረት የሆነውን ሃብት መነጠቁ። በጫትና ሌላ ሱስ የደነዘዘው ወጣት ትውልድና ከሃገሩ የተሰደደው ይኼን አደጋ በቀላሉ ማየቱ በታሪክ ያስጠይቀዋል።

5. በአብዛኛው ሲታይ፤ የውሎቹ ዝርዝር አይታወቅም። እውነቱና ጉዳቱ ወደፊት ይወጣል የሚል ግምት አለን። ሁለት አበይት ጉዳዮች ግልጽ ናቸው። አንድ፤ በፌደራልና በክልል ደረጃ የገዢው ፓርቲና ባለኃብቶች የተያያዘ ጥቅም አላቸው። ይህ ሁኔታ ሙስናን አጠናክሯል። የመሬት አሰጣጡና ውሎች ለአድልዎ፤ ለጉቦና ለፖለቲካ ቁጥጥር መሳሪያ ሆነዋል። ሁለት፤ ለአገሪቱና ለሕዝቡ እድገትና የኑሮ መሻሻል፤ ብሎም፤ ለምግብ ዋስትና አስተማማኝነት ውጤት አልታየም። ዘጠና በመቶ የሚሆነው ምርት ወደ ውጭ ስለሚላክ የአገሪቱን ጥገኝነት ያጠናክረዋል። ድህነትን ያባብሳል።

6. በሚቀጥሉት መቶ አመታት፤ የምግብ መሬትና ውሃ ከዘይትና ከወርቅ የበለጠ ዋጋ ይኖራቸዋል። ኢትዮጵያውያን ካወቁበት፤ አገራቸውን ወደ "እንቁ" ለመለወጥ ይችላሉ። ኢትዮጵያ ከሳውዲ አረቢያ፤ ከዱባይና ከሌሎች የአረብ አገሮች የበለጠ እድገት ለማሳየት ትችላለች። ስደትን ለማቆም ትችላለች። እንደ ኢትዮጵያ ያሉ የእርሻ መሬትና የውሃ የተፈጥሮ ሃብቶች ያላቸው አገሮችና ሕዝቦች ይከብራሉ። ይህን የሚወስነው ባለቤትነትና አጠቃቀም ነው። የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት መሬትና ሌላ የተፈጥሮ ሃብት የሕዝብ ነው ይላል። መንግሥት የተፈጥሮ ሃብትን በአደራ እየተንከባከበ፤ ለሕዝብ ጥቅም፤ማለትም፤ የኑሮ መሻሻል የማዋል ኃላፊነት አለበት የሚለው አንቀፅ 40 በገዢው ፓርቲ በተከታታይ ተጥሷል። የተፈጥሮ ሃብት የጋራ መሆኑ አክትሟል። የአገሪቱ ሃብት የአንድ ፓርቲና የደጋፊዎቹ ሆኗል። ለውጭ ከበርቴዎች የሚሰጠው ቅጥ ያጣ ድጋፍ ለአገሪቱ ደህንነትና ለሕዝቧ ሉአላዊነት፤ ፍትሃዊ እድገትና ለተከታታይ ትውልድ መሻሻል አደጋ ፈጥሯል። ህወሓት/ኢህአዴግ የረጅም ጊዜ ጥቅምን በአጭር ጊዜ ስልጣንና የጥቂቶች ባለጠጋነት ለውጦታል። ኢኮኖሚስት የህወሓትን አመራር የዘመናዊ ኢኮኖሚ "ደንቁርና" ያለው ለዚህ ነው። የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሃብት ለሕዝቧ ኑሮ መሻሻል አልዋለም።

አንድ ኢትዮጵያዊ የህግ ባለሞያ ባደረገው ጥናት፤ የመሬት ችርቻሮ ዘመቻ፤ ለእድገት፤ ለነዋሪዎች ኑሮ መሻሻልና ለስራ መፍጠር ማነቆ ሆኗል። ዓለም ባንክ ባደረገው ጥናት፤ Rising Interest in Farmland በኢትዮጵያ፤ የመሬት ሽሚያ ግልፅነት የሌለበት፤ የተጠቃሚውን ሕዝብ ሙብት የማያስጠብቅ፤ ለአካባቢው አደጋ የሚያመጣ፤ ለደሃው ነዋሪ ዋስትና የማይሰጥ ነው" ብሏል። እድገትና ኢንቬስትሜንት የተያያዘ መሆኑን ተቀብሎ፤ ጥቅሙ ለማን እንደሆነ በግልጽ አይታይም ይላል።

በሌላ በኩል፤ ጎልድማን ሳክስ፤ ሞርጋን ስታንሊ፤ ብላክ ሮክ ካልጋሪ ወዘተ የእርሻ ካፒታል ለኢትዮጵያ እድገትና ለደሃው ሕዝብ ኑሮ መሻሻል ይረዳል ብለዋል። እኛ የምንገነዘበው፤ የዓለም ካፒታል ዋናው ሚና ለኢንቬስተሮች ትርፍ ማስገኘት መሆኑን ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ምን ጥቅም እንደሚያገኝ አላብራሩም። ኢትዮጵያውያን የተፈጥሮ ሃብታቸው ባለቤት ካልሆኑ፤ ጥቅሙ ለሌች ይሆናል። ለሃገሪቱ ዘመናዊነትና ለመላው ሕዝብ ኑሮ መሻሻል የሚረዳው አስተማማኝ ፖሊሲ ገበሬዎችን፤ ነዋሪዎችን፤ የግል ባለ ካፒታሎችን፤ ስደተኛውን ወዘተ ማደራጀት፤ ማበረታታት፤ ማጎልመስ፤ የተፈጥሮ ሃብቱና መርቱ ባለቤት እንዲሆን ጥረት ማድረግ ነው። ኢትዮጵያውያን ዘመናዊ እርሻ ለማስፋፋት ችሎታ እንዳላቸው እናምናለን።

የኢትዮጵያን የተፈጥሮ ሃብት ማን በባለቤትነት ይዞታል?

የተፈጥሮ ሃብት፤ በተለይ የእርሻ መሬትና ውሃ የማይገኝ ጥሪት ወይንም ፀጋ ነው። ማን በባለቤትነት ይዞ ይጠቀምበታል የሚለው ጥያቄ በልማት መስፈርት ሲታይ ወሳኝ ነው። የመሬት ችርቻሮን ጉዳት በጥናት ያብራራው፤ የግሎባል ላንድ (መሬት) ፕሮጀክት ነው። የዚህ ተቋም ጥናት ቁጥር አንድ፤ በ2010 ያቀረበው ሃቅ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት የገባው ውል ለውጭ ባለኃብቶች የማምረትና ወደ ውጭ የመላክ ሙሉ ሙብት ሰጥቷቸዋል። ገዢው ፓርቲ ይህን ሙብት ከኢትዮጵያውያን ወስዶ ሲሰጥ ብዙ ግድፈቶችን ወደ ጎን ትቷል። ከህንዶችና ከሌሎች የበለጠ የኢትዮጵያ ገበሬዎች አካባቢያቸውን ያውቃሉ። ምን እንደሚበቅልና መቼ፤ ሰው፤ እንስሳና የተፈጥሮ ሃብት እንዴት አብረው እንደሚኖሩ፤ ተከታታይ ትውልድ ተፈጥሮን እንዴት እንደሚንከባከብ ያውቃሉ። ገዢው ፓርቲ ከነዋሪዎች ነጥቆ መሬት ሲሰጥ አብሮ ያጠፋው የማህበረሰብ ልምንድን፤ እውቀትን፤ ታሪክን፤ ባህልን፤ ማንነትን ነው። (Destruction of Social Capital). ይህ ልምድና እውቀት አንድ ጊዜ ከጠፋ መተኪያ የለውም። በሰሜን ኢትዮጵያና በሌሎች የሆነው የአካባቢ ውድመት ለም በሆኑ ክልሎች ይከሰታል። ይህን ስርአት ወለድ ጥፋት ስንመለከት፤ የኢትዮጵያ መንግሥት በማን ተማምኖ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የምግብ ዋስትና እቅድ አለኝ እንደሚል እንቆቅልሽ ሆኗል። የችግሩ መሰረት፤ ገዢው ፓርቲ የተፈጥሮ ሃብትን በሙሉ፤ በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም፤ ለራሱ ስላደረገው ነው። የፈጠረው ህገመንግሥት ይደግፈኛል ይላል። የተፈጥሮ ሃብት፤ የውጭ እርዳታና ሌላ ገቢ ሁሉ የገዢው ፓርቲ ሆኗል። ባለቤትነት የሌለው ሕዝብ በህይወቱ ለማዘዝ አይችልም። <u>አደገኛ ነው የምንለው፤ የተፈጥሮ ሃብት ከኢትዮጵያ ነዋሪዎች ተነጥቆ ለሌሎች ሲዘዋወር፤ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ፤ ሊመለስ የማይችል ቀውስ ስለሚያመጣ ነው።</u>

ጥናቱ፤ "የመሬት ድርድር የዛሬውን የባለቤትነት ሙብት አጠቃቀምና ሥርዓት በአናቱ አቁሞታል። በነዋሪው ሕዝብ ላይ አስቃቂ ችግር ፈጥሮበታል። ባለቤትነቱንና ማንነቱን ክዶታል" ብሏል። የተከታታይ ትውልድን እድል ዘግቶበታል። "ኢትዮጵያ፤ ማዳጋስካርና ሱዳን ወደፊት አደጋ ከሚደርስባቸው አገሮች መካከል ይገኙበታል" ሲል ደምድሟል። በግልጽ የሚታወቁትን የገዢው ፓርቲ የፈረማቸውን ሃያ ስድስት ውሎች መርምሮ፤ ቢያንስ ሶስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለውጭ ባለኃብቶች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንደተሰጠ አረጋግጧል። ቅድመ ሁኔታ ስንል፤ የመንግሥት ባለስልጣናት ያቀረቧቸውን--ዘመናዊ መሳሪያ ወይንም ቴክኖሎጂ ወደ ኢትዮጵያ ማስገባት፤ ለነዋሪዎች መሰረተ ልማት (ትምኅርት ቤት፤ የጤና ጣቢያ፤ የገጠር መንገድ፤ መፀዳጃ፤ ገበያ ወዘተ) መስራት፤ የትምኅርት እድል ማስፋፋትና በሌለበት ማቋቋም፤ ለደሃውና ስራ ለሌለው የስራ እድል መፍጠር፤ መሬታቸው ለተወሰደባቸው ተተኪ መሬት መስጠት፤ የውጭ ምንዛሬ ማግኘትና መልሶ ለነዋሪው ጥቅም ማዋልና የአካባቢው የተፈጥሮ ሃብት ተከታታይነት እንዲኖረው መጠባበቅ ይገኙበታል። እነዚህን የማህበረሰብ ጥቅሞች ስንመረምር ከውጭ ምንዛሬ በስተቀር ሌሎቹ አልተከበሩም። የችርቻሮው ጉዳት ሊቀነስበት የሚችል የፖሊሲ ዘዴ ነበር። ጥቂት መቶ ሄክታር መሬት በውድድር ተመርተው፤ አካባቢውን ጠብቀው፤ የነዋሪዎችን ጥቅም አክብረው፤ ትምኅርት አስፋፍተው ለመስራት ለሚፈልጉ ኢንቬስተሮች ለተወሰኑ--ቢበዛ ለሃያ አምስት አመታት--አከራይቶ ውጤቱን ማየት(Pilot) ማድረግ አማራጭ ነበር። አሁንም ነው። ዘላቂነት የሚኖረው ከነዋሪዎች ጋር ተነጋግሮ ጥቅምና ጉዳቱን መርምሮ የሚሰራ ፕሮጀክት ሲሆን ነው። ሊታረስ ከሚችለው ከሰባ አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት፤ ስድስት ሚሊዮን እንደሚሸጥ አሳውቋል። የዚህ ውጤት በ2009 የፋኦው ዴቪድ ሄልማን ያለው ስኬታማ እንደሆነ ያሳያል። "አስቡ፤ በረሃብ በምትታወቅ ኢትዮጵያ ባዶ ተሸከርካሪዎች ወደ አምራች ቦታዎች ሄደው የውጭ ኢንቬስተሮች የሚያመርቱትን ሰብል ጭነው ለውጭ ገበያ

ሲያቀርቡ ኢትዮጵያውያን ምን ይላሉ። የዚህ አደጋ ምን ይሆናል?” በተመሳሳይ፤ ናንሲ ማክዶናልድ አቡ ዳቢ ያየችውን ስትመዘግብ፤ “ያየሁት ፍራ ፍሬና ቅጠላ ቅጠል የመጣው በረሃብተኛነት ከምትታወቅ ኢትዮጵያ ነው” ብላ ነበር። የገዢው ፓርቲ የለም መሬትና የውሃ ችርቻሮ ውጤት ይህን ይመስላል። ስፋቱንና ጥልቀቱን ከደራሲው መጽሃፍ በተወሰደ ማስረጃ በሰንጠረዥ አንድ እናሳያለን።

ገዢውፓርቲ ሕዝብ ሳይነጋገርበት፤ የተያያዘ ብሄራዊ እቅድ ሳይነደፍና ባለሞያዎች ሳያጠኑት የእርሻ መሬትና ውሃ ከነዋሪዎች ነጥቆ መሸንሸንና መሸጥ ከጀመረበት ወቅት እአአ ከ2006/2007 ወዲህ ሰላሳ ስድስት አገሮች፤ ቢያንስ ዘጠኝ መቶ ፈቃድ ለተሰጣቸው የውጭ አገር ጥቅም ፈላጊ ግለሰቦችና ድርጅቶች የታወቀ አራት ሚሊዮን ሄክታር አስረክቧል። ሌላ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር እንደሚሰጥ ይገመታል። ይህ ሁሉ ሲሰጥ ሰላሳ ስድስት በመቶ የሚገመተው የቀረው ለእርሻ የሚለማ መሬት ለኢንቬስተሮች ይሰጣል ማለት ነው። አብዛኞዎቹ ወራሾች ህንዶች ናቸው--ካሩቱሪ፤ አልሚዳህ፤ ሮምቶን፤ ኢማሚ ባዮቴክ፤ ሩች፤ ሮምቶን፤ ሶናናሊ፤ ቢኤች አ፤ፓናሻ፤ ፓሎንጅ፤ ሻፑርጅ፤ ስፔንቴክስ፤ ወዘተ፤ ስማቸው በወሰዱት መሬት ላይ ሲታወቅ ልክ ፑንጃብ ያለን ይመስላል። እንጋፋው የሳውዲዎች ሁለ-ገብ ድርጅት ሳውዲ ስታር ሁለተኛውን ከፍተኛ መሬት ተረክቧል። የግብጹ ብሄራዊ ባንክ፤ የቻይናው ዴፌንዩአን ሰፋፊ መሬቶች ይዘዋል-- በተጨማሪ፤ የጀርመን፤ የካናዳና ሌሎች የበለጸጉ አገሮች ኩባንያዎች ከፍራ ፍሬ ዘይት ለመጨመቅና በሃገራቸው ለመሸጥ መሬት ገዝተዋል። ጋርዲያን የተባለው ጋዜጣ፤ ሳውዲ ስታር የወረሰውን መሬት ተምኖ ልክ “የቤልጅግን አገር ያክላል” በሚል መዝግቦታል።

ጋርዲያን፤ ለኢትዮጵያ የመሬት ነጠቃ “የሃያ አንደኛው መቶ አመት ውል (The Deal of the Century)” የሚል ስም የሰጠበት ስፋቱን፤ ጥልቀቱንና ብሄራዊ ጉዳቱን አይቶ ነው። ካሩቱሪ በጋምቤላ የያዘው መሬት “ሉክሰምበርግ” የተባለውን አገር ያክላል። በስፋቱ አንድ አገር የሚሆን መሬት የሚሸጥባት አገር ኢትዮጵያ ብቻ ናት። ካሩቱሪ በሄሊኮፕተር ጋምቤላን ዞሮ አይቶ፤ “የጥቁር ወርቅና እንቁ” ያለውን ሶስት ሽህ ኪሎሜትር እርዝመት ያለውን መሬት ከሰማይ በማየት ብቻ ለሄክታር አንድ ዶላር ከሃያ አምስት ሳንቲም ከፍሎበት ነበር። መንግሥት በዋጋው ተቆጭቶ፤ ውሉን እሰርዛለሁ ሲል፤ ለቀረው መሬት ካሩቱሪ ለሄክታር ስድስት ዶላር ከሰባ አምስት ሳንቲም ከፍሏል። በሰንጠረዥ አንድ እንዳሳየነው፤እስካሁን ገዢው ፓርቲ ለውጭ ኢንቬስተሮች የሰጠው መሬት ቢደመር ባህሬንን፤ ጓምን፤ ሉክሰምበርግን፤ ፖርቶ ሪኮን፤ ካታርን፤ ሲንጋፖርና ቶንጋን ያጠቃልላል። መንግሥትና ደጋፊዎቹ ለዚህ መልስ አላቸው። “ጠፍ መሬት” ቢሰጥና ቢለማ ምን አለበት የሚል። ይህን ፈለግ ይዘው ብዙ  ኢትዮጵያውያን ተመሳሰይ ግንዛቤ ያቀርባሉ። ለዚህ ጥያቄ አግባብ ያለው፤በማስረጃ የተደገፈ፤“ታላቁ የመሬት ስጦታ” የሚል በደራሲው የተዘጋጀ መጽሃፍ መልሱን እንደሰጠ እንተማመናለን። ለዚህ ክፍል ለአንባቢ የምንቃርበው ማስረጃ የሚከተለው ነው።

1. ቁጥሩ እየጨመረ ለሄደውና ለሚሄደው የኢትዮጵያ ሕዝብ የምግብ ዋስትና ሊያስገኝ የሚችለው ስድስት ሚሊዮን ሄክታር ለም መሬትና ውሃ ለውጭ ኢንቬስተሮች ሲሰጥ፤ ለኢትዮጵያውያን ገበሬዎችና ወደ ዘመናዊ እርሻ ለመግባት ለሚፈልጉና ለሚችሉ የአገር ኢንቬስተሮች መፈናፈኛ ነስቷቸዋል። የለም መሬትና ውሃ ፍላጎት በጣም ይጨምራል። የኢትዮጵያውያን ባለቤትነት አስፈላጊ ነው። በሰንጠረዥ አንድና ሁለት ያቀረብነው “ወረራ” የሚመስል የመሬት ሽንሸናና ሽያጭ አደጋውን ያሳያል። የመሬት ንግድ እንደ ሌላው አይደለም። ዜግነትን ያጠፋል።

2. ከማንኛውም ኃብት የበለጠ፤ ለም መሬትና ውሃ፤ የከተማ ቦታና ሽያጭ ለጉቦ፤ ለማጭበርበርና ለሙስና ቁልፍ ሆኗል። የኢትዮጵያውያን ባለቤትነት አለመኖር ሁኔታውን አባብሶታል።

3. በሰንጠረዥ አራት እንዳሳየነው፤ ገዢው ፓርቲ ከመሬት ችርቻሮ ብዙ ቢሊዮን ዶላር ሰብስቧል።

4. የኢትዮጵያ ወጣት ትውልድ--ለመስራት፤ ለማምረት፤ አዲስ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ፈጥሮ ወገኖቹን ለመቅጠር የሚችለው የሕዝብ ቁጥር ከአምሳ በመቶ በላይ ነው። ይህ የሕዝብ ስርጭት የተፈጥሮ ሃብት ለመጠቀም ካልቻለ እድሉ ስደት ወይንም ጥገኝነት ይሆናል። የእድገት መሰላል የሆኑትን ክፍሎች ለጥቂት ባለስልጣናትና ወደጆቻቸው፤ ለውጭ ኢንቬስተሮች ማስተላለፍ በአዲሱ ትውልድ ላይ የኢኮኖሚ ማግለል ወንጀል እንደ መፈጸም ነው።

ሰንጠረዥ አንድ፤ የመሬት ነጠቃና ሽንሸና (አዲስ ቅኝ ገዥነት)

| የክልል ስም | ለውጭ ኩባንያዎች የተሰጠ/የተከራየ ለም መሬት በሄክታር* |
|---|---|


| | |
|---|---|
| ትግራይ | የተሰጠ መሬት የለም |
| አፋር | 409,000 slated; National Bank of Egypt, 25,000 |
| አማራ | 175,000 (Pansha International, India, 2,500 ha) |
| ቤኒ-ሻንጉል ጉሙዝ | 1,149,000 (Saudi Star, 200,000 ha; Shapoorji (India) 50,000 ha; Spentex Industries (India), 25,000 ha; 200 foreign investors 271,000 ha) |
| ጋምቤላ | 1,800,000 (Saudi Star 500,000 (Saudi Arabia); Karuturi (India) 300,000; Ruchi Soya (India), 25,000, BHO Agro (India) 27,000, Sonannali Agro (India) 10,000 |
| ኦሮሚያ | 1,319,000 (የጂቡቲ መንግሥት) 3,000; Almidha (India), 28,000; Romton Ag. PLC (India) 30,000; Saudi Star ሰፊ ይዞታ አለው። 1,100 የውጭ ኢንቬስተሮች ሰፊ ይዞታ አላቸው። |
| ደቡብ | 300,000, Karuturi (India) 50,000 |
| ሶማሌ | 65,000, Dafengyuan (China), 25,000 |

*ለውጭ ኢንቬስተሮች ለመስጠት የታቀደውን ይጭመራል

ልዩ ልዩ ማስረጃዎች የሚያመለክቱት የኢትዮጵያ መንግሥት ቢያንስ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር ለም መሬትና ለዚህ የሚደግፍ ውሃ ለውጭ ኢንቬስተሮች እንደ ሽጠ ወይንም ቃል እንደ ገባ ነው። ኢትዮጵያውያን ከፈርኦኖች ዘመን ጀምሮ ሲታገለቡት የነበረው ለም መሬትና ወንዝ በገዢው ፓርቲ መንግሥት ለውጭ ኢንቬስተሮች እየተቸረቸረ ነው። የጊዜው ገደብ በዝቅተኛ ሃያ አምስት፤ በከፍተኛ ዘጠና ዘጠኝ አመታት ነው። የአገር ውስጥ ኢንቨስተሮችም የመሬት ሽንሽናና ነጠቃ ተጠቃሚ ሆነዋል። በጋምቤላ ብቻ፤ ቢያንስ አምስት መቶ ሄክታር ለትግራይ ተወላጆች እንደተሰጠ የኦክላንድ ኢንስቲቱተ ማስረጃ አቅርቧል።

ሰንጠረዥ ሁለት መንግሥት እስካሁን የሸጠውናና በተቀማጭ የያዘውን ያሳያል። ሰንጠረዡው የሚያሳየው፤ ኢትዮጵያ ሊታረስ ይችላል ከምትለው መሬት ምን ያህል እንደተሸጠና ወደፊት ምን ያህል ተጨማሪ እንደሚሸጥ ያመለክታል። አገር ውስጥ ላሉ ኢንቬስተሮች የተሰጠውን ወይንም ወደ ፊት የሚሰጠውን አይጨምርም። አገር ውስጥ ያለው ችርቻሮ ጎሣዊ መሆኑ አደገኛ ሁኔታ ፈጥሯል።

ሰንጠረዥ ሁለት፤ የተሸጠና ለጥበቃ “በባንክ” የተያዘ  ለም መሬት





የመሬት ነጠቃ፤ ሸንሸናና ሽያጭ የሚታይ ከመንግሥት "የእድገት አላማ" ብቻ አይደለም። እድገት ብቻውን የዜጎችን ኑሮ አላሻሻለም። መታየት ያለበት ከአገሪቱ፤ ከህብረተሰቧና ከነዋሪዎቹ ጥቅም፤ የኑሮ መሻሻልና ለተከታታይ ትውልድ ትተውት ከሚሄዱት የተፈጥሮና ቁሳቁስ ሃብት አንጻር ነው። የተሃድሶ ግድብ ስኬታማ ሲሆን እድገት ይጨምራል። የቤኒ ሻንጉል-ጉሙዝ ሕዝብ ይጠቀም አይጠቀም ገና አይታወቅም። በእኛ አመለካከት የነዋሪዎችን ኑሮ የማያሻሽል ፕሮጀክት ባለጠጋነት የሚፈጠረው ለባስልጣናት ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ የስራ እድል፤ የምግብ ዋስትና፤ የጤና፤ የትምኅርትና ሌሎች ፍላጎቶችና አገልግሎቶች ይጠይቃል። ለም መሬቱና ውሃው ለውጭ ኢንቬስተሮች ሲሰጡ፤ ለነዋሪዎቹና ለህብረተሰቡ የሚቀረው በጣም ይቀንሳል። አርሶ ለመኖር የሚፈልገው መሬት አይኖረውም። አስከፊ የሆነ የእርሻ መሬት ጥበት አለ።

በተፈጥሮ ኃብት አጠቃቀምና በሌላው መስፈርት ሲታይ፤ ገዢው ፓርቲ የኢትዮጵያውያንን የወደፊት እድል አደጋው ውስጥ አስገብቷል። የውጭ ምንዛሬ ጥቅም ብቻ መፈለግ አገር አያለማም። እአአ በ2000-2009 ገዢው ፓርቲ የውጭ ኢንቬስተሮች ለኢንቪስትመንታቸው ካወጡት ዘጠኝ ቢሊዮን ሁለት መቶ ሚሊዮን ዶላር አግኝቷል። ከዚያ ወዲህ እስከ 2010 መጨረሻ አራት ብሊዮን ዶላር ሰብስቧል። ይህ የውጭ ምንዛሬ መሰብሰብ ለጋምቤላ ሆነ ለሌላው የመሬት ነጠቃ በሰፊው ለተካሄደበት ሕዝብ ያስገኘው ጥቅም አይታይም። የሚታየው ለገዢው ፓርቲ ያስገኘው ጥቅም ነው። 81/

ሰንጠረዥ ሶስት፤ ከመሬት ሽያጭ የሚፈሰው የውጭ ምንዛሬ (Foreign Direct Investment)

(በቢሊዮን ዶላር)




አንባቢው እንዲገነዘበው የምንፈልገው መሰረታዊ ሃሳብ፤የዱሮዋ ብዙ የእርሻ መሬት የነበራትና የሕዝቧን ፍላጎት የምታሟላ ኢትዮጵያ ዛሬ የለችም። መሬቱ ተበልቷል። እየጠበበ ሄዷል። የእርስ በእርስ ግጭቶች መንስኤ ሆኗል። የመሬት አጠቃቀም አልተሻሻለም። ለገጠሩ ደሃ ሌላ አማራጭ የለውም። የሕዝቡ ቁጥር በሚያስደንቅ ሁኔታ ጨምሯል። ከሰባት እስከ አስራ ሶስት ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን በውጭ አገር የምግብ እርዳታ ይኖራሉ። የኢኮኖሚው መዋቅር ከዛሬ አምሳ አመት እምብዛም አልተለወጠም። የዋጋ ግሽበት ከዓለም ከፍተኛ ከሚባሉ አንዱ ነው። በዝቅተኛ ሲገመት አምሳ በመቶ፤ በከፍተኛ ሲገመት ሰማንያ በመቶ የሚሆነው ወጣት ፈጽሞ ስራ የለውም። ሃያ አምስት በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በህይወቱ ዘላቂነት ያለው ስራ ሰርቶ አያውቅም። ጥልቀት የሚያሳዩ መዋቅራዊና ፖሊሲ-ነክ ችግሮች አሉ። መንግሥት በእነዚህ ችግሮች ሌላ መዋቅራዊና ስርአታዊ መሰናክል ጨምሯል። አንድ የታወቀ ኢትዮጵያዊ ደራሲ ይህን ህወሓት/ኢህአዴግ የወለደውን፤ አሁን መዋቅራዊ የሆነውን ጠንቅ፤ “ኢህአዴግ እና ሙስና የአንድ ሳንቲም ግልባጮች” ናቸው ሲል በትክክል አስቀምጦታል። መንግሥት “ያልታረሰ መሬት አለ። ሕዝብ በዛ ይላል። ሕዝብ ስራ ጠፋ። ኑሮ ተወደደ” ይላል። መሬት ለሚያለሙት መስጠቱ ጥሩ ነው ለሚሉት ጥያቄ አለን። ኢትዮጵያ ዛሬ ዘጠና አራት ሚሊዮን ሕዝብ ለመመገብ ካልቻለች፤ የዛሬ አስራ ሶስት አመት የሕዝቡ ቁጥር አንድ መቶ አስራ ዘጠኝ ሚሊዮን ሲደርስ ምን ልትሆን ትችላለች ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው። የተባበሩት መንግስታት የወደፊት ዘገባ የሚያሳየው እአአ በ 2050 የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ሁለት መቶ ሰባ ስምንት ሚሊዮን ይደርሳል። ከፍተኛ ቁጥር ከሚኖራቸው አገሮች መካከል አንዷ ትሆናለች።

የኢትዮጵያ መንግሥት ዋና ሃላፊነት ምንድ ነው?

በየትኛውም ዓለም፤ አንድ አገር ጤናማ መሆኑ ወይንም አለመሆኑ የሚገመተው በልቶ በሚያድረው ወይንም በምግብ እጥረት በሚሰቃየው የሕዝብ ቁጥር ነው። በፍጥነት ያደጉት፤ እንደ ኮሪያ፤ ኢንዶኔዢያ፤ ታይላንድ፤ ማሌዢያ፤ ብራዚል፤ ቦትስዋና፤ ቻይና፤ ህንድ፤ ቬትናም ወዘተ የሚጋሩት የእድገት መስፈርት ፍጹም ረሃብንና ፍጹም ደሃነትን መቀነስ ነው። ህሊና ላለው ኢትዮጵያዊ፤ በከተማና በገጠር ረሃብ አይኑን አፍጥጦ ይታያል። ህጻን፤ ጎልማሳ፤ ሴት፤ ወንድ፤ ክርስቲያን፤ እስላም፤ ኦሮሞ፤ አማራ፤ ትግሬ ወዘተ አይለይም። የረሃብተኛ ወዝና ሰውነት ያስታውቃል። በአገርና በመንግሥት ያለውን እምነት ያጠፋል። ከሁሉም በላይ የተራበ ሰው ክብርና ሰብእነት ያጣል። አንድ ሃላፊነት የሚሰማው መንግሥት ከሁሉም እድገቶች በላይ ቅድሚያ የሚሰጠው፤ ገበሬዎችንና ሌሎችን አገር ወለድ አምራቾችን ማጎልመስና የምግብ ዋስትና በአፋጣኝ ስኬታማ ማድረግ ነው። ህወሓት፤ በትግራይ በማድረግ ላይ ያለው የተለየ የልማት ትኩረት ይህን ይመስላል። ሌሎችም ተመሳሳይ እድል ይገባቸዋል።

በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የተከሰተው የኢትዮጵያ መታወቂያ የሆነው "ታላቁ ረሃብ" የአንድ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያንን ህይወት ከቀሰፈ ወዲህ የምግብ ዋስትና ችግር አሁንም አልተፈታም። እትዮጵያ ዝናብ፤ ወንዝ፤ ሊለማ የሚችልና በመስኖ የሚታረስ መሬት፤ታታሪ የግብርና ልምድ ያለው ሕዝብ ባለፀጋ ናት። ራሷን ችላ ለውጭ ገበያ የሚተርፍ ምርት ለማቅረብ ትችላለች። ችግሩ የአየር ጠባይ፤ የተፈጥሮና የአካባቢ አይደለም። አገሪቱ ዘጠና በሞቶ የሚሆነውን ምግቧን ታመርታለች፤ የሚያመርቱት የኢትዮጵያ ገበሬዎች ናቸው። አንዳንድ አካባቢዎች ከአካባቢ ከፍላጎት በላይ ያመርታሉ። ለምሳሌ፤ የተባበሩት መንግሥታት የእርሻ ድርጅት፤ ኤፍፐሪ የተባለው የምግብ ፖሊሲ ተቋም፤

የነጻነት አለመኖር ችግሩ፤ ገዢው ፓርቲ የአገሪቱን ገቢ እንደፈለገው ይጠቀምበታል። ፈሰሱ (the flow of investments by the federal government) ሁኔታውን አባብሶታል። ገዢው ፓርቲ ከማንኛም ምንጭ የሚሰበሰበውን የውጭ ምንዛሬ መጠን፤ በአገር ውስጥ ከታክስ፤ ከጉምሩክና ከሌሎች ገቢዎች የሚገኘውን እንዴትና ለምን እንደሚጠቀምበት በትክክል ለማወቅ አይቻልም። ለብዙ አመታት፤ መንግሥት ከስደተኛው የሚሰበሰበውን የውጭ ምንዛሬ ብሄራዊ ባንክ ዝቅ አድርጎ እንዲያቀርብ ያስገድድ ነበር። ዓለም ባንክ ከፍሎ ጥናት ያደረገበት ምክንያት መንግሥት የሚሰጠው ማስረጃ አስተማማኝ ስላልሆነ ነው። ገዢው ፓርቲ ይህን ያደረገበት ዋና ምክንያት ለጋሾች የሚሰጡትን እርዳታ መጠን እንዳይቀንሱ ወይንም እንዲጨሩ ነው። በአገር ውስጥ፤ መንግሥት ለልዩ ልዩ ክልሎች የሚያፈሰውን የልማት ባጀት በትክክል ለሕዝብ አያስረዳም። ከባንኮች የሚበደረውን ገንዘብ መጠንና አጠቃቀም ለሕዝብ አይገልጽም። <u>ግልጽነት አለመኖሩ ጎሳዊ አድልዎንና ሙስናን አጠናክሯል።</u>

ይህን መሰረተ ሃሳብ ከልማት ጋር ማያያዝ አለብን። የእድገት መስፈርት የሚያሳየው፤ ለመላው ሕዝብ የቆሙ መንግሥታት አሰቃቂ የሆነ ረሃብተኛ የለባቸውም። የተፈጥሮ እልቂትን የመቋቋም አቅማቸው ጠንካራ ነው። አንድ ሃላፊነት የሚሰማው የመንግሥት አመራር ከሁሉም እድገቶች በላይ ቅድሚያ የሚሰጠው (the most essential growth agenda of any responsible government) ለምግብ ዋስትና ነው። የውጭ ኢንቬስተሮች ዋስትና አያመጡም። ገበሬዎችንና ሌሎች አገር ወለድ አምራቾችን አጎልምሶ የምግብ ዋስትናና የድህነትት ቅነሳ በአፋጣኝ ስኬታማ ማድረግ የኢትዮጵያ መንግሥት ሃላፊነት መስፈርት ሆኗል። እስካሁን፤ ገዢው ፓርቲ በዚህ መስፈርት ወድቋል። የምግብ ዋስትና ስኬታማ ያላደረገውን አገዛዝ "ተአምራዊ እድገት" አምጥቷል ማለት ዘበት ነው። እውነት አይደለም።


ደጋግመን የምናመለክተው፤ ማንም መንግሥት ይምራ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ መራብ የለበትም። ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሃብት ባለፀጋ ናት። የእርሻ ልምድ ያለው ብዙ ሚሊዮን ኢትዮጵያዊ አለ። የመሬት ስሪቱ የማምረት ችሎታውን ገድቦታል። ዛሬ ዘጠና አራት ሚሊዮን ኢትዮጵያውያንን ለመመገብ ያልቻለ መንግሥት፤ የሕዝቡ ቁጥር ወደ ሁለት መቶ ሰባ ስምንት ሚሊዮን ሲጨምር ምን እንደሚሆን ከአሁኑ ማሰብና መዘጋጀት የመንግሥትና የህብረተሰቡ ሃላፊነት ነው። ለሕዝቡ ቁጥር ማደግ ዋስትና ያለው የእድገት መንገድ መሬት ለውጭ አትራፊ ኢንቬስተሮች መስጠት አይደለም ። አስተማማኙ አማራጭ የአገሪቱን የእርሻ መሬት ሃላፊነት ባለው መንገድ ተንከባክቦ ዝቅተኛ አምራቾች ባለቤት እንዲሆኑ መደገፍ ነው። ኢትዮጵያውያን ወደ ዘመናዊ እርሻ እንዲገቡ የፖሊሲ ማነቆዎችን ማስወገድ አስፈላጊ ነው። የውጭ ኢንቬስተርት ከነዋሪዎችና ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር በጋራ እንዲሰሩ፤ የጥቅሙ ተካፋዮች እንዲሆኑ ማድረግ አማራጭ ነው። መተኪያ የሌላቸውን ለም መሬቶችና ወንዞች፤ መአደንና ሌሎች ሃብቶች ዘላቂነትና ተሳትፏዊነት ባለው መንገድ ለህብረተሰቡ ጥቅም ማልማት ድህነትንና ስራ አጥነትን ይቀንሳል። የተፈጥሮ ሃብትን ለአጭር ጊዜ፤ ለግል ትርፍና ለፖለቲካ የበላይነት መጠቀም የአገዛዝ ጉድለት ያሳያል። ቀጣይነትና ተሳታፋዊነት ያለው ልማት መሰረት እንዳይዝ በክሎታል። ባለፉት ጥቂት አመታት፤ የቻይና፤ የህንድ፤ የተርኪ፤ የፓኪስታን፤ የሳውዲ አረቢያ፤ የግብጽና የሌሎች አገሮች ኩባንያዎች ለኢትዮጵያ መንግሥት ባለስልጣናት "መደጎሚያ" በመስጠት የእድገት ምሰሶዎችን (Pillars of the national economy) በመግዛት የበላይነት አግኝተዋል። ኪራይ ሰብሳቢ የሆነው ገዢው ፓርቲ እነዚህን ጋብዞ ለራሱ ትርፍ ያገኛል። የዚህ እድገት ሂደት ጥገኝነትን ያጠናክራል። ስለዚህ፤ የኢኮኖሚው አመራር ውጤት ፀረ-ፍትህ (unjust) ፀረ-ርትእ (unfair and unequal) ሆኗል።

በአእምሯችን እንድንቀርፀው የፈለግነው፤ የሕዝብ ቁጥር መብዛቱን አይደለም። ህንዶችና ቻይናዎች ከኢትዮጵያ የበለጠ የህዝብ ብዛት አላቸው። በነዚህ ፍጹም ረሃብተኛ የለም። ህንዶች የአረንጓዴ አብዮት አካሂደው ተፈጥሮን ተቆጣጥረዋል። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚው ከሕዝቡ እድገት ጋር አብሮ አይሄድም። የሕዝብ ተሳታፊነት አይደገፍም። መንግሥት በጋምቤላና በሌሎች ክልሎች የሚሰጠው መሬት ሰው አይኖርበትም ሲባል የዘላኖችን፤ የገበሬዎችን፤ የነዋሪዎችን ወዘተ ህልውና ይክዳል። የመረጠው ሕዝቡን ሳይሆን መሬቱን ነው። ለጭቁኖች ቆሜአለሁ ለሚለው

ህወሓት/ኢህአዴግ “የተፈጥሮ ሃብትን” ከነዋሪው ሕዝብ ነጥቆ ለውጭና ለምርጥ የውስጥ ኢንቬስተሮች ማዘዋወር የራሱን የጎሳ-ህገመንግሥት ዋጋ ቢስ አድርጎታል። ገዢው ፓርቲ የሚፈልገው የጭቁኖችን መብትና የኑሮ መሻሻል አይደለም። በጭቁኖች ላይ መነገድ ሆኗል። የኦሞ ሸለቆና የጋምቤላ ሕዝብ ሰቆቃ የሚያሳየው አስከፊ ስእል ይህን ነው። ከሁሉም በላይ የሚያስደንቀው፤ ህወሓት/ኢህአዴግ የነዋሪዎችን መሬት ነጥቆ ለህንዶች፤ ለሳውዲዎችና ለሌሎች ሲሰጥ የነዋሪዎቹን ድምፅና ተሳትፍ አልጠየቀም።

ገዢው ፓርቲ ኢትዮጵያውያንን አግልሎ በጥቂቶች ድርጅታዊ ጡንቻ የሚንቀሳቀስ ድርጅት ነው። አገዛዙና ለምዝበራ የተመቻቸ ሆኗል። የማይካደው ሃቅ፤ የአገሪቱ የምርት ውጤት የተራውን ሕዝብ ፍላጎት ለማሟላት አልቻለም። ፖሊሲውን መቀጠል አደጋ እንደሚፈጥር አንጠራጠርም። ገዢው ፓርቲ ላራሱ፤ ለቤተሰቦቹና ለወዳጆቹ ኢኮኖሚውን ከውጭ ኢንቬስተሮች ጋር በመጋራት፤ ማርኮ ይዞታል። የጥቂቶች የኢኮኖሚ የበላይነት ውጤት የአብዛኛውን እድል ዘግቶታል ። ሙስና ለዚህ አድልዎና የእድል ዝግነት አስተዋጾ አድርጓል። በእኛ ጥናትና ግምት፤ ሙስናና  ኢህአዴግ “የአንድ ሳንቲም ግልባጮች”ናቸው የተባለው አያከራክርም። በሰንጠረዥ አራት እንደምናሳየው፤ የሕዝብ ቁጥር እያደገ ሲሄድ ምርቃት ነው። በአንጻሩ ይህን ሕዝብ የሚደግፍ ኢኮኖሚ አለመገንባት ደግሞ አደጋ ነው እንላለን። የሕዝብ ቁጥር ተመጣጣኝ የማምረት ችሎታ ይጠይቃል። ገዢው ፓርቲ የዚህ አይነት ችሎታና ብቁነት አላሳየም። ያተኮረው ትርፍና ለትርፍ ቁጥጥር የሚረዳውን የኢኮኖሚ ክፍል ማሳደግ ነው። የአበባ ንግድና በቅርቡ የሚደረገው የመከላከያ ኢንዱስትሪ ማስፋፋት ምሳሌዎች ናቸው።

ሰንጠረዥ አራት፤ የተባበሩት መንግስታት የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ጭማሬ ተመን





የሕዝቡን ቁጥር ብዛት ብቻ ማየት አይበቃም። የእድሜ ስርጭቱ ወሳኝ ነው። የአሜሪካ የስለላ ድርጅት ከአምሳ በመቶ በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ እድሜ ከአርባ አመት በታች ነው ብሏል። አርባ ስድስት በመቶ የሚሆነው ከአስራ አራት አመት በታች ነው። ይህ ወጣት ትውልድ ትምኅርትና ስራ ያስፈልገዋል። እነዚህን ዝቅተኛ ፍላጎቶች ማሟላት ለወጣቶቹ ብቻ ሳይሆን፤ ለሚኖሩበት አካባቢና ለአገራቸው ጥቅም ይፈጥራል። የትምኅርትና የስራ እድል ከሌለ አማራጩ ስራ አልባነት፤ ስደት፤ ወይንም ሌላ ህብረተሰቡን ጎጂ የሆነ አማራጭ ይሆናል። የመንግሥት ዋና ሚና ከአሁኑ የትምኅርትና የስራ ፈጣሪና አጎልማሽ የሆነ የማህበረሰብና የኢኮኖሚ መሰረት መፍጠር ነው። እድሎችን የሚያጠናክር የተፈጥሮ ሃብት ባለቤትነት ህጋዊ ማድረግ ነው። የዘመናዊ መገናኛ ስርጭት ለሁሉም እንዲደርስ አፈናን ማስወገድ፤ አድልዎንና ሙስና ወጣቱን ትውልድ እንዳይበከሉት ሕገወጥ ነው ብሎ ማወጅና መተግበር ወዘተ አስፈላጊ ናቸው። ሙስና መኖሩን ተቀብሎ ዳር ዳሩን “ማጽዳት” አያዋጣም። የሚያዋጣው ከፍተኛ ሙሰኞችን ለፍርድ ማቅረብና ቅጣታቸውን ይፋ ማድረግ ነው። ሙሰኞች ሙሰኞችን ለመዳኘት አይችሉም። ሙስና፤ ቀጣይነትና ፍትሃዊነት ያለው ልማት ይጻረራሉ።

ወጣቱ የወላጆቹን ኑሮ ሊኖር አልቻለም

ከሁሉ በላይ ኢትዮጵያን የሚያሳስባት ለወጣቱ ትውልድ የስራ እድል ለመፍጠር አለመቻሏ ነው የሚል ግምት አለን። የአብዛኛው አፍሪካ አገሮች ሁኔታ ሲታይ፤ ወጣቱ ትውልድ ከወላጆቹ የባሰ ኑሮ እየኖረ ነው። ተምሮም ኑሮውን ለመቋቋም አልቻለም። ተስፋ ስለቆረጠ፤ በገፍ አገሩን ለቆ ወደ ልዩ ልዩ አገሮች ይሰደዳል። የኢትዮጵያን ወጣት ትውልድ ሁኔታ ያባባሰው ድህነት ብቻ አይደለም። ከግፈኛ አገዛዝ የመጣ የአስተዳደር ሽኩም ነው። ስርቆት፤ ጎሳዊ አድልዎና  ሙስና በሚዘገንን ደረጃ የሕብረተሰቡን ኑሮ ለማሻሻል የሚችለውን የተፈጥሮና የገንዘብ፤ የመንፈሳዊና የሰው ሃይል ኃብት አባክኖታል። የማይካደው ሃቅ፤ ዛሬ በኢትዮጵያ የመንግሥት ስልጣን መያዝ ለግል ባለጠጋነት ዋና መንገድ

ነው። ባለስልጣናት፤ ምንም ሳይሰሩና ሳያመርቱ፤ ከወላጆቻቸው ሳይወርሱ፤ ቢሊየኔርና ሚሊየኔር ሆነዋል። ይህ የግብረገብነት መሻገት (Moral decadence and decay in governance) በቁጥር እያደገ ለሄደው አዲስ ትውልድ የሚዘገንን እሴት ሆኖበታል። ስለዚህ፤ የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ ከኢትዮጵያ ወጣት ትውልድ ተስፋ፤ ፍላጎትና የመንፈስ ብቃትጋር አብሮ ለመሄድ አልቻለም።

ሰንጠረዥ አምስት፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የእድሜ ስርጭት፤ የአሜሪካ የስለላ ድርጅት (2011/2012)





በፍጥነት የሚያድጉ አገሮች ታሪክ የሚያስተምረን ወደኋላ የቀሩ አገሮች ሕዝብ ከገጠር ወደ ከተማ እንደሚንቀሳቀስ ነው። የገጠር ኢኮኖሚ መድረሻ አይደለም። መነሻ ነው። የገጠሩን ኢኮኖሚ ዘመናዊ ማድረግ ለከተማው ኢኮኖሚ ድጋፍ ይሰጣል። በሌላ በኩል፤ የከተማውን ኢኮኖሚ በፍጥነት ማስፋፋት ለገጠሩ ኢኮኖሚ ገበያና የስራ እድል ይፈጥራል። ሁለቱ ተቆላልፈው ሲሄዱ ሚዛናዊ የሆነ የልማት መሰረት ይፈጠራል። የገጠሩን ሕዝብ ለፖለቲካ ቁጥጥር ኋላ ቀርና ደሃ አድርጎ ማቆየት ሁሉንም ህብረተሰብ ይጎትታል። ገዢው ፓርቲ የሚያደርገው የአገዛዝ ስልት ከዚህ የተለየ አይደለም። በሰንጠረዥ ስድስት እንዳሳየነው፤ በአብዛኞዎቹ የአፍሪካ አገሮች ከተሜው የሕዝቡ አርባ በሞቶ ሆኗል። በኢትዮጵያ አስራ ሰባት በሞቶ ነው። የኢትዮጵያ ከተሜነት የማይቀር ነው። (Ethiopia's urbanization is inevitable). ጥያቄው መቼና እንዴት የሚለው ነው። በከተማ እድል መፍጠርና የከተሜውን ኑሮ ማሻሻል የመንግሥት ሃላፊነት መሆኑን በሌሎች አገሮች አይተናል። የኢትዮጵያ መንግሥት ከተሜነትን እንደ ችግር ያየዋል። እኛ እንደ እድገት መሰረት እናየዋለን። የገዢው ፓርቲ ምክንያት የከተማ ሕዝብ ለመቆጣጠር አስቸጋሪ ስለሆነ ነው። ምርጫ ዘጠና ሰባት ለዚህ ዋቤ ነው። ገዢው ፓርቲ በሚገዛባት መዲና ተሸንፏል። አንዳንድ ተመልካቾች፤ ህወሓት/ኢህአዴግ የገጠሩን ሕዝብ ጥገኛ አድርጎ ለመቆየት የሚፈልገው ለቁጥጥር ስለሚያመቸው ነው ይላሉ። በእኛ እምነት፤ገዢው ፓርቲ የተፈጥሮ ሃብትንና ከለጋሶች የሚጎርፈውን ብዙ ቢሊዮን ዶላር ለመቆጣጠር የሚችለው ሕዝቡን በመከፋፈል፤ የከተማውና የገጠሩ ሕዝብ ግንኙነት እንዳይኖረው በማፈን ነው።

መከፋፈል ለሙስና ጠቃሚ ነው

መከፋፈል ዋጋ ይከፈልበታል። የገጠሩ ሕዝብ፤ በተለይ ወጣቱ ትውልድ ደሃ፤ ረሃብተኛና ጥገኛ ሆኖ እንዲቆይ ይገደዳል። የዚህ አይነቱ ስርአት ለአድልዎና ለሙስና ይረዳል። የተወሰነ ክፍል በጣም ሃብታም ይሆናል። አብዛኛው ደሃ እንደሆነ ይቆያል። ባጭሩ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ከተሜነትን እንደ እድል ፈጣሪ አላየውም። ኢንዱስትሪና የከተማ መሰረተ ልማት ከሕዝቡ የመግዛትና የመኖር አቅም ጋር ተያይዞ መስፋፋት ይኖርበታል። የገጠሩ ኢኮኖሚ ከከተማው ኢኮኖሚ ጋር በእቅድ መቆራኘት አለበት። ሁለቱ ክፍሎች ተደጋጋፊ ሆነው ካደጉ ኢትዮጵያ ሁለት የሕዝብ እድገት ችግሮችን ለመወጣት ትችላለች። አንድ የወጣት ትውልድ ብዛት እድል ፈጣሪነትን። (Converting the youth bulge crisis into opportunity). ሁለት፤ የከተሜነት መስፋፋት ህይወት ለዋጭ ነው። (Transforming the urbanization crisis into vital economic hubs). ከተሜነትን መንግሥት ሊያግደው አይችልም። ገዢው ፓርቲ ለወጣቱ ትውልድ "ተማርና ተሰደድ" እያለ ፓሥፖርት ሲሰጥ አይኖርም። ገጠሬውን መሬት ባይኖርህም በገጠር ኑር እያለ ሊቆይ አይችልም። ለማይቀሩ ችግሮች ለህብረተሰቡ ጠቃሚ የሚሆኑ አማራጮች ማቅረብ ብልህነት ነው።

ሰንጠረዥ ስድስት፤ ከተሜነት በኢትዮጵያ፤ የአሜሪካ ስለላ ድርጅት (2011)




ህወሓት በበላይነት የሚገዛው መንግሥት የሚመራበት የልማት ፖሊሲ መዋቅሮችን እንዳሉ ይዟቸዋል። ምክንያት ስንፈልግ ያተኮረባቸው የእድገት ክፍሎች ለትርፍ፤ ለምዝበራና ለቁጥጥር አመች ሆነው አግኝተናቸዋል። ሶስት ምሳሌዎች እንሰጣለን። አንድ፤ የአበባ ምርት ለውጭ ገበያ አቅርቦት። ሁለት፤ የእርሻ መሬት ሽያጭና ውጤቱን ለውጭ ገበያ አቅርቦት። ሶስት፤ የመንግሥት የነበሩትንና ትርፍ የሚገኝባቸውን የወርቅ ማእደን ለውጭ ኢንቬስተር ሽጦ የውጭ ምንዛሬ መሰብሰብ። የመጀመሪያው የአገር ውስጥ የምግብ ዋስትናን ያገለለ ነው። ሁለተኛው አገሪቱና ህብረተሰቡ የውጭ ምንዛሬ ምሰሶ በሆነ የተፈጥሮ ሃብት ሙሉ ቁጥጥር እንዳይኖራት አድርጓል። የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ፖሊሲው ከሃገሪቱና ከሕብረተሰቡ ዘላቂ ጥቅም ጋር አልተያያዙም። ሶስት፤ አስጊና አደገኛ የፖሊሲ አመራር ብለን የምንገምተው፤ የኢንዱስትሪ ባለቤትነት ለውጭና ለምርጥ ባለኃብቶች መሰጠቱ ነው። አገር ወለድ ኢንዱስትሪ ከከተሜነት ጋር አብሮ ይሄዳል። በእቅድ ከተሰራ፤ ለወጣቱ ትውልድና ከገጠር ወደ ከተማ ለሚንቀሳቀሰው ሕዝብ የስራ እድል ይፈጥራል። ይህ እድል ገቢን ይጨምራል። መካከለኛ መደብ ያሰፋፋል። የአገሪቱ የምርት ውጤት ይጨምራል። የትምኅርት እድል ለሁሉም መዳረስ የልማት መሰረት መሆኑ አያከራክርም። ለአንድ ህጻን/ወጣት ወዘተ የሚፈሰው አንድ ብር (investment of one birr per child) ሰባት ብር ይፈጥራል። ትምኅርት ህይወትን ያሻሽላል። ለአገር የማምረት ሃይል ወሳኝ ነው። ሆኖም፤ ገቢና የመኖሪያ ደህንነት የሌለው ቤተሰብ ልጁን ለማስተማር አይችልም። መሬት ሲወሰድ አብሮ የሚወሰደው የልጆች እድል ነው።

የገዢው ፓርቲ እርዳታ አግኝቶ የትምኅርት እድል አስፋፍቷል። ፈሰሱ (ኢንቬስትሜንቱ) ከምርት ጋር እንዲያያዝ አላደረገም። የተማረው ወጣት እድል ተምሮ ስደት ከሆነባቸው ምክንያቶች አንዱ ትምኅርትና የስራ እድል አለመያያዛቸው ነው። የወጣቱ ትውልድ የነፍስ ወከፍ ገቢ "በድንጋይ ፈለጣ" ሊያድግ አይችልም። በተመሳሳይ፤ "ከእጅ ወደ አፍ" ሆኖ የቆየው የገጠሩ ደሃ ገበሬ ኑሮ፤ የከብት አርቢና የሌላ ባለሞያ የነፍስ ወከፍ ገቢ በተአምር አይጨምርም። ሊጨምር የሚችለው ገበሬውና ሌላው ኢትዮጵያዊ የተፈጥሮ ሃብቱ ባለቤት ሲሆን ነው። ገበሬዎች አገር ውስጥ የሚመረት ማዳበሪያ በዝቅተኛ ዋጋ ለመግዛት መቻል አለባቸው። የተማረው ወጣት ልዩ ስልጠና ያስፈልገዋል። ሰቲት ሁመራና ሌሎች ቦታዎች እንደሆነው፤ ወጣቱ ወደ ዘመናዊ እርሻ ሲያመራና ከእርሻ ጋር የተያያዘ ኢንዱስትሪ ለማቋቋም ሲችል የገጠሩን ኢኮኖሚ ወደ ዘመናዊ ኢኮኖሚ ይለውጠዋል። ሁሉም ይቻላል። ማነቆው አገዛዙ ሆኗል። ገዢው ፓርቲ የገጠሩ ሕዝብ ኑሮ "እየተሻሻለ ነው" እያለ በፕሮፓጋንዳ ሊኖር አይችልም። ሌሎች የአፍሪካ አገሮች ኢትዮጵያን ቀድመዋታል።

ከማንኛውም የተፈጥሮ ሃብት የበለጠ፤ አንድ አገር በፍጥነትና በቀጣይነት ለመልማት--የሰው ኃይል፤ እውቀት (የተማረ ሰው) ፤ የእርሻ መሬትና ውሃ፤ ገንዘብ (ካፒታል)--ያስፈልጉታል። ከእነዚህ ዋናው የሰው ኃይል፤ ለም መሬትና ውሃ ናቸው። የገዢው ፓርቲ እድገትን የሚያው ከሰው ኃይልና ከሰው ኑሮ ለይቶ ነው። የውጭ እርዳታ በገፍ ይቀበላል። ችግሩ ገንዘብ አይደለም። ችግሩ አብዛኛው ሕዝብ የማይሳተፍበት ኢኮኖሚ መሆኑ ነው። ሕዝቡ በእርዳታ ላይ መብት እንዳለው ለመናገርና የመንግሥት ባለስልጣናት ገንዘብ ሲያባክኑ በፍርድ የመጠየቅ ሃላፊነት እንዳለባቸው ለማመልከት አይችልም። ምክንያቱም፤ አገዛዙ ፍጹም ግፈኛ (Tyrannical) ነው። መብት ያለው ግለሰብ "መብቴ ነው" ሲል በልዩ

ልዩ የፈጠራ ወንጀል ያስረዋል ወይንም ያሳድደዋል። በተፈጥሮ ሃብት ሙብት የለህም ከተባለ፤ በእርዳታና በፌደራል ባጀት ሙብት ሊኖረው አይችልም። የእርዳታ ገንዘብ መባከን የሙብት ጥያቄ መሆኑን እናረጋግጣለን። ይህ ዝግና አፋኝ የሆነ አገዛዝ፤ በመጽፉ አርእስት ላይ እንዳስቀመጥነው፤ "ድርጅታዊ ምዝበራን" ተቋማዊ አድርጓል። ድርጅታዊ ምዝበራ ተቋማዊ ባይሆን ኖሮ ኢትዮጵያ ካለችበት አስገ ደረጃ አትደርስም። የአርባ ቢሊዮን ዶላር እርዳታን አይተን ድህነትን ስንመረምር ያገኘነው ውጤት የመንግሥቱን አመራር ስግብግብነትና ጨካኝነት ነው። እንዴት?

ለኢትዮጵያ የሚጎርፈው እርዳታ ዋና አላማ ፍጹም ድህነትን በፍጥነት መቀነስ ነው። የጥቂቶችን ኪስ ለመሙላት አይደለም። Oxford University Multidimensional Poverty Index 2010/2011/2012 ያሰመረበት ዘጠና በሙቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ደሃ መሆኑን ነው። የነፍስ ወከፍ የቀን ገቢው ከሁለት የአሜርካ ዶላር በታች ነው። ይህን የገቢ ድህነት ያባባሰው በየሙቱ ከአገር የሚሸሸው ብዙ ቢሊዮን ዶላር ነው። አንድ ከፍተኛ የፖለቲካ ባለስልጣን ከሶስት ቢሊዮን ዶላር በላይ ባለጠጋ ነው። አስር በሙቶ የሚሆነውን የአገሪቱን የ2012 (GDP) ጠቅላላ ገቢ የሚገሙት አንድ ቤተሰብ ይዟል። የሌሎቹን ከስልጣን ጋር የተያያዘ ገቢ ስንደምር ዘረፋው ከቁጥጥር ውጭ መሆኑን ያሳየናል።

ይህን የሚዘገንን በስልጣን መባለግ ከአገዛዙ አንጻር እንየው። Mo-Ibrahim African Governance Index በተደጋጋሚ ያወጣው ዘገባ ከላይ ያቀረብነውን መስፈርት ያጠናክራል። የኢትዮጵያ አገዛዝ ከአምሳ ሁለት የአፍሪካ አገሮች፤ በሕግ የበላይነት 49ነኛ። በኢኮኖሚ ቀጣይነትና የኑሮ መሻሻል እድሎች ከፍትነት 49ነኛ። በሠብአዊ እድገት 44ነኛ፤ በሕዝብ ተሳትፎ 35ነኛ ወዘተ ያሳያል።

ስንጠረዥ ሰባት፤ የሞ-ኢብራሂም የአፍሪካ አገሮች የአገዛዝ ደረጃ (2010) (ከአንድ (ጥሩ ደረጃ) ወደ አርባ ዘጠኝ (መጥፎ ደረጃ) ይነበብ)

| አገር | ደህንነትና የህግ የበላይነት | ተሳትፎና ሠብአዊ ሙብቶች | ቀጣይነት/የኢኮኖሚ እድል | ሠብአዊ እድገት |
|---|---|---|---|---|
| ቦትስዋና | 2 | 4 | 2 | N/A |
| ኬፕ ቬርዲ | 3 | 1 | 3 | N/A |
| ኢትዮጵያ | 49 | 35 | 49 | 44 |
| ሊቢያ | N/A | N/A | N/A | 1 |
| ሞሪሸየስ | 1 | 2 | 1 | 3 |
| ናሚቢያ | 5 | N/A | N/A | N/A |
| ሴሸልስ | 4 | 5 | 4 | 2 |
| ደቡብ አፍሪካ | N/A | 3 | N/A | 5 |
| ቱኒዢያ | N/A | N/A | 5 | 4 |

ይህ ዘገባ አመልካች ነው። የፈለገው እድገት አለ ቢባል፤ የሕግ የበላይነት(ማንም ግለሰብ በሕግ ፊት እኩል መሆኑ)፤ የእድሎች ከፍትነት (አድልዎ የሌለበት)፤ የሠብአዊ እድገት (ለሁሉም የትምኅርት፤ የጤና፤ የመፀዳጃ፤ የመኖሪያ ወዘተ መሻሻል እድል)፤ የሕዝብ ተሳትፎ (በፖሊሲና በባጀት አጠቃቀም፤ በተፈጥሮ ሃብት ባለቤትነት፤ በሠብአዊ ደህንነት፤ በምርጫ ሚዛናዊነት ወዘተ) ከሌሉ ዘላቂነትና ፍትሃዊነት ያለው ልማት አይቻልም። በእነዚህ መስፈርቶች ጥሩ የአገዛዝ ውጤት ያሳዩ አገሮች የነፍስ ወከፍ ገቢያቸው ከፍ ያለ ነው። የህብረተሰባቸው ኑሮ ከኢትዮጵያ የተሻለ ነው። እነዚህ የኢኮኖሚና የማህበረሰብ ሙብቶች መስፈርቶች በተከታታይ በስራ ካልተተረጎሙ፤ የአብዛኛው ሕዝብ የነፍስ ወከፍ ገቢ አያድግም። አብዛኛው የአገር ገቢና እርዳታ ለግል ጥቅም ይውላል። የአገሪቱ ምርት አይጨምርም። የሚጨምሩ ክፍሎች፤ በአብዛኛው፤ በገዢው ፓርቲና በፈጠራቸው ድርጅቶች፤ በመረጣቸው የውስጥ ደጋፊዎችና በውጭ

እንቬስተሮች ባለቤትነት የተያዙ ይሆናሉ። የእነዚህ ምርታቸው ሊያድግ ይችላል። ለትርፍ የተፈጠሩ ስለሆነ ውጤታቸው ለውጭ ገበያዎች ይውላል የሚል ግምት አለን። የገዢው ፓርቲ ወደ ውጭ በሚላክ ውጤት ላይ ብቻ ማተኮሩ ለሙስናና ገንዘብ ለማሸሽ ቁልፍ ነው። የሞ-ኢብራሂም ዘገባ የሚመረምራቸው የአገዛዝ ክፍሎች የሚያተኩሩት የአፍሪካ መንግስታት ከብዙ አመታት በፊት በአሩሻ በተሰማሙባቸው የሠብአዊ መብቶችና እድገቶች ተቆላላፊነት ዙሪያ ነው። ገዢው ፓርቲ እነዚህን ለዜጎች አስፈላጊ የሆኑ የአገዛዝ መስፈርቶች በተደጋጋሚ ጥሷል። ጥናታችን ያሳየው የመንግሥቱ የበላዮች የሠብአዊ መብቶችን የሚጥሱበት ዋና ምክንያት የግል ጥቅማቸው ከአገርና ከህብረተሰቡ ጥቅም በላይ ስላደረጉት ነው። እነሱ ደጋግመው የሚሉት የተለየ ነው። እድገት ከኢትዮጵያውያን መብቶች ጋር ምንም ግንኙነት የለውም የሚል። አባባሉ ለሙስና ይበጃል። እኛ፤ የእድገት መስፈርት የዜጎች ኑሮ መሻሻል ነው እንላለን።

የቁጥጥር አስተዳደር ዋጋ ከፍተኛ ሆኗል

የኢኮኖሚና የማህበረሰብ መብት የሠብአዊ መብት አካል ነው። የተባበሩት መንግስታት ይህን በመገንዘብ ደጋግሞ ባወጣቸው የጋራ ስምምነቶች "የሠብአዊ መብቶች" ካልተከበሩ ረሃብንና ደሃነትን ለማስወገድ አይቻልም ያለውን እንጋራለን። የህወሓት/ኢህአዴግ አፈና ድህነትን አባብሷል። ለዚህ ስርአት ለፈጠረውና መንግሥት ለማስተካከል ላልቻለው የተዛባ የእድገት አመራር ዋጋ የሚከፍሉት አገሪቱ፤ ህብረተሰቡ፤ ተራ የክልል ነዋሪዎችና ወጣቱ ትውልድ ናቸው። መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት የአገዛዝና የአመራር ለውጥ ያስፈልጋል። ከሙስና ሌላ ከዚህ ጋር አብሮ የተያያዘው ክስተት፤ የኢትዮጵያ ምሁራን፤ የፖለቲካና የማህበረሰብ መሪዎችና ስብስቦች ያለ ፍርሃት የማይነጋገሩበት የፖለቲካ ኢኮኖሚ የሕዝብ ስርጭትና የወጣቱ ትውልድ ሚና ይገኙበታል። ህወሓት በበላይነት የሚገዛው መንግሥት ሕዝቡን በቋንቋና በሃይማኖት ለያይቶታል። ከፍፍሉና ፍርሃቱ ለቀጣይና ለተሳትፏዊ ልማት ማነቆ ሆኗል። ህብረተሰቡ ለጋራ ልማት ያለውን የተፈጥሮና የሰው ሃይል ለመጠቀም አልቻለም። በቁጥጥር የሚካሄደውን የአስተዳደር ዋጋ ከፍተኛ አድርጎታል። (The administrative cost of ethnic and religious conflict management is immensely high and is getting worse by the day). ገዢው ፓርቲ አገሪቱን፤ በተለይ ወጣቱን ትውልድ ለማባበል፤ በተከታታይ ለመግዛትና አገሪቱን ለመመዝበር ስለፈለገ ህብረተሰቡን በያቅጣጫው መቆጣጠሩን አስፋፍቶታል። ይህ ቁጥጥር የአስተዳደሩን ዋጋ የአገሪቱ ገቢ ከሚችለው በላይ ጨምሮታል። ውጤቱ ለምርት እድገት፤ ለስራ አጥነት መሻሻል፤ ድህነትንና ረሃብን ለመቀነስ የሚውለውን የአገሪቱን ምጣኔ ሃብት ተቆጣጣሪዎችን ለመግዛትና ለመደጎም አውሎታል። ሁለት ምሳሌዎች እንሰጣለን።

አንድ፤ ለወጣቱ ትውልድ ስራና ለስራ እድል የሚከፈቱበትን ሁኔታ ለማመቻቸት አልቻለም። ገዢው ፓርቲ አሁን የሚከተለው ፖሊሲ ህብረተሰቡን በበለጠ መቆጣጠር ነው። ለዚህ የመንግሥት አቅም ወይንም ጡንቻ መሳሪያ ያደረገው ወጣቱን ነው። በሕዝብ ስርጭት እንዳሳየነው፤ 46 በመቶ የሚሆነው ከ0-14 ባለው እድሜ ውስጥ ይገኛል። አምሳ አንድ በመቶ የሚሆነው የማምረት እድሜ በሚባለው ከ15-64 ባለው እድሜ  ውስጥ ይገኛል። እድሜው ከ65 በላይ የሆነው 2.7 በመቶ ብቻ ነው። የቁጥጥሩ ኢላማ የወጣቱ ትውልድ ሆኗል። አንድ ጥናት ያሳየን፤ ከጠቅላላው ሕዝብ ውስጥ፤ 65 በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሃያ አምስት እድሜ በታች ነው። ስርአቱን ለመቀጠል ከተፈለገ ይህን ወጣት ትውልድ ማባበልና ማስፈራራት ያስፈልጋል። ይህን በማጤን፤ ገዢው ፓርቲ ለወጣቱ የቀየሰውና የተከተለው ፖሊሲ ሰፊና ለምርት የሚጠቅም የስራ ከፋች እድል ሁኔታዎችን ማመቻቸት አይደለም። የለመደውን የቁጥጥር ፖሊሲ ማጠናከር ነው። የአዲስ ሪፖርተር እንደገለፀው፤ ከተሞች በቀጠና፤ በሰፈርና በጎጥ (block) ይደራጃሉ። በአብዛኛው፤ አባላቱ ሁሉም ወጣቶች ይሆናሉ። አንዱ በሌላው ላይ ስለላ ያካሂዳል። ይህ የእድገት መንገድ ነው ተብሎ ይነገራል። ዘዴው፤ "ወጣቶች መንደራቸውን ለማልማት ይሰማራሉ" የሚል ስም ተሰጥቶታል። ወጣቱ ትውልድ በልማት መሰማራት እንዳለበት በዚህ መጽሃፍ አሳይተናል። የኢትዮጵያ እድገትና ልማት ያለ ወጣቱ ተሳትፎ አይታሰብም። አድልዎ፤ ፍርሃት፤ ስደት፤ ማጭበርበር፤ ጉቦና ሙስና አደገኛ ደረጃ ላይ በደረሰበት የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ ወጣቱ ትውልድ በልማቱ ለመሳተፍ አልቻለም። የታወቀው የደቡብ አፍሪካ መንፈሳዊ መሪ፤ ቢሾፕ ዴስሞንድ ቱቱ ያለውን ማስታወስ ይጠቅማል። "ከጥቂቶች በስተቀር፤ የአፍሪካ መሪዎች አሁንም ለሕዝባቸው፤ በተለይ ለወጣቱ ትውልድ ሃላፊነት አያሳዩም።" የኢትዮጵያ መንግሥት ለሕዝባቸው ሃላፊነት ከማያሳዩ መንግስታት መካከል የመጀመሪያውን ደረጃ ይዟል። ወጣቱን ትውልድ ከመቆጣጠሩ በሻገር፤ በአገሩ ፖሊሲዎችና እድገቶች ያለምንም ተፅእኖ እንዳይሳተፍ አግሎለታል። ከታች በስደቱ ሰንጠረዥ እንዳሳየነው፤ የአብዛኛው እድል ተምሮ ስደት ሆኗል። በልማት ስም በየመንደሩ ያለምንም ካፒታል፤ ያለምንም እቅድ፤ ወዘተ ተደራጀ የተባለው ወጣት ለቁጥጥር ያመቻል። ብዙ አገር ወዳድ ታዛቢዎች አዲስ አበባ በጫማ ጠራጊነት፤ በታክሲ ነጂነትና በሌሎች ስራዎች የተሰማሩ ወጣቶች በምስጢር አነጋግረው የነገሯቸው ሁለት ስራ እንዳላቸው ነው። አንዱ በይፋ የሚሰሩት። ሌላው ለመንግሥት "ጆሮ ጠቢ ሆነው" በተሰጣቸው ቦታ የሚሰሩት ነው። ቁጥጥር ዋጋ ስለሚከፈልበት፤ አብዛኛዎቹ በወር ስድስት መቶ ብር ይከፈላቸዋል።

ይህ ከፍያ አይመዘገብም። (We call this incentivization of state sponsored control of Ethiopian youth). ይህ ወጭ ከሌላው የአስተዳደር ወጭ ጋር ሲደመር አገሪቱ የማትችለውን ተሸከማለች ማለት ነው።

ባለፈው አመት በዳካር ስለ አፍሪካ ወጣት ትውልድ የተካሄደው ስብሰባ ከማንኛውም ሃብት የበለጠ የአፍሪካን ልማት የሚወስነው ወጣቱ ትውልድ መሆኑን ተቀብሏል። ለወጣቱ ትውልድ ሃላፊነት የማያሳዩ አምባገነን መንግሥታት የሚጋብዙት የራሳቸውን መጥፊያ መሆኑን አመልክቷል። “የአረብ አገሮች ሕዝባዊ አብዮት” ያሳየው፤ጥቂት ሙሰኞች አብዛኛውን ሃብት ከያዙት ወጣቱ ለሙብቱ፤ ለነጻነቱ፤ ለህይወቱ መነሳቱ አይቀርም የሚል ነው። የ 21st Century Rebellion የሚነሳው የመንግሥታት መሪዎች እድገት አለ ብለው እያወሩ “የእድገቱን ውጤት ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው አድርገውታል። ውጤቱን ከሌላው ጋር ሳይካፈሉ ሲቀሩ ላራሳቸው ችግር ይፈጥራሉ።” በተጨማሪ፤ ስብሰባው የተጋራው፤ እድል የሌለው ወጣት ለአገሩ “የጠፋ ህይወት(Dead Social Capital).” ሶማልያ የወደቀችበት አንዱ ምክንያት ወጣቱ የመስራት፤ የመፍጠርና የተሻለ ኑሮ የመኖር እድሉ ስለተዘጋ ነው። የገዢው ፓርቲ ትምኅርት ጥራት የለውም። የስራ እድል አልከፈተም።

የፓርቲው አባላት ሸክም መሆን

ኢትዮጵያ የተሸከመችው ጉድ ተቆጥሮና ተሰፍሮ አያልቅም። ገዢው ፓርቲ ስድስት ሚሊዮን አባላት አሉት። ሶስት ወይንም አምስት ለአንድ የሚለው የስለላ መረብ ዋጋ ይከፈልበታል። ለአገር ውስጥ ደህንነት የሚወጣው “ከኢትዮጵያ መከላከያ ባጀት ይበልጣል የሚሉ ብዙ ታዛቢዎች አሉ፤ በምስጢር ስለተያዘ ሃቁን ለማወቅ ያስቸግራል። ማንም ያለድጎማ፤ ያለማጭበርበር ለመስራት አይችልም። አገሪቱን ለማስተዳደር ብቻ የሚወጣው ወጪ፤--ለአንድ ግለሰብ በወር ጠቅላላ የመንግሥት ወጪ/ድጎማ ሁለት መቶ ብር ይሆናል ብለን በዝቅተኛ ወጪ ብንገምተው--ገዢው ፓርቲ ቢሮክራሲውን ለመደገፍ ብቻ በአመት ቢያንስ አስራ ሁለት ቢሊዮን ብር ያወጣል። እነዚህ ሁሉ ለሕብረተሰቡ ሸክሞች ናቸው። ማንም ለመገምገም ስለማይችል፤ በመንግሥት መዝገብ የሚታየውና በድብቅ የሚወጣው መጠን አይታወቅም። ይሉኝታ በሌለበት ደረጃ ታማኝነትን ለመሸመት የሚወጣው ወጭ ለሕብረተሰቡ ሸክም ነው። የውጭ አገር መንግሥታትን ለማባበልና ለማሳመን የሚወጣው ወጭ ሸክም ነው። ያለ አግባብ የሚፈሰው ወጪ በምስጢር ስለሚሰራ ግምቱ ዝቅ ወይንም ከፍ ሊል ይችላል። የማይካደው ሃቅ፤ ድርጅታዊ ምዝበራ (State sponsored extraction of rent and plunder) ድርጅታዊ ቁጥጥር ያስፈልገዋል። ድርጅታዊ ቁጥጥር ያለ ብዙ ወጭ አይታሰብም። ይኼ ሁሉ ሸክም ተደማምሮ አገሪቱ በምርኩዝ እንደምትንቀሳቀስ ያሳያል። አገሪቱን በቁጥጥር ለማስተዳደር የሚያወጣው ገንዘብ ከአገሪቱና ከህብረተሰቡ አቅም በላይ ሆኗል። ይህ ወጪ ምርት ከማሳደግና ደሃነትን ከመቀነስ ጋር ግንኙነት የለውም። የስለላና የመከላከያ ቢሮክራሲው ባጀት ከአገሪቱ አቅም በላይ ነው።

በ February 2013 የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የንግድ ባንኮችን ተቀማጭ (reserve requirement) ከአስራ አምስት በሙቶ ወደ አስር፤ ከዚያ ወደ አምስት በሙቶ እንዲቀንሱ ትእዛዝ አስተላልፏል። ይህ ትእዛዝ ያሳየን ኢኮኖሚው አገዛዙ በፈጠረው ቀውስ መበከሉን ነው። ባንኮቹ ለማበደር ገቢ ያስፈልጋቸዋል። አንዱ የገቢ ምንጭ ገንዘብ ያላቸው ነጋዴዎች በባንክ የሚያስቀምጡት ገንዘብ ነው። ስርአቱን አንፈልግም ብለው ገንዘባቸውን በቤታቸው ካስቀመጡት ውይንም ከአገር ካሸሹት በባንክ ያለው ተቀማጭ ይቀንሳል። ሌላው ምንጭ ከባንክ የተበደሩ ግለሰቦችና ኩባንያዎች የተበደሩትን በጊዜው ሲከፍሉ ነው። ተበድረው ከሰርን ካሉ ወይንም የተበደሩትን ከአገር ካሸሹ ባንኮች የእዳው ተሸካሚ ይሆናሉ። የሚያበድሩት ይቀንሳል። ተራው ኢትዮጵያዊ የሚያስቀምጠው ቀርቶ የእለት ፍላጎቱን ለማሟላት እየተቸገረ ነው። ሁኔታውን ያባባሰው ባለፉት አመታት መንግሥት ባንኮችን እንደ ራሱ ካዝናዎች በመቁጠር በልማት ስም “እያለበ” ስድሳ ቢሊዮን ብር ወስዷል። ብዙ ከፖለቲካ ግንኙነት ሌላ መያዣ የሌላቸው ግለሰቦች ተበድረው ህንጻ ወይንም ሌላ የሰሩ መክሰራቸው ይወራል። አንዳንዶቹ ከአገር ጠፍተዋል። ብዙ ቢሊዮን ብር ወደ ውጭ ምንዛሬ እየተለወጠ ከአገር ሸሽቷል። ስለዚህ የማበደር አቅም ዝቅ ብሏል። የሚጎዳው ተጣጥሮ የሚሰራው ተበዳሪው ነጋዴና መላው ህብረተሰብ ነው። የፖሊሲ ነክና መዋቅራዊ ችግር የፖሊሲና የመዋቅር ለውጥ ያስፈልገዋል።

ገዢው ፓርቲ፤ በአንድ በኩል ህንዶችን፤ ቻይናዎችን፤ ግብጾችን፤ ሳውዲዎችንና ሌሎችን እየጋበዘ የተፈጥሮ ሃብትና የልማት ምሰሶዎችን ያስረክባል። በሌላ በኩል ኢትዮጵያውያን ከክልላቸው ውጭ ሙብት እንደሌላቸው አድርጎ የብሄርና የቋንቋ ልዩነቶችን ይጠቀማል። የዚህ ውጤት ሰላም የሌለው ሕብረተሰብና የተዛባ ልማት ነው። ገዢው ፓርቲ የተዛባ ገቢ፤ የተዛባ የብድር አሰጣጥ፤ የተዛባ ገበያና የተዛባ ህብረተሰብ ፈጥሯል። ህወሓት ይህን ዘዴ የተጠቀመበት ዋናው ምክንያት ሁሉን ብሄር/ብሄረሰቦች አናሳና አብዛኛውን ሕዝብ ደሃ ለማድረግ ይመስላል። በአመራሩ ሂሳብ (The mathematics of ethnic composition and the youth bulge) የሕዝብ ብዛትና የብሄር ስርጭት በፖለቲካ ውሳኔ ሊለወጥ ይችላል የሚል ነው። በእኛ ግምት በፖለቲካ ውሳኔ አይለወጥም። የነዋሪው ህይወት የሚሻሻለውና የአገሪቱ

የማምረት ሃይል የሚጨምረው በቋንቋ ልዩነት አለመሆኑን አሳይተናል። የኑሮ መሻሻልና የምርት ውጤት ለማደግ የሚችለው እኩልነትን፤ ፍትህ-ርትእን፤ አብሮ መኖርን፤ አብሮ ህይወት ማሻሻልን፤ አብሮ የተፈጥሮ ሃብትን ተንከባክቦ መጠቀምን የሚያስችል አገዛዝ ሲፈጠር ነው። በፖለቲካ ውሳኔ አንዱን ብሄር ደሃ፤ ሌላውን ሃብታም ማድረግ የእርጋታን መሰረት መናድ ሆኖ አግኝተነዋል። በማንኛውም መስፈርት ስናየው፤ ከብሄርና ከቋንቋ ልዩነት የመነጨ አድልዎና ማግለል (marginalization) የወጣቱን እድሎች እየዘጋ ነው። እርጋታ አይኖርም። ከቀጠለ እልቂት ሊኖር ይችላል።

የገዢው ፓርቲ የማግለል ዘመቻው በልዩ ልዩ መንገዶች ተከስቷል። ኢትዮጵያ ከሕዝብ ፍላጎት ጋር አብሮ ያደገ ዘመናዊ የመኖሪያ ቤት ዝቅተኛ ከሆነባቸው የዓለም አገሮች የመጀመሪያውን ደረጃ ይዛለች። ብዙ የውጭ ታዛቢዎች የኢትዮጵያ ሕዝብ በሁለት ዓለም እንደሚኖር ይናገራሉ። አንዱ የጥቂቶች የድሎት ዓለም ነው። ሌላው የአብዛኛው አሰቃቂ የሆነ የኑሮ ዓለም ነው። ጥቂቶቹ ኃብታሞች በዓለም ከፍተኛ የሆነውን የመኪና አደጋ ሞት ፈጥረዋል። መንግሥትና አዲስ ባለ ኃብጠጋዎች ሞቱን እንደ ተራ ነገር ቆጥረውታል። የከተማ ቦታና ቤት አያያዝ ከሕዝቡ ፍላጎት ጋር ግንኙነት የለውም። በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች ደሃ ቤተሰቦች “መሬታችሁና ቤታችሁ የእናንተ አይደለም” ተብለዋል። ከቤታቸው ተባረዋል። ዜግነታቸው ተገፏል። ቅኝ ገዢዎችም ይህን አላደረጉም። መኢአድ ይህን በገዢው ፓርቲ የሚካሄድ የፀረ-ዜግነት ፖሊሲ አግባብ ባለው መልክ መዝግቦታል። ህወሓት/ኢህአዴግ “ሕዝብን ባሪያ አድርጎ የሚያኖር መንግሥት ሆኗል”። ሕዝቡ መብቱን ለመከላከል አቤቱታ ስያቀርብ የሚደርስበት ስድብና ሌላ ብልግና በሌላው ዓለም ከስራ የሚያስወጣ ነው። በብዙ ከተሞች የመንግሥት ሰራተኞች ቢሩቸው አይገኙም። “የሉም፤ ስብሰባ ናቸው፤ ነገ ይመለሱ፤ ፋይሉ አልተገኘም” ወዘተ የተለመደ ሆኗል። ይህን በከተሞች የሚደረገው ስርአታዊ ግፍ ለወጣቱ ትውልድ ጠንቅ ሆኗል። የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት የምእራብ መንግስታትንና እነዚህ መንግስታት የሚደግፏቸውን ወይንም በበላይነት የሚያዟቸውን የእርዳታ ድርጅቶች ድጋፍ ካገኘ ሃያ ሶስት አመታት ሆኖታል። አርባ ቢሊዮን ዶላር እርዳታ ወደ ካዝናው አስገብቷል። የውጭ እርዳታ በገፍ መግባቱ የድህነትን፤ የጤና ችግርን፤ የስራ አጥነትን ወዘተ ሰለባ በተፈለገው መጠን አልቀነሰም። አንዱና ዋናው ምክንያት፤ ስርአት ወለድ የሆነው የምዝበራ ክበብ ብዙ ቢሊዮን ዶላር ከአገሪቱ ገቢ እያጭበረበረ ወደ ውጭ አገሮች ለግል ጥቅም ስላዋለው ነው። የውጭ ምንዛሬው ብዛትና አይነት ለምዝበራው ወንፊትነት ረድቷል። የስደተኛው ገንዘብ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

ምእራፍ ሰባት፤ የስደተኛውን ታሪክ ሂደት፤ ለወገኑ የሚያደርገውን አስተዋጽኦና ለገዢው ፓርቲ የሚያበረክተውን ድጋፍ ይመረምራል። የድጋፉ አይነተኛ አስተዋጽኦ አገር ቤት በሚፈሰው ገንዘብና ኢንቬስትሜንት አልተወሰነም። አብዛኛው የውጭ ምንዛሬ ለገዢው ፓርቲ ጡንቻና መቆያ፤ ለሕብረተሰቡ ዘመናዊ አፈናና ለሙሰኞች የውጭ ምንዛሬ ማሸሺያ ሆኖ እያገለገለ ነው።

ምእራፍ ሰባት

ስደተኛነት የእድገት ውድቅትን ያሳያል

“የአንድ ሃገር ሕዝብ በሁለት ይከፈላል። አንዱ ሃገሩን ወዳጅ ሲሆን፤ ሌላው ስልጣኑን ወዳጅ ነው።”

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ--ዲሞክራሲና ኢትዮጵያ

“ኢትዮጵያ አዲስ ናት። የድሮዋ ጠፍታ ስለነበረ፤ የድሮው አዋጅ ሁሉ እንደገና መታወጅ አለበት።”

የእንግሊዝ መንግሥት--ከጠላት ወረራ በኋላ

“ኢትዮጵያ በብዙ ሽህ ዓመታት ካፈራችው ስልጣኔ ልትኮራበትና ልትጠቀምበት የሚገባው በብዙ ሚሊያርድ (ትሪሊየን) ብር የማይገዛው ጥበቧ ይሞታል። በኋላም ባወቀችው ጊዜ ወቅቱ የተላለፈ በመሆኑ ትንሣኤ ሊያገኝ አይችልም። በማስተማርም የማይገኝ ይ

ሆናል።”

ዶር ከበደ ሚካኤል፤ ሥልጣኔ ማለት ምንድነች?

በህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ አንጻር ስናያቸው እነዚህ ሶስት አባባሎች የተያያዙ ናቸው። ጎሳ-ተኮር ፌደራሊዝም የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በተለይ ወጣቱ ትውልድ በሁለት እንዲከፋፈል አድርጎታል። አንዱ አገር ወዳድ እንዲሆን ሌላው ገንዘብ/ስልጣን/ጎሳ ወዳድ እንዲሆን። ገዢው ፓርቲ ወጣቱን ትውልድ ያስገደደው፤ ልክ እንግሊዞች ለአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት፤ በጠቅላይ ሚንስትር አክሊሉ ሃብተወልድ አማካኝነት “ኢትዮጵያ አዲስ ናት፤ የድሮዋ ጠፍታለች” የሚል ነው። ሻቢያ፤ ህወሓትና ኦነግ ኢትዮጵያን ስር ነቀል በሆነ መንገድ በቋንቋ አዛብተውና አመሰቃቅለው አዲስ መንግስታዊ ቅርፅ ሰጥተዋታል። በበላይ ሆኖ አገሪቱን የሚገዛው የአናሳ ጎሳ ተወካይ ነኝ ብሎ ራሱን የሰየመው ህወሓት የኢትዮጵያን ሕዝብ መሬቶች የራሱ አድርጎ አዲስ የጂኦግራፊ መልክ ሰጥቶታል። የተለየ ትኩረት ያገኘው የአማራው ብሄረሰብ የሚኖርበት የጎንደር፤ የወሎና የጎጃም ክፍለ ኃገሮችን ይሸፍናል። ስለዚህ የድሮዋ ኢትዮጵያ የለችም ወይንም ጠፍታለች ሲባል፤ ዶክተር ከበደ ሚካኤል እንዳስጠነቀቁት፤ “የኢትዮጵያ ስልጣኔ፤ የኢትዮጵያ እውቅናና ማንነት” በሙሉ ይጠፋል። እየጠፋ ነው። ለዚህ ህወሓት የተጠቀመበትና የሚጠቀምበት ዘዴ ኢትዮጲያ ተብለው የሚጠሩ ተቋሞችን ማጥፋትና በኢትዮጵያዊነታቸው የተሰበሰቡና ለመሰብሰብ የሚፈልጉ የፖለቲካ፤ የሞያ፤ የሲቪክና የኃይማኖት ስብስቦችን ማጥፋት፤ የሚያብቡትን ከፅንሳቸው መደምሰስ ነው። ደራሲው በተደጋጋሚ እንዳሳሰበው፤ ታሪክ፤ ባህል፤ እሴት፤ ልምድ፤ እውቀት ወዘተ ከጠፋ በኋላ በቢሊዮን ዶላር ሊሸመት አይችልም። ከመሬት ተቆፍሮ አይወጣም። ትውልድ ለስደት ሲዳረግ፤ አገር ውስጥ ያለው በሚዘገንን ደረጃ ሲታፈን አብሮ የሚጠፋው ታሪክ፤ ባህል፤ የአገር እውቀት ወዘተ ነው። ኢትዮጵያም አብራ የመጥፋት እድሏ በመወሰን ላይ ያለው አገር ወዳዶች ከጎሳቸው በላይ ለሃገራቸው እንዳይደራጁ መደረጉ ነው። የኢትዮጵያ ስደተኞች ማሰብ ያለብን፤ ኢትዮጵያንና ከትውልድ ወደ ትውልድ የተላለፉ ቅርሶችን በስደት ሆነን ልንተካቸው እንደማንችል ነው። በስደት የሚመሰረተው ተቋም፤ ወዘተ አገር ውስጥ የፈረሰውንና የሚፈርሰውን ሊተካው አይችልም። ስደተኛው ይህን መሰረተ ሃሳብ ከረሳ ባህሉን ይረሳል። አገሩን ያጣል።

በእኛ ግምት፤ ከታች በሰንጠረዥ ስምንት የምናሳየው የሕዝብ ስርጭት የኢትዮጵያ መለያ፤ የኢትዮጵያውያን የጋራ ሃብት ነው። የኢትዮጵያ ጥንካሬ ሁሉም ብሄር፤ ብሄረሰቦችና ኃይማኖቶች የሚጋሩት የወሉ ሰብሳቢ ሲሆን፤ የባህል፤ የታሪክ፤ የወግ ማእረግ ወዘተ ልዩነቶችና መታዎቂያዎች ሲከበሩ ነው። የሚጋሩት እሴት ከሌለ የሚለያያቸው እየጎላ ይሄዳል፤ ዛሬ ህወሓት/ኢህአዴግ የሚያደርገው። የመንግሥት መሪዎች ካወቁበት ይህን የጋራ ሃብት ስልት ባለው መንገድ ለአብሮ ማደግና ለአብሮ ኑሮን ለማሻሻል መጠቀም ይኖርባቸዋል። በሚቀጥሉት አርባና መቶ አመታት የተባበረና ወደ አንድ የልማት አቅጣጫ የሚጓዝ ስብጥር (diverse)

ህብረተሰብ ዘመናዊና ሃብታም ይሆናል። በአንጻሩ፤ የተከፋፈለ፤ የግል ሃብት በሕግ ያልተከበረበት፤ የእርስ በእርስ ግጭት የተስፋፋበት ህብረተሰብ ኋላ ቀር፤ ደሃና ወደ ስደት የሚያተኩር ሆኖ ይቆያል። የኢትዮጵያ የተማረ የሰው ኃይል ተከታታይ ስደት የአገዛዝ አፋኝነት መስፈርትና የኢትዮጵያ መቅሰፍት ነው። ከሁሉም በላይ ሁኔታን ያባባሰው የህወሓት አምባገነናዊና ጎሳዊ አገዛዝ ነው። ቋንቋን ተጠቅሞ ከዚህ ውጣ የሚል፤ ቋንቋን ተጠቅሞ የሚቀጥር፤ ቋንቋን ተጠሞ የሚበይንና የሚያጉላላ ወዘተ። ተከታታይ ፍልሰት ቅስፈት ሊባል ይገባዋል። <u>የትዮጵያ ሕዝብ ገንዘቡን አፍሦ</u>

የሚያስተምረውና የሚያስለጥነው የሰው ኃይል በገፍ ከሃገር እየተሰደደ የሕዝብ ብዛት ያላት አገር የሚያለማትና የሚቆረቆርላት የሰው ደሃ ሆናለች። ለምሳሌ፤ CUSO International, Canada, የተባለው ተቋም፤ ኢትዮጵያ ከአሰለጠነቻቸው 3700 ኃኪሞች 3000 ሺህ ወደ ውጭ መሰደዳቸውን አመልክቷል። ይኼ ከፍተኛ ፍልሰት በሌሎችም ሞያዎች ተከስቷል። ማንም አገር የተማረና የሰለጠነ የሰው ኃይሉን ለመንከባከብ ካልቻለ መሰረታዊ ስርዓት ወለድ ችግር አለበት ማለት ነው። የአምባገነናዊው የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት በዲሞክራሳዊ አገዛዝ ይተካ ብለን የምንከራከርበት አንዷና ዋናው ነጥብ ይኼው ነው። ዛሬ የኢትዮጵያ የመካከለኛ መደብ የሚገኘው ቫንኩቨር ካናዳ (አስር ሺህ ኢትዪጵያውያን የሚኖሩበት፤ ዋሺንግቶን ዲሲና አካባቢ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የሚገመት ኢትዮጵያዊ የሚኖርበት ወዘተ ሆኗል። ይህ ግዙፍ ስደት ካላስጨነቀን ለሃገሪቱ የወደፊት እድል እናስባለን የምንለው አያዋጣም። እየደማችና እየደከመች ለሄደች ኢትዮጵያ አይሆናትም።

ወደኋላ ሄደን ስንመራመር፤ ኢትዮጵያውያን መሰደድ ባህላቸው አይደለም። በሃያኛውና በሃያ አንደኛው መቶ አመታት የመጣ ክስተት ነው። በምርምር የደረስንበት፤ እአአ ከ 1876-1922 ከኢትዮጵያ ፈልሰው የሄዱት ኢትዮጵያውያን ቁጥር ሰላሳ አምስት ነበር። እአአ ከ 1941-1974 ሃያ ሽህ ኢትዮጵያውያን ለትምኅርትና ለስልጠና ወደ ውጭ ተልከው፤ አብዛኛዎቹ ወደ አገር ተመልሰዋል። ከ 1951-1960 ስድሳ አንድ ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ስደተኞች ሆነዋል። የመጀመሪያው የፖለቲካ ስደተኛ በገፍ መውጣት የጀመረው በደርግ አምባገነን ዘመን ከ1974-1977 ባለው ወቅት ነው። በገፍ የወጣው የግራ ክንፉ ታጋይ ኢትዮጵያዊ ነው። ይህ መፍለስ በተከታታይ እየጨመረ የሄደው ከ1991 ወዲህ ነው። ዛሬ በሰሜንና በደቡብ ሱዳን ሁለት ሚሊዮን፤ በሰሜን አፍሪካ፤ በመካከለኛው ምስራቅና በቀረው የጥቁር አፍሪካ ሁለት ሚሊዮን፤ በበለጸጉ የምእራብ አገሮች ከአንድ እስከ ሁለት ሚሊዮን፤ በጠቅላላው የታወቀ ከአምስት እስከ ስድስት ሚሊዮን ኢትዮጵያዊ ስደተኛ አለ። ያሁኑ ስደት ከበፊቶቹ የሚለይበት ምክንያት ምንድን ነው? ዋናው ምክንያት የኅሰኝነት አድልዎና ልዩነት፤ የስራና የኑሮ እድል መዛባት ወይንም አለመመቸት፤ የሰብአዊም መብቶች አፈና ናቸው። Bendixen and Amandi International, በ 2010 ለዓለም ባንክ ያደረጉት አገር አቀፍ ሰፊ ጥናት በሰንጠረዥ ዘጠኝ ያቀረብነውን ስእል ያሳያል። የኢትዮጵያውያን የስደት ባህል እንዴት እንደ ጀመረ ለማጤን የሚከተለውን ሰንጠረዥ ስምንት እናቀርባለን።

ሰንጠረዥ ስምንት፤ የስደት ጉዞ ኅርፍ

| አመት-እ አ አ | የስደተኛው ቁጥር |
|---|---|
| 1876-1922 | 35 |
| 1951-1960 | 61 |
| 1974-1991 | 250,000 |
| 1991-2014 | 5-6,000,000 (የተገመተ) |

- ስደተኛነት የኢትዮጵያውያን ባህልና ታሪክ አልነበረም። ግለሰቦች ወደ ሌላው ዓለም ቢሄዱም በገፍ የወጡበት ዘመን ፈልገን ለማግኘት አልቻልንም።

- ስደተኛነት እየሰፋና እያደገ የሄደው ከየካቲት አብዮት በኋላ ነው። አስከፊ ደረጃ ላይ ደርሶ ተቋማዊ የሆነው ህወሓት/ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ በኋላ ነው።

- ህወሓት/ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘበት ወዲህ የወጡ ስደተኞች ሲጠየቁ የሰጧቸው ዋና ምክንያቶች ሁለት ናቸው። የአገዛዝ አፈናና አድልዎ፤ የስራ እድል መጥፋትና የግል ስራ ለመስራት ሁኔታው አፋኝ መሆኑ። (Restrictive regulatory environment). የአገሪቱ አለመረጋጋት፤ የፖለቲካ ጭቆና። በተጨማሪ፤ ለልጆች ጥሩ ኑሮና የትምኅርት እድል አለመኖሩ። የኢህአዴግ ደጋፊዎች ጭምር እነዚህን ምክንያቶች ለስደት ይጠቀሙባቸዋል። ህወሓት ከፍተኛ ቅልጥፍና ከሚያስይባቸው ተግባሮች መካከል ለፍትህ የሚታገሉ ግለሰቦችን ማሰርና ከሃገር ለመውጣት ለሚፈልጉ ሁሉ ፓስፖርት የመስጠት ልምዶች ይገኙበታል።

- የሚሰደደው ከሁሉም ብሄር/ብሄረሰቦች/ኃይማኖት ተከታዮችና ጾታዎች የተውጣጣ፤ የተማረና ወጣት ትውልድ ነው።

- ለመሰደድ የመጀመሪያ ደረጃ ወይንም ምርጫ የያዘው ሰሜን አሜሪካ ነው። ከዚያ አውሮፓ፤ ከዚያ አውስትራሊያ፤ የመካከለኛ ምስራቅ፤ የቀረው አፍሪካ ይላል።

- በቤተሰብ ደረጃ መነሻ ሲታይ፤ ስድሳ አምስት በመቶ የሚሆነው ከገጠር ነው። ሰላስ አምስት በመቶ የሚሆነው ከከተማ የፈለሰ ነው።

- ከስደተኞች ሰማንያ አራት በመቶ የሁለተኛ ደረጃ ትምኅርት ጨርሷል። ሃያ ዘጠኝ በመቶ ኮሌጅ የጨረሰ ነው። ቢያንስ አምሳ በመቶ የህክምና ባለሞያ ይሰደዳል። ከዚያ በላይ የሚገመት ሌላ ባለሞያ አገሩን ይለቃል። ዝቅተኛ ትምኅርት ያላቸው ወደ መካከለኛው ምስራቅና ሱዳን ይሄዳሉ።

- በሰንጠረዥ አስር እንደሚታየው፤ የዛሬ ሶስት አመት ጥናቱ ሲገባደድ፤ ስደተኛው ሶስት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ዶላር በባንኮች ወደ ኢትዮጵያ ልኳል። ስድሳ አራት በመቶ የሚሆነው የተላከው ህወሓት በሚቆጣጠራቸው ውይም ለፓርቲው ድጋፍ የሚሰጡ ተባባሪ የገንዘብ ቸርቻሪና ላኪ ኩባንያዎች አማካይነት ነው። (Through remittances companies). ሃያ አንድ በመቶ የሚላከው በባንኮች ነው። ስለዚህ፤ አብዛኛው ወደ ሃገር የሚገባው በጥቁር ገበያው አማካይነት ነው።

- ስደተኛው ቀጥታ በሆነ መንገድ በአመት አምስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ደሃ ዘመዶቹን ይደግፋል። እያንዳንዱ ከውጭ የሚላክ ገንዘብ ተጠቃሚ ቤተሰብ፤ በአማካይ፤ ሶሥት አባላት አሉት። ከአስራ ስድስት ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን በላይ ነው። የውጭ እርዳታ ከሚደግፈው ከፍ ያለ እርዳታ መሆኑ ነው።

- እያንዳዱ ገንዘብ ላኪ (remitter) በአመት አምስት ጊዜ <u>በአማካይ መቶ ሃያ አምስት ዶላር</u> ይልካል። ከውጭ ገንዘብ የሚላክላቸው ቤተሰቦች የወር ገቢ በዝቅተኛ አንድ ሽህ ብር፤ በከፍተኛ ሶስት ሽህ አምስት መቶ ብር ተገምቷል።

- ይህን ገንዘብ በምን ላይ ታውሉታላችሁ ተብለው ሲጠየቁ ፤ ሰማንያ ስድስት በመቶ የሚሆኑት ለምግብ፤ ለልብስ፤ ለቤት፤ ለመድኃኒት ብለዋል። በአጠቃላይ ለአስፈላጊ የፍጆትና የኑሮ ማማያ ማለት ነው። “ለቁጠባስ ትልካላችሁ” የሚል ጥያቄ ሲጠየቁ፤

- አስራ አራት በመቶ የሚሆኑት ለትምኅርት፤ ለቁጠባና ለአዲስ በቀጣይነት መተዳደሪያ ለሚሆን የግል ኢኮኖሚ መመስረቻ፤ ታክሲ፤ ቡና ቤት ወዘተ ብለዋል።

- ዘጠና አራት በመቶ የሚሆኑት በሚላክ ገንዘብ (Remittance) የሚተዳደሩ ሞባይል አላቸው። ገንዘብ ከሚልኩላቸው ጋር ግንኙነት የሚያደርጉት በሞባይል ነው። መከላከከያ ብዙሃን ብርቅ በሆነባት ኢትዮጵያ ይህ ሌላ ዘመናዊ መገናኛ ለሌለው ሕዝብ አስፈላጊ የሆነ መሳሪያ ሆኖለታል። መንግሥት ሊያሰራጨው ያልቻለውንና የሚከታተለውን ቴክኖሎጂ ስደተኞች እያሰራጩት ነው። ብዙ ጥቅም ያለው መሳሪያ ነው እንላለን።

አንባቢ ከዚህ ብዙ ነገር ለመቅዳት ይችላል።

አንደኛ፤ ስደተኛው ከውጭ እርዳታ የበለጠ ድጋፍ ለደሃ ዘመዶቹና ለሃገሩ ይለግሳል። ተቀባዮቹ ከረሃብና ከድህነት ወጥመድ ነጻ እየሆኑ ነው። ይህ የሚመሰገን ነው።

ሁለተኛ፤ አብዛኛው የሚላከው ገንዘብ ቀጣይነት ላለው ብሄራዊ የምርት እድገት ወይንም የስራ እድል ፈጠራ አይውልም። “ከብልጭልጭነት (Glitz) ውጭ፤ የኢኮኖሚውን መዋቅር እምብዛም አልቀየረውም።

ሶስተኛ፤ የስደተኛው ገቢ ከፍተኛ ስለሆነ፤ ስደተኛው በአገር ቤት የሚገዛ መሬትና የሚሰራ ቤት ዋጋ አባብሷል። አገር ቤት የሚሰራውና የሚኖረው የተማረ፤ በመካከለኛ መደብ ውስጥ ያለና ደሃ ከስደተኛው የመግዛት አቅም ጋር ለመወዳደር አልቻለም።

አራተኛ፤ ስደተኛው ከያለበት የቀዳውን አዲስ ባህልና ልምድ ወደ አገር ቤት ያስገባል። የህብረተሰቡ ባህል፤ ልምድና ታሪክ ሁለተኛ ደረጃ ይዟል።

አምስተኛ፤ ስደተኛው የሚሰጠው የውጭ ምንዛሬ የገዢው ፓርቲ መጋቢና ጡንቻ ሰጭ ሆኗል። ለሙስናና ከአገር ለሚሸሸው ብዙ ቢሊዮን ዶላር አስተዋጽኦ አድርጓል።

ስድስተኛ፤ ስደተኛው ወደ ሞራል ውድቀትና ተጠያቂነት (Moral crisis or predicament) በመግባት ላይ ይገኛል። ወቀሳውን ያባባሰው፤ ገዢው ፓርቲ ሌሎች አገሮች--ፓኪስታን፤ ህንድ፤ ቻይና፤ ኤል ሳልቫዶር፤ ጋና ወዘተ--እንደሚያደርጉት የስደተኛውን እውቀትና የፖሊሲ ምክር አይጠይቅም።


ሰባተኛ፤ ቢቀበልም ባይቀበልም ገዢው ፓርቲ ከስደተኛው የሚየሚፈልገው የውጭ ምንዛሬና ተባባሪ ኪራይ ፈላጊ የሆነ ደጋፊ ነው። ይኼን በማጤን ህወሓት ልዩ ትኩረት ሰጥቶና ስትራተጂ አውጥቶ ስደተኛውን ያባብላል፤ ለመከፋፈል ሲል አዘውትሮ ይሰራል፤

ሰባተኛ፤ ገዢው ፓርቲ የስደተኛውን የገንዘብ፤ የእውቀት፤ የአገር ወዳድነት ወዘተ ባህርይ ስለሚያውቅ የተለየ ትኩረት ሰጥቶ በስለላ፤ በማስፈራራት፤ በተቋሞች ክፍፍል (ለምሳሌ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያንን በመከፋፈል፤ የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮችን በማባበል፤ ከክርስትያኑ እንዲለዩ በማድረግ፤ የሚጠራጠራቸውን በመከታተል) በያመቱ ብዙ ሚሊዮን ዶላር ወጭ ያደርጋል፤ በውጭ ያሉ አገር ወዳዶችንና  የሰብ አዊሙብት ተከራካሪዎችን የተለይ ክትትል በማድረግ አንዳዶቹን በሌሉበት ፈርዶባቸዋል፤

ስምንተኛ፤ የህወሓት በስደተኛው ላይ ትኩረተ የሰጠው የአገዛዝ ዘዴ ስደተኛውን የእድገቱ ተካፋይ ለማድረግ በመሞከር፤ ለመገዛት የማይችሉትን/የማይፈቅዱትን በመወንጀል፤ ዜግነታቸውንና ሃብታቸውን በመካድ የውጩ ህብረተሰብ አገር ቤት እንዳለው እንዲከፋፈል አድርጎታል። በሃይማኖት ያለው ልዩነት የፍልስፍና ሳይሆን ስርአቱ የፈጠረው የከፋፍለህ ግዛው ነጸብራቅ ሆኗል።

ስደተኛው የኢትዮጵያን ሕዝብ ስርጭት የሚወክል ቢሆንም በጎሳ ተለያይቶ የጎሳ ቤተ ክርስቲያኖች ሰርቷል፤ በሰርግና በሌላ ብዙም አይገናኝም። በኤትዮጵያ ጉዳዮች ላይ ከጎሳ በላይ መወያየት ቀርቷል ለማለት እንገደዳደለን። በዚህ አንጻር ሲታይ አገር ቤት የሚኖረው ሕዝብ የተሻለና የኢትዮጵያን ሕዝብ ስርጭት የሚወክል ውይይት ያደርጋል እንላለን። ይኼም ሁሉ ሆኖ የሚያስተባብረውና የሚቀሰቅሰው የአገር ውስጥ ሰብሳቢ የሃሳብ አንድነትና አመራር ቢያገኝ ገንቢ የሆነ ሕብረተሰቡን የማስተባበርና የማቀራረብ ሚና ሊጫወት ይችላል የሚል ግምት አለን።

ሰንጠረዥ ዘጠኝ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ስርጭት (Ethiopia's Mosaic)




[ማስታወሻ፤ኦሮሞ፤ ሰላሳ አራት ነጥብ አምስት በመቶ፤ አማራ፤ ሃያ ስድስት ነጥብ ዘጠኝ በመቶ፤ ሶማሌ ስድስት ነጥብ ሁለት በመቶ፤ ትግሬ፤ ስድስት ነጥብ አንድ በመቶ፤ ሲዳማ፤ አራት በመቶ፤ ጉራጌ፤ ሁለት ነጥብ አምስት በመቶ፤ ወላይታ፤ ሁለት ነጥብ ሶስት በመቶ፤ ሃዲያ፤ አንድ ነጥብ ሰባት በመቶ፤ አፋር፤ አንድ ነጥብ ሰባት በመቶ፤ ጋሞ፤ አንድ ነጥብ አምስት በመቶ፤ገዲኦ፤ አንድ ነጥብ ሶስት በመቶ፤ ሌሎች፤ አንድ ነጥብ ሶስት በመቶ ተብሎ ይነበብ። ህወሓት ሆነ ብሎ የሚከተለው የሕዝብ ቆጠራ የአማራውን ቁጥር በየ ዓመቱ እየቀነሰው ይገኛል፤ ይህ ከጎሰኛነት ጥላቻ የመጣ የአማራ ቁጥር ቅነሳ ስሌት ጋር አብሮ የሚሄድ ነው]

ይህ የአገሪቱ የሕዝብ ስርጭት እንዳለ ሆኖ፤ የወደፊቱን ስናይ ሁኔታው ተስፋ አያስቀርጥም። ምንም እንኳን ገዢው ፓርቲ በአገር ቤት የኢትዮጵያን ሕዝብ በጎሳና በሃይማኖት ቢከፋፍለውና መብቱን ቢያፍነው፤ ስደተኛው ካሰበና ከፈለገ መከፋፋፈሉን ወደ ጥንካሬ ለውጦ የተከባብሮ መኖር አርአያ ሊሆን ይችላል። የሞነርበት ህብረተሰብ አርዓያ ሊሆነው ይችላል። የኢኮኖሚ ስደት የመንፈስ ስደት አልፈጠረም የሚል ነው። ሌላው፤ ሰላምና እርጋታ ከሌለ ስደተኛው የራሱ ጥቅም--የኢንቬስትመንት፤ የወላጅና ዘመድ ወዘተ መጎዳት ራሴን ይጎዳኛል ከሚል ግንዛቤ ላይ ያደርሰዋል። ብዙው ስደተኛ በየቦታው የግል ኢንቬስትሜንት አለው። የአሜሪካ የልቦና ክፍል በቅርቡ ያደረገው ምርምርና ድምዳሜ አገዛዙ ከማይወጣቸው የፖሊሲና የመዋቅራዊ ማነቆዎች አዙሪኝ ውስጥ መግባቱን ያሳያል። እነዚህ ምክንያቶች ለአገሪቱ የመውደቅ አዝማሚያ መቀስቀሻ (trigger) ሆነዋል እያለ አስጠንቅቋል። እንደዚህ ያለ ቀውጢ ቀን ከመጣ ብሄርና ሃይማኖት አይለይም። ስደተኛው መገንዘብ ያለበት የአገሪቱ የመውደቅ አዝማሚያ ከአብዛኛው ሕዝብ አሰቃቂ ኑሮ ተለይቶ ሊታይ እነደማይችል ነው። ከላይ እንዳሳየነው፤ የአስጊና አሳፋሪ ሙስና መነሻዎቹ ግልጽ ናቸው። የከተማና የገጠር መሬት አመራር፤ ፈቃድና አስተዳደር ከፍተኛ ደረጃ ይዘዋል። ሌሎቹ ምንጮች፤ አስመጭና ላኪ፤ ኮንትራቶች፤ ፈቃዶች፤ አቅርቦቶችና ግዢዎች፤ (State sponsored supplies and procurements) ልዩ ልዩ የውጭ እርዳታዎች ናቸው። ስደተኛው የሚልከው ገንዘብና ባለስልጣናት ወደ ውጭ ሲሄዱ የሚወስዱት የውጭ ምንዛሬ መጋቢ ናቸው።

ስደተኛው መሬት ሲገዛና ቤት ሲሰራ በስርአቱ ውስጥ ነው። እውነተኛ፤ ውድድር ያለበት፤ በሕግ የሚተዳደርና የሚገዛ የመሬት አስተዳደር የለም። ክፈል የተባለውን ይከፍላል። ማንኛውም የግንባታ ስራና ፈቃድ ባለስልጣናት ካልፈቀዱ ሊሰራ አይችልም። መንግሥት ለስደተኛው ባለቤትነት እድል ስለሰጠው መልሶ የሚጠይቀው ድጋፍንና ታማኝነትን ሆኗል። ስደተኛው በፍርሃትና በአጎብዳጅነት ዓለም ውስጥ ይኖራል የሚሉ ብዙ ታዛቢዎች አሉ። በስደተኛው

ኢንቬስትመንት ሲታይ፤ አብዛኛውን የግንባታ፤ የአግልግሎትና የውጭ ምንዛሬ ንግድ ስራ የሚቆጣጠሩት ህወሓት፤ የህወሓት አጋር ድርጅቶችና ግለሰቦች ናቸው። ስደተኛው ከዚህ መረብ ውጭ ሊሰራ አይችልም። ካልቻለ፤ ልክ ኢትዮጵያ እንደሚኖረው ሕዝብ እውነተኛ መብቱ ተገፏል። ከላይ የጠቀስነው ዓለም ባንክ ደግፎት የተካሄደው ጥናት የሚለው፤ “በኢትዮጵያ በፍጥነት በሚያድጉት (የሙስና ምንጮች ማለቱ ነው) የቤትና የህንጻ፤ የመንገድና የድልድይ፤ የጤናና የትምኅርት ቤት፤ የግድብና የመገናኛ ስራዎች” ከገዢው ፓርቲ ቁጥጥር ውጭ አይታሰቡም። እውነተኛ ውድድር፤ ነጻና ብሄራዊ የሆነ ተቆጣጣሪ የለም። (Zero Checks and Balances). “የግንባታው ስራ ለሙስና ዋና መነሻ ሆኗል” የሚሉ ማስረጃዎች አቅርቧል። በተመሳሳይ፤ Global Financial Integrity and the University of Massachussetes ያወጧቸው ዘገባዎች በማያሻማ ሁኔታ፤ደሃ፤ ረሃብተኛና የእርዳታ ጥገኛ ከሆነችው ኢትዮጵያ በያመቱ ብዙ ቢሊዮን ዶላር እንደሚሰረቅና ወደ ውጭ እንደሚሸሽ መዝገበዋል። ለሙስና መጋቢ ከሆኑት ምንጮች መካከል በተደጋጋሚ የሚጠቀሰው ስደተኛው በያመቱ የሚልከው ገንዘብ (Remittances) ነው። ይህ ገንዘበ ለገዢው ፓርቲ የውጭ ምንዛሬ ምንጭ፤ ከአገሪቱ ተሰርቆ ለሚሸሸው ብዙ ቢሊዮን ዶላር ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ተረጋግጧል። መንግሥት፤ የመንግሥት ደጋፊዎችና ከመንግሥት ጋር ተባባሪ የሆኑ ነጋዴዎች በብዙ የውጭ ምንዛሬ በሚያስገኙ የንግድ ዘርፎች ተሰማርተዋል። እነዚህ አትራፊዎች የስደተኛውን የባህልና የቁሳቁስ ፍላጎት ወደ ገበያ ለውጠውታል። በቅርቡ ጠቅላይ ሚንስትር ሃይለማሪያም ደሳለኝ ስለ ጤፍ ውድነትና እጥረት ሲናገር “የጤፍ መወደድ ምክንያት ቀድሞ ሊመገብ የማይችለው አርሶ አደር እንጀራ መብላት መጀመሩ ነው” ብሏል። እነጀራና ጤፍ ለትርፍ ወደ ውጭ ስለሚላክ ነው ቢል አግባብ ይኖረው ነበር። ከእልፈቱ በፊት ጠቅላይ ሚንስትር መለስ ያለውን ያስታውሰናል። “የስኳር እጥረት የተከሰተበት ዋና ምክንያት ሕዝቡ ለመጀመሪያ ጊዜ ስኳር ስለቀመሰና መግዛት ስለቻለ ነው።” ሌላው ያለው፤ “እንደ ኢትዮጵያ በፍጥነት በሚያድጉ አገሮች አቅርቦትና ፍላጎት በአንድ ላይ አይሄዱም።” ሁለቱም ጠቅላይ ሚንስትሮች የተናገሩት ተመሳሳይ ነው። እጥረትን የፈጠረው የፍላጎት ለውጥ ነው የሚል። ችግሩ እንደዚህ በቀላሉ የሚገለጽ አይደለም። አቅርቦት ከፍላጎት ጋር አብረው አልሄዱም። ገዢው ፓርቲ፤ ከሁሉም በላይ የውጭ ምንዛሬ ይወዳል። የምርት ውጤት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ይፈልጋል። ስደተኛው የዚህ የተዛባ የኢኮኖሚና የገበያ አመራር ሰለባና ተካፋይ ሆኗል።

ለመግዛት የሚችለው፤ በተለይ በምእራብ አገራት የሚኖረው ስደተኛ ከኢትዮጵያ ጋር የቀረበ ግንኙነት አለው። ብዙ ቁሳቁስ ይገዛል። በገፍ ይመላለሳል። “ትኩስ እንጀራ በኢትዮጵያ አየር መንገድ እየተላከ ይገዛል።” የአገር ቤቱ ሕዝብ በምግብ ዋጋ ግሽበት ባይሰቃይ ኖሮ መግዛቱ አያጠያይቅም ። ጠቅላይ ሚንስትሩ “የጤፍ እጥረትና ዋጋ ችግር” ከገበሬው የጤፍ እንጀራ ፍላጎት ጋር አብሮ የሚሄድ ነው ብሎ ሲናገር ስደተኛው ይህ ከሆነ እንዴት እኛ “የትኩስ እንጀራ ሸማች ልንሆን ቻልን” ብሎ መጠየቅ ይኖርበታል። የሚላከው እንጀራ በአመት ከአስር እስከ አስራ አምስት ሚሊዮን ዶላር ነው። ይህ ምንም ልዩነት አያመጣም ለማለት ይቻላል። መታየት ያለበት የእንጀራው ኤክስፖርት የሌሎች ችግሮች ነጸብራቅ ነው። እንጀራ በአውሮፕላን ተጭኖ ሲመጣ እጥረት ይፈጥራል። በሕግ ያልታወቀ ሃብታምነት ይፈጥራል። አገር ቤት ለሚኖሩትና የመግዛት አቅማቸው ዝቅተኛ ለሆኑ የዋጋ ግሽበት ያመጣል። ልክ እንደ ከተማ መሬትና ቤት። የምግብ ዋጋ ግሽበትን ቀደም ብለን አቅርበነዋል። በምርጫ ዘጠና ሰባት አምስት ብር ያወጣ ምግብ ቢያንስ ሰባት ጊዜ አድጓል። ስደተኛው ለዚህ ሕዝብ ላማረረው የኑሮ ውድነት አስተዋጾ አድርጓል። ቢቀበልም ባይቀበልም፤ በአብዛኛው ሕዝብ ገቢና የኑሮ ሁኔታ መባባስ፤ ስደተኛውም የችግሩ አካል እየሆነ ሄዷል።

የኢትዮጵያን ስደተኛ ከሌላው ምን ይለየዋል?

የኢትዮጵያን ስደተኛ ከአብዛኛዎቹ የሚለየው ገንዘብ በመላኩ አይደለም። ገንዘቡ የፖሊሲ ለውጥ ለማምጣት አልቻለም። ለአደገኛው የኑሮ ውድነትና ለሙስና ጫና አስተዋጽኦ አድርጓል። ስደተኛው ራሱን ከማገልገል ባሻገር፤ “በመንግሥት ሚና ላይ ጠቃሚ ሃሳቦች ለመስጠት መብት የለውም።”  ከአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚሰነዘርበትን አግባብ ያለው ትችት አዳምጦ የአስተዋፆውን አይነትና ዘዴ እንደ ገና መፈተሽ አለበት። ስደተኛው በኢትዮጵያ ቤትና ሌላ የመግዛት አቅሙ ከአብዛኛው ሕዝብ ጋር ሲወዳደር ከፍተኛ ነው። የሚኖረው ኑሮ አገር ቤት ከሚኖሩ ጥቂት ኃብታሞች ጋር የተጠጋ ሆኗል። ይህ ሁኔታ ለአብዛኛው ሕዝብ የሚጨነቅበት ግንዛቤ ሰጥቶታል። ስደተኛው ጡሮታ ሲወጣ ወይንም ለሽርሽር ሲሄድ ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመቸውም የተሻለ እድገት አግኝተዋል የሚለው የስደተኛው አመለካከት የራሱን የተሻለ ኑሮ ወደ ሕብረተሰቡ መሻሻል አያይዞ ሃቁን ሸፍኖታል የሚል ስሜት አለ። ይህን ግንዛቤ እንጋራለን። በዚህ መጽሃፍ እንዳሳየነው፤ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የዛሬ ሃያ አምስት አመት ይኖረው የነበረውን ኑሮ ለመኖር አልቻለም። ይህን የኑሮ ወደ ኋላ መጎተት የሕዝብ ቁጥር መጨመር ብቻ ሊገልፀው አይችልም። የእድገቱ ውጤት ያመጣው የፍላጎት ለውጥ ነው ሊባል አይችልም። <u>ዋናው ችግር አቅርቦት (የአገር ውስጥ ምርት) ከፍላጎት ጋር አብሮ ለመሄድ አለመቻሉ ነው። ባጭሩ፤ መዋቅራዊ ለውጥ የለም።</u>

ጥቂት ኃብታሞች፤ በየጊዜው የሚጎበኘው፤ ጡሮታ የሚወጣው፤ ሁለት ኑሮ የሚኖረው ወዘተ ስደተኛ "እድገት አለ" ሲል ይህ እድገት ለማን እንደሆነ ለመግለጽ ተስኖታል። የኢኮኖሚው ሃቅ፤ ጥቂት ኃብታሞች የተወሰነውን አቅርቦት ሲሻሙት ዋጋ እየናረ መሄዱ ነው። አቅም የሌለው በቀን ሶስት ምግብ ቀርቶ ሁለት ምግብ ለመብላት ተቸግሯል። ስደተኛው ይህን ሃቅ የረሳው ይመስላል። ባለፉት አስር አመታት፤ "WE ARE THE WORLD/1984" የሚል የአስቃቂ ተፈጥሮ ረሃብ (Famine) አለም አቀፍ ትእይንት አላየም። ያላየበት ምክንያት ምርት ስላደገ አይደለም። ለጋሶች በተከታታይ የምግብ ድጋፍ ስለሚሰጡ ነው። ይህም ሆኖ በረሃብና ከረሃብ ጋር በተያያዘ በሽታ የሚሞቱት ኢትዮጵያውያን ቁጥር አድጓል። ረሃቡና የተያያዘ ሞት እነደሌላው ችግር "የለም" ተብሎ በመንግሥት ታፍኗል። የተፈጥሮ ዕልቂት ቢመጣ ያለፈው ዓለም አቀፍ አቤቱታ እንደሚደገም ስደተኛው መገመት ይችላል።

ሰደተኛው ሊረሳው የማይችለው ሃቅ፤ በስደት የሚያገኘው ገቢ በኢትዮጵያ የሚገዛውን አቅም አይቶ ተራው ሕዝብ በልቶና ደልቶት ያድራል ከሚል የተሳሳተ ድምዳሜ መድረሱ ከእውነቱ የራቀ ነው። ከታላቁ ረሃብ ወዲህ የኢትዮጵያ መንግሥት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የምግብ ዋስትና አላስገኘም። ማንም ሃላፊነት አለብህ ያለው የለም። ገዢውን ፓርቲ ስደተኛው የሚልከውን የውጭ ምንዛሬና እርዳታ "እንዴትና ለማን ጥቅም ታውለዋለህ" ብሎ የጠየቀው የለም። በኢትዮጵያ እንደ እስክንድር ነጋ ያሉ ጋዜጠኞች ገዢውን ፓርቲ በሙስና ሲያጋልጡት ወደ እስር ቤት ልኳቸዋል። ገዢው ፓርቲ ወደ ካዝናው የሚገባውን ገንዘብ በብሄር፤ በቋንቋ፤ በእድሜ ወይንም በፆታ አይለየውም። "ገንዘብ ገንዘብ ነው" ብሎ ለምዝበራ፤ለሙስና፤ ለማሸሽ ይጠቀምበታል። ስደተኛው ቢያንስ ለገዢው ፓርቲ "በምታገኘው የውጭ ምንዛሬ ልዩነት የማታደርግ ከሆነ በስልጣን መከፋፈል፤ በስራ እድል፤ በትምኅርት፤ በጤና፤ በመሬትና በቤት፤ በግል ሃብት ባለቤትነት ወዘተ የጎሰኛ አድልዎ ማድረግህን ማቆም አለብህ ለማለት ይችላል። ሕዝብ እየተራበ በአውሮፕላን "ተጭኖ የሚመጣ እንጀራ መግዛት አንፈልግም። የንግድ ፈቃድ ስለምትፈቅድ መከልከል ግዴታህ ነው" ለማለት ይችላል።

በእኛ ግምት ይህን ማለቱ ብቻ በቂ አይሆንም። ገዢው ፓርቲ ዋጋ እንዲከፍልና ለለውጥ ክፍት እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል። ስደተኛው ገዢው ፓርቲ ለውጥ ካላደረገ፤ የውጭ ምንዛሬ መላኩ ራስን ከመጥቀም ባሻገር ዘላቂ መፍትሄ አያመጣም ብሎ ለመወሰን ይችላል። የፖሊሲ ለውጥ ከሌለ፤ "እኛ የዱሮዎቹ" ማለት ተከታታይ ይሆናል። ረሃብተኛውና ደሃው በማይታወቅ ወይንም በተሸፈነ (silent) አስቃቂ አገዛዝ ይኖራል። የተፈጥሮ ሃብቱን ጥቂቶች--ከፍተኛ ገቢ ያላቸውን ስደተኞች ጨምሮ--ይከብሩበታል። ገዢው ፓርቲ ዲሞክራሳዊ ለውጥ ካላደረገ ስደተኛው የውጭ ምንዛሬ አንልክም ለማለት መብቱ ነው። የገዢውፓርቲ አመራር ስደተኛውም "በኔ ቁጥጥር ስር ነው" የሚል እምነት እንዳለው ካወጣው አምሳ ገጽ በላይ የሆነ መመሪያና መቆጣጠሪያ ሰነድ (strategy) ለማየት ችለናል። ስደተኛው ይህን ሰነድ በይፋ የአፈና ሰነድ መሆኑን ተቀብሎ በያለበት ገዢውን ፓርቲ ሊያጋልጠው ይችላል። ምርምራችን ያስተማረን አንድ ተጨማሪ ነገር አለ። ይህም፤ የማንም አገር ስደተኛ እንደ ኢትዮጵያ ስደተኞች "ፈሪ፤ ራሳቸውን ወዳዶችና የፖለቲካ መጫወቻ የሆኑ ለማግኘት አልቻልንም" የሚሉ ታዛቢዎች ብዙ ናቸው። ይህ ሁኔታ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ ጋር አይሄድም።

ገዢው ፓርቲ ነጋዴ ሆኗል

ገዢውፓርቲ ነጋዴ መሆኑን አሳይተናል። በህጻናትና በልጃገረዶች ይነግዳል። ስደተኛው ይህን የአገዛዝ ኪራይ ሰብሳቢነት ሃቅ ተገንዝቦ ያለውን እውቀት፤ ልምድ፤ ገንዘብና የውጭ ግንኙነት አቅም የኢትዮጵያን ሕዝብ ከዚህ ራሱን ወዳድና ጎሰኛ ቡድን ነጻ ለማውጣት ምንም አልሞከረም። ቢፈልግ በኢትዮጵያ ዲሞክራሳዊ ስርአት እንዲመሰረት ታሪክ የሚመዘግበው አስተዋጽኦ ለማድረግ ይችላል። ይህን ካደረገ፤ ለአብዛኛው ሕዝብ፤ ለራሱ ልጆች፤ ለዘመዱና ለተከታታይ ትውልድ ዘላቂነት ያለው አስተዋጽኦ ለማድረግ እንደሚችል አንገምታለን። የሚጎድለው ፍላጎት አለመኖር፤ ከብሄር፤ ከሃይማኖትና ከሌሎች ሊታረቁ ከሚችሉ ልዩነቶች ነጻ አለመሆን፤ ከግል ጥቅምና ሃብት፤ በተለይ ከፍርሃት ባሻገር ነጻነትና እኩልነት ሊያመጡ የሚችሉትን እድል በልቦና ቀርጾ ተግባራዊ ለማድረግ አለመቻል ይገኙበታል። በአብዛኛው፤ ስደተኛው የሚኖርበትና ገቢ የሚያገኝበት አገር እንዴት ከዚህ ደረጃ እንደደረሰ ለመጠየቅ የቻለ አይመስልም። የአድልዎን፤ የማጭበርበርን፤ የሌብነትን፤ የአስተዳደርን፤ የሙስናን ዋጋ ክብደት ፈጽሞ አላሰበበትም።

ያለፉት የህወሓት/ኢህአዴግ--ሃያ ሶስት--የአገዛዝ አመታት የምዝበራ አመታት መሆናቸው ምንም አያጠያይቅም። መለስ፤ የራሱ ፓርቲ የፈጠረው አገዛዝ ምዝበራ ወይንም ዘረፋ እንደፈጠረ ተቀብሎ በመጽሄቶቹ የወቀሰው ጥቂት ባለስልጣናትንና የግል ነጋዴዎችን ነበር። የፍልስፍና ተሰጦ የነበረው ቢሊየኔሩ "ማርክሲስት-ሌኒኒስቱ" መለስ የፈጠረው አገዛዝ ምዝበራ ፈጣሪ አለመሆኑን ለማሳየት፤ በህወሓት ውስጥ ጥቂት ራስ ወዳዶችና ስግብግቦች፤ በሱ ቋንቋ፤ "ቦናፓርቲስቶች" እንደሆኑ ተችቷቸዋል። ግራ ክንፉ "ቦናፓርቲዝምን" የሚተረጉመው እንደ "ፀረ-አብዮት፤ ፀረ-ሕዝብ፤

ፀረ-ዲሞክራሲ" ነበር። የዚህ ትርጉም ችግሩ በአፈጻፀም ጉድለት ታይቷል። የዘረፋ ስርአት ወለድ አገዛዙ ከሆነ ከፍተኛ ዘራፊዎች ባለስልጣናት መሆናቸውን አገዛዙ አልተቀበለም። አብዮተኛ ነኝ ብሎ ለመፎከር አይችልም። በእኛ ጥናት፤ "ሁሉም ባለስልጣናት ቦናፓርቲስት" ናቸው። አዲስ ኃብታም ያልሆነ ከፍተኛ ባለስልጣን ፈልገን ለማግኘት አልቻልንም። ስለዚህ፤ መለስ ሃቁን አለመቀበሉ እውነቱን ዋጋቢስ አያደርገውም። እንዲህ ብሎ ነበር፤ "እኛ እንደፈለግን እንዳንሰርቅ፤ እንደፈለግነው መብት እንዳንገፍ፤ በሌላ አነጋገር አብዮታዊ ዲሞክራሳዊ ባህሪያችንን እንዳናጠፋ ፈቅዶ የሚያዘን ሃይል የለም።" ቅንጅት ሲያሸንፍ አመራሩን አስሯል። ንጹህ ኢትዮጵያውያንን ገድሏል። አርባ ሽህ አስሯል። ጋዜጠኞችን አባሯል ወዘተ። አብዮተኛ ህይወቱን ለፍትህ መስዋእት ያደርጋል።

የውስኪ ሙሰኛ ከቢሊየኔር ሙሰኛ ጋር አይወዳደርም

የሙስናን ክብደትና ጉዳት አይቶ መሳቅ አይቻልም። ህወሓት/ኢህአዴግ ስልጣን በያዘበት ማግስት የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ስለ አለፉት ገዢዎች ዘራፊነት እንዲህ ብሎ ነበር። "ስልጣናቸውን ተጠቅመው ካፒታል ለማከማቸት ዝርፊያ በሚያካሂዱበት ጊዜ የመንግሥት ባለስልጣኖችም የሚችሉትን ያህል <u>እንዲቦጭቁ፤ ገንዘብ አከማችተው የካፒታሊዝም ገዢ</u> መሬት እንዲቀራመቱና በዘላቂነት ለመደላደል መሞከራቸው የግድ ነው። ስለዚህ ነገሩ ሁሉ የአባትህ አገር ሲወረር አብረህ ውረር ይሆናል፤ የስርዓቱ አንድ መለያ ባህሪይም ሙስና ይሆናል።" አባባሉ ባለስልጣናት የፖለቲካ ስልጣን ተጠቅመው ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው "ለመቦጭቅ፤ ገንዘብ ለማከማቸት፤ ለመዝረፍና ገንዘባቸውን" ተጠቅመው መሬት ለመግዛት፤ ህንጻ ለመስራት፤ ገንዘብ ለማሸሽ ይችላሉ ማለት ነው። አስቂኝ የሚሆነው ገዢው ፓርቲ የገለበጠው፤ በያካባቢው በጦር ተከቦ ኢትዮጵያንና ስልጣኑን ለማዳን ይታገል የነበረው የደርግ መንግሥት ባለስልጣናት ቢፈልጉም የሚሰረቅ የውጭ ምንዛሬ አልነበራቸውም። የስልጣን ብልግና አልነበረም ማለት አይደለም፤ ነበር። የሚያሳፍርና የሚያስጠይፍ። ከውስኪ፤ ከጠላ፤ ከሰጋ፤ ከግል ብልግና፤ ከፍየልና ከዶሮ ወጥ በላይ ሊሰርቁ አልቻሉም። ብዙዎቹ አገር ወዳድ፤ ለአብዮቱ ተገዢ ነበሩ። መንግሥቱ ሃይለማሪያም በጨካኝነት መወገዙ ተገቢ ነው። ከሁሉም በላይ አገር ወዳድ የነበረና ለአገሩ በቀን ብዙውን ሰዓቶች ይሰራ የንበረ መሪ ሙሰኛ አልነበረም። ኮሎኔል አጥናፉ አባተ፤ ከኢትዮጵያ ለመውጣት አመቻቼ ሁኔታዎችን የፈጠረልኝ አገር ወዳድ የደርግ አባልና መሪ በግል ሳጫውተው መንግሥት ኃይለማሪያም "ደፋር፤ ቆራጥ፤ አገር ወዳድ፤ ቀን ከሌት ለሃገሩ የሚሰራ" ነው ብሎ ነግሮኝ ነበር። በመካከላቸው ልዩነቶችም እንደ ነበሩ፤ እሱ ያለ ምሁራን ተሳትፎ "አገሪቱ አደጋ" ይደርስባታል የሚል እምነት እንደነበረውም አማክሮኛል። <u>ባጭሩ ለማለት የምንገደደው መንግሥቱ ኃይለማሪያም የሚመራውም መንግሥት ስልጣኑን ተጠቅሞ የተደራጀ ዘረፋ አላካሄደም።</u> የአጼ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት በሚመለከት ያቀረብነው ማስረጃ ተመሳሳይ ነው። ጉቦ መስጠት በኢትዮጵያ ባህል የተለመደ መሆኑን ከልጅነቴ ጀምሬ አውቃለሁ። ይኼን የዶሮ፤ የፍየል፤ የዊስኪና ጠጅ ጉቦ ከዛሬው ዘረፋ ጋር ለማወዳደር አይቻልም። ሙሰኛ ለመሆን በሙስና አግባብነት ማመን ያስፈልጋል። ሙሰኛ ለመሆን የሚሰረቅ ገንዘብ መኖር አለበት። ሙሰኛ ለመሆን ከአገርና ከወገን የበለጠ ለራስ፤ ለጠባብ ቡድንና "ለጎሳ" ማሰብ ያስፈልጋል። ሙሰኛ ለመሆን አብሮ መኖርን መካድ፤ መገንጠልን መቀበል ያስፈልጋል። ገንዘብ ማሸሺን ከዚህ ብልጣ ብልጥነት ጋር አጣምሮ አዲስ እሴት ማድረግን ይጠይቃል። ሙሰኛ ለመሆን "ፍርሃተ እግዚአብሄርን" መካድ ያስፈልጋል። ሙሰኛ ለመሆን ስር ዓቱን፤ ሕገ መንግሥቱን፤ ዳኞችን፤ የፌደራል ፖሊሶችን፤ አስተዳዳሪዎችን፤ ሃላፊዎችን ወዘተ ማሳመንና ለዚህ አዲስ እሴት ተገዢና ተጠቃሚ ማድረግ ያስፈልጋል። የህወሓት/ኢህአዴግን አገዛዝ ከሌሎቹ የሚለየው እነደዚህ ያሉ ባህሪዎችንና ተግባሮችን አዘውትሮ ስለሚጠቀምባቸው ነው። "እኛ እንደፈለግን እንዳንሰርቅ፤ እንደፈለግነው መብት እንዳናፍን... የሚያዘን ሃይል የለም" ሲባል የምናቀርበውን አስኳል አገርና ሕብረተሰብ ጎጂ እሴት ያካትታል። "በጭቁን ብሄር/ብሄረሰብና ሕዝቦች ስም ታግለን የፖለቲካ ስልጣን የያዝንበት ዋና ምክንያት አለ። ራስን ኃብታም ማድረግ ይባላል። መንግሥትንና ህገመንግሥቱን እስከ ተቆጣጠርን ድረስ ሠብአዊ መብቶችን ለማፈን፤ አገሪቱን ለመዝረፍ፤ ገንዘበ ለማሸሽ መብታችን ነው" የሚል የአገዛዝ ስልት ነው። 82/

ሂሳቡ ምን ያሳያል?

የተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅት፤ UNDP, Illicit financial flows from the least developed countries: 2000-2008, David Spencer, UNDP, Capital Flight, Illicit Flows and Cross-border Tax Evasion, Transparency International and Global Financial Integrity የሚጋሩት የኢትዮጵያ ሙስና አደገኛ ደረጃ ላይ መድረሱን ነው። የተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅት ያሳሰበው ከፍተኛ መሪዎች ስልጣን እየተጠቀሙና ከሌሎች ጋር እየተመሳጠሩ "ሕገወጥ በሆነ መንገድ በጣም ደሃና የእርዳታ ጥገኛ ከሆኑ አገሮች ወደ ውጭ የሚሸሸውና ለግል ጥቅም የሚዘዋወረው ብዙ ቢሊዮን ዶላር ለልማት ዋና ማነቆ ሆኗል" የሚል ነበር። የገዢው ፓርቲ ባለስልጣናትና ደጋፊዎች ገንዘቡ እንዴት ወጣ፤ ማን አወጣው የሚሉት ክርክር ዋጋ ቢስ ነው። ወንጀሉን ከራሳቸው ሃላፊነት ወደ

ሌላው ለማዘዋወር። አምባገነናዊ በሆነው የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ ከፍተኛ ባለስልጣናት "መስረቅ፤ ማጭበርበር፤ መዝረፍ፤ ገንዘብ ማሸሽ፤ ሠብአዊ መብቶችን ማፈን" ታግለን ስልጣን የያዝንበት ዋጋ ክፍያ ነው ብለዋል። (Reward for fighting and winning). The University of Massachussets, Capital Flight from Sub-Saharan Africa, 1970-2010 ከሁሉም ዘገባዎች ጥልቀት፤ ስፋትና ጥራት ያለው ሆኖ አግኝተነዋል። ዓለም ባንክ ካስደረገው ጥናት በላይ ከሕግ ውጭ የሚሸሸውን ገንዘብ አቅርቦታል። ለማጠናከር የምንፈልገው ሙስናውና ወደ ውጭ የሚወሰደው ብዙ ቢሊዮን ዶላር እንዴት ይወጣል የሚለውን የዘዴ ጥያቄ ነው። የሚከተሉትን ዘዴዎች ይጨምራል።

- የውጭ ንግድ ዋጋን በመደለዝ (Misinvoicing/mispricing); export underinvoicing or overinvoicing). በውጭ ንግድ በኩል ዋናው የስርቆት፤ የሙስናና ከህግ ውጭ የገንዘብ ማሸሺያ መንገድ ሆኗል።

- ወደ ውጭ የሚላከውን እቃ ባለመመዝገብ። (Cross-border trade and the like).

- ከውጭ ለሚመጡ ከፍተኛ መሳሪያዎች የሚከፈል ኮሚሽንና ጉቦ። (Commissions, kickbacks and bribes).

- ስደተኛው የሚልከውን የገንዘብ መጠን መቀነስ። ችርቻሪዎችን በየቦታው ተክሎ ዶላሩ፤ ፓውንዱ ወዘተ ውጭ ተመንዝሮ እንዳይገባ ማድረግ። እአአ በ 2012፤ ብሄራዊ ባንክ በመንግሥት ትእዛዝ ወደ ባንክ ገብቷል ያለው ከተላከው ከግማሽ በታች ነበር። በሰንጠረዥ አስር እንዳሳየነው፤ የዓለም ባንክ ጥናት ከመካሄዱ በፊት ገዢው ፓርቲ ስደተኛው ገንዘብ የሚልከውን ገንዘብ ቀንሶ የሚያሳይ ማስረጃ ያቀርብ ነበር። በተጠቀሰው አመት ከአንድ ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ዶላር፤ በባንክ የተገኘው ስድስት መቶ ስድሳ አንድ ሚሊዮን ዶላር ነበር። ብዙ ቢሊዮን ዶላርና ተመሳሳይ የውጭ ምንዛሬ በባን አይመዘገብም፤ የት እንደ ሄደና እንደተደበቀ ለማሰብ አያስቸግርም።

- ለመከላከያ፤ ለስለላ፤ ለፀረ-ሽብርተኛነት ዘመቻ የሚገኘውና የሚወጣው የውጭ ምንዛሬ። የመንግሥት ምስጢር የሚባለው ከፍተኛ ነው። (National security related state secret).

- ብር ወደ ውጭ ምንዛሬ በመለወጥና በስደት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ብር በዶላር እንዲለውጡ ማባበል። የውጭ ምንዛሬውን ወደ ውጭ ማሸሽ ወይንም ውጭ ማስቀረት።

- ለመንግሥት ስራ ወደ ውጭ የሚሄዱ ወይንም ለሚሄዱ ታማኝ ግለሰቦች ከሚያስፈልገው በላይ የውጭ ምንዛሬ መስጠትና ውጭ እንዲቀር ማድረግ ይገኙበታል።

ህወሓት/ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘበት አመት ጀምሮ እስከ 2010 ድረስ ወደ ውጭ ከሚላከው የአገሪቱ እቃ ከሚገኘው የውጭ ምንዛሬ ሃያ አራት ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ዶላር ጠፍቷል። ("$24.9 billion of Ethiopia's export earnings have been drained through mispricining...Ethiopia's capital flight is larger than the estimate reported"). Global Financial Integrity, December 2011 report on Illicit flow ያቀረበው ተመሳሳይ ሁኔታ ያሳያል። እአአ ከ 2000-2009 $11.7 ቢሊዮን ተዘርፏል። በ 2009 ብቻ $3.26 ከአገር ወጥቷል። ከበፊቱ አመት እጥፍ ሆነ። የኬ አሁንም እንደሚካሄድ እንገምታለን። (Illicit outflow doubled in 2009). የዛሬ ሁለት አመት የማሳቹሴትስ ዩንቨርስቲ ያጠናው ይህ ከፍተኛ ቁጥር በያመቱ እንደቀጠለ ያሳያል። በዝቅተኛ ግምት ሲታሰብ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለፉት አስራ አራት አመታት ብቻ እስከ ሃያ አምስት ቢሊዮን ዶላር ተዘርፏል። ከላይ የተጠቀሱት የምርምር ተቋሞች ከሚያውቁት ሌላ ከሕግ ውጭ ከአገር የሚወጣ ገንዘብ እንዳለ እንገምታለን። ስደተኛው ወደ አገሩ የሚልከው የውጭ ምንዛሬ በአግባብ አይመዘገብም። አንባቢውን እንደ ገና ለማሳሰብ፤ ባለፉት ጥቂት አመታት ስደተኛው ወደ ኢትዮጵያ በአፊሻልና በሌላ መንገድ የሚልከው የውጭ ምንዛሬ ኢትዮጵያ ከእርዳታ ከምታገኘው የበለጠ ነው። ስደተኛው የሃገሪቱ የግንባታ ስራ (massive construction in the form of houses, villas, condominiums etc.) ተባባሪ፤ ተጠቃሚና ተሳታፊ ሆኗል። በአብዛኛው ስደተኞች መንግሥትን ስለማያምኑ ገንዘብ በድብቅ ቢልኩ ራሱ ህወሓት ስልጣን ከመያዙ በፊት ይጠቀምበት የነበረውን ዘዴ ተጠቀሙ ማለት ነው። ብዙ የከተማ ቤቶችና ህንፃዎች የሚሰሩት በስደተኛውና በቤተሰቦቹ፤ በዘመዶቹ፤ በወዳጆቹ፤ በተባባሪዎቹ ነው። ስለዚህ በድብቅ ተላከ ብሎ "ሌባን ሌባ" ብሎ መናገር አስቸጋሪ ይሆናል። መለስ እንዳለው ያይቱን እንዳላዩ፤ የሰሙትን እንዳልሰሙ መሆን ዛሬ የተለመደ ሆኗል። አገዛዙን እስካላስፈሩት ድረስ ማንኛውም በሌሎች አገሮች ህገ ወጥ የሚባል ነገር ሁሉ ኢትዮጵያ ይካሄዳል።

ያለምንም ገደብ ለማለት የምንችለው በእየ ዓመቱ ብዙ ቢሊዮን ዶላር ከሕግ ውጭ ይላካል ወይንም ወደ ሃገር በመግባት ፋንታ በውጭ ይቀራል። በአገው ውስጥም ይንቀሳቀሳል። እንደዚህ ያለ ሃፍረትና ይሉኝታ የሌለበት ዘረፋ በማንኛውም የኢትዮጵያ መንግሥት ተካሂዶ አያውቅም። እአአ ከ 2000--ጀምሮ ይኼ መፅሃፍ እስከተዘጋጀበት ድረስ ሰንጠረዡ የሚያሳየው ወደ ውጭ የሚላከው፤ ወይንም በውጭ የሚቀረው ገንዘብ ከፍ እያለ መሄዱን ነው። ብሄራዊ ባንክ የመዘገበውና ለዓለም ሕዝብ ያስታወቀው በ 2008-2009 እየቀነሰ እንደሄደ ያሳያል። ለምን ስንል የዓለም ኢኮኖሚ ቀውስ ስለነበረ ይባላል። ሆኖም ላኪዎቹ መላካቸውን፤ ቤትና ሌላ መስራታቸውን አላቆሙም። ከእርዳታ፤ ከውጭ ንግድ፤ ከስደተኛው ወዘተ ይምጣ አይምጣ፤ በተክክል ለማወቅ አይቻልም፤ ከምርጫ ዘጠና ሰባት ወዲህ ብቻ በአመት ቢያንስ ሶስት ቢሊዮን ዶላር ከሕግ ውጭ ወደ ሌሎች አገሮች ይላካል። ወደ መንግሥት ካዝና ገብቷል የሚለውን በአመት ስምንት መቶ ሚሊዮን ዶላር አማካይ ብንቀበል-- ከተላከው ሃያ አንድ ቢሊዮን ዶላር-- አስራ አምስት ቢሊዮን ዶላር የት እንደገባ አይታወቅም። የማንጠራጠረው ወደ ውጭ ባንኮችና ወደ ሌሎች መደበቂያዎች እንደተላከ መሆኑን ነው። ይኼ ሁሉ ተደማምሮ "የማህበረሰብ ቀውስ ፈጥሯል።" 83/

የሙስና ወንፊቶች ጉዟቸው

ብዙ ቢሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ከሚሰበሰብባቸው መንገዶች መካከል፤ በድምሩና በተከታታይነቱ ሲታይ ስደተኛው ከሚልከው የበለጠ ምንጭ (source) የውጭ እርዳታ ነው። የስደተኛው ብብዙ የተለያዩ መንገዶች ስለሚዘዋወር። በሰንጠረዡ አስራ አንድ እንዳሳየነው፤ ገዢው ፓርቲ ስልጣን ከያዘበት ጀምሮ በኦፊሴልና ከኦፊሴል (በባጀት ከሚታየው) ውጭ ያገኘው ገንዘብ ከአርባ ቢሊዮን ዶላር አልፏል። የኦፊሴሉ ብቻ በአመት አራት ቢሊዮን ዶላር ሆኗል። ዓለም ባንክ ደግፎት ባወጣውና በዓለም ባንክ የውስጥ ነጻ የምርምርና የፍተሻ ተቋሞች ዘገባ እንዳየነው ብዙው የእርዳታ ገንዘብ ለገዢው ፓርቲ ቁጥጥር ውሏል። ገንዘቡ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በአደራ የሚሰጥ ቢሆንም የሚሰጠው ለመንግሥት ነው፤ የሚቆጣጠረው መንግሥት ነው። ከስራ ላይ የሚያውለው መንግሥት ነው። ማስረጃ የሚያቀርበው መንግሥት ነው። ስለሆነም፤ ማንም ነጻ ተቋም የማይፈትሸው የውጭ ምንዛሬ የት እንደገባ ለማወቅ አይቻልም። በማያሻማ ደረጃ ለማለት የምንችለው፤ የእርዳታው ገንዘብ ለሙስና መጋቢ መሆኑን ነው። ሰብሰብ አድርገን ስናየው፤ ወደ ውጭ ከሚላከው እቃ የሚገኘው የውጭ ምንዛሬ፤ ስደተኛው ከሚልከው የሚገኘው የውጭ ምንዛሬና ሰፊው ከእርዳታ የሚገኘው የውጭ ምንዛሬ የሙስና ወንፊት ሆነዋል። ስርአቱ በምስጢርና በዘዴ የሙስና ወንፊት ፈጥሯል። በአገር ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ የሚዘረፈው የአገሪቱና የደሃው ህብረተሰብ ገንዘብ መጠን በትክክል አይታወቅም። የምናውቀው ባለፉት ሃያ ሶስት አመታት ብዙ አስር ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ሃብት መሰረቁንና ከአገር መውጣቱን ነው። ሌላው በነጻ ድርጅቶች ምርምር የተገመተው በአመት ቢያንስ ሶስት ቢሊዮን ዶላር ከአገር ተደብቆ እንደሚወጣ ወይንም ወደ አገር መግባት የነበረበት በውጭ እንደሚቀር ነው። ተመልካቾች ገዢው ፓርቲ እየሰረቀም ይሰራል ይላሉ። የዚህ አይነት መስራት ለስርቆት ያመቻል እንላለን።

ለማወቅ ያልቻልነው፤ ማን፤ እንዴትና ወደ የት የሚለውን ነው። ሙሰኞቹ ህገወጥ በሆነ መንገድ የሚዘርፉትን በያመቱ ብዙ ቢሊዮን ዶላር በምን ዘዴ፤ በማን ስም፤ በየት አገር እንደሚያንቀሳቅሱትና እንደሚያስቀምጡት። ይህን በተመለከተም የምናውቀው ነገር አለ። መለስ እንዳለው "ለመስረቅም ጎበዝ መሆን ያስፈልጋል።" ጎበዝ ሰው ዘዴና ግንኙነት ይፈጥራል። መነሻውንና መድረሻውን ይደብቃል። የሃገሩን ጥቅምም መነገጃ ያደርጋል። ገንዘብ ለማሸሽና ለመደበቅ የሚችሉት ግለሰቦች በልዩ ልዩ አገሮች ግንኙነት ያላቸው፤ አገሮችን ለመጎብኘት አቅምና ምክንያት ያላቸውና ከውጭ ድርጅቶች ጋር የመዋዋል ብቃት ያላቸው፤ በኤምባሲዎችና ሌሎች አለም አቀፍ ስብስቦች ለመገኘት የሚችሉ ናቸው። ሆንግ ኮንግ ለመደበቅ፤ ከቻይናዎች ጋር ግንኙነት ያስፈልጋል። ማላየዢያ ለመደበቅ፤ ከግልሰቦች፤ ኩባንያዎችና ከመንግስት ባለስልጣናት ጋር ቁርኝት አስፈላጊ ነው። በሆንግ ኮንግ "የኢትዮጵያ የሃይል ኩባንያ" ሲመሰረት ቻይናዎች የፈጠሩት አይደለም። ያለ ካፒታል ሊመሰረት አይችልም። መስራቾና ባለቤት ሊሆን የሚችለው ገንዘብ ያሸሸና የመንግሥት ድጋፍ ያለው ኢትዮጵያዊ ነው። አንዳንድ የውስጥ አዋቂዎች የኢትዮጵያ ከፍተኛ ሙሰኞች የካሪቢያን ደሴቶች መጎብኘት፤ ለምሳሌ ኬይማን፤ ከጀመሩ ቆይተዋል ይላሉ። የምስራቅ ኤዢያን ከዳሰሱ ቆይተዋል። አሁን የመደበቂያ ምድሩን አስፋፍተዋል። ገንዘብ ፈላጊዎች እስካሉ ድረስ ሽማች እንደልብ ነው። የኬይማን ደሴቶች ለገንዘብ ድብቃ መድረሻ ከሆኑ ቆይተዋል። ከፍተኛ ካፒታል ያላቸው የኢትዮጵያ ሙሰኞች በኬይማን ደሴቶች የድብቅ ሂሳብ (secret accounts and deposits) እንዳላቸው ይነገራል። ወደነዚህ ደሴቶች ለመሄድ በአሜሪካ ማለፍ ያስፈልጋል። ገንዘቡን ለማሸጋገር የአሜሪካን ወይንም የሌሎች አገሮችን ባንኮች መጠቀም አስፈላጊ ነው። ባጭሩ ለማለት የምንችለው ገንዘብ የሚሰርቁትና የሚያሸሹት የምስጢር ዘዴውን ጥበብ ያደረጉ ናቸው። የበላዮች ባይሆኑ ወይንም አገዛዙ ባይደግፉቸው ከዚህ ደረጃ አይደርሱም። ለአንባቢው የምናሳስበው፤ የውጭ እርዳታው፤ ስደተኛው የሚልከውና ከውጭ ንግድ የሚገኘው የውጭ ምንዛሬ በገፍ እየተዘረፈ ነው። ስለዚህ አብዛኛው ገንዘብ ለአገሪቱና ለኅብረተሰቡ

አገልግሎት አለመዋሉን እናስምርበታለን። ደጋፊዎች ደጋግመው የሚሉት፤ ምዝበራ አለ። ሆኖም፤ ይህ መንግሥት ከሌሎቹ በበለጠ አገሪቱን ዘመናዊ አድርጓታል ነው። እኛ የምንከራከረው፤ የህወሓት/ኢህአዴግ የመንግሥት ካፒታሊዝም የፖለቲካ ስልጣን ይዞ በደሃው ላይ የሚነግድ ካፒታሊዝም ነው። አገር ወዳድ ሰርቆም የሰረቀውን ለአገሩ ልማት ያውለዋል። ህወሓት/ኢህአዴግ የፖለቲካ ስልጣን ይዞ ምዝበራን በተደራጀ መልክ የሚያካሂድ አገዛዝ ነው። ደሃነትና ስደተኛነት ጥልቀትና ስፋት ቢይዝ፤ አገሪቱ አደጋ ውስጥ ብትገባ፤ ዜጎች በኑሮ ውድነት ቢማረሩ፤ የእርስ በርስ ግጭት በየቦታው ክስተቶች ቢያሳይ፤ የሰብአዊ መብቶች አፈና ለ አላኬይዳና አል ሸባብ አመፀኞት መግቢያ ከፋች ቢሆኑ ወዘተ ደንታ የለውም። "ስልጣን ወይም ሞት" ብሎ የተመሰረተና የሚሰራ ቡድን ነው።

"ገዢው ፓርቲ ፍጥነት ያለው መሰረተ ልማት አካሂዷል። ስግብግብነት ፤አድልዎና ሙስና ቢኖሩም፤ የስርአቱ ጥቅም ከጉዳቱ ይበልጣል" ይላሉ። እኛ የምንከራከረው፤ ገገዢው ፓርቲ የመንግሥት ካፒታሊዝም አመራር የተከተለው፤ ለራሱ ጠባብ ጥቅም ነው። ዘላቂነትና ፍትሃዊነት ያለው የልማት መሰረት ለመጣል አልቻለም፤ አይጥልም። ለሕዝብ ተገዢነት የለውም፤ በሕግ የበላይነት አያምንም እንላለን። እውነተኛ፤ አገሪቱን የሚወክል ሃብታም የካፒታሊስት መደብ አልፈጠረም። በጠባብ ጎሰኞች የበላይነት ቁጥጥር ስለሚካሄድ ቀጣይነትና ፍትሃዊነት ያለው ብሄራዊ ልማት ስኬታማ ለማድረግ አይችልም ። አገሩን የሚወድ ሙሰኛ ገንዘብ አያሸሽም። ባይሆን ገንዘቡ ሰርቆ አዲስ ፋብሪካዎች በሃገሩ ይመሰርታል፤ ለወጣቶች የስራ እድል ይፈጥራል። አዲስ ባለጠጋዎች ሃብታም የሆኑት በሚታይ፤ በሚዳሰስ፤ በሚለካ የምርት ውጤት አይደለም። ስንት ኩንታል ገብስ ወይንም ጤፍ አመረቱ? ስንትና ምን አይነት ፋብሪካዎች አቋቁመው ለአገርና ለውጭ ገበያ የምርት ውጤት አቀረቡ? ስንት የማዳበሪያ ፋብሪካዎች ሰሩ የሚሉ ጥያቄዎችን እናቀርባለን። ለስንት ኢትዮጵያውያን ወጣቶች የስራ እድል ከፈቱ? እንላለን። ዘመናዊ ካፒታሊዝም ቀጣይነት ሊኖረው የሚችለው ለአብዛኛው ሕዝብ እድል ሲከፍትና ብሄራዊ የሆነና የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚመስል ወይንም የሚወክል ብሄራዊ ከበርቴ ሲፈጠር ነው። የመካከለኛው መደብ እየሰፋ ኢትዮጵያን የሚመስል ቅርፅ ሲኖረው ለሕዝብ አገልጋይ፤ የሕዝብን ህይዎት ለዋጭ የልማት ስልት ተከትሏል ለማለት እንችላለን። ለአብዛኛው ሕዝብ እድል ካልከፈተ፤ የሞራል ብቃትነቱ ያከትማል። የህወሓት/ኢህአዴግ የኢኮኖሚ አመራር የመንግሥት ካፒታሊዝም አመራር የሞራል ብቃት የለውም። ፍትሃዊ አይደለም ለማለት የምገደደው ለዚህ ነው።

ኪሱ የማይሞላ ሙሰኛ

ኢትዮጵያ፤ የካፒታል ደሃ፤ ኋላ ቀርና በእርዳታ የምትንቀሳቀስ አገር ናት። የካፒአል ደሃ የሀነችበትን መሰረታዊ ምክንያቶች አቅርበናል፤ ጉቦ፤ ሙስና ከሕግ ውጭ ሃብት ማሸሺ የችግሩ እምርት ናቸው። ከአገር ውስጥ ገቢዋና ከቁጠባ የሚገኘው ካፒታል አስፈላጊውን የልማት ፍላጎት አያሟላም። የውጭ ምንዛሬ ህገወጥ በሆነ መንገድ ከአገር እየወጣ ወይንም እንዳይገባ እየተደረገ ለደሃነት፤ ለረሃብና ለበሽታ ቅነሳ የሚውለውን ካፒታል በጣም ቀንሶታል። የሚካሄደው ምዝበራ በመቶ ሽህ ዶላር አይደለም። በቢሊዮን ዶላር ሂሳብ ነው። በአንጻሩም ምዝበራው ያገለገለው ጥቂት ባለስልጣናትን፤ ተባባሪ የሆኑ ነጋዴዎችንና የውጭ ባንኮችንና ኢንቬስተሮችን ነው። የገዢው ፓርቲ አለቃዎች ስርቆትን፤ ማጭበርበርን፤ አድልዎንና ሙስናን እንደ ካፒታሊዝም አገዛዝ ጥበብ አይተውታል። ሙስና ነውር ነው ብለው አያውቁም። "የዘረፍነው ይበቃናል" የሚል ስሜት የላቸውም። በሌላ አባባል፤ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የፖለቲካ ስልጣን የያዘ የመዝረፍ "መብት አለኝ" የሚል ፍልስፍና ተቋማዊ ሆኗል። ሠብአዊ መብቶችን ሙሉ በሙሉ ማፈን ከምዝበራው ጋር አብሮ የሚሄድ የአገዛዝ ዘዴ ሆኗል። እኛ የሰብአዊ አፈናን ከፖለቲካና ከኢኮኖሚ የበላይነት ስልት ነጥለን አናይም። የሳንቲሙ ግልባጭ ናቸው። የገዢው ፓርቲ ባለስልጣናትና ተባባሪዎቻቸው የመንግሥቱን ካዝና በሙሉ ለሚፈልጉት ጉዳይ ወይንም ጥቅም እንዲውል በሚረዳ መንገድ ይቆጣጠሩታል። ከገዢው ፓርቲ ቁጥጥር ነጻ የሆነ ብሄራዊ "አይን ጠባቂ" ተቋም አለመኖሩና የኢኮኖሚው አመራር በሕግ አለመስተናገዱ፤ የአገሪቱ ባጀት የአንድ ፓርቲ ባጀት እንዲሆን ረድቷል። ቴድ ቬስታል እንዳስቀመጠው፤ የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት ስትራተጂ "ሊጋሶችን ለማባበል የተጠቀመበት ዘዴ ነው። ለዲሞክራሲ፤ ለካፒታሊዝምና ለነጻ የውድድር ኢኮኖሚ አመራር (the free enterprise system) ቆሜአለሁ" የሚል ነበር። ጥናታችን የደመደመው የገዢው ፓርቲ ባለስልጣናትና ደጋፊዎቻቸው ስርአቱን ለግል ታይቶ የማይታወቅ የኃብት ማካበቻ መሳሪያ አድርገውታል። ሳይሰሩና ሳያመርቱ ሃብታም ሆነዋል። ቀውጢ ቀን ቢከሰት፤ የተደበቀው፤ የሸሸው ሃብት ያገለግላል ማለት ነው።

ጉቦና ሙስና በሌሎች አገሮችም እንዳለ እናውቃለን። በአሜሪካም አለ። ልዩነቱ፤ ዲሞክራሳዊ በሆኑ አገሮች ብሄራዊና ነጻ የሆኑ ተቋሞች፤ ህያውና ነጻ የሆኑ የማህበረሰብ ድርጅቶች ፤ ነጻ የሆነ የሕግ አገልግሎት፤ ከመንግሥት ቁጥጥር ውጭ የሆነ ፕሬስና ያልታፈኑ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መኖራቸው (A system of checks and balances) ከፍተኛና ዝቅተኛ ሙሰኞችን ለፍርድ ለማቅረብ፤ ለዜጎችና ለዓለም ሕዝብ ለማስታወቅ አስችሏቸዋል። የማህበረሰብ ድርጅቶች

ወሳኝ ናቸው። በህንድ አገር በየቀኑ የሚደረገው ሰላማዊ ሰልፍና የፕሬሱ ሽፋን ሙሰኞች እንዲጋለጡ፤ የመንግሥት ፖሊሲ ወሳኞት ሕዝቡን እንዲያዳምጡና የኢኮኖሚው አመራር እንዲለወጥ ጫና እያደረጉ ነው። አዲሱ ፕሬዝደንት ሞዲ የተመረጠው ሙስናን፤ የአስተዳደር ብልሺትን ተቃውሞ ነው። ህወሓት የማይፈልገውን ማለት ነው። በዲሞክራሳዊ አገዛዞች ችግሮች የሉም ለማለት አይቻልም። አገዛዙ የሕዝብ ድምጽና ተሳትፎ ስላለበት፤ በጎሳ የተመሰረተ አድልዎን፤ ጉቦንና ሙስናን ለማጋለጥ፤ የመንግሥት አመራርን ለመለወጥ ያስችላል። እንድ ሕንድ አገር። በአንጻሩ፤ የኢትዮጵያ ገዢ ፓርቲ በሕግ የሚመራና የሚዳኝ የቁጥጥርና የምርምር ተቋምና ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ አይፈቅድም። የከለከለበት መሰረታዊ ምክንያት አለ። ምዝበራ፤ አድልዎ፤ ሙስናና የሡብአዊ መብቶች አፈና እንዳይታወቁ ለማድረግ። በእኛ ግምትና ሌሎች ባለሞያዎች የሚሉት ገዢው ፓርቲ ግልጽነትንና የፕሬስ ነጻነትን የሚፈራው፤ ከፍተኛ የሆኑ የመንግሥት፤ የፓርቲና ተባባሪ ሙሰኞች የሚዘርፉት የገንዘብ መጠንና በዘርፉት ገንዘብ የገነቡት ሃብት እንዳይታወቅ ነው። በተጨማሪ፤ አፈና ካለ ነጻና ፍትሃዊ የፖለቲካ ምርጫ ለማካሄድ አይቻልም። ስለዚህ፤ የቁጥጥር አገዛዝ የባለጠጋነት ጥቅም አለው። አፈናው ሕዝቡ ማወቅ የሚገባውንና የማይገባውን ፤ እውነቱንና ውሸቱን ለመወሰን፤ ለመደበቅና ለመዳኘት ረድቶታል። የገዢው ፓርቲ የበላዮች ስደተኛው የሚልከው ገንዘብ ግማሽ ብቻ እውቅና ይኑረው ብለው ሲወስኑ የግል ጥቅም ምክንያት አላቸው። አራቱን እንጠቅሳለን።

አንድ፤ ከእርዳታ የሚገኘው የውጭ ምንዛሬ እንዳይቀንስ፤ እንዲያውም እንዲጭምር፤

ሁለት፤ የመንግሥት ከፍተኛ ባለስልጣናት "ንጹህ፤ ታማኝና" ለሕዝብ የቆሙ ናቸው እንዲባል፤ ያላቸውን ተጠቅመው አገሪቱን አስደናቂ በሆነ መንገድ እያሳደጉ ነው የሚለው ስሌት አ እምሮ ውስጥ እንዲቀረፅ፤


ሶስት፤ እየተሰረቀ ሕገወጥ በሆነ መንገድ ከኢትዮጵያ የሚወጣው ወይንም በውጭ እንዲቀር የሚደረገው የውጭ ምንዛሬ መጠን እንዳይታወቅ፤ "የሌለ አይሰረቅም" እንዲባል፤

አራት፤ ለዓለም ባንክና ለአይኤምኤፍ ተከታታይ የውጭ ምንዛሬ እጥረትና ችግር እንዳለ ለማሳየትና እርዳታው እየጨመረ እንዲሄድ።

ባለፉት ሃያ ሶስት አመታት፤ የገዢው ፓርቲ በውጭ እርዳታ አቀራረብ ሂሳብ ተጫውቷል። It has doctored and manipulated official data. በኦፊሴልና በሌላ መንገድ የሚገኘውን ገንዘብ መጠን እየለየና እየቀነሰ- OECD የሚያውቀውን ብቻ- በመዝገቡቹ ያሳይ ነበር። የካናዳ የእርዳታ ድርጅት የልዩነቱን ምክንያት ለማወቅ አንድ የግል ተቋም ከፍሎ ጥናት አደረገ። ከታች በሰንጠረዥ አስራ አንድ እንዳሳየነው፤ ጥናቱ ያሳየው የኢትዮጵያ መንግሥት ከኦፊሴል እርዳታው ያላነሰ (Off budget) የባጀት ማሟያ ከውጭ ለጋሶች እንደሚያገኝ ተረጋግጧል። ይህ እርዳታ የሚሸፍናቸው የአስቸኳይ፤ የሡብአዊ ፍላጎት፤ የክልሎች ልዩ ፕሮጀክቶችና ስራዎች (ለምሳሌ ህወሓት ልዩ ትኩረት ለሰጠው፤ ለትግራይ ክልል ጀፍ ሳክስና ሌሎች የሚሰጡትን ሰፊ እርዳታ) ይጨምራል። ከመቶ አምሳ በላይ የመንግሥት ያልሆኑ የውጭ በጎ አድራጊ ድርጅቶች የሚንቀሳቀሱባት ኢትዮጵያ የውጭ እርዳታ የሚፈስበት መንገድ ብዙ ሆኖ አግኝተነዋል። ይህ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኝ መንገድ ሙሉ በሙሉ በመንግሥት አይመዘገብም። የኢትዮጵያ መንግሥት ብሄራዊ ባንክ ከስደተኛው የሚቀበለውን የውጭ ምንዛሬ ቀንሶ እንዲያሳይ ሲያስገድደው ቆይቷል።

ብሄራዊ ባንክ ነጻ አይደለም። እንደ ማንኛውም ተቋም በፖለቲካ ቁጥጥር ስር ወድቋል። ሃቁን የማሳየት መብት የለውም። ጥናቶች የሚያሳዩት፤ የሚላከው ገንዘብ ቢያንስ ሰንጠረዥ አስር ከሚያሳየው እጥፍ መሆኑን ነው። በተጨማሪ ከባንኮችና ከገንዘብ ለዋጭ ላኪ ኩባንያዎች--ብዙዎቹ በህወሓት ደጋፊዎች የሚንቀሳቀሱ--ከውጭ የሚላከው በኦፊሴል ከሚላከው በላይ ነው የሚሉ ብዙ ታዛቢዎች አሉ።

ሰንጠረዥ አስር፤ ስደተኛው የሚልከው ገንዘብ ተደልዞ ሲታይ (በሂሳብ የመዋሸት ምሳሌ/ በ $)




የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአግባብ፤ በግልፅነት፤ በሕግ የበላይነትና በውድድር አይሰራም። የጥቁር ገበያው እየተስፋፋ፤ በበርበራ፤ በጅቡቲ፤ በሰሜንና በደቡብ ሱዳን፤ በኬንያ ጠረፍ፤ አየር በአየርና በሌሎች የንግድ በሮች የሚንቀሳቀሰው የጥቁር ገበያ ኢኮኖሚ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ እንዳለበት ተረድተናል። አንዳንድ አገር ቤት የሚኖሩ “አዋቂዎችን” ስናነጋግር፤ የጥቁር ገበያው ኢኮኖሚ በጣም ማደጉንና በአንዳንድ የንግድ ክፍሎች ከሕጋዊው ኢኮኖሚ “እንደሚበልጥ” ነግረውናል። ይኼ ሰው ስራሽ እጥረቶችን ፈጥሯል። የመከላከያና የሕዝብ ደህንነት ኃይሉ የራሱን መንግሥት የሚያንቀሳቅስ ይመስላል፤ ልክ እንደ ግብፅ ማለት ነው። ይኼ “በመንግሥት ውስጥ መንግሥት” የሚመስል ስርዓት ራሱ የሚያንቀሳቅሰውን ኢኮኖሚ መጠን ለማወቅ አይቻልም። የተሃድሶ ግድብ ኩንትራት ለመያዝ ከህወሓት አመራር ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት ያስፈልጋል፤ አቅም ያስፈልጋል። ለዚህ ሁሉ የሚደግፍ አስተማማኝ የተጻፈ መረጃ ስላላገኘን የሂሳብ መጠኑን ለማቅረብ አልቻልንም። ሆኖም፤ የመከላከያውና የደህንነቱ ክፍሎች ከፍተኛና ወሳኝ የኢኮኖሚ ሚና እንዳላቸው እናምናለን። የውጭ መንግሥታት በፀረ-ሽብርተኝነት ላይ ለኢትዮጵያ መንግሥት የሚሰጡት ከፍተኛ እርዳታ በምስጢር የተያዘ ነው። ምን ያህል የውጭ ምንዛሬ እንደሚገኝ “የመንግሥት ምስጢር” ነው።

ሆኖም፤ የጥቁር ገበያው ሰፊና ጥልቀት ያለው፤ ከሕጋዊው ኢኮኖሚጋር እነደሚወዳደርና ለዋጋ ግሽበት አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ተረድተናል። የጥቁር ገበያው ስፋትና ጥልቀት ለውጭ ምንዛሬ መደበቂያና ማሸሽያ ወንፊትነት (sieve and porousness) አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ተገንዝበናል። የፖለቲካ፤ የስለላና የመከላከያ ተገን ያለው ቡድን የፈለገውን ንግድና የውጭ ምንዛሬ ሽሽት ለማካሄድ ይችላል። በበርበራ፤ በጂቡቲ፤ በሰሜንና ደቡብ ሱዳን በድብቅ የሚካሄደው ንግድ በአይነቱ ከሌሎች፤ በሕግ ከሚመሩ አገሮች ይለያል። ህወሓትና ወዳጆቹ የበላይነት አላቸው። በደቡብ ሱዳን በሰፊው የሚካሄደው ንግድ የዚህ የበላይነት ክስተት ነው።


ሰንጠረዥ አስራ አንድ፤ የውጭ እርዳታ ፈሰስ አይነቶች (OECD/DAC/IMF/2009/2010)

| አይነት | አላማ | ውጤት | ተሳታፊዎች | ገንዘብ በመቶ ሚሊዮኖች ዶላር |
|---|---|---|---|---|
| አስቸኳይ/ጊዜያዊ ሠብአዊ | ረሃብ | የሰው ህይወት ማዳን/ምግብ | USAID/FAO/WFP/World Bank as part of Safety Net ፤ ባለፈው መስከረም ዓለም ባንክ ስድስት መቶ ሚሊዮን ዶላር ሰጥቷል | 90 በመቶ የአሜሪካ እርዳታ፤ በአመት $1 ቢሊዮን. |
| ሠብአዊ ድጋፍ | የተጎዱ | ለተወሰኑ ክፍሎች | Care, Catholic Relief, Save the Children, Oxfam-about በጠቅላላ ከመቶ አመሳ በላይ የመንግስት ያልሆኑ በጎ አድራጊዎች አሉ | ብዙ መቶ ሚሊዮን ዶላር በአመት(መንግስት የማይመዘግበው) |
| ቀጣይነትና ፍትሃዊነት ያለው ልማት | የኢትዮጵያ ድሃ | ድህነትን መቀነስ/መሰረተ ልማት ማስፋፋት | Thirty bilateral and multilateral agencies: the World Bank, ADB, UNDP, USAID, DFID, CIDA, SIDA and others. ከሰላሳ በላይ የሚሆኑ ድርጅቶች፤ ቻይናንና ሌሎች አዲስ ለጋሶችን አይጭምርም | 1991-2012 ግምት $40 ቢሊዮን. IMF and World Bank data-net ODA rose from $1.3 billion in 2005 to $4 billion in 2012 |

ለማጠቃለል፤ የፖለቲካ ስልጣን ይዞ ከማጭበርበር፤ ከመስረቅ፤ መረጃዎችን ከመለወጥ፤ ከማዳላት፤ ከሙስናና ከፖለቲካ ስልጣን ጋር የተያያዘ ድርጅታዊ ምዝበራ (Organized state sponsored plunder and robbery by top ethnic elites) በአገር ደረጃ በተከታታይ ተካሂዷል። ህብረተሰቡ፤ በተለይ የወጣቱ ትውልድ እየደማ ነው። ለተራው ኢትዮጵያዊ ውጤቱ ግልጽ ነው--ጥቂት፤ ከመንግሥቱ ቁንጮ ላይ ሆነው--የፖሊሲ፤ የፕሮጀክት፤ የኢንቬስትመንትና የገንዘብ አጠቃቀም ውሳኔዎች ስልጣን ያላቸው ግለሰቦች፤ ቤተሰቦች፤ የመሰረቷቸው ድርጅቶችና በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ የተሰራጩ ኢጋሮቻቸው የተደራጀ ምዝበራ አካሂደዋል። አሁንም ያካሂዳሉ።

ድርጅታዊ ምዝበራ እንዲሁ ስኬታማ አልሆነም። ለጥቂቶች ታይቶ የማይታወቅ፤ ከፖለቲካ ስልጣን የመነጨ አዲስ ኃብታምነት ያስገኘው አንድ አምባገነናዊ ፓርቲ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ዘርፎችን ሙሉ በሙሉ ስለተቆጣጠራቸው ነው። ይህ አዲስ ባለጸጋነት ከአብዛኛው ህብረተሰብ የተለየ የገቢ፤ የሃብትና የኑሮ ልዩነቶችን ፈጥሯል። ስርአቱ ብዙ ቢሊዮን ዶላር ሕገወጥ በሆነ መንገድ ከህብረተሰቡና ከአገሪቱ ተነጥቆ ወደ ውጭ እንዲሸሽ አመቻችቷል። ይህ አገዛዝ-ወለድ የምጣኔ ሃብት አስተዳደር፤ አጠቃቀምና ምዝበራ አደገኛ፤ ፀረ-ፍትህ፤ ፀረ-ርትእ የሆነ፤ የኑሮና የማህበረሰብ ልዩነቶችና ቀውሶች ፈጥሯል። (An unprecedented and rising wealth, income and social inequality).

ሰንጠረዥ አስራ ሁለት፤ ፒራሚዳዊው የጥቂቶች የገቢ፤ የኃብትና የኑሮ የበላይነት ቅርፅ




ብዙ ቢሊዮን ዶላር ከአገሪቱ በተከታታይ ... ም ይወጣል። ይህ አስከፊ የማህረሰብ ጉዳት ውጤት አለው። ለህብረተሰቡ ኑሮ መገ... ገንዘብ ወይንም ካፒታል ከህብረተሰቡ

ተመዝብሯል። ተመዝብሮም፤ ልክ እንደ ኢንዶኔዢያ፤ አገር ውስጥ አልቀረም። በኢትዮጵያና በሌሎች ደሃ አገሮች የተደረጉ ጥናቶች የሚያመለክቱት ተቋማዊ በሆነ ሂደት የገቢ፤ የማህበረሰብ፤ የኃብትና የኑሮ ልዩነቶች እየሰፉ ይሄዳሉ። የአሁኑና ተከታታይ ትውልዶች ገቢያቸውንና ኑሯቸውን የማሻሻል እድላቸው እየጠበበ ይሄዳል። መዋቅራዊና ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ድህነት ያመጣል። በደቡብ አፍሪካ የባንቱስታን ስርአት እንደታየው፤ የመሻሻል እድል ፈጽሞ ይጠፋል። ተጨማሪ ወደፊት ኃብትና ስልጣን የሚኖራቸው አሁን ኃብት ያካበቱትና ሃብት ያሸሹት መሆናቸው አይቀርም። Corruption and Illicit outflow will have multigenerational impact. ለምሳሌ፤ የትግራይ ክልል--ጭፍን በሆነ የጠባብ ጎሳ አድልዎ--ዛሬ የዘመናዊነት ቅድሚያ ከተሰጠው፤ ነገና ከነገ ወዲያ ከጋምቤላ፤ ከአፋር፤ ከኦጋዴን፤ ከቤኒ ሻንጉል ጉሙዝ ወዘተ ይቀድማል። የጋምቤላ ክልል ሕዝብ መሬቱ ሲነጠቅ፤ ተከታታይ ትውልድ ደሃና ጥገኛ ሆኖ እዲቆይ ተፈርዶበታል ማለት ነው። ይህ ለብሄራዊ ሰላም፤ አብሮ መኖርና አብሮ ማደግ ማነቆ ይሆናል። በተጨማሪ፤ አይን ያወጣ ምዝበራ፤ ገቢ፤ ኃብትና የኑሮ ልዩነት ለሰላም፤ አብሮ ኑሮን ለማሻሻል፤ ለእርጋታ፤ ለብሄራዊ ዘመናዊነት፤ ለአገር ግዛታዊ አንድነትና ደህንነት ወዘተ ማነቆ ይሆናሉ። እየሆኑ ነው።

ሰንጠረዥ አስራ ሁለት ያሳየው ፒራሚዳዊው የህወሓት/ኢህአዴግ ኢኮኖሚ ከላይ ጥቂት ከገዢው ፓርቲ ጋር ቀጥታ የጥቅም ግንኙነት ያላቸው በገቢ፤ በሃብትና በኑሮ ከፍተኛውን ቦታ መያዛቸውን ነው። ቁጥራቸው ስንት እንደሆነ ባይታወቅም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ እነማን እንደሆኑ ያውቃል የሚል ግምት አለን። ከዚህ አዲስ የሃብታም መደብ ቀጥሎ አለ የሚባለው በራሱ ጥረት የሚኖረው፤ በመንግሥት ስራ የተሰማራውና ሌላው ገቢው ከደሃው ሻል የለ፤ በዓለም ባንክ ትርጉም የመካከለኛ መደብ የሚባለው ነው። የኢትዮጵያ መካከለኛ መደብ ከሌሎች የአፍሪካና አገሮች በጣም አንስተኛ ነው። ለምሳሌ፤ ገቢው ዝቅተኛ ስለሆነ የሚኖረው ኑሮ “ከእጅ ወደ አፍ” የሆነ ነው የሚሉ ብዙ ተመልካቾች አሉ። በኢትዮጵያ ተገጣጥመው የሚሰሩ መኪናዎችን ለመግዛት አይችልም። በቻይና፤ በቬትናም፤ በታይላንድ፤ በናይጀሪያና ሌሎች አገሮች የመካከለኛው መደብ ዋንው ሸማች ነው። ገቢው ከእጅ ወደ አፍ በላይ ስለሆነ። ልጆቹን ያስተምራል፤ ጤናው ይጠበቃል። አገሩን ወይንም የውጩን ዓለም ለማየት ይችላል። ለክፉ ቀን ይቆጥባል። መኖሪያ ቤት ይኖረዋል ወዘተ። ከላይ በተደጋጋሚ እንዳሳየነው ይኼን ለማድረግ የሚችለው የኢትዮጵያ የመካከለኛ መደብ የሚሰራውና የሚኖረው በውጭ አገሮች ነው፤ በተለይ በምእራቡ ዓለም።

በሌሎች አምባገነናዊና በጎሳ ወይንም በሃይማኖት ልዩነቶች የተበከሉ አገሮች እንዳየነው፤ በኢትዮጵያ የተከሰተው ከፍተኛ የኃብትና የኑሮ ልዩነት አደጋ ፈጣሪ ሆኗል። በጥቂት አዲስ ሃብታሞች በአንድ በኩል፤ በመካከለኛውና በደሃው መደቦች በሌላ በኩል ያለው ልዩነት የሰማይና የምድር ነው። ዘጠና በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ገቢው በቀን ከሁለት ዶላር በታች ነው። ስለሆነም፤ የሚኖረው ሕይወት ከእጅ ወደ አፍ የሆነ አስቃቂና አሳሳቢ ነው ብንል ከእውነቱ የራቅን አይመስለንም። የጎሳ ጭቆና ነበር፤ አሁንም አለ የሚሉ የጎሳ ስብስቦችና አፈ ቀላጤዎች በእውነቱ የወሎን፤ የጎንድርን፤ የጎጃምን፤ የሰሜን ሸዋን የከተማና የገጠር ዜጎች ኑሮ በፍጹም አያውቁትም ለማለት እንገደዳለን። ከጥቂቶች በስተቀር የሚኖሩት ኑሮ ከአፄ ኃይለ ሥላሴና ከደርግ መንግሥት የባሰ እንጂ የተሻለ አይደለም። በደቡብና በኦሮሚያም ያለው ሁኔታ ከዚህ የተሻሰለ ነው ለማለት አንችልም። የእለት ኑሮውን ለማሟላት የሚደክም ዜጋ ጨቋኝና ተጨቋኝ፤ ጥላቻን የሚከተል ነው ለማለት ሃሰትን እንደ እውነት እሴት ማድረግን ይጠይቃል። የሚያዋጣው አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ደሃ መሆኑን ተቀብሎ ለዚህ መፍትሄ መፈለግ ነው። ለማለት ይምንገደደው እድገት ታሳያለች በምትባለው ኢትዮጵያ ከፖለቲካ ስልጣን የመነጨ የገቢና የኃብት ጥቅልነት (Heavy Concentration of Income and Wealth at the Top) ህሊና በሚፈታተን ደረጃ  እንደ ተከሰተ በነፍስ ወከፍ ገቢ፤ በኑሮ ውድነት፤ በተራው ሰው ኑሮ፤ በሙስና፤ በስራ አጥነት፤ ከአገር ተሰርቆ በሚወጣ ገንዘብ፤ በወጣቱ ትውልድ ስደት ወዘተ አይተናል። የአይን ምስክሮች ብዙ ናቸው። ለአንባቢ እንዲቀል፤ ይህን ከፖለቲካ ስልጣን ብልግና ጋር የተጣመረ አዲስ ባለጠጋነት፤ ፒራሚዳዊ ካፒታሊዝም ብለን ሰይመን ከላይ በሰንጠረዥ አስራ ሁለት አቅርበነዋል። የዚህ አይነት ከአገዛዝ ብልግና፤ ከሡብአዊ መብቶች አፈና፤ ከተፈጥሮ ሃብት መማረክ ወዘተ የተገኘ ባለ ኃብታምነት የአገሪቱን የማምረት ሃይል ቀንሶታል። የተራውን ሕዝብ የነፍስ ወከፍ ገቢና የወጣቱን ትውልድ የስራ ወይንም የራስን ድርጅት የማቋቋም እድል አፍኖታል። የፒራሚዱ ሰንጠረዥ እንደሚያሳየው፤ አብዛኛው ገቢና ኃብት የተያዘው የመንግሥቱን ፖሊሲና ውሳኔ በሚያሽከረክሩት፤ ከቁንጮው ላይ ባሉ በጥቂቶች ከፍተኛ ባለስልጣናትና ተጣምረው በሚሰሩ ግለሰቦች፤ ቡድኖች፤ ለተወሰኑ ቡድኖች ለተደራጁ ተቋሞች፤ የውጭና የውስጥ ኩባንያዎች ነው። በአይን ቢታይ ኖሮ፤ የገቢና የሃብት ክምችቱ የአብሊስክ ሃውልት ወይንም የግብጽን ፒራሚድ ይመስላል። ከላይ ጥቂቶች፤ ከእነሱ በታች መካከለኛው ሰርቶ አደር መደብ፤ ከታች ከዘጠና በመቶ በላይ የሚገመተው የኢትዮጵያ ሕዝብ--የነፈስ ወከፍ ገቢ ደሃ-- ይገኙበታል። አንባቢውን ለማስታወስ፤ የስልጣን ሚሊየኔሮችና ቢሊየኔሮች በፈጠረው የህወሓት/ኢህአዴግ ስርአት፤ ዘጠና በመቶ የሚገመተው የአገሪቱ ሕዝብ የሚኖረው በቀን ከሁለት ዶላር በታች በሚሆን ገቢ ነው።

በፍጥነት ያደጉና የሚያድጉ አገሮች ፍትሃዊ የኢኮኖሚ አመራር የሚመርጡትና ኢኮኖሚያቸውን ያለ አድልዎ ለሁሉም ዜጎች ክፍት የሚያደርጉት ምርትና ገቢን ለማሳደግ፤ ለወጣቱ ትውልድ ዘመናዊ የኑሮ እድል ለመፍጠር፤ መካከለኛውን መደብ ለማስፋፋት ወዘተ ነው። አምባ ገነንም ብትሆን በአገር ወዳዲች የምትመራው ቻይና ያደረገችው ማለት ነው። ቻይናም ሆነ ቬትናም፤ ታይላንድ ሆነ ማሌዢያ፤ ቦትስዋና ሆነ ሞሪሽየስ የሚታዩት መስፈርቶች እድገት የጋራ ሲሆን ለሁሉም እድል ይከፍታል የሚል ነው። በኢትዮጵያ የሚታየው የኢኮኖሚ አመራር መካከለኛውን መደብ በተፈለገው መጠን አላስፋፋውም። መካከለኛው መደብ ወደ ቁንጮው ለመሄድ የሚችልበትን በር ሁሉ እየተዘጋበት ነው። ለአብዛኛው ሕዝብ፤ የከተማ ቦታና ቤት የመያዝ መብቶች፤ የገጠር መሬት ባለቤትነት መብቶች ተዘግተዋል። ደሃው እንዳለ በድህነቱ የቆመ ይመስላል። <u>ዛሬ ደሃ የሆነ</u> <u>የገጠር ቤተሰብ ነገ ደሃ የሆነ ልጅ ይኖረዋል ማለት ነው። ልክ በፒራሚዱ ያሳየነው የገቢ፤ የሃብትና የኑሮ መዛባት። እድገት አለ ቢባልም፤ የእድገቱ ውጤት ስርጭት ሚዛናዊና ፍትሃዊ አይደለም።</u> አንድ ወጣት ወላጆቹ በቂና ስራ ለመክፈት የሚያስችል ገቢና ሃብት ቢኖረው አገሩን ለቆ በየመን ተሻግሮ ሳውዲ አረቢያ አይሄድም ነበር። ራሱን አልጠላም፤ ውርደት አይፈልግም። የኢትዮጵያን የገቢና የሃብት ስብስብና ክምችት የፒራሚድ ካፒታሊዝም (Crony Capitalism is another name) ሆኗል የምንለው ለዚህ ነው። ካፒታሊዝም ለጥቂቶች፤ በጥቂቶች ማለት ነው።

የዚህን ፒራሚዳዊ ካፒታሊዝም አሰራር አደጋና የሚያመጣውን አመፅ በቱኒዚያ፤ በሊብያ፤ በግብጽ፤ በየመን፤ በሶሪያ፤ በፊሊፒንስ (በማርቆስ ጊዜ)፤ በናይጀሪያ ለብዙ አስርት አመታት፤ በአንጎላ፤ በኬንያ (በተለይ በፕሬዘደንት ሞይ ጊዜ) ወዘተ አይተናል። ብዙዎቹ መንግሥታት በሕዝብ አመጽ ተለውጠዋል። የኢትዮጵያው ከእነዚህ አገሮች ይብሳል። የኢትዮጵያ ሕዝብ የገቢ ደሃ፤ ረሃብተኛና የእርዳታ ጥገኛ ነው። የእርዳታ ጥገኛ ሆኖ፤ እርዳታው በገፍ "ይሰረቃል።" የሚሰረቀውና ከአገር የሚወጣው ሃብት ከእርዳታ፤ ከውጭ ንግድና ከስደተኛው የሚገኝ ለልማት መዋል የነበረበት፤ ከፍተኛና ተከታታይ የሆነ ነው። ከሃገር ተሰርቆ የወጣው ገንዘብ በሌላ አነጋገር ቢቅርብ ቢያንስ ሶስት የተሃድሶ ግድቦች ያሰራል። ጥቂት ከፍተኛ የፓርቲና የመንግሥት ባለስልጣናት (መለስ የመንግሥት "ሌቦች" ያላቸው) በስልጣናቸው ብቻ ሚሊየኔሮች ከሆኑባቸው አገሮች መካከል ኢትዮጵያ ከፍተኛውን ደረጃ ይዛለች። ሌላው የኢትዮጵያ ሁኔታ ከሌሎች የሚለይበት፤ የሚሸሸው ገንዘብ ረቂቅነትና ዘመናዊነት ባለው መንገድ ነው። ሌላው ይኺን የመሰለ ግዙፍ ገንዘብ ከሃር እየወጣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሃላፊነትና በአገር ወዳድነት ይኼ ሙስና፤ ይኼ ገንዘብ ማሸሽ ሙሉ በሙሉ መቆም አለበት፤ የተሰረቀውና ከሃገር በምስጢር የወጣው መመለስ አለበት የሚል የመንግሥት የበላይ ሆነ፤ ነጻ የሆነ ተቋም የለውም። ለሃገሪቱና ለመላው ሕብረተሰብ የቆመ አለመኖሩ ለሁላችንም ያሳፍራል። ለህብረተሰቡ ደህንነትና ለሃገሪቱ ዘላቂነት የሚያስፈራውና አገር ወዳድና ዲሞክራሳዊ አማራጭ መንግሥት አጣዳፊ በሆነ ደረጃ ያስፈልጋል የሚለውን መሰረተ ሃሳብ የሚያጠናክረው ሙሰኞች መደበቂያቸውን ከአገሪቱ የዲፐሎማቲክና የንግድ ግንኙነቶች ጋር አያይዘው ስላስፋፉት ጭምር ነው። ልክ በሌሎች አገሮች እንደሚሰራበት ልምድ አድርጎ። ሙስና ተቋማዊ ሆኗል ያልንበት ለዚህ ነው። ዱሮ የአፍሪካ አገሮች አምባገነኖች የሚሰርቁትን ገንዘብ በቅኝ አገሮች ዋና ከተሞች፤ በስዊትዘርላንድ ወዘተ ይደብቁ ነበር።

የህወሓት/ኢህአዴግ ስርአት የፈጠራቸው ሚሊየኔሮችና ገንዘባቸውን በምእራብ ባንኮች በቀጥታ አይደብቁም። በምእራብ አገሮች ልዩ ልዩ ኩባንያዎች፤ በልዩ ልዩ ስምና ዘዴዎች ፈጥረዋል። ቤቶች በልዩ ልዩ ቦታዎችና በልዩ ልዩ ግለሰቦችና ቤተሰቦች ስም ገዝተዋል። ብዙ ቢሊዮን ዶላር ተሰርቆና ሸሽቶ በምስጢር ከሚደበቅባቸው አህጉሮችና አገሮች መካከል በብዛት የሚጠቀሱት መካከለኛው ምስራቅ፤ ምስራቅ ኤዥያ፤ ካይማን ደሴቶችና ደቡብ አሜሪካ ይገኙበታል። ይህ ተከታታይ ሙስናና ከአገር ሕገወጥ በሆነ መንገድ የሚወጣው ብዙ ቢሊዮን ዶላር ካላቆመ የኢትዮጵያ ሕዝብ ካለበት የኑሮ ውድነትና ረሃብ፤ የስራ እጥረት፤ የገቢ ደሃነት፤ የወጣት ትውልድ ስደት ወዘተ ሰቆቃ ነጻ አይወጣም። አንዳንድ ታዛቢዎች እንደሚሉትና ባለፉት አመታት እንዳየነው፤ እድገት ይኖራል። መሰረተ ልማትና ሌላ ለጉቦ፤ ለአድልዎ፤ ለሙስናና ገንዘብ ለማሸሽ ወንፊቶች እንደሆኑ በማስረጃ አቅርበናል። ስርዓቱ እድገት ማሳየት ግዴታውም ነው፤ እርዳታ ሰልሚያገኝና የኢትዮጵያን ሕዝብ ድጋፍ ስለሚፈልግ። እድገት ካላሳየ ስርአቱ ይወድቃል። አሁንም ሊጥለው የሚችለው የአብዛኛው ሕዝብ ኑሮ አለሻሻል፤ ገዢው ፓርቲ በተፈለገው ፍጥነትና ስፋት በያመቱ ስራ ለሚፈልገው ሁለት ሚሊዮን ተኩል ወጣት የስራ እድል ለመፍጠር አለመቻሉ ነው። የግሉ ክፍል ካልተስፋፋና የኢትዮጵያን የሕዝብ ስርጭት ካልወከለ ግጭት የማይቀር ይመስለናል። ይኼን ከስርዓት የመጣ ሰው ሰራሽ ችግር ለማስወገድ ይቻላል። ገዢው ፓርቲ የችግሩን ክብደት መቀበል የመጀመሪያው ሄደት ነው። ሰብአዊ መብቶችን ማክበር፤ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ እንዲካሄድ መፍቀድና መሰናከል አለመሆን፤ ብሄራዊና ማህበራዊ ችግሮቾን በጋራ ለመፍታት ደፍሮና ቆርጦ መነሳስት የወቅቱ አስኳል ጉዳዮች ሆነዋል። በእኛ እምነት የኢትዮጵያ የጋራ ችግሮች በጋራ ሊፈቱ ይችላሉ የሚል ነው። ለዚህ ተቆርቋሪነት፤ ሃላፊነት፤ አገር ወዳድነት፤ መላውን ሕዝብ አፍቃሪነት አስፈላጊ ናቸው። ጭፍን የሆነ "ስልጣን ወይንም ሞት" የሚል የጠባብ ጎሰኝነት የአገዛዝ፤ የስልጣንና የሃብት የበላይነት መሰረተ እርዮት

በምንም ዘላቂነት ሊኖረው አይችልም። የምንጨምረው፤ እድገቱ ለአድልዎና ለሙስና መጋቢ ሆኗል። ሌሎችን አግልሏል፤ አስቆጥቷል። ይኼም ሆኖ ለመካድ የማንችለው ለጋሶች በአንዳንድ ክፍሎች እድገት ካዩና የራሳቸውን ጥቅም አገልጋይ የሆነ ቡድን አስተማማኝነት ካረጋገጡ የሚሰጡትን እርዳታ መጠን አይቀንሱም። የሚቀንሱት ሕዝብ እየተቆጣ ሲሄድ፤ ተቃዋሚዎች ሲተባበሩ፤ የሕዝብ ድምጾች በተያያዘና ተከታታይነት ባለው መልክ በየቦታው ሲከሰቱ፤ ተቃዋሚ ነን የሚሉ ሁሉ ሰብሳቢ የሆነ የዓላማ አንድነት ቀርፀው ገንቢ የሆኑ አማራጮችን ለሕዝብ ሲያቀርቡ ነው። በውጭ የሚገኙ የፍትህና የዲሞክራሳዊ መብቶች ጠበቃዎች ሊያደርጉት የሚችሉት አስኳል ስራ ለጋስ መንግሥታትና ድርጅቶች የሚሰጡትን እርዳታ በቀጥታ ከሰብአዊ መብቶች መከበርና ከነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ጋር እንዲያያዝ ማድረግ ነው። በቅርቡ የእንግሊዝ ከፍተኛ ፍርድ ቤት (July 2014) ጋምቤላን በሚመለከት የሰጠው ፍርድ ጥሩ ምሳሌ ነው። ይኼ ፍርድ የሚለው በዓመት ሶስት መቶ ፓውንድ ለኢትዮጵያ መንግሥት የሚሰጠው የእንግሊዝ መንግሥት በጋምቤላና ሌሎች ቦታዎች የሰብአዊ መብቶች መከበራቸውን የመከታተልና የመቆጣጠር ሃላፊነት አለበት የሚል ድምዳሜ ነው።

ለመደምደም፤የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዚህ አሰቃቂ ከሆነ ድርጅታዊ ምዝበራ ነጻ መውጣት መብቱ ነው። የእንግሊዙ ኢኮኖሚስት መጽሄት እንዳሳሰበው በሃላፊነት ያልተደገፈ "እርዳታ የማህበረሰብ አቅም ስለማያጎለምስ" ጥቅሙ ያነጋግራል፤ እንዲያውም ጉዳቱ ሊያመዝን ይችላል። በጥቂቶችና ለጥቂቶች የበላይነት የሚያገለግለው ጠባብና ጎሰኛ የኢኮኖሚ አገዛዝና እርዳታ ራሱ የፈጠራቸውን የፖሊሲና የመዋቅር ችግሮችን ለመፍታት አይችልም። አድልዎን፤ ጉቦን፤ ሙስናንና የአስተዳደር በደልን የፈጠረ፤ ቢያንስ ያባባሰ ገዢው ፓርቲ ነው። አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የእድገቱ ተሳታፊና ተጠቃሚ አልሆነም። ስለዚህ፤ ከተከታታይ ደሃነት፤ ከረሃብ፤ ከስራ አጥነት፤ ከስደት፤ ከተፈጥሮ ሃብት ሽግግር (massive transfer of resources)፤ ከአካባቢ መናጋት አደጋ ወዘተ አደጋዎች ነጻ ለመውጣት መወሰን ያለበት የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። በተለይ ሰፊው የኢትዮጵያ ወጣት ትውልድ። የችግሩን ክብደት የተሸከመውና በተከታታይ ዋጋውን የሚከፍለው ሕዝቡ ነው። ባለ ስልጣኑና ባለ ሃብቱ አይደለም። 84/

የመጨረሻው ምእራፍ ስምንት አገሪቱን ከውድቀት፤ ህብረተሰቡን ከረሃብና ከደሃነት፤ ወጣቱን ከስደት ለማዳንና ሁሉን የሚያስተናግድ የዘመናዊ ኢኮኖሚ መሰረት ለመጣል ምን መደረግ አለበት ለሚለው ጥያቄ፤ መፍትሄዎችን ሳይሆን፤ አቅጣጫዎችን ያቀርባል።

## ምእራፍ ስምንት

## የፖሊሲ አቅጣጫዎች

“የኢትዮጵያ መንግሥት ዛሬ በዓለም ከሚገኙ፤ የፕሬስና የዘመናዊ መገናኛ አፋኝ ከሆኑ አስር መንግስታት ከፍተኛውን ደረጃ ይዟል”

Committee to Protect Journalists

“በነጻነት የሚኖር ግለሰብ ብቻ ነው ለመደራደር የሚችል። እስረኛ ኮንትራት ለመፈራረም አይችልም”

ኔልሰን ማንዴላ

“በውርደት ከመኖር በክብር መሞትን እመርጣለሁ”

አጼ ገላውዲዎስ

በዚሕ መጽሓፍ፤የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት የተፈጥሮ ሃብት አያያዝና የኢኮኖሚ አመራር፤ በአብዛኛው፤ የበላዮችን ወይንም የጎሳ ባለስልጣናትን አገልጋይ መሆኑን አሳይተናል። አንድ የአገር ውስጥ የኢኮኖሚ ባለሞያና አንድ ከሃገር ተገዶ የተሰደደ ጋዜጠኛ ያሉትን ተመርኩዘን የደረስንበት አጠቃላይ ድምዳሜ “አስራ ስድስት የሚሆኑ ስርአት ወለድ ኃብታሞች ቢያንስ የአስራ ስድስት ቢሊዮን ዶላር ሃብት” እንዳላቸው ይነገራል። ከአገሪቱ የ2012 ጠቅላላ ገቢ ከግማሽ በላይ መሆኑ ነው። የውጭ ተመራማሪዎች የቀድሞው ጠቅላይ ሚንስትር፤ መለስ ዜናዊ ብቻ የሶስት ቢሊዮን ዶላር ባለፀጋ መሆኑን ገልጸዋል። ይኼን ነው ወይንም አይደለም ወደሚል ክርክር አንገባም። እውነቱ ወደፊት ይወጣል። የገዢው ፓርቲ ፈጣሪዎችና ከፍተኛ መሪዎች እንደገና ፈጥረናታል በሚሏት ኢትዮጵያ፤ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም እንዳስቀመጠው፤ “የአገዛዝ ሥልጣን የሚመራው በግል ጥቅም ነው። የእውቀት ባለሞያ የሚመራው በእውነት ነው። ግጭት በመሰረቱ በእውነትና በውሸት መሃከል” የሚካሄድ የእሴት ግጭት ነው። አሸንፊያለሁ ባዩ እስከ አፍንጫው የታጠቀና የግል ጥቅሙን በሃይል የሚጠብቅ ቡድን ነው። “ኃይል ወይንም ሞት” የሚል። ስለዚህ፤ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫን ሕዝብ በተከታታይ ካላስገደደው በስተቀር ፈቅዶና ወዶ እንዲካሄድ አይፈቅድም። ይኼን እንጋራለን። ታሪክ፤ ወግና ማእረግ ላላት ኢትዮጵያ የሚያሳፍረውና የሚያሳስበው ስርዓት ወልድ የሆነው የራስ ወዳድነት፤ የአጭበርባሪነት፤ የአድልዎ፤ የጉቦና የሙስና ባህል ህብረተሰቡን መበከሉ ነው። ይኼ መጥፎ ባህል ማህበረሰቡን በክሎታል። በሺታው እንደ ወረርሺኝ ተዛምቷል። ሌላው ቀርቶ መንፈሳዊ “አባቶች” የመንፈሳዊ ስራቸውን ትተው የግል ሃብትና የግል ዝና ለማካበት ከሃገር ሲሰደዱና ሲሯሯጡ የችግሩ ክብደትና ጥልቀት ከምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ ያሳያል። ማንም ሰው ሌላውን እንዳያምን፤ አባት በልጁ፤ ወንድም በእህቱ፤ ጓደኛ በጓደኛው ላይ እንዲሰልል፤ ምስክር እንዲሆን ወዘተ ሲገደድ ማየት ከጥንት የተወረሱ ቅርሶችና እሴቶች እንዴት ዋጋ ቢስ እንደሆኑ ያሳያሉ። ይኼ የቁልቁለት ሄደት ለኢትዮጵያና ኩሩና ታታሪ ለሆነው ሕዝቧ አደገኛ ሁኔታዎችን በመፍጠር ላይ ይገኛል። ምሁሩም ሆነ ተራው ሰው ቂመኛነትን፤ የጎሳና የኃይማኖት ጥላቻን፤ ለጥቅም ተገዢነትን፤ ሃሜትን፤ ሰርጎ ገብነትን፤ መጠላለፍን፤ “ሌላው ነው ቡዳ” ባይነትን፤ በመንደር ደረጃ መከፋፈልን፤ ያለፉትን ያለምንም ማስረጃ ኮናኝነትን፤ አክራሪነትን ወዘተ በማዘውተር ዓለም ውስጥ ይታያል። አዙሪኝ የሆነ የሚበታትን ዓለም ማለቱ ነው። ይኼ ባህል ለአገሪቱ አደገኛ ነው፤ ለሕብረተሰቡ መቅሰፍት ነው። መቆም አለበት። ኢትዮጵያ የሁሉም ጎሳዎችና ኃይማኖቶች አገር ናት። አገሪቱን ከመፈራረስ፤ ሕብረተሰቡን ከእልቂት ማዳን ያለበት ሁሉም ነው፤ በተለይ ወጣቱ ትውልድ። ጊዜው ዛሬ እንጂ ነገ አይደለም።

ኢትዮጵያ ሃብታም ለመሆን የምትችል የተፈጥሮ ባለ ፀጋ ሃገር ናት--ወንዝና ጅረቶች፤ ዝናብ፤ ለም መሬት፤ ሰፊና ገና ያልተነካ የመስኖ መሬትና ደኖች፤ መአደን፤ በአፍሪካ ሁለተኛውን ደረጃ የያዘ የሕዝብ ብዛት ወዘተ ያላት አገር ናት። ደሃና ኋላ ቀር መሆን የሌለባት አገር ስርዓት ወለድ በሆኑ ተከታታይ መንግሥታት ተበድላለች።

አንድ አገር በፍጥነት፤ በቀጣይነትና በፍትሃዊነት ለመልማት የሚችለው የአብዛኛው ሕብረተሰብ ተሳትፎ፤ የሃብት ባለቤትነት፤ የመደራደርና ኮንትራት የመፈራረም ሙብቶች በሕግ ሲረጋገጡ ነው። መብቶቹ የታፈነ ሕዝብ ለመንቀሳቀስ፤ ለመደራደርና ውል ለመፈራረም አይችልም። የኢትዮጵያ መንግሥት እነዚህንና ሌሎችን የህይወት

መለወጫ መብቶች አፍኗል። አብዛኛው ሕዝብ የእድገቱ ተሳታፊ አልሆነም። የፍርሃት ዓለም ሕብረተሰቡን በክሎታል። ችግሮቹን አሳይተናል። ከዚህ በታች የፖሊሲ አቅጣጫዎችና አማራጮችን እናቀርባለን።

1. <u>ነጻ ፕሬስ፤ ነጻ የማህበረሰብ ስብስቦችና ድርጅቶች ለልማት ቁልፍ ናቸው</u>

ጠንካራና ከመንግሥት አፈና የተላቀቀ ተቃዋሚ ፓርቲ ወይንም ፓርቲዎች፤ ሁሉን በእኩልነት የሚያስተናግድ የፍርድ አስተዳደርና የሕግ የበላይነት ለዘላቂና ፍትሃዊ ልማት አስፈላጊ ናቸው። ፍትሃዊ እድገት ያለነጻነት በምንም አይታሰብም። አይቻልም። የኢትዮጵያ መንግሥት የጭቆና አስተዳደር መጥፎነት መታወቂያ መስፈርቶች ብዙ ናቸው። ከእነዚህ መካከል ጋዜጠኞችን ማሳደድ፤ በፈጠራ ማስረጃ ማሰር፤ ንብረታቸውን መውረስ፤ ቤተሰቦቻቸውን ማሰቃየት አንዱ ነው። ህወሓት ስልጣን ከያዘበት እስካሁን ከመቶ አምሳ በላይ የሚሆኑ ጋዜጠኞች ከከትትል ለማምለጥ አገር ለቀው ወጥተዋል፤ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሃላፊ ጆን ኬሪ ኢትዮጵያን ከመጎብኘታቸው ጥቂት ቀናት በፊት ዘጠኝ ጋዜጠኞች ታስረዋል፤ ከዚያ በፊትና በኋላ ሌሎች ታስረዋል። "ከኤርትራ አፋኝ መንግሥት ቀጥላ ኢትዮጵያ በአፍሪካ አህጉር ጋዜጠኞችን በማሰር ሁለተኛ ሆናለች፤ ከዓለም አስር ጋዜጠኞች አፋኝ አሳሪ መንግሥታት መካከል ኢትዮጵያ አንዷ ናት።" ኢትዮጵያ ብዙ ሽህ የፖለቲካ እስረኞች ከታጎሩባቸው አገሮች መካከል ከፍተኛ ደረጃ ይዛለች። ይኼ ሁሉ ለምን ተደረገ? በፖለቲካ ያልተበረዘ ዜና ለሕዝብ ማቅረብ ለፍትህ፤ ለሰብአዊ መብትና ለዲሞክራሲ ቁልፍ ስለሆነ ነው።

ዜናና እውቀት ያለምንም ገደብ ማግኘት ሠብአዊ መብት ነው። ከቁጥጥርና ከአፈና ነጻ የሆነ፤ ችግሮችን በቀጥታ ለሕዝብ ለማቅረብ የሚችል ፕሬስ ከሌለ የአገዛዝ በደሎች ሁሉ ይደበቃሉ። የአንድ ፓርቲና የፈጠራቸው ድርጅቶች የበላይነት ያመጣውን የኢኮኖሚ እድገት መዛባትና የማህበረሰብ ቀውስ በአስተዳደር በደል፤ በአድልዎ፤ በጉቦና በሙስናው ዙሪያ አሳይተናል። ይህን የተዛባና አፋኝ የሆነ ስርአት-ወለድ የፖሊሲ ችግር ለማስወገድ የሚቻለው ከላይ ያቀርብናቸው ተቋም ነክ የሆኑ ነጻነቶችና መብቶች በሕግ ሲከበሩ ነው። ገዢው ፓርቲ የአገሪቱን የምርት ውጤት፤ የተራውን ሕዝብ ኑሮ መሻሻል፤ የወጣቱን ትውልድ የመፍጠርና የራሱን የግል ድርጅት የማቋቋም አቅም አግቧል። ከዝቅተኛ ሙሰኞች ውጭ ስልጣን የያዙና ከባለስልጣናት ጋር የተቆራኙ የስልጣን ሙሰኞች የሚዘርፉትን ብዙ ቢሊዮን ዶላር ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ ከአገር ለማሸሽ ችለዋል። ምክንያቱም፤ እነሱና መሰሎቻቸው ከሕግ በላይ ናቸው። የመጀመሪያው አስፈላጊ ለውጥ (Reform) የሕግ የበላይነትን ተቋማዊና "ሕጋዊ" ማድረግ ነው። ነጻ ፕሬስ፤ የማህበረሰብ ድርጅቶችና ሌሎች አብረው ሕጋዊ መሆን አለባቸው። ከሁሉም በላይ ወጣቱ ትውልድ ለመብቱ መቆም ግዴታው ነው። ዛሬ ስልጣንና ከስልጣን ግንኙነት የተገኘ የብዙ ሚሊየንና ቢሊየን ዶላር ኃብት ያካበቱት የልጅ ልጆቻቸውን የወደፊት ህይወት አስተማማኝ አድርገዋል። የፕሬስ ነጻነት ስለተከለከለ፤ ያካበቱትን ኃብት የሚያውቅ እንዳይኖር አድርገዋል። ህብረተሰቡ "መብቴን የሚከለክለኝ የለም" ብሎ መነሳት የራሱን ክብርና የኑሮ ዋስትና እንደሚያስገኝለት አንጠራጠርም። እነዚህ ያቀርብናቸው ተቋሞች ሕጋዊ ካልሆኑ፤ የፈለገው ጥረት፤ ጥናትና የውጭ እርዳታ ወዘተ ቢጎርፍ አፈና፤ ጎሳዊ አድልዎና ሙስና አይቆሙም። በውጭ የሚደረገው አቤቱታ ተደማጭነት የሚኖረው በአገር ቤት ያሉ ሕብረ-ብሄር ድርጅቶች ለአላማ አንድነትና ለተባበረ ትግል ተገዢ ሲሆኑ ነው። ሕገ መንግሥቱ የሚፈቅደውን መብቶች ሙሉ በሙሉ የመጠቀም መብት የሕዝብ ነው፤ ሕዝቡ ከተባበረ ምንም ኃይል አያቆመውም።

አገር ወዳዶች--በእኛ ስሌት አገር ወዳድነት ከጎሳና ከኃይማኖት በላይ ነው--ለፍትህ-ርትእ፤ ለእውነተኛ እኩልነትና ዲሞክራሲ፤ ለሁሉም የኢትዮፖያ ሕዝብ እኩልነት የቆሙ ሁሉ--ከማንኛውም በላይ መስራት ያለባቸው--ነጻ፤ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ቁጥጥር ውጭ፤ ዓለም አቀፍና ተደጋጋፊ የሆነ የማህበረሰብ እንቅስቃሴ እንዲፈጠር ተግቶ መስራት ነው። የማህበረሰብ ጥንክርና የሌለበት አገር ዲሞክራሳዊ አማራጭን ለመመስረትና ተቋማዊ ለማድረግ አይልም። ፈረንሳዊው ፈላስፋና የታሪክ ሊቅ፤ አሌክሲስ ዲ ቶክቪል፤ Democracy in America በሚለው መጽሃፉ ያቀረበው ለዚህ አላማ ጠቃሚ ነው። "Nothing in my opinion, is more deserving of our attention than the intellectual and moral association of Americans. In democratic countries, the science of association is the mother of science; the progress of all the rest depends upon the progress it has made." ህወሓት የኢትዮጵያ ሕዝብ በዜግነቱ ለመብቱ እንዲደራጅና፤ አማራ፤ ኦሮሞ፤ ጉራጌ፤ ትግሬ ወዘተ ሳይል ተባብሮ እንዳይታገል መሰናክሎችን እንደፈጠረ አሳይተናል። ተቃዋሚው ይኼን ማነቆ ሰብሮና መጥቆ መውጣት አለበት። በዓላማ አንድነት ላይ፤ በኢትዮጵያ ነጻነትና ዘላቂነት ላይ የተመሰረተ ድርድርና ትግል ያስፈልጋል። ቂም በቀልነትን ለመወጣት ሳይሆን ሰላም፤ እርቅ፤ ተባብሮ ችግሮችን ወዘተ ባህል ለማድረግና ፍትሃዊና ዲሞክራሳዊ እትዮጵያን ለመመስረት። ኢትዮጵያን ለመታደግ የሚቻለው የሕዝቧን የሕግ እኩልነት ተቀብሎ አብሮና ተባብሮ መስራት መጀምር ነው። ለዚህ ተራው ዜጋ ሃላፊነት አለበት፤ተባበሩ፤ መከፋፈል ለማንም አያዋጣም ሊል ይችላል። በእኔ ግምት ተራው ዜጋና የማህበረሰብ ድርጅቶች ለፍትሃዊ ስርአት መሰረቶች ናቸው። የማህበረሰብነት፤ የዜግነት፤ የእውነተኛ እኩልነት ወዘተ ባህል መሰረት

ካልያዘ፤ ሕዝብን የሚወክል፤ ለሕዝብ ተጠያቂና ሃላፊነት ያለው የመንግሥት አመራር ለመመስረት አይቻልም። የአሁኑ መንግሥትም ቢለወጥ ተተኪው ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል። ዜጎችና የማህበረሰብ ድርጅቶች የፖለቲካውን ውድድርና ፉክክር መቅደምና መዳኘት አለባቸው።

2. የዘመናዊ መገናኛ ቴክኖሎጂ ስርጭት ለልማት መሰረት ሆኗል

ወጣቱን ትውልድ ከደሃነት፤ ከስራ አጥነት፤ ከጥገኛነትና ከስደት ነጻ ለማውጣትና በአገሩ ኮርቶ እንዲኖር፤ አገሩን እንዲጠብቅና እንዲያለማ፤ ለህብረተሰቡ አገልግሎት እንዲሰጥ ከተፈለገ፤ ዘመናዊ መገናኛ፤ በተለይ ሞባይልና ኢንተርኔት በሕግ የተከበረ የተጠቃሚ መብት መሆን አለበት። ገዢው ፓርቲ በችሮታ የሚሰጠው አይደለም። አብዛኛው የሌሎች አፍሪካ አገሮች ወጣት ትውልድ የአዲስ ቴክኖሎጂ መብቱ በህግ የታወቀ ሆኗል። የኬንያ፤ የባንግላደሽ፤ የህንድ፤ የቻይና፤ የቬትናም ወዘተ ወጣት ትውልድ ዘመናዊ መገናኛ ቴክኖሎጂ እየተጠቀመ፤ አዲስ አገር ወለድ የግል ምርትና አገልግሎት ተቋሞችን መስርቷል። ከፍጹም ደሃነት ነጻ ወጥቷል። ገቢውን አሳድጓል። ኑሮውን አሻሽሏል። የመካከለኛ መደብና በዓለም ተወዳዳሪ የሆነ የኢኮኖሚ መሰረት ጥሏል፤ በመጣል ላይ ይገኛል። ገዢው ፓርቲ ቴክኖሎጂን የሚጠቀምበት ለስለላና ለቁጥጥር ነው። በያመቱ ለቁጥጥር የሚያፈሰውን ብዙ መቶ ሚሊዮን ብር ለወጣቱ ትውልድ ማጎልመሻና የማጎልመሻ መሳሪያ ግብአቶች ማዋል ግዴታው ነው። የወጣቱ ትውልድ መብት ነው። ዘመናዊ መገናኛ ቴክኖሎጂ ዋናው የነጻነትና የዘመናዊይነት ማንቀሳቀሻ መሳሪያ ሆኗል። ገዢው ፓርቲ ኢትዮጵያውያንን፤ በተለይ ወጣቱን ትውልድ፤ የዚህ ቴክኖሎጂ ደሃ ማድረጉ መቆም ተቀባይነት የለውም። ለዚህ መብት መታገል ያለበት ማህበረሰቡ ነው። የቴክኖልጂውን መብት መከልከል ሕዝቡን በደሃነት መኖር ይኖርብሃል ብሎ እንደ መፍረድ እንቆጥረዋለን። ወጣቱን ትውልድ በፕሮፓጋንዳ ስነ ልቦናውን መማረክ፤ በፍርሃት ለገዢው ፓርቲ አገልጋይ እንዲሆን በገንዘብ መደለል <u>"ዘመናዊ ባርነት" ነው።</u> በሳውዲ አረቢያ ያየነው አይነት ማለቴ ነው።

የኢትዮጵያ መንግሥት ለወጣቱ ትውልድ የዘመናዊ መገናኛ መብት መስጠት ብቻ ሳይሆን በመንግሥትነቱ ለወጣቱ ትውልድ፤ በተለይ ለሴቶች ልዩ የስራ እድል፤ ልዩ የራስን የግል ስራ ፈጠራ ትኩረት ያለው እቅድ ማውጣት ግዴታው ነው። የመንግሥትና የውጭ እርዳታው በዚህ ትውልድ ላይ ትኩረት ሰጥቶ አቅሙን ካጎለመሰው ብዙ ብሄራዊና ማህበራዊ ችግሮች ሊፈቱ ይችላሉ ከሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰናል።

ጎረቤቷ የእድገት "ነብር" (the Tiger economy next door) አገር

ሩቅ ሳንሄድ በኬንያ ሲካሄድ የቆየው የዘመናዊ መገናኛ ብዙሃን እድገትና የስራ መፍጠር አቅም ግንባታ (what the Economist calls a "technological boom") በኢትዮጵያ መንግሥትና በኬንያ መንግሥት የኢኮኖሚና የማህበረሰብ አመራር ያለውን ህይወት ለዋጭ ልዩነት ያሳየናል። የኬንያው የቴክኖሎጂ ለውጥ የጀመረው በሞባይል ስርጭት ነበር። ዛሬ ይህ ህይወት ለዋጭ ቴክኖሎጂ በፍጥነት በአፍሪካ አገሮች እየተሰራጨ ነው። በኬንያ፤ የሞባይል ስርጭት ሰባ አራት ሞባይል ለአንድ መቶ ሰዎች ነው። በሌሎች አፍሪካ አገሮች አማካይ ስድሳ አምስት ሞባይል ለመቶ ሰዎች ደርሷል። አምሳ በመቶው የአፍሪካ ሕዝብ ሞባይል አለው። በናይጀሪያ ብቻ መቶ ሚሊዮን ሞባይል ተጠቃሚዎች አሉ። ሰባት መቶ ሚሊየን አፍሪካውያን ቴክኖሎጂን ለብዙ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ሲጠቀሙበት ይታያል። ለግል ስራ፤ ገንዘብ፤ ዜናና እውቀት ለማስተላለፍና ለማሰራጨት ጭምር። የእርሻ ምርት ውጤት ለመከታተልና ለመሸጥ። የአየር ጠባይ ለውጥና የማህበረሰብ አደጋዎችን ለመከታተል። የገጠሩን ሕዝብ ከከተሜው ጋር ለማገናኘት። ምርምር ለማካሄድ ወዘተ። በኬንያ፤ ኡሻሂዲ፤ ነጻ የሆነ የተፈጥሮና የማህበረሰብ አደጋዎች ተከታታይ ቴክኖሎጂ ህይወት እየለወጠ ነው። "Ushahidi (Kiswahili for Witness), a free online crisis-mapping platform, was created during the post-election period in Kenya to track and map incidents of violence and peacer (ሰላምን ፈጣሪ) efforts... has become one of the most successful exports out of Africa...by May 2011, it had been used 14,000 times in 128 countries to map everything from the 2010 earthquake in Haiti, the Japanese tsunami and the Arab Spring." 85/

ኬንያ እንደ ኢትዮጵያ በብሄር/ብሄረሰብ ልዩነቶች፤ በጎሳ-ተኮር አድልዎ፤ በሙስናና በፖለቲካ ውጥረቶች የተበከለች አገር ነበረች፤ ችግሩ ሙሉ በሙሏ ተፈቷል ለምለት አንችልም። ጅምር ስራ ነው። ለማለት የምንችለው ኬንያውያን የፖለቲካውን፤ የማህበረሰቡንና የኢኮኖሚውን ሜዳ አስፋፍተውታል። ችግሮች የሚፈቱበትን ባህልና ተቋም እየፈጠሩ ነው። የፖለቲካ ችግሮችን በጠመንጃ ከመፍታት በነጻ ምርጫ መፍታት ጀምረዋል። አዲስ የዲሞክራሲ ባህል ፈጥረዋል። ለወጣቱ ትውልድ ታይቶ የማይታወቅ፤ ከአዲስ ቴክኖሎጂ ጋር የተያያዘ እድል ፈጥረዋል። ኬንያውያን የሚኮሩበት ድልድይ መስረተዋል። ቴክኖሎጂው የሚያስቀናና ህይወት ለዋጭ ነው የምንልበት ምክንያት ግላዊ ወይንም

ጎሳዊ ሳይሆን ማህበረሰባዊ ስለሆነ ነው። ("Ushahidi is a social product. The big money maker has been M (Mobile)-Pesa (money)...created by (the privately Kenyan owned) Safaricom... it is the most developed mobile payment system in the world... on October 9, 2012, the Kenyan government reported that Kenyans had deposited $8 billion in M-Pesa and other mobile services for the year." ቴክኖሎጂው ማህበረሰባዊ ነው ያልንበት ምክንያት፤ ስራና የግል ክፍል ኢኮኖሚ ፈጣሪ፤ አስፋፊና አገር ወለድ ስለሆነ ነው። "The more important was the number of people employed in the M-Pesa business... the number of mobile agents rose by 16 percent to 40,079... and subscriptions rose by 12.13 percent to reach 19.5 million in a country with a population of 42 million." 86/

ቴክኖሎጂው የጾታ ልዩነቶችን እያጠበበ ነው። ስድስት መቶ ሽህ የባንክ አገልግሎት ያልነበራቸው ኬንያዊ ሴቶች M-Pesa accounts አላቸው። የገጠር ኢንተርኔት በፍጥነት ተስፋፍቷል። "A Kenyan Company Craft Silicom, one of the fastest growing financial software companies in Africa, is now exporting to Latin America and Europe after winning contracts with over 200 financial institutions in 40 countries." ይህ አስደናቂ ለውጥ ነው። ከጥቂት አመታት በፊት፤ ኬንያ በሙስና የተበከለችና የጎሳ-ልዩነቶች አገሪቱን ወደ ውድቀት ያሻገራት፤ እልቂት የታየባት አገር ነበረች። ለጋሶች እርዳታቸውን አቁመው ነበር። ዛሬ የቴክኖሎጂ ማእከል በመሆን ላይ ናት። የዚህ ለውጥ መሪና ዋና ተጠቃሚ ወጣቱ ትውልድ ነው። ማይክሮሶፍት፤ ጉግል፤ ወዘተ፤ የኬንያን ቴክኖሎጂ ስርጭት ኬንያውያን የራሳቸው እንዲያደርጉት ደግፈዋል። ቴክኖሎጂ ከባህላቸው ጋር ተያይዟል። በዓለም ተወዳዳሪ እንዲሆን ድጋፍ እያገኘ ነው። እነዚህ እድል ፈጣሪ ኬንያውያን ትርፋቸውን የማይደብቁበትና ከአገር ያማያሸሹበት ምክንያት አለ። በአገራቸው እምነት አላቸው። ትርፍ አግኝተው ወገኖቻቸውን ይቀጥራሉ። የመካከለኛው መደብ እንቀሳቃሽና አጎልማሽ ሆነዋል። ይህን ከኢትዮጵያ ጠባብ ጎሳዊነትና ሙስና ጋር አብረን እንየው። የኢትዮጵያ ወጣት ዋና ቀጣሪ መንግሥትና ገዢው ፓርቲ ናቸው፤ የግል ክፍሉ ጫጩት ስለሆነ እድል ከፋችነቱ ተጎድቷል ለማለት እንችላለን። በራሱ ጥረት ሃብት ያካበተ ዜጋ የሚፈራው ነገር የለም፤ በአገሩ ዘላቂነት፤ በህይወቱ አስተማማኝነት ያምናል። ሃብቱን እንዴት ልደብቅና ላሺሽ የሚለው የተወሰነ ነው። "The Africans who flee Africa with their wealth are the ones who got it corruptly. That group does not bring their money back once it becomes difficult to keep it in Swiss and other European and American banks. They take it further afield to Asia and Latin America and, to the Caribbean islands." 87/

የአፍሪካ አገሮች የአገዛዝ መሻሻል ወይንም መባባስ የቴክኖሎጂ ስርጭትን እድገትና ስፋት ይወስነዋል። "We got the Transparency Corruption Perception Index, the Mo Ibrahim Index, the UNDP Development Report, the Economist Intelligence Unit's Democracy Index, Freedom House's Freedom Index and several others on press freedom and Internet freedom...and pulled data...on other factors such as achievements in immunization, health, nutrition, investments in infrastructure, improvements in agriculture." The anaylsis showed stark contrasts among governments, with "Ethiopia near the bottom because of democracy issues." በኢትዮጵያ፤ የሠብአዊ መብቶች አፈና የመገናኛ ቴክኖሎጂ ስርጭትንና አገር ወለድ ሆኖ ሊፈጠር የሚችለውን የግል ክፍል አብሮ አፍኖታል። የፖሊሲና መዋቅራዊ ለውጥ አልተቻለም። ያባባሰው የገዢው ፓርቲና የተባባሪዎቹ አብረው የሚሄዱት የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት ነው። "We need to address our structural bottlenecks and impediments (policy, our emphasis) and work towards ensuring our economies are better integrated and more competitive." በዚህ መጽሃፍ እንዳሳየነው፤ የፖለቲካው አገዛዝ ክፍትና ተወዳዳሪ ካልሆነ (Political pluralism) ወይንም አምባገነናዊ ሆኖ ከቀጠለ፤ የግል ክፍሉ ዝግ ይሆናል። የገበያ ውድድር አይኖርም። ይህ የግል ድርጅት የማቋቋምና የስራ እድል የመፍጠር አቅምን ያግባል። የአገሪቱን የማምረት አቅም ይገድበዋል። "Political transformation is one of the most important points of departure in terms of Africa realizing this great economic leap forward...Unfortunately, political transformation has been reduced (by ethnic elites , our emphasis) to the institution of five-year electoral processes... I do not think this is the kind of political transformation we need" to grow sustainable and equitable development. 88/

በኬንያና በሌሎች አገሮች የሚታየው ክስተት የፖለቲካ አመራሩ በቀጣይነትና በፍትሃዊነት ልማት ያለው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ በቴክኖሎጂ አጠቃቀምና ስርጭት አሳይተናል። የህወሓት/ኢህአዴግ "እድገታዊ መንግሥት" መአከላዊነት እንዴት ቁልፍ እንደሆነ አውጀ‌ል። ማእከላዊነት አግባብ እንዳለው እናምናለን፤ ሁሉን የሚያስተናግድ፤ ከጎሳዊ አድልዎ

ነጻ ሲሆን። የህወሓት/ኢህአዴግ መአከላዊነት በተግባር ያላሳየው፤ የኢኮኖሚው እድገት ውጤት ተጠቃሚዎች ጥቂቶች መሆናቸውን ነው። የኬንያ አገር ወለድ ቴክኖሎጂ የግል ክፍሉን አስፋፍቷል። ኬንያዊ ሆኗል። በእኛ ይቀኑ የነበሩ ኬንያውያን እኛን እየቀደሙ ነው። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በጥቂት የጎሳ ፖለቲካ የበላዮች ቁጥጥር የተያዘ ሆኗል። የገዢው ፓርቲ ርእዮት ሶሻሊዝም አይደለም። ተወዳዳሪነት ያለው ካፒታሊዝም አይደለም። የበላዮችን ያስተሳሰራቸው የጎሳ ልዩነት፤ የቀድሞው ስርአት "ጥላቻና" ከዚህ የሚገኝ የግል ጥቅም ነው። ይኼ የግልና ጠባብ ጎሰኝነት ጥቅም የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥቅም ለማገልገልና ለማስተናገድ አልቻለም። "A developmental state is one that assures that the relationships between the national economy and outside players who come to deal with it follow rules and that the national is not just protected but also promoted." The problem is that the TPLF/EPRDF government neither protects nor promotes the national interest. It simply uses its governance to protect and promote its priviledges and economic interests. የኬንያው የእድገት አመራር ያሳየው እድገቱ ለወጣቱ ትውልድ ስራ ፈጣሪ መሆኑን ነው። የኢትዮጵያው እድገቱ ለጥቂቶች ታይቶ የማይታወቅ ባለጠጋነት ፈጣሪ መሆኑን ነው። የትኛው አስተማማኝ መሆኑን ለመገመት አያዳግትም። የሕዝብን ነጻነትና አቅም ያጎለመሰ አገር ያድጋል። 89/

ባጠቃላይ ስናየው የኢትዮጵያ ዘመናዊ የመገናኛ ቴክኖሎጂ ከአፍሪካ አገሮች የመጨረሻ ነው። የኬንያ ሞባይል ስርጭት ከቻይና በልጧል። በወጣቱ ትውልድ የተስፋፋው የኬንያ የቴክኖሎጅ ለውጥ በሶስት ነገሮች ተደግፏል። አንድ፤ የኬንያ መንግሥት ፖሊሲ ደጋፊና አመቻች ሆኗል፤ ሁለት፤ የኬንያ የቴክኖሎጅ አዋቂዎችና የለውጥ ሃዋርያት ጉልበታቸውና ያላቸውን ገንዘብ ተጠቅመው አዳዲስ ከሃገር የማምረትና የአገልግሎት ፍላጎት ጋር የተቆራኙ ቴክኖሎጂዎች ፈጥረዋል፤ ሶስት፣ ለህብረተሰቡ የሚሰራጭበትን ዘዴ ሕዝቡ በሚችለው ዋጋ አቅርበዋል። የኢትዮጵያ ገዢ ፓርቲ አመቻች ሳይሆን አፋኝ ነው። ቻይና የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂ ለህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት ሸጣለች። በኢትዮጵያ የዘመናዊ መገናኛ ስርጭት ተቆጣጣሪ መንግሥት ነው። አስመጭና ላኪነት በገዢው ፓርቲና በመረጣቸው ድርጅቶች ይካሄዳል። የግል ክፍሉ ሚና የለውም። ይህ ፍጹም የሆነ የቴክኖሎጂ ቁጥጥር የኢትዮጵያ ወጣት ትውልድ ቴክኖሎጂውን ተጠቅሞ እንደ ኬንያውያን ወጣት ትውልድ የራሱን ስራ እንዳይፈጥር አድርጎታል። የቴክኖሎጂ ማእከል እንዳይመሰርት አፍኖታል። ከአገሩ ባህልና ልምድ ጋር የተያያዘ የብሄራዊ ዘመናዊነት ለውጥ እንዳያካሂድ ማነቆ ሆኗል። የኢትዮጵያ መንግሥት፤ ዘመናዊ መገናኛ ቴክኖሎጂን ይፈራል። ያልተበረዘ፤ እውነቱን የሚያስተጋባ የዜና አቅርቦትና ስርጭት ለሙብቶችና ለዲሞክራሲ ግንባታ ወሳኝ ነው። ህወሓት ነጻ ጋዜጠኞችንና ነጻ የመገናኛ ብዙሃን ስርጭትን የሚፈራበት፤ ጋዜጠኞችን በገፍ ያሰረበትና ያልታሰሩት እንዲሰደዱ ያደረገበት ዋና ምክንያት ቴክኖሎጂውና ነጻ ጋዜጠኞች ዜናና እውቀትን በፍጥነት ስለሚያሰራጩ ነው። ገዢው ፓርቲ ዜናና እውቀት ያለው ሕዝብ ከቁጥጥር ውጭ ይወጣል የሚል ግንዛቤ አለው። በእኔ ግምት ይህ ፖሊሲ የኢትዮጵያን ወጣት ትውልድ የቴክኖሎጂ "ደንቆሮ" አድርጎታል። ለሙብቱና ለእድሉ እንዳይጣጣር ማነቆ ሆኖበታል። የኢትዮጵያ መንግሥት የቴክኖሎጂ ስርጭትና መስፋፋት ማነቆ ፖሊሲውን ማንሳት አለበት። የቴክኖሎጂው ባለቤት የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በተለይ ወጣቱ ትውልድ መሆን አለበት። የዘመናዊ መገናኛ ብዙሃን ስርጭት ከሙብቶች ከፍተኛውን ደረጃ የያዘ ወጣቱ ትውልድ ሊሚገትበት የሚገባው ሙብት ነው።

3. ሁሉን የሚያስተናግድ ህብረተሰብ መፍጠር ከእልቂትና አገሪቱን ከመፈራረስ ያድናል

የኢትዮጵያ ሕዝብ በጎሳዎች የማይታረቁ ልዩነቶች ምክንያት ሆድና ጀርባ ሆኖ አብሮ ሊኖርና አብሮና ተሳስቦ ኑሮውን ሊያሻሽል አይችልም። በአብዛኛው፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የእርስ በርስ ጥላቻ የለውም። ገዢው ፓርቲ ለጥቂቶች የኢኮኖሚ ጥቅም በማሰብ በቋንቋ ልዩነት የተዋቀረ ከፋፋይ ማህበረሰብ ፈጥሯል። አንዳንድ የፖለቲካ ተመልካቾች የክልል ስርዓት ሙብቶችን አበርክቷል፤ መነካት የለበትም የሚል ሃሳብ ያቀርባሉ። የወደፊቷ ኢትዮጵያ ምን አይነት የመንግሥት ስርዓት ያስፈልጋታል (አሃዳዊ ወይንስ ፌደራላዊ) የሚለው ጥያቄ ለለውጥ ማነቆ መሆን የለበትም። በጥናትና በሕዝብ ውይይት መፈታት ይችላል። የመሬት ይዞታም ሰፊ ውይይትና ጥልቀት ያለው ውይይት ያስፈልገዋል፤ ከሌሎች አገሮች ብዙ ልምዶችን ለመሸመት ይቻላል። ልንከደው የማንችለው አሃዳዊ ይሁን ፌደራላዊ ኢትዮጵያ ችሎታ ያለው፤ ከጎሰኝነት ነጻ የሆነ፤ የተዛባውን እድገትና ገቢ የሚያቃና፤ ለአናሳና ወደ ኋላ ለቀሩ ጎሳዎች፤ ለሴቶች መከታ የሚሆን፤ አካባቢውን የሚያስከብር፤ የአገሪቱን ደህንነት የሚያስጠብቅ፤ ሁሉን የሚያስተናግድ ዘመናዊ የሆነ ማእከላዊ መንግሥት ያስፈልጋታል። ጎሳዊነት ያስከተለው ዘመናዊው "የመሳፍንት ዘመን" መንግሥት የሚያሳየው ማእከሉ ከፍተትና ድክመት እንዳለበት ነው። ዝንባሌው የጎሳ ስብስቦች ወደ አፀደቁት አንቀፅ ሰላሳ ዘጠኝ የሆነበት ዋና ምክንያት ክልሎች ዘመናዊ መሳፍንትን ስለ ወለዱ ነው ለማለት እንደፍራለን። መሳፍንትነት ከዲሞክራሳዊ ሙብቶች ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፤ በተለይ በሃያ አንደኛው፤ ሕዝብ በሚገናኝበትና ለጋራ ጥቅሙ በሚቆራኝበት ዘመን። አዛዦቹ የጎሳ የበላዮች ናቸው፤ሕዝቡ አይደለም።

የህወሓት/ኢህአዴግ አስተዳደሩ የዱሮውን የሶቭየት ዩኒየንና የደቡብ አፍሪካን አፓርታይድ ፈለግ ተከትሏል። ውጤቱ የተዛባ የነፍስ ወከፍ ገቢ፤ በክልሎች መካከል የተዛባ እድገት (ትግራይን ከኦሮሚያ ጋር፤ ትግራይን ከደቡብ ወይንም ከጋምቤላ ጋር ማነጻፀር)፤ በአስተዳደር በኩል አገሪቱ የማትችለው የቁጥጥር ባጀት ያሳያል። "ጎሳ-ተኮር ፌደራሊዝም በብሄር/ብሄረሰቦች መካከል ያለውን ልዩነት አላስወገደውም።" ለምን እንደሆነ ቀደም ብለን ተንትነናል። ዶክተር ብርሃኑ ጉተማ ቡልቻ እንዳስቀመጠው፤ "የጎሳ-ተኮር ፓርቲዎች የበላዮች (Ethnic elites) የመንግሥትና የውጭ እርዳታ ገንዘብ ለማግኘትና ስልጣናቸውን ለመጠበቅ" ከመሻማት ውጭ ለአብዛኛው ነዋሪ ኑሮ መሻሻል አስተዋጽኦ አላደረጉም።" የዘመኑ መሳፍንቶች መሻማትን እንደ ብሄረሰቦች መብት አድርገው ለራሳቸው የበላይነት ይጠቀሙበታል። በቂ ለምና በመስኖ የሚለማ መሬት ባላት ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሃብት ሺሚያና ግጭት መካሄድ የለበትም። የግጭቱ ፈጣሪዎች ለሕዝብ የሚቆረቆሩ አይደሉም፤ ለስልጣንና ለግል ሃብት የሚሻሙ ናቸው። ነዋሪዎች ከቀያቸው ሲባረሩ፤ ማእከላዊው መንግሥት "እኔ የለሁበትም" ይላል። የክልል መሪዎች እኛ የለንበትም ይላሉ፤ማን ለወንጀሉ ሃላፊና ተጠያቂ ይሆናል ብለን ብንጠይቅ አጥጋቢ መልስ አናገኝም። የጋምቤላ ሕዝብ አቤቱታውን የሚሰማው የኢትዮጵያ ፌደራል ወይንም ክልል መንግሥት ሃላፊ ስላላገኘ የነበረው አማራጭ እርዳታን መሰረት አድርጎ በእንግሊዝ አገር ክስ ማቅረብ ነበር። ለኢህአዴግ መንግሥት ይኼ ውርደት ነው። የሚያሳየው የኢትዮጵያ መንግሥት ለሕዝብ አቤቱታ ምንም ደንታ እንደሌለው ነው። በአጭሩ፤ የክልል መሳፍንቶች የማእከላዊው መንግስት ደጋፊና ስራ አስፈጻሚ ሆነዋል። የሞራል ግዴታ አድርገው የሚከራከሩበት ያለፈ ጭቆናና ለብሄራቸው ታማኝነት ነበር። ይኼ ቀፎ ነው፤ ያለፉት መንግሥታት ወንጀል ሰሩ ቢባልም የአሁኑን ኢ-ሰብአዊ ተግባሮችና የነዋሪዎችን ከቀያቸው ተገዶ መሰደድና ሌላ የማህበረሰ በደል አልፈጠሩም። የጎሳዎች ክልሎች አለቃዎች ዛሬ የሚያገለግሉት የራሳቸውንና የቤተሰቦቻቸውን ጥቅም ነው። ለሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያገለግለው የመንግሥት አማራጭ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ የስልጣኑ ባለቤት ሲሆን ነው። ሕዝቡ ለሕዝቡ ተጠሪ የሚሆኑ ተወካዮቹን ያለምንም ገደብና ተፅእኖ እራሱ መምረጥ መብቱ ነው። ወጣቱ ትውልድ ለዚህ አማራጭ መታገል አለበት። መብቱ ስለሆነ ማንም ሊከለክለው አይችልም። ቆራጥነትና ድፍረት ያስፈልገዋል።

4. ሃላፊነት የጎደለው የአንድ አምባገነን ስርዓት መተካት ሕብረተሰቡን "ከእልቂት" ያድነዋል

መልካም ወይንም ጥሩ አገዛዝ (Good Governance) ከብዙ የከፉ ችግሮች ይከላከላል። በኢትዮጵያ ባለፉት ሃያ ሶስት ዓመታት የታየው ምንም እንኳን የሰብአዊ መብቶችን ያቀፈና ሕጋዊ ያደረገ ሕገ መንግሥት ቢመሰረትም የኢትዮጵያ ሕዝብ በተከታታይ ከአምባገነናዊ አገዛዝ ነጻ አለመውጣቱን ነው---የአፄ ኃይለ ሥላሴ በደርግ መንግሥት ተተካ፤ የደርግ መንግሥት በህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት ተተካ። "ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያሳምርም" እንዲሉ ሕብረተሰቡ ከአንድ አምባገነናዊ መንግሥት ወደ ሌላ የአዙሪኝ አገዛዝ ውስጥ ገብቷል። የአሁኑን የከፋ የሚያደርገው ጎሳዊና አድሏዊ መሆኑና ክልሎች የራሳቸውን አትድረሱብኝ የሚል "የመሳፍንት ዘመን" አይነት አገዛዝ እየመሰረቱ ሕዝብን ከሕዝብ ጋር ማጋጨታቸውና አገሪቱን ወደ ከፋ አደጋ ማሸጋገራቸው ጭምር ነው። አምባገነናዊ አገዛዝ አደጋ ፈጣሪ፤ ሰብአዊ መብቶችን አፋኝ ነው፤ አሊያ አምባገነን ሊሆን አይችልም። የዚህ ተጻራሪ የሆነ የአገዛዝ ስርዓት አማራጭ ዲሞክራሲ ወይንም በሕዝብ ስልጣን የተመሰረተ፤ ለሕዝብ ተገዢ የሆነ ነው፤ የጋና፤ የጀርመን፤ የካናዳ፤ የሕንድ ወይንም ሌላ አይነት ሊሆን ይችላል። ውሳኔው በነጻና ፍትሃዊ ምርጫና በህዝብ ውይይት የሚደረግ እንጂ የጥቂት ልሂቃን ወይንም ስልጣን ፈላጊዎች አይደለም። የአንድ ገዢ ፓርቲ ተደጋጋሚ የበላይነትንና ሰብአዊ መብቶች አፋኝነትን፤ የኢኮኖሚ የበላይነትን ወዘተ ያጠኑ ብዙ ምሁራን አሉ። ከእነዚህ ብዙ ፓርቲዎችን መርምሮ ገንቢ የሆኑ አቅጣጫዎች ያቀረቡትን የኤድዋርድ ፍሪድማንና ጆሴፍ ወንግን አስኳል ሃሳቦች አቀርባለሁ።

"Democracy (with all its imperfections) is about institutionalized contestation (electoral contests) producing winners and losers…requiring losers to remain faithful to the results of the game." በዘጠና ሰባቱ ምርጫ ህወሓት ያልተቀበለው ማለት ነው። ዲሞክራሳዊ ስርዓትን ለመመስረት ግልፅነትና ሃላፊነት ያለው ደንብ፤ አመራር፤ ሕግና እነዚህን የሚያስፈፅም ነጻ የሆነ የምርጫ ተቋም ያስፈልጋል ማለት ነው። ተወዳዳሪዎች ተመጣጣኝ አቅም፤ ተመጣጣኝ የመገናኛ ብዙሃ ወዘተ ያስፈልጋቸዋል። የዚህ አይነት ምርጫ አሸናፊውን አስቀድሞ አይመርጥም፤ አሊያ ምርጫ ዋጋ የለውው። ተሸናፊውም አሸናፊውም ዓለም በተቀበለው ደንብ፤ ሕግና አሰራር መመራት አለበት። የዛሬ ተሸናፊ የነገ አሸናፊ ሊሆን ይችላል የሚል ልምድና እምነት መቀበል ቁልፍ ነው። ችግሩ ህወሓት/ኢህአዴግ ማሸነፍን እንጅ መሸነፍን ፈጽሞ አይቀበልም። ላለመሸነፍ ሲል ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዳይንቀሳቀሱ፤ መንቀሳቀሻ ገንዘብ እንዳይሰበስቡ፤ ቢሮ እንዳይከፍቱ፤ መንግሥት የሚቆጣጠረው የመገናኛ ብዙሃ እንዳይጠቀሙ ወዘተ ማነቆዎችን ያዘወትራል። ተቃዋሚዎች ገዢው ፓርቲ ከሚፈልገው መስመር ውጭ ሲሰሩና ለስልጣኑ አስጊ መሆኑን ሲገነዘብ ያስራቸዋል፤ ያሳድዳቸዋል። በነጻና ፍትሃዊ ውድድር የሚያምን ገዢ ፓርቲና መንግሥት ይኼን አያደርግም። ገዢው ፓርቲ ይኼን ጫናና አፈና የሚያደርገው ለምን ይሆን? ጥናቱ እንዲህ ይላል። In contrast to democratic parties

and governments, "Authoritarian single-party states, a kind of dominant party system, feel vulnerable to losing their hold on power." ህወሓት/ኢህአዴግ ፍርሃት (ስጋት) አለበት ማለት ነው። ሕዝቡን አያምነውም። የገዢው ፓርቲ መሪዎችና ከፍተኛ አባላት የፖለቲካውን ዓለም የሚያዩት "በፍፁም መጥፎነትና በፍፁም ጥሩነት" (Absolute Evil and Good) ነው፤ በመጥፎነት (ቡዳነት) የሚታየው ተቃዋሚው ይሆናል፤ በጥሩነት (መልአክነት) የሚታየው ገዢው ፓርቲ ብቻ ይሆናል። ስለዚህ፤ ቡዳዎቹን ማሰር አግባብ ይኖረዋል። ምርጫ ዘጠና ሰባት የሚያስተምረን ይኼን ኋላ ቀርና ፀረ-ዲሞክራሲ፤ ፀረ-ፍትህ አስተሳሰብ ነው። ቅንጅትና ህብረት አሸንፈው ማሸነፋቸው ሲታወቅ በጭራቅነት ተወገዙ፤ የሌለ ወንጀል ጫና ተካሄደባቸው። የሕዝብ ድምፅ ዋጋ ቢስ ሆነ። ገዢው ፓርቲ የቅንጅትን አመራር በሙሉ ያላወጣለት ስም የለም። ለምሳሌ፤ የሯዋንዳ አይነት እልቂት ፈጣሪ የሚል። ምሁራኖቹ በጥናታቸው የደረሱበት ድምዳሜ አምባገነን ፓርቲዎች ይኼን የሚያደርጉበት ዋና ምክንያት "ስጋት" ስላለባቸው ነው። የሚሰጉበት ምክንያት ስልጣን እናጣ ይሆናል፤ ያለንን ጥቅምና ሃብት እንቀማ ይሆናል፤ በፍርድ እንጠየቅ ይሆናል ወዘተ የሚል እምነት ስላለ ነው። አብረው የማያዩት ማንም አምባገነን ፓርቲ ለዘላለም ሊገዛ የማይችል መሆኑን ነው። አገዛዙ አለመረጋጋትን፤ ሽብርተኛነት፤ ተገንጣይነትን፤ ደሃነትን፤ ስደትን፤ ብልግናን፤ ሙስናንና ሌሎች የማህበረሰብ ችግሮችን እንደፈጠረ፤ የፈጠረው ለራሱን አስጊ መሆኑን አልተገነዘቡትም። ቢገነዘቡትም የሚመኩበት መሳሪይ አላቸው--የገንዘብ፤ የስለላ፤ የመከላከያ፤ የልዩ ፖሊስ፤ በመንግሥት ካዝና ባጀት የሚደገፍ የብዙ ሚሊዮን የፓርቲ አባላት ድጋፍ፤ የዲፕሎማሲ ወዘተ አቅም። ተቃዋሚው ተመጣጣኝ አቅም የለውም፤ አቅሙ የሕዝብ ድጋፍ ነው። ይኼ የሕዝብ ድጋፍ ተከታታይና አገር አቀፍ ሲሆን የሚገታው ኃይል የለም። ዩክሬን፤ ግብፅ፤ ቱኒዝያ፤ ሊቢያ፤ ሶሪያ፤ በርማ ወዘተ። 90/

ኢትዮጵያንና መላውን ሕዝቧን ከአደጋ ለመታደግ የሚከተሉትን ሃሳቦች እንሰነዝራለን፤

አንድ፤ የሰብአዊ መብቶች ሙሉ በሙሉ መከበር፤ የፖለቲካ እስረኞችን መፍታት ትኩረትና ቅድመት እንዲሰጠው ሁሉም ጥረት ማደረግ ብሄራዊ ግዴታ ሆኗል፤

ሁለት፤ ገዢው ፓርቲ የፖለቲካውን፤ የማህበረሰቡን፤ የኃይማኖቱን፤ የኢኮኖሚውን ወዘተ መልክአ ምድር ክፍትና ለተወዳዳሪነትና ለፍትህ የሚደግፍ ማድረግ አስፈላጊ ነው፤

ሶስት፤ ኢትዮጵያ ከመቸውም በበለጠ ደረጃና ፍጥነት የሰላም፤ የእርቅ፤ የድርድር የውይይቶች በአገር ቤትና በውጭ ማካሄድ ይኖርባታል። ባለፉት ዓመታት በየቦታው ያነጋገርናቸው የሰብአዊ መብት ተቋሞችና ተደማጭነት ያላቸው ኢትዮጵያውያንና ፈረንጆች ትኩረት እንዲሰጥበት ያቀረቡት አስኳል ምክር ይኼን ነው። ማን፤ እንዴት፤ መቸና የት የሚሉት ጥያቄዎች ማነቆ ሊሆኑ አይችሉም፤ ይኼን ለማዘጋጀትና ለማመቻቸት የሚችሉ ብቃት ያላቸው ኢትዮጲያዉያንና ፈረንጆች አሉ። ዋናው በመሰረተ ሃሳቡ ላይ ውይይት መጀመር ነው።

አራት፤ ዘጠና አራት ሚሊዮን የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ተካሂዶ ሙሉ ተሳታፊ የመሆን ፍላጎትና መብት አለው። ገዢው ፓርቲ "በስጋት ዓለም" ተወጥሮና ተበክሎ ይኼን መብት ማገብ ሕብረተሰቡን ተስፋ አስቆቆርጦታል። አገሪቱን ለከፍተኛ አደጋ ይዳርጋታል። ይህን አስቀድሞ አስቦ ለመከላከል ይቻላል። ስለሆነም፤ገዢው ፓርቲና ከፍተኛ የገንዘብና ሌላ ድጋፍ የሚለግሱት መንግሥታትና ለጋስ ድርጅቶች የሞራል ግዴታ አለባቸው። ይኼውም፤ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ እንዲካሄድ ቅደመ ሁኔታዎችን ከአሁኑ ማመቻቸት ነው። በእኛ ስሌት በነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ያሸነፈና የተሸነፈ የምርጫውን ውጤት በእርጋታ፤ በትእግስትና በኢትዮጵያውያን እሴቶችና ልምዶች አርአያነትና ፀጋ መቀበል ልምድ መሆን ይኖርበታል። ተቃዋሚው ካሸነፈ የቂም በቀል እርምጃ እንደማይወስድ እምነት አለን። ህወሓት ከተሸነፈ ውጤቱን መቀበል ግዴታው ነው። በእኔ እምነት የኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅነቱን በተከታታይ አሳይቷል፤ ቂም በቀልን አይቀበልም።

5. ኢትዮጵያ የባህር በሯን ባለቤትነት ማስመለስ መብቷ ነው

ገዢው ፓርቲ የኢትዮጵያን የባህር በር በራሱ ፈቃድ መዝጋቱ ኢኮኖሚውንና ህብረተሰቡን ጎድቶታል። በሃላፊነት ያስጠይቀዋል። ወደ ውጭ የሚላከውና ወደ አገር የሚገባው እቃ ዋጋ የናረበት አንዱ ምክንያት ኢትዮጵያ--በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ-የሌሎች አገሮች ጥገኛ ስለሆነች ነው። ወደ ውጭ የምትልከው እቃ የመጓጓዣ ዋጋ ከፍተኛነት የመወዳደር አቅሟን ቀንሶባታል። የሕዝቧ ቁጥር እያደገና ኢኮኖሚዋ እየተስፋፋ ሲሄድ የባህር በሯ ተዘግቶ ጥገኛ መሆኑ ለደህንነቷም ሆነ ለእደገቷ ማነቆ ይሆናል። ከሁሉም በላይ የአገሪቱን ደህንነት በክሎታል። ለአደጋ አጋልጦታል። ይህን ድክመት አይተው፤ የአረብ መንግሥታት ኢትዮጵያ የረዥም ጊዜ ጥቅሞቿን እንዳታስከብር በማድረግ ላይ ይገኛሉ። የህወሓት መስራቾች ካስከተሉት በደል መካከል የባህር በሯን መዝጋታቸው ወይንም እንዲዘጋ ፈቅደው ማመቻቸታቸው

ለዘላላም ተጠያቂዎች ያደርጋቸዋል። ስልጣን ይዞ ከሃላፊነት የሳደለው ተከታታይ ትውልድን የቀጣ ውሳኔ ነው። ስለዚህ፤ ተቃዋሚዎችና ወጣቱ ትውልድ ለባህር በር መብት መከራከር አለበት። ኢትዮጵያ ወደ ጦርነት ትሂድ ማለታችን አይደለም። የባህር በር መብቷን በአለም አቀፍ ሕግ ሆነ በድርድር ማስከበር የአሁኑና የወደፊቱ ትውልድ ግዴታ ሆኗል ማለታችን ነው።

6. የኢትዮጵያ መንግሥት ተቀዳሚ ሃላፊነት የምግብ ዋስትና መሰረት መጣል ነው

አስደናቂ እድገት አለ እየተባለ የኢትዮጵያ ሕዝብ በልቶ የማያድርበት ኢኮኖሚ አያኮራም። የኢትዮጵያ መንግሥት የመጀመሪያ የእድገት ሃላፊነት ለመላው ሕዝብ የምግብ ዋስትና ስኬታማ ማድረግ ነው። በእኛ ግምት ይቻላል። ሆኖም፤ የምግብ ዋስትና ያለ ነጻነትና ያለ ባለቤትነት አይቻልም። ችግሩ የገበሬው ስንፍና ወይንም በዘመናዊ እርሻ ኢንቬስት ለማድረግ የሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን አለመኖር አይደለም። አሉ፤ ከዚህ በፊት ችሎታቸውን አስመዝግበዋል። የአፄ ኃይለ ሥላሴና የደርግ መንግሥት ከፍተኛ ትኩረት የሰጡት ለእርሻ ዘመናዊነት ነበር፤ በተለይ ደርግ የመሬት አዋጅ ማውጣቱ ለዘመናዊነትና ለባለቤትነት በር ከፍቶ ነበር። ሁለቱም ኢትዮጵያ ማንኛውንም አይነት ምርት ለማቅረብ እንደምትችል፤ ራሷን መግባ ለውጭ ገበያ እንደምትተርፍ ያውቁ ነበር። በሰቲት ሁመራ፤ በአዋሽ ሸለቆ፤ በአርሲ፤ በጭላሎ፤ በወላሞ፤ በዋቢ ሸበሌ፤በጣና በለስ ዙርያ ወዘተ ተካሂደው የነበሩት የዘመናዊ እርሻና ከእርሻ ጋር የተቆራኙ ኢንዲስትሪዎች የሚያኮራ ውጤት አሳይተው ነበር። በአብዛኛው እንዚህ የተሰሩት በኢትዮጵያውያን ነው። በደርግ ዘመን ሶሻሊዝም በሚል አመራር የግል የነበሩ አምራች ድርጅቶች ተወርሰው መሰረታዊ ችግሮች አስከትለዋል። በሌላ በኩል አስደናቂ ጅምር ናቸው ከሚባሉት ፕሮጀክቶች መካከል ዓለም ባንክ በፖሊሲ ደረጃ መደገፍ አለበት የሚለው የታወቀው የጣና በለስ ፕሮጀክት ይገኝበታል። ከላይ እንዳሳየነው ህወሓት ይኼን ፕሮጀት ማፈራረሱና መሳሪያዎቹን ነቃቅሎ መውሰዱ ግፍና ወንጀል ነው። የማይካደው የኢትዮጵያ ገበሬዎችና የአገር ውስጥና የውጭ ኢንቬስተሮች በግልና በጋራ እርሻን ዘመናዊ የማድረግ ችሎታ አላቸው። ደርግም ህወሓትም ያልተገነዘቡት ማለት ነው። ብዙ ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያ ዝቅተኛ ገበሬዎች የማምረት ችሎታ ያምናሉ። የኢትዮጵያ ገበሬዎች ዘጠና በመቶ የሚሆነውን የምግብ ፍላጎት ያቀርባሉ። አግባብ ያለው አመራር ቢኖር የቀረውን አስር በመቶ ዝቅተኛ አምራቾችን በማጎልለምስ ለማሟላት ይቻላል። ስራ በመፍጠርና የምግብ ዋስትናን ስኬታማ ለማድረግ ዋንው ዘዴ ኢትዮጵያውያንን ማጎልመስ፤ ያልተቆጠበ ድጋፍ መስጠት፤ የተፈትሮ ሃብታቸውና የምርታቸው ባለቤት ማድረ ነው። የተባበሩት መንሥታት የእርሻ ድርጅት፤ ኤፍፕሪ የተባለው የምግብ ፖሊሲ ተቋም ወዘተ እና እንደ ካናዳዊው ፕሮፌሰር ሚኬል ቾሱዶቭስኪ ያሉ ልሂቃን የአፍሪካን፤ በተለይ የኢትዮጵያን የተዛባ የእርሻ መሬትና በሃገሪቱ ብቻ የሚያድጉ ሰብሎችን--ጤፍ፤ ዘንጋዳ፤ ማሺላ፤ አተር፤ ገብስና ሌሎች--አጠቃቀምና የባለቤትነት መብት ማጣት እና የምርት አቅርቦት ድክመቶችን አይተው አስቸኳ ለውጥ እንደሚያስፈልግ አሳስበው ነበር። የአመራር ጉድለት ያለባቸውን ጥቂት ምሳሌዎች እንይ።

በ2000 የተካሄደ ጥናት ያሳየው፤ ቢያንስ ስምንት ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን በተደጋጋሚ ረሃብተኞች መሆናቸውን ነው። ችግሩ መዋቅራዊና ስርዓታዊ ስለሆነ መሰረታዊ የፖሊሲ ለውጥ ያስፈልገዋል። ትርፍ ምግብን ከሚመረትበት ወደሚፈለግበት ቦታ ለማቅረብ ባለመቻሉ በከተማም ሆነ ገጠር ምርት በተፈለገው መጠን የማይገኝበት አካባቢ ረሃብተኛ ነው። ለምሳሌ፤ የአማራው ክልል ከሚፈለገው ሃያ በመቶ በላይ ያመርታል፤ ሆኖም፤ በዚያው ክልል ወደ ሶስት ሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ ይራባል። በኦሮሚያ ክልል ስድስት መቶ ሽህ ቶን የሚገመት ትርፍ እህል ይመረታል። ሆኖም፤ ወደ ሁለት ሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ ይራባል። ችግሩ ምርት ሳይሆን አግባብ ያለው፤ ለፈላጊው በወቅቱ የሚያቀርብ ተቋምና መሰረተ ልማት አለመኖሩ ነው። መሰብሰቢያ ጎተራ ባለመኖሩ የሚባክነው እህል ከፍተኛ ነው። Michel Chossudovsky, "Monsanto and the Bio-tech Conglomerates: Sowing the seeds of famine in Ethiopia," May 23, 2014 ባቀረበው በማስረጃ የተደገፈ ትንተና እንዲህ ብሏል። "በከተማ የደሞዝ መግዛት አቅም ወድቋል (urban wages have collapsed). በገጠር መሬት የሌለው ሕዝብ ብዛት በሚያስፈራ መጠን እየጨመረ ነው...በአጠቃይ ሲታይ ደሃነት አሳፋሪ ደረጃ ላይ ደርሷል (abysmal).

ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ከፍተኛውን እርዳታ እያገኘች ይኼ እንዴት ሊሆን ቻለ ብለን እንጠይቅ። አንባቢው እንዲገነዘበው የምንፈልገው ገዢው ፓርቲ ከፍተኛ እርዳታ ለማግኘት የቻለበትን ምክንያት ከላይ አቅርበናል። ባጭሩ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት በአፍሪካ ቀንድ ሽብርተኛነትን ለመከላከል ከምእራብ መንግሥታት፤ በተለይ ከአሜሪካ ጋር የጥቅም ግንኙነት ስለፈጠረ ነው። ከዓለም ባንክና ከአይኤምኤፍ ጋር የፖልሲ ለውጥ ለማድረግ ስለተስማማ ወዘተ ነው። እነዚህ በአፍሪካ አገሮች የፖሊሲ ጫና እያደረጉ (Structural adjustment) የለመዱትን አመራር በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ጭነዋል። የአሚሪካው የእርዳታ ድርጅት የእነዚህ ኢጋርና አማካሪ ሆኖ (አሜሪካ ከፍተኛ ድምፅ ስላላት) የፖሊስ ለውጥ

እንዲደረግ ግፊት አድርገው ገዢው ፓርቲ ተቀብሏል። ለምሳሌ፤ ኢኮኖሚው በመንግሥትና በገዢው ፓርቲ የበላይነት በሚመራባት ኢትዮጵያ በ1990s ሁለቱ አለም አቀፍ ድርጅቶች ለኢትዮጵያ Policy Framework Papers (የመንግሥት ፖሊሲ አመራር) አዘጋጅተው የኢትዮጵያ መንግሥት እንዲቀበል አድርገዋል። በዚህም መሰረት የመንግሥት የነበሩ፤ ትርፍ የሚያስገኙ፤ ለኢትዮጵያውያን የስራ እድል የሰጡ፤ የሃገሪቱን ባለቤትነት ያስመሰከሩ ባንኮች፤ ሆቴሎች፤ የጨርቃ ጨርቅ፤ የመጠጥና ሌላ አምራች ድርጅቶች፤ መአድኖች፤ ዘመናዊ እርሻዎች ወዘተ በጅምላ የግል እንዲሆኑ ተደርጓል። ቻያን ያላደረገችውን፤ በቻይና የማይታሠበውን ኢትዮጵያ ተቀብላለች። አብዛኞቹ የግል የሆኑት በተዘዋዋሪ ለህወሓትና ለፈጠራቸው እንደ ኤፎርት ላሉ ደርጅቶች፤ ታማኝ ግለሰቦችና ለአላሙዲ በእርካሽ ዋጋ፤ ግልፅነትና ውድድር በሌለበት ሁኔታዎች ተሸጠዋል። ሰራተኞት ተባረዋል፤ ብዙዎቹ እንዲሰደዱ ተደርጓል። ዓለም አቀፋዊ ስርዓት (Globalization) የአገሪቱን ሕዝብ የማምረት ኃይል በሚያዳክምና የኢትዮጵያን የሃብትና ጥሪት ባለቤትነት ባማከነ ደረጃ ስር ሰዶ ገባ። ከህወሓት የበላይነት ባላነሰ ደረጃ የውጭ ድርጅቶችና መንግሥታት ተሰሚነት፤ ባለቤትነት፤ አዛገርነት መሰረቱ። በሕዝብ (መንግሥት) ባለቤትነት ይካሄዱ የነበሩ ተቋሞች "በነጻ የገበያ ስርዓት" (free market) አማካይነት ለግል እንደ በረከት ሲሰጡ አብሮ የተከሰተው ሙስና ነው። ስለሆነም፤ አንዱ የሙስና አጠናካሪ የውጭ እርዳታና በነጻ ገበያ አመካኝቶ የሚደረገው የትርፍና የኪራይ ሰብሳቢነት ባህል ነው። ትርፍ የማያስገኙ፤ ለሃገር ሸክም የሆኑ ድርጅቶችን መሸጥና ትርፍ የሚያስገኙትን በሕዝብ (መንግሥት) ባለቤትነት መያዝ የተለያዩ ጉዳዮች ናቸው። ዓለም ባንክ ለቻይና አበዳሪ በነበረበት ወቅት ቻይናዎች የተከተሉት ፖሊሲ መንግሥት የያዛቸው ድርጅቶች በመንግሥት ቆይተው ራሳቸውን እንዲያሻሽሉ፤ ትርፍ እንዲያስገኙ፤ በዓለም ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚል ነው። ቤሌላ በኩል፤ የግል ክፍሉ ማደግ አለበት፤ ቻይናዎች ከፍተኛውን ድርሻ መያዝ አለባቸው፤ ቀስ በቀስ የግል ክፍሉ ከመንግሥት ክፍሉ ተወዳዳሪ መሆን አለበት የሚል አመራር ተከትለው አስደናቂ ውጤት አሳይተዋል። አገር ወዳድ መንግሥት ሁለቱን ክፍሎች ስትራተጂክ (ዘዴአዊ) በሆነ መንገድ ያስተናግዳል፤ የሕዝብ ሃብት አያባክንም።

የህወሓት "የነፃ ገበያው" ፖሊሲ የውጭ ኢንቬስተሮች በገፍ ወደ ሃገር እንዲገቡ አመቻችቷል። ያሉትን የምርትና የአገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ወደ "ግል" ለማሸጋገር አገር ውስጥ ከሚገኙ አጋሮች ጋር በመሻረክ አዘዋውሮ በራሳቸው አቅም የሚንቀሳቀሱትን ኢትዮጵያዊ የግል ድርጅቶች ጭምር አድክመዋል። የመጓጓዣ፤ የማዳበሪያ፤ የምርጥ ዘርና ሌሎች ግብዓቶችና አቅርቦቶች ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያውያን ቁጥጥር መውጣት ጀመሩ። ዓለም ባንክና አይኤምኤፍ በሰጡት አመራር መሰረት የዋጋ ቁጥጥር፤ ቢያንስ መመሪያ እንዳይደረግ ተወሰነ። የዋጋ ቁጥጥር አለመኖር ለተጠቃሚው ሕዝብ ጉዳት አለው። ማንኛው ቁሳቁስና አገልግሎት በተፈለገው ዋጋ እንዲሸጥ ተደረገ። እጥረት ባለበት አገር፤ የሚሻማውን ለመግዛት የሚችለው ከፍተኛ ገቢ ያለው ነው። በግብርና ስራ ላይ የታየው ግድፈት ከዓለም አቀፋዊነትና ከነጻ ገበያ ጋር ተያይዞ የተከሰተ ነው። አንድ ሰሞን የአሜካ የእርዳታ ድርጅት ለመሬቱ አግባብ ይኑረው አይኑረው ጥናት ሳይደረግ ማዳበሪያ ለገሰ። እርዳታ ለመለገስ አሜሪካና ሌሎች የሚፈልጉትን ማድረግ የተለመደ ነው። የአሜሪካን እርዳታ ለማግኘት ኢትዮጵያ ቅድመ ሁኔታቸውን የመቀበል ግዴታ ነበረባት ማለት ነው። የኢትዮጵያ ገበሬዎችና ኢትዮጵያውያን የግል ክፍል በማጎልመስ ፋንታ የምግብ እርዳታ ተቀባይነት አገኘ። ምንም እንኳን ገዢው ፓርቲ የጦፈና በተወዳዳሪነት የሚመራ ብሄራዊ ኢኮኖሚና የገበያ ስርዓት ባይፈቅድም፤ ፈረንጆች፤ ዓለም ባንክና ተመሳሳይ ድርጅቶች የሚፈልጉትን ሁሉ ተቀብሏል። ለምሳሌ፤ የካፒታል ገበያና ውድድር (Stock Market) ፈጽሞ በሌለበት አገር የእርሻ ውጤቶችን ገበያ ዘመናዊ በሆነ መንገድ እንዲሰራ የኢትዮጵያ Commodity Exchange ለውጭ አምራቾችና ሻጮች በሚጠቅም ሁኔታ ተቋቋመ። ጥያቄው ለማን ጥቅም፤ በማን ትእዛዝ የሚለው ነው። ይኼን የምርት ገበያ አመቻች ተቋም የደገፉት የአሜሪካ የእርሻ ኃብታም ድርጂቶች ናቸው፤ እንደ ካርጊል፤ ሞሳንቶ፤ አርቸር ዳንኤልና ሌሎች። አመቻቾች የአሜሪካ የተራድኦ ድርጅት፤ ዓለም ባንክና ተመሳሳዮች ናቸው።

*ተደጋጋሚ የምግብ እርዳታ ለምግብ ዋስትና ማነቆ ነው*

አሜሪካ ለኢትዮጵያ የምትሰጠው እርዳታ የሚታወቀው በምግብ ድጎማ ነው። የማይካደው የምግብ እርዳታ ህይወት ያተርፋል። ኦክስፋም አሜሪካ በOctober 2009, Band Aid and Beyond: 25 years after the Ethiopian famine, what have we learned? ጠቃሚና አመልካች ዘገባ አቅርቦ ነበር። "In 1984, one million Ethiopians died during a catastrophic famine…But drought still costs Ethiopia roughly $1.1 billion a year-almost eclipsing the total overseas assistance (net inflow) to the country." ይኼ ኢትዮጵያ ልትወጣው የሚችል ችግር ነው። ሆኖም፤ የፖለቲካና የኢኮኖሚ አመራር ፈቃደኛነት ያስፈልጋል። አመራሩ አግባብ ያለው ከሆነ የምግብ እርዳታው ይዘት መለወጥ አለበት። ማለትም፤ እርዳታ ሰጭ መንግሥታትና ድረጅቶች የኢትዮጵጵያን ገበሬዎች አቅም ማጠናከር ተገቢ ይሆናል። በእኛ ግምት የአሜሪካ የምግብ እርዳታ ሌላ ተግባር አለው፤ የአሜሪካን የፖለቲካና ኢኮኖሚ ጥቅም ማስከበር። Food Aid or Hidden Dumping, March 2005, "Food is sometimes used to capture new

markets." It always is. አብዛኛው የምግብ እርዳታ የሃብታም አገሮችን ገበያና ገቢ የሚያጠናክር ነው። ኦክስፋም ያወጣው ዘገባ እንዲህ ይላል። "የእኛ የአሜሪካኖች የምግብ እርዳታ በሕግ የሚያስገድደው ምግቡ ከአሜሪካ ተገዝቶ፤ በአሜሪካ መጓጓዣ፤ በአሜሪካ ሰራተኞች ለሚፈልጉ አገሮች ማሰራጨት ነው" ይላል። ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል ማለት ነው። ከላይ ባቀረብነው ምሳሌ፤ በኦሮሚያ ትርፍ እህል ከተመረተ አሜሪካኖች ይኼን እህል ኢትዮጵያ ገዝተው ለኢትዮጵያውያን ለማቅረብ ይችላሉ፤ ከፈቀዱ ማለት ነው። ገበሬውን ጠቅመው የተራበውን በቀላል ዋጋ ለመመገብ ይችላሉ። Oxfam, Food Aid: a critical program, ripe for reform, May 5, 2014. ኦክስፋም ተመሳሳይ ሃሳብ የዛሬ አምስት ዓመት አቅርቦ እስካሁን ምንም ለውጥ የለም። በዚያ ወቅት፤ ብርሃን ውልዱ የተባለች ኢትዮጵያዊት ከታላቁ ረሃብ ህይወቷ በውጭ የምግብ እርዳታ የተረፈ የተማረችውን አቅርባ ነበር። "ከድርቅና ተከታታይ ረሃብ የተማርኩት የምግብ ችሮታ የረዢም ጊዜውን የፖሊሲና መዋቅራዊ ችግር አይፈታም።" እንስማማለን።

ታዲያ መፍትሄው ምንድን ነው? መልሱን ሙሉ በሙሉ እናውቃለን የሚል ግንዛቤ አናቀርብም። የውጭ መንግሥታት፤ በተለይ 91 በመቶ የሚሆነውን የሰብአዊ እርዳታ የሚሰጠው የአሜሪካ መንግሥት የሚለግሰው ከአሜሪካ የሚመጣ፤ ትርፉ ለአሜሪካ የግል ክፍል ምግብ አምራቾች የሚጠቅም የምግብ ድጎማ ነው። ካላይ ብርሃን እንዳሳሰበችው የኢትዮጵያን የምግብ ችግር ዘላቂነት ባለው ሁኔታ ለመፍታት ፍላጎት ካለ እርዳታው ከምግብ ድጎማ ወደ አምራቾች ብቃት መለወጥ ይኖርበታል። በአሁኑ አያያዝ፤ አምራቾችን ለማጠናከር የሚሰጠው እርዳታ ትርጉም የሌለው 0.14 percent ነው። "አባይን በጭልፋ" እንደማለት ነው። የአሁኑ የምግብ እርዳታ ከቀጠለ ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ረሃብተኛ የውጭ የምግብ ለጋሶች ምርኮኛ ሆኖ ይኖራል ማለት ነው። ማንኛውም የውጭ እርዳታ ጥቅም አከራካሪ ነው የምለው ለዚህ ነው። አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ (ሰማንያ ሶስት በመቶ የሚሆነው በገጠር ይኖራል) ከእርዳታ የሚያገኘው ጥቅም መጠነኛ ነው። ለኢትዮጵያ ሕዝብ ባለውለታ ነኝ የሚለው የአሜሪካ መንግሥት ተራድኦ ድርጅት ኢትዮጵያ ራሷን ለመመገብ እንደምትችል ያውቃል። እስካሁን ያመቻቸው የአሜሪካን ጥቅም መሆኑ አያከራክርም። የኢትዮጵያን ዝቅተኛ አምራቾች በማጎልመስ ፋንታ የራሱን ጥቅም አገልጋይ በመሆን ሁለት ኢትዮጵያን ጎጂ የሆኑ ነገሮች ሰርቷል፤

አንድ፤የተራበው ሕዝብ እንዳይሞት በያመቱ ወደ አንድ ቢሊዮን ዶላር የሚገመት የምግብ እርዳታ ለግሷል። "በ1999-2000 USAID sent 500,000 tons of genetically modified maize" to feed Ethiopians. ይኼ ከፍተኛ የምግብ እርዳታ ሲሰጥ የአሜሪካ መንግሥት የሚገዛው ከአሜሪካ ኩባንያዎች ነው። በሰብአዊ እርዳታ ስም ትርፉን አሜሪካኖች አገኙ ማለት ነው። በአማራና በኦሮሞ ክልሎች የምርት ትርፍ አለ ብለናል። የአሜሪካ መንግሥት ረሃብን ለመቆጣጠርና ኢትዮጵያውያን ሃብታም ኢንዲሆኑ ከፈለገ በአማራና በኦሮሞ ክልሎች የሚመረተውን ትርፍ ሰብል፤ እህል ሸምቶ ለማስረጨት ይችል ነበር። በተጨማሪ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በምግብ አቅርቦት ራሱን እንዲችል ዝቅተኛ አምራችን ለማጎልመስ አማራጭ ነበረው፤ ገዢው ፓርቲ እምቢ ቢል እርዳታ ከፈለጋችሁ ራሳችሁን እንድትችሉ አምራቾችን አጎልምሱ ሊል ይችል ነበር። ያደረገው ተጻራሪውን ነው። ከላይ በቾሶዶቭስኪ የቀረበው ምርምር እንዲህ ይላል "Africa is treated as the dustbin of the world—To donate untested food and seed to Africa is not an act of kindness but an attempt to lure Africa into further dependency on foreign aid," Michel Chossoudosky, "Globalization of Poverty and the New World Order." ኢትዮጵያ የጥገኝነት ዋና ምሳሌ ሆናለች። በእርዳታ ስም የሕዝብ የማምረት አቅምና የሃገር ዘላቂ ጥቅም ይነገድባታል። ጀኔራሎቹ ሳይቀሩ ሃብታም ስለሆኑ መሰረታዊ ለውጥ እንዲካሄድ አይፈልጉም።

ዓለም ባንክ ያቀነባበረው የሕዝብ መሰረታዊ አገልግሎት ፕሮግራም ተመሳሳይ የሆነ ጉዳት አምጥቷል። አንድ ለገዢው ፓርቲ ቁጥጥር አመቻች ሆኗል፤ ሁለት "ምግብ ለስራ" በሚል ዘዴ አምራች ሊሆኑ የሚችሉ ኢትዮጵያውያንን ጥገኛና ሸባ አድርጓል። ሁለቱም የኢትዮጵያን ገበሬዎችና ሌሎች የማምረት ችሎታና ፍላጎት አፍኖታል ወይንም በጭራሹ በማጥፋት ላይ ይገኛል። የተኩት ከውጭ በሚሸመት ምግብና ሌላ ተፈላጊ ቁሳቁስና አገልግሎት ነው። ከዚህም ሌላ፤ አገር ወዳድና ለሃገር ተቆርቋሪ መንግሥት ስለሌለ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ሰብሎች (indigenous varieties) ወደ ውጭ እንዲዛመቱ ተደርጓል፤ ለምሳሌ ጤፍና ገብስ። ፈቃድ ሳይጠየቅ፤ የኢትዮጵያ ባለቤትነት ህጋዊ ሳይሆን። ዛሬ ጤፍና ገብስ በአሜሪካ ተመርቶ ለገበያ ቀርቧል። Rural Advancement Foundation የተባለ ተቋም ይኼን በደል እንዲህ ሲል አቅርቦታል። "US farmers already earn $150 million annually by growing varities of barley developed from Ethiopian streans. Yet, nobody in Ethiopia is sending them bills." ተቆርቋሪ መንግሥት የሌለው አገር ይበላል፤ ይዳከማል፤ ሁሉም ነገር ለትርፍና ለጥቅም ስለሚሸጥ ዘላቂ ጉዳቱ አይታወቅም። ይኼም አዲስ የመጣ ክስተት ነው። ቾሱዶቭስኪ እንዳስቀመጠው የደርግ መንግሥት አደጋውን በማየት መከላከያ ተቋም መስርቶ ነበር።

"The Dergue government through its Plant Genetic Resource Center had implemented a program to preserve Ethiopia's biodiversity." ይኼ ሃላፊነት ያለው የሃገርን የማይተካ ሃብት ለራስ ሕዝብና አገር ልማት መጠቀም ያሳያል። በምግብና ሌላ እርዳታ ጥገኛ የሆነችው ኢትዮጵያ የራሷን የተፈጥሮ ሃብት ለራሷ ሕዝብ ኑሮ መሻሻል አልተጠቀመችም። የኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና ስኬታማ ሊሆን ይችላል። የማሳስበው "የአደጋ ምግብ ድጋፍ" መፍትሄ ሊሆን አይችልም። "The emergency programs (USAID and World Bank, etc) are not the "solution," but the cause of famine. የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሃብት ለአጭር ጊዜ ትርፍና ጥቅም፤ ከውጭ መንግሥታትና ድርጅቶቻቸው ጋር ለሚደረግ የጥቅም ሰንሰለት መሸጥ ለተከታታይ ትውልድ በደል ነው። ይኼን በሚመለከት ከጥቂት ዓመታት በፊት በኢትዮጵያ ላይ የደረሰውን አሰቃቂ በደል አስመልክቶ ቾሱዶቭስኪ የጻፈው አግባብ አለው። "Now in Ethiopia, 15 years after the last famine left nearly one million dead, hunger is once again stalking the land. This time, as eight million people face the risk of starvation we know it isn't just the weather that is to blame." It is public policy and globalization under the new order." በተመሳሳይ፤ ላቂ ማሪያም ደምሴ የኢትዮጵያን የተፈጠሮ ሃብት መነጠቅ አስመልክቶ እንዲህ ብሏል። "A vast historical contribution (to the USA) counts for little; the West reaps Ethiopia's genetic harvest," World Times, November1999.

የኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና ስኬታማ ሊሆን ይችላል። ገበሬው የፍላጎትን ዘጠና በመቶ ሊያሟላ ከቻለ ሌላውን አሟልቶ ለውጭ ገበያ ትርፍ ምርት ሊያቀርብ ይችላል። ይኼን ለማድረግ የዝቅተኛ አምራቾች መብትና የማምረት አቅም መከበር ይኖርበታል። የምግብ እርዳታ መቆም አለበት። የሚረዳው የአሜሪካኖችን አምራቾችና አትራፊዎች፤ የአገር ውስጥ ተባባሪዎችን ነው። ገበሬው ጠንካራና አካባቢውን የሚያውቅ፤ አብዛኛውን ምርት ለሸማቾች የሚያቀርብ፤ ልምድ ያለው ነው። ዋናው ማነቆ የመሬትና የሌላ ተፈጥሮ ሃብት ባለቤትነት ፖሊሲ አለመኖር ነው። ፖለቲካ። ገዢው ፓርቲ ሕገ መንግሥቱን ተጠቅሞ የከተማና የገጠር መሬት የገዢው ፓርቲ የግል ሃብት አድርጎታል። እንደፈለገው ይሸጠዋል። ያከራየዋል። ትርፍ ያገኝበታል። ወዳጆች ይገዛበታል። ተቃዋሚውን ይቆጣጠርበታል። በገጠር ዘመናዊ የሆነ፤ የገዢው ፓርቲ "ጭሰኝነት" ይዞታ ተፈጥሯል። በከተማ፤ ነዋሪዎችን ከመሬታቸውና ከቤታቸው እያስወጣ የቤት እጥረት ፈጥሯል። በአጠቃላይ፤ የተፈጥሮ ሃብት ባለቤትነት ከኢትዮጵያውያን እጅ እየወጣ ወደ ገዢው ፓርቲ፤ ታማኞችና ወደ ውጭ ኢንቬስተሮች ተሸጋግሯል። የባለቤትነት መከልከል፤ የዜግነት መከልከል ሆኗል። ባለቤትነት የዜግነት መብት ነው። የኢትዮጵያ ዝቅተኛ ገበሬ በበሬ አርሶ፤ ወይንም ቆፍሮ ኑሮውን ለማሻሻል አይችልም። የእርሻው መሳሪያ መሻሻል አለበት። መንግሥት የግል ክፍሉ ብዙ አንስተኛ የማዳበሪያ ፋብሪካዎች እንዲያቋቁም ማንኛውንም ድጋፍና መደጎሚያ መስጠት አለበት።

ገዢው ፓርቲ ኢትዮጵያውያን በዘመናዊ እርሻዎች ስራ እንዲሰማሩ ፖሊሲውንና ደንቡን አጎልማሽ ማድረግና ዝቅተኛ አምራቾች ከታላላቅ ዘመናዊ እርሻ ስራዎች ጋር ጎን ለጎን ተደጋግፈው እንዲሰሩ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል። "ጠፍ መሬት አለ" የሚለው አደገኛ ፖሊሲ በአስቸኳይ መለወጥ አለበት። አብዛኛዎቹ የዘመናዊ እርሻ ስራዎች በኢትዮጵያውያን ባለቤትነት መያዝ አለባቸው። የእርሻ መሬት ያላቸው ነዋሪዎች ለራሳቸው የሚጠቅማቸውን የጋራ (Joint ventures) ዘመናዊ እርሻ ለማቋቋም መብታቸው መጠበቅ አለበት። ይህም ሆኖ፤ የእርሻ እድገት ብቻውን የአብዛኛውን ሕዝብ ህይወት አይለውጠውም። ለተማረው ብዙ ሚሊዮን የስራ እድል አይፈጥም። የግብርና ስራ ከቴክኖሎጂ፤ ከኢንዱስትሪ፤ ከማኒፋክቸሪንግ፤ ከመሰረት ልማት ወዘተ ጋር አብሮ መሄድ አለበት። በየትኛውም ክፍል የሃብት ባለቤትነትና ሃላፊነት ሕጋዊና ተቋማዊ መሆን አለበት እንላለን። የኢትዮጵያውያን የተፈጥሮ ሃብትና የሌላ የግል ሃብት ባለቤትነት፤ አገዛዝና አስተዳደር መሰረታዊ የፖሊሲ ጥያቄ ሆኗል። ረሃብንና ደሃነትን አስወግዶ ለገጠሩ ሕዝብ አዲስና የተሻሻለ የኑሮ ደረጃ ስኬታማ ማድረግ የልማት ዋና መሰፈርት ነው። ለዚህ ዋናው መነሻ ገበሬው የመሬቱ ባለቤት፤ ከተሜው የቤቱና ቤቱ የተቀመጠበት ቦታ ባለቤት ሲሆኑ ነው። መካከለኛው መደብ መስፋፋት አለበት። ከተሜው የሚኖርበት መሬት ባለቤትነት በሕግ መከበር አለበት። ወጣቱ ትውልድ የአሁኑን የአንድ ፓርቲ የኢኮኖሚና የተፈጥሮ ኃብት የበላይነት፤ አፋኝነትና ጎታችነት መቃወም መብቱ ነው። ካልተቃወመ በራሱ አገርና በአገሩ የተፈጥሮ ሃብት መብት፤ ባለቤትነት፤ ሃላፊነት፤ ድምጽና ግዴታ እንደማይኖረው መገመት አለበት። የኦክላንድ ኢንስቲቱት እንዳለው፤ "ዛሬ በኢትዮጵያ የውጭ አገር ሰዎች ከኢትዮጵያውያን የበለጠ ሃይልና ተደማጭነት አላቸው።" ይህ፤ በኢትዮጲያ የመጀመሪያ መሆኑ ነው። 91/

7. የኢትዮጵያን ማህበረሰብ ካፒታል መንከባከብ ለልማት አስፈላጊ ነው

ኢትዮጵያ የብዙ ብሄር/ብሄረሰብ/ሕዝብና ሃይማኖቶች ባለ ፀጋ ናት። ይህን ፀጋ በመንከባከብ መጠቀም---የትምኅርትና ስልጠና፤ የጤና፤ የምግብ፤ የመጠለያ አገልግሎት ያለ ምንም አድልዎ መስጠትና መፍቀድ--ለምርት እድገት፤ ለተባበረና

ለሚተሳሰብ ህብረተሰብ ግንባታ፤ ለቀጣይና ፍትሃዊ ልማት መሰረት ነው። በወጣቱ ትውልድ አንጻር ሲታይ፤ የትምኅርት ፍልስፍና ብሄራዊ፤ ጥራት ያለውና ከአንድ ፓርቲ ቁጥጥር ውጭ መሆን አለበት። መንግሥት ለትምህርት ትኩረት መስጠቱ ባይካድም፤ ትምህርቱ ጥራት የለው፤ ብፋብሪካ እንደሚመረት ይገባኛልነት ሆኗል። ግለሰቦች በፖቲካ ግንኙነት ውጤት ከገዙ፤ ዲግሪ ከገዙ የትምህርት ጥራት ዋጋቢስ ሆኗል ማለት ነው። ትምህርት እንደ ሙስና መሆን የለበትም። በፈጣን ያደጉ ወይንም በማደግ ላይ ያሉ አገሮች-- ኬንያንና ጋናን አይተናል-- ሶስት ነገሮችን አጣምረው በተግባር ያሳያሉ። አንድ፤ አኅልማሽ መንግሥት፤ ተወዳዳሪ ገበያና ብሄራዊ የግል ክፍል አስፈላጊ መሆኑ። ሁለት፤ የመንግሥት ሚና መሰረተ ልማት ማስፋፋትና ጥራት ያለው አስተዳደር እንዲኖር ማድረግ መሆኑ። ሶስት፤ መንግሥት ወጣቶች ስራ የሚይዙበትንና የሚፈጥሩበትን በር ሁሉ መክፈት ዋና ተግባሩ መሆኑ። በኢትዮጵያ ገዢው ፓርቲ የግሉን ስራ ተክቷል። የወጣቱን ትውልድ ተሳትፎ፤ የመፍጠር፤ የምርትና የአገልግሎት ድርጅቶች የማቋቋም አቅሙን ጎድቶታል። ወጣቱ ትውልድ ነጻነትና መብት ከሌለው አገሩን ካለችበት ኋላ ቀር ኢኮኖሚ ወደ ኢንዱስትሪ ለማሸጋገር አይችልም። የተለያዩ ጥናቶች በተደጋጋሚ ያሳዩት የኢትዮጵያ መንግሥት ሕዝቡ የሚፈልገውንና የሚመካበትን እቃዎች ለመፈብረክ አልቻለም የሚል ነው። ገዢው ፓርቲ የግሉ ክፍል ሊሰራው በሚችለውና በሚገባው የምርት ስራ ገብቶ ለማምረት አልቻለም። አስቸጋሪና አድሏዊ ሆኖ ያገኘነው፤ የትግራይን ክልል እድገት ስናይ፤ ልዩ ልዩ ለወጣቱ ትውልድ ስራ ፈጣሪ፤ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ አቅራቢ፤ እውቀት አቅራቢ የሆኑ ተቋሞች መስርቷል። ጥያቄው ሌሎች ክልሎችስ? ሌሎች ወጣቶችስ? ይህ ጎሳዊ አድልዎ መነሳት አለበት። ለአፋር፤ለኦጋዴን፤ ለጋምቤላ፤ ለቤኒ ሻንጉል ጉሙዝ፤ ለአሞ ሸለቆ ወጣቶች የትምኅርት እድል አለመስፋፋቱ በጣም አደገኛ ነው። ይኼ ችግር ትኩረት ይሰጠው እንላለን።

የማህበረሰብ ካፒታል (Social capital) ወደ ምርታዊ ካፒታል መለወጥ የልማት መስፈርት ነው። ኢኮኖሚው፤ ገበያውና የተፈጥሮ ሃብቱ በጥቂቶች፤ ለጥቂቶች ታፍኖ ተይዟል። ግለሰቦች የሚሰሩበት መሬት፤ የሚበደሩት ገንዘብ፤ የሚሸጡበት ገበያ ወዘተ ታግቧል። ገዢው ፓርቲ እድሎችን ዘግቷል። ራሱንና ታማኞቹን ብቻ አገልጋይ ሆኗል። ባጀት፤ትምኅርትና የስራ እድል በፖለቲካ ሲወሰን ማህበረሰብ ጎጂ የሆነ ውጤት አለው። እድሉ የተዘጋበት ደሃ ይሆናል። ስራ ለመፈለግ ይሰደዳል። የገቢና የኑሮ ልዩነት ይፈጠራል ወዘተ። በፍጥነት ያደጉና የሚያድጉ አገሮች ወጣቱን ትውልድ ድጋፍ እየሰጡ የግል ድርጅት ለማቋቋም ለማስፋፋት ችለዋል። ዘመናዊ መገናኛን ለቁጥጥር የሚጠቀመው ገዢው ፓርቲ ቴክኖሎጂን ሲያግብ አብሮ ያገበው የስራ እድልንና ምርትን ነው። መሬትን በፖለቲካ ውሳኔ ለሚፈልጋቸው ብቻ ሲሰጥ፤ ያቆረቆዘው የምርት ኃይሉንና የኑሮ መሻሻልን ነው። የእርሻ መሬት ከነዋሪዎች ነጥቆ ለውጭ ኢንቬስተሮች ሲለግስ፤ የፈጠረው ደሃነትን፤ ስራ አጥነትን፤ ረሃብን ነው። ኢትዮጵያ ያላትን የተፈጥሮ ሃብት ተጠቅማ የስራ፤ የማምረትና ኑሮን በፍጥነት የማሻሻል እድል መፍጠር አለባት። ገዢው ፓርቲ ይህን አላማ በቁጥጥር እደርስበታለሁ የሚል መሆኑን ተረድተናል። (the Ethiopian developmental state assumes that incomes and wealth will trickle down eventually). ቁጥጥር የምርት ኃይሉን ይገድባል።

ብሄራዊ ካፒታል ከሰማይ አይወርድም። በአዋጅ አይፈጠርም። ከአገር ተሰርቆ ከወጣ አይመለስም። ካፒታል የሚፈጠረው የሡብአዊ ኃይል በመንግሥት ተደግፎ ያለውን እውቀት፤ ባህል፤ ልምድ፤ የመፍጠር ችሎታ ወደ ምርት ሲለውጠው ነው። ትምኅርት የዚህን የመፍጠር፤ ድርጅት የማቋቋም፤ ለአገርና ለወገን ሃላፊነት የመውሰድ እሴት ማጠናከር አለበት። ወጣቱ ትውልድ "ታሪክ የለህም፤ አዲስ ታሪክ ፈጥረንልሃል፤ እኛ ከምናስበው ውጭ ለማሰብ አትችልም፤ እኛ ከሌለን ህይወት አይኖርህም" ከተባለ፤ ለራሱ፤ ለአገሩና ለህብረተሰቡ የማያስብ ትውልድ ይሆናል። ገዢው ፓርቲ የፈጠረው ማህበረሰብ እየባከነ የሚታየው ለዚህ ነው። የዚህ ውጤት የአገሪቱ ኢኮኖሚ መዋቅር አለመለወጥና ምርት አለማደግ ሆነዋል። አፋኝ አገዛዝ ሠብአዊ ችሎታን ያደነዝዛል። ችሎታ ወደ ስራ የሚተረጎመው ነጻነት ሲኖር ብቻ ነው። ኔልሰን ማንዴላ እንዳለው። "እስረኛ ለመደራደር፤ ኮንትራት ለመፈረም አይችልም።" ገዢው ፓርቲ ኢትዮጵያውያን እንዲደራደሩ፤ ለመብታቸው እንዲቆሙ ፈቅዶ አያውቅም። ይህ የፖለቲካ ባህል የጎዳው ወጣቱን ትውልድ ነው። ሌላው በማህበራዊ ካፒታል የሚታየው ቀውስ ልዩ ልዩ ብሄረሰቦችና ማህበረሰቦች ያላቸው የኢኮኖሚ ባህል፤ ልምድና ታሪክ መባከኑ ነው። ምንነትና ማንነት የኢኮኖሚ ጥቅም አለው። ገዢው ፓርቲ ብሄራዊ እውቀትን ለልማት አያዋልም። አስጊ ባህል ፈጥሯል። ማንነቱንና ምንነቱን የተነፈገ ወይንም የተገፈፈ ሕዝብ በራሱ ተማምኖ ለመፍጠርና ለመወዳደር አይችልም። ጎረቤት አገር ኬንያ "የነብር ኢኮኖሚ" አገር ወለድ ልማት እየፈጠረች ነው ያልነው ለዚህ ነው። ትቀድማት የነበረችው ኢትዮጵያ እየተቀደመች ነው።

ብሄራዊ ልምዶችን፤ ችሎታዎችን፤ ባህሎችን፤ ታሪኮችን (Indiginous knowledge and culture) መንከባከብና መጠበቅ ለልማት ቁልፍ ነው። ሁሉ ነገር በውጭ ካልተሰራና ካልተፈጠረ ዋጋ ቢስ ነው ማለት የልማትን መሰረት አለማወቅ ነው። ጥራት ያለው ትምኅርት የሕዝብ ስብጥርነትን እንደ ችግር አያይም። ለሁሉም ተሳትፎና የእድል እኩልነት ትኩረት ይሰጣል። የህወሓት/ኢህአዴግ የትምኅርት ፍልስፍናና አመራር ለህብረተሰቡ መተማመንና አብሮ

ተደጋግፎ ደሃነትን፤ ረሃብንና ሌሎችን ብሄራዊ ችግሮች ለማስወገድ ትኩረት አልሰጠም። መለስ እንደተናገረው፤ አዲሱ ትውልድ የተማረው የኑሮ ማሻሻያ መንገድ "የአባትህ አገር ሲወረር አብረህ ውረር" የሚል የስግብግብነት ፖለቲካ ኢኮኖሚ ባህል ነው። ይህን የፈጠረው ስርአቱ ነው። ብዙ ቢሊየን ዶላር ከእርዳታና ከስደተኞች የሚገኝ ገንዘብ ቢጎርፍ ቀጣይነትና ፍትሃዊነት ያለው ልማት አይኖርም። ለልማት የሚውለው ካፒታል ይሰረቃል። ከአገር ይወጣል። ከአገር ልምድና ባህል ጋር አልተያያዘም። ሌላው ገዢው ፓርቲ ሆን ብሎ የቀየሰው የማህበረሰብ ካፒታል ፖሊሲ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ እየከፈለ ያስተማረው የሰው ሃይል እንዲሰደድ ማድረጉ ነው። ከሶስት ሺህ ሰባት መቶ ሃኪሞች ሶስት ሽዎቹ ከኢትዮጵያ ሲሰደዱ ወይንም ሲወጡ የሚጎዱት ሕክምና የማያገኙ ኢትዮጵያውያን ናቸው፤ ታይላንድ ወይንም ደቡብ አፍሪካ ሄደው ለመታከም የማይችሉት። አስተምሮና አሰልጥኖ ለውጭ ገበያ ማበርከት የአገሪቱን የተማረና የሰለጠነ የሰው ሃይል ቀንሶታል። አገር ወለድ ኢኮኖሚ እንዳይፈጠር ማነቆ ሆኗል። የተማረ የሰው ሃይል የሌለው አገር ዘመናዊ ሊሆን አይችልም። ባህሉና ልምዱ ለውጭ ሰለባ ይሆናል። ገዢው ፓርቲ ዜናና እውቀት እንዳይሰራጭ አፈና አድርጓል። ከላይ እንዳቀረብነው፤ በኢንተርኔት ስርጭት ኢትዮጵያ ከአፍሪካ አገሮች አምሳ ሁለተኛ ናት። ከሶማልያ ዝቅተኛ መሆኗ ነው። በህንድ አገር፤ የገጠር ነዋሪዎች ዜናና ዘመናዊ እውቀት በቀላሉ ያገኛሉ። ኢኮኖሚስት የተባለው ጋዜጣ የህንድን የገጠር ኢኮኖሚ ዘመናዊ ያደረገው "ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ነው" ብሏል። የኢትዮጵያ መንግሥት ዘመናዊ ቴክኖሎጂን ከወጣቱና ከገጠሩ ነዋሪ ጋር ማያያዝ ለስልጣኑ አደጋ ይፈጥራል የሚል ግምት ያለው ይመስላል። ስለዚህ፤ ወጣቱ ትውልድ የራሱ የእውቀት፤ የልምድ፤ የታሪክና የባህል ሰለባ ዋጋ ከፋይ እንዳይሆን ለሙብቱ መነሳት አለበት። "ህይወቴ ዋጋ ቢስ መሆን የለበትም" ለማለት መድፈር አለበት። 92/

8. የኢትዮጵያ የተማረ ሰው ሃይል ፍልሰት መቆም አለበት

ስደት የኢትዮጵያውያን መታወቂያ መሆኑ አሳፋሪ ነው። ከላይ ላቀረብነው የፖሊሲ ለውጥ ተባባሪ፤ የተማረ፤ የሰለጠነና ልምድ ያለው የሰው ሃይል ስደት ቀጣይነት ያመጣው ቀውስ ነው። የስደተኛነት ባህል ፍትሃዊነትና አገር ወለድ ለሆነ ልማት ማነቆ ሆኗል። ገዢው ፓርቲ ሆን ብሎ ለመሰደድ ለሚፈልግ ሁሉ እያበረታታና ማነቆዎች እየፈጠረ "የስደት ፓስፖርት" ሲሰጥ ቆይቷል። ስደት ተወዳዳሪን ይቀንሳል። የውጭ ምንዛሬና ደጋፊ ይፈጥራል። የአገር ባህል፤ ልምዶች፤ ታሪክ እንዲባከኑ ያደርጋል። ከአገሪቱና ከህብረተሰቡ አንጻር ስናየው፤ ስደት ከገንዘብ ካፒታል ሽሽት ተመሳሳይ ወይንም የባሰ ጉዳት አለው። ገንዘብ በእርዳታና ስደተኛው በሚልከው ይተካል። የሰው ሃይል ልምድና እውቀት አይተካም። ስደተኛው የሚልከው ገንዘብ በብዛት ተሰርቋል። ከምርት ላይ አልዋለም። በአገሪቱ ልማት ላይ ያለው አስተዋጽኦ መጠነኛ ሆኗል። የተማረውና የሰለጠነው የሰው ሃይል በያለበት፤ የአሁኑና የወደፊቱ ትውልድ "የስደተኛ ትውልድ" እንዳይሆን አፋኝ የሆኑ የመንግሥት ፖሊሶዎች እንዲለወጡ መታገል አለበት። በአገር ውስጥ እድል ካለና አፈና ከቆመ፤ ኢትዮጵያን ለማሻሻል፤ የነፍስ ወከፍ ገቢን ለማሳደግ፤ ራስን ረድቶና ኮርቶ አገርንና ህብረተሰብን ለመርዳት ያለው እድል በውጭ ካለው እድል የበለጠ ይሆናል። ጥሩ አገዛዝ ከተፈጠረ፤ ኢትዮጵያ አስደናቂ የልማት ውጤት ታሳያለች። ደሃነትና ረሃብ ይጠፋሉ። በዚህ አንጠራጠርም።

9. ልጃገረዶችና ሴቶች የልማት መሰረት ናቸው

በቅርብ የማውቀው የዓለም ባንክ ፕሬዝደንት (ዘረኛነትን ለማቆም አማካሪ በነበርኩበት ወቅት) ጀምሥ ወልፎንሶን ኢትዮጵያ በጎበኘበት ወቅት ለመለስ ፊት ለፊት የነገረው "የኢትዮጵያ ሴቶች ሙብት መገፈፍ ለሃገሪቱ አሳፋሪ" መሆኑን ነበር። በተጨማሪም፤ ለወጣቶች ስራ ካልተፈጠረ ዘላቂነትና ፍትሃዊነት ያለው ልማት እንደማይኖር ነግሮት ነበር። በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለው የትምህርትና የስራ እድል ልዩነት የኢትዮጵያን እድገት ጎድቶታል። ይህ የገዢው ፓርቲ ችግር አይደለም። የህብረተሰቡ ችግር ነው። የተማሩ ወንዶች የሴቶችን እኩልነት፤ የሴቶችን ሙብት፤ የሴቶችን ተሳትፎ አልተቀበሉም። የሴቶች እኩልነት ጥያቄ የሠብአዊ ሙብቶችና የልማት ጥያቄ ነው። ሴቶች ነጻና እኩል ካልሆኑ፤ ነጻነትና እኩልነት ሊኖር አይችልም። አበው እንደሚሉት፤ "አንድ ሰው በአንድ እጁ ብቻ ሊያጨበጭብ አይችልም።" አገር በወንዶች ብቻ ሊያድግ አይችልም። የምስራቅ ኤዢያ አገሮች በፍጥነት ያደጉት ልጃገረዶችን በማስተማርና በማሰልጠን፤ በዘመናዊ ኢኮኖሚ እንዲሳተፉ ቅድመ ሁኔታዎችን በመፍጠር፤ ተመጣጣኝ ደመወዝ በመክፈል፤ ሙብታቸውንና ክብራቸውን በሕግ በማክበር ነው። የብሄራዊ ምርትና አገልግሎት ውጤታቸውን አሳድገዋል። ዛሬ ሴቶች የማይሳተፉበት የኢኮኖሚ ዘርፍ የለም። የኢትዮጵያ ሴቶች፤ በታሪካቸውና በሚናቸው የቤተሰባቸው መሰረቶች ናቸው። ዝቅተኛ የአገልግሎት፤ የመመገቢያ፤ የሆቴልና ሌሎች ተቋሞች የሚያካሂዱት በብዛት ሴቶች ናቸው። የገጠሩ ኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ሴቶች ናቸው። ከሁሉም በላይ ለልጆቻቸውና ለቤተሰቦቻቸው ደህንነት፤ ጤንነት፤ ትምኅርት፤ ሰላምና ፍቅር ምሰሶ ሆነው የሚያገለግሉ ሴቶች ናቸው። የሴቶችን ሙብቶችና ችሎታ በከፍተኛና ዘመናዊ በሆነ ደረጃ ማንቀሳቀስ የትውልድ ጥያቄ ሆኗል። መንግሥት ምሳሌና አርአያ መሆን ይኖርበታል። የኢትዮጵያ ህብረተሰብ በግማሽ

አካሉ ቀጣይነትና ፍትሃዊነት ያለው ልማት ለመመስረት አይችልም። ልጃገረዶችን ለሃያ አንደኛው "የሰው ሃይል ባርነት" መዳረግ፤ የአገርንና የህብረተሰብን ክብር ማዋረድ ሆኖ አግኝተነዋል። ስደተኛው ለሴቶች መብት አስተዋጽኦ ለማድረግ ይችላል። የእኩልነት ጠበቃ መሆን አለበት እንላለን።

10. የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት መጨመሩ ችግር አይደለም

ኢትዮጵያ የሕዝብ ብዛት በፍጥነት ከጨመረባቸው አገሮች መካከል አንዷ ናት። ዛሬ 94 ሚሊዮን የሆነው በ2050 278 ሚሊዮን መሆኑ አከራካሪ ቢሆንም ከሁለት መቶ ሚሊዮን በላይ መሆኑ አይቀርም። በሕዝብ ብዛት ኢትዮጵያ ከዓለም አስረኛ ትሆናለች ማለት ነው። የመስኖ እርሻ በሰፋት መስፋፋትና መለመድ አለበት። ህወሓት በቂመኛነት የጣና በለስን የተያያዘብ፤ በእቅድ የተዘጋጀ መለማመጃ ማፈራረሱ አገሪቱንና የአካባቢውን ነዋሪዎች በጣም ጎድቷል። ከስድሳ በመቶ በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሰላሳ አምስት አመት እድሜ በታች ነው። አገሪቱ ይህን ሕዝብ የሚደግፍ የተፈጥሮ ሃብት--ዝናብ፤ ውሃ፤ ለም መሬት፤ የመስኖ ሃብት፤ መአደን ወዘተ አላት። የሕዝብ ቁጥር ጭማሬ ለከተማና ለገጠር መሬት፤ ለውሃ ወዘተ ያለውን ውድድርና ሽሚያ ያባብሰዋል። የሕዝብ እድገት ባለሞያዎች የወጣቱን ብዛት "demographic bubble" ብለውታል። ይህ እንፋሎት የማህበረሰብና የኢኮኖሚ ጥቅም አለው። የገጠሩ ወጣት ትውልድ ተምሮ በእርሻ፤ በቴክኖሎጂና በተመሳሳይ ስራ እንዲሰማራ ቅድመ ሁኔታዎችን መፍጠር አስፈላጊ ነው። አመራርና አመቻች መሆን የመንግሥት ሃላፊነት ነው። የመሬት ባለቤትነት፤ መጠለያ፤ መንገድ፤ መጸዳጃ፤ ንፁህ ውሃ፤ ትምኅርት ቤት፤ የጤና አገልግሎት፤ ዘመናዊ መገናኛ፤ገበያ፤ ወዘተ መስፋፋት አለበት። የመንግሥት ፖሊሲ የማህበረሰብ፤ የኢኮኖሚ፤ የፖለቲካ፤ ወዘተ ማነቆዎችን ማስወገድ ይኖርበታል። የገጠሩ ሕዝብ ከከተማው ሕዝብ ጋር የተያያዘ ህይወት እንዲኖረው ጥረት መደረግ አለበት። የገጠሩ ደሃ ወይንም ስራ ፈላጊ በከተማ ስራ እንዲኖረው ኢንዱስትሪ መስፋፋት ይኖርበታል። እነዚህና ሌሎች ደጋፊ አገልግሎቶች ከተመሰረቱ የሕዝብ ብዛት ወደ ምርታዊ እድገት ያመራል። የገጠሩ ኢኮኖሚ ወደ ዘመንዊ ኢኮኖሚ ይለወጣል። ይኼ ከሆነ ኢትዮጵያ ታላቅ አገር ትሆናለች፤ ሕዝቧ ከደሃነት ቀንበር ይላቀቃል።

11. የኢትዮጵያ የግል ኢኮኖሚ ክፍል መታፈን መቆም አለበት

ዓለም ባንክ በተግባር ባይተረጉመውም በተከታታይ ያሳሰበው የኢትዮጵያ የግል ክፍል መስፋፋት አለበት ይሚል ነው። የህወሓትና የፈጠራቸው ድርጅቶች የኢኮኖሚ የበላይነት የኢትዮጵያን የግል ክፍል አፍኖታል። ይህ የበላይነት ፖሊሲ (party and endowment ownership and monopoly) መለወጥ አለበት። ፍላጎትና ችሎታ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ተስፋ ቆርጠዋል። አንዳዶቹ አገር ለቀዋል ወይንም ንግዳቸውን ዘግተዋል። ሃቁ የፓርቲው ደጋፊ፤ በተለይ የትግራይ ተወላጅ ያልሆኑ ግለሰቦችና ኩባንያዎች ለመወዳደር አይችሉም። ገዢው ፓርቲ ለውጭ አገር ኩባንያዎችና ለምርጥ የውስጥ ደጋፊዎች የሚያደርገው አድልዎ የአገር ወለድ የግል ክፍሉን አፍኖታል። የአገሪቱ የማምረት ሃይል ተጎድቷል። ሕጉ፤ ደንቡና መመሪያው ለፓርቲውና ለደጋፊዎቹ አድልዎ ያደርጋል። የኢትዮጵያ የግል ክፍል ከአፍሪካ አገሮች ሁሉ ኋላ ቀር ነው። የኢትዮጵያ ነጋዴዎች በመንግሥቱ አመራር ምንም እምነት የላቸውም። ዓለም ባንክና ሌሎች፤ ኢኮኖሚው ለውድድር "ዝግ መሆኑንና የፓርቲው የበላይነት" የአገሪቱን የማምረት ሃይል እንዳገበው አሳስበዋል። ስለዚህ፤ ገዢው ፓርቲ ከግል ስራ መውጣት አለበት። (The governing party should get out of the business of mixing politics with business). አለበለዚያ አገር ወለድ ልማትና ከፍተኛ የስራ እድል አይፈጠርም። ጉቦ፤ ሙስናና የውጭ ምንዛሬ ህገወጥ በሆነ መንገድ ከኢትዮጵያ ማሸሹ ይቀጥላል። በትግራይ ክልል የግል ክፍሉ በመንግሥት ድጎማ እንዲያድግ ደገፎ በሌላው የሚከለከልበት ወይንም መሰናከሎች የሚፈጥርበት ምክንያት የጎሳዊ የበላይነት መሰፈርት ሆኖ አግኝተነዋል። ጎሳዊ አድልዎ መወገድ አለበት። 93/

12. የውጭ መንግስታትና አበዳሪዎች ለሠብአዊ ሙብቶች አፈና አስተዋጽኦ ማድረጋቸው ይቁም

የኢኮኖሚና የተፈጥሮ ሃብት ሉአላዊይነት ለተከታታይ ትውልድ ህይወት መሻሻል ወሳኝ ነው። ሉአላዊይነት የሌለው ህብረተሰብ "ለዘመናዊ ባርነት" ይዳረጋል። ኢኮኖሚው በጠባብ ጎሰኛ ቡድን መያዙ ለአብዛኛው ወጣት ትውልድ አማራጭ አልፈጠረለትም። "ተምሮ ለስደት" የሚያሰኝ ሁኔታ ተፈጥሯል። ታማኝ የሆኑ ዘገባዎች የሚሉት፤ ዛሬ፤ የኢትዮጵያ ዋና ለዓለም ገበያ አቅርቦት( lead export) የሰው ሃይል ሆኗል። በሳውዲ አረቢያና በገልፍ ሃገሮች ሁለት ሚሊዮን። በሰሜንና በደቡብ ሱዳን ሁለት ሚሊዮን። በምእራብ አገሮች ከአንድ እስከ ሁለት ሚሊዮን። በሌሎች አገሮች ብዙ መቶ ሽህ ስደተኞች ይገኛሉ። ከአምስት እስከ ስድስት ሚሊዮን በላይ ስደተኛ ያበረከተ መንግሥት የእድገት ምሳሌ አይደለም። የተስፋ መቁረጥ ምሳሌ ነው። ከሰብአዊ መብቶች መገፈፍ ሌላ፤ ኢትዮጵያ፤ እአአ በ 2011 በጤና ጥበቃ አገልግሎት ከአለም 109ኛ፤ በንጹህ ውሃ አቅርቦት፤ ከአለም የመጨረሻ፤ በሰው ኑሮ ደህንነት (Human Safety

and Security) ከአለም 106ኛ ፤ በሰብአዊና በግለሰብ ነጻነት 110ኛ (ከሁሉም አገሮች ነጻነት የሌለባት)፤ በዘመናዊ የመገናኛ ቴክኖሎጂ አቅርቦት--ኢንተርኔት፤ ሞባይል-- ከመቶ አገሮች ሃያ አምስተኛ፤ በመኖሪያ ቤት የማግኘት እድል፤ ከ 108 አገሮች ዘጠና አንደኛ፤ በህግ የበላይነት 101ኛ ፤ በግለሰቦች መካከል ባለው የገቢ/የኑሮ ልዩነት (Income, wealth and social--jobs, education, health-- inequality) ከዓለም 20ኛ መሆኗን ያሳያሉ። እነዚህን ፖሊሲ ነክ ችግሮች የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት በቀላሉ ሊያጠፋቸው አይችልም። በሰብአዊና በግለሰብ መብቶች በኩል ያለው ጫና ከሁሉም በላይ አሳሳቢ መሆኑን የአሜሪካ መንግስት የውጭ ጉዳይ ሚንስቴር (Department of State) በያመቱ የሚያወጣውን ዘገባ ብቻ ማየት ይበቃል። የሠብአዊ መብቶች ሲታፈኑ የኢኮኖሚ ተሳትፎም አብሮ ይታፈናል። የዚህ ውጤት የተዛባ የሃብት ባለቤትነትና የተዛባ የገቢና የኑሮ ልዩነቶች ናቸው። አገዛዙ የኢኮኖሚ ፍትህ (Economic justice) ለመፍጠር የማይችል ሆኗል። እድገት ይኖራል። ሆኖም እድገቱ በብሄር/ብሄረሰብ መካከል ያሉትን ልዩነቶች ያባብሳቸዋል። ሰፊ የገቢ፤ የሃብትና የኑሮ ልዩነቶች ሲፈጠሩ፤ ቀደም ሲል የነበሩት የብሄር፤ ብሄረሰብና የጾታ ቅራኔዎች አደገኛ፤ የተፈጦ ሃብት ሽሚያ ይባባሳል፤ የነሳ ማጽዳት ዘመቻው አደገኛ ደረጃ ላይ ይደርሳሉ። 94/

ፌዝ ካሪሚ በሲኤንኤን September 3, 2012, "የሰብአዊ መብት ተቋሞች እንደሚሉት ከሆነ፤ መለስ የግለሰቦችን ነጻነትና መብቶች ደጋግሞ ጥሷል። የመገናኛ ብዙሃንን አጥፍቷል። ጋዜጠኞችን አስሯል። ዛሬ ኢትዮጵያ ከኤርትራ ቀጥላ "ጋዜረኞችን" በማሰርና በማሳደድ ሁለተኛውን ደረጃ ይዛለች። ህወሓት ተቃዋሚ ድርጅቶችንና መሪዎችን መንጥሯል። የምእራብ አገሮች ይህ ሁሉ ሲሆን፤ የመለስን ድክመት እንዳላዩ አልፈውታል። ለእነሱ፤ መለስ ጸረ-ሽብርተኛ ሆኖ በአፍሪካ ቀንድ መቆሙ የወዳጅነት ዋና መለኪያ ሆኗል።" ገዢው ፓርቲ አፋኝና ሽብርተኛ መሆኑ አይነገርም። ጠናካራ ጎን ብቻ በማንሳት፤ የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት ተቃዋሚ የሆነውን ሁሉ መግደል፤ ማሳደድ፤ ከሃብትና ከመሬት ማስውጣት የአገዛዙ ስልት አድርጎ መጠቀሙን ችላ ብለውታል። በረጅም ጊዜ ጥቅም ሲታይ ይህ አያዋጣም። ለሽብርተኛነት ዋና መንስኤ የሆነውን ደሃነት ነት ለማጥፋት የፖሊሲና መዋቅራዊ ማነቆዎችን ማስወገድ ያስፈልጋል። ሰብአዊ መብቶች ካልተከበሩ የፖሊሲና መዋቅራዊ ችግሮች አይፈቱም። ከሁሉም በላይ ሽብርተኝነትንና ሽብርተኞችን ለመከላከል የሚቻለው አድልዎና ደሃነት፤ ሙሰኛነት ወዘተ ሲጠፉ ነው። ለጋሶች ይህን መሰረታዊ የልማት ጉዞ ዘንግተውታል። የአሁኑ አገዛዝ ያተኮረው ሽብርተኞችን ከማጥቃት ላይ ነው። ለሽብርተኛነት መነሻ የሆኑትን የፖሊሲ ችግሮች ከማስወገድ ላይ አይደለም። ገዢው ፓርቲ ሽብርተኛነትን የእርዳታ ምንጭ አድርጎታል። እርዳታውን ለሠብአዊ መብቶች አፈና መሳሪያ ተጠቅሞበታል። አንዳንድ የውጭ ተመልካቾች "ገዢው ፓርቲ ሽብርተኛ ሆኗል" ብለዋል። ባጭሩ፤ የውጭ እርዳታ ከጥቅሙ ጉዳቱ አመዝኗል።

የአጃንስ ፍራንስ ፕሬስ ጀኒ ቮጋን፤ በ September 1, 2012, ሚኬላ ሮንግን (Michela Wrong, an authority on ethnic elites in Africa) በመጥቀስ፤ የመለስን ማረፍ እንዲህ ብላ አስቀመጠችው። "የገዢው መደብ የበላዮች (the Ruling Elites) ፍላጎት ጥቅማቸውን ማስከበር ብቻ ነው። እርጋታን የሚፈልጉት ለዚህ ነው።" እርጋታ መፈለጋቸው በቀጥታ ከምእራባውያን መንግስታት ጋር ያላቸውን ግንኙነት አጠናክሮላቸዋል። ሁለቱም፤ ከነጻነትና ከእውነተኛ ዲሞክራሳዊ ስርአት በላይ እርጋታን ይፈልጋሉ። ተቃዋሚዎችም ሆኑ፤ ህወሓት/ኢህአዴግ ይህን የተሳሰረ የጥቅም ግንኙነት በመነጋገር ለመፍታት መቻል አለባቸው። ይህ ካልሆነ ህብረተሰቡ በችግር አዙሪኝ ሲሰቃይ ይኖራል። የህወሓት/ኢህአዴግ ደጋፊ መንግስታትና ለጋስ ድርጅቶች ያልሞከሩቱን መሞከረ የሞራል ግዴታቸው ነው። ሽብርተኛነት መኖሩን እየተቀበልን ለማሳሰብ የምንፈልገው ለሽብርተኛነት ዋናው መንስኤ የአንድ ጎሳ-ተኮር አምባገነናዊ አገዛዝ ሆኗል። የምናየው የአገዛዝ ክፍተት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጠቃሚ የሆነ የፖለቲካ፤ የማህበረሰብና የኢኮኖሚ ድርጅትና አመራር አለመኖሩ ነው።

እየቆየ የሚታየው ሃቅ ለጋሶች የሚሰጡት እርዳታ ለሙስናና ለሠብአዊ መብቶች አፈና መጋቢ መሆኑ ነው። ከ 2000-2009 አስራ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ተሰርቆ ከአገር ሸሽቷል። በ 2009 ብቻ ሶስት ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ዶላር ተሰርቆ ከአገር ወጥቷል። ከዚያ ወዲህ በአመት ቢያንስ ሶስት ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ዶላር ከአገርና ከሕዝብ እየተሰረቀ ህገወጥ በሆነ መንገድ ከኢትዮጵያ ወጥቶ በልዩ ልዩ አገሮች ይደበቃል። ደሃነትን ለማጥፋት የሚያስችል ብዙ ቢሊዮን ዶላር ከደሃው፤ ከወጣቱ ትውልድ ይነጠቃል። የኪራይ ሰብሳቢው አገዛዝ ይህን ተአምራዊ እድገት ብሎታል። እኛም እውነት ነው እንላለን። የሚዘረፈውና ከአገር የሚወጣው ገንዘብ "ተአምር ነው።" ይህን እድገት ከአመት የነፍስ ወከፍ ገቢ አንጻር ስናየው፤ የኢትዮጵያ ከሶስት መቶ ስባ ዶላር አላለፈም። የአፍሪካ አማካይ ገቢ $1,070 ነው። የጎረቤቷ ኬንያ ገቢ $1,700 ነው። የምናውቀው፤ ከዚህ ደረጃ ለመድረስ የሕዝብ ተሳትፎ፤ የግል ክፍል እድገት፤ የወጣቱ በገፍ በስራ መሳተፍ አስፈላጊ መሆናቸውን ነው። የውጭ እርዳታ ለግሉ ክፍል  መስፋፋት፤ ለገበሬው ምርት እድገትና የመሬት ባለቤትነት ወዘተ አልዋለም። ስለሆነም፤ የውጭ እርዳታ ከጥቅሙ ጉዳቱ እያመዘነ ሄዷል። ስለዚህ፤ ኢትዮጵያውያን በያሉበት ለጋሶች የሚከተሉትን ፖሊሲ ከአገሪቱ፤ ከደሃው ሕዝብና ከወጣቱ ትውልድ፤ ከምዝበራና ከሃብት ሸሸት፤

ከሰብአዊ መብቶች፤ ከፕሬስ ነጻነት፤ ከፖለቲካ ተሳትፎ፤ ከግል ክፍሉ እድገት ግድፈቶች አንጻሮች እንዲያዩ ያልተቆጠበ ዘመቻ ማድረግ አለባቸው። በተጨማሪ፤ ለጋሶች በሙሉ ነጻ የሆነ፤ በኤክስፐርቶች የተደገፈ፤ በለጋሶች የሚመራ የአድልዎ፤ የጉቦ፤ የሙስናና የገንዘብ ሽሽት ፍተሻ ማድረግ የሞራል ግዴታቸው ነው። በእኛ ግምት፤ ይህ ፍተሻ ተደርጎ ውጤቱ ለሕዝብ ይፋ እስከሚሆን ድረስ፤ ለጋሶች የልማት እርዳታ ማቆም፤ ቢያንስ እርዳታቸውን ቀጥታ በሆነ መንገድ ከሰብአዊ መብቶች መከበር ጋር ማያያዝ አለባቸው። ምክንያቱም የልማት እርዳታው የሚመግበው አፈናን፤ አድልዎን፤ ሙስናንና የአስተዳደር ብልግናን ሆኗል። 95/

13. ስደተኛው የሚልከው የውጭ ምንዛሬ ሙስናን አጠናክሯል

ስደተኛው አስራ ስድስት ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን እንደሚደግፍ አሳይተናል። ይህ የሚያኮራ አስተዋጽኦ ነው። ሆኖም፤ ቀጣይነት ያለው፤ ምርትን የሚያሳድግ፤ የኢኮኖሚውን መዋቅር የሚለውጥ አስተዋጽኦ አይደለም። በተጨማሪ፤ ልክ እንደ ውጭ እርዳታው፤ አብዛኛው ስደተኛው የሚልከው የውጭ ምንዛሬ ቢያንስ፤ ሁለት ችግሮችን ፈጥሯል። አንድ፤ ለገዢው ፓርቲ አፈና ረድቷል። ሁለት፤ አብዛኛው የውጭ ምንዛሬ የዘረፋው አካል ሆኗል። በአመት ከሚላከው ከአራት ቢሊዮን ዶላር በላይ ከሚገመተው፤ ግማሹ የት እንደገባ አይታወቅም። የምንገምተው፤ ከአገር ህገወጥ በሆነ መንገድ እንደሚሸሽ ወይንም ጨርሶ ወደ አገር እንደማይገባ ነው። ስለዚህ፤ ስደተኛው ገንዘብ የሚልክበትን መንገድና ዘዴ አገርንና ወገንን በሚጠቅም ሁኔታ ለመላክ መወሰን አለበት የሚል ምክር እንሰጣለን። በተጨማሪ ስደተኛው ገዢው ፓርቲ የፖለቲካ፤ የማህበረሰብ፤ የኢኮኖሚ አመራር ለውጥ እንዲያደርግ መግፋት ይኖርበታል። ይህን ካደረገ ለአገሪቱ መፈራረስ ያለውን አደጋ ለማገብ አስተዋጽኦ ያደርጋል። የህብረተሰቡ አስቃቂ ኑሮ ዘላቂነትና ፍትሃዊነት ባለው መንገድ እንዲስተናገድ ይረዳል። እርምጃው የአገር ፍቅር መስፈርት ነው። አለማድረጉ የራስ ወዳድነት መስፈርት ነው።

13. ለም መሬትና ውሃ ከኢትዮጵያውያን እጅ መውጣቱ ዜግነትን አፍርሷል

ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሃብት ባለ ጸጋ ናት። መራብ የለባትም። የሚያስርባት መጥፎ የቁጥጥር ስርአት ነው። የሕዝብ ስንፍና አይደለም። የመጀመሪያው የመንግሥት ሃላፊነት የምግብ ዋስትና ነው። ህወሓት/ኢህአዴግ፤ የገጠሩን አምራች ለቁጥጥር ዳርጎታል። ለም የእርሻ መሬት ባለበት ሁሉ ነዋሪውን ለድህነት እየዳረገው ነው። ይባስ ብሎ፤ ከአራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በላይ ለሰላሳ ስድስት አገሮች- በመለስ መንግሥት አማካይነት፤ በግብዣ ለመጡ--የውጭ አትራፊዎች ሰጥቷል። ከግማሽ ሚሊዮን ሄክታር በላይ ለትግራይ ተወላጆች ብቻ ሰጥቷል ሲል Oakland Institute በማስርጃ አቅርቧል። ለትግራይ ተወላጆች ሲሰጥ ሌሎች ኢትዮጵያውያን መብት የላቸውም ማለቱ ነውን? አንድ ነገር እናስተውል። የአማራ ብሄረሰብ አባላት ከክልላችሁ ውጭ ለመኖር፤ ለመስራት፤ ለመንቀሳቀስ፤ ሃብት ለመያዝ አትችሉም የሚለው ህወሓት/ኢህአዴግ፤ ትግሬዎችን ለይቶ የትም ክልል መሬት፤ ሃብት፤ ቤት፤ ለመያዝ ይችላሉ ይላል። ከዚህ የበለጠ አይን-ጭፍን ጎሳዊ አድልዎ ሌላ አገር አይታይም። ዛሬ ኢትዮጵያን ከሌሎች አገሮች የሚለያት አንዱ የጎሳ አድልዎ ነው። ሌላው ህጋዊ የግል ሃብት የመያዝ መብት አስተማማኝ አለመሆኑ ነው። የግል ሃብት፤ የተፈጥሮ ሃብት ጨምሮ፤ ለእድገት ወሳኝ ነው። በእድገት ስም፤ የሃገርን የወደፊት መረጋጋት፤ የተተኪ ትውልድን እድል፤ መበረዝ መሆኑን ልንክድ አንችልም። የሃብት ባለቤትነትን የነሳው አገዛዙ ነው።

ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሃብቷን በጥናትና ምርምር በተደገፈ እቅድ የተፍጥሮ ሃብቷን ተጠቅማ ጠንካራና ሃብታም ሕብረተሰብ ለመፍጠር ትችላለች። ለም መሬት፤ ውሃ፤ ወንዝ፤ ማእደን፤ ለሃገር እድገት ቁልፍ ናቸው። ህንድ፤ ቬትናም፤ ቻይና፤ ቦትስዋና፤ ሳውዲ አረቢያ ወዘተ እድገት ያሳዩት የተፈጥሮ ሃብታቸውን ለውጭ ሃብታሞች ያለ ጥቅም በመስጠት አይደለም። ያደረጉት፤ የዝቅተኛ አምራቾችን፤ አገር ወለድ ሃብታሞችን በማበረታታትና ዘላቂነትና ፍትሃዊ የሆነ እድገትን መሰረት በመገንባት ነው። የለም እርሻ መሬት፤ ያለሕዝብ ድምጽ፤ ተሳትፎና ባለቤትነት እንደ ሸቀጥ ተሽጦ ለውጭ ምንዛሬ ተብሎ፤ ተመሳሳይ፤ ለነዋሪው ሕዝብና ለሃገር የሚያስገኘው ጥቅም ሳይታይ ፖሊሲ አይሆንም። ለዘጠና ዘጠኝ አመታት አይሰጥም። ማንኛውም ለአገሩና ለህብረተሰቡ ሃላፊነት የሚሰማው መንግሥት ባለሃብቶች ከሚያመርቱት፤ አብዣኛውን ለአገር ፍላጎት ማርኪያ ሳያረጋግጥ ውል አይዋዋልም። በኢትዮጵያ ነዋሪዎች መብት ስለሌላቸው ከኢንቬስተሮች ጋር ለመነጋገርና ለመደራደር አልቻሉም። ህወሓት/ኢህአዴግ፤ ግልጽነት በሌለበት መንግድ የመሬት ቸርቻሪ የሆነው ለማን ጥቅም እንደሆነ መጠየቅ አለበት። የህንዱ ካሪቱሪ፤ የሳውዲው ሳውዲ ስታር፤ ያለምንም ገደብ አምርተው፤ ነዋሪውን ከመሬቱ አስወጥተው፤ አማራጭ ሳይሰጡት፤ መሰረተ ልማት ሳያቀርቡለት፤ ለአካባቢው ዘላቂነት ሃላፊነት ሳይወስዱ፤ ከትርፋቸው ለነዋሪው ሕዝብ ሳንቲም ሳይሰጡ ከዓለም በዝቅተኛ ዋጋ የኢትዮጵያን ለም መሬት ተረክበዋል። መሬትና ውሃ ለውጭ መንግሥታትና ኩባንያዎች ማስረከብ ለነዋሪዎችና ለአገሪቱ ሕዝብ በሙሉ አደገኛ ነው። ሞዛምቢክ የዚህ አይነት ሰለባ መሆኗን አሳይቻለሁ። የኢትዮጵያ ሕዝብ እየተራበ፤ እየተሰደደ፤ እድገት አለ፤ የምግብ ዋስትና ይገኛል ብሎ መናገር አይቻልም። የምግብ ዋጋ ሰማይ እየደረሰ፤ ኢትዮጵያ ለም መሬቷን ለቻይና፤

ለህንድ፤ ለአረብ አትራፊዎች የምትሰጥበት ምንም የእድገትና የሕዝብ ህይወት ደጋፊነት ምክንያት የለም ከሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰናል።

የመሬት ነጠቃና ቅርሚት በሕዝብ፤ በተፈጥሮ ሃብት አያያዝና አጠቃቀም ላይ ያለው አደጋ መጠን የለውም። በነዋሪው ሕዝብ በኩል ብናየው፤ ከኦሞ ሸለቆ ውጭ፤ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊየን (1.5) ኢትዮጵያውያን ከሚኖሩበት መሬት ሲባረሩ፤ እድገት አለ ለማለት አንችልም ። አርጀንቲናና ብራዚል በቅርቡ በህግ አስገድደው፤ የውጭ ለም መሬት ያዡዎች የፈረሟቸውን ውሎች ለውጠዋል። የለወጡበት፤ አደጋውን በማየት፤ ከፍተኛ ዋጋ ማግኘት መብታችን ነው በሚልና አካባቢውን በዘላቂነት ለመጠበቅ በመወሰን ነው። እትዮጵያ፤ ዛሬ ዘጠና አራት ሚሊዮን ሕዝብ ለመመግብ አልቻለችም። ሕዝቧ ሁለት መቶ ሰባ ስምንት ሚሊዮን ሲሆን (በ2050)፤ ምን ሊበላ ነው ብለን መጠየቅ መብታችን ነው። ለወጣቱ ትውልድ የስራ እድል እንዴት ሊፈጠር ነው ብለን መጠየቅ ያለብን ዛሬ ነው። ስደተኞችና ተቃዋሚዎች ሁሉ በተፈጥሮ ሃብት፤ በተለይ በእርሻ መሬት ፖሊሲ ላይ አቅዋም መውሰድ አለባቸው። ሙስና ከተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም፤ ከእርዳታ፤ ከንግድ ፤ ከአስተዳደር፤ ወዘተ.ጋር የተያያዘ ነው። ኢትዮጵያውያን እነዚህን የተያያዙ ጉዳዮች አብረው ማየት ብሄራዊ ግዴታቸው ሆኗል። በተፈጥሮ ሃብቱ ላይ የባለቤትነት መብት የሌለው ሕዝብ ለስደት፤ ለደሃነት፤ ለጥገኝነት፤ ለስራ አጥነትና "ለዘመናዊ ባርነት" ይጋለጣል።

14.ሙስናና ህገወጡ (Illicit) ወደ ውጭ የሚጎርፈው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሃብት መቆም አለበት

በApril 2014, World Forum on Governance, Prague በተካሄደ ዓለም አቀፍ ውይይት ስለ ሙስና የወረርሺኝ በሽታ ለኤትዮጵያ አግባብ ያላቸው ጉዳዮች ተነስተዋል። የሕዝብ አገልጋዮች ነን የሚሉ በሕዝብ ደሞዝ የሚተዳደሩና ለሕዝብ ሃላፊነት አለባቸው የሚባሉ መሪዎችና ግለሰቦች የተረከቡትን ሃላፊነት ለግል ጥቅም፤ ማለትም ለግል ገቢና ሃብት ማካበቻ ሲያደርጉ በሕብረተሰቡና በሃገራቸው ላይ ወንጀል ፈጸሙ ማለት ነው የሚለውን አጠቃላይ ሃሳብ ተቀብለውታል። ጋናዊው ኮፊ አናን የተባበሩት መንግሥታት ዋና ፀሃፊ በነበረበት ወቅት፤ በዓለም ባንኩ ጀምስ ወልፈንሶህንን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ሙስና <u>"የሚዘገንን የተስቦ</u> <u>በሽታ ነው"</u> ብሏል። አማካሪው ሆኘ ያገለገልሁት ወልፈንሶህን "ሙስና ካንሰር ነው" ብሎ ዓለም ባንክ ሃላፊነት እንዳለበት ወሰኖና መመሪያ ሰጥቶ ነበር። በስራ ላይ ያልዋለ። የሙስናን አይነትና ጎጂነት በፊሊፒንስ፤ በኢንዶኔዢያ፤ በኬንያ፤ በቀድሞዋ ጋና፤ በናይጀሪና ሌሎች አገሮች አይቻለሁ፤ ትምኅርቶት ሌላው የማምነው ሙስና ስርአታዊና ተቋማዊ ለመሆን የሚችለው ከፍተኛ የፓርቲና የመንግሥት ባለስልጣናት፤ ቤተሰቦቻቸውና ውዳጆቻቸው የሙስናው ተሳታፊና ተጠቃሚ ሲሆኑ ነው። <u>"አሳ የሚገማው ከራሱ (ከቁንጮው ነው"</u> የሚለው የቻይናዎች አባባል ለዚህ ተገቢ ነው። ከላይ ከገማ ከታች ያለውን ለመከላከል አይቻልም። "<u>Ending Global</u> <u>Corruption</u>", Washington Post, Mark Wolf, July 23, 2014 ያቀረበው ዘገባ አግባብ አለው። እንዲህ ይላል። "Corruption is extraordinarily costl, consuming more than 5 percent of the global gross domestic product. Developing regions lose more than ten times in illicit financial flows (ከህግ ውጭ ሌቦች ከሃገር ሰርቀው የሚያወጡት) than what they receive in foreign aid." ከእርዳታ ከሚገኘው አስር ጊዜ ከፍ ያለ ነው የሚለውን አንቀበልም ለሚሉ ቢያንስ ግማሹን፤ ማለትም አምስት ጊዜ የሚለውን መቀበል ግዴታ ነው። ከኢትዮጵያ የሚሰረቀው በዓመት በአማካይ የሚሰረቀውና የሚሸሸው ሶስት ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ዶላር ነው። ስለዚህ ከኢትዮጵያ ከህግ ውጭ ተሰርቆ የሚሸሸው ዶላር ከእርዳታና ከውጭ ንግድ ከሚገኘው ንጥር ገቢ (net inflow) በላይ ነው ያልኩት ትክክል ነው። እንዲያውም ዝቅ አድርጌዋለሁ። ሙሰኞች ገንዘቡን የሚያሸሹበት ዘዴ በጣም ረቂቅና የተለያየ ነው። ይኼን በሃገርና በሕዝብ ላይ የሚደረገ በደል ከፍተኛና ይቅርታ የማይደረግለት ወንጀል ነው እላለሁ። እንደ ዩክሬንና ግብፅ የታደሉ አገሮች ሕዝቦቻቸው አፈናንና ሙሰኛነትን አንቀበልም ብለው መንግሥቶቻቸውን በሕዝብ አመፅ ሃልይ ለውጠዋል፤ ህይወታቸውን ሰውተዋል።m 96/

ከህብረተሰቡ ህይወት መሻሻልና ከኢትዮጵያ ደህንነት አንጻር ስናየው አስከፊው ውጤት የተከሰተው የዲሞክራሳዊ አማራጭን በመገንባትና የሰብአዊ መብቶችን በመታደግ በኩል ነው። እነዚህ ከሌሉ ዘላቂነትና ፍትሃዊነት ያለው ልማት አይቻልም። ዛሬ ወድቀዋል ወይንም በመውደቅ ላይ ናቸው የሚባሉት አገሮች--አፍጋኒስታን፤ ሶማሊያ፤ ሱዳን፤ ኢራክ፤ ሶሪያ፤ ዩክሬን፤ አስራ ሰባተኛዋ ኢትዮጵያ--በተከታታይ የሚያሳዩአቸው ግፎች የዜጎችን መብቶች በመግፈፍ ነው። አንባቢው የተለየ ትኩረት እንዲያደርግበት/እንድታደርግበት የምፈልገው ደሃውና ወደ ኋላ የቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ምንም መከታና ጠበቃ እንደሌለው ነው። መሬቱ ተነጥቆ ውጣ ሲባል ከመጮህ በስተቀር አቅም የለውም። ከላይ በሰፊው <u>እንዳሳየነው ሙስና ገንዘብ በመስረቅ ብቻ የተወሰነ አይደለም።</u> ዜጎችን በአስተዳደር ጉቦ እንዲከፍሉ ማስገድና ማጉላላት ሙስና ነው። ቋንቋን ተጠቅሞ ችሎታ ያለውን ግለሰብ አለመቅጠር ሙስና ነው። የምርጫን ድምፅ መደለዝና ማኮላሸት ሙስና ነው። በግለሰቦች ላይ ብልግናና ግድያ የፈፀሙትን በሃላፊነት በሕግ አለመጠየቅና ፍርድ አለመስጠት

ሙስና ነው። የጎሳ ማጽዳትና ግድያ ሙስና ነው። የሰብአዊ መብቶችን፤ የመናገር፤ የመፃፍ፤ የመንቀሳቀስ፤ የመሰብሰብ፤ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብቶች መከልከል ሙስና ነው። እነዚህን የሙስና ከፍሎች በማየት የተባበሩት መንግሥታት ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት አስፈላጊ ነው ብሎ International Anti-Corruption Court ለማቋቋም ጥረት እየተደረገ ነው። የተባበሩት መንግሥታት የሙስናን ደዌነት (Plague) በማጤን Convention Against Corruption የሚል መመሪያ አውጥቶ ነበር። አምባገነኖች እንዲከተሉት የሚያደርግ ሕግ የለም። ስለሌል ሙሰኞት እንደፈለጉት ይሰርቃሉ፤ እንደፈለጉት ብዙ ቢሊዮን ዶላር ከአገር ያወጣሉ። የመንግሥት ባለስልጣናት ሙሰኞች በሕግ የሚጠይቃቸው ኃይል የለም።

አግባብ የሚኖረው የተባበሩት መንግሥታት ከሰራ ላይ የሚውል ሕግና መመሪያ አውጥቶ ይኼን ጥርስ የሚሰጡት መርማሪዎች ሙሰኝነት በተከሰተባቸው አገሮች መላክ ነው። በተጨማሪ፤ የተባበሩት መንግሥታት ለጋሶችና አበዳሪዎች ሙስናና የሰበአዊ መብቶች በታፈኑባቸው አገሮች እርዳታ እንዳይሰጡ ማገብ ነው። አለያ፤ ሰላምና እርጋታ አይኖርም። ሽብርተኛነት አይቆምም። ለጋስና ለዲሞክራሲ ተቆርቋሪ የሆኑ መንግሥታት፤ ለምሳሌ አሜሪካና የአውሮፓ የጋራ ማህበር ሙሰኞችን ከአገር ሲወጡ ለፍርድ ለማቅረብ ይችላሉ፤ ይኼን ማድረግ እንዳለባቸው ማሳሰብ ያለበት የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በተለይ በውጭ የሚኖረው የተማረ ክፍል ነው። በአጭሩ <u>የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት የሙሰኛነትን ወረርሺኝ በመላው</u> ኢትዮጲያና በውጩ ስደተኛ ተቋማዊና መዋቅራዊ አድርጎታል። ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ በራሱ መንግሥት እየደማ ነው። 97/

የኢትዮጵያ ሕዝብ ህወሓት/ኢህአዴግ በሁሉም አቅጣጫ ሲዘርፍ እንዲኖር መፍቀድ የለበትም። ለመብቱ መነሳት አለበት። ሃቁ፤ ህብረተሰቡ በጠቅላላ በራሱ መንግሥት አድሏዊነት፤ በራሱ መንግሥት የአስተዳደር በደል፤ በራሱ መንግሥት ጎቦኛነትት፤ ምዝበራና አፈና በባሰ ደረጃ ደሃ እየሆነ መሄዱ ነው። ይህን የመብት አፈና መቀበል የለበትም። በዚህ መጽሃፍ እንዳሳየነው፤ ዛሬ ኢትዮጵያ በመንግሥት የተደገፈ የተደራጀ ምዝበራ የሚካሄድባት አገር ሆናለች። የደሃነት፤ የረሃብተኛነትና የስደት ዋና መነሻዎች ኢኮኖሚው አለማደጉ፤ ስራ በተፈለገው ደረጃ አለመፍጠሩ፤ የግል ክፍሉ በሚፈለገው ፍጥነት አለማደጉ ወዘተ መሆናቸው አያከራክርም። ችግሩ ይህ ብቻ አይደለም። አፋኙ አገዛዝ አስተዋጽኦ አድርጓል። ይህ አፋኝ አገዛዝ ታይቶ የማይታወቅ አድልዎ፤ ሙስና፤ ስርቆትና ከሕግ ውጭ ከአገር የሚሸሽ ሃብት ፈጣሪና ደጋፊ ሆኖ አግኝተነዋል። ምርጫዎችን ያለ ውድድር ማካሄድ ሙስና ነው። በአመት፤ ቢያንስ፤ 3.3 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ገንዘብ ተዘርፎ ይወጣል። ከውጭ እርዳታና ከብድር ከሚመጣ፤ ስደተኛው ከሚልከው፤ ከሸቀጥ ሽያጭ ከሚገኘው ንጥር የውጭ ምንዛሬና ገቢ (net inflow) በያመቱ ብዙ ቢሊዮን ዶላር ይሰረቃል። ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ምንም ተቆርቋሪ የሌላቸው ይመስላል። ሙስናና ከሕግ የወጣ ገንዘብ ማሸሽ ልክ እንደ ካንሰር ወይን እንደ ተስቦ በሺታ ተቋማዊና የማይፈቱ ሆነዋል። ዛሬ ብዙ ቢሊዮን መስረቅ ልምድ ከሆንባቸው ደሃና የእርዳታ ጥገኛ ከሆኑ አገሮች መካከል፤ ኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ ይዛለች። ደሃነት፤ ረሃብ፤ ስደት፤ ተስፋ መቁረጥ፤ መዋቅራዊ፤ የሆነ፤ የተዛባ ገቢና የኑሮ ሁኔታ (Gross income and asset inequality) በይፋ ይታያሉ። በያመቱ፤ ከእርዳታና ስደተኛው ከሚልከው የውጭ ምንዛሬ፤ ቢያንስ አርባ በመቶው በተደጋጋሚ ይሰረቃል። ወደ ውጭ ከሚላከው ሸቀጥ የሚገኘው አብዛኛው የውጭ ምንዛሬ የት እንደ ገባ አይታወቅም። የመጽሃፉን አርእስት ድርጅታዊ ምዝበራ ያልንበት ዋና ምክንያት ለዚህ ነው።

አስር ሽህ ኩንታል ቡና በቀን፤ በትሬንታ ኳትሮ ተጭኖ፤ ከሕግ ውጭ ከአገር ተሰርቆ ጠፍቷል። ድንጋይ ወርቅ ነው ተብሎ ለብሄራው ባንክ ቀርቧል። የኮትራባንድ ንግድ ከህጋዊው ንግድ "እየበለጠ ሄዷል" የሚሉ ብዙ ናቸው። ለዚህ አስቃቂ ብሄራዊ ምዝበራ ተጠያቂው የህወሓት/እህአዴግ የበላይ አመራር ነው። የግሉ ክፍል ብቻ ሊሆን አይችልም። ሙስና፤ አድልዎ፤ ጉቦ፤ ስርቆት፤ የኮንትራባንድ ገበያ፤ የአየር-በአየር ንግድ፤ በይፋ የሚሰራበት አገር ውጤቱ ምን ሊሆን ይችላል ብለን ብንጠይቅ የምናገኘው መልስ አለ። ደሃነት፤ ረሃብ፤ የኑሮ ውድነት፤ ስራ አጥነት፤ ጥገኝነት፤ የሞራል ውድመት፤ ስደት፤ እርጋታ ማጣት፤ ወዘተ ይባላሉ። ለእነዚህ ሁሉ ተጠያቂ ገዢው ፓርቲ ብቻ አይደለም። ሁላችንም ነን። እኛስ ምን እያደረግን ነው ብለን መጠየቅ የዜግነት ግዴታ ሆኗል።

አከራካሪው ህብረተሰቡ ይህን ሸክም ይዞ እስከ መቼ ይቆያል የሚለው ነው። አገር ወዳዶች፤ የውጭ የሠብአዊ መብቶች ድርጅቶችና ሌሎች ሊሰሩት የሚችሉት አለ። ይህም፤ የገዢውን ፓርቲ የበላዮች ለዓለም ሕዝብ ያለመሰልቸት ማጋለጥ፤ ማዋረድና ለፍርድ ማቅረብ። ለጋሶች እርዳታቸውን ከሠብአዊ መብቶች ጋር እንዲያይዙ ጫና ማድረግ ወዘተ ይገኙበታል። ከሁሉም በላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ የኢኮኖሚና የተፈጥሮ ሃብት ባለቤትነቱን መብት ለማስከበር በመተባበርና በድፍረት መነሳት አለበት።

15. የእርሻ ዘመናዊነት ብቻውን የአብዛኛውን ሕዝብ ኑሮ አያሻሽልም

የእርሻ ምርት ዘመናዊ መሆን አለብት የሚለው አያከራክርም። ሆኖም፤ እርሻ ብቻውን በፍጥነት የጨመረውንና የሚጨምረውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ህይወት አይደግፍም። አገሪቱ ከእርሻ ዘመን ወደ ፋብሪካና ኢንዱስትሪ ዘመን መሸጋገር አለባት። ኢትዮጵያ ዘመናዊ የሆነ፤ በእቅድ የሚመራ፤ አገር ወለድ የሆነ፤ ኢትዮጵያውያን ባለቤትና አዛዥ የሆኑበት፤ በተቻለ መጠን ከእርሻ ጋር የተያያዘ የኢንዱስትሪ ፖሊሲ ያስፈልጋታል። (Ethiopia needs to initiate a nationally-oriented and urban-based manufacturing and services industry that will make it competitive with the rest of the world and enable it to meet domestic demand). አደገኛ ሆኖ ያገኘነው የገዢው ፓርቲ የኢንዱስትሪ ዘመናዊነት ፖሊሲ "በግብዣ ይቻላል" ብሎ ማመኑና የአገሪቱን የኢንዱስትሪና የማኒፋክቸሪንግ ምሰሶዎች ለውጭ ኩባንያዎች ማስርከቡ ነው። ይህን በመኮረኘር፤ ሰደተኛው አገሪቱን "በጉብኝት" አሳድጋለሁ ከሚል አዙሪኝ ውስጥ ገብቷል። ይህ አደገኛ፤ ጥገኛ፤ ፀረ- አገር ወለድ ካፒታሊስት ፖሊሲ ነው። አገር ወዳዶች ይህን ፖሊሲ እንደማይቀበሉ ድምጽ ማሰማት አለባቸው። በአገር ወዳድ መንግሥት የሚመራ ካፒታሊዝም እድልና መካከለኛ መደብ ፈጣሪ፤ የሡብአዊ እድገት አጎልማሽ፤ የምርት ኃይሎችን ያለ ገደብ አጠናካሪ መሆኑን እንገነዘባለን። የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት ከዚህ የተለየ ፖሊሲ ይከተላል። በፍጥነት በመለወጥ ላይ የሚገኙ የአፊርካ አገሮች ለወጣቱ ትውልድ የዘመናዊ መገናኛ ቴክኖሎጂ ጥቅም አቅራቢዎች ሆነዋል። ነጻነት ያለው የኬንያ ወጣት ይህን ቴክኖሎጂ ለኢንዱስትሪ እየተጠቀመበት ነው። ዛሬ ናይሮቢ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ምርምርና ሰፊ አጠቃቀም ከሚካሄድባቸው ከተማዎች መካከል አንዷ ሆናለች። ማይክሮሶፍት፤ ጉግል፤ አይቢኤም፤ ኦሬንጅ፤ ባኢዱና ሌሎች የደገፏቸው ኬንያዊ የሆኑ ተቋሞች ተስፋፍተዋል። አይቢኤም ህይወት ለዋጭ ቴክኖሎጂ በመጠቀም፤ ስድስት ሽህ በኬንያ ሸለቆ የሚኖሩ ነዋሪዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ብሮድባንድ ተጠቅመው ዘመናዊ መገናኛ እንዲያገኙ በማድረግ ላይ ይገኛል። እነዚህ ቴክኖሎጂዎች ለብዙ ሽህ ወጣቶች ስራ ፈጥረዋል።

የዘመናዊ መገናኛ ቴክኖሎጂ መስፋፋት፤ ለገጠሩ ስራ ፈላጊ፤ በተለይ ለወጣቱ፤ አዲስ እድል እየፈጠረ ነው። እአአ በ 2002፤ የአፍሪካ ሁለተኛ ደረጃ ትምኅርት ያጠናቀቀው ትውልድ ብዛት ሰላሳ ሁለት በመቶ ነበር። ከኢትዮጵያ የበለጠ ማለት ነው። በ 2020 ቁጥሩ ወደ አርባ ስምንት በመቶ ያድጋል። እያደገ ሲሄድ የስራ እድል መፈጠር አለበት። በኬንያ፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ፤ ይህ ቴክኖሎጂ ከአገሪቱ ጠቅላላ ገቢ ሰላስ አራት በመቶ እንደሚሆን ይታሰባል። የኬንያ መገናኛ ሚኒስተር ቴክኖሎጂው የገጠሩን ኢኮኖሚ ወደ ዘመናዊ ኢኮኖሚ እንደሚለውጠው ተናግሯል። ሌላው ከዚህ በፊት ከዘመናዊው ኢኮኖሚ ጋር ያልተያያዙ አንስተኛ የምርትና የአገልሎት ድርጅቶች ከዘመናዊው ኢኮኖሚ ጋር እንዲቆላለፉ እያደረገ ነው። ህወሓት/ኢህአዴግ በዘመናዊ መገናኛ ቴክኖሎጂ ላይ የሚያደርገው አፈና ለወጣቱ ትውልድ፤ ለገጠሩ ሕዝብ፤ ለአንስተኛ ድርጅቶችና ለግል ክፍሉ ኢኮኖሚው በፍጥነት ማደግ ማነቆ ሆኗል። ገዢው ፓርቲ እስካሁን የተከተለው የኢንዱስትሪ ፖሊሲ"አገር ወዳድ" ነው የሚለውን መስፈርት አያሟላም። ያሳየው የኢኮኖሚ አመራር ለአሳታፊና ለአገር ወለድ ልማት ማነቆ ሆኗል። የገዢው ፓርቲ ትኩረት ከራሱና ከታማኞቹ ላይ መሆኑ ማቆም አለበት። 90/

ባጭሩ፤ የገዢው ፓርቲ ካፒታሊዝም የፖለቲካ የበላዮች (Political Elites) አገልጋይ ነው። የዓለማቀፋዊነትን ጥቅም እንጅ ጉዳት አያይም። ከዓለም አቀፋዊነት ኢኮኖሚ ተጠቃሚ ሆኗል። አገር ወዳድ የሆነ መንግሥት ካልመራው፤ ዓለም አቀፋዊነት፤ የተዛባ ኢኮኖሚና የተዛባ ማህበረሰብ ይፈጥራል። አገር ወለድ የሆነውን ክፍል ይጫነዋል። አንዳዶቹን ያጠፋቸዋል። ዛሬ በኢትዮጵያ እንደምናየው ማለት ነው። የመንግሥት አመራር አገር ወዳድ ሲሆን፤ አለምአቀፋዊነት የሚያመጣውን አደጋ ይከላከላል። አገር ውስጥ ለሚጥሩ ግለሰቦችና ኩባንያዎች የታከስ፤ የፈቃድ ወዘተ አድልዎ ያደርጋል። የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ ራሱን አገልጋይ ነው። አገሪቱና ህብረተሰቡ የገጠማቸውንና የሚገጥማቸውን አደጋዎች በፖሊስ ለመቋቋም ብቃትና ፈቃደኛነት አላሳየም። የምርት ሃይል ምሰሶዎችንና የመሬት ነጠቃን ታሪክ ስናይ ገዢው ፓርቲ ብሄራዊ የሆነ የኢኮኖሚ ፖሊሲ የለውም። ስለዚህ፤ ወጣቱ ትውልድና አገር ወዳዶች አገዛዙ እንዲሻሻል፤ ካልተሻሻለ እንዲለወጥ ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ አለባቸው። 97/

16. መሰረተ ልማት አስፈላጊ ነው

የልማት ባለሙያዎች የመጓጓዣ፤ የዘመናዊ መገናኛና የሡብአዊ ልማት ኢንቬስትሜንት ለቀጣይ እድገት አስፈላጊ ነው ይላሉ። በእኛ ግምት፤ ከሌሎች የእድገት ዘርፎች የበለጠ፤ ገዢው ፓርቲ በመንገድ፤ በድልድይ፤ በግድብ፤ በትምኅርት፤ በጤና ያደረገው ጥረት የሚያስመሰግን ነው። ጥረቱን እንደግፋለን። ኢትዮጵያ አሁንም የመሰረት ልማት (Physical and Social Infrastructure Investments) ሰፋትና ጥራት ያለው ኢንቬስትመንት ያስፈልጋታል። ይህ ኢንቬስትመንት ከምርት ሃይሎችና ከህብረተሰብ አገልግሎት፤ ከኑሮ መሻሻል ጋር ከተያያዙ፤ አዲስና ዘመናዊ ኢትዮጵያ እንደምትፈጠር አንጠራጠርም። ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ሙብቷን ተጠቅማ በወንዞቿ ላይ የምታደርገው ጥረት--

ለምሳሌ የአባይ ሕዳሴ ግድብ፤ የጊቤ ግድብ ወዘተ ኢንቬስትመንት ግዙፍ ስለሆኑ--የአረብ አገሮች ጥረቷን ለማቆም እንደሚሞከሩ አንጠራጠርም። በ February 27, 2013, የሳውዲ መንግሥት ለአረብ አገሮች፤ በተለይ ለግብጽና ለሰሜን ሱዳን ጠበቃ በመሆን፤ የአባይ ግድብ የግብጽን ህልውና አደጋ ውስጥ አስገብቷል ብሏል። ይህ ተደጋጋሚ የሆነ የሚመጣ አደጋ ምልክት ነው። "የኢትዮጵያ መንግሥት አላማ የፖለቲካ ነው። የኢኮኖሚ ልማት አይደለም" ያለው ከእውነቱ የራቀና የጦርነት አዋጅ ይመስላል። ኢትዮጵያ ዓባይን የማልማት መብት አላት። ህወሓት ለፖልቲካ ስልጣን አይጠቀምበትም ማለት አይደለም፤ ይጠቀምበታል። በዚህ መጽሃፍ እንዳሳየነው፤ ቀደም ሲል፤ የሳውዲ መንግስት በእርሻ ኢንቬስትመንት፤ በሃይማኖት፤ በንግድና ሌላ ወደ ኢትዮጵያ የገባው የአረቦችን ዘላቂ ጥቅም ለማስከበር ነው። የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሃብት፤ በተለይ የእርሻ መሬትና ውሃ ለመቆጣጠር ነው ያልነውን ያጠናክራል። ኢትዮጵያ ወንዞቿንና ጅረቶቿን ለራሷ ደህንነት፤ ዘመናዊነትና ለሕዝቧ እድገት የመጠቀም መብት አላት። አጼ አምደጽዮን፤ አጼ ላሊበላ፤ አጼ ገላውዲዎስና ሌሎች ለኢትዮጲያ ጥቅም ዓባይን መጠቀም "መብታችን ነው" ያሉትን ስኬታም ማድረግ የኢትዮጵያዊነት መስፈርት ነው። ኢትዮጵያ ያለፈውን የቅኝ ገዥዎች ፖሊሲ መከተል የለባትም። በየቦታው የሚደረጉ የወንዞች ግድቦች ለአገሪቱ ልማት ወሳኝ ናቸው። የአካባቢና የማህበረሰብ ዘላቂነትና ጥቅም እስከጠበቁ ድረስ ማንም የኢትዮጵያ መንግስት ቢሰራቸው እንደግፋቸዋለን።

የእድገት መሰረት ነው ብለን ያቀረብነው መሰረተ ሃሳብ፤ የመንግሥት ተቀዳሚ የእድገት ስራ የሕዝቡን የምግብ ፍላጎት ዋስትና ስኬታማ ማድረግ ነው። ይህን ለማድረግ የመስኖ እርሻ መስፋፋት አለበት። ከዚህ ሌላ የመብራት ሃይል ለኢንዱስትሪ ድጋፍ እንዲሰጥ፤ ለከተማና ለገጠሩ ሕዝብ የመብራት አገልግሎት ስርጭት እንዲውል ማድረግ ተገቢ ነው። ሰማንያ አምስት በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ምህደር የመብራት አገልግሎት የለውም። ሰማንያ በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ የኤሌክተሪክ አገልግሎት አያውቅም። የመንግሥት ተቀዳሚ ሃላፊነት እነዚህን ፍላጎቶች ማሟላት ነው። በእኛ ግምት ገዢው ፓርቲ የሕዝብን ድጋፍ የሚያገኘው ለውጭ ምንዛሬ ትኩረት በመስጠት አይደለም። ትኩረቱ መሆን ያለበት የአገሪቱን የምርት ሃይል ማሳደግ፤ የሕዝቡን ፍላጎት ማሟላት፤ ኢንዱስትሪን ማስፋፋትና ሰብ አዊ መብቶችን ማክበር ነው። ብሄራዊ አንድነት በባዶው ስኬታማ አይሆንም። የገዢው ፓርቲ የውጭ ምንዛሬ ታሪክ አሳፋሪ ነው። የመብራት ኃይልን ለውጭ ምንዛሬ ብቻ ማዋል አደጋ አለው። አብዛኛው የውጭ ምንዛሬ ለሙስናና ህገወጥ በሆነ መንገድ ለሚሸሽ የሃብት ምዝበራ ውሏል። ሌላው ለአፈና መሳሪያ መግዣ ውሏል። የውጭ ምንዛሬ ሚናው የአገሪቱን የምርት ኃይል ለማሳደግ መሆን አለበት። ኢትዮጵያ ጠንካራ ከሆነች ማንም የውጭ ሃይል አይፈታተናትም። ኢትዮጵያውያን ከኃይል ማመንጫ የሚገኘው የውጭ ምንዛሬ ለህብረተሰቡ ጥቅምና አገልግሎት እንዲውል መከታተል ይኖርባቸውል። በተጨማሪ የሚሰሩ ግድቦች ሁሉ የነዋሪዎችንና የአካባቢውን ደህንነት ጠብቀው በእቅድ እንዲሰሩ መከታተል ይገባቸዋል። እነዚህ ሁሉ ማህበረሰቡን ሊሰበስቡ የሚችሉ ህይወት ለዋጭ ግቦች ናቸው።

በዓባይ ግድብ ላይ የተለያዩ ሃሳቦች እንዳሉ እናውቃለን። የአገር ወዳዶች አቋም የማያወላውል መሆን አለበት። ኢትዮጵያ ወንዞቿንና ጅረቶቿን ገድባ የራሷን ሕዝብ ከደሃነት፤ ከረሃብና ከስራ አጥነት ነጻ ማውጣት መብቷ ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት በህወሓት/ኢህአዴግ ስለሚመራ ብቻ መቃወም ስህተት ነው። የአባይን ግድብ ለመስራት እቅድ ያወጣው የአሁኑ ገዢ ፓርቲ አይደለም። አላማው በአጼ ላሊበላ/በአጼ አምደጽዮን ወዘተ የጀመረ ሆኖ፤ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ሰፊ ጥናት የተደረገበት ፕሮጀክት ነው። ደርግ የጣና በለስን የመሰረተው ይኬን መብት ተጠቅሞ ነው። መቃወም ፀረ-ብሄራዊነት ነው። በአንድ በኩል ገዢውን ፓርቲ የባህር በሯን ዘግቷል፤ ማስመለስ ብሄራዊ ግዴታው ነው እንላለን። በሌላ በኩል "ሃውልት" የሚሆኑ አገሪቱንና ሕዝቧን በጋራ የሚያገለግሉ ፕሮጀክቶችን እንቃወማለን። ይህ የሚያስታውሰን የሶማሌ ወረራ ጊዜ "መንግስቱ ሃይለ ማሪያምን ስለምንቃወም የሶማሌን ወረራ እንደግፋለን" የሚለውን ተቃዋሚ ታሪክ ነው። ኢትዮጵያውያን፤ አረቦች በኢትዮጵያ የውስጥ ፖለቲካና ልማት ውስጥ ጣልቃ መግባታቸውን ሙሉ በሙሉ መቃወም ብሄራዊ ግዴታቸው ነው። ይህ መንግሥት ያልፋል። አገርና ለአገር የተሰሩ ሃውልቶች ዘላለማዊ ናቸው። ህወሓት/ኢህአዴግ የሚሰራውን ሁሉ መቃወም ተገቢ አይደለም። ብዙ የምንቃወማቸው ፖሊሲዎች እንዳሉ በዚህ መጽሃፍ አሳይተናል። መግፋት ያለብን፤ ገዢው ፓርቲ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ በሩን ክፍት እንዲያደርግ ነው። ይህን ካደረገ የአረቦች ዛቻ ኢትዮጵያዊውያንን ሊያስፈራ አይችልም። ኢትዮጵያ አትፈራርስም። 98/

17. በሃይማኖት ላይ ያለው አፈናና ሰቆቃ ይቁም

የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት ለልማት መሰረት ነው። የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖት መሪዎችና ተከታዮች ለደረሰባቸው አፈና ድምጽ እያሰሙ ነው። ገዢው ፓርቲ የቀረጸው ከፋፍለህ ግዛው በራሱ ላይ አደጋዎችን እያመጣበት ነው። ቀድም ሲል በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን ተቋምና ተከታዮች ላይ ጫናና ናዳ አድርጓል። በእስልምና ሃይማኖት ላይ አፈና መጀመሩ የኃይማኖት ነጻነት ጠላትነቱን አስምሮበታል። ይህን ስንል፤ ከኃይማኖት ጀርባ ኢትዮጵያን

ለመፈታተን፤ ሕዝቡን ለማጋጨት፤ አገሪቱንና የተፈጥሮ ሃብቷን ለመቆጣጠር የሚፈልጉ ሃይሎች የሉም ማለታችን አይደለም። አሉ። የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖቶች በሰላም፤ በእኩልነት፤ በኢትዮጵያዊነት አብረው መኖር መብታቸው ነው። መንግሥት እነዚህን ሃይማኖቶች በስልት፤ በመቻቻል፤ በራሳቸው የውስጥ አመራር መብታቸው ተከብሮ አገራቸውን እንዲጠብቁና ተባብረው በሁሉም አገር ወለድ የልማት ዘርፎችና በመንፈሳዊ እድገት ላይ እንዲያተኩሩ ጥረት ማድረግ አለበት። ኃይማኖትን ለፖለቲካ ስልጣን መጠቀም በክብሪት እንደ መጫወት ነው። ዞሮ፤ ዞሮ፤ ገዢውን ፓርቲ "ያቃጥለዋል።"

18. የአገዛዝ ክፍተት (The Governance gap)

የህወሓት/ኢህአዴግ መስራቾች የመረጡት አገዛዝ ከሌሎች የተለየ መሆኑን አሳይተናል። ጎሳ-ተኮር ፌደራሊዝም፤ ጎሳ-ተኮር የኢኮኖሚ፤ በአምባ ገነንነት የሚመራ "ልማታዊ መንግሥት"፤ የማህበረሰብና የፖለቲካ የበላይነት ባህል ፈጥሯል። ምእራባውያን፤ በተለይ አሜሪካ፤ እንግሊዝ፤ የአውሮፓ የጋራ ማህበር፤ ካናዳ፤ዓለም አቀፍ ለጋስና አበዳሪ ድርጂቶችና የግለሰቦች ተቋሞች፤ እንደ ቢል ጌትስ፤ ክሊንቶን፤ ሳክስ፤ ስቲግሊትዝ፤ ብሌር ያሉት ለገዢው ፓርቲ ከፍተኛ ገንዘብና ምክር ለግሰውታል። ከምስጋና ጋር። እንደመለገሳቸው መጠን መንግሥት የሚያቀርበውን የሂሳብ ፈሰስ ተቀብለውታል። ተጠቃሚውን ሳይጠይቁ፤መረጃውን ሳይመረምሩ ወዘተ። አምባገነናዊ የልማት መንግሥት ማስረጃ ፈጣሪ ነው፤ ሕዝቡን አያማክርም፤ ተሳትፎውን አይፈቅድም። "እኛ እናውቅልሃለን" የሚል አመራር ይከተላል። ለጋሶች አስደናቂ ለውጥ ይታያል የሚሉበት ዋና ምክንያት ገንዘባቸውና ምክራቸው ውጤት እንዳስገኘ ለማመልከት ነው። አይፈረድባቸውም። <u>የኢትዮጵያን ሕዝብ ጎጅ ሆኖ ያገኘነው ከገንዘባቸው መባከን በላይ ምክራቸው በማህበረሰቡ ህይወት ላይ ያተኮረ፤ ለግለሰቦች ነጻነት፤ ጉልመሳ፤ መብትና ተሳትፎ ትኩረት ያልሰጠ መሆኑ ነው።</u> የታወቀው የሰብአዊ መብት ተቋም፤ Human Rights Watch, "Development without Freedom" በሚል አርእስት ያቀረበው። ነጻነትና የሰብአዊ መብቶች ሲገፈፉና ሲታፈኑ ተጠቃሚው የመደራደርና ራሱን የማሻሻል አቅሙ ፍጹም በሆነ ደረጃ ይበከላል። "መሬቴን አትውሰዱ፤ ምግብ፤ ምርጥ ዘር፤ ማዳበሪያ ወዘተ በታማኝነት መስፈርት መስጠታችሁን አቁሙ፤ የመምረጥ መብቴን አትከልክሉ፤ ጉቦና ሙስናን አቁሙ ወዘተ" ለማለት አይችልም።

ቢል ኢስተርሊ የተባለው በዓለም ከታወቁት የመልካም አገዛዝና የልማት ልሂቃን የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘው (በኔ አመለካከት) ፕሮፌሰር በቅርቡ ባወጣው መጽሃፉ ስለጭቆናና ልማት እንዲህ ብሏል። "Oppression has broad consequences that hold back development. It promotes a lack of trust that inhibits trade and facilitates more oppression. It entrenches a <u>hereditary political and economic elite</u> that blocks the creative destruction necessary for development. Oppressive rules underinvest in public goods for the majority. This last point will bear on the question raised by the contemporary Ethiopia story on whether autocrats are usually good at reducing child mortality" and, we add overall poverty by raising employment and productivity. የግለሰቦችና የስብስቦች የነጻነትና የሰብአዊ መብቶች ጭቆናና አፈና በመንግሥት ላይ ያለውን እምነት እንደሚያፈርስ ደጋግመን አይተናል። ሕጉና ደንቡ ያጠናከረው የጥቂቶችን የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነትና ጥቅም ነው። ኢስተርሊ ይኼን ሰብሳቢና ወሳኝ የአቅጣጫ ሃሳብ ያቀረበበት ምክንያት ለጋሶች ከራሳቸው ጥቅም አንጻር ብቻ አይተው ደሃነትን በመቀነስ ሰበብ የፈጸሙትን ስህተት አጉልቶ በማስረጃ ለማሳየት ነው። ለምሳሌ፤ የቀድሞው የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚንስትር ቶኒ ብሌር በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን አፈና እያየ ለመለስ ዜናዊ ከፍተኛ አድናቆትና ድጋፍ ሰጥቶ ነበር። ድጋፉን ለማጠናከርና መለስና የሚመራው መንግሥት በዓለም ደረጃ እውቅና እንዲያገኝ የአፍሪካ ኮሚሽን የሚል ተቋም መሰረተ፤ መለስ አባል እንዲሆን አደረገ። መለስ ከሌሎች ጋር ሆኖ የአፍሪካ ኮሚሽን ሪፖርት እንዲጻፍ ተደረገ። የሪፖርቱ ዋና ትኩረት የውጭ እርዳታ ደሃነትን ለማጥፋትና ዘላቂና ፍትሃዊ እድገት ለመመስረት አስፈላጊና ጠቃሚ መሆኑን አሰመረበት። The Report "allowed Meles to praise himself with sentences such as how "more and better  foreign aid can support positive changes." It asserted that aid to Ethiopia-- that soon became the darling of the donor community—had enabled the country to make "encouraging progress" and that "social progress" (such as reduction in child mortality, maternal care, HIV/AIDS etc "has been good." This justified the "doubling of aid to Ethiopia over the next five years." Meles was able to achieve this goal before he died. 99/

ይኼ ምእራባውያን ምስጋና ያፈሰሱለት ልማት ለነጻነትና ለሰብአዊ መብቶች መከበር አስፈላጊነት ምንም ቦታ አልሰጠም። የኢትዮጵያ ሕዝብ እርዳታ እስካገኘ ድረስ ልማታዊውን መንግሥት መደገፉ አይቀርም በሚል ስሌት። "The idea of a benevolent autocrat" (Meles can hardly fit this descrption; he was a dictator)

implementing expert advice (the World Bank, IMF, Blair, Stigliz, Sachs, Gates and numerous others offered ad-infinitum) to achieve great results in Ethiopia was already in place in 2005...But Meles was about to demonstrate the weak spot of the benevolent autocrat idea---a ruler with no checks on his powers is likely to abuse individual rights." በሁሉም የእድገት ዘርፎች አስደናቂ ውጤት ታይቷል የሚለው የገዢው ፓርቲና የለጋሶች ድምዳሜ በዓለም ገበያ እንዲውል ተደረገ። መለስ እና ጓደኞቹ ዓለም ያደነቀው እድገት ባጭር ጊዜ ለማሳየት ከቻልን አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተደስቷል ማለት ነው፤ ኢህአዴግ በነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ሊሸነፍ አይችልም ወደሚል ድምዳሜ ተደረሰ። የዘጠና ሰባቱ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ የሕዝብን ጭንቀትና ብሶት በጥልቀት ባለማወቅ ተካሄደ፤ ህወሓት/ኢህአዴግ ተሸነፈ። ሕዝቡ በራሱ ድምፅ ነጻነትን፤ የሙብት መከበርንና ዲሞክራሲን እንደሚፈልግ በጅምላ አሳየ። "Meles may have believed his popularity was sufficient for him to win a free election. Instead, discontent with Meles was so great that the election gave the opposition (ቅንጅትና ህብረት) surprising victories." ከዚህ በኋላ የሆነውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ያውቃል። መሸነፉን ሲያውቅ፤ መለስ የምርጫውን ውጤት ቀለበሰ፤ የቅንጅትን መሪዎች አሰረ። "In response Meles manipulated the vote count to produce a victory for his own party. When student demonstrators took to the streets to protest, Meles' Security forces opened fire, resulting in more than 100 deaths." 100/

ቁም ነገሩ አምባገነኑ መንግሥት የፈጸመው ወንጀል ብቻ አይደለም። አቅሙን ያጎለመሱትና ድፍረት የሰጡት ለጋሶች (የአሜሪካ፤ የእንግሊዝ፤ የዓለም ባንክ፤ የአይኤም ኤፍና ሌሎች ባለስልጣናት እንደዚህ ያለ የንጹህ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ደም ሲፈስና ከአርባ ሺህ በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ሲታሰሩ ምን አደረጉ፤ የወደፊት እርዳታቸው ከነጻነት፤ ሰብአዊ መብቶች መከበርና ከዲሞክራሳዊ አገዛዝ አማራጭ ጋር እንዲያያዝ አደረጉ? አላደረጉም፤ እንዲያውም ሁኔታዎች ተባብሰዋል። ለይስሙላ ጩኸት አሰምተዋል። እርዳታቸውን ጨምረዋል። "The donors made some cosmetic changes...they would direct the aid to local governments rather than to the discredited national government." ከላይ እርሻን በተመለከተ እንዳሳየነው ለክልሎች ይሰጥ የተባለው እርዳታ ትርጉመ ቢስ ሆኗል። ክልሎቹን ከላይ ሆኖ የሚቆጣጠራቸውና የሚያዛቸው ህወሓት የሚመራው ማእከላዊ መንግሥት ነው። በኢስተርሊ አባባል "This tactic (channeling aid to regional governments) overlooked the reality obvious to everyone—that the national government controlled local governments...Aid was eventually redirected back to unrestricted transfers to the budget of the national government" that distributes it as it wishes. አሁንም እንዳለፈው የለጋሶቹ ሃላፊነት ለራሳቸውና ለገዢው ፓርቲ ሆነ። የሰብአዊ መብት ድርጅቶች በተደጋጋሚ ያቀረቡት ማስረጃ፤ ማለትም፤ገዢው ፓርቲ እርዳታን መቀጣጫና ታማኝነት መግዢያ አድርጎታል የሚለው ሂስ ዋጋ ቢስ ሆነ። አንድ የዓለም ባንክ ኢኮኖሚስት ስለ ኢትዮጵያና የለጋሶች ሚና ስጠይቀው ታዝቦ "ስሜን እንዳትጠቅስ እንጅ እኛም የምናደርገው አገሪቱን ከደሃነትና ከኋላ ቀርነት ነጻ የሚያወጣ አይደለም። ይኬ መንግሥት እንደ ቻይና ወይንም ቬትናም አይደለም። የምናገለግለው የኢትዮጵያን ሕዝብ በሙሉ የሚወክል መንግሥት አይደለም። የጎሳዎች ስብስብ፤በተለይ የትግራይ ነጻ አውጭ የበላዮችን ነው" ብሏል። ዊኪ ሊክና ኢስተርሊ የሚሉት ተመሳሳይ ነው፤ የውጭ እርዳታ ጥንካሬ የሰጠው ለአንድ ፓርቲ አምባገነናዊ መንግሥትና ስርዓት ነው። ለጋሶች የኢትዮጵያ ሕዝብ በመታፈኑ፤ብዙ ሺህ ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ እስረኞች በመሆናቸው ወዘተ የረባ ጩኸት አላሳዩም፤ ወደፊትም ሁኔታው ካልተባባሰ አያሳዩም። "Not even shooting and jailing the opposition, manipulating aid to starve the opposition, seizing the lands of villagers and relocating them against their will, and perpetrating violenence against villagers who protested has been enough to shake the technocratic faith that autocrats can be trusted to be benevolent implementors of technical solutions." 101/

በማንኛውም መስፈርት ስንመረምረው ለጋሶችና የእነሱ አማካሪዎች ነጻነት፤ የሰብአዊ መብት መከበርና ሁሉን የሚወክል መንግሥት ወይንም ዲሞክራሲ የሚባለው መመስረት ከዘላቂና ፍትሃዊ እድገት ጋር ያለውን ቀጥተኛ ግንኙነት ትኩረት አልሰጡትም። የራሳቸው እሴትና ልምድ እርዳታቸው ከእነዚህ ወሳኝ እሴቶች ጋር እንዲያያዝ ቢያመለክትም፤ የአጭር ጊዜ ጥቅማቸው የረዢም ጊዜውን የፍትህ ጥያቄ አፍኖታል ወይንም በርዞታል ለማለት እገደዳለሁ። በጣም የሚዘገንነው ደሃነትን አጥፍቶ የመካከለኛ ገቢ ደረጃ ማድረስ ዋናው ራእዩ የሆነው የዓለም ባንክ ፕሬዝደንት ጅም ኪም "ኢትዮጵያ አስደናቂ ተሃድሶ እየተቀዳጀች ነው። ይኼም የሆነባቸው ምክንያቶች አግባብ ያላቸው ፖሊሲዎች፤ የረጂም ጊዜ አመለካከት ያለው የረጋና ሕብረተሰቡን አገልጋይ የሆነ መንግሥት ስላላት ነው" ያለው ከሃቁ የራቀ ነው። ለሃገሪቱ የረዢም ጊዜ ጥቅም የቆመ መንግሥት በየቀኑ ተቃዋሚ አያስርም፤ የተማረውና የሰለጠነው የሰው ኃይል እንዲሰደድ አያመቻችም፤ ድርጂታዊ ጉቦ፤ አድልዎና ሙስና አያካሂድም፤ የግል ክፍሉን አያፍንም ወዘተ። ምንም አስተማማኝ መዝገብ በሌለባት ኢትዮጵያ በያመቱ የሚወለዱ ህፃናትን ቁጥር መደብ በማድረግ፤ በ2010 የተባበሩት መንግሥታት

የገመተው በህይወት ከተወለዱት መካከል አምስት አመት ሳይሞላቸው 106 ህጻናት ከ1000 ይሞታሉ። የመንግሥትን ታማኝነት የሌለው ሂሳብ የተቀበለው ቢል ጌትስ፤ ከአንድ ሺህ ሰማኒያ አንድ ብቻ ይሞታሉ ብሏል። በሁለቱ ዘገባዎች መካከል ያለው ልዩነት ሰፊ ነው። በኢትዮጵያ የዚህ አይነት በእድገት ሂሳብ ማምታታት የተለመደ ሆኗል። ለጋሶቹ ልክ በአንድ ድምፅ የሚናገሩ ይመስላሉ። ድምፅ የሌለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ሁሉም ለነጻነት ዋጋ አልሰጡም፤ ዓለም ባንክ በፖለቲካ ጣልቃ አልገባም በሚል ጊዜ ያለፈበት ታሪክ የአፍሪካን፤ በተለይ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጎድቷል። በኔ ግምት፤ እርዳታ ፖለቲካና የፖለቲካ መሳሪያ ነው፤ ህወሓት ደርግ ያላገኘውን እርዳታ አግኝቷል፤ የፖለቲካ ውሳኔ ያበረከተው በረከት።

የዓለም ባንክ ፕሬዝደንት ኪም ልምዱን የተዋሰው ከበፊቶቹ የዓለም ባንክ ፕሬዝደንቶች ነው። ለኢትዮጵያ ከሚለግሱ ድርጅቶች መካከል የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘው ተቋም፤ "Public Sector Capacity Building" በተባለው ፕሮግራሙ የኢትዮጵያ መንግሥት "ለዲሞራሳዊ ውክልና፤ ለሰብአዊ መብቶች መከበር፤ ለሕግ የበላይነት፤ ለእርቅና ሰላም" ቃል ገብቷል በሚል ብዙ ሚልዮን ዶላር ፈሰስ አድርጎ ነበር። ይኼ በሆነበት ሁለት ወር ሳይሞላ፤ በJuly, 2012, የታወቀው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ስለ አረቦች የፀደይ አብዮት ስለ ፃፈ ታሰረ፤ የአስራ ስምንት ዓመት የእስራት ፍርድ ተፈረደበት። የዓለም ባንክ ፕሬዝደንት ሮበርት ዞሊክ "ለምን ታሰረ፤ ይፈታ" ብሎ ድምፅ አላሰማም። ባንኩ በሚጽፈውና በሚሰራው መካከል ምንም ግንኙነት አለመኖሩን አሳየ። የኢትዮጵያ መንግሥት ሰብአዊ መብቶችን ለማክበር ቃል ከገባ ዓለም ባንክ ይኼን መተግበር ግዴታው ነው። "The Ethiopia and Zoellick stories illustrate the authoritarian status quo that still remains in the development community made up of the World Bank, the United Nations, the development efforts of the rich nations, and the professional class of development consultants," foundations such as Gates and Clinton and numerous think-tanks. 102/

ዓለም ባንክና ሌሎች ትኩረት ያልሰጡትን የነጻነት፤ የሰብአዊ መብቶች መከበር፤ የተሳትፎ፤ የዲሞክራሲ ስርዓት ቁልፍነት ሰፊ ጥናት ተደርጎበታል። Human Rights Watch, "Development without Freedom, How Aid Undewrites Repression in Ethiopia, Abuse-Free Development: How the World Bank Should Safeguard Against Human Rights Abuses" are among the most noteworthy fact based assessments of the direct link between freedom, respect for human rights and human wellbeing. እነዚህ ጥናቶች እርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ሊከተሏቸው የሚገባቸውን መስፈርቶች አመልክተው ነበር። ለምሳሌ፤ በጋምቤላ "የአዲስ መንደሮች ሰፈራ" የነዋሪዎቹን ህይወት እንደሚጎዳ፤ እርዳታ በታማኝነት ከተሰጠ ደሃነት እንደማይቀንስ ወዘተ። አበዳሪዎቹ የኢምንት ያክል ቁም ነገር አልሰጡትም። "If you wonder what you can do about global poverty, here is virgin territory for action." ይኼም ማለት፤ ለነጻነትና ለሰብ አዊ መብቶች መከበር ድምፅ እናሰማ። አልያ፤ እርዳታ ቢጎርፍ ደሃነትን፤ መሰደድን፤ ተስፋ መቁረጥን አያስወግድም። እንዲያውም፤ እርዳታው ለባሰ አፈና ያገለግላል፤ ጥገኛነትን ያባብሳል፤ ሙስናን ያጠናክራል። "A 2010 HRW Report subtitled How aid underwrites repression in Ethiopia documented how Meles Zenawi used donor funds to black-mail starving peasants into supporting his regime, denying donor financed food relief to opposition supporters." Donors never uttered the term "No democracy, no aid." Ethiopians who said it are either in jail of have fled. "We can choose not to let our own govermnets and our development agencies forget democracy, not to let them forget rights, not to let them forget Eskinder Nega in Jail." 103/

ነጻነትና የሰብአዊ መብቶች በማይከበርባት ኢትዮጵያ የተዛባ ገቢ፤ ኑሮና የክልሎች ልማት ቢከሰቱ አያስገርምም። ኢትዮጵያ የደሃነት ቅነሳና የእድገት መለማመጃ ሜዳ ሆናለች። ልማት በየመቱ የእድገትን አሃዝ ማሳደግ ብቻ አይደለም፤ የሕብረተሰቡን የማምረትና የአገልግሎት ኃይል አጎልምሶና አስፍቶ ህይወቱን ማሻሻል ነው። ነጻነት ከሌለ ይኼ ሊሆን አይችልም። ሌላው ቀርቶ እውነቱን ለመናገር አይቻልም። "A leading candidate to explain growth (with sustainability and equity, my emphasis) would be the change in freedom. It makes sense to explain the change in development with a change of freedom… China has actually had a strong positive change in both political and economic freedom since the death of Mao and the loss of power by his cronies." Ethiopia is the reverse. Political and economic freedoms are more restricted now than even under Meles. "Chinese citizens today enjoy stronger rights than they did in those dark days." ቻይናን የተለየች የሚያደርጋት ገዢው ፓርቲና አመራሩ አገር ወዳድ፤ ሁሉን አገልጋይ፤ ችሎታ ያለው፤ የውጭ እርዳታን ያላባከነ፤ የግል ክፍሉን ያሳደገ ስለሆነ ነው። የቻይና የግብርና ስራ የሚሰራው በግለሰብ ቤተሰቦችና ዝቅተኛ አምራቾ ነው። ደሃነታቸው ለልማት ማነቆ አልሆነም፤ መንግሥታቸው ምርት እንዲያሳድጉ አጎልምሷቸዋል። የኢትዮጵያ ከዚህ

የተለየ ነው፤ ገበሬው ታዛገር እንዲሆን ተገዷል። ስለሆነም፤ ለውጥ አስፈላጊ ነው። ለውጥ ያለ ሕዝብ ትግል አይመጣም። “When autocrats make moves toward increased political freedom, we often see this happening under pressure from protest movements (as indeed it often is).” ዋናው መልእክት አምባገነኖች ለፖለቲካና ለኢኮኖሚ ነጻነት ለስለስ የሚሉት በሕዝብ አመፅ (ሰላማዊ ሰልፍ፤ እገባ ወዘተ) በመሳሰሉ ግፊቶችና ጫናዎች ነው። እስካሁን እንዳየነው የኢትዮጵያ ገዢ ፓርቲ በራሱ ፈቃድ ማንኛውንም መብት አይፈቅድም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለራሱ ህይወትና መብት መታገል ግዴታው ነው። 104/

ከጅምሩ፤ የህወሓት መስራቾች እና የውጭ እርዳታ ሰጭዎች የልማት ስልት ነው ብለው የወሰኑት የፖለቲካ ሂደት፤ ማንኛውም የቅድመ ህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት፤ ልማትና ዘመናዊነት “አፋኝ፤ ግራ-ተኮር፤ ኮሙኒስት፤ አቆርቋዥ፤ ጨቋኝና አደገኛ ነበር” የሚል ነው። እርዳታውን በከፍተኛ ደረጃ ለህወሓት/ኢህአዴግ የለገሱት መንግሥታትና የሚቆጣጠሯቸው ድርጅቶች የተከተሉት ፖሊሲ ከላይ ወደ ታች የሚል፤ ከሕዝቡ ጥቅምን መብት ጋር ያልተያያዘ መሆኑን አሳይተናል። እርዳታ ሰጭዎቹ የፈጠሩት መንግሥት ከአጼ ኃይለ ሥላሴና ከደርግ የባሰ የጠባብ ጎሰኛ ማእከላዊ መንግሥት ነው። የህወሓትን ቡድን የበላይነት ያጠነከረ። የደርግን መንግሥት የተካው ምን ይመስላል ብለን ስንመራመር የምናገኘው “አዲስ አገዛዝ” ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት (natiዲሚክራሳዊ አይደለም። (The ethnic-based struggle led to the formation of an ethnic-state with ethnic elites at the top of the policy and decision-making process...this is what experts call political capture that leads to economic capture). ይኼን ፒራሚድ የሚመስል የጥቂቶች የገቢና የሃብት የበላይነት፤ የመካከለኛው መደብ ለመስፋትና ለመሻሻል አለመቻሉን ወይንም መታፈኑን ያመለክታል። ስር ዓቱ የተፈጠረው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት መመሪያችንና መድረሻችን ናቸው በሚል አይደለም። እነዚህ ፈርሰው በጎሰኛነት የፖለቲካ አመራር መተካት አለባቸው የሚል ነው። የበፊቱም አምባገነናዊ ነው ቢባል፤ የተተካው የጠባብ ጎሰኛ ቡድኖች የበላይነት ነው። “ፀረ-ዲሞክራሲ” የሆነውን ያለፈ ስርአት ለመተካት “የብሄር/ብሄረሰብና ሕዝቦች” ፖለቲካ ፓርቲ የበላይ መሪዎች (Ethnic elites) የተስማሙበት ሶሻሊዝም፤ ኮሙኒዝም፤ ካፒታሊዝም ወዘተ አይደለም። የተመሩበት ትግል የብሄር/ብሄረሰብ/ሕዝቦች ነጻነት ነው። የአገዛዝ አወቃቀሯና የእድገት አመራሩ በብሄር/ቋንቋ ልዩነቶች የተመሰረተ ህገመንግሥትና ነው። ይህ የከፍተኛ ጎሳ-ተኮር መሪዎች ርእዮት ለአባላት ድርጅት መሪዎች የተለየ ጥቅም ፈጥሮላቸዋል። አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ በደሃነት ዓለም መኖር በሰፊው በማስረጃ ተደግፎ ቀርቧል። የገዢውን ፓርቲ መሪዎች የሚያስማማቸው አበይት ጉዳይ አለ። ይህም፤ ብሄራዊ የሆኑ ድርጅቶችንና ግለሰቦችን በመቆጣጠርና ነጻነታቸውንና ሰብአዊ መብታቸውን በማፈን የበላይነቱን መቀጠል የሚል ነው። የዚህ አስከፊ ውጤት፤ ሕብረተሰቡን፤ በተለይ የደሃውን የማምረት፤ ሰራ የማግኘትና ህይወቱን የማሻሻል እድል አፍኖታል። ካስፈለገ ማንኛውንም በሰላም ሆነ በዓመጽ የሚቃወም ግለሰብ ወይንም ስብስብ ሳይለዩ በሃይል መደምሰስ አለብን የሚል ነው። የአፋርን፤ ኦጋዴን፤ አሞና ጋምቤላን ሕዝብ ኑሮ እንደ ማስረጃ በማቅረብ “ለጭቁኖች” መብት ቆሚያለሁ የሚለው ህወሓት/ኢህአዴግ መብታቸውን አፍኗል። የውጭ መንግሥታትና ለጋስ ድርጅቶች አምባገነኑን ስርዓት መደገፋቸው ሁኔታውን አባብሶታል። ስለሆነም፤ የእድገቱ ተጠቃሚ ያልሆነው አብዛኛው የኢትዮጵያ የውስጥም ሆነ የውጭ ተቆርቋሪ የለውም። ለራሱና ለወደፊቱ ትውልድ ህይወትና ጥቅም ሲል ለነጻነትና ለሰብአዊ መብት መታገል ግዴታ ሆኖበታል የሚል መሰረተ ሃሳብ እሰነዝራለሁ። 105/

የዚህ ተከታታይ ውጤት በምርጫ 97 እንደታየው፤ “ብንሸነፍም መሸነፋችን አንቀበልም” የሚል አምባገነናዊነት ነው። ህወሓት/ኢህአዴግ የጎሳ መሪዎች ስብስብ፤ የፓርቲ፤ የመንግሥትና የተቋሞች አንድነት (organic link) የአገዛዙ ስትራተጂ ያደረገበት ዋና ምክንያት ተቀናቃኞችን ለማንበርከክ፤ ብሄራዊ ድርጅቶችና መሪዎች እንዳይኖሩ ለማድረግ ነው። የህወሓት መሪ መለስ በተደጋጋሚ አገር ወዳድ፤ ብሄራዊ፤ ህብረ-ብሄራዊ የሆኑ የተቃዋሚው ክፍል መሪዎችንና ድርጅቶችን ለማጥፋት የቻለው በዚህ አመራር ነው። በተለይ መሪዎችና ሌሎች አስጊ ተቃዋሚዎች ለገዢው ፓርቲ እንዲያጎበድዱ አድርጓል። እስር ካቆየ በኋላ ለመልቀቅ ሲወስን “ይቅርታ እንዲጠይቁ” ያስገድዳቸው ነበር። ይህ ከፉ የአገዛዝ እሴት ሆኖ አግኝተነዋል። ሰብእነታቸውን፤ ክብራቸውን፤ አንደበታቸውንና መንፈሳቸውን ለመስበር ይሞክራል። በዚህ ድርጊት የተሰበሩም አሉ ይባላል። ይህ ኢትዮጵያውያንን፤ በተለይ ብሄራዊ መሪዎችን፤ የማዋረድ ባህል በኢትዮጵያ ላለው አዲስ የፍርሃት ባህል አስተዋጽኦ አድርጓል። በፐሮፌሰር መረራ ጉዲና አባባል፤ “እኛ የኢህአዴግን ጠመንጃ እንፈራለን። ኢህአዴግ ደግሞ 97 ላይ የመጣበትን የሕዝብ ጎርፍ ይፈራል።” ነባራዊ ሁኔታዎች የሚያመለክቱት የኃይሉ ሚዛን ወደ ሕዝብ እንዳመራ ነው። ሆኖም፤ ቀስቃሽ፤ የዓላማ አንድነት፤ ኢትዮጵያውያንን የሚሰበስብ ማእከል፤ ብሄራዊ ድርጅትና አመራር ይጠይቃል።

ለዚህ ለማይቀር የሕዝብ ድል፤ የተቃዋሚው ክፍል መከፋፈል፤ በብሄር/ብሄረሰብ መደራጀት፤ ለፍርሃቱ ባህል ስለባ መሆን--ለጊዜውም ቢሆን-- ገዢውን ፓርቲ አጠንክሮታል። ገዢው ፓርቲ የኢትዮጵያን ሕዝብ አመኔታ፤ ተቀባይነትና

ክብር አግኝቷል ለማለት የሚያስችል ምንም ደጋፊ ማስረጃ አላገኘንም። ይህ ግንዛቤ ወደ ዋናው የፖሊሲ አቅጣጫ ያመራናል። በኢትዮጵያ የሚታየው ዋና የፖለቲካ አደረጃጀትና አመራር ክፍተት አገራዊ የሆነ፤ ለሁሉም የቆመ፤ ብቃት ያለው፤ የፖለቲካ ድርጅትና በጥበብ፤ በዲሞክራሲ፤ የሚዳኝ፤ ለሕዝብ ተገዢ የሆነ የፖለቲካ አደረጃጀትና አመራር አለመኖሩ ነው። አገሪቱን ለአደጋ የዳረጋት የገዢው ፓርቲ ጥንካሬ ብቻ አይደለም። የማህበረሰብ ድርጅቶች በብዛት አለመቋቋምና የተቃዋሚው ክፍል መከፋፈል ዋናዎቹ ናቸው። ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጠቅመው፤ ማንኛውንም ጥቃቅን ልዩነት ወደ ጎን ትቶ፤ ሁሉንም የሚያስተናግድ፤ ለኢትዮጵያና ለመላው ሕዝቧ አጋር፤ እኩልነት፤ መከታ፤ አጎልማሽ፤ ደጀን የሆነና ከታች የተያያዘ ማህበራዊ እንቅስቃሴ (civic organization and movement) ማደራጀት ነው። በሌሎች አገሮች እንዳየነው፤ ከውጭ ያለው አገር ቤት ካሉ ታጋዮች ጋር መቆላለፍ፤ የገንዘብ፤ የቁሳቁስ፤ የሃሳብ፤ የዲፕሎማቲክ ድጋፍ መስጠት አማራጭ የሌለው ወገናዊ ጥሪ ሆኗል። ውጭ ያለው አገር ቤት ያለውን የፍትህ ትግል ሊመራ አይችልም። ውጭ ያለው በእየቀኑ ሊሰራው የሚችል ብዙ ነገር አለ። አላደረገውም።

አፋኝ የሆነ አገዛዝ ፍትህ ፈላጊ ይጠይቃል። ፍትህ የፈለገ ሌላ አማራጭ የለውም። ለፍትህ መታገል አለበት። ሠብአዊ መብት ታፈነ ማለት ብቻ አይበቃም። “መብቴ ተነጥቋል፤ መብቴን ማስከበር የራሴ ግዴታ ነው” ብሎ ከብሄር፤ ከሃይማኖት፤ ከገቢ፤ ከጾታ፤ ከእድሜ ወዘተ በላይ ማሰብን ይጠይቃል። ከአሁን በኋላ፤ ኢትዮጵያውያን ከአምባገነናዊ አገዛዝ ነጻ ለመውጣት ከፈለጉ፤ አንዲት ኢትዮጵያ የምትባል አገር መኖሯን መቀበል አለባቸው። እኩልነትና ፍትህ ከሌለ አንዲት ኢትዮጵያ አትፈጠርም። ሁሉን ብሄር/ብሄረሰቦችና የሃይማኖት ተከታዮች የሚያስተናግድ ለሕዝብ፤ በሕዝብ ተገዢ የሆነ የፖለቲካ አማራጭ ለመመስረት በጋራ መታገል አስፈላጊ ሆኗል። ከአሁን በኋላ፤ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን እኩልነትና ፍትህ ለመታገል ያልቆረጠ ተቃዋሚ አማራጭ ሊሆን አይችልም።

እኛ ለመመለስ የምንፈልገው አንድ የትውልድ ጥያቄ ነው። ይህም፤ “ለመሆኑ እኛ ኢትዮጵያውያን መቸ ይሆን የአገራችን አበይት ችግሮች በመተባበር፤ በመከባበር፤ በእኩልነት፤ በጨዋነት ለመፍታት የምንችለው?” የምንጨምረው፤ እኛ በጎሳና በኃይማኖት በመከፋፈላችን፤ ከህወሓት/ኢህአዴግ በጥቅም ከተያያዘ አቅም በበለጠ ደረጃ ያደከመን መበታተናችን ነው። ለአንድ ሃገር፤ ለአንድ ሕብረተሰብና ለአንድ ሕዝብ ፍትህ ከማሰብና አብሮ ከመስራት ይልቅ መበታተናችን ለምንቃወመው ገዢ ፓርቲ ጥንካሬ እየሰጠን ነው። አብዛኛዎቻችን “ዲሞክራሲ፤ ዲሞክራሲ” እንላለን። ፍትህና መብት ለአንድ ግለሰብና ለአንድ ጎሳ አለመሆኑን ለመቀበል አልቻልነም። ስለሆነም፤ የሃገሪቱን ችግር በሚገባ አላወቅነውም። ዲሞክራሳዊ ስርአት ከመመስረቱ በፊት የማህበረሰቡ ባህልና ፍላጎት ምን እንደሆነ ማወቅ አስፈላጊ ነው። ከሁሉም በፊት ኢትዮጵያ የምትባለውን ረጂም ታሪክ ያላት አገር ከውድቀት ማዳን አለብን። ከኢትዮጵያ ያላነሱ የጎሳዎች ቁጥር ያሉባት ዛምቢያ፤ “አንድ አገር፤ አንድ ሕብረተሰብና አንድ ሕዝብ” ብላ ወጣቶቿን ታስተምራለች። እኛ ወደኋላ ሄደን የጋራ የሆነ ታሪክ የለንም እንላለን። ህወሓት ከሻቢያ፤ ከኦነግና ደጋፊዎች ጋር ሆኖ የኢትዮጵያ አካል የነበረችውን ኤርትራን “የቅኝ ግዛት ናት” ብሎ የጦር ኃይል ስልጣኑን ተጠቅሞ፤ የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝብ ሳይማከር፤ ግልፅነት በሌለው ሬፈረንደም የኢትዮጵያን ባህር በር ዘጋ፤ ለሌሎች ተገንጣዮች በሩን ከፈተ። ማቆምያ የሌለው በር። የኤርትራ ጉዳይ ድሚክራሳዊ በሆነ ውይይትና አዲስ ሁሉን አስተናጋጂ የሆነ መንግሥት ሊፈታ ይችል ነበር። ገዢው ፓርቲ ለሃገር ተቆርቋሪ ስላልሆነ፤ ደንታ ስለሌለው፤ ለወደፊቱ ስለማያስብ፤ ዋናው ግቡ ስልጣን ለመያዝ ስለነበረ ኢትዮጵያን በቋንቋ ከፋፈላት፤ የጥላቻና የሕዝብ እልቂት የፖለቲካ ባህል ስር እንዲሰድ አደረገ።

የወደፊቱ የመንግሥት ስርዓት በጥቂቶች ሊወሰን አይችልም። ምን አይነት መንግሥት፤ ምን አይነት አገዛዝ የሚለውን መመለስ ያለበት የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ከላይ ያቀረብነው የጸሃፊው ትውልድና የአሁኑ ትውልድ መሰረታዊ ጥያቄ ሆኖ አግኝተነዋል። የአቅጣጫ አማራጮች ስኬታማ የሚሆኑት ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመስጠት ስንችል ነው። ዛሬ በሃገሪቱ ላይ አንዣቦ የምናየውን የመፈራረስ አደጋ ለመከላከል ካልቻልን ስለ አማራጭ የመንግሥት ስርዓት መነጋገሩ ዋጋ ቢስ ነው። ኢትዮጵያ ከጠፋች ነጻነት፤ ፍትህ፤ ዲሞክራሲ፤ እድገት ወዘተ ትርጉመ ቢስ ነው። በኤርትራ እንዳየነው፤ ከጎሳ፤ ከኃይማኖትና ከራስ ጥቅም በላይ ተመካክረንና ቆርጠን ካልተነሳን የቀረችው ኢትዮጵያም ብትፈራርስ የሠብአዊ መብቶች አፈና ይባባሳሉ እንጅ አይፈቱም። ኢትዮጵያ ባትበታተንም የአገሪቱ ሃብት ለጥቂቶች የግል ጥቅም ይውላል። አሁን እንደሚሆነው፤ በያመቱ ብዙ ቢሊዮን ዶላር ተሰርቆ ከአገር ይሸሻል። ኢትዮጵያ ብትፈራርስ አሁን ያለው ስደተኛነት አያቆምም። ስደተኛነት የአሁኑና የወደፊቱ ትውልድ እጣ ይሆናል። ደሃነት ይስፋፋል። ሰላም አይኖርም። ከኬንያና ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር ለመወዳደር አይቻልም። እድገት አይኖርም ማለታችን አይደለም። ዘላቂነትና ፍትሃዊነት ያለው ልማት አይኖርም ማለታችን ነው። ኢትዮጵያን ከአደጋ ተከላክሎ ፍትሃዊና ዲሞራሳዊ የሆነ መንግሥት ለማቋቋም ይቻላል ብሎ በአንድነት መነሳት ከዚህ አደጋ ያድናል የሚል እምነት አለን።

## 19. 'ጠላቴን ስጠብቅ ወዳጅ ገደለኝ'

ያለፉት ሃያ ሶስት ዓመታት የሚያስተምሩን አስኳል ነገር የህወሓት አመራር ስነልቦናችን ጠንቅቀው በማጤን ራሳችን የራሳችን ጠላት እንድንሆን ማድረጋቸው ነው። የፖለቲካ ስልጣን ለገዢው ፓርቲ ታይቶ የማይታወቅ የገንዘ አቅም አበርክቶታል፤ ከእርዳታ፤ ከስደተኛው፤ ከተፈጥሮ ሃብት የበላይነት፤ ከቀረጥ ወዘተ የሚገኝ ሃብትና አቅም። የፌደራል ፖሊስ፤ የደህንነት ተቋም፤ የማዘጋጃ ቤት፤ የንግድ ፈቃድ፤ የመሬት አስተዳደር፤ የማዳበሪያ አቅርቦት ወዘተ የበላይነት። አንድ ለአምሥት የሚለው የስለላ መረብ በቤተሰብ ደርጃ ሳይቀር ልጅ በአባቱ እንዲሰልል አድርጎታል። ሁሉም ዘላቂ ጥቅሙ ሊከበር የሚችለው ስርዓቱ እስከ ቆየ ድረስ ነው የሚለው ስልት ዜጎች እርስ በርሳቸው እንዲናከሱ፤ እንዲጋጩ፤ እንዳይተማመኑ ወዘተ አድርጓቸዋል። የአንዱ ቤት ሲፈርስ፤ አንዱ ሲታሰር ወይንም ሲሰደድ በኔ ላይ እስካልደረሰ ድረስ ምንም አይደል የሚለው ብዙ ነው። በሃቅ ለሃገርና ለወገን የሚታገሉ ግለሰቦች ከሚያውቁት "ጠላት" በባሰ ሁኔታ ያስጠቃቸው የልቡን የማያውቁት "ወዳጃቸው" ነው የሚል ይመስላል። ህወሓት ስልጣን እንደያዘ ሰሞን፤ የመብራት ምሰሶዎች፤ የጣና በለስን ጨምሮ ጭኖ ሄዷል። የተነቀለበት አካባቢ ተጎድቷል። የባስ ብሎ ነዋሪዎችን የመብራቱ ምሰሶ አደጋ እንዳይደርስበት የአካባቢውን ገበሬ ዘብ እንዲቆም አድርጓል። አንድ ይኼን የራስን መብት መገፈፍ በራሱ ሰው ተጠቅሞ የማስከበር ትእይንት የተመለከተ ግለሰብ "አንተ ምን ትሰራለህ ከኤሌክትሪክ ምሰሶው ተጠግተህ የማይህ" ይለዋል። " አየ አንተየ፤ አዲሶቹን አለቆችን ራታቸውን እያበላሁ" ይለዋል ይባላል። የጣና በለስ ምሰሶዎች ተነቅለው ሲጫኑ፤ የአካባቢው ነዋሪዎች ይኼ ነገር ልክ አይደለም፤ "እኛ የመብራት መጠቀም መብታችን ታግዶ ወደ ህወሓት ክልል ሲወሰድ አንቀበልም፤ ይኼ ሌላም፤ ሌላም ያስከትላል" አላለም። ምሁሩና ልሂቃኑም ዝም ብሎ አልፎታል። የጎንደርና የወሎ መሬት ተወስዶ ወደ ክልል አንድ ሲጠቃለልም የሆነው ተመሳሳይ ነው። ደፍሮና ተባብሮ ከዚህ የባሰ ህይወትና ታሪክ ለዋጭ ውርደት ያመጣ ውሳኔ ሊከሰት አይችልም ብሎ በቁርጠኛነትና በደፋርነት የተነሳ የለም።

ህወሓት/ኢህአዴግ/ኦነግ ኢትዮጵያን በማያሻማ ሁኔታ በአዲስ መልክ ለመቅረፅ ያላደረጓቸው አደገኛ የሆኑ የጂዖ-ፖለቲካል ውሳኔዎች እንደ አፈር ናቸው። ለምሳሌ፤ ዓባይን ለመቆጣጠር፤ የጎጃምን ክፍለ ሃገር ሕዝብ ለማድከም፤ አማራውን ከሌላው ጋር ለማጋጨት ወዘተ ሲባል የቤኒ-ሻንጉል ጉሙዝ ክልል ተፈጠረ። የዚህ ሕዝብ ፍላጎት ምን እንደሆነ ድምፅ አልተሰጠበትም። ቁም ነገሩ ይኼም ሲሆን የተጎዳው ሕዝብ ለራሱ የወደፊት ጥቅም ሲል አቤቱታ አላቀረበም። ጉዳዩን አስፈጻሚው ህወሓት የፈጠረው የአማራው የፖለቲካ ድርጂት ነው። የራሱን በራሱ። ስልቱ፤ ሕዝቡን ለመጉዳት በራሱ፤ ከአብራኩ በተገኙ ራሳቸውን በሚወዱ መጠቀም ያስፈልጋል የሚል ዘዴ ነው። ህወሓት የኢትዮጵያን መሬት ለባውለታው ለሰሜን ሱዳን መንግሥት ሲያስረክብ የተጠቀመው የአማራውን ድርጅት ነው። ሌላው ቀርቶ የኃይለማሪያም ደሳለኝ መንግሥት አፄ ምኒልክ፤ አፄ ኃይለ ሥላሴና የቀድሞው የኢትዮጵያ ፕሬዝደንት መንግሥቱ ኃይለማሪያም ያልተቀበሉትን ውል ተቀብለዋል በሚል የፈጠራ ወሬ ለማጽደቅ ሲፈልግ የጎንደርን ነዋሪዎች በማባበልና በማስፈራራት ምስክሮች እንዲሆኑ ለማድረግ "ተቀበሉ፤ ፈርሙ" ብሎ ነበር። ለህሊናና ለሃገር ጥቅም የቆሙ ኢትዮጵያውያን አንቀበልም፤ "የፈለጋችሁትን አድርጉን" ብለዋል። አሁንም የአገር ወዳድነት መንፈስ እንዳለ አሳይተዋል።

ይኼ የራስን ጥቅም በራስ የመጉዳት ባህል በሌሎች አገራዊ በሆኑ አበይት ጉዳዮች ላይ ተፈጽሟል። ህወሓት የራሱ የሆነ ኃብት፤ ገንዘብ፤ አቅም ከሰማይ አይፈጥም። የዓባይ ግድብ ጥናትና እቅድ መኖሩን እየተረዳ የተከዜን የመብራት ኃይል ግድብ የኢትዮጵያን ሕዝብ ባጀትና በኢትዮጵያ ሕዝብ የሚገኝ ብድር፤ የንግድ ክሬዲት ከቻይና ተጠቅሞ አስተማማኝ የውሃ ፈሰስ በሌለበት ወንዝ ትልቅ ግድብ ሰርቷል። የተሰራው ክልል አንድን ለማገልገል ነው። ከዚያ ወዲህ በመሰረተ ልማት፤ የሃዲድ መንገድና ሌላ ከሱዳን ጋር ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር የሚደረገው ሰፊ ኢንቬስትመንት ፈሰስ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የሚገኝ ነው። በአይን የሚታየው ይኼ ኢንቪስትመንት ከቀረው ኢትዮጵያ ጋር ያለው የኢኮኖሚ ግንኙነት፤ የማህበረሰብ ትሥስር ምን እንደሆነ አጥጋቢና ግልፅነት ያለው ጥናት ለሕዝብ አልቀረበም። ቁም ነገሩ፤ እነዚህን በመሳሰሉ ውሳኔዎች ላይ ተቆርቋሪዎች--የፖለቲካ ፓርቲዎች፤ የማህበረሰ ስብስቦች፤ ግለሰቦች፤ ምሁራና፤ ልሂቃን ሃሳብ አልሰነዘሩም። ህወሓት በየትም ቦታ የሃገሪቱን ባጀትና እርዳታ እየተጠቀመ ያልተያያዙ ልማቶች ያካሂዳል። ይኼ ሁሉ ሲካሄድ የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በተለይ የተማረው ክፍል ማንኛውንም የህወሓት/ኢህ አዴግ ስራዎች፤ጉዳትም ቢኖራቸው ለንገ ትቷቸዋል። ይኼ ለይደር የሚተው አገርና ህይወት ለዋጭ ስራ ሊገባን ወደማይችልበት የባህል አዙሪኝ ውስጥ አስገብቶናል። በይሉኝታ፤ በትእግስት፤ ነገ ይፈታል በሚል አስተሳሰብና በፍርሃት መካከል ያለው የዜጎች አስተሳሰብና ስነልቦና ልዩነት እየጠበበ ሄዷል።

እንዲያውም፤ አስተሳሰቡ ለውጥ የሚፈልጉትን ግለሰቦችና ስብስቦች ሺባ እያደረጋቸው ነው። ለምሳሌ፤ ወዳጅ እንደ "ጠላት" የሚሰራ ከሆነ አንተም ወይንም አንችም ከገዢው ፓርቲ በበለጠ አጥፊ ነህ፤ ወይንም ነሽ ብሎ ማጋለጥ

ያስፈልጋል። ወገኑ ወደ ተራራ ተወስዶ በራሱ “መንግሥት” ወይንም በራሱ ወገን ሲወረወርና ሲሞት እያየ “በኔ አልደረሰም” የሚል በራሱም ላይ ነገ እንደሚመጣበት አያስብም፤ ለወገኑም ደንታ የለውም ለማለት እንገደዳለን።፡ ገዢው ፓርቲ በተደጋጋሚ ለህብረተሰቡ ወይንም ለተወሰነ ክፍል ጎጂ የሆኑ ስራዎችን ከሰራ “ለነገ ይሁን፤ በትእግስት” እንየው የሚለው ቂልነትና ፍርሃት ነው ወደሚል የባህል ለውጥ መሸጋገር አስፈላጊ ነው። አለያ፤ ሁሉ ነገር “ጂብ ከሄደ ውሻ ጮኸ” ይሆናል። ገዢው ፓርቲ በሰላም ለውጥ ለማምጣት የሚፈልጉ ፓርቲዎችንና ግለሰቦችን “ደካሞች፤ የተከፋፈሉ፤ እርቅ የማይፈልጉ፤ የዱሮውን መንግሥት ለመመለስ የሚፈልጉ፤ ቂም በቀለኞች፤ ትምክህተኞች፤ ነፍጠኞች፤ ኢሰፓዎች” ወዘተ እያለ ይኮንናል። ይኼ የመበታተንና የማስፈራራት ስልት ነው። የዱሮውን መንግሥት ለመመለስ የሚፈልግ እንደሊለ ብዙ ማስረጃዎች አሉ። ፍትህ ፈላጊዎችን እያሰረና እያሳደደ አመራር የላቸውም ይላል። ብቃት የላቸውም ይላል። መለስ ዜናዊ የአመራር ልምድና ብቃት ያገኘው በጫካ አይደለም፤ ኢትዮጵያ በበላይነት ሆኖ በመግዛት ነው። የህወሓት የበላዮች ስትራተጅ ወይንም የአገዛዝ ስልት ለፍትሃዊና ዲሞክራሳዊ ስርዓት አማራጭ የቆሙትን ሁሉ ማሳደድ፤ ማደኼየት፤ ማሰርና ከሃገር ለቀው እንዲወጡ ማድረግ ነው። ተቀናቃይና ተቆርቋሪ አገር ወዳድ እንዳይኖር።፡የተማረው፤ የሰለጠነውና ልምድ ያለው አገር ለቆ ሲወጣ ወይንም ለእስር ቤት ሲዳረግ የአማራጭ ክፍተት የማይቀር ነው።

አውቀውም ይሆን ሳያውቁ የገዢውን ፓርቲ ፕሮፓጋንዳ ይዘው የሚያራግቡ “የውስጥ” አርበኞችና ሰርጎ ገቦች ብዙ ናቸው። የክክልን ስርዓት ወደ መንደር ልዩነት ያሻገሩት ብዙ ናቸው። ለምሳሌ፤ “የአማራ ክልል” ተብሎ በጎሰኞች በተሰየመው አካል በጎንደር፤ “ሰሜንና ደቡብ ጎንደር” በሚል ልዩነቶች እንዲስፋፉ ተደርጎ ነበር። ያ አይበቃ ብሎ አሁን ደግሞ በመንደር ደራጃ፤ “ለምሳሌ ፋርጣ፤ ጋይንት” ወዘተ የሚል ልዩነት በቤተክርስትያን ሳይቀር ተከስቷል። አንድ ተቆርቋሪ እንዳስቀመጠው “ጎንደሬው በጎንደሬው፤ አማራው በአማራው ላይ የሚደረገው ጥልና ልዩነት ህወሓት ከሚያደርገው በባሰ ሁኔታ እየጎዳን ነው። ይኼ በተማረው ክፍል፤ በተለይ በውጭ በሚያራግበው ዘርፍ ተባብሷል። እኛ የራሳችን አጥፊና መሰናክል ሆነናል። ይኼን ወደ መንደር የተላለፈ መከፋፈል ህወሓት አስገድዶን የምናደርገው አይደለም፤ ህወሓትማ የሚሰራውን “የከፋፍለህ ግዛው ስልት ያውቃል። የኤርትራንና የትግራይን አማርኛ ተናጋሪዎች አማራዎች ናቸው ብሎ በጎንደርና ሌሎች ቦታዎች የበላይ የሚያደርግ ፓርቲ ማንም የለብኝም የሚል እምነት እንዳለው ያሳያል። ታዲያ እኛ ይኼን ተቀብለን እርስ በርሳችን እንድንጣላ፤ ችግራችን በሕብረት እንዳንፈታ፤ መሳቂያ እንዳንሆን ጥረት አናደርግም። እርግማን መሰለኝ” ብሏል። በመንደር ደረጃ ከፋፋዮቹ ተጠቃሚዎች ናቸው የሚሉ ብዙ ናቸው። በአማራው ክልል የለውጡ አጋር ነን የሚሉ ማለታችን ነው። አንድ ግለሰብ የተቃዋሚው ክፍል ወቃሽ የገዢው ፓርቲ አወዳሽ በሚሆንበት ወቅት እውነተኛ አቋሙ የት እንደሆነ ለመደምደም አያስቸግርም። በትእግስት፤ በይሉኝታ እንየው፤ “ጠላት አናብዛ” የሚሉ ከገዢው ፓርቲና ደጋፊዎች በባሰ ሁኔታ ለውጥ እንዳይመጣ መሰናክል ሆነዋል የሚለው ትችት የሚሰማው ለዚህ ነው። ባጠቃላይ ፍትህ፤ በሕግ ፊት የሁሉም ኢትዮጵያውያን እኩልነት፤ ሕዝብን የሚወክልና ለሕዝብ ተገዢ የሆነ አማራጭ አስፈላጊ ነው ካልን <u>በትእግስትና በፍርሃት መካከል፤ “በጠላትና በወዳጅ” መካከል ያለውን</u> ልዩነት ለይቶ ማወቅ አስፈላጊ ነው። ወጣቱ ትውልድ እውነተኛ ጠላቱን ከእውነተኛ ወዳጁ ለይቶ ካላወቀ ለዚህ ጎጂ ባህል ሰለባ አይሁን። ለምሳሌ፤ የትግራይ ወይንም የኦሮሞ ሕዝብ የአማራው ሕዝብ ጠላት አይደለም። ጠላት ናቸው ብለን ካመን የህወሓትን የጎሳ ርእዮት ተቀበልን ማለት ነው። ክርስትያኑ የእስላሙ ጠላት ነው ብለን ካመን የኢህአዴግንና የአክራሪዎችን ስልት ተቀበልን ማለት ነው። የኢትዮጵያን ሕዝብ ከእልቂት፤ አገሪቱን ከመፈራረስ ለማዳን ከፈለግን የጎሳና የኃይማኖት ጥላቻን መታገል የዜግነት ግዴታችን ነው።

## 20. የወደፊቱ የኢትዮጵያ ትውልድ ዓለም

በአፄ ኃይለ ሥላሴና በደርግ ዘመን አገራችን በየሞያችን በቅንነት ያገለገልን ሁሉ ወደፊት ያለን ሕይወት ቢበዛ ሃያ አምስት አመታት ነው። የኔ ትውልድ እያለፈ ነው። ስለሆነም፤ እኛ የምናውቃት ኢትዮጵያን በደርግና በህወሓት መንግሥታት የተወለደው ትውልድ አያውቃትም። ህወሓት በፍፁም ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ታሪክ እንዳያውቅ ተደርጓል። ስለሆነም፤ በእድሚያችን ገፉ ያልነው ኢትዮጵያውያን ቅርስ ለመተው የምንችለው ዛሬ ብቻ ነው፤ ነገ የለንም። አኩሪ ታሪኩ፤ በተለይ ሃቀኝነት፤ የሞራል ብቁነት፤ ደፋርነት፤ አገር ወዳድነት፤ ሕዝብ አገልጋይነት ወዘተ እሴቶች ወዘተ መለያዎቻችን ናቸው። ወጣቱ ትውልድ ከናቃቸው እራሱን ያስንቃል። ራሱን ለስደት ይዳርጋል። እነዚህ እሴቶች መናዳቸው ያስከተለው መዘዝ ብዙ ነው። የወደፊቱ ተከታታይ ትውልድ እድል በሙስና ወረርሺኝና በጠባብ ጎሰኛ ቡድኖች የሃብትና የፖለቲካ ስልጣን ሽሚያ ተበክሏል። ግፈኛው የህወሓት ቡድን የኢትዮጵያን ግዛታዊ አንድነትና የረዢም ጊዜ ጥቅሟን የሚቀበሉና ለዚህ አበይት ጉዳይ የቆሙትን ሁሉ በያሉበት አሳዷቸዋል፤ ማሳደዱን ቀጥሏል። እትዮጲያና ኢትዮጵያውያን በራሳቸው መንግሥት እየተሰቃዩና እየተዘረፉ ነው። ከሙስና ብቻ የተከሰተውን ወንጀል ከእኔ በበለጠ በማስረጃ ያቀረበው ግሎባል ፋይናሺያል ኢንተግሪትይ የተባለው ተቋም እንደሚከተለው አቅርቦታል።

"The people of Ethiopia are being bled dry. No matter how hard they try to fight their way out of absolute destitution and poverty, they will be swimming against the current of illicit capital leakage." 106/

በቋንቋ የተመሰረተ አድልዎ፤ በጎበ ብልግና የሚተዳደር መንግሥት፤ ከሕግ ውጭ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ብቻ ሃያ አምስት ቢሊዮን ተሰርቆ ከሃገር የወጣበት ሕብረተሰብና አገር፤ "የጣና በለስ ፕሮጀችት" እንደዋዛ የፈራረሰበትና መሳሪያዎች ከቦታው ተነቅለው ወደ ትግራይ ክልል የተወሰዱበት ወዘተ አገር ጤናማ ነው ለማለት አይቻልም። በድምራቸው፤ ሙስና፤ አድልዎ፤ አፈና ወዘተ ጉዳታቸው ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፋል የሚል ግምት አለን። ግጭት መፍጠራቸው አይቀርም። ጨዋነትን እንደ ፍርሃት የሚቆጥረው ህወሓት ራሱን ለመለወጥ አለመቻሉ ድንቁርና ነው። ሙብቱና ክብሩ የተገፈፈ ሕዝብ መነሳቱ የማይቀር መሆኑን ከኢትዮጵያ ከሌሎች አገሮች ታሪክ ለመማር ይቻላል። ወጣቱ ትውልድ ለራሱ የወደፊት ህይወት፤ ለራሱ ክብርና ሙብት መታገል አለበት። ስደት መልስ ሊሆን አይችልም። በውጭ የሚኖረው የኢትዮጵያ ስደተኛ ሁኔታውን ዝም ብሎ ለማየት አይችልም። ምን አይነት አገዛዝ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሚደገፍ መምረጥና ደፍሮ መናገር አለበት። ኢትዮጵያ በአፍሪካ "ጋዜጠኞችን በማሰር ሁለተኛ፤ በዓለም ከሚያስሩ አስር መንግሥታት አንዷ" ነው ሲባል ሁሉም ለህሊናው ጭምር ሲል እንዴት ይኼ ይሆናል ብሎ ድምፁን ማሰማት አለበት። ስደተኛ ሆነን የመንፈስ ስደተኛ ሁኑ ብሎ የሚያስገድደን ኃይል የለም። ተከታታይ ትውልድ ለስደት እንዲዳረግ እንመርጣለን ወይንስ በአገሩ ሰርቶ፤ ሙብቱ ተከብሮ፤ የምርት ሃይሎችን አሳድጎ ራሱን፤ ወገኑንና አገሩን ከደሃነት፤ ከረሃብና ከኋላ ቀርነት ነጻ ማውጣትን እንመርጣለን ብለን መልሱን ራሳችን ማቅረብ ይኖርብናል። ምርጫዎች ከፊታችን ተደቅነዋል። በሃገር ሰርቶና ተከብሮ መኖር ምርጫ እንደሚሆን ተስፋ አናደርጋለን። ከሆነ፤ ተከታታይ፤ ትውልድ የሚያመሰግነው፤ ታሪክ የሚመዘግበው አስተዋጽኦ ለማድረግ ብቃት አለው።

በስደት የምንኖረው ምን ለማድረግ እንችላለን?

(i) በቀላሉ ለማድረግ የምንችለው። በመከባበር፤ በመደማመጥ፤ በሃቅ፤ የመወያየት፤ ባህልን ስራ ላይ ማዋል የመጀመሪያው ነው። አንዱ በሌላው ላይ የሚያደርገውን ክስ፤ ሃሜት፤ ጠለፋ፤ ያቁም እንላለን። ለዚህ፤ እመርታዊ የባህል ለውጥ፤ የአስተሳሰብ ለውጥ ማድረግ አለብን። ለአገር ካሰብን ይቻላል። ለቡድን ካሰብን አይቻልም። ጃፓኖች፤ ኮሪያዎች፤ ቻይናዎች፤ ቱርኮች፤ ለእድገት ሲሉ አድርገውታል።

(ii) ከሁሉ በላይ የሚጎድለን ፈቃደኛነት፤ አብሮ ችግሮችን መፍታት ነው። እኛ፤ የመቻቻል፤ የመከባበር፤ የመደጋገፍ፤ ባህል አለን። አገራችን የቆየችው በዚህ ነው። ዛሬ፤ ከልደት፤ ከሰርግና ከሞት ውጭ ይህን የመደጋገፍ ባህል ከስራ ላይ አናውለውም። ዘወር ብለን አይተን፤ ከቦረና፤ ከኩናማ፤ ከኦሮሞ፤ ከጉራጌ፤ ከአማራ ወዘተ ልምዶች ጠቃሚ የሆኑቱን ችግር መፍቻ ብናደርግ ይጠቅመናል።

(iii) እኛን የሚያሳስበን፤ የተቃዋሚው ዘርፍ አሁንም የሚገዛው በሕዝብ/ለሕዝብ ሙብትና ተጠሪነት አይደለም። "እናውቅልሃለን ተከተል ለሚል" ፍልስፍና ይመስላል። ቡድናዊነት፤ ግለሰበነት፤ ጠባብነት፤ "የኔ ድርጅት" ባይነት ነው። ለመረዳዳት፤ ለመደጋገፍ ማነቆ ሆነናል። ህወሕትን/ኢህአዴግን ለማድከም አስፈላጊው ታጋዮችን የሚሰበስብ፤ ለአንድ አገራዊ፤ እትዮጵያዊ አላማ የቆመ ተደጋጋፊ ዓለም አቀፍ የማህበረሰብ እንቅስቃሴ መሆኑን ሙሉ በሙሉ እናምናለን።

(iv) የድርጅትና የአመራር ክፍተቱን ለመሙላት የአስተሳሰብ ለውጥ (Paradigm shift) ያስፈልጋል። ይህ የባህል ለውጥ የሚጀምረው ከእያንዳንዳችን ነው። ለአስተሳሰብ ለውጥ ከሚረዱት የባህርይ ለውጦች መካከል፤ በኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነትና በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እኩልነት እምነት መኖሩ ዋናው ነው። መላውን ሕዝብ ያለአድልዎ ለማገልገል ዝግጁ መሆን አለብን። በእኛ ግምት፤ ለውጥ አንድ አምባገነን መንግሥት አስወግዶ በሌላ መተካት አይደለም።

(v) በእኛ እምነት፤ የተቃዋሚው ሃይል መከፋፈል- ከሁሉ በላይ የጠቀመው-- ገዢውን ፓርቲ ነው። የመከፋፈል ባህል፤ ተቃዋሚው ያለውን የገንዘብ፤ የእውቀት፤ አብሮ የዓለምን ሕዝብ ለማሳመን የመስራት አቅም አዳክሟል። አገር ቤት ለሚታገሉ፤ ለታሰሩ፤ ሊነሱ ለሚችሉ፤ ወገኖች ዘላቂነት ያለው ድጋፍ የመስጠት ችሎታችን ተጎድቷል። ሕዝቡ በተቃዋሚው አመራር እምነት እንዳይኖረው አድርጓል። ጥናቶች ሁሉ የሚያሳዩት የተቃዋሚውን ድክመት መከፋፈሉ ነው። የውጩ አማራጭ ይዞ፤ አገር ቤት ካሉ ልዩ ልዩ

ሃይሎች ጋር መቆላለፍ አላሳየም። ይህ ሁኔታ መለወጥ አለበት። “ተባበሩ፤ አሊያ ተሰባበሩ” የሚለው አግባብ አለው።

(vi) ላለፉት ሃያ ሶስት አመታት የፖለቲካ፤ የህብረተሰብና ሌሎች ተቃዋሚዎች ያላሳዩት ሃቅ፤ አብሮ መስራት ጠቃሚ መሆኑን አይደለም። መከፋፈል እንዴት ጎጅ እንደሆነ ነው። የገዢውን ፓርቲ አገልግሏል። የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጠይቀው ላለፈው መወቃቀስን አይደለም። ቂም በቀልን አይደለም። ለአሁኑ ጭብጥ ሁኔታ “ተደራጁ። አብራችሁ ስሩ። ፊታችሁን ወደ ኢትዮጵያና ወደ መላው ሕዝብ አዙሩ” የሚል ነው።

(vii) ለዚህ የሕዝብ ጥሪና የታሪክ አደራ የሚበጀው የልዩነት “ባርኔጣ” ለብሶ አለሁልህ ማለትን አይደለም። ለኢትዮጵያ እኩልነት፤ በኢትዮጵያዊነት ብቻ መታገልን ነው። “ኢትዮጵያ ሃገሬ ናት፤ ዜግነቴ ኢትዮጵያዊ ነው” ብለን ለፍትህ ብንታገል የዓለም ሕዝብ ያዳምጠናል፤ ያከብረናል። ፍትህ፤ ነጻነት፤ ክብር፤ በሰላም በአገር፤ ሰርቶ መኖር፤ ዘር፤ ጾታ፤ እድሜ፤ ትምህርት፤ ሃብት፤ ኃይማኖት አይለይም። ህወሓት፤ ቢያንስ 65 በዘር የተመሰረቱ ፓርቲዎች ሲደግፍ ለመከፋፈል እንዲረዳው ነው። ተቃዋሚው ስለፈቀደለት ሰደተኛውንም በልዩ ልዩ መንገድ እየገባ ከፋፍሎታል። አብዛኛውን በጥቅም ገዝቶታል። ለዚህ ሃላፊነቱ የሰደተኛው ነው። የገዢው ፓርቲ የበላዮች አይደለም። መብታችን ለመጠበቅ ከቆረጥን ገዢው ፓርቲ አያዝብንም።

(viii) በሙስናና በሰብአዊ መብቶች አፈና ላይ የሚካሄደውን በደል ስንመረምር፤ ምሁራንና ተቃዋሚው የጎደለው በድፍረት ለአንድ አገራዊና ሕዝባዊ አላማ አለመቆሙ ነው። አድልዎን፤ ጉቦን፤ ሙስናን፤ ህገወጥ የሃብት ሽሽትን ለማጋለጥ አለመድፈሩና አለመቻሉ የፍርሃት መስፈርት ነው። የፖለቲካ ፍርሃት እስካለ ድረስ ፍትህ አይገኝም። ያለው አፋኝ ስርአት አይለወጥም። ኢህአዴግ ራሱን ለማሻሻልና የሕዝብን አመኔታ ለማግኘት ፍላጎት ካለው ሊያደርጋቸው ከሚችለው አጣዳፊ ተግባሮች መካከል ሙስናን ከቁንጮው ለመታገል መድፈር ነው። ከቁንጮው የገማ የሙስና ስር ዓት አገሪቱን በበለጠ እያደሄያት ነው። የቻይና መንግሥት መሪ ዢ ጅንፒንግ በተደጋጋሚ ያሳየው አዲስ ፖሊሲና ተግባር በሙስና ላይ ነው። በዚሁ መሰረት የቀድሞው የአገር ውስጥ ደህንነት ሃላፊ ዢው ዮንግካንግ በሙስና ተከሷል። በፊት አይነኩም የተባሉ የመንግሥት መሪዎች ተራ በተራ ክስ እየተመሰረተባቸው ነው። “Xi’s anti-corruption drive has been the most far-reaching and sustained in China’s modern history.” ይሕ አገር ወዳድ መሪ ስር ዓታዊ ምዝበራና ሙስና ካልጠፋ የኮሙኒስት ፓርቲውና አገሪቱ አደጋ ይደርስባቸዋል የሚል ስሌት ነው። ከግለሰቦች በላይ ለሕብረተሰቡና ለቻይና ጥቅምና ደህንነት ቅድሚያ መስጠት የሚል። ኪሱም፤ አካሉም፤ ስልጣኑም ያበጠው የኢህአዴግ አመራር ከቻይና ሊማር ይችላል። ለዚህም ግፊትና አቤቱታ ማሰማት ያለበት የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በተለይ ወጣቱ ትውልድ ነው። 107/

በመጨረሻ፤ ይህ መጽሃፍ ችግሮችን ማስረጃ በመጠቀም፤ በተቻለ መጠን፤ ከሁሉም አቅጣጫ ተንትኖ እነዚህ ስርዓት ወለድ ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉበትን አቅጣጫዎችም ለኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በተለይ ለወጣቱ ትውልድ መወያያ እንዲሆኑ ሰንዝሯል። የደራሲው ሙብት የተጠበቀ ሆኖ፤ ግድፈቶችንና ትችቶችን በሃላፊነት ይቀበላል።

## መረጃ ጽሁፎች/ብብሊኦግራፊ


1. Bertelsmann Stitfune Transformation Index—Ethiopia country report, 2012

2. World Economic Forum, Global Competitiveness Report, 21012/2013

3. Freedom House--Freedom in the world, 2012

4. African Development Bank--Briefing Notes for AfDB Long-Term Strategy, 3/7/2012

5. Calderisi, Robert, the Trouble with Africa, NY 2006

6. IMF, World Economic Surveys Regional Outlook for Africa, April 2012

7. Agence France Press, Septemeber 2012

8. Birara, Aklog, Waves, Washington, DC 2010

9. ፍቅረሥላሴ ወግደረስ፣ እኛና አብዮቱ፣ ጸሃይ አሳታሚ. ታህሳስ 2006 ዓም

10. Vestal, Theodore, Meles Zenawi, the Marxist-Leninist "Capitalism Speak," 2012

11. Ibid

12. Ibid

13. Easterly, William, The Whiteman's Burden, New York, 2006

14. Wrong, Michela, It is Our Time to Eat, HarperCollins Publishers, 2009

15. Ibid

16. Vestal, Theodore, Meles Zenawi, the Marxist-Leninist, "Capitalism Speak," 2012

17. ተመስገን ደሳለኝ, የመለስ አምልኮ፣ መጋቢት 2004 ዓም

18. International Crisis Center, Ethiopia: Ethnic federalism and its discontents, 9/2009

19. Sabacchi, Alberto, Ethiopia under Mussolini, London, 1985

20. Ibid

21. Ibid

22. International Crisis Center, Ethiopia: Ethnic federalism and its discontents, 9/2009

23. Ibid

24. ጌታቸው ረዳ, ይድረስ ለጎጠኛው መምህር, San Jose, 2002

25. Ibid

26. Ibid

27. International Crisis Center, Ethiopia: Ethnic federalism and its discontents, 9/2009

28. የዳንኤል እይታዎች፤ ነጠላና ጋቢ...www.danielkibret.com, 2012

29. Ibid

30. Ibid

31. Vestal, Theodore, Meles Zenawi, Marxist-Leninist, “Capitalism Speak,” 2012

32. Ibid

33. ተመስገን ደሳለኝ፣ የመለስ አምልኮ፤ መጋቢት 2004 ዓም

34. Ibid

35. Human Rights Watch, Development without Freedom: how aid underwrites repression in Ethiopia, October 2010

36. Rothkopf, NSE Running the World...Architects of American Power, NY 2004

37. Erlich, Haggai, Saudi Arabia and Ethiopia: Islam, Christianity and Politics, 2006

38. አዲሲቱ ኢትዮጵያ፣ የህወሓት/ኢህአዴግ የስለላ መረብ፤ ከውስጥ የተገኘ ግርድፍ መረጃ 2004 ዓም

39. Ibid

40. Ibid

41. Ibid

42. Ibid

43. National Geographic, A Global Rush on Fresh Water—Saudi Arabia Status Claim on the Nile, November 2012

44. Ibid

45. Pearce, Fred, When Rivers Run Dry and Land Grabbers, Boston, 2012

46. National Geographic, A Global Rush on Fresh Water...., November 2012

47. Ibid

48. Grain, Land Grab Deals, 2010, 2011, 2012, http://www.grain

49. Deguefe, Taffara, Minutes of an Ethiopian Century, Addis Ababa, 2010

50. Getahun, Haileleul, Assault on Poverty, the case of Ethiopia, USA, 2001

51. Deguefe, Taffara, Minutes of an Ethiopian Century, Addis Ababa, 2010

52. The World Bank, Where is the Wealth of Nations, Washington, DC 2006

53. Ibid

54. Ibid

55. Bailey, Ronald, the Secrets of Intangible Wealth, the Wall Street Journal, 9/2007

56. Ibid

57. IEG, the World Bank, World Bank Assistance to Ethiopia-1999-2006, "the silence hunger," June 2007

58. Ibid

59. Ibid

60. Ibid

61. Ibid

62. Human Rights Watch, Mechanism used to control rural communities, http://www.hrw.org, 2005/Ethiopia

63. IEG, the World Bank, Assistance to Ethiopia, 2007

64. Ibid

65. Klitgaard, Robert, Controlling Corruption, U. of California Press 1991

66. The World Bank, Independent Evaluation Group, Ethiopia country assistance evaluation, January 2007

67. Human Rights Watch, Development without Freedom: how aid underwrites repression in Ethiopia, October 2010; and "One hundred ways of putting pressure: violation of freedom of expression and association in Ethiopia, March 2010

68 Plummer, Janelle, the World Bank, Diagnosis of corruption in Ethiopia: perceptions, realities and the way forward for key sectors, 2012

69. Ibid

70. Ibid

71. Ibid

72. Kilimanjaro International Corporation, Ethiopia Corruption Survey, 2012

73. Ibid

74. Ibid

75. Ibid

76. Ibid

77. Ibid

78. Ibid

79. Ibid

80. Ibid

81. Ibid

82. Ibid

83. Center for Strategic and International Studies, Ethiopia: assessing risks to stability, 2011

84. Stefan Dercon, Ruth Vargas Hill and Andrew Zeitin, In Search of a Strategy: rethinking Agriculural-Led Growth in Ethiopia, May 2009

85. The Economist, Development Aid: it doesn't take a village, 11/2012 and Innovation in Africa: upwardly mobile, 8/12

86. Ibid

87. Ibid

88. Society for International Development, Development: African strategies for transformation. Volume 55, Number 4, December 2012

89. Ibid

90. Edward Friedman, Joseph Wong, Political Transitions in Dominant Party Systems, Routedge, 2008

91. Birara, Aklog, Waves: Endemic Poverty that Globalizaton Can't Tackle But Ethiopians Can, Signature Books, 2010

92. Ibid

93. Birara, Aklog, Ethiopia: The Great Land Give Away (የመሬት ነጠቃና ቅርሚት). Signature Books, 2011

94. Ibid

95. Birara, Aklog, Waves: Endemic Poverty that Globalization Can't Tackle But Ethiopians Can, Signature Books, 2010

96. Mark Wolf, "Ending Global Corruption," the Washington Post, July 23, 2014

97. Ibid

98. Birara, Aklog, Waves: Endemic Poverty that Globalization Can't Tackle But Ethiopians Can, Signature Books, 2010

99. William Easterly, The Tyranny of Experts: economists, dictators, and the forgotten rights of the poor, Basic Books, NY, 2013

100. Ibid

101. Ibid

102. Ibid

103. Ibid

104. Ibid

105. Birara, Aklog, Waves: Endemic Poverty that Globalization Can't Tackle But Ethiopians CA, Signature Books, 2010

106. Global Financial Integrity, www.gfintegrity.org/Ethiopa, December 2011

107. William Wan, Corruption Probe hits top ranks in China, the Washington Post, July 30, 2014

*****************************************

### ከዚህ በፊት በደራሲው የቀረቡ መጻህፍት

1. Roots for Democratization in Ethiopia: why unity of purpose matters, Signature Books, Rockville, Maryland, USA, 2007
2. የዲሞክራሲ መሰረቶች በኢትዮጵያ፣የዓላማ አንድነት ወሳኝ ነው፤ Signature Books, Rockville, MD, USA, 2007
3. Waves: Endemic Poverty that Globalization Can't Tackle But Ethiopians Can, Signature Books, Rockville, MD, USA, 2010
4. Ethiopia: The Great Land Give Away: የመሬት ነጠቃና ቅርሚት። Signature Books, Rockville, MD, USA, 2011
5. Hundreds of articles and commentaries on governace, political economy, corruption etc posted on major websites

▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪▪

****************************************************************************************************
****************************************************************************************************
*********************************